# ጦንቷ የኢትዮጵያ
# ትንሣዔ ታሪክ



መሬ· ራስ ኤ· ኤም· በላይ

ከመጽሐፈ ሱባኤ
የተዘጋጀ

# የጥንቷ ኢትዮጵያ
# ትንሣኤ ታሪክ

በመሪ· ራስ ኤ· ኤም· በላይ

ከመጽሐፈ ሱባኤ
የተዘጋጀ

በ1985 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ታተመ

በቦሌ ማተሚያ ድርጅት

ማስታወሻውን በሆታ ተፅፎ የነበረውን በመቅደሱ መዘክርና
ስለገባው እንግሊዞች በሲያው መመልከት ይቻላል

# መቅድም— መጀመሪያ

ይህን መርሀ የሚሆን የጥንትዋ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ መቅድም መነሻ ሆኖ መቅረቡ የእግዚአብሔር ፍጡር የሆነውን የአዳም ዘሮች የሆኑትን የእግዚአብሔርን ካህናቶችና በካህናቶቹ እየተረዱና እየተመሩ በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ የነገሡትን ነገሥታት በኢትዮጵያ መንደሮችና ቀበሌዎች የሚኖሩትን ጐሣዎችና ነገዶች ስምና ታሪክ እጽፍላችኋለሁ ይህንም ልጽፍላችሁ እግዚአብሔር ፈቃዱ የሆነበት እውነትና ጽድቅን ለሰው ልጆች ታሪክ እግዚአብሔር በየጊዜው የሠራላቸውን ታምር ለማሳወቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ልጆች ዘራቸውና ነገዳቸው ከየት እንደወጣ የትስ እንደነበሩ ማን ሲመራቸው ማንስ ሲገዛቸው እንደነበር የሚያስረዳ የሰው ልጆች የሕይወት ታሪክ ነው ።

ይህን መርሀ የሚሆን የኢትዮጵያን ትንሣኤ ታሪክ የሚወድና የሚሻ የሀገሩን ታሪክ የፈለገ ለሌሎች አውቆ ለማሳወቅ የታነሳ ጀግና በታሪኩ ኮርቶና ደፍሮ ለመናገር እንዲችል ነው ።

ስለዚህ የኢትዮጵያን ሕዝብ አመጣጥና የነገሥታቱን ታሪክ ለማወቅና ለመማር የተዘጋጃችሁ ወንድሞቼና እህቶቼ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ማለት ከአዳም እስከተፈጸሚተ ነገሥት አጼ ኃይለ ሥላሴ ድረስ በምታነቡበት ሰዓት የብዙ ጀግኖችና የብዙ ደካማዎች ታሪክ ልታገኙበት ትችላላችሁ ስለዚህ ይሄ ለምን ተፃፈ ማለት የለባችሁም በሌላ በኩል ደግሞ የእገሌ ነገድ ታሪክ የታለ የእገሌ ንጉሥ ታሪክ መቼ ተፃፈ እንዳትሉ ለምን እኔ ያገኘሁትን አቅርቤላችሁ አለሁ ብዙ ጊዜ ደግሞ ደጉን ከፉ ከፉን ደግ እያሉ የፃፉ ስለሚገኙና ክርስቲያኑ ለክርስቲያን ንጉሥ እስላሙ ለእስላም ንጉሥ ያልሰራውን ያላደረገውን እያጋነኑ እያወደሱ ስለሚጽፉ እኔ ግን ሁለቱን ወገኖች በማመዛዘን ጽፌላችሁአለሁ ከዚህ ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥት እንዴት እንደሚነግሥ አቅርቤላችኋለሁ ።

ሥርዓተ ንግሥ በየጊዜው ተቀያይረዋል በየጊዜው አዲስ የንግሥና ሥርዓት ተካሄዷል ይሄውም ከኢትዮጵስ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ

ዘመን መንግሥት በዓፄን ጋር በእለ በድንጋይ መንበር ላይ ሆነው ይነግሱ ነበር መንግሥታቸውም የዘንዶ መንግሥት ይባላል ።

ከቀዳማዊ ሚኒሊክ እስከ አጼ አፈላስ ዘመን መንግሥት በቤተ መቅደስ ውስጥ በታቦተ ጽዮን ፊት ታላቅ አልጋ ይዘረጋና የሚነግሡበት በአልጋው ላይ ወይም በሰረገላ አልጋ ላይ ተቀምጠው ይነግሣሉ ይህም የአሸናፊው አንበሳ መንግሥት ይባላል ።

ከአጼ አፈላስ እስከ አጼ አብርሃ ዘመን መንግሥት በአደባባይ ላይ ታላቅ የሰረገላ ዙፋን ተቀምጦ አንበሳና ጉንጅ ከፊቱ ታስሮ አን በሳውን አጼው በጦር ወግቶ ይገድሉዋል በደሙ ይነከራል ከዚያ በኋላ የከዋክብት ምልክት ያለበት ዘውድ በራሱ ላይ ይደፋለታል ይህም ሺህ ዓመት ንግሥ ተብሎ የንጉሥ ኮከብ መንግሥት ይባላል ።

ከአጼ አብርሃ እስከ አጼ ገብረመስቀል ከሌብ ዘመን መንግሥት ከዙፋኑ መስቀልና ጥና ይዘው ብሩክ በዶመዐሉ በስመ እግዚአብሔር እያሉ ይዘምራሉ ። ከብሉይና ከሐዲስ ለንግሥና የሚናገረውን ቃል በዝማሬ እየዘመሩ በሉትም እያደረጉ ንግሥናውን ያከብሩለታል ሕዝብ ሁሉም የሰሌንና የወይራ ቅጠል ይዘው በእልልታና በሆታ በየደንቁ ንግሥናውን በእል ያከብሩለታል ። ይህም የመስቀል መንግሥት ይባላል ።

ከአጼ ገብረመስቀል እስከ አጼ ዘርአያዕቆብ ዘመን መንግሥት ብዙ ጊዜ በእክሱም የሚደረገው ሥርዓት በሌላ ላስታ ውስጥ የሚዘጋ ጀው የንግሥና ሥርዓት በቀጥሉት ይብሪ ጸት የነበረው የንግሥና ሥርዓት ሁሉም እንደታየው ያዘጋጁና ይነግሱ እንደነበር በማዳር እን ጋንዳቸውን ፅሮት ነበር አሁን ከአጼ ዘርአያዕቆብ እስከ አጼ ኃይለ ሥላሴ ድረስ የነበረውን የንግሥና ሥርዓት እቀርብላችሁ እለሁ ይህም የአሸናፊው አንበሳ ዘመን መንግሥት መሆኑን ላንረሳ ነው ። ሞኣ አንበሳ ዘኢምንገድ ይሁዳ እያሉ ሁሉም ይነግሱ እንደነበረና መንግሥታቸውን በአንበሳ ይመስሉት እንደነበር እህቶቹና ወንድሞቼ ሁሉ ሳታውቁት አትቀሩም በጉንደርና በሸዋ በቅርብ ጊዜ የነበረውን የንግሥና ሥር ዓትና ሕግ አቀርብላችኋለሁ አጼ ወይም ንጉሥ የሚባሉት እሁድ ቀን ሙሉ ሌሊትና ጨረቃ ታይቶ ባህታዊና የሕግ አዋቂዎች ተጠይቀው ነው የንግሥናው ሥርዓት የሚካሄደው በቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ።

ሥርዓቱም ይህ ነው የንጉሡ ነጋሪት ሁሉን ከቀኑ ማህሌት ገብቶ ይዘረጋል ቅቤና እበባ በበላዩ ይነሰንሳል ። መሳፍንቱና መኳንንቱ ሥር

ራሱን እንደ ማዕረጉ ይዞ ይቆማል ካህናቱ ጕማሽ ልብሰ ታልሰናዩ የሚለውን ጸሎት እየደጋገሙ ያዜሙታል መዘምራንም እየተቀበሉ በከበሮና በጸናጽል ይዘምራሉ ። በዚህ ጊዜ አልጋወራሹ ወይም አቤቶ ይሁን ሲባል የነበረው የንጋሢ ዘር በብዙ መራዊት ታጅቦ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ይገባና በተዘጋጀለት ዙፋን አጠገብ ሄዶ ይቆማል ። ከዚያ ጳጳሱ ከራሱ ላይ ጠጉሩን በመቀስ ቆርጦ ከሰባት ቀቶር እጣን ጋር ዘርን ለተሳላሚዎቹ ይሰጣል ቀሳውስቱም በጥናው ውስጥ እያደረጉ ዙፋኑን ሶስት ጊዜ እየዞሩ ያጥኑታል ከዚያ መልሰው እምቀተው የንጉሥነት መሣሪያ ከሚባለው ድንጋይ ላይ ንጉሡ ንጉሥቱን አስቀምጠው ከጽናው ውስጥ ያለውን እሳት ፍሙን በወርቅ ጻሕል አድርገው ቅባአ ሜሮን የምርጃናብ ዘበል ያፈስበታል ።

ከዚያም ከዳዊት መዝሙር ንጉሥ አነ እምሀ ወዳ ከሚለው ጀምሮ ወትብልእ ቅባእ ቅዱስ እስከሚለው ድረስ ይደገማል ካህናቱም ተከ እዉ ሞገስ እምከናፍሪከ ይሉና ቅንነት ሰይፈከ ሃያል ውስተ ሃቌከ እያሉ ባለወርቅ ሰገባ ሰይፍ ያስታጥቁታል ከዚያም አርቅእ ተሰ ፊሀ ወንግሥ ይሉና ወይቤሎ መቅደሱ ይገባሉ ከዚያም ጳጳሱ ቅባአ ሬሀ ወንግሥ ይሉና ወይቤሎ መንግሥት የተባለውን የሜሮን ዘይት በራሱ ላይ ይደፋለትና አዲሱን መንግሥቱን ይሁን ሰምከ አዜ እንዴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ ሰዩመ ኩሙ መንግሥቱን ይሁን ሰምከ አዜ እንዴ ንጉሡ ነገሥት ዘኢ... እግዚአብሔር ይሉታል ።

ቀስ እጁው የወርቅ ዘንግ ያስጨብጡዋል እራቅ ማስሬው ዘው ዳን በከበር ያዘ ቀደቶ በራሱ ላይ ያስቀምጡበታል ። ከዚያ እራቅ ማስሬው ጃህ ዓመት ያንግሥህ ብሎ ስሙን ይጠሩዋል ከዚያም ሕዝቡ ሶስት ጊዜ ያስገነዳለታል ጃህ ዓመት ንጉሥ እያሉ እንቢልታና ነጋሪት ሶስት ጊዜ ይመታል ።

ከዚያም የወርቅ ዘንጉን እንደያዘ የወርቅ ዘውዱን እንደደፋ ብቶ ዘጋጀለት ዙፋን ላይ ይቀመጣል ካህናቱ መንበርከ እግዚእ ለአለም ክርቤ ወቅንአት የሚለው ላይ ሲደርሱ ሊያቶን ወሕልእልኮ ጉሩሃ እምሕገወምና ያላል እጨጌው ወይም ንቡረ እዱ ከሉታስ ወንጌል ብእሲ ከቡር የሚለውን ሲያነቡ ጳጳሱ በእንተዝ ቀብአከ እግዚአብሔር አም ላክከ ብለው እንደገና ልዩ የሆነውን ቅባአ መንግሥት ይቀቡታል ። ይህ ልዩ የሚያደርገው ከሃያ አራት አዕዋት የተቀመመ ቅባአ ንግሥት ወይም ቅባአ መንግሥት ስለሆነ ነው ።

እነዚህም እነኚ ፤

1. ሰባቱ ቀለማት ወይም ነድ ቀለም
2. ክርቢ
3. ከረፋማ
4. ኤሊቱ ጥቁር እርያን
5. ናትረ ነጭ እርያን
6. የሎሚሽት እምትባል ቅጠል
7. ሰንደል
8. ቅርንፉል
9. ጃውሌ የድንጋይ እጣን
10. ሰንቡል
11. የባህር እጣን
12. እፀ መአዛ
13. የወይራ አበባና ፍሬ
14. የትርንጉ አበባ
15. የጽጌ አበባ
16. የእንኮይ አበባ
17. የጠንበለል አበባ
18. የቀጋ አበባ
19. የጽጌረዳ አበባ
20. የእንጆሪ አበባ ፍሬ
21. የዋንዛ አበባ
22. የእፀ አብርሂት
    ቅርፊትና አበባ
23. ጤና አዳም ቅጠሉና አበባው
24. የእፀ ሐረግ አበባው

እነዚህ ሁሉ ተጠራቅመው በንፁህ ስፍራ ተዘጋጅቶ እርጥ... ይደረደሩና በእርባ ቀናቸው መጀመሪያ ቅባታቸው ቀጥሎ ... ሉቱ ዓቦች ይጠራቀማል ከዚያ በሱባኤ ፀሎት ይወሰደበታል ... ከዳዊት እየተቀባ ሃያ አራተኛውን የዳዊት መዝሙርና ...

ነመብታል ቅብአመንግሥት የሚባለው በሁለት ይህ ነው ከእነዚህ እበዋ
ፉች የወጣ ነው ።

አሁን ወደ ንግሥናው ሥርዓት እንመለስና ከዚህ በኋላ ቅዳሴ ያገባሉ ። ምስባክ እስመ በየዐቢ በበረከት በናዜ . . .ወንጌል ደግሞ ነሐታብ ወንጌል ወይም ከማቴዎስ ይነበባል ።

ምልጣን በመንፈስ የሃውር መዝሙር ምእዋደ አልቦ ዘየአቢ ይባላል ቅዳሴው ካበቃ በኋላ ንጉሡ ከቤተክርስቲያኑ ወጥቶ ፊት ለፊት በሰረገላ ሁኖን ላይ ይቀመጣል እራቅ ማሰሬው ተፈሰሁ ሲል ከዘ ናዩ ተፈሳሁን ወተሣለሁን ይላሉ የብዙ ለአምላክ እገሌ ንጉሥ ንግሥት ባለ ኒዜ ደግሞ ካህናቱ ንጉሡ ይላሉ ጳጳሱ በስንቱም ንጉሡ ከሕዝቡ ጋር ሰሎት ያደርጋሉ ከጸሎት በኋላ በረከተ ቀሰጠንጢኖስ ወተዎዶስዮስ ይደረገዋል ሲሉ አጨብጌው ደግሞ በኢትዮጵያ ንጉሥታት ስም በነ አብርሃና በንካሌብ ስም ይባርኩታል ሕዝቡም ሺህ ዓመት ንግሥ እያሉ በከብሮና በእንዚልልታ በዕታና በእልልታ ያከብሩሉታል ።

ከዚህ በኋላ ያዋጅ ነጋሪ ታሉ ንጉሡ መንግሥተ ወበርቱ ከበሮ እስመሰገኑ ለእልፍኤል ውሰጉ እስከሚደሎ ድረስ ያጉብቡ ይላል ። ከዚህ በኋላ ወደቤቱ መንግሥቱ ያደድና ሹም ሽር ምህረት ሲያደርግ ያሰንብታል ።

ሴት ንግሥት ደግሞ ሥርዓቱ ንግሥናዋ ሲሆን እንደዚህ ነው ንቱ ወይም ኪቲኒቱ በተዋበና በአማረ የወርቅ ጌጥ የተንቆጠቆጠች ልብስ በተለያዩ ጌጣ ጌጦች አሸብርቃ ንጉሥ በአለበት ሁኖን መኖታ በንጉሡ ቀኝ ትቀመጣለች ካህናቱ በዝማሬት ወትቀውም ንግሥት በየማንከ ሲሉ ሕዝቡ ወይም መጣፍንቱና መኳንንቱ ወይዘሮና ለመኪ በሉሉ ትውልደ ትውልድ ወትስይም ይቀው መዓእስተ እያሉ እስከመጨረሻው ይዘምራሉ ከዚያ ሊቀ ሊቃውንት ቄስ አጼው አጼጌ (እጨጌ) ይባርካቸዋል ፊት ማሰሬው ቅብአመንግሥት በጳጳሱ እጅ ከተቀባች በኋላ ዘውዱን በራስዋ ይደፉላታል ንግሥቲቱ ቀጥ ከመሃል የሰሎሞን መሰዋ እስክ በኋላ መቀደስ እስከሚደሉ ታገብእለች ከዚያም በክብር ወደቤተመንግሥቱ ንግሥቲቱና ንጉሡ በተዘጋጀላቸው ሰረገላ ተቀምጠው ይጓዛሉ ሀዝቡም በእልልታና በሆታ እቴ እጣዜእትን እጊጣዜ ሲሉ ይወናናሉ ከዚያም ቅልቅ ይስታ ይታያል ።

ስለአነጋገሩ ከአቀረብኩላችሁ በኋላ ንጉሥ ነገሥት ወይም ንጉሥ መሆን እሚገባው እንዴት ያለ ሰው ነው የተማረ ነው

ወይስ ደግንነት ያለው ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል ። ንጉሠ ነገሥት መሆን የሚገባው መጀመሪያ ቀንደኛ ሆኖ የተገኘው ወይም ደግና ይሆንና ጠላት የመሰለውን አገርን ከጠላት እጅ ያዳነውን ሌላ አገርም ወር ገባር ያደረገ በሁሉ ዘንድ ጉበዝና የታወቀ ደግና መስፍን ከዚያም አልፎ ንጉስ ወይም ንጉሠ ነገሥት ይሆናል ። እንጅ መግ አይታይም ሌላው ደግሞ አባቱ ንጉሠ ነገሥት ይሆንና ሊሞት ሲል የተናዘዘለት ወይም አስቀድሞ አልጋ ወራሽ ሆኖ የተቀመጠ ይነግሣል ብዙ ጊዜ ግን በግዛት ከሚኖሩት ከነገሥታት ልጆች አንዱን መግ ፍንቱ መርጠው ያነግሡታል ።

እንግዲህ ንጉሠ ነገሥቱ ከነገሠበት ቀን ጀምሮ ገዥብ የሌለው ክብርና ስልጣን ስላለው በነገሠበት ሃገር ላይ የልቡን ያደርጋል ይሾም ያለው ይሾማል ይሙት ያለው ይሞታል ይታሰር ያለው ይታ ሰራል ። ከሁሉ የሚያስገርመው ንጉሡ በዚህ አገር ሄዶ በአደባባይ እንድትሰቀል ብሎ በሚፈርድበት ጊዜ ተፈራጁ ያለ ዘበኛ ወደተ ሰው ሃገር ሄዶ በአደባባይ ተሰቅሎ ይሞት ነበር ። ባአንድአንድ ነገር በመርነት ወይም በእጁ የንጉሠ ነገሥቱ እጅ ወይም እግር የተቆረጠ እንደሆነ ደግሞ ቤተሰቡ ሁሉ እንደንጉሡ ነገሡቱ እኩ እጅ ወይም እግራቸው ይቆረጣል ።

ሊሞት ደግሞ አብረው የሚሞቱ አሉ ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ከነ ሠበት ቀን ጀምሮ የንጉሠ ነገሡቱ አካልና ህይወቱ በቤተ ሰቡ አካልና ህይወት ስለሆነ አክብረው ተጠንቅቀው ይደብቁታል ይጠብቁታል ።

ንጉሠ ነገሥት ወይም ንጉሥ የፈለገውን ወይም የወደደውን ለማድረግ የሚከለክለው ስለሌለ የሚስቶቹና የቁባቱ ብዛት መጠ የለውም ልቡ ከፈቀደ እህቱን የእህቱን ልጅ ፣ አክስቱን ፣ የአክስቱ ልጅ ማግባት ይችላል የሚናገረው ወይም ለምን ይህን አደረገ የሚ ሰው አይተኝም ቢናገርም ምላሱ ይቆረጣል ። ስለዚህ ብዙ ልጆች ይወልዳል ከሚወልዳቸው ልጆች አንድ ብቻ ስለሚነግሥ ሌሎ ተይዘው መንግሥቱን እንዳይረብሹ ሃገር እንዳያውኩ ተብለው በግዞ ይኖራሉ የሚበጠብጡትም ይገደላሉ ስለዚህ ከንጉሥ የሚወለዱ ሁሉ መፈጠራቸውን ይጠላሉ እናቶቻቸው ከንጉሥ ወንድ ልጅ በወለዱ ጊዜ ከሚደሰቱት የሚያዝኑት ይበልጣሉ ነገር ግን በአንድ በኩል ያለው በአንድ በኩል ሃዘን ቢኖር በንጉሠ ነገሥታቸው ከፉ ማስ ተርቶ አርጋኑ የሞተለት ለመሞት የሚዘጋጁ ብዙዎች ናቸው ። ይህውም

እንደኛው ልጅ ወይም ሌላው ቢነግስ በአዲሱ ንጉሥ ትእዛዝ የሟች ንጉሥ ቤተሰብ ሁሉ መታሰር መደብደብ መዋረድ ይደርስባቸዋል ።

ቆንጆዎች ተመርጠው ለአዲሱ ንጉሥ እቁባት ወይም አገልጋይ ይሆናሉ ይህን እድል ያላገኙት ግን እንደባሪያ እንደእንስሳ ተቀጥረው ሁሉንዘ ይሰቃያሉ ። ስለዚህ ንጉሣቸው እንዳይታመሙ እንዳይሞቱ እንደአይናቸው ብሌን ተጠንቅቀው ይጠብቁታል ። የሚበላውን የሚጠጣውን ተቆጣጥረው በወንድሙ በእህቱ እጅ የተዘጋጀ ምግብ ፈጽሙ አይሰጡትም ይኸውም ስለማያምኑዋቸውና ስለሚጠራጠሯቸው ነው ። የንጉሥ ንጉሥቱና የቤተሰቡ እድል ይኸው ሆኖ ለየትም የሚለው ከዚህ የንጉሥ ንጉሥቱ ዋና ባለሟሎች ንጉሡ ንጉሥዎቸው ከመሞቱ በፊት ለነሱ የሚበጃቸውን የሚያምኑላቸውን የንጉሥ ልጅ መርጠው በቅድሚያ በእንክብካቤ እያሳደጉ ቤተሰብ ሆነው ይቆያሉ እንጂ ከሁለት ተከፍለው እከሌ ይንገስ እገሌ ይንገስ እያሉ ተከፋፍለው እንደኛው አሸናፊ አንዱን የንጉሥ ልጅ ያነግሡ እንደሆነ ተሸናፊው ወገን ወዮለት አሸናፊው ማናቸውን የአብሪት ስራ ይፈጽሙበታል ።

አሁን ከአዳም እስከ መልከጸዴቅ የዘራችን አመጣጥ ከመልከጸዴቅ ልጅ ኢትዮጵ ከተባለው ከኢትኤል እስከ አጼ ኃይለሥላሴ ማዕበል ነገስት ወይም ተፍጻሜት ነገሥት ያለውን የኢትዮጵያ ነገሥታትና የኢትዮጵያን ትግሎች ታሪክ ከመልከፈ ሰባአና ከመጽሐፈ አክሱማይ ሲራክ በማዳር በእንጻቤት ከጼፈው ከኢትዮጵያ ታሪክ ነገስት ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለኢትዮጵያ ህዝቦችና ታሪክ ወዳድ ለሆናችሁት ሁሉ አቅርቤላችኋለሁ ።

ይኸውም እኛ ኢትዮጵያውያን ታሪክ እያልን ታሪክ እንደሌለን ሁሉ የታሪክ ድሃ ሆነን እንኖራለን እራሳችን የራሳችንን ታሪክ ቆፍረን ማጥናትና መመርመሩ ቀርቶ ከቆመው ያወቀትና ከተሰባበሩት የቀሩት ቅርሶች ከፈረሱትም ግንቦች ላይ ያለውን ቅርጽና ፅሁፍ ለመረዳት አልቻልንም ።

ስለዚህ የውጭ ሃገር ሰዎች ታሪክ ለማወቅና ለመመርመር ወደ አፍሪካ በይበልጥ ወደግብፅና ወደኢትዮጵያ እየመጡ በአክሱም ጭርቃ በሀዋ በላሊበላ በፋሲለደ በመቀሌ በዝርክናዎ በደቀመሃሬ በድ ሀዋ በደብረዳሞ በአዶሊስ በማዕጣት በቆሰታ እንደዚሁም በጉብያ ጭርቃ በናዖታ በመርዊ በናግአ በዋጂሌ በሻምቡር ኪርናት በጀበል ባርነ በጀበል ኑባ እንደዚሁ በዝዋል በበርበር በደንቀልዋላ በጀንዶ

በማስበርዳ ያለውን የጥንት ቅርፅ በርቶና በሁሉ እያስጠጋቹ ለአለም ህዝቦች በሙሉ አሳወቁ ።

እንደዚሁም የኢትዮጵያ ልጆች ለትምህርት ወደውጭ ሃገር ሲሄዱ በሃገራቸው ስለሚያለስሙትን ያላወቁትን ስለኢትዮጵያ በሙሉ ያውቃሉ ነገር ግን እኛም ከነሱ ይልቅ መመርመርና ማጥናት አለ ብን ስለሃገራችን ታሪክና ቅርጸ ቅርጽ በሰፈው እውቀን ለብዙሃ ህዝብ እናሳውቅ የሚል እያገኝም ቢገኝም የሃገሪቱ መሪዎች ሊገባ በርቀቸው ቀርተ የጥንት ታሪክ ብቻ የሚናገር ተመራማሪ ቢገኝ ይገድሉታል ስለዚህ ሁሉም የውጭ ሃገር ሰዎች የአፈላቸውን እያ ነበሩ ግን ዝምብለው አያልፉም ።

እህቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ሃገር ማለት እራሳችሁ ስለሆናችሁ የራሳችሁን ታሪክ ከራሳችሁ ተምራችሁና አውቃችሁ ለሌላው አስተምሩ እንጂ ታሪካችሁን ከሌላ አትማሩ እናንተ የራሳችሁን ታሪክ ካላወቃችሁ ሌሎች የናንተን ታሪክ እንዴት አውቀው ሊያ ንተን ሊያስተምሩ ይችላሉ በውጭ ሃገር ሰዎች የተጻፉት ሊሆን ይችላል ተብለው በግምትግ (በግምት) የተጻፈ እንጂ ከእውነተኛው ታሪክ የተገለበጠ አላገኘሁም እኔም ይህን የጥንትዋ የኢትዮጵያ ታሪክ የተገለበጠ ከቤመጽሃፈ ሲራክ ሉዳን እዋበሉ በንበርኩበት ጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ ከቤተክርስቲያን እንደሌለ ስለ ድንጋይ ቀብሩና ስለሌላም ስከታተል እንደምገኝ እያነበብኩ ሳለ ቀይ መደሚባለው ሃገር ሄጄ የጥንት ቤተክ ጀቢል ኩራርና ጀቢል አባ መቃብር እንዲሁ ከዚያም ጀበል ክርስቲያን ፍርስራሹና የክርስቲያን መቃብር አግኝተ ስሙ እንደ ለአንድ ሰባት ወር እንዳተቀመጥኩ እንደ ሽማግሌ ብለውኝ አባ ከለ ቀኛ ውስጥ የክርስቲያኖች መፅሐፍ አለ ብለውኝ አባ አገኘን እንደገና ብዙ በብራና የተጻፉና የተቀዳደዱ መፅሃፍቶች ቁርጥራጭ ካለምንን ቀኝ ሄደን ስንቆፍር ብዙ ቅሉቶችንና ቁርጥራጭ ከነዶችን መፅሐፍ ከነድ አንድ መቶ ስልሳ አራት ብራና የአክሱማይ ሲራክን መፅሐፈ የሱባን ቀዋንቋና የሱባን ታሪክ የያዘ መፅሐፈ ሱባኤ እንደዚሁም በጣም የረጃጅ ሁለት መቶ ብራና አራት መቶ ገፅ ያለው የኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክ በግዕዝ ቋንቋ ቤት ተፈልፍሎ የድንጋይ ቀዶ ከተልባና ከአመድ ጋር ተቀብሮ ተገኘ ።

መፅሃፈ ሱባኤ ከአዳም እስከ ቀዳማዊ ምኒሊክ መፅሃፈ አክሱማይ ሲራክ ከቀዳማዊ ምኒሊክ እስከ የዲት መፅሃፈ ታሪክ ነገሥት ትዮጵያ በግዕዝ ዘእንደበት የተጻፈ ከዮዲት እስከ በካፋ ልጅ ማዊ ኢያሱ ከዳግማዊ ኢያሱ ወዲህ እስከ ኃይለሥላሴ ማገበ

ሥላት ከመርጌታ ኀብሌ ጉጃም ሊበን ውስጥ ከተገኘ መፅሃፍ በብዙ ችግርና ድካም ለማሳተም ወደ ኢትዮጵያ በ1966 ዓ.ም ይዤው ገባሁ።

አጋጣሚ ነገር ሆኖ በመጥፎ ጊዜ ስለደረስኩ ምንም ለማድረግ ስላልቻልኩ ደብረ ሊባኖስ አጠገብ ከምትገኝ ደብር ስምዋ ገነተ ማርያም ከምትባል ቦታ መጽሃፉን ይዤ ሄድኩኝና ለማንኛውም ነገር ገልብጬው ቅናውን በዋሻ መቅበር አለብኝ ብዬ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ከዳደኛዬ ጋር በደብተር ገልብጠን ቅናውን ቀብሬ ወደ አዲስ አበባ ለማሳተም ሄድኩ በዚያን ጊዜ የነገሥታት ታሪክ ማን ሰቶና ማወደስ ይቅርና እንኳን ለማጻፍ እኔም ለህይወቴ አስጊ ስለ ሆነብኝ ቅጂውን ይዤ ወደ ጉጃም ሄድኩ ከዚያም ጊዜው እየከፋ በሙን ሰው እየበላው ስለሄደ በማውቀው መንገድ በመንበሬ ወደ ሱዳን ሄድኩ ከሱዳን አሁን ወደአለሁበት ሃገር አሜሪካ ገባሁ። ሁልጊዜ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማሳተምና ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማዳረስ ብዙ ጊዜ አስብኩ ግን ለጊዜው ሊሳካልኝ አልቻልኩም። አሁን ግን እግዚአብሄር ፈቃዱ ሆነና በመንፈስ ቅዱስ ወንድሞቼ በሆኑ እድ ማሰና በአይነኩሉ ካሳዬ ድካም ሊታተምና በገበያ ላይ ሊውል ችሏል። ስለዚህ እግዚአብሄር አምላካችንን በንፁህ ሀሊና ሳመሰግ ነውና በቀና መንፈስ ላገለግለው ይገባል።

እህቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ይህ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ የእኛ ታሪክ ስለሆነ በቀላሉ ልናየው እንችልም ብዙ ተፈላጊ ስር ዓቶችና ብዙ ስህተት የሆኑ ህጐች ቢኖሩትም ተፈላጊ ሥርዓት ከሆነ ብቻ ሳይሆን ከስህተት ብዙ መማር ማወቅ አለ የትኛው ወድቆ የትኛው መያዝ ያለበት የእኛ እንጂ የታሪኩ አይደለም ታሪክ ምን ግዜም ታሪክ ነው ምንም ዘመኑ ቢረዝምና ተረት ቢመስል ከታሪክ ነቱ አያልፍም ያው የጥንት ታሪክ ነው ስለዚህ ነው የጥንትዋ የኢ ትዮጵያ ታሪክ ብዬ የሰየምኩት ስለዚህ እውታችሁ ላላወቁት እስ ተምሩበት ቢታሪኩም እቀራረብ ሆነ የታሪኩን ቃላት በማቀናበር ለምትተባበሩኝ ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ ወደታሪኩ እስተላልፋችኋለሁ የናንተው

መሪራስ አ.አም በላይ

## ነገረ አዳም

አዳኙ መጀመሪያ ድምጽ ነበር በድምፅ በገድም ቃል ነበር የህይወት መንፈስም ከድምጽ ከሚገኘው ቃል ጋር ምትሶ ነበር ። ይህ ከድምፅ የሚገኝ ቃል በፈቃዱ ሰማያትንና አለማትን ፍጥረቱን ሁሉ በመፍጠሩ ፈጣሪ መሆኑ በፍጥረቶቹ ዘንድ ታወቀ ተረዳ ። ይኸውም ሰማያትና መሬት ይሁን ብሎ ፈጠረ ሁሉም ፍጥረት በእርሱ ሆነ ከሆነው ሁሉ አንድኛው እንኳን ያለ እርሱ የተፈጠረ የለም ሰማይና ምድር ነፋስና ውሃ መሬትና እሳት ፤ ፀሐይና ጨረቃ ፤ ከዋክብትም በውስጣቸው የሚገኙት ሁሉ በተፈጠሩ ቀን ልደታቸው ይህ ነው ።

ይህ ቅዱስ ቃል በፍጥረት ባህሪይ ሊመረመር የማይቻል ረቂቅ በፍጥረት አይን ሊታይ የማይቻል ስውር በፍጥረት እጅ ሊዳሰስ የማይቻል እሳት የእሳትነትና የእሳት መንፈስ ነው ህያው ነዋሪ ነው በዚህ ዓይነት ተጀመረ እይታውም ፍጥረቱን ይሁን ብሎ ከፈጠረ በኋላ ለፈጠረው ፍጥረት መኖሩን የሚያሳውቅ ሕይወትን አደለው ይህ ቅዱስ ድምፅ እውቀት ነው ቃልም ጥበብ ነው መንፈስም ማስተዋል ነው ። በእነዚህ ቃል ፍጥረት ተጀመረ እነዚህም ሶስት ስም ቢሆኑ በአንድነት በመለኮት አንድ አድራጊ ፈጣሪ አንድ አይከፈሉም አይለያዩም ።

ይህ ቅዱስ ፈጣሪ በቃሉ ምድርን ከመሰረተ መንፈሱ አለምን ከሞላት በኋላ እንዲህ አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር የባህር አሶችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ ፈጣሪም ሰውን በመልኩ ፈጠረ የእርሱን መልክ አስመስሎ ፈጠረው እንደፈለገ ሶስት አራት ባህሪያትን አዋህዶ ፈጠረው አራቱ ባህሪያት የተባሉት ነፍስ ሥጋና መንፈስ ናቸው ለእነዚህም አራት አራት የሆኑ መገለጫዎች አሏቸው እነዚህም የነፍስ መገለጫ ህይወት ልባዊነት ፤ ነባቢነት እውቀት ናቸው የሥጋ መገለጫ ነፋስ ፤ ውሃ ፤ መሬት ፤ እሳት ናቸው የመንፈስ መገለጫ ማስተዋል መመርመር እምነት ተስፋ ናቸው ።

አራት አበይት ባህሪያትን አስራ ሁለት መንገዶችን አንድ አካል አንድ ባህሪ አድርጐ አበጀው በርቀቱ እሱን የመሰለ በባህሪ ሥጋ ውን የሚመስል ነፍስና እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ ስለዚህ የመጀመሪያው በፈጣሪ ቃል የተፈጠረው ሰው አዳም ተባለ አዳም ማለት ሰማያዊ ያማረና የተዋበ መልክ መልካም ማለት ነው ለአዳምም ልጅነትን ሰጠው በእራሱ ማዕዘንና በምድር ያሉትን ፍጥረታት ሁሉ አስገዛው በንጉሣዊም አስለጠነው ልደቱም ነው ፈጣሪም በአዳም ከባድ እንቅልፍ ጣለበት እንቅልፍም ከገኑም አንድ አጥንትን ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው ፈጣሪም ከአዳም የወሰደውን አጥንት ሴት አድርጐ ወደ አዳም አመጣት አዳምም አለ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋዋም ከሥጋዬ ናት እርሷም ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል አለ ሴትም አላት ።

የሴትዮዋ ልደት ይህ ነው ። ከአዳም ጐን አጥንት ወስዶ መፍጠሩ ዘር ከተባት እንጅ ከእንስት አለመሆኑን ሲገልፅ ነው የአዳም እናት የምድር አፈር የሄዋን እናት የአዳም ጐን ናቸው ። ስለዚህ ሰው እናት አባቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሆነው ይኖራሉ ።

አዳምና ሴቲ መወደድ ባለው በምሥራቅ በኩል በገነት እኖሬቸው ፈጣሪ ከፈጠረው ሁሉ ደስ ያላቸው ዘንድ ከክፉ በቀር ያለ መከልከል ሰጣቸው ከሉ ነገር ከሆኑችው እንጨት ትእዛዝ ወሰናቸው ። ይህችም እንጨት ባይበሏት በጐ ቢበሏት ክፉውን የምታስታውቅ ናት ከእንጨቷም ቅጠሉን ሆነ ፍሬውን እንዳይበሉ ትእዛዝ ወሰነባቸው ይኸውም የፈጣሪና የፍጡር ልዩነት እንዲለ ትእዛዝንም የመፈጸም ሆነንም የመጠበቅ ምልክት ነው ። ከእንጨቷም ፍሬና ቅጠል የበሉ እንደሆን የሞት ሞትን ይሞታሉ ብሎ ትእዛዙን የፈጸሙ ሆኑን የጠበቁ እንደሆን የዘላለም ህይወት ይሆንላቸዋል ብሎ በዚህ ይጥንትና ክፋት ፈጣሪና ተፈጣሪ ህይወትና ሞት እንዲለ የመታወቂያ ምልክት ነው ። ሆኖም ግን አዳምና ሴቲቱ በትንና ሰርን ግን ስለተባለቱና ስለአፈረሱ ሞት ተፈረደባቸው አበይቱ ባህሪያት የተባሉት ነፍስና ሥጋ መንፈስም የሚለያዩ ሆነ ነፍስ ወደፈጠረው ህያው ወደሆነ ፈጣሪው ሲገባት ሥጋ ወደተገኘበት አፈር ሲመለስ መንፈስ ግን የቃል ኪዳኑ ተስፋ እስከሚፈፀም እንደተገለጠው ሥጋውን ይዞ ለዓለምኛው ደኢታ ይቆያል ። አፈር የሆነው ሥጋ የማይበሰብስ የማይፈርስ ሆኖ ነፍስን እንደገና ተዋህዶ በፈጣሪ ፈቃድ ይነሳል ያም ነፍስን እንደገና የተዋሀደው ሥጋ መንፈሳዊ ለበዓለም

የማይጠፋ ህይወታዊ አካል ሆኖ ይኖራል ። ትንሳኤውን በስጋ እንደምትቀበል የእንጨት ዘር የዘር ግብርና የደመባህሪ ግብር ባለው ፈሳሽ ዘር ላይ በእግዚአብሄር ፈቃድ ህያው የሆነ ነፍስ ከመጀመሪያ እንደተዋሃደው መረዳት ነው ። ይህ ቃል የሚረዳው ማስተዋልና መመርመር እምነትና ተስፋ የሌለው ምትሃታዊ መንፈስና ደመ ነፍስ ያለው አካል ነው ። ነገር ግን ሰው የፈጣሪውን መልክ እንደሚመስል ያለምሳሌ ሁሉ እንዳልተፈጠረ የሚያመለክት ብፁእ ሰው ነው በእሱ ዘንድ ሁለትና ቁርቁር ፈጽሞ የለበትም ።

የአዳምን ልደትና የነበረበትን ቦታ የአዳምን የህይወት ታሪክ ለማወቅ እንዲያግዝ በክፍሎቻችን ለመፃፍ በህሊናችን ውስጥ ለማንበብ በየጊዜው እንሞክር ።

ፈጣሪ የምድርን አራዊትና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ በምን ስም እንደሚጠራቸው ያይ ዘንድ ወደአዳም አመጣቸው አዳምም ለእንስሳት ለሰማይ ወፎች ለምድር አራዊት ሁሉ ስም አወጣላቸው እናንተ በሆናችሁበት ያርባችሁ ያብዛችሁ ብሎ ስም አው ጥቶ ሰይዳቸው አዳምም ለእንስሳት ሁሉ በስም እንደጠራ ስም ያው ሆን ። እንስሳትና አራዊት አስዋና ሁሉ ወደ አዳም ሲመላለሱ አግቶ መንፈስ በመንገዳቸው ሲሄዱ አያቸውና ከዛት ቀያችሁ ወዴትስ ትሄዳላችሁ አላቸው በየተራ እነሱም ከኤደም ወደ አዳም አሉት ጌታችን እባካችሁ እስከትሉኝ አብሬአችሁ ልሄድ ቢላቸው አዳም ጌታችን ረድኤት መልክ መልካም የፈጠረንን የሚመስል የአምላክ ዘጋና ክብር የተሰጠው ህያው ነፍስ ያለው ነው አንተ ግን ይህ ሁሉ ክብር የለህ ምንም አስቀያሚ ስለተቀኘ መንፈስ ነህ አሉትና ሁሉም አልፈውት ሄዱ የቃሉን አነጋገር የልቡን አስተሳሰብ አራዊት እንዳልተቀበሉት ሲያስብ ፈጣሪ አዩና እንዴት ተዋህዶ በህሊና አድሮ እንደሚገባ ሲያስብ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ተንኮለኛ የሆነው እባብ ብቻውን ሲመጣ አየውና ወደ እባቡ ተጠግቶ በለስላሳ ድምፅ ወዴት ትሄዳለህ አለው ። እባብም ወደ ጌታዬ ወደ አዳም ሲለው እባክህን አብሬህ ልሄድ ለእሱ እለው እባብም ጌታዬ አዳም መልክ መልካም ሰማዊ ክብር የተቀዳጀ ህያው ነፍስ የተዋሃደው ነው ያለው የፈጣሪ መንፈስ የተሞላው ህያው ነፍስ ያለው ነው በቃሉ አንተ ግን ተንኮልና ክፋት የተሞላህ አጋች ነህ እለው በቃሉም እስተ አጋች መንፈስ ክፉ ከሌላ ደግነት በምን ይታወቃል ውርደት ከሌላ ክፉ አግ ከሌላ መልክ መልካም በምን ይታወቃል ውርደት ከሌላ ክፉ አግ መንፈስ ከሌላ እውነተኛው የፈጣሪ መንፈስ መኖር በምን ይ ቃል ሞት ከሌለ የህያው ነፍስ ለዘላለም የሚኖር መሆኑ በምን

መቃል ያለ ሁሉ ሊታወቅና ሊወደድ የሚችለው እንዲህን የመሰሉ ሲኖሩ ነው ከቶ ስራ በከቶ ስራው ሲጠፋ መልካም ስራ በመልካም ሥራው ሲከበር ነው እኔ ተንኮለኛና ከቶ አስተሳሰብ ያለኝ እርኩስ መንፈስ ከሌለሁ የፈጣሪ ቅዱስ መንፈስ የተሞላው ሀያው ነፍስ መኖሪያ ለአዳም አይታወቅም ሲለው ነገሩን ተቀብለው የምትለው ሁሉ እውነት ከን ነው ብሎ አስከትሎት ሄዶ ማለት በሃሳቡ ጥበቱ በሀሊናው ሲመሳሰል ቀይቶ በልቡ አደረ በእእምሮው ተዋሃደ እሳቸ ነገር ላይ ምግረ የሚመስል ውስጡ የከቶ ከሃሞት የመረረ አሰታቂ ነው ቃሉን ስለአመነበት ከቶ ሥራ አሳስቦ በአዳም ላይ እንዲሰራ ከደሰታ ወደስቃይ ከህይወት ወደ ሞት እንዲመለስ በሁለቱ መደብ ላይ እንዲወድቅ አደረገው ሁለት መደብ ያሉናቸው ክብርና ውርደት ህይወትና ሞት ናቸው ።

ከቶ አስተሳሰብ የተዋሃደው አባብ ወደአዳም ሄዶ የሰማያትና የምድር ንጉስ ሰላምታ ይገባሃል ብሎ ሰገደለት አዳምም እንዴው አለው እኔ የምድር ንጉሥ እንጂ የሰማያት ንጉስ ሁላችንን የፈጠረ ፈጣሪያችን ነው አለው እባብም አዳም ነገሩን እንዳልተቀበለው አይቶ ወደ አዳም ሚስት ሄዶ ተንኮል በተሞላው አንደበትና ደስ በሚያሰኝ አነጋገር የሰማያትና የምድር ንግሥት ሰላምታ ይገባሻል ሲላት ደስ አላት ቃሉን ተቀበለችው ወዲያውን እሳቸ መንፈስ በእእምሮዋ ተሰራጨ እባብም ልያኛ የጠየኳት እንደሆን ታውቅ ብኛለች ብሎ ፈጣሪያችን ምን ብሎ ምንድን አትብሉ ብሎ አዘዘችሁ አላት ሔዋንም ለእባቡ አለችው በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬና ቅጠል እንበላለን ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፍ ፍሬና ቅጠል አትብሉ አትንኩት በዚያ እንዳትጠፉ ሞትም እንዳትቀምሱ ብሎ አዘዛል አለችው ።

እባብም ሔዋን እንዲህ አላት ከእርሱ በበላችሁ ቀን አይናች ችሁ እንደሚከፈቱ እንደፈጣሪም መልካምና መጥፎውን እንደሱ ፈጣሪ እንደምትሆኑ ስለሚያውቅ ነው እንጂ አትሞቱም አላትና ከዚያ ወደዛፉ ሄዶ ተሰወረ ።

ሔዋንም የበለስ ዛፍ ለመብል ያማረ ለአይን ያስጎመጀ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች ። ነገሩን ሰምታ በመረመረችው ጊዜ ፈጣሪ እየናለው ብላ ልበላ ልብላ አለኛት ከፍሬውም ወሰደችና በልታ ለባ ሏም ሰጠችው እርሱም ከእርሷ ጋር አንድ ጊዜ በሉ የሁለቱ አይናች ቸከፈቱ እራቁታቸውን እንደሆኑ ከብራቸው እንደተገፈፈ አወቁ

እርስ በርሳቸው ተጣፈሩ የበለስን ቅጠሎች ቀርጠው ያፍረታቸውን አለበሱ ከፈጣሪአቸው ትእዛዝ ወጡ እራሳቸውን አጥፊ ሆኑ ከገነት ወጡ ምድረበዳ ወረዱ መልካምና መጥፎ ደግና ክፉ ፣ ደስታና ሃዘን ወደሚፈራረቅበት ነው የሁለቱ አይኖች ተከፈቱ ማለት ህይወትና ሞትን ከፋትና መከራትን ለይተው አያውቁም ነበር ለዘላለም ለክብርና ለደስታ ብቻ ነበሩ የተፈጠሩ ነገር ግን ስለበሉ እንዚህን ሁሉ አዩ በነሱ ላይ መጣ።

አዳምም ከፈጣሪው ትእዛዝ ስለ ወጣ ፈራ እርስዋም ቀን በመሸ ጊዜ የፈጣሪ ድምጽ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ ሁለቱም ከፈጣሪ ፊት ለመሸሸት ሲሉ በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።

ፈጣሪ አዳምን ጠርቶ ወዴት ነህ አለው አዳምም አለ በገነት ውስጥ ድምፅህን ሰማሁ እራቁቴን ስለሆንኩ ከአንተ ፊት ሸሸሁ ተሸሸግሁም ፈጣሪም አለው እራቁትነትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ እንዳትበላ ከአዘዝሁህ እንጨት በውኑ በላህን አዳምም አለ ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ ፈጣሪም ሴቲቱን ይህ ያደረግሽው ምንድነው አላት እባብ አሳተኝና በልቼ ለአዳምም አበላሁት አለች።

ፈጣሪም እባብን አለው ይህን ስላደረግህ የተረገምክ ትሆናለህ በሰው ልብ ገብተህ እንዳሳትከ በሆድህ ትሄዳለህ አለው ለሴቲቱም አለ በፀንስሽ ጊዜ ጭንቀትሽን አበዛለሁ በጭንቀትም ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል ለእርሱ ተፈጥረሻልና የወለዱሽን ትተሽ ለእርሱ ትገዢለሽ ከእርሱም ተወስደሽ ትኖሪያለሽ አዳምንም አለው የሚስትህን ቃል ሰምተሃልና ከርሱ እንዳትበላ ከአዘዝሁህ ዛፍ በልተሃልና ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን በህይወትህም ዘመን ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ እሾህና አሜኬላን ታበቅልሃለች የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ ምግብህን ከአፈር ስለመጣህ አፈር ነህና ወደአፈር ትመለሳለህ አለው።

አዳምም ፈጣሪዉ እግዚአብሔር ሆይ የሥጋዬን ሥራ ከአፈር ስለ ፈጠርከኝና ወደአፈር እንድመለስ ነገርከኝ በርቀትህ አንተን በበደልም እኔን የመሰለው ከሥጋዬ ጋር አዋህደህ የፈጠርከውን ነፍሴንስ አለው።

ፈጣሪ አምላክም አለ የሰጠሁህ ሴት እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝ ስላልከው ከሴት ልጅህ ያለዘር ተወልጄ ከዛፉ ስለበላህ በዛፉ ግንድ ተሰቅዬ የምትከውን ሞቼ ያዳታችሁን አሳች እርኩስ መንፈስ በፍ ቅርና በትህትና ድል ነስቼ ከአንተ የተነሳ በተረገመችው መሬት ነፍስህን ካስታቂ ሲኦል ወደገነት አግብቼ ከብርሀንና ደስታህን እወ ርስሀለው ። ያኔም ነፍስህ እንደ ሥጋህ ዳግመኛ ኀጎትን አያይትም በዚች የተሰፋ ቀን እኔ እንደተነሳው ሁሉ በፍጻሜ ቀን ነፍስህን ከሥጋህ ጋር አዋሀጄ ዳግመኛ የማይሞት የማይበሰብስ መንፈሳዊ ሥጋ ሆኖ ይነሳል ነገር ግን የዘርህ ነፍሶች ከሁለት ይከፈላሉ መል ካም የሠራ እንደሥራው ወደማያልፈውና ወደማይጠፋው መንግስተ ሰማያት ለዘላለም ለደስታና ለክብር ወደ ተዘጋጀላቸው ይገባሉ ። እነዚህም ሰማያት የተባሉ አዲስ አለሞች ሰባት ናቸው ። አርያም ፤ ኢዮር ፤ እራቂ አርያም ለሰው ልጆች ሶስቱ ኢዮር ትርጓሜው እንዳስ ቀመጠው ለባዊና ነባቢት ህያውና /እውቀት/ ዋብባዊ ነፍስን ፈራጅ ሥጋ ላላቸው ነው ። እነርሱም ሙታው ይነሳሉ ሞት የተዘጋጀባቸው በአንገት የተነሳ ስለሆን ሁሉም ሞትን ቀምሰው እንደገና ይነሳሉ ።

ሁለተኛው ክፍል ዘርህ በአንተ የተነሳ ክፋትንና ሃሰትን ስለ ወደደ እንደክፋት ሥራው እስተያሚና እሥቃዩ ወደሆን ለሁለተኛ ሞት ወደገሃነም እሳት ከአሳተውና ከአስተማረው ከእርኩስ መንፈስ ጋር ይወርዳል ለዘላለም በማይጠፋ እሳት በማያንቀላፋ ትል ተከቦ ይኖራል ይህ ሰው ልጅ ዳግመኛ መንፈሳዊ ሥጋ ለለበሰ ሁሉ እወ ቃሌ ይሆናል ይህ ሊሆን ግድ ነው ።

የምታያቸው ሰማይና መሬት የዘርህ ነፍሶች እስከ ትንሳኤ የሚቆዩበት ሲኦልና ገነት ይጠፋሉ እማያልፉት ለዘላለም የሚኖሩት የአንተ ዘርና የመላእክት ነገድ መንግስተ ሰማያት ገሃነም እሳት አያልፍም አይጠፋም ለዘላለም ይኖራል ይህ ተስፋሁና መዳኛህ ስለሆነ በዘርህ ልብ ይፃፋል መንፈሴን በሁለተኛው ዘርህ ለእያን ዳንዱ እንደ አገልግሎቱ እሰጠዋለሁ ። እስከዛና ቃል ኪዳኑን የሚሰ ብክት ብሩህ በሆነ ድንጋይ ላይ ለፈስት ተሰወረ ይህም ቃል ከድምፅና ከመንፈስ ጋር ሁኖ ይሰማውና በመንፈሱ ያየው ነበር አምላክም ለአ አዳም መልካምና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደአንዱ ሁኑ እሁ ንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞ ከህይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘላለም ህያው ሆኖ እንዳይኖር ስለዚህ አምላክ ከገነት አስወጣው የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ ወደህይወት ዛፍ የሚወስደውን ሰው

ጠባቂት ኪሩቤልና የሚገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በገነት ምስራቅ
አስቀምጠው የነበረበትን የደስታ ቤታ በሰሙ ኤዶም ተባለች ።

ከዚያም አዳምና ሚስቱ ወደ ምድረ ፋይድ ወረዱ ምድረ ፋይድ ማለት የፍዳ መቀበያ የሀዘንና ደስታ ፣ ልቅሶና ሳቅ መወለድና መሞት መብቀልና ፣ መድረቅ ማበብና ፣ ማፍራት የሚታዩበት እንደ ዚሁም አዝመርና ረሃም ፣ ቀጭንና ወፍራም ፣ ደግና ግብታም ፣ ደካማና ሃይለኛ የሚታዩበት አድልዎና በለት የሚገኝበት ምድር ነው ።

አዳምም ለሚስቱ /ሄለስማዋ መዋር/ ሄዋን ብሎ ስም አወጣላት ሄዋን ማለት ህይወት ወይም በእውነት በሰማዊ ኑሮ ማለት ነው ይሄውም ከሰስቱ ድምፅ ቃል መንፈስ እንደኛው ቃል የተወለደው እግዚአብሔር በአሉዋ በኩል ለመጣው በሀጢአት ከሴት ልጁ ያለ ሰለው እምላክ በእሱዋ በኩል ለመጣው ልጁ ምክናያት እንደሆነ ፋካቢና ያስወር መወለዱንና በተወለደው ልጁ ምክናያት እንደገና እምላክ የሰው ህይወት ማግኘቱን እውቂልና ሄዋን ህይወቴ አላት እምላክ የሰው ህይወት ማግኘቱን እንድ ሁንውም ኖሩ ።
ቅን እንቁ አርጊ ማጫ ብሎ ሰጣት እንድ ሁንውም ኖሩ ።

አዳምም ሚስቱን ሄዋንን አወቀ ወነሰችም ቃየልንም ወለደች እርሱም ወንድ ልጅ ከእምላኬ አገኘሁ አለች ደግሞም ወንድሙን አቤልን ወለደች አቤልም በግ ጠባቂ ነበር ከብዙ ቀን በኋላም ቃየ ልን ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መስዋእትን አቀረበ አቤልንም ደግሞ ከበጉቹ በኩራትና ከስቡ አቀረበ ። እምላክ ፊጣሪም ወደ አቤልና ወደ መስዋእቱ ተመለከተ ወደ ቃየልና ወደመስዋእቱ ግን አልተመለከተም ቃየልም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ እምላክ ፊጣ ሪም ቃየልን አለው ለምን ተናደድህ ለምንስ ፊትህ ጠቆረ መልካም ባታደርግ ግን የጠ ባታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን መልካም ወደአንተ ነው አንተ ግን በእሷ ላይ እት በደጅህ ታደባለች ፊቃድዋም ወደአንተ ነው አንተ ግን ሴቱ ንዓበተ አለውና የፈጣሪ የድምጹ ቃል ከእሱ ፊት እንዲተቀበለ አቤል ቃየልን የወንድሙን አቤልን መስዋእት እምላክ እንደተቀበለ ወደ ቀናበት ተንኮልም በልቡ አደረ ከዚያም ወደምድረ ፋይድ ወደ ወርደው ምንም አጠገብ ቆሞ ሲናደድ ሳለ ሁለት ጥቁር እሞራዎች ሲጣሉ አየ ከዚያ እንዱ ወደምንጩ ውሃ ሲጠጣ እንደኛው የተ ላቶ ያለውን ድንጋይ ቢገፋው ተንከባሎ ከምንጩ ሲጠጣ የነ ቅቶ ጎነበሰውን እሞራ መታና ሲገድለው እያና ሞት እንዳለ አወ ቃየልም ወደ አቤል ሄዶ ና ወደ ሜዳ እንሂድ ከዚያም ከምንጩ ውሃ እንጠጣለን አለው ሁለቱም ወደ ምንጩ ወረዱና አቤል ሲጠ ተጉንብሶ ሳለ ቃየል ድንጋይ አንስቶ አቤል ወንድሙን መት ገደለው ።

እግዚአብሔር ፈጣሪም ቃየልን አለው ወንድምህ አቤል ወዴት ነው እርሱም አለ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን አለውና ምን አደረግህ የወንድምህ የደሙ ድምፅ ከምድር ወደ እኔ ይጮሀል አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ ምድርንም ባረስክ ጊዜ እንግዲህ ሃይሏን አትሰጥም በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ ቃየልም እግዚአብሔር አለው ኃጢአቴን ልሸከማት የማልችላት ታላቅ ናት እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ ። የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል እግዚአብሔር አለው ከእንግዲህ ቃየልን የገደለ ሁሉ ሰባት እጥፍ ይበቀልበታል ፤ እግዚአብሔርም ቃየልን ያገኘ ሁሉ እንዳይገድለው በግራ እጁ መዳፍ ምልክት አደረገበት ቃየልም ስሙ ቃየል ተባለ ከእግዚአብሔር ፊትም ወጣ ከኤደንም በስተምስራቅ ወጥቶ በኖድ ምድር ተቀመጠ ሚስቱም አገባና ሄኖህን ወለደች በባህር ዳር ውስጥ ለውስጥ ከተማን ሠራ ከተማዋን በልጁ ስም ሄኖህ አላት ሄኖህ ማለት ሰላም የሆነ እረፍት ተስፋ ማለት ነው በሱባ ቋንቋ አዳምም እንደገና ሚስቱን ተገናኛት ። ወንድ ልጅም ወለደች ስሙንም ቃየል በገደለው በአቤል ፈንታ እግዚአብሔር ሌላ ዘር ተክቶልኛል ስትል ሴት አለችው ለሴት ደግሞ ወንድ ልጅ ተወለደለት ስሙንም ሄኖስ አለው በዚያን ጊዜም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ተጀመረ ሄኖስ ማለት ሰላማዊ ተስፋዎች ማለት ነው ። በሱባ በልጅ ልጃቸው የእግዚአብሔር ተስፋን ያያሉና ተስፋ አደረጉ ።

አዳምም አባታቸው ሁለት መቶ ሠላሳ አመት ኖረ ልጁንም በምሳሌው እንደመልኩ ሴትን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ አመት ሆነው ሴቶችም ወንዶችንም ወለደ ሴት ልጆቹን ለወንድ ልጆቹ ኪጋባና ልጅን በተራቸው መውለድና መተካት ሲጀምሩ እድሜውን አይቶና ጠግቦ ሞተ የኖረበትን ዘመን ሁሉ በጠቅላላ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ አመት ነው የአዳምም የህይወት ታሪክ ከመዘገፈ ሱባኤ ከሱባ ቋንቋ ወደ አማርኛ የተተረጎመው ይህ ነው ። የኖሩበትንም ምድር ኤደምያ ይባል ነበር ይሄም ከሁለተኛው ኤደምያስ በስተምስራቅ የሚገኘው ምድር ነው በዚያም ምድር ሙት ባህር በስተ ምእራብ በኩል ነው ።

ሥላሴዎች ለአዳምን ማጫ ያደረጉት ዘንድ እንቆ አርአያና እን ቃየንን አቤልም ኢያሞያስ ለተባለው ለአዳም ሰጡት አዳምም ለአዳምን እንቀበርያን ሚስት እያፈራት ሄዋንም ለአዳም ወንድ ልጅ ወለደች በመንግሥ ምትክ ሰጉል ሴት አለችው ሴትም የሰላም ተብሎ የተባለውን ሄኖስን ወለደ ሴትም የእግዚአብሔር ምሳሌ እስኤል ተብሎ 912 ዓመት ኖሮ አንቀላፋ ሄኖስም ቃየንና እሳዬ ባልቤት የተባለውን ወለደ ሄኖስ ኢልሄና የእምነቱ ሰላም ተብሎ የኖረበት ዘመናት 905 ነው ።

ቃየንና የእግዚአብሔር አመቀት የተባለው መላልኤልን ወለደ ቃይናን ቁምይና የነሳ ሰው ተብሎ 910 ዓመታት ኖሮ አንቀላፋ መላልኤል ድምፃዊ የተባለውን ያሬድን ወለደ መላልኤል የእምነቱ ኃይል ላልኤል ተብሎ 895 ዓመታት ኖሮ አንቀላፋ

ያሬድ ማስረጃ የተባለውን ሄኖክን ወለደ ያሬድ የፈጣሪ ድምፅ ያሬኤል ተብሎ 962 ዓመታት ኖሮ አንቀላፋ

ሄኖክ ደገኛ የተራራ ሰው የተባለውን ማቱሳላም ወለደ ሄኖክ የእምነቱ ቃል ኪዳን ሄኖኤል ተብሎ 365 ዓመታት ኖሮ እንደልባ ተነ እንቀላፋ

ማቱሳላም ዘንካራ የተባለውን ላሜህን ወለደ ማቱሳላ የፈጣሪ ድምፅ ኤልሬ ተብሎ 969 በዚች ምድር ኖሮ አንቀላፋ

ላሜህ እረጅም እረፍት የተባለውን ኖህን ወለደ ላሜህ ላሜኤል ተብሎ የኖረበት ዓመታት 747 ነው እርሱም እንደአባቶቹ አንቀላፋ

ኖህ የፀደይ ሙቀት ወይም በሰብ ልጅ ሰላም የተባለውን ሄም በኖህ ዘመን በምድር ላይ ወለደ እንደዚህም ሆኖ ኖህኤል በተባለው የእግዚአብሔር የሚኖሩ ሁሉ በክፋት ቀሞሉ ስለዚህ ኤል የተባለው ሃሳብ እንደ ምድር እንደተበላሹ ሥጋ የለበሰው ሁሉ በምድር ላይ ሃይቅ በሎ ተበላሽ እየና ሊያጠፋው ፈቀደ ሆኖም ግን ኖህ ፍጹም ፃድቅ ሰው እንደሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በለአደረገ እይታ የፍጥረት ዘር እን

ላይጠፋ ቢል ኖህን እንዲህ አለው አንተ በእኔ ዘንድ ምኅረትን ስለአገኘህ ከጥፋት እንድትድን መርከቡን ሥሩ እኔም በከተማዎቹ ሥራ የተነሣ ምድር በግፍ ተሞልታለችና ስለዚህ ከሰማይ በታች የሕይወት ነፍስ ያለውን ሥጋ ሁሉ ለማጥፋት በምድር ላይ የጥፋትን ውሃ አመጣለሁ በምድር ያለው ሁሉ ይጠፋል ቃል ኪዳኔም ከአንተ ጋር አቆማለሁ ወደ መርከብም አንተ ልጆችህንም የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ትገባለህ ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ሕይወት ነፍስ ካለው ሥጋ ሁሉ ከየወገኑ ተባእትና እንስት ሁለት ሁለት ታገባለህ ምግባቸውንም ታዘጋጃለህ ለአንተም ለእነርሱም መብል ይሁን አለው ኖህም የእግዚአ ብሔርን ቃል ሰምቶ እንዳዘዘው አደረገ ።

ኖህም እግዚአብሔር ግባ ባለው ቀን ወደመርከቢቱ ገባ የጥፋ ትም ውሃ በምድር ላይ አርባ ቀንና ሌሊት ነበረ ውሃውም መርከ ቢቱን አንሳት ከምድር ከፍ ከፍ አለች በምድር የሚኖሩ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ጠፉ ።

እግዚአብሔርም በምድር ላይ ነፋስን አሳለፈ ውሃውም ጉደለ መርከቢቱም በመቶ ሃምሳ ቀን በአራራት ተራራዎች መካከል ተቀመ ጠች ኖህም የመርከቢቱን መስኮት ከፈተ ቁራንም ላከው ነገር ግን ስላልተመለሰ ርግብን ላከ እርግብም የወይራ ቅጠል በአፍዋ ይዛ ተመለሰች ።

እግዚአብሔር ለኖህ እንዲህ ብሎ ነገረው አንተ ሚስትህን ልጆች ህን የልጆችህን ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ አብረው ያሉት ሁሉ ይውጡ በምድር ላይ ይብዙ ይዋለዱ አለ ኖህም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ኖህ ለእግዚአብሔርም መስዋእትን አቀረበ እግዚአብሔርም የኖህን ልጆች ባረካቸው እንዲሁም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት አስ ፈሪነታችሁ በምድር አራዊትና በሰማይ ወፎች በባህር አሶችም ይሁን በእ ጃችሁ ተሰጥተዋል መብልም ይሁናችሁ ነገር ግን ነፍስና ደሙ ያለበትን ሥጋ አትብሉ የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ ይፈሳል እኔ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሬዋለሁና አላቸው ።

እግዚአብሔር ኖህን አለው በእኔና በእናንተ መካከል ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳኔ ምልክት ይህ ነው ቀስቴን በደመና አድ ርጌአለሁ የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል በምድር ላይ ደመናን ቢጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመና ትታያለች በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘለዓለም ቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው አለው ።

ከመርከብ የወጡት የኖህ ልጆች ሴም ፥ ካም ፥ ያፌት ናቸው ።

ኖህም የ600 ሰው እድሜ ነበር ። ኖህም በምድር ገበሬ መሆን ጀመረ ልጆቹም እንደዚሁ ታናሹ ልጅ ካም የከነአን አባት ወይን ተከለ እኅቶቹንና ወንድሞቹን ከነልጆቻቸው ኑ ብሎ ሰበሰበ እንዲሁም እኅ ቶቹ አንድ ቀን ከእኔ ቤት ከሴም ቤት አንድ ቀን ከያፌት ቤት ቸው አንድ ቀን ከእኔ ቤት ተሰብስበን የወይን ጠጅ እየጠጣን እንድናደርግ ከልጆቻችንም ቤት ተሰብስበን የወይን ጠጅ እያደረግን እንጠጣ እባካ ችንም ደስ ይበለው ስመንም ማህበር እንበለው አላቸው እነሱም ሊሞክሩ ተስማምተው የማህበር ድግስ እንዲዘጋጅ በየተራ አደረጉ ።

ከዕለታት አንድ ቀን በካም ቤት ማህበር ተደረገና አባታቸው የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ በድንኳኑም ደጃፍ እራቁቱን ሆኖ ሸና ከነአንም እየመና ማቀበት ካም አባቱ እራቁቱን እያየው ከሔደ ሄደና ለወንድሞቹ ተናገረ ሴምና ያፌትም ሸማ ወስደው አለበሱት በበነጋታው ኖህ ከወይን ጠጁ በነቃ ጊዜ ታናሹ ልጁ ያደረገበትን አውቀ እንዲሁም አለው በቤትህ አትዘባበት ልጅህ በአንተ አይመጣ ከነአንንም እያቶ እንዲህ አለው ከነአን ርጉም ይሁን ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይሁን ሴምንም እንዲህ አለው የሴም አምላክ እግዚአብሄር ይባረክህ እግዚአብሔርም ያፌትን ያስፋ በሴም ድንኳን ይደር ከነአንም ለእነርሱም ባሪያ ይሁን አለው ።

ኖህም የኖረበት ዘመን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ሆነውና ሞተ ።

የካም ልጆች ኩሽ ፥ ምፅር ፥ ፋጥ ፥ ከነአን ናቸው ። ካም ከማእሌ ተላቆ የኖረበት ዘመን ሰባት መቶ ሰባ ሁለት ነው ። እነርሱም በአ ራት ዋሻ ላለ እድሜን ጠግቦ ሞተ ። ታላቁ ልጁ ኩሽም ከአፍሪቃ እስከ ኤርትር ባህር ድረስ ድንኳን አስተከለ ልጆችንም ወለደ ስሙም ኤል ዘቦ ተባለ ያኔም ሃገር የወርቅ ሃገር ስለሆነ በስሙ ኤልዘቦ አለው ።

የኤልዘቦ ልጆች ሳባ ፥ ኤውላጥ ፥ ሰብታ ፥ ራዕማ ፥ ሰበቅታ ናቸው ።

ሳባም ሳቢስ ፕርዋኢኤል ተባለ በአዜብ መኖሪያውን አደረገ ሳቢስ የከሀኑቱን ስም ኑናኤል የተባለውን ኑባኩንግ ወለደ ኑባኩንግ ካሲዋኢኤል የተባለውን ጋናንን ወለደ ናሁመልክ የተባለውን ኢታን ወለደ ኢታን የንጉሶቹ አባት አበመልክስ የተባለው ናምሩድን ወለደ ናምሩድም በምድር ላይ ታላቅ ንጉሥና ሃያል ሆነ አበመልክስ የተባለው ናምሩድ በምድር ላይ ሃያል በሆነ ጊዜ ግብፁን ከግዮን እስከ አፍሪቃ በአለው ህዝብ ላይ ጣለ እንዲሁም አላቸው በሲናኦር አገር ከተማን እንስራ ብሎ እወጀ በዚያም ካልዳቲ እርጌድ ኤሬክን አበራ ሰሉት ከተ

ሞቹ በተሰሩ በሰባ አምስተኛው ዓመት የሰው ልጆች ቋንቋ ተደባልቆ እንዱን እንዱ አልሰማው አለ ሁሉም ለየብቻው አዲስ ቋንቋ ፈጠረ ሁሉም ለየብቻው ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ተሰደደ በዚያን ጊዜ ናምሩድ ከተማዋን ባቢሎን አላት ከዚያም ልጆቹን ይዞ ወንድሙ ንእስርን እስከትሎ ወደነነዌ ሄዶ ከዚያም ካለህን ሰራ አቢመለክስ የተባለው ናምሩድ የመንግሥቱን ዙፋንም በነነዌ እና በካለህ መካከል ተከለ ስሙንም ሬሴን አለው ሬሰንም ታላቋ ከተማ ተባለ ይኸም የረዘባት ህዝብ ከተማ ናት ።

ናምሩድም የኖረበት ዘመን መቶ ሃምሳ ዓመት ነው ሞተ በፈንታው ልጁ አዳግዱግማልቲ ተብሎ ነገሠ እዳግ በሃያ አንድ ዘመን መንግስት ስለሞተ ልጁ ሬፈልባ ሬፈኤል ተብሎ ነገሠ ሬፈኤልም መቶ ሃያ አምስት አመት ኖሮ ሞተ ልጁ ቁናህ (ኪና) የንጉሥ አባት አቢመሌክ ተብሎ በሬሴን ነገሠ በሬሴን ሳለ ታላቁን ልጅ ጌራራን ወለደ በልጁ ስም በኤልዳዮና በሱር መካከል ጌራራ የምትባል የታላሰች መንደር ከተማ አድርጎ ሰራ አቢሜሌክ በጌራራ ብዙ ዘመን ኖረ ልጁንም ጌራራ የንጉሶች ንጉስ የአዋቂዎች አዋቂ አድርጎ ወደከነአን ምድር ላከው የኢልዛቦ ንጉስ ቴድአል የኤላም ንጉስ ኮለዶ ጎመምር በከነአን ምድር ለተቀመጠው ጌራራ ግዞ በረከትን አመጡ የንጉሶቹ ንጉስ እንተነህ ሲሉ ሰገዱለት የዕደምም ህዝብ ተገዛለት ነገሥታቱም በየጊዜው እየመጡ ከእግዚአብሔር ካህን ከራጌ ተባርከው ይሄዱ ነበር ።

ጌራራም ከተማን ሠራ ስምዋንም በሚስቱ ስም ሳሌም አላት ሳሌም የራእይ ከተማ ናት ።

በግልም ለጌራራ ሶስት ወንድ ልጆች ተወለዱለት እነዚህም የቴድአልን ልጅ ሲኖን አግብቶ የኢልዛቦ የአዜብ ንጉስ የሆነው ኢትኤል በባቢሎን የራቢ ንጉሥ የሆነው ሃሙኤል በአባቱ ስም አቢሜሌክ ብሎ የሰየመው የፍልስጥኤል ንጉስ ሜሌክ ናቸው ። ሜሌክ በአባቱ መንግስት የተቀመጠና ወራሽ ሆኖ የቀረ ነው ።

እንደዚህም ሆኖ ጌራራ የነገሰታት መግናኛ ሆኖ ሀገንም ስርአትንም እያሳየ በሳሌም ከተማው ተቀምጦ ሳለ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደራማ ተራራ ኢትኤልንና ሃሙኤልን ይዘህ ውጣ በዚያም ለእምላክህ መስዋዕት አቅርብ አለው ።

ጎልጎታም እንደተባለው ሊጀቹንና ያልተሸለተውን በግ ይዞ ወደ ሪማ ተራራ መጣ ከዚያም ለአምላኩ የበግ መስዋእት አቀረበ የበጉ መስዋእቱንም አምላኩ ተቀበለው የታረደውና በእሳት የተቃጠለው መስዋእት ሆኖ የቀረበው በግም ከሞተበት ተነስቶ እንዲህ አለ የአ ስዐበት ቦታ ቅዱስ ነውና የሰላሙ ንጉሥ እስከሚመጣ በዚሁ ቆይ አንተም የእግዚአብሄር ከሀን የእውነት ንጉሥ ትባላለህ ። ስለዚህ ስምህ መልከጼዴቅ እንጂ ጎራራ (ጎራናጊ) አትባልም ።

ሃሙኤልንም አለው በኤፍራጥስ ወንዝ በባቢሎን ከተማ የራቢና የረሆቦት ንጉስ ሆነህ ትኖራለህ ስምህም የሙራቢ ትባላለህ ።

ኢትኤልንም አለው ግዮን በሚፈስበት ምድር ትኖራለህ ስምህም ኢትዮጵ ትባላለህ አላቸውና ወደ ሰማይ ሲአርግ እያዩት ባለ ንም መጣቸና ሽፍና ከሪማ ተራራ ሃሎ ወደሚባል የወይን ቦታ አወረዶቸው ከዚያም የያዙትን የወርቅ ገንቦና የወርቅ መሶብ ቢያዩት በገንቦው የወይን ውሃ በሞሶቡ የስንዴ ሀብስት ሞልቶ አገኙት መልከጼዴቅ የእግዚአብሄር ከሀን ከዛሬ ጀምሮ መስዋእት በስንዴ እንጀራና በወይን ጠጅ ይሁን እንጂ ለእግዚአብሄር የበግ ወይም የሌላ ደም አፍስሰን አናቀርብም ሲል ለልጆቹ ሥርዓት አስተማረ በዚህን ጊዜ የአብራሞ ነገድ የሆኑ ስሙ አብራም የተባለ ከለዳዊ ገወምርና የቢታኞቹን ነገሥታት ድል አድርጎ እንደሀጋቸው ወደ መልከጼዴቅ ሲባረክና አስራትን ሲሰጥ መጣ መልከጼዴቅም አብራም የእግዚአብሄር ሰው እንደሆነ በመንፈስ አይቶ የስንዴ እንጀራንና የወይን ጠጁን ይዞ ሊቀበለው በሴዊ ሸለቆ ወጣ በዚያም ተገናኝተ ባረከው እንዲህም አለው የእግዚአብሄር ሰው አብራም ሆይ ሰማይና ምድርን የሚገዛ ታላቁ አምላካችን የተመሰገነ ቅዱስ ነው ። ጠላቶችህንም በእጅህ የጣለልህ ታላቅ አምላክ የተባረከ ጌታ ነው አለው የእግዚአብሄርንም መስዋእት አቀረበለት አብራምም አምላኩን አመስግኖ አብር በላ ለሳሌሙ ንጉሥ ለእግዚአብሄር ከሀን ከሁሉ አሥራትን አውጥቶ ከአባቶቹ የተረከበውን እንቁአርያ በረከት ብሎ ሰጠው መልከጼዴቅም ሰምቶን ሰጠኝ ወርቁንና ከብቱን አንተ ውሰድ አለው አብራም ግን ሰማይና ምድርን ወደሚገዛ ወደታላቁ አምላኬ እሌ ሻዳይ እጄን ከፍ አድርጌአለሁ ስለዚህ አንተም ባለጠጋ አደረግ(ሁት) እንዳትል ብላቴኖቹ ከበሉትና ከጠጡት ቢቀር ከአኔ ጋር ለመጡት ከጀዴት በቀር ከአንተም ከምርኮዎችም ሃብት እንደማልወስድ አወ ሁሉም ድርሻውን ይውሰድ ብሎ ከግሌምና ከሴዊ ሸለቆ ተነስቶ ወደ መምሬ አድባር ተመለሰ ።

ከሰለታት አንድ ቀን እንደዚህ ሆነ ሰቡቱ ተንስተው ሄሎ ወደ ሚባለው የወይን ቦታ ወረዱ መስእዋትንም ለእግዚአብሔር አቀረቡ ከዚያም አብራም ለመልከጼዴቅ አስራት ብሎ የሰጠውን እንቁ አርያ አንድ መደብ ሀብስት የያዘው የወርቅ መሶብ አንድ መደብ ወይን የያዘው የወርቅ ገንቦ አንድ መደብ ከሶስት መድበው አጣ ተጣጥሰው ቢካፈሉ እንቁአርያው ለኢትኤል የወርቁ መሶብ ለአባ ታቸው ለመልከ ጼዴቅ የወርቁ ገንቦ ለሃሙኤል ደረሰ ።

መልከጼዴቅም እንዲህ አላቸው ትንቢትም ተናገረ አንተ የጣ የን ወሃ የምትጠጣ እንቁአርያ የደረሰህ የያዝከውን እንቁአርያ ከም ድር ከምታገኘው ሉልና የከበረውን ፍቅ እንቁ ከወርቅ ያመሌግል ጋር ይዘህ መጥተህ ለአምላክህ ለጌታህ ጋዳ አቅርብለት ከርቤና እጣን አምጥተህ አጤስለት በፊቱም ሰግድለት ይኸም የምትሰግድለት ሰው የሰላምና የደህንነት ንጉስ ነው አለው ኢትኤልም እንዴት እርሱ የሚመጣበትን ጊዜውን ቀኑን ሳውቀው እችላለሁ መልከጼዴ ቅም አለ እርሱ ጌታ እስከሚያመለክትህ ቀን ድረስ እንቁአርያውን ተመልከተው አራብ ዘመን ሲሆን ይጠቁራል ይዘጋል ። የበረከት ዘመን ሲሆን መልኩ ይጠራል ። እንደዚህ ጊዜውን የሚነግርህና የሚመራህ የጉጋት ኮከብ እስከምታየው ድረስ በሀሊናህ ያፈው በአንደበትህም ተናገረው በልብህም አስተምጠው አለው ሁሉም እየተንስ ትንቢት ተናገሩ በመጨረሻ መልከጼዴቅ ለኢትኤል እን ዲህ አለው እርስትህም ምድርህም ግዮን የሚፈስበት ምድር ነውና ሚስትህን ልጆችህን ይዘህ ወደ ግዮን ምድር ሙጣ አንተ ታናሹ ልጄ ሃሙኤል እርስትህም ምድርህም ኤፍራጥስ ወንዝ የሚፈስበት ምድር ነውና ወደ ኤፍራጥስ ወንዝ ውረድና ሚስቶችህንና ልጆችህን አስፍርበት ለዘላለም የወይን ውሃ ከበዶ ከገንቦ እንደተገኘ ከበዶ ምሬት በወጣ ውሃ ትከበርአለህ እኔ ግን የዘላለሙ አባት እስከሚ መጣና የዋርዳኖስን ወንዝ የሚፈስበትን ምድር ይዤ ከመጨረሻው ልጄ ጋር እኖራለሁ ። ብሎ አባትና ልጆቹ ተለያይተው ወደ የክፍል ሃገራቸው ሄዱ ከኢትኤል ታሪክ ተመልከት ።

## ምዕራፍ ሶስት

ኢያስኤድ ፡ ኢ፤ የኢትዮጵያ ዘመነ መንግሥት

ስሙ ፡ እልፋ እየን እማን ኤል ኢያስኤድ

ፊደሉ ፡ /ኢ/ /ኢ/ /ኢ/ /ኢ/ /ኢ/

/ኢትኤል ማለት የእምነት ስጦታ ኢትዮጵ የወርቅ ስጦታ ማለት ነው ።/

የክህነቱ ስም /ኢትኤል የተባለው ኢትዮጵ የአበ መልከስ ናምሩድ ወልደ የልጅ ልጅ ነው ። ናምሩድ እላማን ወለደ ፤ እላማ ፡ ራፋኤልን ወለደ ፤ ራፋኤል ወይም ኬናን ወለደ ፤ ኬና ወይም ቀና ጊራራን ወለደ ፤ ጊራራ ወይም ንጉሥ ያመሠበ የክህነት ስም መልከጸዴቅ የተባለው ታላቁ የስሙም ንጉ ኢትን ወለደ ኢትም እንደአባቱ ሰና የእምነት አገልጋይ በደብረማለም ታላቅ ተጎጅ ስለነበረ ኢትኤል ተባለ እምነቱን ወዳድና ለፈጣሪው ማለት ነው ።
ኢትኤል ማለት የእምነት ስጦታ ማለት ነው ።

ኢትኤልም በእምነቱ መንፈስ እየተመራ ግዮን ወንዝ ወደሚፈስበት ምድር ሄዶ ተቀመጠ ያንንም ምድር ኢያስኤድ የሚባለውን ከርስቱ ድንጋይ ጋደና ከጥፋት የተነሳ የሚያገናኘበት ኢያስኤድ የሚባለው ወርቅና ከብር የቁ ድንጋይ የሚገኝበት ነው ። ስለዚህ የቁ በሚባለው ውድ ድንጋይ ሃብታም ስለነበረ ኢትኤል መባሉ ቀርቶ ኢትዮጵ በእንቁ ድንጋይ እንቁ ቁባለ ሚሊዮም ሊና መባሉም ቀርቶ እንቁዩቋ - እንቁቁዩጸግዩን ተባለ ልቾ በሃገሪ ዩቅጣን እንደዘ ያን የሚባሉት አበ-ሳውያን እንቆ እንቁል ግዩን የሚባለው ስም እንቁዩጸግዩን ብለውታል ይሄውም የእባይ ወርቅ ማለት ቀርቶ የዕዮን ወርቅ እንዲባል ብለው ነው ።

ኢትኤልም ግዩን ወንዙን ለወንዝ ኢጠራቅሞና ሰብስቦ እስከሚገኝበት ያለውን ምድር ሁሉ በስሙ ኢትዮጵያ እንዲባል አድርጋል በግዩን ዳርቻ ሄዶ የልጅ ልጆቹ በሚነግሱበት ጊዜ በዚህ ድንጋይ ላይ ተቀምጠው ቅባአ መንግሥታቸውን እንዲቀቡና እንዲነግሡ ሲል ለዮ ንኤል ብሎ በክብር ለማሳሰቢያ ትልቅ የድንጋይ ሀውልት አስቀምጧል ።

ይህም ምድር ከሳሌም እስከ ግዮን ድረስ የኢትዮጵ ልጅ አዜብ ይገ
ዛው ስለነበረ አዜብያ ይባላል ።

አዜብ መልከጼዴቅ ንጉሥ በግራ ክፍል የሚገኘውን የግዮን ግዛት ሰሜ
ያዊ ግዮን ወንዝ እስከሚፈልቅበት ምድር ድረስ ግዛቱን አስፋፍቶ
ስለነበረ ፤ ምድር እስከ አሁን አዜብ ወይም አዘቦ ይባላል ። አዜብያ
በሚለው ሃገር ውስጥ አብርሃም ሳይጓል አብሬራም ብዙ ቀናት በእንግ
ድነት ተቀምጦ በት ነበር አብሬም በዚሁ መርቅና በብር ከብሮበት
ነበር ይሄም ታሪክ በሴም ነገዶች ተፅፎ ይገኛል ። አዜብ 132 ዓመት
ግዝቶ የኢትዮጵ ታላቅ ልጅ አቴባ መርካዞ ንጉስ በቅኝ በኩል ያለ
ውን የግዮን ግዛ ወንዞች የሚፈልቁበትን ሃገሮች እንዲገዛ አንግሶ
ለደደው አቴባም በአባቱ በኢትዮጵ ስር ሆኖ እስከ ታላቁ ባህር በሚ
ገኙት ጉጎዎች ላይ በሰባ አቆጣጠር ሰባት ሰባኤ ገዝቷል ።

ከሆነ ኢትኤልም በኢትዮጵያ ምድር ሆኖ ምድሪቱን ከባረካትና
ልጆቹም የመገናኛ በዶ ልር ከአስተማራቸውና በርእት መንግሥት
ከአባታቸው በኋላ ንጉሥ ነግሥት በተባለ በአስራ አራት ሰባኤ 98
ዓመት ግዛት ነው ። በተወለደ በአንድ መቶ አምሳ አንድ አመት አን
ቀላፋ ልጆቹም መልከጼዴቅ ከአስፈለፈለውና ከአሥራው ቀኝ ውስጥ
ወበደው አስቀመጡት በኢትዮጵ መጨረሻ የግዛት ዘመን እረዥብ ነበ
ረና አብራውምን ወደ ምስር የተሰደዱበት ዘመን ነው ።

## ነገደ ኢትዮጵ

ኢትዮጵ የተባለው ኢትኤል በፋቲራ የተድአልን ልጅ እንቁ
ፍጹን አግብቶ አስር ወንዶች ሰስት ሴቶች ወለደ የወንዶች ስማቸው
አቴባ ፣ ቢአር ፣ ቢኢራ ፣ ተያምና ፣ ኢቴር ፣ አቨን ፣ አከለብ ፣ መሬግ
ተወስቢ ፡ ቶሳ ፡ አዜሚሌክ የተባለው አዜብ ናቸው ሴቶችም ይግም ስማ
የሚልካሰባ ናቸው የአቴባና የመጨረሻው ልጅ የአዜብ ዘሮች ነገዶ
ታት ናቸው የቢአር ዘሮች መናፍስት በመጥራት የተያምና የኢቴር የአ
ቨን ዘሮች የተለያዩ ቅርፆች በመስራት የሰው ልጆች የሚያገናኙበትን
ያባቶቻቸውን የሚገልጹበት ምልክት ወይም ጠልሰም ታሪክ የሚያቀናበት
ትን ስራት የሚያቀርቡ ፈላስፋዎች ናቸው ። ይሄውም ለመጀመሪያ ጊዜ
በአምላኩ ስም ፈደልን ቀርጾ ለእያንዳንዱ ቃል ትርጉሜ አቅርቦ ያስ
የማራቸው አባታቸው ኢትኤል ነው ከዚያ በፊት የትውልድ ታሪክ
በቃል ሲነገር በልብ ሲጻፍ ቆየ እንጅ ሌላ በዶ አልነበራቸውም የአ

ከዚ.ብና የመራባ ዘሮች ዘላኖች ናቸው የተሰሉ ዘሮች የእምነት አገል
ጋዮች ትንቢት ተናጋሪ መሞቸውን በማወቅ የታወቁ ናቸው ። ከንዚህም
ዘር የተወለደው ታላቁ ነቢይ ቲስቢያዊ ኤልያስ ነበር ። የቶላ ዘሮች
እንጨረኞች ግማሽ ነጋዴዎች ነበሩ ።

ቢእር እራሞን ወለደ እራም ናጌን ወለደ ናጌ ሃጌን ወለደ ሃጌ ሁለተኛውን ቢእርን ወለደ ቢእር በለአምን ወለደ በለአም ከምሥር እብራውያን ሲወጡ በእስራኤል ላይ በመንፈስ እየተመራ ትንቢት ተናገረ የተናገረው ቃልም እንደዚህ አለ አየዋለሁ አሁን ግን አይደ ለም እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል በእስራኤል በትር ይነሣል ። ከያዕቆብ የሚወጣ ገዥ ይሆናል ሲል ስለ መሲሁና ስለእርሱ ነገድ ደግሞ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሯል ። ማደሪያህ የፀና ነው ጐጆህም በአምባ ላይ ተመርቶአል ነገር ግን አሶር እስኪማርከህ ድረስ ቄናዊ ኬናዊው አንተ ለጥፋት ባርነት ትሆናለህ እምላክህ ይሄን ሲያደርግ እወይ በህይወት ማን ይኖራል ከኪቲም ዳርቻ መርከቦች ይመጣሉ ያስጨንቃሉ አሶርንም ያስጨንቃሉ ኤቦር ንም ወላትህን ያስጨንቃሉ ነገር ግን እርሱም ደግሞ ይጠፋል ። ብሎ የተናገረውን ልጁ ደጃት ትንቢቱን ሲከታተል በቀትር ጊዜ ከምንጩ ዳር ተቀምጦ ፍልስጥኤማውያን በአዝዋሪት ውሃ ሲያጠናና ሲፈልጉ ለዳ ልእም የታየውትከተለ እንደገና ለደጀት ታየው የአዝዋሪቱን እረፍትከተ እየተከታተለ ሲሰሙ ድንግል ሴት ያለ ዘር የተወለደ ልጅ ታቅፋ እያት ወሊያውኑ ያየውንና ወደድንግሊቱ የመራውን ኮከብ ስእል በናስ ሰሌዳ በሰማ ቀርጾ ድንግሊቱን ልጇንም እንደታቀፈች በወርቅ ሰሌዳ ስዕሉን ቀርጾ ለልጆቹ አስቀመጠው ሲሞት ሲል ይህን ኮከብ የሚመለከቱም ሥራቅ በኩል ሲወጣ እይታችሁ ጨረሩን ወደ ሚያመለክታችሁ ምድር ተጓዙ ከምድራችሁ ከምታገኙት የምድር አበል ወርቅ ፣ እጣን ፣ ከርቤ ፣ ልብስ ይዛችሁ ይህን አምላኬችን ለአባታችን አዳም ለሄዋን እንዲሰጥ የሰጠውን አብርሃም ለአባታችን መልከጼዴቅ እሥራት ብሎ የሰጠውን እንቅአርፆ በኮብር ይዛችሁ የኮከብ ብርሃን ልበገዩለት ስግዱችሁ ስጦት ሰሉና ዩል የወርቅ ያመልጣል ለእናቱ ስጡሰት ይህ እስከሚሆን ድረስ እንቆ እርያውን ተመልክቶት እርያብ ዘመን ሊሆን ሲል መልኩ ይጠቀሰልየዋጋብ ዘመን ሊሆን ሲል መልኩ ያበራል ቅባት ይጭረቀረቃልሲል እናንተም ማርና ወተት ወደሚፈስባት ምድርሂዳችሁ ትኖራላችሁ ብሎ ለልጆቹ በተወለደ በአስራ አንድ ሰባኤ ሞቷል ። ይህም ዘመን በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም ። በእስራኤል ላይ የነገሠው ንጉሥ ለዚ

ቅዱም በመንፈስ የታየውን ትንቢት እንዲህ ሲል ተናገረ በፊቱም ኢት ዮጵያ ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥ ታት ስጦታን ያመጣሉ የአረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀር ባሉ ።

ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል አሕዛብ ሁሉ ይገዙለታል ። ሲል ከዶሽት በኋላ ተናግሯል ይህም ትንቢት ለመሲሁ እንጅ ለሰለሞን አይደለም ነገር ግን ከመርት በፊት ስም ስለሚቀር ብስምሞሰለሞን ወርት የመሲሁ ትንቢቱ ተፈጽሟል ።

በሌላም መንት የምታንኅ የነበረች የሸምሸልን አባት ተሁሚደን ወሰደ በ፺ ወንዶችና ሴት ሸምሸልን ወሰደ ሸምሸል ፈላስፋው ደሽ ትን ወለደች አባቱ አይታወቅም ይባላል ከዚህ ላይ ታሪክ እለፈአለሁ የደሽት ልጆች ማጂ ጂማ መንዳ መደባይ ናቸው የማጂ ዘሮች በከፋብ የሚያመልኩ መንፈስ ሃይል የተሰጣቸው መሆኑን የሚናገሩ በመን ፈስ ስለመነጋገር የሚያምኑ ናቸው ማጂ ማሬን ዣማን ጂምማን ይወ ልዳል ጂማ አረርቴን ገትቴን ሞረን ይወልዳል እነዚህ ሁሉ የግዛን ምንጭ በሚፈልቅበትና በሚከበው ምድር ሄደው ሠፈሩ በአባታቸው ስም ምድሩን ደሽት አሉት ነገሥታት ደግሞ ከደሽት መቋለዳቸውን ለመግለፅ ዘረደሽት ዠረደሽት አሉት ነገር ግን በንጉሥ ጉዛንም በዳሞው ልጅ ስም ጉጀም ተብሎአል ይኸም ስም የተቀየረ በ፲፰፻ ዘመን መን ግሥት በአሬት ሽህ አምስት መቶ አመት ከተቀጠረ ነው ማሬ ከመጣሽ ቀለዶቱ ቤተሰቦችን ይዞ ወደ ፀሃይ መውጫ በተራሪሚው ሃገር ሁሉቱ ሄዶ ተቀመጠ ጎንች ኢዶምን ይወልዳል ኢዶም ወደ ፀሃይ መውጫ ወደሚገኘው ባህር ሄዶ መኖሪያውን አደረገ ።

ቀለመ ፍቅ የተባለው ዘግዱር የገምሞን ነገዶች ግማሹን ታሪክ ዋና አድርጎ ቤተእንግዳ የዛሬ አንዱ ቤት ግማሹን የመደባይ ነገዶች በሩናች ወደሚኖሩበት ቤተ ማራ የዛሬው መርሃቤቴ ላካቸው ያንም ሃገር በአባታቸው ስም ወንዙን ግማ አሉት በዚያንም ሃገር የማሩ ነገዶች ይኖሩበታል እነዚህ ማሩ የሚባሉ ሁለተኛው ዘግዱር አሚናዝ የተባለውን የአብነልሃኪም የልጅ ልጅ ሠግቢዎች ጋር በአደረገው ጦርነት ለአርዳታ ሄደው በዚያው ቀርተዋል ። ያም የሰፈሩበት ሃገር አማ ራ ይባላል ። ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ ከኖሩ በኋላ በ፲፮ ላሊበላ ዘመን መንግሥት ከጥበብ ወደኢትዮጵያ መጥተው በቤተምግራ ከሚ ኖሩት ጉዳዮቻቸው ጋር ተቀላቅለው ኖሩ እነዚህም የዛሬዎች አማራ ዎች ናቸው ። ከነገደ አማራ ኢትዮጵ አቴባን ወለደ አቴባ ሁለተ

ኛው አዜብን ከማዱንያ ልጅ ቂቂ ከምትባል ንግሥት ወለደ አዜብ ሰቢን ወለደ ሰቢ በግዮን ዳርቻ ስሙ መንግሥቱ ሞረሽ መለክ ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በሃያ አንድ ነገሥታት በአርባ አምስት ሃገሮች ላይ ነገሠ ግዛቱም በስሙ ሞሪያ ከተባለው ተራራና እስከሱኒ ባህር ድረስ ነው ። ሞረሽ መለክ ሠራዊቱን ሃገር እንዲያቀኑ ማለት እንዲያስፋፉ ወደመካከለኛው ግዛትና ወደታላቁ ባህር ላካቸው እነሱም ምድሩን እርስት አድርገው በዚያው ቀርተዋል በስሙ ምድሩን መርታንያ ህዝቡን ሞረቴ ተብለዋል ግዛቱም ሰባ ሰባት አመት ነው በፈንታው ልጁ ልብና ነገሠ ሞረሽ መለክ የተባለው የአዜብ ልጅ ሰቢ በመርታንያ ልብናን ወለደ ልብና በግዮን ዳርቻ ስሙ መንግሥቱ ሊባኖ ተብሎ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ አርባ አራት አመት ነገሠ ልብና ከፍልስጤማውያንና ከአማሌቅ ጋር ሲዋጋ በጊራራ ሞተ ለልብና አንድ ልጅ ስለነበረው በፈንታው ሱካውያንን አዜባውያን አነገሡበት የልብና ልጅ መሴክ ስሙ መንግሥቱ አቢሜሌክ ተብሎ በጊራራ ነገሠ በነገሠ በሶስት አመት የአባቶችን ህግና ሥርአት ለመፈጸም በግዮን ዳርቻ እንደገና ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ዳግመኛ ነገሠ ግዛቱም ሶስት ሱባኤ ተኩል ነው ። (ሃያ አራት ) አቢሜሌክ የተባለው መሴክ ጋዛያን በጊራራ ወለደ ጋዜያም በአባቱ ፈንታ አበስኚ ተብሎ በሲና አዜባውያንና ሱካውያን አነገሡት በጋዛያ ዘመነ መንግሥት ብዙ ህንፃ ተመሰረተ ያንንም ምድር በስሙ ጋዛ ተባለ ግዛቱም ሰባት ሱባኤ ነው ። ይህም አርባ ስምንት ነው ። አቢሲኒ የተባለው ጋዛያ አድያምን ወለደ አድያምም በግዮን ዳርቻ ስሙ መንግሥቱ ላክንዱን ተብሎ በኢትዮጵያ ምድር ነገሠ የግዛቱም ዘመን ሰማንያ ሶስት አመት ነው ላክንዱን የተባለው አድያም ታላቁ ንጉሡ ነገሥትን ታንጋንን ወለደ ።

እንዲዚህ ሆኖ የአድያም ልጅ ታንጋን አስራ ሁለት ወንዶች አስራ ሁለት ሴቶች ከአራት ሚስት ወለደ የወንዶች ስማቸው ሲኒ ፣ ጉሜዚ ፣ ጉድሬ ፣ ኩንፉ ፣ ክፈን ፣ ጉምዝ ፣ ክሬሽ ፣ ጉፍ ፣ ሐማ ፣ ዝሪ ፣ ሣምራ ፣ ፍቸሮ ፣ የሴቶቹ ስም ካሳኪ ፣ ቲካ ፣ የኗና ፣ ብሌኒ ፣ ቢሸሎ ፣ ችሊጋ ፣ ልሂዎ ፣ ሰሊታ ፣ ኤፍራታ ፣ ወሊታ ፣ ቆቂና ፣ ነጋዶች ፣ ናቸው እነዚህ ሁሉ አባታቸው ኢትዮጵ ንጉስ የሚባል ታላቅ ድንጋይ ለማሳሰቢያ በአስቀመጠበት በግዮን ዳርቻ ላይ ተወለዱለት ታንጋን ስሙ መንግሥቱን ኖርእስ አሰኝቶ በግዮን ዳርቻ ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በነገሠ ጊዜ ሶስቱ አራት ንጉሶች ሲያገግሱ ታላቁ ልጁን ሲኒን በኩርናት የመጠሪያውን ልጁን ከህንትን አምላኩን እንዲያገለግል ሁሉቱን የአባቶችን አሰ

እንዲጠብቁና በቦታው እንዲቆዩ ወደ እርስታቸው ወደ ምድያም ላካቸው ሌሎቹን ሴቶችና ወንዶችን ይዞ ከብዙ ሠራዊቱ ጋር ወደ ቀራራማው ሃገር ሄዶ ቤቱ መንግሥቱን ቆረቆረ ስምዋንም ዋይዘ አለ የታንዛን ልጆች ያገኙት ምድር ዛፍ የምንጭ ውሃ ታላላቅ ወንዞች የሚገቡት ለምለም መሬት ሆኖ ስላገኙት ለእይንም ሆነ የዛፍ ፍሬ ለመልቀም አመቺ ስለነበረ በመካከላቸው ጠብና ግጭት እንዳይኖር



የዮዲት ታሪክ

ለሃያ ሁለት የታንባን ልጆች ተካፈሉት ከነሱ ቀጥለው የማኚ ልጅ መደባይ የማሬን ልጆች ሃገር አልምተው ነበርና ሥርጉት ቢያነሱ ሌተ ባበሩ በታላቅ ተራራ ስር በደጋው መሬት ቃል ኪዳን አደረጉ በየደረጃቸው የታላቅነትና የታናሽነት ምልክት የሚገልፅ የማገኛው ልጅ መሆናቸውን የሚያስረዳ ከትባት አደረጉ ፊታቸውን ተቆረጡ የመጀመሪያው ልጅ ሲኔ ወደምድያም ስለሄደ የቁርጡ ከትባት ምልክት በሁለት ይጀምራል ይሄውም የመጀመሪያውና የሁለተኛው ልጆች መሆናቸውን የሚገልጽበት ቁጥር ነው ። 11-111 እያለ እስከሰባት ሲደርስ እንደነና በግንባራቸው ላይ ከብ አይነት ቆረጣ ያደርጋሉ ።

ከነዚህም ሐማ የተባለው የጎሳው ቆዳ በጣም የጠቆረ ቁመቱ ረጂም አስፈሪና አስደንጋጭ ነበረ ሐማ ማለት በሱባ የኢውንት ዛፍ ነህ ማለት ነው ። የሐማ ልጆች ጉጂ ጂን ሱት ሻቃ ጂንጀር ማሌ ናቸው ። ሻቃ ጠንካራና እንደአባቱ አስፈሪ ጥቁር ነው ትርጉሙ የአምላክ ትንፋሽ ማለት ነው ሻቃም በአባቱ ሥር ሆኖ በግዩን ዳርቻ እስከ ደጀት ድረስ አራት ሱባኤ ተኩል ገዝተዋል ። የሐማ ልጅ ጀንጀር ፈጣኑ ርዋጭ ናይጀርን ወሰደ ናይጀርም እያቱ ታንባን ባርኮና አንግስ ግዛ ብሎ እስከታላቁ ባሕር ድረስ ፈቀደለት ንጉሥ ናይጀርም የሄደበትን አገር ወንዝ በስሙ ናይጀር እንዲባል አደረገል ። አልጀር ብሄል ርዋጭ የሐማ ልጅ ማሊ መጣይ ካህን ስለነበረ እያቱ እንደተርአብ ከህንትን ስለባረከለትና በፈቀደውና በወደደው መሬት እንዲቀመጥ ስለፈቀደለት የሄደበትን ሃገር በአያቱ ስም ታንባን አለው ልጆቹ የው ሖኬን ሥራ አጥብቀው የሚወዱና የሚያፈቅሩ ናቸው መጣይ በሁሉ ቀን ንሁሕ ሆነው ተላጭተው በጀርባቸው ጊጣጊጥ እንጠለጥል አድርገው ይቀርባሉ ህግና ሥርዓት ሆኖ እስከዛሬ ድረስ አለ ።

ከእለታት አንድ ቀን ሐማ በግዩን ዳርቻ መኖሪያውን አደረገና ከዛፍ ስር ተቀምጦ ሳለ መልኩዋ የሚያምር የሚያንፀባርቅ ልብስ ለብሳ እንዲት ሴት ልጅ ከባሀሩ ውስጥ ወጥታ ከአለበት ዛፍ መጥታ እንደቆጣ ሆና ስትገባ አያትና ቢፈልግ አጣት ።

ከዚያ ወደቤቱ ሳይሄድ ከወገኖቹ ተለይቶ በዛፉ ስር ለብዙ ቀን ከኖረ በኋላ ተገለፀችለትና ለምንድነው ይሄን ያክል ቀን የተቀመጠከው አለችው እፍቅሬሽ አላት ከአፈቀርከኝ አግባኝ ብትለው እፍቅሬት ነርና እጂ አላት ስምህ ማነው ብትለው ሐማ አላት ይህም ዛፍ ሆማ ነው አለችው ያንቺስ ሺባ እባላለሁ አለችው ተጋብተው ብዙ አመታት ከሆናቸው በኋላ የወገኖቹ ሴቶች ልጆች ጂና ለንክ የሚባሉ እያ

ሄደው ሳለ አገኙትና ለምን እንደመጡና ወደ ቤቱ የማይሄዱበትን ቀዳይ አጥብቀው ጠየቁት እሱም ሁሉን ነገር ገልጾ ነገራቸው እንሱም አብረው እንዲኖሩ ቢጠይቁት ሺባ ባለቤቱን አስፈቅዶ አብረው ከወ ተናቻቸው ተለይተው እንዲኖሩ አደረገ ከዚያም ሁሉቱን በሥጋ እንባ ቸውና ልጅ ወለዱለት የሆማ የልጅ ልጆች እየበዙ እንዲደዱ ሲያውቁ በዘራችን ያለአምልኮት እንኖርምና ለስዚህ ከወገኖቻችን ሄደን የም ናመልከበት ነገር እናምጣ አሉዋት ለሺባ እሷም እኔን ብታመልኩ ጠላት ቢመጣ እስወራችኋለሁ የምትፈልጉትን ሁሉ እሰጣችኋለሁ ጠላታችሁን አሳልፌ ለእናንተ እንድትገድሉት አደርጋችኋለሁ በለእ ምልኩቱ ሥርዓት አስታችሁ ያሳያችኋል አለቻቸው ።

ሆም ሆማም እሚያመልኩበትን ጌታ በጥቁር እንቁ አሰርቶ ሸባ ሻንቃ ለወንዶች ልጆች ሻንቀል ለሴቶች ልጆች ማምለኪያ አደረገላ ቸው ወደሻበሻንትና ወደ ሻንቀል ለአምልኮት የሚገቡ ሁሉ ከበል ፈጭተው አሉመው ከቡልቃ ዱቄ ጋር ለውሰው ተቀብተው መግባት አለባቸው ሴቶች ደግሞ ጥቁርና ቀይ አፈር ከቡልቃው ዱቄ ዘይት ጋር ለውሰው ተቀብተው ይገባሉ ይህም የአምልኮ ባህልና ልማድ እስከዛሬ ድረስ አለ ከቡዳና ከሺንዱ የዶማኖት ጋር ይስማማል ከነዚህ እንደመነጨ የሚያስረዳው የሀንዶች እምነት ከዚህ የተያያዘና ሺባ በጣም በሀንዱ የታወቁች ናት ሺባ የምትባለው ነጭ ነገር ስለምጠላ ባጭ ያደቀ ቅርፊቱን በሚቀልበት ሰዓት በተሎ እንዲጠቁር ያቃጥሉ ታል ከነሱ መሃል ነጭ ልብስ ሰው ቢጠለድ ጎለመ ያቀብሬታል ወይም ያቃጥሉታል ይችውም የመንፈስ ዘር ታምርን በመሥራት ከአዶጋ ነገር በመሰወር የታወቁች ስለነበረች ሃገሪ የሚባሉ ጉማዎች ወርቅና ልጃቸውን ስእለት በየጊዜው ይሰጡዋት ነበር ሻቃ የሚባለው በመን ፈስ እናቱ ሸበሻንቃ በተባለው ማምለኪያ የታመነ ስለነበረ ወርቅና በከብት የከበረ ሆኖ መቀመጫውን በጣፍን ወንዝ አደረገ ልጆቹም በአባታቸው ስም ሻንቅላ ተባሉ ወንድሞቹም ጀንና ሉቅ በቆቫና በድ ንጋይ በር ቤታቸውን አደረጉ ባህላቸውም ከታላቁ ወንድማቸው ሻቃ ጋር ተመሳሳይ ሆነ ቢጋብቻቸው ጊዜ ከሂን ከሉቅ ልጆች ጋር ሴት በሴት ተቀያይረው ይጋባሉ ሴት አሀት ከሌለው አንዱ ከነሱ ዘጋ ውጭ የሆነውን ሰው ገሉ ስለባ በማድረግ ስለባውን አሳይቶ ሴት ማግባት ይችላል ። ጅማንነቱ ከብዙ ዥመቱ ሁሉ በኋላ ዘንድ ስለባ ብቻ ነው ሌላ በኩርንት ያለው እለቃ መሪ ሊሆን ይችላል ።

እነዚህ ጐሣዎች የባህ ፍሬ ለቅመው ሥር ቆፍረው የእንስሳትን
አውሬና በራሪ ወፍ አሞራ ገድለው ከመብላት በስተቀር ከብት አርብ
ተው አታክልት ተክለው አያውቁም ነበር ነገር ግን የሚሰሩት ነገር
ሁሉ በህብረት ነው ።

ኖርአብ ታንባን ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ በተባለ በሰማንያ
አምስት አመት አብራሐምን ከግብፅ አርጎት ነፃ ወጥቶ ወደ ከነአን አገ
ሲተዩው በተመለሱ በስድስተኛው ዓመት በተወለደ በመቶ ሠላሳ አንድ
አመት እንቀላቀ በፈንታው በሲና በረሃ የሚኖረው ራጉኤል የተባለው
ታላቅ ልጅ ዮቶር በሚባን ፋርቆ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ
ነገሠ በምድያምና በሲና ምድር የኤልኖላይ ካህን የክህነቱ ስም
ራጉኤል የተባለ የታንባን ልጅ ዮቶርአብ የሚባል ነበር ።

ለዮቶር አብ አስር ወንዶች ሰባት ሴቶች ነበሩት ወንዶች ኤልሳ
ዛም ኡራኤል ንኤል አልባኤል ፣ ኤልባ ፣ ኤልያ ፣ ዙርባኤል ፣ ተሙዓ ፣
አባብሂር ሴቶች ሲፖራ ፣ ልሂ ፣ ዘሃራ ተምና ለውይዛ እስድ ፣ ዘኑባ
ናቸው ። እነዚህ ሁሉ በምድያም ምድር ተወለዱለት ።

የኤል አገልጋይ የምድያም ካህን ራጉኤል በምድያም ምድር ሳለ
የአባቶችን ታሪክና ስም የያዙ የፈጣሪን ቸርነትና ረዳትነት የሚገልፁ
መጻሕፍቶችን በበግ ፣ በፍየል ፣ በፈረስ ቆዳ ጽፎ ለሕፃናት በኢትዮጵያ ቋን
ቋ በልጆቹ በስነ ሥርዓት ቢጠይም ከአዋንትና ከእንጨት ከተሠራ
ሰሌዳ ላይ ከመጻፍ በስተቀር በብራና ተፅፎ አያውቅም ነበር ። ራጉኤል
በብርና በወርቅ በከብትም ከመክበሩ ሌላ በአስተዋይነቱና በታማ
ብዛት በሞአብና በአሞን ልጆች በአማሌቅም ልጆች በፈርዖን
በአሞራውያን በከነአናውያን በአሁሳውያን ታውቆ ነበር ። የብዙ
ለማየት እውቀቱን ለመማር ወደእሱ ይሄዱ ነበር ። ከነዚህም ከግብ
ተነስቶ ወደ ራጉኤል ከሄዱት አንዱ ሙሴ ነበር ። ሙሴም በራጉኤ
ቤት ባለ የአምላክ አገልጋይ ካህንና ትሁት ሰው ለመሆን ይተጋ
ነበር ። የምድያም ካህን ራጉኤልም የአምላክ ሰው መሆኑን አውቆ
ውሎ ታላቋቸን ሴት ልጁን ሲፓራን ለሙሴ አጋብቶ በቤቱ
ዶሱ ላይ ኖረው ሙሴም ብዙ ቀናት አብሮት ተቀመጠ ።

እንደዚሁም ሆነ ግብፃውያን በእብራውያን ላይ የሚያደርሱት
ግፍ የእስራኤል አምላክ ተመለከተ የእብራውያን የዘንና ልቅሶ
አምላክ ደረሰ ስለዚህ አምላክ ከግብፃውያን አርጎት እጅ ህዝቡን እስ
ራኤልን ያወጣ ዘንድ ለሙሴ በአምላክ ቁራራ በኮሬብ በነበልባ
ውስጥ የአምላክን መላክ አየ ሙሴም ወደ እየበት ዛፍ ተጠጋ በነበ

ባሉም ውስጥ እንደዚህ የሚል ቃል ሰማ ሙሴ ሙሴ ሆይ ወደዚህ አትቅረብ የቆምክበት ሥፍራ የተቀደሰ መሬት ነው በቅድሚያ የአብ ራውያን ትምህርት የሆነ ጫማህን ከእግሮችህ ፈጽመህ አውጣ ደግሞም እኔ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው ።

ህዝቤን እብራውያንን ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደፈርዖን እልክሃለሁ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ እኔም የላክሁህ ምልክቱ ይህ ነው ህዝቤን ከግብፅ ባወጣህ ጊዜ በዚህ ተራራ ላይ ለአምላካችሁ ትገዛላችሁ አለው ሙሴም የአባቶችን አምላክ ቃል ሰምቶ ወደ ግብፅ ወረደ ከዚያም በዚሁ ተአምር እብራውያንን ከግብፅ አርነት አውጥቶ በአምላክ ረዳትነት ተመልሶ መጣ በዚያም አማቱ ራጉኤል በአምላክ ተራራ በኮሬብ ወደሰፈረ ሙሴ መጣ ሙሴንም እኔ አማትህ ዮቶር እና ሚስትህ ሲፓራ ልጆችህ ጌርሳም እልአዛር መጥተንልሃል አለው ሙሴም አማቱን ሊቀበል ከድንኳን ወጣ ሰገደም ሳመውም እርስ በራሳቸው ደህንነታቸውን ተጠያየቁ ወደድንኳኑም ገቡ ሙሴም አምላካቸው በግብፅ ባለሥልጣኖችና በፈርዖን ላይ ስለ እብራውያን ያደረገውን ሁሉ በመንገድም ያገኛቸውን ድካም ሁሉ ኢልሻዳይ አምላክ እንዳዳናቸው ለአማቱ ነገረው ።

ካህኑ ራጉኤልም ለእብራውያን ስላደረገው ቸርነት ሁሉ ከግብፅ ውያን አርነት ስላዳናቸው ደስ አለው ። ራጉኤልም በሙሴና በእብራውያን ሽማግሌዎች መካከል ቆሞ እጁን በርግቶ እንዲህ አለ ከግብፅውያንና ከፈርዖን እጅ ህዝቡን ያዳነ የእስራኤል አምላክ ይባረክ አሁ ሻዳይ አምላክ ከአማልክት ሁሉ የበለጠ የእስራኤል አምላክ እንደሆነ አሁን አወቅሁ አለ እንደዚህም ብሎ የእህል መስዋት ሰንደልና ስጋን በአባታቸው በመልከጼዴቅ የታዘዘውን ሁሉ የሚቃጠለውንም የሚጠበሰውንም ለአምላክ ወሰደ ሁሉቱም በአንድ ላይ መስዋዕትን አቀረቡ ኢልሻዳይ አምላካቸው መስዋእታቸውንም ተቀበለ የሚቃጠለውን ሁሉ ከሰማይ እሳት ወርዶ በላው በአምላካቸው ፊት ከሙሴ አማቱ ጋር የእብራውያን ሽማግሌዎች የመስዋእት እንጀራ ሊበሉ መጡ ።

እንደዚህም ሆኖ በነጋው ሙሴ በህዝብ ሊፈርድ ተቀመጠ ህዝቡም ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ በሙሴ ፊት ቆመው ነበር ራጉኤልም በህዝቡ ሙሴ ያደረገውን በየጊዜው ይህ በህዝብ የምታደርገው ምንድነው ሙሴም አማቱን ህዝቡ አምላክን ለመጠየቅ ወደ እኔ ይመጣሉ ነገርም ሲኖራቸው ወደእኔ ይመጣሉ በዚህና በዚያ ሰውም መካከል እፈርዳለሁ የአምላክን ህግና ሥርዓትንም አስታውቃቸዋለሁ አለው ።

ራጉኤልም አለው አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደ ለም ይህ ነገር ይከብድሃል ሕዝቡም ይከብደዋል አንተ ብቻህን ልታደር ገው አትችልም አሁንም እመክርሃለሁ ቃሌን ስማ እምላክ ከአንተ ጋር ይሆናል አንተ በእምላክ ፊት ለህዝቡ ሁን ነገራቸውንም ወደ እም ላክ አድርስ ሥርዓቱንም ህጉንም አስተምራቸው የእምላክን ህግና ሥርዓቱን ከቃልህ ሰምተው የሚጽፉ ፀሃፊዎች አዘጋጅላቸው በጆ ሮአቸው ጧትና ማታ የሚነግሩአቸውና የሚያስተምሯቸው አዋቂዎችን ምረጥላቸው የሚያደርጉትን ሁሉ ለአስተማሪዎች አስተምራቸው ስለነ ገራቸውም ደግሞ እንደዚህ አድርግ ከህዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን እምላክን የሚፈሩ የታመኑ የግፍን ሥራ የሚጠሉ ሰዎች አስመርጥ ከእነርሱም የበላይ አዛዥ የሺህ መቶ የአምሳ የአስር አለቆች ሹምላቸው በህ ዝቡ ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ ለመፍረድ የማይችሉትን ወደ አንተ ያምጡት ታናሹን ነገር ሁሉ እነሱ ይፍረዱ አለው ይህ ነገር ለአ ንተ መልካም ነው ይቀልሃል ይህንም ፈጽመህ ብታደርግ እምላክ ቢያዝህ መቆም ትችላለህ ይህ ህዝብ ደግሞ በሰላም ወደሥፍራው ይደርሳል የነመልከጼዴቅ የነኢትኤል ህግና ሥርዓት እንደዚህ ነው አለው ።

ሙሴም የእማቱን የራጉኤልን ቃል ሰማ ያለውን ሁሉ አደረገ ሙሴም አዋቂዎችን ሁሉ መርጦ በህዝቡ ላይ የበላይ አዛዥ የሺህ የመቶ የአምሳ የአሥር አለቃዎች ፀኃፊዎችና አስተማሪዎች ሁሉ አዘጋጀና ሾመላቸው በህዝቡም ላይ ፈረዱ የከበዳቸውን ነገር ግን ወደሙሴ አመጡ ከዚያም ሁለቱ በሰላም ተሰነባበቱ ።

ከዚያም የከህነቱ ስም ራጉኤል የተባለው ዩዮር አብ በተወ ለደ በስልሳ ሰባት ዓመቱ እብራውያን ከግብፅ በወጡ በሶስት አመት አባቱ ኖርአስ ታንዛን ስለሞተ በግዩን ወንዝ ዳርቻ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ በነገሠ በሃያ ሁለት ዓመቱ አንቀላፋ ከእሱ ቀጥሎ በፋንታው ልጁ አባብሂር ስመ መንግሥቱ ኢትዮጵ ተብሎ ነገሠ ። አባብሂር እብራዊያንን የረዳ መንገድ የመራቸው ስለነበር ከእብራዊያን ወገን የምትሆን የአሚን አዳብ ልጅ ሩት አሚን የም ትባለውን አግብቶ ወደግዮን በሚያወርደው ምድር ተቀመጠ በዚ ያም ኢትዮጵስን ወለደ አባብሂር በደከመ እንዛዝ አስር አመት ከገዛ በኋላ ልጁ ኢትዮጵስ ስመ መንግሥቱ ሰንደቅ ዣን ተብሎ በግዮን ዳርቻ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ታላቁዋን ከተማ ሱባን ሰራ በሱባም ታላላቅ ግንቦች ተገነቡ የውሃ

መከማቻ ጉድጓዶች ተዘጋጁ በምድርም እንደሴባ ያለ ከተማ አይገኝም ነበር ።

ኢትዮጵስ የሱባውያን ንጉሥ ናኦድ በእስራኤል ላይ መስፍን በነበረ ጊዜ በሳሌምና በአካባቢዋ የሚኖሩ መንደሮች ያለጦርነት በሰላም ኖሩ በሱባ የሱባ ንጉሥ ኢትዮጵስ በዘመኑ ምድር ከማካፈልና ከተማ ከመቆርቆር የሃገር ስም ከማውጣት በስተቀር ጦርነት አድርጐ አያውቅም ልጁን ሄቤርን በቃዴስ በፀአናይ መካከል አንግሶት ስለነበር እብራዊያንና ሄቤር የቃዴስ ንጉሥ ቃል ኪዳን ስለነበራቸው የሄቤር ሚስት ኢያኤል የምትባለዋ የኢያቤስን የጦር መሪ ሢሣራን ገደለችና የግድያውንም ምልክት እራሱን ለእስራኤል ልጆች ሰጠች በዚያም እብራውያን ስለተደረገላቸው እርዳታ አምላካቸውን አመሰገኑ በሄቤርቤትና በእስራኤል ልጆች ቤት ወዳጅነታቸው ፀና ።

ኢትዮጵስ ሰንደቅ ዣን በየበርሃው መንደር እየቆረቆረ ቤት አግብቶ በቆረቆረው መንደር ሁሉ ማስቀመጥ ይወድ ነበር ። ስለዚህ ንግሥት የተባሉት ሰባት ስለነበሩ አምሳ ልጆች ከነሱ ወለደ። ከነዚህም አስራ ሶስቱ የነገሡ ናቸው ። እነዚህም የአዜብያ ንጉሥ አማም በአዜብ በርሃ የምትገኝ መንደር የመጀመሪያቱ ሳባ የሳባ ንጉሥ ቲራ ፣ የአፈር/የዛሬው ውጋዴን/ ንጉሥ ሽሚዳ ፣ የኤውላጥ ንጉሥ ሃሺሞን ፣ የመደባይ ንጉሥ እናሪያ ኋዋላ በሰሙ እናሪያ የተባለው የዛሬው ሊሙ መደባይ መንዲ የሚባሉት የዛሬዎቹ አረሞ (ጋላ) ናቸው/ የመንዲ ንጉሥ ኢያቢስ ፣ የኪና ንጉሥ ጂማ ፣ የልብና ንጉሥ አልብኖን ፣ የቃዲ ንጉሥ ሄቤር ፣

በሰንደቅዣን ስር ወይም ዙፋን ወራሹ ኤልካኖ በሰብያ የሱባ ንጉሥ ሲሆኑ አስሩ ወንዶች ናቸው ሴቶች ደግሞ የአዲን ንግሥት በሰሣ ፣ የኤደን ንግሥት አሊና ከሁሉም ልጆቹ በላይ ይወዳት የነበረችውን ኢትግዝያ ከግዮን መገናኛ እስከ ሱኪ ድረስ ባለው በአብያ ምድር ሁሉ አነገሳት ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ የሚል የማረግ ዘውድ በራስዋ ላይ ደፋች ኢትግዝያም በአባትዋ ስር ሆና አርባ አምስት አመት ከገዛች በኋላ በተራራማው ሃገር ዋሻ ውስጥ ሄዳ ተቀመጠች ያንንም ሃገር ያማራ ዜጐች የሚኖሩበት ምድር ነው።

ሰንደቅዣን የተባለው ኢትዮጵ ስም አርባ ስድስት አመት በክህነት እስከ ታላቁ ባህር ድረስ አስር አመት ገዝቶ በመልካም ጊዜ አረፈ በፈንታው ልጁን ኤልካኖን ስመ መንግሥቱን በአባቱ ስም ኢትዮጵስ ተብሎ በግዮን ወንዝ ዳርቻ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከኪቲም እስከ ታላቁ ባህርና በባህር ውስጥ በሚገኙት ደሴቶች ሁሉ ላይ ነገሠ ።

## ምዕራፍ አራት

ዘመን ከተቆጠረ ሶስት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አንድ አመተ አለም ላይ ሱባ ሱባያ በሚባል ከተማ ላይ ማግን በሚፈለስበት ምድር የአምላክ አገልጋይ ካህን የነበረና የንጉሰች ንጉሥ ቤተ መንግሥቱ እንደአባቱ መጠሪያ ስም ኢትዮጵስ የተባለ ኢሊካና የሚባል ነበር ኢሊካዋ ኢትዮጵስም በንጉሡ በአምስተኛው ዓመት ከከለዳ ጉማ ማሩታ የምትባለውን የሰቢን ልጅ አግብቶ ሰባት ወንዶችና ሰባት ሴቶች ወለደ ከሰባቱም ወንዶች ታላቁ ንጉሥ ነገሥትና የኢሊ እን ሴጋይ ኢሊ ወይም እጼ በንደቅ ኢልማ ወለደ ።

እጼ በልጅነቱ ጀምሮ አስተዋይና ተመራማሪ ስለነበር ከአለ ታት አንድ ቀን ዱር ለዱር እየተዘዋወረ የወፍ ጐጆ አሰራሩን ከተ መለከተ በኋላ የወፍ ጐጆ አስመስሎ ወለል ቤቱን በዋሻና በዋ ላይ መስራት ጀመረ እንደዚሁ እያለ ከሰማይ ወፍና ከምድር እል ቂት ጥበብን ሲማር የንብ ማር ቀርጦ ሲበላ ቆይቶ የማሩን በፈዋ አሰራር ሲያስተውል ለንቡ አመራር የተሠራውን የሰፈፉን ሁኔታ ተመልክቶ ለአባቱ ወስዶ አሳየው አባቱም ኢልካና በሰንበ ታሪክ በሰሌው ከነገረው በኋላ እጼ የንብን ሁኔታ ከሌሎች ፍጥረት ለይቶ ሲያጠና ከአለታት አንድ ቀን የንብ አውራዎች በሰራዊት ተከበ ሳለ እርስ በራሳቸው ተገናኝተው ይናከሱ ጀመር ከዚያም ሌላ ችም አውራዎች እየመጡ ይታገሉ ጀመር ከዚያ አንዱ ሶስቱን ንደቅ በድል አድራጊነት ንቦች ወደአዘጋጁት ክፍል ሄደና ሲገባ እየ እጼም የንቦችን ስርዓት ከአየ በኋላ ለአባቱ ሄዶ እንዲህ አለው እ የአንተ ልጆች ብዙ ነን ስለዚህ አንተ አንድ ንጉሥ ስትሆን ለማ ገኖችን ነው እምትሰጥ አባቱም ኢልካና ለበኩር ልጁ ለት ለኩማናን እለው እንደዚሁ አይደለም ምንም ፊትና ኋላ ሆነን እ ንተ አብረሃ ብንወጣ ሁላችንም ልጆችህ ስለሆንን ለመጀመሪያ መስጠት የሌብህም የአንተን መንግሥት የፈለገ ሁሉ መግዛትና ጋት አለበት ያዉቃ መንግሥትህን ወራሽ ነው በካህኑም እጅ ርቶ ይንገሥ ካህን ለመሆንና የአምላክን ሥራ የሚያስተምርና

ብርሃ ለትልቁ ልጅህ ይሁን አለው አባቱም ሌሊሳና ከአባቶቻችን ከእሊትሌል የመጣውን ሥርዓት እናፈርስም አለው ።

ልጃም እሌ የጎጉሥ ልጅ ባይቆጋ ባይገድል መንግሥ የለበትም ይሄም የመንግሥት ስርዓት ከንብ እንደመጣ የጎጉሥ ልጅ ሁሉ ይወቅ ይስማ አለው ።

በዚሁን ጊዜ እጼ በአባቱ ዘመን ስለአገዛዝ ስለአመራር ከዱር አራዊትና ከሰማይ ወፍ ጋር በንብ በጉንዳን በግብረ ጉንዳን በሥ ስለ ያለውን ሥርዓት ሲመለከትና ሲያጠና ኖረ አባቱ ኢትዮጲስ የተባለው ሌሊሳና በነገሠ በሃያ አምስት አመቱ ስለሞተ ልጁ ከግርጋ ነገሠ ነገር ግን እጼ ሃይለኛና ተዋጊ ስለነበር አስገ በመ ራት መንግሥቱን ለቀቀለት አጼም በአጐቱ በንጉሥ አበኔ እጅ በቡ ሌቶና በወይራ ፍሬ በዶት በቀይና በጥቁር አፈር ተለውሶ ተቀባ በሾኛ በሉል የተሠራውን የዘንዶ ምስል ዘውድ ከራሱ ደፋ ።

እንደነዚህም ሆነ በልጅነቱ በአስራ አምስት አመቱ ዘመን ከተቆጠረ በአራት ሺህ አመተ አለም በነገሠ ጊዜ በአንደኛው ወር መጀመሪያ ሱባ በሚገኘው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በአስቀመ ጣቸውና በሚያጠናባቸው በምስጥና በጉንዳን ታላቅ ጦርነት ተካ ሄደ በዚሁን ጊዜ ከሶስት ቀን ጦርነት በኋላ ምስጥ ድል ሆነና ጉን ዳን እየነፈ ጉንዳን የምስጥን እራሳ አጥዖ ከወረሰ በኋላ በተለቀቀለ ቱ ቤቱ ውስጥ ለሚገኘው ለእንቁላሉ የምስጡን እራሱና እንቁ ላል በጠውና አሽገው ከታሽገው ውስጥ ያሉት የጉንዳን ልጆች ውጡ የተቀባቀሉ ትልቅል የጉንዳንና የምስጥን መልክ ከምስጥ የጉንዳን ፈጣንነት ያለው ጠባይ ይዘው ተወለዱ አጼም ከተመለከተና ከአጠና በኋላ አንድ መቶ አምሳ ሺህ ወጣቶች ለሶስት አመት የጦርነት ስልትና ዘዴ ያስተምራቸው ጀመር በሶስተኛው ዓመት የምእብንና የኢትዮጵያ ስን ሃገሮች ወረረ ማረከ ጠረፍንንም አፈረሰ የሚያንንም ቤቱንና ወንዱን በአቢሲና ታላቁ ወንድሙን አንግሶ ከሀንድ እስከ ጠረፍ እስከ ሚያን ያሉትን ነገሥታት በቢታች እንዲታዘዙትና ከአደረገ በኋላ ወደ ተራራማው ሃገር ሄዶ ምርኮ ከሱባውያን ከኑባውያን ከአዜባውያን ጋር እንዲጋቡ እንዲበሉ አደረገ ስማቸውም ቺያያንንም ትልቅል ታላቁዋን ከተማ ሳባን እንዲሰሩ አዘዘ ሳባም ሲቆረቆር አመት ግዛት የአስራስምንት ዓመት አድሜ ወጣት

ነበር ዓፄን ሲያሠሩ የወንዙን ስም እንሳሳ አለው በዚያም ታላቅ ግድብ ውሃ አሰርተዋል በአካባቢው የሚገኙት ወንዞች አንዱን ሥራ አለው መረብ ስሉ ማለት ነው ሌላውን ደግሞ ባርካ አለው ባርካ ሰፋ ማለት ነው ። በዚህን ጊዜ የንጉሥታቱን መቀመጫ ከሱባ ወደ ማባ አዛወረው ከሱባ እስከ ሳባ ያለው ምድር አኩብ ይባል ነበር። ምንጊዜም ምድር ወርቀዘቦ የሚገኝበት ነው የመልክ ጻዲቅ ልጅ ኢትዮጵ የተባለው ኢትኤል ብዙ ዘመናት የነበረበት በየቱ ወርቅ የበ... በረበት ሃገር ነበር ።

እዚ የአባቶቹ ነኩሽና ቀብበ የባምኑድና ዋኢትዮጵ አፅም በተቀበረበት ቀኝ አጠገብ ሄዶ የንጉሥታት መዲና መከተሙንና ስመ... ንም በኩሽ ልጅ ሳባ ብሎ መሰየሙ የአዩሩን ጠባይ በምን እንደ... ወደደው ወይም የአባቶቹን አፅም ለማስከበር ይሁን ለማስታወስ... አይታወቅም በመፅሃፈ ሱባኤ ውስጥ የሚዘረዘር ነገር የለውም ።

እዚ ስንደቅ አላማ ለልጆቹ በየአስር አመቱ የንጉሥ ልጅ ሁሉ ሊነግሥ የፈለገ ከንጉሥ ጋር መግጠም አለበት ብሎ ህግ ስለመ... ረቱ ከግዛ በአስር አመቱ የሚገጥመው ስለጠፋ በአንበሳ በረ... ውስጥ ያለውን አንበሳ ሁሉ ገጥሞና ታግሎ በቡጢ እየመታ ... በሳምንቱ ገደለ ስለዚህ የሚመስለው ጀግና ስለጠፋ ለልጁ ... የሳባን ግዛት ሰጠው ታምሪን በገዛ በአስር አመቱ ከወንድሙ ጋር ገጥሞ ተገጣጥሞ ስለሞተ ሸሚያ ኢዮቁራ ተብሎ ነገሠ እሱም በአስር አመቱ ስንደቅ አለማእከናሁብ ለሚባለው ወንድሙ ... ቤተሰቡን ይዞ ወደ አባይ ተሰደደ በአክናሁብ ዘመነ መንግስት በሰፊ... ልዩ ቀለም ያላቸው ባንዲራዎች በየመሩ ማገባርና ንገሱ በሰረ... ቤታ እንዲሰቀሉ አደረገ አክናሁብም ከማደሩ የሚባለው ልጁ ... በረኛው አመት ተገጥሞ ስለተወቃ በፈንታው ልጁ እሱም ... ተብሎ ለአስር አመት ነገሠ ቀጥሎ በኑ ቀብቶ ስንገሥ ይባል... የበኑ ልጅ አሚን ከኖስ የአሚን ልጅ አሰሩሩ ይውስ የነ... አምር መረብሳባ ቀጥላ አዙቱ ብሊና ኢትዮ መሸመሪያዊ ... ዘማሬር ቀለመጥቁ ተብሎ የዐፈትን ቀለም ወደጥቁር የቀየሩ ... ልጅ ጆርጂቶር ግዳር ሳባ ቀጥሎ ወንድሙ እንጋባ በአንበሳ ... ሁሉ በሳባ አስር አስር አመት ገዝተው አለቀ፤ በንጉሡ ነገሥታ... ላቁ እዚ ስንደቅ አላማ በልጅ ልጁ በአምስተኛው የልጅ ልጅ ... ኢጋብዖ ተብሎ በመቶ አምሳ ስምንት አመቱ የሳባን ግዛት ... ነገሥነ ግዛት ጋር ወምር ይባል ጀመር እንደዚህም ሆነ በራ... የናስ ቁር የሚያደቀ ከእዞ ቆዳ የተሠራ ኢጀና ጥሩር የሚለብሱ

ግራቸው የናስ ኀንባሌ የሚያደርጉ መርዘኛ ቀስትና ጦር የወርቅ ጋሻም የሚይዙ አንድ ሚሊዮን ሰምንት መቶ ሽህ ወረኞች አዘጋ ጅና ከንብዐ እስከሞአብ ያሉትን ሃገሮች ወረረ እግሌትንና ፍል ስጤምን አስገበረ ስለዚህ ያስገበረውን ሃገር በስሙ አጼያ አሰው ትርጓሜውም ታላቁ ሃገር ማለት ነው እንደሰባውያን አጼያ ሲሆን እንደአብራዊያን እሲይ ይባላል ።

በዚህን ጊዜ በጀንና በምዕዲ በሚገኙት ሸለቆዎች ውስጥ ድንኳን አስተክሎ ሳለ የመልከጼዲቅና የኢትኤል አምላክ በራእይ ተገለፀለትና እንዲህ አለው ይህ ያለህበት ምድር እርስትህ ይሆን ዘንድ የአባቶችህ አምላክ አልፈቀደም አሁንም ወደመጣህበት ተመለስ በዚያም በግዮን ወንዝ ዳርቻ ለኢትኤል ቃል ኪዳን በአደረኩ በት ሥፍራ ሂድ በዚያም ዳግመኛ እገለፅልሀ አለው አለው አጼም በዚህ እንዳልኖር የሚከለክለኝ ምን ነገር አለው ለዘለአለም የሚ ኖረው ቃል ኪዳኑ ለልጅ ልጅ የሚሆነው ቅዱስ አምላካችሁ ይህን ምድር ለእስራኤል ልጆች ይወርሱት ዘንድ ፈቅዶላቸዋል ። አሁንም ፍቶዱ ይቃጠፍ ዘንድ አይቻልም ይህም ህዝብ እንደአንተ አህዛብ የሚገዛቸው ባሪያ የሚያደርጋቸው ንጉሥ የላቸውም ንጉሳቸው አምላካቸው ነው የሴም መንግሥት ለዘላለም ይኖራል የርስትም ሆኖ የሚያስተምራቸው የአምላክ ካህን ነቢዩ ነው አለው ። አሁን ከዚህ ተነስና ሂድ አለው አጼ እንዲህ አለ እንደቃልህ እኛዳለሁ አንድ ነገር ከአንተ ለመጠየቅ እሻለሁ ከምትለኝም ሁሉ እንዲቀየን ቃል አተምቅ ዘንድ አይቻለኝም አሁንም የአንተን ህግ የሚያስተ ምር ነቢይ አምላኩን ሰው አይቶ እጅ መንሻ ጋዳ ሰጥቼው እሄድ ዘንድ ፈቃድህ ይሁንልኝ አንተ ለመረጥከውና ለወደድከው ነቢይ ለእሱ ነፍሴን እሰጣለሁ አለው አምላክም አለው አባቶችህ ያላ ቀን ታያለህ እድሜህም በብዙ ትጠግባለህ መንግሥትህም ታስረዝማለህ እጅ መንሻ ጋዳ በዘርህ እና በቃል ኪዳኑ ቀን እንጂ ዛሬ አይሁን ለማየት የፈለከውን የወደድከውን ለማድረግ ተፈቅዶልሃል አለውና በተ ራራዎች መካከል ሲያልፍ ሰስት ሆኖ ከዚያ ከራእይ ጋር ሳለ የፍልስ ጤዎች የጦር አለቆች እንደተሰበሰቡና እንደተዘጋጁ ሰማ ፍልስጥ ኤማውያን ለማጥፋት ሲነሳ በፍልስጥኤም ዘንድ ታላቅ ነጐድጓድ አንጐዳጐደ አስደነገጣቸው የእስራኤል አምላክም መታቸው የእስራ ኤል ሰዎች ከምዕዲ ሸለቆ ወጡ ፍልስጥኤማውያንንም አሳደዱ ከአጼ ጋር ያሉ ሰባውያን ኩሳውያን ጭፍሮች አምላካቸውን የእስራኤልን አምላክ አመሰገኑ ።

በዚያም እጼ እሴ ነቢዩን ሳሙኤልን የእምላክ መላክ ንግርት ነበርና ከ
እጼ ጋር ተገናኘና እጁን ሳመው ሁሉቱም እንደሚተዋወቁ ሰዎች ሆነው
በአንድ ላይ እምላካቸውን አመሰገኑ በተገናኙበት ቦታ ሳሙኤል አንድ
ድንጋይ ወስዶ በምዕጻና በሺን ሲን መካከል አኖረው ስሙንም እም
ላኬ ረድቶኛል ሲል አቤን ኢዘር አለው በፍልስጥኤማውያን ተዋረዱ
እስራኤሎች በዚያ ቦታ ባለእርስት ሆኑ ሰባውያን ኩማውያን በደህና
ወደግዛቶቻቸው ተመለሱ የእጼ እኑጋንስ እጼ በንግሥ በ14ኛው አመት
ንጉሠ ነገሥት ክብር እንደገና ለማክበር እንደተነሳ። እንመልከት የአ
ንድ መቶ ሃምሳ ስምንት አመት እድሜ ሰው ንጉሠ ነገሥት ለማድረግ
ለሰላሳ ሶስት ነገሥታት ለአንድ መቶ ጉማዎች በየቋንቋቸው ለሹማ
ምንቱና ለአለቆች አዛውንት ለየንዳንዱም ሃገር እንዲጽፉለት እንደቋንቋው
ተጻፈና በእጼ ሰንደቅአልማ ቀለበት ማህተም ተደረገ ፀሁፉም
በኩሳውያንና በሱባውያን በአዜባውያን በሱባያ በተወለዱትና በፈጣን
ፈረሶችና ግመሎች በተቀመጡ መልክተኞች እጅ ሰደደው በዚህም
ፀሁፍ በከተሞችና በዋሻ የሚኖሩ ሁሉ እንዲሰበሰቡና የንጉሠ ነገሥት
ነቀን በአል እንዲያከብሩ አለቆቻቸው ባይልኩ የሃገሩንና የህዝቡን
ሠራዊት ሴቶቻቸውንና ህፃናቶቻቸውን ሁሉ እንዲያጠፉና እንዲገድሉ
ትእዛዝ አስተላለፈላቸው ።

በዚህ ፀሁፍ ከከተሞም እስከ ሙት ባህር ከታላቁ ባህር እስከሬሴን
ያሉ ጉማዎችና የጉሳዎች አለቃ በዓሉን ለማክበር ተሰተሰቡ ነገር ግን
በአሶርና በግብፅ በሚደንግም ያሉ አለቆች የግብፅ ፈርኦኖች እልተገ
ኙም የፀሁፉን ትእዛዝ አላከበሩም ነበር የንግርት ንግሥ አከባበር
እንደዚህ ነው ከእዋጅና ከትእዛዙ በኋላ ስድስት ወር በግዩን መገ
ናኛ ኢትዮጵ ኢትኤል በስሙ ምድሩን ኢትዮጵያ በወንዘን ኢል
ብሎ ስም አውጥቶ የከበረ ድንጋይ በአስቀመጠበት ምድር ላይ
ሉትና ቀን የተለያዩ የራስ ጌጦች ስማቸው ጌራ የሚባሉ ልዩ ልዩከ
በር ባርኔጣዎች የእጅ ቀለበቶች ከእንቁዩጸና ከአልማዝ ድንጋይ ሺህ
ጊዜ መቶ ሺህ የሚሆኑ የወርቅና የብር መክሊቶች ተዘጋጁ ኢኤል ማለት
የእምላክ ፍንጣሪ ግዩን ፈላሺ ማለት ነው ። ከስድስት ወር በኋላ ንጉሠ
ነገሥቱ እጼ ሰንደቅ አልማ አንድ መቶ ሺህ ሰረገሎች በአስር ሺህ
አንድ መቶ እምላ ፈረሰኛ ሰባት ሺህ ልዩ ልዩ ፈጣን ግመሎች በወ
ርቅና በብር ጌጥ የተሸለሙ እግረኛ ሰራዊት ግን በእግሩ እንዳይሄድ
ተከልክሎ ስለነበር ። ፈጽሞ የለም በነዚህ ሁሉ ታጅቦ ወደ ግዩን
ዳርቻ ወረደ በዚያም በመንፈስ የሚመራው በነቢዩ ራኤል በካህ
አባ እጅ ከተለያዩ እንሰሳት አበባዎችና ቅጠሎች ሽታቸው በሩቅ

ከሚሸት የእንጨት ቅርፊቶችና የተለያዩ የእንጨትና የድንጋይ ሙጫ- ዎች ከተዘጋጀ ሽቱ /ቅባአ መንግሥት/ ሰባት ቀን ከዐጠነበት በኋላ በስምንተኛው ቀን እሁድ ሌሊት በቅዐና ቀንዲል መብራቶች በያዙ በአስራሁለት ሚሊዮን አለቆች ፊት ከተልባ እግር በተሠራ ሃር ልብስ አልብሰው በግዮን ባህር ውስጥ እስከ አንገታቸው ድረስ ተውጠው ቅባአመንግሥትን በራሱ ላይ አፍሰሰው ከአልማዝና ከእንቁዩል የተሠ- ራውን የአባቱ ቅርፅ ዘውድ ደፋለት ሺህ አመት ንጉሥ እንተን የሚ- መስል የሚስተካከል ንጉሥ ፈጽሞ አይመጣም ስምህም ለዘለአለም በዘርህ ዘንድ አጼ እንጅ አጼ ወይም እሴ አትባልም የመንግሥትህም ስም ያዩት በንጉሥ ቅአልማዝ ሲባልና በተለያዩ ቀለሞች በአለም ላይ ሲ...ነበሰ ሀ አድኖዉ አለህ ብሎ ነቢዩ ዕሌል ትንቢት ምናገረለት ፊሌል ማለት የእምነቱ ብርሃን የተሰጠው ንጉሡ ነገስት አጼ ሰንደቅ አልማ በሁለቱ ከዘናቶች መካከል ሆኖ በግዮን ዳርቻ ባለው በተከበረ ውና በአማረው እያስጌጥ ድንጋይ ላይ ከባዱ ወጥቶ ተቀመጠ በፊቱ ያሉ ሀገሮች በየቋንቋቸው በመንግሥትህ ስር ሁነን እንገዛ ለን ሰላ- ትህን እናጠፋለን ሺህ አመት ንጉሥ እያሉ በልልታና በክብር እየሠዉ ዋሽንት እንቢልታ በቀንደ መለከት እየነፉ ለሙን እየመሰገኑ ይጠሩት ጀመር ። ከዚያም ከግዛቱ ሟገሮች ሰላሳ ሶስት ነገሥታት የነበሩትና ሌሎችን ትእዛዙን አክብረው እጅ መንሻን የከበረ ድንጋይ ያመጡ- ለትን አለቆች አሥሩ ስድስት ዉዳሮ በድምፁ አርባ ዘጠኝ ሰዎች ተመርጠው ከግዮን ባህር ተብተው እንዲወጡ ከአደረገ በኋላ የንጉሥ የዘንጅን ማዕረግ አዲስ ስም እየሰጠ እንደየደረጃቸው ከአልማዝና ከከበረ ቱስ ወርቅ የተሰራውን ባርኔጣ ከዋልና እያስጌጠ ከሚባል ድንጋይ የተሠሩ ቀለበትና ዋንጫ ሰጣቸው ከንጉሶች በታች ላሉት ዘጠና ዘጠኝ ባለ ሥልጣኖች ከብርና ከነሃስ የተሰሩ መታጠቂያ ቀበቶዎች ታደሉ እነዚህንም ሲሾም አንደኛው አንዱን እንዲያከብር የአንደኛ ውን ሐሳብ አንደኛው እንዳይቀበልና እንዳያስተናግድ እንደደረጃ ነገሬ ግን በሚከበሩቸው ነብቶ እንዲያስታርቅ የንጉሥንት ማዕረግ ከዘሩ እንዳይ- ወጣ ለጀ በንጉሡ ጊዜ የሚገባውን ጋሻ እጅመንሻ ወደንጉሡ ነገሥቱ ይዞ መጥቶ ንጉሥንቱን እንዲያሳውቅና ንጉሡ ነገሥቱም እንዲያፀድቅ ለቅና ንጉሡ ነገሥት ያሄዳል ወደተባለበት ሃገር በቅርብ ያለው ጀዶ እንዲቆይ መንገድ እንዲጠርግ የሚል በግመልና በፈረስ ብሬና በቡባ ሞገቶ ራዶል ተዕር ለየንጉሶች ታደለ ከዚያም ከታደለት ይብዳቢ ሙበት የታላቁ የኢትዮጵ ኢ.ትኤል ህግ አብር አለ የፈጣሪህን አወቅ፤ አፈጣሪዘ ተገዛ የሚል ቃል በዚህን ጊዜ ከመጀመሪያው ሥርዓት ላይ የተማዘው ሥርዓተንግሥ ለመፈጸም ይዘው የመጡትን የዳር አሁሩ

አንበሳና ፡ ነብር በፊቱ ላይ በጦር እየወጉ በሰይፍ አንገቱን እየቆረጡ ደሙን አፈሰሱት ፡ አልገባም ያሉ የተማረኩ ሰዎችም በሰይፍ አንገታቸውን ሊቆርጡ ሲል ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ እስረኞችን እንዲለቀቁ አድርገዋል ከአሁን እኛጅ በኋላ ግን ንጉሠነታቸውን አምነው የሚያከብሩና የሚገብሩ እንድትገዙ ሲል በፃፈው ደብዳቤ ላይ እንደገና እስር አድርጓቸዋል ። ይህን የመሰለ የንጉሥ ነገሥትነት ሥርዓት በሚፈጸምበት ሰዓት ለአራት የተከፈሉ ሃያ ዳኞች በየንጉሡ እንዲኖሩ አስሩ ስለግብር ጉዳይ ሌሎች አስሩ ደግሞ ስለመሬትና ስለሚደገፉ ሰዎች የሚፈርዱ ናቸው ። እነዚህም የሃይድ ጣቶች ምሳሌ ናቸው ።

ሌሎች ደግሞ ውስጥ የንጉሡ አማካሪና እንደራሴዎች ውስጥ ግራና ቀኝ የእጆችና የእግሮች ምሳሌ የበላይ ጦር አዛዦች እንዲኖሩ አሳሰ ህግ ሰላሳ የሚሆን አቅርቦአል ። መቅድሙን ከመጨረሻ ስላላሰቁ ደመው ታላቅ አጼ የደነገገው ህግ ይህ ነው ።

1ኛ/ አል ህገምችን እንደኛ መደብ የተባለውን ፈጣሪ መንፈስ ነፍስን ከፈራሽ ሥጋ ጋር ያዋሃደ ዳግመኛም ነፍስን ከሥጋ ነፃነት የሚወስደን በህይወት የሚያኖርን አምላክ በቅን ልቦና ማመን ምንግዜም ማንኛውም ሰው በሀሊናው አምላኩን ማመስገን ነው ምንም ሀሊናውን ባንገባው ሥጋውን ስለምን ግዛው ሳያምንና ሳይሰግድ ቢቀር ከሕዝብ ስለሆነ እንዲጠፋና እንዲገደል ህግ ተደንግጓል ።

2ኛ/ ንጉሡ ነገሥቱን ወይም አጼው ያነገሠውን ወይም በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ የተከበሩትን እስራኤ የተባሉትን ባለሟሎችና መልእክተኞችን እንዲሰለኪው አድርጎ ካላከበረና ካልሰገደ በአደባባይ እንዲገረፍ ወይም እንዲሰቀል ሃብቱም እንዲዘረፍ ተደንግጓል ።

3ኛ/ ንጉሡ የመረጣቸውን የሾማቸው የህዝብ መሪዎች ከሚያገኙት ገንዘብ ውስጥ ቀረጥ ወይም እጅ መንሻ እንዲከፍሉ ባይከፍሉ ባሪያ ሆነው ለንጉሡ እንዲያገለግሉ ተደንግጓል ።

4ኛ/ አጼው በሄደበት ሃገር ሁሉ ሰራዊቱ እንዳይራብና እንዳይጠማ የንጉሡ ወታደሮች አስቀድመው ሄደው የንጉሡትን ለህዝብ ብ ጋጅቶ ባይቀይ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው ብቻ ሲቀሩ ሃብታቸውን እራሳቸው ባሪያ ሸጊውና ለንጉሥ አገልጋይ ሆነው እንዲቀሩ ይደቸው ተደንግጓል ።

5ኛ/ ለንጉሡ ነገሥቱ የሚሆን ፈጣን ሩጫሙችና ቀልጣፋ የፖ ሰጣቶች በየጊዜው ከተለያዩ ሃገሮችና መንደሮች ውስጥ ተመርጠው

እንዲሳኩ ተመርጦ ወይም አልመረጥም ያለ ሁሉ ታድኖ እንዲገደል በአካባቢው የሚገኘው ንጉስ ሃገን ባይገድል ወይም ፡ ሌሎችም ባይሉኝ ከንጉሥነት እንዲሻርና ሌላው ንጉሥ የአርሱን ግዛት ያዘ እንዲገዛው በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

6ኛ/ ንጉሱ ያስገበረውንና ያቀናውን ሃገር በንጉሡ ነገሥቱ ፊት በየአራት አመቱ መጥቶ እንዲያሳይ ከአስገበረው ግብር አስር እጅ አንዱን እጅ ለአጼው እጅ መንሻ (ጋዳ) እንዲያመጣ ባያመጣ ወይም መክዳቱ ቢታወቅ በንጉሡ ነገሥቱ ሰራዊት እንዲደመሰስ በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

7ኛ/ ማንኛውም ባለሥልጣን የሀገር ለአታ በሞተ ጊዜ ሥልጣኑን አለቅነቱን ለመጀመሪያው ልጅ እንዲሰጥ ልጅ ባይኖረው ለተከታዩ ወንድም ልጅ አሱም ባይኖረው የሃገር ሽማግሌዎች ለመረጡት አስተዋይ ሰው እንዲሰጡት አለቃ የሆነውም ለበላዩ ንጉስ እጅ መንሻና ግዳይ ይዞ ሄዶ እንዲያስታውቅ በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

8ኛ/ ያለአጼው ፈቃድ ንጉሱና ንጉሥ ተጣልተው በድንበርም ይሁን በተቅም የተነሳ ቢዋጉ ማንኛው ጥፋተኛና ድንበር ገፊና በሀ ተኛ ሆኖ የተገኘው መንግሥቱን ለቆ ያለው ሃብት ተወርሶ ከአለበት ሃገር ለቆ ወደሌላ እንዲሄድ ሁለተኛ ቢያጠፋ ቢገኝ በአደባባይ ላይ በእንጨት እንዲሰቀል በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

9ኛ/ አንደኛው ንጉሥ አንዱን እንዲያከብር የአንደኛውን ልዓት አንዱ ንጉሥ ተቀብሎ እንዲያስተናግደና እንዲያሪዳ በሁለቱ ሥልጣን ያለውን ጉዳይ ከተረዳ በኋላ ጥፋተኛውን ቀጥቶና ለተበደለው አስከፍሎ በአሉ የእጅ ጣቶች ቁጥር ፊት እንዲያስታርቅ እርቁን የማይሰ [illegible] ውን ወንበር ያላከበረ ፊቱም በሩም ሆኖ እራሱ እንዲጠፋ በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

10ኛ/ የንጉሥነት ማዕረግ ከመቀበሉ በፊት [illegible] ቀለ ጥና ይፋር መሆኑን ለመግለፅና ለማሳወቅ አራት ፈተናዎች [illegible] አለ በቅ አንደኛው ከነገሡም በኋላ ሆነ በፊት ንጉሡ ነገሥቱን አሳከብሮ ብሎ አስገዛ ያለን ንጉሥና ባለሥልጣን የገበረን ሄዶ ገድሎ ግዳያ አም ጥቶ መጣል የገደያን እጅ አንባርና የግራ ጆሮ እንዲጥል ሁለቱ በአጼው ግቢ በሚገኙ የግራና የቀኝ ሁለት ቋሚዎች እጅ መቀመጫ ሁለ ተኛው ንጉሥ ሆኖ የቤተኞቹን ተዋጊዎች ማስከተብ ሲያስፈር ሲገኝ የገ ዳ ለሰተኛ የንጉሡ ነገሥቱን አቋጅና ሆኖ ሲያቀልና ሲገኝ የሚያየ

የውን የህዝብ አለቃ በሥስክር መሃል የገደለ አራተኛ ማንኛውንም
ከመግደሉ በፊት ከንጉሠ ነገሥቱ ዳኞች ፍቃድ አግኝቶ ለማንም ሰው
ሳይገልጽ ለጨረሰ ልዩ ማዕረግናስ ም እንዲሰጠው ህግ ተደንግጓል

2ኛው መደብ

ለንጉሠ ነገሥቱ የሚላክ ጋዳ እጅ መንሻ በክብር ተይዞ
11ኛ/ በእልልታና በሆታ እንዲደርስ በአጼው ደጅ ከመድረሱ በፊት ለአሰሩ
እግረኞች ዳኞች እንዲነጋገርና በነእሱ እጅ ተይዞ ለአስር ቀን እንዲ
ቆይ በህጋችሁ ተደንግጓል ።

12ኛ/ አብነ ግዩን ጥቁር አልማዝ ከባህር ውስጥ የሚገኝ እንቁ ግዩን
አልማዝ የተባሉትን ድንጋዮችና ሰማያዊ ነጭ ብጫ የሆኑ ሉልና ክብር
ዩጳ ድንጋዮች የአገኘ በአስቸኳይ በአካባቢው ለሚገኙት አዛውንቶች ሪህ
ዝብ አለቆች ተናግሮና አሳይቶ በንጉሡ እጅ አጼው ወዳለበት ሳባ ከተማ
የአገኘውንና ክቡር የሆነ ዩጵ ድንጋይን ይዞ በክብር እንዲመጣ ለአ
ግኘው እድለኛ ሰው በካህኑ እጅ ለንጉሡ ከወርቅ የተሠራ አንባር
የጀሮ ጌጥ ሎቲው አስር መክሊት ወርቅ እንዲሰጠውና የንጉሥ እማች
እንዲሆን በህጋችሁ ተደንግጓል ።

13ኛ/ የንጉሠ ነገሥቱን እንጥረኞችና የቤተ መንግሥት ባለሚሎ
ችን የእልፍኝና የቀኝ ቤት የግራ ቤት ሰራተኞችን ተጠግቶ ያነጋገረ
ወይም የጠራ ተጠሪውም ሰምቶ ጠጋ ብሎ ቢያዳምጥ ሁለቱም በቆሙበት
ወይም በተቀመጡበት ቦታ እንዲሰቀሉ ፈጽሞ በህጋችሁ ተደንግጓል

14ኛ/ የንጉሠ ነገሥቱ ጸሃፊዎችና እንጥረኞች ሸክላ ሰሪዎችና
ብረት ቀጥቃጮች ልዩ ልዩ ቦታና መንደር እንዲሰጣቸው ተደንግጓል፣

15ኛ/ ካለንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ማንኛውንም ቅርፅ ለአምልኮም
ሆነ ለሹመት የሚሆን ጌጥ ተሰርቶና ተቀርጾ ቢገኝ ሰሪው እንዲገደል
ነገር ግን ፈላስፋ መሆኑ በህዝብ ዘንድ ከታወቀ በአስሩ ዳኞች እማኝ
ኝነት ተመልምሎ ቆይቶ በንጉሠ ነገሥቱ ፍቃድ እንደየችሎታው
በተፈቀደለት ጥበብ እንዲሰለፍ በህጋችሁ ተደንግጓል ።

16ኛ/ከነብርና ከአንበሳ ከቀበሮ ቆዳ ልብሶች የሚሰፉና በተለያዩ የ
እንስሳ ጠጉር ተፈትለው ለካባና ለምንጣፍ የሚሆኑትን ልብሶች ለሚሰሩ
ፈላስፋዎች በአመት አንድ መክሊት ወርቅና በየወሩ ቀለብ እንዲሰፈ
ርላቸው ነገር ግን በሚሰጥበት ልዩ ልዩ ልብሶች ውስጥ ያለንጉሠ ነገ
ሥቱ ፈቃድ ቢሸጥ ወይም በወርቅ ቢለወጡ ገገርውና ሻጭው በአደ
ባባይ እንዲሰቀሉ በህጋችሁ ተደንግጓል ።

17ኛ/ ንጉሠ ነገሥቱ ቤተመንግሥት ወይም ከዚኅ ሲያሠራ በእዘዘበት ቀን ንጉሠ ነገሥቱ የሚገባቸው ሃገሮች በየተራ መጣበቀው እና ጳጳሶችንና ፈላስፋዎችን እንዲረዱ ባይመጡ ሽጊ ባሪያ ሁነው ለሌሎች ሃገሮች ተሸጠው በተሸጡበት ዋጋ የተጀመረው ሥራ እንዲያልቅ ።

18ኛ/ ንጉሠ ነገሥቱ ከማያገባው ሩቅ ሃገር ተሰደው ጥገኝነት ቢጠይቁና ለንጉሠ ነገሥቱ እንገዛለን በሀገሩ ሥር እንድራለን ብለው ለደተኞች የሆኑ እንግዶች ቢመጡ ተቀብሎ ሁሉቱ ዳኞች በመረጡላቸው ምድር ማስፈር ከእንግዶች ውስጥ ከአምልኮአቸው በስተቀር ሌላ ህግና ሥርዓት እናደርጋለን የሚል ቢገኝ ፈጽሞ እንዲገደል በሀገሮቹ ተደንግጓል ።

19ኛ/ ከንጉሠ ነገሥቱ ማዕት ውጭ ያሉ ንጉሥታት ለኢጴው ክብር ሲሉ እጅ መንሻ ቢያመጡ ከእብራዊ ህዝብ በቀር በእስሩ ዳኞች እጅ ታይቶና ተመርምሮ ንጉሠ ነገሥቱ በሚያከብረው በዓል ቀን እንዲያቀርብ ይደረጋል እብራዊ ግን የአምላካችን ስራዊት ህዝብ መሆኑን በመንፈስ ለእኔ ለእጴ እስኪታዩኝ ድረስ ጋዳ እጅመንሻ ልዩ ልዩ እጣኖችና ከርቤዎች ሽታ ያላቸው እንጨቶች ይዞ ሄዶ ለንጉሳቸው ማቅረብና መስገድ ይኸም የሚሆን አባቶቻችን እንደነገሩን የጋራቱ ክብብ ወጥቶ እስከሚመራን ድረስ ነው ።

20ኛ/ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ልዩ የክብር ዘበኞች አጼው በሚያድርበት በልዩ መንግሥቱ ሌት ተቀን ንቅተው በየንታቱ መጣበቅ አበጋዞቹ አምስት ሺህ ለቀን አምስት ሺህ ለሌሊት እንዲሆኑ ተደንግጓል ።

21ኛ/ ንጉሠ ነገሥቱ የሚውልበት የክብር ቦታ ሁሉ የአጴው ቤተ መልእክተኞች አጫዎቾችና አሳላፊዎች ንግስቲቱ ኢትዮም ሆኑ ከአጴው ፊት ዳኛ ፈቃድ ወይም የአጴው እና ተናጋሪ ዳኛ ፈቃድ አጴው በአለበት የክብር ቦታ ሁሉ መግባት ወይም መቅረብ ፈጽሞ የተከለከለ ስለሆነ ቢገባ ወይም ቢጠጋ በአጴው የክብር ዘበኞች በፍጥነት በጦር እንዲወጋ በሀገሮቹ ተደንግጓል ።

ስድስተኛ መጽሐፍ

22ኛ/ ሀያው አምላካችን ለአባታችን ለኖህና ለልጆቹ ለእኛ ለተፈጠርን እንዲህ አለ በእኔና በእናንተ መካከል ከፍጥረት ጋር ላለው በሀያው ነፍስ ሁሉ መካከል ለዘላለም የማያደርገው የቃል ኪዳኑ ምልክት ይህ ነው ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ የቃል ኪዳ

ኑም ምልክት በሰማና በምድር መካከል ይሆናል በምድር ላይ ይመ ናን በጋረደው ጊዜ ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች ። እሷም ዛሬ በዐ ያው እምላኬ ፈቃድ በአባቶቼ ዘሩን በረገጡዋቸው ምድር በኢረቶብት መሬት በቀመሱትና በተጠመቁበት ውሃ ድንበር ሆኜ ይህን ለዘለ አለም የሚሆን በሀገብና በመንግሥት መካከል ያለውን የፍቅር ምልክት አዋጅ በከፍታ ቦታ ላይ ሰቅዬ አመሰብልብላችኋለው እሬ ንጓዴ ፡ ቢጫ ፡ ሰማያዊ ፡ ቀስም መሆኑ አረንጓዴ ምድራዊ ብሜው የፍቅር አበባ በማያዩው የሰማያውያን መንፈሳዊ አካል እንዳለን የመጣበ ምልክት ነው ይህን አዋጅ አይተም ሆ ምት ያላከበ ሩና ያላመነን በሬያ ሆኖ እንዲኖር በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

23ኛ ማንኛውም ንጉሥ ነገሥቱን የሚገልፅ በንደቅ አዋጅ በፊት በፊቱም ሆነ በኋላው ሊሰቅል ይችላል ነገር ግን ከማድረጉ በፊት ለንጉሡ ንጉሠ ነገሥቱ ቀለሙን ማሳየትና ማስመረጥ አለበት ይህ ሳይ ሳውቅ ቢሰቅል ከመንግሥቱ እንዲወርድ ማድረግ ባይወርድ እን ዲገደል በሀጋችሁ ተደንግጓል ።

24ኛ የእጼው የሰላም ሰራዊትና የጦር ሠራዊት አዋጅ ከን ጉሠ ነገሥቱ በታች በንት ንጉሶች እንዳሉት የሚገልፅ የተሸነሸነ አዋጅ በፊትና በኋላቸው እሲዘው እንዳሄዱ በሀጋችሁ ተደንግጓል።

25ኛ በሰንደቅ አዋጀው [እምድ ላይ] ዘንግ ላይ ከወርቅና ከብር ከነሃስም የተሰራ የክነብ ቅርፅ ማስቀመጥ ይህንን ሳያደርግ ሰንደቅ አዋጅ የሰቀለ በአደባባይ እንዲሰቀል በህግ ተደንግጓል ።

26ኛ ማንኛውም ንጉሥ በሰው የመክልይት ብርና ወርቅ ሊያስቀርፅ ቢፈልግ በቅድሚያ ለንጉሠ ነገሥቱ የከበረ ሉል ድን ጋይና ሊያስቆጵ ክርስቶ ድንጋይ ከበርር እንቁዩልን ይዞ መቅቶ እጅ መንሻ ማምጣት አለበት በእጼው ፊት የከበረ ሆኖ ከተገኘ በሰው እንዲያስቀርፅ ይፈቀድለታል ነገር ግን በገዛ መብቱ ቀርፆ ቢገኝ እጼው በእሥራው ወህኒ ቤት ተግዞ እንዲኖር ፈጽሞ በህግ ተደንግጓል ።

27ኛ የንጉሥ ልጆች ሁሉ ተሰብስበው በአንድ ልዩ ቦታ በአዘጋጀው በአስረኛው እመት መኖር አለባቸው ንጉሠ ነገሥቱ ፍቃደኛ የሆነ ከንጉሥ በዓል ቀን ለውድድር መቅረብ አለባቸው በዘዘሁ ፊት ከንጉሥ ዘርንት እንዲወ ጋር ሲገናም ያልፈቀደ ይደረጋል ።

28ኛ፤ ከንጉሡ ጋር የገጠመና ድል ያደረገ የተጠቂውን ስም በልዩ አክብሮ መዋል አለበት ቀረ እለው የሆኑ መግቢያ ቃል መቅደሙ ።

ኢል ፈጣሪ እንዳለ እንደሚኖር የምናየውና የማናየውን ሁሉ ከእኛ በፊት ከእሱ እንደተፈጠሩ ሰምታችኋልአውቃችሁማል ። ስለዚህ እኛን ለክቶ ሳይሆን ለመልካም ለፈጠረን ለኢል አምላክ የምንሰጠው ስጦታ በፍፁም ሀሊና እምነን ማምለክና ትእዛዙን መፈጸም ሁሉን ማክበር ነው ፍጹምነት የሌለውን ሀሊና ይንቅፍ ። በንሰሐም ተሰናክላችሁ ዘንድ ብዙአማልክቶችን ያስነሳባችኋል ። የአማልክቶች አምላክ ፍፁምችን ያነሳ ትወድቃላችሁ ። ነገር ግን ቀዋል ከፍ ከፍም ያደረጋቸዋል ። እኔም እላለሁ ወደ አምላኬ ተሰፉ በዚ ሰወጣ የማይስተሰኘ ቢኖር እንቅፋት ሳይሆን ናፍን እልካለሁ ያልወጣ ያም ተሰባብሮ ወደታች ይወድቃል ወየውሎት ሳይሰበር የሳመውን ተሰባብሮ ልወጣ ቢል ይደቃል እንጂ አይድንም ደቁ የሙገባ ሸክላ ሰሪ ሰባሪውን ጠጋኝ የሆነው እስከሚመጣ ስለእሱ ሆኖ እንደ ውን እጅ መንኛ ጋዳ ይዘን እስከምንሄድ በምልፍላችሁ ቢመጣ ፈጽሞ ይገ ቅቁዩ ሆኖን የሚያድስ እንጅ ሆኖን የሚሰበር ለማበጠር ነው የመጣ ስለዚህ በማ ደል ሆኖ የተበተነውን ሰብስቦ በእውቀትም ቀነ ስለዚህ ቴተዋል ተዘጋጁ በትብብም ተመሰረተ ከሆነ ይቃጠላል ነገር ከሆነ ይወጣ ሲበጠር ትድፍ ነው ትድፍ በሆነ የምትኖሩ ሁሉ ፍሬዎችሁና ግን ፍሬ ከሆነ ይዘራል ይለቀማልም ሆኑን ተቀበሉ ሥርዓታችሁም ይህ ነው ።

በሊሊ ምር ሆነው የሃርን የሚገቡት ባለሥልጣናት | በአጼው ቤተመንግሥት ውስጥ የሚገኙት ባለሥልጣናት

| የሱሳ ቋንቋ | ትርጉም | | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| አጼ መሻዛ | አስፈሪ ግርማ ከበር ዘበኛሥት | አጼማገስ | ንጉሠ ነገሥት |
| ጠ'ገጀር | ከበር ንጉሥ | (አቶ) አቅቃ | ንግሥት |
| ገጋን | ንጉስ | አቴማገስ | ንግስቶ ነገሥት |
| ጀጎ | ከበር ሰዎ ለንጉሠ ነገሥት ለጅ ሰርዊግን | | አስተዳደም የሚሰጠው ሰዎ በአጼው ጋር የሚቀመጠው ታላቅ የቤተመንግሥት ጉዳይ |
| ገገንሳም | የንጉስ ሀኪል | አጼሉን | ካስስፈተድ ወይአጼው |
| ጀጎም | የሆር ጠቅላይ አዛዥ | አቴገ | አስረዳኛ አዛገር |
| ሣንሰርዊ | የሆር መሪ | አቃቴዋር | የግቢ ሹም |
| መንዋቢ | የከብር ሰዎ ለአፈ | ሣንዓቂን | ከመናበን የሚያስቀምር |
| ኢመገርዊ | በየቦታው ተላላኪ ጆሮው ታዳጋሪ | የግኒ | የልጆች እስቃ |
| ንዋዶ | (አጅ) ያልዓይ ለዓ | ሃዋኒስ | የአጼው ልጆች |
| አጎ | (አጎር) የዓርድ ዳኛ | አከዓኒስ | የእጼ ሴሚች |
| ኢጋል | የብልያን እልቃ | ኢጋዋዋ | የግራ ክፍል ኳታ |
| ሰጋንዉ | የሰዲቃ እልቃ | ኤዞዋዋ | የቀኝ ክፍል ኳታ |
| እግሥርዊ | የጼሀ እለቃ | አዶሥል | የሴት ዘበኛ |
| እግስል | የሙቀ እለቃ | ዳሥል | የቀን ዘበኛ |
| እግእን | ምክትል መቶ እለቃ | አሴግ | የበጋሬዎች አለቃ |
| እግሜ | እስር እለቃ | ጩር | የከሪት እለቃ መሪ |
| ጀሰ | የሰዓም ሠራዊት | ዘቢጩር | የጀሆን ምክትል መሪ |
| አቾስ | የሆር ሠራዊት | አርስባው | ፈላሰፋው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አበበጉ | የንጉሥ ዘውድ ጸሐፊ | አሰግድ | የምስበር ቤተ ቤት ሹም |
| አበቱ | የአፄ ምኒስ | ኢማርሻ | የአፄ መልእክተኞች |
| አቶ | የኛ ግብ ቤቶ | ጌም | የአፄ ጋሻ ጃግሬ |
| ዋንጋሪር | ከአፄው ፍቃድ | ቄስ አፈ | በሸሩ ብዙ ሰዓት የአፄው ነገር አቀባይ |
| ጃል ጀነር | ከአፄው ፊት የደረሰ | ግን ደረሳ<br>ገገገ ጀን | የንጉሥ ነጋሪት ባለሟል (ስጦች)<br>የአፄው አልባሌ |

## ምዕራፍ አምስት

የኢትዮጵያ ዘጎች የሚተኙባቸው ትርጓሜና መንደሮች የወንዞቻቸውና
የተመለከቻቸው ስም ዝርዝር በአፄ ስንደቅ አሉማ የሚመሩት የነበሩት ስም ዝርዝር

| ንጉሥ ሻንጀር | ሃገሩ | ወንዙ | ጉማው |
|---|---|---|---|
| የዳም ልጅ ኮንጎ | አውሳተ | የቢ የሚገባት ወቅያኖስ | ያበላት ፡ ጉንት ፡ ጂሌ |
| የኮንጎ ልጅ ወንዳ | ኬንያ ሃድያ ሰግል | ነገሌ | ቦረና ወላም ቢረቶማ |
| የበኮንስ ልጅ ሰጂካ | ሌዘ ፡ ሃድያ 31 | ገናሌ ገናሌ | ቢረቶማ አባል ጉጋኛ |
| የዋሊ ሃሞሞት | ሌሰ ጊያን | ሾሌታ | አሸንቲ—ጊሰ |
| የሙ ልጅ ገዳን | ኬራሮ ኬራሮ | ዋዝ | አበስ ሉማሊያ መራዊያን |
| የዳም ጋሙል | አዳር የዳሙ ከተማ | ውዓቦ | በወር መዓቦ ደራሲ<br>ኢሰማክዘ አሰማተኛ |
| የመጋዝ ልጅ ጂባብ | ወረማያ | ጂባ | ማያ ወረማ ቀቤና |
| የአሚን ልጅ አሌሰታት | የጅገ ወገራያ | ቀገበቢ ሰማያዊ ማገን | በጂያ ሳሰታ ዩያ የዳረው<br>አገው ሃርር ማሾርዚያ<br>የዳረው ቅማራይ |

የሰሰሁሉ ልጅ ኢርትውስ

ለገሩና ኳዶር
የማማ ልጅ ቆሰሌ
የሻዋ ልጅ ለተ
የገበያ ትርጆኖን
የፈንታሉ ልጅ ጭጫሶ

ቀጸፊበ መጋል
የሰበሉ ልጅ ሂርቶት

የሚሊሎ ለት ልጅ ብሉና

የሳባ ልጅ

አዶሊ

አሙሃጉጀር

ጆጎጀር
የሞራ ልጅ ጆሌ

የአለምገንጀው ጋሯ

ማራ አማርና
ማቀቢያ
ኑባ ኑብያ
ሰት
ጆንጎላ መርጀ
ሐብና ሐብያ
ጀዋር ያኔ አሬር
አቅልልያ
ዋራ መጎደያ
ሲኒ ኄራራ
አሲደጎያ
ሱባሁሉ ፀያ

ቀጀ ጊሚያ
ቀራና
ቁር አዶሲስ
ቁጥሬዎ
ጀን ሰሙቲ
ጀሲ ሰሲ
ጅናጀጀር ናጀጀር
ፋደሰ ሜዳጀ

ሳዋ
ሳዋ
ዋረጂ ዋራዎገያ
የገሩ
ኬና ኬንያ

ጎማ
ካጀሌ
የማሮን መጎናዊ
ጎማ
እሊ
ኪቂ ባወር
ከሉዋጂ አበጆት

ማጂ
አርጎሩ ባወር

መራብ
ነሙ አባጆ
ጂጆባ
መጎር
በንበቢኪ
—ካሰሰዋ— መሮ
ያጆዋር
ዋሊ ጆባ

ተጀላ
ተጀላ
ያባቄ ቢሪያ በያራ
ወጋዞ
ጆርጌ

ጭም ባጀያ አማራ ምግሬ
ነፀሴ ኢሉር
እባ ለንጉሉ ዋግ ሽሬስ
ፈራማ ሂማን ቢገናም
ሽሉባ የውላ ቢሮና ደንገል
ናባቱ ጊማያ በዋርት
ሃሽን በርቱም ሲሳም

ማያ ሆርወፋበ ቦረን ኢቱጀሉ
ቅበሬር ኑማጂ ጀባሉ እባ ሁርቃ

ሃርጊት ብጾው አበገዱ
በቀባ ምን አማርና ኬናማ ብሉን
ጀማሪት ራጆጃን
ናጆበ ወገኔ በዐ ጀኑብ
አዶሉት ብሉማ ትንጋጀናር
ትምባ ብኛንግባ ጋሊ
ማቡሩ ያበን በርት አዋክ
ትውና ውጀብ ወጆዋ ደጋኒ
በርት
ቡሲ ሱማ አደል አላ ሻሆ
ሽርቃባ አበቲ ባላምራ
ሂወላጂ ቀጄራት ባላምራ
ሂሉላጂ ቀጄራት ሲዎ
ሽሉክ ሙራ ፍራ
ጉማው
ማሲያ ኪኩያ ሲሲ

| | |
|---|---|
| | ጅላ ሱዳ |
| የጉንደር አምር | ኀበማን |
| የ5| ንጉሥ አበት ሰም | ሞጣ |
| የጅማ ልጅ ጂማ | ዘሳ ሲሙ እናሪያ |
| ዝንጀር | ፊዶርያ |
| | ጋንዝያ |
| ኒለሃሬ | ሉማ |
| | ቀትያ |
| | ናዋታ |
| | እሌ ሲያክ |
| | ሃርላ |
| | ሆቦበ |
| የሰዋ/እድራዋቅ | ሆር ናዓራን |
| | ጆንጉልያ |
| | ማድጋስከያ |
| የቤራ ክልጀ ከውሳዘዮስ | ሃሌን |
| ጀጁና | ጊንቤ |
| | ሶንበን ሶንበንያ |
| | እዶሞ |
| የሰዋ ልጅ ጌዣም | ዶጀት |

| | |
|---|---|
| ለማያዊ ማዕን | |
| አዋቤሬ | ኩጂ ኩማዊ ሱሳ ሶብ በቴ |
| የሌዋጀ ሞንቃ | መደለይ ማጀ ማያ እሰቴሊት |
| የማዋን ሃይቅ ጣና | ጋፉት ወግኒ ጀንጋጀ |
| አዋሳ ዴሬጣ | ጣበሶ ሶንጋ ጃንጋዘ ጉን |
| ጉጀብ | እሊግ ፊላበሉ ዋቻ |
| ቀውት መገር | ባጀ ነምቦ ዋሎውት ጃከ |
| ኩሚይ | ፋበጀ አሉ ጀንጉላ ቨኒ |
| ዞንጉ | ይማግ ፊሉ |
| ማደንያ ሰበርት | አንኮሌ |
| ሙካር | ፋሉ ብጊል ፊላበሉ መሊጅት |
| በሙቅያናስ ድንበር | ቂድነሰያ ኬሎ ናፋጀ |
| ጊጀብ | ጀሌ ጋዋ |
| መሬብ | ባሪያ ሀሳን መንጉብዋን |
| ሰኢጋሌ | ይግሌሎ ጀንጉልያ ዋሬት |
| ዶሌት ታሳቂ ባሀር | ሉፆ ጀማ ሀሉ |
| ቢጓ ብሴን አውርጌ | ኩናት |
| ጣዋን | ጋንጀር ፊማሮ |
| ጎንባዚ | ማጊንቢር ቤኢራያ ቢጉባ |
| እዋዬ | ኡጋሌት ምቄ ኡሰዋኢሌ |
| ማዋን የከበበው ሱሳ | ማጂ (በዛሌ በየይ) መንዲ |
| | መደለይ |

ሰንደቅ አላማ እጹ ሰርአተ ንግሥን በአክበረ በአንደኛው ቆብሉ በምዕዳና በሲን መካከል ያየው የመልከጸዲቅና የኢትኤል አምላክ እንደየና ተገለፀለትና እንዲህ አለው በራእይ

ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለዘለአለም የሚኖር ከላይ እስከ ታች የሚመለከት ከውጭ እስከ ውስጥ የሚያይ ሀሊናን የሚመረ ምርና የሚያውቀው ሁሉን የፈጠረ ፈጣሪ የፈጣሪ ቃል በመንፈስ እንደምትሰማው በሥጋህም እንደምታየው እኔ ፈጣሪህ ሰሪህ ነኝ ለከንቱ አልፈጠርኩህም አንተም እንደ አንዳችን ስትቆጥር ከእኛ አንዱ እንዳንተ ይቆጠራል ሥልጣን ሁሉ ለእሱ ይሰበሰባል ምላስ ይገዛለታል ጉልበት ይንበረከክለታል የሚያውቁት በሥጋ ሲንቁት የሚያውቁት በመንፈስ ያከብሩታል በሰው አምነው ይገዛሉ መንግሥቱን ይወርሱ ዘንድ ይህም ሲሆን ግድ አለው አቤቱ አምላኬ ሆይ ይህ የሚሆንበትን ጊዜውን ወሩን እንዳውቀው ፈቃድህ ይሁን ልኝ አምላክም አለው እንደአንተ ሰው ሆኖ የሚቆጠር ከአንድ ቀን ተኩል በኋላ ነው ከዚያች ቀን በኋላ ሁለት ቀኖች ያሉት የመስ ናኸያ ቀኖች ይባላሉ ። ከመስናኸያ ቀኖች ቀጥለው የሰው ልጆች ዘይወታቸውን የሚያገኙበት እጮት እውቀትን የሚረዱበት ቀን ማስተዋልን የሚያደርጉበት ጊዜ አራት ቀኖች ናቸው ለነዚያ ቀኖች የተዘጋጀ ሁሉ ምርጥ ጭማቂ ዘሮች ይባላሉ ነገር ግን በእውቀታ ቸው ይበናሉ ይሰባሰባሉም ከእነዚህ ሰባት ቀን በኋላ መልካም ሰራ ወደመልካም ከፋ ሰራ ወደ ከፋ ቀን ወደሚያ-ቅጠርበት የዘላለም ኑሮ ይተላለፋሉ አለው ። ፈጣሪዬ አምላኬ ሆይ ወፍ ጉጆዋን እንደ ምትሠራ ሠርተኸኛልና ሌሎችንም እንደሸክላ ሰሪ ሰርተሃቸዋልና ሁላችን እንዳምህረትና ብዛት እያፍርስን በከንቱ መንግሥትህን እንወርስ ዘንድ ለዘላለም በደስታ እንኖርም ዘንድ ከመልካም ሥራ እያርቀን በከፋ እንዳጠፋለንና አንተው ለመልካም ምራን እንጂ አምላክም አለው ቃሉን ሰምቶ የመጣና ቢቃሉ የሚሄድ ቃሉ ይመራዋል ከጥፋትም ያድነዋል ይጠብቀዋል ። እያለ በተራራዎች መካከል ሲያልፍ እየው ከዚያ ይህን ቃል በእባቶች መፅሃፍ ውስጥ ፅፎ አስቀመጠው ይህን ራእይ እንዳየ እኔ ልዩ ልዩ ልብስ በለበሰ ሠራዊት ታጅቦ ልዩ ሠረገላ ተቀምጦ በፊት አንድ መቶ ሺህ ፈጣን ፈረሰኛ ሠራዊት በኋላ ሰላሳ መቶ ሺህ ፈረሰኛ ሠራዊት አምሳ ሺህ ፈጣን የሆኑ ሰጋር ግመል የሚጋልቡ በነዚህ ሁሉ በድምር አምስት ሚሊዮን ሠራዊት ጋር ከኢያሳ ኒል ተነስቶ ግዮን ወደሚፈልቅበት ምድር ደረሰ ያም ምድር ደሸት ነው ። በዚያም ምድር የነገሰው ንጉሥ ጉግም ይባላል ጉግም ማለት እምስተኛው የሰላም ንጉሥ ማለት ነው የጋፋትና የወንጌ

ነገድ የሚኖሩበት ሃገር የማር ወለላና ወተት የሚፈስበት ምድር ነው በፊልዶ ያየውን አራት ተራራዎች በጋሃድ አያቸው በእግሩም እየዞረ ጐብኛቸው እነዚህም አራት ተራራዎች ያሉበት ቦታ በረዶ እንደ ድንጋይ የተከመረባቸው ውሃው ከትዘታቸው የተነሳ ወደ በረዶ የሚቀየርባቸው ናቸው ። ሠራዊቱ ከባርዱ የተነሳ መቆየት ስላልቻለ ወደሰተምዕራብ ወደሚገኘው ወይና ደጋ ስፍራ አደረገ ነገር ግን ለዳንጉላ ነገዶች ደጋውን መሬት እርስት ይሆናቸው ብሎ ስማቸው እስከዛሬ ድረስ ዳንጉላ ተብለው ይጠራሉ የዳንጉላ ነገድ የጉንጉሙ ነገሥት ሥርዓት በፈጸመበት በግዮን ዳርቻና በነዚህ አራት ተራራዎች እንዲኖሩ ማድረጉ በአራት ተራራዎች ምሳሌ ልዩ ልዩ የሆነ ዘመድ ለሞግሙ ንጉሥ ዳሞ ልጆች ለሃድያው ንጉሥ ኮንሺ ለዶሼት ንጉሥ ጉዋም ለሊባር ንጉሥ ጋውል ለዳንጉላ ንጉሥ ዳጉ በመደባይ ካሃናት እጅ በራሳቸው መድፍቶና ከሌሎች ነገሥታት ለይቶ ማክበሩ ትንቢቱ በተፈጸመ ጊዜ ከእባሩውያን /እስራኤል/ ነገድ ለሚወለደው ንጉሥ ወደ ተወለደበት እንዲሰግዱለት እጅ መንሻ እንዲያቀርቡለት ወርቅና እጣን ከርቤ ሰባን ከምድራቱ ከሚገኘው ክቡር ነገር ሁሉ እንዲወስዱለት ነው ይህም በባዜን ዘመነ መንግሥት ተፈጽሟል ።

ይህን ልዩ ክብር ለአራት ነገሥታት በአደረገበት ቦታ በስሙ እንደጠርሙስ የሚመስለውን ኢያስጰድ ድንጋይ ተከለ ነገሥታቱም የታልህ ሪድኤት ይድረሰን ሲሉ በኢያስጰድ ድንጋይ ዙሪያ በስማቸው ሌሎች ድንጋዮች አቆሙ እነዚህ ድንጋዮች እስከዛሬ ድረስ አሉ ቁመታቸው ከሰው ቁመት በላይ እንደሠራገሙ ሁነው ይታያሉ ነገሥታቱም ምድሩን በአባታቸው ስም ዳሞ አሉት ንጉሥ ኮንሺም የሃዲያን ምድር ዳሞ አለው ኮንሺ የታላቁ ንጉሥ አባላ ዳኔ አባት ነው እንደዚህም ሆነ አጼ ሰገደት አልማ በዳሞ እንዳለ ቢገልፅ ከሰማየ ሰማያት እንደ ተራራ የሆነ ደመና ከባድ ጉም ወረደ በሙን ሰው አያየውም ከጉሙ ብዛት የተነሳ እንደውሃ ይገፋል ከዚህ መሃል በሱባ ቋንቋ እንዲህ የሚል የነጉድጓድ ድምፅ ተሰማ በድምፁ ውስጥ ለአጼውና ለንጉሥታቱ ለሠራዊቱም የሚረዳ ቃል ነበር ቃሉም ይህ ነው ፡

ይህ የምትሰሙት ድምፅ ፍጥረቱን የጀመረ የፍጥረቱን መሮ ሠሪያ ያበጀ ምድርን በውሃ ላይ ያፀና አለምን እንድትኖር የሠራ ካለእርሱ ሌላ ፈጣሪና አድራጊ የሌለበት የዲቅ አምላካችሁ ነው እርሱም እውነተኛ ቅዱስ አምላክ እንደሆነ እናንተም በእርሱ ታድ

ሳችሁ በህይወት እንድትኖሩ እውነተኞች ቅዱሳን ሁሳችሁ ሁኑ እርሱ የዘላለም ህይወት ነውና እናንተም ታድሳችሁ ለዘላለም በህይወት እንድትኖሩ ከዚህ አትውጡ ከትእዛዙም አትተላለፉ ይህን የሚጠብቁ ትእዛዙን የሚፈፅሙ ምድርን ይወርሷታል ያሉፈጸሙ ግን በራቸው ይዘጋል ዓለመኛ ህይወትን አያዩም እናንተ የህይወት ልጆች እውነትን ያዙ ፅድቅንም ታጠቁ እያለ የንጉድጓድ ድምፅ ከነርሱ እራቀ በዚህ ዓም በሚቢባለው ሃገር ሰሁሳት ወር ከቆየ በኋላ ነገሥታቱን ወደ የሃገራቸው በክብር አሰናብቶ ሸንቶ ንጉሥ ዳም በሚገባት በማዮን ሃይቅ ከተማ በምግ እድርጐ ታላቁ ሞን ሞይብ ከተማ ጉብኝቶ ሞናሁ መዲና ከተማ ሳባ በወጣ በአመቱ ተመልሶ ገባ በዚሁ ዓመት የልጁን ልጅ ተሞሲያ ሁፋን ወራሽንትና የኢዜብን ንጉሥንት የማዕረግ ምልክትንት በራሱ ላይ ደፋለት እጼ ሰንደቅ አላማ ለተሞስያ የኢዜብን /አዘቦ/ ምድር ግዛት ሲሰጠው ዕስት መቶ ሰማንያ አመት የእድሜ ሰው ነበር ፡፡

እጼ ሰንደቅ አላማ ለአምላኩ በየጊዜው የሚያቀርበው የምሥጋና ፀሎት ይህ ነው //

- አልፋኤል አኤል የመጀመሪያው እውነተኛው መንፈስ በአምላክነትህ ታምኜ ማንኛውንም የሰበአዊን ሥራ ስጀምር ፈጣሪ ሃይልህ ረዳቴ ነውና ለዘላለም ከእኔ ጋር ይኖራል ፡፡

- እየንኤል አኤል ሥርዓትን በሥርዓት ጊዜን በጊዜ የምትቀይርና አዲስን ድንቅ የሆነን የምትሰጥ እውነተኛው መንፈስ በአንተ ታድሼና አምሬ በአለም ፊት እታያለሁ ፀጋንና ክብርን በሃይልህ ብሳለሁ እውነትህንም እታጠቃለሁ ፡፡

- እማንኤል አኤል እውነተኛው መሪ መንፈስ በአንተ ስላለሁና ስለቆምኩ በሰላምና በክብር ለህዝብህ ፀጋና እረድኤት እሆናለሁ በሃይልህም ከፍ ከፍ እላለሁ በስልጣንህም የህዝብን ተቃራኒ ሁሉ ድል እደርጋለሁ አንተ በእኔ እድረህ ፈቃዱን ፈጽመሃልና እመሰግናለሁ ፡፡

- ኤል ኤኤል እድራሽና ፈጻሚ የሆንክ ቃላቁ መንፈስ በአንተ ስለአመለኩና ስለፀለይኩ ፍቅሬንና መስተዋድዱን ነፍስ በቀሰጠው ሥጋ ሰባኝ ልብ ሁሉ ጸፍላቸው በሀሊናቸው እመላልሳለሁና ነፍሴም በአንተ ክበረ ፡፡

- ኢያቡስድኤል ኢኤል ለዘላለም ንዋሪና መሰረት የሆንከው ረዳቴ ፈጣኑ መንፈስ በአንተ ስለከበርኩና ስለታወኩ መንፈሴን በመንፈስህ ምሬው በሃይልህም አጠንክረው ነፍሴ ስለአንተ ሥራ ደስ ተሰኘ ።

- ኡድኤል ኡእል በሰማያትና በምድር በአየርና በባህር በውስጥና በውጭ የምትገኝ ቅርብ የሆንክ እውነተኛ መንፈስ በአንተ ስለምኖር ሥጋዬ የፈለገውን የተመኘውን መባውን ስብሰብለት እስካብርለት ነፍሴንም በጸጋህ ደስ አሰኘው ለዘለአለሙ ከአንተ ጋር በክብር ይኖራልና ።

ኤልአኛ አየኤል የሚታዩና የማይታዩትን ረቂቅ ተንቀሳቃሽ ሁሉ የፈጠርከና ያስገኘህ ለዘላለም የምትመሰገን የአምላኬ መንፈስ ወና ኑፎውን ሰው ማደሪያውን እንደሚሰራ እኔንም አንተ ሰርተኸ ኛልና በሃይልህ አድሰኝ በስልጣንህም አንፀብርቀኝ ያአንተ ማደሪያህና ማረፊያህ ነኝና አታሳፍረኝ እውነተኛው መንፈስ ያለበት ሁሉ ለዘለአለም ወንቶ ይኖራል ህያው ሆኖ በአንተ ፊት ይከብራል ።

ኤውታኤል ኡዶኤል ክብርና ምስጉን የሆንከኝ የታላቆች ታላቅ እውነተኛው መንፈስ ፍቅርና ሰላምን እድሜን ጤናን አድለኝ እንዚህ ለሥጋዬ ወጋ ለነፍሴ ክብር ሰጠውና ስለዚህ መንፈስም በአንተ እየተ መራ በእውነት ጎዳና ይጓዛል ።

ኡዋወኤል ኢዋኤል ግሩም መንፈስ በአስደናቂ ሃይልህ በረቀቀ ሥልጣንህ ለህይወቴ መከታ ለነፍሴ አለኝታ ሁንኝ ከሚቃወሙኝ አድ ነህ ተቃዋሚዬንና ከምድር ፊት አጥፋልኝ በፈጣን ሃይልህ ደምስስልኝ መንፈሴ በአንተ ተጠብቆ ለዘለአለም ይኖራል ስለአንተ በአንተ ነፍሴ ደስተሰኘ ።

አሚጋኤል አኤል መፈጸሚያና መጨረሻ የሆንከን ቅዱስ መንፈስ ለዘለአለም የምትኖር ተመጻዳሪ የሌለህ ምስጉን ክብር ነህና ፈቃድህ በአንተ እንደሆን በእኔ በማደሪያህ ይሁን የመንፈሴንም የሥጋዬን የነፍሴንም ደስታ ሰጠኝ በአንተ እኖራለሁ ለዘለዓለም በሃይልህ ድል አደርጋለሁ በስልጣንህም ከፍ ከፍ እላለሁ አንተ የመንፈሴ መሪ የሥጋዬ ክብር የነፍሴ ህይወት ነህና ለዘለዓለም አመሰግንሃለሁ።

ከዚህ በላይ የአቀረብኳቸው ከመጽሃፈሱባኤና ከግእዝ የተቀዳ ቀለሙን ቋንቋ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለታሪክ መዳጀትና ለተመራማ

ሪዎች አቅርበላችኋለሁ ። ከዚህ ቀጥሎ በሱባ ፊደሌ ቁጥር ልክ የሱ ብያ ከዘፍጥና ትንሳኤ የሚያሳዩት ዐሎት እቀጥላለሁ ።

ዋኤል ከአለም በፊት የነበርክ

ውኤል አለምን የፈጠርክ

ወኤል በአለም ተዘዞን የገለጽክ

ዊኤል በውን በአምሳልህ የተፈጸከውና የህይወት ነፍስን የሰጠ ኸው

ዊኤል ለሕይወት መኖሪያ የሆንክ የሃይል መንፈስ የመንፈስ ድምጽና ቃል ሆይ እኛ አገልጋዮችህ ተመልከት የልፋችን ቃልና የልባችን አሳብ በፊትህ ምግረ ይሁን ለዘለአለምዐለታችን እድምጥ የልመናችን ድምጽ ሰማ በአንተ በአምላካችን አመንተኛ መንፈስ ታምነናልና እናፍርም በእምነታችን ወንተን በአንድነት ለአንተ እን ግዛለን በክብር ለዘለአለሙ ከፍ ከፍ እንላለንና ምሥጋናን በአንደ በታችን እንጀምራለን ። በቅዱስ መንፈስ የሚመሳለስ ሁሉ ሀሊና የን ቁና የተባረከ መንፈስ ነው ።

ውኤል መንፈስ በመንፈስ የገለጽከና በአለም የሞላኸው

ውዋኤል ነፍስን በሀይወት የመሰረትከና ለዘለአለም የምትኖር

ውይኤል ሀግሆን በሥጋችን ላይ የደንገግህ የታል ኪዳንህን ስር እተ ያፀናህ

ውዋኤል መዐንህ የማይመረመርና የማይለካ

ዊኤል የመንፈስ አገልጋዮችን ያዘጋዘና ለአለም የላክ የሃይል መንፈስ የመንፈስ ድምጽና ቃል ሆይ አንተ የምናምንህ ተከታችን ህይወታችን ነህና በምንለምንህ ጊዜ ያልቀረብንልህን ልመናና ዐሎት ተቀበል ስማን ለልመናችን መልስ ስጠን በእውነት ያለጥርጥር እገ ቱን ቅዱስ መንፈስ ያመነ አይወድቅም ወንቶ ይኖራል ።

ይህ ኤል እየተባለ የሚጠራ አምላክ የሚያስደይ ወሎት በሱቢባ ፊደል ልክ የተፃፈውን ለማቅረብ ብዙ ገፅ ስለሚወስድ ወደታሪኩ ተመልሼ አለሁና ወንድሞቼና እህቶቼ ቅር እንዳይላችሁ እያሳሰብኩ ወደሌላው ታሪክ ከተመላለሰ በፊት የሱባን ፊደል እያሳያችኋለሁ ።

የእናባቢው ፊደል ጠልሰም

እድ

አሚጋ o u e ኢያስድቋ

ኤል d i l አማን

ኡዋን ω w m ኤጡታ

አየን አሚን ኤል

ኤሉኝ

ኡ -ኤልፋ

d

የድምፁ ጠልሰም

o i w ኢያስቋድ ኤድ ኤሎሃ

u m e

ω m d e u w

ኤጡታ ኡዋል አሚጋ

m ω o

የተነባቢዎች ፊደል ተራኢ ቀማመጥ

በ

ዋ ዋ ያያ ኛና ቀገር ባ/ ኦግ

ራሓ ሄዳ ጫታ ማፃ ተለዛዛ ጫፆ

ፐዣ ፀ እንጣ ን- ጋጋ ቃካ ፃ

የሱባ ቁጥር

አጸጸቶ

ትርጉም

እሃዙ

ድምፁ ማ ን ጌ ጊ ት ገሾ ጉይ ማቼ ን እግ እን እኔ

እግ እግ እግ ኤግ ኢግ ኤግ ኡየግ ኡይግ እግ እግ

እስር መቶ ሽህ ሚሊዮን ብልዮን ትርልዮን

## ምዕራፍ ስድስት

### የማክዳና የልጅዋ የምኒሊክ ዘመነ መንግሥት

/ማክዳ እናት ክላ ኢት ስመታ ኢትዮ የተሰጠች ማለት ነው ።

ሳባ በምትባል ከተማ አጼ ሰንደቅ አልማ የሚባል ታላቅ ንጊ ሥና ንጉሥ ነበር ይሄም በንጉሥነት አስር አመት በንጉሡ ነገሥትነት የአውሬ ንጉሥ ተብሎ መቶ አርባ አመት በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ገዛ እንደገና የህዝብና የአራዊት ንጉሡ ነገሥት ተብሎ ስሙን አጋ ብዕ አሊ ወይም አጼ አሰኝቶ ነገሠ ሲነግሥ የአንድ መቶ አምሳ ሰምንት አመት እድሜ ሰው ነበር ይሄም ንጉሥ የአጼ የልጁ ልጅ የአንጋቦ ልጅ እንጂ የኤልካና ታላቁ ንጉሥ አፄ አይደለም ታላቁ ንጉሥ አጼ ለልጆች በየአስር አመቱ በተራ እንዲነግሱ ከአዘዘና ሆነ ከደነገገላቸው በኋላ ተሰውሯል ። የሚሉ አሉ ነገር ግን ነገ ሥታቱና ህዝቡ እንዳልተሰወረና እንዳልሞተ በሉ ሚያምኑ እንደነና የሳባን ንጉሥነትና በመቶ ሁለት ሃገሮችና በአርባ ዘጠኝ ነገሥታት ላይ የሰውና የአውሬ ንጉሥ ሆነ ብለው በእጁና በኢትኤል ሁፋን ላይ አስተምረውም ካህናቶቹ ስለአነገሱት በዚሁ ታሪክ ሁሉም ተስ ማምቶ ሁለት መቶ አምሳ ሰባት አመት ነግሦ በድምሩ የዘንዶው ምስል በንጉሡ ነገሥት ላይ የገዛው ዘመን አራት መቶ ዘጠን ነው ይሆም የዘንዶ ግዛት ይባላል በመቶ ሁለት ሃገሮች ላይ ለሚነግሱ ትና ለሚሾሙት የበላያቸውና ባርኮ እንጋኛቸው ሲሆን ለሳባ ከተማ በሥሩ ሌላ ንጉሥ አለ እነዚህም በተራ የነገሡት ቸአምር ልጅ ኩር ፋን ሳቢሳባ ተብሎ አምሳ አምስት የኩርፋን ልጅ ሰርፌ ግን ዛዐ ተብሎ ሳባ ከተማዋን አዜብያን ወይም አዘቦ የተባለውን ሰማንያ ሁለት የሰርፌ ልጅ አኪላሀን ቆዖ የሳባና የቆዖ ንጉሥ ተብሎ ሰማንያ አመት ገዛ ከዚያም የሰርፌ ልጆች ቋርስቅላ እንዘዐ አርባ አመት አቅጃዐ በባ አምሳ አመት ኢጋቦና ተዋስያሳቢ የመቶ አምሳ አንድ ሰው 16 ዓመት ነግሶ ሞተ ።

እንደዚህም ሆኖ የተዋበች ባቢ የመጨረሻ ሴት ልጁ አዝሜና የምትባል ቆንጆ ልጅ ነበረች እሱዋም አጋቦስ በተባለው በእጁ ፊት ቁጣ ዘፋኝና አሜዎች ነበረችና ለእቅመ ሄዋን እንደደረሰችም በእጁው ግቢ ውስጥ ከሚኖሩት ከጃንደረባዎች ጋር ስትጫወት ከጃንደረባዎች አንዱ በፍቅሯዋ ተይዞ አብሯዋት እያደረ ምንም ከብርናዋን ባያፈድ በእፊ ማህፀኑዋ ላይ ዘርን ስለዘራ አዝሜና እርጉዝ ሴት ልጅ ወለደች ስሙዋንም ኢትዮ አለቻት ኢትዮጵያል ማለት እምላክ ሰጠኝ ማለት ነው ንጉሡ ንጉሥነቱ እጁ ግን ልጅ መውለዷዋን ስለሰማ ያስረገዛትና አዝሜናን ከልጅዋ ጋር እንዲገደሉ ስለ አዘዘ ኢትዮ ቆንጆ መልክ መልካም ስለነበረች የታዘዙት ገዳዮች በእሱዋ ፊንታ ሌላ ልጅ ገድለው ኢቲዮን ወስደው በተዋሰያ ቤት በድብቅ እንድታድግ አደረጉ ኢትዮም የእናት አባትዋን ገዳይ እጁን ለመግደል ብዙ ዘመን ከወሰደባት በኋላ እንደአናትዋ ዘፋኝ ነበረችና በእጁ ልደት ቀን ከደናግል ሴቶች ልጆች ጋር በንጉሡ ንጉሥነፊት ልትዘፍን ገባች እጁውም በፍቅሯዋ ተይዞ ወደልዩ ቦታ እንዲወስዷዋትና በዚያ እሱን በዘፈን እንድታብደስተው አዘዘ እሱዋም ስትዘፍን ሳለ አንድ ቀን ከተኛበት ገድላ ያለበትን ቤተንጉሥ እሳረገ አቃጠለችው ። ከዚያም እሱዋ እንደገደለችውና የጀርውን ትትም ሱቲ የከንዱን አንባር የራሱን የዘንዶ ቅርፅ ያለበትን ዘውድ ወስዳ የግድያውን ስለባ ምልክት አሳየች ነገሥች ። በዚህን ጊዜ ሱባውያንና አዜባውያን ሲገዙዋት ሱካውያን ኩሳውያን ኪታውያን የሚባሉት አልተገዙላትም ነበርና በገደለችው በእጁ ሰንደቅአለማ አጋብሶ በተባለው መታበር ላይ ሆኖ ሌትና ቀን እያለቀሰች ትወለይ ጀመር በስባተኛው ቀን ትልቅ ዘንዶ መጥቶ ሲገድሉዋት የሚፈልጉዋትን ኩሳውያንና ሱካውያን በላ በየቤታቸውም የሚገኙትን እንስሳና ህፃናት አበቦች እየነደፉ ገደሉአቸው በዚህ አይነት ሆዘቡ አሚያደርገው ስለአማ ለኢትዮ እንገዛም ብለዋት የነበሩት ሁሉ በእሱዋ እድሜ ዘመን ልጅ ሳትወልድ በድንግልና ሆና ልትገዛቸው ቃል ገቡላት እሱዋም ልትወልድ ድንግልናዋን ሳትቀየር ቃል ገባችና በግዮን ዳርቻ በርዓት ንግሥዋን ለመፈጸም ወረደች በዚህን ጊዜ በእጁ ስር ሆነው ሲገዙና ሲኖሩ የነበሩ አዛውንቶች አርባ ዘጠኝ ንጉሥታትና ከመቶ ሁለት ሃገሮች የሚኖሩ ልዩ ልዩ ጉጣዎች ሥርዓት ንግሥናዋን ለማክበር መጡ በዚህን ጊዜ እንደአባትዋ እንደ እጁ ሰንደቅ አለማ በግዮን ወንዝ ዳርቻ የንጉሶች ንግሥትና የአባትዋን የአጋቦን ግዛት አዜቢያ የተባለውን ሃገር ንግሥት ሆና ነገሠች የንጎስችበትን ምድር ናፓታ አለችው ናፓታ ማለት እኔ እናታችሁ

አባት ሆነናቸው ማለት ነው በሰባ ቋንቋ ንግሥት ንግሥታት ዘኢ
ትዮጵያ ተብላ የነገሠችበት ዘመን ከተቆጠረ 4463 ዓመት ነበር ።
ኢትዮጵያም በግዮን ወንዝ ፍሰት ብላ በሰየመችው ሥፍራ አስራ ሁለት
የቤት ንጉሥታት አርባ አንድ ንጉሶች እንዲያሬጋግጡቸው ከእነዚሁ
የቤት ነገሥታት አርባ አንድ ንጉሶች እንዲያሬጋግጡ ከአደረገችል
ቻቸውና በራሳቸው ላይ የዘንዶ ቅርፅ ያለው ዘውድ ከአደረገችላ
ቸው በኋላ ሳባን ትታ በአደገችበት ሃገር አዜቢያ ሄዳ ተቀመጠች ።

ኢትያ በነገሠች በአስራአንደኛዋ አመት ወደሳባ ጉዞ አደረገ
ችና በግዛትዋ ውስጥ የሚገኙ ትን ነገሥታት የልጅ ልጅ ጉማ ነገ
ሥት ጥሪ አደረገች በዚህን ጊዜ ከባህር ማዶ የምትገኘው የሁለተ
ኛው ናግራን ልጅ የአድልአባር ንጉሥ ልጅ በሌኪሰል አረብ የም
ትባል ንግሥት የኤርትራን ባህር ተሻግራ ከባህሩ ሠራዊት ጋር
ማብሩዋንና ዝን በረከትዋን ይዛ መጣች አድልአባር አባቱዋን
እንደሌሉቹ ባልዋን ገድላ ስለመጣች ከንግሥተ ነገሥታት ኢትያ
ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ለሰለሞን ንጉሥ እቁባት እስከ
ምትሆን ድረስ ወደሃገሩዋ አልተመለሰችም የመደባይና የማጂ ያግሬ
የካሳዊ ከማውያን የበጂያ የሹሉት የማሲ ነገሥታትና አባወንት
ከኪቴ እስከማድጋ የሚገኙት ነገሮች ተሰበሰቡ በዚህን ጊዜ ህዝቡ
የሚበላው ስለአጣና የሃጋሬውን የሶብ ያንና የሕዜባውያን ግመልና
በግ ያለመፍቀድ እየአረደ ስለበላባቸው በሳባ አካባቢ የሚገኙት
ህዝቦች ተሰብስበው ለንግሥቲቱ የሆነውን መሬብ መቻገሩን በሃይል
መዝረፉን መቀማቱን አመለከቱ ንግሥቲቱ ኢቲያ ህዝቡን ለአስገ
ዛችለትና ጠላትዋን አባብና ዘንዶ ልክ ከአስራጀሳት ለገደለችው
ለአጼ ከመቃብሩ ሄዳ ትፀልይ ጀመር እንደካህናቱ መላክ እንደ
ህዝቡ ቀንድ ያለው ዘንዶ መጣቶ አጼ ከሞተበት ሥፍራ ላይ
የበቀለውን የአሳር ፍሬ አሳጭድችና አስወቅተች አስደቁሳ ጋግሮ
አብያቸው አሳት አሰቀም እንዳላት አድርጋ ለህዝቡ ታብላ ጀመር
ህዝቡ የተሰበሰበበት ስብሰባ እስኪያልቅ ድረስ የሌላ ሃብት አልነ
ኩም ያኔም የሳር ፍሬ ከባሙ ሌላ በመብርከቱ መባሬጡ ሌሎ
ጤፍ አሉት ስለዚህ እህል በማሌም የነገሠው ዳዊት ንጉሥ ስለሰማ
ለኢትዮጵያ ምግብን ሰጣቸው ሲል ለአብሬውያን ተናገረ ።

ንግሥተ ነገሥታት ኢትያ ነገሥታቱንና ካህናቱን አባቶቻችን
በአብሬውያን ለሚነግሠው ንጉሥ እጅ መንሻ የሚሆን ገፀ በረከት
ይዛቸው ሄዳችው በገዳሴት ወርቅና ከርቤ እጣንንም አቅርበሉት ።
በሳሉን አውን እንዲድና በማደን እናቅርብለት አለች በዚህን ጊዜ የማ
ጂና የመደባይ የጉባ ነገዶች ከደቡት ከእናሪ ከቆሌ የመጡ ሁሉ እን

ጺሀ ሲሉ መለሱለት አሁን በሰሌም የነገሠው ዳዊት ይባላል ፡፡ እሱም እንደ አባቶቻችን ለሚወለደው ንጉሥ በፊቱ ኢትዮጵያ ይሰግዱለታል ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል እህዛብ ሁሉ ይታዘዙለታል ሲል ትንቢትቱን ተናግረዋል አሉዋቸው ፡፡ የጋቶት የማጂ ንጉሶች እንዲህ ሲሉ መለሱለት ነቢዩ በለአም በእብራውያን ላይ ያየው ራእይ ይህ ነው ፡፡ አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል በእስራኤል ብትር ይነሳል ከያዕቆብ የሚወጣ ገዢ ይሆናል፡፡ ሲል የተናገረውን አባታችን ደሸት ፈላስፋው ደግሞ ይህን ኮከብ የሚመስል ሲወጣ አይታችሁ ወደወጣበት ሃገር ጨረሩን ወደሚያመለክታችሁ ሆድር ከምታገኙት የምድር አበል እጣን ከርቤ ወርቅ ልብስ ይዛችሁ ሂዱ ብሎ ከብረትና ከወርቅ የተሠራ ሰሌዳ ሰቶናል ስለዚህ የሚመራን ኮከብ እስከሚመጣ ድረስ እንሄዳለን አሉዋቸው ፡፡

በዚህን ጊዜ ዣንሸዋ የሚባል የሱባውያን መፅሃፍ ነበራቸውና የሳባ ህዝቦች ተሰብሰበው እንዲህ አሉዋቸው እስራኤሎች ከአሁን በፊት ንጉሥ አልነበራቸውም አሁን ግን እውነተኛ የአምላክ አገልጋይ ንጉሥ ስላላቸው ለእሱ ሄደን እንስገድለት እጅ መንሻ እናቅርብለት ኮከብ ይመራችኋል ያሉት ዣንሸዋ የተባለው መፅሃፍ እንጅ የሰማዩ ኮከብ አይደለም ሲሉ ተናገሩ ንግሥተ ነገሥታት ኢትዮጵያ በዚህ ንግግር ተስማምታ ልትሄድ ስትዘጋጅ ስለነሁ በዣንሸዋ መጽሃፍ በኋላ እውደ ፀሃይ ወይም እሙደንገሥት የተባለውን ቢመለከቱ አትሂጂ ጊዜው ገና ነው የሚል ቃል ስለአገኙ ዝንብለው በየዓመቱ ዘመን እየቆጠሩ ቆዩና በፋንታቸው ሱባ ከተማ የነገሠው ንጉሥ ታምሪ መጥቶ በኢየሩሳሌም ስላለው ንጉሥ ስለቤተመንግሥቱና ሥነሥርዓቱን ስለጥበቡና ስለክብሩ ነገራት ፡፡ በዚህን ጊዜ የሳባን አዛውንትና መሣፍንት በነገሥ በሰላሳ ሶስት በሰላሳ ሁለት አመትዋ እንዲሰ በሰበ ቀሪ እድርጋ ወደ ኢየሩሳሌም ስለጉዞው ብትጠይቃቸው የዣንሸዋን መፅሃፍ አንባቢዎች ሂጂ ይልሻል አሉዋት አዛውንቱ ሽማግሌዎችም በቃሉ ስለተስማሙላት ወደኢየሩሳሌም ለመሄድ ዝግጅት ታደርግ ጀመር በዚህን ጊዜ በመድኖ የምትባል በስሯ የኢኪላ ግዛት የነበረውን ቀዐና አዘበን የምትገዛው ንግሥት ግዛቷ ለላዋ ደግሞ ኤርትራን ባህር ተሻግራ ከእሱዋ ጋር የምትገኘው ከአረብ ነገድ የመጣች በልኪሳ ወይም በልካሳ ንግሥት አብረዋት ሲጓዙ ቀንሱ ፡፡ በዚህ ጊዜ በሱባው ንጉሥ ቢታምሪ እየተመሩ ለሰሎሞን የሚገባውን ግዞ በረከት ይዛ በብዙ ሠራዊትና ደንገጡር

ታጅባ አባቶችዋ ትንቢት የተናገሩለት እሱ መሆኑን እስመሆኑን
ለማረጋገጥ ከመስማት ይልቅ ማየትን መርጣ ወደኢየሩሳሌም ወረ
ደች ኢየሩሳሌም በደረሰች ጊዜ ንጉሡ ሰለሞን በክብር በደስታ ተቀ
በላት እርስዋም ከግዛቷዋ ውስጥ የሚገኘውን የከበረ ሉል ወርቅ
እንቁ ልዩ ገፀ ሰጠችው ሰለሞንም ስጦታዋን ከተቀበለ በኋላ የተለየ
ማረፊያ ቦታ ለእርስዋና ለሠራዊቱዋ ሰጣት ።

እንደዚሁም ሆነ ሰለሞን በእስራኤል ላይ በነገሠ በአስራ ስምንት
አመቱ ለኢትዮ ሰባ ንግሥተ ንግሥታት ለክብሩዋ ትልቅ ግብር አዘ
ጋጅቶ ጠራት ከዚያ በፊት የቤቱንና የቤተመንግሥቱን የቤተ መቅ
ደሱን አሠራር ሲያሳያት ስንብቱ በተዘጋጀለት ግብር ደግሞ የግብሩ
ንና የአዳራሹን አይነት የመጠጫዎቹንና የመኳንንቱን አገባብና አቀ
ማመጥ ለማሳየት ለሳባ ንግሥት በቀኝ በኩል በግራ በኩል ለራሱ
ዙፋን አዘጋጅቶ ማንኛውም ሥርዓት እንዲታያት አድርጐ እስቀመ
ጣት በዚህ በልዩ የወርቅ ዙፋን ላይ ተቀምጣ የባለሟሎችን አቀ
ማመጥ የሌሎችንም አለባበስ በየክፍሉ የሚያገለግሉትን የወይን
ጠጅ አሳላፊዎችን የሥራቸውን ትልቀትና የመኳንንቱን አቀማመጥ
እየተመለከተች ተደነቀች ንጉሡ ሰለሞን ግብሩ ሲያልቅ ሊያነጋግራት
ወደ ወደእልፍኙ ዙፋን ሄዶ ኢትዮጵያም እንደዚህ አለችው ስለነገር
ህና ስለጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ግን እውነት ነው እኔም
መጥቼ በአይኔ እስካላየሁ ድረስ የነገሩኝን አላመንኩም ነበር ። አሁ
ንም እኩሌታውን አልነገሩኝም ነበር ጥበብ ሀና ሥራህ ከነገሩኝ ይበ
ልጣል በፊትህ ሁልጊዜ የሚቆሙ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና
አገልጋዮችህ ምስጉኖች ናቸው አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን
ያስቀመጠህ አምላክህ የተባረከ ይሁን ፈጣሪ እስራኤልን ለዘለአለም
ወዶታልና ስለዚህ ፅድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጐ አስ
ነሳህ አለችውና ፊት ከሰጠችው በስሙ ከአስቀረቻቸው መቶ ሃያ
መክሊት ወርቅ ለእሱዋ የተዘጋጀውን ገፀ የከበረም ትልቅ እንቁ
ሰጠችው ከእስራኤል የምትወጣው ትንቢት የተነገረልህ አንተ ነህና
ስትለው እኔስ አይደለሁም በኋለኛው ዘመን የሚወለደው በመንፈስ
ቅዱስ እንጂ እኔስ አይደለሁም አላት ። እሱዋንም የአባቶችሽን ታሪክ
አከብረሽ በመምጣትሽ በጣም ነው ደስ ያለኝ እንዴት በድንግልና
ትኖሪያለሽ አላት ኢትዮጵያም ታሪኩዋን በድንግልና ቃል ኪዳን ገብታ
ለህዝቧ እንደነገሥታት ነገረችው ነገር ግን ለእሱ ያላት ፍቅር ንፍስ
አልቀራትም ነበርና ድንግልናዋን ሰጠችው እሱም በስምዋ ከስልሳ
ሚስቶቹ እንዷ እንድትሆን ቤተ መንግሥት አሠራላት ለዐበች

ወር አብረው ተቀመጡ እንደፀነሰችለት ነገረችው ኢትዮጵያም ተከትለው የሄዱት የቆቦ ንግሥት ግዛት በኢትዮጵያ አጠገብ ለሚኖሩት አረብና ለካሳዊ ነገድ ንግሥት የሆነች በልኪስ ለሰለሞን ከሰማይ እቀባተኛ ውስጥ ሆኑ በልኪሣ በሰለሞን ቤተ መንግሥት ስትቀር ግዛቷ ግን ከኢትዮጵያ ጋር አብራ ተመለሰች ሁሉቱም ለሰለሞን አርግዘው ነበርናግዛቸ በጉዞ ላይ ሳሉ ወለደች ስመንግሥቷ.ጋዜ አለችው /በመጀ ማለት ነው ኢትዮጵያም ሳባ ከተማዋ በገባች በወሩዋ ወለደች ወንድ ልጅ ስሙንም እብነልሃኪም አብነል መላክ አለችው አብነ መልመላክ የንጉሥ ልጅ እብነሃልሃኪም የብልህ ልጅ ማለት ነው። በአስራ ሰስት አመቱ ከብዙ መርቅና ሉል የአገሯን የሰለሞንን ማስታወሻ የወርቅ ቀለበት አሲዛ ከብዙ ታማኝ ወታለደሮቹዋ ጋር ወደኢየሩሳሌም ላከችው አባትየው ሰለሞንም እብነልመላክ ልጁን ባየው ጊዜ በጣም ደስተኛ በክብርም ተቀበሉ ግብር አደረገለት በዚህን ጊዜ የግዛቷ ልጅ ዘጋዊና የኢትዮጵን ልጅ እንደእብራውያንን ህግ አስገርዞ ለምስት አመት ሰርአተ መንግሥት ን የአሪትን ህግ አስተምር ወደ ሃገሩ በደስታ ላከው በዚህን ጊዜ በእብነልመለክና በሳባ የሚኖሩ ህዝቦች ሊያስተምሙት አልቻለም የይማኖቱንም ሆነ ግረዛውን ስለማይፈቅዱ እንደሚገሉት አውቆ ወደአባቱ ወደኢየሩሳሌም ተመለሰ ሄዶ ወዲያውኑ ንጉሥ ሰለሞን ልጁን እብነልመለክን በሳሁኑ ግዶት እጅ ቅባቱ መንግሥት አስቀብቶ በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ ንጉሠ ነገሥት እንዲሆን አስዘርኮ አስራ ሁለት ሺህ ምርጥ ተዋጊዎች የወርቅና የብር እንጠ/ዎችና አንድ ሺህ እናጠዎች ሃያ ሰባት ሺህ በሥፋርና በጋዛ ምድር የንበሩ ወምር ላከው ከብዙ ሁሬዊት ጋር መምጣቱ ስለተሰማ አዘባውያንና ሱካውያን ሊወጉት ተሰለፉ በዚህን ጊዜ የሁለቱ ጦር ግጥሚያ እንደጀመሩ ኢትዮ ሰምታ የራሱዋን የግል ጦር ይዛ በኋላ ደርሳ ትወጋቸው ጀመር በፊታቸው የእስራኤል የሰለሞን ጦር በኋላ የራሳቸው ጦሣ ስለወጋቸው አዘባውያን ሱካውያን ኩሳውያ በጀፊ የሚባሉ ነገዶች ሁሉ አስር ሺህ የሚሆኑ ሲማረኩ ከአስራ አምስት ሺህ በላይ ተገደሉ ንግስቲቱም ለልጇዋ ታላቅ ስልጣን ክብር አደረገችለት ያንንም ሥፍራ ማይ በላ አሉት ማይብላ ማየበላ ኢትዮ ለእርዳታ በደረሰችላቸው ጊዜ አግኢዚያን ልጇዋ ለምኒልክ እራያ ንግሥት ዘቦ ንግሥተ ቆቦ አሉት በዚህን ጊዜ የአለችበትን የጎር እራያ አሉት እራያ እያት እናት ማለት ነው እናቲቱም አብረውት በአንድ ላይ ስመጡት እስራኤላውያን ጥሩ ቦታ መርጠው እንዲቀመጡ አደረገች እነዚህ የጀራውያን የሚበዙበት የሲም ልጅ የዩቅጣን ልጆች ናቸው የዩቅጣን ልጆች

ኢልሞዳድ ማሌፍ ያገሬዎች ሳባ አፌር ኤውሳዎ ፀባብ ናቸው እነዚህ ሁሉ ለየቅማን ተመልደውሴት የዘራቸው ዘሮች በሰፋርና በማሌ መካከል ይኖሩ ነበር ። እንደአረቡ ክማሺ እንደሚለው ዮግሌ ወይም ሌሴ ኒሚ ባል ሃገር ተነስተው ስለመጡ የስፈሩበትን ቦታ ያማሴን አሉት ገባ ባል ሃገር ተነስተው ስለመጡ የስፈሩበትን መሬታቸው ስለነበር በማቸው እግሊ የሚባል የጋዛ ጉሳ አለታቸውና መሬታቸው ስለነበር በማቸው እግላ ዘያን እንዲባል አባንሌመለክ አደዘ ። እናቱንም ማኪና አሏት ማኪና ማለት እናት መሆናን ነቻ ማለት ነው ጉሱ ማከዳ በጥቅሉ ማለት እናት መሆናን ነቻ ማለት ነው ጉሱ እም ከዳ በዚህን ጊዜ ንግሥት ሲጠሉ ተበትኖ ሲጠሉ ጉሱ እም ከዳ በዚህን ጊዜ ንግሥት ሳባ ንግሥታት ኢትያ ልጆዋን አብንሌመለክን በጣዮን ወንዝ ዳርቻ ንግሥታት ኢትያ ልጆዋን አብንሌመለክን በጣዮን ወንዝ ዳርቻ እንደአባቴ እንደአባቶቴም ህግ ወርዶ እንዲነግሥ ብትጠይቀው እንደአባቴ እንደሰሰዎን እንደወገኖቼ እንደትስራሌሌ ህግ እንጅ እንደ እንቺ ዘመዶች ሥርዓትና ህግ በወንዝ ዳር ሄጄ ሥርዓተ ንግሥን አልፈጽ ምም ብሎ በነሀኑ ዛዶቅ ልጅ በአዛርያስ እጅ ቅባል መንግሥት ተቀቶ ብቶ እናቴ ስትገዛው የነበረውን ካኪት እስከ ማድጋ ከዑማ እስከ ኣእሳይ ግብፅ በአራት ነገሥታት ላይ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ስሙ መንግሥቱም ምኒልክ ተባለ አብረውት የመጡትን የዩቅማንን ዘሮች ሌዑሳውያንን ተስደው አብረው ስለመጡና ስለአገሉ ግሎት ህዝቡን እንደአረብ አበሺ እንደሚለው አቡስ መቃደሩን እግእዚ ኤል ተብሎ የሚጠራውን አምላክ እግዚአብሄር ብሎ አዲስ ስም አወጣ እግእዚያን ማለት ነገሮች ነጻአውጭዎች ማለት ነው በግእዝ ከብዙ ዘሮች ስለተቀላቀሉ አቡስ ቅልቅል ፍርትም ስለተዋሃሉትና ስለነገ ሉት ኢግእዚ ነጻ አውጭ ጌቶች ገገሮች አምላክ ሃገሩን ስለሰጠው እግዚአብሄር የነጹ ጌታ ማለት ነው ስለዚህ የሴም ልጅ የዩቅማን ነገዶች ቋንቋቸው ግእዝ ተባለ ልግእዝ ብሄረ እግዚ ወገሁ እግ እዝያን ይላል እንዚህ ህዝብ አቡሳውያን ገገሮች እግእዝያን የሚባ ሉትን የናቱን ወገኖች አዜባውያን ሱባውያን ኩሜውያንን የዛሬው ካማዊ/ኪታውያን" በጀያውያንን ኑባውያንን እየለያዩ ከእነጋና ከነ ደሉ በኋላ በበሊያቸው ጅም አስቀመጣቸው ።

አቡሳውያንና ሃደሬውያንም በፈለጉት ሃገር እንዲቀመጡ ስለ ተፈቀደላቸው በነባታቸው ስም አዲስ ስም እየአወጡ ከአስራ ሁለት ተከፈሉ ነገደ ላዊ ነገደ አቢሚኤል ነገደ ያዊላ ወደያመን ተሻገሩም ሃገር እያቀኑ ቢኑብቻ በባዕሲ መስለው ተቀመጡ ነገር ግን አዲ የቀ ከሰውን መንግሥት እያፍተው አዲስ መንግሥት አቋቋሙ በዚህን ጊዜ ሰለሞን የሬስራኤል ንጉሥ ሞቶ ልጁ ሮብአም ነግሶ ሳለ ከኢት

ም ጋር ወደኢየሩሳሌም ወርዳ ለሰለሞን አቁባት የነበረችው በል ኪሣ ከነበረችበት ከኢየሩሳሌም መጥታ በአባትዋ ዙፋን እንድትቀ መጥ አደረጉ ።



በዶው በረካች — ሠባ

ነገደ ሃደራም ነገደ አውባሊ ዘሳን የተባሉት ነገደ ደቅላ ደገከል የተ ባሉት እነዚህ ሰሩቂ በሷው ከሲው ፈለው ከደው ከሚባሉ ጕሳዎች ንጉስ አንግሥው ከተገኙ ኤርትራ ባሀር በሳሬው ቀይ ባህር አካባቢ

ድረስ ሄደው ተቀመጡ ከለው ፈለው ንጉሥ በለው ገበሬ ከደው
በረከኛ ዘላን ነው ንጉደ አፈር ንጉደ ኢወላጥ ንጉደ ኢዋዴድ በዛሬው
እጋዴን ሄደው ፊት ከነበሩት ነገሥት ጋር ተስማምተው ተቀመጡ
እግአብሄርን ያላቸውን ምርጥ ወታደሮቹን ቤተ ዘላ ቤተ ሚል ቤተ
ግራሚል ቤተ ቤተታግ ቀልላ ቤተ ሃማራ ቤተ መራ ቤተ እንደ ቤተ
እሹር ቤተ ጉድረት ቤተ ለእላት ቤተ ሃኒ እያለ የገሩን አዲስ ስም
እወጣላቸው ወታደሩንም እችስ መባላቸው ቀርቶ ጁዋ እንዲባሉ
እዘዘአበራ ዑሔት የጁዋ ሠፈር አደረገ ።

በሰልፍና በጦር የታወቁትን የእስራኤልን ልጆች 1ኛ የአምናን
የበኩር ልጅ ዋን የዛሬው እንዳቤት በየጉቱ ቤተ እንዳ መቀመጫ
ውን አድርጉ የቋራ ንጉሥ አድርጉ ላከው በዚያም ጉምዝያ የሚባሉ
ሉት ጉማዎች ይኖሩበታል ሁለተኛ የይትርናዎን ልጅ አዲል በዛ
ሬው የጁ በየጉቱ ጎንት መቀመጫውን አድርጉ በዛሬው በመሬዝቤቱ
እስከ ቤተመራ ድረስ እንዲገዛ እንግዳ ላከው በዚያም፤ ዛሬውች
እማራዎች የየጉቱ መሬዎች ጉማ ይኖሩበታል ።

ሶስተኛ የሲሞን ልጅ የሚሆን ሃልሃልን ከበጉስ ልጆች ጋር
ቤተ አዥር በዛሬው በጂዳ ወይም ወገራ እንግዳ ላከው በዚያም የበጂዳ
ጉማዎች ይኖሩበታል ።

አራተኛ የዳዊት ወንድም የማሚል ልጅ ኢያኦስ የኢዮአስ ልጅ
አቢሜሌክ የሚባለውን እናቱ ያደገችበትን ሃገር እዘቦንና በሰሜ
ሃዊ ጣቂን በዛሬው ተከዜ ዳር ለጓር በሚኖሩት ጉማዎች ላይ እንግዳ
ላከው እነዚህ ሁሉ የእስራኤል ልጆች ናቸው ።

አምስተኛ የሚወዳቸውንና ታማኞቹን ለሌሎቹ ለአበቱ ልጅ
ለሚሆን ለዚጋዊ ሰጥቶ ዚጋዊ መባሉ ቀርቶ ዛጉዌ እንዲባል ይሄው
ከአምስቱ ንጉሶች በላይ ከሚኒሊክ በታች ማለት ነው ለዚህ ለዛጉዌ
ከአምስት ንጉሶች በላይ አድርጉ ከእንግሡው በኋላ ዋና መቀመጫ
ውን የዋግ ከተማ ቀይገ ላይ እንዲቀመጥ ላከው በዚህም ሃገር የዛ
ሬና የሂንዲን ሃይማኖት የሚከተሉ ዘማቾውና ዘንቋቸው ሥርዓታቸው
ለየት ያለ በጂያ ወይም ቺያ የሚባሉ ነበሩበት በዚህ በዛጉዌ ዘመን መን
ግሥት ሚኒሊክን ለመርዳት ሄደው ልጁን ተማይን ሀገሬ ብለው
እንግሠው ሲመለሱ የቺያ ተዋጊ ጁዋ በራዊት እንገው ተብሎ ምንጊ
ሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በእናቱ ወገኖችና አዲስ በመ
ሁት አቡሳውያን ላይ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ በንግሥ ጊዜ የአሥራ
ስምንት አመት እድሜ ወጣትሰው ነበር ኢትዮጵያ እናቱም ንግሥት

ንግሥት ዘኢትዮጵያ በተባለች በስምዋ አንድ በተወለደች በሰሌሳ ስድስት አመትዋ እንቀላፋች ልጅዋ ሚኒሊክ በሰሌፍ እንደሥርዓት ንግሥት አቀባበር አክብሮ የአባቱዋ አለም ወደሚገኝበት ዋና ተራራ ወስዶ በክብር አስቀበራት ያንም የገር ንጉሥ ይባላል ።

ቀዳማዊ ሚኒሊክ በአራት ሺህ አምስት መቶ ሰባራአራት አመታት ዘመን ከተቆጠረ ንጉሡ ንግሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ሊመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ ንግሥታት ሥርዓት አፍርሶ በአራት ካህናትና በኢጋእዝያን ጴጥ ሠራዊት እየተረዳና እየተመራ እንደእስራኤል ሥርዓት እንደፀየን ሀግ ሥርአተ ንግሱን አከበረ ስርአተ ንግሡን በሚያከብርበት ጊዜ ለአንድ ሺህ ዘመን የቆየውን የዘንዶ ምስል ዘውድ በደሸት ነቢይ የታዘዘውን የኮከብ ምስል አውርዶ በፈንታው የአንበሳ ምስል አስቀመጠበት እንደዚህም አለ ከኩሺ ነገድ የወረደ የአባብ መንግሥት ተቀጠቀጠ የደሸት ኮከብ ረገፈ ከይሁዳ ነገደ የመጣው አንበሳ አቸነፈ የአቸነፈው የአንበሳ ዘር በሰብሆ ዙፋን ላይ ነግሶ ስሙ ነገደ እግዚአብሄን ሃገሩ ብጹረ እግዚ ቋንቋቸው ልሣን ግእዝ ሲባል ይኖራል በበታች ለሚገኙት ንግሥታት ሁሉ በአረብና በግእዝ ቋንቋዋ አኖሯል ካሉ ።

ቀዳማዊ ሚኒሊክ የአናቱን መንግሥት ወደአባቱ ወደ በሰሞን ከአዛወረ በኋላ የፈላስፎችን የሱባውያንን መፅሃፎችን እንዲቃጠሉና እንዲጠፉ ካህናቶችም አዋቂዎችም እንዲገደሉ ቅርጾችም የውሊቶችም እንዲፈርሱ ተብቅ አዋጅ አሳወጀ በሱባውያን መፅሃፍቶች ፈንታ ሙሴ ያጻፋቸው የአሪት መፅሃፍቶች በካህኑ በመልከ ጼዴቅ በአዘጋጀው የአህል መስዋእት ፈንታ ደቦል ያለተገለተ በግና ፍየል እንደዚሁም ወይፈን በሬቱን በሚታየው በዘንዶው ፈንታ አንበሳ እንዲቀመጥ የአሪትን ካህናት እንዲያደርጉ አዘዘ የካህናቱም አለቃ አዛርያስ የሳዶቅ ልጅ ነበርና በኮከብ ምስል ፈንታ ታቦት ጽዮንን አስቀመጠ እግዚአብሄንም ከአራት ካህናቶች ጋር እየተባበሩ የእስራኤልን ታሪክ ሲጽፉ የተከበረውና የታወቀው ኢትዮጵያኑን የሚባለውን ሁሉ ወርቅ አፅን ልቡን እንቅፋል ግሩን የሚባለው እንቁ ወርቅ እንቀልፀፉን ወይም እንቅፋልፃፉን የሰውታል ብሎ ስም ተደረው ነበር በግእዝና በአረብ ይደውም ግን የሚባለው መልክ ወይም ንጉሥ አሉት በዚሁ ዘመን በኢትዮ ኢታቤት ውስጥ ያለው መጽሐፍ ሲቀር በኢትዮጵያ በዕብር ይሲ ሰንደቅ አልማም ዘመኑ መንግሥት የተጻፉ የምግባርና የተዉስ የእንቆቅልኙም መጽሃፍቶች ተቃጠሉ ፃግ ሽዋና መጽሃፍ ሰባኤ

የሚባሉት መሳፍንቶች ግን በራሳቸው በንጉሥታቱ ውስጥ እንዲ
ቀመጥ የሚሆን ነገር እንዲመለከቱት ተደርጐ በሰንበር አልጠፋም
በሚኒሊክ ዘመን መንግሥት ወደግብፅ እየተሰደዱ የሚኖሩ ሳባው
ያንና አዜባውያን ሱካውያንና ኩሳውያን ነበሩ እንዲሁም በግብፅ ላይ
በአየሱ ጊዜ የሰለሞንን እግት ልጅ ቴቄምናስን ፈርኦን ገድለው በእዱ
ዘመን መንግሥት በናኤል ወንዝ የነገሡው የካይሮን ልጅ ሺሻቅን
እንግሥው ኢየሩሳሌምን ለመውረርና ተመልሰው በሳባ የነገሡው
የሰለሞንን ልጅ ሚኒሊክን ለማጥፋት ተነሱ በዚህን ጊዜ ሰለሞን
ሞቶ ልጁ ሮብአም ንጉስ ሳለ ወደኢየሩሳሌም ወርደው ኢየሩሳሌምን
ወረሩ በፊንታቸው ብዙ መፅሃፍት አቃጠሉ እጠፋ ሰለሞን ያሠ
ራውን የወርቅ ጋሻ ሁሉ ወሰዱ ከኢየሩሳሌም ተመልሰው የሚኒ
ሊክን ከተሞችና እሱ ያነገሳቸውን ንጉሶች ለማጥፋት መንደሮች
ንም ለማቃጠል በሺህ ሁለት መቶ ሰረገሎች በማጓያ ሽህ ፈረሰ
ኞች አስልፈው ሄዱ በተራራማው የሚኖሩት ከኢትዮጵያ ቀጥለው
የነገሱት የማጂ ዘሮች የረገሙት እርጉም የመረቁት ምሩቅ የሚሆን
በሰንበር የሚኒሊክ እናት ወታደሮች በናፓታ ሰፍረው ሁሉቱ በእ
ንድነት ሆነው ነኛን አልፋችሁ እታወሩም ሲሉ ከለከሏቸው ቴቄ
ምናስን አስገድሎ በግብፅ ላይ ንጉስ የነበረውን ሺሻቅ ያምንባቸው
ስለንበር ከማጂ ዘሮች ብዙ ፈላስፋዎችና መናፍስት ጠሪዎችን በሰ
ላም ከተነጋገረ በኋላ አብረውት እንደሄዱ ግማሹን የእሱን ወታደር
ተሰደው የነበሩትን ሱካውያንና አዜባውያን በፈለጉትና በመረጡት
ቦታ እንዲቀመጡ ከማጂና ከሚኒሊክ ባለሥልጣኖች ጋር እስታ
ርቆ ወዲያውኑ ወደሃገሩ ተመለሰ ።

እንዲሁም በጂናኛቃ ልጅ በጋዩ እየተመሩ በመካከለኛው
ግዩን ወንዝ ደንበር ተቀመጡ በዚህም ጊዜ ዚግህ የምትባለውን
ከተማ ቀረቁሩ ።

የማጂ ዘሮችም ለብቻቸው ደንጋን በሚያስደንቅ አሰራርና ጊዜ ጊዜ
አጥር አጥረው በሩያም ከተማ ሥውርድብቅ ነው ይባላል ።
ያሞሩ ንጉሥ ሁለተኛው የራስ የመንዲን ጉሣዎች ለሥራ እንዲያግ
ዛቸው ልከዋል ሌላም ግምብ የሚሆን ወርቅ ሉል ደንጋይም እግዜ
እንደዚሁም የደጃት ልጆች ባሉበት ቀን ሥውር ከተማዋ ደንጋ ተብሎ
ተሰይማለች እነሱም ደንገብ ተባሉ ደንገብ ማለት እሞኖቲ ፈላበት
ማለት ነቶ ሱካውያንና አዜባውያን በያሉታቸው በሰባት ተከፈሉ
ያሉቆቻቸው ስም ጉንት ፣ ቀማ ፣ ጉንጋ ፣ ሉሉ ፣ ጉማ ፣ ዲጋ ፣ ጉንጋ
ይባላሉ ። የሰፈሩበትንም ሰፈር ባለቆቻቸው ሥም ተጠሩ

በጆኖቫኖቅ ይመን መንግሥት መዮተው ስለፈናና እንኳ ስለቀረ ቆሩ በስሙ ጀኖቬቅ ወይም ጀኖኛ ተባሉ በአረቡ ጀኖቅ ጀጂክ ይለ ቀል ። በሚኒልክ ትዕዛዝና ፍቃድ የተሰመው አዲሱ የማዕረግ ስም

1ኛ/ ራት ማስሬት ንጉሥ ነገሥትና ንጉሥ በንጉሥ ቀኝ ዘውድ ያደናና የበላይ አዛዥ

2ኛ/ ንጉሥ ሕገባይ ነጋሪት አከመች

3ኛ/ ደልከሚ ደጃዝማች

4ኛ/ ሊቀመጠኔ የሚፈርድ ዳኛ

5ኛ/ ዋን ወንጀለኛ የሚቀጣ

6ኛ/ ቀሰብማ አገዝ አሊቃ ለቤተ መንግሥት

7ኛ/ ሊቀማና ባልደናበ

8ኛ/ ሠርጉቀይ ደርሰኔ ቢትወደድ

9ኛ/ ዶጊል ሶፎ አዛዥ

10ኛ/ ደቀ ሠርጓድ በለምሶር ቃና የአምቢልተኞችም የመለከተኛ አሊቃ

## ምዕራፍ ሰባት

### የቀዳማዊ ሚኒሊክ ንግሥና እረፍት

ቀዳማዊ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ /መሊበል መምሰከተል ሱባይ/ ተብሎ በነገሠ በሃያኛው ዓመት ከህንድ ውቅያኖስ እስከ ኬቲም ባሕር ድረስ ለአሉት ነገሥታት ጥሪ አድርጐ ወደ ታላቁ ከተማ ሀብ ሄዶ ሀብ የሆባው ንጉሥ የጂማ ዘር ልጅ ሞሪካ ኬታ ነበር በዚህም ሃገር የሚኖሩት የመደበኛ ጐሣዎች ስለሚኖሩበት መንዲ ይባላል ። ይሄም ሃገር የእናሩ ንጉሥ ልጆች ሃገር ስለሆነው እናሪያ የባሬው ሰሙ በክፉ ሠሶት የሚገኝ ሃገር ነው ።

እንደዚህም ሆኖ በዚህ በሀብ ከተማ ጥሪውን አክብረው የመጡት ነገሥታት አርባ ናቸው ለንጉሡ ለአርባው ነገሥታት ከምሳ በኋላ ለሀዝቡና ለነገር ለሁሉ ከአደረገና የሚነግሩውን ከአንገስ በኋላ ለሀዝቡና ለነገሥታቱ በየቋንቋቸው አዲስ ትእዛዝ አዲስ አዋጅ አሳወጀ የአባቶቻችን ቀደም ትእዛዝ እንደዚህ ነበር የእኛ መንግሥት ከአባታችን ከሰሎሞን መንግሥት በእግዚአብሔር ፈቃድ የበተሉን ስንሆን በዚህ ምድር የቆየውን የአርጌውን ሥርዓት መንግሥት ቀጥቋጦ ነቅለን አጥፍተነዋል እኛ ለእናንተ አዲስ የፃፍ መንግሥት ግንድ ስንሆን እናንተ በእኛ ጥላ ስር እረፉ እንግዲህ በጥላችን ያረፈ ሁሉ የመንግሥትን ሥልጣን ፍሬ እንሰጠዋለን ይሆንንም የምንሰጣችሁን ስልጣን ልትሰሩበት ነው እንጂ ለስም ብቻ አይደለም ይሄውም ልታስገብሩ አልገባም ያለውን በሥልጣናችሁ ልትገሉ የተገዛውን ሥልጣን ከእለኛ ፈቃድ ስተተናኙ ይሆን የሰጠናችሁን የመንግሥት ሥልጣን ከእለኛ ፈቃድ ለማንም እንዳትሰጡ ድንገት አሳልፋችሁ ለሌላ ብትሰጡ እስከ ዘራችሁ ባሪያዎቹ ተብላችሁና ሆናችሁ ትገዛላችሁ ሲል ለነገሥታቱ ተናገረ ለህዝቡ ደግሞ እናንተ ተገዢዎች የነገሥ ባሪያዎች ንጉሣችሁን ነቅታችሁ ጠብቁ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ ንብ ለአውራው እንደሚገዛ ያለ አውራም እንደማይኖር እንደዚሁ ይሆን የንጉሠ ነገሥቱን አዋጅ ባታ ከበሩ ትእዛዙን ባትፈጽሙ

እንደሚሆሉ በማይቀበር ጼዋ ሠራዊት እንደዝንብ እናወፋችኋለን ከምድረ ገፅ ብሎ በግእዝና በእብራውያን በአረብ ቋንቋ አዕር ለንጉሠ ታቱ ሁሉ ቃጽሉ በዚህ አዋጅና በአዲሱ አምልኮ ስርዓት የመደባይና የማጂ ነገሮች ብዙ የደሸት ካህናቶች የሱባን ቋንቋና ፊደል የሚያውቁ እንቀበልም ስላሉ ተገደሉ ሁሉቱኛም የሱባን ፊደል ሲፅፍበት የሚገኝ መደባይ ቢገኝ እንዲገደል ሉሉ እግእዝያን የተባሉት የአቡግመዎን ነገድ ለአዋጁ ተናገሩ ስማቸውንም መደ ባይ መባሉ ቀርቶ አርሙን አሉአቸው ከዚሁ ብዛት ከግእዙም ከሱባውም ስለራቁ አርሙን መባላቸው ቀርቶ አረሙኔ በግእዝ አርሞ በሱባ ደጄም ማለቱ ጨካኝ ሲላቸው ሱባው ሞራገጫም አላቸው አዋቂ ማለት ነው ንጉሥ ምርካም ለሚኒሊክ ብዙ የወርቅ ቡችላና ሎሌ ድንጋይ ስለሰጠ በምስራቅ እስከ ዳዋር በምእራብ እስከሱኪ ያስ ውን ሃገር እንዲገዛና እንዲያስገብር ፈቀደለት በእናረያና በሃ ድያ ለአራት ሺህ የጼዋ ሠራዊት መቀመጫ አደረገ እነዚህም ጼዋ ሠራዊት አምልኮታቸውን በአዲሱ በአራት ህግና ስርዓት ስለነበር የጥንቱ መደባይ የዛሬዎቹ አርሞ የእነሱን ባህልና እምነት ስለተከተሉ እስከ ዛሬ ድረስ በዚያው ባህል ጋብቻውንም ሆነ ሌላው ከእብራውያን ጋር ይመሳሰላል

ቀዳማዊ ሚኒሊክም ከዙባ በእምስት መቶ ሽህ ሰራዊት ከሰ ላሳ አንድ ነገሥታት ጋር ሃገር እያቀና ለምለም ቦታ (ሃገር) ባገኘ በት ሥፍራ ሁሉ አዲስ ሰፈር እያደረገ በነገሌ አድርጐ ኪንዶ ገባ የኪንዶውም ንጉሥም በሰልፍና በክብር ተቀብለው የትልቁ ንጉሥ ሾም ልጅ ከረም የኮሬም የልጅ ልጅ ዲንዳ ነበር በዚህ ሃገር ለአ ንድ ወር ከተቀመጠ በኋላ በሀንድ ውቅያኖስ ለሚኖሩት ጉሣዎች እንደ አንድ ንጉሥ እየሾመ ሃገር እንዲያቀኑ ግብርም እንዲያስገ ቡና ላከ ከነዚህም ለዛን ዚባሩ የማሲ ነገድ የሆነውን ባር በሬ ሃኒ በቤተ ሃጌና በዛይላ ለሚገኙት ለጂሪና ለመራይዎን ነገዶች የፌትማን ነገድ የሆነ ሴሎችም በአፈር በኤውላጥ ለሚገኙት ሁሉ እንግስ ላካቸው ።

ከኪንዶ በረሃውን አቋርጦ ወደታላቁዋ ከተማ ሳባ ሲመጣ ብዙ ሠራ ዊት በሀመምና በውሃ ጥም እልቆበት ሳለ ከግመሎን የዛሬው ኩሣዊ አዜባውያን የዛሬዎቹ ማያ ወይም ጥልባል በድንገት ደርሰው ሞገተው ገደሉት ቀዳማዊ ሚኒልክ በተወለደ በሰላሳ ዘጠኝ አመቱ በንጉሡ በሃያ አንድ አመቱ ሞተ ያኔም የሞተበትን ቦታ ሃኪም ይባ ላል ሃኪም መባሉ ቀርቶ ሃካም ካም ወንዝ ይባላል እብንልሃኪም

ተብሎ ሲጠራ ስለነበረ ነው ከዚያ ከጦር ያመለጡት ወታደሮች ወደ ቆማ ከተማ ከሻሬው የጁ አካባቢ ዋዝ ሄደው ለወንድሙ ለዛጉዌ ንጉሥ ዛጉዌም በአስቸኳይ በአካባቢው የሚገኙትን የጁዋ ጦር ሰብስቦ ወደአዛል(አዳል) ሃገር ሄዶ የገደለውን ገድሎ የማረከውን ማርኮ ብዙ ስለባ በግመል አስጭኖ የወንድሙን አፅም ከተቀበረበት አስወጥቶ በክብር ማባ አጠገብ ከሚገኘው ምእራር አበው ከሚባለው ዋሻ ውስጥ አስቀበረው በፈንታው የሚኒልክን ልጅ ቶማይን ስመ መንግሥቱን ሃንድዩን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አሰኝቶ በአራት ሺህ አምስት መቶ መቶ ሰላሳ አምስት ዘመን ከተቆጠረ አንገሠው በዚህን ጊዜ በሚኒሊክና በዛጉዌ ዘሮች ላይ ለልጅ ልጅ የሚኖር ሥርዓት ቃልኪዳን አደረጉ።

1ኛ/ በሰለሙሞን ልጆች በዛጉዌና በሚኒሊክ በካከል ያለው ፍቅርና ሰላም በተባበርና መረዳዳት በልጅ ልጆቻቸው ለዘለአለም ፀንቶ ይኖራል ። ይህን ቃል ኪዳን ያፈረሰ ልጅ መንግሥቱ ለባእድ ትሂዳለች እርሱም እንደተራ ሰው ሆኖ ይቀራል ነፍሱም ገሃነመእሳት ግቢ ትባላለች ።

2ኛ/ የሚኒልክ ዘር በነገሠ ጊዜ የዛጉዌ ዘር የሆነው መጥቶ ለንጉሡ ነገሥቱ የሚገባ ውን እጅ መንሻ ሰጥቶ ከእሱ በታች መሆኑን የሚኒሊክን ዙፋን እንደሚቆጣጠርውና እንደሚጠብቀው ቃል ገብቶ መሄድ አለበት

3ኛ/ በዛጉዌ ዙፋን የተቀመጠው ንጉሥ እንደሌሎች ነገሥታትና መሣፍንት ግብር ክፈል ተብሎ እንዳይጠየቅ እሱም ይዞ እንዳይመጣ

4ኛ/ በሚኒሊክ ዙፋን የተቀመጠው ንጉሠ ነገሥት ቢታመም ወይም ቢሞት በዛጉዌ ዙፋን ያለው ንጉሥ መጥቶ የሚኒሊክ መንግሥት መጠበቅ መቆጣጠር አለበት የሚኒሊክ ዘር የሆነው ከዙፋን እስከሚወጣ ድረስ የጁዋ ሠራዊትና ነገሥታቱ በሥሩ መታዘዝ አለባቸው ።

5ኛ/ የሚኒሊክ ዘር የሆነው ሥርዓት ንግሱን ሲያከብር ያእንበሳ ጸቦሉን በጦር ሲወጋ የዛጉዌ ዘርም ነብር በጦር ወግቶ መግደል አለአለበት

6ኛ/ የሚኒሊክ ዘር የእንበሳ ለምድ ለብሶ በጉሽ ምንጣፍ ላይ ሊቀመጥ የዛጉዌ ዘርም የነብር ለምድ ለብሶ በአጋዘን ምንጣፍ ላይ መቀመጥ አለበት

7ኛ/ የሚኒሊክ ዘር በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የጣንቱ ዘር በብር ዙፋን መቀመጥ አለበት

8ኛ/ የሚኒሊክ ዘር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲሆን የጣንቱ ዘር የእስራኤል የታላቅነቱ ከተማ የዋይዶች የእስራኤል /ዘብ/ ንጉሥ መሆን አለበት የእስራኤል ዘር ለሌላ ዘር እንዳይሰጥ በተማ ከጣንቱ ዘር በስተቀር

9ኛ/ ከሚኒሊክ ዘሮች ውስጥ ወንድ ቢጠፋ የጣንቱ ዘር መግዛት ይችላል ከእሱ ቃል ከስማቸው ንብቶ ሊያስታርቃቸውና ሊጻኝቸው ይችላል የወጣ ቃሉን ያቀለለ ቢኖር ፈጽሞ ይነደላል

10ኛ/ ይህ የቃልኪዳን ውል ለልጅ ልጃቸን ፀንቶ እንዲኖር በእግዚአብሔር ፊት ድና ኢጋኘኑት የሰሎሞን ልጅ ሚኒሊክና የሰሎሞን የልጅ ልጅ ተማይ ምንድኖ ቃልኪዳን አድርገናል ለዚህ ቃል ኪዳን ሪዳታችን እግዚአብሔር ምስክራችን የኢትዮጵያ ምድር ነው ይህን ውል አትም የሚያፈርስ ትውልድ ቢመጣ መንግሥቱ ለባእድ ሀይሉ ለውርደት ይሆናል ምድሪቱም የአባቶችን ቃል ኪዳን ስለአፈረሰ ትተፋቸዋለች ሊትሸከመው አትችልም ይህ ቃል ኪዳን በነገሥታት ታሪክና በሃይማኖት መፅሐፍቶች ውስጥ እብሮ እንዲጻፍና ሊተከረነው ትውልድ እንዲያውቀው ተጻፈ ይደረጋል ዘመን ከተቆጠረ 4535 መንግሥት ከካም ወደ ሴም ተዛውሮ ዘመን ከተቆጠረ በሃያ አንድ አመቱ ልጆች ወደእብራዊያን እስራኤልያን ከተዛወረ በዛኛ አንድ አመታት ልጆችና ለሚኒሊክ ልጆች ማለዉ ለጣንቱ ልጆችና ለሚኒሊክ ልጆ ላይ ቃል ኪዳን አድርገናል ማለዉ ለጣንቱ ልጆችና ለሚኒሊክ ልጆች እንዲታወቅ አድርገናል ። የምኒሊክ ልጅ ለከኔኛና ለነገሥታቱ ሁሉ እንዲታወቅ ጣንቱ ንጉሠ እስራኤል የእስራኤል ንጉሥ ጣንቱ ተማይና የሰሎሞን ልጅ ጣንቱ ንጉሥ እስራኤል ከአስቀመጠ ከአደላደለ በኋላ ለምኒሊክ ልጅ በአባቱ ዙፋን ላይ ከአስቀመጠ ከአደላደለ በኋላ ወደ ሃገሩ በሰላም ተመልሶ ተማይ ምንድኖን እስከ ሀገሩ ድረስ ከኃይና ከአስገበረ በኋላ በተወለደ በሰላሳ ስስት አመት በነገሠ በአስራስድስት አመቱ እንቀፋፋ በፈንታው ልጅ ዘሚዶር ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በተወለደ በአስራ ሁለት አመቱ ነገሠ ከመ መንግሥቱ እስ ተብሎ ተብሎ ተጠራ ዘመኑ ከተ 14548 ነው ።
አሚን ሆ ተብሎ ተጠራ ዘመኑ

እንደዚሁም ሆነ አሚንሆ በነገሠ በአስራ አምስተኛው አመት የሱባዔውያን ፊደል እስራኤላውያን በሆኑት በእግአዝያን ስለተከለከለ የሆነው የሰባውያን ፊደል እስራኤላውያን ፊደል ጀሚያሮ /ሴምያሮ/ ለሆነው ማሪያት እግሊትናም የእብራውያን ፊደል እንደእናቱ ሰሎ ግእዝ ቋንቋ እሚልቀ አልጀፍ በላለ አዲሱን ፊደል እንደእናቱ በጋ አቀማመጥ አድርጎ በሰባት እንዲን ድምፅ እባገዞ ማደፍ ጀመረ አጀማመሩም አ ማለቱን ትቶ ሀ ብሎ ጀመረ ይሄውም አ ማለት አለ እዳም አብርሃም የመጀመሪያ ስም ፊደል ቢሆን ሀ ማለት ሃሌ አለ

ሳይፈጸሙር የንበሬ ሉቃ እለዎምን እንልፎ የሚኖር ማለት ስለሆነ በዛ
ጀመረው በሰባት ቀኖች ምሳሌ እንዲን ድምፅ ከሰባት እስቀመጠው
የሰባ ፈደል እስር ያደርገዋል ይሄው እዲስ የግእዝ ፈደል አሚንሀ በእዘ
ጋጀውና ታሪክ ነገሥትን በያዕቁበት የመገበያው መካሊት ወይም
ንንዘብ በሚግርያትና በንብርውያን ፊደል ነበር ተከታዮቹ ንገሥታት
ያቀቀበት አሚንሀ በኢትዮጵያ ሃገሮች በእሉት ነገሥታት ላይ ጥሪ
አድርጉ ግዛ ቃቸውን እንዲያሰፋቱ ሃገር እንዲያሰሙ ባርከና ሽልሞ
ወደየሃገራቸው ሰደዳቸው በዚህን ጊዜ የመጀመሪያዋ የታላቁ ከተማ
የሰባ ንጉሥ የታምሪ ልጅ ዝሪ ነበር ዝሪም በጣም ግዙፍና
የደለኛ ሰው ነበር ዝሪ የሰባ ንጉሥ በተባለ በሰላሳ እራት አመቱ
እስራኤልን ለመግባት ይሁዳንም ለማስገዛር ወደ ኢያሩሳሌም ዘረደ ።
በእስራኤል የነገሠው ሰማርያን የሠራ ዘንበሬ በይሁዳ የነገሠው አሳ
ነበዩም የአደድ ልጅ አባርያስ ነበሩ ዝሪም ሶስት መቶ ሰረገሎች
አስር መቶ ሺህ ጰኛ ሠራዊት ይዞ ሄደባቸው ዘንበሬ ገሽ ሲንገም
አልፈለገ የይሁዳ ንጉሥ አሳ ግን ዝሪ በሠራዊቱና በጊታው በእ
ሚንሀ ተመክቶ ስለመጣ ወደ እግዚአብሄር ፀለየ እግዚአብሄርም ፀሎቱን
ሰማ በዝሪና በሠራዊቱ ሁከት ተነሣ እግዚአብሄርም መታቸው ይሁ
ዳም ብዙ ሠራዊትና ብዙ ግመሎች ማረከ ተከታትለው እስከ ጌራራ
ድረስ አባረሩዋቸው ታላቁዋ ሰባ የሰባያ ከተማ ከዚያ ቀን ጀምሮ
ታናሽ ከተማ ተባለች ንጉሡ ነገሥቱም አሚንሀ የዝሪን መጨቃቃትና
መሸነፍ በሰማ ጊዜ በጣም አዘነ ማቅም ለበሰ በራሱ ላይ አመድም
ነሰነሰ በጣም ይወደውና ያከብረው ነበርና ግን በሰባ የነበሩ አይሁድ
ደስ ተሰኙ ኢትዮጵያውያን ተዋረዱ አይሁዶች ከበሩ እያሉ በእልል
ታና በሆታ ሰነበቱ በዚህን ጊዜ ብዙ አይሁዶች የአረት ክህናት ታሠሩ
ብዙዎም ስለተገደሉ በንጉሡ ነገሥቱ ላይ ውስጥ ውስጡን ያምፁ ጀመር
እንደዚሁም ሆነ ከወገናቸው ከእስራኤል ከምሬፍ ነገድ ከምትወለደው
ከዘጀና ልጅ ማርያ የሚወለደውን ታላቁን ልጅ ተዋዋሰያን እንገ
ሠው አሚንሀ የተባለውን ዘግዱር ንጉሡ ነገሥቱን ገድለው እን
ግሡት በዚህን ጊዜ የጣንተ ልጅ በራኪ የእዜብ ንጉሥ ዘግዱር ንገ
እንገሡት በዚህን ጊዜ የጣንተ ልጅ በራኪ የእዜብ ንጉሥ ዘግዱርን
አግእዝያን የተባሉት አቡጎውያን እንደገደሉት ሰምቶ እስራሁሉቱን
የእዊ ጦር ሠፈር ጥሪ አድርጐ በሃያ አምስት ሺህ ጰኛ ሳባ ከተ
ማዋን ከበባት እንደዚሁ በላእለይ ግብፅና በናፓታ የሚኖሩ ዘግዱር
አሚንሀ ከግብጾች ጋር ጦርነት በአደረገ ጊዜ በድል አድራጊነት ያስ
ቀመጣቸው አምስት መቶ ሺህ የሃማሪ ነጋዶች የሆኑ ልቶ የእክሱማይ
ጴኛ ሠራዊት ከበራኪ ጋር ተባብረው በአንድ ላይ ሆነው ተዋሰያንን

ያነገሡና እሚገዛ ንጉሡ ነገሥቱን የገደሉትን አይሁድ በጭካኔ ሰብ
ሰበው ገደሉአቸው ተቀብሯቸውንም በአደባባይ በነገሡ በሃያ አምስት ቀኑ
ሰቀሉት የቀጣይ ወንድም የሚጊኢሉ ልጅ ባራኬድ ከገዛ ቀጥሎ በሱባ
ነገሡ ባራኪድም በእናቱ ወገኖች በባሬዎቹ ከሳውያን በጥንቶቹ ሱባው
ያንና ኩሼዎች ዘንድ ከብሮን ስላገኘ በራሱ እየተረዳ በወንድሙ ልጅ
በአፈሳስ አጼነት ፍቃድ ማቀቡን አሰፋፋ ከባራኪድ ቀጥሎ ታናሽ ልጅ
ቅብርሂ አቀበሩ ተብላ በአዜብ ላይ ነገሡች አቀበሩም ወንዙን በስሙም
ጠራችው የጌዋ ስፈሩዋን ጀቢት አደረገች ንግሥት አቀበሩ ለእግዚአብሄርን
በወደጹት ቸገር እንዲቀመጡ ፈቀደች በዚህን ጊዜ አቡሳውያን(አበሺ)ተብ
ሰው በሚጠሩትና በኢትዮጵያውያን በኩሳውያን ሰላም ቀመበረ፤ ከኋላም
ያንም የእግዚአብሔን ግእዝ ቋንቋ መናገር ጀመሩ ።

ሴም ፤ አርፋክሳድ ፤ ቃይናን ፤ ሳላ ፤ ኤቦር ፤ ፋሌቅ ፤ ራግው ፤ ሼሩሀ ፤
ናኮር ፤ ታራ ፤ አብርሃም ፤ እንዚህ ሁሉ ከኤቦር ጀምረው ቋንቋቸው እብ
ራይስጥ ስዎች እብራውያን ይባላሉ ። እብራውያን ስለሚባሉት እስራ
ኤል ወይም አይሁድ ስለሚባሉት አጭር ታሪክ ከአዳም እስከ አብር
ሃም ሃያ አንድ ትውልድ ሆነ አብርሃም ከወገኖቹ ተለይቶ በካራን
ልዩ ሥፍራው አር የባሬው ኢራቅ ከተባለው ተነስቶ የባሬው አደሩ
ላቂ ምድር ከነዐን ምድር ከዜቶሰበ ጋር ገባ ስለዚህ በእያቆ
ማሬም ወደዚያነው ከነአን ምድር ከቤተሰቡ ጋር ገባ ስለዚህ በአያቆ
በአብርሃም አባት በታራ አባት ስም በኤቦር እብራውያን ተባሉ ቀጥሎ
አብርሃም ከሸመገለ በኋላ ይሳቅትን ከሚሽቱ ከሣራ ፤ እስማኤልን ከገ
ሬዶ ከአጋር ወለደ ይሳቅም ኮሚስቱ ከርብቃ ኤሳውያንና በኋላ እስራ
ኤል የተባለውን ያእቆብ ወለደ ፤ ያእቆብም አስራሁለቱን ነገደ ልጆች
ወለደ ልጆቹም መጀመሪያ ያእቆብ ቀጥሎ እስራኤል በተባለው በአባ
ታቸው ስም እስራኤል ተባሉ ከነዚህም ከአስራ ሁለቱ ነገዶች የሌዋ
ዊ ልጆ ዮሴፍ የተባለው ልጁ ሌሎቹ ወንድሞቻቸውን የሌዋን ወደ ግብፅ
አቡቱ ይወደው ስለነበር ቀናተው ወንድሞቻቸውን ዮሴፍን ሸጡ
ለሚወርድ ነጋዴ ሸጡት ነጋዴውም በግፅ እንደደረሰ ለጶጢፋር ሸጠ
ው ጶጢፋርም ለቤቱ ሁሉ አላፊ አዛዥ አደረገው ወደውም እን
ወጣ አደረገው ከዚያ ምጥርታው ሚስት ለሥጋ ፈቃድ ጠየቀችው እሱ
ሱም ጌታዬ ባያይ እግዚአብሔር ያየኛል ብሎ እንቢ ስላለ ባልዋ ሲመጣ
የነገሩትም ባሬያ እብራዊው ከልያገለገለ ብሎ ሲተናነቀኝ ከመሀ ሬብሶ
ዋሉ ሽሽ አለችው ጶጢፋራም ሚስቱ ያለችው እውነት መስሎት የሌዋ
ወህኒ ቤት አስገባው የሌዋም በህልም አፈታት ምክንያት ወጥቶ ነገ
ብፅ ንጉሥ ፈርኦን ጋር ተዋውቀና ባለሟል ሆነ በዚሁ ዘመን
በእለም ረሃብ ተነስቶ ነበርና የሚሸመት እህል ለመፈለግ የሸመ
ወንድሞቹ ከከነአን ወደ ግብፅ መጡ እርሱም ወንድ ሞቹን
ወንድሞቹ ከከነአን ወደ ግብፅ መጡ እርሱም



ምናለሽር

ቃቸውና አባታቸውን ይዘውት እንዲመጡ አዘዛቸው እነሱም እንደ ተባሉት ወንድማቸው በህይወት እንዳለ ለአባታቸው ነገሩው ሰባአ ነፍስ ሆነው ግብፅ መጥተው በክብር ተቀመጡ እነዚህ እብራውያን በግብፅ አራት መቶ ዘመን በላይ እንደተቀመጡና በበረከተ ጊዜ የግብፅ ንጉሥ ፈርኦን ራምሲስ ባሪያ አድርጋቸው ነበር በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር ሥቃያቸውን ተመልክቶ በሙሴ አማካኝነት ከግብፅ አወጣቸው ሆኖም በሙሴ ሰጣቸው ከዚያም በኢያሱ መሪነት የከነአንን ነገሥታት አሸንፈው ለአባታቸው ለአብርሃም ወደ ተሰጠው ምድር ገቡ ከሙሴ እስከ ሳሙኤል በመሣፍንት በካህናት ሲተዳደሩ ቆይተው በመጨረሻ እንደሞአብ እንደ አሶር እንደአሕዛብ ንጉሥ ይደረግልን ብለው ጠየቁና በእግዚአብሔር ፈቃድ ሳኦል በመጀመሪያ ነገሠ ከዚያም ዳዊት ቀጥሎ ልጁ ሰሎሞን ነገሠ ከሙሴ እስከ ሰሎሞን ድረስ በአንድ መሪ ይገዙ የነበረውን አሁን በርብዓም ዘመን ሁለቱ ተከፈሉና እሥራኤ ነገዶች ሰማርያን ርዕሰ የመጀመሪያውን ንጉሳቸው ኢዮርብዓም ሆነ ሁለቱ የይሁዳና የብንያም ነገዶች በኢየሩሳሌም ቀርተው ለዮብዓም ይተዳደሩ ጀመር ስማቸውም በአባታቸው በይሁዳ አይሁድ ተባሉ በሰሎሞን በኢትዮ ዘመን መንግሥት ገና ሳይከፈል ከእስራኤላዊ ነገድ ተዋቅው ምኒልክን በብዓያቸው እንግስው ወደኢትዮጵያ ምድር ገቡ የገቡትም በጋዛ መሪነት ስለገቡ አግአዝያን ተባሉ ከይሁዳ ነገድ የወጣው አንበሳ አሸነፈ የሚለውን ስም እስከ ክርስቶስ ልደት ይዘው ቆዩ ።

## ምዕራፍ ስምንት

### የአክሱም አመሠራረትና

### የአጼ እዛና አክሱማይ ራሚስ አፈላስ ተብሎ እንደነገሠና

### ግብፅን ጨምሮ እንደገዛ

መጀመሪያ የኩሽ ዘር ናምሩድ አበመወክስ ተብሎ እንደነገሠና ታላቋን ከተማ ኢሬቢንን ሰራ የኩሽ ዘር የሆነው የቶር አብ ልጅ አባብዬር እብራዊቱዋን የእሜን አደብን ልጅ ሩትኢሚንን አግብቶ በግዮን ምድር ኢትዮጵስን ወልዶ ኢትዮጵስም በገደትዋን ተብሎ በግዮን ዳርቻ ሆኖ ከነገሠ በኋላ ታላቋን ከተማ ሱባን ሰራ ሱባም የፈላስፋዎች የገር ስለነበረች የታላቅ ታላቅ የሆኑ ግንቦች ታንፀውበት የከተማዋ ስም ሱባ የሃገሩም ስም ሱባያ እየተባለ በአማሌት ልጆች እስካሁን ይጠራል ። ብዙዎች ነገዶች የሱባ ከተማ ከጠፋ የሃገሩ ስም በአረብ ሱባያ ይባላል ከሱባ ቀጥሎ እንደ እብራውያን አል እንደኩሳውያንና እንደሱባውያን አጼ የሚባለው በንጉሥ አለማ የየልካና ልጅ ታላቂቱን ከተማ በኩሽ ልጅ ስም ሳባ ብሎ ቆረቆረ መንበሩንም እንሳበ አለው ከተማዋን አሥርቶ ከጨረሰ በኋላ የንጉሥ ታቱን መቀመጫ ከሱባ ወደሳባ አዛውሯል በሱባ ንጉሥ እንዲቀመጥበት አዘዘ ከናምሩድ እስከ አጼ ድረስ በሳባና በሱባ በአሬብ ንጉሥ ነገሥት የሚባሉት እነዚሁ የኩሽ ዘሮች ናቸው ። ከኢሬቢን ወደ ሱባ በኢትዮጲስ ዘመን መንግሥት ከሱባ ወደሳባ በአጼ ዘመን መንግሥት ጊዜ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የንጉሥ ነገሥቱ መቀመጫ እንደተዛወረ አሁን ደግሞ ከሳባ ወደ አክሱም በአክሱማይ ዘመን መንግሥት ተዛወረ ።

እንደዚሁም ሆኑ እብንልሃኪም /ምኒሊክ/ ቀማይን ወልዶ ቀማይ ዘግዱርን ወልዶ ዘግዱር እሚሆን ተብሎ በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ንጉሥ ነገሥት ሆኖ ሲገዛ ሳለ ልጁ ተቀብሞ በአይሁድ እየተረዳ በበሳቱ ነግሶ ስለገደለው በዓዮ ላይ ግብፅና በናፓታ ራሚስ ተብሎ የነገሠው አክሱማይ ልጁ በአራ ሦራዊት ከአማርኛ ወደሳባ መጥቶ

ታላቅ ወንድሙን በንጉሡ በሃያ አምስት ቀን ገድሎ የዛጉዌ ዘርን ባሉበት ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በአባቱ በሚኒሊክ ዙፋን ላይ ተቀመጠ ስመ መንግሥቱም አፈላስ ተባለ አፈላስ ማለት በሱባውያን ቋንቋ የኢውቀቶች ቃል ማለት ወይም የአዋቂዎች ቃል ታሰሚ ማለት ነው ራሚስ የተባለበት በንጉሥነት አፈላስ በንጉሠ ነገሥትነት ነው ዘመኑም 4589 ዓ. ዓለም ነበር ።

ወግዳር አሚንሀ አክሲማይን ራሚስ ብሎ ከኩሳውያን ወገን ከምትሆን ከአናቱ ከራሚሌ ልጅ ከንግሥት ሳቦኒ ጋር በናፓታ አገ ግሶት ይኖር ነበር አክሱማይ ራሚስ በሰባት ዓመቱ ሲነግሥ እናቱ ማያኒ በመንግሥቱ ታገዘት ስለነበር ያንሩን በስምዋ ማዩኒያ አለ ችው ማዮኒያ ታላቁ በረሃ የሚገኝ በት ነው ደንገሉም እስከ ኪቂ ባዘር ድረስ ነው ማያኒያ የሄፈው ማሃራ ነው ከማያኒ ሱዳኔ ተባለ

አክሱማይ አፈላስ ተብሎ ንጉሠ ነገሥትነትን በተረከበ በሙ ሉተኛው አመቱ በስሙ አክሱም ብሎ ታላቋን ከተማ ቆረቆረ በሰባ የእናቱን ወንድም ዲማንዶና ዋስ የሳባ ንጉሥ ፈንያስን የአዛ ርያስን ልጅ ለቤተመቅደሱ ድብተራ አራት ብሎ ሹሞ የንጉሥ ነገ ሥትን መቀመጫ ከሳባ እራሱ ወደቀረቀረው ከተማ አዛወረው ።

በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ የነበሩ ለሚገኙት ነገሥታት ዋራ አደረገ በተረው መሰረት ለታላቁ ንጉሠ ነገሥት ከሰንደት አልማ እስከ ኑቱማከድ ኢትያና ከምኒሊክ እስከ ወግዳር ድረስ ሉሳባ ነገ ስተ ነገሥታት ማህበርና እጅ መንገዳ ሲያመጡ የነበር ነገሥታትና የልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ የመኳንንት አዛውንቶችና ሹሞች ተሰበሰቡ የታወቁ ጥበበኞች የኢሊጣና የፈላ ነገዶች እስከመሣሪያቸው መጡ እንዲገነቡም ሆን በናፓታ ራሚስ ተብሎ የነገሠው በሳባ አፈላስ ተብሎ ንጉሠ ነገሥት የሆነው አክሱማይ በራሱ ስም ሰይሞ በከ ተማኢት የነገዶችን አለቆችና ሹሞች ለኑአን ያያን የሆኑትን የበኧያ ነገዶች የጋፋትን ነገዶችን የመደባይን ፈላሰፋዎች የማጀንና የሰገሌን አዋቂዎች ኩሳውያን ወገኖችን ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ አለ በኢትዮጵያ የነበሩ የምትኖሩ ህዝቦች ሆይ ሰሙኝ በኢየሩሳሌም የነገሠው የዳዊት ልጅ ሰለሞን ለእግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታቦት መቅደስን እንደሰራ እኔም ለዕዮን ማደሪያ የሚሆን ከኒግን ሰለምሥራ ከእናንተ አስተዋዮችና አዋቂዎችን መርጣችሁ እንድታቀርቡልኝ ይሄም ቅዱስ ስራ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳኑ ታቦት ማረፊያ ይሆን እንጅ ለእኔ ወይም ለእናንተ አይደለም አለ በዚህን ጊዜ 165 ከመቶ

በልባ አምስት/ የገሮች የመጡ አለቆች ከሰባ አንድ መንደሮች የመጡ ነገሥታት ግብራቸውንና እጅ መንሻቸውን ካቀረቡ በኋላ ከየጉባቸው ፈላስፋ የሆኑ ኢስተዋዮችና አዋቂዎችን መርጠው ሰጡ ወደ ፊትም ወደየገራቸው ተመለሱ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በቤተ መዛግብቱ የሚቀመጥ ንዋየ ቅድሳት ከወርቅ ድንጋይ የሆኑ ሰሌዳ አፈር ቶቋ ሌላም ልዩ ልዩ የሆኑ መልክ ያላቸው እብነ በረድ እንልካለን ብለው ለንጉሡ ነገሥቱ ቃል ገብተው ወደየሃገራቸው በደህና ተመለሱ ኢልማኖችና ፈላኖች ለማነፅ ተዘጋጁ አፈላስም የእግዚአብሄርን ቤተመቅደስና ሌሎቱ የሚሆን በቤተመንግሥት ለመስራት ሰባት መቶ ሽህ አንጥረኞች አናጺዎች ሁለት መቶ ሽህ ባለሠረገላ ድንጋይ አመላላሾችና ድንጋይ ጠራቢዎች አራት መቶ ሽህ የሚሆኑ ባሏጋዳ ግብር ሰብሳቢዎች አስተናጋጆች መረጠ በበላያቸውም የላይኒን አባት ሌሜሌን አለቃ አድርጐ ሾመ ወንድሙን እድሜስን የአንጥረኞች የአናጺዎች አለቃ አድርጐ ሾመላቸው በዚህን ጊዜ በመልካሚቱ ሃገር በተራራማው ሃገር በሳዶሂያ በርሻ በቃዲስ ዱር

የሚኖሩ ልዩ ልዩ ጉጣዎች ለቤተመቅደሱ ከዚማና ለቤተመንግሥቱ ማሠሪያ የሚሆን ከወርቅ ድንጋይ ሰሌዳ አፈር እንቁዩቋ እየያዙ መጣተው ጋዳ አቀረቡ ንጉሡ ነገሥቱ አፈላስ ጋዳ ለላኩት ነገሥታት ለጉባ አለቆችና አዛውንቶች በስሙ የተሠራ ሻረከና የወርቅ መክሊት እንደየደረጃው ሽልሞ በተላኩት መልክተኞች ላከላቸው ።

ከዚያ በኋላ አፈላስ ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በነገሠ በአስራ አንድ አመቱ ዘመን ከተቆጠረ አራት ሽህ ስድስት መቶ ላይ ሥራው ተጀምሮ በአስራ ሁለት አመቱ ተፈጸመ በአፈላስ ዘመን መንግሥት በኢትዮጵያ ሃገሮች ፍቅርና ሰላም ሃብትና በረከት ሞልቶ ነበር በፋርስና በሚዶንያ ሃገሮች በኢየሩሳሌምና በሱባ በአህጉታ ከተማዎች መርነትና አረማብ ወንቶ ለሰንበር ህዝቡ እየተሰደዱ ይመጡ ነበር ንጉሡ ነገሥቱ አፈላስም ከስደተኞቹ በአሠራቸውና በእደላቸው ከተሞች አስቀመጣቸው እነዚህም ከተሞች የአሁም መጠሪያ ተብለው የሚጠሩት አምሊስ ዳህላቅ ቀሃይቶ በርባሬ መከላ ናቸው ቤተ መቅደስ ከዚማ የተሠሩባቸው መንደሮች የሃ ከስከሲ ቆሃይቶ ደራ መታራ ጎንደር ጉንጂ ናቸው አጼ አፈ/ ከስደተኞች እና ነገሥታቶቹና አለቆች የማሉባቸውን ቀንበር ስለሰማ በክለላ ነገሶ ለነበረው ለናሁ ከደንደር እንደኛው በዛብሉንና በሩማን በሶርያም ላሉ ነገሥታት ሁሉ ደብዳቤ አሲያ ላከ በዚህን ጊዜ ግብጻዊያን ላእላይ ግብጽና ጌዛር የምባትለውን መንደር ወረሩ የሚል ስለሰማ ኃያላን የሆኑ

ጼዋ ሠራዊት አፈሳስ ልኮ ግብጸውያን መታ ቢቀዲስ የሚኖሩት መን
ደሮች ኢትጠስ የሚል ወሬ ስክለዳ ንጉሥ ደረሰው የከለዳው ንጉ
ሥም ለሱሳ ንጉስ ለጤርስ ለአስር ንጉሥ እንዲህ ብሎ ላከ የሱብያ
ንጉሥ በሠራዊቱና በአምላኩ ተመክቶ እኛን ለመውረር የትምክህት
ደብዳቤ ላከልኝ ደብዳቤውም እንደዚህ ይላል የከለዳ ንጉሥ ከዶን
ፆር ሆይ ህዝብን ሳያጠፋ የምታጠፋ ከሆንክ በንሱ ስም ሆኜ አጠፋ
ሀለሁ ሆዘቡ የሚበላው ሳያጣ የምታበስር ከሆንክ ያለርሀራሄ አሰረ
በረሃብ እንልሃለሁ ሆዘቤ መኖሪያ ሳያጣ ማረፊያ ስለከለ ከዶ
ከውና ከቶ ቀንበርን ስለማልከበት መጣሁብህ የሚል ላከብኝ
አሁን ደግሞ ግብፅንም መታ ቢቀዲስ ያሉትን መንደሮች ኢትጠስ
የሚል ወሬ ሰማሁ ስለዚህ ኑ እንሰባሰብና ተማክረን እንግጠመው
አለ የሰሜና የአሶር ንጉሦችም ይህ የምትለው ቃል ሁሉ ልክ አይደለም
በእኛና በአንተ መካከል በሰማርያና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁዶ
ሁሉ ሰላምን አጥተው ሰላም ፍለጋ ወደግብፅ ወደ ሱባ ሄደው ተቀ
ምጠው ሳለ ስለነገሩት እንጂ ይህ የታላቅ ህዝብ ንጉሥ ከእኛ ይልቅ
ህዝባችን ስለወደደው ብንገጥመው ድል አድርጐ ያጠፋናል ።

ስለዚህ የሚለንን ሰምተን ማድረግ እንጂ ሌላ ነገር አታስብ የሚል
መልስ ላኩለት የከላዳ ንጉሥም ጠብቆቶችና አዛውንቶችን ሰብስቦ
ቢያማክራቸው ይህን ቃል ስለደገፉትእንጂ መንግሥ ለመቀ እምላ ሰዎች
እሲህ ወደመርዊ ላካቸው የመርዊ ንጉሥ ኮሸም ንጉሥ ነገሥት አፈ
ላስ ወደሚኖርበት አክሱም ከተማ ከሠራዊቱ ጋር ላካቸው አፈላስም
ከከለዳው ንጉሥ ከዶንፆር (ከዶንፆር ለናቡከደነጾር ቅድመ አያቱ ነው
ሊሉ ተማጽነው እምስተኛው ተወልዶ የልጅ ልጁ ነው የሚሉ እሱ
መላኩቸውንና ንጉሱም ልጁ የምትለኝን ሁሉ አደርጋለሁ የሚል ደብ
ዳቤና ገፀበረከት ስለላከ የተላኩትን በክብር ተቀበሉ ብሎ የወርቅ መከ
ሊትና የብር ወንግ እሲህ ላከለት በከለዳው ንጉሥና በአክሱም
ንጉሥ ፍቅር ስለተ መሰረተ አፈላስ ሬብላ የምትባለው ልጁን ለከዶን
ፆር ሚስት እንድትሆን ትሆንው ሰጠው ሬብላም ከከዶንፆር የናቡከደነ
ጾርን ቅድመ አያት ናቦላሳርን ወለደች ከተማዋንም በስሟ ሬብላ
አለቻት ንጉሥ ከዶንፆር ከአክሱም ንጉሠ ነገሥት ጋር የጠበቀ ፍቅር
ስለነበራቸው ብዙ ጠቢባንን ላከለት አፈላስም ሀገ አዋቂዎችን የእብ
ራውያንን ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትን የመንግሥት አማካሪ ላከለት የመጀ
መሪያው ከእበ ስንገድ የሆነ አዲግን ላከለት ከአዲን ቀጥሎ እስከ ናቡከ
ደነጾር ድረስ የነበረው የአዲን የልጅ ልጅ አቢመሌክ ነበረ አፈላ
ስም በዚሁ ዘመን የእሰም አባት ተባለ

እንደዚሁ ሆነ አፈላስ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በአርባ አመቱ አመተ ከተቀጠረ አራት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ ላይ (4629) በቀዳማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት እንዲጠፋ የታዘዘውን የእባ ቀችን የነመ ልከጸዱትና የኢትኤልን ሀግና ሥርዓት እንደገና እንዲታደስና የወደቀው የምኅሉ ምስል እንዲነሳ ሲል የእለማን ፀጋፊዎች የመደባይን እኛቂዎችንም አጠባውያንንም ሰብስቦ እንዲህ ሲል አዋጁን አፀር እናገረ በልቶ ልቶ ቋንቋም አፀር ወደነገሥታቱ ላከው ወደ የነገሥታት ራስ የጠቢባን ልብ አፈላስ እንዲህ ይላል በዚህ አለም ምድር የምትኖሩ ነገሥታትና አዛውንት ቃሌን ስሙኝ ትእዛዜንም ፈጽሙ የምላችሁን ሁሉ አድርጉ ቃሌን ስምታችሁ ትእዛዜን ፈጽማችሁ ብትገኙ ለእናንተ ክብር ለወገናችሁ ደስታ ለልጅ ልጃችሁ ደህንነት ለጉልማችሁ ሰላምና ፍቅር ይሆናል ኢል ብቸአምጠራው አምላኬ በሰማይ እርሱ በአየር የህይወት መንፈሱ በምድር በምስራች ቃሉ ለዘለአለም የሚኖር እርሱ ብቻ ነው ስሙም ቅዱስ አምላክ ለዘላለም ነውእንደሌሎች አማልክት አይመስለም ተወዳዳሪ ፈጽሞ የለውም ባህርዩ የማይገመት መልኩ ሊያዩት የማይቻል ስውር ሊቀርቡት የማይቻል የቃልና የመንፈስ ሃይል ነው የምስራች ቃሉ ግን ከሰው ልጅ ሰው ሆኖ የሚታይበትን የሚያሰሰበት ቀን ይመጣል ለዚያ ትውልድ እያየው ባለማየቱ ወተለት የህይወት መንፈሱ በዋንግዜ ለየአንዳንዱ የሰው ልጅ ህይወትን ከማስተዋል ጋር ይሰጥ ዘንድ በቃል ይመራል ለሰው ልጆች የተዘጋጀውን ሁሉ ያደላል ይህ ሁሉ ሲሆን ግድ ነው ይላል የህይወት መንፈስ እናንተ አህዛብ በባህር ዳር አምትኖሩ በዋኛ የምትተመጡ ስሙኝ አድምጡኝ የምታምኑበት መገዘያና አምልኮት ሁሉ ያሰበሰል ይደቃሉ እንዱን በአንዱ መልክ አትመስሉት ወዮላችሁ ታፍራላችሁ መሀረምን በጨረቃ ብታህ ተቲሆን በኮርማ ወይፈን ሃይርን በላም በዛፍ ክሊኦምን በበግ ሚዛንን በተኩላ ሰበንን በትትት አሞራ ስታርን በኮከብ ሃኑስን በጅራ አሞራ ገዲን በንስር አፈርቀንምንና ሆትን በእባብ ሲሲትን በዘንዶ በአሮና ሁባስቲስን በድመትና በነብር ሁተን በእንሽላሊት አሞንን በወያይ ሁድሃን በነፋስ ሺባንና ሂንዱሆን በአሳት ማርታህን አድሉን በቀራራና በኮሪብታ የምትመሰሉና የምታመልኩ አህዛብ ሆይ ይህ ሁሉ እናንተ ስለሠራችሁትና ስለ መሠላችሁት እንደናንተ ፈራሽ ነውና ወደማይፈርሰውና ወደማይጠፋው የህይወት መንፈስ የምስራች ቃል ኑ እሱ እራሱ ሁሉን ይገልፅላችኋል ይሰጣችኋልም ይህን ብታደርጉ እናንተ ይመስላል እናንተም እንደሱ እርሱም እንደ ነው እናንተም በአንድ ትሆናላችሁ አሁን ግን ያላችሁ በሞትና በህይወት መካከል ናችሁ አባቶቻችን ቢበድሉት ታናናሾች አባቶች የታላ

ቆችን አባቶች ህግና ትእዛዝ አፈረሱ ይኸውም አባትንትን ያጠፋ ዘንድ
ነው እኔ ግን አባትንትን እኖር ዘንድ የሁሉንም ህግና ትእዛዝ መርጫ
ልኬላችኋለሁ ። አዳም የፈጣሪውን ትእዛዝ ባይፈጽም ከህይወቱ
ተባረረ የማይጠፋ ሞትን አገኘ የአምላክን ቃል ሰምቶ መርከቡን
ቢሰራ ከአለም ጥፋት አምልጦ ዘርን አተረፈ መልከ ጼዴቅ የተባለው
የኢትኤልና የምሥራቢያ አባት የአለምን ሞት የሞሀንመኛን አይቶ በሀ
ይወቱ አምላኩን በፈጣሪው የህይወትንም ቃል በሚሰው መስዋእት
መሰሰው ስለዚህ ሰሙ የሰላም ንጉሥ የድህንንት ካህን ተባለ ልጄ
ኢትኤል የአባቴን ምክር ተቀብሎ የፈጠረውን ህግና ትእዛዝ ቢያ
ደርግ እንደአባቶቹም እንደመልከጼዴቅ የእግዚአብሄር ካህን ቢሆን
አባትንትን አገኘ ይችንምድር እርስትህ ብሎ ሰጠው ከዘሩም ጭን
ቃቁን የህግ ንጉሥንጉሥት እጁን እስንባለት ቃሉቁ ንጉሥ ነገ
ሥት እጁ ህይወቱን በአምላኩ ግዛቱን በዘንዶ ቢመስለው አምላኩ
እድሜን ሰጠው የእስራኤላት ትውልድ የልጅ ልጄን እኛ እዳም አባቴ
በሴት ተሳስቶ እንደወደቀ እሱም ህግን ቢተላለፍ እንዲሁ ወደቀ እስ
ራኤል ይሁዳ ልጄ በትረመንግሥትን ይዞ የአንበሳ ደቦል ሆኖ ቢያ
የው ለበለአም ደግሞ ከእስራኤል ኮከብ ሲወጣ አየ ሙሴ የይሁዳን
ድምጽ ቢሰማ የእባቡን የብረት ምስል ሰቅሎ እስራኤልን ከእባብ
መርዝ አዳናቸው ይሸት በማየን ምንጭ ላይ ሆኖ እንዳዋረደን እያየ
ቢፈለሰፍ ለበለአም ከእስራኤል ሲወጣ የታየው ኮከብ ለእርሱም ታየ
ውና እሱን ሲከተል ድንግል ሴት ልጅ ወንድ ልጅ ወልዳ ታቅፋ
እያት ድንግሊቱ ወልዳ የታቀፈችው ልጅ የሰላሙ ንጉሥ በሰማያትና
በምድር ሁሉ ላይ ለዘለአለም አባት ሆኖ የሚኖርን ስልጣን በእጁ
ጨብጦ አየው ስለዚህ ከምድራችን ከምናገኘው ምርጥ ነገር ወስደን
አንድን ሰጠው ይሸት ለልጆቹ አዘዘና እብነልያሊም እብነል መልክ
ምኒልክ የኖረውን የኢትኤልንና የእጁን ህግና ሥርዓት አጥፍቶ በም
ትኩ የለየን ሥርዓትና ሙሴ የጻፈውን ህግ ብቻ ህዝቡ እንዲቀበለው
ቢያዝ ኤል ተብሎ የሚጠራውን የሰማይና የምድር ጌታ ብቻ ነው
ሲል እግዚአብሄር ብሎ ሰሙን ቢጠራው እስከሥራቂው በአካል ህዝ
ቦች ተመትቶ ወደቀ

ዘግቶር አባቴ ከእናቴ ጋር ወደግብፅ በልጅነቴ ቢሰደኝ እግዚአ
ብሄር አምላኬ ከግብፅ እንደጠራኝ ከሞት እንዳሳለፈኝ አወኩት ከዚ
ያም የስደት ጊዜየ ሲያልቅ ወደሳባ ተመልሼ በአባቶቼና በእናቴ እትያ
ዙፋን በትረ መንግሥትን ይዤ እንድቀመጥ አደረገኝ ።

እኔ ግን እላችኋለሁ ከጥሩ መሃል ክፉ ከክፉ መሃል ጥሩ እንዳለ እንዳይጠፋችሁ ክፉ እንዳለ በጥሩ እንዳለ ይወጣል ጥሩ መብል በተበላሸ ፍሬ ይጠፋል ስለዚህ በመካከላችሁ ህይወትና ሞት ደስታና ሃዘን ክብርና ውርደት አቅርቤላችኋለሁ ። ከሁለት አንዱን መምረጥና ግን ሳት የናንተ ነው የወደቀውን የኮከብ ምልክት ከባሬ ቀን ጀምሬ በእጼስ ጨረቃ ላይ እስቀምጬላችኋለሁ ይሄም ኮከብ የሰው ቅርፅ አምሳል ግራና ቀኝ የሆኑ እጆና እግር ያለው ነው የአራት ማእዘኑ የመስቀል ባለቤት እስከሚረከበው በዚሁ የኮከብ ምሳሌ ስትመሩ እንድትቆዩ ይህም ኮከብ ለኢትኤል ዘር በእስራኤል ላይ ሲወጣ የታየና ወደ እስራኤል የሚያመራ የንጋት ኮከብ ነው ይሄን ኮከብ የሚከተል ሁሉ እውነተኛውን ፍቅርና ሰላም ያለበትን የዘለአለም መንገድ ይያገኛል ከሐድቅና ከህይወት ሃገር ያገባል የሥራውንም ፈጣሪውን ያያል በእባቱ ዙፋን የሚቀመጠውን የክብርና የፀጋ ባለቤት ሁልጊዜ ምስጋና የብቁ የሆነውን መድሃኒት ዓለምን ያሳያል በተስፋ አይቶ የእመነውና ትእዛዙን የፈጸመ ሁሉ ለዘለአለም ይድናል እንጅ አይጠፋም ።

ከንጋት ኮከብ ቀጥሎ እርሜ ብርትን-(የእባብ ቅርፅ) በበትረ መንግሥቱ ላይ የእቻናፈውን የአንበሳ ቅርፅ በዙፋኑ ላይ እንዳደረኩ እናንተም ነገሥታት እንዲሁ እንድታደርጉ ይሄም የበላይነት ምሳሌ እንጅ የአምልኮት ምሳሌ አይደለም ብዙ አምልኮቶች እንዳሉ ለምታችኋል ነገር ግን የአምልኮቶች ራስ አንድ ነው የአማልክቶች አምላክ እርሱ እራሱ ነው የራስ ምሳሌው ህይወት እንጅ ሌላ አምሳል እንደሌለች የለውም እርሱ እራሱን የሚመስል ፍጹም የህወት መንፈስ ነው

የመንፈስ ቃል ነው እሱም ለዘለአለም መንፈሱ ከናንተ ጋር ነው እንግዲህ ከቅዱስ መንፈስ ጋር ካላችሁ ቅዱስ ቃሉ ከናንተ ጋር እንደሆነ እወቁን ታውቃላችሁ ስለዚህ ለእናንተ የሚሆን ስለምላችሁ ተቀብላችሁ በልባችሁ ጻፉት በከንፈራችሁ እስሩት እስራኤል ልጅ ርበዘር የኢትኤል ልጅ እከሰማይ ቢሉ በኢትዮጵያ ሀገሮች ለነገስት ነገሥታት በሸለቆና በበረሃ በተራራና በሜዳ ለሚኖሩ ነገዶች አለቆች በየቋንቋቸው በየፊደላቸው እጽፎ ላክ እነዚህም የነገዶች ቁጥር የታወቁትና ንጉሶች ያላቸው እነዚህ ናቸው ።

1ኛ/ በጌራራ ደሴቶችና በኤርትራ ባህር አጠገብ የሚኖሩ ጉማዎች ዋና ከተማቸው አዶሊስ በንጉሡ ነገሥቱ ትእዛዝ የሰፈሩት ሠራዊታቸው ፈላይልፍ አዛዣቸው ፈዶል ኮሬቢቶቻቸው ተመሳሳይ የሆኑት

1ኛ/ ኩሳ - ካሳዊ ኩሽ ጣመል የሚያፈልቡ ጌራራ ጊዘር
ሳንኮት
2ኛ/ ቅክሬር - በእኔ
ማሀዳ
3ኛ/ ጀሊሉ - ጀሉ
4ኛ/ አማሁርታ - የሌን ሰሃርት ምድረ አግአዚ - አክሰጉማይ
5ኛ/ የርጊት ከአርባ አመት በላይ የሚያናኑ ባእ
6ኛ/ ባሬቻ ፊታቸው የሚተለትሉ ጻሬማ



ዋንቀሳ

7ኛ/ ምናእሚር መጽሀፍት መፃፍ የሚወዱ ባለታሪክ አቡሳው
ናግራን
ጆ

8ኛ/ ኩናማ (የውሻ) ውተት የሚጠጡ (ተኩላ የሚበሉ) ፊታቸውን የሚሸፍኑ ሜቲኢ

9ኛ/ ብሔን - በንጉሠነገሥቱ ዘንድ የተከበሩ ዘፋኞች

10ኛ/ ምናእሜርና ዘላኖች የቀንድ ከብትን የሚጋልቡ ኢጋላት እግእዚ

11ኛ/ ሀማን - ሃብሳት ተዋጊ ነገዶች አቡሳውያን ምድረ ቤጃ

12ኛ/ ራይዳን - ሂማራት የሰባን ፊደል ያላጠፉ ቅልቅል ሕዝቦች ሣባ

13ኛ/ መንጉርቶን በጨው ባህር የሚኖሩ ጨው ወሃ የሚያጠጡ ኤሪማ

14ኛ/ የውሃ አውሊ ሂሊ በረግረግ የሚኖሩ አሣ አውጭዎች ጋዘል

15ኛ/ ዜንጋቤኔ ጂልባ በመስራት የታወቁ አረብ ሶልን

16ኛ/ እንጋቤ ቅንድባቸውን የሚቀርጡ ጂባ ጂቤት

17ኛ/ ሲጃየን በመሬት ውስጥ እጉድጓድ የሚኖሩ ቀጀል

18ኛ/ ሲጃየን በዘንዶ የሚያመልኩ እንጋቦ

19ኛ/ አራቢት - ያገኙትን ሁሉ ለቅመው የሚበሉ ቲያማ

20ኛ/ ቲያሞ - በዋሻ ውስጥ የሚኖሩ ቀለባቸው እንበጣ የሆነ ቦጣ

21ኛ/ አታልሞ ዋኩል አባብ የሚባሉ በባምትራ የሚያመልኩ አታጋው

22ኛ/ ቤጋ - በጉስ ከአቡሳውያን ጋር መጋባት የሚወዱ ጋባ

23ኛ/ ሱኮሜ ራውየን በእውሬ ጉዱጓድ የሚያድሩ ኢትቢት

24ኛ/ በዶው - በዶው - በረኸኛ ዘላን ቢጌኔ

25ኛ/ ከሰው - ፊውንቱ እራቁ የወይን ጠጅ የሚጠጡ አቋ

26ኛ/ ፈለው አርሆ እንጋዳ ነጋዴ ከአዶሊስ ወደ አክሱም የሚመላለሱ አዶሊስ

27ኛ/ ሃርር የመጀመሪያ ልጃቸውን ለጣኦት የሚሰው ቤጋስ

28ኛ/ ደንዳኔ በከርስ ጥብብ ሥጋ የሚመገቡ ሐማሴ

29ኛ/ ሱላ - የንጉሥ ነገሥት ዘር ያላቸው በሁሉ የሚከበሩ ሰሚኢን አበኬ

30ኛ/ ቦዲ - የከብቶቻቸውን ጆር የሚተስትሉ ኢጋሜ
31ኛ/ ቦጋ - ሂሌፋዝ ራቁታቸውን የሚኖሩ ኬብቶ
32ኛ/ ኢሌማ የንጉሡ ነገሥት ባለሟል ፈላስፋዎች ሥጊት
33ኛ/ አቦሚከ - ማስዑጂ ማደሪያቸው በዛፍ ስር የማጀንያ
34/ኛ ብሌንማ በኢትዮጵያ ወንዝ የሚኖሩ በዋና የሚተመሙ ተገረሰስ

እነዚህ ጐሳዎችና ነገዶች ከአክሱም ወደ ሰሜን በኩል የነበሩ ፋሮ ዛሬም ግቂቶች የሚገኙ ናቸው ።

2ኛ/ ከፍል ተመሳሳይ ጉርቤት የሆኑት ጐሳዎች ሀገራቸው ከአዘብ እስከ ታላቁ ባህር ውቅያኖስ ጫፍ ዋና ከተማቸው ሂንዶ እዘል በርበራ ወንዙ እዋሽና ዋቢ ፥ አዋ ፥ ጂባ ፥ ጃዋ ፥ ደሳነው ሀገራቸው ወታደራቸው መለሳ

እዋላት
1ኛ/ ተንት በኮርቤና በእልገን የከበሩ በከላ
2ኛ/ ጆር - ጂራ - ጊር አፈርአጋዶን
3ኛ/ አበል - ሱማሊያ በዛላንነት የሚኖሩ ኮፈገር
4ኛ/ ሙራ ሆን ዋራ
5ኛ/ ሻርቃል ነገብ
6ኛ/ አቡቴ ቀጋራ ታጁራ
7ኛ/ በሰላ ቀርማ
8ኛ/ ዋራራ የሌላን ጉሣ መግደል የሚወዱ ጀጀ ጂድያ
9ኛ/ ኢጣው - ኢጣ እላዎች ፈጣን ሯጭ የገራ
10ኛ/ ሻሆ - ዛፍ በምላበትና ከዛፍ ስር የሚኖሩ ነገብ
11ኛ/ ፋሊ - ፈላስፋዎች የሰውን ቋንቋ መጽሐፍ የሚያውቁ ማዳድ
12ኛ/ ሃርላ ሆብሆብ
13ኛ/ ቴድሮስያ በግና ግመል ማርባት የሚወዱ ሃብታሞች ፊድል
14ኛ/ ኪሉንፋዚ አሊና እሣ መብላት የሚወዱ የባህር ሰዎች እየዋ
15ኛ/ ሱላጪ ሱላሚጦስ መልካቸው ያማረ ገሆን የሚያደርሱ እልዛብ
16ኛ/ ሱማያ ከሆገር ወደሌላ ሆገር ሲሆሩ የሚኖሩ ዘላ አዛንያ
17ኛ/ ራውዚ - ሄል እስነ
18ኛ/ ሃድራሞት ልጃቸውን ለባህር ሰውተው የሚኖሩ ሲሰ
19ኛ/ ሣትራሞት በሜዳ የሚኖሩ ምግባቸው ቅጠል

20ኛ/ ኪታብን እምነካቸው ቅርብ የሆነ ነፍስ የሚያጠፋ ላግ
21ኛ/ አርድ ዛፍ በምላበት ሀገር የሚኖሩ ዳዋሮ
22ኛ/ ያሟላ ከወገቡ በላይ ጥቁር ያለው በግ የሚያረቡ ዝቡራ
23ኛ/ ሚንበር ወንዝ ለወንዝ ዝቡራ
24ኛ/ ዜንቦ - ጃሳር ሸረሪትና ዝንብ የሚበሉ ታንዛን
25ኛ/ ሱኔርያ አውራ በማዶን የሚኖሩ መግዶራ
26ኛ/ ቡዶ ቡዶ -የግሥላና የነብር ቆዳ በወገባቸው የሚታጠቁ ቆሬ
27ኛ/ ጆሜ ዣሜ - የሰውን ሥጋና እንቁላልዋን የሚመገቡ ሃሰያ
28ኛ/ ሀብር ሥጋዲ በወርቅና በከብት የከበሩ ብልሀ ነገዶች ሀድያአሌ
29ኛ/ ድርሃናጊ ያለውሃ የሚኖሩ የዛፍስርና ቅጠል የሚበሉ ጋቱር
30ኛ/ አባሌት ከርቢና ብርተድ ከሚገኝበት ቦታ የሚኖሩ አበዞ
31ኛ/ ቱድሮስ ሴትና ከብት ልጅ የጋራ የብታቸው የሆኑ በተራ
32ኛ/ ሃርርጀማን እንበጣና ተንዚዛንለትመው የሚበሉ ማሌ
33ኛ/ ቱማልአባል - አዳል ጋማ ከብትና ቀንድ ከብት የሚያረቡ ገበል
34ኛ/ ጉርጉራ
35ኛ/ ሃብር ማጋዲ
36ኛ/ በርሱከና
37ኛ/ ያባሬ

እነዚህ ጉማዎችና ነገዶች ከአከሱም በስተምስራቃዊ ደቡብ የነበሩና አሁንም ተቂት ያሉ ናቸው ።

3ኛው ከፍል ተመሳሳይና ጉረቤት የሆኑት ጉማዎች ሀገራቸው ከግዮን ምንጭ እስከ ታላቁ ባህር ውቅያኖስ ድረስ ከተሞቻቸው ታላቁ ከተማ ከንዶ ማልበ እናሪያ ዙባ መንዱ ሃዲ ሰገል ኢዝዋድያ ወንዞቻቸው ዲዲሳ ፣ አዋ ፣ ነገሌ ፣ ጉጀብ ፣ ገናሌ ፣ ጋናላ ፣ ባሮ ሀባሌ ፣ ሴኢጋል ዛዮን ፣ ኮንጋ ፣ ሴንጋሌል ፣ መገር የወር ሠራዊታቸው ሉባ

ሀ ገ ራ ቸ ው

1ኛ/ አሪዋን -አርዋ(በውሃ የሚያመልኩ) አርያ
2ኛ/ ጋሊ - ጉጋዳና ከብት አርቢዎች ውቅሮ
3ኛ/ ዲራ - ዶራሳ ሆርውሳቦ
4ኛ/ ቦረን - ቢዛም ኪንዶ ሃድያ



5ኛ/ በርቱማ ሴት ልጅ የሚያከብሩ ተምጋ
6ኛ/ ኮሪም - ክረዩ ሰፋሪዎች መረዋ
7ኛ/ ኢጤ - ኢቲ ዋራ
8ኛ/ እቀጨ - እክዩ ወረን
9ኛ/ ሊበን - ጃዊ በሸፍትነት የሚኖሩ ጉግም
10ኛ/ ሜጫ ከብት አርቢዎች ሱሚ ሉማሜ
11ኛ/ ሰል - ሰላሌ አራዊች በለአዝመሬ ጆንት ጉንት
12ኛ/ ሰላዋሬ - በዱር ውስጥ ተደብቀው የሚኖሩ አዋሩ
13ኛ/ ጃሌ በላኖች ግመል የሚያረቡ ቸሩ ጨሩ
14ኛ/ ኢዳል ፈጣን ፍጥረቶች ፋር አንፋር
15ኛ/ ሃሮን በወፍ የሚያመልኩ ሃሮንጊ
16ኛ/ ማያ -ሲዳማ ባለመርዝ ቀስተኞች ገበማን
17ኛ/ ሰደቻ በአባብና በዘንዶ የሚያመልኩ ቆቦ
18ኛ/ ዶራ አርሀ ግድያ የሚወዱ ሞት የማይፈሩ ጉማዩ
19ኛ/ ቦፋት ብትር የሚያዘዋወሩሩ ትቢ
20ኛ/ ከምባታ በየ ወላዋ ማልበርጺ
21ኛ/ ቦኛ - ፋት ፋድ የሚል ወርት የሞላቸው ከፋ -ባሱ
22ኛ/ ሂርና አማር ሃንጋዘ የጥብስ ሰዎች ኩሌ አናሪያ ዘላ
23ኛ/ ጃሬዋ ጃራዎች ባለመርቆች ኢጦላጥ ሁለተኛ ዶዋሩ
24ኛ/ ወረም ረጃጅም ሕዝቦች ኢባር ወረማያ
25ኛ/ አባታሊት የዝሆን ቆዳ የሚለብሱ ሰገሌ ሰገሌያ
26ኛ/ ዶርጼ - ጥልፍ በመጥለፍ ልብስ መስራት የታወቁ የጉንጉ/ እገል ጋዶች
27ኛ/ ሱካ ቦንጋ ቀስተኞች ከሀገር ወደሀገር ሲዘዋወሩ የሚኖሩ
28ኛ/ ማጂ ሰብአሰገል የመደባይበር ገበማን ሰገል

እንዚህ ጉሣዎች ከመካከለኛው ግዛት ወደ ደቡብ የሚኖሩ ባሬም ጥቂቶች ያሉ ናቸው ። 4ኛው ክፍል በአክሱም አካባቢና በተራራማው ሀገር የሚኖሩ ተመሳሳይ ነገዶችና ጉሣዎች የሠፈሩባቸው ሥራቸት ኢዋ

አንጌት
1ኛ/ ኛዋ ንብና የንብማር የሚበሉ የወርቅ ጌተ የሚያበዙ መንሃድ ሌትን
2ኛ/ በጂያ ተዋጊ ሃይለኞች በዘራቸው የሚመኩ አዋር
3ኛ/ ሜራ ከተልባግር ከጥጥ የተሠራ ልብስ የሚለብሱ ቤተሃማራ
4ኛ/ ሁባቤቱ መልኬቸው የሚያምር ትንቢት ተናጋሪዎች ቤተሃጌ - ሀረርጌ
5ኛ/ ተረት ገበሬዎች በቁፋር የሚኖሩ ቤተአንጻ
6ኛ ሜሆ ሰዶስ ካለዘራቸው የማይጋቡ አዋቂ ፈላስፋዎች ቤተዋሜ
7ኛ/ ሀማን የሃር ልብስ በመስራት አዋቂ ፈላስፋዎች ኮሰኔኮ
8ኛ/ የመንተር ብዙ ዘመን ሚኖሩ ደጐች ወንጌ
9ኛ/ ናደብ ብትር የሚያዘዋውሩትሩ በዛፍ በዋሻ የሚኖሩ ሞአራፈላሞ
10ኛ/ ማከርቢያ የዛሬዎች ትግሬ አሜዌርሕዝቦች ቤተበሜና
11ኛ/ ቺያ - በጂያ -ወረኞች እና ፈጣን ወረኞች እመኪና
12ኛ/ ዓስታ እንግዳ ተቀባዮች ሰው አክባሪዎች እንዳጌ
13ኛ/ ፋርታ ትማንት ገበሬዎች ቋንቋቸው የተወደደ ቤተማራጌ
14ኛ/ ጀንጋዌር በማዮን ምንጭ የሰፈሩ ጥቂት ሕዝቦች ቤተዘላ
15ኛ/ ማንጀር በአውሬ የሚያመልኩ ዘንዶ የሚበሉ ወማዳ
16ኛ/ ፈግኖ የዱር አውሬ አባሪው የሚይዙ ፈጣን ሯጭዎች ቤተማል
17ኛ/ ሃንዲ ሰው ሲሞት በእሳት የሚያቃጥሉ ጎራርጌ
18ኛ/ ማጂ የሰለጠኑ ሕዝቦች ምግብ መርጠው የሚበሉ ከበጌ
19ኛ/ ቅማንት የእንጨት ፍሬ ለቅመው የሚበሉ ዳንግላ
20ኛ/ ቁግታ አውሬ አድን የሚወዱ ቆዳ የሚለብሱ
21ኛ/ ደራማ የፈረስ ሥጋውን በሉተው ቆዳውን የሚለብሱ
በተአሹር ወጌ
በጌ ምድር
22ኛ/ ጀማን ጠንካራ ቆዳ አፍንጫቸው የተደፈጠ ቆዋራ
23ኛ/ ጉምዝያ አሜዌር ሕዝቦች በድርጭት የሚያመልኩ ቤተሰአዳት
24ኛ/ ሻንቅላ ቆዳቸው የጠቆረ ሰው መግደል የሚወዱ የሚጋድል
25ኛ/ ጂን ወንተ ከቶ መንፈስ ያላባቸው እራሳቸውን ቤተሰአዳት
ቤተንድሪት
26ኛ/ ናራ ሊቅ ሹሉቅ አታክልት የሚበሉ
27ኛ/ ኩንፍ -ኩንፈል በእንጨት የሚያመልኩ በልያ ቤተኩፋል

28ኛ/ አዜብ - አህጉር ሁለተኛው የአፍሪካ ሕዝብ　　አደዖ
29ኛ/ ኩናማ ኩሽ የአፈጣጠር የእናቱ ትውልዶች　　ሞጣ
30ኛ/ ሳባ - ሻባ ከእስራኤል ዘሮች ጋር የተቀላቀሉ　　የማሴን
31ኛ/ ሺናሻ ሺናሻች ሻቆራ በአባይ ወንዝ የሚኖሩ　　ዳንጎ ጎንጋ
32ኛ/ ዳንጊል የበግ ልምድና ከበግ ጠጉር የተሠራ የሚለብሱ　　ቤተ እስራኤል
33ኛ/ ዳሬማ - ሂማን የወርቅ ዘንግ የሚይዙ ሃላፊዎች　　ዳሱ ተጉለት



ዳሦማ

በእነዚህ ጕጣዎች ላይ ቀዳማዊ ሚኒልክ ቋንቋቸው ግእዝ ሀገሩ-
ቸው ምድረ አግአዚ-ጋዛ እምላካቸው የምድር ንጉሥ እግዚአብሔር
ስማቸው አግአዝያን የተባሉት አቡሳውያንን ሾሞ ጴጥ ሠራዊት እድ
ርጉ እስቀምመባቸው ይኖሩ ነበር እንሱም የባላባቱን ልቶ ልጅ እየ ወ
ስዱ አግብተው ልጅ ወልደው ተቀላቅለው ነበርና ስማቸውን በቋንቋ
ቸው አቡስ በሌሎች አበሺ እየተባሉ ይጠሩ ጀመር በዚሁ በእልፈላስ ዘመን



ባሪያ ሾረማ

መንግሥት ከክንአን ምድር የእስራኤል ልጆች በጦርነት ከረሃብ ብዛት የተነሳ እየተሰደዱ መጥተው በአክሱም ከተማ ሰፈሩ ሀገርዋም ሞኢት በዚህን ጊዜ አበሺ በተባሉት እቡሳውያንና አሲስ በመጡት እስራኤል ከባድ ግድያና ጦርነት ተካሄደ ይኸውም በሁለቱ መካከል ካልተገረዙት በመጋባትና በመገረዝና ባለመገረዝ የተነሳ ነው ስለዚህ ንጉሥ ነገሥቱ አፈላስ አሲስ የመጡትን እስራኤሎች ሰብስቦ ግንኙነታችሁ ሰው በሃይማኖቱ ይሄዳል የእምነቱንም ሥርዓት ይይዛል ልቡ ያሰበውን አሳቡ የፈረሰበትን ይስ ያለውን አምላክ ያመልካል እንጅ ሊታስገድዱት አትችሉም ስለዚህ ሰፈራችሁን ለይታችሁ ተቀመጡ ሲል ነገራቸው ስማቸውንም ስደተኞች ሲል ፈላስያን -ፈላሻ አላቸው ቤተእሹርያ የሚባለውን ታላቁ ቀራራ ያለበትን መርጦ ሰጣቸው ከዚያ ቀን ጀምሮ በአይሁዶችና በፈላሾች ወገድ የከረረ ጠብና ቂም እየበዛና እየጠነከረ ሄዶ ሆኖም ፈላሾያኖች የንጉሥ ነገሥቱን ደራክና ድረ መከሊት ከወርቅና ከብር እየሰሩ አፈላስን አስደስተውት ስለነበር ሁሉ አልወጠም እቡሳውያን ግን በላብና በአዶሊስ መቀመጥ ጀመሩ እንጅ አፈላስን በመፍራት ሊወጉዋቸው አልቻሉም ።

የአጼ አፈላስ ዘመነ መንግሥት የአክሱም አጼዎች ግብሯን ጨምረው እንደገዙ

5ኛው ክፍል ከአክሱም ወደሰተምዕራብ ደቡብ በግዛንና በአወር ወንዝ እስከ ኪቲ ባህር ድረስ የሚኖሩ ተመሳሳይ ነገዶችና ጉሣዎች ወገኖቻቸው የግዛን ስር ሠራዊታቸው ሄክሶስ

የነራቸው

1ኛ/ ኦብ ባት ውሻን እንደቅዱስ እንስሳ የሚያዩ — ኦብያ
2ኛ/ ሀንዳንጉላ ቅዱስ ህዝቦች ከሙቶ እድሜ በላይ የሚኖሩ — ዳሞኤል-ኖዩ
3ኛ/ ንግን አሬሬ አዳኞች የአገኙት የሚበሉ — ጊዘን
4ኛ/ ዙልክኹልግ ጥርሳቸውን የሚሰብሩ — መርዌ-ባዊ
5ኛ/ (ቢሮኖ) ቦርኖ ከንስሳ ጋር የሚደለያዩ ዘላኖች — ጀዲያ
6ኛ/ ሃውሳ እማተኞችና ዘላኖች በበረት የከበሩ — ቻዶ
7ኛ/ ኖባቱ ሄማያ የተመር ፍሬ የሚበሉ — ልብና ሊስ
8ኛ/ (ታሊት) ሃንጋዝ የአገኙትን የሚበሉ አረጆዎች — ባርኬ
9ኛ/ አዶሊት ቢጋ እንበጣ የሚበሉ — ጃባ ታኔት
10ኛ/ አእጉሊፋል ቅንጫጭ የሚለቅሙ — ኖጅር

11ኛ/ ናይዐ ቦፋ ሴቶች ከእንስሳ ላይ ማብረ ሥጋ የሚያያደርጉ የሚያምትማት

ማይንያ

12ኛ/ ባዐ እርጥብ ሥጋ አዘውትረው ሚበሉ ማይስ
13ኛ/ ጂት ባርጂን በቀኝ የሚኖሩ ጂን
14ኛ/ ማብሩ የነብር ቆ የሚለብሱ ማቤቱ
15ኛ/ በርታ ሃፍረታቸውን ብቻ ቆዳ የሚሸፍኑ
16ኛ/ አኘክ ማብላ አባብ የሚበሉ በአውሬ ጉድጓድ የሚኖሩ ጉንት

አሸንቂ

17ኛ/ ሃሸንዳ ያገኙትን የሚበሉ ሱኪ-ሹኪ
18ኛ/ ውይጣውይት ያገኙትን ሚበሉ አውሬ አዳኞች
19ኛ/ በርት በከንዳው ጠፍር የሚያስሩ ከታብ የሚያበዙ ሹናይጅር

ፋቅ

20ኛ/ ሄሌፋል ኤሊን የሚመገቡ ቀረሽ ቀሪታንያ
21ኛ/ ሙሬ ጃርትና ኤሊ በጣ የሚወዱ ሖማ
22ኛ/ ሩብሺ ደንጥብ ፍጥረቶች እንበጣ የሚበሉ ቱትያ
23ኛ/ ዳማባ አፍንጫቸውን የሚነድሉ ናዋታ ካርናቅ
24ኛ/ አንክ የአንበሳና የነብር ለምድ የሚለብሱ ካማይ
25ኛ/ አሌ ፈላስፋዎች አሳ አጥማጆች ቡንጋይ
26ኛ/ ጉርጉስ ያገኙትን ሁሉ የሚበሉ ቱጆ
27ኛ/ ቡጋንዳ ያገኙትን ሥጋ የሚበሉ በካማ
28ኛ/ ቡኪ ያገኙትን ሥጋ የሚበሉ ማሉ
29ኛ/ ሙመገሊያ ያገኙትን የሚበሉ ዳንጉልያ ኖባት
30ኛ/ ደማልሌ ያገኙትን የሚበሉ የቅለሃራ
31ኛ/ ቡይ አቦሸማ (በሽማን)ሕሪቁታቸውን የሚኖሩ ማይጋ
32ኛ/ ጃርኖ የገላቸውን ቆዳ ሚተለትሉ ጋንገሬ
33ኛ/ ቀታውት-ወይጣውይት ያገኙትን ሥጋ የሚበሉ

እነዚ ነገዶችና ጉሣዎች አሊታቸውንና ጉትጓቸውን በጥሬው ጉሣዎች መሰረቅ በሌሉት በነዚህ በአንድ መቶ ስልሳ አምስት ጉሣዎች ለራሳቸው ግንም እንዲኖራቸው ታላቅ ግንም ነገሥት አፈላስ ዛሬ እስተካከሉላቸው ሆነም ዷር ሰጣቸው ።

እነሱም በትእግሥ በሥራት በበላያቸው ብዙ ንግዶች ንጉሥ እን ግሉ ብዙዎቹ ጋር ለፍር እየተኙ ለከለኩ ተደበቀው የሚኖሩ ሆኑ ።

እንደዚህም ሆነ በታሪታዊ ግብፅ በመምረስ የሚኖሩ ምሽሮች-(ምስሮች) ሂክሶስ የሚባሉትን የድሳንና የአማሌትን አረቦች አስነስተው ናፓታን ወረሩዋት (የባሬምቹ አዶንዳዊ) አክሱማይ የፀሐይ ልጅ ፊሚሱ ተብሎ ይባላት የነበረውን ዋና ከተማ ሃገ ናፓታ ተቃወለች የሚል ወሬ ሲሰማ ከአክሱም አምስት መቶ ሰረገሎች አንድ ሚልዮን ሠራዊት ይዞ ወርዶ ሂክሶስ የተባሉትን የሚጸስ ሠራዊትን አጥፍቶ በምትኩ የእናቱን እህት አዚትን አንግሶ ሰምዋን ቀዳማዊት ሆንዶኬ ብሎ ሰይሞ በሰላም ወደአክሱም ተመለሰ በዚሁ በናፓታ የሚኖሩ ጺዋ ሠራዊት ሁሉጊዜ ከምስሮች ጋር እየተዋጉ በበላያቸው ሴት ንግሥት ሆንዶኬ እያሉ ያስቀምጡ ጀመር ይኸውም በናፓታ የምትቀመጠው ንግሥት ሆንዶኬ በአጼው ሥር ሆና እስከ ጋዛ ባለው ሃገርና በአረቦች ላይ ስትገዛ የምትኖር የሴት ንግሥት ሁሩን እንዲኖር በአጼ አፈላስ ተደነገገ ሆንዶኬ የተባለበትም የሆንድ ዘር አክሱማይ አፈላስ አጼ ከመባሉ በፊት የነበሩት ፊጣን መልእክተኞች ለሠርነት ያዘጋጃቸው ቁጥር ታላላቅ መርከቦች የሚያንቀሳቅሱ አራት መቶ ሺህ ጀልባና ታንኳዎችን የሚቀስፉ ሰባት ሺህ በሥረገላ የሚጓዙ ፊጣን ተዋጊ ጦሮችና የብረት ልብስ ለባሾች ሰባት መቶ ሺህ ነበሩት እንዚህም በተዘጋጀላቸው ሃገር የሚቀመጡ ለሠርነት ተዘጋጅተው የሚኖሩ አፈላስ ያዘጋጃቸው ጠበብቶች የሃር ልብስ ከቲትና ከእንዝርት ብለው ጠንጉር የሚሰሩ አሰር ሺህ ሸማኔዎች ከአንበሳ ከነብር ከነብር ከቀበሮ ቆዳዎች በአልማዝና በወርቅ አስጊጦ ለሥጋድ የሚሰሩና ጥልፍ ጠላፊዎች ሰባት ሺህ መቶ ነበሩት ለነዚሁ ቀለብ እየተሰጣቸው በከብር የሚኖሩ ነበሩ እንጅ ከአንዱ ሃገር ወደሌላው ሃገር የሚሰደዱ አልነበሩም ። እንደዚህም ሆኖ አክሱማይ የአሚንሆ ልጅ ከእስራኤል ነገድ ከይሁዳ ዘር የሚወለደው በናፓታ የፀሐይ ልጅ ፊሚሲ በሳባ የአዋቂዎች ቃል ተሰማ - አፈላስ ተብሎ በንጉሥ በእርግ ሰባት አመቱ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ስም በአክሱም ዙፋን ላይ ለሚቀመጠው ንጉሥ ንጉሥት እንደታላቁ ንጉሥ ንጉሥት አጼ እየተባለ እንዲንግሥና አንበሳ ገድሉ በደሙ እንዲነከር ይኸም ህግና ሥርዓት ሆኖ እንዲኖር በሥሩ ለነገሡት ንጉሥታት በየቋንቋቸው አሰሮ ላከላቸው አፈላስም አጼ አክሱም በሎኝ ብሎ በራሱ ላይ የሀገሮ ቅርፅና የቦከብ ቅርፅ ያለው ዘውድ ደፍቶ ግራና ቀኝ ከወርቅ የተሠራ ያንበሳ ምስ

ሎች ከአለቤት ዙፋን ላይ ተቀምጦ በግራ እጁ በትረ መንግሥቱን ይዞ በቀኝ እጁ የስንዴ ዘለላዎች ተሸክሞ እጁ እስከሰማይ አፈላስ ተብሎ በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ዳግመኛ በአዲስ ስም ተጠራ ታላቁ ንጉሥም ተባለ በዚሁ እለት ማርቴና የምትባለው ሚስቱ ወንድ ልጅ ስለወለደች ትልቅ ግብዣ (ግብር) ተደርጐ ከእሱ ቀጥሎ አጼ ተብሎ እንዲነግሥ ሲል ለሚስቱ ማርቴና ቃል ገባላት ስሙንም እውሳብዮስ አለው እፈላስ የሚባለውን ታላቅ ልጁን አንግሶ ወደ ሰባ ከተማ ላከው አፈደስ ፊደል ይባላል በአባቱ ፈቃድ ሴሪክ የሚባለውን ገንዘብ በስሙ አስቀርጾ በእየሩሳሌምና በሳባ በሱባም ከተማ ህዝብ ይገበይበት ነበርና በዚሁ በገንዘቡ ምክንያት ከሰባ እስከ ኑብያ ያሉት ጉጣዎችና ነገዶች ተገዙለት እሱም ከምርኮኞች ሺናስቲ ጋር ሆኖ አሞን ለሚባለው አምላኩ እየሰገደ ለእዋንም የመስገጃ ቤት በሱባ ስለሰራ አባቱ አፈላስ ሰምቶ ጺዋ ሠራዊትን ልኮ አስገደለው የመስገጃ ቤቱንም ቤት እንዲያፈርሱትና ፊደሉም እንዲያቃጥሉት አዘዘ በሱ ቦታውንም ቤት እንዲያፈርሱትና የንግሥት ትብርኛ ልጅን ባም አጥብሩ ተብላ በአዘብ የነገሰችውን የንግሥት ትብርኛ ልጅን እንግሶ ላከው በዚሁ ዘመን በኢ ታዜናን ከአፈላስ ቀጥሎ እንዲነግሥ አንግሶ ላከው በዚሁ ዘመን በኢ ትዮጵያ ሀገሮች ላይ ሰላም ሆነ መሬትም ፍሬዋን ስለሰጠች በዚሆን ጊዜ በኢትዮጵያ ሀገሮች የሚኖሩ ጉጣዎችና ነገዶች አፈላስን እዉን እግዚአ የሚባል ስም ሰጡት ።

በአጼ አፈላስ ዘመነ መንግሥቱ ሕግና ሥርዓት ሆኖ ለልጅ ልጅ እንዲተላለፍ የአዘዘውና (የደነገገው) አዋጅ ይህ ነው ።

1ኛ/ ታላቁ ንጉሡ ነገሥት አጼን ለማስተዋስ በአክሱም ዙፋ ንላይ ተቀምጦ በትረ መንግሥቱን ይዞ የሚነግሰው አጼ ተብሎ የንጉሥነት ትና የመጣፍንት እራስ ይሆናል መንግሥቱም የንጋት ኮከብ ተብሎ ይጠራል ።

2ኛ/ ለአጼ አክሱም ድረስ መጥቶ ግብርና ገፀበረከት የማያቀርብ ንጉሥ ወይም መስፍን ቢኖር የጺዋ ሠራዊት በአለበት ሀገር እንዲሄ ደል ልጆቹም ሚስቱም ባሪያ ሆነው እንዲኖሩ ሠራዊቱ ፈጽሞ እን ጠፋ ተደንግጓል ።

3ኛ/ አጼውን የሰደበ ምላሱ እንዲቆረጥ የመታ እንዲገደል የገደለ ወገኖቹ ሁሉ ከርሱ ጋር በአደባባይ እንዲሰቀሉ ተደንግጓል

4ኛ/ አጼው ቢሞት ልጅ ልጁ ባይኖረው ወንድሙ ወይም የወ ንድም ልጅ አጼ ተብሎ በአክሱም ዙፋን ላይ በተደነገገው ሕግ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ በስሙ እግዚአብሔር ተብሎ ይነግሣል ።

5ኛ/ አጼው ቢታመምና ቢያከም ለሚወደው ልጁ ቢናዘዝ በኑዛዜው ቃል ይፈጸማል ።

6ኛ/ በአጼው ትእዛዝ ለጦርነት ክተት ተብሎ የጼዋስ መሪ ወይም የጦሩ ወታደር አዋጁን አክብሮ በቶሎ ባይመጣ ወይም ምትክ ባይልክ ይገደል ቤቱም ይቃጠል ።

7ኛ/ አንድ ሰው የንጉሠ ነገሥቱን ሕግና ሥርዓት ሳይቃወም ለህዝብ የሚጠቅም ጥበብ ፈልስፎ ቢያስተምር ወይም ቢሰራ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ዘንድ እንዲከበር እንጅ እንዳይዋረድ ይደረጋል በሕዝብ ዘንድ ተከብሮ በመረጠው ቦታ ላይ መቀመጥ ይችላል ብለን ደንግገናል ።

8ኛ/ እንዲሁ አንድ ሰው ከሃገሩና ከእመነው እምነት የተሻለ ሃይማኖት ቢሰብክ ሕዝቡም ከቃሉ የተነሳ እምነት ቢከተለውና በሕዝብ ዘንድ ሰላምና ፍቅርን የሚመሰርቱ ከሆነ ሰባኪው ሰው እንዲከበር እንጅ እንዳይገደል እግዚአብሔር በዋኒዜው ነቢያትን ወደ እኛ ይልካልና ከሚልካቸው ነቢያት አንዱ እንዳይሆን ስለዚህ ታሪክን እስተውሉት ከቃሉ አነጋገር የተነሳ እውነተኛ ነቢይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደሆነ ታውቁታላችሁ ነገር ግን ሕዝቡን በሕዝብ ላይ የሚያስነሳና ተከታዮም በአደባባይ ይሰቀል ተብሎ ተደንግጓል ።

9ኛ/ አንድ ፈላስፋ ሰው ቀልጣፋ የሆነ የአነጋገር ልሳኑ በአዘጋጅ አትቃወሙት እኛ ከእግዚአብሔር የተማርነው እንድንመርጥ ክፋትና ደግነት ብልህነትና ሞኝነትን ጦርነትንና ሰላምን አትርፎልናል ስለዚህ ከሁለቱ አንዱን መያዝ የእኛ እንጅ የእሱ እንዳልሆነ እውቀናል ። መምረጥና መቀበል የእናንተ እንጅ ያዘጋጀው አይደለም ስለዚህ ፈላስፋው በወደደው ሀገር ተከብሮ እንዲኖር ተደንግጓል ።

10ኛ/ በአጼው ዘንድ የታወቁት ነጋዴችና ጎሣዎች ከበላያቸው የንጉሠ ንጉሥ እንዲኖራቸው እንጅ የአንዱን ጎሣ ንጉሥ ሌላው ጎሣ በጦር ሃይል ወግቶና አዋርዶ በበላዬ እንዳይነግሥበት ነገር ግን በአጼው ትእዛዝ ያመፀውን ጎሣ ተዋግቶ ድል ካደረገ በኋላ የራሳቸውን ሰው መርጦ መንገስና ለአጼው በየዘመኑ የንጉሠው ንጉሥ ግብሩን እንዲከፍል ተደንግጓል ።

11ኛ/ አጼው ከእግዚአብሔር በታች በምድር የፈጣሪያችን እንደራሴ እንደመሆኑ መጠን በአባቶቹ ዙፋን ከወጣ ቀን ጀምሮ የተናገ

ረው ቃል ሁሉ ይፈጸማል ይሙት ያለው እንዲሞት ይዳን ያለው እን
ዲድን ቃሉ አንድ ጊዜ ከወጣ የማይታጠፍ እንዲሆን ተደንግጓል ።

12/ የአፄውን ጠላት አፄው በፈቃዱ እንዳይፈርድበት ነገር ግን በአስራሁለቱ ወንበር ዳኞች ተፈርዶ በአደባባይ እንዲሰቀል እንጅ በድብቅ እንዳይገደል ተደንግጓል

13ኛ/ የሕዝብ ጠላት የሆነውን ወንበዴ ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ሚፈርድበት የንጉሥ ጠላቶች የሆኑትን ሁሉ ከሕዝብ ተመርጠው በቀረቡ አስራ ሁለቱት አባውንት ቃል እንዲፈረድባቸው ተደንግጓል

ይህ ሕግና ትእዛዝ ለኢትዮጵያ ነገሥታትና ለሕዝብ አለቆች አዲስ ንጉሠ ነገሥት በነገሠ ጊዜ ይነበብላቸዋል ። ከዚህ መጽሐፍ ሌላ የአፈላሰ የግብፅና የሕግ መጽሐፍቶች አርባ አምስት ናቸው ።

አጼ አፈላሰ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ አቡነ ሰላማ ወአይን እግዚ እየተባለ የኢትዮጵያን ምድር በሰላምና በፍቅር በገዛ በ85 ዘመን መንግሥቱ በተወለደ በመቶ ሰባት አመቱ አርፎ በከተማት በአክሱም ከተማ ውስጥ በሚገኘው ከጺማ ታላቅ ሥርዓት ቀብር ተደርጎ ተቀ በረ ከእሱ ቀጥሎ በፈንታው ከግር ቱና የሚወለደው ልጁ አውማብ ብቶስ አጼ ሲራሀ በንጉሠበት ዘመን አሥር አመት ሙሉ በሀገር ላይ እሌቱት ሆነ ሰው በወጣበት መቅረቱ በየቦታው በየአርሻ ሙቶ ወገ ኘት ሆነ ዘመኑም አመተ ፍዳ ተባለ አጼ ሲራሀም በሁለት ላይ እንደ ተቀመጠ ሙቶ ስለተገኘ አብራሂሊዩስ የተባለው ታላቅ ልጁ አጼ በአፀያይ በንጉሥ በ17ዓመት ምስሮች ናፓታና መተው ወረፋት ንግ ሥቶ ሀገደኒ ፲፲ ሁለተኛኑትን ከአበት ቀጥሎ የንጉሡቹውን ንድዲት የሚባል ወራ ዲሰማ ወደግብፅ ወርዶ በዚህ ዘመን ሂክሰሶች እየ ባሉ የሚጠሩትን የራኩዲን ሥራዊት አጥፍቶ በናፓታ የኗኗ ሴት ልጅ ከንዳክስን (ቅንዳቅ ቅሰን) ሆንደኒ ሶስተኛ ብሎ አንግሿት ሲመለስ እን በራ በሚባለው በአመር ወንዝ ዳር -(ኒል) ድንገት ታሞ ሞተና በ ያው ቀበሩት ከእሱ ቀጥሎ ልጁ ወረደ ፀሃይ በ4699 ዘመን ከተቀ ጠረ አጼ ደንግሸ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በአባቱ ዙፋን ላይ ተቀመጠ ፀአጼ ደንግሸ ዘመነ መንግሥት ፍቅርና ሰላም መሬትም ፍሬን ሰጠች ነገሥታትም በደስታ ተገዙለት አጼ ደንግሸ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በ30 ዓመቱ ወንድሙ ታውደ ስለገደለው የበኩር ልጅ ሆንደር በ እለም በገድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በ4729 ዘመን ከተቀመጠ ነገሥ አጼ ለም በገአድን እስራውያን ፒያንኪ ይሉታል ። እሱም ንጉሠ ያልነበረበትን በኢድቶ ቢታኒስ በኖፍ በደስታ በሳይስ በመድኒዓብ በቀዳሚ

ማግኘት እንዲቀመጥበት አደረገለት ብዙ የአጭር ልቦለዶች እንዲያነብበት ታሪክ ነጋሪነትን እንዲለማ አባሉ ፡፡ አጼ አስምሮም በዘመኑ መንግሥቱ የሕብተቱን የንጉሠነገሥቱን ሀገና ሥርዓት ከማክበር በስተቀር ሰውን የሚያ ድሉለዩት ያለ የግፍ አስተዳደር አላደረገም በኢትዮጵያ ሃገሮች የሚኖሩ ነጋሥታትና የግብፅ አለቆችና መማክንት ተገዝተዉ በናፓችና በመርዌ ከተማዎችስ ቀብሮ የእንግሊዞችው ንጉሥ ሰማርያ በአዜብ የንጉሠው የዛጉዌ ዘር ዳሌው በቡባ እናቱያ የንጉሠው ገዳ (ከ፩) በየአፊት አመት ነበ በረከት ግብሬቻቸውን ያዘው መገብተው ያቀርቡለት ነበር እንጂ በዘመኑ መንግሥቱ የአመፀበት የለም ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ አጼ አስምሮም ተብሎ በንገሥ በ፵፩ ዓመቱ ስለሞተ በፈንታው ልጁ ተርሃቃ ታረክ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ አጼ ወረደ ነጋሽ ተብሎ በኢትዮ ጵያ ሃገሮች ላይ ነገሠ ተርሃቃም ሥራው የሙት ልጅ ተባለ አጼ ወረደ ነጋሽ በዘመነ መንግሥቱ እስከሚደርሱት ሬዩብ በሀገር ላይ ሆነ እርሱም ግብፅን ወደ ኛብያካን ገድሎ ፊርንትንን ያዘ አጼ ወረደነጋሽ በንገሥ በአርባ ስድስተኛው አመት ላይ የአንበጣ ዘመን ሆነና አንበጣ አገበ ጣውን የሚበላው የዛፍ ቅጠል ሣርና ሰለአጣ ተበላለ አይጦችም በምድር ላይ ፈሉ በምድር ላይ ታላቅ እልቂት ሆነ ከረሃብና ከበሽታ የተነሳ ሕዝቡ የሚባለው አያጣ የሰበሰውንና የሚተናኘበትን የከብት ቆዳ በላ በዚህ ዘመን ብዙ ጉዳዮች አልቀው ያለፉ ቀሩ አጼ ወረደ ነጋሽ በንገሥ በ፵፰ አመቱ በግብፅ በናፓና ሰለሞተ ልጁ አመስያ በፈ ንታው አጼ አርድአሚን ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በኢትዮ ጵያ ሀገሮች በ፬፻፴፰ ዘመን ከተቆጠረ ነገሠ ፡፡

አጼ አርድ አሚን ሲነግሥ ከዓር እስከዓር ያለው የኢትዮጵያ ምድር በለምለም ዛፍ ተሸፈነ ዛፎችም ፍሬያቸውን ሰጡ ሰውም እም ባቱን አመስግኖ የሚኖር የጋማ ከብት ግልገሎች የቀንድ ከብት ጥጃ ዎች በሜዳ ላይ ዘለሉ በምድር ያሉ እንስሳትና አራዊት ከጥጋባ ቸው ብዛት ቀንና ሌሊት እሽካኩ ከዱር ወደሜዳ ከሜዳ ወደ ዱር እየተመላለሱ ያዘሉና ያፈረጡ ጀመር ሰውም በአለበት ሀገር ሆኖ የጤና እንጀራውን እየበላ የወይን ጠጁን እየጠጣ ከበግ ጠቦር የተ ሰራ በርኖሱን ለብሶ ከተልባ እግር የተሰራ የሀገር መጐናጸፊያውን ተጐ ናጽፎ ከጥጥ የተሰራውንልብሱን ለብሶ በደስታና በሰላም ተቀመጠ እንጂ ከአንድ ሀገር ወደ አንድ ሀገር አልተሰደደም ከሚባለው አትርፎ ለቤት እንስሳዎች የተረፈውንና የሰንደሉውን ፍሬ ያበላ ነበር ፡፡

እንደዚህም ሆነ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዎ በአፍርና በሰሜናዊ ቅሉቅ የምድር መናወጥ ሆነ በዚህ ምድር መናወጥ የተነሳ ታላቅ

ባህር(ውቅያኖስ) የኤርትራን ባህር ሞላት ኢዮሞያስንና ኢዮዓምን አጥ
ለቀለቀት በዚሁ ዘመን በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበረው አርእድ
አሜን ለይሁዳ ንጉሥ አዝያን ለእስራኤል ንጉሥ ለወልደ ኢያኦስ ልጅ
ኢዮር ብለም የመጀናኛ ደብዳቤ ጽፎና በአምስት መቶ ሰረገሎች
የዋብስና የስንዴ ፍሬ የበለስ የወይን ጣፋጭ አስጭኖ ላከላቸው እንስሳም
እምላኪዎቹን እመሰግነው የፍቅር ደብዳቤ በነቢዩ በአሞጴ አስፈሡ
ላኩ የእስራኤል አምላክ የኢትዮጵያን ህዝቦች ባረከ የአጼ አርእድ አሜን
ዘመን መንግሥት እስከሚያልቅ በምድር በረከት ሆነ አጼ አርእድ
አሜን በነገሠ በሃያ አምስት አመቱ የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ነቢዩ
ኢሳይያስ የአሞፅ ልጅ ወደሶምቢር ወረደ በዚያም ወረደ ንጋሽ ተብሎ
በንግሡው በቴርሃቅ ዘመነ መንግሥት የጦር መሪ የነበረ ነኝው ከሠ
ረው የሚባል ወሬ ሲሰማ አስራ አምስት ሺህ ባለሠረገላ ተዋጊ ጦር
ልኮ የተባለ ሠራዊት ከታሠረው አስፈቱት ደካሙንም አስረው ወደ
አገሩም አመጡት አጼ አርእድ አሜን ደካሙን የፈርኦንንትን ማለ
ረማ እንደያዘ ታሀታቋ ማብለን በመምፈስ ላይ ተቀምጦ እንደገና
በአከሱ አማላጅነት መልሶ ላከው ።

አጼ አርእድ አሜን የቴርሃቅ ታናሽ እህት መገዘሴቢያ የምትባ
ለመን በስሙ አሜን ሪትስ . . .ሰድስተኛይቱ ሀገደሴ የናፓታ ንግ
ሥት ብሎ በዓእዓይ ማብቷ እንገግሥት እሉዋም ሳባ ተካን ገድላ ደካሙን
ብቻ አንባች በተባይድ የታብና የናፓታ ንግሥት ሆነች እሉዋም የአ
ምላከዋን ቤተመቅደስ በአቴር ወንዝ ዳር አሰራች ይሄም ወንዝ
የማዱን እግር ነው ከመገዘሴቢያ ቀጥሎ እንግዳ፣ አንበሶፓ፣ እንሰጣሚያ የሚ
ባሉ በፍቅር እንደሰሩዋ ነግሰዋል ነቢዩ ኢሳያስን የአሞፅ ልጅ የእግዚአብ
ሔር ሰው በአከሱም አመት ከተቀመጠ በኋላ ወደኢየሩሳሌም ለመጠ
ረድ አጼ አርእድ አሜንን ፈቃድ ጠየቀው ንጉሠ ነገሥቱም ፈቀ
ሳሌም ቤተመቅደስ የሚሆን ብዙ ከወርቅና ከብር የተሠራ የፈለስ
ሰን መቶ ሺህ ዳሪክ ሰጠው ይኄውም እስር ሺህ መክሊት ነው ሁለ
ቱም በሰላም ተሰነባብተው ተለያዩ ።

አጼ አርእድ አሜን 30-(ሰላሳ) አመት በእባቱዋ ዙፋን ተቀምጦ
በአከሱም- በአከሱም ከነገሠ በኋላ ከፈረስ ላይ ወድቆ ስለሞተ ታላቅ ልጁ
ኢልማልዱን እንደምስርና እስር ታኢታመን እንዲ እሱማውያን አበ
ውንን አጼ አ/መን አሜን ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ መሲ ጸ እግዚአብ
ሔር ተብሎ ነገሠ አጼ አመን አሜን የሃይልሰው ከጀግንነቱና ከፍቅ
ነቱ የተነሳ እብ ካሪ ይባላል በሌላ በኩል የናቱ ወገኖች ከእስራኤል እም
ላክ ይልቅ የሞአብንና የአሞንን የሞሰረንም አምላክ ይከተሉ ስለነበር

እሱም እንደሱ እየሄደ ሳቢኤል ቢሴል ሰቢኤል ጋቁራ ሰቢኤል ፋቁራ ሰቢኤልጋውል ይሰግድ ነበር ስለዚህ በእሱ ዘመን ፈራርሶ የነበረው ማምለኪያ እየድ ታደሰ በዚሁ ዓኖፍ ማምለኪያ ቦታ ሄዶ ሳለ በህ ልሙ በቀኝ ክንዱ አንዱ አባብ በግራ ክንዱ አንድ ሲወጣ አይቶ የእ ምነቱ ካህን ይህን ህልም ተርጉምልኝ ብሎ ቢጠይቀው ሁለቱ እባ ቦች ኢትዮጵያና ግብፅ ናቸው ከክንድህ መውጣታቸው ሁለቱም ሀገ ሮች ይገዙልሃል በክንድህ በሃይልህ ያድራሉ የምትለውንም ሰምተው ያደርጋሉ ብሎ ተረጉመለት

በዚህን ጊዜ አጼ እሙን አሚኔ በህልሙ አፈታት ተደስቶ ለካህ ኑና ለሠራዊቱ ትልቅ ግብር አደረገ በኖፍ የሚገኘውን የመሪጀን ቤተመቅደስ አሠራ ለካህናቱም ብዙ አልባሳትና ወርቅ ሸለማቸው እነሱም የብርሃን ልጅ ለዘለአለም የሚኖረው ንጉሥ አሉት ።

አጼ እሙን አሚን ከኖፍ ቤተመቅደስ ተነስቶ ወደናፓታ ሄደ ከዚህም በደሴታና በፍቅር እንደ ሰንበተ ከናፓታ ተነስቶ ኤሌፋንቲን ኤልፋንቲብኝቶ ቴብ በሰላም ገባ በቴብ የሚኖሩት ህዝቦች ሴትና ቀን እልልታና የደስታ ጩኸት እሰሙ ከዚያም ከቴብ ወደ መምፊስ ደርሶ ጠላቶቹን አጠፋ በጌታህ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለጌታህ ስካሪስና ለፓስ ክት መስዋእት አቀረበ ።

በመምፊስ ሳለ ጠላቶቹ ሁሉ መጥተው ምህረትን ጠየቁ የእንተ ብሮች እንሆናለን ሲሉ በአንድ ቃል ተናገሩ እሱም እምላኩን አመስ ግኖ ያለመውም ህልም ደረሰ ለኢሚንሪትስ ንግሥትም የወርቅ ዘውድ ደፋላት ።

አጼ እሙን አሚንም የምስርን አለቆች ሰብስበው ሹም ሽር አደ ረጉ የበላይ አለቃ የአረብ ነገድ የሆነውን ካኪንን የፓስቲትን ሹም አለቃ አደርጉ ሾሞ ወደ የሃገራቸው በሰላም መለሳቸው ።

አጼ አርእድ አሚኔ አባቱ የሾመውንና በክብር በመምፊስ ያስ ቀመጠውን ኒካውን የቴብና የናፓታ ንግሥት አሚኔ ራትስ ገዐ በረክ ትዋንና ግብሩዋን ይዞ ስትመጣ ባለመምጣቱና ከጠላቶቹ ጋር ሆኖ በመውጋቱ ገደለው እንደሚገኘኝ የአጼ እሙን አሚን መምጣትስምታ ሚኒሱ አሚን ራትስ ኒካውን ገድላ ጭንቅላቱን በማህደር ወስዳ ለአጼ እሙን አሚኔ ስላሳየችው ግዛቱዋን እንድታስፋፋ ዘውድ ደፍቶ እንደ ገና አነገሣት ይላሉ እሱም ወደአከሹም እንደተመለሰ ከመምፊስ የኒ ካው ልጅ አቱማሃ ወደነነዌ ሄዶ ከአሶር ንጉሥ አሱርባኒፓል ጋር

ተገናኝተው ከእስር ባኒያል ወራሪዎቹ ጋር ሚጠብሰያ እናቱን አባሮ በእ
ብቻ ዙሪያ እስሞሚ ፈርሶ ተብሎ ነብሰ የእስር ወታደሮችም ተባበ
በሊተመግኘነት የነበረውን እታወቢዎት የሙሉቶችንም አፈራረሱ
ወርቅና በወርቅ የተጠለፈ የእንበሳ ቆዳ ለምዶች ወደንነዊ ተሜኑ
ሀገሬነቶም ሁሉ እፈሳቸውን ፈጠፈጡአቸው መኳንንቱም በሰንሰለት
ቃለረው ወደእስር ንጉሥ እሰር ባኒባል በጥያል ሰብስበው መስዶሉ
እቸው ንጉሡም ቆዳቸውን ገፎ በሃውልቱ ስር ላይ እንጠፈው ።

እጁ አሙን አሚን እከሰም ላይ ሆኖ በታሜቅ ዙፋን ላይ እንደ
ተቀመጠ የእስራውያን ወታደሮች በንጉሣቸው እሰር ባኒባል ትእዛዝ
በመምረስ መሞልስ ንጉሥ አብማዮድ እየተመሩ የሽማቸውን የዘዘብ
እስቶች ገደሉ ቲብንም አታጠሉዋት የቢተመቅደሷን ንብረት ከር
ፈው አፈራረሱት የሙሉቶችንም ቢታትኑት የሚል ወሬ ደረሰው ። በዚ
ሀን ጊዜ በራሱ ላይ የነበረውን የወርቅ ዘውድ መርጦ ጣለሙ ከዚ
ያም በየሃገሩ ያሉትን የዳግማዊዎቹን የሲባሆን የኢትዮጵያን ነገሥታት
እዮርጋም ዕርያንም ሰማርያንም ለመመረር ጥሪ አደረገ ከምስራቅ
እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያለው እሰ ቃና የአለቃ መሬ ከሙ
ራዊቱ ጋር መጥቶ በእባይ ዳር ተሰበሰበ ብዛቱ እንደአንበጣ ሰራዊት
ቅልጥፍናው እንደተንጋጋ ነበረ በአይነ አድቶ ቆጥሮ ለመድረስ እይ
ቻልም የመሩን ብዛት በማየት ለመናገር ምላስ ያዳግተው ነበር ።
ሆኖም ግን እሙን አሚን ናፓታል ላይ እንደደረሰ በንፋስ በሺታ በሰ
ሞቱና ብዙ ሚሊዮን የሆነ ሠራዊት በዚሁ በሽታ በሳለቀ ከሞት የተ
ረፈው ወደየሃገሩ ተመልሰ በዚሁ ዘመን እስራኤሎችን ናቡ ከደነጾር
ወር ወደባቢሎን ባሪያ አድርጉ እናልሶ ወሰዳቸው እጁ አሙን አሚ
ንም ግብጽንና ኢትዮጵያን ሲገዛቸውም እንደ አድርጉ ሰላስ ዘመን
39 ዓመት ከገዛ በኋላ በዚሁ በናፓታ ሙቶ በእስራው ቤተ መቅደስ
ከተቀበረ በኋላ የኢልሳልዩን - እሙን አማኒአድ ቆማየዋን በ4877
ዘመን ከተቀመጠረ ሰው መንግሥቱን ቆማኢያን ተብሎ በኢትዮጵያ
ምድር ላይ ነገሰ ተማ ልዑን የሚሊሉት እሉ እጁ ቆማሰደድም በሃያል
ከመርዌ እስከ ሉባ - ሊቢያ ከሳባ እስከ ባንዚ ድረስ ባሉት ነገሥታት
ላይ ሃያ ዘጠኝ አመት ገዙቶ ሞተ በፈንታው ልጅ ባስልዩስ እጁ
ገድረት ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በ4906 ዘመን ከተቀመጠ
ነው ።

እጁ ገድረት በነገሰ ዘመን ትልና እሡር ዝገብ አንበጣና ደምብ
እይተና ጃርት ጠቶ ሰማይ ዝናምን ምድር ፍሬን ሰጡ በአለም የሚ
ኖሩ ህዝብ ሁሉ ፍቅርና ሰላምን ደህንነትና እድሜን የአህል ፍሬን

ረድኤትን አየ ሁሉም ማቱሳ እንቅልፍን አገኙ መሬትም በባሕ አመት ከመርነት አረፈች በዚሁ ፍሬንና ረድኤትን አየ ከሰባ አመት በኋላ ግን ገዶረት ሹሉቅንም ሚጉማንም ይብልቅ ህዝብ የሆኑትን አሁስንም አረብንም ፍልስጤምንም ሚከሮቢያንንም ሁሉ አለቆችንም ንጉሶችንም ከአስገበረ በኋላ መልካም ግዞትንና ረጅም እድሜን አግኝቶ በነገሰ በሰባ አመቱ በተወለደ በዘጠና አምስት አመቱ አረፈና በአክሱም አደባባይ ተቀበረ ።

በፈንታው ልጁ አውጥጥ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ወሰደ እግዚአብሔር አጼ አብረሃም ተብሎ በ4976 ዘመን ከተቀበረ ንጉሠ አጼ አብረሃ በአሁሳውያንና በረሳሰያን ዘንድ ሴራክ ይሉታል አጼ አብርሃ በዘመኑ ከመከሊትና ከድሬክ ገንዘብ ሴላ ድሪ የሚባል ከወርቅ ከብር ከነሃስ በስሙ ገንዘብ አሰርቷል ። በዚሁ በድሪ የአረብና የአሶር የባባ ኑጋዶዎች ይገበዩበት ነበር ። ዘጠነኛይቱ የናፖታ ንግሥት እንስጣጥያ ብዙ ዘመን ከገዛች በኋላ ስለሞተች የጌትማር የምትባለውን ግብጽዊንት አጼ አብርሃ አግብቶ አስረኛይቱ ሀንደኬ ተብላ በናፖታ እንድትቀመጥ አደረገ ።

ንግሥት የጌቲማር ከአጼ አብርሃ ፒያን ወለደች ፒያን ማለት በሱባውያን አውነተኛው ጌታ አንተነህ ማለት ነው ፒያን በተወለደ በአስራአምስት አመቱ አጼ አብርሃ 42 (አርባ ሁለት) አመት ከገዛ በኋላ በወባ በሽታ ታሞ ሞተ በፈንታው ልጁ ፒያን ጊር አጼ ዘዋሬ ንብረት ተብሎ በአክሱም ሁቶንና በናፖታ የንግሥት ወንበር ላይ ተቀመጠ ከዚህ ቀጥሎ ፒያንኪያኖ አጼ ዘዋሬ ንብረት ተብሎ እንደ ነገሠ ከሥዕሬ ሲራክ አክሱማይ የኖትር ኢትዮጵያ ብሎ በሰየምኩት መጽሃፌ እሰፋለችኋለሁ ። አዘጋጁና የዚህ ታሪክ አሳፊው መሬራብ ኢኢም በላይ

## ምዕራፍ ዘጠኝ

የቢያምጊር አጼ ዘዋሬ ንብረት ዘመን መንግሥት በ2ኛ ደቱ ሆን ደኪ ንግሥትና በእስክንድር ጋብቻ ናፓታ ከአክሱም መንግሥት እንደተነጠለ

በላእላይ ግብፅ ዛሬ ጃበል ባርካ በሚባለው ሃገር ናፓታ የምትባል ታላቅ ከተማ ነበረች ይችም ከተማ የቆረቆረቻት የኢብነልሃኪም - ምኒልክ እናት ሞና መቀመጫዋ አቢብ ላይ የአረብና የሳባ ንግሥት የሆነች እትም ነበረች ። በዚች ከተማ ላይ አጼ ኢፈላስ አዜንአለም የተባለው ሆንደኬ እየተባሉ በምስሮችና በአረቦች ላይ የሌቶች ንግሥታት እንዲቀመጡበት ይንግግሥዋል ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ሆንደኬ ተብላ የነገሰችው አክስሱ አዜት ሁለተኛ ደቱ ሆንደኬ ኔእ ሶስተኛ ደቱ ሆንደኬ ቅንደቅስ ፋኛ ደቱ ሆንደኬ ሰማርታ ፯ኛ ደቱ ሆንደኔ ካሺታ የቱርሃቅ እናት ፩ኛ ደቱ የካሽታ ልጅ መገለብያ ሆንደኬ አሚን ሬቅስ ትባላለች ይችም በጣም ከመልከዋ ከሀያም ግብቱዋ የተነሳ አለም ይብረከትላትና ያደት ሁሉ ነፍሱን ይሰጣት ነበር ይሄውም መገለብያ በምትባልበት ጊዜ አጼ እርእደ አሚን የአባቱን እህት አግብቶ ወልዶላት ሳለ ምቢሬዊ እካሙን እዋ ቅራ ሳግባው ብላ ጠየቀችው እሱም ምንም ቢያፈቅራት ጥያቄዋን ከፍቅር የተነሳ እንቢ ሊላት አልቻለም ስለዚህ እሺ ብሎ እካሙን የፈርእንነትን በሙድ ብቻ የመሥራቱ ንጉሥ አሚኔ ሬቅስ ስድስተኛ ደቱ ሆንደኬ ብሎ የናፓታ ንግሥት ብሎ አንግሶ ቀኑዋ እዚያ የኒ ከስቦ ንጉሥ የነበረን ሳባ ተካን አግብታ ስትኖር በመጨረሻ ከእ ምሳ ባሏዎቹዋ ጋር ገድላ ጀነውን አግብታ ብዙ ቀን በቆየ በኋላ ጀካሙ እንደዋተ እንደሄና ሁለት መቶ አርባ አምስት ባሌዎች ነበሩዋት ይባ ላል ። በግብፅን ዳር - እቱርእው ታላቅ ቤተመቅደስዋን አሠርታ ንግሥት በሆነች በመቶ አንድ ቤተወለደች በአንድ መቶ ስላሳ አንድ ዘመን እረፈች ከእሱዋ ቀጥለው ሶስት ሴቶች ነግሠውዋል ። እንዚህም እን ጥያ ፣ እንስጥያ ፣ እንስጥጥያ የፍቅር አምልኮት ይባላሉ ። የእንስጥጥያ አገልጋይ የነበረችው የኔትሜኔር አስረኛ ደቱ ሆንደኬ ተብላ ነገሰች አሉ ዋም ከአጼ አብርሃ ፒያንን ወለደች ይችም ሴት እመቤትዋ መገለ ብያ ልጆች የፍቅር አምላኮች ተብለው እንደተመሰከሩ እሱዋም በሳይበ በለዶታ የምሁሪት እናት እየተባለች እስከዛሬ ድረስ ትመለከላች ። ልጅዋም ፒያን ፒያንጊር ተብሎ አባቱ አጼ አብርሃ ከእርሱ ቀጥሎ



ዲያግኒስ በአምሃራ፡ ጣሰ የተደረገለት አቀባበል

ፒያኖን እንዲያጎናጽፍ ተናግዘለት ሲሞት በጣይቱና በደራሲ በሚኖሩ
ኢዮ ወራሾቹ ታጅቦ ከናዖታ ወደአክሱም መጥቶ በ5018 ዓመት ከተ
ቆጠረ አጼ ዘዋሬ ንብረት ንጉሥ ነግሥት ዘኢትዮጵያ ወምስር ተብሎ
ነገሥ ሲነግሥ የአስራ አምስት ዕመት ወጣት ነበረ ፒያን እውነትኛ
ጌታ ሲሆን ፒያንጊር ማለት ደግሞ የአራት ማዕዘን እውነተኛ ጌታ
ማለት ነው ስመ መንግሥቱ ዘዋሬ ንብረት ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚጠራ
ፒያንጊር ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በናዖታ የሚገኘው ባለስረገላ
ዙፋን የሚረሊሚን ልጅ ይባል ስለነበር ህዝቡና ወራሾቹ በፊት ሲሰ
ግዱ ሜሪሊሚን ሜሪአሊን ይሉት ነበር ሃይማኖቱ እንደምስሮች እንጅ
እንደአበ ሳውያን አልነበረም ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ዘዋሬ ንብረት በንጉሠ በአስረኛው ዘመነ
መንግሥት በከርናቅ የሰማይና የምድር ፈጣሪ አሚኒ ወይም አሞን
የሚባለውን የአማልኮት ቤተመቅደስ ማሰራት ጀመረ ሥራው በተጀ
መረ በዛሬው ሽምጺር በጥንቱ ካርናቅ መንደር በአስራአንድ አመቱ
አበቃ ይሆንም ቤተመቅደስ ካርናቅ ላይ ሊያሰራው የፈለገበት በዚሁ
ከአንድ ጀህ ዘመን በላይ ሲመለከበት የነበረ በመሆን ነው ካርናቅ
ማለት ትርጉሜው በሱባ ቋንቋ ፈላስፋ የሆነው ትልቅ መሪያ ነው ይሄ
ውም የጥንት ነገስታት አውቀታቸውን የሚገልፁበት ሃውልት ቀርፀው
ለአሞን ቤተመቅደስ ጥለው ይሄዱ ነበር ። አጼ ዘዋሬ ንብረት ግን
ቤተ መቅደሱን በሚገዛቸው ጉጣዎች ቁጥር አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ደረጃዎች በሥሩ በሚመሩ ነገሥታት ቁጥር በመቶ ሰላሳ አራት
እምዶች ኢትዮጵ ከአፈጡ ፊደል የቀረበና የተመሳሰለ አጼ አሚ
ንሆ ከአኛኛለው ፊደል አርቆ በራሱ አስቀሳስቦ አዲስ ፊደል አዘጋ
ጅቶ በማድማዳውና በአምዱ ላይ አስቀርጾ ማምለኪያውን ቅርፅ አስ
ቀመጠበት ብዙ ጊዜ ካራ ይባላል ካራ ማለት ብርሃን ተለየልን በሃይ
ብርሃን አሞን መጣልን ማለት ነው ።

በማድማዳውም የተጻፉት ቃላቶች የሚሉት በኤንደራሲ አስፐርታና
በሆዛብ ዘንድ ዘለአለም እምናር ፒያንጊር የጌት ሜር አሚን ልጅ የዓ
ብሰና የሱብ የኢትዮጵያም ሃገሮች ንጉሥ ነገሥት እኔ በቱም እምላክ
(በሰው አምሳል) ከአማልክት የሰረፅኩ ንጉሥ ነኝ የጌትሜር አሚን
የሃገረ ንግሥት ከፍቅር አማልክቶች ከመሀልብሄ ከአንጥያ ከአስማርያ
የምትባለዋ የፍቅርና የምህረት አምላክ ናት በሌሰዋ ውስጥ ያለ በ
ሃይ ብርሃን መጥቶ ያደረ ብርሃን ነው ይህም ብርሃን እኔን ወለደ እ
የናንተ ብርሃን ነኝ ደግ ነኝ የተወደድኩ ነኝ እያለ በማድማዳዎች ላይ

በምሺር(ምስር) ቋንቋ አጽናፈብታል ይኼውም የሆነ በንጉሥ በሃያ አንድ ኣመቱ ነው ።

በመውጫው በኑሉ ባለው የድንጋይ ሰሌዳ ደግሞ በራሱ ፊደል በአሶር ቋንቋ እንዲህ ሲል ጻፈበት በኦቶር ከተማ እስከዛሬ መግቢያ ያሉ ያሉት የታፍኒቅሃት የሞኒት የካሃሰቢን የሃፒና የመምፊስ ወታደሮች ወደናምሩድ ግዛት ወደሄርሞ ፖሊስ ከተማ ኼዱ ስውንም ከብቱንም ማርኩ ለአሞን ቤተመቅደስ አምጥታችሁ ሰው ቲብንም ውጉን እንጉዛም ያለውን አጥቶ አምላካችሁ የሚሻችሁን ሰው ብሎ ዕር እስቀምጦታል በእደብባይ መካከል ያለው የድንጋይ ሃውልት ላይ ደግሞ ተብብሆና ምክርህ እኛን ሰራዊቶችህን ትመራለህ በእካላችን ውስጥ ሆኖ ለንሆአችን ስንት ነው ተግችንም ያረካል ጽል አድራጊው አንተ ንጉሥ አምላክ ነህ ተብሎ ተቀርጾአል ።

እንደዚህ ሆኖ አጼ ዘዋሬ ንብረት ግብፅን ሶርያን አሶርን ባቢሎን ሞአብን ወር አስገብሯል ። ሮሆንና ኬሮንንቋንም ጉብኝቶ የአሞንን ቤተመቅደስን አሰርቶአል አጼ ዘዋሬ ንብረት በሚሄድበት ሃገር ሠራዊቱን ካልተዋጓዋቸው ቀድማችሁ እንዳትወጉ የገበረን አክብራችሁ ተቀበሉት ከማለት በስተቀር በግድ አስገብሩት ደርባችሁ ውጉት ብሎ አያውቅም የሰውን ደም በከንቱ ማፍሰስ ሃብትን መማረክ የማይወድ ደግ አባት ነበረ ጠላቶቹ ሊወጉት መጥተው መልካም ቃል ከመመለስ በስተቀር ክፉ ቃል ከአፉ አይወጣም ነበር አጼ ዘዋሬ ንብረት 41 አመት ታላላቅ ሃገሮችን አንድ አድርጐ ከገዛ በኋላ በአምስ ስድስት አመቱ ድንገት ታሞ ስለሞተ በመርዌ ተቀበረ መንግሥቱን የእህቱ ባል እንደለሉች ቢት ልጁን ኛርናሮትን ያጣባ ካሺታ በመርዌ ነገሰ በዚህን ጊዜ በአክሱም የመጀመሪያ ሚስቱ የሚወለደውን ሰይፉን ንጉሡ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ አጼ ዣን ሸዋ ብለው በአክሱማይ ዙፋን አንግሰው አስቀመጡት ካሺታም ለአክሱም አጼ አልገብርም ብሎ የባለ ንጉሥ አፈርካራ ሄዶ ገደለው ግብፅንና አባን ሸባኬ ለሚባለው ለአፈርካራ ተሰጠው በዚህ ዘመን የፒያን - (ፒያንኪ) እናት ስለሞተች ፒትሃር የምትባለው 11ኛ የናፓታ ንግሥት ህንደኬ ተብላ ተቀመጠች።

አጼ ዣንሸዋ በንጉሥ በሰላሳ ስምንት አመቱ ስለሞተ ሪመሃይ ንጉሰ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አጼ ደንቀዝ ተብሎ በ5097 ዘመን ከተቆጠረ ነገሰ በአጼ ደንቀዝ ዘመን መንግሥት ታላቅ የምድር መናወጥ እረሃብና ቸነፈር የንፋስ ሽታ መጥቶ ብዙ ሚሊዮን ህዝብ አለቀ ኮከብ ወደታላቁ ባህር ወድቆ ሲከሰከስ ዕያ አጼ ደንቀዝም

ማንም በመንግስቱ የተነሳ ጠላት ሳይኖረው በሰላ አመት ገዝቶ ሞተ በፈንታው ልጁ ሃንዲ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ አጼ ሞዚባ ተብሎ ነገሠ በአጼ ሞዚባ ዘመን መንግሥት ከባህር ዳር እስከ ባህር ዳር መሬት ፍሬን ሰማይ ዝናምን ሰጡ የእስላም ህዝቦች ተደሰቱ ጠፍቶ የነበረው ሥልጣኔ እንደገና ብቅ አለ ብዙ ቤቶች ታነፁ ።

አጼ ሞዚባ ኪመክሊትና ከዳሪክ የተሰጥ የመሬት ፍሬን እንደ ያዘ በእንጥረኞች አዲስ ድሪ የሚባል ገንዘብ አሰርተዋል እንደዚሁም ቀዳዳ ያለ ራያ የሚባል ከወርቅና ከብር የተሰራ ገንዘብ አስቀርጸ እምልኮቱም እንደሊፍላስ እንደአባቱ ሪመሃይ ነበር እንጂ የግብ ፃን እምልኮት አይቀበልም ነበር ። አጼ ሞዚባ በነገሠ በሁለተ ኛው ዘመን መንግሥት አስራአንደኛይቱ ሀገደኤ ፒተሃር ስለሞተች በፈንታዋ 2ኛ/ ቅንዳስ የምትባለው አስራሁለተኛ ሀገደኤ የናፓታ ንግሥት ተብላ ነገሰች ይችም ንግሥት በድል አድራጊነቱ ለእስከ ንግሥት ተብላ ነገሰች ይችም ንግሥት ለባቢ ንድር ሚስት የሆነችና ናፓታን ከአክሱም መንግሥት ነጥላ ለባቢ ሎን መንግሥት ያሳለፈች ናት ።

ታሪኩ እንደዚህ ነው ታላቁ የእስም አባት የተባለው አፈላስ በና ፓታ የሴት ንግሥት እንድትቀመጥበት ያዘዘውን በ2ኛይቱ ቅንዳቅስ ንግሥትነት ከናፓታ ወደመርዌ ተዛወረ ።

በናፓታ ሀገደኤ ንግሥት ዘናፓታ እየተባሉ የነገሱት

1ኛ/ አዜት የአክሱማይ አክሰት
2ኛ/ ደደ
3ኛ/ ቅንደቅስ
4ኛ/ ሰማርታ
5ኛ/ ካሺታ የቲያርቅ እናት
6ኛ/ መገዘልቢያ አሚንሪትስ የተባለችው የፍቅር እምላክ የሆነች
7ኛ/ እንጥያ የመገዘልቢያ ልጅ
8ኛ/ እንስጥያ የእንጥያ ልጅ
9ኛ/ እንሲጣዋያ የእንስጥይ ልጅ እነዚህ አራቱ ከቀንጆናቸው የተ ነሳ የታመሙ በመልካቸው አይቶ ከሀመሙ ይድን ነበር ይባላል ።
10ኛ/ የኔት ሜር የሮያን እናት
11ኛ/ ሃትሃር የኧርማኪስ ሚስት

12ኛ/ ዳግማዊት ቅንዳቅስ በናፓታ የመጨረሻዋ ሆንደኬ ንግሥት እንደዚሁም ሆነ በ5144 ዘመን ከተቀጠረ ከፊልጶስና ከኦሎምፒያ በመቄዶንያ ከተማ በፔላ እስክንድር ተወለደ እስክንድርም አሪስቶት ከሚባለው መምህር እየተማረ አደገ አሪስቶት እንደ ሌሎች አስርጣጣሊስ የሚባለው መምህር እስክንድርን ከአስተማሪዎቹ ከሆሰም ተቀባይነቱ የተነሳ ይወደውና ጊዜውን እሱን በማስተማር በመምከር ያሳልፍ ነበር ። እስክንድር ከአስተማሪዎቹ ሌላ ጀግና ደፋር ወጣት ነበር ከእለታት አንድ ቀን በአደባባይ ያልተገራ ፈረስ በአባቱ ፊት ጉብዝናቱ ለመጋለብ ሞክረው አቅቶአቸው ሳለ እስክንድር ተመልክቶ ማልገል ፈረሱ ወደአለበት ሄዶና ፈረሱን በእጁ ዳበሰው ከዚያም ከፈረሱ ዘሎ ወጣበት ፈረሱም ሰው ወጥቶበት አያውቅም ነበርና ይዞት ሮጠ ከዚያም ንጉሡ አባቱ ፊሊጶስና ህዝቡ ፈረሱ እስክንድርን ከደንባራነቱ የተነሳ ገድል ላይ ይጥለዋል እያለ ሲጨነቅ በትልቅ ሥጋት ሲጠብቅ እስክንድር ፈረሱን በማለማመድ አድክሞ ይዞት ብቅ አለ ከዚያ ከፈረሱ ወርዶ ወደአባቱ ፊሊጶስ ሲሄድ አባቱም ጀግንነቱን አመስግኖ ለአንተ መቄዶንያ ይጠብሃልና ፈረስ የምትጋልብበት ሌላ ትልቅ ሃገር ግባ ማለት ነው ብሎ ወዲያውኑ ዙፋኑን ለቆ ለእስክንድር ሰጠው በዚህን ጊዜ ለአባቱ የቲብ ከተማ ሁለተኛይቱ ማለት ነው አንዝዛልሁም ብለውት ነበርና እስክንድር ሄዶ አስገበራቸው የአባቱን ጠላቶችም ፈጽሞ አጠፋቸው ከዚያም የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ ግብሩንም ወር መቅደንያንም ሊወር ሲመጣ እስክንድር ተዋግቶ መለሳቸው ከዚያም ወደ ሳያደር ፋርስን ወሮ ለራሱ ግዛት ለማድረግ ተነሳ ግብጾች በፋርስ ጎብቶው የነበሩትን ተዋግቶ በድል አድራጊነት ፈንቄ ሄዶ ጢሮስን ተዋግቶ ያዘ ለራሱ ግዛት አደረገ የግብፅንም ህዝብ ከፋርሶች ግፍና በደል የተነሳ እስክንድር በደስታና በእልልታ ተቀበሉት የአሞንን ካህናቶች ትልቅ ግብር አድርጉ የሊብስና ከወርቅ የተሰራ ፅናፅ ከፋርሶች ወታደር የተማረከው ሰጣቸው የናፓታ አስራሁለተኛይቱ ሆንደኬ ንግሥት በዚሁ ግብር ላይ ተገኝታ ታላቅ ክብርና የወርቅ ዘውድ ደፋችለት የራኩዲ ህዝቦችም የተለያዩ የወርቅ ጌጦች እያመጡ ገፀ በረከት አቀረቡለት ራኩዲ ይባል የነበረውን ከተማ በስሙ እስክንድርያ አለው በዚህን ጊዜ በአክሱም ንጉሡ ንጉሥት ዘኢትዮጵያ የሆነው አጼ ዋዜብ በነገሡ በአስራ አንድ አመቱ ወደ አዜያ ወርዶ የእስክንድር ሰራዊትና የአጼ ዋዜብ ጦር ሁለቱም ለወርነት እንደተዘጋጁ በመካከላቸው ንግሥት ሆንደኬ 2ኛይቱ አስታራቂ ሆና በሁለቱ መካከል ስለቆመች ናፓታ ቴብ ታህታይ ግብፅ ለባቢሎን ለጊዜው

ለእስክንድር ሆነ የናርታ ንግሥት ህንደኬ እስ
ለመቄዶንያ ንጉሥ ለእስክንድር ከሶስት መቶ ሰልሳ ሚስቶች
ፊሁስተኛይቱ ቅንዳቅስ ለእስክንድር ሚስቱ ሆናለች ። በእክሱም መንግሥትና በመ
ጺማሚቷ ቅንዳቅስ ሚስቱ ሆናለች ተመስርቶ የጹዋ ጦር ሠራ
ቄዶንያ ንጉሥ መካከል ፍቅርና ሰላም ተመሥርቶ ለእስክንድር ቀስ
ቺትን ከተለያዩ ጉብኞች ሃያ አንድ ሽህ ይበላል እስክንድር ለእክሱም
ሠው ለንዚህ አሲታቸው ከሲንቀስ ደብሏል እስክንድር ለእክሱም የሆ
ንጉሡ ንግሥት ለእጹ ዋዚብ አንድ ሽህ የመቄዶንያ ተወላጆች ከናርታ ተንስተው
ኑትን ጀግና ተዋጊ ጦሮችን ስትተዋል ። እንዚህም ቀዝባም ልዩ ሃገር መርጦ
እጹ ዋዚባን አጅበው እክሱም ገቡ እጹ ዋዚባም መቄዶ ወይም መቄት ይበ
ሰጣቸው ያገኝ ሃገር በስማቸው እስከዛሬ ነበር እጹ ዋዚባ ወደ እዝ
ላል ። እንዚህም ቆንጆቻቸው የነረሱ ሴግን ጋር እንደተበማው በመርዌ
ስም ከመመለሱ በፊት ከእስክንድር በባውያን በሱባውያን በደን
እንደእባቶቹ ሆንደኬ ንግሥት ተብላ እንድትቀመጥበት እዘዘ እስ
ተላውያን ላይ የሴት ንግሥት ተበሏ ሃያ አንድ ሽህ በከሲዮስ
ክንድር ከእስክንድርያ ኢትዮጵያውያንን ሃያ ሽህ በድምሩ እርባ እንደ
እየመራ መቄዶኒያውያን ሰራዊትንም ሃያ ሽህ በኩል አድርጐ ከሶስተኛው ዳር
ገበ ጦር ይዞ በኤፍራጥስ ወንዝ በኩል አድርጐ ከሶስተኛው ሰስተኛው
የስ ከዳርዮስ ንጉሥ ጋር ለመዋጋት ሄደ የዳርዮስም ንጉሥ ይጠባበቀው
ዳርዮስ አንድ ሚሊዮን ከአምስት መቶ ሽህ ጦር ይዞ ጀግንነት
ጀመር ሆኖም ዳርዮስ እስክንድር በግዛቱ ላይ ያደረገውን ወንዝ
ሲሰጣ ሌትዮዋን ልጁን ለሚስትነት ለስጥህና ከኤፍራጥስ ለእሌ
በስተምስራቅ ያለውን እገር ለአንተ ወደምስራቅ ያለውን እገር እሲታውን
ይሁንና በሰላም በሃገራችን እንቀመጥ ካለው በኋላ የጦር እንደእንተ
ያርማጌዶን ምን ይሻላል ብሎ ጠየቀው እሱ መልሶ እኔ እን
እስክንድር ብሆን እርቁን በተቀበልኩ አለው እስክንድርም ሲል መል
ተት ያርማጌዶን ብሆን ዋር እስክንድር ነኝና አልቀበልም ስለዚህ እና
ሰለት ለዳርዮስም በአንድ ሰማይ ሁለት ጎዳናች ዋሉም ሲል ለላከቸው
አንተ በምድር ሁለት ሃያላኖች ሆነን እንኖርም
መልእክተኞች መልስ ላከለት ።

ዳርዮስና እስክንድር ሠራቸውን ይዘው ከጤግሮስ ወንዝ ወደ
ምስራቅ አርቤላ ከሚባለው ሃገር ላይ ጦርነት ገጥመው ዳርዮስ ተሸ
ነፍና እምልጦ ሲሸሽ ቢሶስ የሚባል ሰረገላ ነጂ ገድለው እስክንድ
ርም የዳርዮስን ሠራዊት ከሞት የተረፈውን ማርኮ በወታደሩ እንደ
ተጀበ ስመ ጥሩይቱን ከተማ ባቢሎንን ያዘት ሁሉም ሃገሮች ለግ
ሬኮች ህዝቦች ተገዢ ሆኑ ።

እስክንድርም ከድል ወደድል እየተራመደ (በዛሬው አፍጋኒስታን ወደ አራኮዚ) ወደ ዛሬው ቱርኪስታን) ወደባክትሪያን ጉዞውን ቀጠለ ከዚያም ወደህንድ ተጉዞ የሂንዱን ንጉሥ ፖሮስን ድል አድርጐ ማረከው በእስክንድር ስር ሆኖ ህንድን እንዲገዛ ፈቀደለት ከዚያም እስያን የበረሃውን አገር ዘዙብና የበረዶውን አገር አራት አመት ሁሮ በድል አድራጊነቱ በየሃገሩ እንደራሴ ንጉሥ ከአስቀመጠ በኋላ በስንት ድካም ተመልሶ የኢላም ከተማ ከሆነችው ሱስ በሰላም ገባ በዚህን ጊዜ የበታቾቹ ነገሥታት የግሪክ የእስራኤል የፋርስ የባቢሎን የሜደን የአሶር የአበሻ ንግሥት የነበረች ቅንዳቅስ የሌሎችም ሃገር ነገሥታት አዛውንት በተሰበሰቡበት የአለም ንጉሠነገሥት እነበረ በዚህን ጊዜ ከአፄ ሞዜማ የተላከ መግፍንት ነበሩ ሞና ጦር መሪ የነበረውን ከዛሀ አደጋ ያዳነውን ኢትዮጵያዊውን ክሊቶስ በግብር ላይ እስክንድር ገደለው ክሊቶስ ከሞተ በኋላ እስክንድር በጣም ወዳጁ ነበርና በገዛ እጁ በመግደሉ ተፀፀተ በጣብርም አስቀበረው ነገር ግን ከእስክንድር ግብር ላይ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ግድያውን ተመልክተው ወደሃገራቸው ተመልሰው ሲመጡ ለአጼ ሞዜማ ነገሩት እስክንድርም በስህተት ሁለቱም ሰክረው ሳለ በሰይፍ መጣላታቸውንና ሞና ወዳጁ ክሊቶስ በሰይፍ ተወግቶ መሞቱን የሚገልጽ ደብዳቤና ከሃያ አምስት ሺህ ሰረገላ ባሪያዎች ወደ አክሱም ካሳ ብሎ ላከ ነገር ግን አጼ ሞዜማም የእስክንድርን የአለም ንጉሠነትን ንቆ ወደፊት ለመርነት ይዘጋጅ ጀመር ከሰርያም የመጡትም ሃገር ለይቶ ሰጣቸው የሰፈሩት እስከ ዛሬ በስማቸው ሰረ ወያም በአበኛ ቋንቋ ሽሬ ይባላል እስክንድርም ከሱስ ሞና ከተማ ያደረገውን ባቢሎንን ነው ። ይችም ከተማ የመልከጸዲቅ ልጅ ሁሙራቢና ናቡከደነጸር ያሳመሩዋት ትልቅ ከተማ ነበረች ። እስክንድርም ባግሪ ሁሉታ አሳምሩዋት ነበር ።

እንደዚህም ሆኖ የአለም ንጉሥ እየተባለ እስክንድር ሲጠራ ፈላስፋ ሰው ይወድ ስለነበር አለምን ወደናቀው ዲዮጋን ሄደ ፈላስፋው ዲዮጋንም ከትንሽ ጉጆው ውስጥ ወጥቶ ለመሞቅ ሲል ሁለቱ ተገናኙና ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ እስክንድር ለዲዮጋን እንዲህ አለው እኔ እስክንድር መሆኔን ታውቃለህ እምን አለው ፈላስፋው ምን እንዳደርግልህ ትፈልግ አለህ እምን እኔ የምለምንህ ፀሃይን እንዳትከለክለኝ ከፊቴ ዞር በል እንዲታደርግልኝ እፈልጋለሁ ። አለው እስክንድርም ሽልማት ሊሰጠው የነበረው ትቶ በንግሩ እየተደነቀ እስክንድርን ባልሆን ኖሮ ፈላስፋው ዲዮጋንን እሆን ነበር እንደዚህም ማለቱ እኔ የአለም ንጉሥ ባልሆን ኖሮ አለምን እንደዲዮጋን

እንቅ ነበር ማለቱ ነው በዚህ አይነት ሲገዛ ሳለ በባቢሎን ከተማ በድንገት ታሞ በ5177 ዘመን ከተቆጠረ በንግሡ በ13 ዓመት በተ ወለደ በ33 ዓመቱ ሞተ እስክንድር ታሞ ሳለ ሊሞት ሲል ከእንቱ ቀጥሎ ለየትኛው ልጅህ ዙፋንክን እንስጠው አሉት የጦር አለቆች እሱም መንገስ ለሚገባው አለችው በዚህን ጊዜ የጦር አለቆች ለእኔ ይሆናል በማለት ብዙ ህዝብ ካለቀ በኋላ ኢሌክሳንደር ኤጐ የተባ ለው በመቄዶንያ ዙፋን በሞግዚት እንዲገዛ ተደረገ ሆኖም ሞግዚቱ ከሞገድር ከእናቱ ጋር ኢሌክሰማንደርን ገደሉ ከሞገድር እራሱ መገ ግሥቱን ያዘ አጼ ቀዚባ እስክንድር በሞተ በሁለተኛው አመት ንጉሥ ነገሥት በሆነ በ22 ዘመኑ መንግሥቱ አረፈና በፈንታው ልጁ ሰር ልያ አጼ ፈንታሌ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ መሲሃ እግዚአብሄር ተብሎ ነገሠ በዚሁ ዘመን ግማሹ ቀን በጸሐይ ብርሃንዋን ከምድር አጠፋች አጼ ፈንታሌ በነገሰበት ዘመን መቄዶንያ ሲገዛ የነበር ከሞ ገድር ፊሊጶስ ነው ሶርያንና አካባቢ ሞገ ሰሌውክስ ሲሆን እስክ ንድርያን ጠፍቶ የነበረውን የላጂድ ዳንስቲ ሰርዎ መንግሥት መሰ ፊች ሆኖ ላጉስ ሲሆን እሱውም ወሊያው እንደሞተ ልጁ ጥቶሌ ሚዮስ ነው ጥቶሌማዮስ በእርትራ ባህር አጠገብ ቡጣ የሚባለውን ከተማ በስሙ ጥቶሌማን ብሎ ሰይሞ አደሰው ይሄም ከተማ የግብ ጽችና የሶርያ ነጋዴ ዎች ወደኢትዮጵያ መጥተው የሚገበዩትን ዋና ከተማ ነበር በዚያም 2ኛ ፊሊደልፍ የሚባለ የግሪክ ተወላጆች ነበ ፋብት አለቃቸውንም ፊደል ይባላል ። አጼ ፈንታሌም አባቱ አጼ ቀዚባ ያዘዘውን ህግ ለመፈፀም ወደመርዌ ወርዶ ሲኖባና ለሰባ ለጸ ንጉሥና ለካባት ህዝብ ሶስተኛዎቱ ሀገሮች ንግሥት ዘንቢያቱ ብሎ እንግዶላቸው ወደአክሱም ተመልሶአል ለመርዌ የቤት ንግሥት ለመ ጀመሪያ ጊዜ የተሾመች መደባይቱ ፋሲላ እኛኒ ናት ይኸም ቤተ ግሪካውያን ዩናያታን ንጉሥ ሱተር ያገባች ናት አጼ ፈንታሌ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በ51 ዓመቱ ሞተና ልጁ አግልአል አጼ ቸላሉ ቸላሉ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ከግብፅ እስከ ባህር እስከ በርበር ድረስ ባለው ሃገር ላይ ነገሰ አጼ ቸላሉም 49 ዓመት ገዝቶ በፈን ታው ልጁ በዋውል አጼ ናግሽሬ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በ5279 ዘመን ከተቆጠረ ነገሰ እሱም እናቱ የሶርያ ሰው ነበረችና በአጼ ቀዚባ ዘመን መንግሥት ወደኢትዮጵያ የገቡት ከሶርያ የመ ጡት ባሪያዎች ነጻ ሆነው እንዲኖሩ ሲል አወጀ በሃገሩም ላይም ባለእርስት አደረጋቸው ዘራቸውንም ከሚከበሩ ከክቡሮች ከምንሞሪና ከጥሮም ጉልቆች ጋር እንዲቀላቀሉ እንዲጋቡ አደረጋቸው ስማቸ

ውም ከሶርያ ስለመጡ የሆነፊው ህዝብ ባለበት ጋር እኩል ስለሆኑ ትግሬ ማለት በሶርያ ቋንቋ ነጋዴ ማለት ነው ይላሉ ።

አጼ ናግሽሬም በአናቱ ወገን እየተረዳ ስባኢ አመት ገዛ እንደ ሞግሼ ንጉሥ ነገሥት ቢሆን በእርግ እመቱ ስለሞተ ስሙ ብቻ እየ እየተባለ 30 ሰላሳ አመት ጨምሮ ገዝቷል ከአጼ ናግሼሬ ቀጥሎ ልጁ በወረስ አጼ ደግሃፌ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በፈንታው ነገሠ አጼ ደግሃፌ ሰማኒያ ሶስት አመት በክብርና በደስታ የኢትዮጵያ ሃገሮችን ገዝቶ በተወለደ በመቶ አምሳ ሁለት አመቱ አረፈና በፈንታው ልጁ መሃሲ አጼ ኢንዛይቀሬ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ አጼ ኢንዛይቀሬ በነገሠ በሰባተኛው አመት ላይ በአለም የሚኖሩ ተንሜው አጼ ኢንዛይቀሬ ሃያ ሰባት አመት ገዝቶ ሽምግሎና እድሜ ጠግቦ ሲሞት በፈንታው ልጁ ናልክ አጼ ራማናልኬ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ።

አጼ ራማናልኬ 47 አመት ኢትዮጵያን ሃገሮች ገዝቶ ስለሞተ ልጁ ባቢን አጼ ሱዚ ቤዛ በነገሠ በስምንት አመት የሰላሙ መሪ የዘላለሙ ንጉሥ አማኑኤል በኢየሩሳሌም ቤተ ልሄም በምትባል መንደር ላይ ተወለደ ዘመኑም ዘመን ከተቆጠረ እንደሱባውያን አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን እንደሱባውያን 785 ሱባኤ ከ5 አመት እንደፈንታውያን 5476 አመታት እንደ አዜባውያን አሰራሉ ሁለት ሺህ ወይም 5500 አመት ላይ ነው ሱባውያን አዜባውያን አቆጣጠራቸው አንድ ነው ይሄውም በእኛ አቆጣጠር አንድ ሺህ አመት በፈጣሪ ዘንድ ቀን እንደምንለው ማለት ነው ስለዘህ አዳም የተፈጠረ በእኛ አቆጣጠር ሳይሆን በፈጣሪ ባህርይ በስድስተኛው ቀን ተከል ነው ። አዜባውያን አመታቸውን የሚቆጥሩ የንበር ስድስቱን ሺህ ከ5 መቶ አዳም ከመፈጠሩ በፊት አምስት ሺህ አምስት መቶ ከአዳም በኋላ እያሉ ይቆጥራሉ በድምሩ አስራ ሁለት ሺህ አመቶች 1714 ሱባኤ ከሁለት አመት ይሆናል ማለት ነው ። አመት መቁጠር ከተጀመረ በአምስት ሺህ አምስት መቶ ላይ የአዳም ዘር የሳዊት ልጅ እንደነሱ የዮሴፍን ልጅ የሴፍ ያሳደገው የፈጣሪያችን ቃል የሆነ የህይወት መሪ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ተባለ ኢየሱስ ብሂል መድሃኒት ክርስቶስ ብሂል ጌታ ማለት ነው አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያው መጨረሻው የፈታኛው የሁለተኛው እሱ ነው ከእርሱ ሌላ የለም የሌ ሉያ ይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ ከአክሱማይ ሲራክ መጽሃፍ ከግእዝ ወደአማርኛ ተርጉሜ ለኢትዮጵያው ያንና ታሪክ ፈላጊ ለሆናችሁ እንድታውቁት አቅርቤላችኋለሁ መሪ መሪራስ አማን በላይ ።

## ምዕራፍ አስር

### የአጼ ሌዛ ቢዛ ዘመነ መንግሥት

የዘላለሙ አባት የሰላሙ አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም እንደተወለደ

አስራ ሁለት ነገሥታት ጋዳ እንዳቀረቡለት በምሥራቅ በኩል ታይቶ የማ ተበሩ በንግሡ በስምንተኛው አመት በምሥራቅ በኩል ኮከብ አምሳሉ እንደሰው ነበር ይታወቅ ታላቅ ኮከብ ወጣ ይሄም ኮከብ ያመለከት ነበር በዚህን ጊዜ ብርሃኑን ሲያዩት ወደኢየሩሳሌም ያመለከት የሚቀመጡበት የጋዳት በዛሬው ጉጃም በደሸት ከተማ ጉጅ-ጉንጂ የሚቀመጡበት አትዮጵያ እንቁላርያንና ሴቶ የሚባ ንጉሥና የእግዚአብሄር ሰው አትዮጵያ እንቁላርያንና ሴቶ ይዞ ወደኢየሩሳሌም ለመ ለውን ቱል ድንጋይ የወርቅ የመልማል ይዞ ወደኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሱ ሄደ ጉዞ ጀመረ በስፍ ሶስት ንጉሶች አብረውት ለመሄድ ተነሱ እነዚህም ነገስታት የዳንጉላ ንጉሥ የዚግዝ ንጉሥ የታና ዲጋ ንጉሥ ናቸው ። እንደዚሁም ኮከቡን አይቶ ከፋንና ወልጋን ሲገባ የነበረ የመደባይ ጎጣ ከአናሬያ ዙባ ከተማ የሚቀመጠው የዶርዲያ በጋል የማጀና የአርመን አርሞ ንጉሥ መጋል ከኢጡሜሳ ንጉሥ ሮሜ ጆች ከኢልቦን አሙላ ከአፈር ንጉሥ ሙርቢ ጋር ሆኖ ከወርቅ የተ ልማል የተሰራ መጥናበሬያና አልባብ መጅባብ የሰንደል እንጨትና እጣን ከርቤም የከበረውን ቱል ወርቅ ይዞ የኮከብ ብርሃን ወደሚ ያመለከተው የገር ወደኢየሩሳሌም ጉዞውን ቀጠለ ። በሌላ የገር ደግሞ የታወቀውን በተሰርሴስና ከዋድዝ ከተማ የሚቀመጠው የእዚባው ዶን አዳል ንጉሥ ኢጋቦን ከሰንዳፊ ከተማከኤል ጊዜር ከሚቀመጠው ከኑቢው ንጉሥ ሃጃቦን በመርከብ የአራተኛይቱ ሀንደኪ የአረብ ንግ ሥት ባል አቡሰላም ። ከጌራራ ከተማ ሳባ ከተማ የሚቀመጠው ይደ አርሳማ ጋር ሆኖ ወርቅና እጣን ከርቤም ይዞ ወደኢየሩሳሌም ሰስት ራጎውን ኮከብ አይቶ ጉዞውን ቀጠለ እነዚህ ነገሥታት አለቆች ሰስት ሲሆኑ ለየራሳቸው በበታቻቸው የሚታዘዙ ሶስት ሶስት ነገሥታት አላቸው ሁሉም ዘውድ የሚኑ ናቸው ሁሉም በግመሎቻቸው ላይ ለየ በፈረሶቻቸው የሀብና የወርቅ የከርቤና የእጣን እንደዚሁ ለኮከብ ብርሃን የገር ልብሶች ከምድራቸው የሚያገኙትን አበል የኮከብ ብርሃን

ለሚመለከታቸው ንጉሥ ጋዳ ገፀበረከት ለመስጠት ቁጥሩም የጾ ሾትና የዳንጉዳ የዚግሀና የታና ዲጋ ግዮን ወንዝ ከሚፈልቅበት ምድር የሰገልና የኢውሳዋ የአባልና የአፋር ነገሥታት ዋቢ ወንዝ ከሚ ፈልቁበት ከሚያፈስበት ምድር በተተርሴስ የአዘቦ አዜብ የጌዘር የመርዌና የሳባ ነገሥታት ሰማያዊ ግዮን -አጥበራ ወንዝ ከሚፈል ቅበትና ከሚፈስበት ምድር ተነስተው የኮከብ ብርሃን ወደሚያመ ለክታቸው ቦታ በግመሎቻቸው ላይ ጋዳ - ገፀበረከት ተጭነው ለመ ሄድ ለምን ተነሱ ለምንስ ኢየሩሳሌም ለሚገኘው ንጉሥ ጋዳ የተ ባለው ገፀ በረከት ያቀርቡለታል የሚል ሰው አይጠፋም ።

እንደዚህ ነው የአሁኑ ትውልድ ነገርን እንደሚከታተልና ነገ ርን ከአንድ ቃል ወደ ሌላ ቃል ተርጉሞ እንደሚያስቀምጠው የቀ ድሞ አባቶቻችን ደግሞ የአባቶቻቸውን ቃል በማስተዋል ሰምተው ያከብሩታል በተግባር ያውሉታል የነቢያቶቻቸውን ትንቢት ሰምተው በሀሊናቸው ይዘው በልባቸው ያኖሩታል ከዚያም ለልጆቻቸው እንደሚስገር አድርገው ይነግሯቸዋል ። ከሀሊናቸው ያለውን ከልባ ቸው የተጻፈውን የትንቢት ቃል አውጥተው ለልጅ ልጆቻቸው እንዲያስተምሩ ይነግሯቸዋል ። ትንቢቱ እንዳይረሳስ አስተዋይ ለሆነ ልጅ እንጅ ለሁሉ ለአገኙት አይናገሩም ስለዚህ ነው አባቶቻቸውን ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ደርሶ ወደኢየሩሳሌም ለመሄድ የተነሱት ስለዚህ ነው በኢየሩሳሌም የሚኖር ስምዖን የሚባል ሰው የነቢያትን ትንቢት ያጠባበቅ ነበርና ኢየሱስን እናቱ አብቴ እንደ ሙሴ ህግ ሁለት ዋልያ ወይም ሁለት ርግብ ሚጠውት መስዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ቤተመቅደሱ ያዘውት እንደሄዱ የልጁን ድምፅ ሰምቶ በመን ፈስ ቅዱስ ተመርቶ ሄዶ አቀፈው አምላኩንም አመሰገነው ።

እንዲህ እያለ "ጌታዬ ሆይ አሁን እንደቃልህ ባርያህን በሰላም ታሰ ናብተዋለህ አይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና ይህም ለአህዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለህዝብም ለእስራ ኤልም ክብር ነው" ብሎ በሀዘበ መካከል ተናግሮ ያረፈ ትንቢቱስ እንዴት ነው የሚል ታሪክ ይኸም ካለ እንደዚህ ነው ።

ይህ የእግዚአብሔር ቃል አሁን ያለ ከመጀመሪያው የነበረ ወደመጨረሻም ለዘላለም የሚኖር ህያው ለራሱ ማህያዊ ለሌላው ነው ይህም የእግዚአብሔር ቃል በባህርዩ ፈጣሪያችን በመለኮቱ አም ላካችን በመንግሥቱ ጌታችን በአካሉ አባታችን ከፈጠረ ፍጥረት ሁሉ ሰውን ወዶና አልቆ ቃሉ የሰው ስጋ ሆነ ይኸውም የእግዚአ

ባሕርይ ቃል ሰው ሆኖ የሰውን ልጅ በክብር ከፍ ከፍ አደረገ ለዚ
ህኛው ዓለም በተወደደ ምስጋና በአንድነት ሆኖ ለዘላለም የሚያ
መሰግነው ይኸውም ምስጋና ሃብቱ ስለሆነ ነው ። እርሱም በሃይል
መለኮቱ የሚቀመጥ የክብር ባለቤት ፀጋን ለሰው ልጆች የሚያድል
ክቡር ቅዱስ እግዚአብሔር ነው ትንቢቱ ቃሉም ለነቢያት በመንፈስ ያናገ
ራቸው ይህ ነው ይህም ትንቢት ሊፈፀም ግድ ሆነና ተፈፀመ እርሱ
እናግሮ ያልተፈጸመ ትንቢት የለምና እንደዚህ ነው አባም ፈጣሪው
ያዘዘውን ሆነ ጥሶ እግዚአብሔር አዘኖለት ብሎ እፀ በለስን ቢበላ እራ
ሱን አዋረደ ሆነ ከገነት ወደምድር ፋይድ ወረደ መልካምና ክፋት
ይለያና ሃዘን ህይወትና ሞት ወደሚገኝበት ምድር ወረደ አም
ላከም አለው የሚሰጥህን ቃል ስምተሃል ከእርሱ እንዳትበላ
ከአዘዝኩህ ዛፍ ቅጠሉን ፍሬውንም በልተሃልና ምድር ከአንተ
የተነሳ እርጉም ትሁን በህይወትህም ዘመን ሁሉ በድካም ከእርሱዋ
ትበላለህ እርስዋም እሾህና አሜኬላ ታበቅልልሃለች አለው የምድርንም
ቡቃያ ትበላለህ ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ
ወዝ ምግብህን ትበላለህ ከአፈር ስለመጣህ አፈር ነህና ወደ አፈር
ትመለሳለህ አለውም ፈጣሪዉ እግዚአብሔር ጌታዬ ሆይ የሥጋዬን ምግ
ባር ነግረከኝ በርቀት አንተን በባህሪው እኔን የመሰልከው ከሥጋዬ
ጋር አዋህደህ የፈጠርከው ነፍስስ አለው ።

እግዚአብሔርም አለው የሰጠሁህ ሴት እርስዋ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝ
ስላልከው ከሴት ልጅህ ያለ ዘር ተወልጄ ከዛፉ ፍሬ ስለበላህ በዛፉ
ግንድ ተሰቅዬ የሞትከውን ሞት ሞቼ ያሳተቻችሁን እሳት በፍቅ
ርና በትህትና ድል ነስቼ ከአንተ የተነሳ ከተረገመችው መሬት አድ
ናና ነፍስህን ከስቃዩ ሲኦል ወደ ደስታ ገነት እግባሃለሁ ክብርና ፀጋ
አወርስሃለሁ አለው አዳምም ለሚስቱ ሄዋን እናት ሄዋን ማለት
ህይወት ከእንቺ አገኘሁ ማለት ነው ። ይኸውም ከድንግልና ከቃል
ከመንፈስ እንደኛው ቃል በእእሱዋ በኩል ለመጣው ድህነት በሴት
ልጅዋ ያስፋበና ያለዘር መወለዱን በተወለደው ልጅ ህይወትን
በመጀመሪያ ሱባኤ ከተጻፈው በጥቂቱ መረራስ አቅርበላችኋለሁ ።

ታላቁ የሰላም ንጉሥ ተራራ ሳሙኤልን የወለደች ሃገ እሴይ
ኢትኤልን የወረቀ መሶብ እሴይ ራሱ ነው በግ ተሸጎኖም ወደራማ
ተራራ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ሊያቀርብ ወጣ በዚያም ተራራ የያ
ዘውን በግ እርዶ መስዋእት አድርጎ ለእግዚአብሔር ከአቀረበ በኋላ
እንደ ፀጋቸው ቆዳውን ገፎ ሥጋውን በልቶ አጠጣቶ ደሙን በግ
ንዶው ሥጋውን በመሶብ ቆዳውን በድንጋይ ላይ አድርጎ አቃጠለው።

ነገር ግን በእሳት የተቃጠለው ከቦታት የተከፈለው ደምና ሥጋ ቅዳሴው እንደገና አንድ ሆኖ በት ከሞተበት ተነሳ በጉም እንደ ሰው ቃል አውጥቶ እንዲህ አላቸው የቆምክበት ምድር ቅዱስ ነውና የሰላሙ ንጉሥ እስከሚደርስ በዚሁ ቆይ ስምህም ጌራራ አይሁን መልከ ጻዲቅ ይባል እንጂ ሃሙኤልንም አለው በኤፍራጥስ ወንዝ የራብ ንጉስ ሁነህ ትኖራለህ ስምህም ሃመራቢ ትባላለህ ኢትኤልንም አለው ማዋን በሚፈስበት ምድር ትኖራለህ ስምህም ኢትዮጵ ትባ ላለህ አለው ከዚያም በት ወደ ሰማይ ሲያርግ እያዩት ባለ ሶስቱ ከቆሙበት ተራራ ላይ ትንሽ ጉም መጣችና ሸፍና ከራማ ተራራ ያሉ ወሰማይዘሌ የወይን ቦታ አወረደቻቸው ከዚያም የያዙትን የወ ርቅ ገንቦና የወርቅ መሶብ ቢያዩት በገንቦው የወይን ጠጅ ውሃ በመ ሶቡ የስንዴ እህል መስዋዕት ሞልቶ አገኙት ከዚያም አባታቸው ሁሉቱ ልጆቹን ለአምላኩ መስዋዕት በህብስትና በወይን እንዲያገ ለግሉት ከእለታት አንድ ቀን በዚያም በእሳት የያዙትን ህብስትና መስዋዕት አቀረቡ መስዋእቱን ከበሉ ከጠጡ በኋላ ሥጋሌዎች ለእ ሳም ልጆቹን ማማ ሰጣት ብለው የሰሙትን እንቆልርያ አንድ መደብ የወርቅ መሶብ አንድ መደብ የወርቅ ገንቦው አንድ መደብ ከቦታት ቦታ አስቀምጠው እዛ ቢጣጣሉ እንቆልርያው ለኢትኤል የወርቅ መሶብ ህብስት የያዘው ለመልከጼዴቅ የወርቁ ገንቦ ለሃሙ ኤል ደረሰ መልከጼዴቅ የተባለው ጌራራ እንዲህ አለ ትንቢትም ተናገረ በመንፈስ አንተ የነቸንን ውሃ የምትጠጣ እንቆልርያ የደረሰህ የያዝከውን እንቆርያ ከምድር ከምትገኘው ሉል ድንጋይና የከበረውን ዋጋ እንቁ የወርቅ ሃመልማል ይበዛ መጥተህ ለአምላክ ጋር አቅርብበት ከርቤ እጣን እምቀትህ አጤሰስት በሬቱ ስንድልት ይሄም የምስጋድልት ሰው የሰላምና የደህንነት ንጉሥ ነው አለው እንዲት እርሱ የሚመጣበ ትን ቀን ሳታውቀው እትኖራለሁ አለው ኢትኤል መልከጼዴቅም አለ እርሱ ጊዜ እስከሚያመልክ ድረስ እንቆልርያውን ተመልከተው የረሃብ ዘመን ሲሆን መልኩ ይዘጋል የጥጋብ ዘመን ሲሆን መልኩ ያበራል ስለዚህ ጊዜውን የሚነግርህና የሚመራህ የጥንት ኮከብን እስከምታየው ድረስ በሀሲናህ ጸሬው በእንደበትህም ተናገረው በልብህም አስቀምጠው አለው ኢትኤልም በፈንታው እንዲህ አለ በመንፈስ ተናገረ አንተ የሰላም ንጉሥ ባይ መሶብ የነበረች ህብስትን ይዛ ስለተገኘችና ለአንተ አደሆና ስለደረሰችህ ይስ ይብ ልሀ ያለህበትም ምድር ቅዱስ ነው በመሶብ ህብስት እንደተገኘ ከድ ንግል ቤት ላይ ቅዱሱ ጊታም የኢትኤል ዘር ይሰግዱል የሃመራቢ ነገድም ያሰናክላል ከቃሉ የተነሳ ይተላለፋል ወዮልህ አንተ ለአምላ

ሉኒታ የማትማ ስለአንተ ምድር ትረዳኛለች ከዚ የማትሰማድ እንዲህ እለ በመንፈስም ትንቢቱን ተናገረ ። አንተ እለ የሙኤል እንዲህ እለ ይዘኸው የነበረ በግ ታረደ ከምት እባቶችን የሰላሙ ንጉሥ ሆይ ይዘኸው የነበረ በግ ታረደ እርስትም ይሁናችሁ ብሎ ሃገርን ለይቶ ተንሳ እንደሰጠሃቸው ተናገረ እርስትም ወደ ወይን ሰጠ እርሱም ወይሰማዩ ኢያሱንም እረገ ስለዚህ እኛም ወደ ወይን ቦታ በትም ወርደን አያቶቻችን ባዶ የነበረውን ሃገሩን የወይን ቦታ ሠረዊን መንፈስ ቅዱስ ተሞላበት እኛም ተመሳስለን መንፈስ ቀም ጠጅ መሰብን መስዋዕት ምላሷን እኛም ቀምሰን ወዳ ምድር እኛን በቅዱስ ላን ባዶ የነበረች የወርቅ ገንቦ የወይን ውሃ ምልታ እኛን በቅዱስ ላን ባዶ የነበረች የወርቅ ገንቦ ተወልዳ ድንግልናዋ ሳይቀር መንፈስ እንዳስደሰተች ልጅ ልጅ ተወልዳ ድንግልናዋ ሳይቀር ልጅን ወልዳ እለምን ታስደስታለች ልጅም የሰላም ንጉሥ ብሎ ሳይዘን የዘላለም እባት ይሆናል እለ መልኬጸዲቅ የተባለው ጌራ ሰላምን የዘላለም እባት ይሆናል ኢትኤል እርስትም ምድርህም ማርን የሚፈስ ራም እለ ታላቁ ልጁ ኢትኤል እርስትም ምድርህም ማርን የሚፈስ ዘት ምድር ነውና ሚስትህንና ልጆችህን ይዘህ ወደማርን ምድር ዘት ምድር ነውና ሚስትህንና ልጆችህን ይዘህ ወደማርን ምድር ውሃ እንተ ታናሹ ልጅ የሙኤል እርስትህም ምድርህም ኤፍራ ውሃ እንተ ታናሹ ልጅ የሙኤል እርስትህም ምድርህም ኤፍራ ቀስ ወንዝ የሚፈስበት ምድር ነውና ወደኤፍራተስ ወንዝ ሙሪ ድና ልጆችህንና ሚስቶችህን አስፍርበት ለዘላለም የወይን ውሃ ከባዶ ገንቦ እንዳገኘህ ከባዶ መሬት ላይ በመጣ ውሃ ትከበራለህ ። ማን የዘለአለሙ እባት እስከሚመጣ የኮርዳኖስ ወንዝ የሚፈስበትን ምድር ይገ ከታናሹ ልጁ ከእባ መሴክ ጋር አርስቴ ሴሴዶ እኛራለሁ ያለ ከዚህ እንደደ ብለው ሰስቴ እባትና መንድማማቾች ተለያዩ ኩሉ መልከጸዴቅ በዓለም ሊቀር ኢትኤል ማርን ወደሚያፈስበት ምድር ሙኤል ኤፍራተስ ወደሚያፈስበት ምድር ወደ አበመልክስ ከተማ ሔራዕሳ ሄዶ ። የኢትኤል ዘሮች ይገም እንዲህ ሲሉ ትንቢታቸ ውን ተናገሩ በለአም ከምድር እስራኤሎች ሲወጡ በመንፈስ እዩት መራ ተናገረ ። እየዋለሁ እሁን ግን አይደለም እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል በእስራኤል በትር ይነሳል ከያዕቆብ የሚወጣ ነገር ይሆናል እለ እንዲዚሁ ነበዊ ይሸን የእባቶ ቶን ትንቢት ሲከተተል ከእለታት አንድ ቀን በግዛን ሞንታ ትቀምጠ ተቀምጠ ፍልስፍናውን በአዝዋሪት ውሃ ሲፈስስና ጠበለእም የታቸው ኮከብ እንደገና ዳዴሾት በአዝዋሪት ላይ ታቸው ከአዝዋሪቱ አረፋ ላይ የታቸውን ኮከብ እየተከተለ ሲሄድ ድንግል ቤት ያልሩበና ያለበር የተወለደ ልጅ ታቅፋ ወዲያውኑ ድንግሊቱን ልጆቹን እንደታቀፈች በመሪቅ በሴዳ ድንግሊቱ ያመራውን ኮከብ በናስ ስሴዳ ስሙና ቀርቶ ስልጆቹ አስቀመጠው ሲሞት ሲል ልጆቹን ሰብስቦ ባርኮና መርቶ ሲወርስ ይህን ኮከብ የሚመስል በምስራቅ በኩል ሲወጣ አይታችሁ የዘርማን ዘረኛን ወደሚያመለክታችሁ ምድር ከምድራችሁ ከምታገኙት የም

ደግ፣ አበል መርት እምነ ከዚህ ሌብስ ይዛቸው ተነሡ ይህን አምላካችን ለአባቶቻችን እናም ለኛም ግን ማኅ እንዲሰጣት የሰጠውን ለኢትዮጵያ እማ ሆና የደረሰውን እንቀበርያ በክብር ይዛቸው የቅኝ ብርሃን ለሰገደለት ሰገዳቸው ስጦት ሉል ተጸ የወርቅ ያመልማል ለወለደችው ድንግል ስጦታ ቢሉ ተናግሯል ። እንደዚሁም በእስራኤል አባቶችና በንቢያቱ ትንቢቱን እናግር ምሳሌውን አሳይቷል ።

ለኖህ ድንግሊቱ በደመና ልጅዋ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምልክት ቀስተ ደመና ሆነው ታይተውታል ደመና (እምግዚ/አልዘ) ከወረደው በማይ ላይ ሆኖ ዝናምን እንደሚያወርድ ድንግሊቱም ያለ ዘር ከንፃው አካልዋ የሰጣም ንጉሥን ወልዳ ለበለአለም ለሰው ልጆች ምሀረት አማላጅ ሆናለች ደመና የድንግል ቀስተደመና የልጅዋ ዝናም የምሀረት ምሳሌ ነው ።

አብርሃም በቀትር ከድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ዛፍ ተገለጠለት እይቶንም እንሳና ወደዛቀ ሲመለከት ሶስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳን ደጃፍ ተነስቶ ሮጠ ወደምድርም ሰገደ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደሆን ባሪያህን አትለፈኝ ብየ እለምንሃለሁ ጥቂት ውሃ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ከዚችም ዛፍ በታች እረፉ ቁራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ ስለዚህ ወደባሪያችሁ መጥታችኋልና አላቸው ።

ይህ በኋላ ዘመን ለሚሆነው ለድንግሊቱ የታየው ትንቢት ነበረ ዛፉ የድንግሊቱ ሶስት ሰዎች የስላሴዎች ምሳሌ ነው ይሄውም አንድን ቁን ሲናገር በፊትህ ሞገስን አግኝቼ ማለቱ ነው ይሄም ጌታ በባህሪዩ አንድ ሲሆን በአካሉ ሶስት ይሆናል ይሄን የእግዚአብሄርን ምስጢረ ሥላሴ የተሰወረበት ታላቅ ከንቱ ሰው እንዳለ እናውቃለን ይሄን ወደሰላሙ ምእራፍ እናቆያለ ወደሌሎች ነቢያት ታሪክ እንለፍ ።

ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወደካራን በሄደ ጊዜ መሸቶበት ከመንገድ አደረ በዚያም ሮዋሩ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ ህልምንም አለመ ህልሙም ይህ ነው መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደሰማይ ደርሶ የእግዚአብሔርም መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር እነሆም እግዚአብሄር በላዩ ቆሞበት ነበር እንዲህም አለው የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሃቅም አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ይህችን አንተ የተኛህበትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ ዘርህም እንደ ምድር አሸዋ ይሆናል ከምስራቅ እስከ ምእራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ትሰፋ

ቆሬስ የምድርም አሕዛብ ሁሉ በአንተ በዘርህ ይባረካሉ እነሆ እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በምትሄድበትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ ወደዚ ችም ምድር እመልስሃለሁ ። የነገርኩህን ሁሉ እስካደረግልህ ድረስ አል ተውህምና ያዕቆብ ከእንቅልፉ ተነስቶ በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው አለ ይኸም መሰላል የድንግል ልጅ የቆመበት ፖርታ የድንግል ቴ ምሳሌ ነው መሰላል መሸጋገሪያ እንደመሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚገኝ በልጅዋ ነውና ከነቢያት ደግሞ ነቢዩ ሙሴ እንዲህ ሲል እግዚአብሔር ተናገረው አምላክህ እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን የአምላኬን ድምፅ ደግሞ አልሰማ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደለመንኸው ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደእኔ ያለ ነቢይ ያስነ ሣልሃል እርሱንም ታደምጣለህ አለው ሙሴም እንዲህ አለ እግዚአብሔር አለኝ የተናገሩት መልካም ነው ከወንድሞቻቸው መካከል እንደአንተ ያለ ነቢይ አስነሳቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝኩትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል ። በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀለዋለሁ ። ሲል አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ቃል በነቢዩ ሙሴ አስቀድሞ ትንቢቱ ተነግሯል ።

እንዲሁ በእስራኤል የነገሠው ንጉሥ ዳዊትም በመንፈስ እንዲህ ሲል ትንቢቱን ተናግሯል በፊቱም ኢትዮጵያውያን ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ የአረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል አሕዛብ ሁሉ ይገዙለታል ሲል የተናገረው ተፈጸመ ነቢዩ ኢሳይያስ ደግሞ እንዲህ ሲል ተናገረ ጌታ እራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ ድን ግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ይልና እሱና ብሎ ደግሞ ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ከዛሬ ጀምሮ እስከዘለዓለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደ ግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም የእግዚአብሔር ቅንአት ይህን ያደርጋል ።

ይልና ስለኢትዮጵያውያን ነገሥታት ደግሞ እንዲህ አለ እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ መርሮቹ ግብፅ ለአንተ ቤዛ አድርጌ ኢትዮጵያንና ሳባ ከተሞቹን ለአንተ



የክርስቶስ በበረት መወለድ

ፋንታ ሰጥቼሃለሁ በአይኔ ፊት የከበርከና የተመሰገንክ ነህና እኔም ወድጄሃለሁና ስለዚህ ሰዎችን ለአንተ አህዛብንም ለነፍስህ እሰጣለሁ ዘርህንም ከምሥራቅ አመጣለሁ ከምዕራብም እሰበስብሃለሁ ይላል ይኸን የመሰለ የእስራኤል ነቢያትና ከኢትዮጵያ ከሚወጡት የእግዚአብሔር ካህናት በየጊዜው በመንፈስ ተናገሩ ትንቢቱም ይፈጸም ዘንድ በምሥራቅ በኩል እግዚአብሔር ምልክትን አሳዩ ስለዚህ ነው ሁሉም በየራሱ ከቦታ ላይ ወደ ኢየሩሳሌም የወረዱ አባቶቻችንና ነቢያት የተናገሩት ትንቢት እንደደረሰ አውቀው በብዙ ሺህ ሠራዊት ታጅበው የኋላ እንደዚሁም ሆነ ብዙ ልዩ ልዩ ቁጥር አሁን ልጅ በአውግስጦስ ቄሳር ዘመን መንግሥት ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ ሄሮድስ በይሁዳ አገር ነግሦ በነበረበት ጊዜ በኢየሩሳሌም አጠራጠሯቸው ሁሉ ከቦታ የነገር በግ መልና በፈረስ ሆነው የመጡትን ነገሥታት ባያቸው ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ታላቅ ድንጋጤ አደረባቸው ሀገር ለመውረር ለመርገጥ የመጡ መሰሏቸው ከዚያም ነገሥታቱ እኛ የመጣነው ልንገዛው ልንሰግድለትና ገጸ በረከት ልናቀርብለት የክብሩ ብርሃን እየመራን እስከዚህ መጥተናል አሉቸው በዚያን ጊዜ የገሊላው ንጉሥ ሄሮድስ ሰማና በጣም ደስ አለው ለእሱ መስሎት ወደእኔ አምጡአቸው ብሎ መልእክተኛ ላከ ከዚያም ከቦታ ላይ ሆነው የመጡት እስራኤላውያን ነገሥታት ተናገሩ እንተን ሆን ተብለው ተጠይቀው ሁሉም ልንገዛው ልንሰግድ የምሥራቁን ኮከብ አይተን መጥተናል ተባብለው የአንድ አጼ የገር ሰዎች ሆኑና በአንድ ላይ ሆነው ወደ ሄሮድስ ሄዱ እነሱም እንዲህ አሉት ባረ በሀልግችን የምሥራቅ ብርሃን ሲመጣ አይተናልና የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው ነገሩን ከምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና አሉት እሱም ለእርሱ መስሎት የነበረው አፈረና ደነገጠ ከእኔ ሌላ ለአይሁድ ንጉሥ አለወይ ብሎ ተጨነቀ የኢየሩሳሌምም ሕዝብ ሰዎች ተጨነቁ በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆች የሕዝብን ጸሐፊዎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንደሚወለድ ጠየቃቸው እነሱም እንዲህ ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አለቃ ይወጣል ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይመጣልናል ስለዚህ መሳፍንት እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ አሳልፎ ይሰጣቸዋል የቀሩትም ወንድሞቹ ወደ እስራኤል ልጆች ይመለሳሉ እርሱም ይቆማል በእግዚአብሔር ሃይል በአምላኩ በእግዚአብሔርም ስም በእግዚአብሔር ግርማ መንጋውን ይጠብቃል እነርሱም ይኖራሉ አርሱ አሁን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ታላቅ ይሆናልና ተብሎ በነቢዩ በምሳሌያቸው በሚክያስ እንዲህ ሲል ጽፎታል

ስለዚህ ክርስቶስ የሚወለደው በይሁዳ ቤተልሔም ነው አሉት ከዚህ በኋላ ሄሮድስ የደረሰበትንና የሰገልን የተናገሩስና የዓለ የአረብያም ነገሥታት በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ በጥንቃቄ ተረዳ ወደቤተልሔምም ሄዱ ስለ ሀጻኑ በጥንቃቄ መርምሩ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው እነርሱም ንጉሡ ሄሮድስን ሰምተው ሄዱ እነሆም በምስራቅ ያዩት የኮከብ ብርሃን ህጻኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው በዚያን ወራት የአለም ሕዝብ ሁሉ ቁጥሩ እንዲጻፍ ትእዛዝ ከአውግስጦስ ቄሳር ወጣ ሁሉም አያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደከተማው ሄደ የቤቱ ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ ቤተልሔም ወደምትባል ወደዳዊት ከተማ ወደይሁዳ ወንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ የበኩር ልጅዋንም ወለደች በመጠቅለያም ጠቀለለችው በእንግዶች ማደሪያም ሥፍራ ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው በዚያን ጊዜ አስፈሪዎቹ ነገሥታት በኮከብ ብርሃን እየተመሩ የተወለደበት ድረሱ ወደቤትም ገብተው ሕጻኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት ወድቀውም ሰገዱ ለት ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና እጣን ከርቤ ከወርቅ የመልሟል የተሠራ እጅ ጠባብ አቀረቡለት ለእናቱም እንቁአርያውን የጸና ሉል ከወርቅ ድንጋይ ከወርቅ የመልሟል የተሠራ መጐናጸፊያ ሰንደል እንጨት እድርገው ሰጡት ለተወለደው ሕፃን ሊሰግዱለትና ሊያመልኩት ከሰቡ ብኋላ ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ በህልም ተረድተው ሕፃኑን እንደሚያስገድለው አውቀው ለእናቱ ይዛው እንድትሰደድ መክረው በሌላ መንገድ ወደሀገራቸው ተመለሱ ።

እነዚህም ነገሥታት ከሄዱ በኋላ እነሆ ጌታ መልአክ በህልም ለዮሴፍ ታይቶ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሳ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደግብፅ ሽሽ እስክነግርህም ድረስ በዚያው ተቀመጥ አለው እርሱም ተነስቶ ህፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ወደግብፅ ተሰደደ ከጌታ ዘንድ በነቢዩ በሆሴዕ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም ወደግብፅ ሄዶ ሄሮድስም እስኪ ሞት ድረስ በዚያው ኖረ ነገር ግን ሄሮድስ ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በህልም ታይቶ የህፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሳ ሕፃኑንም እናቱንም ይዘህ ወደእስራኤል ሀገር ሂድ አለው እርሱም ተነስቶ እናቱን ያዘና ወደእስራኤል አገር ገባ በአባቱም በአር



በሉቃ. ወንጌ. ምዕራ. ፪ ፳፪ ክርስቶስ ሲመለስ ኢየሩሳሌም ያለውን
ታ ን ንዳ እንዳቀረበ

ድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደነገሠ በሰማ ጊዜ ወደዚያ መሄ
ድን ፈራ፤ በህልምም ተረድቶ ወደገሊላ ሀገር ሄዶ በናዚሬትና ናዝሬቴ
ይባላል ። የተባለው ይፈጸም ዘንድ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ ሄዶ
ኖረ በዚህ ግዜ ሕፃኑ እድሜው የሰባት ዓመት ልጅ ነበር ።

እንደአይሁድ አነጋገር መሳደቢ በየአመቱ በፋሲካ በዓል ወደ
ኢየሩሳሌም በእል ይመጡ ነበር፤ የአስራሁለት አመት ልጅ በነበረ
በት ጊዜ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸው ሲጠይቃቸው
ይውል ነበር፤ ለናትና አባቱ በሰአውቀቱና በሰማስተዋሉ ይገረሙ ነበር፤
ነገር ግን አይሁድ ያገሉበትል በግብፅ በናዝሬት ይብቃውት ይኖሩ
ነበር፤ ከዚያም የሃያ ሁለት አመት እድሜ በነበረ ጊዜ ወደ ግብፅ
ወርዶ ሲኖር ከዚያም ወደ ነባ ሄዶ የሀባን ጉማዎች ከሚኖሩበት
ምድረ ቢሀ ከሚባለው ሀገር ላይ አመት እያስተማረ ተቀመጠ ያሄም
ሀገር ይብሪቢያን ተብሎ የቅዱሳን ሀገር መኖሪያ ሆነ ከዚያ
ሲጀሮን የሚባሉትን በዘንዶ ያመልኩ ነበርና እንዳያመልኩ አስተ
ምሮ በእግዚአብሔር ስም ብቻ እንዲያመልኩ አደረገ በዚያም ትም
ህርቱን ስምተው ከጀንዶ ከተማ የመጡ ጉማዎች ነበሩና በሀገራቸው
ስም ሀገሩን ይሞ አሉት ከዚያም ትልቅ ተራራ ነበርና አርባ ቀን ተቀ
መጠበት ስመኝም ይብሪሸም ከዚያም ወርዶ ዋልድባ ከሚባለው ምድር
ሰነበተ ከዚያም ከጋፋትና ከሚረ ጉማዎች ወደ ማናን ምንጭ ሄዶ ምእ
ራፍዋ ከሚባለው ጂን ሲጠፋ ባህር ውስጥ ከምትገኝ ደሴት ውስጥ
ሲያስተምርና ሲመክር በእግዚአብሔር ብቻ እንዲያመልኩ አደረገ
የዚያም ሀገር ሰዎች ስሙን እንሰሀያው አሉት ትርጓሜውም
የህይወት ልጅ ማለት ነው እግዋለ እመሀያው ከሉ የህይወት
እናት ወልደችህ ማለት ይሆናል ትርጓሜ በጋፋትና በእግዚአብ
ቋንቋ ነው በዚህ ዘመን በአክሱም የነበረው ንጉሥ ነገሥት አጼ ሰንፈ
አርእድ ነው ። ይሄውም አጼ ሰንፈ አርእድ እግዋለሀያው በሚሉት
በኢየሱስ እጅ ካለበት ድረስ ሄዶ ተባርኳል ያንም የተባረከበትን
ምድርና ኢያሱስን ያገኘበትን ተራራ በስሙ ራስ ዳሽ አለው ኢያ
ሱስም የሃያ ሰምንት አመት ሰው በነበረበት ጊዜ ወደሀገሩ ወደኢየ
ሩሳሌም ልዩ ቦታው ናዝሬት ወደሚባል መንደር ሄዶ በእዚያም እና
ቱን ከወላቂዋ ከዮሴፍ ከስሎሜ ጋር በደህናእንዳገኛቸውመዶቹጠፋእያሉ
ያጨንቁ ነበርና ሲያዩት በጣም ደስ አላቸው ። የእናቱን የማርያም
ንና የአራሱን የኢየሱስን የህይወት ታሪክ የፈለገ ነገረ ማርያም
ተብሎ በሚጠራ መጽሐፍ ውስጥ በጉጃምና በአንዳንድ ደብሮች
በለሚገኙ በሰፊው ለመረዳት ይቻላልና እሁን ወደኢትዮጵያ ታሪክ

እንመለስ አጼ ሴዛ ቤዛ የተባለው ባዚን ከክርስቶስ ልደት በፊት ስም ንት ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ ዘጠኝ ዓመት በድምሩ አስራሰባት ዓመት ገዝቶ ገብቶ ሲሞት ልጁ ራስደቪ በፈንታው አጼ ፀንፈ አርእድ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ።



ክርስቶስ በ12 ዓመቱ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ

እንደዚሁም ሆኖ በአጼ ፀንፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት የመርዌ ንግሥታት አምስተኛይቱና ስድስተኛይቱ የአክሱምን መንግሥ ከደው ለአውግስጦስ ቄሳር ገቡ አውግስጦስም አምስተኛ ህንደ የነበረችውን ሚስት ሲያደርጋት ስድስተኛይቱን የመርዌ ንግሥት ህን ኬን አፍቅሮ እንደደነበር በሰፊው ይነገርለታል ይሄውም እናቱቱ ልጆቱን በማብሬ ሆነን ያዘ ማለት ነው ። በነዚሁ ሴቶች ምክንያ እስከኢንድራያንና ናያታን ከሮም መንግሥት ጋር አቀላቅሎ ይ ጀመር አውግስጦስ ቄሳር ስድስተኛይቱ ህንደኬ ንግሥት የነበ

ችን በናፖታ ይዞት ሳለ የመርዌን ግዛት ከሮም ለመጨመር ከርእሊዎስ ካዮስን የጦር መሪ አድርጐ ፈላዩ ላይ ላይ ከአጼ ፀንፈ አርእድ ሰራዊቶች ጋር ታላቅ ጦርነት አድርጐ ድል አድርጐ ቴብንና ፊላዮን በቁጥጥሩ ሥር አደረገ ሕዝቡንም አስገበረው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ፀንፈ አርእድ ታናሽ እህቱን ለእሊት ገርማዎትን በባተኛይቱ የመርዌ ንግሥት ሆንደኬ ብሎ ከሁለት መቶ ሺህ ሰራዊት ጦር ከአራት መቶ ሺህ ፈረሰኛ ጦርና ከሰበት መቶ መርከበኞች ጦር አድርጐ ወደመርዌ ላካት እሷም ተዋግታ ፈላዩንና ኡሌፋንቲንን ከአውግስጦስ ቄሳር ወታደሮች ነጻ አወጣች ስለአውግስጦስ ክብር ሲባል በሮማን ቤተ መቅደስ ይሸፍ ተሰርቶ የነበረውን ሐውልት አፈራረሰች ከዚያም ለእንደገና በግብፅ በሮማ ሕዝብ ብርታት ፈላዩንና ኢሊፋንቲንን በያዘች በስድስተኛው ወር አስለቀቋት ከዚያም ከናፖታ በመለስ ለሮም መንግሥት በእርቅ ለቀቁና በሁለቱ መካከል ፍቅር ለትንሽ ጊዜ ተመሰርቶ ነበር አውግስጦስቄሳር ክርቶስ በተወለደ በአስራአራተኛው አመተ ምህረት አርቁ ፈረሰ አጼ ፀንፈ አርእድም ሃያ ሁለት ዓመት ገዝቶ መንግሥቱን ንቄ የዚህን ዓለም ይስታ ትቶ መንኖ በርሃ ገባ ለታናሽ እህቱ ለመርዌ ንግሥት ህንደኬ ለቀቀላት ። እስዋም እቴ ህንደኬ ንግሥት ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ወይም እቴ ግርማዊት ተብላ በአክሱም ዙፋን ላይ ተቀምጣ ከቴብ እስከ በርበር ባሉት ነገሥታት ላይ ትገዛ ጀመር ።

እቴ ግርማዊት በበላላ ዘጠኝ አመተ ምህረት ሰምንት ዓመት ገዝታ ስትሞት የወንድምዋ የፈለስ ፃሺ ልጅ ሰፈን አጼ ኡዛና ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ፍቁረ እግዚአብሔር ተብሎ ነገሰ አጼ ኡዛና በዘመኑ መንግሥቱ ባሀር ተሻግሮ ሬውዋንና ሳላትና ከቄሳር መንግሥት ነጻ አውጥቶ በበላያቸው ሃቅሌ የሚባለውን የጦር መሪ አንግሰላቸው በሰላም ወደ አዶሊስ ተመለሰ ከአዶሊስ ወደቆያ ሄዶ ትልቅ ቤተ መቅደስ ከኗላ አሠራ በስሙም ከነሃስ ከብር ከወርቅም ድሪ የሚባለውን ገንዘብ አሠርቶ አለም እንዲገበይበት አደርገዋል አጼ ኡዛና በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ሃያ አመት ከገዛ በኋላ እንደአባቱ የዚህን አለም ይስታ ንቆ ታላቅ ሴት ልጁን ብሉብላ የምትባለውን 3ኛ እቴ ህንደኬ ዣን ንግሥተነገሥታት ዘኢትዮጵያ ብሎ አንግሶ ዙፋኑን ለቀቀላት በበታችዋ ታናሽ ወንድምዋን የኒራራ ደሴቶች ገዥስ ዳሀላቅ አዶሊስ ዘስቃሴስ ብሎ የንጉሥ አክሊል ደፋለት አጼ ኡዛናም የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓት እየአስተማረ በፅዋ ገዳም እይሚኖረውን በዚያው ዉረደ እንጅ ተመልሶ ወደ አክሱም አልመጣም ።

እቴ ሀንደኬ ግን ንግሥተነገሥታት በሆነች በአስራ አንደኛው ዘመን መንግሥቷ ወንጌላዊ ማቴዎስ መርጫ ከተማ ገብቶ ሲያስተምርና ሲያጠምቅ ሰምታ ወደሷ ይዘውት እንዲመጡ ላከች ነገር ግን እቴ ሀንደኬ ግንም እሱ ከመምጣቱ እኔ መሄድ አለብኝ ብላ በብዙ ሺህ ጦር ታጅባ ወደመርጫ ወረደች በዚያም ቅዱስ ማቴዎስን አግኝታ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ የአለም ንጉሥ እንደሆነ አምናለሁ ነገር ግን በጥምቀት ዳግመኛ ከእግዚአብሔር መወለድን አላውቅም ነበር አሁን ግን አወቁ ከትምህርትህ የተነሳ ቅዱስ መንፈስ ገለፀልኝ ስለዚህ አጥምቀኝ ብላ ከማቴዎስ ጋር ወደባህር ወረዱ በዚያም ሠራዊቷንና መኳንንቱን አጠመቀ እስዋም ተጠምቃ ፍጹም ክርስቲያን ሆነች ከዚያም ወደአክሱም ማቴዎስን ይዛ መጥታ ቤተሰቦቿን ልጆችዋን እስ ጠመቀች አክሱስ የሚባለው ባኃን በኢየሱስ ሥም አስጠመቀች ማቴዎስም የጉባኤና የናግራን ሕዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ አጥምቶ ክርስቲያን አደረገ ።

እንደዚህም ሆነ እቴ ሀንደኬ ግን ክርስቲያን በሆነች በአስራ ሶስት አመትዋ አቢስ - (አበሻ) የሚባሉት የአዶሊስ ሕዝቦችና በአክሱም አካባቢ የሚገኙ ቀላስያን - (ፈላሾች) ወንድሞቻቸን ከተባበሩ አጼ ባዘረ ሰዶ ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ብሔሙ በበላይዋ ላይ እንግ ሰው እስዋንና ልጆቿን ይዘው በሳት አቃጠሏት አዲስ የክርስቲያንን እምነት የሚከተሉና የሚያምኑ እንዲገደሉ በአዋጅ ተናገረ ከዚያም መሲ ንጉሡና መኳንንቱ በድብቅ መሰሉን በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ስም እያመኑ ያስጥምቀት ተቀመጠ በዚሁ ዘመን በኤርትራ ባህር አጠገብ የሚኖሩ የግሪክ ሕዝቦች የንጉሡ ከንግሥቱን መርከብ ሠራዊ ዋች ሂክሶስ የሚባሉትን አስነስተው ብዙ የጁዊ ጦር ገደሉ እራሱም አጼ ባህር ሰገድ በሃያ አራት ዘመን መንግሥቱ በ81 ዓ.ም. ከግሪኮች ጋር መታራ - ወይም መተሃራ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ጦርነት አድርጎ ተማርኮ ሞተ ።

በዚህን ጊዜ በአክሱም የሚገኙት መሣፍንትና መኳንንት የአም

ሰላሳን ዓመት ልጅ ግርማ ሰፈር እጼ ግርማ አስፈሪ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ብለው በአባቱ በባህር ሰገድ ዙፋን አስቀምጠው እንገ ሰት እንደዚሁም ሆነ እጼ ግርማ አስፈሪ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በአባቶቹ ዙፋን ከተቀመጠ በሁለተኛው ዘመነ መንግሥቱ አረቦች እስ አውደ የሚባሉቸው ኢሳያድ በሞግዚቱ ዘርአይ እየተመሩ በኤርትራ ባህር አጠገብ የሚኖሩትን ከተማዎች አዶሊስን ዳህራቅ ቆያቂቱን ዋና መቀመጫቸውን ንጉሣቸው የሚኖሩበትን ተቶሉማ ይን ከተማዎች ተዋግተው ድል አድርገው ሕዝቡን ለአክሱም ግዛሬ እንዲሆን አደረጉት ሱባ ታላቅዋ ከተማ ተብላ ስትጠራ የነበረችውን ግሪካዊ ፕቶሉማዮስ በስሙ ሰይሟት ሲኖር እነዚህ ኢሳያድ የሚባሉ ተዋጊ ጦሮች ወረው ለራሳቸው አድርገዋት ሲኖሩ በስዋኪን ጊዜ በእጼ ግርማ አስፈሪ በአምስተኛው ዘመነ መንግሥቱ በሮም ከትራያ ኖስ ቄሳር ቀጥሎ አርያኖስ ቄሳር በነገሠ በአንደኛው ዓመት የእ ርና የግብፅ ተዋጊ ጦሮች ደንገት ደርሰው ከተማዋን በእሳት አቃጠ ሏት ሕጻናቱን አዛውንቱን በግፍ በጭካኔ አረዷቸው ከተማዋም ፕቶሌማ ስማይስ እንዳልነበረች ሆነች በዚህን ጊዜ አርያኖስ ቄሣር ከሮም ናፖታ ድረስ መጥቶ በመርዌና በናፖታ ሁለተኛ ጦርነት እንዳይ ከሄድ አድርጎ ሁሉቱም በኩል ወዳጅነትን መሥርቶ ከግብፅ ወደሮም በሰላም ተመልሰ በዚሁ በአርያኖስ ዘመነ መንግሥት ከፈርዖኖች እንደልባቸው ከአንድ ሀገር ወደአንዱ ይጓጓዙ ነበር ። እጼ ግርማ አስፈሪ የኢትዮጵያን ሀገሮች በገዛ በሰላሳ ዘመነ መንግሥቱ በተወ ለደ በሰላሳ አምስት አመቱ አረፈ በፈንታው ልጁ ሰርግዋይ እጼ ዛን ቢዛን ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ።

* በእጼ ዛን ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ሀገሮች ተጋብ ሆነና ብዙ ሮማውያንና ሰራውያን እየተሰደዱ ይመጡ ነበር ሕዝቲም በኮብርና በሰላም ተቀብሎ ልጆቻቸውን እያገባ ያስቀምጣቸው ነበር እጼ ዛን ቢዛን አርባ አመት ገዝቶ ልጁ ዘርአይ እጼ ደቀመሃሪ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በፋንታው ነገሠ እጼ ደቀመሃሪ በሀያ ዘጠኝ ዘመነ መንግሥቱ ወንድሙ ,ጋፋሌ ስለገደለው የአክሱም መማ ክራንና መኳንንት ልጁን ሰብስበው እጼ ቢጋማይ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ። እጼ ቢጋማይ አውራ አደገ ሂዶ ከፈረሰ

ላይ ወድቆ ንጉሠ ነገሥት ስሆን በአቤሴ ዘመን አሥራ ስለሞተ ልጁን ጻዮን ነግን አጼ ሕዝብ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ ነገሠ ።

አጼ ሆሀብ ሰገድም በጀነሙ አኩሀ በ22 ዘመን መንግሥቱ ድግ አጼ ሣን ጎት ኋላም ስለሞተ ከዕርሱ ቀጥሎ ልጁ አንዷር አጼ ተተመጠ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በአባቱ ዙፋን በፈንታው ሰገድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ሰሞት ነገሥ ሊሆን አጼ ሣን ሰገድም አስፈዘሰኝ ዓመት ነገሡ ለሞት በኢትዮጵያ ተብሎ ልጁ አልአሜዳ አጼ መድፈአለዷድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ አሰከ ሀገድ በ294 ክርስቶስ ከተወለደ ነገሠ አጼ መድፈ አርአጹም አስከ ሀገድ ውቅያኖስ ድረስ ወናቶ የንበራሀን ሀገር አለምቀ በጎንደሬ ንጉሥ ጋሬቅ ጃሎም እየሸሰመ ሊመሰስ ማሰንያ በርሃ ሰዶ አስኔ መሪሚት ያሜ ነፋስ ተንሰቶ በአሸዋ ቀብሮና ሞቶ ቀረ በዚህን ጊዜ ባሕርና በኢት ባለሀን ልጁን በ318 ዓ. ም. ላይ አጼ አሰበሃ ንጉሠ ነገሥ በኢት ዮጵያ መሬት አግዚአብሔር ተብሎ ነገሠ በአጼ አሰበሃ ዘመን በኢት መንግሥት ለማይ ዝርመን ምድር ፍሬሞን በሙ ክርስ ጀሰሰ ጳጳ በኢት ዮጵያ ሀገሮች ያሉ ነገሥታት ተገዘሰት ።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

የአጼ አብርሃና የአጼ አጽብሃ ዘመነ መንግሥት የአክሱም ዙፋን ክብሩ በክርስቶስ ስም እንደታደሰችና በአጼ አብርሃ ትእዛዝ የክርስቲያን ሕግ እንደጸና ።

አልአሜደ ስመ መንግሥቱ አጼ ሰይፈ አርእድ አብርሃና አጽብሃ የሚባሉ ሁለት መንታ ልጆች ነበሩት ። አብርሃ በሱባ ቋንቋ አማን ነው ወይም ሰላም ሆነ አጽብሃ ማነው ፡ ማን ሆነ ማለት ነው ይባላሉ የሀሴን ጕዳ የሆነች ሰመመ ንግሥቲቱ እቴ አህየዋ የተባለች እናታቸው ንግሥት ሶፍያ በምትወልዳቸው ጊዜ መጀመሪያ አብርሃ ሲወለድ ሰላም ሆነ ተብሎ ሳለ እንደገና አጽብሃ ብቅ አለ ማነው አሉት ስለዚህ አብርሃና አጽብሃ ተባሉ ።

እንደዚሁም ሆነ በተወለዱ በአሥር ዓመታቸው አባታቸው ስለ ሞተ የመጀመሪያውን ልጅ አብርሃን አጼ አብርሃ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው በአባቶቹ ዙፋን አነገሡው አስቀመጡት በዚህን ጊዜ እናቱ ንግሥት ሶፍያ በሙሉና በውስጥ ያለውን የመንግሥት አስተዳደር ለአብርሃ ሁለት አመት ያክል ታዘና ትመራው ነበር ። አጼ አብርሃ የሃያ ሁለት ዓመት ልድሜ ሰው ሲሆን እራሱ ጠቅሎ ወንድሙን አጽብሃ አልጋ ወራሽና ተጠባባቂ አድርጎ ያስተዳድር ጀመር ሕዝቡም በአስተዋይነቱና በፍርዱ ይደሰቱ ነበረ ። በዚህን ጊዜ በኢትዮጵያ ያሉ ካህናት ገድ በረከትና ማብሩን ስለአስቀሩ ወንድሙን አጽብሃንና የመር መሪውን ሃዲፉን ወደሲያምና ወደካማቂ ሀገር ወደጌዘር ላካቸው አጽብሃ ወንድሙና ሃዲፉ የሰባት ነገሥታትን አገር ድል አድርገውና አስገብረው አዲስ ንጉሥ በጕዛዎች ላይ ሹመው ሰባቱን ነገሥታት ማርከው ለአጼ አብርሃ አቀረቡለት አጼ አብርሃም ምርኮኞቹን ከወቀሰ በኋላ በነጻ ተለቀው እራት ሸህ የቀንድ ከብት ሰባት ሺህ የጋማ ከብት የሚሆን የተማረከውን ተመልሶ እንዲሰጣቸውና ከጥንት ከአባቶቻቸው የቆየውን የአስራት ግብር እንዲያመጡ መልሶ ላካቸው ከዚያም ወንድሙ ከነገሥታቸው ጋር ተስማምተው ይገዙና ገድ በረከቱንና አስራታቸውን በየአመቱ ይገብሩ ጀመር ።



የአክሱም ሃውልት



እጼ አብርሃ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በሃያ አሙሉ ጽዋ የሚባለ ሠ
ሠራዊት ፀገር ተጠባባቂ አድርጎ አምስት መቶ ሺህ ሠርዊ የሚባል
ሰዎ ሰዋቶ ወደኢዘበና ወደነባ ላካቸው እነሱም ከአራት ተከፍለው
ሰሜቸው አንደኛው መሃባ ሠርዊ ሁለተኛው ሙቴን ሠርዊ ሶስተኛ
ኛው ዳቁን ሠራዊ አራተኛው ዳቀሃራ ሠራዊ ይባላሉ እነዚህም
ከዶቶ የነበረውን የደዳንና የዳንጉላን የበጌንና የሀወንቴን ሕዝብ

ተቀማጥተው ድል ካደረጉ በኋላ ሕዝቡም እንግዳይፈልን ያልከፈሉ ውን አስራት ሁሉ ከተወገበት ቀን ጀምሮ እንሰጣለን ስላሉ በበላያቸው የአብርሃ ማህተም ያለው የወርቅ አክሊል ለንጉሣቸው እየሰጡ በምስራቅ በምዕራብ ፣ በደቡብና ፣ በሰሜን ያለውን ሀገር ሁሉ ከዳር እስከዳር እንዲገዛ አደረጉት በአጼ አብርሃ ዘመን መንግሥት የነበሩት ነገሥታት ሰባ አለቆች ሙቱ አስር ነበሩ ።

እንዲሁም ግብራቸውንና እጅ መንሻ በየዓመቱ ሲያመጡ በኢዛና ስም የተቀረጸውን ከወርቅና ከነሃስ የተሰራውን ዲናር ነበር የሚያመጡ እንጅ እንደአለቆቶች ነገሥታት በፊና ጎደር ሙከት አይቀበሉም ነበር ። እንደዚሁም ሆኖ አጼ አብርሃ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በሃያ ሁለት አመቱ በሶስት ሙቶ ሰላሳ ሁለት ላይ በሕዝቦች ከተሞችና በአክሱም የሚገኙት ከኒሣዎች ቤተመቅደስ ከአራት ሕግ ወደቅዱስ ወንጌል ሕግ በአራት መጽሐፍ ፊንታ ቅዱስ ወንጌል ከበግ መስዋዕት ፋንታ የስጋዶ ህብስት የወይን ውሃ እንዲሆን አጼ አብርሃ አዲስ ሕግ አወጣ በዚህን ጊዜ ብዙ አይሁዶች የአራት ክህናቶች እንቢ ወንጌል አንቀበልም ብለው ተከራከሩ ብዙችም አጼ አብርሃን እየተባደቡ ሞትና ግርፋት ያገኛቸው አቡሳውያን ፈላሲያን አበሾችና ፈላሶች ብዙ ናቸው በአሙቱ ሁሉም ከተስማማና ከተረጋ በኋላ አክሱም ጽዮን በወንጌል ታድሶ ተሰራች ለኢትዮጵያና የሀገሮች የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የክርስቲያን ማደሪያ ተብላ ተጠራች የመጀመሪያው ጳጳስ ጽንተ ሙሴን የባረኩት አቡነ ሰላማ ይባላል ታሪካቸው እንደዚህ ነው ።

በጢሮስ ሃገር ሜሮጲዮስ የሚባል የገዳክ ነጋዴ ተበበኛ የነበረ ሰው የኢትዮጵያን ሃገሮች ለማየት ዘመዶቹ ከሆኑ ከሁለት ልጆች ጋር መጣ እነዚህም ስማቸው ፍሬምናጦስ ኋላ ሰላማ የተባለ አድስዮስ ኋላ ሲድራክስ የተባለ እነዚህን አስከትሎ ሃመረ ሃይቅ ከሚባል ቦታ ላይ ሲደርስ የያዘውን እቃ ሽፍቶች ደብድበው ቀሙት ከዚያም ወደ አክሱም ደርሰው በሊቀ ካህናት (አፈታሜ ነው) እንበረም ቤት አደሩ ሜሮጵያስ ዩጂንስም ሽፍቶች በጣም ደብድበውት ነበርና በእድሜ የገፋ ሰው ስለነበረ ወዲያውኑ ልጆቹን ለሊቀ ካህኑ እንበረም አደራ ሰጥቶ አረፈ ። ሊቀ ካህን እንበረም አጼ ሰይፈ አርእድ ወደተባለው ወደአልአሜዳ ወስዳቸው በዚያም የአልአሜዳን ልጆች ኢዛናንና ሲዛናን እያስተማሩና እያሰለጠኑ ተቀመጡ በዚህን ጊዜ አጼ ሰይፈ አርእድ እንደሞተ ልጁ ኢዛና አጼ አብርሃ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ፍሬምናጦስና ሲድራስ በቤተመንግሥት በጣም የተወደዱ ባለሟል ሆኑ ።

ከእለታት አንድ ቀን ፍሬምናጦስ ወደሊቀካህን እንበረም ቤት
ሄዶ እንዲህ አለው የኢትዮጵያ ህዝቦች እንደ አራት ሕግ ትገሪዓለችዋ
ሥራዓታቸሁ ባህላችሁ እንደ እስራኤል ናቸው በኢየሱስ ክርስቶስ
በእግዚአብሔር ልጅ ታምናላችሁ ነገር ግን ተጠምቃችሁ ሥጋ ወደሙ
አትቀበሉም ።

ሊቀ ካህኑ እንበረም ለፍሬምናጦስ እንዲህ አለው ማዘረትን
አባቶቻችን ሊቀውያን አዲስ ኪዳንን የአቴ ሀንደኬ ባለሟልና ንግ
ሥት ብልፅላ ሀንደኬ ግን አመጡልን ነገር ግን ተጠምቀን ሥጋ
ደሙ ለመቀበል ግን ጳጳስ አልመጣልንም ስለዚህ አጼ አብርሃን
መደሙን ለመቀበል ግን ጳጳስ አልመጣልንም ከእርሱ ስልጣን ተቀብለህ
ሊማከረውና አንተ ከሊቀጳጳስ ዘንድ ሂደና ከእርሱ ስልጣን ተቀብለህ
ጳጳስ ሆንህ ና አለው ፍሬምናጦስም እሽ ብሎ እንደሔልከኝ አደርጋ
ለሁ አለው ከዚያም በአጼ አብርሃም ፍቃድ ለፍሬምናጦስ ብዙ የወ
ርቅ ዲናርና ክብር የተሰራ ድሪ ሰጥቶ ላከው እሱም ወደኢየሩሳሌም
ሄዶ ከሊቀጳጳሱ ከአባ አትናቴዎስ ዘንድ እንደደረሰ ስለኢትዮጵያ
ህዝብ ባህልና እምነት ነገረውና ሊቀጳጳሱ በጣም ደስ ብሎት ስሙን
ሰላማ ብሎ በመላ ኢትዮጵያ የገርች ጳጳስ አድርጐ ስልጣን ሰጥቶ
ላከው በፍቅርም ተሰነባብተው ተለያዩ ሰላማ ማለት ስሙን ከእግዚ
አብሔር የሚያስታርቅ ማለት ነው ።

አቡነ ሰላማም ወደኢትዮጵያ ተመልሶ መጥቶ በኢትዮጵያ የሚ
ኖሩትን ከአባ የጽላት ቤተመቅደስ ጽላታቸውን ባርኮ ከአራት ወደቅ
ዱስ ወንጌል ሀግ እቨገራቸው በበግ መስዋዕት ሰንዴና በወይን እንዲ
ሆን አደረገ ይሄም ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነ አጼ አብርሃ ንጉሥ ነገሥት
እንዲሆን አደረገ ይሄም ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነ አጼ አብርሃ ንጉሥ
ነገሥት በሆነ በሃያ ሰባት ዘመን መንግሥቱ በሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት
ዓ.ም ነው በዚሆን ጊዜ በየሃገሩ ያሉት ሰባት መቶ ከኒሣዎች ጽላቶቻ
ቸው ተባርኮ እንደገና ወደ ቤተ መቅደሳቸው ገቡ አቡነሰላማም ከሳቴ
ብርሃን የሚባል ስም ተሰጣቸው ።

በዚሁ ዘመን የቁስጥንጥንያ ንጉስ ቆንስጣ ወልድ ፍጡር ከሚ
ለው የአርዮስን ትምህርት ሲቀበል ስለነበርና ክርስቶስን የአንድ
ባህርይና ፍፁም አምላክነት አለው የሚሉትን የእስክንድርያውን
ሊቀጳጳስ አባ አትናቴዎስን ጥላቻ ስለነበረው ፍሬምናጦስ ከአባ አት
ናቴዎስ የቋቋሱና ሥልጣን ተቀብሎ ሄደ የሚባለን ሲሰማ ተናደ
ለአጼ አብርሃና ለወንድሙ ለአጿዛና እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጻፈላቸው
ቢክተሪዩስ ኮንስታንስ ማክሲሙስ አውግስጦስ ለኢዛናና ለሳይዛና ወንድሙ
ለኢዛና እግዚአብሄር የሰጠን ትምህርትና ማስተዋል ለሁሉም አለ

ያና ልቅድን ለሚፈልግ ሁሉ እንዲያደርስ ስሙን በአናንቶና በሮማው ምንም በተክርስቲያን መካከል አንድነት እንዲኖር ይገባል ። ከሽሙቱ የተሻረው አትናቴዎስ ፕሮቴስታንቶችን ሹም ልኳልና በተለይ ፕሮቴስታን ቱን መልዕክቱ ለተከበረው ጳጳስ በጴጥሮስ ወንበር ለተቀመጠው ለአባ ጊዮርጊስ ላኩትና የርሱን ነገር እርሱ ይጨርሰው የአባ አትና ቴዎስ ሥራ ግን ከናንቱ በቀር አለም አውቆት አላሰጠጋውም ስላለው እናንተን መጠጊያ አድርጎ ሊያታልል ይፈልጋል ፕሮቴስታንቶስ ጳጳስ ለመሆን ከፈለገ የሀይማኖቱን ታሪክ ለተሳሳቱት ገልጾ የቤተክህነትን ሀሳብ ሥርዓት በደንብ ተምሮ ወደ አገሩም መጥቶ ወደ ጵጵስናው ሥራ ይመለሳል ፣ በጣም የተከበራችሁ ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ያጠብቃችሁ ።

ይሉ ነበር ነገር ግን አጼ አብርሃ የፕሮቴስታንቶችን የሕያውነት ታሪክና የሚናገረው ቃል እውነትን የያዘና ወደእውነት የሚመራ መሆኑን ተረድቶ እያሰብ ፍፁም የእግዚአብሔር ልጅ ፍጹም የማይከፈል ባህሪይ ያለው ፍፁም አምላክ መሆኑን ተረድቶ ለደብዳቤው መልስ ይቅርና የአሪዎስን ትምህርት የሚከተል እሊንደሉ ሲል በአዋጅ ተናገረ አቡነ ሰላማንም ከሳቴ ብርሃን ብሎ ልዩ የወርቅ ወንበርና የወርቅ አክሊል ሰጣቸው ።

በእስክንድርያና በሮም ያለው ልዩነት እንደዚህ ነው እሌኒ የምትባል ክርስቲያኒቱ ቁንስጣንን አግብታ ታላቁ ቆስጠንጢኖስን ወለደች ቆስጠንጢኖስም የእናቱን ሃይማኖት ተከትሎ ክርስቲያን ሆነ ወላጅ ነው ቆስጠንጢኖስ የአባቱን የቁንስጣን መንግሥት በመረከብ ጊዜ የሮማው ንጉሥ ማክሰንስ በሰራዊቱ ታጅቦ ሊወጋ ለመነሳት ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በጣም ፈርቶ ነበር ነገር ግን ሌሊቱን በሰማይ ላይ የእሳት መስቀል ተስሎ በአጠገቡ መልአክ ቆሞ ጣቱን ወደመስቀሉ እያመለከተ በዚህ ምልክት ታሸንፋለህ አለው ይህን ህልም ለእናቱ ለእሌኒ ንግሥት ነገራት እሷም የሠራዊትህ ልብስና የፈረሶች እቃ ላይ የመስቀል ምልክት አድርግ አለችው እርሱም እንዳለችው አደረገና በጦርነትም ሠራዊቱ ተመውሶ ማክሰንስም ድል ሆኖ ሲሸሽ ሮማ አጠገብ ከሚገኘው ትብሮስ ወንዝ ላይ ወድቆ ሞተ ከዚያም ቆስጠንጢኖስ ሌሎችንም ጠላቶቹን በመስቀል ምልክት ድል ካደረገ በኋላ ክርስትያን የሰራው ቁርኝን ጠቅሎ ይገዛ ጀመር ፣

በዚሁ ዘመን ቄሳሮች ሲሰቃዩ ሲሰደዱ የነበሩ ክርስቲያኖች በቆስጠንጢኖስ ዘመን መንግሥት ያዘታቸው ተመልሶ እንደልባቸው

እንዲያስተምሩ እንዲሰብኩ ሲል አዋጅ ተነገረ ቆስጠንጢኖስ ሮማንም መቀመጫ በሚገባበት ሰዓት ወደቁስጥንጥንያ አዛውረው ቁስጥንጥንያ በሌሎች ቢዛንስ ይባላል ይኸም አገር በማለት ብራንትያ ይባላል ። በዚሁ ቢቆስ ጠንጢኖስ በመንግሥቱ ሰው ሁሉ የወደደውን ያምልክ ብለው ለሃይማኖት ነጻነት ሲሰጥ በዚህን ጊዜ ክርስቲያኖች ከአራት ተከ ፈሉ እነዚህም አንደኛው የሮማ ሊቀ ጳጳስና የጴጥሮስ መንበር ሁለተ ኛው የእስክንድርያ ሊቀጳጳስና የማርቆስ መንበር ሶስተኛ የኤፌሶን ሊቀጳጳስና የዮሐንስ መንበር አራተኛ የአንጾኪያ ሊቀጳጳስና የጴጥ ሮስ መንበር እየተባሉ ተቀመጡ ።

በእስክንድርያ የመጀመሪያው ጳጳስ አባ እለ እስክንድሮስ ነው በዘመኑ ቅድስናው አርዮስ የክርስቶስን አንድነት ሳይክድ ከአብ ጋር ያለውን እኩልነት የሚክድ ትምህርት አመጣና እንዲሁ እለ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፈቃድ አለምን ለማዳን የተፈጠረና የተላከ መልእክተኛ እንጂ እራሱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ትክክል የሆነ አምላክነት የለ ውም እያለ በየቦታው እያስተማረ ተከታይ አብዛ ስለዚህ የዚህን ትምህርት ቆስጠንጢኖስ በኒቅያ በተባሌ ተመልክቶ ለመወሰን 318 ሊ.ቃውንት ሰብስቦ ሁሉም አርዮስን አወግዘው ለዩት እርሱ ራሱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ የሰውን ሥጋ እንደተዋሃደና ከአምላክነቱ ባህሪይ እንዳልተለየ የሚገልፅ መጽሐፍ ለፈው ጸሎት ሃይማኖትን አዘጋጅተው በአዋጅ አፀኑ በተባለው ተከራከረው የረቱት ሊቀጳጳሱ አለእስክንድሮስ እለ ተባለው አትናቴዎስ በደስታ ወደ እስክንድርያ ተመለሱ ። በርም ግን የሚነሱት ቂጣሮች የአርዮስን ትምህርት እየደገፉ እስከ ቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ በመንግሥት ቆየ በእስክንድርያ በርም ሊቃውንት ጳጳሳት መንበር ልዩነት የነበር ስለዚህ ነው ቆንስጣ ለእጼ አብርሃ በጻፈው ደብዳቤ ላይ አቡነሰላማን መልሳችሁ ወደእኛ ላኩት ያለ እጼ አብርሃ ከወንድሙ ከኢዛና ጋር እየተማከሩና እየተስማሙ የኢ ትዮጵያ ንጉሠነገሥታት ቤተ መቅደስ በወንጌል ከአደሳቸውና ሀገሪቱንም ክርስቲያን ካደረጉ በኋላ ወንድሙን ኢዛናን እጼ አፅብሃ ንጉሥ ነገ ሥት ዘኢትዮጵያ ብሎ በዙፋኑ ላይ አስቀመጠው ከዚያም ለእኔ እርጅ እመት በቤታቸው ሆነው እንዲያገለግሉኝ እኔም በፋንታዬ እንተን በዋ ጁም ልብ ለማገልገል ተነስቻለሁ ብሎ እጼ አፅብሃ የበላይ እጼ አብ ርሃ የበታች ሆነው አምሳ ዘጠኝ አመት በድምር ዘጠና ዘጠኝ አመት ኢትዮጵያን በፍቅርና በደስታ ገዝተው በተወለዱ በመቶ ዘጠኝ አመ ታቸው ሁለቱም ጥዋትና ማታ በአንድ ቀን ሰለሞቱ በክብር በአክሱም ጽዮን ደጀሰላም 409 ዓ.ም. ሥርዓተ ቀብሩ በደንብ ተፈጸመ ።

ከዚህ በኋላ የኢዛና የአጼ አልዓሚዳ ልጅ አሰፍሀ አጼ ዋዜብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በ409 ዓ.ም. ነገሠ፡ በዚሁ በአጼ ዋዜብ ዘመነ መንግሥት በሮም መንግሥት ላይ ቄሳር የነበረው ትልቁ ቴዎድዮስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስና መንበር የተቀመጡት ደግሞ አባ ቴዎፍሎስ ነበሩ፡ በሮም አባ አምብሮሲዮስ በቁስጥንጥንያ ከአንጾኪያ ተዛውሮ አባ ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት የሚባሉት ነበሩ፡ ቴዎድስዮስም በኒቅያ ጉባኤ በ318 ሊቃውንት የወሰኑትን የተዋሕዶ ሃይማኖት እንዲፀና አደረገ፡ አጼ ዋዜብም ከዚሁ ከታላቁ ቴዎድስዮስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸውና በዋንጋው በደብዳቤ ይገናኙ ነበር ነገር ግን ቴዎድዮስ ሙቶ ልጆች ስለተነሱ ከሮም መንግሥት ጋር የነበረው ግንኙነት አቋረጠ። ነገር ግን ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ የሚባል ተነሥቶ በሮም እንደነገሠ የቁስጥንጥንያ ሊቀጳጳስ የነበረው አባ ንስጥሮስ ለክርስቶስ ሰውነታዊና መለኮታዊ የሆኑ ሁለት ባሕርያት ስላሉት በሰውነቱ ከአብ አይወለድምና የፀጋ ልጅ እንደዚሁም በመለኮቱ ከማርያም መወለድ አይችልምና ማርያም ወላዲተ አምላክ አትባልም እያለ ክርክርና ጠብ ነበረና የዚሆን ጉዳይ በ424 ዓ.ም. በኤፌሶን ግዛት ከተማ ሊቃውንቱ እንዲሰበሰቡ ተደረገ ከኢትዮጵያም የተላኩ ነበሩ፡ በዚሁ ጉባኤ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አባ ቄርሎስ ነበሩ ሊቃውንቱም ከተከራከሩ በኋላ ክርስቶስ ሰው እንደሆነው አምላክ ነበረው አካል ከተዋሐደ አንድ ባሕርይ ነው ብሎዎም ሥጋና መለኮትን አንድ ያደረገ ስለሆነ አምላክ ነው። እናቱም ወላዲተ አምላክ ትባላለች ብለው ንስጥሮስ ተረቺ ቄርሎስ አረቺ ሆነው ተለያዩ ንስጥሮስ ታስሮ ወደ ደብረ እስያ ተላከ እንደዚሁም በዋንጋው የተለያዩ ሃሳቦች ያሉ ልጆች ተያ እየተነሱ ብዙ ክርክር ደም መፋሰስ መታሰር መሰደድ ደርሶባቸዋል።

አጼ ዋዜብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በዙፋን በመግ በ31 ዘመነ መንግሥት ልጁ አርፍድ አጼ አላሚሪዶስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በ440 ዓ.ም. በአባቶቹ ዙፋን ተቀመጠ እሱም አስራአንድ አመት ገዝቶ ሲሞት ልጁ አምዳ አጼ ሳላዶባ-ዛ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ አልአሜዳ የሚሉትም አሉ በአጼ ሳላዶባ-ዛ ዘመነ መንግሥት በሮም በነገሠው በመርቅያን ዘመነ መንግሥት በምስራቅ ቁስጥንጥንያና በሮም ለክርስቶስ የሰውነትና የመለኮት ሁለት ባሕርያት አሉት የሚሉና በእስክንድርያ የሰውነትና የመለኮት ባሕርይ አንድ ነው የሚል ክርክር ተነሳና በንጉሡ መርቅያን ትእዛዝ በጉባኤ እንዲቆይ ተወሰነ ይሄም ጉባኤ በኬልቄዶን ግዛት

636 ሊቃውንት ተሰብስበው በሁለቱም ክፍል ዶጋፊ ስለአገኘ የሮ-
ማው ሊቀ ጳጳስ ልዮን ይመስክር ተብሎ ተወሰነ እስቶልዩን ሁለት
ባህሪይ አለው ብሎ የካቶሊክን ሃይማኖት አመነ ሊቀ ጳጳሳቱም አንድ
ባህርይ የሚለውን ዲዮስቆሮስን ገዘቱት እሱም ልዮንንና ደጋፊዎችን
አወገዛቸው በዚህን ጊዜ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስን አባ ዲዮስቆሮስን
በመርቅያን ሚስት በብርክልያ ትእዛዝ ተደብድቦ ወደ ጋንግራ ደሴት
ሄዶ እንዲታሰር ተደረገ ነገር ግን ለነአባ አትናቴዎስ እና አባቄርሎስ
የተጋደሉበት የአንድ ባህሪይ ሃይማኖት በእስክንድርያና በኢትዮጵያ
ጸንቶ ኖረ ። እጼ ሳላደባ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በአስር ዓመቱ በ461
ዓ.ም. ስለሞቱ ልጁ እለማሬስ እጼ እለአሚዳ ተብሎ ነገሠ ።

የልዮን ተከታዮች ወልድ በመለኮቱ የመለኮትን ሥራ በእሩሱ
የሰውነትን ሥራ ያደርጋል ስለዚህ ሁለት ባህርያት ያለው ነው የሚ-
ሉት ካቶሊክ ተብለዋል ። የዲዮስቆሮስ ተከታዮች ደግሞ የእግዚአ-
ብሔር ቃል ከሥጋ ጋር ከተዋሃደ ሥጋና መለኮትን አንድ ባህሪ ሆነ
እንጂ ሁለት ባህርያት ይዞ አልተከፈለም የተዋሃደው ሥጋ ከበሃሪ
መለኮቱ የማይለይ አምላክ ነው የሚሉ ተዋህዶች ናቸው ይህም ትርጉም
ኦርቶዶክስ ተብሎ በሌላ ሃሳቦች ተለይቶ በግሪክ በአርመን በመስኮብ
ቤተ መቅደስ ፀንቶ እስከዛሬ ድረስ አለ ።

እነዚህ የሮማ ሊቀ ጳጳሳትና የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት እንደዚ-
ሁም የቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳሳት በሃሳብ እየተለያዩ ለክርስቶስ አንድ
ባህሪ ነው ያለው የለም ሁለት ነው መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ
ያንሳል የለም እኩል ነው ክርስቶስ በግብሩ ሥጋ አረገ የለም በረቂቁ
ነው እየተባባሉ አዲስ ሐሣብ እያፈለቁ በየጊዜው ብዙ ፍጅትና ሁከት
ጠብና ክርክር ሆነ በዚህን ጊዜ ንጉሡ ለወደደውና በሚነግሥበት
ሰዓት ለተባበሩት እየሆነ የጠላውን ክፍል ማሰር መግደል ሆነ ከዚያም
የሃሳቡ ተከታይ የነበረው መታሰርንና መገረፍን ፈርቶ ይሰደዳል ከዚህ
ፍራቻ የተነሳ ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው የገቡትን የዘጠኙን ቅዱሳን
ታሪክ ከዚህ ቀጥዬ አቀርብላችኋለሁ ። ፀሐፊውና አዘጋጁም ከእነዚ-
ማይ ሲራክ መፅሐፍ ከግእዝ ወደአማርኛ የተረጎምኩት መሪራስ
አማን በላይ ።

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

የአጼ አልአሜዳ ዘመነ መንግሥት ዘጠኙ ተሰአቱ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡና የአጼ ካሌብና የልጃቸው የአጼ ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት የአጼ ሣላዶ ባሕሳ ልጅ አልሜርሲል አጼ አላሜዳ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በነገሠ በ461 ዓ.ም. ላይ ክርስቶስ መለኮትና ሰውነቱ ተዋሀዶ አንድ ባህርይ ሆኗል የሚሉት ወገኖች ክርስቶስ በመለኮቱ አንድ ባህርይ በሰውነቱ አንድ ባህርይ በሚባሉት ወገኖች እየተሰደዱ ከአጼ አብርሃ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ አንድ ባህርይ እያሉ ወደአመኑት ህዝቦች ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው መጡ እነዚህም ፡

1ኛ ዘሚካኤል አቡነአረጋዊ የተባሉት ከሮም

2ኛ ጰንጠሌዎን

3ኛ የመስፍያኖስ ቄሣር ልጅ ይስሐቅ ገሪማ የተባለው ከሮም

4ኛ ሊቃኖስ ከቁስጥንጥንያ

5ኛ ይምአታ ከቆስያ ኢጣሊያ

6ኛ ፅሕማ ከአንጾኪያ — (ሶርያ)

7ኛ ጉባ ከኪልቅያ ግሪክ

8ኛ አፍጼ ከእስያ

9ኛ አሌፍ ከቂሣርያ

እነዚህ ተሰአቱ ቅዱሳን አባሰላማ ከሣቴ ብርሃን የአስተማረውንና የሰበከውን የአንድ ባህሪያ ተዋህዶ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሰሜን ክፍል በሚገኙት አውራጃዎች ተበትነው በአትና ገዳም እያበጁ አስፋፉ እንዚህንም እስከዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ያከብራቸዋል ። ከነዚህም በህዝብ ዘንድ የታወቁትና የተወደዱት አቡነ አረጋዊ ናቸው እነሱም በደብረዳሞ ገዳማቸው ገድመው እስከዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ እያከበራቸው ይሳለሙዋል ። አባ አረጋዊ የደብረ ዳሞን ገዳም ሲገድሙ ሌሎች ደግሞ

አባ አሰፋ የሀበሀን — ኢይሱስ ገዳም

አባ ፅሕማ የስድዶን ገዳም

| | | |
|---|---|---|
| አባ ገሪማ | የመደራ | ገዳም |
| አባ አፍጼ | የየሐ | ገዳም |
| አባ ጰንጠሌዎን | የአክሱም | ገዳም |
| አባ ሊቃኖስ | የደብረቆናጽል | ገዳም |
| አባ ጉባና አባይምዓታ | የገርአልታን ገዳም | |

እንደዚሁም በየቦታው ስማቸውን ያላገኘሁትን ብዙ ገዳሞች ገድመዋል ከዚህ ላይ ልታውቁት የምፈልገው ገዳም የተጀመረ በነዚህ አይደለም ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በክርስትና ሃይማኖት የተስፋፋ ማለት ነው እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረሊና ገዳም በደብረሬዳዋ በጾጋ እስጢፋ በትንንሽ ገዳሞችና ተራራዎች ነበረ በዚያ አለምን ንቀው የሚኖሩትን ባህታዊዎች ሁሉ በአንድ አምባ በእግዚአብሔር ስም ብቻ እንዲያደምጡ አድርገዋል ምንኩስና የመጣ ግን በነዚህ በዘጠኙ ቅዱሳን ዘመን ነው ከዚያ በፊት የነበሩት ባህታዊ ብቻ ነው ። የሚ ባሉ በተሰማሩ ቅዱሳን አማካኝነት በብዙት የኢትዮጵያ ሃገሮች ባለበ ሊማሩት ፍፁም ክርስቲያን ሆኑ እምነቱ ተጠመቁ ፊት በአሉት ከቡ ጻህ በእምነ ካህናት ሲሰበኩና ሲማሩ የነበር አሁን ግን በቅዱስ ወን ጌል አስተማሪዎችና የምስራች ተናጋሪዎች ይመሩ ጀመር የእግዚአ ብሄርንም ህግ የሚያከብሩ ትእዛዙን የሚፈጽሙ ሆኑ ቅዳሴውና የማ ህሌቱ ዜማ ግን ከየሁት አልወጣም ይኼውም ዛሬ ባለንበት ዘመን የቡ ድሃ መነኩሴና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመዘምራኑ ትርጓሜው ቢሊያም ዜማው አንድ ነው ከተሰአቱ ቅዱሳን በፊት ቺያጼ በጂያ የሚ ባሉ ነገሮች ነበሩ እንዚህም ነገሮች ከአራት ለየት ብለው የቡድሃን ሃይማኖት የሚከተሉ ነበሩ ነገር ግን በተሰአቱ ቅዱሳን ስብከት እም ነው ፍጹም ክርስቲያን ሆኑ ።

በዚሁ ዘመን የነበሩት ንጉሡ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ አጼ አልአሚዳ አስፈሁሰሽ አመት ገዝተው በመነኩሳቱ ስብከት የዚህን አለም ደስታ ንቀው መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለታዜና (ቴዎና) ለቀው መንኩሰው ገዳም ገቡ ታዜናም አጼ አየዛና ሃሉን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስዩመ እግዚአብሔር ተብሎ በአባቱ ዙፋን ተቀመጠ እሱም ብዙ ልጆችን እንደወለደና አስር አመት እንደገዛ ድንገት ታሞ ስለሞተ ታላቁ ልጅን ካሌብ የአክሱም መንግሥት መኳንንት በአባቱ ዙፋን አስቀ መጡት ካሌብ ንግሥና ለሚፈልግ ሰው እንጂ እኔ አልነግሥም ብሎ ነበር ካህናትና መኳንንት እግዚአብሔር ፈቅዶልሃል አንተ እያለህ ሌላ የንጋሲ ዘር ከዙፋን ላይ አይወጣም ብለው ስለመከሩት የመንፈሳዊ

አባቶቻቸውን ታሪክ ሰምተው ፍጥነዋል አጼ እለአጽብሐ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መሲሃ እግዚአብሔር ተብለው በ6ኛው ዓ.ም. ነበሩ ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ካሌብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በሰላሳ አምስት ዘመን መንግሥታቸው ሃይማኖቱ አይሁድ የሆነ ዱኖዋስ ፊንሐስ በሚባል ዘመነ ንጉሥ ክርስቲያኖች ተገፉቸው እየበዛ ስለሄደ አይቶ ከአረብ ሺህ በላይ የሚሆኑትን ክርስቲያኖች በግዛቱ ውስጥ የነበሩትን ሁሉ ገደላቸው ከዚያም የናግራንን ንጉሥ አሬታስን ለእኔ እንጂ ለአክሱም መንግሥት እንዳትገዛ ብሎ መልእክት ላከበት እሱም እሺ እንዳለው ናግራን ከተማውን ሌት ፈንሐስ መጣና ከበባት በእሳትም አቃጠላት መነኮሳቱንና ካህናቱን ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን እስከ ልጆቻቸው ገድሎ አስቆፍሮ በውስጡ እሳት አስነድዶ ክርስቶስን እንክድም ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደእሳቱ እያስጣለ አቃጠላቸው ንጉሡን አሬታስን እስከዚ ተሰበ ክርስቶስን ካድና ለማርያም ጣዖትህንም ልፍቀድልህ አለው አሬታስም ለፈንሐስ እንደዚህ አለው እንዳንተ ያለ አታላይ ከሃዲ አምላኩን ንጉሡን ያከዳል እንጂ እኔና እንደእኔ ያሉ አሙኝተኞች አምላካቸውን ክርስቶስን አይክዱም አለው በዚህን ጊዜ ተናዶ የአመንትን አምላካቸውን የካዱትን ሁሉ በእሳት አቃጠላቸው አሬታስን ግን አንገቱን አስቆረጠ በእሳት አቃጠለው መጨረሻ በስማይትንት አረፈና አሬሳውን ወደ እሳቱ ቢጥሉት እሳቱን አጠፋው በዚሁ በናግራን አልቂት ያለቁት ክርስቲያኖች ሃያ ሰባት ሺህ ነበሩ ይህን ሁሉ የቁስጥንጥንያው ንጉሥ ዩስቲኖስ ሰማና በጣም አዘነ ዩስቲኖስ — የስጢኖስም ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባ ጢሞቴዎስ አስትራቦስ እንዲህ ሲል ጻፈለት ለአክሱም ንጉሠ ነገሥት ደብዳቤ ብትጽፍለት የአንተን የአባቱን ምክር ይሰማልና በናግራን የተገደሉትን የምእመናንን ደም በሚገባ ይበቀላልና ጻፍለት ብሎ መከረው ።

የእስክንድርያውም ሊቀጳጳሳት አባ ጢሞቴዎስ ዩስጢኖስ እንደ ነገረው ለአክሱም ንጉሠ ነገሥት ለአጼ ካሌብ ላከ፤ አጼ ካሌብም የተላኩትን መልእክተኞች በክብር ተቀብለው ከኢንጋዶቻቸው በኋላ ጀልባና አስደስተው ወደሃገራቸው እንዲመለሱ አደረጉ ።

አጼ ካሌብም በእያላ በክሊስማ በዱርሲ በቀልዝም በአዶሊስ ቢታጁሩ በበርበር ያለውን የጁዋ ጦር በመርከብ ሆኖ ወደአረብ እንዲ እንዲሻገር ትእዛዝ አስተላለፉ ከዚያም ወደአክሱም ፅዮን ወርቅ በተለበጠ ሰረገላ ሆነው ሄዱ ከቤተክርስቲያኑ እንደደረሱ ሲብስ መንግሥታ

ቸውን አውልቀው በርናስ ለብሰው ወደአምላካቸው እንዲህ ሲሉ ፀለዩ
እግዚአብሔር ሆይ ሁሉን የፈጠርክ አልፋ አእላፋት መላእክት የሚገ
ዙልህ ኪሩቤልና ሱራፌል የሚያመሰግኑህ የጌቶች ጌታ የንጉሶች
ንጉሥ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሰውን ከአፈር ወደ
ክብር ይመልሰው ዘንድ ልጅህን ኢየሱስን ወደኛ የላክህ እኛን ለማዳን
ሰው በሆነው በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ምክንያት ይህ ፈንሃስ ከሃዲ
ያደረገውን ሁሉ አይተሃል ክርስቲያኖች እንደታረዱ ቤተክርስቲያኖች
እንደተቃጠሉ አይተሃል ስለዚህ ከዚህ ወጥቼ የክርስቲያኖች ጠላት
አይሁዳዊውን በስምህ አጠፋቸዋለሁ በክርስቶስ ሃይል ደምስሼ ድል
አደርገዋለሁ ። ለወገኖቼ ለምእመናንና ለአንተ ለፈጣሪዬ ቀንቻለሁና
አታሳፍረኝ ከሃዲአቱ ብላት ግን ልመናዬን የማትሰማ ከሆነ ከአለሁበት
ግደለኝ አሌቱ ምድርህን አንተ ለማያውቁ አሳልፈህ አትሰጠኝ ከዚህ
በሉት በኋላ በባሕር ጦር ይዘው መቶ ሰባአራት መርከብ አሰልፈው
ወደየመን ዘመቱ ከዚያም እንደደረሱ አጼ ካሌብ ከመርከብ የአይሁድ
ንጉሥ ፈንሃስ በየሱስ ሆነው ብዙ ቀን ከተዋጉ በኋላ ሁሉም ተርበው
ሳለ ፈንሃስ ከጥቂቶቹ ወታደሮች ጋር ዕረፍት ለማድረግ ሲሄድ የአጼ
ካሌብ ጀዋ ጦር እህል ፍለጋ ሄደው ሳሉ ተገናኙ ከዚያም የፈንሃስ
ወታደሮችን ገድለው እርሱን አስረው ተሸክመው ወደአጼ ካሌብ አመ
ጡት ከዚያም አጼ ካሌብ እግዚአብሔርን አመስግነው ፈንሃስን አስረው
በእሱ እየተመሩ የሳባን ንጉሥ ወግተው ድል አድርገው ገደሉት ።

ከዚያም የፈረሱትን ቤተክርስቲያን እንዲሰሩ አደረጉ በዚያም በሳባ
አብርሃ የሚባል ንጉሥ ጭግራን የሚሾም የኢፌታስን ልጅ ሁሩዳን
በዛፋር አርእያትን የሰነአ ንጉሥ ብለው አንግሠው በሰላም ወደአክ
ሱም ተመለሱ አጼ ካሌብም ለእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት ለአባ
ጢሞቴዎስ የድል እድራጎታቸውን ደብዳቤ ጻፉላቸው በክርስቲያን ሀገ
ሮች ታላቅ ደስታ ሆነ ። አጼ ካሌብ ወደአክሱም ዋና ቤተመንግሥታቸው
እንደተመለሱ ለእግዚአብሔር ምን ላድርግለት እያሉ ሲያስቡ ከርመው
ንጉሥ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአርበኛው ዘመናቸው መን
ግሥታቸውን ለልጃቸው ለገብረመስቀል ሰጥተው ይህን ዓለም ንቀው
ልብሰ ምንኩስናቸውን የውሃ መጠጫ አንድ ትምሕና አንድ ምንጣፍ
ብቻ ይዘው አባ ጰንጠሌዎን ገዳም አጠገብ ካለው ዋሻ ውስጥ ገብተው
እየፀለዩ ተቀመጡ ሁለተኛም ወጥተው ዓለምን ላያዩ ማሉ ቤተ
መንግሥታቸውን ለቀው በሚሄዱበት ጊዜ የንግሡበትን ዘውድና በትረ
መንግሥታቸውን ለኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳሳት ለአባ ዮሐንስ የጌታችን የኢየ
ሱስ መቃብር ደጃፍ ይሰቀሉልኝ የሚል ደብዳቤ ጨምረው ላኩላቸው

ለአጼ ካሌብ እንዲህ የሚል በግእዝ ተጽሪለላቸው ሰላም ለካሌብ ትእምርተ ሀድግታ ለብሶሉ እንተ ፈነው እክሊሉ በኢየሩሳሌም ይሰቅሉ ዝንቱ ሃይል እይትመነሀ በሃይሉ እመ በእደው ሠራዊተ ሳባ ተቀትሉ ዘኢንበየ ይትርፍ እሃዶ እምእሉ ።

አጼ ካሌብ በመነኑ ጊዜ በዙፋናቸው ላይ ተቀምጦ የኢትዮጵያን ሃገሮች እንዲገዛ የፈቀዱ ገብረመስቀል የሚባለውን ልጃቸው ነበር ነገር ግን መጣፍንቱና መኳንንቱ ተማክረው ታላቁ ልጃቸው ቤተ እስራኤል የሚባለውን በአባቱ ዙፋን ላይ አወጡት በዚህን ጊዜ የቤተ ክህነቱ ክፍል እሳቸው አጼ ካሌብ የፈቀዱለት ገብረመስቀል ይነግሳል እንጂ ይሄኛው ቤተእስራኤል አይገዛም በማለት አንድ ወር ከተጣሉ ውቁና ከተከራከሩ በኋላ አቡነ አረጋዊ አባቱ የፈቀዱለት ይነግሳል እንጂ ያልፈቀዱለት አይነግስም ብለው ከቦታቸው ተነስተው እስከም ድረስ መጥተው ስለተናገሩ ገብረ መስቀል አጼ እለሃታ ዘ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ በአባቱ ዙፋን ተቀመጠ አጼ እለሃታ ቤሳ ልም ታሪክ ነገሥቱና ገድሉ አጼ ገብረመስቀል ይጸኑል እረ ሰውም ስመመንግሥቱን ትቶ አጼ ገብረመስቀል በሉኝ ብለዋል ። አጼ ገብረ መስቀል አቡነ አረጋዊ በሚኖሩበት በደብረ ዳሞ ተራራ ወጥቶ ከአቡነ አረጋዊ ቡራኬ ተቀብሎ ሲያበቃ አባቴ ከዚች ቅድስት ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን ልሰራ ይፍቀዱልኝ የምሰራበትንም ቦታ ለይተው ያሳዩኝ ብሎ ጠየቃቸው አቡንአረጋዊም እኔ አይደለሁም የምፈቅድልህ የሰማዩ አባታችን እግዚአብሔር ፈቅዶልሃል በዚህች ሥፍራ ላይ ስራ ብለው ተናገሩት ።

አጼ ገብረመስቀል ቤተክርስቲያን ተሰርቶ እስከሚያበቃ ሁለት አመት ሙሉ እብሮ በሰረገላ በከብት እንጨትና ድንጋይ እየተጓዘ ወይተራረሙ እየወጣ ዛማረና በተዋበ እሰራር ተሰርቶ አቡታ እንደአበቃም ብዙ የወርቅ አልባሳት የብር ፅዋ ፃህል መስቀል ዕና በወርቅ የተጻፉት መጻሕፍቶች ለቤተ ክርስቲያንዋ ሰጠ ከዚያም የኋሚቤታችንን ታቦት አስገብቶ ቅዳሴውን አቡነአረጋዊ ቀድሰው ጳጳሱና አጼውን አቁረቡ ከቅዳሴው በኋላ ሳገለገሉ አብረው ለደከሙ መኳንንት ግብር ከአደረገ በኋላ ብዙ ሽልማት በጥቶ አስደሰታቸው ገድለ ያሬድ ይገልጻል ።

## የቅዱስ ያሬድ ታሪክ

በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት መዘገበ ክብር በምትባል መንደር በአክሱም ከተማ የሚኖር የአክሱም ካህን ነበረ ይሄውም ካህን ዘበዘብ

ቅዱስ ከመባሉ በፊት አዳም ይባል ነበር እናቱም ሌዊ ከሌዋውያ ነገድ የምትወለደውን ትውክልያን አግብቶ ድንን ወለደ ድን ማለትን ሙሉ ስምንት ጊዜ በሰባ ማለት ሲሆን በግእዝም ሌላ ትርጓሜ ተሰቶት ይገኛል ያሬ ውም እንተርጉር ማለት እርሱም ለምንተኛውን ልጅ ወይም የመጨረ ሻውን ልጅ ድንን ይሰጥቅ ለሚባል ለህጻናት አስተማሪ ስጠው ግን በዚህን ጊዜ ዘዝበ ቅዱስ ስለሞተ እናቱ ትውክልያ ለወንድሟ ለአባ



ያሬድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመዝሙር አባት

ጌዲዮን እያስተማረ እንዲያሳድገው ሰጠችው አባ ጌድዮንም የእስራ ምን ማብዝና ተቀብሎ ህጻናቱንም እያስተማረ በእስራም ፀሮን ትጥር ውስጥ ይኖር ነበር ድኅም ከእንጦ ጋር በድስት አመት ተቀምጦ ሳሞት መድኅም ይቅርና ፊደል እንኳ ለይቶ ማወቅ አታተው በዚህን ጊዜ ህጻናት ጓደኞቹ አንተ ደደብ እያሉ ስለሰደቡት እንጦንም አባ ጌዲዎን ለምን እንደጓደኞችህ አትቀፅልም ብለው ስለደበደቡት ትምህርትም እንደ ማይገባው ተስፋ ቆርጦ ወደ መደባይ ሃገር ከእንጦ ወፍተ ሲሄድ ከመንገድ ላይ ሃይለኛ የሆነ ዝናብ ጣለና ማይከራቹ ከሚባል ምንጭ አጠገብ ከአለ ትልቅ ዛፍ ስር ተጠጋ ።

ከዛፉ ስር እንዳለ በትምህርት ከጓደኞቹ ሁሉ እንደሆኑ ለኢሉ እግዚአብሔር ለምን ለትምህርት እንጦሉን እንዳልከፈተለት ሲያስብ ሲያማርር ሳለ አንድ ትል ጉንዳን የሚለውም አሉ ጉንዳን ካሉ ሆኔል ፍሬ ትል ካሉ ማንጉን ተሸክሞ ከመሬት ወደዛፉ ለመውጣት ስድስት ጊዜ ወደዛፉ ሜፍ መጥቶ ማንጉን በዛፍ ቅጠል ላይ ሉጉንጉን ሲያዘጋ ያየዋል ከዚያም እምላኬ ምንው እኔንም እንደዚህ ትል ብትረዳኝ ብሎ ገና ልመናውን ሲጀምር ትሉ በድስት ጊዜ ወድቆ በሰባተኛው ቀጥታ ወደዛፉ ሜፍ መድረሱን ያስተውላል እኔም በድስት አመት ነው ትምህርት አልገባኝ ብሎ የነበረ አሁን ግን ብመለስ እግዚአብሔር እእምሮዬን ለትምህርት ይከፍትልኛል ብሎ አምላኩን ተማምኖ ሰሀቱ ቱንም ተረድቶ ወደ አክሱም ተመለሰ ከዚያም እንጦን ይቅር በሉኝ ብሎ ከእግሩ ሥር ወድቆ እንጦትየውም ይወደው ስለነበረ እቅፎ ሳመው ትምህርቱንም እንዲቀጥል ፈቀደለት ።

ድኅም ወደቤተ ክርስቲያን በመግባት አምላኩን ሲያመሰግን የሚሰሙት ካህናት ሁሉ ይደነቁና ይገረሙ ነበር ።

መንፈስ ቅዱስም ተሰጠውና ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳንን በየ ቀኑ ወራቶች ውስጥ አጠናቆ አውቆ መተርጐምና ማዚም ቻለ በእ ብራይስጥና በግሪክ ቋንቋ የተጻፉትን መፃህፍት ወደ ግእዝ እየተረጐመ ቀኗቸዋል በዚህን ጊዜ ገና በልጅነቱ ሳለ እንደአባቱ እንጦንዮ አባ ጌዲዎን እረቀና የእንጦን ሥራ ይዞ ያስተምር ጀመር ከቦሊያኑ ሃገር ችና ነገዶች ትምህርቱን ለመማር ድምፁን ለመስማት ይመጡ ነበር የነቢያት አምላክ የያሣርያት ጌታ የቅዱሳን አባት እግዚአብሔር በእ ማረና በጣም ድምፅ ለመመስገን ወደ ድጓ ድጓን የሚያስተምሩት ድምፃው ያን የሆኑ ሶስት ወሮች ሳኩለት እነዚህም ወሮች በድጓ ፊት ሰሩት በሚገኘው ወይራ ዛፍ ላይ ሆነው ለሰላሳና ልብን የሚመስጥ መንፈስን

የሚያደርስ እጹብ ዜማ አሰሙት ከደቀመዛሙርቱ ጋር የሚጠጣ ቃሉም እን ዲህ ይላል "ያሬድ ያሬድ አንተ አንተ ትርጓሜው ከሰባ ወደአማርኛ ሲተረጎም የዜማ ባለቤት በጊዜ ተደሰት ነበር የሚል በሚስዝ ይማም ሲተረጎም የዜማ ባለቤት ከርስ እንተ ሪትክ ወበዙኅተ አጥባት "ብፁዕ ወብፁር ያሬድ ብዕሲት ከርስ እንተ ጸረከ ትር ሚጠባም የቢቃሁና የተባረከ እንተ እለ ያጠባከ" አሉት ይላል ያሬድ የተሾሙትም ዞሮ የቤቶች ያሳደገዘ ሙቶች የቤቴ ናቸው ይላል ያሬድ ተጊሠመ ልማን ተባለ ያሬድ አምላኩን ከዚች ቀን በኋላ በሙ ያሬድ ቅዱስ ተነቀቶ በመንበረ በሚያመሰግንበት ሰዓት ዘሌናው በመንፈስ ቅዱስ ተነቀቶ በመንበረ ምስጋና የቤት ፊት ለሥት ቁመው የሚያመሰግኑትን ካህናት ሰማያን ምስጋና ቸውንና ዜማቸውን ያሰማ ነበር ከዚያም በዘሌናው ተቀኘ በእንደቤቱ ትልቶ ከበዜና ሰማይ የሰማውን ዜማ በየቀኑ በየሌሊቱ ለእድሜ ልክ ያሰማ ነበር ቅዱስ ያሬድ በሚያዘምርበት ጊዜ የታመመ ከዘመመ ያዜተኛን ከሃዘኑ ያስረሳ ነበር ።

ቅዱስ ያሬድ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ፀጋ ይዞ ከመዓእከት እየሰማ ከዘበረና ከደብል ድምፁ በሚያሰጠው ድምፁ በዘመረ ጊዜ እንስሳት እእዋፍ ከዛፍ እራቂት ከዱር መጥተው ያዳምጡት ነበር እንስሳት የሚበሉትና የሚያትሙትን ሳርና ፍሬ ትተው ያዳምጡት ነበር ከእለ የሚበሉትና የሚያትሙትን ሳርና ዋና በዘፈው ወገሪ እያዜመ ሲሄድ ታት እንደ ቀን አሰቦር በሚባል ቦታ በዘፈው ወገሪ እያዜመ ሲሄድ የሚያደርሰት በሬዎች ጀሮአቸውን አቁመው ሲያዳምጡ ዝቢሬው ተቆ ጥቶ አንተ በሬ ፊት ያብቀሉ ዝንብለህ እንዳትሄድ ከዚማዝ የተነሣ በሬዎች አላርስም ብለው ቆሙ ብለ በያዘው ጅራፍ ያሬድን ገረፈው እየተባለ እስከዛሬ ይነገራል ።

እንደዚሁም በያሬድ ጊዜ የነበሩት አፄ ገብረመስቀል ካሉ ያሬድ በእክሱም ፅዮን ቤተ ክ ውስጥ ማህሌት ቆሞ ሳለ እጹው በድምፁ ተማርከው ከዙፋናቸው ወደእሱ በብተ ኗዱ ከዚያም መቋሚያውን ሲያወ ዘውዘው እያቀተው በትረመንግሥታቸውን እንስተው ቸያሬድን እግር ወጉ እርሱም መወጋቱን ሳያውቅ ሳያስማው አምላኩን በሚያመሰግ ወጉት እርሱም መወጋቱን ሳያውቅ ሳያሰማው ቆይቶ ማህሌቱ ሲያልቅ ነው ምስጋና ዘሌናው ተውጦ ሲያመሰግን ቆይቶ ማህሌቱ ሲያልቅ እግሩን ቢያዩ በበትረ መንግሥቱ እንካሴ ተወግቶ ደም እንደወጣ እየፈሰሰ እንዳየ አሉም አቶ ።

አጼ ገብረመስቀል ደሙን በማየታቸው ደንግጠው የደምህን ካሣ ጠይቀኝ እኩል መንግሥቴንም እሰጥሃለሁ አሉት ።

እርሱም እንዲህ አላቸው የፈለኩትን ሊያደርጉልኝ ቃል ይግቡ ልኝ ቃሉንም የፈለከውን ልሰጥህ ብለው በእግዚአብሔር ስም ማሉ

እርሱም የሀይማኖቱ ዘመን የኢትዮጵያን ህዝብ በማስተማርና በመመገን እንዳሳለፉ ይናገራሉ፡ አባቸው አጼ ገብረመስቀልም እንዲለያቸው አይወዱም ነበርና በጣም አዘኑ ከዚያም ፈቀዱለትና እየተዘዋወረ በየ ገዳማቱ እየገባ ማስተማር ጀመረ ።

ቅዱስ ያሬድ ኢየሱስ ክርስቶስ የረገጠውን ገዳም በጣና ሃይቅ ውስጥ ከሚገኘው ዳጋ እስጢፋኖስ ምእራፍ የተባለውን ሥፍራ "ሲያስ ድስና ሲያሰራ በዚያም እያስተማረ ለሁለት አመት ተቀምጦበታል ከዚያም አጼ ገብረመስቀል በመዳኛቸው በአቡነ አረጋዊ ስም በዙር አምባ ተራራ በአሰሩት ቤተ ክ/ ለሶስት አመት ያክል ተቀምጦአል በዚያም ብዙ ሊቃውንቶች የዝማሬና የመሥዋዕት መምሪያን አውጥቷል ከዚያም ተነስቶ ወደ ደብረ ዳሞ ተራራ ወጥቶ አጼ ገብረ መስቀል ያሰሩትን ቤተ ክርስቲያን ጐብኝቶ ይኖሩበቶ መጻሕፍት አለ በሰማያት እስመ ማህደረ መለኮት ይእቲ አመድኅኖ መርኢኩ ስነ ህንጻ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን እያለ ዝርጋታ ትርጉም የሰማያት መጻሕፍት ይትነብኝ ቃል የቤተ ክ/ ህንፃ እያየሁ ወርኢት ማለት ነው ይህም ተራራ እግ ዊአ አመህያው ክርስቶስ የነበረበት ዳሞ ነው በዚሁ ገዳም ከአቡነ አረጋዊ ጋር በፍቅርና በሰላም አምላካቸውን ሲያመሰግኑ ኑረው የመ ንፈስ ቅዱስ አባቱን ተሰናብቶ ወደ ደብረ ቢዘን ገዳም ሄደ በዚያ በገዳሙ የሚኖሩት መነኮሳት በክብር ተቀብለው አስተናገዱት ። ከደ ብረ ቢዘን ወደ ሰሜን ሄዶ በረዶ በሚከመርበት ተራራ ሄዶ ቀዋና ገባ በአካባቢው ያሉትንና ከሩቅ ሃገር የሚመጡትን ሊቃውንቶች የዜማ ስሌትና ሙያ እያስተማረ ብዙ ዘመናት ኑሮዋ በኋላ በሰባ ስምንት አመቱ በአምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ዓ/ም አጼ ወሰንሰገድ የተባለው ብቸጋር በነገሰ በሰባተኛው ዘመን መንግሥቱ በዋሻው ውስጥ ገብቶ መሰወሩን አረዳቶቹና ተማሪዎች መስክረዋል ።

ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው መፃህፍቶች

1ኛ/ ድጓ አሁድ ቀንና በአመት በዓል የሚዘጋጅ የቤ/ክ/ዜማ
2ኛ/ ጾመድጓ፤ በአቢይ ጾም የሚዘመር ስለጾም ሥርዓት የሚ/ዜማ
3ኛ/ ዝማሬ ከቁርባን በኋላ ለቅዱስ ቁርባን የሚቀርብ ዜማ
4ኛ/ መዋሥእት ለሙታን ዘሉት ፍትሃት በሥርዓተ እርያም ዜማ
5ኛ/ አኢጋረ እግዚአ ከቅዳሴ በኋላ በግእዝ የሚነበብ ንባብ
6ኛ/ መፃሃፈ ብርሃን በሱባኤ በቀዋና ሆኖ የሚደመር መዝሙር
7ኛ/ ምእራፍ እንደዚሁም ብዙ መፅሃፍቶችን በደጋ እስጢፋ

ሞቱ ቆድ ሲኖር በየዲት ዘመን ተቀምጠዋል ከዚህ በላይ ያሉት የስም ዝርዝር ግን እስከዛሬ ድረስ ልዩ የሆነ ምልክት ተደርጎላቸው በየ ገዳሙና በየአድባራቱ አምላካችንን እያመሰገኑ በየግዛቤቱ ይዘምሩባ ቸዋል እንዲሁም በሶስት አዶንት ዜማዎች ይጠቀሙባቸዋል ስማቸ ውም ግእዝ እዝል አራራይ ይባላሉ እንዲሁም የስላሴዎች ምሳሌ ናቸው ።

እንደዚሁ ሆነ አጼ ገብረመስቀል በነገሡበት ዘመን አጼ ካሌብ በየመን ላይ ያነገሡት አብርሃ አርያትን የሰንአን ንጉሥ ገድሎ እራሱ ብቻ ይገዛ ጀመር በዚህን ጊዜ አጼ ገብረመስቀል አባቱ ያነገሡውን በግፍ ፈቃዱ በመግደሉ አብርሃን እንደዋለው ብለው ጦሩን ሲያዘጋጁ እዚ ለእስከዛም ንጉሡ ንጉሥ ዓርያት ታላቅ ነኝ ስለዚህ ደሜ ቋጎ ውና ብቻ በወርቅ ብልቃጥ ይሙን በወርቅ አንልግል የየመንን አፈር ያታሽኙኑበትን የገባሪነቱን የሚያመለክት መልእክት አሲዞ ወደ አክ ሱም መልእክተኞችን ላከ አጼ ገብረመስቀልም ከአብርሃ ቆተላኩትን መልእክተኞች ከተቀበለና ከነጋገረ በኋላ የመንን ጠቅልሎ እንዲገዛ ፈቀደለት ።

አጼ ገብረመስቀል በነገሡ በ14 ዓመታቸው የዚህን አለም ደስታ ንቀው አልጋቸውን ቆስጠንጢኖስ ለሚባለው ልጃቸው አወርሰው እንደአባታቸው መንኩሰው ገዳም ገቡ ። በዚህ ዘመን መሳፍንትና መኳን ንቱ ንብረቱን ለድሃ እየሰጠ ቤቱን የብቱ እንደምን እየተወ መመንኑና ገዳም መግባት ሆነ ።

የኢትዮጵያ ታሪኮች ተከፈሉ ተሰኖዩ ሁሉም ለየራሱ መንግሥት አቋቋመ በዚህ ምክንያት የየመኑ ንጉሥ አብርሃም ሞቶ ልጁ አክ ሱም ይገዛ ነበር ከእርሱም ቀጥሎ ወንድሙ ማዝሩቅ ነገሠ ። በማዝ ሩቅ ዘመን መንግሥት ሚዲ ካሪብ የሚባል ዘመዱ ከፋርስ ንጉሥ ከኮስሮዬ ጋር ተስማምቶ በብዙ ሺህ ወታደሮች የመንን መጥቶ ወረረ ማዝሩቅም ለአክሱም መንግሥት እርዳታ እንዲላክለት ደጋግሞ ቢለፍ እርዳታ ቀርቶ መልስ ሊያገኝ አልቻለም ማዝሩቅም እስከ ተቻለው ተዋግቶ ሞተ ከዚህ በኋላ ፈረንሳዮች የማዝሩቅን ከተማና የሰንአን ከተማ ተቆጣጥረው ሹም ሽር እያደረጉ የመንን ይገዙና ያስተዳድሩ ጀመር ይኸውም አረቦች እስከሚነሱ ድረስ ለአንድ መቶ ዘመን በፈረ ንሳዮች እጅ የመን ወደቀች ።

የአጼ ገብረመስቀል ልጅ ቆስጠንጢኖስ አጼ እስገበዝ ንጉሥ ነገ ሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ሃያ ስምንት አመት እንደገዛ እሱም እሰምን ንቆ መንኖ ሀገሩንም ሥራዊቱንም አልተሰናበተም በፈንታው ልጁን

በገርጋር አፄ ወሰን ሰገድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ የአክሱም መሳፍንት እንገሡት አጼ ወሰንሰገድን ወንድሙን ዳንኤልን የሚባለውን ገድሉ ነገሡ ነገር ግን ህዝቡ እንገዛልህም ብሎት የዐለምትና የወሊታይቱ ጺዋ ሄዶ ወግቶ ገደለው ከዚያም የአጼ ወሰን ሰገድ ልጅ ፍሬሁን አጼ ፍሬ ገብኝ ተብሎ የዋጉዱ ዘሮች ባሉበት እንገሡት አጼ ፍሬገብኝ በደከመና በፈዘዘ አስተዳደር ሃያ ሰባት ዓመት ገዝቶ አለፈ በአጼ አልኦጋሽ ዘመን የህዝብ ንግግር ከግእዝ ወደ አረብ ቋንቋ ተቀደር መንጋገሪያ ሆኖ ነበር አጼ አልኦጋሽ ሃያ አመት በፍቅርና በሰላም ኢትዮጵያን ገዝቶ ሲሞት ታላቅ ልጁ አክለው ዶም በስድስት መቶ ሃያ ሶስት (623) ዓ/ም አጼ አርማህ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሰ ይህም ንጉሥ ከነቢዩ መሃመድ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበረው ።

## ምዕራፍ አሥራ ሶስት

### የአጼ እርማኸዐ ዘመነ መንግሥት የነቢዩ መሐመድና የእስልምና መንግሥት ጠላጅነት

ከአጼ ካሌብ እስከ አክሱም ውድቀም ዘመነ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ያለ መሟጥጥትና መዳከምንት የዚህን አሰም ደብታ እጆናቁ በምንኩ ስናና በብሀትውና የተሰማሩበት ሲሆን በዚህን ጊዜ ሃጫት የነበረው የእስልምና መንግሥት ዘቶ እያለ ሄዶ በየበታው ሽፍታና መንዘዶ እየተ ነዓ የለማውን ሃገር ይዘርፍና ይነዋቅ ጀመር ።

በርም በቁስጥንጥንያና በእስክንድርያ የእንድ ባህሪይ ተከታዮች ወይም ተዋህዶች የሁለት ባህርይ ተከታዮች ካቶሊኮች ተዋትና ማታ ጭቅጭቅና ክርክር እንደዚሁ መጋደል አድርገው ሳለ በዚህ መካከል በአረብ አገር ከአርዮስ ትምህርት ምንም ያህል የማይርቀውን የእስላምን ሃይማኖት የመሰረተው መሐመድ አጼ አለ ገብረ በኢትዮጵያ በንጉሠብት ዘመን ተወለደ ዘመኑም 563 ዓ.ም. ነው ።

### የነቢዩ መሐመድ የትውልድ አጭር ታሪክ ይህ ነው ።

መሐመድ — (ሙሐመድ) ወይም ማሐሜት አብደላ አብዶል ሙታ ሌብና አሚናስ ከሚባሉ ተወለደ የአባቱ ስም አብደላ የእናቱ አሚናህ ይባላሉ እንተች የአባቱ ወንድሞች አቡታ ሊቭና አሌአብስ ዘሩ ከሐሼሚት ቤተሰብ የወረደ ከፍ ያለ ነገር ነው ሐጅሚት ዘሩ በኢትዮጵያ ምድር ቁርሽና ከረሽት የሚባሉ ናቸው መሐመድ ሕፃን ሳለ አባቱ ስለሞተበት እስከ ስድስት ዓመት ድረስ ከናቱ ጋር ሲኖር እናቱም ስለሞተችበት አቡታሊብ የሚባለው አባቱ ወን ድም ወሰዶ የበግ እረኛ አደረገው ከዚያም ከፍ እያለ ሲሄድ እረኝነቱን ትቶ ለነጋዴዎች በደሞዝ ተቀጥሮ ግመሎች እየነዳ ሸቀጥ ያመላልስ ጀመር በዚሁ ምክንያት ከድጃ የምትባል ሃብታም ነጋዴ መጀመሪያ በእሽክርነት ለንግድ ቀጠረችው በመጨረሻ የሃያ አምስት አመት ወጣት ሳለ መልኩ ስለአስደሰታት በባልነት አገባቸው ለአስራ አምስት አመት ያክል ከእርስዋ ጋር በኖረበት ጊዜ ወደሶርያ ወደግብፅ ሲወርድ ከትርፍ ይልቅ ስለሃይማኖት በጥብቅ ያሰብና ከነጋዴዎችና

ከመንገደኞች ጋር ያወራና ይጨቃጨቅ ነበር እንዲሁም በሶርያ ባለ አባ ባሂራ ከሚባል መነኩሴ ጋር ስለክርስትናና የይሁዳዊነትና ስለኦሪት በሰፊው እየተነጋገሩ ። ከዚያም ወደሃገሩ ሲመለስ ወረቃ ከሚባለው ከሚስቱ አጎት ልጅ አይሁዳዊ ስለነበር ብሉይ ኪዳንን በሚገባ አጠናቆ እየጠየቀ ተረድቷል በሌላ በኩል በአረብ አገር ያሉት ክርስቲያኖች የስላሴዎችን አንድነትና ሶስትነት የአንድ ባህሪነትና የሁለት ባህርይነት ያለውን ክርክርና ግጭት እያየ ጊዜውን ሁሉ ለሀይማኖት ያሳልፍ ነበር ። በዚህን ጊዜ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንጂ አምላክ አይደለም የሚሉትን የአርዮሳውያን ስብከት ከሌሎች ለየት ብሎ ይረዳው ነበር ። በዚሁ ጊዜ ደግሞ በአይሁዶችንት በክርስቲያንነት በሁለትና በአንድ ባህሪይ በሌሎችም አግብ ሲነታረኩ ሲጨቃጨቁ የራሱ ወገኖች የመካ ህዝብ በልዩ ልዩ ጣኦት አምልኮ መያዙን በቁማርና በስካር በዘፈን ተውጦ መጨነቁን አይቶ መካሪና አስተማሪ በማጣቱ ለህዝቡ በጣም አዘነለት እርሱም ለዚህ በጣም ያስብበት ጀመረ ። ከእለታት አንድ ቀን መሃመድ ከእንዲት ኮረብታ ላይ ተቀምጦ ስለወገኖቹ ኑሮ ስለሃይማኖታቸው ሲያስብ አንድ መላክ ከፊቱ መጣና የጨርቅ ሰሌዳ በእጁ ይዞ እኔ መላኩ ገብርኤል ነኝ ይሄን አንብበው ቢለው ማንበብ አልችልም ብሎ መለሰለት መልአኩም እንደገና አንብብ ሲል ትእዛዙን አጠንክረበት ከዚህ በኋላ ንባብ የማያውቀው መሃመድ ማንበብ ጀመረ ቃሉም እንዲህ የሚል ነበር አምላክህ ታላቅ ያደርገሃል ከፍ ከፍ ያደርግሃል ሽማሀንም ያጠራዋል ከርኩሰትህ ሽሽ አምልኮ አምላክህንም ጠብቅ እንዲህንና እንዲህ ሌመሰሉ ቃላቶች አንቦ ሲጨርስ መልአኩ እስከነሰሌዳው ተሰወረው ። ከዚህ በኋላ ወደ ቤቱ ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ለሚስቱ ነገራት ከዚያም በየጊዜው ራእይ በማየቱ ከእግዚአብሔር የተላኩ ነቢይ ነኝ ሲል ከአይሁዶች ሃይማኖት ከአርዮስ ትምህርት የራቀውን የእግዚአብሔር እውነተኛ አምላክነት አንድነት በየጉባኤው በየአደባባዩ ይሰብክና ያስተምር ጀመረ ።

አላህ አንድ እግዚአብሔር ነው
መሃመድም የአላህ መልእክተኛ ነው
አላህ አይወልድም አይወለድም ሁልጊዜ አንድ ነው
ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ አትስገዱ

አትስረቁ ሃሰት አትናገሩ በሃሰት አትመስክሩ አትቀንዝሩ . . እያለ በማስተምርበት ጊዜ የሰማይ ቤትን አውቃለሁ እያሉ ከሰሚዎች እንደአንዶች ያፌዙበት ነበር እርሱ ግን ይሄን የመሰለ በማስተማሩ

ጠንክሮ ተከታዮቹም በተቻቸው አገኘ የሃይማኖቱን ስም ለአላህ የተገዛ
ሲል እስላም ብሎ ሰየመው ።

ትምህርቱን የተቀበሉና በጉኑ የተሰለፉ ሁሉ የእግዚአብሔር መል
እክተኛ ነው መሐመድም ከእግዚአብሔር ዘንድ በመልአኩ በገብርኤል
እጅ የወረደለት እያሉ አመነበት ነገር ግን የጣኦትን ከንቱነት ሲያስ
ተምር ጣኦቱን ከልብ የሚያመልኩና ከካአባ መቅደስ በስለት ብዙ ገን
ዘብ የሚያገኙት ሃብታሞች ሊገድሉት ተነሱበት መሐመድም ከያ
ትረብ አገር ተከታዩ ስለአገኘ ከመካ ሸሽቶ ወደያትረብ — አልመዲና
በሃምሌ 16 ቀን በ615 ወይም በ616 ዓ.ም. በተወለደ በአምሳ ሶስተኛ
አመቱ ተሰደደ ይህ የተሰደደበት ቀን ሂጂራ የሸሸበት ሌሊት የምት
ባለው በእስላሞች ሁሉ የታሪክ መነሻ የቀን ቁጠራ መጀመሪያ ሆኖች
ከዚያች ቀን ጀምረው ዘመናቸውን ይቆጥራሉ ።

ከዚህ በኋላ መሐመድ እግሩን ካሳረፈበት ቦታ ትልቅ መስጊድ
ተሰራ ከዚህ በኋላ በርሱ ሃይማኖት ያመኑትን አንድነት የአቢታሊብን
ልጅ አሊን የብታመን አቡበክርን ወደርሱ ወገን ካደረገ በኋላ እነሱም
በቅን ስለአገለገሉት በመዲና የርሱ ተከታይ ከቀን ወደቀን እየበዛ
ሄደ ከዚያም መካን በለቀቀ በስምንተኛው አመት አስር ሽህ ወታደር
አስከትሎ ወደመካ ከተማ ገባ ጀመረ የመሐመድን መምጣት ሰው
ሁሉ ሲሰማ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ሃብቱን እየተወ ከከተማ ወደዱር
እየወጣ ይቀመጥ ጀመር መሐመድም አልካስዋ በምትባለው የጭን
ግመሉ እንደተቀመጠ በወታደሩ ታጅቦ ያለአንዳች ተቃዋሚ መካ ገባ
ከዚያም የሃባል ጣኦት ወደሚገኝበት ወደታላቁ የካአባ ቤተ መቅደስ
ከነወታደሮቹ ሄዶ በግመሉ ላይ እንደሆነ እውነት መጣ ሃሰት ሸሸ
ብሎ በያዘው በትሩ ሀንፃውን ሲመታው ተከታዩ ሁሉ ቤተ መቅደ
ሱን አፈራረሰው በዚህ አለት ሶስት መቶ ስልሳ የሚሆኑ የጣኦት
ቤተመቅደስ እየዞረ አፈራረሰ እንዚህም ብቻ ሳይሆኑ ሶስት አካላት
አንድ መለኮት ባሀሪይ ተወለደ ተሰቀለ ሞተ ተነሳ የሚሉትን ክርስቲ
ያኖች ሁሉ ገደለ ቤተክርስቲያኖችንም አቃጠለ አፈረሰ ሌሎች አይሁ
ዶችንም መሲህ አልተወለደም መሐመድም የእግዚአብሔር ነቢይ አይ
ደለም የሚሉትን ሁሉ ከመካ አጠፋ መሰብሰቢያቸውን ሁሉ አስፈረሰው
ከእስላም ሃይማኖት በቀር የቀረው አልነበረም ነቢዩ መሐመድ ከዚህ
ቀን ጀምሮ የእስላም ሃይማኖትን መሰርቶ በቁራን የተጻፈውን የጸም
የኑሮ ህግና ሥርዓት አፅንቶ በሙሉ የአረብ አገር ላይ የመንፈሳውያ
ኑም የሥጋውያኑም አስተዳደር አደላድሎ ይመራ ጀመር በዚህ ጊዜ
ነው በጉረቤት ሃገሮች ለሚገኙት ታላላቆች ለሆኑት ለቁስጥንጥንያ

ንጉሥ ሄርቅልዮስ ለፋርስ ንጉሥ ኮስሮዌ ፓርዌዝ ለኢትዮጵያው
ንጉሠ ነገሥት አርማህ ደብዳቤ አሲዞ በመልእክተኞች የእስልምናን
ሃይማኖት እንዲቀበሉ ላከላቸው እንደዚሁም ሆነ አጼ አልጋነሽ በኢ
ትዮጵያ ሃገሮች ላይ በነገሡ በአስራሶስት ዘመነ መንግሥቱ በመካ መሃ
መድ የሚባል ነቢይ ተነስቶ እግዚአብሔር አንድ ነው የእግዚአብሔር
መልእክተኛም መሃመድ ነው እያለ በሚያስተምርበት ጊዜ የመካ ሀዝ
ቦች ክርርቲያኖችና አይሁዶች ሌሎችም ለጣኦት የሚሰግዱና የሚያ
መልኩ ሁሉ መሃመድንና ተከታዮችን ለመግደል ተነሱ በዚህን ጊዜ
መሃመድንና ተቂቶቹን ይዞ ወደመዲና ሲሄዱ ግማሾቹንና ቁርሺ ሃሺ
ሚት የሚባሉ ትን ነገዶችን የአጉቱን ልጅ ጃፋርን አለቃ አድርጎ
ወደ ሱባያ መሬት ሄዱ በዚያ የአበሻው ንጉሠነገሥት አልነጋሽ ፍርዱ
ቅን እውነተኛ ስለሆነ ለእውነት የቆመ ስለሆነ ይቀበላችኋል ፡፡ አላቸው
ጃፋርም የመሃመድን ተከታዮችና ወገኖቹን ይዞ በስንት ተአምር ከጠ
ላት እጅ እየዳኑ በሰላም አክሱም ደረሱ በዚህን ጊዜ በሮምና በቁስጥ
ንጥንያ የነበረው ንጉሥ ሄራቅልዮስና የቁስጥንጥንያው ሊቀጳጳስ አባ
ሰርግዮስ ለአክሱም ንጉሠ ነገሥት አልጋንሽ ወደአንተ የመጡ አር
ዳ ውያንና የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነኝ የሚል የሚሉሚት ተከታ
ዮችና አማኞች ከአንተ መጥተው መጠጋታቸውን ሰምተናልና ይዘህ
እንድትልክልን የሚል ደብዳቤ ከወታደሮቻቸው ጋር ላኩ ፡ አጼ አልጋ
ነሺም ከመካ የመጡትን የእስላም ሃይማኖት ተከታዮቹንና ከሄራቅል
ዮስ የመጡትን ወታደሮችና የሀይማኖት መሪዎችን ሲከራከር በኋላ
ጃፍር ከብሉይና ከሃዲስ እየጠቀሰ ስለነቢይ ኢሳ ያለአባት መወለድ
ካስረዳ በኋላ አልነጋሺም እግዚሀብሔርን አመስግኖ እነዚህ ሰዎች
እውነተኞች ናቸው ሲል ተናገረ ከዚያም ክርክሩ ካበቃ በኋላ እኔን
ብለው የመጡና ወደእኔ የመጡትን ምእመናን ለጠላታቸው አሳልፌ
መስጠት እኔን እራሴን አሳልፌ መስጠት ማለት ነውና ብሎ ከሄራቅ
ልዮስ ተልከው የመጡትን ወታደሮች አሳፍሮ መለሳቸው ከዚያም
ልዩ ሃገር ተሰቶአቸው በክብር ተቀመጡ ከዚያም ተከታዮቹ እየበዛ
ሲሄድ ወደነቢያቸው መሃመድ ያላላኩና የአክሱም ንጉሠ ነገሥት ያደ
ረጓቸውን ውለታ ይፅፉለት ነበር ፡፡ ነቢዩ መሃመድም መካንና መዲ
ናን በቁጥጥሩ አድርጐ የእስላም ሃይማኖትን በሰፊው ካስተማረና ህዝቡን
እስላም ካደረገ በኋላ ለአክሱም ንጉሠ ነገሥት ለአልነጋሽ እንዲህ የሚል
ደብዳቤ ጻፈለት ፡፡ ከነቢዩ መሃመድ ከእግዚአብሔር መልክተኛ በሱባያ
ንጉሠ ነገሥት አልነጋሺ እውነትን ለሚያደርግና በእግዚአብሔር መን
ገድ ለሚሄድ ሁሉ ሰላም ይሁንለት አንተ በእውነትና በቅን መንገድ
እንደምትሄድ የአላህ መልክተኛ አይቶሃል አሁንም በእውነት መንገድ

የሚሄዱትን የእግዚአብሔርና የአላህ ባሪያዎችን ተቀብለህ እንደአስተና
ገድክ እኔም ወደእስልምና ሃይማኖት መጥተህ ደህንነት እንዲሆንልህ
እጠራሃለሁ ለዘለአለም አለህ በክብር ያስቀምጥሃል ፀጋንና ደስታን
ለአንተ ይሸልምሃል እሱ ሲጋሽ ደግ ነውና መንገዱም የቀና ነው የአ
ላህ መድከተኛም ሃቀኛ ነውና ወደእኔ ለመምጣት ጊዜ አትውሰድ ።
ማህተም መሃመድ የአላህ መልእክተኛ ነቢዩ መሃመድ ይሄን ደብዳቤ
በሚልኩበት ጊዜ አጼ አልነጋሺ ሞተ ልጁ አጼ አርማህ በአባቱ ዙፋን
ተቀምጦ ነበርና ደብዳቤውን ተቀብሎ እንግዶቹን በክብር ከአስተናገደ
በኋላ ብዙ ልዩ ልዩ ከወርቅና ከአልማዝ የተሰሩ ጌጣ ጌጦች ለነቢዩ
መሃመድ የሚሰጡ ናቸው ብሎ አባቱ አደራ ብሎ ሰጥቶኛል ብሎ
ሰጥቶ በሰላም ወደሃገራቸው መለሳቸው በአክሱም አካባቢና በእስክ
ንድርያ ያሉ መነኮሳት ለአጼ አርማህ እንዚህ ሸኙተው የመጡ እስላ
ሞች ከሃዲዎች ናቸውና ሃገራቸውን ሳያበላሹት ይውጡልን ወይም
ለእኛ ስጠን ብለው ብዙ ወርቅና አልማዝ አቀረቡለት አርማህም
እንደአባቱ ንጉሴ ልድርጎ ሁሉቱን ወገኖች ሲያከራክር የመሃመድ የአ
ጎት ልጅ በቁራን በአራተኛው ምዕራፍ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ
ከማርያም ያላባት የተወለደ ነቢይ ነው ብሎ ከመጀመሪያ እስከመጨ
ረሻ በንጉሱ ፊት ቀርቦ ስለተናገረ አጼ አርማህም በንግግሩ ደስ ስለተ
ሰኘ በሃገሬ ለመቀመጥ የፈለጉ ሁሉ ይቀመጡሉ እንዲሄዱ ያሉ በክ
ብር ይሄዳሉ እንጂ እናንተ እንደምትሉት አይወጡም ለጠላቶቻቸውም
አሳልፌ አልሰጣቸውም እናንተ እኔን በሃሰት ልትቀይሩ ወርቅና አል
ማዝ አመጣችሁ ብሎ ተቆጥቶ ግማሹን ሲገድል ግማሹን አሰራቸው
ይባላል ።

በዚሁ ዘመን በመካው ንጉሥ መሃመድና በአጼ አርማህ መካ
ከል ብዙ ጊዜ የወዳጅነት ደብዳቤ ተላልከው እንደነበር አክሱማይ ሲራክ
ልርሳቸዋል ምንም እንዳንድ መንፈስ ደካሞች ታሪኩን ባይደግፉት
ለእውነተኞችና ታሪክ ለሚፈልጉት ወዳጆቹ ከብዙ በጥቂቱ አቅርቢ
ላችኋለሁ መረራስ አሉም በላይ

አጼ አርማህ ስምንት አመት እንደገዛ በኤርትራ ባህር ውስጥ
በባህር ሞገድ ሰጥሞ ስለሞተ ልጁ ግርማ አስፈሬ አጼ አልባህር
ነጋሺ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ።

በአጼ አልባህር ነጋሺ ዘመን መንግሥት በነገሠ በሃያ ስድስት
አመት ነቢዩ መሃመድ ሞተ ከእርሱ ቀጥሎ የአይሻህ አባት ቢጋዝ
አሚር አቡበክር ሰዲቅ ነገሠ እርሱም ለነቢዩ ረሱልአላህ የአላህ መልእ

ክቶም የሚባል ቦታ ሲሰጠው ለተከታዩ ደግሞ ከሊፋ እንደራሴ ተክ ታይ የሚባል ስም ተሰጠው ሌላም ከሊፋ አሚር አልሙም ኒን የእማ ኞች መሰፍን የሚባል ስም አለው እርሱም ሁለት አመት ተኩል ገዝቶ ሲሞት የመሃመድ ተከታይ ከሊፋ ኡመር አብንልሃጠብ ነው በኡመር ዘመን መንግሥት የእስልምናን ሃይማኖት ተከታዮች እየበዙ ሄዱ ከሊፋ ኡመር ግብፅን ኢየሩሳሌምን በራሱ መንግሥት ሥር ቁጥጥር አደረገ ከዚህ በኋላ አረቦች እያየሉ እየበረቱ ስለሄዱ በእስያ በሰሜን በምዕራብ አፍሪካ ያሉትን ሃገሮች ተቆጣጥረው በእስላም ሃይማኖት ኢጣሊያንና ፈረንሳይን ወረው እስፓኝንም ጨምረው ያስተዳድሩ ጀመር ።

በዚሁ ዘመን አልባዘርኑጋሽ አስራ አምስት አመት ገዝቶ ሞተ ልጁ ገብረጋዝ አጼ ጀንአስፍሀ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በአ ክሱም ዙፋን ላይ ነበር እርሱም አስር አመት ገዝቶ ልጁ ድግና አጼ ግድና ሚካኤል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ በአጼ ግድና ሚካኤል ዘመን መንግሥት በሜንና ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ጐሣዎች በእስልምና ሃይማኖት አመኑ በዚህን ጊዜ አዲሱን የእስል ምና የሚከተሉ ጐሣዎች በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ እየተነሱ በኤ ርትራ ባህር አካባቢ የሚኖሩትን የባህር ወደቦችንና መርከቦችን በእ ሳት አቃጠሉ እንዚህም ከታወቁት አይላ ክሊስማ ታጂራ በርበር ሲቃ ጠሉ ዙፋን ዳህላክን አደሊስን በንዚሁ በኢትዮጵያ እስላሞች ቁጥጥር ይተዳደሩ ጀመር አረቦች ግን የነቢያቸውን የመሃመድን ቃል ስለሚ ያከብሩና ከአክሱም ንጉሠ ነገሥት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ስለነበራ ቸው ስለሚያውቁ የአባቶን ክርስቲያን ንጉሥ ለመውጋት ቀርቶ ለመ ጣላት እንኳ የሞከረ አልነበረም ነገር ግን በአካባቢ የሚኖሩት እንዚሁ ከአረብ ጋር ቢጋብቻና በሃይማኖት የተሳሠሩት በጐሣዎች ጠቦትና ሚታ እየወጉ አደከሙት አጼ ግድና ሚካኤል ሃያ ስድስት አመት በደከመ አገዛዝ ከገዛ በኋላ ልጁ ባህረ ኢክላ አጼ አባኤል ወይም አባጼል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ እርሱም በጀግንነት ብዙ አገር መልሶ ከአስገዛረ በኋላ በአባል ጐሣዎች በነገሠ በአስራዘጠኛ አመቱ ተገደለ ከርሱ ቀጥሎ ልጁ ጎም በፋንታው አጼ ገርሰም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በአባቱ ዙፋን ተቀመጠ በአጼ ገርሰም ዘመን መንግሥት እስላሞች እንደልባቸው በፈለጉት ሃገር እንዲያስ ተምሩ ተፈቀደላቸው እርሱም አሪያና ድራም የሚባል ገንዘብ ከወርቅና ከሃያስ አሰርቶ ያገበያበት ነበር አጼ ገርሰም በሰላምና በፍቅር ኢት ዮጵያን ሃያ አራት አመት ገዝቶ ሲሞት ልጁ አስጉምጉም አጼ በካ

ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ በነገሡ በአምስት ዓመት ገዝቶ ሲሞት ልጁ ልጅም አጼ ኢዮአስ ነገሡ አጼ ኢዮአስ እናቱ ፈላሻ ስለነበረች በእርሱ ዘመን በየመን የሚኖሩት ፈላሾችን እያመጡ ሃገር እየተሰጣቸው በከተማ ተቀመጡ ነገር ግን መሣፍንቱ መኳንንቱ የከረረ ጠብ አድርገው በመድሃኒት በነገሡ በአስራስድስት ዓመቱ አስገደሉት ልጁን ተክለሃይማኖትን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ትና ልጁን ተላትም አጼ እንደኢሉስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ አጼ እንደኢሉስም ሃያ አንድ ዓመት ገዝተ ሲሞት ልጁ አደጉሽ ነገሡ አጼ እንደኢሉስም ... አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ንጉሠነገሥት ተብለው ነገሡ እርሱም አጼ ተክለጊዮርጊስ ... አጼ ተክለሃይማኖት ንጉሠነገሥት ተብለው ነገሡ እርሱም ሶስት ዓመት ነግሶ ሞተ በፋንታው ልጁ እያሱ ስርአተንግሥናውን በሚያከብርበት ቀን በጣብያ ላይ ስለሞተ ልጁ ድድም አጼ አስፈሬም በሚያከብርበት ቀን በዙፋን ላይ ተቀመጠ አጼ አስፈሬም አምስት ንጉሠ ነገሥት ተብለው በዙፋን ላይ ተቀመጠ አጼ ዳንኤል ተብለው ነገሡ እርሱ አራት ዓመት ገዝቶ ሞተ በፋንታው ልጁም አጼ ዳንኤል ተብለው ነገሡ እርሱ አስር ዓመት ገዝቶ መንግሥቱን ትቶ መነኑ ልጁ ውድም አስፈሬ ሰምም አስር ዓመት ገዝቶ መንግሥቱን ለልጁ ውድም አስፈሬ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ በዘመነ አጼ ውድም አስፈሬ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ በውድም አስፈሬ ዘመነ መንግሥት የቤተክህነት ባለስልጣኖች ከፍ ያለ ድም አስፈሬ ዘመነ መንግሥት የቤተክህነት ባለስልጣኖች ከፍ ያለ መብት ተሰጥቶአቸው ብዙ ፈላሻዎችንና እስላሞችን አስገደሉ አሳረዱ መብት ተሰጥቶአቸው ብዙ ፈላሻዎችንና እስላሞችን አስገደሉ አሳረዱ በእሳት ውስጥ እያከተቱ አስገደሉ ብዙዎችም ተሰደዱ በክርስቲያንና በእሳት ውስጥ እያከተቱ አስገደሉ ብዙዎችም ተሰደዱ በክርስቲያንና በእስላሙ በፈላሻዎች መካከል የከበደ ጥላቻና ጠብ እየበረታ ሄደ ።

አጼ ውድም አስፈሬ ሰላሳ አመት ገዝቶ በተወለደ በአምሳ አመቱ አጼ ዘርአ ያዕቆብ ተብለው ነገሡ እርሱም አም ሲሞት ልጁ እርሜዝ አጼ እስቶስጠብዲኖስ ተብለው ነገሡ እርሱም አም ስት ዓመት ገዝቶ ሲሞት ልጁ ዳንግባግን አጼ ድግናጃን ተብለው በስ ምንት መቶ ሰላሳ ዓ.ም. ነገሡ ።

አጼ ድግናጃን በነገሡ ዘመን መሬት ፍሬን ሰጠች በረከት በዛ ገር ሞላ በዚህን ጊዜ የንጉሥታት ልጆች እየተያዙ በደብረዳሞ ተራራ በግዞት ይኖሩ ነበርና እራሱ ጃዶ ሁለተኛ ልጆቹም ሆኑ ወንድሞቹ ማንኛውም የንጉሥ ዘር እንዳይታወር ሲል በእጃቹ ተናግር ከተጋዙ ቤት ከደብረዳሞ ተራራ አውጥቶ እነሱም አስቀመጣቸው አጼ ድግና ጃን በነገሡ በ19 አመቱ እስላምና ፈላሻውን ቀስቅሰው ጦርነት ገጠ ሙት እርሱም ድል ሆነና ወደ ዳሞቱ ንጉሥ መርጃን ተሰደደ በዚ ያም ሳለ ታሞ ሞተ ።

በዚህን ጊዜ የአጼ ድግናጃን ሞት በአክሱም ሲሰማ እኔ ልንገስ እኔ ልንገስ በማለት ሁሉም ለየራሱ ጦር አዘጋጅቶ ተነሳ በዚህን ጊዜ የአጼ ንጉሥ መሬ መሞቱ የዳንግባግን ልጅ ግዳጃን አጼ ሀገዘናኝ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው አንግሰ የንጉሥታትን ልጆች አስሮ

ወደነበሩበት ደብረዳሞ ተራራ አስመጥቶ በዚያ ያስጠብቃቸው ጀመር፤ አጼ ህዝበናኝ በ፲ኛ አመት በደከመ አገዛዝ ገዝቶ ሲሞት በፋንታው ልጁ ውድም አጼ አንበሳ ሰገድ ተብሎ ነገሠ። እርሱም ሃያ አመት ገዝቶ ሲሞት የአክሱም መንግሥት ወራሽ የአፄ ልጆች ከሃገር ወደ ሃገር እየተሰደዱ የሚኖሩ ሆኑ መንግሥታቸው ለሌላ ተሰጠ።

## ምዕራፍ አስራ አራት

### የቅዱስ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት

#### የዲት የአክሱምን ንጉሠታት አጥፍታ እንደነገሠችና መራ ተክለሃይማኖት ከዮዲት ቀጥሎ እንደነገሠ

ከሰሎሞን የሚወለደው ከዛጉዌ ዘሮች ሳይወጣ የሚኖር የአክሱም መንግሥት ነበረ ይህም መንግሥት በቀዳማዊ ምኒልክ ዘሮች በር ሆኖ ዓብር ከፈል እድ መንገድ አቅርብ ሳይባል ለአንድ ሺህ በምንት ሙቶ ዘመን ከዛጉዌ እስከ መራ (መድራሪ) በባእ ትውልድ ድረስ ተከብሮና ተፈርቶ ይኖር ነበር ይህም አክሱም ከኢትዮጵያ ሃገሮች ውስጥ በይበልጥ ታላላቅ ከተሞች ነበረበት ከተሞቹ የገነቡበት ቀይ ጥ የአስል (አጻል) ጉልማዎች የወረዳ የዛፈው ወረዳዎ ከተማ አያገዝ የሰሌ ጉማ ዎች ፣ የሞግ ቤማኖች ጉማዎች የዛፈዎች አገው የሚኖሩበት ሃገር ሆኖ ላስታ ከተማው አደፋ ይባል ነበር በዚህ በወራናቹው ከተሞች ሥር የሚመሩ ሙቶ ሰባ ሁለት መገዶሮች አሉአቸው ለነዚህም ንጉሣቸው መረ የዛጉዌ ዘር የሆነ የአዜብ (አዘቦ) ንጉሥ ነው መራ ወይም መራራ የሚባለው በመርቅና በክብት የከበረ ነበረ በዚህም ንጉሥ አንዲት ቆንጆ ልጅ ነበረችው እንጂ በዙፋኑ የሚቀመጥ መንግሥቱን የሚ ወርስ ወንድ ልጅ አልነበረውም ።

እንዲዚህም ሆኖ በአክሱም የሚኖሩት የንጉሠታት ልጆች ከተ ጋዙበት ማረፊያ ከደብረዳሞ ወጥተው አባታቸውን የአርማህን ልጅ ድግናጀን ተብሎ የነገሠው ዳንግግን ጦርነት ገጠሙት እሱም ድል ሆነና ወደ ዳሞት ንጉሥ ሙርጀ ተሰደደ ሙርጀም እጁ ዳንግግ ወደሰ መምጣቱን ሰምቶ በክብር ተቀብሎ ማርና ወተት ወደሚገኝበትና ደገ ገቦችና ጀናሃዎች ወደሚኖሩበት ሃገር መርጦ በዚያ አስቀመጠው በዚ ያው ሳለ ሞተ የሞተበት ሃገር በስሙ ድንግግ ተባለ ጀንግግ ድግናጀን እንደሞተ ልጆቹ ሰሙና እኔ ልንገሥ እኔ ልንገሥ በማለት ጦርነት በለእነሱ የአዜብ ንጉሥ መራ ልጁእን በሆኑ በሃይሉ የጁሩ ሠራዊት ታጅቦ አክሱም ደረሰ ወዲያውኑ መራ በአባቱ ዙፋን መቀመጥ ሲገ ባው ሊታላቁ ልጅ ለማዳእጀን የነገሠ ንጉሥቱን መቀመጫ ዙፋን

ለማስከበር የንጉሣውያን ልጆች ወደ ነበሩበት ደብረዳሞ ተራራ አስ
ወሰዱ በዚህ ያስጠብቋቸው ጀመር ግዳጃቸውም አጼ ህዝቡናኝ ንጉሡ

ንጉሥ በኢትዮጵያ አለኝቶ በስምንት መቶ አርባ ዘጠኝ ዓ.ም. አን
ሰው መሬ ከእለታት አንድ ቀን በአክሱም ገበያ ሲዘዋወር እንጨት
ጠርቦ የሚሸጥ የእስራኤምስት እመት ልጅ የደም ግባቱንና ቁመቱን
ተመልክቶ ይህስ ጋሻ ጀግና ዘበኛ ይሆነኛል ብሎ ሠራዊቶችን ልክ
አስመጣውና ስምህ ማን ይባላል አለው እሱም ሰሎሞን አበሜሌክ እባ
ላለሁ አለው በል እኔ ያስመጣሁህ ከእኔ ጋር እንድትሆን ነው ሲለው
እጅ ነስቶ እሺ ጌታዬ ብሎ ለወላጆቹ ሳይናገር አብሮት እሱን ተከትሎ
ሄደ ሰሎሞንም በጌታው ቤተመንግሥት ተወዳጅና ተፈቃሪ ሆነ በዚ
ሆን ጊዜ እንቁጳል ወድጄዋለሁና ላግባው ብላ ለአባትዋ ጠየቀች
አባትየውም እንኳን ለጋሻ ጀግናው ለሌላ ንጉሥ ልጅ ብታገቢት
ባልዋ ወይም የምትወልደው ልጅዋ የአንተንም ሆነ የአክሱምን
ንጉሥ ነገሥት ዙፋን ይወርሳል ሥርዓታችሁን ያፈርሳል በዓቅምና
በሚኒልክ ዘሮች ላይ ያለውን ቃል ኪዳን ይሽራል የሚባል ንግርት
ጠቢባንና ባህታዊዎች ይናገሩት ስለነበር ስለዚህ ላይድርጅች በቤተ



የላሊበላ ሃውልትና የአደባባይ መስቀል ወደ ኢትዮጵያ
ሲገባ

መንግሥቱ ውስጥ በሚገኘው እልፍኝ ይብቃት ይኖር ነበር ሆኖ ግን ንጉሱ ስለአስፈራው የሃገር ጠቢባኖችንና አዋቂዎችን ሰብስቦ ምን ማድረግ ይሻለኛል እንዲቱ ልጅ ጋሻ ጃግሬዬን ካላገባሁት እሞታለሁ አለችኝ ስለዚህ ምክሩኝ አላቸው ከሁለቱ አንዳቸውን ማጣል አለብ ይዳን ካላደረግህ የተነገረው ንግርት ይደርስብሃል አሉት ልጁን እን ዳይገድል እንዲት ሴት ልጅ ብቻ ነው ያለው ጋሻጃግሬ ብሎ ያመጣ ውን እንዳይገድል በጣም ይወደው ስለነበር ለመግደል ፈራ ። እዚህ በጣም ተከዘ ልጁን አጋብቶ እንዳያስቀምጠው ንግርቱ ደርሶ መንግ ሥቱን የሚቀማውና የሚያጠፋው መስለው የንጉሥ ልጅ የድሃን ልጅ ማግባት ከልክልና ወርደት ስለነበር ሁልጊዜ ያዝን ይተክዝ ጀመር ከለታት አንድ ቀን የንጉሡ አማካሪ የሆነ ንጉሥ ሆይ ለምን ትተክዛለህ አለው የምወዳት አንዲቷ ልጄ ይህን ጋሻጃግሬዬን ካላ ገባሁ ት እሞታለሁ ስለዚህ በቅርብ ቀን አስታውቀኝ ብላኛለች እኔም ለጊዜው መከሬ አሰቤ እስከምነግርሽ ጊዜ ስጭኝ ብያታለሁ አለው አማካሪውም ንጉሥ ሆይ እሱን አግብታ መንግሥትህንና ስምህን ከምታረክሰው ይልቅ ጋሻጃግሬህን አስገድለህ በርያ የዱር አውሬ እንዲበላው አስጥለው ሲለው ንጉሡ ደግሞ ጋሻጃግሬዬን በጣም ስለ ምወደው ዉስኙ ለማስገደል አልሆነልኝም ሌላ ዘዴ እንዳለ ምከረኝ አለው ለማስገደል ካልፈለክስ ልጅህ አንድ ጊዜ ፍቅር ይዟታልና ታገባዋለች እሷ ከምትጠፋህ ያልወለድከው ይጥፋ ይህን ባትፈቅድም ግን ማዶታ ታገባዋለች ። ስለዚህ ከነብርና ከውርደት አንዱን ምረጥ አለው ንጉሡም ሳትገድሉ በሳጥን አድርጋችሁ ወደ ገደል ባህር ጣሉት ብሎ ለንጉሡ አማካሪና ለሎሌዎቹ አዘዘ እነሱም እንደታዘዙት አደበሩ ወይም አሉማኖን ብሄል በማያዊ ነሃስ አሰሩሁለት ቀን በባሕሩ ተከዜ በጥንቱ ሰማያዊ ማዣን ላይ ወስደው በሳጥኑ ከተው ጣሉት ሃይለ እንቁጹ ወይም መሰበውርቅ የምትባለው የንጉሡ ልጅም ከቤተ መንግሥቱ ውስጥ ስታጣው ጊዜ በጣም እያለቀሰች ገድላችሁት እንደ ሆን እሬሳውን ወይም የቀበራችሁበትን አሳዩኝ እያለች ስትጮህ በጣ እጅግ ህይወቷን እንዳታጠፋ ተብሎ እሱን ቤተሰቦቹንና ወላጆቹን ለማ የት ሄዷል ተብሎ በበርኛ ትጠበቅ ጀመር አለመመለሱን አይታ ከብዙ ቀን በኋላ ከዋይዋ ወይአክሱም ከነጋሹ ጋር የንጉሥ ልጅ ሳትመለስ በድብቅ ሄደች ከዚያም ከሄደችበት ሃገር ብዙ ቀን ፈልጋ ስታጣው በገቢያው መካከል አድርጋ ወደሃገሯ ልትመለስ ስትል የምትወደውን ታናሽ ወንድሙን ታይና ሮጣ ሄዳ አልሞትክም በህይወት ነህ ያለህ ብላ ስታቅፈው ወንድምየውም ይደነግጥና የሚናገረው ሲያጣ ስሙን አይደለህም አለችው እሱም የምትይው ሰው ወንድሜ ነው እንጂ እኔ ግን አይደለሁም ወንድሜም ከሞተ ሰባት አመቱ አለፈው እንደሌት መም

ቀን አወቅሁ ከእኛ ወላጆቹን ለመጠየቅ ከመጣ አራት አመቱ ከእኛ ጋር ሶስት አመት ተቀምጦ ነበር ስለዚህ ከናንተ ከተለየ ነው ሰባት አመቱ ለሁሉም ወደቤትህ ወስደኝና ከወላጆቹ ጋር አስተዋውቀኝ ብላ ወደቤቱ አንድ ላይ ሄዱ ከዚያም ትንሽ ቀን እንደሰነበተች የነሬ አድርሰኝ ትመለሳለህ ብላ ወደየነሩዋ ጎንቱ ይዛው ተመለሰች ከየነሩ ዋም እንደደረሰች አባቱዋን ይሄን ነው የማገባው ሁለተኛ ደግሞ ይህን አታገቢም ካልክ ያለ ልጅ እንደምትቀር እወቅ አለችው ንጉሡ ትዋትብኛለች ብሎ ፈርቶ እንዴን ከማገባቱ በፊት የንጉሥ አማች ለመሆን ጀግንነቱ በህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ ጦር ሜዳ ውጦ ድል ያድርግ በድል አድራጊነቱ በህዝብ ፊት ልጄን ሰጥቼሃለሁ እለዋለሁ ይላታል ለሃይለኛም እንቁዬል ወደጦርነት መሄዱ ይስ ባይላትም የንጉሥ አማች ለመሆን ብዙ ግድያና በጦር ፊት ያፋር መሆኑ ጀግንነቱም በይበልጥ ለህዝብ ግልፆ ማሳወቁን ስለምታውቅ እሺ አለችው ነገር ግን በእኛ በኩል የጦር ሠራዊት እንዲያገለና የምወደውን ሳላገባ እንዳ ይሞት ደግሞ አብሬ ጦር ሜዳ ድረስ እሄዳለሁ ብላ ከአባቱዋ እግር ወድቃ በእንባ እግሩን አራሰችው አባትዋም መሪ መሪሪ ባህር ባሉ ማለው አዝኖና ተከዞ ሲኖር አሁንም እንደገና በሃዘን በትካዜ የልጁን የሃይላን ሃሳብ ለመሙላት ከብዙ ወታደርና ከልጅቱ ጋር ወደጦርነት ላከው ነገር ግን መጀመሪያ ወንድሙን ወደስማያቂ ግዞን ወንዝ መሰደው የጣሉት በንጉሡ ልጅ መሆኑን ስለሚያውቁ አሁንም በጦር ነቱ ፊት ለፊት ተዋግቶ እሏዋት ተደረገ የምትወደውን ሰሎሞንን ም ሆነ ወንድሙን ነገዜን አባቱዋ በግፍ ሠራዊቶቹን መክር እንደ አስገደላቸው እውቃ ተረድታ ወደ አክሱም ተሰደደች አባትዋም ሰምቶ ሠራዊት ልኮ እንዲያመጡዋት ቢያዝ እንቁዬልዝዎን የተላኩትን ሠራዊት የጁዋ ጦር ገደለች የተረፉትም ተመልሰው ለአባትዋ የአደረ ገችውን ሁሉ ነገሩት አባትየውም ብዙ ሠራዊት አስከትሎ ተከት ሎት ነበር ነገር ግን እንደማትመለስና እንደፈለገች አውቆ ተዋግታ ድል ያደረገችበትን በታ አይዳ ብሎ ሰየመው ንጉሥ መሬ ይወደው የነበረው ጋሻጃግሬውን ሰሎሞንን በሳዋን አስደርጎ ወዳ እንዲወስ ደው ስለአደረገ ከሀሲናው ሊጠፋ ስላልቻለ ሁልጊዜ ስለሚተክዝ ሰሎሞንን ከአስጣለበት ወንዝ ሄዶ ያለቅስና ይተክዝ ጀመር ስለዚህ ወንዙን ትካዜ ብሎ ሰየመው ከቀን ብዛት ተቀይሮ ተከዜ ተባለ እን ቁዬሏ አባትዋ እንደሚያስፈልጋት አውቃ ስምዋን ቀይራ ትርጓሜ ገብዝ አሰኘታ የሰሎሞንና የንጉዜን ወላጆች እየረዳች ተቀምጣ ሳለ ከእለ ታት አንድ ቀን የአክሱም ንጉሥ አፃት በዚሁ በአክሱም ገበዝ ቤት ሳለች አዪ ሀገበናኝ ከመልኩና ከቁንጅናዋ ማማር የተነሳ አፍቅሯት

ሠራዊት ልኮ አስወሰዳት ትርጓሜ ቋንቋም በነበረው እልፍኝ ውስጥ ብቻዋን ሳለ ገድላ ደጃቱን ዘግታ ወጣች በዚህን ጊዜ አባትዋ ወደ አክሱም መምጣቱን ስለምታውቅ ወደ ቡግና ንብረቷ የቡግናን መሳፍንትና ባላባት ሰብስባ ሃገቱ የሚገኘውን የአባትዋን ቤተመንግሥት አፈረሰች በቤተመንግሥቱ ውስጥ የተገኘውን ዘበኛ ያለርኅራኄ ገደለች መሣሪያውንም ወረሰች በዚህን ጊዜ በላስታ በዛሬው ላስታ በወልቃይት በፀለምት በበጌዳ በዛሬው ስሜን ወይም ወገራ ከክርስቲያን መንግሥት ጋር ጨትና ግታ በየጊዜው አንድ ጊዜ ሲገብሩ አንድ ጊዜ ሲያምፁ የሚኖሩት ፈላሾች ጊዜ አገኙና የአክሱምን ከተማ በጊዴዎን መሪነት ለመውረር ተዘጋጅተው መጡ ነገር ግን የሀዘበናችንን መሞት የሰሙ ነገሥታትና መሳፍንት መጥተው በአክሱም ከተማ ተሰብስበው ነበር የመጡትም ነገሥታትና መሳፍንት የሰባት አመቱን ልጅ ውድምን ስመ መንግሥቱ አጼ አንበሳ ውድም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው አነገሡት ሥርዓት ንግሡን በሚፈጽሙበት ሰዓት ድንገት ደርሶ ፈላሾች ጦርነት አንስተው ከተማውን ከበቡ በዚህን ጊዜ በየሃገሩ የሞተውን ንጉሥ ለመቅበር ልጁን ለማንገሥ የመጣው የጌዋ ሠራዊት በየመሬው በየአለታው ተሰልፎ ጦርነት ገጠማቸው ፈላሾችም ድል ሆንና ሸሹ ንጉሣቸውም ጊዲዮን ተያዘና በአደባባይ በእንጨት ተሰቀለ ።

ግዳጇን አጼ ህዝበናኝ ተብሎ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በዘጠኝ አመቱ የገደለችው ሴት መሆኗን የአዜብ ንጉሥ መራ ወይም መራራ ልጅ እንደሆነች አወቀና ወደሃገሩ በቶሎ ተመልሶ ሲሄድ መምጣቱን ሰምታ ከመንገድ ትጠብቀው ጀመር በዚህን ጊዜ የሁለቱ ሠራዊት ንጥቅ አንድ ቀን ሙሉ ሲዋጋ ከዋለ በኋላ በንግርትዋ መንሳትዋን የሚያውቁ ጊዋ ሠራዊት እየከዱ ወደ እንቆቁሌ እምነው ገቡ አባትዋም ድል ሆንና ሲሸሽ ተከትላ ያዘችው ያንንም ቦታ በአባትዋ ስም መራ ወይም መራራ አለችው ከወንዝ ላይ ነው የተያዘ ካሉም የወንዙ ስም ነው ።

ለአባትዋም የበደላትን ሁሉ ከነገረችውና ከወቀሰችው በኋላ ይቅር በለኝ አባቴ ብላ ከእግሩ ስር ወደቀች እሱም እትዋ እንቺ ይቅር በይኝ እንቺን ብቻ ሳይሆን እምላኬን ነው የበደልኩት ዛሬ ስተኛም ስነሳም ባህር ያስጣልኩት ጋሻ ጃግሬ በፊቴ ድቅን ይላል ብሎ አለቀሰ ሁለቱም ሲያለቅሱ ከቆዩ በኋላ በሠራዊቷ ታጅበው በክብር ወደዋይዝ ከተማ ተመለሱ ቤተ መንግሥቱን ከፊቱ አብልጣ አሰርታ ለአባትዋ አስረከበችው እሱም ባል አላገባም ብላ በድንግልና ትኖር ጀመር በዚህን ጊዜ ክርስቲያን በሆነው በኑብያ ንጉሥ መርኩራስ ላይ

በቁርኝ ሥር ሆኖ ግብፅን የሚያስተዳድረው አብዱል አዚዝ ማውሬታ ንያን የሚገዛው ከሊፋ አብደል ከሪም ሆነው በአንድ ላይ ኖባንና ሶባን ሊወጉ ነው የሚባል ወሬ ለአክሱም ንጉሠ ነገሥት ለአንበሳ ሰገድ ደረሰው በዚህን ጊዜ በአማካሪው ልደታ አሚንና በእንደራሴው በሰንጥ ቃል አስፈጻሚ ወዲያውኑ በኢትዮጵያ ሃገሮች ለሚገኙት ነገ ሥታት ለአባው ንጉሥ እንዲረዱት ትእዛዝ ተላለፈ ይሄው የአዜብ ንጉሥ መሪ የበጃያን ነገዶች አሰልፎ ወደኑባ ተጓዘ ከዚያም እንደ ደረሰ ከተለያዩ ጎሳዎች የተሳሰሩና አምስት ንግሥታት በአንድ ላይ ሆነው ከሙርታንያ የመጡትን የእስላም ጦር ድል አድርገው መሰሉ ግብጺ ውያን ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጦር መሳኩን ሰምተው ለመው ጋት ፈርተው አልመጡም ፡፡

በዚሁ እለት የኑባው ንጉስ መርኩሪስ ሊረዱት ለመጡት ንጉሥታት ከሁሉም ለከበረው ለአዜብ ንጉሥ ግብር አድርጐ ሳለ አንድ አስተዋይና መልኩ ከኑባዎች የተለየ መልከ መልካም ሰው ሲናገር ባህር ያስጣለው መስሎ ታየው ንግግሩን ሲሰማ በንግግሩ ሀሊናው ከመጠን በላይ ረካ መንፈሱ ታደሰ አእምሮው ጋሻ ጃግሬውን ባህር ካስጣለው ቀን ጀምሮ በጭንቅ ይኖር ነበርና አሁን ግን ሁሉንም ያስተውልና ያዳምጥ ጀመር ልቡም ከመጠን በላይ ተደሰተ የግብሩም ሥርዓት ካበቃ በኋላ ሁሉ ንጉሡ መሪ የኑባው ንጉሥ መርኩሪዘን ያኔ ቅድም ንግግር ያደረገው ምንህ ነው መልኩም እናንተን አይመስልም ብሎ ጠየቀው የኑባ ውም ንጉሥ መርኩሪ ሠራዊቱ ወደ ጀቡቲ ንጉሥ ልኬያቸው ሳለ ሲመለሱ ከአጥቢራ ባህር ላይ ተንሳፎ በተሰበረ ሳጥን ውስጥ ሆኖ አገኙትና ከዚያ ይዘውት መጡ የባህር ልጅ ሲሉ ስሙን ባህር ሰይፍ አሉት ከእኛ ቤትም ከመጣ ቀን ጀምሮ ሃብትና በረከት በየገራችን ሞላ ቤተሰቦቼም ተፋቅረው በሰላም ይኖራሉ ህዝቤ ሁሉ ስለወደደው በበታቹ እንደራሴ አድርጌ ሾሜዋለሁ ፡፡ ከየት እንደመጣ ትውልዱን ምን እንደሆነ ጠይቀኸው ነበር አዎን ጠይቄው ነበር ነገር ግን ትውልዱን አይቶ ለማወቅ አልቻለም ከባህር የጣለህ ማነው ቢለው የንጉሥ ልጅ አፍቅሬኝ ሳለ ሎሌዎቹ ቀንተው በሳጥን ውስጥ ከተው ባህር ጣሉኝ አለኝ እኔ ቢቀኑብህ አያስገርምም አምትወደድ ልጅ ከብር የተሰጠህ ነህ አልኩት የንጉሡም ስም ጠይቄው ሊያውቀው አልቻለም እንደእኔ ግምት የአቡስን (አበሻ) ቋንቋ ማወቅ ስለሚችል ከኩናማ ወይም ከብ ሌን ጉሣ የመጣ ይመስለኛል አለው ፡፡

የአዜብ ንጉሥ መሪ ለንጉሥ መርኩሪ ሳይነጋገረው እፈልጋለሁ

ና ወደእኔ ሄደህ ላክው ሲለው የንብወም ንጉሥ የአዜብን ንጉሥ ያከ ብር ነበርና ባህርሰፍን ወደአዜብ ንጉሥ ሄዶ የሚጠይቀውን እንዲ መልስ ያዘዋል ። ባህር ሰፍ ከንጉሡ መሪ ፊት እጅ ነስቶ ይቆማል ንጉ ሡም ስምህ ማነው አለው ስሙን እንዲናገረው ሁሉ ከባህር በሉተገ ፕሁ ባህር ሰፍ እባላለሁ የተወለድኩበት ሃገር ማን ይባላል መዘገበ ከብር ይህ የምትለውን አገር አላውቀውም እንዴት ወደዚህ አገር መጣህ በልጅነቴ አንድ ትልቅ ንጉሥ ሰው ከተወለደበት ሃገር ወስዶኝ ጋሻ ጃግሬ አድርጎ በጥሩ ሁኔታ ይዞኝ ሳለ ልጁ ወደደችኝ ስለዚህ ሥራዊቶቹ ቀንተው ወደባህር ወስደው ከዋንዛ ግንድ በታፈለ ፈለ ሳጥን ውስጥ አሽገው ከወንዝ በዘር ጣሉኝ ከዚያ የወሃ ሙላት ይዞኝ ወደዚህ አገር ሲያመጣኝ ሰዎች ከባህሩ አውጥተው ወደዚህ ከተማ አመጡኝ የንጉሡን ስም ታውቀዋለህ አላውቀውም ጌታዬ ነበር ሁላችን የምንለው ልጁንስ ልጅ እንዲት ናት ስምዋ መሳብ ወርቅ መን ይሩ ይብረመርት ይባላል ንጉሡንና ልጁን ትወዳቸው ነበር በጣም እወዳቸዋለሁ ጌታዬንም ብንግራቸው ሃገሩን የምትጠራውን ስላላወ ቅኩው ወደየት ብየ እሰድሃለሁ ስላሉኝ ነው እንጂ ሃገሩን ባውቀው ኖሮ ለአንድ ቀን የጥንቱን ጌታዬንና ልጁን ፊታቸውን አይቼ ብመለስ እንዴት ያለ ደስታ በተሰማኝ ሲል ንጉሥ መሪይ ወደው ነበርና ፊቱን ወር አለቀስ በል አሁን ከእኔ ጋር ጌታህን አስፈቅጄ ወደሃገሬ ይዤህ እሄዳለሁ ከዚያ የምትለውን ሰዎች አይተሃቸው ትመለሳለህ ሲለው በጣም ደስ አለው ከዚያ ለኑባው ንጉሥ ታሪኩን በምስጢር ነገረውና ይሁት ወዳሃገሩ ተመለሰ ገና የንጉሡ ልጅ በሩት ስታየው እሮጣ ሄዳ እቅፉ ሳመችው ከትንሽ ቀን በኋላ ወደተወለደበት ሃገር ልቶ ሲ መዘገበ ከብር ይዛው ሄደችና ከወላጆቹ ጋር አገናኘችው እናቱም ነገሩ ልጃቸ መሆኑን እረሲታ ብዙ ሰዓት ፈዛ ቆመች አላመነችም ትርጓሴ ገበዝ እንቀዮቹን ወይም ትርጓሴገበዝ ከንጉሬቻትና እሱቱ ገበዝ አቤሜሌክ ልጁ መሆኑን አለጥርጥር ሲያቅፈውና ሲስመው አይታ እናቱም እሰመሞቱን አምና እየአለቀሰች ታቅፈውና ትስመው ጀመር የመሪሰ ልጅ እንቁዮቹ በእከሱም ትርጓሴ ገበዝ የተባለችበት የንጉሥ የአቤሜ ሌከ ሁለት ልጆች በእሱዋ ምክንያት ስለተገኙሉ የምዋቶቹን ወል ጆች ልትረዳ ስለገባች አቤሜሌክ የአከሱም ገበዝ ስለነበር ትርጓሴ ገበዝ ትባል ነበር ሆኖ ግን እኒ ግዳጇን ህዝበናኝ ስለገደለች ከአከሱም ወደዋይዝ ተመልሳ ሄዳ ነበር ከቀን በኋላ የአዜብ ንጉሥ ሴት ልጅ ንጉሡንጉሥቱን ህዝበናኝን መግደልዋ ስለታወቀ ማንም የህዝበናኝ ልጅ ውድም ቢሆን ሀገን እሚካሪዎችን ለመግደል ቆርጦ ነበር ወደዋ እያቸለ ስለሄደ የሚደፍራት ጠፋ ከአከሱም እንደተመለሰች ወደዋ

ከተማ ቡግና ሄዳ የምትወደውን ሰለሞንን አግብታ በስነ ስርዓት በአ ባትዋ መንግሥት ላይ በመመንግሥቱን ንጉሥ ባህር ሰዶ ብላ እንገ ሥታቸው እሱዋም ነግሣ በአባቷ ዙፋን ተቀመጠች በትንግሥዋ በሥዋ እንቆቋዝዋን ተብሏል ። በዚሁ ዘመን አባትዋ ጌዲዮን የሚባል በአክሱም አደባባይ ተሰቅሎ የምትባት አስቴር የተባለች ፈላሻ ወደ ቡግና መጥታ ከትርዳ አገበዝ ቤት ሊታገለግል ገባች ከዚያም የአባት ዋን ገዳዮች ነገሥታት ጠላት መሆኗን ስለምታውቅ ሌት ተቀን ሳት ደክም ንግሥቲቱን እንቆቁዲዝዋንን ታገለግል ጀመር ንግሥቲቱም እን ቁዲዝዋን እንደሷ ብርቱ ሴት መሆኗን አይታ በውስጥና በውጭ ባሉ ሠራተኛና አገልጋይ ሁሉ የበላይነቱን ሰጠቻት ። ከሴሎቹም ወንድ ጅል ወለደችና ስሙን ተከለሃይማኖት አሉችው ከዚያም ባኋ ስለመንግሥ ታቸው የማይዋጋ ዘሉተኛ ጸድቅ ሰው ስለነበር አስቴርን የጴጥ ብላ የጴጥ ጦር ሠራዊት አሲታ እያረገዳት የዲትም የሕዝቦቹምና የወገና ቻን ገዳዮች ለማጥፋት ምኞት ነበራትና ሠራዊትዋን ከቀን ወደ ቀን እያበዛች ሄደች በዚህን ጊዜ በጠለምትና በወሊታይት በጂዳ በሰሜን በባሬው ወገራ የሚኖሩ ፈላሾች ወገኖቻቸው የምትሆን አስቴር የጦር መሪ አዛዥ መሆንዋን ሲሰሙ ለትርዳ አገበዝ ግብርና እጅ መንሻ ይዘው እየመጡ ይገቡ ጀመር ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር በሃይማ ኖት ቅራኔ የነበራቸው የአረብ ነገሥታት ምንም በንቢዩ መሃመድ በአርማህ በልጂም በአልነጋሺ ዘመን ወዳጅነት ቢኖራቸው የእስልም ናን ሃይማኖት አስተማሪዎችና የጦር አለቆችን በኢትዮጵያ ጎንሮች ላይ እየላኩ የአክሱምን ግዛት ለሁሉቅን ሙሉዋን ታሪራ ኦሎሊስን ስዋኪን በርበራን ያሲዙበት ነበርና እየደከመ መጣ ስለዚህ የአክሱም መን ግሥት የባህር ጉዞና ብዙ መርከቦች የነበረው ጥሩ አሁን ሃገሮቹን ቀርቶ እራሱን የሚከላከልበት የጦር ሠራዊት ጹዋ ስለሌለው አይተው አስቆመና ፈላሻው ተንሳበት እንደዚሁም ሆነ የህዝብናኝ ልጅ አንበሳ ውድድ የተባለው ውድም በንጉሡ በሃያ አመት በተወለደ በሃያ ሰባት አመቱ የጴጥ ሠራዊቱን አሠልፎ በግሥጋሤ ከአክሱም ወደ ቡግና ትርዳ አገበዝን ለመውጋት ሄደ ትርዳአ ገበዝም ከተዋጊነቱዋ ሌላ መሰኛ ነበረችና የሃገሬውን ባላባትና መማፍንት ሰብስባ የአክሱም ንጉሡ ነገሥት አንበሳ ውድድ ሃብታችን ሊዘርፍ እኛን ሊያጠፋ ጦር ከተት ብሎ እዋጅ ነጋሪ መጥቶአልና በየቤታችሁ ወይን እዚጋጅታ ችሁ ቆዩ ሲመጡ ሠራዊቱን እስከሚሰከር አጠጡት ብላ አዘዘች በዚ ህን ጊዜ ዘመኑ አረሃብ ነበርና ተርቦ ተጠምቶ የነበረ ሠራዊት በየባላ ገሩ ቤት ተሰማርቶ የተዘጋጀለትን ወይን ጠጥቶ ሰከረና በየጎሮው ወደቀ በዚህን ጊዜ ንጉሡ ነገሥቱ ከሠፈረበት ሠፈር ሄዳ ከትንሽ

ወታደር ጋር እየኖቸውና አስከብባ ማረከችው ትርዳኢ ገብዝም አባት
ከነ ድንግልናየን ሊያጠፋ ሲል የገደልኩት በሥራው ነው አሁንም
እንተም እንደከቱ ሥራህ እንልሀ ነበር ነገር ግን ለእምላኬ ስል እሌ
ገልሀም ብላ በለላም ወደአከሱም መለሰችው የማረኬችበትን ሃገር
መላይዳ— (መልዛ) አሉት እንደዚሁ በመጫ ነው ሠራዊቱን በየቤቱ
አስደግበኝና አስከረኝ የያዝኳኝ እንጅ እንደጀግናዎቹ በጦር ሜዳ ገጥ
መኝ አልያዝኸኝም ብሎ ለጦርነት ሊገጥማት ላከባት ከዚያም በተ
ቃጠሩት ቀን የሁለቱ ሠራዊት ገጥሞ የትርዳኢገብዝሞኖሩ ድል አደረገ
ድል ያደረገችበት ሃገር በለላ አሉት ሙድያም በጦርነቱ ድል ሆነና
ሸሽቶ አመለጠ ዮዲት የተባለችው አስቴር ተከታትላው አክሱም ደረ
ሰች ከዚያም እንደማትተወው አውቆ ከትንሽ ጴጥ ጦር ጋር ቤተሰቡ
ቹንና የእስር እመት ልጁን ድልነዓድን ይዞ ወደጉጃም ጄደ ጉጃምም
እንደደረሰ ንጉሥ ዳንግግ ልጆቹ አባረውት ሳለ በዚያው ተሰዶ የወለ
ዳቸው ልጆች የአባታቸውን መንግሥት ለመያዝ ዙፋኑን ለመውረስ
ይመኙ ነበርና ሸሽቶ መምጣቱን ሰሙና ሊገሉት ከአለበት ሠፈር
ድረስ ሄዱ ከዚያም አምልጦ ሸዋ ወደሚገኘው ንጉሥ ማሙዬ ጄደ
ንጉሥ ማሙዬም የሄሬው ሸዋ የየንቱን ገዢማን እስከ ሞላሉና ፈን
ታሌ ድረስ በአክሱም ንጉሠ ነገሥት ስር ሆኖ ይገዛ ነበርና በክብር
ተቀብለው ከዚያም ባጀባ በቤተ መራ በሄሬው መራ-ቤቱ በቤተ ዳን
የሚኖሩ የጴጥ ጦርና ባላባቶች እየመጡ እጅ መንሻና ግብር እየያዙ
መጥተው ተቀውቁ በዚህን ጊዜ ዮዲት ማምለጡን ሰምታ በአክሱም
አካባቢና በዳህላቅ በአዶሊስ የተሠሩትን ቤተ ክርስቲያናት እንዲቃ
ጠሉ ካህናቶቹና የነገሥታት ዘሮች እንዲገደሉ አዘዘች ከክርስቲያን
መንግሥት ጋር የከረረ ጠብ የነበራቸው ፈላሾችና እስላሞች በደስታ
እዋጁን ተቀብለው ቤተ ክርስቲያኖችን እያጠፉ ሃውልቶችን እያፈረሱ
የነገሥታትን ጴጥ ሠራዊት በያሉበት እየሄዱ ገደሉ ዮዲትም እንደ
ዘመኑ ሥርዓትና ልማድ የውስጥ ጦርነት እንዳያስነሱ ተብለው በደብረ
ዳሞ ተራራ ላይ በዘበኛ ይጠበቁ የነበሩትን የነገሥታት ልጆችና መሣ
ፍንት ሁሉ ሰብስባ አሳረደቻቸው ከዚያም እሬሳቸውን በአንድ አዳራ
ሽ ውስጥ አስተኝታ አቃጠለቻቸው በዚህን ጊዜ የቀሩትም ንግሥት
ትርዳኢ ገብዝ ቤተ ክርስቲያኑንና ቤተ መንግሥቱን ማቃጠሏን ሃው
ልት ማፍረሷን የነገሥታትን ልጆች ሰብስባ አርዳ ማቃጠሏን ሰለሰ
ማች ይህ የምሰማው ሁሉ አድርገሽ ከሆነ እንቺንም ሆነ ዘርሽን
እንዳያደረግሽው ሁሉ አደርጋለሁ ካለፍቃዴ ሠራዊቱን ሁሉ ሰብስበሽ
መቅረትሽ አልበቃ ብሎ የነገሥታትን ልጆችና የእግዚአብሔር አገ
ልጋይ የሆኑ ካህናትን በማስገደልሽ መጣሁብሽ ጠብቂኝ ብላ ለዮዲት

ላከችላት ዮዲትም ከፊቱ የበሰጠ ከፈላጆችና ከአረቦች የተቀላቀለ ጭፍራ ስላላት በትምክህት እንዲህ ስትል ላከችባት ሥራዊትሽ ሥራዊቴ ነው ግዛትሽም ግዛቴ ነው ልጅሽም ባሉ ነው ስለዚህ እኔ ያንችን ስወስድ አንቺ ከእኔ የምትወስጂው ስለሌለ ጭፍራቱ ከአንቺ ሥራዊት ስለሚበልጥ በክብር አርፈሽ ተቀመጭ እመጣለሁ ካልሽ አንቺ ከመድከምሽ እኔ መጣሁልሽ ብላ ላከችባት ከዚህ መሃል ሁለቱም ወታደራቸውን ሲያደራጁ አንድ ክረምት አለፈና በየካቲት ወርሀ በጂዳ ከሚባለው ቦታ ላይ ተገናኙና የሁለቱ ሥራዊት ጦርነት ጀመረ ሆኖም ግን ሁለት ቀን ከተዋጋ በኋላ በዮዲት ሥራዊት ሃይል የትርዳእ ገበዝ የጦር ሥራዊት ከአበር ሽሀ በላይ ተገደለ ትርዳእ ገበዝም ድል ሆነችና ተማረከች በዚህን ጊዜ ዮዲት አንቺ እናቴ እንጅ ጠላቴ አይደለሽም የአስገደልኩት ጠላቶችሽን እንጂ ወዳጆችሽን አይደለም በህይወቱም የጨከንኩት ሴት አትንግስም አትገባም ስለሚሉ የወንጌልን ካህናት ብቻ ሳይሆን የእምቢንም የአረት ካህናት በጭርድ አስገድያለሁ አሌቻችና ታርቀው በክብር ከብዙ ሥራዊት ጋር ወደቡግና መለሰቻት ዮዲትንም ስምዋን ጉዲት እንጂ ዮዲት አትበሏት ሰውን ገድላ ስለምታታጥ ልሁልጊዜ አግቶ እንጂ ሴት ወይም አስቴር አትበሏት ተብሎ በአዋጅ ተነገረ ያኔም የተዋጉበት ቦታ ቢገላ ይባላል ትርዳእገበዝም ሃይሏ እየቀነሰ ስለሄደ በብስጭት በተወለደች በአምሳ ሰባት አመቷ አረፈች ባሏ ባዘር ሰፍ በፍቅርና በክብር በሀዝብ ዘንድ እንደጸደቅ ተወዶ ሲኖር እሱም ሚስቱ በሞተች በሰባተኛው ቀን አረፈና አብረው በአዘጋጁት ቀኛ አለት ውስጥ ተቀበሩ።

እንደዚህም ሆኖ ትርዳእገበዝና ባዘርሰፍ ከሞቱበት ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ረሃብና በሽታ ሆነ እንሰሳና ሰውም እየታመመ በየዱሩ በየመንገዱ እየሞተ ይገኝ ጀመር የውድም አስፈፊ ልጅ የሀዝብ ባርኮ ልጅ አክሱማይ ሲፈስ የንዋየ ቅድሳቱንና የልዩ ልዩ ምስጢር እቃቤት አላፊ ስለነበርኩ የኢትዮጵያን ነገሥታትና የእግዚአብሄር አገልጋይ የሆኑ የካህናቶቹን ታሪክ የያዘውን መፅሃፈ ሱባኤ ይዤ ወደግብፅ ከሚሄዱት ነጋዴዎች ጋር ሄድኩ ከዚያም በናፓታ በመርዌ በደልታ በሳይስ በአማርና ከቆየሁ በኋላ በንባው ንጉሥ በጊዮርጊስ ትእዛዝ ወደጂባ ተላኩ መፅሐፉን ለዕሰት ሃገሮች በአቡሳውያንና በኪቲያውያን ቋንቋ ፅፌ ላኩ ከዚያ ወዲህ በኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥትና በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ የሆነውን አላውቅም የጂባን ሀዝብ ከእስለወንኩ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ንጉሡ ኑባ ተብየ እንደተነገበኩ የኢትዮጵያን ታሪክ ፅፌ ወደአንዳንድ ሃገሮች ላኩኝ ከአክሱማይ ሲፈስ

ቀኖቱ ዘግዳር ዘቤተ እንዳ የጸፈውን ታሪከ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመ
ራራስ አማን በላይ እንደኖና የተዘጋጀውን ጉዲት የተባለችው ዮዲት
የአክሱምን ነገሥታት ዘርና ካህናቱን አጥፍታ ያለእረፍት ያለደለት
በሥቃይ የበላይ ሳይኖርባት በአክሱም አካባቢ ያሉትን ሃገሮች ሃያ
አምስት አመት ገዛች በዘመኑዋ የእስልምናን ሃይማኖት ተከታዮችና
አይሁዶች እየተሰደዱ እየመጡ ለእስላም ቢንባቱ የግንቡ ተወላጅ ሥራ
ቂቱን አድብቶ እየገደለ አልገብርም እያለ በጣም አስቸጋሪት ነበር
በዚህን ጊዜ የንጉሥ ዘር የሆነ ክርስቲያን ካዳግማዊ እረፍት አታገኝም
ሀገሩም ሰላምና ደስታ እያገኘም ብለው ትንቢት ተናጋሪዎች የአራት
ክህነቶች ስለነገሩዋቸው የመጀመሪያ ባሉዋን ተከለሃይማኖትን ምንትም
ከአንተ ጋር ያለያዩትና ከእናትህ ጋር ያባለን ከተ ቀን አሁንም ይህ
ከቶ ቀን አልፏልና የአባቶችህን መንግሥት አሁኑኑ መጥተህ ተረከብ
በአባቶችህም ዙፋን ተቀመጥ ብላ ላከችበት ተከለሃይማኖትም እንደም
ትወደው ያውቅ ነበርና ከዮዲት ያካንሰ ሥራዊት አስከትሎ መጣ እሷም
ቤተ አሹር ከሚባለው ሃገር ላይ በወገኖቹ በጭፍራዎቹ ታጅባ ቀናችው
የተገኙበትን ሃገር ወገራ አሉት ከዚያም ሁለቱ በአንድ ላይ ሰንበ
ቂና ወደአክሱም ሥርዓተንግሡን ለማክበር ሄዱ ነገር ግን ከአይሁ
ዶች በቀር የሁለቱን ሰዎች መተባበር ህዝቡ አልደገፍላቸው ብሎ ከሬቂ
ዶች በቀር የሁለቱን ሰዎች መተባበር ህዝቡ በክርስቲያንና በፈላሾች
የባለ ጦርነት በየቦታው ተቀሰቀሰ በዚህን ጊዜ ከአክሱም ወደቡግና ተመ
የነበረው ቅያሜ ስለበረታ ተከለ ሃይማኖት ከአክሱም መካከል ቂም ባይኖር
ልሶ ሄዶ ተቀመጠ በዮዲትና በተከለሃይማኖት መካከል ቂም ባይኖር
በሰዘቡ ዘንድ ያለው ጥላቻ ከቀን ወደቀን እየከፋ ሄደ በዚህን ጊዜ
ከጭግ ወደትግሬ ተከለሃይማኖት መጥቶ እንደሰነበተ በክርስቲያን እና
በአይሁድ በእስላሙ ህዝብ ላይ የርስ በርስ ጦርነት ተነሳና እነዚህም
ከተማዎችንና በአካባቢ የሚገኙት መንደሮች ሁሉ በእሳት ተቃጠሉ
የሁለቱ ሰዎች ጭፍራ ያለርህራሄ በሰይፍ ታረዱ እርስ በራሳቸው ተዋጉ
እንዲሁ እንዴ በመር ይወጋዋል በሰይፍ ያርዳዋል በሰው ዘንድ ፍቅርና
ሰላም ጠፋ ጉዲት የተባለችው ዮዲትም በነገሠች በአርባ አንድ በተቀ
ለደች በስልሳ ዘጠኝ አመትዋ ከፎቅ ላይ ወድቃ ሞተች እንደሚገባ
ህዝብ ተከለሃይማኖት ንጉሥ ጣሉት ይባላል ከዚያ የበጀያ (የአገው)
የጠለምት ነገዶች ሥጋዋን ከአርባ ቆርጠው ከሃገራቸው ወስደው እሷ
ጠሉት እንደሚገባ እምራ ይብላት ብለው ጫካ ወስደው ጣሏት ይባ
ላል ከዚያ ተከለሃይማኖት አክሱም መኖር ስለፈራ ወደሀገሩ ወደ ቡግና
መጥቶ በአባ ጴጥሮስ በሚባል መንኩሴ እጅ ቅባአ መንግሥት ተቀ
ብቶ በዘጠኝ መቶ አሰራዘጠኝ ዓ.ም. ላይ ሀዳር አስራ ሁለት ቀን
ትርጓሜገበዝ ድል ባደረገችበት ምንጭ አጠገብ ሥርዓተ ንግሡን አከበረ

ቆየ በዚያም ቦታ የሚካኤልን ታቦት አስተክሎ ስሙንም መራ ተክለ ሃይማኖት በሉኝ አለ ነገር ግን መንግሥቱም ከሰሎሞን ልጅ ከዛጉዌ ዘር የወረደ መሆኑን ለመግለፅ ስመ መንግሥቱ እንደአክሱም ሥርዓት አጼ ዛጉዌ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ የአባል የመደበኛ የጋፋት የትግራይ የአገው ንጉሶችና ነገዶች እጅ መንሻና ገፀበረከት እየያዙ መጥተው ንጉሠ ነገሥታችን አንተ ነህ እያሉ ሰገዱለት አጼ ዛጉዌ በንግሥናት ዘመን የሰላም ጊዜ ስለነበረ ህዝቡ ከአንድ ወደ አንድ ሃገር እንደልቡ ይዘዋወር ጀመር በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ሁሉ እህል በአራሽ ጉተራ ስለሞላ ከዳር እስከዳር እምቦ ተገባለት በዚህን ጊዜ የመድም ልጅ ዮሴ ነዓኮ ዮዲት እንደሞተች ሰምቶ ከቤተ መራ ከተማ ከዶባ ወደአክሱም መጥቶ ሊነግሥ ነበር ነገር ግን የትግሬ የአባል የበጌዳ ነገዶች ጌታችንና መሪያችን ንጉሣችንም አጼ ዛጉዌ ነው ሲሉ ተቃውመው መለሱት የድልነዓድ አባት በስደት ላለ ልጄን እንድታነግሡልኝ አደራ ብሎ ተናዞ ሞቶ ስለነበር በዚያው ዳጉ በሚ ባለው ተራራ ስር በዛሬው ተጉለት የሸዋ ህዝቦች አነገሡት ነገር ግን የንጉሠ ነገሥትን ያክል ክብር ስላልሰጡት መንግሥቱ እየደከመ ሄደ ይሄውም ለመራ ተክለሃይማኖት አጼ ዛጉዌ ተብሎ ለነገሠው የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉ ከዳር እስከዳር በሰላምና በደስታ ስለተገዙ ለት አውቆ ፈራ ንግሥናውን ተወው እንደዚሁም ሆነ አጼ ዛጉዌ ንጉሠ ነገሥት አዲስ ሥርዓ መንግሥት መስራች ከመሆኑ ሌላ የሰሎ ሞን ዘር መሆኑን አስታውቆ ከእሱ ተተክለው የሚነግሡት ሃጼ አርባ አመት እንዲነግሡ ብሎ አሳወጀ ለግመኛም ከአርባው አመት እንዳይጨምሩ እንዳይቀንሱ አርባ አመት ብቻ እንዲነግሡ ብሎ ተና ዘዘ በንጉሥ በሰላሳ ዘጠኝ ለአዘብ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በአስራ ሶስት አመቱ አርፎ ደብረሮሃ ተቀበረ በፋንታው ልጁ ጠጡ ውድም ስመ መንግሥቱ ዐር ሰገድ ሃጼ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ በ932 ዓ.ም. የምሴ አምስት ቀን ነገሠ ሲነግሥም የሰላሳ አምስት አመት ሰው ነበር ። አጼ ዐር ሰገድ (ጠላት ሰገደለት ማለት ነው ። የተባለው ጠጠውድም የአባቱን መንግሥት ከወረሰና ከዙፋን ከወጣ ቀን ጀምሮ ጉዲት በተባለችው በአባቱ ሚስት በዮዲት የፈ/ሰውን የውሏት እንደገና በሁሉን አድማስ ድንጋዩን እያቀለጠ እያያዘው ከተቀበረበ ትም እያስወጣ እቃመው ብዙ ቤተ ክርስቲያኖችንም በየቦታው ተተ ክሎ እንደዚሁም በዮዲት ዘመን ወደጉብያና ወደግብፅ የተሰደዱ ክርስቲያኖች ተመልሰው ወደሃገራቸው ገቡ በዚህን ጊዜ በግብፅ የነ በሩ ሉሊማኖች በኢትዮጵያ የነበረው የክርስቲያን መንግሥት በአን ዲት አይሁድ ፈጽሞ ጠፋ እያሉ በኑቢያና በግብፅ የሚገኙትን

ክርስቲያኖች ያስታጥቁአቸው ጀመር ነገር ግን እንደገና አዲስ የክርስቲ
ያን መንግሥት ተመሰረተ ክርስቲያን ወዳጅ ነው የሚባል ወሬ በእስክ
ንድርያ ስለተሰማ ምንም በግዛቱ የእስላሞች ሃይል እየበረታ ቢሄድ
የቱርክ መንግሥት የሊቀ ጳጳሱን መቀመጫ ከእስክንድርያ ወደ ካይሮ
እያዞረች ነገር ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቀዝሞስ ከደስታቸው ብዛት በእስቸ
ኳይ አቡነ ጴጥሮስ የሚባሉትን መርጠው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ ከአቡነ
ጴጥሮስ ጋር ብዙ ክርስቲያን የሆኑ ግብጻውያን አብረው መጡ ንጉሠ
ነገሥቱም አጼ ፀር ሰገድ አክሱም ጽዮንን ያሠሩ ነበርና ከሁሉም
ይልቅ ጳጳስ ከቀረ ብዙ ጊዜ ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱና ህዝቡ በታላቅ
ክብርና ደስታ ተቀበሏቸው በዚህን ጊዜ ድልነአድ ለአዲሱ ጳጳሳት
ለአቡነ ቀዝሞስ ወደእኔ ነው መምጣት የሚገባቸው ሲል ቅሬታቸው
ነበር ነገር ግን በጊዜው መንግሥቱን ሲቆጣጠረውና ሲገዛ የነበረው
ይኸው የፃጉቱ ልጅ በመሆኑ አቡነ ጴጥሮስ ከአጼ ፀር ሰገድ ጋር
በፍቅርና በሰላም ብዙ ዘመን በቤተ እንግዳ በጉንድ በፀጥታና እየተዘዋ
ወሩ ኖሩ ። እንደዚህም ሆኖ የንጉሠ ነገሥቱ የጠጠ ወንድም ሁለት
መንታ ልጆች አኩቴትና በእምነት የሚባሉ ነበሩት አባቱ መራ
ተክለሃይማኖት ለአንድ ሰው አርባ አመት ብቻ እንዲገዛ ስለሰጠውና
ሥርዓት ሆኖ እንዲቀር ብሎ ስለአዘዘው ግዛቱ አርባ አመቱ ስለሞላ
ጳጳሱን አቡነ ጴጥሮስን ጠርቶ ከሁለቱ መንታ ልጆቹ ለማንኛው መን
ግሥቱን ያውርስ ብሎ ጠየቃቸው ጳጳሱም አስተዋይ የሆነው ታናሹ
አኩቴት ይንግሥ ብለው አስታወቁ አጼ ፀርሰገድም በነገሠ በአርባ
አመቱ ታናሽ ልጁን አኩቴትን ስመመንግሥቱን ጃን ሰዩመንጉሠ
ነገሥት በኢትዮጵያ አሰኝቶ በአቡነ ጴጥሮስ እጅ ቅብአ መንግሥት
አስቀብቶ ለቀቀለት አኩቴትም ጃን ሰዩም ተብሎ በ972 ዓ.ም. በዘ
ጠኝ መቶ ሰባ ሁለት ዓመተ ምሕረት ነገሠ በዚህም ጊዜ በእምነት
የአባቱን መንግሥት በጳጳሱ ምርጫ ለታናሹ ወንድም ስለተሰጠበት
ጳጳሱን የሚበቀልበት መንገድ ሲፈልግ ሳለ እርሱን የሚወዱ አቡነ
ጴጥሮስን የሚጠሉ ሁለት መነኩሴዎች ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት
ከአባ ቀዝሞስ ዘንድ እንደመጣ አስመስለው ሃሰተኛ ደብዳቤ ፅፈው
ለትልቁ ልጅ ለበእምነት ሰጡት ደብዳቤውም የሚለው አባ ጴጥሮስ
ከሊቀ ጳጳሳት ተሹሞ ሳይመጣ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት የሚ
ያታልል ሃሰተኛ ጳጳስ ነው ሁለተኛ በዙፋን ሊቀመጥ የሚገባው
የንጉሠ ነገሥቱ የበኩር ልጅ እንጂ ትንሹ ሊቀመጥ አይገባውም
የሚል ስለነበር ይህን ደብዳቤ ይዞ ብዙ ሠራዊት አስታጥቆ ተዋጋ
ድል ከአደረገው በኋላ የንጉሡውን ወንድሙንና ጳጳሱን ከሹመታቸው
አውርዶ አስሯቸው ደብዳቤ ያመጡትን መነኩሳት አንዱን አቡነ

ናስ በጳጳሱ ምትክ ሌላውን አባ ፊቅጦር የሚባለውን ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾሞ አስቀመጠ ። በዚህን ጊዜ በሁለቱ መካከል ክርክር ተነሣና ተከራክረው ከቆዩ በኋላ ፊቅጦር የሚባለው ከአባ ሚናስ ቤት ያገ ኘውን ወርቅና መክሊዶች አጠራቅሞ ዘርፎ ወደግብፅ ሄዶ ከዚያም ወደእስልምና ሃይማኖት ተመልሶ ቀረ ። በዚህ ጊዜ የአባ ሚናስን ኢታማኝነት ገንዘቡ ሰርቆ የሄደው ጓደኛው ስላጋለጠበት ሊቀ ጳጳሳቱ ሰምተው አቡነ ጴጥሮስ እውነተኛ ጳጳስ ለንደሆኑ በሚናስ ላይ የውግ ዘት ቃል ለንጉሡ በእምነት ላኩለት ንጉሡ በጳጳሱና በወንድሙ ላይ ያደረገውን ውርደትና እስራት ተፀፅቶ ሃሰተኛውን ጳጳስ ሚናስን በአደባባይ ሰቀለው አቡነ ጴጥሮስን መልሶ በክብር አስቀምጦ ሲሞ ሾም ቢፈልግ በግዞት ሳሉ ሙተው ሳያገኛቸው ቀረ ። በዚህን ጊዜ በሃገሩ በኢትዮጵያ ምድር ረሃብ ቸነፈር ስለበዛ ሊታረኝ ወንድሙ አግዚን ሰዶም ተብሎ ንግሥ ለነበረው ለእኅቱት ለቀቀለት እኩሌቱትም ለበእምነት አብረን በአንድ ቀን በለተወለደ መንታ ስለሆኑ አርባውን አመት አንድ አንድ ሰው አብረን እንገዛለን ብለው ለጊዜው ጳጳስ ስላልነበረ የአቡነ ጴጥሮስ እንዲሁም ለነበረው በኢጵስ ቆጶስ ማርቆስ ቅብአ መንግሥት ተቀብተው ሰው መንግሥቱም ግርማ ሰዶም ተብሎ በአንድ ላይ ይገዙና ያስተዳድሩ ጀመር ። አንዳንድ ፀሐፊዎች ሃያ ሃያ አመት ተከፋፍለው ነው የገዙት ስለሃይማኖት አይቸገሩም ነበርና ከግ ብፁ ጳጳስ ለማስመጣት አልተሃፃፉም ሲሊቀ ጳጳሳቱ የሚላከውን ግብርና እጅ መንሻ አስቀሩ እየተባለ ምሬት ተቀርሶባቸዋል ።

በእንደዚህ ዓይነት አጼ ጀንሰዶምና አፄግርማን ሰዶም በአንድ ላይ አርባ ዓመት በፍቅርና በሰላም ከገዙ በኋላ ላባ እምነት ልጇ ለመ ደራሬ ዙፋናቸውን ለቀቁለት ።

መደራረም ስመ መንግሥቱ አጼ ድልንአድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ ትዮጵያ ተብሎ በአንድ ሽህ አስራ ሁለት ዓ.ም. 1012 ነገሠ በዚህን ጊዜ ከሊፋ ሃኪም የሚባለው የግብፅን ሃገር ሁሉን በቁራን ለማሳመን ሲል ክርስቲያኖችን ማሰር መግደል ጀመረ ሊቀ ጳጳሳቱንም አቡነ ዘካርያስ የሚባሉትንም አሠራቸው በዚህን ጊዜ ቤተክርስቲያናት ሲቃጠሉ ስለአዩ ብዙ ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ይኸው ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ድልነአድ ተቀብሎ እርስትና ጉልት ሰጥቶ በምድሩና በሉ ሲታ አስቀመጣቸው የሚበዙት ግንት በመርቂና በናፖታ በእማራና በሚኖሩ ጼዋ ወታደሮች ነበሩ እነሱ ከመጡ በኋላ ከኢትዮጵያ ብዙ ጥቅም ስለቀረባቸው ተቋርጦ የነበረው ግንኙነት እንደገና ቀጥሎ ኑሯ ዱ ይመላለስ ጀመር በዚሁ ዘመን በአቡነ ክሪስቶዱሉ ሊቀ ጳጳስና

ዘመን አብሬዱ የሚባል ሃሰተኛ ደብዳቤ ይዞ መጥቶ አባ ቄርሎስ ተብሎ በኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነ በዚህን ጊዜ በነጋዴዎች አማካኝነት ወዜሩ ሰማና እሱን ሳታስፈቅድ ወደኢትዮጵያ ጳጳስ የላከ ብሎ ቢጠይቃቸው ሊቀጳጳሱም አባ ክሪስቶዶሉ አላኩም ሲሉ መለሱለት ከርሳቸውም ቀጥለው አባ ቄርሎስ የሊቀ ጵጵስናውን ሥራ ያዙና በወዚር ባድርኤል ጀማል ትእዛዝ የእስላሞች ወዳጅ የሆነትን አባ ሳዊሮስን ቀብተው ወደኢትዮጵያ ላኳቸው በዚህን ጊዜ ሃሰተኛው አባ ቄርሎስ ጳጳስ ነኝ ብሎ በኢትዮጵያ ተቀምጦ የነበረው እውነተኛው ጳጳስ መምጣቱን ሰምቶ ወደ ዳህላቅ ሸሽቶ ሄደ በዮዲት ዘመን የአክሱም መንግሥት ስለወደቀ ዳህላቅ በዐረቦች እስላሞች እጅ ስለነበረ ሃሰተኛውን ጳጳስ ይዘው ወደግብፅ ላኩትና በወዚሩ ትእዛዝ አንገቱ ተቆርጦ ተገደለ።

አዲሱ ጳጳስ አባ ሳዊሮስ ከንጉሡ ነገሥቱ ከአጼ ድልነአድ ተገናኝተው በክብርና በማዕረግ ተቀምጠው ሥራቸውን ጀምረው ሳለ በእስላሞች ሹም ተመርጠው ስለመጡ በኢትዮጵያ ሃገሮች ሁሉ እስላሞች እንዲበረክቱ መስጊድ በየቦታው እንዲሰሩ አምልኮታቸውንም እንደልብ እንዲያመልኩ ጠዋትና ማታ ይረዷቸው ጀመር። ንጉሡ ነገሥቱ አጼ ድልነአድና ህዝቡም ተቆጣና በጳጳሱ አርስዎ የክርስቲያን አባት የክርስቲያን ሃይማኖት መሪ ሲሆኑ ቤተክርስቲያን እንደማሠራት መስጊድን ያሰራሉ ክርስቲያን ህዝብን እንደመደገፍ እስላሞችን እንዴት እየደገፉ ይረዳሉ ብሎ አሠራቸው በዚህን ጊዜ የጳጳሱ ወንድም አብሮ ይኖር ነበርና ወደግብፅ ሄዶ ለወዚሩ ባድር ኤል ጀማል ለእስላሞች ባደረጉት እርዳታ መታሰራቸውን ገለፀለት ወዚሩም ተናደደና በግብፅ ያሉትን ቤተክርስቲያኖች ሁሉ አፈርሳለሁ እኔ የምልውን እስከአላደረገ ድረስ ብሎ ጻፈለት አጼ ድልነአድም ሃሰተኛ ጳጳስ በመላከህ አልበቃ ብሎ ደግሞ አንድ ቤተክርስቲያን ብታፈርስ ለመስጊድህ ያዘጋጀኸውን ድንጋይና መስጊድህን አስፈርሼ እሰራለሁ ብሎ ላከለት ሆኖ ግን መደራረሩ አጼ ድልነአድ ጳጳሱ ካለሃይማኖታቸው ገብተው መስጊድ በማሰራታቸው ተናዶ አሰሯቸው እንጂ እስላሞች በሉ ጊዜ እንደልባቸው የፈቀዱትን ያደርጉ ነበር የንጉሡ ነገሥቱ እናት የዐረብ ሃይማኖት ተከታይና አማኝ ስለነበረች እሱም ሃይማኖቱ ዐረብ በየጁ እምነት ነበር ይባላል ለህዝቡም የመረጣችሁትን ሃይማኖት መቀበል ትችላላችሁ ይል ነበር እንደ አባቶቹ ሥርዓት እርባ አመት ከገዛ በኋላ የአጎቱ ልጅን ሥዩም ልጅ ለየበ ዙፋኑን ለቀቀለትና እሱም ፍየል እያሰረበ ይኖር ጀመር ከየዘል መንጋ ብዛት ጠባቂዎቹ 2 ሺህ ነበሩ። ጃን ሰዩም ተብሎ የንጉሡ የእኅቱት ልጅ ሃርቤ ስዩመ እግዚአብሔር ቅዱስ በአንድ ሺህ አም

ሁለት ዓ.ም. ታህሳስ ሃያ ዘጠኝ በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ ነግሦ ። እንደዚሁም ሆነ አጼ ሃረየን መስቀል ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ በሚባልበት ቀን ትባሕመንግሥት ቀብቶ የሚያነግሰው ጳጳስ ጠፍቶ ሳለ በሚነግሥበት ቀን ህዝቡ ሲጨነቁ ሲያዝኑ ሲተክዙ የንግሥና ሥርአት ቀረ እያሉ ሲፀልዩ ሰንበቱ አንድ ባህታዊ እግዚአብሔር፤ እንግሥው ብሎ እዝዞኝ ነው ብሎ የቀንድት መጣና ገና የሚርትን ብሌታዋ ሲከፍተው ተንፍሶ ህዝቡንም ንጉሡንም አረጨው ከዚያም ሥርዓተ ንግሡ እስከሚያልቅ ድረስ በህዝቡ ላይ እንደዝናብ ይወርድ ጀመር በራሱ ላይ ደግሞ የብርሃን መስቀል ስለታየ ስመ መንግሥቱ ሃረየን መስቀል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብሎ ባህታዊ በራሱ ላይ ዘውድ ደፋለት ከዘውዱም ላይ ነጭ እርግብ መጥታ አረፈች በዚህም ቅዱስ ስፍራ ከእናቱ ማህፀን ገና ሳይወለድ የተመረጠ ንጉሠ ነገሥት እንደሚነግሥበት ባህታዊ ተናገር ከህዝቡ ፊት ተሰወረ ሥፍራው ርሃ ተባሊ ተከፈተ ማለት አጼ ሃረየን መስቀል እስራሰባት አመት ሙሉ እንደነገሡ በዘፋኑ ሳይቀመጥ የተጣላ ሲያስታርቅ የታመመ ሲጠይቅ ሌሊት ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ሲሰግድ ሲፀልይ ያድራል ። ንጉሠ ነገሥት እንደመሆኑ መጠን ህዝቡ ሲሰግድለት ለእግዚአብሄር ለአምላካችን ስገዱ እንጅ ለእኔ አትስገዱ እያለ ይናገር የሚሰማው ስለጠፋ መንግሥቱን ጥሎ ሠራዊቱን ሰብስቦ የተጣላ እስታርቄ የታመመ እርዱ ብሎ መንግሥቱ ይባረክና ይእቀብከ እግዚአ የሚባሉትን ሾሞላቸው በንጉሡ በአስራ ሰባት አመቱ መነኑ በዚሁን ጊዜ ለሃያ ሶስት አመት ድረስ የእሱ ግዛት እስከሚያልቅ ድረስ ከሰው ሳያጣላ አውሬ ፈጽሞ ከብትን ሳይበላ እህል ከጐተራው ሳይጎድል ኖረ ከሃረየን መስቀል ቀጥሎ የመጀመሪያ ልጁ እስዶ አጼ ይምርሃነ ክርስቶስ ተብሎ በአንድ ሽህ ዘጠና ሁለት ዓ.ም. መስከረም አንድ ቀን ነገሠ በግእዙ አሲዳ ሲለው በአረቡ ሸንዳ ብሎታል እስዳ አጼ ይምርሃነ ክርስቶ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ሲነግሥ የሰላሳ አመት ሰው ነበረ ።

እንደዚሁም ሆነ አጼ ይምርሃነ ክርስቶስ ወደኑብያ ወርዶ ከኑብያ ንጉሥ ከጊወርጊስ ልጅ ከሚካኤል ጋር ተገናኝተው ወደግብፅ የሚወርደውን የአባይን ውሃ መገደብ ጀምረው ነበር ነገር ግን የግብፅ ሱልጣኖች ስለሰሙና ውሃው እየቀነሰ በለሄደ ወዚር አፍዳል ሲቀ ጳጳሱን ከእስቁርቆስ ቀጥለው ተሹመው የነበሩትን አባ ሚካኤልን ከኢትዮጵያ ንጉሥ ጋር ሄደው ተነጋግረው ውሃውን ያስለቅቁልን ብሎ ልኮላቸው አባ ሚካኤልም በግብፅና በኢትዮጵያ ያለው ወዳጅነት ከፈቱ

የበለጠ እንደሚሆን ገልፀው በአባ ሳዊሮስ ምክንያት ጳጳስ ቀርቶ የነበረውን አባ ጊዮርጊስ የሚባሉትን ጳጳስ ሾመው ግድብ ተጀምሮ የነበረውንም ውሃ አስለቅቀው ወደካይሮ ተመለሱ አዲሱ ጳጳሱም አባ ጊዮርጊስ ከስስታቸው ብዛት ገንዘብ ከየደብሩ እያስወጡ ይሰበስባሉ በንግድም አስመስለው ወርቅ ይሰበስባሉ ተብለው ወደግብፅ አጼ ይምር ሃነ ክርስቶስ መልእክታቸው ግብፅ እንደገቡ ወዲሁ አፍሯል በዚሁ የተነሳ አሥራቸው በዚህን ጊዜ አጼ ይምርሃነ ክርስቶስ በጣም ሊቅ ስለነበሩ በሃገራችን የሃገራችን ሰው መርጠን ጳጳስ መሾም አለብን ብለው ለካህናትና በደብረ መጣና በደብረ ዳሞ በደብረሊባኖስ በገዳሙ ጉን ላሉት መነኮሳትና ለታወጉት ተናግረው ነበር ነገር ግን የፍትሐ ነገሥቱን ሀግ እንጂሮም ብለው መነኮሳቱ ስለተናገሯቸው በዘመና ቸው ጳጳስ ይሾመው ሳያስመጡ ቀሩ ፍትሃነገሥት ምን ይላል የሚል እንዳለ ኢትዮጵያውያን አለቃቸውን ከግብፅ ይሹሙ ስለሚል ነው አጼ ይምርሃነ ክርስቶስም ኢትዮጵያን አርባ አመት ገዝተው እንደ ቅዱሱ አባታቸው ስም ልጃቸውን ድግግ ሃርቤ ያሉትን በዙፋናቸው አስቀምጠው መንግሥታቸውን በፍንታው እውርሰው ለቀቁለት ይምር ሃነ ክርስቶስ ተብለው የነገሡት አሰዳ ከሃርቤ ሌላ ሁለት ወንዶች አንዲት ሴት ልጆች ነበሯቸው እነዚህም ስማቸው ከሃርቤ ቀጥሎ ሀዝ ባይ ከሀዝባይ ቀጥሎ ተአብሃ ከተአብሃ ቀጥሎ ላሊበላ ናቸው የላሊበላ እናት ግብሬ መስቀል (መስቀል ግብረት) ትባላለች ። ይምርሃነ ክርስ ቶስን በግእዙ አሰዳ በአረቡ ሸአዳ ሲል ሃርቤንም በግእዙ ሲኖዳ ገ/ማርያም በአረቡ ሲኖዳ ብሎታል ። ሃርቤ ስመ መንግሥቱ ገብ ረማርያም ንጉሠነገሥት በኢትዮጵያ ተባሉ በአንድ ሽህ አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ዓመተ ምህረት በአባቶቹ ዙፋን ተቀምጦ በሃርቤ ዘመነመንግሥት በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት የነበሩት አባ ገብርኤል ሁለተኛ ይባላሉ ።

እንደዚህም ሆኖ በካይሮን የሚገኙት ሱልጣኖች ከኢትዮጵያ በል ጳሉ ምክንያት የሚገባው ግብርና እጅ መንሻ ከቀረ ብዙ ጊዜ ሆነ ብለው አባ ጊዮርጊስ የሚባሉት በስስትነትና በሌላም ተወንጅለው ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ተደርጎ ነበር ከሳቸው ወዲህ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ይምርሃነ ክርስቶስ ጳጳስ ይምጣልኝ ብለው የግብፅን ነገሥቶች ሳይጠይቁ ስለነበር ጉዳቱ ለግብፅ መሆኑን ተረድተው ለራሳቸው ሊቀጳጳሱን አባገብርኤል መርጠው ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ ይላኩ ተብለው ታዘዙ በዚህን ጊዜ ዋንትም የሃገሬውን ግእዝ ቋንቋ መናገር የሚችሉና ወዳጅ የነበሩትን አባ ሚካኤልን ወደዋና

ከተማው አደፋ ሳሉቸው የኢትዮጵያ ህዝብም በደስታና በክብር ተቀብሎ ካስተናገዳቸው በኋላ ወደንጉሠ ነገሥቱ አጼ ገብረማርያም አቀረቧቸው አጼውም በክብር ከተቀበሏቸው በኋላ ለመሆኑ እኔ ሳኩልኝ ጳጳስ ያስፈልገኛል ሳልል የምገርም ነገር ሆነ ሊቀጳጳስ የላኩ ለምንድነው ብለው ቢጠይቋቸው እሳቸውም የኢትዮጵያ ህዝብ ያለጳጳስ እንደማይኖር አለቃየም መንግሥቱም አስበውና ተማክረው ነው የሰደዱኝ አሁን የእርስዎም ፍላጎት ከሌለም መመለስ እችላለሁ ብለው ተናገሩ ንጉሠ ነገሥቱም መቀመጥዎንም ሆነ መመለስዎን ከሰባት ቀን በኋላ እስታውቅዎታለሁ አሏቸው አጼ ሃርቤ ስመ መንግሥታቸው አጼ ገብረማርያም የተባሉት አማካሪዎቻቸውንና ሊቃውንቱን ሰብስበው ጳጳሱ ይመለሱ ብለው ቢጠይቋቸው ሁሉም እንዲቀመጡ ምክር አቀረቡ ንጉሠ ነገሥቱም አባ ሚካኤል ካሉበት ድረስ ሄደው ይበሉ እንዲቀመጡ ህዝቤም እኔም ፈቅደናል ነገር ግን ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ሹመት በኒቅያ ጉባኤ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሊቃውንት የወሰኑትን ህግ ተመልክተው በኢትዮጵያ ሃገሮች እየሆኑ ክርስቲያናን ለህዝቡ የሚያስተምሩ ከኢትዮጵያ መነኮሳት ውስጥ ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት ይሾሙልን ብለው ጠየቋቸው ጳጳሱም ይህን የመሰለውን ነገር የሰሙን ሊቀ ጳጳሱን አባ ገብርኤልን ሳልጠይቅ አላደርገውም ብለው መለሱላቸው ንጉሠ ነገሥቱም አጼ ሃርቤ (ገብረማርያም) ከኢትዮጵያ ሊቃውንቶች ጋር ተማክረው ስለ ሊቀ ጳጳሳትና ለከሊፋ አልሃፊዝ ደብዳቤ የኤጲስ ቆጶስ ሹመት ለማስፈቀድ መልእክተኞቹን ላኩ በዚህን ጊዜ በግብጽ ያሉት ሊቀ ጳጳስ አባ ገብርኤልና አገሪ ገዢው ከሊፋ አልሃፊዝ ከጥንት ሲያያዝ እንደመጣው ደንብ አንድ ጳጳስ ብቻ ነው የኤጲስ ቆጶሳት ሹመት አያስፈልግም የሚል ደብዳቤ ለንጉሠ ነገሥቱ አሲዘው መልእክተኞቹን መለሷቸው በዚሁ ምክንያት የንጉሠነገሥቱ ሃርቤ ጥያቄ ሳይፈጸም ስለቀረ በጳጳሱ በአባ ሚካኤል በሊቀጳጳሱ በአባ ገብርኤልና በአጼ ሃርቤ መካከል መጥፎ ጥላቻና የበረታ ጠብ እንደዚሁም ብዙ ክርክር ተነስቶ ነበር በኢትዮጵያ ያሉት መነኮሳትና ሊቃውንት ንጉሠ ነገሥቱ ሃርቤ ጳጳሳችን አላከበሩ እያለ ብዙ ሃሜት ስም ማጥፋት ይካሄድባቸው ጀመር በቤተመንግሥቱም በየሃገሩም በየጊዜው ጦርነትና ረሃብ አላቋረጠም ነበርና እግዚአብሔር በጳጳሱ ምክንያት መቅሰፍት በኢትዮጵያ ላይ አወረደበት እየተባለ በመፅሐፍ ተጽፎአል ነገር ግን ጳጳሱ ክብራቸውን ሳይጠብቁ ከአረብ ሃገር መጥተው ከሚኖሩት እስላሞች ጋር ከተወዳጁ በኋላ በነሱ እጅ ካልሆነ ቢታ ተገደሉ ብሎ ዘግዱር በሰፊው ቆሮታል እኒህ ጳጳስ የላሊበላ ደጋፊ አጼ ሃርቤ (ገብረማርያም) በነገሱ በአርባ አመታቸው እንደአባቶቻቸው ሆነና ስርአት

ዘሩፋኖቻቸውን በወጭ ሃገር ሲኖር ለነበረው ለላሊበላ ለቀቁለት የቅዱስ ላሊበላን ዘመነ መንግሥት ታሪክ ከመፃፌ በፊት የላሊበላን ልደትና እድገት ልደትና ንግሥ አቀርብላችኋለሁ ። አዘጋጁ መሪራስ አማን በላይ

ከኢትዮጵያ ሃገሮች ውስጥ አዘብ — አዘቦ በሚባል ሃገር በአዘቦ ከ/ርሃ አለቃና ገብረመስቀል የሚባሉ በሉሉና በኩብት በወርቅና በሐብስ የከበሩ ሃብታም ባልና ሚስት ነበሩ ለእነዚህም ጻድቅ እስተዋይ እግዚአብሔርን ፈሪ የሆነ ልጅ ሰጥ ላሊበላ የተባለ ነበረቸው ላሊበላ የተባለበትም በተወለደ ቀን የተወለደበት አዳራሽ በንብ ተከበ የተወለደውንም ልጅ ንቦቹ ዙሪያውን እንደማር ከበው ሲያንበገበገት እናቱ ሰላቶች ላሊበላ አሉትው ላሊበላ ማለት ንብ አውራውን አወቀ ማለት ነው በቻያ ወይም በአገው ቋንቋ በሱቢያ ወይም በሱባ ቋንቋ ግን የንብ አውቀት በማር ታወቀ ምስጢሩ ላሊበላ የማር ሥራ በንብ ታወቀ ንጉሥ መሆኑ በንቦች ታወቀ ማለትዋ ነው ላሊበላ በተወለደ በት ቀን ብዙ ገቢረተአምር ተደረገ በንጉና ፍየሉ ፈረስና አህያው ከብቱም የዱር አንበሳ ሁሉ እየመጡ በቤተመንግሥቱ በሚገኘው ሜዳ ዘለሉ እሽካኩ አድረው ሄዱ ለመቆጠርና ለመናገር በዚሁ አቴሚ በለአድገቱ እንግራችኋለሁ ። ላሊበላም በሰባት አመቱ ዳዊት ደግሞ በዘጠኝ አመቱ ከአባ ጊዮርጊስ ከሀንት ተቀብሎ በጺቁና ልየንን ሲያገለግል ሳለ በእናቱ የማይገናኙት ወንድሙ ሀዝባይ በአስተዋይነቱና በአውቀቱ ቀናበት ይሄውም በጻድቁ ሃርቤ ሥርዓተንግሥ ላይ አንድ ባህታዊ ከእናቱ ማህፀን ገና ባይወለድ የተሠረለ ጻድቅ ንጉሠነገሥት እንደሚወለድና እንደሚነግስበት ስለተናገረ ላሊበላን የሚያየው ሁሉ ይህ ባለትንቢቱ ጻድቁ ንጉሥ ነው ነግሶ አይቶነው የሚል ህዝብ በፊቱ ይሰግድለትና ይከተለው እንደነበር ከቅናት የተነሣ ሲገለው ፈልጎ ከእለታት አንድ ቀን ከርሃ ወደአደባ ከአባቱ ከአለቃ ጋር ንጉሡ ንጉሠቱን ሃርቤን ወንድሙን ለማየት ሄደ በዚህን ጊዜ ሀዝባይ ላሊበላን በእናት አባቱ ልጅ በወንድሙ ቤት ሲያየው ከሃዲቻው የተነሣ መልኩ ጠቁሮ ፊቱ ተጨማደና ከፍቶበት ይታይ ነበር ሃርቤም ወንድሙን ሀዝባይን ጠርቶ ምንው ከፋህ ለምንስ ፊትህ ጠቆረ የሰላችህው ሰው እንዳለ ንገረኝ አለው ሀዝባይም በሁሜናና በርሃ ያሉ ህዝቦች ላሊበላ የአባታችን ልጅ እንደሚነግስ ትንቢት የተነገረለት ጻድቅ አስተዋይ ንጉሥ እንደሆነ ስለሚያውሩ ነው አለው ሃርቤም ትንቢት የተነገረለት እራሱ ይመስለው ነበር እንጅ ይህ በእናት ከማይገናኘው ለወንድ ለላሊበላ መሆኑን አያውቅም ነበርና ለለሰማ ቀና ለጊዜው

እንዳይታወቅብኝ ብሎ ሊያስገድለው አልፈለገም ነበር ነገር ግን ከቤተ መንግሥቱ ወጥቶ እንደሄደ ለእናቱ ልጅ ለአሁኑ ለታላቁ በመርዝ እንድትገድለው ነገራትና በምግብ አዘጋጅታ ሰጠችው ሆኖ ግን ላለ በላ ምግቡን ሳይበላ እናቱ ግብሬ መስቀል ጠራችውና ተነስቶ እንደሄደ አንድ ድሉ ከማዕድ የተረፈ ምግብ መስሎት በልቶ የተረፈውን ለውሻ ሰጠው ድሉውና ውሻውም አንድ ጊዜ ሞቱ ስለዚህ ወንድሞቹና እሁሱ እንደሚገድሉት እናቱ አውቃ አባ አጨብርጋዝ ከሚባሉ መነኩሴ ጋር የክህነትን ትምህርትና ስርዓት እንዲያጠና አደራ ብላ ሰጠችው አባ አጫብርም ከላስታ ልዩ ቦታው ከአይላ ሚካኤል ወደጉጃም ከጉጃም ወደ ላም ገጼ አባይ (የአባይ ምንጭ) መጥተው ጉዶራ ከሚባሉ መምህር ጋር አገናኙት ያለም ሃገር ከተገት ጀምሮ የጺዋ ስፈር አቡሳውያን ከጋፋቶች ጋር ተጋብተው የሚኖሩበት ሃገር ነው በዚያውም ሃገር የማይሄድ የቆመ ባህር ይገኝበታል ላሊበላ ከመምህር ጉዶራ ቅዱስ ያሬድ የደረሰውን ድጓም እየቀፀለ ተቀምጦ ሳለ በቀለም ተቀባይነቱ በአስተዋይነቱ ፈጽመው ጓደኞቹ ቀንበትና ከእለታት አንድ ቀን በላሊበላ አኮፋዳ ውስጥ የሰው እጅ ቆርጠው ከተቱበት በዚህን ጊዜ እራት ሊበሉ ተሰበሰቡ ተማሪዎቹ አኮፋዳቸውን ይዘው ቀረቡና በሌማታቸው ላይ ሲዘረግፉ ከላሊበላ አኮፋዳ ውስጥ የሰው እጅ ከእንጀራው ጋር ተዘረገፈ ሰው በላ ብለው ሊገሉት ሲሉ አምልጦ ጉንጂ ወደሚባል ሃገር ሄደ ከዚያም የመንፈሳዊን ትምህርትና የያሬድን ዜማ ሲከታተል ብዙ ቀን ቆየ ። ከእለታት አንድ ቀን ገብሩ ለአብ የሚባለው መምህር ተማሪዎች ተሰብስበው እንዲህ አሉት መምህር ሆይ እኛ ከእርስዎ ከመማን ትምህርትዎን ለማወቅ ከሞከርን ብዙ አመታት አለፈን አሁን ከእኛ በኋላ የመጣው ላሊበላ የሚባል ተማሪ ከእኛ በልጦ ይታያል ስለዚስ አንድ መድሃኒት አድርገውለት ይሆናልና ለእኛም ያድርጉልን ብለው ጠየቁት መምህሩም እንዲህ አሉ ላሊበላ ግና ከእናቱ ሆድ ሳለ ነው ሆላእና አድርጎ የመጣው የእሱ መድሃኒት ደግሞ ከልቢ ውስጥ ስላለ ስምት አውጥታችሁት በሉት እንደሆነ እንጅ አሁን አታገኙትም አሉአቸው በዚህን ጊዜ መምህሩ ይሞታል ብለው ተማሪዎች ሲጠብቁ አልሞት ስላሉአቸው ገደሉና ልባቸውን ተካፍለው በሉት ላሊበላ ግን አስደናቂና አሳዛኝ ጉድ አየና ስምትን ቀርቶ ሃገሩን እያሳየኝ ብሎ ሸሸ ከዚያም ወደተወለደበት ሃገር ወደሮሃ ቢሄድ አባቱ አስዳ ሞተው ያረፈ ከትንገሽ ቀን በኋላ እናቱ ግብሬ መስቀል ዕርገት በአልተቢያት ኋላ መስቀል ከብሬ የተባለችውን አጭታ በሃያ አንድ አመቱ አጋባችው ዕርገት በአልተቢያንት እንዳገባ ንጉሥ ነጋሥቱ ገብረማርያም የተባለው ወደእደፋ አስመጣው ከዚያም በዛግ

እጭቶ ያገባትን ሚስቱን መስቀል ክብራን የአባታችን የጴጥ ሚስት (የወታደር ሚስት) ቀምተህ ነው ያገባሃት ብሎ ከሳሼና መስካሪ እስክሰቶ በገበያ ላይ እያዞረ አስገረፈው ከዚያም ከታሠረበት አምልጦ ጉንግዶት ወደሚባል ገዳም ሄዶ መንኖ ተቀምጦ ሳለ መስቀሉን በመስ ቀለኛ ምድር ላይ አስቀምጠው የሚል ቃሉን በሰሌዳ ላይ ተቀር ሶስት ጊዜ በራእይ አየው ጉንግዶት የነሩ ወረባ ከተማው አቡነ ንገዱ ሰሉ ነው በዚህን ጊዜ ከሃይቅ በምዕራብ ወደሚገኘው ሃገር ሲንገ መስቀለኛውን ምድር አገኘውና ድንጋይ አስቀመጠበት በአባቴ ዙፋን እንደምታስቀምጠኝ አመቅአለሁ ስለዚህ አምላኬና መድሃኒቴ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚች ቦታ መስቀልህን እንዳስቀምጥ ቤተክርስቲያንህን እን ድሰራ የአባትህ ፈቃድ ይሁንልኝ ብሎ ተሳለ በዚሁ ሌሊት በራእይ ተገለጠለትና እንዲህ አለው ወዳጄ ላሊበላ ሆይ መስቀሉን በልብህ እንዳስቀመጥከው በዚህ ባለህበት ምድር እንዳስቀመጥከው ይቀመ ጣል ። ይሄውም ስለትህና ተስፋህ ይፈጸም ዘንድ በአንተ ዘመን ሳይ ሆን ህገን በሚያከብሩና ትእዛዙን በሚፈጽሙ ነገሥታት ዘመን መስ ቀሉን ከአረፍክበት መስቀለኛ ምድር ላይ እንዲያስቀምጡት ከባህሪ አባቴ ፈቃድ ነው ምልክቱ በልብህ የተቀመጠው መስቀል ሃይልህ ነው ድል ለአንተ ነው ስለዚህ ስምህም ገብረመስቀል ይባላል አሁን ተነስና መስቀሉ ወደአለበት ሃገር ሂድ አለው ላሊበላም ያንን ቦታ ማሼን መስቀል አለው ከማሼን ተነስቶ በገበያን አድርጎ እናሪያ ሊመ ገባ ከዚያም ወደሱዳን እንደደረሰ ወደግብፅ ከሚወርዱ ነጋዴዎች ጋር አብሮ ሄዶ በደህና ግብፅ እንደገባ ከካይሮ ወደእስክንድርያ ከእስክንድ ርያ ወደካይሮ እየተዘዋወረ ከብዙ ክርስቲያኖችና ከብዙ መንኮሳት ጋር ተዋወቀ ከሁሉም ይልቅ ከሊቀጳጳሱ ከአባ ገብርኤልና የኢትዮጵ ያን ቋንቋ ከሚናገሩት ወደኢትዮጵያ ከመጣባታቸው በፊት ከጳጳሱ ከአባ ሚካኤል ጋር በመተዋወቁ በጣም ደስ አለው በዚህን ጊዜ ከኢ ትዮጵያ ከአደፋና ከደብረዳዊ የመጡ መነኮሳት መጥተው ነገር ለሊቀ ጳጳሱና ለጳጳሱ ለሚካኤል ላሊበላን የእስዳ ክ/ልጅ እንደሆነና ህዝቡ ላሊበላን ለማንገሥ ፍላጎት እንዳላቸው ስለገለጹላቸው ላሊበላንም በስውር ጠርተው ለምን አንተ የንጉሥ እህት ልጅ መሆንህን አልነገር ከንም ብለው ከነገሩት በኋላ በልዩ ክብር ቦታ አስቀመጡት ሊቀ ጳጳሱም ለከሊፋው የንጉሡ ልጅ እንደሆነና ህዝቡም እሱን ለማንገሥ ፍላጎት እንዳላቸው ወንድሙ ቀንቶ ሊገድለው እንደሚፈልገው የሰ ሙትን ሁሉ በዝርዝር ነገሩት የግብፅም ከሊፋ በክብር ከአለበት ቦታ እስመጥቶ ከተዋወቀ በኋላ ለምታደርገው ሁሉ እንተባበርሀለን ወደፈለከው ቦታ ለመሄድ ከሰው ጋር እንልክሃለን አለው በዚህ ጊዜ

የመስቀል ጦርነት በሚባለው በናዝሬትና በጥብርያዶስ መካከል ሃይለኛ ጦርነት አድርገው ከእስላሙና ከክርስቲያኑ ብዙ ህዝብ አልቆ ስለነበር አረቦችንም ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት ስላልተቻለ ወደኢየሩሳሌም ክርስቲያን የሆነ ሰው ለመሄድ በጣም ችግር ነበር ነገር ግን በግብፅ ገዢ በከሊፋ ላሊበላ ከብርን ስላገኘ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየዞረ የአስተማረበትን የተወለደበትን ቤተልሄም የተጠመቀበትን የርዳኖስ ወንዝ ተቀብሮ የተነሳበትን ጎልጎታን በኢየሩሳሌም የሚገኙትን መንደሮች እየዞረ ሊመላለስምና ለመጐብኘት ችሏል ።

ላሊበላ በኢየሩሳሌም ውስጥ በጉልጉታ ብዙ ወራት ከተቀመጠ በኋላ ወደካይሮ ተመልሶ ከአዲሱ ሊቀጳጳስ አባ ዮሃንስ ጋር የጠበቀ ወዳጅነትና ፍቅር እንደነበራቸው እራሱ ላሊበላ የሲራክን መቅደስ ከሱባ ወደግብፅ ልድ ሲጨርስ ከመዝገቡም ላይ በወዳጁ በሊቀጳጳስ አባ ዮሐንስ ጸሎትና በእግዚአብሔር እብ ፈቃድ ተርጉሜና ለፌ ጨርሼ ወደሃገሬ ይገርሙ ሂደለሁ እኔ ሃጺኒ ላሊበላ የአባል(አባል) ሰው ለጠላት በመድሃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሃይል የማይሸነፈው የሞራራ ልጅ (መራተ(ሃ) የጀን ሥዩም ልጅ (አኩቴቶ) የአባዳ ልጅ (የይምርሃን ክርስቶስ) ሀጸኤ ማለት የንጉሡ ነገሥት የአጼ ዘርች ማለት ነው ላሊበላ የሲራክንና መፅሐፈ ሱባኤን ፅፎ እንደጨረሰ ከዶልታ ወደ አማርኛ ተግዞ በየገሩና በአማራኛ በጣሙን ወንዝ ዳርቻ የሰፈሩ በዘግዱር አሚንዞ ዘመን መንግሥት ለጦርነት ሄደው በዚያው በታ ተሰቷቸው የሚኖሩ ሳይስ የሚባሉ የአማራ ጐሣዎች ነበሩ እነሱም በመርዊና በናፓታ በጄባ በሶባና በኑባ በጣም የታወቁ የክርስቲያን ጭፍራ ጦር ነበሩ ነገር ግን የእስላም ጦር ሃይል እየበረታ ስለመጣ ሃይላቸው ተቀንሶ በእስላም ሃይማኖት መሪዎች ስር ተጨቁነውና ተረግጠው ሳለ ቀንትም አባቶቻቸው ለአክሱም መንግሥት እንጅ ለእስክንድርያው ቄሣር ተገዥ ለካይሮን ሱልጣን እንገዛም እያሉ የሚኖሩ በለንባሩ ላሊበላን የክርስቲያኑ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ልጅ ነው ብለው ሊቀጳጳሱ አባ ዮሃንስ ስለአስተዋወቁት እሱም የኢትዮጵያ ታሪክ ከመፅሐፈ ሱባኤና ከመፅሐፈ ሲራክ አክሱማዊ ስለነበሩ መምጣት ብፅፈው አንብቦ አስረዳቸው ወደፊትም የኢትዮጵያ መንግሥት እደፋ ላይ የሚገኘው ክርስቲያን የሆነ ወታደርና ጠቢብ እንደሚፈልግ ስለነገራቸው በደስታና በእልልታ ተቀብለውት በዚያው በአማርኛ ለሁለት ዓመት እንደ ተቀመጠ ሊቀ ጳጳሱ አባ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ሰመ መንግሥት አጼ ገብረመስቀል ብለው ሰይመው አንግሠው በዚህ ጊዜ የአማራ

ጉባዎችን በየጸሎታቸው ሊቀጳጳሱ አባ ዮሐንስ ፀሎት አድርገው ላሊበላን በሕዝቅያስ ዙፋን እንዲያስቀምጡት አደራ ብለው በራኢ ሰጥተው አሰናበቱቸው በዚሁ ስራ የተነሳ ሊቀ ጳጳሱን አባዮሐንስን የማብሎ ከሊቄ የሰአሱ ፍቃድ በመንገሳቸው ከሹመታቸው አውርደ አራተኛው አባማርቆስን ሊቀ ጳጳስ ብሎ ሾሞ እሳቸውንም ከሀገሪቱ እንዲይወጡ አደ ?? አባ ጊዮርጊስ የሚባሉትን ጳጳስ አድርድርገው ሊቀ ጳጳሱ ሾመውሉቸ ኑሮ ከግቸው ጋር ንጉሥ ነገሥቱ አጼ ገብረመስቀል በአማራ ሠራዊት ታጅበው ሁለቱ አባይ ከሚገናኙበት ሥፍራ ደረሱ ያንም የጎደ አራስ ነው ከዚያም ጥበበኛውን በጥበብ ጠረኛውን በመር ከፍሉ አደቃ ሾማቸው ጥበበኞች ሰባት ሺህ መሬኞች የታወቁት የፊት ተሞጊ ስልቱ ሽህ እሱን የሚጠብቁና ሥርአት የሚያሳዩ ሰልፈኞች ሶስት ሽህ ነበሩ እንዚህም የንጉሡ ነገሥቱን ቃል የሚሰሙና በአለቃቸው የሚሠማሩ ክርስቲያኖች ናቸው ከዚያም ከአባይ መገናኛ ተነስተው አባይ ለአባይ ሲመጡ ጀቢራ ከሚባል ሥፍራ ላይ ሰፍረው ሳለ የመይጣውጥ ንግሥት የምትሆን ኪንቲ ነገሥቷን ከአባይ ወንዝ እግ አስወጥታ ጠብላ ይዛ ቀየዎቸው ንግሥቲቱንም ወደንጉሡ አቀረቢት ላሊበላም ከባረካት በኋላ የወርቅ ዘንግ ሰጥቶ በአካባቢው ለሚገኙት ነገዶች ንግሥት አድርጎ ሾማት ያንንም ቦታ አሳይዛ አሉት በዚያም የጊዮርጊስን ቤተክርስቲያን ተክሉ መግለሚያ ጊዮርጊስ ተባለ የጠ፤ ሠራዊቱ የነበረበት ቦታ ሁለተኛው ሀገሬ ተባለ እስከዛሬም ያን አካባቢ ስሙ አልተቀየረም የአጼ ገብረመስቀል ሠራዊት አሳይዛ ከሚባለው ሠፈር ተነስተው ሃገር እያቀኑ እያስገበሩ የአመፀውን አጥፍተው የተቀበሉቸውን ባላባቱን እየሾሙ በቁራ በእንፍራዝ አድርጎ ከአራት ወር ታህሳስ ሃያ ሶስት ቀን አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባሁለት (1172) ዓ.ም ቤተ እንዳ ደረሱና ከወንድሙ ከሃርቤ ጦር ጭፍራ ጋር ገጠሙና ድል አድርጎ ያንንም ቦታ ቤተ እንዳ መባሉ ቀርቶ ቤተ እንዳ በዛሬው አማርኛ የመጀመሪያ አንድ ቤት ማለት ነው ከዚያም ታህሣሥ ሃያ አምስት ቀን ከእንዳ ቤት ገስግሰው ዙር አንባ ላይ የሁለቱ ጦር ገጠሙ ግን ድል ሆንና የሃርቤ ጭፍራ ለላሊበላ ግማሹ ሲማርክ ግማሹ ንጉሣችን እንተንሁ እያለ በሩቅ በቅርብ ያለው እየመጣ ገባለት በዚህን ጊዜ አጼ ገብረማርያም ተብሉ የነገሠው ትልቅ ወንድሙ ሃርቤ በህልም የእግዚአብሔር መልአክ በታህ መንግሥትህን ለብቻ ወንድምህ ሊቀበለት ብሎ በህልሙ ስለነገረው ከእንቅልፉ ነቅቶ በሁለት ቄሶች ወንድሜ እንኳን ደህና መጣህ በአባቶቻችን አምላክ ብለህ በእንተ ላይ ያደረኩትን ከፉ ሥራ ሁሉ ይቅር በለኝ መንግሥቴም በእጅህ ናት ተረከበኝ ብሎ ላከለት አጼ ገብረመ

ስቀልም ዋድላ ከሚባለው ላይ ታህሣስ ሃያ ዘጠኝ ቀን የልደት ቀን ከወንድሙ ከሃርቤ ጋር ተገናኝተው ዕርቅና ሰላም አድርገው ዋሉ በዚህን ጊዜ የሃርቤ ዘመን መንግሥት አላለቀም ነበርና ተረክበኝ ቢለው የአባታችን የመራ ተ/ሀ/ ሕግ አልሽርም ብሎት ሁለት አመት በዚያው በተገናኙበት በዋድላ ሰፍር ሳይቀበለው ቀየ ከዚህ መሐል በተለያዩ በሰባት አመታቸው መናኝ ሆኖ በገዳሙ መጣ ባልቴቶችን ስትረዳና ስታገለግል የነበረችው ዕርሂት ምት የተባለው ባሏ ላሊበላ በህይወት ኖሮ መምጣቱን ሰምታ ከነበረችበት ገዳም ወጥታ ተገናኘ ችው ላሊበላም ገና ሲያት ሀልምና እውነት መሆኑን ማወቅ አቅቶት ከትንሽ ሰዓት በኋላ ተቃቅፈው ይላቀሱ ጀመር ከዚያ ለሁለት ዓመት ከቆዩ በኋላ ወንድሙ ሀርቤ መንግሥቱን ሲለቅለት በአንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት (1172) ዓ.ም. ታህሣሥ 29 ቀን ሚስቱን መስቀል ክብራ አስኝቶ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መቀመጫ ዙፋን ተቀመጠ በኢትዮጵያ ሀገሮች ያሉ ንግሥታት የልዩ ልዩ ነገዶች አለ ቆች እየመጡ ንጉሣችን እንቶንሀ እያሉ ገበሩለት አቀረቡ ። በዚህ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት በግብፅ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ከሚያስጨ ቸውና ከሚያገለግሏቸው ከእስላሞች ጋር አብሮ መኖርና መቀጠል ስላልቻሉ ንብረታቸውን ሀገራቸውን እየተው ከሃይማኖት ወንድሞ ቻቸው ጋር ለመኖር ከግብፅ ወደኢትዮጵያ እየመጡ ተቀመጡ ላሊበ ላም በግብፅ በነበረበት ጊዜ አከብረው ተቀብለው እንደነበር ሁለተኛ ደግሞ እስላሞች ክርስቲያኖችን እንዴት ሲያሰቃዩአቸው እንደነበረ አይቶ ስላየና አሁን እነሱን እምነው በመምጣታቸው ቦታ እየመረጡ እንዲቀመጡ ሲል አወጀ በደስታም ተቀብለው ደስታው ቦታ መረ ቸው ባለርስትም አደረጋቸው ከደሉታ ግብፅ ስለመጡ ነው እነሱም ከሀገሬው ጋር ተቀላቀለ ከአጼ ገ/መስቀል ጋር አብረውት የመጡት የጹዋ ጦር ጭፍራ ግማሹ ጉማቸው ወደሚኖሩበት ቤተእ ግሬ በሄሬው አገሬ ሳይገቡ ሄደው ተቀላቅለው ተቀመጡ የጦር ስልት ያላቸውን ኢዋ ሠራዊት ግን እንደየንጉሱ ሥርዓት በየሀገሩ በች ለሀገሩ ላይ ምሪተኛ ጭቃ ሹም እየሆኑ ተቀመጡ እነዚህ እግሬ ያበ ጹዋ ጦር ተብለው የሰፈሩበት ደንቢያ እናሪያ እንደቤት ቤተሹር ወግሬ ቤተ መሬ - መሬቤቴ ድባ ተጉለት ነው ሌሎች ልዩ ጦረኞች የግሬ ሃይሎች ከረን የቀኝ ሃይሎች ኮረም ተብለው በባላባቱ ላይ ተደል ድለው ሠፈሩ ያገም የሰፈረበት በስማቸው ከረን ኮረም ተባለ አጼ ገብረመስቀል በተወለደበት ሥፍራ በሮሃ በአባቱ በበርቶ ምትክ ሲሄ መስቀልን የግንዲያችና የጥበበኞች እለቃ አድርጎ ሾሞ የአብ ያተ ክርስቲያናት ህንፃ ለማሠራት ይዘጋጁ ጀመር በቅድሚያ እራሱ

ድንጋይ ያስቀመጠበትን ስለት የተባለበትን ኢያሱስ ክርስቶስ በራእይ የተገለጠበት ቦታ አሰበ ከዚያም ብዙውን ሳያድር በበጃያና (በእንጦጦ) በአባል (አዳል) በእማሪሩ በበጋ (ትግሬ) እንደዚሁም አብረውት በሚ ኖሩ በግብፃውያን ሕዝብ ታጅቦ የመሠዋይ ነገሮች ስለ - ሰላሌ ወደ ሚኖሩበት ሄደ በዚያም እንደደረስ እራሱ ከሕዝቡ ጋር እንጨት እየቀ ረጠና እየተሸከመ የእግዚአብሔር አብያ ቤተ ክርስቲያን በሚያምር ሁኔታ በአምስት ወር ሰርተው ጨረሱ ስሙንም የንጉሥታት ልጆች በጋሊዉና በእጁው ላይ ወር እንዳንሱ የእግዚአብሔር ሕግና ትእ ዛዝ የሚያስረዳ ቃሉንም የሚያስተምር መምህር ተደርጎላቸው የሚኖ ሩበት አንባ መሰብሰቢያ ስለሚሆን ስሙን ግሸን መስቀል ያለውን አንባ ነጋሲት ብሎ ሰየመው ነገር ግን አሁ ናእድ በዘመን መንግስታ ቸው የነገሥታት ልጆች እንዲሔዱበት ብለው ከተናገሩ ማርያም ቤተክርስቲያን ሲያሰሩ ስሙን ግሸን ማርያም አሰኛዚውን የሰሉ - (ሰላሌ) የጀሌ ነገሮች ስለሚኖሩበት አንባ ሰሉ (አንባሰል) ብለው ታል አጼ ላሊበላ ገብረመስቀል በዚተሀሣሥ የዛሬን ተድባበ ማርያም የተገነቱትን መቅደሱ ዕየንን ጉብኝቶ በጻውንት አድርጎ የተንቱላስያ- ዊያ- ወደዛሬው ላስታ ልዩ ሠራሩ ሮሃ ግን ዱቀና ጀን ጹቶ ከሚባ ለው ሠራዊቱ ጋር በሰላም ተመልሶ ገባ ።

አጼ ገብረመስቀል በተልጊታ ባለ በኢያሩሳሌም የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ባገሩ ላይ ለማሠራት ስለት አድርጎ የነበረውን አሁን በአባቶቹ ዙፋን ላስቀመጠው አምላኩ በንፁህ ልቡና አምላኩን ለማገልገልና ይስ ለማስገኘት አብያተ ክርስቲያንን በርሃ የሚገኘውን አለት ለማስፈልፈል ንጉሡ ንግሥት በኢትዮጵያ በተባለ በሶስተኛው አመቱ በአለትና በጭንጫ መሬት ውስጥ በአብነእድሜስ እንደቀኛ አድርገው መኖሪያ ቤት መሰራት የሚችሉትን የኢትዮጵያን ተወላጅ ጥበበኞች ኢሊጣኖችን ጥሪ አደረገ በጥሪው መሠረት የመጡትን የግን ጹቶን ሠራዊት በአንድ ላይ አቀላቀሉ በዚያው በተወለደበት ሥፍራ ላይ በርሃ ከአስር ክፍሎ አለቱን ልዩ ልዩ ክፍል አድርጉ በርም መስኮትም ግድ ግዳም ጣሪያም በራሱ አመራር እያስወጣበጉ እያሳመረ አስር አብያተ ክርስቲያናትን አሠራ ። እነዚህም የተሠሩት የአብያተ ክርስቲያናት የስም ዝርዝር

1. ቤተ መድኀኔት —መድኀኔዓለም
2. ቤተ ጐልጐታ
3. ቤተ መስቀል
4. ቤተ ማርያም
5. ቤተ ደናግል
6. ቤተ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል

እነዚህ በሌላ ድንጋይ ባንድነት የሚገኙት ሲሆን ቀጥለው- ያሉት ደግሞ ለብቻ ተፈልፍለው የተሠሩ ናቸው ።

7. ቤተ አማኑኤል

8. ቤተ መርቆሪዎስ

9. ቤተ ገብርኤል

10. ቤተ ጊዮርጊስ አስረኛው ግን ለብቻው በሆነ ስፍራ ተፈልፍሎ ተሠርቷል ።

ስለብዙስ ቅዱስ በጌቶ ፍቅር ስትል አስራአንደኛውን ቤተ አባሊባኖስን በእልትነ ሂተመስቀል ክብር አሰርታለች ቅዱስ ላሊበ ላም ወደም አጼ ገብረመስቀል ለባለቤቱ ለመስቀል ክብሩ በእለተ በሃት ለክብሯ ሲል መንና ለነበረችበት በመናፈና በኢንግሊ መካከል ለሚገኘው ለአባመጣኢገዳም ልዩ ሥፍራው ሃና ጂምዝ ሠራዊ የግራ ሃይል የሚኖርበት ምድረብርን የቀኝ ኃይል የሠፈሩበት ምድረ ኮረም የፊት ሃይል የተቀመጡበት ምድረ ጃራ - ጃራተክታይ ሃይል የተደለደሉበት ምድረ ፀለምት በዚሁ በአባ መጣእ ገዳም ለሚኖሩት መነኩሳትና ደናግልን ጉልት ተክሎላቸዋል ። እነዚህን አብያተ ክርስ ቲያናት ከአለት ውስጥ መፈልፈልና ማስጌጥ ባስጀመረ በሃያ አመታ ቸው ሥራውን በእግዚአብሔር እርዳታ ፈጸመ ፤ የነዚህን ሥራ እንደ ፈጸመ በኢትዮጵያ ሀገሮች በየአውራጃዎችና ንጉሥ በሚኖርባቸው፡ መንደሮች አብያተ ክርስቲያናትን ለማሠራት ከአንድ መቶ ከፍለ አምስት መቶ አምስት መቶ ልዩ ልየ እናጺዎች መድቦ ለአንድ መቶ ሀገ ሮች እሰቱን ፈልፍለው ታቦቱ እንዲተከሉ ለኳቸዋል። በነዚሁ በአስራፈለፈላቸው አብያተ ክርስቲያን አጠገብ የሚያልፍ ከሌላ ወንዝ እንደአባይ አሠርቶ ስሙንም የርዳኖስ ብሎ ሰይሞ እንዲፈስ አድርጎአል ።

በዚሁ አጼ ገብረመስቀል በንጉሠበት በሃያ አምስተኛው ዘመን የጋፋት ዘር ያልሆነ የመደባይ ጉዛ ሰሙ መቻክል ሰመ መንግሥቱ ዞረ ቀመስ ንጉሠ ጉዛምን (በጉጃም ውስጥ የሚገኝ ሀገር ነው) የተ ባለ ሚስቱ ከላንጉገኘው ንጉሥ የልጅ ልጅ የምትወለድ ስምዋ ማብቶ ላላ የተባለች ለአጼገብረመስቀልም እንገዛም እንገብርም እያሉ አጼ ገብረ መስቀልም ቤተ ክርስቲያን በየሥፍራው እንዲተክሉ የላኩዋቸውን እናጺዎች እያጉላሉ ስለአስቸገሩ የወንድሙን የሀርቤ ልጅ እልመ ክንንን የጦር መሪ አድርጎ ወደጉዛምን ላከው እልመክንንም ጉዛምን በደረሰ ጊዜ ከዞረ ቀመስ ከተባለው ከመቻክል ጋር ጦርነት አድርጎ

በመስቀል ክብሬ ወሎንና በራሱ ወሎት አሸንፎ ማረከው በዚያው በማረከበት ቦታ ለመስቀል ክብሬ ማኅሰቢያ ሲል የአባ መጣል ሊባኖስን ቤተክርስቲያን ተከለ ምርኮኛውንም በሰንሰለት አስሮ ላሊበላ ካለበት ድረስ ይዞት መጣ አጼ ገብረመስቀልም ዘረ ቀመሰን ባየ ጊዜ ለምን አልገዛም አልክ እኔ የላኳቸው ቤተ ክርስቲያኑ የሚሰትን ለምንስ ከለከልክ አለው እሱም እኔ በአንተ መንግሥት ላይ ክፉ አላሰብኩም አሁንም አገዛለሁ ቤተ ክርስቲያንንም የሚሠሩትን እረዳለሁ ነገር ግን አንተ የላክኸቸውን እንዳይሠሩ የሚያጉላሉ የአክሱም ንጉሥ ንግሥት የነበረው የአጼ ላንግሣ የልጅ ልጅ ባለቤቱ ማተቆልላና ልጁ መአተ ጉኒ ናቸው እነሱንም አንገዛም እንጂ ቤት የሚላቸው የዳሞት ንጉሥ የዳንግሣው ዘር ነሰንገሩ ነው ብሎ መለሰ አጼ ገብረመስቀልም እነሱን እንዳትሰማ እኔ የምልህን አድርግ ብሎ ከቀሳውስት ጋር ወደሀገሩ መልሶ ላከው ለዳሞቱ ንጉሥ ሲደገስጥቶ ባላባት ለገውንገላ ለምንድነው አልገዛም የምትል ሲላውንም እንዳይገብር የምትከለክልና የምትመክር ብሎ መልእክተኛ ላከበት እሱም ለእኔ አጼንቱ ቢቀር ላንተ የምገብርበት ነገር የለም እንዲያውም በገበማን በተተለት ያሉት ወንድሞቼ የንጉሥ ንግሥቱን ዘሩን ካላስመለሱ እኔ እራሴ ከአንተ ነጥቄ እወስዳለሁ የሚል የዛቻና የኩራት መልስ ላከላት በዚህን ጊዜ አጼ ገብረመስቀል የሰባት ጉሣ ዘሮች ከአባልከቸያ ከቡናማ ከአማሩ ከቡንፊል ከብሉን ከሰሌ የጴዋ መር አዚንጅቱ ወደ ዳንግሣ ላካቸው እነሱም ገሥግሠው ቀስትትለው ከእንዱ ተራራ ሥር ላይ አግኝተው ከነድልድት በኋላሁውኑ ዘርፈው ምርኮኞውን ይዘው ገግጽቼ ተመለሱ አለቆችና የቺያ ጉሣዎች ግን ሀገሩ ለምለም የከብት ሀገር ማርና ወተት የምታፈስ የወርቅ ሀገር ሆኖ ስላዩት ቀሩ ስማቸውም ሰባት ቤተ አገው ተባለ ከሰባት ጉሣ ተዋግተው ስለሄዱ ነው በዚህን ጊዜ ወደጎጃም የሚሻገሩን ሰው ጎጃሞቹ እንደ አህያና እንደበቅሎ ያደርጉታል ጀሁን እንደፈረስ ይጋልቡታል ወደአክሱም የሚሄደን ሰው ፈላሻዎች ማድጋን ገንቦ አድርገው ውሃ ይቀዱበታል ሲል አድቄ ላሊበላ ተናግሯል ። እየተባለ ለብዙ ዘመን ሰው ከሰው ሳይገናኝ ኖረ ።

እንደዚሁም ሆኖ አጼ ገብረመስቀል በነገሠ በሃያ ዘጠነኛው ዓመት የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው የሚወዳውን ወደው የሚጠላውን ጠልተው ከነብሩ ወደኢትዮጵያ አብረው የገቡት አባ ጊዮርጊስ የተባሉት ጳጳስ እረፉና እራሱ በሰራው በቤተ ጉልጉታ በክብር አስቀበሩቸው በዚህን ጊዜ ከመሬት በታች በሚገኝ አለት ውስጥ አሰጀ

ምርት የነበረውን ቤተ መንግሥትና እያማረማረንም ለጋሀ መንበረ ጳጳሳት ብሎ ሰዶማት የነበረውንም ታላቂን ሀገሩን የዚህ አለም መንግሥትና ክብር ከንቱ መሆኑን ተረድቶ በሕዝቡ እንደ መቶ ሽህ ሠራተኛ የነበረውን ሁሉ አሰናብቶ ደጃፉን ዘጋው እንዳልነበረም አደረገው ሌላም ነው አህዶና ግብር አባይ ከሚገናኙበት ላይ ለመገኘርቱም አሰኝቶ የግብፅ አስላሞች በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርጉትን በቀል ለመመለስ ውሃውን ለግፋ በረሃ ለማሰባሰት በእብነ አድማስ ድንጋዮን በድንጋይ ላይ እቅሎ እየያዘ ግድብ አሰያምር ነበር ግን ኢያሱስ ክርስቶስ ከፉን በከቶ እንቀመጡ ጠላቶችሁን ወዳጁ ያሉውንአስበና ተጀምሮ የነበረውን አስፈረሰው የዚህን ዓለም ሥራ ናቶ በዚህን ጊዜ አጼ ገብረመስቀልና ባለቤቱ መስቀል ክብራ መንግሥታቸውን ለወንድሙ ልጅ ለአስፍገው ለንአኩቶ ለአብ ተረከበው አለው ነአኩቶ ለአብም ለአጼ መንግሥት መውረስ በዙፋን ላይ መቀመጥ አያገባኝም ብሎ ተከራከረ ነገር ግን መስቀል ክብራ አባትህ የሚልህን አትፈጽምም ብላ ስትጠይቀው በሃዘንና በልቅሶ ከባለቤቱ መንግሥትን ተቀበለ በራሱ ላይም ዘርክና መርቆ ዘውድ ደፋለት ነገር ግን በጳጳሱ በአባጊዮርጊስ የተሾሙት ሰባቱ ኤጲስ ቆጶሳት አባ ሳሙኤል አባ ሚካኤል ሁለተኛው አባ ያርዳእ ሚካኤል አባ እዝራ አባ ሄሮን ክርስቶስ አባ መስቀሉ ለወልድ አባ እንድርያስ ሊቀጳጳስ ሌሎችም አባ ዮሴፍና መነኮሳት ከአባቶች ሲያያዙ የመጣውን ሥርዓት ለምን ታፈርሳለህ አርባውን ዓመት በዙፋንህ መኖርት አስብህ ብለው ስለመከሩት የአባቶችን ሥርዓት ማፍረስና የኢጲስ ቆጶሳትን ምክር መጣስ ትልቅ ስህተት መሆኑን አውቆ ይቅር በሉኝ አባቶቼ ብሎ አርባውን ዓመት እስኪሞላ በዙፋኑ ሊቀመጥ ቃል ገባላቸው ያንንመውን አጼ ነአኩቶ ለአብንም የንጉሥ ንጉሥነት የክብር ዘውድ አዲደፋ በክብር ከብዙ ሠራዊት ጋር የአጼን ሥልጣን እንደያዘ በቅቅዮና አገርና በዋድላ ከተማ በዙፋኑ እስኪቀመጥ እንዲቆይ አለ ።

እንደዚሁም ሆኖ አጼ ገብረመስቀል የሚወዳቸው ጳጳሱ አባ ጊዮርጊስ ስለሞቱ በሳቸው ምትክ ሌላ ጳጳስ ለማስመጣት ገፀበረከት አሲዞ ወደካይሮን መልክተኞቹን ላከ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ከሃገርን እንዳይወጡ የታዘዙት አራተኛው አባማርቆስ የግብፁ ሡልጣን ኢልኢዲል አቡበክር ኢብን እዩብ ይባላሉ የተላኩትም መልክተኞች ከአጼ ገብረመስቀል የተላከውን ገፀ በረከት ለሊቀ ጳጳሱ አባ ማርቆስ አስረከቡው የመጡበት ጉዳይ ጳጳስ እስፈቅደው ይዘው

ለመሄድ እንዳይሆን ገልፀው አመለከቱ ሊቀ ጳጳሱ ግን ሱልጣኑን በመፍራት እንጂም እሺ ሳይሉ የተላኩትን መልእክተኞች ያነሳሏ ቸው ጀምር በዚህን ጊዜ መልእክተኞችም በአምስተኛው ወር አባ ሚካኤልን ይዘው ወደሀገራቸው ተመለሱ ።

በዚህን ጊዜ አጼ ገብረመስቀል የጳጳሱን መምጣት ሰምተው በሠራዊቱ ታጅበው በሰልፍ በብዙ ክብርና ደስታ ተቀበሏቸው ለአዲሱ ጳጳስ ለአቡነ ሚካኤል አርባ መንደር መተዳደሪያ አርገ አሽከሮች ተሳላኪዎች በንጉሡ ነጋሪት በአጼ ገብረመስቀል ትእዛዝ ተሰጣቸው እንደዚሁም ሆነ በአጼ ገብረመስቀል በሰላሳ አምስተኛው ዘመነ መንግሥት አባ ሚካኤል በመጡ በአምስተኛው አመት በአባ ጊዮርጊስ

የጳጳስና ዘመን ከተሾሙት ኢጲስ ቆጶሳት ጋር እንደዚሁም ከመ ሰቀል ክብሬ ወንድም ከገብርን ጋር የከረረ ጠብ አድርገው በሾቀት ነገሩም እየከፋ ስለሄደ ከአጼ.ፋ ወደ ከይሮ በቶሎ ጠፍተው ሄዱ ከዚያም እንደደረሱ እኔ ያልሾምኳቸው ኢጲስ ቆጶሳት ተማከረው ሊገሉኝ ሲሉ አምልጬ መጣሁ ብለው ለግብፅ ሡልጣንና ለበላያቸው ሊቀጳጳስ አመለከቱ ሡልጣንና ለበላያቸው ሊቀጳጳስ አመለከቱ ሡልጣኑም ነገሩ እንዲጣራ ብለው አባሙሴ የሚባሉ መነኩሴ ወደኢትዮጵያ ላኪ አባ ሙሴም በሳስታ በረሃ በአጼፋ ተቀምጠው የተላኩ በትን ጉዳይም ለአጼው ገልፀው ነገሩን ሲከታተሉ እራሳቸው አቡነ ሚካኤል የሰቃ ቤቱን ቄስ ወርቅ ሰረቁ ብለው ስለአስገደሉና ነገሩ ስለታወቀባቸው የጊዩን ወገኖች ፈርተው ነው የሄዱት ኢጲስ ቆጳሳትና መነኩሳትም እሬ ጳጳሱ ገብርም ቢሆን የጠሏቸው ጳጳስ ሆነው ሰው ቢግስደ ላቸው ስለሰሙ ነው እንጂ በሌላ አይደለም የጳጳሱ አሽከሮች የሮአ ገዳዮችም አቡነ ሚካኤል ግደሉት ብለው አዘዙን ብለው በእራሳቸው ፊት ስለመሰከሩ ነው ስለዚህ አባ ሙሴ ነገሩን አጣንተው እውነት ማስገደላቸውን አረጋግጠው ወደ ካይሮ ተመለሱ ።

በዚህን ጊዜ ከአባ ሙሴ ጋር ሌላ ጳጳስ ለማስመረጥ ሌሎች መልእክተኞች ለአዲሱ ሊቀ ጳጳስ ለአባ ቄርሎስ በኢትዮጵያ ተበበ ሮች ልዩ ልዩ ሀረግ ያለው የወርቅ ዘውድና በሳሲበላ ስም የተቀረፀ መቶ አምሳ የወርቅ መክሊትና የመጀመሪያው ግንዘብ 500 ብር ለአዲሱ ሱልጣን ለማሌክ ከሚል አንድ ዝሆን አንድ አንበሳ ድበል አንድ ቀጭኔ አንድ የሜዳ አህያ ልዩ ልዩ ከተልባ እግር ጥጥ የተሠሩ የሃር ልብስ ይዘንና ሌላም ገፀበረከት ይዘው ካይሮ ደረሱ ከንጉሡ ነጋሥታቸው ከአጼ ገብረ መስቀል የተላከውን ገፀበረከት ለሊቀ ጳጳሱ ለአባ ቄር

ሎስ ለሥልጣን ለመሳክ ካሚል መልእክተኛ ሲያቀርቡ ሰዓሙር ክርስቲያኑ ሕዝብ ተመልክቶ በከተማው ሲያደንቅ ሰንበተ ከዚህ በኋላ ሶስት ወር እንደተቀመጡ አባ ሚካኤልን ሽረው ሌላ አዲስ ጳጳስ ለመሾም ትልቅ ጉባኤ ተደረገ በዚሁ ጉባኤ አባ ሙሴ በዓስታ ሲሰነብቱ በሰሙትና ራሳቸውም መርምረው በደረሱበት ነገርሰው አስገድለው አባ ሚካኤል በመምጣታቸው ስለመሰከሩ ከቋቋና ደረጃ ተዋርደውናተወግዘው እንዲለዩ ተደረገ በአባ ሚካኤል ምትክ ከአባ እንጦንንዮስ ገዳም የመጡ ሁለት መነኩሴዎች ምርጫ ተደርጎ አባ ይስሐቅ የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ዮሴፍ ኤቆስ ቆጳስ ረድእ ተብለው ተሹመው ከተላከት መልእክተኞች ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጡና አባ ይስሐቅ ልዩ መንደር ተሰጣቸው በክብር ተቀመጡ ስሙ መንግሥቱ አጼ ገብረመስቀል የአባል ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሲጠሩት የማይቀርነፈው የራሞራራ ልጅ (ይምርሃነክር) ቅዱስ ላሊበላ ለሚወደው ለመንፈስ ልጁ ለነአኩቶ ለአብ ስሙ መንግሥቱን መከበበ ነገሥት አስይዞ በአባ ይስሐቅ እጅ ቅባመንግሥት አስቀብቶ በአንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሁለት (1212) ዓ.ም ሚያዝያ ሃያ አንድ እሁድ ቀን በዙፋኑ አስቀመጠው አጼ ገብረመስቀል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሆነ በአርባ በመኑ በተወለደ በሰባሁለት አመቱ ሰኔ አስራ ሁለት ቀን ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሁለት ዓመተ ምህረት አረፈ በአሥራው በቤተ ጕልጕታ አስቀብሩኝ ብሎ ተናገር በንር በዚሁ በቤተ ጕልጕታ በክብር ተቀበረ ነገር ግን የተቀበረበት መቃብር በየበተኛው ቀን ተመሠረ ይባል ።

አጼ መከብበ ነገሥት እንደሌሎች አልመከኑን ነአኩቶ ለአብ የላሊበላ ልጅ ይትባርክ እያለእሱ መንገሡ መጀመሪያ ላሊበላ ነግሰ ሳለ ልጅ አልነበረውምና ከእኔ ቀጥሎ የሚነግሠው ዙፋን ወራሽ ማን ይሆን እያለ ሲያስብ ሲፀልይ መርከብ የምትባል ፃድቅ ሴት በወንድሙ ብሃርቤ ቤት የምትኖር ነበረችና በሀልሙ መላኩ ገብርኤል መጥቶ ወንድምህ እንደአንተ የሆነ ፃድቅ ሰው መርከብ ከምትባለው መካን ሴት ይወልዳል ስሙንም ነአኩቶ ለአብ በለው ይህም ልጅ እንደ አንተ ብፅድቅ ጉብና የሚገዝ የመንፈስ ልጅህን ከአንንተ ቀጥሎ የሚነግሥ ወራሽ እሱ ነው አለው ላሊበላም ከእንቅልፉ ነቅቶ እግዚአብሔርን አመስግኖ ሰዉዶስ ወንድሙ ቤት ሄዶ ወንድሙም ሽማግሌ ከአሊን ይጠሉ ነበርና የሃርቤ አገልጋይ መርከብ ልታገለግለው ወደላሊበላ ሄዶች ላሊበላም ወደእሱ ስትመጣለትና ደስ ይበልሽ በዛሬ ሌሊት እግዚአብሔር የእንቺን ማህፀን አስበ ስለ

ዚህ ከአንቺ የሚወለደው ልጅ የእኔ ወራሽ በመንግሥቱ ላይ የሚነግሥ
በዙፋኔ የሚቀመጥ እሱ ነው ያላት መርከሬዎስ መካን ሆና ትኖር
ነበርና በጣም ደስ አላት በዚ እግዚአብሔርን እናመስግነው ስትል
ነአኩቶ ለአብ አለችው ላሊበላም ሰማ ም እሱ ነው አላት የእግዚ
አብሔር መላክ አስቀድሞ በራእይ የነገረውን ስም ሲታነሳ በጣም
አድንቆ ወደቤቱ ተመለሰ መርከሬዎስ መካን በመሆንዋ በኀዘንና ስት
ኖር በዚያች ሌሊት መጥቶ ሲነግራት እግዚአብሔርን አመሰገነች
ወንድ ልጅም ወለደች ስሙንም ነአኩቶ ለአብ ተባለ ። አባቱም ሃርቤ
ስለሞተ በላሊበላ ቤት ከእናቱ ጋር ሲኖር ላሊበላ ገብረክርስቶስ የሚ
ባል መምህር ቀጥሮለት የመንግሥትን ሥርዓትና አስተዳደር የቤተ
ክህነትንም ትምህርት አጠናቆ አወቀ በሃያ አመቱ ንጉሡ ማርያም
የምትባለውን ቆንጆ ልጅ አጭተው አጋቡት እሱም ለሚስቱ በድንግ
ልና እንኑር ብሎ ስለጠየቃት ተስማምተው በድንግልና ሃያ አምስት
ዓመት ኖሩ በዚህን ጊዜ ላሊበላ እንደራሴ አድርጐ ሾሙት ላለ በላሊ
በላ ፍቃድ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በምድረ ቆቅሆና አሠራ
በዚሁ ዘመን የመስቀል ክብራን ማህፀን እግዚአብሔር አሰበና አጼ
ገብረመስቀል በነገሡ በሃያ ሁለት ዓመቱ አብያተ ክርስቲያን ታን
ፁው በአሉቁበት ዘመን ወንድ ልጅ ወለደች ስሙን ይትባረክ አለችው
መስቀል ክብራ ከማህፀንዋ ከተወለደው ልጅ ይልቅ ያሳደገችውን ነአ
ኩቶ ለአብን ትወደው ስለነበር እሱም የእናቱ ከመርከሪ መስቀል
ክብራን ይወዳል ይትባረክ ደግሞ ከእናቱ ከመስቀል ክብራ መከርዘ
ስለሚወድ ከእሷ ጋር ሆኖ አደገ ነአኩቶ ለአብ ይትባረክንሃያ-
ሶስት ዓመት ይበልጠዋል በዚሁ በላሊበላ ዘመን በፍቅርና በሰላም
ሲኖሩ ቅዱስ ለላሊበላ መንግሥቱን ከሥ ሞቱ በፊት ለነአኩቶ ለአብ
አወረሰ ይትባረክም ከነአኩቶ ለአብ ጋር በዚሁ የተነሳ ተጣልቶ ...
ባቱ ከላሊበላ ጋር ከጣብዕ ወደኢትዮጵያ የገቡትን የጁዋ ...
እንዲደታዘዙለት ላለላበላም ሲገብሩ የነበሩትን እንዲደገብሩለት ...
ጉሪ እነሱም ልጁ ተቀምጦ ላሊበላ ለማይወለደው ልጅ በዙፋኑ በ...
ስቀመጡ ቅር ብሏቸው የነበሩ ግብፃውያን የቤጋ ሕዝቦች ግብሩን
ከለከሉ በዚሁ የተነሳ እነሱ በመፈሩበት በሚኖሩበት ሀገር ለደቶ
ዝናም አስወግዶ ምድሩን ድርቅ አደረገባቸው ስለዚህ ከብቱም ሰን
ብና በውሃ ጥምተቸገረ ።

በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ተቸግሮ ሳለ አንድ ማማስ የሚባል ግብፃ
ሰብሳቢ ለላሊበላ የምትገብሩትን ግብር ስለከለከላችሁና እንግዲህ
ህም ስለምትሉት ነአኩቶ ለአብን አሁን የእሱ ዘሎት ነው ሀገራችን

ከሌላው ሀገር ለይቶ ድርቅ ያደረገባቸን ሲል ገለጸላቸው በዚህ ጊዜ ለአምስት ዓመት አቁመው የነበሩትን ግብርና እጅ መንሻ ይዘው ወደንጉሡ ለአብ የአመጡትን ገፀበረከትና ግብር አቀረቡለት እርሱም ግብሩን ከተቀበለ በኋላ በጸሎቱ የዘጋውን ዝናም በጸሎቱ መልሶ ሀገሩን በጎርፍ አጥለቀለቀው ደርቆ የነበረውም ተክል እንደገና ሞላ እንደዚሁም ሆነ ሚስቱና ንጉሡ ለአብ በድንግልና ሃያ አምስት ዓመት ሲኖሩ ልጅ ትወልዳለህ ተብሎ እመቤታችንና ሩፋኤል በራእይ ስለነገሩት ሚስቱን በሥጋ አወቃትና ወንድ ልጅ ወለደችለት ስሙንም በሃይለ መስቀል ተባለ በዚህ ዘመን ላሊበላ አስጀምሮት የነበረውን ቤተ መቅደስ በአሸቱን ሀገር አሰርቶ አስወረሰ ።

በነአኩቶ ለአብ መከተበ ንግሥት እንደሌሎቹ አለመሆኑን በንጉሡ በሰላሳ ሶስት አመቱ ላይ አባ ተክለሃይማኖት የሚባሉ መነኩሴ ከሸዋ ወደላስታ መጥተው ሳለ የግዛቱን ዘመን እንዲለቀ የንጉሡ ነገሥትን ሁሉን ሶስት መቶ ሰባ አራት ዘመን ለተነጠቁት ለቀዳማዊ ምኒልክ ዘሮች እንዲለቅ በመንፈሳዊ አባትነታቸው ጠየቁት እጼ መከተበ ንጉሥነትም የእሱ መንግሥት አርባ አመቱ እንዲለቀ የዛጉዌ ዘሮች የንጉሡ ንግሥቱን ሁሉን ከዮዲት ቢመራ ተክለሃይማኖት አማካኝነት በወረሱት በሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት ዘመን የአባቶቹን ቃል ኪዳን ሙሉ አስደርጎ ተስፋ ኢየሱስ ለሚባለው ሌላው ሌለት ለት ቃል ገባ ነገር ግን አንድ ሺህ ሁለት መቶ አምሳ ሁለት ዓ.ም 1252) ከመድረሱ በፊት ተስፋ ኢየሱስ የተባለውን የምኒሊክ ዘር የላሊበላ ልጅ ይትባረክ ስላሳደደው በንዚሁ በተክለሃይማኖት እጅ በ1252 ዓ.ም ላይ እጼ ይኩኖ አምላክ ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው ቅብአ መንግሥት ቀብተው አነገሡት ይትባረክም የነአኩቶ ለአብ ዘመነ መንግሥት እንዲለቀ ከአባ ይስሐቅ ቀጥለው በነበሩት በአባ ቄርሎስ ጳጳስ እጅ ቅብአ መንግሥት ተቀብቶ ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ይኩኖ አምላክ የተባለው ተስፋ ኢየሱስ በንጉሥነት ዘመን ነገሠ ነገር ግን ሕዝቡም ወደ ምኒልክ ዘር በኋላ በተክለ ሃይማኖት አማካኝነት ስለዞረ እንደላስቶች በሁለት ዓመት እንደሸዋዎች በአርባ ቀን በንጉሡ ይኩኖ አምላክ ይትባረክ መንግሥቱን ሲሰማ ከምድረ ደኑ የአማራን ጂዋ ሥር ደዘ መጥቶ አንበሳ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ግጥም ደል አደረገው በዚህን ጊዜ የይትባረክ ሰዎች ከልጁ ከዋርበየዘባይ ጋር መጥተው ወደ ይኩኖ አምላክ ስለገቡ ሃርበዘ ሕዝባይን የዋግ መስፍን የትግሬ መኮንን በሥሩ እንዲገዛው በዚያው በአቡቶቹ ሁሉን በክብር ወንበር ተቀምጦ እንዲገዛ የንጉሡን ወንበር ስጥ

ቶት ንጉሥ ነገሥት ወደተባለው ዋናር ተመለሰ የዛጉዌን መንግሥት እመሠራረትና ወደምኒልክ ዘር እንዴ ተዛወረ የሚገልፀውን የይኩኖ አምላክን ዘመን መንግሥትና ከእሱ ቀጥሎ የሚነግሡትን የነገሥ ታት ታሪክ ይቀጥላል ። አቅራቢውና አዘጋጅው መራሪስ ኤ.ኦ. በላይ

ይህ የዛጉዌ ዘመን መንግሥትና ሥርወ መንግሥቱ የቆየት ከቀ ዳማዊ ዛጉዌ ከሰለሞን ልጅ ጀምሮ የነበረ ስለሆነና ታሪኩ ተቀብ ሮና ተደብቆ ስለነበር ከመጽሐፈ ሰባኤና ከመጽሐፈ ሲራክ ዘግዱር ከጻፈው ከኢትዮጵያ ታሪክ ተመልክቼ ስለጻፍኩት ስሙን የተገኙትም የኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ ብዙ ስለምኩላችሁ ለእግዚአብሔር የክብር ምስጋና ይገባዋል አሜን ።

ከአጼ ላሊበላ እስከ አጼ ይኩኖ አምላክ የነበሩት የመሳፍንትና መኳንንት ስልጣንና በማዕረግ ስማቸው ።

| ብሉይ—አርጌው ስም | ትርጉም | አዲሱ ስም |
|---|---|---|
| ሃፃኒ—ሃፃኒስ | የአጼው ልጆች | አቤቶ እቴጌ |
| እቴ | ንግሥት የአጼው ባለቤት የሀገር እመቤት | |
| ጃንደርባ ጸጋዊ | የአጼው ባለሟል - በልብ | አፈንጉሥ |
| ቄስ አጼ | የአጼው ንስሃ አባት | እጨጌ |
| አራት ማሰሬ | ለአጼው ዘውድ የሚደፋ | ርእሰ መኳንንት |
| ቀለብላ | የእቃ ቤት ኃላፊ አለቃ | አዛዥ |
| ንጉሥ | ከአጼው በታች የአንድ አገር ገዢ | |
| ደል ኮሚ | ከንጉሥ በታች የሆነ | የገሬ ደጃዝማች |
| | መሳፍንት የሚባሉ ከዚህ ቀጥለው ያሉት ነው ። | |
| ዲግልሃን | ጠቅላይ ጦር አዛዥ | መልአከ ሃይል |
| ሠርጊዋይ ጻርስጊ | አማካሪ | ቢትወደድ |
| በስትግራ | የእስር ቤት አላፊ | ቢትወደድ |
| ዳቀ ሠርግዋይ | የሙዚቀኞች አለቃ | አዛገር |
| ሊቀ ዲያቆናት | ንዋየቅድሳቱን ተረካቢ | ገበዝ |
| ሊቀመጠእ | የሚፈርድ ዳኞች | ሊቀመጣኒ |
| ንጉሥ ሕዝባይ | ነጋሪት አስመቺ | |
| ምግዋ | ወንጀለኛ የሚቀጣ | |
| ሃስግዋ | የዙፋን ቤት ተጠባባቂ | ራስ |
| ብሉቴን | የቤተመንግሥቱን ልጆች የሚቆጣጠር | |
| ሊጋባ | የንጉሡን ልጅ የሚያገባ | |
| ብሆትወደድ | የከበረ ባለሟል | ቢትወደድ |
| ፃሀፈላም | ግብር አስገባሪ ሰብሳቢ | ፀሃፊ ትእዛዝ |
| ሠራዊ | የንጉሥ ሠራዊት | ክቡር ዘብ |
| ጼዋ - ጩዋ | የንጉሥ ወታደር | |

## መኳንንት የሚባሉ ከአማርኛው ቋንቋ የተወሰደ

| | |
|---|---|
| ፊት አውራሪ | ቀድሞ የሚገባ |
| ቀኛዝማች | በቀኝ ለሚዘምተው መሪ |
| ግራዝማች | በግራ ለሚዘምተው መሪ |
| ደጃዝማች | ከኋላ ላለ ደጀን ጦር መሪ |
| በጅሮንድ ባ | በጅሮና በእጅ የመንግሥትን እቃጅ የሚገልፅ |
| ባላምባራስ | አምባ ጠባቂ |
| ከንቲባ | የከተማው ተቆጣጣሪ |
| ባላደራስ | ከንጉሡ ፊት የማይርቅ |
| ነጋድራስ | በንጉሥ ከቤተመንግሥት የማይጠፋ |
| ሊቀ መኳስ | አስከሽ ዳኛ ወይም አስታራቂ |
| ክቀደራ | ዳር ጠባቂ |
| ጭቃ ሹም | ምድር የሚለይ |
| ላሻ | ገዳኝ |
| አቃቤ ሰዓት | ሕግ አስከባሪ |

## ጦር አዝማቾች ወይም መኳንኖች የሚባሉት

| | |
|---|---|
| መኮንን አልፍ | የሺ አለቃ |
| መኮንንሚት | የመቶ አለቃ |
| ሠርግማሾ ግዮኝ | ጭቃ ሹም ግብር አስገባሪ |
| ትግሬ መኮንን | የባሬው የአክሱም ንቡረእድ |
| ቃል አጼ | የንጉሥ ቃል የሚልፍ |
| ሊቀ ደብተራ | የደብተራ አለቃ |
| ሊቀጠበብት | የሠራተኞች አለቃ |
| ሊቀ ሊቃውንት | የአዋቂዎች አለቃ |

# ምዕራፍ አስራ አምስት

ጉዲት ዮዲት የምትባል የጊዲዎን ልጅ በአክሱም የነበረው የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በጎላጤች ጊዜያ በቅዱስ ወንጌል የሚያምነውን የቀዳማዊ ምኒልክን ዘርና መንግሥቱን ክርስቲያን በምትገድልበት ጊዜ ወድመን ድል ሆነና ከአክሱም ሸሽተው ቤተማራ ወደሚ ባለው የዛሬው መራ ቤቴ ወደሚባለው ሀገር ሂዶ ተቀመጠ በዚ ያም ንጉሠ ነገሥት ዘኢ/ና የሰለሞን ዘር በመሆን ከልጁ እስከ ልጆቹ ተከብረውና ተፈርቶ ይኖር ነበር እሱም ልዩ ሀገሩ ግሸ ከሚባል በመንዝ ውስጥ የልጅ ልጅ አይቶ ሞተ ድልነአድ አግብአ ጽዮንን ወለደ አግብአ ጽዮን ወንፈ አርእድን ወለደ ወንፈ አርእድ ንጋሽ ዛሬን ወለደ ንጋሽ ዛሬ አስፍሆን ወለደ አሽፍ ያእቆብን ወለደ ያእቆብ ባሀረ አሰግድን ወለደ ባሀረ አሰግድ አድምአሰግድን ወለደ እንዚህ ሰባቱ በሸዋ ሲነግሱና መንግሥታቸውን ሲመሠርቱ የጸዋ ጦር ያዘጋጁ ጀመር ነገር ግን እግዚአብሔር ያላለው ስለሆነ በዘመናቸው ሊሆን አልቻለም ።

እንደዚህም ሆኖ በአማራ አገር ሲዘዋወሩና ሲሸሹ ብዙ ዓመታት ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ዓመት ከልጅ እስከልጅ እስከሰምንት ዘር ከቆዩ በኋላ አድም አሰግድ የሚባለው ከመደባይ ጉማ ከዛሬዎች ኦሮሞ( ከአባቸ ሜላ ልጅ ሃዊ ጊፍቱ መንደፉ ከምትባለው ከቦረና ዘር ተስፋ ኢየሱስ ኃይለ ይኩኖ አምላክ የተባለውን ወለደ ተስፋ ኢየሱስም ችኩልና ቀበጥባጣ ስለሆነ አባቱ አድም አሰግድ የሰሎሞን ዘር መሆኑ ሲታወቅ ይገድሉብኛል ብሎ በአምባማሪያም ደብቆት ሲኖር ከዚያ አምልጦ ተራ ሰው መስሎ ላስታ ለሚገኘው ንጉሥ ለንአኩቶ ለአብ ሎሌነት አደር ገባ ተስፋ ኢየሱስ ለንአኩቶ ለአብ ዋና በደፍ ያዘና ጋሻ ጃግሬ ነው የቤተመንግሥት ሥርዓትና ሕግን ከዚያው ላለ አጠናቶ አወቀ እንደዚህም ሆኖ በንአኩቶ ለአብ ዘመነ መንግሥት በቤተመንግሥቱ ውስጥ አንድ አውራዶሮ የእኔን እራስ የበላ ይነግሳል የዳዊት መንግሥት ይመለሳል እያለ ሲሊትና ቀን ሲያሞግስ ንጉሡ የሰማ ቋንቋ ያቁ ኑሮ የዶሮውን ጩኸትና ትርጉሜ ሰማ ንጉሡ ንአኩቶ ለአብ አሊመኩኝን በጣም ፈራ ደነገጠ እንዲህ

እየፈራ ሳለ ተክለሃይማኖት የሚባሉት ፍሥሐጽዮን ከማሼ መንዝ ወደዋድላ ሄደው ሳለ ለነአኩቶ ለአብ ቤተሰቦቹ አንድ መንኩሴ በርሀ ከተማህ ገብተዋል አሉት ይሀን ወሬ በሰማ ጊዜ ፈጥኖ በሠራ ዊቱ ታጅቦ ፍሥሐጽዮንን ወደአሉበት ቤት ሄዶ እጅ ነሳ እሳቸውም በደስታና በፈገግታ ተቀበለው ሁለቱ ብቻቸውን ያወሩ ጀመር እሌ መክሩን የተባለው የኩና አምላክ የዶሮውን ጩኸትና የጩኸቱን ትር ጓሜ ነገራቸው እሳቸውም ሲጠየቁኝ ነገር ሥማኝ ልንገርህ ያ ዶሮ የእኔን እራስ የበላ ሰው መንግሥት ከወገኑ አይወጣም እስከ ልጅ ልጁ ይነግሣል የዳዊትን መንግሥት ይወርሳል ብሎ እንደተናገረ ፈጥነህ ዶሮውን ይዘህ እርደህ ራሱን ብላው አሉት ።

ንጉሡ ነአኩቶ ለአብ ተመልሶ ወደቤተ መንግሥቱ ገባና ገረ ዱን ደሊላ የምትባለውን ጠራና ያን ሌሊት ቀን የሚጮኸውን አውራ ዶሮ አምጭ አላትና እርጂ ፈጥነሽ አዘጋጅና አምጭልኝ አላት ይሀን የዶሮ ሥጋ ስትሰሪ ማንም ሰው ባጠገብሽ እንዳይደርስ ለማንም እንዳታወሪ አላት እሷም እንደተባለችው በጥንቃቄ አዘጋጅታ ሰርታ ወሰደችለት ነገር ግን የዶሮውን እራስ ጥላው ስለነበር ጋሻጃግሬው የነበረው ተስፋ ኢየሱስ ከምድጃ የጣለችውን የዶሮ ራስ አግኝቶ አንስቶ በላ ፈጥኖም ጠገበ ንጉሡ የዶሮውን እራስ ከማዕዱ ላይ በጣው ጊዜ ፈጽሞ አዘነ ልቡናው ተሸበረ ከዚያም ወደፍስሐ ጽዮን ወደእ ቸው ቤት ሄዶ እንዲህ ሲል ነገራቸው እንደአዘዙኝ እንደመከሩኝ አድረጌ ነገር ግን ገረዴ የማልበላው መስሏት የዶሮውን እራስ ጣለ ችው ከጣለችበት ቦታ አንድ ገና ሄዶ ብትፈልገው አጣችው ያን ጊዜ እዘንኩ ስለዚህ የዚህን ዶሮ ጥሩት ምክንያቱ ይህ ነው አባቴ በተቻ ለዎት በፀሎትዎ ይርዱኝ አለ ።

በዚህን ጊዜ ፍሰሐ ጽዮን ለንጉሡ ሲፀልዩ ሳለ መልአኩ ከእግ ዚአብሔር ታዞ መጥቶ የዛጉዌ ልጆች መንግሥት አለቃ አበቃ አሁን በቤቱ ውስጥ ለሚያገለግለው ለጋሻ ጃግሬው ለሰለሞን ዘር የጌታውን መንግሥት መልሼለታለሁ የልጅ ልጁ ይገዛል ንጉሡ ቀድሞው የዶሮ ጩኸትም እራሱ እንዲተባበረውና እንዲያምነው ነው ይህም መን ግሥት ለሰለሞን ዘር ለሆነ ለተስፋኢየሱስ በተመለሰ ጊዜ ከመ ንግሥቱ ሲሶ አንድ እጅ ይሰጥሃል እሱም ለአንተ ልጅ እንዲሆንህ ፀልይለት ይሀን መንግሥትና ሥርዓት ያፈረሰ ሰው ቢኖር መርገመ ገበሬን ይወርሳል ይሄው ምስጢሩን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ገልጬ ነገርኩህ አንተም ቅባአመንግሥት አዘጋጅተህ ቅባው አለው ።

ይህን ከነገረው በኋላ መልአኩ ወደሰማይ አረገ ፍስሐ ፅዮን ሲባሉ የነበሩት ተክለሃይማኖት ለንጉሡ የሆነውን ሁሉ ነገሩት በቤትህ ውስጥ የሰለጠነ ዘር ስላለ የዶሮውን እራስም የበላ እሱ ስለ ሆነ የዶሮው ጩኸትን ትርጉሙን ያወከሙና እግዚአብሔር የገለፀ ልህ ለእሱ አረዳት እንደሆነው ነው አሉት ነአኩቶ ለአብም ለጊዜው ቅር ቢለኝ በዓፄዎና በቀዳማዊ ሚኒልክ ልጅ በተማይ የተደረገ ውን ቃል ኪዳን እንደኛና እንዲታደስ ቃል ያስገቡልኝ አሉዋቸው እሳቸው እሺ ሲያደርጉ ተደሰቱ ። ለተክለሃይማኖት በንጉሡ ጊዜ ከመንግሥቱ ሲሶ መንግሥት ሲሰጥ ለንጉሡ በዓፄዎና በተማይ የተደረገውን ቃል ኪዳን ሊፈጽም ቃል ገባ የተቀዋሚቱትም ውል ይህ ነው ።

1ኛ/ የነአኩቶ ለአብ ዘመን መንግሥት እስኪያልቅ ድረስ ንጉሠ ነገሥት መባሉ እንዲቆይና የርሱ ዘመን መንግሥት ሲያልቅ ተስፋ ኢየሱስ በመባ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንዲባል ።

2ኛ/ ተስፋ ኢየሱስ መንግሥቱን ከተቀበለ በኋላ ከዛጉዌ ዘር አንድ መስፍን እየመረጠ በላስታ አልጋ እንዲሾም የላስታም ግዛት ከዛጉዌ ዘሮች እንዳይወጣ

3ኛ/ ላስታን የሚገዛው መስፍን የዛጉዌ ዘር ለመሆን ምልክት ይህ ነው ወንድ ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስመቱን የዘበኞቹ ጦር ባለብር ሽህ የሰንደቅ አላማው መያዣ ጫፍ የብር እንዲሆን

4ኛ/ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የሆነው ንጉሥ በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታው መስፍን በብር ወንበር እንዲቀመጥ

5ኛ/ የላስታው መስፍን ከንጉሥ በተገናኘ ጊዜ ወንድም ከወንድሙ ጋር ሲገናኝ እንደሚያደርገው እንደሰላሙ እንጂ የላስታው መስፍን እንደሌሎቹ መሳፍንት መሬት እንዳይስም

6ኛ/ እንደሌሎቹ መሳፍንትና መኳንንት ግብር እንዳይገብር መጠን አውጣ ተብሎም እንዳይታዘዝ

7ኛ/ ይህን ውል ያፈረሰ ወይም የናቀ ቢገር ንጉሥ ወይም መስፍን ፤ መንግሥቱ ሌላ እሱ ወደወርደት ይደርሳል ሲሉ ሁለቱ በፍስሐ ጽዮን አባትነት ተዋዋሉ ይህ ውል ለሚመለከታቸው ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባ ጊዮርጊስ ለኢትዮጵያው ጳጳስ አባ ቄርሎስ ለሃይቁ መምህር አባ ኢየሱስ ሞአ ለደብረዳሞው መምህር አባ ዮሃኒ ለነዚህና ለሌሎች ሁሉ ግልባጩ ተላከላቸው ።

በዚሁ ውል ባለ የባሊበላ ልጅ ይትባረክ ሰምቶ ተስፋ ኢየሱስን አባድሞ እስዎ አሠረው ከዚያም ከታሠረበት ቀኝ በባስታ እግራዎች እርዳታ አምልጦ ሬት በልጅነቱ ሲማርበት ወደነበረው ወደ ቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ሃይቅ ሄዶ ከአባ ኢየሱስ መአ ጋር ተገናኘ አባ ኢየሱስ ሞዓም በደስታ ተቀብለው በክብር አስቀምጠውት ባለ ተክለሃይማኖት መታሠሩንና አምልጦ ወደሃይቅ መሄዱን ሰምተው ከሸዋ ወደሃይቅ እራሳቸው ሄደው ይህ የሃይቅ ገዳም ለባስታ ቅርብ ስለሆነ ያስፈራዋልና ከእኔ ጋር ሄድ ብለው ከአባ ኢየሱስ ሞአ አስፈቅደው ወደሸዋ ይዘውት ሄዱ. በዚያም በሆፋት በመንዝ በተጉለት በመራቤቴ በአማኑኤልን እየዞሩ የምኒልክ ዘር መሆኑንና ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵ' እንደሚሆን ለባላባቶች አስተዋወቁት ተክለሃይማኖት በየአውራጃው እየተዘዋወሩ ወንጌል ሲያስተምሩ በዚሁ በስብከትነታቸው በየሀገሩ ቃውቀው ተፈርተው ይኖሩ ነበርና በዚሁ በወንጌል ስብከታቸው ላይ ለየትኛልቁ ሰው የሚገኘ ዘሮች ከሚኒልክ ዘር አባአግባብ ነው ያወስዱት ስለዚህ ለምኒልክ ዘር ለተስፋ ኢየሱስ ሲመለሱ ይገባል እያሉ ይሰብኩ ስለነበር ። የአማራ ጭዋ ጦር በወግዳ ፣ በደምቢ በመገር፣ በወረብ ፣ በቦካልሺ የባሬው ቡልጋ ፣ በሙሐል ፣ በመራቤቴ ፣ በመንዝ ፣ በተጉለት ፣ በአማራ ሳይንት የአሉ ሁሉ የመደባይ ጉሣዎች ሳይቀሩ ተሰበሰቡለት ለማንገስ በየአውራጃው በየገዳማቱ ያሉት ባላባቶችና መነኩሳት ተሰበሰቡ በዚህን ጊዜ ተክለሃይማኖት እንደገና ወደላስታ ሄደው ከነአኩቶ ለአብ ጋር ተነጋግረው ውሉ ለምን ፈረሰ ቃል ኪዳናችን እንደዚህ ነው ብለው በአባትነት ጥያቄ ጠየቁት እሱም የአጎቴ የባሊበላ ልጅ ነው ይሄን የሠራ እንጂ እኔ አይደለሁም አለ የባኒበላ ልጅም ይትባረክ ቢጠይቁት እኔ የሰለሞን ዘር ነኝ ከአንድ መጽሀፍ (የባሬምና አርሞዎች) የተወለደ የሰለሞን ዘር ነው ቢሉኝ አልቀበልም አላምንም አላቸው በዚህን ጊዜ ተክለሃይማኖት ቃላቸውን ለሰማና ቃል ኪዳኑን ለአፈረ ለነአኩቶ ለአብ ቡራኬ ሰጥተው በይትባረክ ንግሥ ተናገው ወደሸዋ ተመልሰው ተስፋ ኢየሱስ እንዲወጋው አዘዙት በዚህን ጊዜ የነአኩቶ ለአብ ዘመን መንግሥት እስከ መያልቅ ተስፋ ኢየሱስ ለሶርነት ይዘጋጅ ጀመር ይህን ሲሰማ የባሊበላ ልጅ ይትባረክ የባስታን የጦማ ባላባቶችን አባድሞ በነአኩቶ ለአብ ላይ አስነሳበት ነአኩቶ ለአብም የማሁቱ እርባ ዘመን አልቆ ነበርና ወደትግሬ ሀገር ልቶ ጌጡ ከሚባለው ሄዶ ተቀመጠ በዚህ ላይ የባስታ አማራዎች ቃል ኪዳኑን ያውቁ ነበርና ከይትባረክ ወደ ተስፋ ኢየሱስ ሆኑ በዚህን

ጊዜ ተስፋ ኢየሱስ በሽህ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት አመት ምህረት ላይ የአጼ ላሊበላ ልጅ ይትባረክ ከነአኩቶ ለአብ ቀጥሎ ነገሠ የሚባለውን ሲሰማ አምስት ዓመት የሰለጠነውን የጭዋ ጦር አስልፎ ሄደበት ንጉሡም ይትባረክ ይሄን ሲሰማ ወደጋይንት ሄደ ከዚያም አንስታ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ተገናኝተው በድንገት ጦርነት ገጠሙ ይትባረክ ድል ሆነና ሸሸ ከዚያም ተከታትሎ ተስፋ ኢየሱስ ገደለው ይላሉ ግማሹ አመለጠ የሚሉም አሉ ከዚያ ተመልሶ በድል አድራጊ ነት ወደሸዋ ተመልሶ ስመ መንግሥቱ ንጉሠ ነገሥት ዘኢ/ አጼ ይኩኖ አምላክ ተብሎ በተክለሃይኖት እጅ ቅባአመንግሥት ተቀብቶ በአንድ ሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ዓመተ ምህረት ነገሠ ይኩኖ አምላክ ማለት አምላክ ይሁነው ማለት ነው በላስታው አልጋ በይ ኩኖ አምላክ ፈቃድ የይትባረክ ልጅ ሃርበህ ዝባይ ከሃርበህ ዝባይ ቀጥሎ ተስፋ ኢየሱስ ከዚያም የልጅ ልጆቹ በቃል ኪዳናቸው መሰ ረት ላስታን ብቻ ይገዙ ጀመር ፡፡

ከዚህ ላይ የላስታ አማራዎችን ስላነሳሁ አማራ ማለት ምን እንደሆነ ትርጉሙና የጐሣው አመጣጥ እንዴት እንደሆነ ማወቁ ያስፈልጋል ስለኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚኖሩት ጐሣዎች አመ ጣጥ ብዙ ታሪክ ተመራማሪዎች ደክመው የመሰላቸውን እንደጻፉ ታውቃላችሁ ነገር ግን ለኔመራራስ በላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ ያለ ድካም አክሱማይ ሲራክና ዘግዱር ዘቤተ አንዳ እንደዚኸውም ከአ ዳም እስከ አጼ ድረስ የአምላክ አገልጋይና የህዝብ መሪ የነበሩትን የንጉሶችን ታሪክ የያዘው መጽሐፈ ሱባኤ ከጀባልኑባ አግኝቼ ተመ ልክቼ ከብዙ በጥቂቱ መርጬ ለታሪክ አንባቢዎች አዘጋጅቼላችኋለሁ ፡፡ ማራ ማለት በሱባውያን ቋንቋ እውነተኛ ብርሃን ማለት ነው ከጊዜ ብዛት የተነሳ እግአዝያን የተባሉት አቡሳውያን ግእዝ ተናጋሪዎች አማ ሃራ ወይም አማራ የሚል ቃል ሰጡት ይሄውም በግእዝ አማራ ማለት መጠቆም ወይም ማመልከት ነው አመረ አመለከተ ካለው ግሥ ይወ ጣል በቅርብ ጊዜ ደግሞ ከአረብ ቋንቋ አማራ ማለት አራሽ ማለት ስላሉ ሃሰት ነው ከዚህስ በራሱ ቋንቋ አማራማለት አማረ ወይም ቤትዬቱ አምራ ሄዶች የሚሉት ይመስላል ሆኖም ግን ከመጽሐፈ ሱባኤ ያገኘሁት ማራ ማለት እውነተኛ ማ ብርሃን ራ እንደሆነ አስ ቀድሜ አገልጥላችኋለሁ ፡

የአማራ ጉማ አመጣጥ

ኢትዮጵያ የተባለው ኢትኤል እንቆቅልን እግብቶ እስር ወንዶች ዕስት ሴቶች ወስዶ ከኢትዮጵያ ነገድ ላይ ተመልክቱ ኢትዮጵ ቢአ ር፣ በእርእራምን ፤ እራም ናኒን ፤ ናኒ ሃኒን ሃኒ ሁለተኛው በእርገ ቢአር በለእምን በለእም ሴት ነቢይ የነበረችውን የሸምሽልን አባት ቀራሚድን ቀራማድ በመንፈስ የሥጋ ዘር በተቀላቀለ ውሃ አፈ ማህ ዮናን ታጥባ ሳለ ሀንስት ዶሸትን ወለደች የደሸት አባት ስሙ አዶታ ወቀም ይሄውም ሽምሽል በረሃ ለበረሃ ስትዞር ውሃ ዶከሚት ከም ንጭ አጠገብ መጥታ የሥጋ ዘር በፈሰሰበት ውሀ ታጥባ ስለመንፈስ ስታስብ ድንገተኛ እውቀ ነፋስ ተነስቶ ለትንሽ ሰዓት ወደ ሰማይ አውጥቶ መልሶ ከነበረችበት ጠላት ድንግል ነበረችና እውቀ ነፋሱ በእነሳት በዘጠኝ ወር እርግዛ ዳሽትን ወለደች ዳሸት ማጂን፣ ጂማን ፤ መንደን ፤ መደባይን ይወልዳል እነዚህ ሁሉ በውሃ የሚያመልኩ ነገዶች ናቸው መንዲና መደባይ የእርጭ ማጂና ጂማ የአማራ የትግሬ የብሔን በካም ልጅ ኩሽ የካሳዊየብናምር አባቶች ናቸው የዛሬዎች ካማዊ የተንቶች ኩሳውያን ናቸው ማጂ ፣ ማራን ፣ ዣማን ጂማን ይወልዳል እነዚህ ዣማን በሚፈስበትና በእነዚቢ ው ሄደው ሥፈሩ በአባታቸው ስም ሀገሩን ደሸት አሉት በሁለተኛው አጼ ዘመን መንግሥት በአራት ሽህ አምስት መቶ ዘመን ከተቀበረ የማራ ጉማዎች ጋፋቶች በየጊዜው ጦርነትና ውጊያ ስለእነሱባቸው ማዣንን ተሻግረው ሄደው ተቀመጡ የሄዱበትን ምድር ወንዙን በነገዳቸው ዣማ ጂማ አሉት ምዮቂን ማራ አሉት ነገር ግን በተዳማዊ ምኒልክ ልጅ በተማይ ዘመነ መንግሥት ጼዋ ጦር ስለተመደበበት በግእዝ ቋንቋ ቤተ መራ ተባለ ከጊዜ ብዛት ከእስያ እየተሰደዱ የአረብ ዘሮች ስለገቡና ስለተሰበሰቡበት መራ ሳይንት ከዚያ አማራ ሳይንት አሉት ማይንት በቋንቋቸው መሰብሰቢያ ወይም ማከማቻ ማለት ነው አማራ ሳይንት ሲሉ አማራ የተሰበሰበበት ማለት በሚባለው ቃገር ላይ የአ ሳይንት ሲሉ አማራ የተሰበሰበበት ማለት በሚባለው ዣንዲር ማራ ጉማዎች ሲኖሩ ስመ መንግሥቱ ቀለመ ዮቁ የቆባለው ዘንዲር የጨዋ ጦር በእሰበት ምድር ሁሉ የዣማን የማጂን ነገዶች እያጥዋ በየጉማው ሲልክ ወደአማራሳይንት የሚበልጠውን ልኳል ።

እንደዚሁም ሆኑ ለሁለተኛው ዘንዲር አሚንሆ የአብንልሃኪም የልጅ ልጅ ከግብጾች ጋር ባደረገው ጦርነት በአማራሳይንት የሚኖሩት አማርኛ ተናጋሪዎች ለእርዳታ ሄደው ድል ከአደረጉ በኋላ በዚያው በግዮን ዳርቻ በቴፕ በደስታ በባይስ በራኩዲ ለሁለት ሺህ ዘመን ተቀምጠው ሲኖሩ ላሊበላ ወንድሙ አጼ ሃርቤ እሳዶት ሳለ በዚያው ከአማራዎች ጋር ተዋውቆ በኋላ ከወንድሞቹው ጋር ለመግና ኝትና ላሊበላንም እንግሥው ከምስር ልቶ ሥናሬው አማርና ከዚ

ያም በዛሬው ሕዳይሳና ሀንፌ ከሚባለው ተንስተው ሀገር እያቀኑ እያስ
ገቡና ባላባቱን እየሾሙ በአራት ወር ጓሰታ ገቡ ከዚያም እስፈረ
የደለኛ ሕዝብ ስለነበሩ ከእጼ ሃርቤ ከወንድሙ ቀምሰው ላሊበላን
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው አነገሡት ቀማኞ በዚያው በርሀ
የገር እብን አድማስ በሚባለው ድንጋይ አለቱን አቅልጠው ቤተ ክር
ስቲያኖች ሰሩለት ቀማኞ ከጥንት ወገኖቻቸው ጋር ተደባለቁ የጨዋ
ወታደርነት ያላቸው በገማን በዛሬው ሽዋ እየተደለደሉ በባላገሩ ላይ
ምሪተኛ እየሆኑ ተቀመጡ ይኼውም በአንድ ሽህ አንድ መቶ ሰባ
አምስት ዓመተ ምሀረት (1175) ላይ ነው ። እነዚህ አማራዎች የጭጭ
ጦር የሠፈሩበት በደንቢያ በአናሪያ በቤተአንገላ በቤተሼር በመራቤቴ
በተጉለት ነው ከነዋሪዎች አገሬው ይልቅ በኋላ የመጡት አማሮች
ስለቤተመንግሥት ሥርዓትና ሕግ ስለጦር በጣም የሚያውቁና
የሰለጠኑ ስለነበር ተክለሃይማኖት አማራዎችን ይኩኖ አምላክን
እንዲያነግሡላቸው አጥብቀው ለመኗቸው ስለዚህ ይኩኖ አምላክም
የተክለሃይማኖትን ቃል ኪዳን ብቻ ሳይሆን አማራዎች ስለረዱት
ከአባቱ ከእግእዝያንና ከግእዝያና ከእናቱ ወገኖች ከአርሞዎች ይልቅ
የአማራን ሰው ይሾምና ይሸልም ይወድም ጀመር በቤተመንግሥ
ቱም በገበያም የአግዝያን ቋንቋ እየወደቀ ወደአማርኛ ቋንቋ ተቀ
የረ የግእዝን ቦታ ያዘ ከአንድ ጐሣ ቋንቋ ወጥቶ አማርኛ የኢት
ዮጵያ ሕዝብ ልዩ ልዩ ጐሣዎች ሁሉ የሚናገሩት ሀገቸውንና ሥርዓ
ታቸውን የሚገልፁበት ቋንቋ ሆነ ።

ቀድሞ ከክርስትና ሃይማኖት በፊት ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ
ከክርስትና በኋላ እስከ ዘጠኝ መቶ ዓም ድረስ በአፄላስ ዘመነ መን
ግሥት አኩሱምያን ወይም አቡስ አበጀ የሚባሉት አግአዝያን የኢትዮ
ጵያን መናገሻ ከተማ አክሱም አድርገው የዛሬውን አፍሪካን ሲቆጣ
ጠሩና ሲገዙ በአረቦች መነሳት ይከመው ሳለ የሴሜን ፈላሾች ከአገ
ዎችና ከበጀ ነገዶች ጋር ቃል ኪዳን አድርገው የምኒሊክን የዘር
መንግሥት ገለበጡባቸው በዚህን ጊዜ የሴባ ቋንቋ ጥበብ ብቻ ማለት
እንደጀመረ በተክለሃይማኖትና በአማራዎች እርዳታ ከዛጉዌ ዘሮች ወደ
ጥንቶች ወደገገርዎች ዘር ሲዛወር የአግዝያን ቋንቋ የሆነው ግዕዝ
ለጊዜው ባይቀንስም የቤተመንግሥቱን ክፍል አማርኛ ቋንቋ ይቀማል
ጀመር ።

የአማራ ጐሣዎች ላሊበላንም ሆነ ይኩኖ አምላክን እረድተው
ከዙፋናቸው ላይ ቢያወጡ እራሳቸው ወይም ከነሱ ወገን ከቢዎድ

ሮስ በስተቀር የንግና ከሁሉት የወጣ የለም ሆኖ ግን የአማርኛውን ቋንቋ የሚናገር መንፈስ ሃይል ስላለው የበላይነቱን ይቀጥል ጀመር ።

## ተክለሃይማኖት የተባሉት የፍሥሐጽዮን አጭር የህይወት ታሪክ

የሰሎሞን ልጅ ምኒልክ ነገደ ቶቅማንን አበሳውያን ምኒልክ አግአዝያን የሚባሉትን አስራ ሁለት ሺህ ሠራዊት አርባ ሽህ ህዝብ ይዞ ወደኢትዮጵያ ሲገባ የሳዶቅ ልጅ አዛርያስ እንደአባቱ የካህናት አለቃ አድርጐ የኦሪትን ሕግና ሥርዓት ታቦተ ፅዮንንም እሲፆ አመጣው አዛርያስም እንደ አባቱ ሕግና ሥርዓት በንዋየ ቅዱሳቱ ሁሉ ያዘበት ነበር እንዲሁም መጀመሪያ በሰባ ቀዋሉም በአክሱማይ ዘመን ያዘበት ነበር መንግሥት አክሱም ላይ የልጅ ልጆቹ በቤተመንግሥት ያዘበት ነበር እንዲሁም ካህናት በደብተራ ኦሪት የተሾሙ የሌዋ ጦር በሰፈረበት ሁሉ ቤተ መቅደስ እያሰሩ ህገ ኦሪትን እያስተማሩ ኖሩ አወማስጦስ ቄሣር በሮም በነበረበት ሰዓት በዚያን በኢትዮጵያ ባዜ ንጉሠ ነገሥት በሆነበት ዘመን ሄሮድስ በገሊላ በነገሠበት ጊዜ እኬንም በአክሱም ቤተ ካህናት በነበረበት ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ ።

እንደዚህ ሆኖ በአክሱምና በአካባቢው በሚኖሩ ሕዝብ መካከል የሃይማኖት ልዩነት ተደረገ ይሄውም ከኢየሩሳሌምና ከአካባቢዋ ተሰ ደው ወደአክሱም የሚገቡ አይሁዶችና ግሪኮች ሁሉ አዲሱን ሃይማ ኖት ወንጌልን መስበክ ስለጀመሩ ነው የኦሪት ካህናት ለህዝቡ እንዳይ ሰበኩ እንዳያምን በየቢዛው ለንጉሥታቱ ተናግረው ነበር ።

ነገር ግን እራሱ የመንግሥቱ ክፍል ህዝብ አዲሱን ሃይማኖት ተቀብሎ በቅዱስ ወንጌል አምኖና ተጠምቆ ከባዜን ልጅ ከፅንፈ አርአድ እስከ አፅብሐና አብርሃ ድረስ በሽሽግም በግልፅም ይነገር ነበር ሆኖም ግን ንግሥተ ነገሥታት በኢትዮጵያ በተባለች በአስራ ሁለተኛው አመት በእግዚአብሔር አብ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምና እንደተጠመቀችና እንዳመነች እንደዚሁም ቅዱስ ማቴዎስ በቤትዋ እንደተጠመቁትም ከዚያ ግዛቱዋ ወደሚሆነው አብያንና ያሉትን ሁሉ እንደጠመቃቸው ከዚያ ግዛቱዋ ወደሚሆነው አብያንና ናዋራትን አስተምሮ ክርስቲያን እንዳደረጋቸው በአክሱማይ ሲራክ ታሪክ ተፅፎ ይገኛል እንደዚሁ የማጂ ዘር የሆነ የመድባይ ጉማ እንደ ባለሥልጣን ግን ደረባ ጃን ደረባ (የንግሥት ባለሙዋል ማለት ነው) ከኢየሩሳሌም ወደጋዛ ሲመለስ በፊልጶስ እጅ ተጠምቆ ክርስቲያን እንደ ሆነ በሃዋርያት መፅሐፍ ተፅፎ ይገኛል ከዚያም ቤተሰቦቹን ክርስቲያን አድርጐ በአይሁድና በሮም ህዝብ እየተባረሩ የሚመጡትን ክርስቲያ

ኖች ያስተናግድ ይቀበል እንደነበር ከዚያም ወደኢትዮ ሆንዶኬዎች ይልካቸው ነበር የማጂ ዘሮች የሆኑሁሉ አባቶቻቸው የጉግሙ ንጉሥ የደሸት ዘር ወይም ጋፋት የተባሉት እትጀ ጂዐን የስጋልና የእናሪያው ንጉሥ መጋል የጉባው ንጉሥ የአጀበን የአበበው ንጉሥ አጋፀን ገበሬስት ወርቅና እጠን ከርቤ በዘዚን በእጹ ሌዘዚዛ ዘመን መንግሥት ጊዜ ወደኢየሩሳሌም ሄደው ለአቀረቡለትና ለሰገዱለት ለክርስቶስ መሆኑን ስለሚያውቁ ብዙዎች አምነው ተጠመቁ ነገር ግን የኦሪት ካህናት ብዙዎችን አስገደሉ በዚህን ጊዜ በሽሽግ እንጅ በግልፅ ላይ ሆን እስከ አብርሃ አፅብሃ ዘመነ መንግሥት ለሶስት መቶ ሰባ አመት ድረስ ኖረ ።

አጽብሃና አብርሃ የሚባሉት ሁለት ወንድማማቾች ንጉሶች አክሱም ፅዮንና በሌሎች አውራጃዎች የሚገኙትን ቤተ መቅደስ ሁሉ ከኦሪት ወደቅዱስ ወንጌል በኦሪት ፋንታ ወንጌል በበግ መስዋዕት ይልቅ በስጋዱና በወይን እንዲሆን አዘዙ ። በዚህን ጊዜ ብዙ የኦሪት ካህናት እየተናደዱና እያኮረፉ በንጉሡ ነገሥቱ ላይ የሚነሳ ጠላት ይፈልጉ ጀመር የአባርያስ ዘር የሆነ በአፅብሃና በካሌብ ዘመነ መንግሥት ህዝብ ቀዳሚ ካህኑ ያፈድንና ንግሥት ህዝባን ወለደ ንግሥት ህዝባን ከግርማ አስፈሬ ንጉሥ አይደለም ህዝበባርከን ወለደች ህዝበ ባርክም ከአክሱም ወጥቶ ባህረ ቀጋ ከሚባል ሃገር ዳውንት ውስጥ ገብቶ እያስተማረ ብዙ ህዝብ እያጠመቀ ተቀመጠ ። ህዝበ ባርክ ተክለ ቀለትን ተክለ ቀለት መቅደላ የምትባል ቤት እግዚእ አግሬ ላይነት ውስጥ ሰባት ልጆች ወለደ እነሱም ታቦተ ፅዮንን የሚያገለግሉ ናቸው ።

ተክለቀለት አፅቀሌዊ በርበ ግጂ ከሚባል አገር ሃርበግጅን ወለደ ሃርበግጂ ይግናህ መስቀልን ይግናህ መስቀል ይቅናእላዊትን ይቅና ላዊት ዘልዑልን ዘልዑል ሚናስን ሚናስ አብደላን ከቆላጂ አውራጃ ዶረፌ ከሚባል ሃገር ሃርበጂን ወለደ ሃርበጂ ህይወት አብነ ፅዮንን ህይወት አብነ ፅዮን በኩረፅዮንን በኩረፅዮን ህዝበ ቅድስን ህዝበቅድስም ብርሃን መስቀልን ወለደ ብርሃን መስቀልም ናዓዊን እግዚእን ፣ ናዓዊ እግዚእ ሴትን ፣ ሴት ወረደ ምህረትን ፣ ወረደ ምህረት ዘርአዮሃንስን ወለደ ዘርአዮሃንስ ፀጋ ዘአብ ነው ። ፀጋ ዘአብ ፍስሃ ፅዮንን ወለደ ፍስሃጽዮን ተክለሃይማኖት ናቸው ።

ወደንጉሥታቱ ዘር እንመለስና አብርሃ አስፍሀን አስፍሀ አርፍድን አምሲን አምሲ አልአደብን አልአደብ አልአሜዳን ወለደ አልአሜዳ

በንግሥናቸው ዘመን ብዙ የሃይማኖት አስተማሪዎች ከግብፅና ከሮም ከግሪክ ወደኢትዮጵያ ገቡ ከነሱም በጠቅ መነኮሳት ናቸው ምንኩስና በአባ እንጦንስ ይጀመራል ። መነኮስ ማለት ሞተ የዚህን አለም ደስታ ጠላ ተለየ ማለት ነው እንጦንስ መቃርስን አመነኮሱ አባ መቃርስ ጳኩሚስን አባ ጳኩሚስ ቴዎድሮስን አባቴዎድሮስ አረጋዊን አባ አረ ጋዊ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገብተው ክርስቶስ ቤዛን አመነኮሱ አባ ክርስቶስ ቤዛ መስቀል ሞአን አባ መስቀል ሞአ ዮሐኒን አባዮሐኒ ተክለሃይማኖትን አመነኮሱ በነዚህ ጊዜ በየሃገሩ በየዱሩ ብዙ ገዳማት ተቆረቆረ የምንኩስና ሥርአት እየተስፋፋ ሄደ የዘጠኙ ቅዱሳን ስም ከአንጾኪያ ሶርያ ከሮም ከግሪክ ከእስያ የመጡት አባ አሌፍ አባሰህማ ፣ አባ አረጋዊ ፣ አባ አፅሌ ፣ አባሊቃኖስ ፣ አባ ጉባ ፣ አባ ይምአታ ፣ አባ ገሪማ ፣ አባ ጰንጠሌዎን ናቸው ። ከነዚህ ቅዱሳን በፊት ኢየሱስ ክር ስቶስ በአረገ በሶስት መቶ መሮጵዮስ የሃገስ ልጅ የሚባል ከግሪክ ሁለት ልጆች አስከትሎ ከአንበረም ቤት እንግድነት አደሩ ነጋዴውም በእድሜ የሸመገለ ነበረና ታሞ ከትንሽ ቀን በኋላ ሞተ እነዚያም ልጆች በአንበረም ቤት ለሰምንት አመት ተቀመጡ ፍሬምናጦስና ሲድራኮስ ይባላሉ ።

ከእለታት አንድ ቀን ፍሬምናጦስ ካህኑ እንበረምን እንዲህ አለው የኢትዮጵያ ህዝቦች ባህል እንደኦሪት ህግ ትገረዛላችሁ በክርስቶስም ታምናላችሁ ነገር ግን ተጠምቃችሁ ሥጋ ወደሙ አትቀበሉም አለው እንበረምም ለፍሬምናጦስ እንዲህ አለው ማዘረትን አባቶቻችን ሌዋው ያን የክርስቶስን ቃል አዲስ ኪዳንን የሀደንኬ እቴ ባለመኖሩ አመጡ ልን ሥጋ ወደሙ ተጠምቀን ለመቀበል ግን ጳጳስ አልመጣልንም አለው ስለዚህ አንተ ከሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ሄደና ከሱሌማን ተቀብለህ ጳጳስ ሁነን አለው ፍሬምናጦስም እሺ ጌታዬ እንዳዘዝከኝ አደርጋለሁ አለው እንበረምም ለፍሬምናጦስ ብዙ ወርቅና ብር ሰጥቶ ላከው እሱም ወደኢየሩሳሌም ሄዶ ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ አትናቴዎስ ዘንድ እንደደረሰ ስለኢትዮጵያ ባህልና እምነት ነገረውና ሊቀጳጳሱም በጣም ደስ አለው ስሙንም ሰላማ ብሎ በመሾ ኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ ሥልጣኑን ሰጥቶ በፍቅር ተቀብለው በፍቅር ሸኙት ሰላማ ማለት ሰውን ከእግዚአብሔር የሚያስታርቅ ማለት ነው አቡነ ሰላማ ወደኢትዮጵያ ገብቶ በኢትዮ ጵያ የሚኖሩትን ቤተመቅደስ ሰአታቸውን ባርኮ ከኦሪት ወደሐዲስ ወንጌል መልሷቸው ከበግ መስዋእት ወደስንዴና ወደወይን አደረጉት ደሙም የሆነ ክርስቶስ በተወለደ በአፅብሃና በአብርሃ ዘመን በሶስት መቶ ሰላሳ ሶስት የሚለውም አለ ።

አሁን ወደ ተክለሃይማኖት ታሪክ እንመለስና ፀጋ ዘአብ እግዚአ ሃርያ የምትባል ሴት አግብቶ በዛሬው ቡልጋ አውራጃው ነው ልዩ ቦታው በዛሬው አቴጌ በምትገኝ ፈጣጋር ፅላልሽ መንደር ውስጥ ሲኖር የዳሞ ዘር ሞተለሚ የሚባል በሬሌ በሚባል የንጉሥ የወላሞ ንጉሥ ነበር ያም ሃገር ዳሞት ይባል ነበር ።

በዚያ ዘመን ዳሞ የሚባል ታላቅ ንጉሥ ነበር ለሚገኘው ኋላም ለአክሱም ንጉሥ ነበር የዚህም ዘር ላባ የአክሱም ነገሥታት በዮዲት ዘመን ከጠፉ ይገብር ነበር ነገር ግን እስከማን ድረስ የበላይ ሳይኖረበት ይገዛ ነበር ከዘር ወደዘር ዉር ሲኖር አለሳዴ ከምትባል ንግሥት ሞተለሚ ተወለደ እየተዛ ንጉሥ መንግሥቱን ሊያስፋፋ የዐለልሺ አውራጃ የሆነውን ተወለደ ይዞም እየወረረ ዞሬን ድረስ ከዚያም የዐጋ ዘአብን ሚስት ፈጠጋርን ማርኮ ለሚስትንት ወሰዳት ከጥቂት ቀናት በኋላ ሚስት እግዚሃርያን ቅዱስ ሚካኤል ታዞ ከሞተለሚ ሠራዊቶች እጅ ነጥቆ በእግዚአብሔር ፈቃድ ራት ወደሃገርዋ መልሶ አመጣት ከባልዋ ከፀጋ ዘአብ ጋር በዚህ ተአምር ነች ፀጋዘአብም ስለሚስቱ መማረክ በጣም እያዘነ በጾም በጸሎት ይኖር ነበርና ሚስቱን በማግኘቱ በጣም ደስ አለው ከዚያም የእምነትን ድግንትና እርዳታውን እያመሰገኑ ሲኖሩ በዚህ አንድ መቶ አምሳ ሁለት ዓ/ም በታህሳስ ሃያ አራት ቀን እግዚአርሃያ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙ ፍስሃጽዮን ተባለ ተሰየመ ነገር ግን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ተክለሃይማኖት ተባሉ ። በሰባት አመታቸው ከአባታቸው ዳዊት ደገሙ ከዚያም ከአባ ጌርሎስ ዲቁና ተቀበለው ከአባታቸው ምንኩስና ወሰደው በሸዋ በዳሞት እየተመላለሱ ወንጌልን በትጋት ያስተምሩ ጀመር ብዙ አረማውያን ወደክርስቲያን ሃይማኖት መለሱ በስልጣናቸውም ልዩ ልዩ ተአምራት ይሠሩ መፈወስ ጋኔን ማስለቀቅ እሳቱ በኢያቡሩሲም በየጊዜው እየደረሱ ይሳለሙና በሌቀ ጳጳሱ ዘን ድም በጣም ታውቀውና ተከብረው ይኖሩ ነበር ።

ለተክለሃይማኖት ዲቁናን ቅስና የሰጡአቸው ግብፃዊ ጳጳስ አባ ጌርሎስ ከሞቱ ወዲህ በግብፅ ሃገር እስላሞቹ በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ ደይደድ ከስከስ ስለዚህ የቋቋስናው ሥርዓት ባይ በመሆኑ ቅስናና ዲቁና የሚሰጥ በመጥፋቱ በኢትዮጵያ ያሉት መነኮሳትና ሊቃውንት ጉባኤ አድርገው ተክለሃይማኖትን ለቋቋስና መረጣቸው ከዚህ በኋላ አቡን ተክለሃይማኖት በቀድሞው ከብረቸው ላይ የቋቋስና ሥራ ሲጨምሩ አባትነታቸው በኢትዮጵያ ሁሉ ታወቀ የኢትዮጵያ በውድና ዙፋን

ከዛጉዬ ዘር ወደሚኒሊክ ዘር ለይኩኖ አምላክ ያስመለሰለት በዚሁ ጊዜ ነው። አቡነ ተክለሃይማኖት በጵጵስናቸው ጊዜ ይኩኖ አምላክን ቀብ ተው አነገሡት ።

አቡነ ተክለሐይማኖት በጵጵስና ብዙ ዘመን ከቆዩ በኋላ የአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት አልፎ በአፄ ይግብአ ፅዮን ዘመን የግብፅ መንገድ ስለተከፈተ ይሁን ኢትዮጵያዊያን እራሳቸው ጳጳስ በመሾማ ቸው ቅር ብሏቸው ይሁን በግብፅ ሡልጣን ፈቃድ ከእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ተሹሞ አባ ዮሐንስ የሚባሉ ስለመጡ አቡነ ተክለሃይ ማኖት የጵጵስና ስራቸውን ለአዲሱ ጳጳስ አስረክበው የጵጵስናውን መሳሪያ መፅሐፍ ክህነቱን ቅብአቅዱሱን ሜሮንን አስረክበው ከጳጳስ ተሰናብተው ወደ ደብረ አስቦ የሄዱው ደብረሊባኖስ መጥተው በራሳ ቸው በገደሙት ገዳም ሲኖሩ በነሃሴ ሃያ አራት ቀን በሺህ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ዓ/ም በተወለዱ በመቶ አሥር አመት አረፉ ።

ወደአፄ ይኩኖ አምላክ የህይወት ታሪክ እንመለስ አፄ ይኩኖ አምላክ በተክለሃይማኖት እርዳታ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሆኑ ጊዜ በስሩ አሥር ንጉሶች ነበሩት እነሱም ጐጃም ንጋሽ ባህር ንጋሽ የሆነ በቀይባህር ባህረንጋሽ (የዳሞት ንጉሥ) ኪንዶ ንጋሽ አባ ንጋሽ ዘይላ ንጋሽ ፣ ዓሊታ ንጋሽ ፣ አናሪያ ንጋሽ ፣ እናሴ ንጋሽ ፣ ናግ ራን ንጋሽ ፣ ትግሬ ንጋሽ ፣ የእነዚህ ሃገሮች ንጉሶችና የባላባቶች መሣ ፍንት ወደምኒሊክ ዘር ለይኩኖ አምላክ የኢትዮጵያ ዘውድና ሁሉን መመለሱን አምነው እየመጡ ንጉሥነታቸውን እያፀደቁ ገፀበረከትና ግብሩን ሊያመጡ ቃል ገብተዋል ። ሌሎችም በየአውራጃው የሚገኙ ባላባቶች የአጼውን የጨዋ ጦር ሊቀበሉና ሥራት እንዲሆን ፈቅደዋል። በጊዜው የወላስማው ዘር እሺ ብሎ ነበር ነገር ግን በሚቀጥሉት ነገ ሥታት ላይ ማመፁንና ጦር በየጊዜው ማንሳቱን ወደፊት ባሉት ነገ ሥታት እጽፍላችኋለሁ ።

አፄ ይኩኖ አምላክ ዳጉ በሚባል በተንቤን ውስጥ ለአስራ ሶስት አመት እንደሸፈቱ ለአስራ አምስት አመት ገዝተው በተወለዱ በሰባ አንድ እድሜያቸው በሺህ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት (1277) ዓ/ም አረፉ በፋንታው ልጃቸው አግብአፅዮን ስመ መንግሥቱ ሰሎሞን ንጉሠ ነገ ሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ የአባቱም አፅም የነገሥታት አፅም በሚ ቀመጥበት በደጋ አስቀመጠው አግብአፅዮንም የአባቱን ምኞትና የሌ ሎችን ምክር ጥሶ ከግብፅች ባለስልጣኖች ስምምነት አድርጎ ሊቀጳጳስ እንዲላክለትና በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች እንደልባቸው እንዲኖሩ

ለንሰሙ ብሁ የሃይማኖት አስተማሪ እንዲገባ ፈቀደ ፡ በዚህ ውል ከፈጄት የሚባሉት አረቦች መግባት የጀመሩና ለአጼ አምደ ፅዮን መንግሥት እንቅፋት ለመሆን የሞከሩ በዚህ ምክንያት ስለገቡ ነበር ።

የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባ ዮሃንስ በስልጣናቸው ትእዛዝ አንድ መነኩሴ አባ ዮሃንስ ሊቀጳጳስ ለኢትዮጵያ ብለው ሾመው ላኳቸው (ስማቸው መኪሄ ነው)

በይኩኖ አምላክ ጊዜ የነበሩት ጳጳስ ኢትዮጵያዊ ተከለሃይማኖት ለአዲሱ መልቀቃቸው ፍትሃ ነገሥቱ ኢትዮጵያውያን ከመነኩሳቶቻቸው ጳጳስ አያሹሙ በሚለው ቃል የተነሳ ይሁን አይታወቅም በዚህ ምክንያት መነኩሳቱና ነገሥታቱ ቢስማሙ ሊቃውንቱና ደብተራው አሻፈረኝ ብለው ነበር ነገር ግን የንጉሡን ቅጣት በመፍራት ሁሉም በአፍ እሺ ብለው ተቀበሉ አጼ የግብአፅዮን ዘጠኝ አመት እንደገዛ ሞተ እሱንም ልጆቹ በእሌጋ ወስደው አስቀበሩት ።

በፋንታቸው አምስቱ ልጆቹ ሰንፈ አርእድ ህዝብ አስግድ አንድ አመት በየተራ ይንገሱ ብሎ አባታቸው ታዞ ኑሮ በየተራ አመት አመት ከገዙ በኋላ በመጨረሻ የአጼ ይኩኖ አምላክ ልጅ አጎታቸው ውድም አርእድ በዙፋኑ ሆኖ በሚያስተዳድርበት በአስራ አራተኛው ዘመን ተከለሃይማኖት አረፉ ውድም አርእድም አስራአምስት አመት ገዝቶ በ፲ ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ዓ/ም አረፈ ።

ከእርሱ ቀጥሎ ጀግናው ልጁ አምደፅዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ የአጼ አምደፅዮን ታሪክ ወደኋላ ተመልሰን በዘመነ መንግሥቱ የሠራውን ታሪክ ተመልከት ።

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

### ቀዳማዊ አጼ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት (የፅዮን ምሰሶ ማለት ነው)

አጼ አምደ ፅዮን የአጼ ይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ የአጼ ውድም አርዓድ ልጅ ናቸው ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥታቸውም ሰይፈ አርዓድ (ገብረ መስቀል የክርስትና ስማቸው ነው) ተብለው የነገሡ በሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ስምንት ዓመተ ምህረት ላይ ነው ።

አጼ አምደ ፅዮን በነገሡ በአንደኛው ዓመት የንጉሥነታቸውን ታሪክ የሚያውቁትንና የንጉሥነቱ ፀሐፊዎች የነበሩትን ሊቃውንት በመሪራስ ከጉል ጥሪ አደረጉ ይሄውም የዲት ቦዳ የምትባል የክርስቲያን ንጉሥና የሚጀልስን ዘር ለማጥፋት በነበረ ጊዜ በአክሱም ግምጃ ቤት የነበረውን የነገሥታት ታሪክ አጥፍተው ስለነበር እንደገና ለማጻፍና በየአውራጃውና በነገሥታቱ ስለሠሩት ገዳም አድባር ለማደል ነው እነ ዚህም ሊቃውንት የሚገኙበት ሃገር ቤተ ማል ፣ ቤተ ገራማል ፣ ቤተ ግእ ፣ ቤተ ዋልሳ ፣ ቤተ ሃማራ(አማራ ሳይንት) ቤተ እንጃ (እንጃ ቤት) ቤተ አሸር (ራስ ዳሽ) ቤተ ጉድረት ቤተ ለአዳት (ደጋሰጤፋ) ቤተ ሃጌ(ሃረርጌ) ቤተ ወንጂ (አፋሊ) ቤተቂሻር (ዘይላ ቤተ መሬ መሪሃቤቱ ናቸው በነዚህ ሃገሮች የሚገኙትን ሊቃውንትና ታሪክ አዋቂዎችን እስከመፅሃፋቸው ጥሪ ባደረጉ ጊዜ የቤተክህነት ባለሥልጣኖችና የደብረ ሊባኖስ እጨጌ አባ ፊልጶስ ደስ አልተሰኙበትም ጥሪ የተደረገላቸው ሊቃውንት የሚጠሩበት በባሬ ግቢ ደብተራ ወይም አዋቂ እንደሚባ ሰው ሆነው ከመፅሐፈ መነኮሳትና ከፍትሃ ነገሥት ከሲኖዶስ የራቁ እንደዚሁም ከግብፅ ጳጳስ መምጣት የለበትም እራሳችን እንቻል ይሉ ስለነበር ነው ሆኖም እነዚህ ሊቃውንት የቤተክህነቱ ሰው ሊያግዳ ቸው ስላልቻለ በአጼ አምደ ፅዮን ጥሪ መሰረት ተሰብስበው ለመጥ ፋት ቀርቦ የነበረውን የባቢንና የአክሱምን ነገሥታት ታሪክ ዝርዝር ከሚኒሊክ እስከ አጼ አምደፅዮን ዘመነ መንግሥት ድረስ ያለውን ታሪክ አዘጋጁ እነዚህም ሊቃውንት ከአለቆቻቸው ከመሪራስ ዘጉባኤና ከአስተናጋጆች ሌላ ፀሐፊዎች ብቻ አምስት መቶ ነበሩ የተጻፉትም መፅሐፈ ሱባዬ ከዳንግግ ደንገቦች ስለተገኘ አሥራ ሁለት ብቻ ተቀድ

ሌላ እንዳይቀጥሉ ተከለከለ የተከለከለበት ምክንያት በአብነልያኒም ለሕ
ዝብ እንዳይደርስ ተግቶ በለነበር ነው ይሄውም የያዘው ታሪክ ከአዳም
እስከ ኢትዮ (ማኩሳ) ድረስ ነው ሁለተኛው መጽሐፈ ሲራክ ከመጽሐፈ
ሰባኤ ጋር የተያያዘ ነው ከኢትዮ እስከ ዮዲት ድረስ የነገሡትን የሳ
ባንና የአክሱምን አጼዎች ታሪክና የዘር ሃረግ ያመለክታል አክሱማዊ
መረፉስ ሲራክ በዮዲት ጊዜ ወደ ምስር ተሰዶ ሲኖር ወደኑብያ ተመ
ልሶ በዚያው በኑብያ ስለጻፈው መጽሐፈ ሲራክ ወመጽሐፈ ሰባኤ
ተብሏል ። የነዚህን የሊቃውንት ጥሬ የሚታወቀው የቤተ ክህነት ባለሥ
ልጣኖች በአጼ አምደጽዮን ላይ አድማ አደረጉ በዚሁ ዘመን ከግብፅ
ተመርጠው የተላኩት ጳጳስ አባ ያዕቆብ በነገሩ ተቀምጠው ሳያ
ውቁ በየገዳማቱ ላሉት መነኮሳትና መምህራን ጥሬ አድርገው የደብረ
ሊባኖስን መምህር እጨጌ ፊልጶስን የኢጵስ ቆጶስነት ማእረግ ሰጥ
ተው በገበጣን (በሸዋ) ላይ ሾሙአቸው አባ ፊልጶስም ከተሰበሰቡት
መነኮሳት አሥሩ እንድ መርጠው አባ አኖሬዎስን ወረብ ፣ አባ አድሀኒ
ዳሞት ፣ ወላዋ አባ ኢዮስያስን ወንጂ(አፋሲ) አባ ማትያስን ቀላልጂ
ፊጣገር (ቡልጋ) አባ ዮሴፍን እናርያ (ሰሙ) አባ ታዴዎስን ያፋት
በረኸት ፣ አባ ገብረክርስቶስን ደባይ ዮረና(ሲዳሞ) አባ ቀውስጦስን
ጥጥ አምባ መሃገይ ፣ አባ ሳሙኤልን አሰቦት ወግግ ደዋር ፣ አባ መርቆ
ሬዎስን መራቤቴ ፣ አባ ኤዎስጣቴዎስን ወግዳና ምረት ሾመው እንዲያስተ
ምሩ አጼው የሚያጽፉትን የነገሥታት ታሪክና የጥንቱን አውደ
ነገሥት መጽሐፍ የሚማር ሁሉ ውግዝ ነው እያሉ ለሀዝቡ እንዲገል
ፁና እንዲያወግዙ ላኳቸው እንዲያውም እራሳቸው አባ ፊልጶስና አባ
አኖሬዎስ ብዙ መነኮሳት አስከትለው አጼ አምደ ፅዮን ባሉበት
ወደ ተጉለት ሄደው በድፍረት ይሄን ያክል የእንጨት ስርማንና
ቅጠል ቀራጭ ደብተራ የሰበሰበክ እግዚአብሔር የማይወደው ሥራ
ነው ብለው ተናገሯቸው አጼ አምደፅዮንም እጅ ጥሬ ያደረኩ
የአባቶቼ ታሪክ እንዳይጠፋ የአባቶቼን ነገሥታት ታሪክን ለማጻፍ
ነው እንጅ እናንተ እንደምትሉት አይደለም እሉ የነገሥታትን የአባ
ቶቹህን ታሪክ ብትፈልግ እኛን መጠየቅና ከእኛ ጋር መማከር እንጅ
እንዲህ የቤተክርስቲያንን ጠላቶችን እንዴት ጥሬ ታደርግላቸዋለህ
አሁንም የፃፉትን ሁሉ ብትቃጠል እስውግዝሃለሁ ሲሉ አባ አኖሬዎስ
ተናገሩ ስለዚህ አጼ አምደጽዮን ከመናደዳቸው የተነሳ በገዘፍ እንዲ
ትገረፍ አዘዙ ። በግርፋት የተነሳ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች እንደገመ
ረሙ የአባቱን ሚስትና እህቱን አግባ ከሃዲ ነው እያሉ አስወሩበት
መጽሐፍ እየጻፉ በየገዳማቱ የላኩ ሌላ ነገር ግን ውግዘቱም ሆነ
ሃሰተኛው ወሬ አጼ አምደ ፅዮንን ከክብረ መንግሥታቸው ሊያወር

ዳቸው አልቻለም እንዲያውም በምርኮትም ሆነ በመንፈሳዊ ሥራቸው ሁሉ አምላክ አልተለያቸውም እንዲያም አምስት መቶ ሊቃውንት ንጉሠ ነገሥቱ በአዘጋጁላቸው ሥፍራ በደብረ ዳን (ተጉለት) ሆነው በአጋሰስ ፈረስ ቆዳ እየተማከሩና እየተረዳዱ እንዱ የአንዱን መልስና እየተቀበሉ ለሶስት አመት ያክል በንጉሡ ነገሥቱ ትእዛዝ መጻሕፍቶችን ጽፈው ወረሱ የተጻፉት መጻሕፍቶች ከታወቁት ውስጥ ጥቂቶቹ፤

1ኛ/ ስነ ፍጥረት — ስለሰው ልጅና ስለእንስሳ ስለመላእክት ልዩነት

2ኛ/ መጽሐፈ ሱባኤ — ስለአምላክ ከሆናቶችና ነገሥታት

3ኛ/ መጽሐፍ ቢሬክ የአክሱምን ነገሥታት ታሪክ ከቶና ደንን ልደቶ የሚያስረዳ

4ኛ/ ሲራክ የጻፈው — መጽሐፈ ኢያሱኤድ — ስለድንጋይ ጥበብ በሰፊው የሚያመለክት

5ኛ/ አመደ ነገሥት — ስለ ሰው ወገይ፣ ስለአለምና ስለኮከብ የሚያሳውቅ

6ኛ/ መጽሐፈ ጥበብ — ስለቤት አሠራር በድንጋይና በእንጨት ያሉትን ዘዴ የሚያመለክት

7ኛ/ ቀኖና ዘሱባኤ — ስለሲኦ፣ ስለነፍስ፣ ስለመንፈስ፣ አንድ ነትና ልዩነት ስለአምላክ ሰው መሆን ሰው በአምላኩ እንደከበረ የሚያስረዳ

8ኛ/ መጽሐፈ መናፍስት — በሰው ልጅ የሚሰለጥኑትን ጠባዮች የሚያመለክት

9ኛ/ ክብረ ነገሥትና ሌሎችም ነበሩ መጽሐፈ ሱባኤ አስራ ሁለት ብቻ ሲጻፍ ሌሎች (41) አርባ አንድ ቅጅ ለየአንዳንዱ በግእዝና በአረብ ቋንቋ ተቀድቶ ወደየንጉሣዊቱና በየአውራጃው ለሚገኙት ሊቃውንት በእጁ አምደ ፅዮን ፈቃድና በመራራስ ወንጌሉ ተልኩዋል ንግሥቱ ግን ለጊዜው እጁውን በመፍራት ተረከበው የጻፉትን ቃል በማክበር አቃቀራቸዋል። ይህን የመሰለ የሊቃውንት ጥረ እጁ አምደ ፅዮን ከአዘጋጁና እጽፈው ከአስወጡሩ በኋላ ልዩ ልዩ የክብር ስምና የወርቅ ካባ እያሸለሙ ሊቃውንቱን ወደየሃገራቸው ከመጽሐፎቻቸው ጋር ላኳቸው።

የኢዜ አምደ ፅዮንን ከወላስሞች ጋር ያደረጉትን የጦርነት ታሪክ ከመረዳታችን በፊት ወላስሞች ወላስማ ማለት እነማን ከማን ሃገር እንደመጡና ከየት ምድር እንደተቀመጡ ማወቅ ያስፈልጋል ።

በስድስት መቶ ሃያ (620) ዓመተ ምሀረት የእስላሞች ነቢይ መሃመድ በእስያ ሃገሮች ተነሳ መካከለኛውን ምስራቅ ሃገሮች ገለባበጠና ያዘ በበላያቸውም ነገሠ የእስላም ሃይማኖቱንም አስፋፋ የኢትዮጵያን ህዝብና በህዝብ ላይ የነገሡትን ነገሥታት ግን አልነካም እንዲያውም አበሻን አትንኩ ሲል አስተምሯል ይሄውም በእነሱም የነገሡት ነገሥታት ከእስያ ተሰደው የሚመጡትን የክርስቲያንና የእስላምን ሃይማኖት ተካታዮች በክብር ከመቀበል በቀር እንገላታዋቸውና አስረዋቸው አያውቁም እንደልባቸው ይወጡና ይገቡ የፈቀዱትንም ሃይማኖት ያስተምሩ ነበር እንጅ እንደእስያና እንደ አውሮፓ ህዝብ አላስታ ያቸውም መሃመድን መልእክተኞችን በክብር አስተናግደው የፈለገው እንዲቀመጥ ያስፈለገ በፈለገ ሰዓት ወደሃገሩ እንዲመለስ ብለው ስለ አስተናገዳቸው ነቢዩ መሃመድ ስለተደረገለት ውለታ ከልብ የሃበሻን ሰው ይወድና ያከብር ነበር ስለዚህ ነው የእስላም ንጉሥ የአላህነቢይ መሃመድ በመዲና ሃያ ሶስት አመት ነገሠና ሞተ ከእርሱ ቀጥሎ አቡ ጋዝ አሚር አቡበከር ሰባት ሁለት አመት ነገሠ ቀጥሎ ኡመር አብን አልሃጠብ አስር አመት ነገሠ እሱም ኢየሩሳሌምና ግብፅን ያዘ ከእርሱ ቀጥሎ ኡስማን አብንአፋን ነገሠ በኡስማን ዘመን መንግሥት በኢትዮጵያ ወስጥ የሚገኙ የመርዊና የከሰሉ የበሰሉም ትግሮች ሰለሙ እስከንድርያንም ያዘ እርሱም በነገሠ በአስራ ዘጠኝ አመት ሞተ ከእርሱ ቀጥሎ በስድስት መቶ ሰባ አራት (674) አመተ ምህረት አሊ ነገሠ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር የማይስማሙ ሻዋርጂን ወርጂ ከንኸሪዋን የሚባሉ ነገዶች ነበሩን አሊ ፈጃቸው ሶስት ሰዎች ብቻ ሲያመልጡ ሌሎችን አራት ሺህ ሰራዊት አረዳቸው ገደላቸው እንዚያ ያመለጡ ሶስት ሰዎን ግን ከንኸረዋን ወገናቸው ሄደው ተሸሽገው ሳለ አባትና ወንድሙን ወገኖቹን ያስቀባት አሊ የገደለባት መልክ መልካም ቆንጆ ነበረች ስምዋም ቀጣሚት ትባላለች እኔን የሚያገባ የአባቴንና የወንድሜን ገዳዮች አልአሊሰንና አሊን መአውያንን የሚገድል ነው አለች በዚህን ጊዜ ሶስት ሰዎች ከጦርነት አምልጠው የነበሩት ሶስቱን ሊገድሉ ሄዱ የመሃመድ ታላቅ አጎቴ የነበረውን አልአሊሰምን ሊገድል የሄደው አሳቡቶ ገድሎ ተይዞ አልአሊስም ምስርን ይዞ ስለነበር በካይሮ ተሰቀለ መአውያን ሊገድል የሄደው አቁስሎ ሳይገድለው ቀረና ተይዞ ተደብድቦ ሞተ ይህ መአውያን የመሃመድ ታላቅ አጎቴ ነበረ

ወደ አሲ. የሄደው አብዱራሕማን ግን በመርከብ ጦር ወጋውና አሲ በሁለተኛው ቀን ሞተ ዘመነ መንግሥቱም አራት አመት ከዘጠኝ ወር ነበረ ። አብዱራሕማን ተይዞ ተሰቀለ ይባላል ። የአብዱራሕማን ጉዳዮች ኸዋርጂን የዛሬዎች ወርጂ ነበሩና አሲ ከሞተ በኋላ በአረብ ሃገር ለመቀመጥ ስለፈሩ ከእስያ ተነስተው ወደኢትዮጵያ ገቡ የኢትዮጵያ መንግሥትም በሥር ሆንና እንገዛለን ስላለ ከሩጂ ወይም ቀሩሲ ከረዥት ተብለው በፈለጉት ሃገር እንዲቀመጡ ተፈቀደላቸው ግማሾቹ ከዘለሉ ጉዳዮች ጋር ግማሾች በግልፅ ወደይፋት አለቁ ይፋት የተባለበት በድብቅ ሳይሆን በይፋ እንደልባቸው እንዲኖሩ ከለተፈቀደላቸው የተቀመጡበትን ሃገር ይፋት አሉት ይባላል ። ሃይማኖታቸው ግን ክርስቲያን ወይም ንፁህ እስላም ስላልሆነ ወላሰማ ተብሉ ወላሰማ ማለት እስላም ያልሆነ ማለት ነው እንዲሁም ወላሰሞች ቋንቋቸው ግእዝና አረብ የተቀላቀለበት የአርጎባ ቋንቋ ይባላል የወላስማ የመጀመሪያው መሪና አለቃ ማህሙድን ይባላል ይኸም ወላስማ የሚባለው ስም በክርስቲያንና በእስላሙ መካከል ሆኖ የመተባበርና የኢትዮጵያን አንድነት የሚገልፅ የሚያደርግ ስም ሆኖ ለሰባት መቶ አመታት እስከ አጼ አምደፅዮን ዘመነ መንግሥት ድረስ የቆየ ነበር በአጼ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ከረሽት ወይም ቁርሱ የሚባሉ የእስላም ህዝብ አማሮች ከአረብ አገር ተነስተው መጥተው በዘይላን በቀይባህር በይፋት ከሚገኙት በመልክ ከሚመሳሰሉት በጋብቻም ሆነ በአንዳንድ የማታለያ ዘዴ ከነዋሪው ህዝብ ጋር ተቀላቅለው በዚህን ጊዜ በክርስቲያን መንግሥት ላይ የሚነሳ ጥና ጠላት ይፈልጉ ጀመር እንዚህ ከረሺት የሚባሉ የሰፈሩባቸው ሃገሮች ደዋር ባሌ ፣ ሻርካ ፣ ሃርላ ፣ ጀድያ ፣ ባሌ ሃድያ ፣ ኢፋል ታረሃ ፣ ገድኢት ፣ አዳል ሁባት ፣ አርባቢ ሃርጋያ በይብልጥ ግን የተቀመጡ ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር ጠዋትና ማታ በሸመት በከብር ከሚጨቃጨቀው በይፋት ከሚገኘው ከወላስማው ዘር ጋር ነው ። እንዚህ ከረሽት ወይም ቁርሱ የሚባሉት የስላም ነጋዶች ከመጣቢታቸው በፊት በኢትዮጵያ ሰፈ ግዛት ውስጥ ምስራቅ ምእራብ ሰሜንና ደቡብ የሚገኙት ነጋዶች በራሳቸው ባላባት እየተገዙ ባላባቱም ለንጉሡ ነገሥት የሚገባውን እጅ መንሻ እያመጣ በሰላም እንደአንድ ጊዜም እያመፀ አለገብርም እያለ ይኖር ነበር አሁን በአምደ ፅዮን ዘመነ መንግሥት ግን የእስላሞች ሃይል በምስራቅ ኢትዮጵያ በየመን በሰሜን በኩል በግብፅ በሲቢያ በተንነበት ዘመን ወደኢትዮጵያም የእስላም አስተማሪ እየላከ ውስጥ ውስጡን እርዳታ እየላከ ባላባቶቹን በክርስቲያን መንግሥት ላይ እንዲያምፁ ያበረታታ ነበር ነገር ግን አጼ አምደ ፅዮን የኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት ተብለው በአባቶቻቸው ዙፋን ላይ ከተቀመጡ ጀምሮ

እንተባበርም ያሉትን የወላጆች ዘሮችንና የእሳልን ባላባቶች ቸል ብለው በሰላም መተው አልሆነላቸውም እንጂ አጠገባቸው ያሉትን የራሳቸ ውን ተገንጥ በሩቅ ሃገር በግብፅ ያሉትን የራሳቸውን ተገንጥ በሩቅ ሃገር በግብፅ ያሉትን የእስላም ባለሥልጣኖች የእስክንድርያን ክርስቲ ያኖች አጠቃቸው ቤተ ክርስቲያኖቻቸውንም አፈረሱት የሚል ወሬ ሲሰሙ ክርስቲያኖችን ማጥቃት መግደል ያልተዋቸው ያፈረሷቸውንን ቤተ ክርስቲያንንም መልሳችሁ ያልሠራችሁ እንደሆነ እኛም የናንተን መስጊድ አጠፋ ነው የማደርገው የአባይንም ውሃ አስገድቤ ወደ ሠሃራ በረሃ እንዲገባ አደርገዋለሁ እያሉ በግብፅ ለሚገኙት ባለሥል ጣኖች ደብዳቤ ይልኩ ነበር ከአጼ አምደፅዮን በፊት ጀምሮ ወንጌላዊ ማቴዎስ ኑቢያን አስተምሮ ክርስቲያን አድርጎቸው ስለነበር ኑብያ በኢትዮጵያ ስር ሆና የራሱ ንጉሥ ስለነበረው አባይን ለመገደብ በየጊዜው ከንጉሡ ንጉሠ ፈቃድ ይጠብቅ ነበር ስለዚህ የግብፅ ህዝብ ባለሥልጣኖች በየጊዜው ይፈሩና ከኢትዮጵያ ንጉሡ ንጉሠ የሚተላለ ፈውን ትእዛዝ በማክበር እሽ ብለው ይፈፅሙ ነበር ነገር ግን ውስጥ ውስጡን በየጊዜው የኢትዮጵያን ህዝብ አንድ ነት ለመበታተን ያላደ ረጉት ጥረት አልነበረም ይሄውም በሃይማኖት እየገቡ ሲያጣሉት ኖረ ዋል ።

ስለዚህ በአጼ አምደፅዮን ዘመን መንግሥት በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል የማቋቋም ሆነ የሃይማኖቱ ጠብ እየከረረ ሄደ እንዲሁም ባላባቶች ውስጥ ውስጡን የግብፅንና የአረብን እገዛ ድጋፍ በማግኘታቸው ለክርስቲያን መንግሥት እንገዛም እሉ ጠባቸውንም ከቀን-ወደቀን ያባብሱ ጀመር ከንጉሡ ንጉሥ ዘንድ ወደምሥራቁና ወደኢፋትሳሉም የሚላኩትን መልእክተኞች እያያዙ ያንገላቷቸው ጀመር ሌላም እንደዚሁ የአጼ አምደፅዮን መልእክተኛ በዛሬ አድርጎ ለማ ለፍ ሲሞክር የአዳሉ ባላባት ይዞ እስር ለይፋቱ ባላባት ለሃቅ አድዲን ላከለት እርሱም ለአጼ አምደፅዮን አልገዛም ማለቱን ለመግለፅ ነው የይፋቱ ባላባት ደግሞ ብዙ ስቃይ በእሥረኛው ላይ ሲፈጽምበት ቆይቶ ሰልፍ ወደእጁ ላከው ።

በዚህን ጊዜ አጼ አምደፅዮን ከልክ ያለፈ ተናደዱና በያሉ ያለ ውን ጭፍራ ሠራዊት ሳይሰበስቡ በጀህ ሰለት መቶ ጫመታ ምግሬት ላይ ከተገለፁት ወታደሮች ጉዞ ተጀመረ በደረሱም ጊዜ ጭፍራ ጦር ሠራ ዊቱን በየፈናው ልከው ከእጋጠማቸው ጦር ጋር እየተዋጉ ዘረፋም ምርኮም ጀመሩ በመጨረሻም የአዳልና የይፋት ጦር ባንድነት በባላ ባቱ በሃቅ አድ ዲንና በወንድሙ በደራደር እየተመራ ተሰብስቦ በን

ንጉሡ ነገሥቱ ጦር ላይ ሴሊት ሊንጋ አቅራቢያ አዶጋ ጥሎ ለመፍጀት ንጉሥም በንጉሡ ነገሥቱ ሠፈር ይረስ ነገር ግን የእስላሞች ጦር መምጣት በተሰማ ጊዜ ሁሉም የጭዋ ጦር ሠራዊት ለጦርነት ከእንቅልፉ ነቅቶ ይዋጋ ጀመር ።

ጀግናው ንጉሡ ነገሥት አጼ አምደጽዮን በፈረስ ላይ ሆነው ሲዋጉ የእስላሞችን የጦር አለቃ እስላሞችን ለማነቃቃት እየመራ ከፊት ሆኖ ሲዋጋ አይተው ጦራቸውን ሰብቀው ቢወረውሩት በደረቱ አልፎ የጦር ጫፍ በጫንቃው ላይ ወጣ ተዋጊውም ደራዳር ከፈረሱ ላይ ወድቆ ባለ የሁለቱም ወገን ፈረስ እየረገጠው ሄደ በዚህን ጊዜ እስላሞች የደራዳርን መውደቅና መሞት ሲያዩ በፍርሃትና ይሸሹ ጀመር የአጼው ሠራዊት ወደፊት እየሮጠ እያባረረ ይፈጃቸው ጀመር ።

የቀረው ወደኋላው እየሸሸ ማምለጥ ያቃተው ምህረት እየለመነ እጁን ሰጠ ዋናው የእስላሞች መሪና ባላባት ሃቅ አድዲን ተማረከና ወደንጉሡ ነገሥቱ አመጡትና ታሰረ በእርሱ ምትክ ለይፋትና ለፈጣገር ግዛት የወንድሙን ልጅ ሰበር አድን ሹመው የወላስማነቱን ማዕቅን ሸልመው በደህና ወደተገሩለት ዳት ተመለሱ ። ከዚያም እስረኛው ሃቅ አድዲን በግዞት እንዲኖር ወደ ዳንጋ ተላከ (ጉጃም ዳንግላ) ከየጉማውና ከየንጉዴ የመጣውን የጨዋ ጦር እየሸኙ በየሃገሩ ላኩት ከትግሬ በመላክ ባህር የሚታዘዘው የባለቤታቸው የገንን ሳባ ሠራዊት ከአካለ ጉዛይ የመጣው ግን በምድረ ከብድ አዋሽ በሚፈስበት ሰፈ ምድር ባለርስት አድርገው አስቀመጧቸው ስማቸውንም ባለቤታቸው ግራባልቲዎች ስለነበረች ግራኚ ተባሉ ጉርአ ከሚባል ሃገር ስለመጡ ጉራኚ ተባሉ የሚሉ አሉ ግን ዋናው ግራ (ጉራኚ የጉርአዎች ሃገር ግራኚ የግራሰዎች ሃገር አድሰኚ የአዲሶች ሃገር ማለት (ግራ ተብሎ ግራኚ ሃረር ተብሎ ሃረሪኚ ግራር ተብሎ ግራሪኚ አዲስ አድሰኚ ከሶ ከሰኚ እቴ እቴኚ እንደሚባለው ነው (ኚ---ብዙሐ)ኚ ማለት የቁልምጫ ስም እትዮ የሚለው እቴኚ ይባላል ።

አጼ አምደጽዮን ከሰብረ አድ ዲንጋር ያደረጉት ጦርነት

አጼ አምደጽዮን ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአስራ ሰንተኛው አመት ላይ ሰብረዲን ወይም ሰብር አድዲን የሚባል የወላስማ ንጉሥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እሆናለሁ ። አብያተ ክርስቲያኑንም ሁሉ ወደእስልምና የይማናት መስጊድ በቁራን ህግ አስተዳድረዋለሁ ብሎ ተነሳና ወደክርስቲያኖች ሄዶ ክርስቲያኖችን መግደል የተረፉትንም

ሴቱን ወንዱን መማረክ፤ ጀመረ ከዚያም ክርስቲያኖቹ ንጉሦች እንደ
ሚያደርጉት በመንዱ በሃድያ ዳሞት በባሌ በፈጣጋር በጉራግም ዳንጋ
በየነቱ ዋጅዋ በትግሬ ሃገሮች ሁሉ መግፍንትን እየደለደለ ይዘጋጅ ጀመር
የዚህን ወሬ ንጉሡ ንጉሥቱ እምዶለዮን በሰሙ ጊዜ በጣም ተናደዱ እንደ
ዚህ ሲሉ ላኩበት ይህ የምንሰማው እውነት ነውን ዜቶ ክርስቲያኑን
እያቃጠልኩ ክርስቲያኖቹን መግደሌህና መማረክህ እውነት ነው
ከዚህ ቀደም ወንድምህን የቀ እድሊን መልክተኞዩን ትእዛንተይ የማ
ባለውን አንድ ታናሽ አገልጋይ ማርኮ ቢወስድ ያደረግሁትን የወንድ
ምህን ደራዳርን እኔ ራሴ በጦር ግንባር መግደሌን አታውቅምን አሁንም
እስር ክርስቲያን ገድለህ እንደሆን እኔ ያንተን [illegible] እገድልሃለሁ
ሰብረዲን (ሰብር አድዲን) ከመልእክተኞቹ ይህን በሰማ ጊዜ እንደዚህ
ሲል ወደ እምደ ፅዮን ላከ በጦር በጉራዱ በሰይፍ በቀስት የሚዋጋ
ከአንተ የሚበልጥ ሠራዊት አለኝ ስለዚህ መግጓዱ ከፍት ነውና ናና
ጦርነት እንግጠም አንተ ያልመጣህ እንደሆነ ግን እኔ እመጣለሁ ።

ሰብረዲንም ይህን ቃል መልስ ከላከ ወዲህ የጦር ሠራዊቱንና
ሹማምንቱን እያደላደለ ለጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ከዚያም ከግዛቱ
የሚገኙትን ወንዶችንና አዋቂዎችን ሰበሰበና ሄደን ከኢትዮጵያ ንጉሠ
ነገሥት ጋር እንዋጋ ወይስ እንቅር እስቲ ንገሩኝ ብሎ ጠየቃቸው በዚ
ህን ጊዜ አንዱ ከመካከላቸው ከዚህ ቀደም አሙኑ ሰላዲን የሚባለው
የሃድያው ንጉሥ ለንጉሡ ንጉሠ ነገሥት ለአጼ እምደፅዮን ገብረሕት እያቀረበ
ለት ወደኋላም ያለውን የሃድያን ንጉሥ አሙኑን እስከሠራዊቱ አዋ
ፍቶ ሌላ ንጉሥ ዘለባ የሚባል እንግሶ ወደቤቱ እንደተመለሰ ሁሉ
እየአወቀ አሁንም ይህ ወንዳይ የክርስቲያኖች መንግሥት አልቆ
ለእኛ ለእስላሞች ተሰጥቷል ። ስለዚህ ውጣና ከክርስቲያኑ ንጉሠ ነገ
ሥት ጋር ተዋጋ ታሸንፈዋለህ ከነህዝቡም ትገዛዋለህ እንተም በምላ
ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለህ ትንግሣለህ ብሎ ነገረው የቀሩትም
ወንዶችም ይህንን ቃል አፀደቁ ።

ስለዚህ ለሰብረዲን የጦር ሰራዊቱን አምስት ላይ ከፍሎ እንዱን
ወደአማራ አንዱን ወደ አንጐት ልኮ ሁሉቱን በፈትና በኋላ እሱ
በመሃል ሆኖ እጼው ወደአለበት ወደተጕለት አመራ ይህን ሁሉ አጼ
አምደፅዮን በሰሙ ጊዜ ሸዋ ረአይ ፣ የንገስ አይበገባ ፣ እንጎትይ ፣ ወቅ
እድንተይ ፣ ዋጎትትንይ ፣ አምላክ ፅናህ ፣ አውራ መንዘል ፣ ሊቀ አፍራስ
ዘዋሚን ፣ የእከል ጋዳ ፣ ሊቀ አፍራስ ዘበምውድምአላ ፣ ሊቃውንቱ ሃራ
ውን (የጦር ሹማምንን) ለጦርነት ተዘጋጁ ብሎ አዘዛቸው ከዚያም ከግምጃ
ቤቱ ወርቁን ብሩን ሽልማቱን ሁሉ አስወጥቶ ሁሉንም ከታናሽ እስከ

ታጣቂ በስሞታ አስደስቷቸው ከዚህ በኋላ የካቲት ሃያ አራት ቀን በ፲፱ ሰባት መቶ አስራ ስድስት ዓመተ ምህረት እግዚአብሔር ድልን ሰጥቶ ያርዳችሁ ብለው ወደ ጦርነቱ ላኳቸው እነሱም ወደጦርነቱ በደስታ ሄደው ተኩላ የሚባሉት ትንንሽ የጦር ክፍሎች ወደ ስብሪዳን ሃገር ደረሱና ውጊያውን ጀምረው በእግዚአብሔር እርዳታ አሸነፉት በኋላም ዋናው የጦር ሠራዊት መጥቶ ወደ እስኪገባ ድረስ የጦር ሠራ ዊቶች እየተከታተሉ ሲዋጉት በመጨረሻ ስብሪዳን በሌላ መንገድ አምልጧቸው ሸሸ እነሱም ከተማውን አፈራርሰው ሰውንም ሁሉ ገድለውበት ከስብሪዳን ቤት ብዙ ወርቅና ብር ወደአረብ ሃገር የሚላክ የከበረ ድንጋይ ሉል ከአረብ ሃገር የተላከለት ልብስ አግኝተው ሁሉ ንም ዘርፈው ሲጨርሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ እንደዚህ ብለው የደስታ ቃል ላኩ ንጉሠ ነገሥት ዘለዓለም ደስ ይበልዎ በመንግሥትዎና በዘፃ ብዎ ላይ የተነሳውን ጠላትዎን አሸንፈነው ከጠፋው በቀር የቀረውን ማማሹን ስንገድል ማማሹን ሚስቶቹንና ልጆቹን ማረክናቸው በቤቱ ውስጥ የተገኘውን የከበረ ድንጋይ እንቁና አልማዝ ወርቅና ብር ልዩ ልዩ የጌጥና የሽልማት ልብስ ብዙ የጦር መሣሪያንና ብረት ለላም መቁጠር የማይቻል መሣሪያ ሁሉ ዘረፍን ። ጀከምን እስከሚችሉ ድረስ ለሸጉራ(ሸንኮራ) ለዘብር ለዚኃ አገር ሰዎች ሰጠናቸው ስብሪዳን ግን በሌላ መንገድ አምልጦ ሸሸ ።

አጼ አምደጽዮን የስብሪዳንን ማምለጥ በሰሙ ጊዜ ታቦቱ ወደ አለበት ድንኳን ገብተው የመሠዊያውን መንበር በእጃቸው ይዘው መድኃኒዓለም ክርስቶስ እንደዚህ ሲሉ ፀለዩ የልቤን ሐሣብ ስጥኝ በአንደበቴ የምለምንህን አትከልክለኝ በሃጢአቴ ምክንያት የምህረትህን በር አትዝጋብኝ ነገር ግን በስምህና በበጎችህ ላይ የተነሳውን ይህን ጠላ ታችን እዋጋው ዘንድ መንገድ የሚመራኝ ደግን መልአክህን ላክልኝ ይህን ፀልየው ሲጨርሱ የታቦት ልብስ ለብሰው ለቤተ እግዚአብሔር ሰጡና ወደውጭ ወጡ ከዚያ ዳሞት ፣ ሰቀልት ፣ ጐንደር ፣ ሃድያ አይደር የሚባሉትን የፈረሰኛና የእግረኛ ወታደሮች በጠብና በውጊያ ጊዜ ለጀግንነታቸው ምሳሌ የሌላቸውን አለቆቻቸውን ፀጋ ክርስቶስን መሪ አድርገው ወደ ቢጌምድር ሄደው ከሰሜን ወገራ ከወለቃይት ከፀገዴ ሰዎች ጋር እንዲዋጉ ላኳቸው ። እነዚህ ሃገሮች ቀድሞ በንጉሡ ካሌብ ጊዜ ክርስቲያን የነበሩ ኋላ ግን በአጼው ላይ ጠላት መንሳቱን ሲሰሙ የሸፈቱና ሃይማኖታቸውን ያጠቁ ስለነበሩ እነሱን እንዲወጉ ላኳቸው ባንድ ወገን ደግሞ ጎድምን የሚባል ከሃዲ ስለሸፈተ የቀን ፀሐይ መሌ ንንት የዋግ ሹም የላስና ሹም የሰሜት ሹም ከበብ ማዕከላ ተዋዝት ፣ ማእከለ ባህር ፣ የሚባሉትን ተዋጉ ብለው ላኳቸው ።

አጼ አምደፅዮን ከርሳቸው ጋር ያሉትን ሠራዊታቸውን ይዘው መጋቢት ስድስት ቀን 1316 ዓ/ም ላይ ተጉዘው ሃገ ደዋሮ ደረሱ የዚ ሀች ሃገር ገገር ስሙ ሃይደራ ይባላል እርሱም አቶን ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር አድርጎ ልቡን ከነሰብረዲን ጋር ያደረገ ነው አስቀድሞ አጼ አምደፅዮን ወደእኔ ቢመጣ አንተ ከነሠራዊትህ መጥተህ ወደአንተ ቢመጣ ከነሠራዊቱ መጥቼ አብረን ሆነን ወግተን እናጠፋዋለን ብሎ ከሰብረዲን ጋር ተስማምቶ ነበር ።

አጼ አምደጽዮን ግን ከደዋሮ አልፎ የማያ ጉማዎች ወደሚኖሩ ቤት ሰማርሀ ሃገር ደረሰ በዚሁ ሃገር በሚያዝያ ሃያ ስምንት ቀን (28) በሰላም የፋሲካን በዓል አከበሩ በዚሁ ዘማር አገር ውስጥ ልዩ ስፈር ጳልሜጳ ዘማር ያ ብለው ንግስቲቱን መንገግን ጥለው ሃያ አምስት ፈረሰኛ ጦር ብቻ ይዘው ተሰውረው በንድ ወገን ሲዋጉ ቆዩ ሠራዊቱም ንጉሡ ነገሥቱን አጥተው የት ሄዱ እንገዲህ ምን ይሻለናል ብለው ሲጨ ነቁ አጼ አምደ ፅዮን ሲዋጉ ውለው የማረኩትን ምርኮ እንደያዙ ወደ ጳልሜጳ ተመለሱ ሠራዊቱም በሄዱበት ሲዋጉ ውለው ወደሠፈር ገቡትው ከንጉሣቸው ተገናኙትው እንደያምን እንደተዋጉ እንደሴት እንዳ ሸንቶሴት ተረከሰት ሰብረዲንም አጼውና ሠራዊቱ መገናኘቱን በሰማ ጊዜ ተጨንቀ በዚያን ጊዜ ወደንግሥቲቱ እንደዚህ ብሎ ላከ በጊታዩ በንጉሡ ነገሥቱ ላይ በደልሁ ከቶ ሠራሁ አሁን ግን በሌላ በባእድ እጅ ከምጠፋት በጊታዩ እጅ ብወድቅ ይሻለኛልና የፈቀደውን ያድርገኝ እኔ ግን መምጣቴ ነው ንግሥቲቱ በብረዲን የላከውን ይዛ ለአጼ እምደፅዮን ነገረችው አጼ አምደፅዮን ግን በሰሙ ጊዜ ከቁጣው አልበ ረዱምና እንደዚህ ብለሽ ላኪበት ብለው ነገሯት ብትመጣም ብትቀርም እያሳዝነንም ሩቅ አረብ ሃገር ብትሄድ በእግዚአብሔር ሃይል እከተል ሃለሁ ወደ ጉድጓድ ብትገባ ብትሸሸግ አንተን ሳላጠፋ ወደሃገሬ አል መለስም ይላሉ መልእክት በሰማ ጊዜ ሰብረዲን ወደ አጼው መጣና በፊታቸው ቆመ በዚህን ጊዜ አጼ አምደፅዮን ወቀሳውን እንደዚህ ሲል ጀመረ ለምንድነው እንደዚህ ያለ ሥራ መሥራትህ ለኔ ያመጣ ኸውን ግብርና ገፀበረከት ለባርቾህ አደልከው የጌንም የራሴን ገንዘብ ለድሆች የሰጠሁትን ብርና ወርቅ ቀማህ ከእኔ ጋር የሚነግዱትን የባህር ነጋዴዎች አሥረህ ከሁሉ የበለጠ ደግሞ ዲያብሎስ ፈጣሪውን ለመሆን እንደተመኘ ዙፋኔን ተመኘኸው ሰብረዲን ይህን ቃል ከአ ጼው ሲሰማ ከፍርሃቱ የተነሳ መልስ አጣ ነገር ግን ጌታዩ ንጉሥ ሆይ ደስ የሚልህን አድርግብኝ አለ በዚያን ጊዜ በአጼው ግራና ቀኝ ያሉት እየቀንሱ ይህ ሊሞት ይገባዋል አብያተ ክርስቲያናትን ያቃጠለ ክርስ

ቲያኖችን የገደለ የተረፉትንም ማርኮ እያሰለመ ከዚያም ወደከፍተኛ ተራራ ወደመንግሥት ለመውጣት አሰበ እያሉ ግግሾቹ በሰይፍ ተመትቶ ግግሾቹ በድንጋይ ተወግሮ ግግሾቹ በእሳት ተቃጥሎ ይሙት እሁንም የመጣው በሥራችን ሊያፈዝ ነው እንጅ እጼ ሆይ ለደህንነትና ለመግባት አልመጣም እያሉ ተናገሩ በዚያን ጊዜ ከመንበ በመቀነቱ ቢፈትሹ ብዙ ስራሰር መድሃኒት ተገኘ በዚያን ጊዜ ንጉሡ በእውነት ይህ ሁሉ ከእጇ ያድንሃልን ብለው ጠየቁትና ሁለት እጁን በሰ ንሰለት አስሩት እንጅ አይገደል ብለው አዘዙ በዚሁም ቀን የደዋሮ ንጉሥ ሃይደራ ገበት የነበረው ሁሉ ለወንድሙ ለግማልዲን (ገማል አድዲን) ከሽልማት ጋር ተሰጠው ።

ከዚህ በኋላ አዳልና ዋራ የሚባሉ ብዙ ሀገሮች ቀባብረው እንደዚህ ብለው መጡ የክርስቲያኑ ንጉሥ ንጉሥት እርሱ ከአገራችን ላይ መጣ እኛ ሄደን እንውጋው ከአለበት ሄደን የወጋነው እንደሆን በኛ ፍርሃት ደንግጦ ወደሃገሩ ይመለሳል ዝም ያልነው እንደሆነ ግን ወደ ሃገራችን መጥቶ ያጠፋናል ይህን ካሉ በኋላ አዳሎች ወደ ደፋት መጥተው የእጼው ሠራዊት በተኙበት ሌሊት ያርሰው ትንሽ ሰው ገድለው ተመለሱ እንዚህም ለብቻቸው የነበሩ ናቸው ስለዚህ ባልጠረጠሩበት ሰዓት መጥተው ገድለው ተመለሱ ቀጥሎም በሌላው ቀን መጥተው የእጼውን የጭፍ ጦር ሠራዊት ገጥመው ብዙ ሰው ፈጁ ብዙ ወርቅና ብዙ ከብት ዘርፈው ሄዱ ከዚያም ሶስተኛ ጊዜ ከሁሉቀድሞው የበለጠ በርክት ያለ ሌሊት መጥተው ከእጼው ጦር ሠራዊት ጋር ገጥመው ድንኳኑን ገለባብጠው ብዙ እቃ ዘረፉ ሲንጋ የእጼ አምደጽዮን ሠራዊት ተከታትለው ደረሱባቸውና ተዋግተው ብዙ ሰው ጨረሱባቸው የተማረከውን እቃና ድንኳን ሁሉ አስመልሰው በደስታ ወደ እጼው ሠፈር ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ በማግሥቱ ሹማምንቱና የጦር አለቆች ተሰብስበው ወደ እጼ አምደጽዮን መጡና እንዲህ እግዚአብሔር ጠላቶችን ከእግር በታች ከአስገዛልዎ አሁን ወደሃገራችን እንመለስ የክረምት ጊዜውም እነሆ መግባቱ ነው ስለዚህ በዚህ በባዕድ ሃገር እንዳንጠፋ ወደ አገራችን እንመለስ አሏቸው እጼ አምደጽዮንንም ይህን የመሰለውን ንግግር ሁለተኛ በፊቴ እንዳትናገሩ እኔ የመጣው ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኜ እንዚህ ባላባቶች እየተዋጉኝ ምንም ቢሆን ወደሃገሬ አልመለስም ። በዚህን ጊዜ ግማልዲን (ገማል አድዲን) ብዙ ገፀ በረከት ይዞ ወደ እጼ አምደጽዮን መጣና ጌታዩ ንጉሤ ሆይ እንዲህ ወደእኔ

ርዎ ይመስሉ እኔን ለዚህ አገር ከሾሙኝና ከእነገሱኝ ፈቃድዎን ሁሉ እፈጽማለሁ እንግዲህ አገሩ ሁሉ ጠፍቶአል የተረፈውን እያጥፉት እስላሞች ሁሉ እኔም ጭምር አሁን የእስም ባሮች ነን አለው በዚህን ጊዜ አምደጽዮን እንደዚህ ሲሉ በቁጣ ቃል መለሱለት እንዚህ በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ የማያምኑ የውሾና የአባብ ልጆች እየነበሱኝ ወደሃገሬ አልመለስም አዱል ሃገር ሳልገባ ወደሃገሬ ብመለስ እዚህ ያለውም የሌለውም እንደወለደችኝ እናቴ ሴት ይበለኝ ከዚህ በኋላ በስኔ ሰባት ቀን ከጭፍ ጦር ሠራዊት ጋር ከጋላ ሃገር ዳልሜዳ ተነስተው አራት ቀን ተጉዙ ከዚያ በፊት ከሠራዊቱ ብቻቸውን ተለይተው መጥተው ቤት ወደነበረው ሥፍራ ደረሱ የበነት ሃገር ባላባቶች ቀበብ ስበው ሌሊት ሲዋጉ መጡ እንዚህም የአዳል ፣ የሞራ ፣ የጢቆ ፣ የበከላኝ ፣ የወገር ፣ የገለባ ናቸው የጦራቸውም ብዛት ከሙቶ ሺህ በላይ ይሆናል ። አመጣጣቸውም ሌሊት አጼው ከነሠራዊቱ ከተኛበት ደርሰን እንድም ሳናስቀር እንጨርሰዋለን ብለው ነው ።

እንዳሉትም ሌሊት ደርሰው የአጼውን ሠፈር ሲከቡ የአጼው የጭፍ ጦር ሠራዊት ንጉሡ ነገሥታችን የት ናቸው እስላሞች ከበውናልና ብለው ሲጮሁ አጼ አምደጽዮን ከድንኳኑ ውስጥ ሆነው ጨለማ ቀን በሰሙ ጊዜ የጦር መሳሪያቸውን ልብስ ለብሰው ሰይፋቸውን ይዘው ከድንኳኑ ወጡና በረቅ በሚባለው ፈረሳቸው ሆነው ጦርነት ገጠሟቸው በፊታቸው የሚቆም ጀግና ጠፋ ከፈረስ ላይ እራሳ ከሙሩት ከሺህ ሰው በላይ ገደሉ እንዚያም እስላሞች አጼ አምደጽዮንን ከመግደል በስተቀር ጦርና ቀስት ተወርውሮ የማይወጋቸው መሆኑን አይተው ተሸንፈው ከፊታቸው ሸሹ ።

እንደዚሁ እየደጋገሙ ሲመጡ በየጊዜው ብዙ ሰው በአጼ አምደፅዮን እጅ አለቀ ተገደለ በመጨረሻው ቀን በርከት ብለው እንደአንበሳ ሆነው መጡ በዚያን ጊዜ ሌላ ፈረስ አባትና በሚባለው መጥተው ጊታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ባሪያህን ዳዊትን ከጦር እንዳዳንከው እኔንም ከእጃቸው አድነኝ ብለው ፀልዩና ወደጦርነቱ መካከል ገብተው ይዋጉ ጀመር በዚህን ጊዜ ከነዚያ ውስጥ አንድ ረጃም ሃይለኛ ወታደር የአጼው ወታደር መስሎ ከወደኋላ መጣና በሰይፍ አንገታቸውን መቶ አጼው የለበሱትን የብረት ልብስና የታጠቁትን የጦር ትጥቅ ቀበቶ በጥስ ሲወስድ ሲል እግዚአብሔር ስላዳናቸው ወደኋላቸው አጼው ተመልሰው ግንባሩን በጦር ወጉትና መሬት ላይ ጣሉት በሌላ ግንባር ያሉት ንጉሠ ነገሥታችን የት ደረሱ እያሉ ለመሸነፍ አዘን ብለው ሳለ አጼ አምደጽዮን ደረሱና እስላሞች በሰይፍ አንገት አንገታቸውን ይቆርጡ ጀመር

አፈሳ ላይ ሬሳ ተከመረ በአጼው ፊት የሚቆም ጠፋ በዚያን ጊዜ የአጼን አገዳደልና አመካከት ተመልክተው ይህስ መላክ እንጅ ሰው አይደለም ብለው ሸሹ ንጉሡ ነገሥቱ አጼ አምደጽዮንም በዚህ ቀን ጦርነት ያልተዋጉትን አዲስ የጭዋ ጦር ሠራዊት ተከታትላችሁ ወጉ ብለው አዘዟቸውና እያባረሩ ይወጉአቸው ጀመር እነሱም የገደሉትን ገድለው ማረኩትን ማርከው የጦር መሣሪያ ሰይፍ ጦር ቀስት ብዙ ልብስ ይዘው ወደአጼው ተመለሱ ንጉሡ ነገሥቱም በጣም ደስ አላቸው ከዚህ በኋላ ወደሌላ ሥፍራ ሄዱና በሰኔ ሃያ ስምንት ቀን 1316 ዓ.ም ሦስት መቶ አስራ ስድስት ቀን የጭዋ ጦር ሠራዊቶቻቸውን ሰብስበው እንዲህ አሉ።

ጉጃምም ወገራም ዳሞትም ሃድያም የምንገዛቸውን ሰሙኝ እነሆ ሁልጊዜ እየተዋጋን ብዙዎችን ገደልናቸው የተረፉትንም ትልቆችንም ትንሾችንም ነገሥቶቻቸውንም ማረክናቸው ይህንን ሁሉ ድል ያገኘነው በእግዚአብሔር ሃይል አይደለምን አሁንም በነዚህ ከሃዲዎች ፊት አትፍሩ እግዚአብሔር ስለኛ ይዋጋልና ፅኑ እንጂ አትጠራጠሩ በሰይፍ ቢመጡባችሁ ሠይፍ አላችሁ በቀስትና በጦር ቢመጡባችሁ ቀስትና ጦር አላችሁ እግዚአብሔር ከእኛ ጦር ሠራዊት ቁጥር በላይ ምርኮን ሰጣችሁ ሲወጉን ከመጡት የሚበልጡት አሉቁ እነዚህ የእግዚአብሄርን ልጅ ክርስቶስን የሚክዱና የማያውቁ ናቸው።

እነሱ አረመኔዎች የሚሉትን አልሰማችሁምን ክርስቲያኖች ቢገድሉን ሰማእትነት እናገኛለን በሰማይ መልካቸው ያማሩ ቆንጆዎች ሚስቶች ይዘው ይቀበሉናል እኛ ግን ክርስቲያኖችን ብንገድል እንደገና ገነትን እናገኛለን እስከሰባት ዘር እንፀድቃለን ነው የሚሉት እነዚህ ሰዎች እንጅ ለደህንነት ተስፋ የሌላቸው ተስፋ ቢሶች ከንቱ ፍጥረት ናቸው።

እናንተስ አብን ከወልድ ጋር መንፈስ ቅዱስንም የምታውቁት በስሙ ተጠምቃችሁ በደሙ የተቀደሳችሁት እነዚያን ከሃዲዎች ለምን ትፈሯቸዋላችሁ ቀድሞ ስለእኔ ለመዋጋት ልባችሁን አስገታችኋልን አሁን ግን መጽሐፈ ቀኖና ለእውነተኛይቱ ሃይማኖት ሰይፍህን ምዝዝና ከከሃዲና ከአረመኔ ጋር ተጋደል እንዳለ እናንተም አሁን ለክርስቶስ ስትሉ ለሞጊያ ፅኑ ሰይፋችሁን ታጠቁ ልባችሁን አጽኑ ነፍሳችሁን አታስደንግጡ ይሄም ግድያ በሀጋችን እንጅ በሃይማኖታችን አይደለም ከበታች ሆኖ ሀግን አለመቀበልና የሀግን ሥራ ፈጽሞ ማድረግ ሀግን አለመፈጸም ክርስቶስን መቃወም ነው ይሄውም የሀግ መሠረት መንግሥታችን ነው የመንግሥታችንም ክብር ሀግ ነው።

ዳዊት በእግዚአብሔር ታምኚአለሁ የሰውን ልጅ ምን ያደርገኛል ብየ አልፈራም እግዚአብሔር ስለሚረዳኝ ጠላቶቼን እመለከታቸዋለሁ እንዳለው እናንተም በእግዚአብሔር ታምናችሁ ፅኑ ደግሞም አህዛብ ሁሉ ከበቡኝ በእግዚአብሔር ስም አሸነፍኋችሁ ብሏል ። ከዚህ አያይዞ በቁጣ ቃል ልባችሁን ቀድሞ ወደነበረበት ወደጦር አድርጉት እንጅ ወደኋላ ለመሸሽ አታስቡ ፍርሃትን ከልባችሁ አስወግዱ እኔ ግን በአምላኬ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይል እነዚህን ከሃዲዎች ሳልጨርስ ቢጋም ቢሆን ከረምት ወደቤቴ እንዳልመለስ ሰማይና ምድርን በፈጠረ በህያው እግዚአብሔር ምያለሁ ልቡንም በክርስቶስ አፅንቻለሁ በዚህን ጊዜ የጭቀ ጦር ሠራዊት ባንድ ቃል ንጉሠ ነገሥት ሆይ አሁን እንዳዘዝከን እንሠራለን ነገር ግን ሁሉም እንዲቀናን ባርከን ሲሉ መለሱላቸው እርሳቸውም በቃላቸው እንደዚህ ሲሉ ባረኳቸው በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን በበላያችሁ ላይ ይውደቅ የናንተ ግን ስደፋችሁ ወደልባቸው ይግባ ጦርና ፍላፃችሁም ወደልባቸው ሥር ይቀርቀር ጎራዴያችሁና ጦራችሁም እነሱን ይምታ እናንተን እስከፍጻሜው ድረስ እግዚአብሔር ቢጋሻው ከልሉ እየሠወረ ሃይልንና አሸናፊነትን ይሰጣችሁ ሲሉ ሠራዊቱ ሁሉ አሜን ይሁንልን እንደቃልህ ይድረሰን ሲሉ በአንድ ላይ ለንጉሠ ነገሥቱ እጅ ነሱና ሰገዱ ።

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አጼ አምደጽዮን ሃምሌ አንድ ቀን ከነሠራዊታቸው ከሠፈር ተነስተው ያስ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው ሞራ እገር ደርሰው ሠፈር አደረጉ በዚያን ጊዜ በክርስቲያን ወገን የነበረችና ወደነዚያ ተሸጣ ሄዳ የነበረች ወደአጼው ሠፈር መጣችና እስላሞች ሰማይ ቀልቶ ሃይለኛ ዝናም ከነፋስ ጋር ሲዘንም ክርስቲያኖችን እንጨርሳለን ብለው አስበዋል ። አለቻቸው በዚሁ ቀን የንጉሡ ድንኳንና ሠፈር ሁሉ አንድ ሳይቀር እስኪወድቅና እስኪበታተን ድረስ ሃይለኛ ዝናም ዘንቦ ነፋሱም ነፈሰ ሠራዊቱ ሁሉ ልቡ በፍርሃት ታወከ በዚያን ጊዜ የንጉሡ አዋጅ ነጋሪ በሠፈር እየዞረ እንደዚህ አለ የክርስቲያን ህዝብ ሆይ ዝናብና ነፋስ ብታዩ አትደንግጡ ይህ እስላሞችን አሸንፈን የምናባርርበት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣልን ምልክት ነው በሃምሌ አምስት ቀን እስላሞች በሌሊት መጥተው የንጉሡን ሠፈር ከበቡ የአጼው ዘበኞችም ወደንጉሠ ነገሥቱ ሮጡ በዚያን ጊዜ አጼ አምደጽዮን ከድንኳናቸው ወጥተው ጥሩንባ አስነፉ ሠራዊቱም እየፎከረ ወደእነሱ ሄደና የንደለውን ገድሎ የማረከውን ማርኮ ወደሠፈሩ

ተመለሰ በሌላ ቀን ደግሞ አፀንግተው ሌሊት መጥተው ጦርነት ጀመሩ ሠራዊቱም ንጉሡ ነገሥታችን የትአሉ እንዳያድኑን ወዲት ሄዱ እያሉ ይጮሁ ጀመር አምጸኞቹን ይዤን በሰሙ ጊዜ ወንታችሁ ተዋጉ ብየ ከአሁን በፊት ነግሬያችኋለሁ ንጉሡ ነገሥት የጦር መሪ ሠራዊቱን እየጠራ ወደጦርነት ማዘዝ ልማድ ነበር ነገር ግን እናንተ እኔን ወደ ጦርነት ለመላክ ትጠሩኛላችሁ ከሴኔ መዋጋት አትችሉምን ብለው ተናገሩና ወደጦርነቱ ገቡ ከዚያም አሌቃ አሊቃውን እየመረጡ በሰይፍ አንገቱን ቀጡት የተረፉት ሸሹ አጼውም በግጭድ ጋር እንደሚያ ጭድ ሰው አስላሞችን ሃይል ሰጥቶ አንገታቸውን ሲቆራርጡ አለ መድ ከማቸውን እያሰቡ ከልብ አምላካቸውን እያመሰገኑ ወደድንኳናቸው ገቡ ።

እንግዲህ በአጼውና በሠራዊቱ ላይ የደረሰውን ጦርነት የምንነግ ራችሁን ስሙኝ ከግንቦት ወር እስከ ሃምሌ ወር ሌትም ቀንም እረፍትም አልነበረም ከመገቡም ትጥቁን የፈታ የለም አጼ አምደፅዮን እንደ ሌሎቹ ነገሥታት ሠራዊቱን ብቻ ወደጦርነት ሳይሰዱ ራሳቸው ቀንና ሌሊት ሳይተኙ ትጥቁንም ሳይፈቱ ጠንክረው እየተዋጉ በእግዚአብ ሔር ሃይል አሸንፈው ከዚህ ቀደም የነበሩት ነገሥታት ያልረገጡ ትን አዳል ሃገር በስንት ጦርነት ተዋግተው ያረሱ ይህም ሃገር ምሥ ራቁና ምዕራቡ አይታወቅም ሃገሩ ያስ ውሃው ቆር ይባላል በዚህም ላሉ የታቦቱ ድንኳን በተተከለበት ዙሪያ ምሥራቁ በዚህ ነው ምዕራቡ ነው እንጂ ምሥራቁ በዚህ አይደለም እየተባባሉ ካህናቱ ይጣሉ ነበር በዚሁ በክረምቱ በረሃው እንደእሳት በውንም እንስሳውንም ያቃጥል ነበር ውሃም የለም ቢኖርም በሰው እጅ የተቀፈረ በጉድጓድ የሚገኝ ቆሻሻ ውሃ ነው እንጂ የጠራ የምድር ምንጭ የለም ድንጋዩም እንደ እሾህ ይዋጋል የዚህም አገር ሰዎች እንደድንጋይ ይንከባለሉ እንደ እግር በእጃቸው ይሮጣሉ እንደዚህ እያሉ ሁልጊዜ ሌሊት እየመጡ የአጼውን ጦር ወግተው ይሮጡ ነበር ከነሱም ብዙ እየተገደለ ይቀር ነበር ።

በዚህን ጊዜ ተሸግሮ የነበረችው ሴት እንደነገረችኝ እንደ እግዚ አብሔር የሚያከብሩት ወንዙን በዘንጉ የሚያጠጡት ሰሙ ቃሊ ሳልህ የሚባል ከባህር ማዶ የመጣ ንጉሥ ነው ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገብ ተው ለጦርነት የተሰለፉት ከዚህ ቤታች የሚገኙት ናቸው ።

የአዳል ንጉሥ    የበከላ ንጉሥ    የሃጎራ ንጉሥ

የፈደሲ ንጉሥ    የግዳድ ንጉሥ    የደንገዜ ንጉሥ

| | | |
|---|---|---|
| የሱባባ ንጉሥ | የሃርላ ንጉሥ | የሆባት ንጉሥ |
| የተርጋ ንጉሥ | የአይድም ንጉሥ | የአልብር ንጉሥ |
| የዜልአ ንጉሥ | የአሊቴ ንጉሥ | የደዋሮ ንጉሥ |

ከነዚህ ነገሥታት ጋር የመኳንንት ቁጥር ሁለት ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ናቸው መኳንንቶቻቸው ሁለት ሺህ ናቸው በነዚህ ሁሉ ተልከው ለጦርነት የተሠለፉት አምስት መቶ ሺህ የተቀጠሩ ወታደሮችና አንድ ሺህ የአረብና የእስላም ሺኮች ለጦርነቱ የሚያልፉና የሚያበረታቱ ናቸው ።

ከአጼ አምደ ፅዮን ጋር የተሠለፉት አምስት ነገሥታት አስራ ሁለት መልእክ የደል ሃያ አራት ለቀሚሬ(የጦር አለቃዎች) ናቸው የሃድያ ንጉሥ የጎጃም ንጉሥ የወገራ ንጉሥ የትግሬ ንጉሥ የአናሬያ ንጉሥ አብረዋቸው ነበሩ ሠራዊቱና የጭፍ ጦር ተብሎ የሚጠራ ሠራዊት ሁሉ በአንድ ላይ ስልሳ ሺህ አራት መቶ ነበረ ።

በዚህን ጊዜ አጼ አምደ ፅዮን ከአስራት ፈትተው በወንድሙ በሰብረዲን አገር የሾሙት ሞግለዲን ከእስላም ነገሥታት ጋር በምክር ተባብሮ ከአጼው ከድቶ ሸፈተ ወዲያው ለእስላሙ ንጉሥ እንደዚህ ሲል ላከበት ሰላም ለአንተ ይሁን ስታላቅትነትህም ምክሬን ስማ ነገሬንም አድምጥ እነዚ የክርስቲያኑ ንጉሥ ነገሥት ሲወጣበት በማይቻለው በሚያውቀው ጠባብ መንገድ መጣ አንተ ግን ለራስህ ከነዚህ ከሁለቱ መንግዶች አንደኛውን ምረጥ ግብርና ገፀበረከት ትሰጠው እንደሆነ ሚስትህንና ልጆችህን ያለህን ሁሉ ስጠው ከአንተ በፊት የነበሩት አባቶችህ ያላደረጉትን ይህን ሁሉ ያደረግህ እንግዲህ ከአንተና ከዘር ዘርህ ለዘለዓለም ባርነት አይወጣም እሁን ግን የምትሠራውን በጥበብ አስተውል በሰይፍ በቀስት ቢጋሻ በጦር በአንካሴ በብረትና በዱላ የሚዋጉትን ሠራዊትህን ሰብስብ እኛም የፈረሰኛና የእግረኛን ወታደሩን ይዠ እመጣና ዙሪያውን ከበን አንድም ሳናስተርፍ እንጨርሰዋለን ።

የእስላሙ ንጉሥ ይህን ሰምቶ ነው እንዚህን ሁሉ ነገሥታቶችና መኳንንቶች ሸኮች ሁሉ ለጦርነት ጥሪ ያደረገ የእስላሙ ንጉሥም አምስት መቶ አምሳ ሺህ አሰከንጉሡ እስከ ሺህ የሚሆን ተዋጊ ጦር ሲያገኝና ሲያይ በነፍሱ ኩራ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ታቦት ያለበትን የድንጊን መቅደስ ለራሴ መስጊድ አደርገዋለሁ በውስጡ የሚገኘውን ወርቅና ብር የተቀደሱትንም አልባሳት ለቤቴ አደርገዋለሁ ክርስቲያኖችንም ከአጼው አጥቼ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ግምልና ከብት ለሠራዊቱ አካፍለዋለሁ ንጉሥት ግን መንግሢንና

አቀባቶቿንም ልጆቿንም ሕፃናቱንም እህል ፈጭ ባሪያ አደርጋቸዋለሁ ኦሉ ይህንን ካለ በኋላ ተንስቶው የምርኮው ንጉሠ ለክፍያ እንዲያገለግ ቦታፋቱ ንጉሥ ምንልኢን ሳይመጣ በፊቸንን የክርስቲያኑን ንጉሡ ነጋሥት እንውጋው ብሎ ለንጉሥታቱና ለመኳንንቱ ለሠራዊቱም ሁሉ ነገራ ቸው ስለዚህ በዚህ ተስማምተው የአዳሉ ንጉሥ እንዲያን ሁሉ ነገሥ ታትና መኳንንት ይዞ መጥቶ ሃምሌ ዘጠኝ ቀን የሕጼ ሠራዊት በለ ለበት ሰዓት የአምደፅዮንን ሠፈር ከበቡ በአጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የአለቆችን ስም ከዚህ ቀጥዬ አቀርብላችኋለሁ።

የንጉሡ አምደፅዮን ሠራዊት ቀስተ ንሀብ አለቃቸው ሰመይ ጀሃል ተኩላ አለቃቸው ጃዋረአድ ኮረም የሚባሉት የግራና የቀኝ ፈረሰኞቹ አለቆቻቸው ድምአላና ድግና ባሪያ አለቃቸው እንዳታይ ሃረብ ጉንዳ አለቃቸው አውሬ ወግዘል ፀዋርያን ወርመት አቢያን አለቃቸው አይና ፀዋርያን ንጎል አለቃቸው አምላክ ፀጋዬ የቀኝና የግራ ፀዋርያን ወርመት አለቆቻቸው አይንተይና ሃንተንጉይ ጉግም የግራና የቀኝ አለቆቻቸው ዋድላይና ሃርብ አጋሬ ዳሞት አለቃቸው ማር ክሰወይ፤ ፀዋርያን አሰይ ፍት አለቃቸው ሃርብ አሰምአ ፀዋርያን መንበር አለቃቸው አኪንአዲ

ፀዋርያን መንሳንሰት አለቃቸው ብሀት አከለ ፈረሰኛ ጉግም አለቃቸው ውድም አሉ ይዐውሩ ወልታ አለቃቸው ጉድፊይ።

እነዚህ ሁሉ የንጉሡ ነገሥቱ አምደፅዮን የቀኝና የግራ የኋላ የፊት ጦር የአምሃራ የጎጃም የዳሞት ሠራዊት ለመጊያ የተዘጋጁ በወርቅና በብር በጌልጋን ያስጌጧቸው ተሰተኞና ጦረኛ የኡጋረኛና የፈረሰኛ ብረት የለበሱ ጭፍሮች የሞቀ ሠራዊት ናቸው።

እነሱም ለዚህ ጦርነት አጼ አምደፅዮን እምነቱን የጣሉባቸው ስለሆነ በሌላ ክፍል እንዲኖሩ ተልከው ነበር በዚህን ጊዜ በአጼው አጠገብ አልነበሩም ነበር በዚያው በጾሎት ከሌሎች ጠላት ጋር ይኖሩ ነበር እንጂ በአጼ አምደፅዮን በኩል የሆነውን አላወቁም ነበር ግን አጼ አምደፅዮን በዚህን ጊዜ ታመው በአልጋ ላይ ተኝተው ነበር ከሰባት ቀን ጀምረው እህል አልበሉም ውሃም አልጠጡም በዚ ህን ጊዜ በአጠገባቸው ያለውን ዘና የማት የሚባለውን ሊቀንቡ ሳን ሂድና ለውጊዎች የሚሰጥ ሥጋ አውሬ አደንህ አምጣ ብለው አዘ ዙት እርሱም አውሬ ፍለጋ ሄዶ ሳለ የአዳሎች ጦር ሲመጣ አየ በዚ ያን ጊዜ አደኑን ትቶ ወደአጼው መጣና ከሁሉ ሠራዊትም የሚበልጥ ጦር እነሆ መጣ ስለዚህ ወደእስዎ ቀመስሉ ከእስዎ ጋር ብንሞት ይሻ ላል ብሎ ላከ ይህንን ለማረጋገጥ ሌሎች ፈረሰኞች ሄደው ለማየን

እንደሚሸፍን ጉም መሬትን እንደሚያለብስ እንበጣ የመበለውን የንጊያን ጦር ባዩ ጊዜ አይኖቻቸው ጨለመ ልባቸው ጠፋ ወደአጼው ተመልሰው እንደዚህ አሏቸው የንጉሥን ሠራዊት ብዛት መሬትን ሁሉ አልብሶታል የኢስም ሠራዊት ትልቁም ትንሹም ተሰብስቦ ቢመጣ እነዚያን ተዋግተው መመለስ አንችልም አሏቸው ።

ይህን ንግግር በሰሙ ጊዜ ከመኳንንታቸው ተነስተው እንደታመሙና እንደደከሙ እግራቸውም መቆም ወገባቸውንም መታጠቅ አቃታቸውና ወደቁ ከዚያ የግራና የቀኝ አዛዦች እንሥተው የጦር ልብሳቸውንና መገልገያቸውን እስ ታጠቅ ቸውና ከሠፈሩ ወጡ ። ሁሉቱ ንግሥቶቹም በእንባ እየተላቀሱ እየተከተሉ እንደዚህ አሉት እንደቀድሞው የሚርገ እግር ቀስት ደግና የሚወረውርና ጦርና ጋሻ የሚይዝ እጅ እለህን ፈረስ ላይ ለመውጣት ይከመህ የለምን

አጼ አምደጽዮንም እኔ እንደሴትና እንደፈሪ ካሉ እንደተኛሁ አልሞትም እንደተጋዳይ አርበኛ አሟሟትን አውቃለሁ ብለው መንገዳቸውን መቀጠል ጀመሩ በዚህም ጊዜ ታናሾቱ ንግሥት ለታላቂቱ ንግሥት ስለክርስቶስ ብለሽ ያገርው እንጅ አትልቀቂው ብትላት አረመኔዎች ከመኳንንቱ ሲገድሉት ሲመጡ እያዘዋለሁን አላደርገውም ነገር ግን ይጸድና እንደወንድ ይሙት እያለች ሁሉቱም አጼውን እንደማያገኛቸው ቀስፋ ቀርበው ሲላቀሱ አጼ አምደፅዮን ፊታቸውን ወደ ነሱ ዞረው ሂዱ ግቡ አትከተሉኝ ለእግዚአብሔር ፀሎት አድርጉ ለሁላችሁም እኔንተም ወደእግዚአብሔር ፀልዩ እኔንም በፀሎታችሁ አትርሱኝ አሉና ከሠፈር ወጡ ንግሥቶቹና ልጆቹ አጼው ብቻቸውን ወደጦርነት ሲሄዱ ባዩአቸው ጊዜ ጌታችን መሞቱ ነው እንግዲህ ወየውልን እያሉ መሪሪ ልቅሶ አለቀሱ ።

ንግሥት ግን መንገሳ ግን ወደሰማይ እንጋጣ እንደዚህ ብላ ፀለየች ጌታዬ አምላክ እስራኤል ሆይ እስራኤልን ከፈርኦን ሰሰናን ከአሳዎች እጅ ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ ያዳንካቸው ሁሉን ማድረግ ይቻልሃል አሁንም የባሪያዬቱን ልቅሶና ጩኸት ስማ ይህን ባሪያህን ያንግሥከው አንተ አይደለህምን ሁሉን በጭ ነሺ አይደለህምን ለሩጫ የሰጠኸው እግር ለመዳበሻ የሰጠኸው እጅ በበሽታ ተንቀጠቀጠ ሞቱን እንኳ እንዳያዩ በፊትና በኋላ የሚሰለፉት የጦር ሠራዊቱ ከእርሱ ጋር የሉም በሃጢአቱ ባሪ ልትቀጣው ነውን የሰውን ሃጢአት ከተቆጣጠርከ እንድ ሰው የሚድን የለም ስለዚህ ባሪያህን ከነዚህ ከአረማውያን እድነው ልትገለው ፈልገህ እንደሆን እንተው በእጅህ ግደለው በነዚህ

ሰዎም ግን በእግዚአብሔር ስም ታግዳችሁ ሙቱ በመርደት ከመሞት
በጀግኖች አሟሟት ክብር ሙቱ ብለው እንደነባር ተወርውረው እጌ
እንበሳ ዘለው በጥቂቱ አረብ አስፈሪ የሚባለው ፈረሳቸው ላይ ወጡ
ወዲያውኑ ዘንአስፈሪ የሚባሉትን የጉልማሶችን ፈረሰኞች እሰታ በቀኝ
በኩል በእስላሞች መካከል ገባ ዘንአስፈሪ የንጉሥ ማፍሰገድ ልጅ
እንደታዘዘ ንጉሥ ተክለ ንጉሥ ወናግሬአድ ንጉሥ በድል መበዝ ለንጉሥ
ቅድማይ የሚባሉትን እስከትሎ ወደመሩ መካከል ገባ እጌ እምደፅዮን
ደግሞ የጠላት ሠራዊት በበረከተበት በኩል ገብተው ፍላጻና ጦር
እንደበረዶና እንደዝናም እየወረደባቸው ይዋጉ ጀመር እነርሱም ተመ
ርጠው በሰይፍ ሊከቧቸው መጡ ነገር ግን የበረታ ሰው ተኛውን እንደ
ሚተስ በቀኚ እንደሚመነጥር በእግዚአብሔር ሃይል በአንድ ጦር ብትር
ሁሉንም አጣምር ጣሏቸው አርእድ በሚባለው ሰይፍ ቆራረጣቸው

እምደፅዮን በጀዱበት በታ መሬቱ በፈላ ተሸፍና እይታይም
ነበር በዚህን ጊዜ የእስላም ሠራዊት ይሸሽ ጀመር እነዚያም በቀኝ
በኩል የገቡት ነገሥታት ብዙ ሰው ገደሉ እጌ እምደፅዮን እስላሞ
ችን እያባረሩ ሲጨፈጭፉ ብዙ ጊዜ እንዘለያ በፊት የሸሹት ተመልሰው
ይዋጉ ጀመር ።

እጌ እምደጽዮን አንድ ጊዜ ከፈረሳቸው ሆነው ሲዋጉ አንድ ጊዜ
ምድር ሆነው በሰይፍ አንገት አንገቱን ሲቀጩ ፈረሱ ሲከተል ይታይ
ነበር ።

የእስላሞች መልካቸው ለኢትዮጵያውያን የማያምር ወገራቸው እንደ
ሴት ወገር የተጐነጐነ ሆኖ ከጆን ጣቸው ይወርዳል ከቆራጥነታው
የተነሳ አንዱ አንዱን ጥሎት እንዲደሸሽ የልብሳቸውን ጫፍ ያስሩ
ታል ስለዚህ ለእጌ እምደፅዮን ሰይፍ አንገት ለመቁረጡት የተመቸ
ሆኖ አገኙት ።

ይህን ሁሉ ሃይል ያገኙት በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም በካህናቱና በባላቤታቸው በንግሥቲቱ ፀሎት ይልቁንም ከሁሉ
በበለጠ በራሳቸው እምነት መተማመን ድል አድርገው እሸንፋቸው
መላእክቱንና ሰማእታቱን እንዲረዳቸው እምነት ልኮላቸዋል ። ከዚህ
በኋላ እጌ እምደጽዮን እንደገና ከአረብ አስፈሪ ፈረሳቸው ላይ ወጡና
የሸሹትን እያባረሩ ይገድሉ ጀመር አብረዋቸው ላሉት ሠራዊት የም
ቱትን የጠላት ወታደሮች ምርኮና ሰለባ ሴቶቹ ይውሰዱ እናንተ ግን
ያልሞቱትን የጠላት ወታደሮች እባሩ ብለው አዘዙ ከዚህ መሃል አንዱ
ወታደር የሞተውን ሰው የራሳ ልብስ ሲገፍ እጅትና በጦር ወጉትና

በምህን በማያውቁ እጅ አሳልፈህ አትስጠው ሥጋህና ደምህን እስቲ እንጅ የእርሱን የጤናትና ከቶ ሥራ አትመልከት የባሪያህን ደህንነቱን እንጅ ሞቱን አሁን አትስጠው ። እያለች ከዐለቶች በኋላ ፊትዋን ወደ እጁው አዙራ እንባዋን በጉንጭዋ እያወረደች ስታለቅስ ሴቲም ሀዘኑም ሽማግሌውም ወጣቱም ከእርስዋ ጋር አብረው በራሳቸው ላይ አመድ እየበተኑ አለቀሱ ።

እጁ እምደ ልቡን ግን በእለበት ሆኖ በትልቅ ድምፅ ወደሰማይ እንጋጦ እጆቹን ዘርግቶ መሐሪ ሃያሉ እግዚአብሔር ሆይ ህዝብህን በሃጢአቱ ምክንያት አታጥፋው ግን በምህረትህ ማረው እኔን ግን ደስ የሚልህን አድርግብኝ ሞቴ ስለህዝብህና ስለአገልጋይህ ይሁን እሱ ይህንንም ያሉበት በወንጌል መልካም እረኛ ስለበጎች ራሱን ይሰውጣል እንዳለው ለሀዝቡ ነው እንጅ ለራሳቸው አይደለም ።

ከዚህ በኋላ የእስላሞች ጦር ሠራዊት በእሩት ማዕዘን ወደፋሾውን እንደመብረቅ እያብለጨለጨ ቀስታቸውን ደግነው ጦርና የብረት እንካሊያቸውን እንደያዙ እንደባህር አሸዋና እንደአንበጣ ድምፃቸው ነፋስ እንዳናወጠው የባህር ማዕበል ቃላቸው በዝናም ጊዜ እንደሚያምህ ነጎድጓድ ሆነው መጡ ።

የእስላሞች ሠራዊት ሲመጡ ንጉሥ ሙ ባዩ ጊዜ የእስላሞች ሰው መጀመሪያ ክርስቲያን የነበረ በሚጠጡት ውሃ ላይ ሥራይ በየጊዜው ያደርጉበታል ሲል ለእጁው የነገሯቸውን ትዝ አላቸና የጉልጉታን እምነትና የየርዳኖስን ፀበል ለእጁው እንቱም ተጠመቀው ለሠራዊትህም እርጨው ብላ ላከችላቸው እጁ እምደልቡንም እንዳለችው አደረገ በተጠመቁም ጊዜ ህማሙም ደካሙም ጠፋ እጁ እምደጽዮን እንደዚህ እሱ ከእጠገቡ ያሉትን ትንሽ ሠራዊት አይዟችሁ እንዚህን የእስላም ጦር ብዛት አይታችሁ አትፍሩ የእግዚአብሔር ሃይል ካሉት ጨመረበት በስተቀር ብዙ ጦር በብዛቱ ማሸነፍ ትንሹም ጦር በማነሱ ሊሸነፍ አይችልም ይህን በተናገሩ ጊዜ ወዳጆቹ እጥፋትና ትክሻውን ሰመው ወደ ጦርነቱ ብቻቸውን ለቀቋቸውና ሁሉም ወደኋላ ሸሹ እጁው ግን ለሚሸሹት ትንሽ ቀማችሁ እንደምገም እየተጋደልኩ እንደምሞት ተመልከቱ እግዚአብሔርን በእጅ የሚሠራውን ተመልከቱ አሏቸው ።

እነርሱ ግን ሽሽታቸውን በቀጠሉ ጊዜ ለንበሩት ትንሽ ሠራዊት እንደዚህ ብለው ቢታላች ድምፅ ጮኹ ወዶች ትሸሻላችሁ ዛሬ እንሬችሁ የምትደርሱ ይመስላችኋልን የትም ብትሄዱ ሊታመልጡ አትች

ሞተ በዚህ ጊዜ ሌላው ፈርቶ የንጉሡ ነገሥቱን ትእዛዝ ተቀብለው እያባረሩ ይወጉ ጀመር ይሄን የመሰለ ጦርነት በሌሎች ነገሥታት ዘንድ ተደርጓል ወይም ሰምተናል ከእኛ በፊት የነበሩት ነገሥታት አባቶቻችን አልነገሩንም ጦርነቱም ከስድስት ሰዓት እስከ ፀሐይ ግባት ሲዋጉ የዋሉበት እጃቸው በደም ከሰይፉና ከጋሻው ጋር ተጣብቆ በግድ ነው የተላቀቀ የእግዚአብሔር ሃይል ይገለጥ ዘንድ የጭዋ ጦር ሠራዊት በሌለበት እንዚህ አረማውያን ቢዋጉት በእግዚአብሔር ሃይ ልና እርዳታ ትንሽ ጦር ይዘው ፈጇቸው የተረፉትንም አባረራቸው በዚህ ጦርነት ያለቁት የእስላም ሠራዊት ከእስላሞች የነበረ በኋላ ተማርኮ የመጣ አምሳ ሽህ በላይ ነው የሚያስገርም ሌላ ደግሞ ከዚህ አሁን የሌሉ በጦር የሚያዋጉ ነጭ ፈረስኛ ግራጫ ፈረስኛ አብረው ነበሩ ብሎናል ። በአጼው በኩል ግን ሁለት መቶ ሃምሳ ሲሞቱ ሰባት መቶ ዘበኞች አንድ ሽህ ሁለት መቶ በእለታ የሚመሩ ሠራዊት ተገኝተዋል የአጼው ዋናው ጦር ግን በዚህ ቀን አልነበረም ጦርነቱ በተፋፋመበት ጊዜ ንግሥቲቱ ከቀሩት ጋር ሆነው አጼ አምደጽዮንን በሩቅ ይመለከቷቸው ነበር በኋላ ግን እያባረሩ ሲዋጉ ከአይናቸው ጠፍተው የሆነውን ሁሉ ሳያውቁ ልባቸው በጭንቀት ተይዞ ነበርና ስለዚህ ንጉሡ ነገሥቱ ጦርነቱ ሲያልቅ ለንግሥቲቱ ለዣን መንገሳ የምሥራች በሕይወት ነውና ያለሁት ብለው ላኩባት ።

ይህን የምሥራች ንግሥቲቱ በሰማች ጊዜ ተንስታ ታቦቱ ወዳ ለበት ድንኳን ገባች ከዚያም በደስታ በልቅሶ አምላክን ታመሰግን ጀመር ።

በመሸም ጊዜ አጼ አምደጽዮን በድል አድራጊነት ሃይል በብዙ ሞገስ ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ወዲያውኑ ታቦቱ ወዳለበት ድንኳን ገብ ተው በመሠዊያው አጠገብ በግንባራቸው ተደፍተው ስብሃት ለከ ርስቶስ ምስለ አቡከ መሃሪ ወመንፈስቅዱስ ማህየዊ ዘወትረ ወአድኅንከነ እምእደ ፀሩ ለእልዋን ወሰባተ ፀዓኢ አረሰይከነ ብለው ፀለዩ ካህናቱም ከርሳቸው ጋር በአንድ ላይ ፀለዩ ከዚያም ከታቦቱ ድንኳን ወጥተ እንደወጣ ንግሥቲቱ ተከትላው ዙፋኑ ወዳለበት ድን ኳን ሲገቡ አብራ ገባችና እጃቸውን እና እግራቸውን ሳመች ወገባቸው ንም ይዛ ጌታዬ ሆይ ደህና ነህን ለእኔ ግን ህልም ነው የመሰለኝ እያለች ታለቅስ ጀመር ከመሸም በኋላ ሌሊት እንዚያ ሠራዊት በሌላ ሀገር ሲዋጉ ውለው የነበሩት መጡና በዚህ ቀን ትልቅ ደስታ ተደረገ በቀን ሀዘን በሌሊት ደስታ ሆኖ ታየ በበነጋታው የሰው እሬሳ ሽታ አላውል አላሳድር አለ ነገር ግን ንጉሡ ነገሥቱ ከነሠራዊቱ ካህና

ቀሳውስቱም ዲያቆናቱም መነኮሳቱም እግዚአብሔር በገብረመስቀል አምደጽ ዮን እጅ የሠራውን አስደናቂ ሥራ እንደሚገር አጭዶ የከመረውን ያለመ ለከቱ ዘንድ አብረው ወጡ እንደ አምላክ እስላሞች የሚመለከቱት የሞራ ንጉሥ ስለዚህ አምደጽዮን ገድለውት ስለነበር ሕዝቡ ሁሉ እን ሊያየው በአንገቱ ተሰቀለ ።

ከዚህ በኋላ አጼ አምደጽዮን የጨዋ ጦር ሠራዊት ሰብስበው እስኪ እንግዲህ ሳትፈሩ ንገሩኝ ወደፊት እንሂድ ወይስ እንቅር ብለው ቢጠይቋቸው የሚመልስ ጠፋ ስለዚህ መልሶ እንደዚህ አሏቸው እውነቱን ነው የምጠይቃችሁ የሚበጀውን እንድትነግሩኝ ወደሀገራ ችን መመለስ የወደዳችሁ በፈቃዳችሁበት ጊዜ ሌትም ቀን እንመለስ አንድ ጊዜ መኳንንት በንጉሡ ፊታድ መሞራት አንድ ሰው ብቻ በፈቀደው መሆን የለበትም ማናቸውም ነገር ያለምክር የተደረገ እንደሆነና በፍራቻ የተጀመረ እንደሆነ ይፈርሳል ፍጻሜው ምእያምርም ስለዚህ ደስ ይላችሁ እንደሆነ ሴቶችንና ልጆችን ከጠባቂ ጋር ጥለን ወደፊት እንሂድ እኔ ግን እናንተም ብትኖሩም ባትኖሩም በሚጠብ ቀኝ በአምላኬ ተስፋ አለኝ እንግዲህ የምትሉትን በሉ ። በዚህን ጊዜ ሕዝበ እግዚአብሔር የሚባል ካህን ለአጼው እንደዚህ አለ እውነት ነው እግዚአብሔር በትናንትና ቀን ከእስላሞች እጅ አድኖሃል የያዝ ከውም ሰይፍ በሰው እጅ እንደተሠራ ሰይፍ አይደለም የሰውን ገላ እንደሳር ሲያጭድ ሲቆራርጥ የጠላትን ሰይፍና ጦር ሲሰባብር አይ ቻለሁ ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ሰይፍ ባይሆን ኖሮ ሁላችንም እንድንገም ነበር አሁንም ጌታዬ ሆይ በማኝ ይህ ያየነው ሕዝብ ሳይ ሞት የተመለሰው አይን አይቶ አይዘልቀውም አሁን ብንመለስ ይሻላል አለ አጼውም በማየ ወዳጄ ሆይ አንተ ልብህ አይጠራጠር እግዚአብሔር እንደሆነ ትናንት አረድቶቸኛቸለሁ ዛሬ ግን አልረዳም የሚል አያምስለህ በፍጹም ልባችሁ እግዚአብሔርን እመኑት በርትታችሁ ታገሉ አትጠ ራጠሩ ለእኔ ያደረገውን ለእሥራኤል በፈርኦን ፊት የሠራውን ፈርኦ ንን እስከሠራዊቱ በኤርትራ ባህር ያስመጠው ይኸን ሁሉ በየጊዜው ለሚረዳውና ለሚጠበቀው አምላክ ተገዙ ልባችሁን ወደ እሱ አድርጉ በእውነት ለእኔ እንደሚመስለኝ በኢትዮጵያ ሀገሮች ሁሉ ያሉት ሠራ ዊታችን መጥተው ቢተኙቸው ለመግደል ብቻ ሰባት ወር ባላስቆ ነበር ነገር ግን ሁሉን ማድረግ የሚቻለውን አምላክ ተባብረውና በብዛታ ቸው ተመክተው ቢመጡ የእግዚአብሔር ኃይል በአንድ ጊዜ ከፊሳ ላይ ፊዳ ከምር መሰላቸው እኔም የያዝኩት ሰይፍ እያሳለ በጃይ ቀጥረኝ የሰውን ገላ በምመታበት ሰዓት እንደጨርቅ ነበር የምቀተረው ሰይፋ

ቸውና መሬቸውን በሙታው እንደሳር ያቆራረጥ ነበር ይህም የእግዚአብሔር ክንድ እንጅ የኢል አልነበረም ይህን ዓይረን አምላክ ወርታወ ምንጃናው ብለው ቢታዓቅ ድምፅ ተነስተው ታቦቱ ወዳለበት ድንኳን ሆረው ሰገዱ ።

ንጉሡ ንጉሠ ነገሥቱም እናንተ ካልመለሳችሁ እኔ የምላችሁን ሰሙ እንግዲህ በመጣንበት እንመለስም የመጣንበትም ጉዳይ አረመኔን አጥፍተን በሀገራችሁ ክርስቲያን ሕዝብ እስከምንተካ ድረስ ሆነውን ሁሉ እያቀናና ሹም ሽር አድርገን እንመለስ አላቸው ሠራዊቱም ፈትም ተጋድለህ ያዳንከን አንተ ወደፈትም አንተ ባልከው እንስማማለን አሉት ።

ከዚያ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ከዚያ ተነስተው ዚባ ወደምትባል ሀገር ደረሱና በዚያ ሰፈራቸውን አደረጉ በማግስቱ ተአረክ ወደምትባለው ሀገር ጦር ልከው የገደሉትን ገድለው ብዙ ምርኮኛ ይዘው ወደ አጼው ተመለሱ በዚያም ቁና የሚባለውን ባዓል ሾመው ከዚያ በየምሌ 19 ቀን ዶቤ ወደሚባለው ሀገር ሄደው ሠፈሩ በማግሥቱም የጭቁ ጦር ሠራዊታቸውን ላኩ ሠራዊቱም ዘሶይ የሚባለውን ሀገር አስገብረው ሺከ አብደላ የሚባለውን ገድለው መስጊዱን አቃጠለው ከብዙ ምርኮ ጋር ወደንጉሡ ነገሥታቸው በደህና ተመለሱ ።

ከዚያም በኋላ አጼው ካሉበት ቦታ ተነስተው የእዳሉ ንጉሥ ሀገር ወደሆነች ተለግ ሄደው ከጣርንት ያመለጡት የንጉሡ ወንድምና ሶስት ልጆቹ ከእግራቸው ላይ ጫማቸውን አውልቀው በራሳቸው ላይ አድርገው ንጉሥ ሆይ ተገዛንልህ እያሉ እጅ እየነሱ መጡና ባገራችን ከትንሽ ሰዎች በቀር የተረፈ የሰምና ማረን ሁለተኛ የቀረነውን አታጥፋን ብለው ለመኗቸው ንጉሡ ነገሥቱ በዚህን ጊዜ እንደዚህ አሉ እናንተና አባታችሁ ሰው የማይበድላውን በሃላችሁ ተገዢ የሆነ ሰው ከንጉሥ ሲሸፍት ወደተራራ ወደሜዳ እየሸሸ እስከምል ድረስ ይጭኃል ወይም ተገዢነቱን ያመን እንደሆን ግብሩን ገብሮኛል ለገኛው ይዞ ይመጣል እናንተ ግን ሁለቱንም ሸሽቱንም መገዛቱንም አልፈጸማችሁም በዚህ ፈንታ እኔን የመዳቁ ኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት ልትወጉኝ መጣችሁ እግዚአብሔር ግን የልባችሁን ክፋት ተመልክቶ በእጄ ላይ ጣላችሁ እንደልባችሁ ክፋት ከፈላችሁ ከፈታችሁም ተመልሶ እግዚአብሔር የሃይለኛቸና የደካሞች የሀያሞቹና የሙታን አምላክ ስለሆነ ከኩብራችሁ አዋረዳችሁ ቀድሞውን ከአባታችሁ ጋር ግብራችሁን ወርቅና ብር የተከበረ

ልብስ ይዛችሁ ብትመጡና የምልክውን መልእክተኛ ብታከብሩ ኖሮ በእናንተና በእኔ መካከል ፍቅርና ሰላም በተመሰረተ ነበር የአዳል ንጉሥ ልጆችም ንጉሥ ሆይ አታሞኙን እኛ ወደቀሩት ነገሥታት እንዲገዙልህ እንዲገብሩልህ እንልክባቸው አለን አጼውም ቢመጡ ይምጡ ባይመጡ በእግዚአብሔር ሃይል የማደርገውን ያያሉ አሏቸው ።

ከዚህ በኋላ የአዳሉ ንጉሥ ልጆች ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ሳይጨርሷቸው ለአጼው ተገዙ ብለው ለንጉሥነቱና ለመኳንንቱ ጸቶ የነዚህን የልጆች መልእክት የአዳሉ ንጉሥ በሰማ ጊዜ የሀገሩን ሕዝብ ሰብስቦ የነዚህን ከሃዲዎች ወሬ አትስሙ ነገር ግን የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት እንግደለው ልባችሁን አፅኑ ክርስቲያኖች ቢገድ ሉን ሰማዕትነትን አገኘተን የሰማይ ቤት ልጆች እናገባለን እኛ ግን ክርስቲያን ብንገድል እስከ ሰባት የልጅ ልጅ ኀጢአት እንመርጣለን ብሎ ሰበከና ሌሎቹም ወንዶም ለመርነት እንዲነሳ አዘዘ ከዚያም የአዳሉ ልጆች የሆነውን ሰምተው ለአጼው አሳወቁ ።

አጼ አምደጽዮን ይህን በሰሙ ጊዜ ወዲያውኑ እኢ የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው መርመንዘ የሚባለው አገር ደርሰው በዚያ ሠፈር አደረጉ ከዚያም ግራና ቀኝ ሠፍን አሰልፎ የአዳሉ ንጉሥ ወዳለበት ደረሱና እነሱም ለመርነት ተሰልፈው ተገናኙና ሠራዊት ከሠራዊት ተገናኝቶ ሲዋጉ የመርን መብረቅነት አይተው እንደነበር ተመርመሮ ከአረብ አስፈሪ ፈረሱ ወጥቶ የሀገሩን ንጉሥ በቀስቱ ደግኖ ቢወጋው ቀስቱ ከአንገቱ መካከል ሾልኮ በረረ በዚያን ጊዜ በጀርባው ወድቆ በጉካሉ ከልቡ ላይ ወጋውና እንዲሰቀል ሲያዙ እስላሞች ሸሽት ጀመሩ በዚህ ጦርነት የሞቱት ሴትና ወንድ አስራ አምስት ሺህ ነበሩ ምንም የቀረው ሰው ከሞቱት ያንሳል ።

በማግሥቱ አጼው ሳሰሜ ወደሚባለው ሀገር ሄደው የእስላሞችን መስጊድ አፍርሰው በዚያ ቤተክርስቲያን ተክለው የመጥምቁ የሐንስ በአል አከብረው ዋሉ ።

ከዚያም በነሐሴ 11 ቀን ዘርአት የሚባለውን ወንዝ ተሻግረው አራቱ የሚባለው ሀገር ሠፈራቸውን አደረጉ የዚህን ሀገር ሰዎች ሰውን ከነህይወቱ ጆሮውን እንደምላጭ በጥርሳቸው የሚቆርጡ ሰውን የሞቱውን ያልሞቱውንም እንዳገኙ ብልቱን ይሰልባሉ በዚህ ዓይነት ጆሮአቸውን ብልታቸውን የተቆረጡ ሰዎች ወደንጉሡ ቀርበው ቁስላቸውን አሳዩ አጼውም በጣም ተናደዱ እዚኑም ምንግዜ አገኘተው ነው እንደዚህ

ያደረጎችሁ ብለው ሲጠይቋቸው ወያ በንቀዳ ሜዳ በንወጣ ሲመጡ ባርደ ቀርጠውን ሲሄዱ ነው ያየን አሉ ።

አጼ አምደጽዮንም የጭጥ ጦር ሠራዊታቸውን ጠሩና ነገ ጠዋት እኔ ጡሩንባ እያስነፋሁ እወጣለሁ እናንተ ግን እስላሞች እንዳያዩአችሁ ግራና ቀኝ በሜካ ተደብቃችሁ ተቀመጡ ብለው አዘዟቸውና በጠዋት ጡሩንባ እያስነፉ ሠራዊታቸውን አስከትለው ጉዞ ጀመሩ በዚያን ጊዜ እስላሞች ወደ ሰፈር ሲመጡ የአጼው ወታደሮች ከተደበቁበት ወጥተው ፈጇቸው ከዚያም ሀጂያ ወደሚባለው ሀገር ሄደው የመከቃዲን በዓል አከብረው ሰንበቱ በዚያም ትልቅ ምሽግ ሠሩ ብለው አዘዙና ተሠርቶ ሲያልቅ ሠራዊቱን ከፍለው በምሽጉ ውስጥ ትተው ጥሩንባ እያስነፉ መንገዳቸውን ሲጓዙ አረመኔዎች ወደሠፈር መጡ በዚያን ጊዜ የተደበቁት ከምሽጉ ወጥተው ፈጅዋቸው ከምሽጉ ውስጥ በአገልግሎታቸው የሰለቡትን ሁሉ አገኙ ያንንም ለአጼ አምደጽዮን ሲያሳዩአቸው አዘኑ በመምታቸው አዘኑ በመምታቸው ተደሰቱ ከዚያ ሰባት ቀን ተጉዘው ብልታዜር የሚባለው ሀገር ደርሰው የእስላሞችን ንጉሥ አስጠሩና ያስለምኳቸውን ክርስቲያኖች አምጣ ብለው አዘዙት እሱም አመጣ በንዚያም በመስለማቸው አግኝው የቀጡትን ቀጥተው ሌሎችን ወደሃይማኖታቸው መልሷቸው የእስላሙን ንጉሥ ግን ከሹመት ሽረው ለወንድሙ ነስረዲን ለሚባለው ሰጡበት ከዚያም ወደላ ደርሰው በዚያ የሚገኙትን እስላሞች አስጠምቀው ቤተ ክርስቲያን ተክለው ወደ ዳት ደረሱ በዚያም የሚኖሩትን ሁሉ ሰብስበው ሹም ሽር አድርገው ወደ ዳዋር ደረሱ የድዋዋርው ንጉሥ ሃይደሬ የሚባለው ከሰበረዲን ጋር በአድማ ተባብሮት የነበረ ስለሆነ ከወሰን እስከወሰኑ ድረስ ሠራዊቱን ሁሉ አስጠፉት በዚያን ጊዜ የሌፍ የሚባለው የሳርካ ሹም ከድዋር ሰዎች በከፋት ተባብሮ ስለነበረ እሱን አሠረና በሀገሩ የሚገኘውን ሀብቱን ወርቁ ፈረሱንም ከብቱንም አዘረፉት ይህን ሁሉ ከአደረጉ በኋላ አጼ አምደጽዮን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አዋሽን ተሻግረው በፈጣሪ ሹም ሽርአድርገው በታላቅ ድል አድራጊነት በብዙ ምርኮ ተመልሰው በደስታ ድልን የሰጣቸውን አምላካቸውን እያመሰገኑ ቤተ መንግሥታቸው ወደሚገኘው ምድረ ዳት ሀገር በሰላም ተመልሰው ገቡ በዚህን ጊዜ ዳሞት በቀሉት ጉንደር አይደርሃድ የሚባሉት የጭጥ ልዩ ጦሮች ንጉሥን የሚባለውን የበዳ ሃይማኖት ተከታዩ አጥፍተው ወገራና በለምት ወገዲ ደንቢያ የሚባለውን ሀገር አቅንተው ከጎጃም ንጉሥ ሰናር ጋር ተገናኝተው መጥተው በዳት አገኛቸው በዚህን ጊዜ ትልቅ ግብዣ

አድርገው ለአንድ ወር ቆዩ ከዚያ የጉዚያን ክርስቲያኑን ንጉሥ ሀገር አቅና ብለው ካህናትና ሊቃውንት ሰዋቱው ወደሀገሩ በሰላም ላኩት የዚህ ጦርነት ታሪክ የሄደ በንጉሥ ሥርና ጊዜ ነው ዘጎንደር የጻፈው ከዚሁ ኖባት የባሬው ጀበል ኑባ ስላገኘው ነው ሌሎችንም ዳሞት ጉንደር በቀልት የሚባሉት የጭዋ ወር ሠራዊት እናንተ ወደዚህ ስትመጡ ሕዝቡ ተመልሶ ቡዳ የሚባለውን ሃይማኖትና የአይሁድ ሃይማኖትን እንዳያምን ሄዳችሁ በወንጌል አሳምናችሁ አጥምቃችሁ ክርስቲያን አድርጓቸው ብለው ከሽልማት ጋር ላኳቸው በቀልት የሚባሉ በደንብያ ጉንደር የሚባሉት በወገብ ዳሞት የሚባሉት በቤተ አንዳ አደደር በኩሶማ ሄደው ሀገር እያቀኑ ተቀመጡ በዚያም የጭዋ ወር ሠራዊት መኖሪያ ሆኖ ቀረ ይባላል ።

ለአጼ አምደ ጽዮን በዘመን መንግሥታቸው የነበረው የአማርኛ ቋንቋ ግጥም ይህ ነበር ።።

ያርበኛ አምደጽዮን ተጋዳይ
መጣለስ የወሰን እልፍ እልፍ ጉዳይ
ወየ እንደመሰን መጣላሽ የወሰን
ከወንጂ ዜብይና ከገንዝ ጠጠን
ምን ቀረህ በወሰን ከድያ አመኖን
ምን ቀረህ በወሰን ከባሊ አሊን
ከደዋር ሄደሬን ከፈጠጋር ዜላርድን

ከኢፋት አምበል አበከርን
ከገደም የሞሊን ከቅማንት አደደርን

ከአንጉት ቄን አሞራን

ከአገው ቤት አገሮርን
ከትግሬ ነገደ ክርስቶስ ይወረድ
አያረግከው ገንዞን

እንዲሠራ ደውጂውን

ማን ቀረህ በወሰን

አላጠፋኸው ፈቱን
አልአስገማረከው ልጅ ሚስቱን
ከጉዛም ጃን ከምርን
ከጋፋት አውሳምን
በዳሞት ሞት ለሚን
ማን ቀረህ ከወሰን
ያለጠፋኸው ፈቱን ያላ
ማርከው ልጅ
ሚስቱን
ያርበኛ አምደ ጽዮን ተጋ
ዳይ
መጣላሽ የወሰን እልፍ
እልፍ ጉዳይ
አምደ ጽዮን ስም የበራ
በወጂ እስከ በጥር አሞራ
(አሞራ ገደል በጣሬው
ጉንደር)
ቋራ ይንሰንስ ቋራ እንደ
ጭራ
በወንዶች ገረገራ
በዪድ እስከ ጉዴራ
በዓሕር እስከ አረንጓሬ

(የፈርኦን ሠራዊት የሰጠ
ጠመበት)
ዓምደ ጽዮን ስምተዉራ

ይህ ግጥም በዚያን ጊዜ የነበረው አማርኛ ግጥም ነው ከአጼው በታች የሚገኙትን ንጉሶች ያነሳል እነዚህም ከመጀመሪያ ግጥም ላይ የሚገኙትን ናቸው ግዛታቸውም ከግብ ባህር እርትራ እስከ ዘይላን ድረስ ነው ምንም በውስጥ ያለው ትናንሽ ጉግ በአመፅና በጀ ፍት ንጉሥ ያላቸው ጉጣዎች በአጼው ሥር ሆነው ነበር የሚገዙ በት ጊዜ የነበረ መንግሥት መጀመሪያ በአክሱም ኋላም በላስታ ቀጥሎ አሁን በሸዋ ሊተነሱት ለኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት በሰላም በፍቅር ሄደው ግብራቸውንና ግዞ በረከቱ የሚያቀርቡ ይሄውም የአ ጼው መንግሥት ከእስራኤል ዘር ሥርዓት ከኢትዮጵያ ሕግ ከጽዮን የሃይማኖት መሪ ከግብፅ ሰዎች አይወጣም እያሉ የነበረ ባላባቶች ልጆቻቸው ይናገሩ ነበር ይባላል ።

አጼ አምደ ጽዮን ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ የቀሰምና የጦር ሰው ብቻ አልነበሩም የአስተዳደር የፍርድ ሥራም ይችሉ ጀግና አዋቂ ነበሩ ።

ስለዚህ በጊዜያቸው የነበረውን ዳኝነት እንመልከት ከሰሊታት አንድ ቀን ሁለት ሰዎች በአንድ ሌሊት አንዲት ቤት ተገናኙ ያች የተገናኙዋት ቤት አርግዛ ወንድ ልጅ ወለደችና መጀመሪያ ተገናኘ ቷት የሄደው የእኔ ነው ሲል ሁለተኛው ደግሞ አብሯት ያደረው ፊቱም መልኩ እኔን ነውና የሚመስል የእኔ ነው ተጣልተው ተጣሉ በዚያን ጊዜ ተከሰው ወደዳኛ ሁለቱም ቀረቡ ሴቲቱ ብትጠየቅ ሁለ ቱም በአንድ ሌሊት እንደተገናኘኋት ተናገረች የመጀመሪያው የትኛው ነው ብትባል መልኩ የማይመስለውን ጠቅሳ አሳየች ዳኛውም ለመጀ መሪያው ፈረደ ግን መልኩን የሚመስለው ይግባኝ አለና እስከአምደ ጽዮን ዙፋን ችሎት ደረሰ አጼ አምደጽዮን ሁኔታውን የልጁን መልክ አስተውለው ይሄን ምን እኔ አፈርድሻለሁ እግዚአብሔር ፈርዶለታል ይሄውም መልኩም ሆነ የአካሉ ቅርጽ የሁለተኛውን የተገናኛትን እንጂ የመጀመሪያውን አይመስልም ይሄውም ምንም ቀድሞ ቢገና ኛት ሃጢአት እንጂ ዘር አይደለም ሁለተኛው ግን ምንም ሃጢአት ቢሠራ ዘር ሆኖ ተቀጠረለት ስለዚህልጁ ነው ብለው ፈረዱለት ነገር ግን የመጀመሪያውን ልጅህ አይደለም ብለው ፈረዱበት ይህን ፍርድ የሰሙ የአናሬያ (ሊሙን) ሰዎች በልጁ አካሉው መጡ በዚያን ጊዜ

ከሳሹ ይህች ሴት ትጠየቀልኝ የወለደችልኝ ለእኔ ስለሆነ መልኩም የሚ
መስል እኔን ነው ብሎ ለእጨ አምደጽዮን አመለከተ ንጉሡ ነገሥቱ እጨ
አምደጽዮን ሚስትህ ናት አይደለችም አሉት ጌታዬ ሆይ ሚስቱ አይ
ደለችም ውሽማዬ ናት ለእስስ ቢሉት አዎን አለ እጨ አምደጽዮንም ሴቲ
ቱን ለምንድነው ይሄን ያደረግሽ ቢሏት ባሌ መካን ስለሆነ ልጅ ፈልጌ
አለች ባልየውን ልጅህ መሆኑን ታምናለህ አሉት ምንም እኔ ባልወ
ልደው በቤቱ ውስጥ ስለተወለደ ልጄ ነው ብዩ የምቀጥረው አላቸው
ጥሩ አልክ ብለው ያንን ልጅ ነው ያለውን የሰው ሚስት በማባለግህና
ከዚያም አልፈህ ልጄ ነው ብለህ እስከእኔ በመድረስህ በሞት ቢታ ብለው
በእናሪያ በገበያ ቀን እንዲሰቀል ፈረዱበት ። ለሴትዋ ባል ደግሞ በቤቱ
ውስጥ ስለተወለደ ልጄ ነው ስላለ ሾመው ሸልመው ልጁን ከርስ
ትና አንስተው በደስታ ወደሀገሩ ሊሎ ላኩት እስከዛሬ ድረስ ያን
ህን ሆኖ ይቀጠራል እንጂ ለተገናኛት ሰው አይሆንም ይሄን የመሰለ
የአስተያየት ፍርድ በየጊዜው ሰርተዋል ለመዳኛም ሆነ ለመናገር
ጊዜ የለንም በዘመነ መንግሥታቸው ኢትዮጵያን ከድንበር እስከድንበር
ግዛተዋል ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት መጽሐፍት በማንበብና በዳኝነት ስለ
ነበር እንደነእጨ ላሊበላ እንደነእጨ አብርሃ የታወቁ ሆነዋ አላሰሩም
ስለሌላው ግን እናንተው የኢትዮጵያን ታሪክ አንባቢዎች ፍረዱት
መረራስ በላይ ይሆን የአምደጽዮን ታሪክ ከመጽሐፈ ሲራክ ከግእዝ
ወደአማረኛ በስደት ሀገር ላይ ሆኜ ጽፌላችኋለሁ ።

የእጨ አምደጽዮን ከርስትና በተነሱበት ቀን የተሰጣቸው ስም
ገብረመስቀል ነው ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ በተባሉበት ቀን አራሳ
ቸው መርጠው ያወጡት ስም ደግሞ ሰይፈ አርእድ ይባላል

እጨ አምደ ጽዮን ከልጅነታቸው ጀምረው እንደሞግዚት ተንከባ
ክበውና ጠብቀው እንደእናት እንደአባት ሆነው ያሳደጓቸውን የደ
ጋው ልጅ መድብይቱን (ጋዳ) ሲነግሡ ግን ሞገሥ የተባሉትን ዳዊን
አገቡ ዳዊም በአምደጽዮን አባት በውድም ረአድ ቤት ያደጉ ዳዊት
ይጋሚ ወሎተኛ ነበሩ ነገር ግን መካን ስለሆኑ እጨ አምደጽዮን
ያለ ልጅ እንዳይቀሩ ብለው ሌላ ሴት እንዲያገቡ አስገደዷቸው በዚያ
ምክንያት ወደ ቡላ ወርደው ሳለ የብሌን ነገድ ጉግ የምትሆን ዕር
ጊት የምትባለውን አገቡ ዕርጊትም ግንቦት ንግሥት በኢትዮጵያ
ተብላ በአንድ ሺህ ሶስት መቶ አመት መጀመሪያ የእንተርታ ከዚያ
አዳል ከመርን ከተመለሱ በኋላ የሰሜን ኢትዮጵያ የትግሬ ንግሥት
ሆነች በምግቢን ውስጥ ደባሩአን ቀረቀረች በሥራም የሚታወቀው
መልአከባህር የሚባለው ቀርቶ ባህርነጋሽ ትግራይንጋሽ ማእከል
ባህር ሥዩም በደብረ ማሪያም ሥዩምዘሬዳ የሲተከሉት ደግሞ እቀቢ

ባሕት ዘመጣሕ የሚባሉ ነበሩ እንዲሁም ከሃማሴን መጥተው በምድረ ከብድ ሰፈሩ ግራኝ ቀባሉ ሃገ ሳባ ንግሥት ለአጼ አምደጽዮን ሰባት ወንድ ልጆች ሦስት ሴቶች ወልደውላቸዋል ።

አጼ አምደ ጽዮን ከጎጃም እስከ ታላቁ ባህር ባሉት ነገሥታት ላይ ሰላሳ ዓመት ከገዙ በኋላ ባልታወቀ ሕመም በተወለዱ በአምሳ ሰባት ዓመታቸው አረፉ ። ከእርሳቸው ቀጥለው የክርስትናቸው ስም ንዋየ ክርስቶስ የሚባሉት ቆስጠንጢኖስ እንደ አባታቸው ሰይፈ አርእድ ተብለው በአባታቸው ዙፋን ላይ ተቀመጡ ። ይሄውም ስመ መንግሥታቸው ሰይፈ አርእድ የተባለበት ምክንያት የአባታቸው ሰይፍ ስም አይቀርም ሲባል ነው ይህ ሰይፍ ለአምደጽዮን የእግዚአብሔር መላክ ሰጣቸው ይባላል ። ሰይፉ ያረፈበት ሁሉ ይዘነጣጠል የሰውን ፀጉ ቀርቶ ድንጋይ ይከፋፍል ይኸውም ሰይፍ አጼ አምደጽዮን ከሬሺት በሚባሉት አዲስአረቦች ላይ አጼ ንዋየ ክርስቶስ ሰይፈ አርእድ በግብፆች ላይ ያሳዩት ግድያ ወሳኞች አረቦች ከሰማይ የመጣ ሰይፍ እንጂ በሰው እጅ የተሠራ አይደለም ሲሉ በታሪካቸው ላይ ፅፈውት ይገኛል ።

አጼ ንዋየ ክርስቶስ ንጉሠ ነገሥታት በኢትዮጵያ በተባለ በአምስ ቱኛው ዓመታቸው ወያኔናታቸው ሀገር ግባት ሄደው ገዳማቶቹን ሁሉ ጐብኝተው መነኮሳቱም በዐሎት እንደሚያደረሳቸው ነግረው ቡራኬም ሰጥተው አመናበታቸው እንደዚሁም አንድ የዘሁ ባህታዊ አባ መድሃኔ እግዚእ የሚባሉ በእስክንድርያ የሚገኙት ክርስቲያኖችን ጳጳሳት በእስላሞች እየተሰቃዩና እየታሠሩ ነውና ሄደህ የታሰሩትንም በሰላም ሆነ በጦርነት አስፈታ እግዚአብሔር አምላክ ብለው መርቀው ወደ ምስር ለኪቸው ከዚያም አጥበራን አድርገው ሲገዙ የበታቻቸው የነባሙ ንጉሠምሥናር የደንባን የደንጕላን የገሙናን ንጉሥና መኳንንት ሰብስበ ለሴላ ሺህ ቀስተኛ ጦር ይዞ ቶያቸው ከዚያም ከተነጋገሩና ለንጉሡ ነጋሥት የሚገባውን ገፀ በረከት ከተቀበሉ በኋላ በሺህ ሶስት መቶ አርባ ዓመተ ምህረት ላይ ለግብፁ ሱልጣን ያስረከባቸውን ክርስቲያኖች ካልፈታህ የፈረሰውንም ቤተ ክርስቲያን መልሰህ ካላሰራህ አንተንም ሆነ መሬቶችህን ይምሰሺ አጠፋሃለሁ ።
ባህር ማዶ ያለውም ኒታገሩ የምታመልከበት አምላክህ አያድንህም ሲሉ ጻፉለት የምስርም ሡልጣን በቁርከ መንግሥት እየታዘዘ ትልቅ ሃይል ስለነበረው ለተላከለት መልስ ሳይሰጥ ለጦርነት ይዘጋጅ ጀመር ለጦ ርነት መዘጋጀቱን አጼ ንዋየ ክርስቶስ በሰሙ ጊዜ የነባሙን ንጉሥ ወደፊት እንዲቀድም አዘዙት በዚያም አማርኛ በሚባለው ቦታ ላይ የሁለቱ ወገን ከወጥቶት እስከማታ ከተዋጉ በኋላ የግብፁ ሡልጣን ሠራ

ቂት ድል ሆነ በዚህ ምክንያት እንደገና ካይሮን ለመውረር እንደተ ዘጋጁ በሰሙ ጊዜ የግብፁ ከሊፋዎች ወደንዋየ ክርስቶስ የታሠሩትን ክርስቲያኖችና ጳጳሳቶች እንደሚፈቱና ወደ ፊት ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋር የፍቅርና የሰላም ውል እንደሚያደርጉ በለዚሁም ታሥረው የነበ ሩትን አባ ማርቆስን ሊቀጳጳሳቱን የእስክንድርያውን ላኩላቸው በዚ ህን ጊዜ አጼ ንዋየክርስቶስ ሊቀ ጳጳሳቱን አቡነ ማርቆስን በማየታ ቸው በጣም ደስ አላቸውና ከእርሳቸውም ቡራኬ ተቀበለው በሊቀ ጳጳሳቱ ቃል ተሰማምተው አባ ሰላማ የሚባሉ ጳጳስ ጋር በደሀና ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ በአባይ ወንዝ ለወንዝ አድርገው የግንቦቸን ሱኪ የምትባለውን ከተማ ጉብኝተው ለንባው ንጉሥ ከብር የማዕረግ ወርቅ ከራሱ ላይ አድርገው በጎሙና ጎንው ውሪቂን ታጅበው አዋሪያ (ሲዋን) ጉብኝተው ከዚያም ዝዚታን የዛሬው ሸዋ መናገሻ አድርገው ተጉለት በአመታቸው ተመልሰው ነው በዚህን ጊዜ ከምበር እንደተመለሱ የደብተቱ ወሳሰማ አሊ የሰብረዲን ልጅ በአጼ አምደጽዮን ጊዜ የአባቱን ግዛት ተቀብሎ ይገዛ ነበር አጼ ንዋየክርስቶስ አለመኖራቸው ሲያ ውቅ ሸፍቶ ኢፋትና አዳልን አሸፍቶ ሀገር እያስወረረ ከብት እያዘረፈ አገኙት ከዚያም እራሳቸው ከእለብት ዘጣ ድረስ ሄደው ተዋግተው ድል ከሆነ በኋላ እጁን ሰጠ ። በዚህ ምክንያት ሹመቱን ለልጁ ለአሁ መድ ሐርብ አራድ ተሹሞበት አሊ በማሆት ሲኖር አጼ ንዋየክርስቶስ በልጅነታቸው ቀን ለአስረኛ ምርት ሲያደርጉ አሊም ተለቆ ሹመቱንም መልሰውለት ከልጁ ጋርም ሲዋጉ ሲታረቁ ከኖሩ በኋላ ልጁ አሁ መድ ሞተ በፈንታው የአህመድ ልጅ ሃቅ አድዲን አቡበከር አጐቱን አሊ እያቱን በጦርነት ከገደለ በኋላ የድፋትን ግዛት ጠቅሎ ይገዛ ጀመር ። አጼ ንዋየክርስቶስ ሰይፈ አርዕድ ሃያ ስምንት አመት ከገዙ በኋላ በሀገሩ ሁሉ በሽታ ገብቶ ብዙ ሕዝብ ከአለቀ በኋላ መጨረሻ እራሳቸው ታመው ሞቱ በዙፋናቸው ልጃቸው ንዋየማርያም ስመ መንግሥታቸው ውድም ረዓድ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ በዚህ በንዋየማርያም ዘመነመንግሥት በሀገሩ ረሀብና በሽታ በጎቶ ስለነበር ከአንዱ ወደአንዱ ሀገር የሚዘዋወር ሰው አልነበረም በነ ገሡ በአንደኛ ዓመት የወላስማው ወንበር ጅሻ የክርስቲያኑን መን ግሥት እንገለብጣለሁ ብሎ ጦርነት አስነሰቶ ባስነሳው ጦርነት ሞተ ሃቅአድዲም ከሞተ እስከ ዘጠኝ ዓመት ሀገሩ ሰላም ሆነ ንዋየማር ያም በነገሡ በአስረኛው ዓመት በተቅማጥ በሽታ ታመው ስለሞቱ ወንድማቸው ዳዊት ያብቃል ተብለው በዚህ ስልት መቶ ሰባ አምስት ዓ/ም በእያታቸው በአጼ አምደጽዮን ዙፋን ላይ ተቀመጡ የአጼ ዳዊት ዘመነመንግሥት ከሚቀለው ተመልከት ።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

### አጼ ዳዊትና የልጃቸው የአጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን መንግሥት

አጼ ንዋየማርያም እንደሞቱ ታናሽ ወንድማቸው ዳዊት አጼ
ይበቃል ንጉሠነገሥት በኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ ከያዘ ቃል ይልቅ
የበቃ ባህታዊ ተገልጾ ስምህ ዳዊት እንጂ ይበቃል እንዳይባል ስላላ
ቸው አጼ ዳዊት በሉኝ ብለው በአዋጅ አናገሩ ።

እንደዚሁም ሆኖ አጼ ዳዊት በነገሡ በአምስተኛው ዓመት ላይ
በኢትዮጵያ ንጉሠነገሥትና በግብፅ ሡልጣኖች መካከል ለልጅ ልጅ
የሚተላለፍ የወዳጅነት ውል ተዋዋሉ በኢትዮጵያ በኩል አረጋውያ
ኀት አባማአምር በእስክንድርያ በኩል አባ ቴርሎስ የነው አከሱም
ላይ ተዋዋሉ ውሉም የሚለው ንግድና ወዳጅነታቸው እንዲቀጥል በኢ
ትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች እንዳይነኩበ በግብፅም የሚኖር ጳጳሳትና
ክርስቲያኖች እንዳይታሰሩ የሚልና ዋናው በኢትዮጵያ በኩል አለ
ፈራ የነበረው የግዮን ወሃ ግድብ እንዳይደፈርና ግብፅም በየጊዜው
ለኢትዮጵያ ጳጳስ እንድትልክ ወደኢየሩሳሌም የሚሄዱ ኢትዮጵያው
ያን ችግር እንዳይደርስባቸው የሚል አስራ አምስት አንቀፅ ነበረ
በዚሁ በአጼ ዳዊት ዘመን መንግሥት ወደኢየሩሳሌም ሄዱ የኢትዮጵያ
መነኮሳት እሌኒ ንግሥት ከተቀበረበት ያመጡትን ጊታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ የተሰቀለበትን እንጨት ለእኛ ይገባል ብለው አመልክተው
አጼ ዳዊትም በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ለእስላም ባለሥልጣኖች የሚ
ሰጥ ወርቅና የዝሆን ጥርስ ለግብፅ ካሊፋ ከወርቅ የተሠሩ ማሰር
ዎችና የወርቅ አክሊል አሲዘው ስለላኩ ሁሉም ተደስተው ለኢትዮ
ጵያኖች እንዲሰጥ ሲሉ አዘዙ በዚህን ጊዜ እጅ ያረፈበት ግማደ
መስቀል ለኢትዮጵያ ሲደርስ ሌላው ለእስክንድርያና ለኢየሩሳሌም
ገዳም ያርቢል ይደሠጡም ከሶስት ተከፍሎ አንዱ የተላለበት በዚህን ጊዜ
አርባ ሰባት መነኮሳት ግማደ መስቀሉንና ቅዱስ ሉቃስ የሳለትን የእ
መቤታችንን ስእል ከልጅዋ ጋር የጌታችንን ስእል አክሊል ሌላ አስደና
ቂክብርና በደስታ ይዘው በመንገዱ ችግር ሳይደርስባቸው ከኢየሩሳ
ሌም ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገቡ አጼ ዳዊትም መምጣታቸውን ሰም
ተው ጊዜሬ ድረስ ሄደው ተቀበሏቸው ከዚያም ከመስከረም 16 ቀን 13

፲፱ ዓ.ም ተጉለት ነበርና በቤተመንግሥቱ አጠገብ ቤተክርስቲያን አሰር
ተው የግደመስቀሉን በክብር አስቀመጡት በዚህን ጊዜ መስቀሉን
ከመስቀለኛ ቦታ አስቀመጡት የሚል ጽሁፍ በጠራው ሰማይ ላይ ሰብ
ዞዎች ሲታይ ለሌሎች ደግሞ በራእይ ታያቸው ነገር ግን መስቀለኛ
ቦታ የተባለውን የሚያውቀው ስለጠፋ ለጊዜው በዚያው እንዲቆይ
ተደረገ በዚሁ በአጼ ዳዊት ዘመነመንግሥት መሃመድ አቡል በራካ
ለድሰድ ዲን በወንድሙ እጎር ተተከተ እስላሞቹን እየመራ የዘላንን
የሸ አማን ምርኩን ድል አድርጉ ዘላንን ወሰደ ብዙ ምርኮ አገኘ
ወዲያውኑ የአጼ ዳዊት ጦር መሬ ዛንሃት መጥቶ ብዙ እስላሞች አጠፋ
ባኑል የሚባለው ክርስቲያን ወታደር ከመሐመድ አቡል ጋር ተጋጠ
መና ግርከው ከዚያም መሐመድ አቡል ባልነትን ወደ ንጉሡ ንጉሥ ነ
አስረው ሲያመጡት ከመንገድ ሞተ ዘላንም በክርስቲያኖች ጁቸ
ሥራዊት ትግዛ ጀመር ቤተክርስቲያንም በየቦታው ተተከለ ብዙ መስ
ጊዶች ፈረሱ አጼ ዳዊትም በሃያ ዘጠኝ ዘመነ መንግሥታቸው የጊታ
ችን የኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል ከመስቀለኛው ምድር ባለማስቀመ
ጣቸው ባዘሉ ፈረስ አረግጣቸው ሞቱ እፊሳቸውም በደጋ ያሴት
በክብር ተቀበረ ከእርሳቸው ቀጥሎ ልጃቸው ቴዎድሮስ አጼ ቴዎድ
ሮስ ተብሎ በአባቱ ዙፋን ተቀመጠ ።

አጼ ቴዎድሮስ በንጉሡ ዘመን በአጼ ይኩኖ አምላክ በትክለሃይ
ማኖት መካከል የተደረገውን የሲሶ መንግሥት ቃል ኪዳኑን አፍርሶ
የቤተክህነቱን መተዳደሪያ ለሀገሩ ማካፈል ጀመረ የቤተክህነቱን
ሃብትም ተዘርክርኮ ነበርና ካህናቱም ሕዝቡም ግፉ አደረገ እያሉ ያለ
ቅሩውና ይወደው ነበር ነገር ግን አራት ዓመት እንደገዛ ሞተና በተ
ድባበማርያም ተቀበረ ከርሱ ቀጥሎ ወንድሙ ይስሐቅ አጼ ገብረመ
ስቀል ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ ።

አጼ ገብረ መስቀል በንጉሡበት ዘመን መረብ በሚባል ሀገር የሚኖሩ
ፈላሾች ቤተክርስቲያን እያቃጠሉ መንገደኛውን እያንገላቱ የሚባል
ወሬ ሲሰሙ መረብ ድረስ ሄደው የቤተእሥራኤልን ሕዝብ የአመፀውን
አጥፍተው በደንቢያና በወገሬ በወልቃይትና በጠለምት ብዙ ቤተክ
ርስቲያን አሰሩ በኮሰቢያም በራሳቸው ስም ይስሐቅ ደብር የሚባል አስ
ተከሉ ከቤተእሥራኤል እንደተመለሱ በዳውንት አድርገው ግሸን ላይ
ሲደርሱ መስቀሉን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጠው የሚል ጽሑፍ በሰ
ማይ ላይ ተጽፎ በራእይ አዩ ከዚያም እየዞሩ ሀገሩን ሲመለከቱ
የግሸን ደብር አቀማመጥ ከመስቀለኛ ምድር ሆኖ አዩት ስለዚህ በአ

ባታቸው በሙሉ ከኢየሩሳሌም የመጣውን ግማደ መስቀል በክብር እምተተው ከመስቀለኛው ምድር ላይ አስቀመጡት ።

እንደዚሁ ነው ላሊበላ ወንድሙ ሀርቤ በአሰደደው ዘመን ጐሐ ጽዮን መድኃኔዓለ ገዳም መንኖ ሳለ መስቀሉን በመስቀለኛ ምድር አስቀም ጠው የሚል ጽሑፍ በብራና ላይ ተፅፎ ሶስት ጊዜ በራእይ እየወ ከዚያም በራእይ ወደ እየው ወደ ምዕራብ ሲጓዝ መስቀለኛውን ምድር እግኘውና ድንጋይ - (ሐውልት) አስቀመጠበት እቤቱ አምላኬ በእባቱ ዙፋን እንደምታስቀምጠኝ አመቴአለሁ ስለዚህ አምላኬን መድኃ ኔቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ቦታ ላይ መስቀልህን እንዳስቀምጥ ቤተ ክርስቲያንህን እንድሠራ የእባትህ ፈቃድ ይሁንልኝ ብሎ ተሳለ በዚህ በተሳለበት ሌሊት በራእይ ተገለጠለትና እንዲህ አለው ወዳጄ ላሊ በላ ሆይ መስቀሉን በልብህ እንዳስቀመጥከው በዚህ በቆምክበት ምድር እንዳስቀምጥከው ይቆጠራል ይሄውም ስለትህና ተስፋህ ይፈጸም ዘንድ በዘመንህ ሳይሆን ሀገን በሚያከብሩና ትእዛዙን በሚፈጽሙ ነገሥታት ዘመን መስቀሉን ከኢሩሳሌም መስቀለኛ ምድር ላይ እንዲያስቀምጡት የባህሪ አባቱ ፈቃድ ነው ምልክቱ በልብህ የተቀመጠው መስቀል ሆይ ልህ ነው ድል ለእንተ ነው ስለዚህ ስምህም ገብረ መስቀል ይባላል አሁን ተነሳና መስቀሉ ወደአለበት ሀገር ሂድ አለው ላሊበላም ይሆን ቦታ ግሼን መስቀል አለው ላሊበላም በግብፅና በኢየሩሳሌም ከኖረ በኋላ ወደሀገሩ ተመልሶ በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀመጠ ወዲያውኑ ግሼን ድረስ መጥቶ እራሱ እንጨትና ድንጋይ እየተሸከመ የእግዚአብ ሔርን እብ ቤተ ክርስቲያን በሚያምር ሁኔታ አሰርቶ ታቦቱን አስባ ርኮ እስገባው በዚህ ቦታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል ማረፊያ ነው ሲል ተናግሮ ነበርና በጽሑፍ ተጽፎ ሲኖር አፄ ገብረመስቀል ከተነሱት እምተተው በዚሁ መስቀለኛ ቦታ በክብር ሲያስቀምጡት የእግዚአብሔርን ታምር ለላሊበላ የነገረ ውን አይነቱ ታሪኩም በቤቱ መንግሥቱና በመጣፍንቱ ፊት ተነበበ ።

አፄ ገብረመስቀል ግማደ መስቀሉን ወስደው ግሼን ላይ በሚያ ስቀምጡበት ጊዜ ብዙ ሕሙማን ከሕመማቸው ዳኑ የታወሩ አይና ቸው በራ ለምጻሞች ነፁ በእፍባቢው የዕለቱ ለት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን ወረደ ።

አፄ ገብረመስቀልም በደሴታና በፍቅር ኢትዮጵያን እርሬ እም ስት ዓመት ገዝተው ለልጃቸው ለእንድርያስ ዙፋናቸውን ሰጥተው መንነው ገዳም ገቡ ።

እንድርያስም አጼ ሣርዌ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ እርሱም ስድስት ወር እንደነገሠ ስለሞተ በፋንታው አጉቴ ዮዳቄት ልጅ ተክለማርያም አጼ ሕዝብናኝ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ነገሠ እርሱም አራት ዓመት ነግሦ ለልጁ ሰርወ ኢያሱስ ለቀቀለት ።

ሰርወ ኢያሱስም አጼ ምህረትናኝ ተብሎ አራት ወር ነግሦ ሞተ እንደዚሁም ወንድሙ አምደኢያሱስ አጼ በድልናኝ ተብሎ በነገሠ በስምንት ወሩ ስለሞተ እግዚአብሔር እንዳስፈቀደላቸው አውቀው በአምባ ነገሥት ተግዘው የሚኖሩትን የአጼ ዳዊትን መጨረሻ ልጅ ዘርአያዕቆብ አጼ ቆስጠንጢኖስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ተብለው ነገሡ ።

አጼ ቆስጠንጢኖስ ዘርአያዕቆብ የሚባለውን ስማቸውን ስለሚወዱ መንግሥታቸውን አደላድለው ከያዙ በኋላ አጼ ዘርአያዕቆብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው እንደገና በአክሱም ነገሡ ።

አጼ ዘርአያዕቆብ ከአጼ ዳዊትንት ከንግሥት እግዚእክብራ በፈጣጋር ውስጥ በዛሬው ጀንትራ በሌዋ ወይም ጥልቀ ሃይቅ እንደሚገኙ ኤሉ ባህር ከዛሬው በሌሣ ከተማ ላይ ተወለዱ በዓት አመት እንደዘሁ ናቸው የንጉሥ ልጆች ወደሚኖሩበት አንባ ነገሥት ግሸን ተወሰዱ ከዚያም መንፈሳዊ ትምህርት እየተማሩ ብሉይና አዲስን አጠናቀው አወቁ ። በዚህ በግሸን ለሃያ አንድ አመት ያክል እንደተቀመጡ 1420 ዓ.ም በምድረሻዋ ልዩ ደብር ደብረመጥማቅ ከሚባለው ሃገር ላይ አጼ ቆስጠንጢኖስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሰዩመእግዚአብሔር ተብለው ነገሡ ።

በዚሁ በንግሡበት ዘመን የሃድያው ገራድ ሚሂክ በአጼው ላይ አመፁና ባሌን ደዋሮን በቁጥጥሩ አደረገ ከርሱም ጋር የትደላ ገራድ ፣ የዳሮ ገራድ ፣ የሃደበ ገራድ ፣ የገንዝ ገራድ ፣ የቡጋ ገራድ የገብ ገራድ የቀብኤ ገራድ የሃሰብ ገራድ የጉንግ ገራድ በአንድ ላይ ሆነው ለሃድያው ገራድ ለሚሂክ ገቡለት በዚህን ጊዜ አጼ ቆስጠንጢኖስ ሚሂክ መሸፈቱን በሰሙ ጊዜ የሚሂክን እኅት ገራድ ባሞን ከዱኅን አስጠሩና የሃድያ ገራድ እንተነህ ብለው ሾመው ብዙ የጦር መሳሪያና ልብስ ሸለሙት ከዚያም በበር ሸተል የሚባሉትን የዳሞት ጺዋ ሠራዊት ከባሞን ጋር ሄደው ሚሂክን እንዲይዙት አዘዙ እነሱም ሃድያአገር ከገራድ በሞን ጋር ሄደው በአለበት ቦታ ቦታ ተዋግተው በጦርነት ገደሉት የሚሂክን እራሱና እጅ ቆርጠው

ለአጼ ቆስጠንጢኖስ ገዳይ ሣለ እርሳቸውም ለገራዶ ባምና ለዳሞት
ሃጸሬ ለረዳቸው ሁሉ ትልቅ ግብር አደረገው ሽልማት የወርቅ ካባ
ሽለሙአቸው የገራድ ባምን ዘር የገንዶቶን ገራድነት እስከልጁ ይሁን ብለ
ው ቃል ገቡለት ።

አጼ ቆስጠንጢኖስ በንግሡ በአስረኛው አመት ወደ አክሱም ለመሄድ
ጉዞ ባደረጉ ጊዜ ከዚህ በታች የሚገኙትን ጸሎ ሥራዊት ያልደረሰው
ሃገር እንዲጠብቁ አስተምረው ሄዱ እንዚህም ግን ፀገና እርቅምድ በውር
ዋጀት በድል ጎዳና በአዳል አምባ በድልድብ በድል ነድ በአዳል መብረቅ
ይባላሉ እንዚህን ሁሉ በደዋር በባሌ በበርበር ያልደረሰው ላኳቸው
እንዚህንም ሲልኩ ለሚሄዱበትና ለተያለያሉት ሃገር እንዲህ ብላችሁ
ንገሯቸው አሉ የሰጠናችሁን አዝማች ባለማክበር ወያኢስላም ሃገር
እየተቫገራችሁ እስላም ሆናችሁ መጣችሁ ስለዚህ በእናንተ ላይ እና
ንተን የሚተጣና የሚመራ አዲስ ጸሎ ስራዊት እግዚአብሄር እንደ
አበዘኝ ልኬላችኋለሁ የተድምውን ከፋታችሁን ትታችሁ በአዲሱ ስር
ዓትና ህግ ኑሩ እንቢ ያላችሁ እንደሆን በእናንተ ላይ የባሰውን ቀን
በር እንጥልባችኋለን ያለርህራሄ እንቀጣችኋለን ብለው በሃድያ በባሊ
በጉራጌም በበጌምድር በሱኪ በእናሪያ በፈጣገር በጾቶት በግድም በበ
በእንጊት በቆዳ በትግሬ በባህር አምባ በሥርዋ በንዚህ አገሮች ሁሉ
አዲስ የጸሎ ሥራዊት ስም እየሰጡ ላኳቸው ። ከዚህ በኋላ በከብር
ጸሎ በድል ሰሞ በዚን ጸሎ ሥራዊት ታጅበው ወደ አክሱም እንደገና
የንግሥን ህግና ሥርአት ለመፈጸም በወረዱ ጊዜ የአክሱም ሰዎች ።
ህዝብና ካህናት በታላቅ ሰልፍ በእልልታና በዘፈን አክብረው ተቀበ

የትግሬ ሹማምንቱና ሠራዊቱ በፈረስ ሆነው ጋሻና ጦራቸውን
ይዘው ሲቱም እየዘፈኑ ወደበሩ በደረሱ ጊዜ የትግሬ መኳንንት የአክሱም
ንቡረ እድግራና ቀኝ ሆነው የትግሬ መኳንንት ኢታቢ ፀንፀንያ የሚባ
ለው ንጉሡ ነገሥቱ እየረገጡት እንዲያልፉ ብሎ ባነጠፈው ሥጋጃ
ምንጣፍ ላይ መቶ አምሳ ወቄት ወርቅ በተኑት ይኸም የጥንት ነገሥ
ታት ለፅዮን ስጦታ የሚያደርጉት እንደነበር ህግና ሥርዓት ነው ።

አጼ ቆስጠንጢኖስ በአንድ ሺህ አራት መቶ ሰላሳ አመት (1430
ዓ.ም) ጥር ሃያ አንድ ቀን እንደገና በፋን ላይ ተተምጠው እጼ
ዘርአያዕቆብ ንጉሥ ነገሥት በኢትዮጵያ መሲህ እግዚአብሄር ሥር
አተንግሳቸውን አክበሩ በዚሁ ሥፍራ ላይ ንጉሡን የሚባርኩና
የሚያመሰግኑ የመዘምራኑ መቀመጫ በንጉሡ ነገሥቱ መቀመጫ ግራና

ቀኝ አስራ ሁለት አስራ ሁለት የደንጋይ ወንበር እለ የጳጳሱ ወንበር ፊት ለፊት ለብቻው ሆኖ ይታያል ።

አጼ ዘርአያዕቆብ በዚሁ እለት የዩኒቨርስቲያችን ሁግና ሥርዓት ደንባን ለመንኮሳቱና ለመዘምራኑ ሰአታት ለሚቆሙት በናአጼ የሚገኘውን ምድር እርስት አድርገው ሰጡ ለዩኒቨርስቲያኑ ብዙ የወርቅ አልባሳት ሰጡ ከዚያም ወደአማራ አገር ተመልሰው ወሃይ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ሲደርሱ አባታቸው አጼ ዳዊት አሰቃምረው የነበሩትን ቤተመቅደስ አዩና ወዲያውኑ እንዲፈርስ አዘው ሁለት ቤተክርስቲያን አሠሩ እንዱን መካነጉል ሁለተኛውን ደብረንጉድጓድ ብለው ሰየሙት ደብተራዎቹ ተከሎበት ከዚያም ወደ ተጉለት ደርሰው በምድረዳጉ ደርሰው ቤተክርስቲያን ተክለው መካነማርያም ብለው ሰየሚት ይችንም ደብር ለባለቤታቸው ለፍሬ ማርያም ሃገ ሃይል መታሰቢያና መቀበሪያ እንዲሆናት ሰጡት ፍሬ ማርያም የብርሃን ዘመድ የመድህን ዘመድ የወበለ ማርያም የድል ድባብ እናት ናት እንዲሉትም በመካነማርያም ተቀብረች ከዚያም ደብረምጥማቅን በተጉለት ሃገር አሳምረው አሠሩ አጼ ዘርአያዕቆብ በዚሁ በደብረምጥማቅ ሳሉ እርቄ በድባይ ለሠርጉት ሲወጋቸው ተዘጋጅተዋል የሚባል ወሬ ሲሰሙ በትንሽ ጦር ጋር ወደደዋር ሄዱ ከዚያም የሠራዊቱን ብዛት አይተው ወደአምላካቸው ወለዩ አቤቱ ሰዓት አምላካችን ጌታችን ሆይ ከእኛ ጋር ያሉት ወታደሮች ጥቂቶች ናቸው እነዚያ ጠላቶቻችን ግን እንደ ባህር አሸዋ እንደሰማይ ከዋክብት ቁጥራቸው የበዛ ነው አሉ ቸው የአጼ ዘርአያዕቆብ ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይደለም እርበኛም በጉልበቱ ብዛት ፈረሰም በብርታቱ ሲያድን አያሰፈም ሲሰጥም አይችልም የሚለው የዳዊትን ቃል አታስተውሉምን እኔ ግን በምህረቱ ይረዳኝ ዘንድ አምላኬን እግዚአብሔር ታምኜበታለሁ ብለው መለሱለት ።

ከዚህ በኋላ አጼ ዘርያዕቆብ ከሠፍናቸው ተነስተው ድባብ እንዲያዝ ጥሩንባ እንዲነፋ ነጋሪት እንዲጐሰም በግራና በቀኝ ተቁም ወርቅ የተሸነሸነ ሰንደቅ አላማ እንዲቆም አዘዙ ከዚያም እርቂ በድባይን ሠርጉት ከበሙትና ብዙ ሽህ ወታደር ገደሉበት እስም አጼውን ሲገድል ተሸሽጉ ሲመጣ አዩትና በሁሉ መሃል ጦር ወርውረው እንዱቱን ወግተውት ከዚያም አንዱ ጋሻጃግሬያቸው እራሱን ቆርጦ ከንጉሡ ንጉሥ ፊት አቀረበው በዚህን ጊዜ ሰላዮችን አመሰገኑ ከዚያም ብዙ ሠራዊት አለቀ የሚበዛው ተማረከ የሃድያው ገራድም የእርቂ በድባይን ወንድም ከረዳን አምልጦ ሲሸሽ ገደለውና እራሱን ቆርጦ ለአጼው ግዳይ ሰላሳ ብዙ ልብስ ተሸለመ ከዚያም በድል አድራጊ

ነት ወደተወለዱበት ሀገር ወደናዝሬት ተመለሰ በዚያም የሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ከተወለዱበት ምድር ላይ አስተክለው ያንም ባልሞ ሚካ ኤል አሉት ሌላ ሁለት ቤተክርስቲያንም ተከሉ አንዱን መርጦ ለሚ ካኤል ሁለተኛውን አዘዞ ሚካኤል ብለው ሰየሙት ከዚያም ተንስተው ምድረአንዘርጓ ደርሰው ደብረሰሏን ብለው የማርያምን ቤተክርስቲ ያን ተከቶ በዚሁ ሳሉ የደብረ አሰቦ መነኮሳት ከአባ እንድርያስ ጋር መጡና እንዲን እረዳዎት ብለው በአንድ ላይ እግዚአብሔርን አመሰ ገኑ ።

አጼ ዘርአያዕቆብም ለገዳሙ መቶ አምስ ጠቀት መሬት ሰላን ባለወርቅ ግምጃ ሰባት የሃገር ልብስ ሰባት የወርቅ መነሳንስ ሰጡ ከን ርሱም ጋር በንጉሡ ተቀምጠው ቃል ኪዳን አደረጉ ። የጌታችን የኢየ ሱስ ክርስቶስን ልደት በየወሩ በ29 በዓሉን ቀን ድል ለአደረገበት ማኅ በሊያ ይሆን ዘንድ መቶ መስፈሪያ ምድር አሳት የንጉሡውም ስም ማህበረአሰበው እንዲባል ደብረአሰበይቦባል የነበረው ገዳም ስሙን ቀይረው በእሊስ ስም ደብረሊባኖስ እንዲባል አደረጉ እስከ ዛሬ ያንም ገዳም ደብረሊባኖስ ሲባል ኖረ በዚሁ ዘመን ደቂቀ እስ ጢፋኖስ የሚባሉ የጎጃም ሊቆች ጌታችን ኢየሱስ ለተሰቀለበት መስ ቀል አይሰገድም እኛም አንሰግድም ብለው ሲከራከሩ ተይዘው በአጼ ዘርአያዕቆብ ፊት ቆሙ እነሱም አንሰግድም ሲሉ በድፍረት ተናገሩ ከዚ ያም ንጉሡ ተናድዶ እንዲገደሉ ሲሉ ብዙ መነኮሳት ፈረዱባቸው ምላሳቸ ውና አፍንጫቸው ተቆርጦ ሞቱ ደቂቀ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግረው በሞቱበት ሀገር በሰላሳሰምንተኛው ቀን በመጋቢት አስር ቀን በአንድ ሺህ አራት መቶ አርባ (1440 ዓ/ም ታላቅ ብርሃን ከሰማይ ወርዶ ሰባት ቀን ለብሶ አደሮች ታየ ብርሃኑም ቅርፁ የመስቀል ቅርጽ ነበረ ። በዚህን ጊዜ ብርሃኑ በታየ በሰባተኛው ቀን ታላቅ ክብር አደርገው ብርሃን የታየበ ትን ቦታ ደብረብርሃን ብለው ሰየሙት በዚያም ቦታ ቤተክርስቲያ ኖች እንዲሰሩ አዘዙ በዚያም ደብር ቅዳሴ ገብተው ሳለ በቁርባን ጊዜ ብርሃን እንደገና ወርዶ ታየ ከዚህ በኋላ አጼ ዘርአያዕቆብ በዚ ያው ቤተመንግሥታቸውን አሠርተው ለመኖር አቀዱ ቤተመን ግሥቱ በሚሰራበት ሰዓት በኢትዮጵያ ሀገሮች ላይ የተቅማጥ በሽታ መጣና ብዙ ሚሊዮን ሕዝብ አለቀ የሚቀብርም ሰው ጠፋ በዚህን ጊዜ በቤተመንግሥቱ በቀኝ በኩል የቂርቆስን ቤተክርስቲያን አሠሩ በዚህን ጊዜ የተቅማጥ በሽታ ጠፋ ለዚሁ ቤተክርስቲያን ብዙ ስጦታ

ሰው ከዚህ በኋላ ቅዳሜና እሑድ እንዲከበሩ አዘዙ አጼ ዘርአያዕቆብ በደብረብርሃን ሳሉ ብዙ መጽሐፍቶችን ደርሰዋል ከታወቁት ዋና ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው ።

1ኛ/ ጦማረ ትስብእት — ስለጠንቋይ
2ኛ/ መጽሐፈ ብርሃን
3ኛ/ መጽሐፈ ሚላድ — ክህደተ ሰይጣን
4ኛ/ መጽሐፈ ባሕርይ — ስለኑዛዜና ስለንስሐ
5ኛ/ ተአቅቦ ምስጢር
6ኛ/ እግዚአብሔር ነግሠ ለቅዱሳንና ለሰማእታት የተደረሰ

አጼ ዘርአያዕቆብ አስራ አራት ዓመት ሙሉ በደብረብርሃን ተቀምጠው አንዳንድ ጊዜም ወደ ምድረፈረጉና ወደደብረ ምጥማቅ ሲሄዱ ኖሩ ዋና መቀመጫ ያደረጉት ግን ያው ደብረብርሃን ነው ።

አጼ ዘርአያዕቆብ ሰላሳ አራት ዓመት ኢትዮጵያን ገዝተው በሰላሳ አምስት ዓመታቸው ስለአረፉ በምትካቸው በእደማርያምን አጼ ቀስሙ ዮድ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው አነገሡቸው

(ከበእደ ማርያም ዘመነመንግሥት ተመልከት)

ለአጼ ዘርአያዕቆብ በዘመኑ አማርኛ ቋንቋ የተገጠመ ግጥም

ዣን ዘርአያዕቆብ በድል ወሐዶ
አንገርት የንረክ በራዶ
ባልዋ የባርዜላዶ
ዣን በደበና ቢታዶ
በአልቱት ያዘለችው ይምሰል ሥርናዶ
አበዛ ይመስል ገሳጋዶ
መስከረምን ይመስል ወሐዶ
ሰይጣን አርዌ በድላዶ
የለመደው በዘርጋዶ
የለመደው በግዳዶ
ዣን ዘርአያእቆብ በድል ወሐዶ
ቀስበው እንደ እንዛዶ
አፈዘዘው እንደሰማ አልዋቀ ዋጋ ይታዶ
በትግሬ በጎንደ ኢያሱስ ጋዶ
ግብፅ የወጣ አርዘኑዶ የከመሩበት ድንጋዶ
ሰማ ዘርአያዕቆብ እንዳያዛዶ

በቅድሚያሊታይ በለጀርጊይ በአንገት አለ ይታይ
ሚስቱ ዜንባ እንዲታይ
ታንጉት እንደመርጠይ
ቅዱቁስ እንደበርበረይ
ሰም በርአያሉቁብ ሃይደብይ
ኪዳን ይሁንህ በሰማይ
ጉልትህን አልሰጥ ላዋይ

ይህ ግጥም ለማስታወስ ያህል ነው የአቀረብኩላችሁ ወዳጆቼና ወንድሞቼ ።

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት

## የአጼ በእደ ማርያም ዘመነ መንግሥት

ይኩኖ አምላክ ስመመንግሥታቸው ሲሆን ተስፋ ኢየሱስ ነው ውድም አርዕድ አምደጽዮንን ንዋየክርስቶስ ይቢታል የተባሉት ዳዊት ዘርአያዕቆብ በእደማርያምን ወለዱ ።

አጼ ዘርአያዕቆብ በ፲፬ አራት መቶ ስልሳ ዓመተ ምሕረት ጳጉሜ ሶስት ቀን እሁድ ሌሊት በነገሡ በሰላሳ አራት ዘመን ሲሞቱ ልጃቸውን በእደማርያምን በዚያው ሌት ነገሡ ኢታቤ በኢቱ አምሃ ጽዮን በትልቁ መንበር ፊት ቆሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ ልጄን በእደማርያምን በእኔ ፈቃድ ሳይሆን በአምላካችን ፈቃድ አነግሰዋችኋሉ ወንድ ጌታቹ ዘርአያዕቆብ አንግሰው ብሎ አዘዘኝ ይህንንም ምስክርነት በመላእክትና በሰው ፊት እሰጠዋሁ እኔም ሀሰት ብናገር መንፈስ ቅዱስ ምስክሬ ነው ከዚህ በኋላ የንጉሥ ነጋሪት የአጼ በእደ ማርያም አዲስ ሕግና ለእስረኛ ምሕረት መስጠት ዙሪያ ጎር አደረጉ በአባቶቻቸው ጊዜ ማንኛውም ሰው ነጭ ልብስ ወይም ቀይ ልብስ መልበስ ክልክል ነበር ነገር ግን ወዲያውኑ በአባታቸው ሀዘን በተቀመጡ ጊዜ ከዛሬ ጀምሮ ቀይም ነጭም ብጫም ልብስ ሁሉ የፈለጋችሁትን ልበሱ እስ በነገሡ በማግሥቱ በወህኒ ቤት በግዞትም ያሉትን እስረኞች ስለ እመቤታችን ስንል አባቴም እኔም ምሕረት አድርገንላችኋልና በደስታ ወደ የቤታችሁ ተመለሱ ይህንንም አዋጅ ካስነገሩ በኋላ በዋን በለው በዋን እስፈፈ በዋን ዳንግግር በዋን ሰጥደ ያሉትን የጭቀ መር ፈረሰኞች በአስብተ ሰብስበው በሥራቸው አደረጓቸው ከዚህ ቀጥሎ በአባታቸው በዘርአያዕቆብ እጅ የነበረውን ሁሉ በትእዛዛቸው ውስጥ አደረጉ ዙሪያ ጎር ያደረጉት ከዚህ ቀጥሎ ነው ።

ከንጉሥ ነጋሪት በታች ያሉት ባለሥልጣኖች ብሀት ወዳድ ዘየማን ቤቱ መጻኢ ብሀት ወዳድ ዘርጋም በግ፫ ጸሀፊላህም መገዘ በዳሞት ጸሀፊላህም በሸዋ ጸሀፊላህም ተንቤት በጉጃም ጸሀፊላህም በቅዳ ጸሀፊላህም በአምሃራ ፕሀፊላህም በመርያ ቤት በአንጓ ቤት (ዋድላ) በአንጎት ንጉሥ በቅዳ ንጉሥ በዳሞር ንጉሥ በወንጅ ፈጣገር (የባሌው

የናዝሬት አሙራጃ) ንጉሥ በገኘ ንጉሥ በሃድያ ገራድ በገንዝ ገራድ በደዋሮ ከንጉሡ በታች ለስላሞች ገራድ በእንተርርታ ስዩም በዋግ ሥዩም በትግሬ መኮንን በይፋት ወላስማ እስኩዋ በግድም እቃቤን በእናሪያ አባ ሲሙ በኩና አበጉባ በፌ እንዲሁም ሁሉ ከሀገራቸው እያስመጡ ሽፍሽፍት አራስ ወርቅ ንቡራን እድ እንደ ሊቃነካህናቱን ሁሉ በራሳቸው አክሊል እየደፉ ሹመቸቸው ከዚያ በደስታ ሀገር እን ዲያቀኑና ሕዝቡን እንዲያስለቱ ወደየሀገሮቻቸው ሰደዱቸው ።

የዚህ ጉዳይ ካለቀ በኋላ የመስቀሉን በአል በደብረብርሃን አክብ ረው ጥቅ በዚያው ቀን ልብስ ተክህኖ ለካህናቱ እየሸለሙ ሁሉን ከትንሽ እስከትልቁ ማስፈሊታቸው ከዚያ የኑረምሉ ወራት በኋላቀ የቤተመንግሥቱ እቃና መገሪያ ሁሉ ከናዝሬት ቤት (ግምጃ ቤት) ከመንግሥት ቤት) መዘጋጃ ቤት) ከበረከት ቤት ከገደል ቤት)ዘም( ጤር እቃ ቤት) ተሰብስቦ ወደ ገስም የባሬ መናገሻ ሸዋ ሄዶ በ በኛ እንዲይጠበቅ አደረጉ በመቶከረም ቶያ ከደብረብርሃን ተነስተው ደብረምጥማቅ ደርሰው (በዛሬው ስላ ድንጋይ) እካባቢ የእመቤታ ችን በዓል አክበሩ ከዚያ መንዝሀል (በዛሬው መንዝ) ከምድረስወረ ገደል ማሽ ደረሱ በግሼ የሚገኘው የአማራው ቶሀዓላህም ዙብ መታያ መብል መጠጥ ደየ በእልልታና በሆታ ተቀበላቸው ከዚያም እባታ ቸው ዘርእያእቆብ ወደአሰሩት ወደ ደብረንጉድጓድ በመኳን ንትና በሠራዊት ታጅበው ሲሄዱ የሀገሩ ሕዝብና ካህናቱ ደብተራው ጠፍ እያበራ በገሬና በቶኝ ተሰልፎ ተቀበላቸው ። በዚያም ቀን ከቅ ዳሴ በኋላ ብዙ ሰንጋ ታረደ ከዚያ ከላንቶ ወደ ሚባለው ሀገር በዓሉ እድርገው እንዲቀበሏቸው ነበ (የምላ) ግምጃ አሲዘው መኳንንቱን ላኳቸው ። ያችን ሀገር ከላንቶን እትሮንስማርያም ተብላ ጠፎት አዲስ ስም አወጡላት ማለት ነው ከዚህ በኋላ ከደብረንጉዋድጓድ ወደአትሮንስ ማርያም ሄዱ በደረሰም ጊዜ ካህናቱና የሀገሩ ሕዝብ የበዓል ልብሳ ቸውን ለብሰው በክብርና በደስታ ተቀበሏቸው ።

በዚያም ሠራዊቱንና ሕዝቡን ከወይራ ዛፍ በቆር ሌላውን ዛፍ ቆረው ድንጋዩን እያነሳችሁ ይልድሉ ብለው አዘው የቤተክርስቲያኑ ግንብ ተጀመረ የቤተክርስቲያኑ ግንብ ሥራ እንዳለቀ በልዩ ልዩ የሀር ልብስ ተገጠና በታላቅ ክብር የማርያም ታቦት አስገቡ ። የቤተክርስቲያኑ ሥራ ካለቀ በኋላ አምዱ ለዚሁዋን የሚባለውን አለቅ ንት ማዕረግ ሰጥተው በብር ያገጠ ልብስ ሰጥተው የዕጌረዳና የወይን ዘለላ ተሰም ያለውም ሁለት አክፋር አክሊል በራሱ ደፍተው ሹመት አክፋርም ከፊት አስራሁለት ከኋላ አስራ ሁለት ዘርፍ ያለው ነበር

አሰራ ሁለት መስቀል ከፊት አሰራ ሁለት መስቀል ከኋላው እን ዲቆምለት አሰራ ሁለት ሰብአመጠ እንዲጋርዱለት በም( በሰማያዊ) ብርሃ እንዲጠጣ ቡብር ቢላዋ በተጌጠ ሥጋ እየተቆጠረ የሚበላበት አዘዙለት ሉላም ብዙ ጌጣጌጥ ያላቸው የአንበሳ ምንጣፎች የወርቅ ጥላዎች ታዘዙለት በዚሁ ቀን ለራት ማሰሬ ሬባንደብር ለመምህራኑ ሬበናቱ ማሀሌት መጋሙር ለተመረጡት ቀሳውስት በአጼ ጊዜ የንበ ሬው የማረግ ስም ዜቢጠር ብለው ሾማቸው ለደብሩና ለካህናቱ መተ ዳደሪያ የሚሆን ብዙ እርስት ሰጣቸው ይህችም ደብር ንዋየ ክርስቶስ ወደማብፅ ሲወርዱ ታቦት አስቀምጠውባት የሄዱ መቅደስ ነበረች ኋላም አባታቸው ዘርአያእቆብ ደብረጸራቅሊጦስ ብለው ሌላ ታቦት ልከው ሳለ ሳያውሩት ሞቱ በአደማርያም ግን እራሳቸው ከቦታው ድረስ ሄደው አውሩዋትና ስምዋን አትሮንስ ማርያም እንድትባል አዘዙ ።

በአትሮንስ ማርያም እንዳሉ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሁሉ ከየደ ብሩ አስጠሩትም የሕጉን መፅሃፍ ይዘው ከተሰበሰቡ በኋላ በአደ ማር ያም አትሮስን ማርያምን ትተው ምድረ ጀጀና ሄዱና ሥርዓተንግሣ ቸውን አክበሩ እንደአባታቸው ሕግ አዲስ ስመመንግሥት ዳዊት የሚባል ስም ተሰጣቸው ይሄው ዳዊት የሚባለው ስም በእጣ ስለወጣ ነው በዚሁ እለት የልጅነት ሚስታቸውን ግራ በእልቴሃትን ሣን ሰይፍ ቀኝአ በእልቴሃትን እሌኒን አድማስ ሞገስ ብለው ሰየሟቸው ።

ከአጼራጅ በወጡ ጊዜ አንድ አንበሳና አንድ ጕሽ እንደተዋጉ— ደው ንጉሡ ነገሥቱ በእጃቸው ወግተው እንዲገድሏቸው ቢያቀርቡላ ቸው ጕሹን ሌላ ሰው እንዲገድለው አንበሳውን ግን ከአንበሶች በረት ውስጥ ተቀምጦ እንዲቀለብ አዘዙ ከዚያም ሥርዓተንግሣቸውን ከአ ከበሩ በኋላ ወደ አትሮንስ ማርያም ተመልሰው የተምቀትን በዓል አከበሩ ከዚያም ወደ ምድረ መንዝ ሄደው ቦታ መርጠው ቤተክር ስቲያን አሰርተው ሲጨርሱ የእመቤታችንን ታቦት አስገብተው ስም ዋን ምሥሃል ማርያም ብለው ሰየሟት ለካህናቱና ለደብሩ መተዳደሪያ እርስት ደልድለው ሰጡ በዚህን ግዜ ዘውትር ፈረስ ይጋልባል እንጅ ተቀምጦ የመንግሥትን ሥርዓት እየፈፀመ ፍርድ አይሰጣም እየተባሉ መታማታቸውን ስለሰሙ በጣም ተናደዱና ሕዝቡንና ሠራዊታቸውን በየሉ ሰብስበው አምታችሁልኛል ብለው ለየቶቻቸው ሠራዊቱም አላል ንም እሉ ከዚያ ሁላችሁም እውነት ከላጠጣችሁ ትገደላላችሁ ስላሏቸው ምንቸውን እያጋለጡ ሰጡ ከነዚህም ከአሥት ውስጥ የጣን እቃቤ ሲቀ መጣኔ ብዙውም መነኩሳት ናቸው እነሱም አላልንም ብለው

ስለካዱ እጃቸው እየተቆረጠ ወደ ዳቅ ፤ ወደጉንደር ፤ ወደጉሽፈር ፤ ወደ ጸሬ ፤ ወደክርስቶስ ፈጠር ፤ እጃቸው ተላከ ወደ አምባ ባሴት ፤ ወደ ደብረ ማርቆ ፤ ወደ ፍንጌ የእሁት ግሼን በግዞት ተላኩቸው በዚህም ጊዜ ሰው ሁሉ ከአዋቂ ይልቅ ያዘ ጨካኝ ነው እያለ ሁሉም ፈራቸው ይሄን የመሰለ ቅጣት ከተቀጡ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ወደፊት በሃይማኖትና በዚህ ንግሥታችሁ ጉዳይ ብለው አዋጅ ከነገሩ በኋላ ከእርሳቸው ጋር የነበረውን የጭዋ ጦርና ደብተራ በሃገሩ በየመደቡ በየጉዳዩ ላኩት እሳቸው ግን በምሥራቅ ማርያም የቆሲካን በዓል እከብረው ልብሳቸውን ሲያዩት ስተቀው ወደ አትርንስ ማርያም ተመልሰው የኢትዮጵያ ሹማምንት የጭዋ ጦር ጥሪ አድርገ ሁሉም በጥሬው መሰረት መጡ የአዳል ሰዎች ለንጉሡ ነገሥቱ የሚቀርበውን ግብር ከት ብዙ ግምጃ ይዘው መጡና ከመንግሥቱ ቤት ከእርሱ በድባይ ልጅ ተልከናል ብለው ገዘ በረከቱን ከአቀረቡ በኋላ የአዳሉ ንጉሥ መንግሥድን ቤት ጌታችን ሆይ እንግዲህ በመካከላችን ሰላም ይሁን እኛም በየዓመቱ ግብርህን እየያዝኩ እመጣለሁ አንተም ጭዋ ወታደር ወደሃገሬ እየመጣ እያወጣን ብሎ አለና አላቸው ንጉሡ ነገሥቱ በእደምርያም ይህን ከሰሙ በኋላ ደስ ተሰኝተው ሽልማት መታወቢያ ሰጥተው በዋቅር አሰናበቷቸው ከዚያም ተነስተው ወደ ምድረ ዳት ደረሱና ቤተ ክርስቲያን አሰርተው ስሟን ደብረ ተራማርያም ብለው ተከሉ ለካህናቱና ለደብሩ መተዳደሪያ ከምድረበዳዎች ሺህ መስፈሪያ መሬት ሰጡ በዚህም ጊዜ ወደ ደባ ሲዘምቱ የተጠሩትን ወደሃገራቸው መልሰው ሲተ መጣኙ ትእይንት ከታል ሃደር ከነዳብ የመርዶ ጋር ከአዳል ንጉሥ ተልከው ሲመጡት መልሥ አንተው እንዳልከው ይሁን ነገር ግን ቃልህን ብትሽርና ብትከድ ተጠንቀቅ ብለው ላኩበት ።

እንዚህን ከላኩ በኋላ አፄን መርሀ ክርስቶስንና መንኮሳቱን ሰበሰቡና እኔ ወደ ዶባ መሄዴ ነው እናንተም ወደሃገራችሁ ተመለሱ በፀሎታችሁ አትርሱኝ ብለው ብዙ የቤተ ክርስቲያን ግምጃ ሰጡቸው እሳቸውም ከዚያ ተነስተው የጭዋታ ሃገር ደረሱ የዶባ ሰዎችም በሃይማኖት ሆነው ተቀበሏቸው በምድረ ይግባ አድርገው እንዲት ደረሱ የእንጦጦም ሰዎች በበር በዘፈን ተቀበሏቸው በዚያም ሃገር መንበረ ማርያም የምትባል ደብር ተከሉ ከዚያ በዋንዛ በቁጥቋጦ በሚፈ ወንዝ አልፈው ቦላል ደረሱ በዚያም ጭዋን ( ወታደር ) ለአያንዳንዳችሁ ሠፈር አብጅታችሁ ተቀመጡ ብለው አዘዙ ። እነዚህም የጭዋ ጦር የግን ቀንበሩ ፤ የግን ወገና ፤ ስብአባሌ ፤ ግን ሰቀልት ፤ ግን ጉንድር ሌሎችም የፈጠጋር የገድም የገኘ ጭዋ ናቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱም በእዶማርያም የአንበሳ ለምዳቸውን ለብሰው ጋሻና ጦራቸውን በእጃቸው ይዘው ከብዙ ሰራዊት ጋር ወደ ዶባ ደረሱ ።

ይንከሌም የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት በሰማ ጊዜ አንድ ፈረስ አንድ በቅሎ ቱብር ጥብር የተጫኑ ሁለት ጋሻ በወርቅ የተለበጠ ሁለት አሬዥም ጦር የወርቅ ጀንፎ ያለው ነጭ በረከት ላከና እኔም ወላጆችህ ወደዚህ ሲመጡ ለመውጋት ከዚህ በፍሬልሰው አለና ላኩቸው እንዳ ቸውም ጥሩ አድርገሃል ። እንዳያመልጠው ወላጆቻቸው ብለው ላኩበት ።

ከዚያ ብዙ ጭፍራ ጦር ጨምረው የባሌውን ገራድ ሄዶ እንዲወጋ ወደምድር ጋም ላኩን ላኩ ግን አስላሞች በርትተው ከንጉሥራዊ አንድ ሰው ሳያተርፉ ገደሏቸው ንጉሠ ነገሥቱም መምቱን ሲሰሙ ለሠራዊታቸው በመርገት አንድ ጊዜ መሸነፍና ማሸነፍ የቆየ ነውና አሁን ፍርሃት በሀሊናችሁ አይግባ ልባችሁን እሰኑ እግዚአብሔር በጊዜው ይረ ዳናል ብለው ተናገሩ ነገር ግን የሆድ በሽታ ስለተነሳ ይፋትን ለቀቁና የትግሬ መኮንን ግባት ወደሚሆን ወደምድረ ሃያ ሄዱ ባለቤታቸውን ምድረአይዳ እንዲቀመጡ አዘዙ ።

ንጉሠ ነገሥቱ በእዶማርያም አባቴ ዘርአያዕቆብ በተገኙበት ያዘዙ ብርሃን እንደመሩ እኔም ደግሞ ለመሞረድ ይችን ታሪክ መጽሐፍ ምምቀንም አምባ በሮዶት በኋላ ብለው አዋጅ አስነገሩ ።

ከዚህ በኋላ የዐለምት ነገዶች ንዶድ የሚባሉትን ሲወጉና አገር ሲያቀኑ የሺዶትን የዘን አምራ የጭዋ ጦር ከፍራሾች ከወለምት ጋር እንዲ መጡ ላኳቸው እነሱም እንደመጡ ግን ሆዶ እኛ ከንዶድ ሰዎች ጋር እየተዋጋን ያገር አቀናን እንትም ወደ ዶብአ በዘመትክ ጊዜ እኛን ሰዎን አትወደንም ነበር አባትህ በዚህ አገር የተከለን ልንዋጋ የንጉሠ ነገሥትን ጠላት ልናጠፋ ያገር ልናቀና አልነበረምን ! አሁንም ጭዋ ወታደር ሁሉ በሚያውቀው ሃገርና መንገድ አራሱን መዋጋት አለበት ስለዚህ እኛ ባርችህ ጠላቶችህን እናጠፋለን ስለእንተም እንዋጋለን አሉት ። የዶብአ ሰዎች ንጉሠ ነገሥቱ እንደማይለቋቸው አውቀው ወደ አዳል አገር ሲሰደዱ ንጉሠ ነገሥቱም መሰደዳቸውን ሰሰሙ የትግሬ መኮንን የሚመራቸውን የጭዋ ጦር የቅንዓ ፃዐፈላህም የዳሞ ትን ፃዐፈላህም ልከው አሰወጓቸው ግማሹንም ማርከው አመጡቸው ከዶብአ ሰዎች የተማረኩትን ከብት ለግን አምራ ፣ ለግን ቀንጠፋ እንዲጠብቁ ምረት ሰጣቸው ምህረት የለመኑትንም የዶ ብአን ሰዎች ወደክርስቲያንነት መልሰው የተማረከውንም ከብት ሰጥተው በመካከላቸውም ዳዊት አምባ በሚባል ገደር የሚባሉትን የጭዋ

ቁጦር ተማሪ አደረጓቸው ። ብዙም አታክልት ትርንጎ ፣ ሎሚ ፣ ወይም ወይን አስተክለው በተክርስቲያን ተክለው የደብሩን ሃገር አሰሙን በዚሁ ሃገር ላሉ ባለቤታቸውን በአልተሸፈነ የሚባሉትን ዳዊት አሬ አስኝተው በታውን ዳዊት አምባ አንገቧቸው በዚሁ ቀን ለጭዋ መር ጋሻ መር በያዛቸውበት እጅ ማረኛ እየያዛቸው እረሱ አገሩን አልሙት የሚያ አዋጅ አስነግረው ከዶብአ ወደ አንጉት ጉዞ ጀመሩ. አንጉትን አድ ርገው ወሲል ከወሲል ግድም ሄዱና ቢላዎ ግዜያ ፈረሱና ከርቻ ጥሩ ያስቆጥሩ ጀመር ከዚያም ወደ ይፋት ሄደው ምድረቀዜና ደረሱ ከዚያም ሳይውሉ ሳያድሩ ወደ ጋሲዶ ወንዝ ሄደው እደሩ በዚህን ጊዜ የደብረሊባኖስ መነኮሳትና የደብረብርሃን ካህናት በሥርዓት ሆነው ድባብና ልብሳቸውን ይዘው ሊቀበሏቸው መጡ በዚያን ጊዜ ይወዷቸው የንበሩት አቡነ ይምርሃነክርስቶስ ከፊታቸው በደረሱ ጊዜ እጅ ሲነሱ ከደስታ ብዛት ወደቁ አጼውም አንሷቸው ብለው አዘው አስነሷቸው ከዚያም በተቀባያቸውና በሠራዊታቸው ታጅበው ወደቤተክርስቲያኑ ገብተው ተሳለሙና ሁሉያውን ሁሉ አየሁሩ ተመልሰው ሲጨርሱ ወደመኖሪያቸው ሥፍራ ደረሱ በልጅነታቸው የተከሉትን የቀጋ ዛፍ አፍርቶ አዩትና ግምጃ አለበሱት ከደብረብርሃን የልጅነታቸው ጊዜ ወደ አሳለፉበት ሥፍራ ወደ ምድረገነዥ ደርሰው ከረምቱ እስከሚ ያልፍ በዚያው ከረሙ በዚሁ እንዳሉ በየምሽ ሃያ አራት ቀን ማሪ ዮስ የሚባለው ግን ደረባ መጣና ርሃና እመቤታችን ወንድ ልጅ ወለደች ብሎ ነገራቸው ንጉሡ ነገሡቱም በጣም ደስ አላቸውና ግብር አደረጉ በአርባ ቀን ክርስትና ሲነሳ እስክንድር ብለው ስሙን ሰየሙት ሁለተኛ ደግሞ ከአራጂ ገቢት ቴዎድሮስ የሚባል ልጅ ተወለደ ።

ከዚህ በኋላ የደጃር ጭጥ የባሌንና የዳዋሮን ሃዲያ ጭጭ ሠር ወደ አዳል ሃገር እንዲዋጉ ላኳቸው እነሱም ጠላትን አጥፍተው በደ ህና ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር በደስታ ደጃር ላይ ተገናኙ ያንም ሀገር አላ ማሉ ይባላል ያንም የባሬው አስቦት ነው ። በዚያው ሳሉ እንበባ ዳዊት የሚባለውን ጉግም ነጋሽ ግብረን ይዘው ና ብለው አዘዙት እንበባ ዳዊትም በደንባና በሸለታ በቀዋሬ ያሉትን ሸኒና የጋፋትን የጭጭ ሠር ይዞ በብዙ ሠራዊት ታጅቦ በዙ ወርቅ ግንዘብ ይዞ ከአጼው ጋር ተገናኙቶ ግብሩን አገባ በእደ "ማርያም" ከልብ ወደዱት አርጋቸውም ልጅ ይሁንህ እንተም አባት ሁነው ብለው እስክንድርን ልጃቸውን ሰጉጀው ንጉሥ ለእንበባ ዳዊት እንደተቀመጠ ከምሳ ላይ አስቀመ ጡለትና በዚሁ ቀን ትልቅ ግብር አደረጉ ለዘኤንም ብዙ ሃብት ሰጡት በዚሁ ጊዜ የንጋድ በሽታ የዘን ከምር ልጅ እንበባው ዳዊትን ያዘውና

በድንገት ሞተ በዚህን ጊዜ ንጉሡ በጣም ከአዘኑ በኋላ ብዙ የጭፍ ጦር መርጠው ሰማቸውን ዳዊት የረሳ ብለው የእንበሳ ዳዊትን ልጅ ንጉሥ ጉጃም ወዳሞት አሰኘተው ስመ መንግሥቱን ወሰን ሰገድ ብለው ወደበሊያ ላኳቸው በዚሁ በሽታ ከአጼ ያዕቆብ ጀምሮ የጦር አሊቃ የሆነው ተክለማርያም ታመመና ሞተ በዚሁ በአዳማል ሳሱ ርምና የሚባሉት ባለቤታቸው ወንድ ልጅ ወልዱና ስሙ እንቶእስራ ኤል ተባለ በዚሁ ወር የጓራዶ ገብረኢየሱስ በባሌ ያሉት ጭፍ ጦር ወደአዳል ሲሄዱ አድመቸል ተባለና ከባሌ ዳሞት ተጠርተው ተያዙና ተገርፈው እንደወንጀሉ እጅ እግራቸውን ከአስቆረጡ በኋላ ግማሹን ጉጃም ከሚገኘው ገምቦታ ምድር በጉጃሙ ነጋሽ በሃይት አጠገብ ወደሚገኘው ግሼን በማዞት ተላኩ ከአዳማል ወደአባሊ ሃገር እያቀኑ ሸዋ ገር እያደረጉ አጼ በእደማርያም ሲሄዱ ሳለ የአዳል ባላባቶች ገራዶች ማመጻቸውን ሰሙ በዚህን ጊዜ ብሆት ወደድንና ባሌ ገራድ የሆነውን ገብረኢየሱስን ከባሌና ከድዋሮ የጭፍ ጦር ጋር በሚያውቁት ሄደው እንዲወጋቸው አዘዙት እሱም አዳል ሃገር በደረሰ ጊዜ ወረራ ሊያደርጉ ለጦርነቱ ተዘጋጅተው አገኘና ጦርነት ጀምረው የሚበዙትን ገደለና የቀሩትን ማረኩ ቸተማረኩትም ቁና ቁና ባላባቶች እነዚህ ናቸው ጉይታ ሰድድ አህመድ፣ ሺህ አሉን ከድር ፤ አርር ገራድ ግራድ ፤ ኮሽም ከራድ ሃንጋይ ገራድ ፤ ግደይ ገራድ ፤ ፍራሽ ገራድ ፤ ሌሎች ባጠ ቃላይ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ናቸው ።

እነዚህን ሁሉ ከማረከ በኋላ ወደንጉሡ ነጋሪት ድል ማድረጉን የሚ ገልፅ ደብዳቤ ላከ ስለዚህ አጼ በእደማርያም ለእግዚአብሄር ምስጋና አቅርበው ለዚሁ ደስታ ቃል ለሠራዊቱ ሁሉ ተናገር ታላቅ ግብር አድርገው ስንበቱ ነገር ግን በዚህ ጦርነት ዋናው የአዳሉ ንጉሥ ኡት ማን ቢይ ስላደማን አልተያዘም ወይም አልተማረከም ነበር ስለዚህ የማራውን ብሆት ወደድ መሀሪ ክርስቶስን የቀኙን ቢትወደድ ገብረ ኢየሱስን ገራዶቹንና የጭፍ ጦርን ሁሉ እስላሞችንም ከሁለት ከፍ ለው በሚያውቁት እንዲመሩ ተደረገና ወደአዳል ሄደው ያልገበረውን አገር እንዲወጉ አዘዙቸው በዚሁ ቢታህሳስ ወር ወደ አዳል የዘመቱ ትን ሁሉንም እስላሞች አቸንፈው ገደሏቸው ንጉሡ ነጋሪቱም ስም ቸው አዘኑ አጼ በእደ ማርያም በየካቲት ወር ከዚያ ተነስተው ገበርጌ ሄዱ ።

በገበርጌ ሳሉ ናእድ ተብሎ የተሠየመው ቀለዩዱ ከአረጁ ገዜት ተወለደ ከዚያም አልፈው ምድረ ወገማር ሄደው ከረሙ አጼ በእደ ማርያም ከነገሡ ሰባት አመት ሆናቸዋል በዚህ ጊዜ ልጆቻቸው ከሮ

ምና ቀኝ ባልቲዎች ፤ (እሌኒን ቀኝ ባሉቲዎችን ሳያገቡ) እስክንድር እንቁ እስራኤልን ከእሬጂ ግዛት ግራ ባልቲዎች ግን ሰይፉ ቴዎድሮስና ናኦድን ወደንገዘ ሄደው ሆነና ሥርዓት እንዲያወኑ ብለው ንገዘ ገራድ ማቲዎስን አዘዙና ከዚያ ተነስተው የደዋሮው ገራድ መሐመድ በጉቲ አረዋዶቱን ቀኝ ባልቲዎች እሌኒን ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ምድረ ዲማ አራራ ጉጀም ውስጥ ሄደው ተቀኑ ዘመን ቆዩ እቴጌ እሌኒ መርጦ ለማርያም የተከሉላቸው በዚያው በሃራራ ላይ ነው ። ንጉሥ ነገሥቱ በእደ ማርያም ንግሥት እሌኒን በጣም ወደዷት ምክንያቱም በዘርዋ የቆሉ እስላም ሆና ስትኖር በደዋሮ ላይ በወባይዋና በመልከዋ ተመልክተው በሰእነቢዋና ክርስቲያን ስላደረጓት ከዚያ ወዲህ በእግዚአብሔር ዘንድ ምልዋችና ቁርባን የምትፈልም ሃይማኖትና ምግባር የተሞላች ፍልምት ስለሆነች በሌላ በኩል ንግግርና ምክር ሆነና የማሰደን ሥርዓት የምታስተምር ስለሆነች ነው በዚሁ ሁሉ ምክንያት እንደናት እንደመቤት አድርገው ንጉሥ ነገሥቱ ይመለከቷት ጀመር ። ከዚያ እንደገና ልማድ ጠይቀው እንደነገሯቸው ሥርአተ በራኬ ለመፈጸም ባለሆኑችን ከአማራ ውስጥ ከአራብት አስጠፍና በጉናቸው አስተምራቸው ባለሆኑችም የለበሱት እንደ ደንቡ በርኖስ ነበር ሃገሩ የዛሬ ዲማ ጊዮርጊስ ነው በነርሱ መካከል ከጉብሬ ሞሀደና ከማርቆስ ከማሬና ከቀኝ ጌቶች በቀር ማንም አልነበረም ከዚህ ቀጥሎ እነዚህ የአማራ ባለሆኑች እንደደንባቸውና እንደህጋቸው በአባተከለእልፍ ከባረኳቸው በኋላ ወደ ሚወዷት ደብር ወደ አትሮንስ ማርያም ተመለሱ ከዚያም እንደደረሱ የቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስን አፅም ከመሪማሌቱ የማርማ እስፈሬን አፅም ከአሥር የሌሎችንም ነገሥታት አፅም የዳዊትን አፅም በክብር በአትሮንስ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስቀመጡት በልጅነታቸው ዳዊት አስደግመው አዲስ ያስቀፀሉአቸውን የመምህራቸውን የተክለአልፋሉስን አፅም በዚያው በደብረ ንጉድጓድ ተመልሶ ከመቅደስ ውስጥ እንዲቀመጥ አደረጉ ። በዚሁ አመት ብዙ ሽልማት ለአስተማሪዎችና ለጭቃ ሹም ለጨዋ ጦር ሰው በአትሮንስማርያም ላይ አንድ ሮማዊ ስእል ባይ አስመጥተው ንጉሥ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአስረኛው አመት የማርያምን ስእልና የኢየሱስን ስእል አስለው እንደአስጨረሱ ብዙ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች እንጉረመረሙ ይሄውም ማርያም ልጇዋን ኢየሱስን ያቀፈችው እንደልቁን "ካቶሊክ ተከታዮች በግራ እጅዋ ስላቀፉችው ነው ። ይሄውም እንደ እስክንድርያ ቤተክርስቲያን በቀኝ አድርጉ ለምን አልሳለትም ነው ።

በዚህ የተነሳ ብዙ የውስጥ ጠላት ካሆናትና ፊራማ ማመርችና ዛሬን ማሰሮች ተነሱባቸውና ባልታወቀ ህመም ታመው ሊሞቱ ሲሉ ልጃቸውን እስክንድርን እንዲሞሱት ብለው ለህዝቡ ይኸን ቃል ተናግረ በተወለዱ በሰላሳ አመታቸው አሥር አመት ኢትዮጵያን ገዝተው በአ ገድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አመተ ምህረት አረፉ በዙፋናቸው ልጃ ቸው ቆስጠጢኖስ ይባል የነበረው እስክንድር ንጉሠ ነገሥት ዘኢት ዮጵያ ተብለው ነገሡ ።

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

## የአጼ እስክንድር እና የአጼ ናኦድ ዘመነ መንግሥት

ከአጼ በእደ ማርያም ከመጀመሪያው ባለቤታቸው ከሮምና የተወ
ለዱት እስክንድር አባታቸው በነገሡ በሶስት አመታቸው ነው አባት
የው ሮምናን ሲያገቡ የአስራ አምስት አመት ወጣት ነበሩ ሮምና በቤተሬ
መንግሥቱ ያደጉና የበእደ ማርያም ሞግዚት ሆነው ያሳደጉ ስለሆነ
ወጣቱን በእደማርያምን ሲያገቡ የሃያ አንድ አመት እድሜ ነበሩ የጐ
ጃሙ ንጉሥ እንበሳ ዳዊትና ብዙ የጭዋ ጦር በንዳድ በሽታ በደዋሮ
ሲያልቁ ሮምና ንግሥት በዚሁ ንዳድ በሽታ እንቆ እስራኤልን እንደ
ወለዱ ሞቱና ተከታይቱ የደዋሮው ባላባትየገራድ መሃመድ ባንቲ ልጅ
እሌኒ ቀኝ ባልተሂት ክብራ ብለው አባታቸው በእደ ማርያም ስላገቧ
ቸው እሌኒም ክብራ የሟቺቱን ልጆች እስክንድርንና እንቆ እስራኤልን
እንደወለዱት ልጅ አድርገው በእንክብካቤ አሳደጓቸው ከነንዝ ከአማራ
ሃገር እስመጥተው በዚህን ጊዜ ሊቃውንቱ ዕራግ ማሰሬ ሊቀ ደብተራ
ቀሲስ አጼ ፥ህጐን ፈጽመው ሥርአቱን አዘጋጅተው የሰባቱን አመት
ልጅ እስክንድርን በሺህ አራት መቶ ሰባ ዓ/ም በአባታቸው ዙፋን
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥታቸውን ቆስጠጢኖስ
አሰኝተው አነገሷቸው የነገሡበትም ሃገር ምድረ የለብሳ ይባላል ።

አጼ እስክንድር ህፃን ስለነበሩ አሳዳጊ እናታቸውን በዚሁ እሌኒ
ቀኝ ባልቲሃት እሌኒን የንግሥተ ነገሥታት ዘውድ ደፋላቸውና ስማቸ
ውንም ዳግማዊ ክብራ አሰኝተው አብረው እንዲሠሩ ተደረገ አቃቤ ስርዓት
ተሰፋ ጊዮርጊስ ግራ ብሀት ወዳድ አምደሚካኤል ቀኝ ብሀት ወደ
በኋላ ርእድ እነዚህ ሁሉ በሥራም ከአሳብም ህግና ሥርዓት ለመውጣት
ያግዟቸው ነበር ።

በነገሡ በሶስት አመታቸው ከኢየሩሳሌም ብዙ ጳጳሳት መጡ
ካህናት በረከቱ አብያተ ክርስቲያናት በየቦታው ተተከሉ በየሃገሩ
ደስታ ሆነ ከምድረ የለብሳ ተነስተው ወደ አምሃራ ሃገር ሄደው ገነ
ጊዮርጊስን ደብረ ነጐድጓድን አትሮንስ ማርያምን ጐበኙ ።

በዘመናቸው ቤተክርስቲያን አስርተው ካህናት ደልድለው ሲጨርሱ ደብረ ምሥዋእ ብለው ሰየሙት በነገሡ በአስራአምስትኛው አመት ወደ አዳል ሃገር ሄደው ዳካር ደርሰው ቢቆዩም መስጊዱንም አፈራርሰው ሲመለሱ በሌላ በኩል ያሉት እስላሞች የምትወደውን አንጫጋ ደሀን ተከልደን የአማራ ጉዛ የሆነው ገደሏት አሏቸው ። እንዚያ ማያ አርማያ (አረመኔ) የሚባሉት የአርሆ ሰዎች ንጉሡ ንጉሥቱ መሆናቸውንም ሳያውቁ በጨለማ ከበው ወግተው ገደሏቸው ።

በነገሡ በአስራ ሶስት አመት በ፲፬ አራት መቶ ሰማንያ ሰባት አመተ ምህረት ግንቦት አስራ ሁለት ቀን አረፉ የንጉሡ ንጉሥቱም አፈሳ ከጸንበኛው ሥፍራ ሄዶ ከመተበኑ በፊት ዘሰሉስ ወገኖቹን ይዞ የእስክንድርን ልጅ እንድርያስ የሚባለውን አምጾልዮንን አነገሡ ነገር ግን የእስክንድር ጭፍራ ጦር ዘሰሉሰን እስከስራዊቱ ገደሉት ጌታቸውን በአሻጥር ማስገደሉን ያውቁ ነበርና ተበቀሏቸው የጌታቸውንም የእስክንድርን አፅም በአስሩት ደብር በደብረወርቅ ቀበሩ ። በዚያን ዘመን እንዳይሸፍት እየተባለ የነጋሲው ልጅ ሁሉ እየተያዘ በአምባ ግሼን በወሎ በዘበኛ ይጠበቅ ነበር የነበረው ንጉሥ ሲሞት ሌላ ለተናዘዘለት ይሆናል ነገር ግን እንደዚሁ እንደ አጼ እስክንድር በድንገት ለኑዛዜ ሳይበቃ የሞተ እንደሆነ የቤተ ክህነቱና የቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች የመረጡት እየወጣ በእጩነት ይነግሣል ። ይሄም የሆነበት የሀገሪ ደም በከንቱ ከማፍሰስ ለማዳን የተዘጋጀ ሥርዓት ነበር ።

ሆኖም ግን በአጼ እስክንድር ጊዜ በእንደራሴነት እንቁን ያስተዳድር የነበረው ብሁት ወደድ አምዳና ዘሰሉስ ናኦድን እንዳይነግሥ ወደአምባ ግሼን ወሰዱ ልኮው የአጼ እስክንድርን የሰባት አመት ልጅ እንድርያስን ሰመ መንግሥቱን ቀማሚ አምጾልዮን ብለው አነገሡት ነገር ግን አምጾልዮን ሰባት ወር እንደነገሡ ስለሞተና ህዝቡ ናኦድን ይወዳቸው ስለነበር በቤተ መንግሥቱ ሁከት ስለተነሳ ከአምባ ግሼን ናኦድን አስመጥተው ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው አነገሷቸው ስመ መንግሥታቸው አንበሳ በዘረ ተባለ የዘአደ ማርያም ልጅ የአጼ እስክንድር ወንድም አጼ ናኦድ በሀገር ጦር በነገሡ ጊዜ ሃገር ፀጥ አለ የኢትዮጵያ ህዝብ በስርዓት እንዲሩ ኩራተኞች ብሁት ወዳድ አምድና ዘሰሉሥ እራሳቸውን አዋረዱ ከቀዮች አማካሪዎች ተወገዱ ምርኮ ሰዎች ተተኩበት አጼ ናኦድ ከአማራ ሃገር ከአትሮንስ ማርያም ወደሸዋ ሲመለሱ ጉዞ ሲጀምሩ ግራ ብሁት ወደድ ተካ ክርስቶስ የጭፍራ ጦር ፈረሰኞቹንና ወገኖቹን አዘጋጅቶ ሊወጋቸው እንደተዘጋጀ ሰሙ ።

አጼናኦድም ይህንን አድማና ተንኮል ሰምተው ምኞቱን ይፈ ጽም እኛ እንደሆን እግዚአብሔር ከኛ ጋር ስለሆነ ይረዳናል በእርስ ላይ ክፋት እንዳንጀምር በመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥ ዙፋን ላይ እንቀመጥ እሱ እራሱ አስምሎናል የሚል ቃል ተናግረው ጉዞአቸው ወደአሰበት ሄነር ቀጠሉ በዚህን ጊዜ በይፋት ያሉት የፅዋ ጦር ስብስበው ለመውጋት ሲል ወደይፋት ሄዶ ሳለ በይፋ ያሉት የንጉሥ ጭፍራ ጦር ይዘው አስሩና ንጉሡ ነገሥቱ ወደሠፈሩበ ድልብድ ማዳ ሄዱ አጼናኦድም እግዚአብሔርን አመስግነው ጠላቶቻ ውን ስለአዋረደላቸው ተመልከተው እሳቸውም እንዳይገደል በማዘ እንዲቀመጥ አዘዙ ነገር ግን ጠባቂዎች አይኑን አጠፉት ከዚህ በ ህዝብ በአጼ እስክንድር ዘመን ይህን መርተዋል ይህን በድለዋል እያ ሰው እርስ በርሱ በመካሰስ ሁከት መብዛቱን ባዩ ጊዜ እንደ ይሄን ሥራ እንኳ ይህን በደል አያሳችሁ እትካሰሱ ወደፊት እንዳ ባዋደኛውን እንደዚህ ብሎ ቢከስ በሞት ይቀጣ የሚል አዋጅ አወ ህዝቡ የዚህን አዋጅ ትእዛዝ በሰማ ጊዜ ጥፋት የሌለበትና ያልበደለ ሁሉ በመካሰሱ ሁከት ሆኖ ነበርና እንኳን ይሄን አዋጅ አወጡ እ ተባባለ የአጼ ናኦድን ብልሀነትና እውቀት በየቤቱ እያነቀ በመራቅ በርስት ነገር የተጉዳው ፍርድ እንዲታይለት ተሾመው ነበር ።

አጼ ናኦድ በዘመናቸው እንደአባቶቻቸው ከእስላሞች ጋር እየ ዋጉ የበረቱትን እያሳዩ በሌላ በኩል ደግሞ በሰላማዊ መንገ ፍቅር ለመመስረት የጋብቻ መንገድ ፈለጉ ። አጼ በርእያቀብ በስላም በክርስቲያን መካከል ፍቅርና ሰላም እንዲመሠረት ብለው የሃድያው ባላባት የገራድ መሐመድን ልጅ የማሂትን እሁት ክርስትና አስነስተው ስመ መንግሥቱን ዋን ዘይላ(የሰማል ንግሥት) ብለው አግብተው የአጼ ናኦድን እባት በእደማርያምን ወለዱ አጼ በእደ ማርያም ከዶ ሮ የገራድ መሐመድ ባንቲ ልጅ እረሞዳቱን እሌኒ ብለው ስመ መ ግሥቷን ዋን ከብሬ አስኘተው በእግሬ ሆነ እንቡ ስለዚህ እሁን አጼ ናኦድ ከዚያው ከዶሮዋ ስላሚቱን የቱሉ በዲሳን ልጅ ባላባቱን እን አባቶቻቸው ሳልሳዊት እሌኒ አስኘተው ስመ መንግሥቷን ናኦድ ሞገ ብለው አገቡ ዳሩ ግን ይህ ሁሉ የጋብቻ ዝምድና በክርስቲያኖችና በእስ ሞች ዘንድ ፍቅርና ሰላም ሊመሰርት አልቻለም ይሄውም የእስላም ሃይ ኖት ተከታይ አገሮች ቢቻል የኢትዮጵያን መንግሥት በእስላም ሃ ማኖት ለመቀየር ባይቻል የዛይላንና የደዋሮን የሃድያን የሌሎችንም የ ላም ሃገሮች ከክርስቲያኑ መንግሥት ለመነጠል በየመን በጂዳ በካይሮ እንዲሁም በበላያቸው በቱርክ እየታዘዙ ያላደረጉት የሰውና የመሬ

ሪያ እርዳታ የለም በዚህን ጊዜ ከባህር ማዶ በመጣለት አዳዲስ መሳሪያና የጦር ጭፍራ ማህፉዝ የሚባል የክርስቲያንን መንግሥት ለመውጋት ተነሳ አጼ ናአድም ማህፉዝን ለመውጋት ሄዱ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት አጼ ናአድ የጦርነት መላ ያውቁ ስለነበር ብዙውን ጦር ወደኋላ ሸሽገው ትንሽ ጦር ወደፊት እንዲቀድም አደረጉ የማህፉዝ የባህር ጦር ጭፍሮችም ትንሽ ጦር መስሏቸው ውጊያ ጀመሩ በዚህን ጊዜ ከኋላ የነበረው የአጼ ናአድ ጦር ደረሰና የእስላሙን ጦር ፈጀው ።

ስለዚህ ማህፉዝ የባህር ጦር በራሚቱ መሞትና መማረክ በሰማ ጊዜ ደነገጠ ፈራ በስማህፉዝ ጀግንነትና የውጭ ረዳት ኃይሎች በመሞታቸውና በመማረካቸው ከድንበር እስከድንበር ያለው የዘይላንና የታጁራ ነዋሪዎች ደነገጡ ፈሩ በዚህን ጊዜ የአዳል ሱልጣን በአጼ ናአድ ሠራዊት መወጋቱን ሲሰማ ለአጼ ናአድ እንዲገደስ አለም የሚልና ብዙ ጊዜ እየተማረኩ የሄዱትን ክርስቲያኖች ንጉሡ ነገሥቱ እንዲያመጡብኝ ብሎ አስቀድሞ ላከላቸው አጼ ናአድም በድል አድራጊነት በጭፍ ሠራዊት ታጅበው በታላቅ ክብርና ደስታ ወደ ቤተመንግሥታቸው ተመለሱ ።

ከዕለታት አንድ ቀን ለመኳንንቱና ለመሣፍንቱ ግብር አድርገው በሚነጋገሩበት ጊዜ ልብነ ድንግል የሚባለው የአጼ ናአድን ልጅ አቶትና ከሚነጋገሩት አንዱ መስፍን ይህ ልጅ አደገ ስምንት አመት አለፈው እኮ ቢል ልጁ ሰምቶ ደነገጠና አወን ለአምባ ነገሥት ግሼን ይርቻለው ምነው ከንጉሥ ባልተወለድኩ ብሎ ምርር እያለ አለቀሰ በዚህን ጊዜ አጼ ናአድ ሲያለቅስ አቶትና ልባቸው በሃዘን ተነክቶ ከልጅዋ ማንንም ወደ አምባ ግሼን አልወሰድም ብለው በመሳፍንቱ ፊት ማሉ እርሳቸውም ከሞቱ በኋላ ደህን ቃላቸውን ጥሰው ልጆቻቸውን ወደአምባ ግሼን እንዳይልኩባቸው መኳንንቱን አስምለው ቃል አስገቧቸው ።

አጼ እምደረዮን በበመናቸው በዚሁ በአምባ ግሼን ተራራ ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን ስም ለማሰራት መሠረያውና እንጨቱ በሰንት ችግር በተራራው እየወጣ እንዲሠራ አዘዙ ነገር ግን ሥራው ከማለቁ በፊት እርሳቸው ስለሞቱ ልጃቸው አጼ ልብነ ድንግል አስጨርሰው የእመቤታችንን ታቦት አስገቡላቸው የቤተ ክርስቲያኑ ሥራውና አድራሻ ከብሮቱ በኢትዮጵያም እንደሚገኘው እንደ ቅዱስ ጥልቅታ ነው ።

እጼ ናኦድ ይህን የእመቤታችን ቤተክርስቲያን ሲያሠሩበት የቻሉበት በዚሁ በአምባ ግሼን ውስጥ ሲጠበቁበት በነበረ ጊዜ ስለት አድርገው ስለነበር ነው ከመንግሣቸው በፊት እንደጸጸቁ ላሊበላ ድንጋይ ተከሰተበት ነበር በዚያም ድንጋይ ላይ ቆመው መልከማርያም የደረሱበት ሥፍራ ነው ይህ መልከማርያም በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በየበዓሉ ቀን እየታደለ የሚደገመው ምእመናን ሁሉ የሚጸልዩበት ጸሎት ነው ።

እጼ ናኦድ የሊታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን እናት ድንግል ማርያምን ከልብ ይወድዋትና ያከብሯት ስለነበር በየ ቀኑ በስሟ ሳይዘክሩና ያጠፉን እስረኛ ሳይፈቱ ውለው አያውቁም በሌላ በኩል ደግሞ ለስሟ ሲሉ አንዳንድ የእመቤታችን ስም የሚነሳ ቅኔና የጸሎት መጽሐፍ ሳይጽፉና ሳይደርሱ ውለው አያውቁም ።

እጼ ናኦድ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብለው አስራ ስምንት /18/ አመት ገዝተው በሺህ አምስት መቶ ዓመተ ምህረት ሃምሌ ሰባት ቀን አረፉ ።

በዚህን ጊዜ ልጃቸው እጼ ልብነ ድንግል በዙፋናቸው ላይ ተቀመጡ በሚወድዋትና በቀደሷት ደብር አምባግሼን ተቀበሩ ያኔ ውም አመት አለም እሳቸው ሲሞቱ ሰባት ሺህ ሆነ ።

/ከዚህ ቀጥሎ የእጼ ልብነ ድንግልን ታሪክ/

## ምዕራፍ ሀያ

የአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት የግራኝ አሕመድ ወረራ ዘኢት ጉሉ ማከዳ ዘመነ መንግሥት ከእስያ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን ግእዝ ተናጋሪዎችን አግአዝያን በማለት አበውሰውያን በአ ፈው አበሺ የተባሉትንና የልጆቻቸውን የተቆጣጣሪ ሚኒሊክ ዘርኝ ታሪክ። ይኩኖ አምላክ የተባለው የተስፋ ኢየሱስ ልጅ ውድማራድ የውድማራድ ልጅ አምደጽዮን የአምደጽዮን ልጅ ንዋየ ክርስቶስ የንዋየ ክርስቶስ ልጅ ዳዊት የዳዊት ልጅ ዘርአያዕቆብ የዘርአያዕቆብ ልጅ በእደማርያም ልጅ ናኦድ የናኦድ ልጅ ልብነ ድንግል ።

አጼ ናኦድ አስራ ሶስት አመት የኢትዮጵያን ሃገሮች ገዝተው ሲሞቱ በሺህ አምስት መቶ ዓ.ም የአስራ አንድ አመት ወጣት ልጅ ልብነድንግል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሆነ መንግሥት ወናግ ሰገድ ተብለው በአባቶቻቸው ዙፋን ተቀመጡ በሱማሌ ወናግ ሰገድ ማለት አንበሳ ሰገደለት ልብነድንግል ማለት በግእዙ የድንግል እጣን ልብነ የተባለው ልባንጃ ወይም ሉባን የሚባለው የድንጋይ እጣን ነው ።

አጼ ልብነ ድንግል ወጣት ልጅ ስለነበሩ የመንግሥቱን ሥራ እናታቸውን የደግሮጵሉ የቱሉ በዶሳ ልጅ ማልማዊት እሌኒ ቀን ሰኔ የቀድሞ አያታቸው የአጼ በእደ ማርያም ባለቤት ዳግማዊት እቴጌ እሌኒ ግን ከብሬ ዶሙሩትና ያዙበት ነበር የናኦድ ሞገሳ እናት ቁሉ በቤተ መንግሥት መዛሬ ነበሩ በዚሁ በአስራ አምስተ ኛው መቶ ዓ.ም ላይ ሃያላን መንግሥታቱ የነበሩ የቱርክ የመስ ኮብ የጀርመን የእንግሊዝ የፈረንሳይ የኢስፓኝ ናቸው ነገር ግን የፖርቱጋል መንግሥት የባሕር መርከብ አዘጋጅቶ ሃገር በመያዝ እስቀድመው ከሃገሩት ከቱርኮች ጋር በቀይ ባሕር እየተመላለሰ በየ ጊዜው እየተዋጋ ሲሸንፍና ሲያሸንፍ ከሰድስቱ መንግሥታት በለጥ ብሎ ይታይ ነበር በሰዚህ ትልቅ መንግሥታት ና ከርስቲያን በመ ሆን ያሉት ውስጥ በእንግሊዝ ከተማ የምትገኘው የአጼ በእደማርያም ባለ ቤት እቴጌ እሌኒ ግን ከብሬ ከፖርቱጋል ንጉሥ ከአማኑኤል ጋር ለመወ ዳጀት ማቴዎስ በሚባል ጀንደረባ ደብዳቤና ገፀ በረከት ላኩ ።

ማቴዎስም በተባለ በሰባተኛው አመት ከዋናው ከተማ ሊስቦን ደረሰ ከንግሥቲቱ ከዳግማዊት እሌኒ ግን ከብሉ የተላከውን ደብዳቤና ገፀ በረከት ለንጉሥ አማኑኤል አስረከበ ።

የፖርቱጋል ሀገብ ከምረት ምሬታንያና የኖርማንዲ መንዲ ጉሳዎች የጸደ ዘር ነው ይህ ምረትና መንዲ የሚባሉት የጥንቶቹ መደባይ አርመን ወይም በግእዙ አረመኔ በሉባው አርሞ የሚባሉት የባሬዎቹ (ጋላዎች) ናቸው ፖርቱጊዝ ካለ የግእዝ ሰዎች አግአዝ ያን አብረው ሄደዋል በማለት ነው እንጂ ዋናው ስም በላቲን ቋንቋ ፖርቱጋል ወይም ፖርትጋል ነው ደብዳቤው የተሰከበት ጉዳይ ዋናው መቀመጫው ቁስጥንጥንያ አስማምዑል የሆነው የቱርክ መንግሥት በባሕም እንደኛና በተከታዩ በሱሊማን ዘመን የክርስቲያኑን የቁስጥንጥንያን መንግሥት አጥፍቶ በግብፅ በሶርያ በሊባኖስ በጋሊሊትን በግብፅ በአረብ አገሮች ከተቆጣና ሥልጣኑን ከዚያን ወዲህ በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን ሱዋኪን ምፅዋን ዳህላክን አዶሊስን ታጁራን የዛሬው ጅቡቲ በርበራን ዋንዚባሬን /ታንዛንያ/ ዝይላን ስለያዘና በያዘውም ሀገር ላይ ክርስትያኖችን እያጠፋ የእስላምን ሃይማኖት ብቻ ስላፀና ነው ደብዳቤውም የሚለው ዋናው ቁም ነገሩ የእኛን የጦር ወታደር ከክርስቲያኑ ከእናንተ ጦር ሃይል ጋር ብናደባልቀው እግዚአብሔር ከፈቀደደልን የሃይማኖት ጠላታችን የሆኑትን እስላሞችን ለማጥፋት እንችላለን ።

ቅድስት ኢየሩሳሌምንም ከነሱ እጅ እናወጣታለን አሁን ያለንበት ከተማ ከባሕር አርቆ ስለሚገኝ እኛም የባሕር ጦር ለማደራጀት ስላልቻልን መርከበኛ ወታደር የለንም ስለዚህ ከናንተው ከባሕር ጦር ጋር ለማደባለቅና ቃል ኪዳን ለማድረግ እንፈልጋለን 2ኛ/ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻችን ወንዶች ልጆቻችሁን ለሴቶች ልጆቻችን በማጋባት በዚህ በጋብቻ ለኛ ደስ የሚያሰኘን /ለሁላችንም ዝምድናን የሚመሰርት ታላቅ ጥቅም ነው የፖርቱጋል ንጉሥም ፍፁም በሆነ በክርስቲያን መንግሥት የሚመራ የምስራቅ ኢትዮጵያ ንጉሥ አለ ማለት ከዘንድ ግዛት አስቀድሞ ሰምቶ ስለነበር በጣም ደስ ብሎት የተላከውን መልእክተኛ በክብርና በደስታ ተቀብሎ አነጋገረው ።

የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤልም መልእክተኛውን ማቴዎስን ደብዳቤ እሲታ ወደሮማ ሊቀጳጳስ ልዩን አስረኛው ዘንድ ሊቀ ጳጳሱም በመልእክቱ ተስማምተው የሃይማኖትና የፖለቲካ ጉዳይ

የሚያነቡናቸውን ተመርጠው ለእቴጌ ዳግማዊት እሌኒና ለወጣቱ አጼ ልብነድንግል ደብዳቤና ገፀበረከት ይዘው በ፲፱ አምስት መቶ ሰባት ዓመተ ምሕረት በመርከብ ወደሕንድ ግዛታቸው ተላኩ ከዚ ንድም ብዙ ወታደርና ጉልበት መርከብ አዘጋጅተው የሚተማማቸ ውን የቱርክ ወታደር እየመቱ ምጽዋ ደረሱ። የአርኪቆ ደሴት ሹም ናይብ ከነሰራዊቱ መጥቶ ከነማቲዎስና ከፖርቱጋሎች ጋር ተገና ኙና እሱም መንገዱን እንደሚመራቸውና እንደሚረዳቸው ገለፀላ ቸው በዚህን ጊዜ የደብረ ቢዘን መነኩሳት ሄደው ከፖርቱ ጋሎችና ከማቲዎስ ጋር ተገናኙ ከዚያም ወደምፅዋ ከተማ ገብተው የእስ ላሞችን መስጊድ አድሰው ለንግሥተ ማርያም ብለው ሰይመው ቅዳሴ ቀደሱበት ቤተክርስቲያኑን ለንግሥተ ማርያም ያሉበት ከፖርቱ ጋሎች ጋር ያላቸውን ፍቅር ለመግለፅ ነው ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ናኦድ የደቆርውን ባላባት የቱሉ በጺማ ቁሉ እግሬ ልጅ ማልማዊት እሌኒ ናኦድ ሞገሣ ብለው አግብተው ሳለ ልብነድንግል ን ወለዱ ልብነድንግል በተወለዱ ጊዜ የእሌኒ ናኦድ ሞገሣ ወንድም ዶሬ እጅ መንሻና ገፀበረከት ለአጼ ናኦድ ይዞ መጥቶና እህቱንም ሊጠይቅ እንደመጣ በእንጻኪያ ብዙ ቀን ሰንብቶ ነጋሥቱ ሲያገለግል እንደቆየ በዚያን ጊዜ አጼ ናኦድ ለዶሬ የንጉሥነት ማዕረግ ሰጥተው የባህር ነጋሺ ግዛትን ተቀብሎ ግን ባባ ከተቆረቆረችው ከደባሩ ላይ ሆኖ ባህር ድንበር ለድንበር ያለ ውን የገርና ደሴቶች የባሬውን ኤርትራን ሁሉ የሚገዛው እሱ ነበር ስለዚህ ፖርቱጋሎች ከአለሉበት ደረሰ መጣና በትልቅ ስልፍና ክብር ተቀበላቸው በሁለቱ መካከል ትልቅ ደስታ ሆኖ ሞና ሰው ፈይላ ቁሉ ነበር ግን በሃገሩ ስም ደዋሪ ዱሬ ተባለ በዚህን ጊዜ ሞናው መልዕክተኛ ማቲዎስ ድንገት ታመመና በዚያው በጠረፍ ሞቶ ተቀ በረ በሌላ በኩል ደግሞ የጉዳዩ ወጣችና አባቢ የነበሩት የአጼ በእደማሪያም ባለቤት ዳግማዊት እሌኒ ግን ከብሬ የመንግሥቱን ሥራ ትተው በእመሩዋት ቤተ ክርስቲያን መርጦለማሪያም ሄደው በጾምና በጸሎት ተጠምደው ሳለ ሞቱ ።

እንግዶችም ምንም ማቲዎስ ቢሞት የተላከበትን ጉዳይ ለመ ፈጸም ከምፅዋ ደብረ ቢዘን ከደብረ ቢዘን ደብረ ሊባኖስ በደብረ ሊባኖስም እስከ ጴጥሮስ መጥተው እስከ እንባቆም ቀመርጠው ደስታ ሆኖ ሳለ እንግዶች ስለደረሱ ትልቅ አቀባበል አድርገው ተቀበሏቸው ።

ከዚያም አጼ ልብነድንግል ወደሚያገኙበት ወደደሴቶቹ እንደ ዚያ ሄደው ከንጉሣቸውና ከሊቀ ጳጳሳቸው የተላከውን ገፀ በረከ ትና ደብዳቤ አቀረቡ ሩሱ ግን ፖርቱጋሎቹ የጦር መሣሪያ ይዘው ይመጣሉ የተባለው ቀርቶ እንግዶቹ የሌተከሆኑትና የሃይሎቻ ሰዎች ስለነበሩ በንጉሡ ነገሥቱ በአጀቢው ቅሬታ ነበር፤ ሆኖም ግን በዋኒዚው በዓይሳን ያሉት የተዘጋጁ አረብ ነገሮችን የአጼ ልብነ ድንግልን አሽከሮች ወርቅና የዝሆን ጥርስ ጥሬን ባሪያ ሌላም ብዙ ሃብት ይዘው ወደአደን እየሄዱ በባህር የሚነግዱትን እየቀሙና እየዘረፉ መንገደኞችንም ባሪያ ብለው እየሸጡ ስለአስቸገሩ ስለዚህ ቅሬታቸውን ገለፁው የወደፊቱን ጉትም የሚከናወንበትን አሳብ ያደ ራጁ ጀመር ።

የፖርቱጋል መንግሥት ዓላማ የክርስቲያኑን የኢትዮጵያን መንግሥት መግዚያ አድርገው በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉትን የዘይ ላን የምፅዋን የሰዋኪን ወደብ ከቱርኮች እየተቀሙ የያዙትን እስ ላቅቀው ለመያዝ ነው የሮማው ሊቀ ጳጳስ አስረኛው ልዮን ደግሞ በፖርቱጋል መንግሥት ውስጥ ተጠግቶ የካቶሊክን ሃይማኖት በሰ ፊው እርቶዶክስን አጥፍቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመስፋፋት ነው ።

አጼ ልብነ ድንግል ከመጡ ስድስት አመት ያለፋቸውን መል እክተኞች የመጡበትን ጉዳይ ከተነጋገሩበት በኋላ ለንጉሡ ለአማኑ ኤል የሚሰጠውን ከመስቀል ወርቅ የተሠራ ዘውድና የከበረ ልብስ ድን ጋይ ደብዳቤ ጨምረው ሊልኩ ሲዘጋጁ የንጉሡ አማኑኤል ሞት ተሰማና ልጁ የሆነስ በሁዋኑ መተካቱ ተሰማ ስለዚህ አጼ ልብነ ድንግል እንደገና ለአዲሱ ንጉሥ ሌላ ደብዳቤ ጨምረው እባ ዘጋ ዘአብ የሚባሉትን ኢትዮጵያዊና ፖርቱጋሎችን በጀልባ አምስት መቶ አሰራ ስምንት አመት ላይ ፍራንሲስኮ ዲሲልቬራ የሚባል መኮንን በመ ርከቡ ያስኬዳቸው ሄደ ።

አጼ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ ለዩሃንስ የላኩት ደብ ዳቤ ጥና ጉዳዮች ከሰለሰነው ከፖርቱጋል መንግስት ልዩ ልዩ ጥበብ የሚያውቁ መምህራን መጥተው አገራቸውን ለማሠልጠን ሌላው ደግሞ ከክርስቲያን ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር የጠበቀ የቃል ኪዳን ገብተው አድርገው ዘወትር የሚያስቸግሯቸው ቱርኮች እና ያዙባቸው የሚያስወጣቸውን አረቦች ለማጥቃት ነበር ነገር ግን ለተላከው ደብዳቤ መልስ ሳያገኙ አስር አመት አለፈ በዚሁ አስር አመት ውስጥ አጼ ልብነድንግል ለክርስቲያን መንግሥት ለጠላታቸው

ለፓርቲያቸው ወዳጅነት እንዲጀምሩና ገፀበረከት ይብዳሌ እንደላኩ የሰሙ የአረብ አገር ባለሥልጣናት የኢትዮጵያን የክርስቲያን መንግሥት ለማጥፋትና ወደሙሐሜ ከሙጭ መንግሥት ጋር እንዲያገናኙ ለማድረግ በካሳዊን በሰማኒያን ትግሬን በምፅዋ አዶሬ ኢሳን በታጁሬ ሱማሌን በዘይላን በሌላም ደሴቶች የሚገኙትን ነገዶች ሁሉ ልዩ ልዩ ጊዜ ጊዜና መማሪያ እየሰጡ እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት እያስተማሩ በክርስቲያን መንግሥት ላይና በሚልካቸው መልእክተኞች ላይ የወሰኑ ቅጣት እንዲያደርጉ ጥላቻ እንዲኖራቸው ያደረጉ ጀመር ።

በዚህ በፊት በአክሱም ንጉሥ ነጋሢ በእርማዝ ዘመን በአደባ በላይታ ንጉሥ ነገሥት በድልአድ ዘመንና በአጼ አምደ ፅዮን ዘመን መንግሥት መጀመሪያ ላይ ብዙ የእስላም ሃይማኖት አስተማሪዎች ገብተው የባላባቱን ቤት ልጅ በየቦታው እያገቡ ይኖሩ ነበርና እነዚህ ቀደም ብለው የገቡት አረቦች ይህን የመሰለ እርዳታ ሲያገኙ የኢትዮጵያን ህዝብ በእስላም ሃይማኖት ለመቀየርና አዲስ የቤሪያ ንግድ ለማስፋፋት ይሯሯጡ ጀመር ይህን በመሰለና በሌላም ነገር በሃይማኖት በዘር በጎሳም ተለያይተው ይተላለቁና ይረዳዱ ጀመር ።

እንዲሁም ሆኖ አንድ የአባል ባላባት ጥና ከአጼ ናኦድ ጀምሮ እየተጥራ ከብትም ሰራዊ እየዘረፈ ሌሎን ጂዳ ለሚገኙት ባለሥልጣናት ይልክላቸው ጀመር ይህም ባላባት የሃይማኖት ማለሪያ አግኝቶ በቱርኮች ፍቃድ ይማም ማሀፉዝ ብለው የዘይላን ሹመት ለአምሬ ሰጥ በጓጉዛው እንዲቀጥም ይረዱት ጀመር እሱም የቱርክ መንግሥትና የአረቦችን ባለስልጣኖች ድጋፍ በማግኘቱና በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ የሌለ አዳዲስ ጠበንጃ በማግኘቱ በባሌም ደብ አለሁና አዳሎችን እየላከ ቤተክርስቲያን ማቃጠል ብዙ ሰውም ግራኝ እያለ መዝረፍ ስለጀመረ አጼ ልብነ ድንግል ወሬቸውን እስኪትሰሙ ማህፉዝን ለመዋጋት ወደ አለበት ሄዱ በዚህን ጊዜ የሀደሩ ሰዎ ነጠመና ከአህን በፊት ያሰለባቸው አባ እንድርያስ የሚባለው መነኩሴ ማሀፉዝን ነጠመና በሰይፍ አራሱን ቆርጠው ለአጼ ልብነድንግል ጎድያ አሳዩ አዳሎችም አዝማቻቸው ማሀፉዝ መሞቱን እንደሰሙ ሲያዩ የያዙትን መማሪያ እየጣሉ ሸሹ የአጼ ልብነድንግል ሠራዊትም አዳል አገር ድረስ ሄደው በዘይላ ያለውን የማህፉዝን ከተማ አቃጥለው ተመርጠ ተማርከ ሂዶ የነበረውን ህዝብና የህዝብ ሃብት አስመልሰው በድል አድራጊ

ነት በሾታና በእልልታ ወደ ዋና ከተማቸው እንደነጸ ተመለሰ ማህቶቱ የሞተበት ቦታ በስሙ ማህቶቱ አሴት ማቆድ ካሉም አባስ የሚባለው ጉማ ባሬ አዳል እንደሚባለው ነው ይኸውም ዝ-ወደደ የተቀየረበትን በአረብኛ ፊደሉና ደምሁ የለም በአረብ አርዋ ይገ ኛል ።

ከዚህ ሥርዓት በኋላ እስከግራኝ አህመድ መንሳት ድረስ ለአ ስር አመት የገር ሰላምና ፀጥታ ሆኖ ይኸም ፀጥታና ሰላም ሊሆንበት የቻለው ዋናው በዶ፡ በቴርክ መንግሥት ሥር እየተረዱ የአረብ ባለ ሥልጣኖች በአደን በጀዳ በመካ በበሊድ በካይሮን በባግዳድ ያሉ ሁሉ የማህቶዝን መሞት በሰሙ ጊዜ ከዳር እስከዳር ተቀስቅሰው በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግስት ላይ የሚነሳ ትልቅ ተዋጊ ወሳት በአዳልና በሱማሌ ያሉ ባላባቶች እንዲወንከሩና በእስቸኳይ የጦር መሪ እንዲመርጡና የጦር መግሪያም እንደሚልኩላቸው የወደሰው ትእዛዝ መተላለፉን የሰማ ሰው ለአጼ ልብነ ድንግል ይነግሩቸዋል አጼ ልብነ ድንግልም በማህታቸው ውስጥ ያሉትን ባለሥልጣኖች ሰብስበው ስለዚህ ጉዳይ ከተማከሩበት በኋላ የአዳል ባላባት የሆነውን የወ ላስማው ዘር የአርዌ በድላይ የልጅ ልጅ አቡበከርን የሆነትን የዘኪራን የደዋርን የታጂራን የዘይላን ሃገሮች ሁሉ እንዲገዛ የናታቸውን እህት አጋብተው ፈቀዱለት በሆኒለው ግብሩን ገበረ ከቀን እንዲያመጣ ሾመው በከባር ሰደዱት ሱልጣኑም አቡበከር በዚሁ ሥርዓትና ቃል ኪዳን አድርጐ ወደሃገሩ ሄዶ በግዛቱ ውስጥ የሚገኙትን አረቦች ሽኮችም በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ሴራና አድማ አድርጐቸኋል ። እያለ ይቀጣቸውና በአደባባይ ይሰቅላቸው ጀመር በዚህ የተነሳ የአዳልና የሱማሌ ባላባቶች በሱልጣኑ ላይ ቂም ወዛ ከቀን ወደ ቀን እያደረጉ ሆዘው እንዲይገባለት አደረጉ በአጼ ልብነድንግል በኩል ደግሞ ከአረመኔውና ከእስላሙ ህዝብ ጋር የሚያደር ጉትን ሽልማት ሽም ሽር ያዩና የሰው መንስላትና ክህደት ሃይማኖትን ካደ ከአህዛብ ጋር ሆኖ ምግብ በላ እንደአረመኔ ትንባሆ ጥረስ እንደእስላም ሚስት ቃመ ብለው አስወሩ እትገዙለት ብለውም ያው ግዙና ያስቱምሩ ነበር ብዙ ጊዜ ይኸን የሚናገሩ ከካይሮን በከሊፋ ውና በሊቀጳጳሱ የሚላኩት መነኩሳት ነበሩ ።

እንደዚህም ሆኖ በአዳል ሃገር ልዩ ሃገሩ ሃባት ከተማው ጠይም መንደሩ ዘካህ ከሚባል ሼህ መሃመድ ቤን ኢብራሂም የሚባል የአ ረብ ጉማ ነበር የግራኝ አህመድ እናትና ከምግባቱ በፊት ከሆርላዋና ከሶዊ ጉማዎች ጋር 2 ሴቶች አግብቶ ይኖር ነበር ። ሼህ መሃመድ

ኢብራሂም ወይም ቤን ሂብራሂም አልጋዛሊ በባሪያ ንግድ ወደዘቢ ድና ወደመካ እያመላለሰ በመርቅና በልብስ በጣም ከብሮ ነበር እሱም ከዘሪባ ባላባት የምትወለደውን ሽምስን ሶስተኛ ሚስት አድርጎ አግብቶ ሶስት ወንዶች ሁለት ሴቶች ልጆች ወለደላት ስማቸውም የወንዶች ኋላ የሀይላን ንጉሥ ተብሎ የነበረውን ይጣም አህመድ ወይም ግራኝ አህመድ ኢብራሂም ሁለተኛው ቤን አሊ ኢብራሂም ሶስተኛ ቤን አብደል ዋሀድ ናቸው ። ሴቶች ደግሞ ፈርዱውስ ኢብራሂም ቀጥላ ሙኒሳ ኢብራሂም እንዚህ ሁሉ ከሸምስ 2ኛ ሚስቱ ዘካሀ ከሚባል መንደር ውስጥ የተወለዱት ናቸው ሸህ መሃመድ ኢብራሂም ወይም ቤን መሃመድ ኢብራሂም የአጼ ልብነ ድንግል የደዋሮው ጦር አዛዥ ቶኮሌል የተሰኙ ልጅ በዘሀገ ሲወር የበቱ ተዘርፎ ወራቱ ስለጠፋ ከሐባት ወደሃረር ልጆቹንና ሚስቱን ይዞ ሄዶ ከዚያም የሃረሩ ገዢ ገራድ አቡን በክብር ተቀብሎ አስቀመጠው ሼህ መሃመድ ኢብራሂም በየጊዜው ወደ ጂዳ ወደዘቢድ እየሄደ ከዚያ ብዙ የዘሀገን ጥርስ ወርቅ ባሪያ ሲወስድ ከዚያ ደግሞ የቱሪን መሳሪያች ከታቦች ልዩ ልዩ ጨርቃ ጨርቅ ሲያመላልስ በተዘ ላይ ከፖርቱጋል የጦር መርከቦች ጋር ተዋግቶ ስለሞተ ልጆቹን ለገራድ አቡን ሰጥቶ ነበርና ሞቱን ሲሰማ ልጆቹን በእንክብካቤ እያስተማረ አሳደጋቸት በዚህን ጊዜ ከዘሩ ከጣድ አድዲን የወረደው የያቆብ ወላስማ ሱልጣን አቡበከር አጼ ልብነድንግል የሃረርን ግዛት ሰተሙት ነበርና ወደ ሃረር ሄዶ ገራድ አቡንና ቤተሰቡን ገደለና ሁሉን ጠቅሎ ይገዛ ጀመር የቤን ኢብራሂም ትልቁ ልጅ አህመድ ግን ያረሳ ባደኖቹን የሱማሌ ነገዶችን ይዞ ወደ ሐባት ተመልሶ ተቀመጠ በዚያም የጦር ልምምድ ያደርግ ጀመር ሱልጣን አቡበከር ግን በደዋሮው ጦር አዛዥ ቶኮሌል ቁጡ እየተረዳ እያልጎና ሱማሌን ይገዛ ጀመር በጥንቱ ሃጌ በዛሬው ሃረርጌ ውስጥ ሀረር ከተማ በስተምዕራብ በሚገኘው ደዋሮ የቶኮሌል ጺዋ ጦር የነበረበት ስፍራ በእሱቱ ስም ቁጡ አማራ ይባላል ። ቁጡ በጺላ የቀባለውን የአጼ ልብነድንግል እናት አባት ነው እንደዚሁም ሆነ ሱልጣን አቡበከር የአረቦችን ወዳጅና የሟቹን የማህቶሂን ልጆችና ዘርች ለማጥፋት በሰተኑሳ በሽሆችና በባላባቶች ዘንድ በጣም የተጠላ ሆነ በዚህን ጊዜ የሃረር ባላባቶችና ሼሆች ከገራድ አቡን ቤት ያደገውን ወጣት አህመድ ኢብራሂምን አስመጥተው በድብቅ አጼ ልብነ ድንግል የሾሙትን ሱልጣን አቡበከርን አስገደሉት አህመድም የገርስቲያንን ወዳጅ ስለገደለ የይማምን ማዕረግ ሰጥተው የከሰምን ግዛት ሰጡት በዚሁ ሱልጣኑን በመግደሉ ከብሮ አገኘ

አባትዋ ማህፉዝ በአጼ ልብነ ድንግል ጦር የምተባትና የአባትዋን ግዳይ ወዳጁ ሆኖ ሲያጠፋቸው የነበረውን ሱልጣን አቡበክርን የ ደል ጀግና ይማም አህመድን የማህፉዝ ልጅ ወበራ ከደስታዋ ብዛት እንዲያገባት ጠየቀችው እርሱም የወላሰማ ዘር እንደመሆኑ መጠን በጣም ደስ ብሎት ስምዋን ባቲ ድል ወበራ ብሎ ሰይሞ አገባ ባቲ ጨረቃ ማለት ነው በዚሁ ሱልጣኑን አቡበከርን ገድሎና የማ ህፉዝን ሴት ልጅ ባቲ ድል ወበራን በማግባቱ ከሱማሌዎች ከአፋ ሮች ከሺሻ ከዘይድ ከሃረር ከባግዳድ ብዙ የተሰበሰቡ ሰራዊቱ መሪ ታቸ ቃል ደብዳቤ ተላከለት በዚህን ጊዜ የወላሰማ ዘሮች የሆኑት ሁሉ ገራድ አሙራጆ አቡንን በመላ አቡበከር ለክርስቲያኖች አግ በመግደሉ ቂም የነበራቸው በቀሉ ስለተመለሰላቸው ለይማም አ መድ ከብርና ትንቢት ያደርጉለትና እንደንብያቸውም ያዩት ጀመር ሁሉም በየጉባው ይታዘዘው ጀመር ሱልጣን አቡበከርን በገደለ በት ቀን ገብ ከቦትና ሰፍርበት አየን ብለው ሺዎች ስለተናገሩ አበሻን በጦሩ የሚገዛ ነው እየተባለ በየገበያው በየጃሚው ይነገር ጀመር ።

የአጼ ልብነ ድንግል የደጃፎው ጦር አዛዥ ፋትአል ቀሉ የአዘ ቂን ባል ሱልጣን አቡበከርን የገደለ ይማም አህመድ ለመግደል ከበለ ጠነው ሠራዊት አጼዋ ጦር ጋር ወደፊቱ ሄደ ግራኝ አህመድም በአባቱ አረብ በእናቱ የዘረብ ነገድ በመሆኑና የአረብ ሀገር ባለሥል ጣኖች የሚበታውን ያክል የጦር መሣሪያና ወታደር እንደሚሰጡት ቃል ስለገቡለት የኢትዮጵያን ክርስቲያን መንግሥት ገልብጦ የእስ ላም መንግሥት ለማቋቋም ሱማሌንና አበሻን በአንድ መንግሥት ሥር አድርጎ ለመግዛት ሙሉ ምኞትና ተስፋ አደረበት በዚህን ጊዜ የናስድ ሞገሳ ወንድም ፋትአል ግራኝ አህመድ ወደአለበት እንደሚ መጣ ሰምቶ አካም ከሚባል ወንዝ ላይ አዳለ ከመጡ ከአረብ ወታ ደሮች ጋር መሽጐ ቆየወና አዳለ በመጣ መግረያ ደጋግመው ተከበ ትና ተመትቶ ከፈረሱ ወደቀ በዚህን ጊዜ የጼዋ ጦር አለቃቸው ፋት አል በጥይት ተመትቶ ሲወድቅ ያዩት ሁሉ ሸሹ ጥቂቶቹ የብረ ልብስ የለበሱት ሠራዊት እስከ ፀሐይ ግባት ድረስ አለቃቸውን ፋት አል ከወደቀበት ቦታ እንስተው በመከላከል እናስማርከም በማለት ሲዋጉ ዋሉ ከዚያም ሌሊት በጨረቃ ቁስለኛውን ይዘው ወደ ደጃር ተመ ልሰው በድብቅ ብዙ ጊዜ ቆዩ ከዚያም ደብረ ሊባኖስ ፋትአል ወደሚባል የአሳ አገር ተጓዘው የግራኝ ወረራ እስከ ሚፈጸም ድረስ በመርገ ሲዋጉ ቆዩ ነገር ግን መርነቱ እንዳበቃ የኢማ ጉባዎች በደብረ ሊባ

የሚገኙትን መንኮሳት ስለጎደሏቸውና ገዳሙንም ስለአቃጠሉት ፋኑኤል ከመንበት ከብዘትውና ጉጃአቸው መጥተው ወደአሰቡት ከአሰቡት በሊዬ ገዳሙ-ዲዎስ ዘመን መንግሥት በጣና ሐይቅ ውስጥ በሚገኘው መንደብ ገዳም ይሆን የአጼ ልብነድንግል ታሪክ ጽፈው ከዘንበት ጉጃ ውስጥ ከበሉት መጽሐፋቸው ውስጥ ተጽፎ ስለተገኘ በግዱር ዘቤተ እንዲ ኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ተጽፎአታል ። መራራስ ኢ.ኤም በላይ ከአንድ ላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጽፈ አትርበላቸኋለሁ ።

የአጼ ልብነድንግልና የግራኝ አህመድ ጦርነት አጼ ልብነድንግል በነገሡ በ19 ዓመታቸው የደቀርው ጦር እዛገ የነበረው ፋኑኤል ቁጥ ድልዞና በሁለተኛው ዓመት ላይ አህታቁውን አመታውቀንን ያገባ መልአክ ሃይል ዲጋል ሃን ከፋኑኤል ቀጥሎ ደቀርን ይገዛ ስለነበር የጦር ኃይሉን ሰብስቦ ወደኢዳል ሀገር ሄዶ እንዲዘምት አዘዙት ዲጋል ማለት የሀይል ተቀጣጣሪ ማለት ነው ። በዚህን ጊዜ መልአክ ሀይል ዲጋል ሀን አዳል ሀገር ደርሶ ከብቱንና ሰውን ዘረፈ ከተዘረፉት ውስጥ የግራኝ አህመድ ዋና ጓደኛው ቀጠን አሚር አቡበክርና የአቡበክር እናት በዘረፋ አብን ቤት ግራኝን እንደወለደቸው ልጅዋ ያሳደገችው ከድጃ ፋጤ ነበረች እሷም በመልአክ ሀይል ዲጋል ሀን ፊት ቁማ እን ዲህ አለች እኔን ብትማርከኝ ምን ይጠቅምችኋል ? ነገር ግን የእኔ መያዝ ለአገሬን ጸባ ይሆንባችኋል የእሁኑ ማሽንፋችሁ ፍጻሜ ወደ መሸነፍ ይመለሳል ተንከባክቤ ያሳደኩት ልጅ ጀግና ለጦርነት ልቤ የፀና እጣ ፋም ደም ለማፍሰስ የፈጠነ ነውና እሱንና ልጄን ለታችሁ ከል ሄዳ ችሁ ከእጃችሁ ሳያድንኝ ልቡ አያርፍም ብላ ገና ስትናገር መልአክ ሀይል ገና ለተናገረችው ቃል ሳይመልስ ግራኝ አህመድ በድንገት እንደመብረቅ ያርስፈረሰኛውን ከፈረሰኛ እግረኛውን ከእግረኛ አደባ ልቆ ሲዋጋ ብዙ ሠንጋቀላቶች ከሰውነት እየተቆረጡ ሲወድቁ በሁለ ቱም በኩል ይታዩ ነበር በመልአክሀይል ዲጋል ሃን የነበረው ሠራ ዊት ግማሹ እዛ ሲዘረፍ መንደር ተሰግስጐ ነበርና ጦርነቱን መጀ መሩና ብዙ ሰው ማለቁን ሲሰማ ግማሹ ወደ ድቀር ግማሹ ወደፈጠ ጋርና ኢፋት ግማሹም ወደጎጃምም ፈረሰና በቅሎውን ሳይዝ ሸሸ በግ ራኝ አህመድ የሚመራው የአረብ ወታደር እየተከታተለ ብዙ ሰው ማረከ በዚህ የሚቆጠርም በጦርነቱ ሞተ ከተማረኩት ምርኮኞች አንድ ሽህ ሁሉቱ ሙቶ በየመን ሀገር ላለው በየአበበዲድ ንጉሥ ለኤሚር ስለ ምግን መሣሪያና ወታደር ለላኩለት ባለሥልጣኖች እንዲያካፍላቸው ላከለት እሱም አቢዶል አበሺ የአበሻ ባሪያ እያለ ለተቆርኞችና ለሌ ሎች ለባለሥልጣን ላካቸው ።

በመልእክ የጀል ጄጋል ሆነ እጅ የነበሩት ምርኮኞች ኤሚር አቡበከር ቀጢን አቡበከርም ይባላል እናቱ ከድሃ ቀተ ልሎችም ከ ብቶቻቸው ጋር በድል አድራጊነት አስመለሰ ። በዚህን ጊዜ በእነሱ ቋንቋ እንዲህ የሚል መዝሙር ተዘመረለት ።

ሕዝቡን ለመከላከል ተነሳ ድል አድራጊው ልጅ ሃያል ልጅ አስመለሰ የተማረኩትን ከሃያላን እጅ የሀዝቡን ንብረት በእጥፍ ተ ቀላቸው ተጋዳይ እጅ ግራኝ አህመድ ከታወቁ ከአጼ ልብነ ድንግል ጦር አዛዦች ጋር ሁለት ጊዜ ድል በማድረጉ በወዳጆቹ አረቦች ቀርቶ በአጼ ልብነ ድንግል ቤተ መንግሥት አስፈሪና አስደንጋጭ ቆራጥ ጀግና የሚባል ስም ተሰጠው ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ወደሀገር እንደገባ ከአረብ አገሮች በሶብሔት ከተርክ መንግሥት በሚያገኘው የማበረታቻ ቃልና የጦር መሣሪያ ብዛት የአባቶቹን ሀገሮች ለመውረርና ከግንዚባሬ እስከ አዶል ድረስ ያለውን አንድ አድርጎ የሰላም መንግሥት በበላዩ ለመመስረት ይዘጋጅ ጀመር ።

የኢትዮጵያ ሀገሮችን ለመውረርና አዲስ የእስላም መንግሥት ለመመስረት እንደተዘጋጀና የአረብ አገሮች ባላባቶችና ባለሥልጣናት ሙሉ መሣሪያና በቂ ወታደር እንደተባበሉት አጼ ልብነ ድንግል በሰሙ ከፖርቱጋሎች ጋር የነበሩት ወዳጅነት የአረብን ሕዝብ ጠላትነት ቀስቅሶ በራሳቸው ላይ ስለመጣ ከዳር እስከ ዳር ለአለው የጦር ሰራዊት ታላላቅ ጦር መሪዎችን ጥሪ አድርጎ ጦር አዝማቾን ጦር መሪው በስድስት ወር ውስጥ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ የሚል ጥሪ ነበረ ።

| የሚከታተሉ ቤተሰብ | የሚገኙበት | የዚያ የሚኖሩ | የደቻ ሥፍር | ወሰራው አጠራር |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| አንደኪያ | ደሴት | አዝማች | ፈጣሪ | ከዳሬት — አዳ |
| ወናማ አምባ | በሬሌ | ደጃዝ ነጋሺ | ደምር | ከአሩሲ — ወርሀረር |
| ድል አንባ | አረር | ባላ ነጋሺ | ትግሬ | አልተቀየረም |
| ገምብራ ኩሬ | አባማ ናበሬት | ጉንጃም ነጋሺ | ጉጃም | ከበርበል — አሰበሶምት |
| ባድቴ | ደብረ ዘይት | የዳሞት ንጉሥ ራስ | ዳሞት | ከጋድጎት ዳሞት ቀበሌ በሊያ |
| ምቀሃሬ | መቀሃሬ | ጻህ ተላህም | ቡንዶደር | አልተቀየረም |
| ጓራርዋ | ሰላሌ ጀዋ | ቢትወደድ | ቤተ አማራ | አማራ ሳይንት |
| ትንጂ | በናዎት | ንጉሥ | ባሌ | አልተቀየረም |
| ዚጋመል | በጅሩ | መኮንን አዝማች | አርሲ | |
| ዋድባ | በዋጂ | አባኮር | ጋንሳን | |
| አድባ | ወረባቦ ወሎ | መኮንን | ዋግ | |
| ዘማሮ | በሰይባ | አዝማች | ወሎ | አልተቀየረም |
| ሳንግዋ | በዋዋት | ራስ | ጎንደር | ጉንደር አካባቢ |
| ደብረ ወርቅ | በትጃም | ባለአባም ራስ | ቀዋሬ | ከበሊያ—ወሊቃድት |
| አድባ | ዝዋይ ሸዋ | ኒቡን ገዢ ነጋሽ | ሱሳ | አልተቀየረም |
| | በአማራሳይንት | አዝማች | ዋድላ | |
| | | ራስ | ሲጋመል | |
| ማርገበር | እድል | የወይብላውያንግኒጂ | ጊሸን | የባሬው ጅፋና ሰላሌ |
| እንደጥጉበ | እንሳሮ | የኪሉ ንጉሥ | አርሲያ | በባሬው አሰላ |
| ዋን አንባ | ግሼ አባይ | | | የባሬው ወሊጋና ከፋ |
| ትብያ ጂበራ | ቡሶት | የጎ/መጋል አባጋል | ማሬርኬ | የባሬው ሰላሌና ግንደ በረት |
| ገሌላ ደባ | በመሳጋ | | | |
| ምድረ የሰባስ | በረንታ ጐጃ | | | |
| ጃራራ | | | | |

በአጼ ልብነ ድንግል የነበሩ የባለስልጣኖች ስም ዝርዝር

| | |
|---|---|
| ጳጳስ አባ ማቴዎስ | |
| ኤጲስቆጶስ አባ ስምዖን | |
| መልአከ ሃይል ዴጋልሃን | የደዋሮና የባሌ ንጉሥ |
| ንጉሥ ወሰን ሰገድ | የዳሞት ንጉሥ ዳሞት ነጋሺ |
| አቤቶ ፊቅጦር | የፈጠጋር አዝማች የልብነ ድንግል በኩር ልጅ |
| አቤቶ ያዕቆብ | የተጉለት አዝማች የልብነ ድንግል ልጅ |
| አቤቶ ገላውዴዎስ | አጼ ገላውዴዎስ የልብነድንግል ልጅ |
| አቤቶ ሚናስ | ተማርኮ ባሪያ ሆኖ የተሸጠ የልብነ ድንግል ልጅ |
| እቴጌ ሰብለ ወንጌል | የአጼው ባለቤት |
| ንጉሥ ማኅፀንቶ | የደዋሮ ንጉሥ የነበረ |
| ባሕረ ነጋሺ ዘወንጌል | የድሆና ንጉሥ መቀመጫው ዘባ |
| ባሕረ ነጋሺ ይስሐቅ ዶራ | የደባርዋ ንጉሥ ከዶራ ቀጥሎ የያዘ ልጅ |
| ንጉሥ መቅጮር የመዘጋ ልጅ | የቢዘንና የቡሬ ንጉሥ የሙታሞወሶ ንጉሥ |
| ንጉሥ ዣን በለው | የአጼውን የቀኝ ጦር አዝማች |
| ንጉሥ ቀዋስ ያግሮያት | ትግሬ ነጋሺ የእንደርታ ንጉሥ ዳሞት ልጅ |
| ጸሐፌ ላሕም ሮቤል | የአምባ ግሸንና የደብሮች ሹም |
| ጸሐፌ ላሕም እምደሚካኤል | የጎጃም ግብር ሰብሳቢ የጭፍራ ሹም ራስ |
| ጸሐፌ ላሕም ተክለ የሱስ | የትግሬ ግብር ሰብሳቢ የጭፍራ ሹም ራስ |
| ጸሐፌ ላሕም ዘሚካኤል | የዳሞት የጭፍራ ሹሞች ራስ |
| ራስ እምኔ አብርያ | የአበርገለ ገዢ የአጼው አማካሪ |
| ራስ ዣን በለው ተስፋ | የሠራዊት ገዢ የአጼው አማካሪ |
| ራስ በለው ሰገድ | የቀዳሚ ሊሉል ልጅ ምግብ ሰብሳቢ |
| ራስ በድል ወልደጊዮርጊስ | ሞና አምጽ አስጊንደና የአጼው አማካሪ |
| ራስ ማኅፀንቶ | የተባለው አለቃ የበላይ አባ ተናጋሪ |
| ራስ ባንዶች የአባ መጋል በር | የተባለል ቀበታዎ አለቃ ታላ እቅራቢ |
| አዝማች እስላ | ከሚገባያን ቀጥሎ የባሌ ጦር አዝማች |
| አዝማች ተክለ ኢየሱስ | የትግሬ የእንጎት ገዢና ጦር አዝማች |
| አዝማች ማውል | የተክለ ኢየሱስ ልጅ የበጌምድር ገዢ |
| አዝማች ይስሐቅ ወልደ ሰገድ | የቄዋራና የድንበር ገዢ |
| ብሕት ወደድ መርጪ | የራስ እምኔ ልጅ የአጼው ልጅ ያገባ |
| ብሕት ወደድ በድላይ | የወሳቦማ ዘር የአጼውን እህት ያገባ |

አጼ ልብነ ድንግል በዱቄ በሚባለው ቤተ መንግሥታቸው ሆነው ከዳር እስከዳር ለሚገኙት ታላላቅ የጦር መሪዎቻቸውና አዝማቾችን ጥሪ ሲያደርጉ የሰላሳ ሶስት ዓመት እድሜ ሰው ነበሩ ። የዘረባ ተወላጅ የሆነች የሸዋዊስና የኢብራሂም መሐመድ ልጅ ግራኝ አህመድ ግን በዚህ ጊዜ የሃያ ሁለት ዓመት እድሜ ሰው ነበረ እንደዚህም ሆኖ ሁለተኛውን የንጉሠ ነገሥት ጦር ሃይል ድል አድርጐ ወደ ሐረር ተመልሶ ሳለ ከጀዳና ከዚባድ የተላከለትን ወታደርና ጠበንጃ ተረክቦ ለኢሚር ማንሱር ማህፉዝ መቶ ፈረሰኛ ሺህ እግረኛ ጦር ለቢዘር አዶሌ አምስት መቶ ፈረሰኛ ሺህ እግረኛ ጦር ሰጥቶ ወደደዋሮ ቱሉ አማራ ላካቸው በዚያም ድንገት ደርሰው ብዙ ሴቶችና ሕጻናትን ዘርፈው ቤተ ክርስቲያኖችን አቃጥለው ወደሀረር ተመልሰው የዘረፉትን ህጻናትና ሴቶች ልጆች ለግራኝ አህመድ አስረከቡት ግራኝ አህመድም ወታደርና የጦር መሣሪያ ለሚልኩለት አንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ሴቶችና ህጻናት ልጆች ስጦታ ላከላቸው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል ከዋና ቤተ መንግሥታቸው ከእንደኪያ ይፋት ውስጥ እንደሉሉ ከሰላዮች እንደሰሙ የኢሳንና የአዳልን የሱማሌንም ጐሳዎች አሰልፎ ወደይፋት ሄዶ ከዚያም እንደደረሰ ከታወቀው ከግራ ጦር አዝማቹ ከይፋቱ ገዢ ከወናግዋግን ጋር ገጥሞ በጦር ብዛት ድል አድርጐ የአጼ ልብነ ድንግልን ቤተመንግሥትና ቤተክርስቲያን ሃብታቸውን ልዩ ልዩ የሆነ የሃር ልብስና የወርቅ ጌጥ ከወሰደ በኋላ አቃጠላቸው በዚያም በአካባቢው ያለውን ከብትና ወርቅ ሴትና ወንዱን ዘርፎ በተለይ ወደሀረር ተመለሰ በዚያም የምርኮ ክፍያ ሆኑና ለግራኝ አህመድ አምስተኛውን እጣ ሲያነሳ አምስት መቶ ባሪያ ሺህ ከብት ሃያ ወቄት ወርቅ በአከስሙና በአደፋ ነጋሥታት ስም የተሠራ አምሳ የወርቅ መከሊት ደረሰው ግራኝም ያንን ተቀብሎ በእስልምና ሃይማኖት ያሉትንና ገና ሃይማኖት የሌላቸውን ነገዶች ሁሉ ጥሪ አደረገ እንዚህ ከታወቁት ጀፈ ደባሪ መራይታን የዛር ማግዷ የግራኝ ዘረባ ወይም ሆርባ ሌላ አዳል ሲም ሃርላህ ዚጦ ባርህ ባርዛ ያቆላህ ጀበር አራብተትኔ የአባቱ ነገድ ነው / አሉካ ሃርቲ ማጆቲ ጀራን ሚዛር መሰሳይ እንዚህ ሁሉ በባሬው ሱማሌ ሆገር የሚገኙ ናቸው ።

እንዚህን ነገዶች ሁሉ ሰብስቦ እንዲህ አላቸው ይህ ሀብት በሙሉ ለምናደርገው ቅዱስ ጦርነት ውጭ የሚሆን ነው እንጅ እኔንና ባለቤቴ እንወስደውም ስለዚህ ለሚረዱን የእስልምናን ሃይማኖት ለሚያስተምሩ ወንድሞቻችን የሚላክ ነው ብሎ ግማሹን ለዘቢድ ግማሹን

ለጀጸና ለካይሮን ባለሥልጣኖች ላከው ። ይህ ሁሉ ሲሆን አጼ ልብነ ድንግል ባዱቂ በሚገኘው ቤተመንግሥታቸው ሙሰዋ ነበሩ ይህ ባዱቂ የሚባለው ከተማ የመንደያ የማጂ የጋፋቶች የማያ ነገዶች ከአረቦች ጋር ሆነው ነጭሰና ትንባሆ እያጨሱ መናፍስትን የሚጠይቁበት ሥፍራ ነበር ኋላ ግን ነገሥታቱ ከተማ በርተው ሁሉም እሳሚዎችን መናፍስት ጠሪዎች አስቀመጡበት እንዲሁም አማራዎች ትግሬዎች ቅጥሮች ከጉራጌዎች አስተናግደና በበረሃ የሚበቅል አብሾ ፍሬ ከፍሬስ አመጣነው ብለው ሰሙን እፀፋሪስ ያሉት ቅጠል ተምመው እየጠጡና እያጨሱ በወዳሰማ ሥር ሆነው የሚገዙትን ነገዶች ኋላ ሁሉም እስላም የሆኑ የእስላም ፍቅሬዎችና ጂሆች የጫት ቅጠል እየበሉ ጋላዎች አርሞዎች ትንባሆ እየጕረሱ ወይም እያጨሱ መጭውን የሚያዩበት ልዩ ቦታ ነበር ስለዚህ ስሙ ባዱቂ ተባለ ባዱቂ ማለት በሱባ ቋንቋ የጋኔን መሳቢያና ማቅረቢያ ማለት ነው ።

በዚሁ በአጼ ልብነድንግል ዘመን መንግሥት ከእናረያ ግዛት ከከፋ የመጣ አባ ቡና የሚባል ግውስ ባሕታዊ ነበረ ይሄም ግውስ ከፋ የሚባለውን የዱር ፍሬ ደቂስ የሚባለና ቅጠሉን እምሰና ቀቅሉ የሚጠጣ በዚህን ጊዜ የዛፉን ቅጠል ጉንጉሙ ከአባ ቡና ወሰደው ስለቀመሱት ተወዳጅነትና ተፈላጊነት ስለነበረው አጼ ልብነድንግል ቅጠሉን እያስፈሉ ይጠጡ ጀመር አባ የማስረጋ ስም ነው ይሄም ግውስ ከታወቁት ከአጼ ልብነድንግል ጦር አዛዥ ከንቡሩት ከሙናኝ ከፋንኤል ጋር ተገናኝተው በደቀኛር ልዩ ቦታው የአቦን ሲኖሩ ከዚያ ሁሉሉ ወዶ ጣና ሃይቅ መጥተው ፋንኤል በጣና ባህር ውስጥ መንደብ ጊዶም አባ ቡኔ በዘጌ ሆነተው ለብዙ ዘመናት ቆይተው ሞቱ አባ ቡና በዘጌ ዘማተው ለብዙ ዘመናት ቆይተው ሞቱ አባ ቡና የቡናን ጥቅም በዚሁ በዘጌ ላሉ በአካባቢያቸው ለሚኖሩት ሁሉ ጥቅሙን አሳውቀው አልፈዋል ስለዚህ አጼ ልብነ ድንግል አፀፋርስና አብሾ ከሚጠጡት መነኮሳት ጫት ከሚቅሙት ጂሆች ትንባሆ ከሚጕርሱት ጋላዎች ጋር ስለሥርነቱ ድል የሚያደርጉበትን ዘዴ ሲጠይቁ ኖረው ነበር ነገር ግን በዚያው ላሉ ግራኝ አህመድ እንዳሲያ የሚገኘውን ቤተ መንግሥታቸውንና ያሰሩትን ቤተ ክርስቲያን ዘርፎ አቃጠለ የሚባል ወሬ ሲሰሙ ጳጳሱ ጥበጻዊ በካይሮን ሰልጣኖች ተሾመው ስለሰሙ እግዚአብሔር ተቀይሞታል ይሄውም ከአረቦች ጋር የቆየውን ወዳጅነት አፍርሰው ከፖርቱጋል መንግሥትና ጠላታችን ለሆነው ለሮማው ሊቀ ጳጳሳት ከአስረኛው ልዮን ጋር ወዳጅነትን ስለወጠኑ መንግሥትዎ ለእስላም ሕዝብ ይሰጥብዎታል ብለው በሊቀ ሊቃውንቱና በኢሔ

ቆጶስ አባ ሰሞን እጅ ደብዳቤ ጽፈው ካሉ አጼ ልብነ ድንግልም በአባ ማቴዎስ ተቀጥተው ከእሱ ቤት በድቄ ድረስ እንዲመጡ ላኩባቸው ነገር ግን እሱን ከቱርክ ውስጥ ለውስጥ ምስጢር ስለነበራቸው ግራኝ ወደአለበት በሀገረር አድርገው በባይሉን በኩል ዘቢድን የማብቂ ከሊቱ ከቱርክ ጋር ሆኖ ይገዛው ስለነበር ወደዘቢድ ጉዱ ከዘቢድ ወደካይሮን ገቡ ዘቢድ የየመን ከተማ ከሰንአን ከምካ ደቡብ በኩል የምትገኝ ከተማ ናት ።

በዚህን ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል ጳጳሱ አባ ማቴዎስ ወደግብፅ በመሰደ ቻው በኩል አድርገው መኳንቶቻቸውን ስለሰሙ እውነትም እግዚአብሔር እንደተቀየመባቸው አውቀው ከባድቄ ወደ ቦካ ተጓዙ ይህም ቦካ በአጼ በርእያዕቆብ በመንግሥት የተሠራ ቤተ መንግሥት ነው በዚያም ልዩ ልዩ የሆኑ የጭዋ ጦር አሉበት በዚያም አፈር ከሚባለው ተራራ ውጥተው የንጉሥታት ልጆች አርባ ወምን የሚያሙት ነበር ። ስለዚህ አጼ ልብነ ድንግል በዚሁ በአፈር ተራራ በሚገኘው ዋሻ ውስጥ ሱባኤ ገብተው እግዚአብሔርን ይቅር በለኝ በሠራሁት ኃጢአት ሁሉ ብለው ለምኑ ነገር ግን ከኃጢአታቸው ብዛት ይሁን ወይም የእግዚአብሔር ትእዛዝ በዘመናቸው በኩል ያለው የተማሩትን ሠራዊትና የሃይማኖት መሪዎች ሁሉ የሚናገሩት ግራኝ ድል አድርጐ የእስላምን መንግሥት በክርስቲያኑ መንግሥት ፈንታ እንደሚተካ አድርገው ያወሩ ጀመር በዚህ ወሬም ብዙ ባለሥልጣኖችና መኳንንት ተደናግጠው ተገድለዋል ሆኖ ግን ወሬው ከዱር እስከ ዳር ስለ ግራኝ ሃይለኝነትና ታላቅነት ይወራ ጀመር ።

አጼ ልብነድንግልም በሱባኤ ውስጥ ከበሰለ እህል እርቀው በሐዘን በችግር እያለቀሱ ማርያምን ከልጅሽ ከወዳጅሽ ከኢየሱስ ክርስቶስ አማልጅኝ ብለው ቢለምኗት ራዕይአልገና ቅዱስ ጊዮርጊስን ተከለያይ ማኖችን አስከትሎ በራእይ እንዲህ አለቻቸው እኔን ሳትወድ ሰምን ሰማን በምሥጋና ታንባለህ የአባትህን የወዳጁን የናአድን ትእዛዝ አፍርሰሐልና ልጁ በዳዊት ልብ እድሮ የጠላቶቹን ፀሎት አልበቀለም የተናገረውን አልሰማህምን ስለዚህ እኔም ፀሎትህን አልሰማህም ብትላቸው የእኔን ኃጢአት ሳታይ የአባቶቼን የዘርአያዕቆብንና የናአድን ቃል አስበህ ከልጅሽ አስምረኝ አሏት ያን ጊዜ ከአባታቸው ናኦድ ጋር እመቤታችን ቃል ኪዳን ነበራትና ናኦድም ለእመቤታችን ያለው ፍቅር ይህ ነው አይባልም ይኸውም ከታወቁቱት ስለማርያም የበኃጀው ፀሎት መልክአማርያም ክብረማርያም አባ ሀርያቆስ ከደረሰት ሌላ ውዳሴ ማርያም የሚባሉ አሉት ሕይወቱን ሁሉ ለድንግል ማርያም

አመጽኛና አንባጋቢዎች እንደነበረ በከራ እንዲህ አለቻቸው እንግዲህ
በሥጋህ ታግናለህ በሰይፉ ትሞታለህ አሁንም ከናአድ ዘር መንግሥት
እንዲያመጣ ያንመህ ንስሃ ግባ ዘርህ እንደአባትህ ናአድ የእሴን ኪዳን
ቢጠብቁ መንግሥታቸው ይፀናል ። ባይጠብቁ ግን መንግሥታቸው
ትጠፋለች አገራቸውም ለአህዛብ ትሆናለች እንግዲህ በንፍስህ ይ
ብለው እስከምንገናኝ ከወገር ወደወገር እንደሸሸህ እንደተደበደብ
ትኖራለህ አለቻቸው አጼ ልብነድንግልም እምሞትበት ሀገርስ የት
ነው ሊያቹበ ከወደዱት ነው የሚነሱ ቢሏት ከእንግዲህስ ወዲህ መላ
ፊትአስ ይንግርሃል ብላ ከብዙ ሠራዊት ጋር ወደሰማይ ስትወጣ አ
ቸት ከዚያ ከጠሉማቸው ነቅና ፊአዩን አጸፉት በጉንጀው ጸሀፊባቸው
በአንበሳ ዳዊት የልጁ ልጅ ኒዮርጊስ ሀንድ እንዲቀመጥ ተደረገ ።

እንደዚህም ሆነ አስማቲዎቹን ተከትለው ሄደው የነበሩትን
ሁለት መንኮሳት አባ ተክለተና አባ ገብረኢየሱስ የሚባሉትን ከነፊ
አህመድ ቢን አሊ ኢመር ቢን ጃኛ ኢመር የሚባሉትን አራት ሰዎች
ያብዛቢ ፊር ግራኝ አህመድ ለአጼ ልብነ ድንግል ላከላቸው የደብ
ቤውም ቃል እንዲህ ይላል ።

በእግዚአብሔር በመሻሪያውና በያቅርባያው ስም ምስጋና ለእግ
ዚአብሔር ብቻ ይሆንንትና በራሴ ለንጉሥ ለመሃመድ ከራሱ በ
ሌላ ነቢይ እያኑባም መሐመድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደሆ
እንመሰክራለን እግዚአብሔርም አንድ አምላክ እንደሆነ እናምናለ
በሰው ይሄን ደብዳቤ ለአፄቸው ንጉሥ ነገሥት ለወናግ ሰገድ የሚ
ላክ ለሃይማኖቱ የሚቸጋ ለወገኑ ሚቀሰል ለሀገሩ የነሳ ለላይ
ንጉሥ የሚታበዘው የእግዚአብሔርን መንገድ ይዞ የሚጓዘው እ
ፊደም መሐመድ ልጅ ይማም አህመድ እራት ነገርኝ ከእንተ እ
ለጋለው እንዚህም አንደኛው ምንም በሰላምና በክርስቲያን መ
የሃይማኖት ልዩነት ቢኖር በአንተ አባቶችና በእኔ አባቶች መካከል
ድኅንና ወዳጅነትን ለመጀመር ሴት ልጆቻችሁን ለወንድ ልጆቻችው ወ
ልጆቻችሁን ለሴት ልጆቻችው ሲሰጡና ሲያጋቡ በዚህ ጋብቻ ብዙዎች እ
ይተጋጠቀሙና እንደተፋቀሩ ሰምተሃል ከነዚህም አንዱ አባትህ ሴ
ሌሎች ደግሞ አያቶችህ ከመሳሰሚው ተመሳጅና ከሲሙ ጉሳ እንደአ
ወዳጅ አባትከን እንደጠፉ ታውቃለህ ስለዚህ ታላቂቱ ሴት ልጅ
እምራጽዮንን ስጠኝና እስልሜ ሚስት ላድርጋት ሁለተኛው
የአንተን ልጅ ሳግባ ከሕንድ ውቅያኖስ በመስስ ዋዜና አሞራ በ
ሱባቸው ሀገሮች ላይ ከእኔ በቀር ሌላ ንጉሥ እንዳያመጣባቸውና
ዳያስገብሩቸው ቢታጀራና በባይላን ላለው በር ሁሉ የበላይ አለቃ

ቀረም ተቀባዩ በእኔ ፈቃድ ብቻ እንዲሆንና እኔም ለአንተ የሚገባ ውን ማክበርና ገፀበረከት በየዓመቱ ይዤልህ እንድመጣ ስለተቸው ደግሞ ከአሁን በፊት ባደረግነው ውርንት ቂም ሳይገዝ ለአንዱ አምላክ ዘገል ይቅር ብለን ቅንኤል የማረከቸውን ታናሺ ወንድሜን ሁሉን ኢብራሂምንና አቡበከር ሚታን ቤን ሞስሲምንና ጀሉቲን ከታሠሩበት እስሬትተህ ላክልኝ ። እንዲልሞቱ የንጉሥ ወሰን ሰነድ ወንድም ወናግ ዋን ትሸም ልዩ ሀገሩ ትግሬምን ከሚባል ሀገር ውስጥ ልዩ እስር ቤቱ ደበሉ ከሚባለው እንዲታሰሩ ነግሮኛል እሱውም እኛን ተጠግቶ ሰልም እስከማስፈት አለ ሰፈ ሀገር የሆነ ግዛትም ስተቹቸለው ። እኔ ደግሞ የዲጋልኛን ጋር መዋቀታው በመርንት የተማረኩትን ትላልቅ የጦር አዝማቶችህን ጊዮርጊስ ዘርአየንና አዝማች ክፍሌን ፊብ ሃብ ርን የሌሉ መርዳን ጌታ ዥቲሳይ በየን እሁተህን ቀለምሲስን ያገባ ውን ዲጋልሳዊንን ፈትቼ ይስ እንዲልህ ልኬልሃለሁ ሌሎችን አራት መቶ የሚሆኑትን ግን ያልከሁን ስታደርግልኝ ፈትቼ እልክልሃለሁ ስዉ ልጅን እንደሚፈልግ አንተም እኔን መርዳት አለብህ ።

የመጠረሸው አፈተኛው ነጋሾችን መሐመድ የተከበረው ንጉሥ ነገ ሥት እርግህ ለሰደተኞች አሸባሪዎች በአደረገው እቀባበልና እርዳታ ምክንያት አበሻን ከርስቲያን ነው ብለሻው ሳይነካቸው እንዲተንኩት ለዛሬን በሰምና በራሴ ለነጪ መሐመድ ይሁንና ታሪን እኔን ሲጀቹ ከሰሰም ወንድሞቹም ካልነኩችሁን እንንኩቸሁም ነገር ግን እንዲህ እራሱ በሁዳችን መካከል ክሌሉ አበሻን በሙሉ ጠቅልዩ እገዛዋ ለሁ በማተክርስቲያን ፋንታ መስጊድ እሰራለሁ በክርስቲያን ሕዝብ ፋንታ እስላም እንዲሆን እደርጋለሁ እዋጅት ሰምቶ ወይእኔ የመጣን ክፈርስቱ እስከሸመቱ ከዛደማዋዩ እስከሚሰቱ በክብር ሳይነካ ይኖ ራል ብለዋቸዋል ።

እዚ ልብነ ድንግል ይብዳይሉን ከመቀበላቸው በፊት ደጃሉን ያለሰኛቸው ፈቃድ ሸኝተው በተመለሱና እሁንም ሐሳት ከሆነው ከግራኝ አህመድ ጋር በንብተው ይብዳሊ ይዘው የመጡትን መንከላት በግዘት እንዲኖሩ ወደግቢን እስላኪቸው ይብዳሊውን ግን ከበዓት ቀን በኋላ ከእስንበትትና ከተማከሩበት በኋላ ከግራኝ አህመድ የተላኩት መልእክተኞች ቤን አሊ ኡመርና ቤን ጀሻ ኡመርን ለጻፈላቸው ደብ ዳቤ መልሱን ላኩለት የተላከውም ደብዳቤ እንደዚህ ይላል ።

ለሰሙ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ይሆድብዳቤ የተላከ ከእቸናፈው እንበሳ ከይሁዳ ነገድ የዳዊት ልጅ የሰለሙን

ልጅ የምኒልክ ልጅ በሥጋ የናኦድ ልጅ የላይኛውና የታችኛው የኢት-
ዮጵያ ሀገሮች ንጉሡ ንጉሥት ከእጼ ዳዊት ወናግ ሰገድ እስንም እንተ
ንም የፈጠረ አምላክ ዛሬ ጊዜ ሰጥቶህ እስከምትጠፋ ለምታ
ፋውአስከምትገደል ለምትገለውና ክርስቲያን ሕዝብ ባሪያ አድርገ
ለምትሸጠው ለአህመድ መሐመድ ደብራሂም ትናንትና ድሉ ለእንተ
ቢሆንም ነገ ለእኔ ድል እንደሚሆን አውቀህ የማረከሐቸውን ሳት
ድል ወይም ባሪያ አድርገህ ሳታሸጋር አቆይተህ በመላክህ አልደነቅ
ይኼውም ለአንተ ምርኮኛ ሆነው ቆይተው ወደእኔ ፈትተህ ብትል
ቸው በሕይወት ከመኖራቸው ይልቅ ተዋግተው እንደሆናቸኝ በጠ
ቢሞቱ ይሻላቸዋል ሰላሙ ደግሞ የአባትህ ዘር የመሳፍንትን ባታ
የእኔን አባቶች ስም ማንሳትህና ልጀን አሰልመህ ለማግባት በ
ጠየቅህ እንዴት ብትደፍረኝ ነው ! ከእሱን በፊት በሌሰሁበት ቤተ
ንግሥቱን አብያተ ክርስቲያናትን በርሃብ በማቃጠልህ ሕዝቡን ባሪ
አድርገህ ወደጌቶችህ በመላክህ አልቤት ብሎ አበሻን በሙሉ እንግሊ
አብያተክርስቲያናት አፍርሼ የማምላኪያ ቤቶች አሰራለሁ ክርስቲ
ንን ሕዝብ አረመኔ አደርጋቸዋለሁ ብለህ መመኘትህ እንዴትስ ፈ
ብትሆን ነው እንዴትስ ጨካኝ አረመኔ ብትሆን ነው ! እንዴትስ
ጊና መካች ብትሆን ነው ! ለንጊህና ከባህር ማዶ የመጡትንና ለእን
ገናችን ነህ ብለው የተገዙልህን ጭፍራዎችን ይዘህ የምትተማመን
ቀን ቀርበህ መልሱን የመጨረሻውን ቃል ላክልኝ ተጻፈ በመጋ
ጥር 23 ቀን 1522 ዓ.ም ድል አገኘ ።

ግራኝ አህመድ ከአጼ ልብነድንግል የመጣለትን ደብዳቤ ከአ
በበ በኋላ የመጨረሻ ቃል እንዳህ የሚል መልስ ላከላቸው ፡
ችን ትልቅ ደካሞችን ብርቱ ድሆችን ሀብታም የሚያደርገው እግ
ዚያ እግዚአብሔር አፈጣጠሩ እንደትንሳን አጠፋክዬ እንደናቲ
ነቱና አመጣቡቱ እንደአቢቱ አድርጎ ቢፈጥረኝ አገባሁ እንደ
አሉሩ ነው ሥራዊቱም ጉብ አሠራውን እንደሚከብ ነው ጉብ አለ
ለመቅሰም እንደሚጠመግራ ሥራዊቱም ለሃይማኖቱ ሲሞት እንደ
አድርጎ በአበሻ ላይ ልክልኛልና በለመርንቱ ቀን ጉብ ሲቀሰም በ
ለአበሀ መጣው ብሎ እንደማይልበት ለእንተም ከዚህ ሌላ የሚላክ
የለም ድል ሲታገኛቸ ለደካሞች እንጂ በበራቸው ለሚመኩ ለ
አይሆንም ብሎ በቁጣ የተጻፈ ደብዳቤ በአንዱት ትንሽ ጀበቃ
አድርጎ ተማርከው ለነበሩ ለንጉሡ ጃንደረቦች ላከው በዚህ
አጼ ልብነድንግል አንድ ቦታ ሆነው ከላር እስከላር ግዛታቸው
ያለው ሠራዊት እስከሚመጣ ይጠባበቁ ነበርና ደብዳቤውን ተመ

ቂና ንግግሩ አስደንቋቸው አፈጣጠሉ እንደተንጎዳገና አጨካከሉ እንደ እናቱ ያለው የንግግሩ ምንጩ አልገባቸው ስላለ ለአማካሪዎቻቸው ቃሉን ተናገሩ እንሰዎም ትንሽን ባለቤት በታ ፈጣን ፈረሰኛ እንዲ ልብ አዘዙና ፈረሰኛው በጉንዳኑ ላይ ጋልቦ ሲመጣ የፈረሱን እግር ቢያውቅ ጉንዳኖች ተጣብቀው ተገኙ አጨካከሱን ለማወቅ ከሩቅ በቅ ርብ ለመጠት መኳንንት ሰብስበው የሚስቱን እራስ ቆርጦ የሚያ መጣ ልጅን አድርሲታለሁ ሲሉ መንግሥት እስጠቻለሁ ብለው በም ስጢር ነገረው ጓደኞቻቸው ንጉር ግን ሁሉም ስጋልጨክን ከፈለጉ እኛን ያገዳሉ እንጂ ሚስቶቻችን ጨክነን እንነልም ሲሉ በሌላው ቀን ለአጼው ተናገሩ እጼሠም ሴቶችን በስሠሩ ጠርጥሠው ለባሎቻቸው እንደተናገሩት ነገሩአቸው ከነዚህም ብዙ ሴቶች የባላቸውን እራስ ቆርጠው ባገልግል ውስጥ አድርገው አቀረቡ አጼ ልብነድንግልም ባሎቻቸውን የገደሉትን አስገድለው ሴት ምን ያክል ጨካኝ እንደሆ ነች ተረድተው ድል ለሰጠው እግዚአብሔር ይሰጠው ብለው ድንግል ማርያም በስድስት እንደሚኖሩ ምንም ብትንገራቸው ከጦር ሠራዊት ብዛት ድል የሚገኝ መስሏቸው ለጦርነት በእንዶጥናዘ ከተማ ሆነው ይዘጋጁ ጀመር እንደጥናዘ የሄደው እንስመ ነው ሀገሩ ፍቹ ይባላል ።

እንደዚሁም ተባለ በደፋት ያሉ የአማራ ልጆች የባንግዚው አጼ ልብነ ድንግል በሃሀገሩ በፈታት የማናደስብእ አላክ ከብር ይብል ቢሆ በባባ እገራቸው አጼው ቢሸፍቱ አላሁ ክበር አለ ግራኝ በታቦቱ ብለው ስለሀሩ እስከባሌ ድረስ እንጻኪያ ሲወረር ሲታጠል የደዱ በት ሀገር በድተመበሉ ቀርቶ ቢሸፍቱ ቀበሉ ከምንቱ በድቀ ከዘፈው ቢሸፍቱ ወደም ደብረ ዘይት እንደሄሉና ሬት ወደሌሉ ሀገር መኖሬ ቸውን ሰምተ ግራኝ አህመድ አስራ ሁለት ሸህ አማረኛ ጦር እራት ሺህ ፈረሰኛ ጦር ከሰባት በየኔት ጸጋዩሉ የጦር ስልትምትና መላ የሚ ያውቁት የአረብ ተወላጆች አምስት መቶ በሚሆኑ ታጅቦ ከሀረር በአምስተኛው ቀን ቀጆ ወንዝ ደረሰ ከዚያም ሰላዮችን ልኮ ያበለል ጀመር በድቀ ከተማ ውስጥ ንጉሥ ነጋሡቱ እንደሌሉና ጥቂት ጦር ብቻ እንዳለ ሰላዮች ተመልሰው ነገሩት ከዚህ በኋላ ወደከተማዋ ሲጠጉ የክርስቲያን ወሬኞች ለውጊያ እንደተዘጋጁ አፄ ፈረሰችሁ ላይ ሠወሩና ወደ ከተማዋ ተጠጉ ነገር ግን ለውጊያ አትቸኩሉ እንሱ ወደእናንተ ሲመጡ ተመልሳችሁ ወጋሁን እስከምትችሉ ቸገሩ ድረስ ሸሹ ከዚያ በኋላ የተከተሏችሁን ለመውጋት ተቀላቀሉ እናንተ የአማረኛ ጦሮች በወንዙ ውስጥ ተደበቁ ብሎ ትእዛዝ ሲያስተላልፍ የፈተኛ ዎሙ የጦር መሪ በበር አዶሉ ከንጉሩ ፈረሰኛውን ይዞ ወደሸለቆው ተቻግሮ ሄደ አማረኛው እንደተባለው ከሸለቆው ተሰገሰጉ ተደበቀ

ከዚያም ሽልቆውን የተሻገረው ፈረሰኛ ጦር ከክርስቲያኖች አገ
ረኛ ጋር ትንቅ እንደገጠመ ተመልሶ ሲሸሽ ክርስቲያኖች ተከትለው
ሲያሳድዱ ሽልቆውን እንደተሻገሩ ተመልሰው ገጠሟቸው። የተሰገሰ
ገውም ከአሰበት እየወጣ በኋላ ደርሶ ይወጋቸው ጀመር። ሆኖም ግን በን
ቅራ አደሱሰና በነርቢል በንአሴር የሚመራው የክርስቲያን ጦር አ
ማያውን ነቅር ለምድና ጥሩሩን ለብሶ እየፎከረ መንገድ የሰነበተው
የሰላም ጦር በጉራዳዱ በጦር ገደለ በስዚህ ብዙ ሰው ሰላሙ
ግራኝ አህመድ ወደአሰበት ምሽግ ሸሽተው ሄዱ። ግራኝ አህመድ የ
ሸሸውን ሠራዊት ዛሬ ጊዜ ከክርስቲያኖች ፊት እንዴት ትሸሻላች
ከዚህ ብታምጡበው እኛን አሳልፈው የሰደዱ መሸሻሻችሁን ካመቱ ይ
ችላል ለመሆኑ ከመንግሥት ሰማያት ረቃችሁ ትሸሻላችሁ እንዴት የ
ንላችሁን ምንም ማድረግ አትችሉም አላቸው። ቃሉን የተቀበሉ ሲ
ቃሉን ሳይሰሙ የሸሹትን የሰማሉን ጉጣዎች ሰይፍና ጋሻ በመ
በያዙ በየመን ወታደሮች በጥይት ተደብድበው እንዲሞቱ አዘዘ በ
ዘን ጊዜ ብዙ ሰው አለቀ ከዚያም ከአረብ አገር የተላኩለትን ድን
ኳኖች እሩር እሩር አሰተከለ የክርስቲያኖች ጦርም ድንኳኖቹን ከ
ሥፍራ ተተክለው ሲያይ ማፈሩን ትቶ ወደከተማው ተመለሰ።

ግራኝ አህመድ ዚዘር አይሉን እንዴት እንደተሸነፋና ብዙ ሰ
ከነሱ እንዴት እንደሞተ ወኖቅው ዚዘር አይሉም ለግራኝ እንዲ
ሲል መለሰለት በኢያንያ የሚመሩ ቀስተኞች የሚወረውሩት ቀ
ሳይወጋ ከመሬት አይወድቅም የተወጋውም ወዲያውም ይሞታ
ማግሽ ያንተላቀል ክርስቲያኖች መጥተው ያንቀያሳፉውን ከወደቀበ
በጦር ወግተው ይገድሉታል ሲለው ከጅዳ የተላኩለትን የአበባ ያ
ፍና የተሸጉረጉረ የሃር ልብሶች አሲዞ ወደ አረም አሊቃ ወደኢል
ሁለት ሰዎች ላከበት እንዲህ ሲል አንተና የአንተ ሠራዊት መርዝ
ቀስት እንዳላችሁና ተዋጊዎች እንደሆናችሁ አውቀሻለሁ እኛ
ከእናንተ የበለጠ ተወርዋሪ እርሳስ አለን ተኩሰን እንደማንገ
ታውቃለህ ስለዚህ በእኛና በክርስቲያኖች መካከል ጣልቃ አ
ቀስተኞች አትሂዱ ብትል ቃልህን ይሰማሉ ይህን ብታደርግ
ላም ሕዝብና በእናንተ መካከል እስከ ልጅ ልጅ የሚተላለፍ
ጅነት እናደርጋለን ለማላሰቢያና ለወዳጅነት በር
ከባሀር ማዶ የመጣን ልብስና አንተ የምትቀመጥበት ምንጣፍ
የለሁ ብሎ ላከለት ከእጁ ናእድ ጅምር የታወቀው የመደበይ
የዛሬዎች አረሞች ማለት ኢማያ የተላኩትን መልእክተኞች
ብሎ በክርስቲያንና በእስላም መርንት መካከል እንደማይገባ ቃል ከ

አድርጉ የሳክሱትን ተቀብሉ የቀሳኩት መልእክተኞች መልስ ያለውን ይዞ እንዲነግሩት ላካቸው። በአረሞችና በእስላሞች ከፋግዬ ፓምር ወዳጅ ጅነት እየሆነ ሄደ ።

የአጼ ልብነ ድንግል ጦር አዝማቾች ለ ኢዚው ምንም ድል ቢያደርጉ በእስላሞች ሰፈር ብዙ ድንኳን ተተኩሉ ሰላዩ ግማሹ እንዲጋሊል ግማሹ ደግሞ እንደመጀመሪያው የተደበቀ ጦር ቢኖራቸው ነው ብዙ ድንኳን ሊተክሉ የቻሉ ሲል ሌላው አጼ ልብነድንግል እስከሚወጡ ድረስ የያዝነውን ሥፍራ ሳንለቅ እንቆይ እያለ ከሶስት ሃሳብ ተከፍሉ የአንዱን ሃሳብ አንዱ አይቀበሉትም ነበር በዚህ በባድቁ በበደሰነ ሰንት ወርኸት ውስጥ ብዙ የሰማሊያ መሬቶችን የሚባሉ ጉጣዎች ሞቱ ። በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ቁስለኞችን እሲህ ሌሊት የመንዲያ ጉጣዎች ወደሚኖሩበት ሀገር ጁዲ መሃባይ የሚባለት አረቦች ለመውጋት ተሰልፈው መጥተው ነበር ግን ቃል ኪዳን ያደረገው ኢልማያ ሰማ እንዲህ ሲል ተናገረ እኛ እስላሞም ክርስቲያንም አይደለንም እነዚህ ለሃይማኖታቸው ሲሞቱ መጡ እንጂ ሀገራችን ሊወሩ እኛን ሊገድሉ አልመጡም ስለዚህ እኛን እስካልነኩ ድረስ ተዋቸው ይለቁ አላቸው ግራኝም አምላኩን አመስግኖ እኛ እናንተ ካልፈቀዳችሁ አርዱትም አንል እስልሙም አንል እኛ ደል ብናደርግ የክርስቲያኑን ሀገር ሁሉ ለእናንተ እንሰጣለን ብሎ በአምላኩ ምሎ ቃል ገባላቸው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል በእራተኛው ከተማቸው ሆነው የጐጃሙንና የጸዋትን የበጌምድርና የትግሬን የጦሩትንም ጦሩ ሁሉ ሰብስበው አዳልና ሱማሌን ሁሉ ለመውረር ሲዘጋጁ በባድቁ ያሉት የጦር መሪዎቻቸው ከርቢልና ከእሰር እንዲህ የሚል ደብዳቤ መጣላቸው ግራኝ አህመድ ከብዙ ሠራዊት ጋር አድብቶ መጥቶ ቢተመንግሥቱንና ከተማውን ወሮ ለማቃጠል መጥቶ ነበር ነገር ግን ጂሀ የሚሆን ሰንገልበት ሁለት ሙቶ ስንማርከበት አሁን ሸሽቶ ወደሀገሩ ተመልሷል ። አባጉቺ ኢልማያ መንገድ እንደለቀቀለት ሰምተናል ስለዚህ ቶሎ ትጉትና ያዙት ወይም ግደሉት ወይም እኔ እስክደርስ ቆዩ የሚሉን እንደሆነ ከዘር ቃልዎን ለመስማት በመጠባበቅ ላይ ነን ።

በዚህን ጊዜ አጼ ልብነድንግል በአዋሽ ተከሰ ኢያሱስ መድህንና በአዝማች ተክለኢየሱስ የሚመራውን የትግሬን ጦር በእንቁብ ሚካኤል ባህረ ነጋሽ ዘወንጌል በትግሬ መድህን ኪርስ በደብረ ቢዘን መሞሸር አረጋዊ ቢዘን በሌሎችም የሚታዘዘውን ቀድሞ የሐማን

ጦር ይዘው ነጋሪት እያስጐሠሙ ከእንጦጦስ ከተማ ተንስተው በድ
ከሚገኘው ቤተ መንግሥታቸው ገቡ ከዚያም እንደደረሱ ይብ
መርዘኛ ጦር ተዋጊ ለሆነው ለአባ ጉቼ ኢልሚያ ተንኮር እኔን ንጉሥህ
በልብስ ቀድረህ ምንም ነገ ያንተ ጠላት ቢሆን ግሬ የክርስቲያን
ሕዝብ ጠላት የሆነውን አሳልፈህና ሸሽተህ እንደሰደድከው ሰምቻለሁ
አሁን በሄደበት ሄደህ በአደረበት አድረህ የዚያን አረመኔ እራስ ካ
መጣህ እንተንና ወገንህ የተማላህና የተናቅህ ሆንህ ትኖራለህ ። ይሆንና
ባታደርግ እኔ ደግሞ እናንተን የቅርቡን ጠላቴን ሳልጠፋ ያንን አረመ
ለያጠፋ ይቻላል እንዳይመስልህ የሚል መልእክት ላኩበት ነገር ግ
ይህን የመሰለ የቁጣ ቃል ሲላክበት ግራኝ ሆኖ እንደሚረዳው አባ
ጉቼ ኢልሚያ ወንኀራ መልእክተኛ ላከለት ።

እንደዚህም ሆኖ ንጉሡ ነጋሦች አጼ ልብነድንግል ወደኢልሚያ
የላኩትን የትእዛዝ መልስ ሳያገኙ ግራኝ አህመድ በአዋሽ ሸለ
ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ከአረብ ጦር ጋር ሆኖ ተመልሶባድቶ
ከተማ ለመውረርና ለማቃጠል ይዘጋጃል የሚል ወሬ መጣላቸው ።

አጼ ልብነድንግል በአንጻኪያ የነበረው ቤተ መንግሥታቸው
መዘረፉና መቃጠሉ በጣም አዝነው ተናደው ስለነበር የቋሞትን
የጐጃም የበጌምድርንም ነጋሲዎች የሌሎች ሀገር መኳንንትና መሣ
ንት የጸዋ አዝማቾችን ሳይጠብቁ ነጋሪት እያስጐሠሙ መለከት እያስነፉ
በየአሉቀው በአዝማቹ ጦሩን ከፍለው መጋቢት ሰምንት ቀን እንደ
ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት ዓ.ም ወደ አዋሽ ጉዞ ቀጠሉ ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ንጉሠ ነገሥቱ ያሉበት ቦታ እሩቅ
ነው ኢልሚያም እንደሚረዳኝ ቃል ገብቶልኛል ምንም አይመጣብኝ
ብሎ ውሃ ባለበት ቦታ ቁስለኞቹን ይዞ እያስታመመ ከቆሰሉት
ዋናው በዚህ ቀን ተዋጋ በዚህ ቀን አትሂድ እንዝሽ እንዋጋ እያ
የሚያደፋፍረውኖናስር አደን ልጅ ሙፍቴ ሲድ አቡበክርና አመ
ሙጃሳህን ያገባው ጎሬድ ካሚልና ኡሚር ሞጃሂድ ከአራት መቶ በላ
ቁስለኞች ስለነበሩና እነሱም በግከም ላይ እንዳለ እንጅ ለመመለ
ተስፋና ምኞት .../ፈጽሞ አልነበረውም ። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ
ወደእሱ መምጣት በሰሙ ጊዜ ለትልቁ ጦርነት ዋዜማ መራር በሆ
ልቅሶና ሐዘን ሜት እየቀመ ጋዥ እያሳቡ በበሉት አደሩና ተዋት ለ
ርነት ዝግጁ ሆኑ ። ሙፍቲ ሲዲ አቡበክር ቁስሉ ተሸሉት አድሮ ነበር
ከቁርዓን የሚገኙትን የጦርነት ቃላቶችን እየጠቀሱ እንዲበረቱ እየ
ግራኝ አህመድ የኢብራሂም ልጅ እግዚአብሔርን በክብርና በምስ

ኢያሱ ስለነቢዩም እየፀለየ በእግዚአብሔር እሙን የእርሱም ድጋፍ ፈልጐ ብርቱዎችና ጀግኖችን ያድርጋቸኋል የጦር መሣሪያቸውን እንዲታጠቁ አዘዛቸው ።

በዚህ በአዋሽ ሸለቆ አካባቢ በዛሬው አዳማ ወይም ናዝሬት በምንትዋ ሽንብራ ኩሬ መርኑት በግራኝ በኩል የነበረው ሕዝብ ሰባት ሺህ ከሁለት መቶ እግረኛ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ሰባ ፈረሰኛ አምስት መቶ የአረብ ጠበንጃ የያዙ ወታደሮች እነዚህ የሚሸሸውን የሚያስገድዱና ግራኝን የሚጠብቁ ናቸው ። እነዚህ ሁሉ በየአለቃቸው በየጉዛቸው እንዲሰለፉ ተደረገ ።



የግራኝ ወረራ

በአጼ ልብነድንግል በኩል አሰፉ አምስት ሺህ ፈረሰኛ አርባ አንድ ሺህ እግረኛ ይኸም ጦርና ጉራዴ ይዞ ቀሚሳ ሰድስት መቶ ጠብንጃ ነበር እነዚህንም የሚመሩት ግን በለው ተክለኢየሱስ እቁበ ሚካኤል ባህር ነጋሺ ዘወንጌል እረንቹ በዛን የሚባሉ የደብረ ሊባኖስ መነኩሴ ርቢል ግርማ ነአኩቶ ለአብ መስቀል ሃይሉን የሚባሉ የአማራና የትግሬ አዝማቶች ሌሎችም የጎራኝ ምርኮኛ የነበረው ደጋልያን አብሮ ነበረ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ የኢራኤልና የጊዮርጊስን ታቦት ተሸክመው በንጉሡ ነጋሪት ፊት ፊት ይሄዱ ነበር ።

በቀዋት ሁለት ሰዓት ላይ ንጉሡ ነጋሪት አጼ ልብነድንግል የማብለቀለቀ የወርቅ ጥላቸውን አዘርግተው ታቦቱን በፊታቸው አስቀመው ሶስት ጊዜ ከሰገዱ በኋላ ይህ አረመኔ ከንአ ጋር ሊዋጋ መሰለቀን ግፋን ተመልከት እግዚአብሔር ብለው ከሥራዊታቸው እስከነፍሱ ይዞልኝ የሚመጣ ልጄን አትሊሰዮን እድርለታለሁ ብለው ተናገሩ ይባላል በዚህ መካከል በግን በለው የሚመራውን ጦር ላኩባቸው እነሱ ግን ፊት ለፊት የሚዋጋ ተቀላቅሉ መሰሏቸው ነበር ነገር ግን ሁሉም ቦታ ይዘው ካሉበት አልተንቀሳቀሱም ግራኝ አሀመድ የጦር ስልት አዋቂ ስለነበር እነሱ ይምጡ እንጅ እናንተ አትሂዱ ምሽጋችሁ አጠንክራችሁን ያዙ ጦራችሁን ደግኑ ሰውነታችሁን በጋሻችሁ ከልሉ የእግዚአብሔርን ስም ሳታነሱ አንድም እርምጃ አትራመዱ አበሻዎች ሆይ ድልን የሚያገኙ ታጋሾችና ጽኑአን መሆናቸውን አስተውሉ ሲል ወሳኞቹ ፈረ ተሸናፊ መሆኑን አወቁ ጽኑአንን እግዚአብሔር ይረዳቸዋል ። ሃይለኞችን ያደክማል ግራ ከእኛ ጋር የሰይፍን ወጊያ ታገስ የፀና ነን ከእኛ ጋርደስ ይለዋል ከዚያም ወዲያ ድካም የለበትም እያለ በወኔት ሲናገር ክርስቲያኖች እየሮጡ ሰይፋቸውን እያብለጨለጩ ባንዲራቸውን እያውለበለቡ ሄዱባቸው ከግራኝ አሀመድ ጉን የተሰለፉት ጠመንጃ የያዙት የባህር ወታደሮች አራት ተከፍለው ፊትና ኋላ ሆነው ተሰለፉ በዚህን ጊዜ ፈረሰኛ እየጋለበ ገስግሶ ሲመጣ የፊተኛው ሲተኩስ የኋላው ወደፊት ይላል የፊተኛው የኋላው ወታደር ወደነበረበት ይመጣና ቀለሁን ያጠግና ሌላ ያጉርሳል ሌላው ደግሞ እንደዚሁ እየተቀያየረ ብዙ የክርስቲያን ፈረሰኛ ጦርፈጀ ከዚህ በኋላ የትግሬ መኮንን አዝማች የሆነው መስቀል ሃይሉን የሚመራው ፈረሰኛና እግረኛ ጦር የጥይት ቀለሁ እውጥተው ሌላ እስኪሚያጉርሱ በጦርና በሰይፍ አጣደፋቸው በዚህን ጊዜ ፈረሰኛ ከፈረሰኛ እግረኛ ከእግረኛ ተያይዞ በግራ በኩል የነበሩት የሱማሌ ጎሣዎች ሊሸሹ ሲሉ ፈረሰኛ አባር ገደላቸው ብዙዎችም ተማረኩ ።

የሀርላ ጕሣዎች በቀኝ በኩል አጥብቀው ይከላከሉ ነበር ነገር ግን አልቻሉም በግራኝ ፊት ለፊት ያሉት የሲያና የዘሪባ በመአግይ ጦር በግራኝ እግች መታንቢን እትማን የሚመሩት ደለና አድርገው ሲከላከሉ እንደቆዩ አዲስ የክርስቲያን ጦር በባህር ነጋሺ ዘመንጌልና በቶናኤል የሚመራው ሄዶ እንዲቀላቀል ታዘዘ በዚህን ጊዜ የአዳልና የሱማሌ የሐላ የጀሬ የዶባሬ የመራይቻን የሀብር ማጋዲ የሀርላ የሲም የሀበር ማጋዲ የሀርላ የሲም የሃርላይ የጊሎመብርህ የባርሀይ የሂቂያ የያቆላህ የጀበር የአራብ ቀላ የኢሴካ የሃርቴ የመሌሳይ ወታደሮች ጕሣዎች በአጠቃላይ ሰባት ሽህ በላይ የሚሆኑ ሞቱ። በመጀመሪያ ከክርስቲያኑ በኩል ብዙ ሕዝብ በተይት የገደሉ የአረብ ጕሣዎች ግራኝን ይዘው እየተከላከሉ ሲገኙ ሲሉ ሚካኤል በጉብኤ የሚባለው ፈጣን ግራኝ አህመድ ከአረቦች መካከል ገብቶ እጁን ሰምሮ በፈረሱ አድርጐ ሲገባ ሲል በተይት ተመትቶ ወደቀ ሌላው ደግሞ ስሙ ያልታወቀ የክርስቲያን ወታደር ሄዶ ማርኮ ይዞት ሲመጣ ድንገት ሳይታሰብበት መልና በፈረስ ሆኖ ከሌላ ነገድ ጋር ተቀላቅሎ አምስት ሺህ ማህሬን የአረብ ወታደር እየተጣደፈ ደረሰና ከዋለው ጦር ጋር ተቀላቀለ ግራኝ አህመድን ከማረከው ሰው ነጥቀው ሌላም ብዙ የክርስቲያን ወታደር ገድለውአዳኑት በዚህን ጊዜ ሌላ አዲስ ጦር መምጣቱ በአጼ ልብነድንግል ሰፈር ስለተሰማ ሌላ አሁንም በብዙው ተቀላቅሎ እንዳይጋ ትእዛዝ ተላለፈ። ሆኖም ግን ቀኑን ሁሉ ሲዋጉ ውለው ስለዉሉም ሁሉም ወደ የሰፈሩ ተመለሰ ወገዙ በእስላሞች እጅ ሆነ ክርስቲያኖች የእስላም ጕሣዎች ወደሚኖሩበት መንደር ድንኳኖቻውን አስተከለው ነበርና ወደዚያው የተማረኩትንና የነሱን ትላልቅ የሞቱትን ሰዎች አስንስተው በተራራው ስር በሚገኘው ሸለቆ አስቀበሯቸው ከክርስቲያኖች የሞቱት 14000 ሺህ እንደሚሆን የታወቀ ነው ይሄውም አገሣቹና ጦሩ በበነጋታው በየቦታው በመደባይ ጕሣዎች ስለተገደሉ ቁጥሩ ሳይታወቅ ቀርቷል። እንደዚህም ሆነ በበነጋታው መጋቢት አስር ቀን አጼ ልብነድንግል መነኮሳቱና ቀሳውስቱ ሳይቀሩ ለመርነት እንዲሰለፉ አዋጅ አሳውጀው ነጋሪት ሲያስጉስሙ መለከት ሲያስነፉ ሳለ ድንገት በኋላኛው ቁጥሩ ይሄ ነው የማይባል መደባይ የባሬዎች ኦረዎች በአባጉሮ ኢልማያ የሚታዘዙት መርዝ የተቀባ ቀስትና ሽተል ወርዋሪዎች ደረሱና ብዙ የክርስቲያን ጦር አድብተው ገደሉ በዚህን ጊዜ መጀመሪያ እነዚህን እናጥፋ ብለው ጦራቸውን ወደእረዎች አዞሩ የሚያበሩት የስሌ ነገዶች የባሬ ስላሌዎች ነበሩ። እነሱም ብዙ ሰው ከገደሉ በኋላ የመደባይ ሱባዎች ብዙዎች ተገደሉ እስለቃቸውም አባመርዞ አባ በላ ንጉሳቸው አባ ክርቶ አባ ጉታ ተይዘው በፈረስ ተጐትቶ ስጋቸ

ቸውን ቆራርጠው ለአሞራ ይብላቸው ተብሎ ተጣለ ሉዓ ማለታ ጠራ
መር በዚህ በአዳማ ወይም በሸንብራ ቆራ ጦርነት የሰው እሬሳ በየቁ
ጥቋጥው በየሚሄደው ወድቆ ይታይ ነበር። አሞራውም ጂቡም ለመብላት
ፍላጐት አልነበረውም በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት መጋቢት
10 ቀን በዚሁን ጊዜ ግራኝ አህመድ የኢሊማያ ጭፍሮች እንደረዱትና
አጼውም ከሰርሱ ጋር መኳንንቶቻቸውን ትተው ወደ ኋላ መሸሻቸውን
ሲሰማ አምላኩን አመሰገነና ለሠራዊቱ እንዲህ አለ እግዚአብሄር እኛን
አረድቶ ጠላቶቻችንን በእኛና በራሳቸው ጦር አዋረደ አሁንም ንጉሡ
ንጉሥነቱን የሚረዳው የሰም ተከትለን እንውጋው ብድቴ ከተማውን
ተመልሰን እንውረር አላቸው የጦር መሳ የሚያውቁት ወታደሮች
የቁርጡና የየመን ተወላጆች እንዲህ አሉት ብዙ ወታደር ከእኛም አልቆ
ያለነው አሁን ትንሽ ነን የምንበዛው ቁስለኞች ነን ብንከተል አንሱ ግና
አልተንኩም ሌላው ደግሞ ለጦርነት እየመጣ ይሆናል እግዚአብሄር
እኛን ሲያድነን ፊልጐ ሌላ ጦር አስንሰቶ አስወጋቸው እንዚያም ብዙ
ሆቸአለቁ። ስለዚህ የእኛን ቁስለኞች ይዘን ወደሃገራችን እንመለስና
ከአረፍን በኋላ ሌላ አዲስ ወታደር እንደመጣልን እየንጠሉን በድብቅ
እንወጋቸዋለን አሉት። ግራኝ አህመድ የሚሉትን ስለሚሰማ እሺ
ብሎ አዲስ ከመጡት አረብ ወታደር ጋራ ወደሃገሩ በድል አድ
ራጊነት ተመለሰ የሱማሌ ነገድ የመራይሃን ነገድ እንደሌሎቹ እንግማ
ከራሱን ብለው መጥተው በጦርነት ስላለቁ እሱን ለመግደል ተነሱ በዚ
ሁን ጊዜ ሱልጣን ኡመር ዲንና የባአድ ዲን ዘሮች አሚሮች ሊገሉት
እንደተማከሩ ሰምቶ ከሃረር የአባቱ ወገኖች ወደሚኖሩበት ዘርባህ
ሃገር ሄዶ ነበር ግን በዘርባህ ሳለ የያሺህ እንደሆነ የአረብ ወታደር
ማህራን ስለተላከለት ጠላቶቹን የወላሰማ ዘሮቹን እያስፈለገ አስገ
ደለ እሱን ሊረዱት የመጡት በሃረር ባላባትነትን አግኝተው እስከ
ዛሬ አሉ እነሱም የሃደያ የዶንዶ ሃገር ስለተሰጣቸው በአደያ አደሬ
የሚባል ስም ተሰጣቸው የሱማሌና የመራይሃን ነገዶች ሱልጣኖችና
አሚሮች ሼኮችና ሸሪፎች ይቅር በለን ባጠፋን ብለው ስለላኩበት
ሳያስገድላቸው ቀረ ከዚያ በኋላ ውስጥ ውስጡን ከአጼ ልብነድንግል
ባለሟሎች ሰላዮችን እየላከ ወደየት እንደሚሄዱ ምን እንደሚያደርጉ
እየጠየቀ እስከ አለቁ ሞታቸው ድረስ ፊት ለፊት ሳይገጥም በስለላ
ዘዴ ተጠቀመ።

አጼ ልብነድንግል በአረቦች ጦር ምንገንያት የሸንብራኩሬ ጦርነት
የድል ባለቤቱ ሳይታወቅ እንደተለያዩ ሁሉቱም ሳይገኙ አንድ ከረ
ምት አለፈ በዚሁ ዘመን ሲያዩ አንድ ከረምት አለፈ አሁንም
በዚሁ ዘመን ለየገዳማቱና ለየአድባራቱ ሠር እግዚአብሄር ወሰጉ

እንዲደርጉላቸው ለመነኩሳቱና ለካህናቱ መብአ ልከው ነበር ግን ለሰ አጼ ልብነ ድንግል በየደብሩ በየገዳሙ የሚመራው በቱርክ ስር ከሚገኘው ከእስክንድርያ ማለት ከግብፅ ፓትርያርክስ ሃይማኖት መዋቀ ከሮማው ካቶ ሊክ ሊቀ ጳጳስና ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ወዳጅነት ሊያደርጉና ሃይማኖታቸውን ሊቀይሩ ሃገራቸውንም ለካቶሊክ ሃይማኖት አሳልፈው ሊሰጡ ነው እየተባለ በግብፅ የሚላኩት መነኩሳት ሊቃውንና ሲሰብኩ ስለነበር መነኩሳቱና ካህናቱ እግዚአብሔር ተቀይሞታል መንግሥትዎን ነጥቆ ለሌላ ባዕድ እንደሚሰጥብዎ ብዙ ባህታውያኖች ተናግረዋል ብለው አባ ነገሴት ዘመስኮት ቀስ አጼ መንሙር የሃገሰ በሚባሉ የቤተክህነት አስተዳዳሪ ላኩላቸው አጼ ልብነድንግልም እግዚአብሔር ተቆጥቶ ግራኝን እንዳስነሳባቸው ተረድተው ከግራኝ አህመድ ፊት ለፊት ሳይዋጉ ጦር አዝማቾቻቸው ሊያዋጉ ወሰኑ በዚህን ጊዜ በአፈር ስር በሚገኘው በካን ወደሚባለው ከተማ ጸዱ በሱባ በካን ማለት የማረፊያ ክፍል ከተማ ማለት ነው የዚጋመል የጌዋ ሥራዊት ግን በቋንቋቸው በካን ማለት ፈራን እንደማራርጊና እንደሌሉኝ ደግሞ ወፈረን ማለት ነው ከዚህ በኋላ ከተማ እንዳሉ የትግሬና የአንጉት የደሮሞ አስተዳዳሪ ገገር ተክለኢየሱስ ፍስሃ ጽዮን ሰላም ሰገድ ፍቅረ ኢየሱስ አብርሃ ወራቸውን ይዘው በየበሩ እንዲሰፍሩ ተደረገ የቪሬ የሠርዌ የቡሬ ዘምቢል ህዝብ በተክለ ኢየሱስ ልጅ በሃብነ ጊዮርጊስ እንዲመራ ተደረገ የበጌምድር የጐጃም የዳሞት በንጉሳቸውና በአዝማቾቸው እንዲሰለፉ ተደረገ ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ራሰ ባንዶት ከዲጋልያን ቀጥሎ ደዋሮን እንዲገዛ ታዞ ነበርና እርሱና የገንግ አንባ ጦር አዝማች ራጂብ ቀሳ ወዳሉበት ሰላዮችን ልኮ ስለግራኝ አህመድ ያላቸውን ፍርሃት ከተረዳ በኋላ እንዲህ የሚል መልእክት ላከላቸው እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ሃገሮች ውስጥ ባሉት ህዝብና ከባህር እስከ ባህር ድረስ ባለው ምድር ላይ የእስላምን አንድ ታላቅ መንግሥት እንዲሚመሰርትናእኔን ሰዚው መንግሥት መሰረት አድርጊ ልትኖል ስለዚህ አሁን ከምር ወደ እኔ የመጣና ከእኔ ጋር የተሰለፈ ነገ ከእኔ ጋር ሹመቱና እርስቱ ልጆቹን ሚስቱ ሳይነኩበት በክብር ይኖራል ቃሌን ያልተቀበለ ግን ቢረያ ሆኖ ባህር ማዶ ይሸነራል ዘሩም ይጠፋል ብሎ አዳል ሾሌና አቢሰኬና የሚባሉ የአጼ ልብነድንግል ባለሟሎች ወደእሱ እምነቱ ገብተው ነበርና ላካቸው አቢል ኬናም እራሱ እራስ በንዶትና ራጂብ ፋላ ካሉበት ሠፈር ድረስ ሄዶ በግራኝና በእናንተ መካከል ወዳጅነት እንደሚመሠረት ቃል ስለገባ ሰላዮች የሚሆኑ ሰዎች መርጣችሁ ገበ

በረከት ጨምራችሁ ላኩሉት የሚላችሁን ብታደርጉ ብዙ ክብር አለ
ብሎ ስለመከረቸው ራስ ባንያት እሺ ብለው ከራጅህ ፊላስፋ ተሰማ
ምቶ መንገድ እንደሚሄለትለትና ወደፊት በላዮች እንደሚልክለት ቃል
ገብቶ ለአቤል ኬና ብዙ ከብት ሰጥቶ መስዶ እንዲያስረክብ መልሶ
ላከው ።

እንደዚሁም ሆነ አጼ ልብነድንግል በነገ ላይ ሳሉ በሳዱንያዙ
የሚቀመጠው የመጨጋ ልጅ ንጉሥ መከተር የገስናንና የወደማውደ
ጉሳ ሰላሳ እንድ ሺህ የጦር ጭፍራ ይዞ ለመርንት ደረሰ በዚህን ጊዜ
አጼ ልብነ ድንግል ከሰቶቸው ተተለ ልጃቸው ገላውዲዮስን ንጉሥ
ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው እንዲያነግሱትና እሁን በዚሁ ተዋጊ
ባለው ከንጉሥ መከተር ጋር ሆኖ ሲላም የአማራ ሁለት ሺህ
ሠራዊት ጨምረው ግራኝን ከለበት ሃገር ሄደው እንዲወጉትና እን
ያጠፉት አዘዙ ነገር ግን ራስ ባንያት ከግራኝ ጋር ቃል ኪዳን
ርጉለት ስለነበር ከገበና ጊላ እንደዚሁም ከውደማውደጥ ህዝብ
ሰናና የሱኬ ንጉሥ ብዙ ጦር ይዞ እንደመጣና ግራኝን ለመውጋት
ሃረር እንደሚመጡ ስለተነገረው ግራኝ አህመድም ጦሩን በዚሁ
ዋር በራስ ባንያትና በራጅህ ፋላ የምንታዘዝ የንጉሡ ነጋሥት እርዳ
ነን ብለው ከመከተር ጭፍራ ጋር እንዲተላቀልና በግራኝ በኩል ትእዛ
ተዋጉ የሚል እስከሚነገራቸው ደርስ አብረው ሆነው እንዲገዙ እደሪ
በዚህ ጊዜ አቤቶ ገላውዲዮስና ንጉሥ መከተር በደዋር በፍረው
ልዩ ቦታው ዶሬ በባሬው ሄርና ማለት ነው ኋላ ግን ድል ባድ
ሁታል በዚሁ በሄርና ራስ ባንያት ከንጉሥ መከተር ጋር ተገናኝ
ውለጣዊ ምስጢሩን ነገርውና ሳይዋጋ ለግራኝ ግብለት ግራኝም በ
ብር ተቀብሎ ልዩ ማረፊያ ሰጠው መከተርም ሰልም ሴት ልጁን
እስልም ለግራኝ ሚስት ትሁንህ ብሎ ሰጠው ሠራዊቱንም አስረከበ
ግራኝ የተረከበውን የገበናና የውደማደውጥ ጉሳ ባሪያ አድርጎ ወደዘ
ድና ወደጅላ ሲልክ የኢሲፓግና የእንግሊዝ መንግሥት ከቱርክ የ
ህር ወታደሮች ዘርፎና ማርኮ ለራሱ አድርጎ ወደ የገረቶ ላከ
በዚህን ጊዜ አቤቶ ገላውዲዮስ ከእስላም ሰገድ ከነ ተከለሳያሱስ
ሆኖ የከዳውንና የግራኝ ጦር ገጠመና ብዙ ታማኞች አገሥጎች ሲ
ቀበትና እሱም ብዙ የአረብ ወታደር ከገደለ በኋላ የቀረውን ያለ
ውን ጦር ይዞ ከባሬ ወደባድቄ ገሰገሰ መጣ ከዚያም አቤቱ አጼ ልብ
ድንግል ከጉጃሙ ንጉሥ ቀከለሃዋርያት ጋር ግሺ (መንዝ) ና
የሚባለን ስለስማ እግዚአብሄር እንደተቀመጣና ግራኝን እንደለ
ባቸው ከባህታውያኖች ሰምቶ ከባድቄ ወደ አምሩ ከአምሩ ወደ ላም

ወደፎገራ ልዩ ቦታው እንፍራዝ ቃርድ ከሚባል ሃገር ሄዶ ተቀመጠ በዚህን ጊዜ ንጉሥ መከተርን ተከትለው ከሱቢና ከንሳ ጊዜን የመጡ የጊሰናና የውጣውረዱ ጉሳዎች ከሁለት ሽህ በላይ የሚሆኑ አቤቶ ገላውዴዎስን ተከትለው ስለሄዱ የገበናን ጉሳዎች በዚያው ጭዝራ ቤተ ባስ ቦታ ላይ አሰፈሯቸው እነሱም እስከዛሬ ድረስ በዚያው አሉ የራሳቸው የሆነ ቋንቋ አላቸው ውይጣይውጦችን ንጉሳቸው ስለከዳ እናንቶ ወደፊትም ታማኝ አይደላችሁም ለሃገራችሁ ጠንቅ ናችሁ ሲሉ በባህር ድንበር በጣና እንዲቀመጡ ፈቶዱላቸው ስማቸውም ውይጣ ውይጥ መባላቸው ቀርቶ ወይጦ ተባሉ ወይጦ የተባሉበት መሬት እንዳያርሱ ከብትም እንዳያረቡ ስለተከለከሉ እስላምም ክርስቲያንም ሳይሆኑ ከሁሉ እርቀው ያገኙትን ሁሉ አያውጉም አሞራውንም ሁሉ በስማበሉ ነው ውሺጦ ምጭ ማለት ነው ንጉሥ መከተር ግን በግራኝ አህመድ ክብር አግኝቶ የወሊጋንና የከፋን ግዛት ተጨምሮለት በዚያው በከፋ ሞና ቤተመንግሥቱን አሰራ አብረውት የሄዱት ሁሉ ውይጣውጥ መባላቸው ቀርቶ ሞታ ተባሉ እንዚህ በአሶሳ በርገራ በከፋ የሚገኙት ውይጣውይጥ ወይጠዋታ በሰማሊ ማይቲ የሚባሉት ዘራቸው ቋንቋቸው አንድ ነው ከውይጣውይጥ የሄዱ ነገዶች ናቸው።

አጼ ልብነድንግል ቦካን በሚገኘው ቤተ መንግሥታቸው ልዩ ቦታው ድል እንባ ከሚባለው ስፈር ሲቀውጣጁ ሳሉ ልጃቸው አቤቶ ገላውዲዎስ ድል ሆኖ መሸሹን የገበን ንጉሥ መከተር መዘጋ እስከ ሥራዊቱ ለግራኝ መግባቱን ሌሎች ብዙ የጦር አዝማቾች በዝሬ በዛሬው ሄርና/ሃረርጌ ውስጥ ነው የሚገኘው) ጦርነት መሞታቸውን ሰምተው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ግራኝን እንደአስነሳባቸውና በየቀኑ ድሉ በግራኝ መሆኑን ስለአመኑ የሊመኗቸውም መሳፍንትና መኳንንት ወደ ግራኝ መግባታቸውንና ወሬም እንደሚያቀብሉት ስለተረዱ የንበሩበቅን ቤተ ድል ከባ አሉት ከዚያም አብረዋቸው ያሉትን ንግሥታቱና እርእስ መኳንንት ይዘው ወደ አማራ ሳይንት ለመሄድ ተነሱ በዚህን ጊዜ የዳሞት ንጉሥ ወሰን ሰገድ ገበርጌ በዛሬው ጂሩ ዚጋ ሙሉ ሆኖ ግራኝን ለማጥፋት ይዘጋጅ ነበርና ለመግባር ወደ አጼ ልብነድንግል ሄደ ነገር ግን አጼ ልብነድንግል ከቀን ወደ ቀን የግራኝ ኃይል እየበረታ ስለሄደ ከሸዋ ወደ አማራ ሳይንትና ከዚያም ወደ ትግሬ ሃገር ለመሄድ ተነስተው ደረሰ። በዚሁ ድል ባድ ባሉበት ሃገር ላይ ሁለት ቀን ሙሉ ከተማከሩና ሹም ሽር አድርገው ከእቴጌ ሳሌጂሬ የሚወለደውን የመጀመሪያው ልጃቸውን አቤቶ ፋትጦርን የባሌንና የደዋሮን ግዛት ሰጥተው ከንጉሥ ወሰን ሰገድ ጋር ሆኖ እንዲዘምት

አዘዙአት ወሰን በገደም ለአህጉሮቻችና ለእያ ሠራዊት እንዲህ ሲል ተናገረ የአረብ ሞኖሬ ባህር ተሻገር ከመንግሥቶቻችሁና ከዙፋኖቻችሁ ጋር ሆነው እንደሚት ድል ሊያደረጋችሁና ሃገራችሁን ደምርን ባሕን ፈጣ ዝርን ለመውረስ ህዝባችሁን ሚስቶቻችሁን ልጆቻችሁን ባሪያ አድርገው ሊወስዱባችሁ ቻሉ ያሄውም እናንተ በሠራችሁት ግፍና በደል ነው ከእናንተ በፊት አባቶቻችሁና አያቶቻችሁ በጀግንነት ተዋግተው ድል አድርገው ሃገራቸውን አስከብረው ተከብረው ኖሩ ተዋል እናንተ ግን አሁን በርትታችሁ ባትዋጉ ከካርፋታችሁ የተነሳ ትዋጋላችሁ ብትማረ ኩም ባሪያ ሆናችሁ ባህር ማዶ እንደሄታ ትለወጣላችሁ ያለክብር በራ ችሁ ይጠፋል ።

በወርደት ከመጣት ከመሸቀ በኪዳርና በጀግንነት ተዋግቶ መሞት ለልጆቻችሁ ነጻነት ሰጥቶና አሳይቶ ማለፍ ይበልጣል ይህን የሚያደ ርግ ሁሉ የሃገር ክብር የወገን መመኪያ ይባላል ስለዚህ እስከአሁን በተደረገው ጦርነት ላይ ከተማረኩትና ወደ ግራኝ ከገቡት ይልቅ በጀ ግንነት ተዋግተው የሞቱት ይበልጣሉና ተነሱ አሁን የግራኝ ጦር ወዳለበት እንሂድ አለ አጼ ልብነድንግልን ተሰናብቶ ወደነበረበት ከአ ቡነ ፈቅሞርና ኪታብሳቅ ጦር መሪዎች ጋር ሄደ ። አቡነ ፈቅሞርና ንጉሥ ወሰን ሰገድ በገበርጉ በፍሬው ቤጋመል ጅሩ ውስጥ በግራኝ አህመድ የበደሬን ቤተመንግሥትና በአጼ ዘርአያዕቆብ ጊዜ የታደሠ ችውን አድአ ጽዮን የምትባል ቤተክርስቲያን ነበረችና የእልማያ ነገ ዶች የመንድያ ዘርች በጣም ያመልኩዋትና ጠርቅ ሰለት ይገባላት ስለ ነበር መንበሩ በወርቅ የተሠራ የነበረውን ለሳውንም ሃብት አውጥቶ ከጨረሰ በኋላ አቃጠለው በእልል ማእርዘር የሚመራው የግራኝ ጦር የዝ ቋሳን ገዳምና ቤተ ክርስቲያን አቃጠለው ጽላቱና ንዋየ ቅድሳቱን ግን መነኮሳቱ አስቀድመው አሸሽተውት ስለ ነበር ሳይቃጠልና ሳይወሰድ ቀረ በዚህን ጊዜ ልእል ግርማ የሚባለውን ጦር አዝማች ንጉሥ ወሰን ሰገድ ፈጣገር ውስጥ የሚገኘውን ላሊበላ በደብብ ያለውን የገር ቀዳሚን ዋንዜን ዋንዜባር አስገብር ሲመለስ ያሰራውን ሳማስ ንበት የሚባለውን ቤተክርስቲያን ግራኝ እንዳያቃጥለውና የቅመወግ ሃመልት እንዳያፈርሰው ልኮት ነበር ነገር ግን በይፋት ያሉ ሃገሮች ለግራኝ ገብተው ነበርና ልእል ግርማን አታለው ገድለውትና ቤተክር ቲያኑ አጠገብ የሚገኘውን እረጅም የድንጋይ ሃመልት አፈረሱት እር ሱንም ዘርፈው ለግራኝ ላሰኩት ።

ግራኝ አህመድ በማሀሬን በአረብ የባህር ጦርና በሊግ ጉማ ታጅቦ እያጥፋሁ እንደጥፋሁ በከብር ገባ ያንም በታ ባህታዊዎችና

ቅንጢት ተናጋሪዎች ትልቅ ከተማ እንደሚመሰረትበትና ትልቅ ንጉሥ እንደሚወጣበት ከሆነር አዛውንቶች ግራኝ ሰምቶ ነበርና በዚያውታላቅ መስጊድ አሰርቶ ሲነግስ ሲል የእሱ ፋትራዎችና ሼሆች ነቢዩ መሃመድ መልእክተኞቹንና እጉቱን ጃፈር ወደላከበትና ንጉሥ ነጋሥት አርማህ ተቀብሎ ያነጋገረበትንና የተቀመጠበትን ቦታ ከሆነበ ከዚያ ላይ በኢትዮጵያ ሃገሮች የአበሻ እስላም መንግሥት መሰራች ተብለህ ትነግሳለህ እንጅ እንዚህ የክርስቲያኖች አዋቂዎች በተናገሩት ቦታ አትነግሥም በወርቅ ስለሉት የተለበጠውን ጌጣ ጌጥ እቃ የወርቅ ወንበርና መቋሚያ የወርቅ መስቀል እንደዚሁ በጉልላት የነበረውን ወርቅ ሁሉ አስብስቦ ከወሰደ ከዚያም በልዩ ልዩ ቀለም የተሳለውን የአእዋፍና የእንስሳ የንጉሥታትም ስዕል ካዘ በኋላ እንዲታጠል አዘዘ በሥራው በጣም ተገርሞበት እንደለቀሰበት በእሱ ታሪክ ፀሃፊዎች ተጽፎ ይገኛል ።

ሆኖም ግን ግራኝ አህመድ ቁጡና መንኩል ለመግደል ቤተክርስቲያንና መስጊዶችን ለማቃጠል ሃወልቶችን ለማፍረስና ለመደምሰስ ከምርኮቱ ይልቅ ለዚህ ጉዳይ በጣም ይደክምበት ነበር ጦር ወደአለበት ከመሄድ የታወቀው ሀገሩን ለማፈራረስ ይቸኩል ነበር ። በምርኮት የተማረኩትን ታላላቅ ባለሥልጣኖች ወደሥራቸው መልሶ ከወገኖቻቸው ጋር ያቀጋቸው ነበር ይሄውም የሰውን ሰንድ ዋጋ ሲቀጋ ሞቷል ።

በዚህን ጊዜ አጼ ልብነድንግል የእንዶጥናህና የወረባ የባድቁ ቤተ መንግሥትና ቤተክርስቲያኖችን መቃጠል ሲሰሙ አገሩነው ተከዘው አቤቶ ያዕቆብ የሚባሉትን ልጃቸውን ዝሆር ለሚባሉት የጭዋ ጦር አደራ ብለው ልብስ መንግሥት አልብሰው ወደአማራ ሳይንት ተሰደዱ ያንንም ቦታ መንገዝ ውስጥ ድልክዳ ብለው የሰየሙት ነው ።

ግራኝ አህመድ የጻዋቅ ንጉሥ ወሰን ሰንድ ከታወቁት ከበሊያና ከቁዋራ ጦር አገግኞች ጋር ሆኖ መምጣቱንና ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ተነጋግርና ተሰናብቶ ግራኝ ከአለበት ድረስ ሄዶ እንደሚገጥመውና እንደሚገድለው ከሰላዮቹ በሰሰማ ጦሩን በየአሊቃው ከፋፍሎ ቅንጅ ጦር በየአለበት እየሄዱ እንዲዋጋ የአበሻው ንጉሥ ነገሥት ካለበት ሃገር ድረስ እየሄዱ ሳይደራጁ ጦሩ እንዲወጉት በየጊዜው የንጉሡ ነገሥቱን የሱብና ምክር የሚያመጣ ሰላይ ብዙ ገንዘብና ሹመት እንደሚሰጠው ተናግሮ በአርባ አንድ መድብ ዓላቸው በዚህን ጊዜ ሰወሰን ሰንድ ሃሰተኛ ወሬ ግራኝ የላከው ግራኝ አህመድ የባሌን ጦርን ተከለሃይማኖት የሚባለውን ገገር ድል አድርጐ ሚስቱንም እኅቱን ግንም እንደማይደርስበት አውቆ በቤተ መንግሥት ተቀምጦ ሹም

ጄር ያደርጋል የሚል ወሬ ሲሰማና ከገበርጌ ወደባሌ ከሌሎ ልዩ ጦረ
ኞቹ ጋር ሆኖ ግራኝን ለመውጋት ሄደ ከዚያም ታግሳ ከሚባለው ትግ
ደረሰና ቢጠይቅ የባሌ ገራድ ተከለሃይማኖት ለግራኝ አምና እንደገባ
ሚስቱንም በጣም የተዋበች ቆንጆ ስለነበረች ለራሱ ሚስት እያረጋት
እቢን ያዞ ወደግንቡ ተመልሷል የሚባል ወሬ እንደሰማ ከሌላ ሰው
ደግሞ ንጉሡ ነጋሦቱ ወደአለበትና የጉጃም ንጉሥ" ወሰን ሰገድ መጣ
ስላሉት ወደወረባ ሄዱዋል በዚህ በባሌ ያሉት ሁሉ እሱ የሾማቸው
ገራዶች እንጂ እጴው ያስቀመጣቸው አይደሉ ማግኘች በጦርነት ሲሞቱ
ማግኘች ወደአደገ ሱልጣን ባሪያ ሆነው ተልከዋል ካሚል የሚባለው
የደጋሌ ልጅ ልጁን መንሰሀን አጋብቶ የባሌ ገራድ አስኝቶ አስቀም
ጦት ነበር ነገር ግን የእንተን መምጣት ሲሰማ ሌት ከነሠራዊቱ ወደ
ደዋሮ ሄዷዋል የሚባል ወሬ ከእውነተኛ ሰው ሰማና ወደደዋሮ ከግራኝ
ጋር በዝሪ በእዳግ ሽንብራኩሬ ጦርነት የዘመትን የንጉሡ ነጋሦቱ እረ
ዳቶች ነን ብለው ነገሩት ወሰንሰገድም እውነት መስሉት ወታደሩን
በየባለንሩ ቤት አርፎ እንዲሰነብት አዘዘው ምንትም ሃገር ሃኔ ይባል የነበረ
ውን እቦምሳ አሉት የጭዋ ጦሮች በዚሁ በእበምሳ ሳሉ የግራኝ ሰላዮች
ወሰን ሰገድ በሃኔ በደዋሮ ውስጥ እንዳለና መጥቶ እንዲገለው ላኩበት
ግራኝ አህመድ ከወረባ ያለውንና የተበታተነውን ጦር ማሰራን ደዋሮ
ድረስ በቶሎ ደርሰን ወሰን ሰገድን ጦርነት ገጥመን ድል እንድናደ
ርግ ብሎ ላከላቸው ወሰን ሰገድም በዚህን ጊዜ ከትንሹ ጦሮች ጋር
ባህታዊዎች ከሚኖሩበት አላማሌ ሃሰቦት ላላማሌ ወደሚባለው ተራራ
ሄደ በዚያም አባ በና የሚባሉ የዘጉ ባህታዊ ነበሩና እሳቸው ስለጦ
ርነቱ ምን ቀን ግራኝ ገጥሞ ድል እንደሚያደርግ ለመጠየቅ ነበር
የሄደ አባ በናም ግራኝ ድል እንደሚያደርግና እጴ ልብነድንግል በስ
ደት እንደሚሞቱ በውጭ ሰው እየተረዳ ድል ያደረገውን በውጭ ክፉ
ሆር ማደ በመጣ ወታደር እንደሚገደልና የክርስቲያን መንግሥት
እንደተና እንደሚመሰረት ነገሩት በዚህን ጊዜ እግሩን የተመታ የቆ
ሰለ ሰው የንጉሡ ነጋሦቱ ባለሟል የነበረ ነው ብለው አባ በና እንደ
የዘጋ ባህታውያን ለወሰን ሰገድ ስለአስተዋወቁት ወሰን ሰገድም የቆ
የተባለው ፋኑኤል መሆኑን ስለአወቀው ወዲያውኑ ተሳስመው ደህ
ንታቸውን ይጠያየቁ ጀመር ሁሉቱም ለአንድ ቀን ሲጫወቱ ከቆየ
በኋላ ወሰን ሰገድ ልጁን እንደአባቱ ዳዊት ብሎ የሰየመውን አደራ
ሰጥቶ ወደ ሃኔ ሲመለስ ብዙ የጭዋ ጦርና ታላላቆች የበሌያና የቆ
ዋራ የእንዝው ምድር ጦር አገማኛች መጥታቸውና መማረካቸውን
እጴው አደራ ብለው የሰጡ አቤቶ ፊቅጦር መሞቱን ሲሰማ ከእለቱ
ፈዞ ቆየ ከዚያም ብቻውን ከትንሽ ጦር ጋር ድል እንደሚያደርግ አመነ

አጼ ልብነድንግል ወደ ተሰደዱበት ሃገር ለመሄድ ተዘጋጁ ያንን ሃገር ጋፋምቦ አሉት ይኸውም ያን መጀመሪያ የነገሠ ንጉሥ ራዳቶች ነን ያሉት የጋላ ነገዶች ስለነበሩ ጋላ እየጋበዙበትበት ነገር ቆፍሮ ቆየኝ ማለት ነው በራሳቸው ቋንቋ ደግሞ ቆቱ አሉ ይኸም ትርጉሜው ቆፋሪ ማለት ነው በዚህን ጊዜ አሙራይ አትማን ፈትመርጎ የገደለው ወሰን ሰገድን ለመግደል ያከታተል ጀመር ንጉሥ ወሰን ሰገድ የማራኝ ጦር እንደተከተለው አውቆ ለጭጥ ጦር የሚያበረታታ ቃል ከተናገረና ከሙ ከራቸው በኋላ አዋሽ ወንዝ አጠገብ የወርቅ አሉጋውን አዘርግቶ በዚ ያለድ ተቀምጦ ነጋሪት እያስመታ መለከት እያስነፋ ቆየ ከዚያም የማ ራኝ አዝመድ ጥና ጥና የጦር መሪዎች እራሱ በአረብ ወታደር ታጅቦ ያረበር ብዙ ጊዜ ድል ካደረጋቸውና ከመለሳቸው በኋላ የአፎም ጉጓዎች የሰሌ ነገዶች የአልሚያ ጭፍሮች ከኢሳዎች ጋር ተቀላቅለው ተጥምት ላለ ማራኝን በሚያምኑት በኩል ከአሰራ ሰድሰት ሺህ በላይ የሚሆን ጭፍራ ቀቀ ማለት ነው ያንንም ቀቀ ሐራ አሉት በጣልያ ይህ ሁሉ ሲሆን ማራኝና የማራኝ ጭና ጦር አዋጊች የወሰን ሰገድ ሥራዊት እስከሚደክም ዝም ብለው ሁሉት ቀን ከቆዩ በኋላ የሁለቱ ጦርት ቀጣቀልና የማራኝ ያል ደከመ ጦር ድል አድርጎ ታላቁ ጀግና የሰዎችን ንጉሥ ወሰን ሰገ ድን ገደሉት አብረውት በዚሁ በመተግራ የሞቱት አባ እንድርያስ ማህቆዝን የሆዱት በብዙ ጦርነት ጀግንነትን የሰሩ የንጉሥ ጀንደ ረባ ተብለው የሚኖሩ የዘጠና ሰምንት አድግኤ ሰው ነበሩ እዝያው እንደሉ በደቀርና በባሌ ለማራኝ የሚያገለግለው ሰላይ እየያዘ ሊሰቅል የነበረና ጀግንነቱን ግራኝ ሲያመሰግነው የነበረ የአንሙ ምድር አዝማች የነበረ የወሰን ሰገድ ወንድም ገራም በዚሁ ጦርነት ሞቱ ከርሰ ቲያኖች አንድ ሺ አንድ መቶ ነበሩ በዚሁ በመተግራ ጦርነት ፊደም የተማረከ አልነበረም በግራኝ በኩል ከአረብ አገር ለእርዳታና ባሪያ አድርገው ህዝቡን ለመውሰድ የመጡት ማዘራን የባህር ወታደሮች ከአንድ ሺህ አራት መቶ በላይ ሞቱ በዚሁ በመተግራ ጦርነት ድል ካደረጉት ለአረብ ወታደሮች የባሪያዎች አደሌ ሃገር በሸንብራ ኩሬ ጦርነት ድል ካደረጉት ጋር እርስት አድርጎ ሰጣቸው ጥና ጦር መሪዎችሁን ሸምሱን ንጉሡ ነጋሥቱ የነበሩትን ከተማ አገ ሮውን ያዳትን እርስትህ ነው ብሎ ሰጠው እሱም ሸምሱ ያዳት ደረሰ ሄደ የሃገሩን ህዝብ አሰለቦ ሸዋ ገር አድርጎ በዚህ አጼ እስክን ድር በወርቅና በብር ያስጌጧት የማርያም ቤተክርስቲያን ነዘረችና ወርቅና ብሩን ልዩ ልዩ የሆነ የአልማዝ የሉል ድንጋዩን ከማምጃቢቱ ነጠቁና ከወሰደ በኋላ አቃጠሏት በዚያ የሚገኙትን የቄሶችና ቄሶችን ልጆች ወጭላል ከራቱ እያስመጣ አረዳቸው ያንም ሃገር በረኸት ይባላል ከዚ

ያም ከግራኝ ጋር በደብረብርሃን ተገናኝተው የሰጠው ሃገር ሁሉ ድል አድርጐ ህዝቡን እንዳሰለመው ነገረው ከቤተ ክርስቲያን ያገኘውን ወርቅና የሐር ድንጋይ ሰጠው ግራኝም ያገኘውን ሁሉ ወደዘቢድ ስለሚልከው ነው ።

እንደዚሁም ሆነ አጼ ልብነድንግል ባለቤታቸውን እቴጌ ሰብለ ወንጌልን ልጃቸውን አቤቶ ሚናስን እህታቸውን አመተ ውዋንንና ሌሎቻቸውም አራት ሴቶች ልጆቻቸውን ይዘው ከአማራ ሣይንት ልዩ ቦታ ተድባበ ማርያም ከሚባለው ተነስተው በሚያዝያ ወር ወደ ጕጃም ሄዱ ልዩ ሃገሩ ሃራራ ይባላል በዚያም በሃራራ ውስጥ በሚገኘው ቤተ መንግሥታቸው ያንም ቤቱ መንግሥት አጼ በእደማርያም አሰርተው ጭዋ ጦር የደለደሉበት ነው ልዩ ቦታው ቀጂ ይባል ነበር ከዚያም አንድ ከረምት አሳለፉ በዚያው ሳሉ የታላቁ ጀግና ንጉሥ ወሰንሰገድ ልጃቸው አቤቶ ፋቅጦር ሌሎችም የጦር አዝማቾች መሞታቸውን ሰሙ እንደዚሁም ታላቁ ገዳም ደብረ ሊባኖስና ሌሎችም ታላላቅ ቤተ ክርስቲያኖች መቃጠላቸውን ሰሙ በዚህን ጊዜ እፀል እልበላም ብለው ለሰባት ቀን በሃዘን በፀሎት ቆዩ ነሃሴ 5 ቀን በ፲፭ አምስት መቶ ሃያ ሶስት /1523/ አመት በላይ የመንዝራ ጦርነት ተፈጸመ አዋሽ /ሸዋ/ ግራኝ አህመድ የክርስትያንን መንግሥት አጥፍቶ የእስላምን መንግሥት ለመመስረት በሚዘጋጅበት ጊዜ የጁማ ወንዝና ግራርጌ በሚባለው ሃገር የሚኖሩትን አማራዎች አፍልሶ ወደዘቢድና ወደ ባግዳድ ባሪያ አድርጐ ሰደዳቸው በቦታው በነሱ ምትክ አርሆ ጀሌ የሚባሉትን የሰል ጕሳዎች አስፈረበት ያንም ሃገር ግራርጌ መባሉ ቀርቶ በስማቸው ሰላሌ ተባለ እሊታቸውም ቱሉማ ውስጥ አባ ይባላል ።

እንደዚሁም ሆነ ግራኝ አህመድ በጅማ ወንዝ ሰወንዝ የሚኖሩትን የአማራ ጕሳዎች እንደዚሁም ተክለሃይማኖት ያቀኑትን የግራርጌን ህዝብ ከሃያ ሺህ በላይ ወደአረቢያ ሲልክ በዚህን ጊዜ የእስፓኝ መንግሥት በባህር ሃይሉ ወታደር ተዋግቶ ድል ከአደረገ በኋላ ምርኮኞቹንና ባሪያዎቹን ከሃገሩ ለሰድስት ወር አቆይቶ በታላላቅ መርከብ አሳፍሮ ወደ አሜሪካ ላካቸው ስማቸው ከጅማ ሰለኸዱ ጀማካ ተባለ በኬኒያና በወማና በባሌ የሚኖሩትን የማያና የመንድያ የአርሞያ ጕሳዎችን ግራኝ አህመድ በቤተ ሃማራ በባሌው አማራ ሳይንት አምጥቶ አስፈራቸው ባልርስት አደረጋቸው ስማቸው ከቦረና ነገድ ተከፍለው ስለመጡ እስከዛሬ ያሉበት ሃገር ቦረና ይባላል ። ግራኝ አህመድ ያልመነውንና የተገዛለትን ከአንድ ቦታ ወደአንድ ቦታ ካዛወረ በኋላ ያላመነውንና ያልገበረለትን መግደል

ቅና መኳንንት እየገደለ የሚቸቸውን ሚስቶችና ልጆች ባሪያ እያደ
ረገ ባህር ማዶ ያሻግር ጀመር ስለዚህ የጥቁሮች ባርነት በሰፊው
የታወቀው በግራኝ ወረራ ዘመን ነው የባሪያ ዘረፋና ንግድ ለአለም
በአረቦች በኩል የላከ ይኸው ግራኝ አህመድ ኢብራሂም ነው ከእሱ
በፊት ግን በጦርነት ድል ሆኖ የተማረከ የአረብ ነጭ ህዝብ
እንጂ ጥቁር ህዝብ ባሪያ ተብሎ ፈጽሞ አይታወቅም ነበር ።
በዚሁ ዘመን አጼ ልብነድንግል እንደሙሴ በደብረ ሲና እንደ
ኢየሱስ በገዳሙ ቆረንቶስ አርባ ጾምን እንደጾሙት ከሃራሬ
በረንታ ወደቤተ ሃማራ— አማራ ሳይንት አርባ ጾምን በመ
ሲል ተራራ ሆነው ሲመጸም መጥተው በደብረ ሳሉ ከሰላ
ጥቂት የጭቃ ጦር ብቻ እንዳላቸው ሰምቶ ሊማርካቸው ሲል
በሰላም ጦሮች ዘንድ ታላቅ አሙሉ ነፍስ ተነስቶ በታተነላቸውና
ከጥቂት ጋሻ የአርባ ጾምን ሱባኤ አቋርጠው ባለቤታቸው ሰብለ
ወንጌል ወደአሉበት የገር ዲማ ሸሽተው ሄዱ በዚህን ጊዜ ቤተ
ማርያም በሚባለው በወሲል ተራራ ስር ሆነው አጼ ልብነ ድንግ
ልን ሲጠብቁ የነበሩ መሣፍንትና መኳንንት ልጆቻቸው አቤቶ
ሚናስና ልእልት አቅሊሲያኖርማንወርቅ ሲሉችሣ ሴቶች በድንገት
በድንኳን ውስጥ እንዳሉ ተማረኩና ወደዘቢድ ከተማ ባሪያ ሆነው
ተላኩ ታላቂቱ ልጅ አምራዕዮን ግን ተጥግታ ሞተች ግራኝ አህ
መድ የአጼ ልብነድንግል ማምለጥ በሰማ ጊዜ የማህራን ጦር በአ
ውራይ አስሚንና በስበር ኢድዲን በሌሎችም የሚመራውን የእስ
ላም ጦር ሰበሰበና በአፍንጃን በአዶል ለሰላ የሚላኩትን የክርስ
ቲያኖችን ሰላዮች አስቀድሞ ልኮ ወናግ ሰገድ አሁን እኛን ሊመ
ዋጋት ቀርቶ አብሮት የሚሄድና የሚሰደድ ሰላለው ተከታትላችሁ
እንድትይዙት ብሎ ከነገራቸው በኋላ እራሱ ምርጥ የሆኑትን የአ
ረብ ወታደሮች ይዞ ሃራራ ነው ያለ የሚባለን ስለሰማ ወደሃራራ
ሄዶ ሲያጣው በሸበልና በበረንታ እንማይ የሚገኙትን ቤተ ክርስ
ቲያኖችንና ታላላቅ መንደሮችን እንዲቃጠሉ አዘዘ በዚህን ጊዜ መር
ጦራርያምን ለማቃጠል ሞከረው እሳቱ እየጠፋ እንቢ አላቸው
ብሎ የአረብ ወታደሮች ባልታወቀ ሁኔታ ታመው አለቁ በዚህን
ጊዜ ክርስቲያኖች እንዲያቃጥሏት አዘዘና በክርስቲያኖች እጅ ተቃ
ጠለች ይባላል ። ከዚያ አጼ ልብነ ድንግል መምጣቱን ሰምተው
ባለቤታቸውን ሰብለ ወንጌልን ከጥቂት ሰዎች ጋር ይዘው ወደዳሞት
ተሰደዱ ልጃቸው አቤቶ ገላውዴዎስ የወልቃይትንና የደንቢያ የወ
ገራንና የበለሳን የጭቃ ጦር ሰብስቦ አባቱን ሊመርዳት ከእሰራ አም
ስት ሺህ በላይ የሚሆን ጦር ይዞ ዳሞት ደረሰና ብዙ የሱማሌና

የአረብ ወታደሮች ገደል ከእስላሞች የሞቱት በዓምት ጦርነት አንድ ሺህ ሁለት መቶ ነበሩ ግራኝ አህመድ ኢብራሂም አዲስ ጦር መመጣቱን ሰምቶ ብዙ ወበጎንጅ መጽሃፍ መሣሪያና ከአረብ ሃገር የታላከለትን ሁሉ መማረኩን ሰለሰማ ከሠሜ ሌላ አርዲታ እስከሚመጣለት ወደአማራ ሳይገባ ተመልሶ መካን ሥላሴና ደብረ ነጐድጓድ የሚባሉትን ቤተ ክርስቲያን በወርቅ ተለብጠ የተሰራውን መንበርና የወርቅ ታቦታት ከወሰደ በኋላ አቃጠላቸው ወርቁንም ወደ መካ ላከው አጼ ልብነድንግል ከልጃቸው ከገላውዲዎስ ጋር ወደ ደንበያ ሄዱና አንድ ከረምት አሳለፉ የቀዋረና የደንቢያ አገሮች ያስገቁ ወ ሰን ሰገደ በዚሁ ቦታ በክብር አስተናገዱዋቸው ግራኝ አህመድ ከኢሳና ከሱማሌ ጉማ እንደገና ሌላ ጦር ተዘጋጅቶ እንዲመጣለት ከሃረርና ከዘይላ ከመቋደ ሽም ለሚገኙት እሱ ለሾማቸው ሱልጣኖች ላከ ሱልጣኖችም የሞስር የባግዳድ የየመን አረቦች ስለነበሩ በቶሎ ብዙ ሺህ የሚሆን ጦር ላኩለት ነገር ግን አጼ ልብነ ድንግል ዳሞትን ለቀው ከልጃቸው ጋር ወደደንቢያ መሄዳቸውን ሲሰማ ዳሞትንና ጐጃምን ለማስገበር ሄዶ በዚያን ጊዜ በአራት መከራከር አድርጐ ህዝቡን ገደለችው እኔ ነኝ እያለ እያስመነ በአንዳድ ጥሩ ቦታ ሲያይ በዚህ መስጊድ እንዲሰራ እያለ ትልቅ ድንጋይ እየተከለ ጕደሬ የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን አፍርሶ ት ልቅ መስጊድ አሰራ ከዚያም እታከሌት ወደሚያበቅልበት ሃገር ሉሚ ጦይና ወርዶ ትርንጉ ሲያስተክል ስንበተ በዚያም የነበረበትን ወንዝ ስሙን ጉራይ ብሎ ጠራው ከጉራይ ዛሬ ገራይ ይባላል ገራኝ ለማት ግራኝ ማለት ነው በዚህም አካሄን አመሰገኖ ሰሌትን ኢዘርስ እንዲገ የሃገሩን ባላባት ጠርቶ ያን ወንዝ ማን ይባላል አለው ሰውየውም የጋፋት ጉማ ነበርና ሊሄታ ማለት ስለማያውቅ ለጭማ አለው ግራኝም ለጭማ ማለት በአረብኛ ሰይብ መሆኑን ስለሚያውቅ ያእላህ ብሎ ጮኸ ሰውየውም ያላሁ ሲል ሲሰማ ላይ በሉት እንጂ ለጭማ ወንዝ አቅ በሉት ብሎ ብሎ ለወገኖቹ ተናገረ ያንም ወንዝ እስከዛሬ ላህ ይባላል ግራኝ አህመድ በጉራይ ገራይ ወንዝ ድንኳኑን አስተክሎ ተቀምጦ ሳለ የደሞትና የጐጃም ህዝብ እየመጣ ገበረለት በበላያቸውም የሰሩትን ክርስቲያን ሰው እየሾመ አርስት እየሰጠ ላከቸው በዚሁ ቦታ አንድ አመት አሳለፈ ከዚያም ፈንጅ ሰበርና አሊ አመር በነበሩል የሚባሉት በላዮቹ መቶተው ወናግ ሰገድ ከልጆቸው ከገላውዲዎስ ጋር ከደንቢያ ወደበለሳ ሄደዋል የገኑሱ እጣቸ የሆነው ወናግ ሸሬ ቁሉ ለእኛ በሞጊዜው ከንጉሥ ነገሥቱ ወናግ ሰገድ የሚተዳለፈውን ትእዛዝና ምንዘር የሚገልልልን እሱ

ብቻ በድንገት በእንፍራንዝ ከተማ የእስላም ጦር ሲመጣ እንዲከላ ከሉ ተተምጣል ሉሉት ግራኝ አህመድም ወደደንገል መሄድ ትቶ የደንጉል ህዝብ በሚኖርበት በረዶ ሃገር አልፎ ሲሄድ ሶስት ሺህ የአረብ ወታደር በጉጃም ጦቂ በበረዶ ሞተበት። የአረብ ህዝብና ወታደር ለእርዳታ በሚመጣበት ጊዜ ባሪያና ወርቅ እንዘርፍለን እያለ ፍቃደኛ ነበርና ግራኝም ከታሰበው በላይ የስልጣን መብት በእጁ ስለነበርና አረቦች የጥቁርን እንድንት ስለማይፈቅዱ ቀንበ ትና ወደሄዱላን እንዲመለስ ተጠይቶ ነበር እሱ ግን እንቢ ስላለ የአ ረብያ ሃገሮች ለግራኝ አህመድ በጣምዳድና በመዲና ተሰብስበው ለእርዳታ ብለን የላክንልህን ማህራን የባዘር ወታደሮች በረዶ በሚ ፈላበት ወኃው ከመቀዝቀዙ የተነሳ ወደበረዶ በሚቀየርበት ሃገር ወስደህ በማስጨረስህ ወደፊት ፈጽሞ እርዳታ እንልክልህም ሲሉ ደብዳቤ ጻፉለት በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ የኢብራሂም ልጅ በኢ ትዮጵያ ሃገሮችና መንደሮች ከሀንድ ውቅያኖስ እስከ ግብፅ ባለው ነገድ ላይ የእስላምን መንግሥት ለመመስረት የነበረው ሀሳብ መነ መንበት ነገር ግን ተስፋ ባለመቁረጥ ከአገሩ ካለው ወርቅና የሱል ድን ጋይ ከአበሻና ከአረቦች ጥርጂ (ወርጂ) አባሎንቶችን መርጦ በግ ብርና በምርኮ ከአገሩ ካለው ወርቅና ሱል ድንጋይ አሲዞ የምቀበትን ሁኔታ አብራርቶው ለአረብ ሱልጣኖች እንዲገልጡለት ላከ ግራኝ አህመድ ከወናጥ ሰገድ ጋር መግጠሙን ቀጥቶ ከውጭ እርዳታ እስከሚመጣለት ድረስ የገበረለትን ሃገር እየዞረ ባለሟሎቹን እየ ሾመና እርስት እየሰጠ ይዕደላቸው

ነገር ግን የአረብ ህዝብ ባለሥልጣኖች እንደዚህም ሆኖ የሸንብራ ኮሬ ጦርነት በሆኑ በአፈት አጠቱ ንጉሥ ወሰን ሰገድ በመተኛራ ጦርነት በሞተ በሶሰት ቆጠቱ በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሰድ ስት ዓ/ም 1526 ዓ/ም ላይ በጊራራ ደሴቶችና በምዕዋ በሃማሴን የሚገኙት ነገዶች የትግሬ ጉጣዎች ሁሉ ያለጦርነት በእልልታ በሆታ እንቢልታ እየነፉ ክበር እየመቱ በዘፈን እከብረው ተቀበ ሉት በዚህን ጊዜ በአረቦችና በወገኖቹ ከነቢዩ መሃመድ አጉት ከጃፋር ጀምሮ የተከበረውን የአህመድ ኒጋሽን መታብር ጉብ ኝቶ መታብሩን ማማሽ ሚሲዮን ዲና በሚፈጅ ወርቅና ብር አስ ጌጦ አሠራለት ነገር ግን ፖርቱጋሎች ድል አድርገው የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ የአጼ ገላውዴዎስን መንግሥት በአፀኑ ጊዜ በአጠገቡ ያለውን መስጊድና መታብሩን የክርስቲያን ወታደር ሄዶ ሲያፈርስ የበለውና የከለው ነገዶች ተዋግተው ተሰብሶ የተሠራውን ወር

ቅና ብር ወደመካ ላኩት ነገር ግን እንደነሱ አባባል በመንገድ የባ ዘር ሞገድ ተነስቶ ሰዎችን መርከቧንም አሰመጣቸው ይባላል ።

አጼ ልብነድንግል ወደፖርቱጋል መንግሥት የላኳቸው አባ ቢጋ ዘአብ ከተላኩ ሰምንት አመት በላለፉና ከፖርቱጋል ከተማ ከሊስቦን የሚገኘው የክርስቲያን መንግሥት ለላኩት መልእክትና ገጸ በረከት መልስ ባለመመለሱ እንደገና እርዳታውን ለማግደፍ የፖርቱጋል ተወላጅ የሆነውን ዮሃንስ ጃን በርሙዴዝ ከፖርቱጋል መንግሥት ጋር ተነጋግሮ የወታደርና የጦር መሣሪያ እርዳታ ይዞ እንዲመጣ በእስጥፋኖስ ከደብረሊባኖስ ጋር ላኩት ።

ዮሃንስ—ጃን በርሙዴዝ በግብፅ አድርጐ በግልፅም በሽሽግም በመርከብ አለፈና በኢያሩሳሌም አድርጐ ወደፖርቱጋል ሄዶ ሊስቦን ሲሚገኘው ለሶስተኛው ዮሃንስ የተላከውን ደብዳቤ አስረከበ ከዚያም የአረብ እስላሞች በክርስቲያኖች ላይ የሚያደርጉትን ግፍና ጭካኔ አቢያተ ክርስቲያኖችንና የቅ/ወንጌል መጻሕፍቶችን ሲያቃጥሉና ካህናቶችም ሲገደሉ በዓይኑ ያየውንና የሰማውን ለፖርቱጋል ህዝብና ለንጉሱ ዮሃንስ አስረዳ ። ስለዚህ የፖርቱጋል ንጉሥ ከዶን ጋርሺያ ቀጥሎ ለተሾመው ለእስጢፋኖስ ደጋማ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እርዳታ እንዲላክለት ትእዛዝ አስተላለፈ በትእዛዙ መሰረት እስጢፋኖስ ደጋማ ወንድሙ ክርስቶፎርስ ደጋማ አለቃ አድርጐ አራት መቶ ፓርቱጊዞችና ሰባት መቶ የዘንድ ተወላጆች ወደምፅዋ ሊልክ ያዘጋጅ ጀመር ።

በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሃያ ዘጠኝ /1529/ ዓ.ም ላይ በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ረሃብና በሽታ ስለነበር በአጼ ልብነድንግል ሰራዊት በግራኝ አህመድ ጭፍራ የተዘቀዘ ጦርነት አላቋረጠም ነበር ።

በዚሁ ዘመን አጼ ልብነ ድንግል በንላ በሚባለው ሃገር ውስጥ እርባ ጸምን ለመቆም ሱባኤ ገብተው ሳለ ግራኝ አህመድ ይህል ነበረና በጾም ላይና ከትንሽ ጦሮች ጋር ነው ያሉት የሚባል ወሬን ሲሰማ ሲዲ መሃመድንና አቡበከር ኩቲምን ከሰባት መቶ ምርጥ ተዋጊ ጦሮች ጋር ተዋግተው ወናግ በገድን የአበሻውን ንጉሠ ነገሥት ማርከው አሸከናፍሎ ይዘውሉት እንዲመጡ አዘዘ በዚህን ጊዜ ድንገት ደርሰው ብዙ አገልጋዮቹን የጦር መሪዎችን ገደሉ ከሞቱት የኢትዮጵያ የጦሩ የክፍና የወሰጋ አገዛዥ ሚካኤል ደርሶ የአርሞ ዘር ነው አባ ቅንላኤ ዘክርስቶስ የደብረ ቢዘን አበምኔት አላሻ ተክለ ጊዮርጊስ ፍስሃ ፅዮን የምግስን ጥሩ የነበረ አገዛዥ

እምነ መሀይምናን የተገኙትን አገሮች የነበረ ራስ ድል ወጊዮርጊስ የአጼው አማካሪ የነበረ ከነሱ ጋር ከስድስት መቶ የማያንሱ የጭዋ ጦር ንጉሡ ነገሥታቸውን አናስማርክም ሲሉ በጀግንነት ሞቱ በዚህን ጊዜ አጼ ልብነድንግል ሚያዚያ በጠኝ ቀን የትንሣኤ እለት ከገበሪ ተራራ ወርደው ከትንሽ ሰዎች ጋር ወደቆላ ወርደ በጀላ በሚባለው አገር አንድ ክረምት አሳልፈው ወደ ደብረ ዳሞ ሄዱ ከዚያ መነኮሳቱ ግራኝን ፈርተው እስከዎን ሲሉ መዋቱ ገዳማችን ያፈርስብናልና እኛንም ይገድለናል ከዚህ ይሂዱልን አሏቸው አጼ ልብነድንግልም እግዚአብሔር እንደተቆጣ አስተዳደሩው እመቤታችን በራሳቸው በለመኗቸው መንግሥታቸው ከለያቸው እንደ ማያልፍ ስለነገሯቸው የዚህን አለም ትተው ደብረ ዋሊ ወደ ሚባለው ታላቅ ተራራ ሄደው በአንዲት ትንሽ ዋሻ ውስጥ ገብተው እየፀለዩ ተቀመጡ።

በዚህን ጊዜ የአጼ ልብነድንግል እኅት የግልማቺት እሌኒ ናእድ ዋንጫ ወንድም ዶሬ ቁሉ በአጼ ናእድ ዘመን መንግሥት የባህር ነጋሽነት ማዕረግ አግኝቶ በጌራራ ደሴቶች መቀመጫውን ያበሩል አድርጎ ከቱርኮች ጋር እየተዋጋ ሲኖር በዚሁ በግራኝ ጦርነት ለግራኝ ሆነው ወገኖቹ ስለገደሏት የአስራ አምስት አመት ወጣት ልጁ ይስሃቅ ዶሬ ከአጼ ልብነ ድንግል ጋር መጥቶ አብሮ ሲያገለግላቸው ነበር።

በዚሁ በደብረ ዋሊ ተራራ ላይ በሚገኘው ትንሽ ዋሻ ውስጥ መንነው በነበሩ በሰባት አመታቸው ከግራኝ ጋር ጦርነት በጀመሩ በአስራ አራት አመታቸው ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ሰው መንግሥት ወናግ ሰገድ በተባሉ በሰላሳ ሁለት ዘመን መንግሥታቸው በተወለዱ በአርባ አምስት አመታቸው በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ዓ/ም ሆኖር ሃያ አንድ ቀን እረፉ ከመሞታቸው በፊት ለእኅታቸው ልጅ ለይስሃቅ ዶሬ የባሕረ ነጋሽነቱን ማዕረግና የእናቱን ግዛት እንዳትከለከለት ብለው ተናዘው ስለነበር በዚሁ ዘመን ልጃቸውን አጼ ገላውዴዎስ መኳንንቱና መሳፍንቱ በሌላ ጉንድ ተክለ ሃይማኖት በሚባል ገዳም ውስጥ ለማንገሥ ወስዱት ቅብአ መንግሥት ሜሮን ቀብቶ የሚያነግሥ ጳጳስ ስላለ በጉንድ አበምኔት አባ ባሀለ ክርስቶስ በሚባሉ መነኩሴ እጅ ሰው መንግሥታቸውን አጽናፍ ሰገድ ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ብለው ቅብአ መንግሥት ቀብተው ሲያነግሡ የዶሬን ልጅ ይስሃቅንም በዚሁ እለት ባህር ነጋሽ ይስሃቅ ብለው ቃል አስገብተው እንዳሉት የአጼ ልብነ ድን

ግል መሞትም በአንድ ሽህ አምስት መቶ ሰላሳ ሶስት ዓ.ም ግንቦት አንድ ቀን ተገለፀና ለየመሳፍንቱ ተላከ የባህር ነጋሽ ይሬ ልጅ ይስሃቅ የአባቱን ግዛት ስለተሰጠው የትግሬ መሳፍንትና መኳንንት በአባቱ ሞት ቁጭት የነበራቸው ሁሉ ከግራኝ እየከዱ መጥተው መሪያ ችን እንተነሀ ሲሉ ለባህር ነጋሽ ይስሃቅ ገቡለት እሱም የግራኝ ጦር እየተዋጋ ምፅዋን ዳህላክን አዶሊስን ሱዋን በእራሱ ቁጥ ጥር አደረገ ቱርኮችም ከዶሴቱ የነበሩትን አስለቅቆ ወደሃገራ ቸው መለሳቸው ።

እጨ ገላውዴዎስም ከእናታቸው ከሰብለ ወንጌል ጋር ሆነው የወገራ ፊላሻ የጠለምት ህዝብ በግራኝ ግፍ የተነሳ የሚባል የፈላሻዎች መሪ ነበርና ተዋግተው ድል አድርገው ግርከው በአ ደባባይ ሰቀሉት በዚሁ ዘመን የተገደሉንና የሽሬን የሰሜንት የወ ሊቃይት ህዝብ ሰብስበው ሽም ሽር አድርገው የግራኝን ጦርና ቃል አቀባይ ሰላይ እየፈታቹ እንዲገሉ ሙሉ ስልጣን ሰጧቸውና እናታቸውን በተንቤን ትተው ወደ ደንቀዝ ሄዱ ።

በዚሁ ዘመን በተስፋ ሲጠብቁት የነበረው የፖርቱጋል መን ግሥት እርዳታ ከስድስት መቶ ሰማንያ ዘጠኝ ወታደሮች ጋር ልዩ ልዩ የሆኑ አዳዲስ ጠበንጃ ብዙ የጦር መሳሪያ ጋር ይዞ መጣላቸው።

ከዚያም ባህር ነጋሺ ይስሃቅ የቱርኮችን ሹም አር ሊዱን አብ ዱላህን ገድሎ ምፅዋን ይቆጣጠር ነበርና የፖርቱጋልን ወታደሮች በክብር ተቀብሎ ካስተናገዶ በኋላ እቴጌ ሰብለ ወንጌል ወደሚገኙ በት ደብረ ዳሞ ስር እየመራ ይዟቸው ደረሰ ።

እቴጌ ሰብለ ወንጌልም በደስታና በክብር የፖርቱጋልን ወታደር ተቀብለው ሲያስተናግዷቸው ሰነበቱ ። ከዚህ በኋላ ፖርቱጋሎችና አብረው ያሉ ለጦርነት የመጡት የሀገር ተወላጆች ለጦርነት ግራኝን ለመውጋት ይዘጋጁ ጀመር ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ ዞብል ላይ የፖርቱጋል ወታደር መምጣቱን ሲሰማ የእሳማውን ጭፍራ በቶሎ አጠራቅሞ ሳይደራጁ ለመውጋት አካለ ጉዛይ እናላ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ሸምቆ ቆያ ቸውና ጦርነት ገጠሟቸው ከቱርክ ከሚላክለት መሣሪያ የበለጠ ስለሆነ ምንም ሊበገሩለት ስላልቻለ ከዚያ ከምባሴን አካለ ጉዛይ ሸሽቶ ወደዞብል ሄደ ።

ከዚያም የአረብ እርዳታ ጉዳዩም ውስጥ በረዶ በሚፈጻበት በሙሉ ቀሙ ሶስት ሺህ በላይ የሚሆን ማህሬን ወታደር በመምታቸው የተጉላ ቀከሏከሎ እንረዳህም ተብሎ ነበርና እንደገና ሃያ አንድ የሚሆን ከማብዕ ከመካ ከየመን ከቱርክ የሚወለዱትን መርጦ ለየመን ሱል ጣን መማሪያና ወታደር ላከልኝ ብሎ ላካቸው እነሱም ሄደው ለጀ ሃድ አሊታና ለየመኑ ሱልጣን ሁኔታውን ገልፀው እንደገና መካ ለሚገኙት አሚሮችና ሱልጣኖች ለመናገር ሄዱ በዚህን ጊዜ መዲና ውስጥ ስብሰባ አድርገው የየመን ሱልጣን መማሪያና ወታደር ላክ ልኝ ብሎ ላካቸው እነሱም ሄደው ለጀሃድ አሊታና ለየመኑ ሱልጣን ሁኔታውን ገልጸው እንደገና መካ ለሚገኙት አሚሮችና ሱልጣኖች ለመናገር ሄዱ በዚህን ጊዜ መዲና ውስጥ ስብሰባ አድርገው የየመን ሱልጣን እንዲልክ ወታደር አዘዙት የየመኑ ሱልጣን አብ ዱራሁማን ሰሙን ነበርና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ቀርከችና ፍታደኛ የሆኑ የምርኩ ባርያና ወርቅ እናመጣለን ብለው ዘጠኝ መቶ አምሳ ተዘጋጅረው ግራኝ ወደአለበት ዞብል መጥተው ተገናኙ ።

በዚህን ጊዜ በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ አራት ዓ/ም በክረምት ወራት ፓርቱጊዞች በኢትዮጵያ ጦር መሪዎች እየተመሩ በአባለ ጉዳይ ወደእጅጉኔ እንደመጡ ግራኝ አህመድ አዲስ ከመጡ ከአረብ ወታደሮች ጋር ጦርነት ገጠማቸው እነዚህ አዲስ የመጡ አረቦች በሚገባ ተዋጊዎቹ በሁለቱ በኩል የበረታ ውጊያና ጥሩ ጀግንነት ያሳዩ ነበር በዚሁ በተፋፋመው ጦርነት ውስጥ ክርስቶ ፎር ደጋማ ወታደሩን እየመራ ከፊት ለፊት ቀድሞ ይዋጋ ነበርና በአረብ ወታደር ጥይት ተመትቶ ወደቀ በዚህን ጊዜ ቁስለኛውን ክርስቶፎርን ወታደሮች ይዘው ወደኋላ ሸሹና በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ ቁስለኛውን አስተኝተው ሲያክሙት የቱርክ ቤት ለግራኝ ምዕዋ ውስጥ ሰላይ ሆና ስታገለግል የነበረች ለክርስቶፎል ወዳጁ ሆና አብራ መኖሯ ነበር አሁን መቁሰሉን ስታይ ለግ ራኝ አህመድ ያለበትን ቤት ወስዳ አሳየች ግራኝ አህመድም ቁስ ለኛውን የተለያየ አስቀያሚ ግብር ፈጸመበት እንደዚሁም የግራኝ አጎት የአባቱ ወንድም ሱልጣን መሃመድ በዚሁ ጦርነት ቆስሎ ነበርና አክምልን አንተም ለእኛ ሁንና ወገኖችህን ወደዚህ እንዲ መጡና ከእኛ ጋር እንዲሆኑ ብሎት ነበር ነገር ግን ቆራጥና መን ፈሳዊ ክርስቲያን ስለነበር በግራኝ አህመድ ፊት ተፋበት ግራኝም ተናደደና ብዙ ጊዜ ከአሠቃየውና ከአስደበደበው በኋላ አንገቱን በሰለት ቆርጦ ለየመን ሱልጣን ላከለት ።

አጼ ገላውዴዎስ የፖርቱጋል መንግሥት ወታደርና መሳሪያ መላኩንና እንዲሁም ከእናታቸው ከሰብለ ወንጌል ጋር መሆናቸውን ሰምተው ነበርና ከደንቀዝ ወደአሲፋ አሸጊ መጥተው ከእንግዶቹና ከእናታቸው ጋር ተገናኙ ። አጼ ገላውዴዎስ ከፖርቱጊዞች የሚደናና የሚያበረታታ ቃል ከተናገሩ በኋላ ለሟቹ ለክርስቶፎር ሃዘን አደርገው ከሰነበቱ በኋላ ለቀሩት ፖርቱጊዞች የወርቅ መዳሊያ እየሰጡ ከአለቆቻቸው በኋላ የክርስቶፎር ዳጋማ ምክትል መሪ የነበረውን ዶን አልፍንዝ ካልዶሶ ጦር ጠቅላይ አዛዥ መሪ አድርገው ሾሙት ። በዶን አልፍንዝ መሪነት በወገራ ላይ ከግራኝ ጭፍሮች ጋር የተጠመደ ድል አደረጉ ። በዚህ ጦርነት ቢሊ መሃመድ ሱልጣን አቡበከር ጆሳ ጎራድ ኡስማን ሌሎችም እሊስ የመሐ የጦር አዛዦች ሞቱና በአጼ ገላውዴዎስ ሠራዊት ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ ነገር ግን አሲሉ ጦር መሪ ዶን አልፍንዝ ካልዶሶ ለሰሞተ ሰለሟቹ ሃዘን ከተደረገለት በሰልፍና በክብር ሟቹን ከአሰቀበሩ በኋላ በእርሱ ምትክ ዶሬቄስ ዲያዝ የሚባለውን ጀግና ጦር መሪ አድርገው እንደገና ሾሙላቸው ። በዚሁ ዘመን የአጼ ገላውዴዎስ ሃይል እየበረታ ስለሄደ ከጉጃም ከትግሬ ከዋግ መኳንንቱና መሳፍንቱ ለግራኝም ገብተው የነበሩት ሁሉ እየመጡ ገቡላቸው ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ የብል ውስጥ ትልቅ መሰጊድ ያሰራ ነበር የላካቸው ጦር መሪዎቹ በወገራ ጦርነት ላይ ስለሞቱና ሰላይ የነበሩት ሁሉ እየከዱት ወደ አጼ ገላውዴዎስ መግባታቸውን ሲሰማ ከንዴቱ የተነሳ አንድ ወር ሙሉ ታመው ይጸልዩም የግራኝ አህመድ የኢብራሂም ልጅ የአላህ ባሪያ ከሀረር እስከ ካዶር ከምፅዋ እስከ "መርካንያ" ድረስ ባለው ሃገር ላይ ታላቅ የእስላም መንግሥት ለመቋቋም የተመኘው ምኞት በመታጠቱና ይህን የምኞት ታላቅ የእስላም መንግሥት በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ ለመመስረት እንደተመኘ የአረብ ሃገሮች ባለስልጣኖች ስለአወቁ በጉጃም ምድር በሥቂው ውስጥ ባለቀት የባህር ወታደሮች አማካኝነት እርዳታ ከልከሉውን ነበርና የግራኝ አህመድ ኢብራሂም መጀመሪያ እሳቸን ሃገር ለመውረር በተነሳ ጊዜ ከአላህና ከነቢያቸን የተፈቀደ ቅዱስ ጦርነት ነው በርታ አይዞህ አለንልህ እያሉ የአረብና የኢሳ የሱማሌ ባላባቶች ያሰፈቀዱትን ሰፊ ወረራ ሲያካሂድ ወገኖቹ በዚሁ ጦርነት የተነሳ አልቀው ሴቶች ብቻ ቀርተው ከቁርከና ከዘመን በመጫጭፍራ ጦር እንደልታ እየተሸጠና እየተሰጡ እሱም ወደተወለደበትና ወደአደገበት ሃገር ሄዶ እንዳይቀመጥ የውስጥ ዘመዱና ወገኑ

ያለቀበት ሰው እንደሚገለው ስለአወቀ በዮብል መቀመጫውን ለማድረግ ከተማ ቆርቁሮ ነበር ። የቆረቆረውንም የከተማውን ስም አርጊዶር ኑርሃር ብሎት ነበር ።

ግራኝ አህመድ መገራስ መኸንፍን የማያውቅ ሞት አለ ብሎ የማያምን የተበታተነን ጉሳ ሁሉ በአንድ ላይ አድርጎ በአንድ እምነት በአንድ ታላቅ መንግሥት ስር አንድ ሃገር አድርጎ ለመግዛት የተመኘው ከውጭ ለእርዳታ ከመጡት የማያውቀውን እውቀትና ዘዴ እየሰማ ለራሱ ለሃገሩ ለህዝቡ ሲያደርግ ሲመኝ የነበረውን ታላቅ ምኞት የሰጠ ካብ ሆነበት ።

በዚህን ጊዜ ግራኝ አህመድ በየቦታው ድንጋይ እያስተከለ መስጊድ እንዲሰራ እዞ የነበረውና በየቦታው በመሠራት ላይ የነበረውን መስጊዶች የአጼ ገላውዴዎስ የጭዋ ጦር በፍንታቸው ማፍረስና ማቃጠል ጀመሩ ይሄን ሲሰማ እራት ሺሀ ማሀራን የባድ ጦር ይዞ ቆላውን ሃገር በገላን ቆዋሊሳን መልሳን ሁሉ እያሰገበረ በለሳ የሚባለው ሃገር ሲደርስ ለአጼ ገላውዴዎስ መምጣቱ ተነገራቸው እሳቸውም በፖርቱጊዞች የጦር ስልትና መሳ እየተረዱ ከአለበት ዘጠኝ ሺሀ በላይ የሚሆን አዶባሲጋዶ ላይ የጁዋ ጦር ሰለጠኑና ከአምስት ከፍለው በወይና ደጋው ሃገር ላይ እንዲቀመጥ አዘዙ እርምጃንተዋ የሚባለውን የጁዋ ጦር ከፊት ከፖርቱጊዞች ጋር ያለው ሲፋጠር የሚባለውን የጁዋ ጦር በስተግራ እናታቸውን ሰብለ ወንጌል የሚመሩት በስተቀኝ በኩል ውዚባ የሚባለውን ልዩ የጁዋ ጦር ከእርሳቸው ጋር በመከላከል ሆነው ሲጠብቁት የካቲት ሃያ ሶስት ቀን በሺሀ አምስት መቶ ሰላሳ አምስት 1535 ዓ/ም በገተራ ሚዳ ላይ ጦርነቱ ሲነጋ ተጀምሮ ቀትር ላይ በሁለቱ በኩል ብዙ ሰው እንደአለቀ በፖርቱጊዞች" አርቄብስ ሲያግዝ የሚመራው ሲፋራ የግራው ጦር የግራኝን ጦር ድል አድርጎ ግራኝ አህመድ ከአለበት ሰፈር ደርሶ ፔድሮስ ሊዮን የሚባለው ፖርቱጊዝ ግራኝን ተኩሶ ደረቱን መታው ግራኝ አህመድ በጥይት መመታቱን ያዩ ልዩ ወታደሮች ይዘውት ወደ ዲንማ ሚባለው "ሃገር ሸሹ ነገር ግን ደንቀዝ የሚባለው የጁዋ ጦር ግራኝ መመታቱንና መሸሹን ሲሰማ ተከታትሎ ደንማ ከሚባለው ሃገር ሳይደርስ ተዋጋና ወታደሮቹን ገድሎ ግራኝን ማርኮ ይዞ ሲመለስ በሺሀ አምስት መቶ ሰላሳ አምስት ዓ/ም በተወለደ በሰላሳ ስድስት ዓመቱ ግራኝ አህመድ መሃመድ ኢብራሂም አረፈና በዚያው እራሱን ቆርጠው ቀሪ ሰውነቱን በወይራ ዛፍ ላይ ሰቅለውት ሄዱ

ያንም የተሰቀለበት ወይራ ዛፍ የግራኝ ሰይፍ ያረፈበት እየተባለ
ዛፉ እስከዛሬ ድረስ አለ ሃገሩንም ግራኝ በር ተባለ የሞተበትን
ሥፍራና የተሰቀለበትን ዛፍ ሄዶ ለመጐብኘት ይቻላል ።

በዚህን ጊዜ ባለቤቱ ድል ወንበራና አደሬ ጭፍሮቹ መሞ
ሲሰሙ ከዙባል ወደ ሃረር ሸሽተው ሄዱ እነሱም አስቀድሞ ግራ
አህመድ ሃረርን እርስት አድርጐ ሰቷቸው ነበርና በሃረር የባላባ
ሴት ልጅ እያገቡ ተቀመጡ በዚህን ጊዜ እነዚህ አደሬ የተባሉት ግ
ራን አረቦችናከርጂ ከባላባቱ ሴት ልጅ ጋር ከተጋቡ በኋላ ቋንቋቸ
ከአረብ ከቱርጂ ከአርጐባ ከግእዝ የተቀላቀለ ስለሆነ በስማቸው የ
ደሬ ቋንቋ ተባለ የግራኝን እራስ የቆረጡት ሲፋጥራ ሰራዊት እራሱ
ወስደው ለአጼ ገላውዴዎስ አሳይተው ግዳይ ጣሉ ይባላል ።

አጼ ገላውዴዎስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በሁለ
ኛው ዘመነ መንግሥታቸው ይህን ድል ሲያገኙ ፖርቱጋል በተላ
ቸው አዲስ መድፍ አሰራ ሁለት ጊዜ አስተኩሰው አምላካቸውን አ
ሰግነው ከትዳሲ በኋላም ለፖርቱጋል ወታደሮች ልዩ ልዩ የሆነ ሽ
ማት ሰጥተው አስደሰቷቸው ሌላም ከግራኝ አህመድ የተማረከው
ወርቅና ሉል ሰጥተው ፍቃደኛ የሆነ እንዲቀመጥ ወደ ሃገሬ እ
ሉሁ ላለ የቻለውን ያክል ወርቅ ይዞ መሄድ ይችላል አሉ እንሄድ
ላሉት ግን ሰፋፊ መሬት እየሰጡ ጥሩ ቆንጆ ሴቶች እያገቡና በግ
ርና በበአል ቀን ከተከበረ ከፍታ ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ሲሉ አ
ህግ በአዋጅ አናገሩ ፖርቱጋሎችም በአዋጁ ተደስተው ከወይዛዝር
እየመረጡ በሚስትነት አግብተው የንጉሡ ባለሟል ሆነው በደስታ
በፍቅር ተቀመጡ ። ለኢትዮጵያ የጁዋ ጦር እርስት እየሰጡ በየሃገ
ላኩት ለግራኝ አህመድ ምስጢርና መንገድ እየመራ ወገኑን ሲያ
ድል የነበረ ሁሉ በአጼ ገላውዴዎስ በኩል ምህረት ሲያደርጉለትወ
ዘመዱ የሞተበት እያደባ ገደለው ይባላል ። በዚሁ አዋጅ የቢሃር ነጋ
ይስሃቅ የእናቱ አባት ሱልጣን አቡበከር ለግራኝ ሆኖ ባሀር ነጋ
ዶሪ ቱሉ የልጁን ባል የገደለና ሌሎቹንም ያስገደለ ስለነበር በዚ
እለት የግራኝ አህመድን ልጅና ከባሌው እዝማች ከተ/ሃ/የወሰዳቸ
ሚስቱን አሰረክቦ ገባ በምዕዋ በኩል ቱርኮች ያስፈሩ ስለ ነበር
ርታ አድርገውለት ከልጁ ልጅ ከባህር ይስሃቅ ጋር ተስማምተው
ዲገዙ ሲሉ የአዶሊስን ግዛት ሰጡት ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ገላውዲዎስ ግራኝ አህመድን እስከ ጭፍራ
እየተከታተሉ ድል አድርገው ካጠፉት በኋላ ያሠራውን መስጊድ እያ

ረሰ ቤተ ክርስቲያን ማስተከል መንደር መቆርቆር ጀመሩ ። አባታቸው
አጼ ልብነድንግል ድንጋይ አስቀምጠውበትና የአባቶቹ ዙፋን ከልጆቹ
ካልወጣ በዚህ ምድር የማሪያምን ቤተክርስቲያን እንዲሰሩ ሲሉ በመጽ
ሃፍትና በው ኑረው እራሳቸው አጼ ገላውዲዎስ ለአባታቸውና ለማርያም
ፍቅር ሲሉ የተድባበ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ባማረ ጌጥ እራሳቸው
ድንጋይና እንጨት እንደ ህዝቡ አብረው እየተሸከሙና እያነፁ አሰርተው
በስድስት ወር አስጨረሱ በዚህን ጊዜ ክርስቲያኖች እስላሞችን ድል
ማድረጋቸው በፖርቱጋልና በሮም መንግሥት ስለ ተሰማ በዚሁ ጦር
ነት ምክንያት ቱርኮች ከግብጽ ጳጳስ መላክ አቁመው ነበርና በታው
ዘፍት ስለነበር የሮማ ካቶሊክ ሊቀ ጳጳስ 3ኛው ጳውሎስ በፖርቱጋሉ
መንግሥት እንደራሲ ሀጎድ በሚገኘውና በራሱ በፖርቱጋል ንጉሥ
አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የካቶሊክ ጳጳስ መላክ ጀመሩ በካይሮ ባገ
ያሉትም ሲልጣኖች ይሄን ሲሰሙ ለበላያቸው ለቱርክ መንግሥት
አስታውቀው ዩሴፍ የሚባሉትን መነኩሴ የኢትዮጵያ ጳጳስ አድርገው
አዲሱ ንጉሠ ነገሥት መቀመጫ ወደሆነው ደንቀዝ ከተማ ገቡ አጼ
ገላውዲዎስም ምንም ሃይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ቢሆን የጳጳሱን መም
ጣት ያስፍቃዳቸው ስለሆነ ደስ አልተሰኙም ነበር ነገር ግን በግ
ብጽ የሚገኙት ክርስቲያኖች በጠላቶቻቸው በእስላሞች ስር ሆነው
እንጅ እነሱ እንደፈቀዱት አጼ ገላውዲዎስም ለአዲሱ ጳጳስ የቤፍ
ልዩ መንደር መተዳደሪያ የሚሆን ሰጧቸው ያንንም መንደር የሴፍን
ጽላት አስቀርፀው ቤተ ክርስቲያን አሰርተው እንዲዚሁ ከእሳቸውቀጥ
ለው የመጡትም አቡነ አብርሃም ለመተዳደሪያ የተሰጣቸውን መንደር
በሞከሻቸው የአብርሃምን ጽላት አስቀርፀው·ቤተክርስቲያን ተከለዋል
አቢያተ ክርስቲያኖች እስከ ዛሬ በዚሁ በወይናደጋው ምድር አሉ ።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

### የአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት

አጼ ገላውዴዎስ ስመ መንግሥታቸው አጽናፍ ሰገድ ንጉሠ ነ ሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአስረኛው ዘመነ መንግሥታቸው በግራኝ አህመድ ጭፍራ የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት እራሳቸው ባለ በቅ እንደገና አምረው እንዲሰሩና አዲስ ጽላት በጠፋው ፋንታ እንዲ ተካ አደረጉ ከተሰሩት ዋና ዋናዎቹን እንመልከት ።

| ተከታዮች | አብያተ ክርስቲያናት |
|---|---|
| በእቡን ተ/ሃይማኖት | የደብረ ሊባኖስ ገዳም |
| አጼ በእደ ማርያም | አትሮንስ ማርያም |
| አጼ ዘርአያቆብ | የደብረ ብርሃን /ሸዋ/ |
| አጼ በዕደ ማርያም | ምስሃለ ማርያም /መንዝ ሸዋ |
| አጼ በዕደ ማርያም | አትሮንስ ማርያም /ወሎ/ |
| | መንበረማርያም /ፎገራ ጎንደር |
| | ገነት ጊዮርጊስ |
| | መካነ ስላሴ |
| | ታእካ መንግሥት /ሸዋ/ |
| አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ | ገነተ ማርያም /ወሎ/ |
| | ደብረ ቤተል |
| | ደብረ ዘይት /ጐጃም/ |
| | መርጦለማርያም |
| | ደብረዘይት |
| | ጉሃ ጽዮን /ሸዋ/ |
| እንበሳ ዳዊት የወሰን ሰገድ አባት | ደብረ ክርቤ /ጐጃም/ |
| | ደብረ እስጢፋኖስ |
| | ኢንድርስማርያም |
| የበእደማርያም ባላቤት እሌኒ ግን ከብራ | መርጦለማርያም /ጐጃም |
| የናእድ ባ/እሌኒ ናእድ ሞገሳ | ደብረወርቅ |
| | ሀለተ ማርያም |
| | አክሱም ፅዮን (ትግሬ) |
| | ደብረ በዚን (ኤርትራ) |

መስን ሰገድ

ሀሴተ ማርያም
ደብረ መሲህ
አክሱም ጽዮን /ትግሬ/
ደብረ ቢዘን /ኤርትራ/

ከዚህ ከጸፍኩአቸው ሌላ አርባ አምስት አብያተ ክርስቲያኖች በአባቶቻቸውና በዛጉዌ ዘሮች በነ ቅዱስ ላሊበላ የታነፁትን ግራኝ አቃጥሏቸውና አጥፍቷቸው የነበሩትን አብያተ ክርስትያኖች እንዲሰሩ ትእዛዝ ስለአስተላለፉ በየቦታው በየጉጡ ከፊቱ የበለጠ አብያተ ክርስቲያኖች ታንፀው የመስጊድ ቤቶች ፈረሱ ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ገላውዲዎስ ተድባበ ማርያምን አሠርተው ሲጨርሱ መካነ ሰማእትን ሲያስጀምሩ ቅድመ አያታቸው አጼ በእደ ማርያም ዳግማዊት እቴገ እሌኒን ግን ክብሬ የቀባሉትን እንደአማራዎች ሀግ ሲያገቡ ተክለአልፍ የሚባሉ መነኩሴ መጥተው ስለባረኳቸው በዚያ ቦታ ጊዮርጊስ ደብርን ተክለው ነበር ነገር ግን ያንሥፍራ አመሙላድ የምትባል የጋፋት ንግሥት ነበረችበትና ከሞተች በኋላ አማራዎች ጋፋቶች ያመልኩበት ስለነበር ቤተክርስቲያኑን አፍርሰውት ቢኖሩ ፅላቱም በዋሻ ውስጥ ተደብቆ ሲኖር የአጼ ገላውዲዎስ እናት ሰብለወንጌል ተክለአልፋ በራእይ ተገልጸው ስለነገሯት ሊታሰራ ሄዶች ስለዚህ አጼ ገላውዲዎስ እናታቸውን ሰብለ ወንጌልን ለማስደሰት ከአማራ ሳይንት ተነስተው በሃራራ አድርገው እናታቸው ወዳሉበት በረንታ ገቡ ከዚያም ከአቡነ ዮሴፍ ቀጥለው አቡነአብርሃም የሚባሉ ጳጳስ ከግብፅ መጥተው ነበርና አብረው ከአጼው ጋር እንደሄዱ የተከለ አልፋን ቤተ ክርስቲያን አሰርተው ሲጨርሱ በጳጳሱ ታቦቱ ተባርኮ ሲገባ ትልቅ እ ውሎ ነፋስ ተነሳና ብዙ መንደር አፈረሰ አውሎ ነፋሱ ፀጥ ሲል ከመንበሩ ላይ በአጼ በእደ ማርያም ዘመነ መንግሥትና በእሳቸው ፈቃድ ተቀርጾ የነበረው የጊዮርጊስ ፅላት ከመንበሩ ላይ ተገኘ ከዚያም ለእቴጌ ሰብለ ወንጌልና ለአጼ ገላውዲዎስ ተነገራቸውና እቴጌይቱም የቤተክርስቲያኑን ቅጥርና ሌሎችን እቃቤቶች እያሰሩ ብዙ ቀን ቆዩ አጼ ገላውዲዎስ ደግሞ የአጼ ናኦድ ሞገስና ባለቤት እሌኒ ናኦድ ሞገሣ ያሰሩትን ደብረወርቅ ማርያምን ግራኝ አቃጥሎት ነበርና ሊያሰሩ ወደ ደብረ ወርቅ ሄዱ በዚያውም መርጦለማርያምን እሌኒ ግን ከብሯን ደብር እራሳቸው በአሉበት በሚያምር ሁኔታ ተሰርቶ ታቦቶቹ ተባርከው በየመቅደሳቸው ገብተው በመንበራቸው ላይ በክብር ተቀመጡ ዘመኑም አንድ ሽህ አምስት መቶ አምሳ 1550 ዓ/ም ላይ ነው ። በዚሁ ዘመን መንግሥታቸው

የግራኝ አህመድ ልጅ ገራድ አሊና ሐጂ ኡመር ዲን በረከት የኢላ ንና የአፍርጉሣ የሱማሌ ባላባቶችን ሰብስበው የአጼ ገላውዴዎስ ሠራዊት ካለበት ድረስ እንደገናህ ድረስ መጥቶ ጦርነት ገጠማቸውና በሁለቱ መካከል ብዙ ጭፍራ ካለቀ በኋላ የእስላም ጭፍራ ድል ሆኖና የክርስቲያን ሠራዊት ገራድ አሊ አህመድንና ሐጂ ኡመርዲን በረ ከትን ማርኮ ለአጼ ገላውዴዎስም ምርኮኞችን ወደ ጉዛም ሸበል እስር ቤት ላኩዋቸው የግራኝ ዘር ታሪክ ሊታወቅ የቻለው በእነዚህ እስረኞች ነው እንደዚህም ሆኖ አጼ ገላውዴዎስ እንማይና ሸበልን ደረቢንና ላበንን ጉዛምንና ማቻከልን ባለባቱን እየደለደሉ በበላይ የጉዋድ ሹም እየሾሙ ወደዳሞት ሄዱ በዚያም ግራኝ አስርቶት የነ በረውን መስጊድ እስፈርሰው በግራኝ ወረራ ዘመን የመጡትን የ ሮና የአርሆ ነገዶችን አሰለቅቀው የአማራውን ጼዋ (ጭዋ) ወታደር ደለደሉበት ሠሮችም ግማሹ ወደ እናሪያ ሄዶ ለኦረሞች ገባሪ ሆኖ ተቀመጠ ግማሹ በዚያው በባላባቱና ለጭዋ ወታደር ገባሪና ታዛ ሊሆን ቃል ገብቶ ተቀመጠ ያንም ሀገር ግራኝ በሚሰቱ ስም ወን በራ ብሎ የሰየመው ነው።

አጼ ገላውዴዎስ ሺንዲ የሚባል ቤተ መንግሥት ወደአባይ በሚ ያወርደው መንገድ ላይ ሲያሰሩ አቡነ አብርሃም ከንጉሱ ጋር ስለነበሩ ከግብፅ ሀገር ሁለት መነኩሴዎች አቡኑን ለመጠየቅ ስለወንድማ ቻው አቤቶ ሚናስና ስለእህታቸው ሮማን ወርቅ የግብፅ ሱልጣ ከአሉበት ፈልጉ እንዲያመጡላቸውና በሁለቱ መካከል ወዳጅነት እን ዲመሠረት የወርቅ ድሬ-መክሊዶትና ልዩ ድንጋይ ላኩለት በዚህ ጊዜ የግራኝ አህመድ ባለቤት ድል ወንበሬ ሰዋኪንና ሰባ-ጎዳያ ለሚገኙት ቱርክ ሻሻ ከአጼ ገላውዴዎስ ጋር ተስማምተው ልጅዋን ገራድ አሊ አህመድን ሌሎችንም ሱልጣን አቡበከር ጀላሊ ገራድ ኤልያስ አብደከዳርን እንዲያስፈቱለት አማላጅ ልኮ ስለነበር ቱርክ ሻሻም ግብፅ ለሚገኙት ባለሥልጣኖች በንገሩ ገብተው ጳጳስና ኤጵስ ቆ ልከው የተሰሩትን እንዲያስፈቱለት ተላልከው ነበርና በዚሁ በአ ገላውዴዎስና በባቴ ድል ወንበሬ ጥያቄ በመነኩሴዎች አላፊነት ሺበ (ጉዛም) ውስጥ ጉጃም የሚገኙትን ገራድ አሊንና እምሳ ሰባት የ ሆኑ የአረብና የሱማሌ ጉሳዎች ከታሰሩበት ተፈትተው ወደ ምስ ለቱርክ ባሻ ተላኩለት አቤቶ ሚናስ ከተሸጠበት ከሮም ልእል ሮማን ወርቅ የዘቢዱ ሱልጣን ስሊማን ልጅ ሱልጣን ዳውድ እ ቷት ነበርና ፈትቶ ላከላቸው ልእልት እትሊስያ ከተሸጠበት ከ ዳድ በጅምር ሃያ እንድ የነገሥታት ዘሮች ተሸጡበት ተፈልገው ወደ

ምዕዋ ተላኩና በዚሁ በሁሉቱ መንኩሴና በቱርክ ባሻ አማካኝነት ተቀያይረው ወደዘመዶቻቸው ተላኩና ለጊዜው በሁለቱም በኩል ታላቅ ደስታ ሆነ ። አፄ ገላውዴዎስ ከሸንዲ ወደ ደንቀዝ መጥተው ወንደ ማቸውን አቤቶ ሚናስን ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው ዙፋን ጠባቂ (ወራሽ) አዛዥ ጌደ ወርቅ ቀፀላ ሊቀ ጠቢባን ራጉኤል ደንግ የቤተ ክህነት ኃላፊና አስተዳደር አድርገው ሾሙና የአባቶቻቸውን ከተማ ለማሰራት ወደ እንጻኪያ ይፋት ሄዱ ።

አቤቶ ያዕቆብ ገሆር ከሚባል ሃገር መንዝ ውስጥ በድብቅ ይኖሩ ነበርና ግራኝ አህመድ ድል ሆኖ መሞቱን ወንድማቸው ገላውዴዎስ በአባታቸው ዙፋን መቀካታቸውን ሰለሰሙ ከሸዋ ወደ ደንተዚ ሄደው ላሉ የወሰን ሰገድን ልጅ የእንበሳ ዳዊትን የልጅ ልጅ የአዘቦን ግዛት ሰጥተው ንግስታ አዜብ አስኝተው ወደተጉለት ልከዋቸው ህዝቡም ለግራኝ ገብቶ ሰልሞ ነበርና እንገዛም እንገብርም አለ ስለዚህ አጼ ገላውዴዎስ ግራኝ ያፈረሰውን ቤተ መንግሥት ለማሰራት ያመፀውን ሃገር ወግተው ከእሳመኑ በኋላ ሹምሽር ለማድረግ ወደ ሸዋ ተጓዙ ።

በአንድ ሺህ አምስት መቶ አምሳ (1550) ዓ.ም. ላይ የቱርክ መንግሥት የግራኝ አህመድ እህት የፈርደውሳ ልጅ ኑር መሃመድ ኡስማን የሚባለውን ለአደሬዎችና ለሱማሌዎች የበላይ እንደራሴ አድ ርገው ሾመውት ነበርና እንደገና ተደራጅቶ ሱማሌንና ኢሲን አዳልን ጀሬ መራይሃን ጀበርን አልካን ይፋትን በረኸትን አርሆን ሰሴን የዛ ሬዎችን ሰላሌዎች እየተላላከ ለጦርነት ይዘጋጅና አንዳንድ ቦታ ለክር ስቲያን መንግሥት የሚረዱትን ያስወርር ጀመር በዚህን ጊዜ የእጉቱ ሚስት ባቴ ድል ወበራን እንደሀጋቸው ወርሶ አግብቷት ነበርና እሷም የወላስማውን ባላባት ሁሉ ወርጅዎችን አርጐባዎችን አስታጥቃ ከቀን ወደቀን አዲሱ ባሏዋን ኑር መሃመድ ኡስማንን ታበረታታው ጀመር ።

በዚህ ጊዜ በአንድ ሽህ አምስት መቶ አምሳ ሁለት ዓ/ም ኑር መሃመድ ኡስማን ወይም ኑር ኢብን ሙቃሂድ የሚባለው የግራኝ አህመድ የእህት ልጅ ከድል ባቴ ወበራ ባታህ ጋር ሰላሳ ስምንት ሽህ ጦር ይዞ መጥቶ አጼ ገላውዴዎስ በግራኝ ወረራ የፈረሰውን የአጼ ልብነድንግልን ቤተመንግሥት በእንጻኪያ ይፋት ውስጥ የሚገኘውን ያሰሩ ነበርና በድንገት ሳያስቡት ደርሶ ከትንሽ ሠራዊት ጋር ጦር ገጠማቸውና ድል ሆነው አጼ ገላውዴዎስ በተወለዱ በሰላሳ ስምንት አመታቸው ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አፅናፍ ሰገድ በተባሉ በአርባ ስባት ገብ ሆኑ

ከዚያም ኑር መሃመድ እራሳቸውን እስቆርጦ ወደሃረር ወስዶ ህዝ
እንዲያውቅ ከትልቅ እንጨት ላይ ሰቀለው በዚህን ጊዜ የሱማሌና የ
ዳል ህዝብ የግራኝን ደም በመስቀሉ ከህንድ ውቅያኖስ እስከ እ
ባህር ኤርትራ ባህር እራያዘቦ ድረስ ያለው እስላም ሁሉ ተገዛለት በ
ህን ጊዜ የሃረርን ከተማ በጥሩ ሁኔታ እስገነባው በመካከሉ ትልቅ
መስጊድ ጃሚ አሠራ ኑር መሃመድ ያሰራው መስጊድና ፍርስራሹ የከ
አጥር እስከዛሬ አለ በዚህን ጊዜ የአጼ ገላውዴዎስ እራስ በሀገ
ከተማ ላይ ስለተሰቀለ በሃገሩ የተቅማጥ በሽታ ገባና የእስላም ጭፍራ
በየቦታው እየወደቀ ሞቶ ይገኝ ጀመር ስለዚህ ወልዮች የንጉሡ ነ
ሥቱ እራስ በአደባባይ ተሰቅሎ ያየው ሰው ሁሉ የሚሞች እላህ ተ
ጥቶ ነው ብለው በየመስጊዱ ስለተናገሩ የአጼ ገላውዴዎስን እራስ
በክብር በወርቀዘቦ ልብስ ሸፍነው ወደእንጾኪያ ላኩት ከዚያም ወ
ደቀ እስጢፋኖስ ጣና ሃይቅ ውስጥ መጥቶ በክብር ተቀመጠ እራሳ
ውን ስለሰቀሉትና በጣና ሃይት እምጥተው እራሳቸውን ስለአስቀመ
ጡት እንዲህ የሚል ቅኔ የጭዋ ሶሮች የአንጐበሩስት ገጠሙላቸው

አጼ ገላውዴዎስ ጌታምን ለመምሰል
አርብ ተሰቀለ ፋሲካውን ሳይውል
ኢየሱስ ክርስቶስ የእሱማ ጌታ
እራሱን እስቀድመ የፋሲካ ለታ

እስቀምጦ እበላው ጠላቱን በተርታ (እስቀምጦ በተቅማጥ
እፅናፍ ሰገድ ቢባል አጼ ገላውዴዎስ
እራሱን ወዳጅ ነው እንደ የሃንስ

አጼ ገላውዴዎስ እራሱን አከብር

ከእሸዋ —(ከሸዋ) ላይ መጣ ባህር ዳሩን ዞር

አጼ ገላውዴዎስ መስሃዊት እስበጊዮርጊስ ቅድስተእማሆዱ በስ
ጊዮርጊስ ሃና የሚባሉት ስድስት ሴት ልጆች ነበራቸው አንድ ወን
ልጅ አልነበራቸውምና ወንድማቸውን እቤቶ ሚናስን ዙፋን ወራ
አድርገዋቸው ነበርና እሳቸው ሲሞቱ እቤቶ ሚናስ ንጉሥ ነገሥ
ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥት ወናግ ጋዲ ተብለው ነገሡ ።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

### የአጼ ሚናስና የልጃቸው የአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት

አቤቶ ሚናስ የአጼ ልብነድንግል ልጅ እቴጌ ሳሉ ጃሳ ከሚባሉት የተወለደ የአቤቶ ፈቅጦርና የልእልት አትለሲያ ታናሽ ወንድም ነው ለአቤቶ ያዕቆብና ለአጼ ገላውዴዎስ ለልእልት ሮማን ወርቅ ለልእልት አምራ ፀዮን በአባት እንጂ በእናታቸው በቀኙዋ ንግሥት በሰብለ ወንጌል አይገናኙም ።

በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ሁለት ዓመተ ምሕረት ሲፈጥራ ማርያም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስለ መንግሥት ወናግ ጋዲ ተብለው በአቡነ አብርሃም እጅ ቅባዕ መንግሥት ተቀብተው ነገሡ ።

አጼ ሚናስ ወናግ ጋዲ ተብለው እንደነገሡ የአቤቶ ያዕቆብንና የአጼ ገላውዴዎስን እናት እቴጌ ሰብለ ወንጌልን የእቴጌነውን ማዕረግ ሽረው ንግሥተነገሥታት ዘኢትዮጵያ እድማስ ሞገሳ አሰኙተው ባለቤታቸውን ስሉስ ሃይላን ሾሙ በዚህን ጊዜ የሃማሴን በቀይ ባሕር የሚገኙትን የሚገዛው ባሕረ ነጋሽ ይስሃቅ ዶሪ እራያ ዘቦን ይገዛ የነበረውን የአቤቶ ያዕቆብን ልጅ ተዝካረ ቃልን አስጠርቶ ደባሩአ ከሚባለው ከተማው ላይ አንግሶ አጼ ሚናስን ሊመውጋት ይዘጋጅ ጀመር ተዝካረ ቃልም እቴጌ ሰብለ ወንጌል የአባቱን እናት በማዋረድ ንጹት ነበረውና ጦሩን ከቀን ወደ ቀን ያበዛ ጀመር አጼ ሚናስ የወንድማቸው የአቤቶ ያዕቆብ ልጅ ተዝካረ ቃል በበላያቸው መንገሡንና ባሕር ነጋሽ ይስሃቅ ለአጼ ሚናስ አልገብርም አለ የሚባለን ወሬ ሲሰሙ አዝማች ዘርአ እስራኤል የሚባለውን የጦር አለቃ ከሁለት ሺህ የጭዋ ጦር ጋር ልከውት ነበር ድል ሆነና ሞተ ከዚህ በኋላ ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆን ጦር አጼ እራሳቸው ይዘው ወገራ ላይ ገጠሙትና የሁለቱ ጦር ሲዋጋ ከዋለ በኋላ በዘጠኝ ሰአት ተዝካረ ቃል ተማረከና በአደባባይ ሰቀሉት ባሕረ ነጋሽ ይሥሃቅ ግን ድል ሆነና የአቤቶ ያዕቆብን ልጆች ገሬም ፋሲልንና ሱግያ ቃልን ይዞ ወደ ደባሩ ተመልሶ ከዚያም ሳይውል ሳያድር በዋኪን ለሚገኙት ሱልጣኖችና ቱርክ ባሻ ከደጦር ከዳጦር ንጉሡ ነገሥቱን አጼ ሚናስን ለመጉዳት ወዳጅነት ጀመረት ቱርኮችም ብዙ መሳሪያ ሰጥተው ወደፊት ብዙ አጼ ሚናስን ለመጉዳ

ወዳጅነት ጀመረ ቱርኮችም ብዙ መሳሪያ ሰጥተው ወደፊት ብ
የጦር እቃ ከሃገራቸው እስመጥተው እንደሚሰጡት ገለፁለት ከዚ
በፊት ለነበረው ቂምና በቀል ትተው ወዳጅነትን ወደፊት ለልጅ ል
እንደሚመሰርቱ ገለፁለት እሱም በየጊዜው ከምፅዋ ያባርራቸው ነበር
ሁለተኛ ከነሱ ጋር ጦር ላይገጥም ቃል ገብቶ አርኪቆንና ምፅዋን ወ
ቡን እንዲቆጣጠሩት ፈቀደላቸው እነሱም በዚሁ ቃል ኪዳን ው
የተነሳ ግዛታቸውን ሊያስፋፉ ቻሉ በዚህን ጊዜ አንድ ሮማዊ የካ
ሊክ ጳጳስ አቡነእንድርያት አቢዶ የሚባል በባህር ነጋሺ ይስሃ
ፍቃድ ወደሸዋ ተልኮ እንዶጥናህ—(እንጦጦ) ሄዶ ተቀመጠ በዚህ
ጊዜ ፖርቱጋሎች ሃይማኖታቸው ካቶሊክ ነበርና በጣም ተደሰተ
ወደካቶሊክ ጳጳስ አቡነ እንድርያስ ሄዱ በዚህን ጊዜ አጼ ሚናስ ያ
ፍቃዳቸው መጥቶ በተቀመጠው ጳጳስና ሄደው አብረውት በተቀመጡ
ፖርቱጋሎች ጋር የከረረ ጠብ መደረጉና የአቤቶ ያእቆብን ልጆች
ቤተሰብ ለማጥፋት ወደ ሸዋ ሄዱ በዚህን ጊዜ በሃገሩ በሽታና እረሃ
መጥቶ ብዙ ህዝብ ያልቅ ነበርና ታመው ሸዋ ሳይደርሱ አማራ ሳ
ንት ላይ በነገሱ በአራት አመታቸው በአንድ ሺህ አምስት መቶ አም
ስድስት 1556 ዓ/ም ሞቱ አሬሳቸውም ተድባበ ማርያም ቤተ ክርስ
ያን ተቀበረ በዚህ ጊዜ ዙፋን ለመያዝ የአጼ ልብነድንግል ዘር
በያሉበት ጦርነትና ክርክር ከአደረጉ በኋላ በወዳጆቻቸው ቤተክ
ነት አላፊዎች እርዳታ ልጃቸውን ሡርፀ ድንግልን ንጉሠ ነገሥ
ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥት መለክ ሰገድ ብለው በአንድ ሺህ አም
ስት መቶ አምስት ስድስት አ/ም አነገሳቸው

አጼ ሚናስ ከእህቶቻቸው ከአቅቢስያና ከሮማን ወርቅ ጋር በ
ሲል ተራራ ስር ሳሉ ከቤተማርያም በግራኝ አህመድ ወረራ ዘመ
ተማርከው ወደዘቢድ ተልከው ከዚያም አረቦች ለሳቲኖች ባሪያ ብለ
ሰጠዋቸው ሲኖሩ ሳለ ወንድማቸው አጼ ገላውዴዎስ በለውጥ ከ
ወደ ሀገራቸው እስመጣቸው በዚህን ጊዜ አጼ ገላውዴዎስ ወን
ልጅ ስላልነበራቸው የጭልጋውን ባላባቱ የድዮንን ልጅ አደነበር
አጋብተው ዙፋን ተጠባባቂ አድርገዋቸው ሳለ አጼ ገላውዴዎ
ሲሞቱ አጼ ሚናስ በፋንታቸው ነገሡ አጼ ሚናስም ከእቴጌ አደነ
ስመ መንግሥታቸው ሰሉስ ሃይላ ማርን ወለዱ ማርም ስመ ክርስ
ቸው ሡርፀ ድንግል ተብለው ከማር ይልቅ ሰርፀ ድንግልን መ
ስለሚወዱ ሡርፀ ድንግል ተባሉ ።

እንደዚህም ሆኖ ሡርፀ ድንግል በተወለዱ በአስራ ሶስት አመ
ቸው አባታቸው ሚናስ ሲሞቱ ከእቴጌ አድማስ ሞገሳ ከቀኝ ባቴ

የሚወለደው ታላቁ ወንድማቸው ብእለ ድንግልን ለማንገስ ስብሰባ ተደረገ ነገር ግን ብእለድንግል ከፖርቱጋሎች ጋር ወደ እንጦጦ ሄዶ ከካቶሊክ ጳጳስ አባ እንድርያስ ዘንድ ተባርኮ ሃይማኖታቸውን ቀይረዋል ስለተባለ ታናሹን ልጅ ሠርፀ ድንግልን ለማንገሥ የቤተ ክህነቱ ባለስልጣን ተስማማ የዳሞት ገዢ የንጉሥ ወሰን ሰገድ ልጆች ዘርአ ዮሃንስና የደንቢያው ገዢ የንግሥተ አዜብ ወንድም ሃርቦ ግን የአጼ ልብነድንግል የልጅ ልጅ የሮማን ወርቅ ልጅ ሃመልማልን ለማንገስ ጉባኤ አድርገው ወሰኑ በዚህን ጊዜ በአጼ ሚናስ ዘመን መንግሥት ከአጼ ሚናስ ጋር እቴጌ ሰብለ ወንጌል ተጣልተው ጉጃም ዳማ ጊዮርጊስ ይኖሩ ነበርና የአጼ ሚናስን ሞት ሲሰሙ ወደ ደንቀዝ ሄዱና መንኩሰው ስለነበር ወደ ቤተ ክህነቱ ክፍል ሆነው ሠርፀ ድንግል እንዲነግሱ ለወዳጆቻቸው ተናገሩ በዚህን ጊዜ አስተማሪያቸው ታላቁ ደራሲ ስብሃት ለአብ ሊቀ ሊቃውንት ክፍለ ማርያም አባ አፅቀ ድንግል የጉንድ አበምኔት አባ ዘድንግል አባገር ተክለ ጊዮርጊስ አምደ ሆነው አቡነ ሳዊሮስ የሚባሉ አዲስ ጳጳስ መጥተው ነበርና በእሁ ጳጳስ እጅ ኮሰጌ ከሚባለው ሃገር ላይ ወስደው ሥርዓተ ንግሡን አድር ሰው ሰመ መንግሥታቸውን መለክ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አሰኙተው በአንድ ሺህ አምስት መቶ አምሳ ስድስት ዓ/ም አነገሷቸው የዚህ ስርዓተ ንግሥ በሽሽግ ከፈጸሙ በኋላ በአደባባይ በደንቀዛ ከተማ አጼ ሚናስ ስለሞቱ ልጃቸውን ሠርፀ ድንግልን መለክ ሰገግ ብለው እንግሡናል ብለው አወጁ በዚህን ጊዜ የሮማን ወርቅ ልጅ ሃመልማል መኳንንቱንና መሣፍንቱን ይዞ ጦርነት ገጠማቸው ድል አደረገ አጼ ሠርፀ ድንግልም ከአንድ ሃገር ወደ አንድ ሃገር ሲዘዋወሩ ከቆዩ በኋላ የሃመልማል ደጋፊ እየከዳ ወደ አጼ ሠርፀ ድንግል ገባ ስለዚህ እራሱ ሃመልማል እስከ ሠራዊቱ ታርቆ ገባና ሰጡት ለሮም ሰገድ ሸዋን ሰጡ ጠላት የነበረው ኋላ አምኖ ስለገባ መንግሥታቸውን አደላድለው ሹም ሽር አደረጉ ።

የወሰን ሰገድን ልጅ ዘርአ ዮሃንስን ጉጃም ነጋሺ ብለው የጉጃ ምን ግዛት ሰጡት የአቤቶ ያእቆብን ልጅ ፋሲልን ከባህር ነጋሺ ይስ ሃቅ ጋር ተጣልቶ ስለመጣ የንብያና የሱኪ ነጋሺ አድርገው በክብር አስቀመጡት ፡፡

ከባጉዩ ዘር የምትወለደውን ማርያም ሰናን ባለቤታቸውን ድልሰና ብለው የእቴጌነትን ዘውድ በራሳቸው ላይ አስደፍተው እርባ ቀን ግብር አደረጉላቸው ።

እቴጌ ማርያምስናም ለአጼ ሠርፀ ድንግል አሙታ ሚካኤል — ቀሲሳዊት መዋሴ ወለተጊዮርጊስ ሃይላ የሚባሉ ሶስት ሴቶች ልጆች ወለዱላቸው ።

አጼ ሠርፀ ድንግል ከጋላዎች ወይም ከኦሮሞች ጋር ያደረጉትን ጦርነት ከማቅረቤ በፊት ኦሮሞ ማለት እነማን ከምን የመጡ? በየት ሃገርስ የሰፈሩ ናቸው ብሎ ማወቁ ለሁላችን ይጠቅማል የአማራን ታሪክ በአጼ ይኩኖ አምላክ እንደገለፅኩላችሁ የኦሮሞችንም ምንም በየታሪኩ ውስጥ ቢገኝ አሁን በጥቂቱ የኦሮሞን ታሪክ ከአጼ ሠርፀ ድንግል ታሪክ ጋር እያይዝ አቅርቤላችኋለሁ መራሪስ ኤ.ኤም. በላይ።

ከአዳም እስከ ኖህ — ያለው ትውልድ ትርጉሜው በሰባ

| | |
|---|---|
| የኖህ ልጅ ካም | |
| የካም ልጅ ኩሲ — ኩሽ — ከሳዊ | ጥላ |
| የኩሽ ልጅ ማባ—ማቢውስ—ማባዋ | በረኸኛ |
| የማባ ልጅ ኑባ—ኖባል ኑባዊ | የንብ ሰፈፍ |
| የኑባ ልጅ ጋናን | ብዙ ቁጥር አሰፈሪ |
| የጋናን ልጅ ኢታና | ስጦታ |
| የኢታና ልጅ ናምሩድ | ሃይለኛ አዋቂ |
| የናምሩድ ልጅ አዳማ | መልካም |
| የአዳማ ልጅ ራፌልብ | አዛዢ ጌታ |
| የራፌሰብ ልጅ ቁና ኬና ኬናዊ | ብልሃተኛ |
| የቁና ልጅ ጌራ ጌራራ መልከ ጸዴቅ | የወርቅ ቀለሞች |
| የጌራራ ልጅ ኢትኤል—ኢትዮጵያዊ | የአምላክ ስጦታ |

ኢትኤል በእምላኬ መንፈስ እየተመራ ከባሴም ተነስቶ ግዮን ወንዝ ወደሚፈስበት ምድር ሄዶ ሰፈረ በግዮን ምድር ኢያሰዱድያ የሚባለው ወርቅ የሚገኝበት ነው ዮቋ የሚባለው ክቡር ወርቅ ያለበት ምድር ስለሆነ በዮቋ ወርቅና በእንቁ ስለከበረ ኢትኤል መባሉ ቀርቶ ኢትዮጵያ ተባለ ሚስቱም ሲና መባልዋ ቀርቶ እንቁዮቋ እንቁዮቋ ግዮን ተብላለች ኢትኤልም ምድሩን በስሙ ኢትዮጵያ እንዲባል አድርገዋል ።

ኢትዮጵ የተባለው ኢትኤል የሩቱራን ልጅ እንቁዮጳ የተባለች ውን ሲናን አግብቶ በግዮን ዳር አስር ወንዶች ሶስት ሴቶች ወልዶል

የወንዶቹ ስም እሚቲባ ፡ ቱብ ግብፅ ውስጥ ቢአር ፡ ቢአራ ተምና ፡ አቱር ፡ አሻን ፡ አክዚብ ፡ በሪሳ ፡ ቱስቢ ፡ ቶላ ፡ አዜብ ናቸው የሴቶቹ ሴባ ፡ ሚልካ ሱባ ናቸው አስሩ ሁሉ የተለያየ ጐሳ ሆነዋል ።

ከነገዶ ቢአርን ዘር ብቻ አቀርባለሁ ።

የኢትኢል ልጅ ቢአር
የቢአር ልጅ አራም
የአራም ልጅ ናጌ
የናጌ ልጅ ሃጌ
የሃጌ ልጅ ቢአራ ቢአር
የቢአር ልጅ በልአም
የበልአም ልጅ ቀራሚድ
የቀራሚድ ሴት ልጅ ሽምሽል

ሽምሽል ሙት የምታስነሳ መንፈስሃይል ያላት ሰው ከፊትዋ የሚያቀርብ ተና ብሎ ማየት የማይቻል እስፈሪ ነበረች ።

ስለዚህ በድንግልና ስትኖር በመንፈስ ከውሃ ላይ በፈሰሰ ዘር አፈማህፀንዋን ስለታጠበች ታላቁን ነቢይና አዋቂ ፈላስፋውን ደሽትን አርግዛ ወለደች የደሽት ልጆች ማጂ ጂማ መንዲ መደባይ ናቸው ማጂ ማራን (የአማራ ጐሳ) ዣማን ጂየማን ይወልዳል ።

ጂማ ገነቴን አረርቲን ሞረንን ይወልዳል እነዚህ ሁሉ በግዮን ወንዝ ለወንዝ ሄደው የሰፈሩ ናቸው ከነዚህ ከአራቱ ነገዶች በየጊዜው ብዙ ጐሣ ሆነዋል የጂማ የመንዲ የመደባይ ዘሮች የሚኖሩበትና በአጼ ዘመን መንግሥት ታውቀውና በእጄው ሥር ሆኖ የሚገዛቸው ንጉሥ የነበረበት ምድርና ወንዝ ።

| ንጉሡ | ሀገሩ | ወንዙ | ጐሣው |
| --- | --- | --- | --- |
| ላሞ | ሞሳ | የግዮን ሃይቅ | መደባይ ማጂ ጋፋት |
| | ኢውላጥ | ዋቢ | ጂሪ ዋጂራት ባንጋ |
| ኮፕሮም | ደሽት | ግዮን የከበበው | መንዲ ወንጊ |
| የላሞ ልጅ ኮንዚ | ሰገል | ነገሌ | ቦረና ቱለማ አባታሊት |
| የሰኮንስ ልጅ ሰአካ | ኢገዘ | ገናሌ | በርቱማ ጋሊ ጀሌ |
| የፊንታሌ ልጅ ጭላሉ | ሃጌ | አዋሽ | ኢግ ሆሽን ሲዳማ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የዳራስ ልጅ መጋል ሞራ | ግቤ | ማያ ሆሮወሳቦ ቦረን ኢቱ | |
| ጋውል | ኢዛር | ጂባ | ውረማያ |

እነዚህ ስምንት ንጉሶች ሁለት ጐሳዎች የጂማ የመንዲ የመደባይ ዘሮች ናቸው መቀመጫቸው በየጊዜው ተቀያይሯል ለምሳሌ ኢያ የሚባለውን ገበማን ከገበማን ሸዋ ተብሏል በእ‹ዝ ጊዜ የመደባይ ዘሮች በገበማን ጊዜ ሃገሩን ሸዋ ብለው እነዚህን ኦሮሞዎችን አስ ቅቀው በግራርጌና በአድስጌ በዝዋይ የአማራን ጉማ ይከፍ አምላ አስፍሮበት ነበር ይሄውም የጭዋ መቀመጫ አደረገ ጭዋውን በበላ ቸው ላይ ሾመባቸው በግራኝ አህመድ ወረራ ደግሞ ግራኝ አማራው አጥፍቶ በግራርጌ ሰሌዎችን አስፈረበት ከአጼ ዘመነ መንግሥት እስ ቀዳማዊ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት አምስት መቶ ዘመን ሲኖራቸው በዚሁ በቀዳማዊ ሚኒልክ ዘመነ መንግስት ደግሞ ቀዳማዊ ሚኒሊ በነገሠ በሃያኛው ዘመነ መንግሥቱ ወደዞባ ሄዱ ሃገሩ እናሬያ ከተማ ዞባ ንጉሡ የጂማ ዘር ሞረካ ኪታ ነበር እናሪያ የዛሬው ወለጋና ከ ነው በዚሁ በዞባ ከተማ አርባ ነገሥታት መጥተው ለቀዳማዊ ሚኒል እጅ መንሻና ግብር ሰጡት እሱም ባልመጡት ነገሥታት ላይ ከባ መቀጫ ጥሎ የመጡትን ነገሥታት ባልመጡት ነገሥታት ላይ ሾ ቸው የቆየውንም ህግና ሥርዓት ትተው በአዲሱ በአሪት ህግ እን መሩ እዘዘ የደሸትን ካህናቶችና መፅሃፍታቸውን አጠፋ ስለዚህ እ ጣጣቸውና ታሪካቸው ተደብቆ ሲኖር በዚሁ በኢትዮጵያ ትኔሳኢታሪ ከመፅሐፈ ሱባኤ አግኝቼ ፅፌላችኋለሁ ።

ስማቸውም መደባይ መባሉ ቀርቶ ኦሮሞ አሏቸው በሱባ ቋን ኦሮሞ ማለት አዋቂ ሞራ ገላጭ ወይም እንባቢ ማለት ነው ይሄው እንድ የመደባይ አዋቂ መፅሐፉን የሚደብቅበት አጥቶ ለላሚቱ አ ላት ከቀን በኋላ ሚኒሊክ ሃገሩን ለቆ ሲሄድ ፈላስፋው ላሚቱን አ ዳት ቢያርዳት መጽሐፉ ሊገኝ ስላልቻለ ስጋዋን ሲመለከት ከሞራ ላይ ተፅፎ ተገኘ ከዚያ በከብቶች ሞራ ላይ የእነሱ ታሪክ እንዳ ለልጆቹ አስተማረ ከቀን ብዛት ወደጥንቁልና ተቀየረ ይባላል ። ያ ሆነ ይሀ ጋሌ ትርጉም አውቆ መቁጠር ኦሮሞ ትርጉሙ ሞራ ገላ ወይም የልብ ምስጢር አዋቂ እየተባሉ ሲኖሩ በአጼ ልብነድንግል ዘመነ መንግሥት ከድተው ለግራኝ ስለሆኑ ኦሮሞ ማለቱን ትተ እግአዝያን በግእዝ አረመኔ አሏቸው አረመኔ ማለት ሃይማኖት የለ ከሃዲ ጨካኝ ማለት ነው ።

እነዚህ ኦሮሞች በቀዳማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት የኦሪትን ባህልና ሥርዓት ስለተከተሉ ብዙ ጋብቻ ውርስ ከእብራውያን ጋር ይመሳሰላል ደንቀራ መጣሉ ዛጉል መበተኑ በውሃ ማጥሪቱ አንድ ነው ሌላው ህጉ ግን የመደባይ ዘሮች ብድራቸውን መልሰዋል ብዙ የኦሪት ካህናት ብዙ ፅላት አጥፍተውባቸዋል ።

በአፈላስ አክሴማይ ራሚሲ ዘመነ መንግሥት ዘመን ከተቆጠረ በአራት ሺህ ስድስት መቶ/ሰላሳ ላይ (4630) ላይ የተጻፉት የኦሮሞ ተመሳሳይ ጉሣዎች ።

| ስማቸው | ሃገራቸው | አጠራሩ |
|---|---|---|
| ኦሮሞ | አርያ | ማያ ወረማያ |
| ጋላ — ገላ | ውቅሮ | ውቅሮያ |
| ደራስ | ሆር ውላበ | አውላብያ |
| ቦረን | ኪንዶ ሃድያ | ሃድያ |
| በርቱማ | ጥሞጋ | ሞጋብያ |
| ከረዩ | መረዋ | መረዋንያ |
| ኢቱ | ሞራ | ሞራና |
| አከቹ | ወረን | ወረያ |
| ሊበን—ጃዊ | ጉጃም | ዶሸት |
| ሜጫ | ሴማ | ሰማሊያ |
| ሰሉ ሰላሌ | ጎንተ ዉሌ | ወልድያ |
| ሰደሞራ | አሙሩ | ሸቦካ ጂራ ዋጂራ |
| ጂሌ | ጨፋ | ጎንቲያ ወረም |
| አዳል—አዛል | ፋዶር | እንፋርያ አባታላት |
| ነሸን | ሃሸንጌ | ሐሸን ዶርዶ |
| ማያ | ገበጣን | ዝዋይ ሱካ |
| ሰዶቻ | ቆቦ | አራያ ማጂ |
| ዶራ አርሆ | ጉማዬ | ጉማያ መንዲ |
| ቦፋት | ትቢ | ቦባሳ ማሲያ |
| ከምባታ | በወላሞ | በያ ኪኩያ |
| ጋፋት | ከፋ | ከፋያ ሲሲ |
| አማሮ | ኩሌ | መንዲያ ቡዱ ማድጋስኮ |

እነዚህ ሁሉ የኦሮሞ ተመሳሳይ ነገዶች ናቸው እነዚህ ተመሳሳይ ጉሳዎች ጥንት ንጉሳቸው ስምንት ነበር በአክሱማይ አፈላስ ዘመነ መንግሥት ማንኛውም ጉሣ በሌላው ጉሣ እንዳይገዛ ስለከለከለ የአዲስ

ህግ ሥርዓት ስለአወጀ ለየራሳቸው ንጉሥና ቋንቋ እንዲኖራቸው
አድርጓል ። ነገር ግን ከጊዜ ብዛት አንዱን ጉሣ አንደኛው ጉሣ እየ
ወረረ ለራሱ ተገዢ አድርጕታል ስለዚህ በስማቸው የነበሩት ሃገር
እስከዛሬ በሃገር ስም ይታወቃል ግማሹ ጉሳ ደግሞ በሃገሩ ስም ይጠ
ራል ጉጃም /ጉጂ/ ጉንደር /ጉንደሬ/ እንደሚባለው ማለት ነው ።

ጉሣዎች ሌላ በየጊዜው ብዙ ነገድ ተነስቷል ብዙም ጠፍቷል
ይሄውም በአጼ ዘመን መንግሥት የመደባይ መንዲ የሚባሉት የሉም
ይሄውም ማጂ ማለት አዋቂ ስለሆነ ለአዋቂዎች ብቻ የተሰጠ ስም
ይመስላል መደባይ ማለት ግን ፈላስፋ መራቂ በረከት ሰጭ ካህን
ማለት ነው ። ስለዚህ የመደበይ ስም እየቀነሰ መጣ አረም የሚባለው
ስም በዚሁ በአፈላስ ዘመን መንግሥት ቃወቀ ሃገራቸውም ሲገል ነው
ወንዙ ነገሉ ይባላል ።

አሮሞች የሚባሉት ከአግአዝያን ዘሮች ሲጋቡ የኖሩ ቢጋብቻ
ከንግሥታት ጋር ተሳስረው እስከ አጼ ልብነ ድንግል ደርሰዋል ከአጼ
ልብነድንግል ዘመን መንግሥት ጀምሮ ግን ታሪካቸው ወደታች እየተ
ደረገ ስማቸው እየተፋቀና እየጠፋ መጥቶ ነበር ነገር ግን ምንም
ቢደበቅ እውነተኛ ታሪክ ጊዜውን ጠብቆ መገለጡ አይቀርም ስለዚህ
ከብዙ በጥቂቱ ከመፅሐፈ ሱባኤ ገልብጬ አቀርብላችሁ ከአጼ
ልብነድንግል ዘመን መንግሥት ጀምሮ ለምን ተደበቀ ለምንስ ተናቀ
የሚል ይኖር ይሆናል የግራኝ አህመድን ወረራ ታሪክ በአጼ ልብነ
ድንግል ታሪክ ላይ ተመልከቱ ይሄውም አባ ገዳ ኦልማያኦባተንክር
አባ ወሰን ቱሉማ አባ ኮርቶ አባ መርዞ አባ ቡላ የሚባሉት የኦሮሞ
ንጉሶች ጋር ሆኖ በሸንብራ ኩሬ ወይም በአዳማ ጦርነት የአጼ
ልብነድንግልን ሠራዊትና ክርስቲያኑን ሕዝብ በመርዝ ሽቶል ስለ
ገደሉ በብዙ ሺህ የሚሆን ስለአለቁ ከአጼ ልብነድንግል ጀምሮ
የከረረ ጠብና ጥላቻ ተደረገባቸው እንጅ ከዚያ በፊት የመንግሥትቱ
ሥራ በአግአዝያን ሥር ሆነው ይመሩ ነበር ለምሳሌ ይኩኖ አምላክ
ከሜላ ልጅ ከጊፍቲ መንደያ ከሃዊ ከአረሞይቱ የተወለደ ነው አጼ
ልብነድንግል የደዋሮይቱ የቱሉ በዲሳ ልጅ የሳልሳዊት እሌኒናአድ
ሞገሣ ልጅ ናቸው የኦሮሞን ታሪክ አጠናቶ ለማወቅ ከመጀመሪያ
እስከመጨረሻው ካነበባችሁት ልታውቁትና ለሌሎች ልታሳውቁና
ልታስረዱ ትችላላችሁ በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመን መንግሥት የተቆ
ጠሩት የቦረና የቱሊማ ነገዶች እነዚህ ናቸው ከውቅሮ እስከ ማልበ
ርዲ ድረስ የነበሩ ሜጫ ፣ ጠሎ ከረዶ ፣ ጂሌ ፣ ኢቱ ፣ ወረንጦሻ ፣ ሰዶ ፣
ገንዝ ፣ ቡሺ ዳሮዶ ፣ ገደብቶ ፣ ጉለላ ፣ ዲሆ ፣ የቶጂራ ፣ ሲዳማ ፣ ሀደቡ ፣

እንፈሎ ፡ ገዲብ ፡ ደረማ ፡ አላባ ፡ ጊድአ ፡ ሥጋ ፡ ቀበና ፡ ከምባታ ፡ ገብ ፡ ማሆ ፡ ኡልባልማ ፡ ጉጋላ ፡ ኢጃቢ ፡ አዘአርንት ፡ በርበሬ ፡ ስልጤ ፡ ኤፌጌ ፡ ኢሣ ፡ ኡልባልማ ፡ ሸሸጐ ፡ ጐሮማ ፡ ቡሺ ፡ ማረቆ ፡ ቀምባራ ፡ ዱባሞ ፡ ናራ ፡ ማልጊና ፡ ደንጋ ፡ ሄኖር ። ጉንጋ ፡ ቢዛሞ ፡ ናቻው እነዚህ ጉማዎች ሁሉ የተለያየ ቋንቋ አላቸው ነገር ግን የጥንቱን መደባይ የዛሬውን አረሞ ቋንቋ ይገናኙበታል ሥርዓታቸውም ጉዲፈቻ ሞጋሳ የሚባል ነው እነዚህ ነገዶች ዓማኞች ዛሬም አሉ ።

በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት የቤተክህነቱና ዋና ዋና የውስጥ አስተዳዳሪ የቤተመንግሥቱ አላፊዎች

| ለቀ ሥልጣናት | የባለሥልጣኖች አለቃ |
| --- | --- |
| ቄስ አጼ | የአጼው ንስሃ አባት |
| እጨጌ (እጩጌ) | የአጼው አማካሪ |
| ንቡረ እድ | የመናገሻ ደብሮች አስተዳዳሪ ስም |
| መልአከ ሃይል | የደብር አለቃ |
| አበምኔት | የገዳም አስተዳዳሪ |
| መሪራስ - ርእሰመሪ | የቤተክህነቱን የቤ/መ)ታሪክ ፀሐፊ |
| ሊቀ ሊቃውንት | የአሊቆች አለቃ |
| ሊቀ ማእምራን | የአስተማሪዎች አለቃ |
| ሊቀ ካህናት | የካህናቱ አለቃ |
| ሊቀ ጠበብት | የሰዓት ቀራጮች አለቃ |
| ሊቀ ዲያቆን | የዲያቆን አለቃ |
| ሊቀ ገበዝ | የገበዝ አዛገር |
| ቄስ ገበዝ | የቤ (ክ) ውስጥ ሥራ የሚቆጣጠር |
| መሪጌታ | የማህሌቱ አላፊ መሪ መካከለኛው |
| ቀኝ ጌታ | የቀኝ ክፍል መሪ |
| ግራ ጌታ | የግራውን ክፍል መሪ |
| ቄስ<br>ዲያቆን | የቤ (ክ) አገልጋይ ባለሥልጣን ተላላኪ ለቤተ መቅደስ |

በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት የባለሥልጣኖች የማዕረግ ስም

| | |
| --- | --- |
| አጼ | ንጉሠ ነገሥት |

1 ቃለ እጼ
2 ራስ የበላይ አዛዥ
3 መሪራስ
4 ጃንሆይ
5 እቴጌ
6 እቤቶ
7 እቶ
8 ዕራግ ማሰሬ
9 ብላታ - ብላቴን ጌታ
10 እቃቤ ሰአት
11 ዳሞት ነጋሺ
12 ጐጃም ነጋሺ
13 ወሌጋ ነጋሺ
14 ሱኪ ነጋሺ
15 ባህር ነጋሺ
16 ጸሀፈላሀም
17 ባሌ ገራድ
18 ጋንዘን ገራድ
19 ጋንዘን
20 ደዋሮ ገራድ
21 ትግሬ መኮንን
22 ዋግ ሹም
23 ሺሬ ሹም
24 ከንቲባ
25 ብትሀ ወደድ
26 ደጃዝማች ደጃች
27 ፀኃፊ ትእዛዝ

28 ጃንጥራር - ዣንጽራር
29 ባሌጋጀ
30 በጂሮንድ
31 ፊታውራሪ
32 ቀኛዝማች
33 ግራዝማች

1 ትእዛዝ አስተላላፊ
2 የበላይ አዛዥ እንደራሴ
3 ፈጻሚ አዛዥ (ታሪክ ፀኃፊ)
4 ባለግርማ ሆይ -
5 ንግሥት ሆይ
6 የኛ ወራሽ ምትክ
7 ባለትዳር የቤተሰብ አላፊ
8 ከእጼ አቅራቢና አስተናጋጅ
9 የእጼው የእልፍኝ ልጆች
10 ንጉሥ ሲንግሥ አስተናጋጅ
11 የዳሞት ንጉሥ
12 የጐጃም ንጉሥ
13 የወለጋ ንጉሥ
14 የሱኪ ንጉሥ
15 የኤርትራ ባህር ንጉሥ
16 የሸዋ የዳሞት ግብር ሰብሳ
17 በእስላሞች ዘንድ የተሾመ
18 ጉዋኝ ምርት ገምጋሚ
19 ባላንባራስ ባለንባራስ
20 ጭቃ ሹም መሬት ደልዳ
21 ከባህር ነጋሹቀጥሎ የተሾመ ግብር አስገባ
22 የዋግ ገዢ
23 የጉራጌ
24 የሃማሴን የደንቢያ ገዢ

25 ደጃንመር አዝማች
26 የእጼውን ትእዛዝ ዕድ አስ
ተላላፊ
27 የእጼውን ጠላቶች የሚቀ
28 የእንደርታ ሹም
29 የን/ጆሮ ጠቢ
30 የግንባር ጦር መሪ
31 ቀኙን አዝማች
32 ግራውን አዝማች

እጼ ሠርፀ ድንግል በጌቤና በዳዊስ መካከል የውይጣውጥ ንጉሥ መክተር በአጼ ልብነድንግል ዘመነ መንግሥት ከድቶ ለግራኝ አህመድ ገብቶ ከሱኪ ሌላ ከፋንና ወሊጋን ኩሌንና ከምባታን ሰጥቶት በእናሪያ ቤተ መንግሥት አሥርቶ ሲኖር በመካከሉ አበደና ሞተ በፋንታው ልጁ ሲቢንዚ ነግሶ ሳለ እጼ ሠርፀ ድንግል ወደእናሪያ መምጣታቸውን ሲሰማ ተዋግቶ ድል እንደማያደርጋቸው አውቆ ብዙ ወርቅና ከብት ይዞ መጥቶ ግብር ስለአገባላቸው ገገርህ እኔ ነኝ ባለህበት እርጋ ብለው ባላባቱን ሁሉ ሰብስበው ሹም ሽር ሲያደርጉ ሰንብተው ከእናሪያ ወደጉራጌ ሀገር ለመሄድ ሲዘጋጁዋቸው የተባሉት ወይጣውይጦች የበረሃውን ሰው ይዘው መጥተው ብዙ የእጼ ሠርፀ ድንግል መኳንንትና መሳፍንት በድብቅ ገደሉ በዚህን ጊዜ እጼ ሠርፀ ድንግል ሲቢንዜን ይሄን ሁሉ የምታደርግ አንተነህ ብለው ቢጠይቁት እኔ አይደለሁም ነገር ግን የአባቶቼ ልጆችና የውይጣውይጥ ነገዶች ናቸው ብሎ ሲናገር በባላባቱና በሲቢንዜ እንዲህ ሲሉ ተናገሩ የውይጣውይጥ ሰው አይታችሁ ሳትገድሉ ብታልፉ ትገደላላችሁ ልጆቻችሁም የምድርን ፍሬ እንዳይበሉ እንዳይጠግቡ ይደረጋሉ ዋታ የምትሏቸው ወይጣውይጦች መጀመሪያ አባቴን ዛሬ እኔን ስለከዱ ከሞት የሚተርፉት ዘራቸው የቀጠሉና የተናቁ ነገዶች ይሆናሉ አሁን ተነሱና በየአሉበት አጥፉአቸው ከነሱ ጋር የበላ ያስተናገዳቸውን ሁሉ አጥፉ ሀብታቸውን ዝረፉ አሉና ብዙ የዋታ ሕዝብ ያለርህራሄ በሀገሩ ባላባትአለቁ በመክተር ጊዜ የዘረፉት ወርቅ ሁሉ ለእጼ ሠርፀ ድንግል ባላባቶች አምጥተው አስረከቡ እነዚህ ወይጣውይጦች ከአቤቶ ገላውዴዎስ ጋር ወደ ደንቢያና ፎገራ ሄደው ስለነበር ያለ እርስት እንዲኖሩ ስለተደረገባቸው ውይጣውይጥ መባላቸው ቀርቶ በአጭር ቃል ወይጦ እየተባሉ በጣና ደንበር እስከ ዛሬ አሉ ወደ ሱማሌ የገቡት ግን ስማቸው ማይቴ ተብለው ግራኝ አህመድ ሀገር ስለሰጣቸው ባለርስት ናቸው በዚሁ በከፋ የነበሩት በየእረሞ ሀገር ተበትነው ስደተኛና ተናቂ ጐሣ ሆነው ይገኛሉ ።

እጼ ሠርፀ ድንግል ይሄን የመሰለ በውይጣውይጥ ጐሣ ቅጣትና ግድያ ያለ እርስትም ሆነው እንዲቀሩ ከአወጁና ከአስፈፀሙ በኋላ በስድስት ወራቸው ወደ ሶዶ ጉራጌ ሀገር መጡ በዚህን ጊዜ የሃድያ ገራድ መጀመሪያ እሳቸው የሾሙትን ሮስገድን ገድሎ ነበርና አሁንም አንገብርም ብሎ የሃድያ ሕዝብ ለጦርነት ተነሳ ነገር ግን በደጃዝማች ተክለጊዮርጊስ የሚመራው የበጌምድር ጦር በንጉሥ ዘርአዮሐንስ የሚመራው የዳሞትና የጐጃም ጦር በአሩሲና በጉራጌ ሀገር መካ

ከል በጉንቱ ዝዋይ ከተማ ጦርነት አድርገው ድል አደረጉና የሃድ
ውን ገራድ ማርከው ለንጉሡ ንጉሥ አቀረቡት እሱም እንደደገ
ሊገብር የጠፋውን ሀገር እንደገና እንዲያለማ ምህረት አድርገውለ
ከደጃዝማች ተክለ ጊዮርጊስ ጋር ሆኖ እንዲገዛ የሃድያን ግዛት ሰጡ
ሆኖም ግን በሌላ ጊዜ ከደጅአዝማች ተ/ጊዮርጊስ ጋር ተጣልቶ በ
ርነት ሞተ ።

አጼ ሠርፀ ድንግልም የሃድያንና የሸዋን የወሊጋንና የከፋ
ሕዝብ ከአስገበሩ በኋላ በወጡ በዓመታቸው ወደ ቆና ከተማቸ
ደንቀዝ ተመለሱ ።

አጼ ሠርፀ ድንግል ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአ
ሁለት አመታቸው 1568 ዓ/ም አርባ ሁለት ሽህ ጦር ይዘው የግራኝ አ
መድን መንግሥት ለማጥፋትና ሕዝቡን ለማስገበር ወደ ሸዋና ወ
ሐረር ጉዞ ጀመሩ እነዚህ የግራኝ አህመድ ቤተሰቦች ከወላስማው
ቢጋብቻ ተቀላቅለው የወላስማውን አሌጋ እነሱ ብቻ ስለሚቆጣ
ሩትና እነሱ ብቻ ስለሚሾሙበት አዳሉንና ኢማውን ሱማሌውን
ጋላውን አደባልቀው ስለሚገዙት በሃይማኖት አንድ አድርገው ስ
በሰቡት ለክርስቲያኑ መንግሥት አንገዛም እያለ በየጊዜው ጦር እ
ነሳ ይዋጋ ጀመር ስለዚህ ነው አጼ ሠርፀ ድንግል በሆገሩ አ
ላይ ያለውን የግራኝ አህመድ ዘር ይማም መሐመድ ኢብን ኢብራ
ምን ለመውጋትና ሀገሩን ለማስገበር ጉዞ የጀመሩ ይማም መሐመድ
የአጼ ሠርፀድንግል ወደሸዋና እሱ ወዳለበት ሐረር መምጣታቸው
ሲሰማ ወንድሙን ቢዘር አህመድ “ ከአውሳ ይገዛ ነበርና የወላ
ማውን ዙፋን እንዲጠብቅ ከአውሳ አስመጥቶ ከሐረር አስቀመ
ውና እራሱ ከብዙ ሺህ ጦር ጋር ከረዩዎች በሚኖሩበት በአዋ
ወንዝ አጠገብ መጥቶ ሰፈረ በዚህን ጊዜ አጼ ሠርፀ ድንግል ሸዋ
እያስገበሩ ኡረር ተራራ ሲደርሱ ይማም መሐመድ በአዋሽ ወን
ዳር እንዳለ ሰሙ በዚህን ጊዜ ብዙ ሕዝብ ከማለቁ በፊት እ
ህን ስጥና የወላስማውንም አሌጋ ልፍቀድልህ ብለው መልእክ
ላኩ እሱ ግን መልስ ሳይሰጥ በዚያው ብዙ ቀን ቆየ ከዚህ መሐ
የወላስማ ዘር ያለበት የአውሳ ገዢ የነበረው የገራድ ጂብሪል ልጅ
ጂሌና ሰዲ አሳአድ በአባታቸው መሞት ቂሞት ነበራቸውና ለአ
ሠርፀ ድንግል መጥተው ገቡ ።

አጼ ሠርፀ ድንግልም ከኡረር እስከ ሙተሃራ ከጭላሎ ተራ
እስከ ይፋት ያለውን ሀገር ለጂሌ ሰጡት ጂሌም ምንጃም በሚ

ለው ሀገር ከተማውን ቀረቀረ መልካ ጂሌ ይባላል ለሲዲ ደግሞ ከአዋሽ እስከ ገላምሶ ሰጡት ሀገሩንም መልካ ሰዲ አሉት ለአሳ አድ ግን ሐረርን ሰጥተውት በሌላ ቀን የመሐመድ ኑር የል ልጅ አሚር ኡስማን ገደለው ይሄን የመሰለ ለወላስማ ዘሮች ማዕረግና ሹመት መነጠቃቸውን የሰማ የእስላሞች ጦር እየከዳ ወደ አጼ ሠርፀ ድንግል ገባ በዚህን ጊዜ ይማም መሐመድ ሸሽቶ ሲመለስ የሲዲ አሽከሮችን የገዛ ጦሩ ገደለው ሱልጣን መንሱርና ገራድ ቢዘር አሀመድ የውስጥ በቀል ነበራቸውና አሮሞች ጋላዎች ሄደው ገድለው ሰቀሏቸው ።

በዚህን ጊዜ የእስላሞች ዋናው መደብ ከሀረር ወደአውሳ ዞረ አውሳውም ከገራድ የሱልጣን መቀመጫ ሆነና ሐረር በሱልጣን ወኪል እየተገዛ ቱርኮች መጥተው እስከሚቆጣጠሩት ቆየ ቱርኮች ከደለደሉት በኋላ ግብጾች መጥተው እስከሚመሩት ድረስ በዚሁ በአውሳ ሱልጣን ወኪል ቆየ በዚህ አይነት አጼ ሠርፀ ድንግል ግማሹን በጦር ግማሹን በስልት ከደለደሉና ሹምሽር ከአደረጉ በኋላ በየቦታው ቤተ ክርስቲያን እያስተከሉ በሰላም ወደበጌምድር ተመለሱ ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ሠርፀ ድንግል ወደበጌምድር ተመልሰው ከቆና ከተማቸው ደንቀዝ ሳሉ በአባታቸው ዘመኑ መንግሥት የከዳውን ባህረ ነጋሺ ይስሐቅን ወደወገኖቹ እንዲመለስና ባለፈው ስህተቱ ይቅር ብለው ከሹመቱ ላይሽሩት ቃል ገብተው እሳቸው እስከአሉበት ድረስ እንዲመጣ መልእክተኞችን ላኩበት ።

ባህር ነጋሺ ይስሐቅ ግን ከቱርኮች ጋር ተስማምተው ጠላት ከንጉሡ ነገሥቱ በኩል ቢመጣ ሊገዙትና ብዙ የጦር መሣሪያና መድፍ ሰጥተውት ስለነበር እንዲህ የሚል መልስ ጻፈላቸው ከእርስዎ ጋር ታርቄ ለመግባት እምነት የለኝም እስዎን ከማመን የቱርክንጉሥኛ ተመን ይበልጠኛል የቱርክ ባሻም እኔን አምኖ በአንድ ሲጋጃ ላይ ማስቀምጠን ቃል ተጋብተናል እነሱም እምጠይቃቸውን ሁሉ ሊያደርጉ እኔም ለነሱ ግዛቴን ከፍየ ሰጥቻቸዋለሁ እንግዲህ ወዲያ ከእስዎና ከሕዝብዎ ጋር እምነትና ፍቅር የለንም ብሎ የመድፍ ጥይትና ደብዳቤውን አሲዞ መልሶ ላካቸው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ሠርፀ ድንግል ለባቻ የተላከላቸውን የመድፍ ጥይት ወደጉንድ ተክለ ሃይማኖት ልከው ለመንኩሳቱና ለካህናቱ ጦርነት ስለምሄድ ፀሎት አድርጉልኝ ብለው ወደትግሬ ጉዞ ጀመሩ ።

ለባህር ነጋሺ ይስሐቅም እንዲህ የሚል መልእክት ላኩባ
እንተ በቱርኮች ብትመካ እኔ ደግሞ በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ተ
ክቼ መጣሁብህ ተዘጋጅተህ ለጦርነት ቆየኝ ብለው ላኩበት ይ
መልእክትና ንጉሡ ነገሥት አጼ ሠርፀ ድንግል መምጣታቸው
የሰሙ በባህር ነጋሺ ይስሐቅ ውስጥ የነበሩት ጦር አዝማቾች ሰ
ወልደ ጻድቅ አስጎዶም በርሄ ያዕቆብ ዘክርስቶስ መጥተው ከ
ሠርፀ ድንግል ጦር ጋር ተደባለቁ የተንቤን ሕዝብና ትግሬ
ንን ግብረ ኢየሱስ እስከ ሠራዊቱ መጣሪያውን እየያዘ መጥቶ ከን
ነገሥቱ ማንባር ጦር ተዋጋ ከተከለ ጊዮርጊስ ጋር ተደባለቀ ።

ባህረ ነጋሺ ይስሐቅም ከደባሩአ ከቱርኮች ጋር ሆኖ ለጦር
ተዘጋጅቶ መጣና እንቴጨው በተባለ ሥፍራ ላይ በህዳር ወር 1571 ዓ.
ጦርነቱ ተጀረ በዚህን ጊዜ ብዙ ህዝብ በሁለቱ በኩል
በኋላ ባህረ ነጋሺ ይስሐቅ ዮሬን ልጅ ሳለ ያሳደጉትና ለአጼ ሠ
ድንግል እንዲላላኩ ሰጥተውት የነበሩት እቴ ወለቱ የሚባሉት ክ
ቶስ ሠምራ መንኩሴው በትህትናቸው የታወቁ ነበሩና እኔ ሄጄ እ
ውና እስታርቀዋለሁ ብለው ወደባህር ነጋሺ ይስሐቅ ሄዱ ባህር ነ
ይስሐቅም የእቴ ወላቱን መምጣት ሲሰማ በክብር ተቀብሎ
ገሬት በኋላ ሲረዱኝ የመጡትን ቱርኮች ከድቼ ልታረቅም
እንቢ ብሎ መንኩሴቱን መለሳቸው እቴ ወለቱም ረግመውት ተ
ለሱና እንቢ እንዳለ ያለውን ሁሉ ለአጼ ሠርፀ ድንግል ተናገሩ ።

አጼ ሠርፀድንግልም በአዝማቹና በአሊቃው እግረኛ
ለብቻ ፈረሰኛውን ለብቻ አድርገው ከአሰለፉ በኋላ በታህሳስ
ጦርነቱ እንዲቀጥል ትእዛዝ አስተላለፉ በዚህ ጊዜ የገራድ ጂብሉ
ልጅ ገራድ ጂሎ ይፋትንና ከረዩን ይገዛ ስለነበር በወላስማ
አልጋ በኩል ሆኖ ሲዋጋ ባህር ነጋሺ ይስሃቅን በጦር ወጋው
ከፈረስ ላይ ጣለው ገራድ ጂሉም በጀግንነት ሲዋጋ ከዋለ በ
ከዚያው ከጦርነቱ ላይ በጥይት ተመትቶ ሞቶ ተገኘ ።

የባህር ነጋሺ ይስሃቅን እራስ የገራድ ጂሎ አሽከር ቆር
ለአጼው አምጥቶ አሳየ አጼ ሠርፀ ድንግልም ለዚሁ ለጂሉ አ
ከር የገራድነት ማዕረግ ሰጥተው ወደባሌ ላኩት በዚሁ እለት የ
ርኮችን አሊቃ ባሻ ከድወርክ ከዳውሮን አቤቶ የናኤል በጦር ወ
ከፈረሱ ላይ ከጣለው በኋላ እራሱን ቆርጦ ለአጼ ሠርፀ ድንግ
አሳይቶ ግድያ ጣለ ።

የባሻ ከድወርከን የባህር ነጋሺ ይስሐቅን መሞት የሰሙ የሁለቱ ወገን ሠራዊት ግማሹ ተማረከ ግማሹ ሸሸ ብዙ መጽሐፍና መሣሪያ ለንጉሡ ነገሥቱ ገባ የምዕዋም ወደብ በአጼ ሠርፀ ድንግል ወታደሮች እጅ ሆነ ።

አጼ ሠርፀ ድንግልም የባህር ነጋሺ ይስሐቅን እራሱና የቱርክ ባሻ ከድወርከ እራስን በሰጋጃ ላይ አስቀምጠው እምላካቸውን እመሰግነው ለታላላቅ ሰዎች ጠርተው አሳዩ ።

ከዚያም የደባሩአን ከተማና ምሽግ የሚጠብቁት ቱርኮች እኛ በእሰዎ ላይ ምንም ጠብና ቂም አንፈጥርም ሰው ይለኩና የንጉሡን የባህር ነጋሺን ሀብትና የቱርኮችን መሣሪያ እናስረክብ ብለው ስለ ላኩ አባ ንዋይ የሚባሉትን የደብረ ቢዘንን መነኩሴ ለጊዜው የደብሩአ አስተዳዳሪ አድርገው ላኳቸውና እቃውን ሁሉ ተረከቡ ።

አጼ ሠርፀ ድንግልም ደብሩአን ከጉብኙና ሹም ሽር ካደረጉ በኋላ ወደአክሱም ተመልሰው መጡ በዚያም ቀሳውስቱ ንቡብሆ እያሉ በክበርና በፀናዕል መኳንንቱ ግማሹ በፈረስ ግማሹ በበቅሎ ሆኖ ምስረ ቃና የሚባለው ጥሩባ እየተነፋ ድብ አንበሳ የሚባለው ነጋሪት እየተመታ የወንዱ ሆታ የሴቱ እልልታ ይሄነው በማይባል ከፍ በአለ ደስታና ክብር አቀባበል አክሱም ገባ የድሉን ሥነሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ ግብር ሲያበሉ ሲሸሙ ሲሸልሙ የወርቅ የብር የልብስ ስጦታ ሲያደርጉ ስነበቱ በዚሁ እለት ለበጌምድር ህዝብ እንዲሁ አሉ የበጌምድር ህዝብ እግሩን ለጠጠር ዶረቱን ለጦር እንዳ ደረገ ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ በበጌምር የለም ግብር በሰማይ የለም ዱር አሉ አጼ ሠርፀድንግል ባህር ነጋሺ ይስሐቅን ድል በአደረጉ በዓመቱ እይሁዶች (ፈላሾች) ጉእሼን የሚባለውን በበ ላያቸው አንግሠው በንጉሡ ነገሥቱ ጼዋ ሠራዊት ላይ አደጋ እየ ጣሉ ወደአክሱም የሚሄደውን መንገደኛ እያጋደሉ የሚባል ወሬ ለአጼ ሠርፀ ድንግል ደረሳቸው አጼ ሠርፀ ድንግልም በ1572 ዓ/ም በታህሳስ ወር ከወይና ደጋ ወደወገራ በሠራዊታቸው ታጅበው ሄዱ ከዚያም እይሁዶች ወደ ተመሸጉበት ራስ ዳሽ ተራራ ተጠጉና ያሉ በትን እንባ ሰፈር አስከብበው በሰላማዊ መንገድ የአይሁዶች አለቃ ጉእሽሚ እጁን እንዲሰጥና ምህረት እንደሚያደርጉለት የነሱን ወገን የሆነ መልእክተኛ ላኩለት ጉእሽሚም እሺ ብሎ ከጥቂቶች ሰዎች ጋር መጥቶ ከአቤቶ ዩናኤል ጋር ተገናኘ በንጉሡነገሥቱ በኩል ሰላም ሆነ ብለው ተደስተው ሳለ አይሁዶች አዘናግተው እቁበ ሚካኤል የሚባለ

ውን ብሀት ወደድ ሌሎችንም ጦር አዝማቾች ገድለው ብዙ መማሪያ ዘር ፈው ሲሄዱ በወሰንጌ አብርሃምና በሴኬው ንጉሥ ተዝካረ ቃል ያዕቆብ በብላቴን ጌታ ሊቀ ንጉማን መቃቢስ የሚታዘዘው የጦር ሠራዊት አባር ገደላቸው ጉአሼም በአቤቶ ዮናኤል እጅ ተያዘና አሁንስ ልምርህም ልገድልህም ሥልጣን አለኝ ወገኖችህም ሆነ አንተ ክርስ ቲያን ልትሆን ቃል ግባልኝና ወደእጼ ይዤህ ልቅረብና ላስታርቅህ አለው ጉአሼም ከንጉሡ ነገሥቱ ፊት ከምቀብርና ክርስቲያን ከም ሆን በዚህ ጨለማ አለም ከምኖርና የወገኔን ሰድብ ከምሰማ ሞ ትን እመርጣለሁ ዮናኤልም እራስህ ከመረጥከው ሞትን ግደለው ከዚ ያም ከተራራው ላይ ያሉት አይሁዶች ብዙ ጦር በናዳፈጁ የንጉሡ ነገሥቱን ወታደሮችም በመድፍ አሻቅበው እየተኮሱ ብዙ አይሁዶች ገደሉ ወታደሮቹም እራሳቸው የተኮሱት የመድፍጥይት ገደሉን ገለ እራሳቸውን ከአሉበት ቀበራቸው ነገር ግን በሠራዊት ብዛትሁሉም በንዴት ተነስቶ ግማሹ በጎመድ ግሹማ በአግሩ እየሮጠ ወደተራራው ወጣና በሰይፍበጉራዴ ተጋደሉ የአሁዶች ነቢይና ዋና ዋና አለቆች እንማረክም ብለው ገደል እራሳቸው ገብተው ሞቱ ።

በዚህን ጊዜ በንጉሡ ነገሥቱ በኩል የሞቱት 9 ሺህ ወታደሮች በአይሁዶች በኩል ከአሰራምስት ሺህ በላይ ነበሩ ። የተማረኩት ሴቶ ችና ሕጻናቶች ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ነበሩ አጼ ሠርፀ ድንግል ምንም አይሁዶች ቢበድሏቸውና ቢወጉቸው የአይሁድ ዘር እንዲ ጠፋ ስለአልፈለጉ እራሳቸው በሚኖሩበት አጠገብ በደንብያ ውስጥ የሚባል ጼዋ ጦር እንስተው እሠፈሩባቸው ባለእርስትም አደረጓ ቸው ሌሎች ግን ብረት መቀጥቀጥ ማረሻና ማጭድ መሥራት የሚ ችሉትን በቆላ ወገራ በወልቃይት በፀለምት በአንዳ ቤት በበለሳ እየላኩ ሀገር እንዲሰጣቸውና ለወታደራቸው ጦር ሾተል ማረሻ ማጭድ እንዲሰሩ ፈቀዱላቸው ።

አፄ ሠርፀ ድንግል ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከቤጌምድር ወደእናሪያ ለመሄድ ተነሱ ከዚያም በጉዞ ላይ በወለጋና በጂማ በከምባታ የከፋ ውን የሸፈተውን ባላባት አልገብርም ያለውን ወታደራቸውን እየላኩ ከአስቀጡና ከአስገበሩ በኋላ እናሪያ ገቡ እንርያ እንደደረሱ የን ጉሥ መኪተር ልጅ ሴቢንሂ ሞቶ ልጁ ባንዶች በአባቱ ወንበር ላይ ተቀምጦ ነበርና የንጉሡ ነገሥቱን መምጣት ሰምቶ ብዙ ሰንጋና ልዩ ልዩ የወርቅ ገፀበረከት ይዞ መጥቶ ተገናኛቸው እሳ ውም የህዝቡን አቀባበል ስርዓት ተመልክተው ክርስትና አስነሱ ተው ስሙን ዘማርያም አስኝተው የንጉሥነት ማዕረግ ሰጡት በዚያ

ዕለት ለብዙ ባላባቶች ሹልማትና አዲስ የማዕረግ ስም እየሰጡ አስደ ሰቷቸው በቦስ የጊወርጊስን ቤት አሰርተው ባላባቱንም ጊዮርጊስ ብለው ወደጁባ ሄዱ ከጁባም ብዙ ቀን ከቆዩ በኋላ  በየቦታው  ቤተክርስቲያን እየተከሉ እራሳቸው የሀገሩን ቀሲስ ብለው ሰይመው የማር(ቤትክ) ተከሉ በዚያም ረዋንጃ የሚባሉትን አራት ሰዎች ሀገር እንዲያለሙ ትተው ወደካሳንትን ሄዱ በዚያም ብዙ ካህናት ደልድለው ሕዝቡን ከአረመኔነት ወደክርስቲያንነት እንዲመለሱ አዘዙ ከከሳን ጉን ወደ ዘንዚባራ ደርሰው በድል አድራጊነት ውቅያኖስን አይተው የዛይላን ሱልጣን አስገብረው በብዙ ድካምና ችግር በሀረር አድርገው ያጋጠማቸውን ልዩ ጉጣ በጦር ብዛት እያሳመኑ በሶስት አመታቸው ተመልሰው በጊምድር ገቡ ።

በዚህን ጊዜ የአጼ ሠርፀ ድንግልን መራቅ የሰማ ወልደ ኢሱም የሚባለው የባህር ነጋሺ ይስሐቅ የእህት ልጅ በቱርኮችና በባህር ነጋሺ ይስሐቅ ሞት ቁጭት በነበራቸው ወገኖቹ ተረድቶ የባህር ነጋ ሺነቱን ስልጣን ይዞ ከንጉሠ ነገሥቱ የተሾመውን ትግሬ መኮንን ዳህራቆትን የሃማሴኑን ከንቲባ አንታወን ሠራዊት በጦርነት ድል አድ ርጐ አባረራቸው ብዙ መኳንንት ገደለ የሚባል ወሬ ሲሰሙ የጪዋ ወታደር በየአለበት እንዲመጣና ለጦርነት እንዲዘጋጁ ብለው ከአሳ ወጁ በኋላ የበላይ አዛዥ የእክሱምን ንቡረእድ ቶማስና ወሰንጊ መሐመድ የጋላን (የኦሮሞን) ጦር ይዞ ማባር ቀደም እንዲዘምቱ አደ ረጉ በዚህን ጊዜ ቱርኮችና የባህር ነጋሺ ወልደኢሲም ወታደር እስከ መረብ ድረስመጥተው ነበርና በእቁበሚካኤል የሚመራው የአማራ ወታደር ሬጇቸው የሚባል ወሬ ለንጉሠ. ነገሥቱ ሲደርሳቸው ተደሰ ተው የባህር ነጋሺ ማዕረግ ሰጥተው የራስ ወርቁን ላኩለት ነገር ግን አጼ ሠርፀ ድንግል ቱርኮች ከአርኪቶ (ደሆኖ) ከጌራራ ደሴቶች ሬድ መው ካልጠፉ ሰላም አለማግኘታቸውን ተረድተው በ፲ህ 581 ዓ/ም ካሉበት ድረስ ሄደው ተዋግተው ድል አድርገው የተማረኩትን እጅ እግራቸውን ቆርጠው እስከነፍሳቸው ባህር ውስጥ ጣሏቸው ሆኖም ግን ምንም ከየብስ ያለው የቱርክ ወታደር ቢያልቅ በመርከብና በጀልባ የሸሸው ዳህላክ ደሴት ውስጥ ያለው ወታደር እያደገ ሊሊት ብዙ የንጉሠ ነገሥቱን ወታደር ገደለ በዚህን ጊዜ በአጼው በኩል ያለው ወታደር ወደ ዳህላክ ሄዶ እንዳይወጋ መርከብና ጀልባ ስላ ለው ከዚህ ሌላ ደግሞ ስንቱ ሆነበት ።

ባህረነጋሺ ወልደኤሉም አዘንግቶ ብዙ ወታደር ከገደለ በኋላ የታወቀው ጀግና ባህር ነጋሺ እቁበ ሚካኤል አባሮ ጦርነት ገጠመውና ወልደኢሱምን ገደለው ከዚያም እራሱን ቆርጦ አብረ

ውት የነበሩትን ቁርኮች ሁሉ እራሳቸውን ቆርጦ በእንጨት ላይ
ሰቅሎ በወታደሩ ታጅቦ አጼ ሠርፀ ድንግል ካሉበት ድረስ ሄደ
እሱም በደረሰ ጊዜ አጼው ነጋሪት አስመቱበት መለከት አስነፋ
ለትከዚያም የወርቅ ሽልማት በአንገቱ አጠለቁለት ለራሱ ክብር የማ
ሰቀል ሰንደቅ ዓላማ ሰጡት በዚህን ጊዜ የሃማሴን ምድር በንጉሠ
ነገሥቱ እጅ ገባ ምዕዋን አርኪቆ ላይ ግን ነዋሪ ወታደ
ናዋ ስላልተቻለ ለቁርኮች በሩ ክፍት ሆነላቸው ይሄውም ወታደ
ማስቀመጥ ያልተቻለበት ለወታደር የምግብማመላለሻ ከዚያው ነዋ
ሆኖ ለመኖር በርሃ ስለሆነ ነው ።

አጼ ሠርፀ ድንግል እንደ አባቶቻቸው ከሙጭ መንግሥት
ጋር ወዳጅነት ጀምረው ነበር ይሄውም በዘመን መንግሥታቸውየፖ
ርቱጋል መንግሥት ወድቆ የኢስፖኝ መንግሥት ተነስቶና ታው
ነበርና ለኢስፖኝ ንጉሥ ፊልጶስ ደብዳቤና ገፀበረከት ልከውለ
ነበር ደብዳቤው የሚለው በኢትዮጵያ እና በኢስፓኝ መካከል የጠበ
ወዳጅነት አድርገን ሕዝቡን የብረታ ብረት ሥራ የሚያስተምሩል
ላክልኝ የሚል ነበር ነገር ግን ደብዳቤው ዘግይቶ ስለደረሰና እሳ
ውም ስለሞቱ ተከታዩ ንጉሠ ነገሥት ጉዳዩን ሊያስብበት አልቻ
ለም ቤታሪክነገሥት በኩል ደግሞ ግራኝ አህመድ በየደብሩና በየ
ዳሙ ያለውን መጽሐፍት አቃጥሎት ስለነበር እንደገና በአጼ ሠር
ድንግል ትእዛዝ በመሪራስ ሰብስቤ አዘጋጅነት በአንዳቤት የተቀ
ረውና በአንዳንድ ዋሻ ውስጥ የተደበቀው የኢትዮጵያ ነገሥታት
ታሪክ ከአዳም እስከ ሠርፀ ድንግል ዘመን መንግሥት ተጻፈ እንደዚ
ሁም የቃሬድ የድጓ ምልክት መዝሙረክርስቶስ መጽሐፈ ጠቢባ
ፍትሃ ነገሥት በአባቶቻቸው ቋንቋ በግእዝ ተጻፈ አጼ ሠርፀ ድንግል
በጣና ሐይቅ በዘጌ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ሲያሰሩና ከአጼልብነድ
ንግል ዘመን መንግሥት ጀምሮ የዘጌትን ባህታዊ አባ ቡና የሚባለ
ትን ጉብኝተው ከዚያም ወደመንደባ ገዳም ሄደው በአጼ ልብነ ድን
ግል ዘመን መንግሥት በጦርነት የቆሰሉት የናኦድ ሞገሳ ወንድማ
ፋንኤል አጽማቸውን ወደ ደቅ እስጢፋኖስ ገዳም ወስደው በክብር
እስቀመጧቸው የግራኝ ሙሉ ታሪክም የተገኘ ከእሳቸው እረድ ከሆ
ነው መነኩሴ ነው ከዚህ በኋላ አጼ ሠርፀ ድንግል በሆነሩ የተቅማጥ
በሽታ ገብቶ ነበርና በዚሁ ታመው በተወለዱ በአርባ ስድስት አመታቸው
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በሰላሳ አራት በሺህ አምስት
መቶ ዘጠና ዓ/ም ላይ አረፉ በዚህን ጊዜ በትልቅ ሐዘንና ልቅሶ
በክብር ራማ ደሴት ወስደው ቀበሯቸው ።

አጼ ሠርፀ ድንግል በሞቱ ጊዜ በዙፋናቸው የሚቀመጥና መን ግሥታቸውን የሚወርስ ከባለቤታቸው ከእቴጌ ማርያም ስና ሴቶች እንጅ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው ነገር ግን እመቤት ሃረገ ከሚባሉ ያዕቆብ የሚባል ወንድ ልጅ ስለነበራቸውና እቴጌ ማርያም ስና ያሳደጉት ስለነበር የልጃቻቸው ባሎች መሬራስ አትናስዮስ የበጌ ምድር ገገር ራስ ክፍለ ዋህድ የትግሬ ገገር ደጃች ዘሥላሴ የእናሪያ ገገርን መክረው በመሬራስ አትናስዮስ ሞግዚትንት የሰባቱን አመት ልጅ ያዕቆብን ስመ መንግሥታቸውን መላክ ጋዲ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው 1590 ደንቀዝ ኢየሱስ አነገሷቸው በዚህን ጊዜ የአጼ ሚናስን ልጅ አቤቶ ዘድንግልን አስረው ደቀ እስጢፋ አጠ ገብ ከሚገኘው ከጣና ደሴት ዘሩባ ወስደው አስቀመጣቸው የአጸ ልብነድንግል ልጅ የአቤቶ ያዕቆብ የልጅ ልጅ የገራም ፋሲልን ልጅ ሱስንዮስንም ይፈሩ ነበርና ይዘው ለማሰር ሲዘጋጁ ሰምተው ወደአ ያታቸው ሀገር ሸዋ ሄደው ተቀመጡ ።

እቴጌ ማርያም ስና መሬራስ አትናስዮስ ራስ ክፍለ ዋህድ ደጃች ዘሥላሴ ሰባት ዓመት ሙሉ ሀገሩን ተከፋፍለው ይገዙት ጀመር ።

መላከጋዲ የተባሉት አጼ ያዕቆብ የአስራ አራት ዓመት ልጅ ሲሆኑ ልዘዛችሁ ብለው ሹምሽር ማድረግ ጀመሩ ደጃች ዘሥላሴን ወደእናሪያ ሄዶ እንዲቀመጥ አደረጉ በዚህን ጊዜ እቴጌ ማርያም ስናና ሌሎቹም ባለሥልጣኖች ንጉሠነገሥቱ አብደዋል ብለው በደ ንቀዝ ከተማ አስወሩባቸውና በእብደት ምክንያት ለደጃች ዘሥላሴ በግዞት ውስጥ አድርጉ እንዲጠብቃቸው ላኩለት ።

በዚህን ጊዜ ዘድንግልን እቴጌ ማርያም ሥና መሬራስ አትናስ ዮስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለንጉሥ እንደማይገዛቸው አውቀው ከተጋ ዞበት ከጣና ሐይቅ ደሴት ዘሩባ ከሚባለው ዘድንግልን አውጥተው ስመመንግሥታቸውን አጥናፍ ሰገድ ንጉሠነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው በ1597 ዓ.ም አነገሷቸው ።

አጼ ዘድንግልም አፅናፍ ሰገድ ተብለው በነገሡ ጊዜ ወደ እስ ፓኝ ንጉሥ 3ኛው ፊልጶስ የወዳጅነት ደብዳቤ በሚሲዮኖች ልከው ነበር ሚሲዮናችም ለማንኛውም የኢስፓኝ መንግሥት ይረዳወታል እያሉ ስለሚነግሯቸው በጣም ይደሰቱና ሀገራቸውን በእጅሥራና በእውቀት ለማበልፀግ ይመኙ ነበር ። ስለዚህ ካቶሊኮችና ኦርቶዶ ክሶች በሃይማኖት ክርክር ሲያደርጉ ወደካቶሊኮች ሃሳባቸውን ሲያ ደርጉ ይታዩ ነበር ።

በዚህን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ከጦር አለቃው ከደጃዝማች ለይ ማርያም ጋር ሆነው ከኦርቶዶክስ ወደካቶሊክ ሃይማኖት ዞረዋ እየተባሉ በቀሳውስቱና በመነኩሳት ይወራ ጀመር ከእስክንድር ተመርጠው የመጡት ጳጳስ አባ ጴጥሮስ ለአፅናፍ ሰገድ የሚታ ዘውንና የሚገዛውን ገዝቻለሁ ብለው መኳንንቱንና ህዝቡን አ ገዙ ።

ይሄን ውግዘትና በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ህዝቡ ማመጹን የሰማ ደጃች ዘሰላሴ አጼ ያዕቆብን እንደገና ከዙፋን ለማውጣት ራ ዘሥላሴ ተብለው የጉጃምንና የወሊጋን ህዝብ በንጉሠ ነገሥ በአጼ ዘድንግል ላይ ለጦርነት ተነሳ ።

በዚህን ጊዜ አጼ ዘድንግልን የጠላ መኳንንት ወደራስ ዘሥላ ዞረ ነገር ግን በደጃዝማች ላእከ ማርያም የሚታዘዘው ወታደርና ሁለት መቶ ሰባ የሚሆኑ ሚሲዮኖች የኢጣሊያና የፖርቱጋል የእስፓኝ ተወላጆች ብረት የያዙና ያልያዙት ሁሉ ተዋግተን እን ሞታለን ብለው በአጼው በኩል ተሰለፉ ።

ከዚህ በኋላ ደንብያ ላይ ባርጫ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ጦር ነት ጀመሩና በንጉሠነገሥቱ በኩል ያለው ወታደር እየከዳ ወደ ራስ ዘሥላሴ ስለዞረ በነገሡ በእመታቸው ንጉሠነገሥቱ ድል ሆነና በጦር ተወግተው ሞቱ እሬሳቸውን እንዳትቀብሩ ስላሉ በሜዳ ወድቆ ቀረ ነገር ግን ሴሊት ባላገሮች በድብቅ ቀብረዋቸው ኖሮ በወዳጃቸው በሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በክብር ከተቀበሩት አስወጥተው ጣና ውስጥ ደሴት ዶጋ አስቀበሯቸው ።

ራስ ዘሥላሴም አጼ ያዕቆብን ካሉበት ከኢናሪያ ግዛት ውስጥ አስወጥተው ሁለተኛ ከዙፋን አስቀመጧቸው ።

ነገር ግን አቤቶ ሱስንዮስ የዘድንግልን መሞት በሰሙ ጊዜ አብረው ያደጉና በጣም ወዳጅ ስለነበሩ በሸዋ ላይ አጉበር እስ ደርገው አስለቀሱላቸው ከዚያም የሸዋን ጦር ሰብስበው ወደ ዋድላ ሄዱና መሬራስ አትናስዩስን እንዲመጣ ላኩበትና እሱም ጥሪውን አክብሮ ካሉበት ድረስ መጥቶ ተገናኘ ። ራስ ዘሥላሴ የአቤቶ ሱስንዮስን መምጣትና ለጦርነት መዘጋጀት ሰምቶ ከጳጳሱ ከአባ ጴጥሮስ ጋር በሱስንዮስ ላይ የሚያደርገውን ጦርነት ጋር ይማከ ሩና ይዘጋጁ ጀመር ።

ከዚህ በኋላ የአጼ ያዕቆብ ጦር በራስ ዘሥላሴ ከአቤቶ ፋሲል ልጅ ከሱስንዮስ ጦር ጋር ተጋጥሞ ይዋጋ ጀመር ነገር ግን በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ አጼ ያዕቆብ በተወለዱ በአስራ ስድስት አመታቸው ስለሞቱ ራስ ዘሥላሴ ሸሽተው ሊባን ጣባኖላዊ ናዝሬት ሄዱ ከዚያም የሱስንዮስ እናት ሃመልማላዊት ሊበን ጣባኖላዊ ናዝሬት ነበረች ። ከእስዋ ስለተወለዱ በሌላ ቀን ልካ አስታረቀቻቸው በዚሁ በጨዋህ ጦርነት የውጭ ሃገር ተወላጆች በዘድንግል መሞት ጊዜት የነበሩቸው ከመራሪስ አትናስዮስ ጋር ወደአቤቶ ሱስንዮስ ገብተው ነበርና ጳጳሱን አባ ጴጥሮስን እንድ የካቶሊክ ሰው በጥይት ተከሶ ገደላቸው ።

የአጼ ያዕቆብ ልጅ ኒጋክርስቶስ ከትንሽ ወታደር ጋር በኑብያ አድርጎ ወደካይሮን ሄደ ከካይሮንም ወደ ኢየሩሳሌም ተሻገር የኢትዮጵያን ገዳም ከጉበኘ በኋላ በናዝሬት በሚገኘው በካቶሊኮች ገዳም ከኦርቶዶክስ ወደካቶሊክ ሃይማኖት እንደዞረ በግልፅ ተናገረ ።

## ምዕራፍ ሃያ ሶስት

### የአጼ ሱስንዮስና የልጃቸው የፋሲለደስ ፋሲል ዘመነ መንግሥት

አጼ ልብነ ድንግል እቴጌ ያዕቆብ ከዶቢያ ዶሎ ባላባት ከንግሥት እቴብ በጋርንታቸው ገራም የተባሉትን እቴቴ ፋሲልን እቴቴ ሥማዎታልን እቴቴ ተገዘካር /ተገዘካረ ቃል/ ወይዘሮ ወለተ ማርያምን ወለዱ ንግሥት እቴብ የወሰን ሰገድ ልጅ ናቸው ። እቴቴ ገራም ፋሲል በአጼ ሠርፀ ድንግል ቤተመንግሥት በደንቀዝ ውስጥ መጀመሪያ የመራራስን ቀጥለው የራስን ስልጣን ይዘው እንደራሴ ሆነው ያገዙ ነበር ። ነገር ግን ከእቴጌ ማርያም ሥና ጋር





የፋሲል ግንብ

በነገር ሆነ በምስጢር ስለሚረዳዱ ዋኝ መስለው ስለሚታዩ ፋሲል ማለቱን ጥለው ገሩም ያኗቸው ማርያም ሰና ናቸው ይባላል ።

እንደዚህም ሆኖ ራስ ገሩም ፋሲል ከእለታት አንድ ቀን ለእቴጌ ማርያም ሰና ኩሶ ታዋኝ ብለው ቢነግሯቸው እቴጌይቱም ምንስ ዋኝ ገሩም ቢሆን የአጼ ዘር አይደለንም ! ብለው ነብያንም ይገዛ ስለነበር አከብረው የኮሰኔ ተወላጅ አባት የፖርቱጋል ወታደር የነበረ በገላውዲዎስ ጊዜ ከብር ተሰጥቶት የሚኖር የነበረ ከዚሁ ወታደር የተወለደች ሃመልማላዊት የምትባል ቆንጆ ልጅ ከእቴጌይቱ እልፍኝ ትኖር ነበርና ኩሶ አጠጥተው ብለው ወደገሩም ፋሲል ላኳት ሃመልማላዊት እጅ ብላ ከሚኖሩበት አዳራሽ ሄዳ ሳለ ከቁንጅናዋ ማማር የተነሳ በጣም ፍቅር ይዟቸው ነበርና እንዳፈቀሯዋት ነገሯዋት እሱዋም ማፍቀሩዋን ገልጻ ስለ ነገሯቸው ሁለቱም በምስጢር ፍቃዳቸውን ፈጸሙ ።

በዚሁ እለት ሱስንዮስ ተፀንሱ ከሶስት ወር በኋላ እቴጌ ማርያም ሰና አንቺ ሃመልማለወርቅ የፅንስ መልክ እየሁብሽ ነገሩ ምንድነው ብለው ቢጠይቋት መገለፁ እንደማይቀር አውቃ ከገሩም ፋሲል እንደፀነሰች ነገረቻቸው እቴጌይቱም ከቤትሽ የሚወለድ ልጅ መንግሥትዎን ይወርሳል እየተባለ ትንቢት ተነግሯቸው ነበርና እቴጌይቱም ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው በፋሲል ተቆጥተው ሲያስፈልጉት ፋሲልም አስቀድሞ ነገሩን ስለሰሙ ፈርቀው ወደ አያታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል ሃገር ጉጃም ሄዱ

ራስ ገሩም ፋሲልም ከዘመዶቻቸው ጋር ተሳልከው ሃመልማላዊትን አፍቅረው ነበርና አስርቀው /ጉጃም/ ወደአልሰበት ደረቤ የበቅላ ከሚባለው ሃገር ወሰዱት ከዚያም በኋላ ይባባ ከተባለው ታምሬ ከሚባለው ሃገር ላይ ሱስንዮስ ተወለዱ ።

እቴጌ ማርያም ሰናም ከባለቤታቸው ከአጼ ሠርፀድንግል ዘር ሁሉን ወጥቶ ለሌላ እንዳይሆን ብለው ከአጼ ሠርፀ ድንግል እቁባቶች አመቤት ሃረግዋ ከሚባሉት የተወለደውን በተወለደ በአመቱ አምጥተው ከቤታቸው ያሳድጉትና ዙፋን እንዲወርስ ያደረጉ በዚሁ ሱስንዮስ በመወለዳቸው የተነሳ ነበር ዳሩ ግን እግዚአብሔር ያለው ስለማይቀር ሱስንዮስ አድገና አጼ ያዕቆብን ድል አድርገው በካቶሊኮችና በጉጃም ባላባት እየተረዱ ጠላታቸውን የሆነውን ሁሉ ከገደሉ በኋላ ጉጃም ቀራንዮ መድሃኒአለም ቤተ ክርስቲያን ስመ መንግሥታቸውን ሥልጣን ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው

በአንድ ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ዓ.ም -1598 ዓ.ም ላይ
ነገሡ ።

አጼ ሱስንዮስ ለጊዜው ከእቴጌ ማርያም ሰናና ከቤተመንግሥት መኳንንትና ካህናት ጋር በጸኑ መጥት ተቀይመዋቸው ስለነበር ወደደንቀዝ ሳይሄዱ በዚያው ጉጃም ውስጥ አጠገብ በሚገኘው በዳሞት በደብረ መዊእ አዴት መድኃኒዓለም ቤተመንግሥት አሠሩ የቤተ መንግሥቱ ፍርስራሽ እስከዛሬ አለ እንደሆነ ቢታይበት ቢታ ስብበት በጣም ጥሩ ነበር ።

እንደዚህም ሆኖ አጼ ሱስንዮስ ከደብረ መዊእ አዴት መድኃኒ ዓለም ወደደንቀዝ ሄደው ከአጼ ሠርፀ ድንግል ባለቤት ከማርያም ሰና ጋር ባለፈው ጥሩ ምህረት ያደረጉልኝ ብለው ታረቋቸው እቴጌ ማርያም ሰናም አጼ ያዕቆብን ተጣግተህ መንግሥቱን መያዝህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ነው ። ከመወለድህ በፊት ቤት የተነገረልህ ስለሆነ በመንግሥትህ አልደነቅም በእግዚአብሔር ሥራና ፍቃድ ግን ሲደነቅና እሱ ያለው የሚደቀር በመሆኑ ላመ ግንው ይገባል ።

ስለዚህ ከልቤ ታርቄሀለሁ አንተም ቢሆን እኔ ያዕቆብ በቤተ መንግሥቱ ያደከ ነህ ስለዚህ የወንድምህን የያዕቆብን አገልጋዮች መኳንንቶች በቂም ምክንያት ከማሰረጋቸው እንዳትሸሬቸው ከእርሱ ታቸውም እንዲቀትትኳቸው የእኔንም በደብረምጥማቅና በአሥራዑት በማ ሀደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስም እንድታስቀብረኝ ቃል ግባ ልኝ ብለው ጠየቁቸው ።

አጼ ሱስንዮስም ያሉት ሁሉ እፈጽማለሁ ብለው ቃል ገቡላ ቸው

አጼ ሱስንዮስ ከደንቀዝ ወደ ጥና ቤተ መንግሥታቸው አዴት መድኃኒዓለም እየተመለሱ በሸዋና በወሎ የነበሩ ኦሮሞች በጦር ነት እየረዱ ደስ አሰኝተዋቸው ስለነበር በዳሞት በበሊያ በወንበርማ በባንጃ አጼ ገላውዴዎስ ተምተው ለጸዋ ወታደር ሰጥተውት የነበ ረውን እርስት ቀምተው እንደገና ሰጧቸው በኮሰኔ የሚገኘውንም የቅማንት ሀገር ለነዚሁ ለረዳቸው ኦሮሞዎች (ጋሎች) ሰጧቸው ለአባቶቻቸው ልጆች የመሬሩስን ሥራ አዛዥ መልካክርስቶስ ብላ ቴን አፈክርስቶስ ብላቴን ጌታ ሳህለክርስቶስ ራስ የማነክርስቶስ ብለው በትልቅ ቦታ በክብር አስቀመጧቸው ።

የቤተክህነቱ ባለሥልጣንና መነኮሳት በጳጳሱ በአባ ጴጥሮስ መሞትና ለአጼ ዘድንግል እረዳት ሆነው ጠላታቸውን በማጥፋታቸው ቂም አድርጉባቸው ውስጥ ውስጡን እያደመና ጠላት እንደማያስ ለባቸው አውቀው በእናታቸው ታላቅ ወንድም ፔድሮ ፓኤዝ እጅ ለአ በፖፕና ለሮማ ቤታዊ ንጉሥ ለዶን ፊሊጶስና ለሮማው ሊቀ ጳጳስ ሲውሱስ ጅኛ ይብላሉ ላኩ ይብላሊውም የሚለው በሃይማኖትና በወ ታደር ስርዓት አንድ ዓይነት አመራሪ እንዲኖረን የሚል ነበር።

ፔድሮ ፓኤዝም የተላከበትን ጉዳይ ከፈጸመና ከአስረዳ በኋላ ከሌሎች መልእክተኛ ጋር በሰላም ተመልሶ መጣ።

አጼ ሱስንዮስ ቤተክርስቲያን እየሰሩ ይባሉ ነበሩና መልእክተኛ ቸውን ፔድሮ ፓኤዝን በፍቅርና በክብር ተቀብለው ከሲገኝ ንጉ ሥና ከጳጳሱ የተላከላቸውን ደብዳቤ ተረክበው ከአስነበቡና ነገሩን ከተረዱት በኋላ ቢታው ተስማምተው አብረው ለመጡት ሚሲዮኖች በትግሬ ፍሬሞና በደንቢያ ጎርጎራ በፋርጋ ደብረታቦር የሚባሉ ስፍራ ቀርቀረው ቤተክርስቲያንም ተከለው እንዲሰሩባቸው የካቶሊክን ሃይማኖት እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ሕዝቡን ፈቀደላቸው።

አጼ ሱስንዮስ ካቶሊኮች በሰፈሩበት ያለውን መንደር ሁሉ ከተማ እንዲሆን የፈቀዱ እራሳቸው ስለሆነ የደብረታቦር ከተማ በኋላቸው ጊዜ ከሌሎች ከኢትዮጵያ ከተሞች በሌሎ ይታይ ነበር ይባላ ከተማ የተወለዱበትም ቢሆን ሁለተኛ ነው በዚያን ጊዜ ከሥራ ፓኤዝ ጋር የተላከው ማንዴዝ አልፎንስ አሰራ ሁለት ጳጳሳት በሥሩ ሹም ሃያ አራት ቄሶች በየከተማው በየመንደሩ እስጋርቶ የካቶሊክን ሃይ ማኖት ያስተምሩና በካቶሊክ እምነት ይጠምቁ ጀመር።

ይህ የካቶሊክ ሃይማኖት አንድ ባህርይ የሚለውን ተዋህዶችን የሚቃወምበት ዋና ቃል ይህ ነው።

ክርስቶስ በሰውነቱ ተራበ ተጠማ ተሰቀለ በተሰቀለም ቀን ከሞት የተነሳ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ብሎ አለቀሰ ግን በአምላክነቱ መታገን አነሳ ለምለን እንደ ውሃን ወይን አደረገ ከመቃብር በሶስተኛው ቀን ተነሳ ስለዚህ ሁለት የሰውና የአምላክ የተለ ያዩ ባህርዮች አሉት ሲሉ ተዋህዶች ይህም ነገር ግን አጼ ሱሰን ዮስ ከተዋህዶች ይልቅ የካቶሊኮችን ቃል በማመኑ በሌላ በኩልም የካቶሊክ ሃገሮች እርዳታ እንደሚያገኙ ተማምነው እራ ሳቸውና ቤተሰባቸውን ወደካቶሊክ መቀበር አንስ ከሆነና

ህዝቡን በግድ በካቶሊክ ቄሶች እንዲጠመቅ አርብና ረቡ
መጾም ቀርቶ ቅዳሜ እንዲጾም የቅዳሜው ሰንበት እንዲሻር የካቶ
ሊክ ሥርዓት ፈጽሞ እንዲከበር ሲሉ አወጁ ሆኖ ግን በተዋህዶ
ሃይማኖት የፀናው ሊቃውንትና መነኮሳት ቀሳውስት ካህናት ለ
ሃይማኖታችን እንሞታለን ብለው በአጼ ሱስንዮስ ላይ አመፁ ሽፈ
አጼ ሱስንዮስ ህዝቡ በካህናቱ አድማ እንነሳለን ማለቱን ሲሰ
ጦር ክተት ብለው አመፀው የተዋህዶ ሃይማኖት መሪዎችን ገደ
በጉብያ ላይ ሰቀሉ ብዙዎችንም ምላሳቸውን ካስቆረጡ በኋላ ነ
አጼ ሱስንዮስ ከእዲት መ/ማ/ ወደ በጌምድር ተጉዘው ደንበያ ወ
ከሚባል ስፍራ ላይ ደርሰው በጳጳሱ በአባ ስምኦንና በሊቀ ሥል
ጣናት አባ አፈክርስቶስ በአባ ዮሐኖስና በአባ ዲዮስቆሮስ የሚመ
ራው የተዋህዶ ሃይማኖቶ ተቆርቋሪ ህዝብ ጦርነት ገጥሞ ብ
ሺህ የሚሆን በሰማዕትነት ሞተ አጼ ሱስንዮስም በዚሁ ጦርነት
የተዋጉትንና ድል ያደረጉትን የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች ደ
ቀዝ ጄደው ማዕረግ እየሰጡ አስደሰቷቸው ርእሰ መራ—መራሕ
ሲባል የነበረውን የአርሞ ተወላጅ አባኘ ጢኖ በሉት እንጂ መ
ራስ አትበሉት አሉ ይባላል። አባኘ ጢኖም ስለአጼ ሱስንዮስ ታ
እከብርና ጸድቅ አድርጐ ፅፎላቸዋል። በአጼ ሱስንዮስ ዘመን መ
ግሥት ብዙ የተዋህዶ ሃይማኖት ካህናት እስከሊተሰባቸው ተሰደዱ
በየዋሻው ተደብቀው ለአሳራ ሰባት አመት ኖሩ በሃገሩም በረቱ
እሌቱት ሆነ በሺታም በሃገሩ ውስጥ ብዙ ህዝብ ጨረሰ።

አጼ ሱስንዮስ በንግሥ በሃያ ሰባተኛው ዓመት ላይ ታመው አን
ደበታቸው ተዘጋ በዚህን ጊዜ በብዙ የአውሮፓ ቄሶች ቢጠመቁ ሊድ
ቀርቶ እጅ እግራቸው ሽባ ሆነ ጆሮአቸው ደንቆረ በዚህን ጊ
ፋሲላደስ የሚባል ልጅ ነበራቸውና እግዚአብሄር ይሆን መሰ
ያመጣባሎቸው ሃይማኖታቸውን ቀይረው የፈሳቸውን ህዝብ ስ
ገደሉ ምላስ ስላስቆረጡ ይሆናል ብሎ በየገዳማቱ በየአድባራቱ
ለሚገኙት መነኮሳትና ካህናት በፀሎታችሁ በሃዘናችሁ አባቴን አድ
ንልኝ እኔም ያጣችሁትን ሁሉ አደርጋለሁ ብሎ አዋጅና ስንደ ላ

በዚህን ጊዜ የጐንደር አበምኔቱ የነበሩ አባ እምደ ሥላሴ በ
ቀሊክና በተዋህዶ መካከል በተደረገው ጦርነት ተሰደው በጳራብርድ
ይኖሩ ነበርና ይሆን የሱስንዮስን መታመም የፋሲለደስን ጥያቄ ሲሰ
ከአባታቸው ተነስተው አጼ ሱስንዮስ ደንቀዝ ነበሩና ወደደንቀዝ
ሄዱ አቤቱ ፋሲለደስም የአባ እምደ ስላሴን መምጣት ሲሰማ ከቤተ
ቤት ድረስ ሄዶ በክብር እንጋግሮ አባቱን በፀሎት ሱባኤ እግዚአብሄ

ለምንው ሊድኑለት እሱም በተዋህዶ ሃይማኖት ተመልሶ የተሰደዱትን ከሀገትና መንኩሳት ወደየቤታቸው ሊመልስ ቃል ገብቶ ተለያዩ የተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች እምነት ይህ ነው ።

1ኛ. በመጀመሪያው ቃል ነበረ

2ኛ. ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ

3ኛ. ቃልም እግዚአብሔር ነበረ እንደሚለው ሲናገር ይህ በመጀመሪያ ቃልም ሥጋ ሆነ "የቃሉ" ቃል ሥጋ ከሆነ ሥጋም ቃል ሆነ ሥጋና ቃል ተዋሃደ አንድ ሆነ መለኮት የተዋሃደው ሥጋ ከቃል ጋር አንድ ባህሪ ሆነ እንጂ ሁለት ባህሪያት አሉት አይባልም የእግዚአብሔር ቃል የተዋሃደው ሥጋ ከባህሪ መለኮት ጋር የተዋሃደ የማይለይ የማይከፈል ነው በተዋሃደው ሥጋ የሰብእዊነትና የመለኮታዊነት ባህሪ አንድ አድርጐ የያዘ ፍፁም አምላክ ነው እሚሉ ተዋህዶች ናቸው ።

በሦስት የተለያዩ ክፍሎች የተከፈሉ ሐይማኖቶች ሰኔፍላችሁአለሁ ይህን ስልም እንደሥላሴዎች አንድ ባህሪ አምላክ ሳይሆን ሶስት የተለያዩ እምነቶች ናቸው ።

1ኛ/ አምላክ የለም የሚል እንዳለ ታውቃላችሁ ስምታችሁማልም አምላክ የለም የሚል ሁሉ አእምሮው የጐደለና ምታዣታሚ ይመስለ የተዋሃደው እርኩስ መንፈስ ማደሪያ ያደረገው ጭንቀተኛ ሰውን ይመስላል ማደሪያ ያደረገው በክፉ መንፈስ እየተመራ እሚያደርገውን ክፉ ተግባር አያውቅም ይህ ክፉ ተግባር የሚያደርግ ምታዣታሚ ይመስል የተዋሃደው ሰው ደግ መስራት ቀርቶ ደግ ሥራ እሚያደርጉትን አይወድም ድንገት ሳያስበው መልካም ሥራ ቢሠራ በመሥራቱ እንደገና ይፀፀታል እኔውም ከክፉ መደብ ነውና አምላክን ስላላመነ ተስፋ እሚያደርገው ሃይማኖት የለውም እኛን ከመሰለ እራቁ ተጠንቀቁ ።

2ኛ/ ሁለተኛው አጥፊ ሁሉን ከመጀመሪያው የፈጠረን የእግዚአብሔር ቃል ወልድን ከባህሪ አባት ለይቶ አምላክ አይደለም ከአብ የተለየ ነው የሚል ታላቅ ሰው ቃል የሌለው የሚያደናግር ድንቁርን ሰው ይመስላል እኔውም አላስተዋለም እንጂ ከልብ የሚመጣውን በአንደበት ጉልቶ የሚሰማውን በቅንፍሹ የሚሰራጨውን ቃል ከአንድ ባህሪ እንዲለወጥና ወደሌላው አዕምሮ ተስተጋብቶ የሚዋሀድ የሚያደርግ ይመስለዋል ነገር ግን ቢያስተውል ኖሮ ከአንድ አካል ውስጥ ከሚገኝ ልብ የሚወጣ ቃልና እስትንፋስ ከልብ ጋር አንድ ባህሪ አንድ ጠባይ እንዳሁ ሶስቱ ልብ ቃል እስትንፋስ እንዳለው በተረዳ ነበር ሆኖም ግን

ስለ አንድነት አያምኑምና ህይወቱ ይበተናል ነፍሱ በማይጠፋ ሞት ይያዛል ለዘለዓለም በሥቃይ ይኖራል ።

3ኛ. እኛ ግን አንድነት አለን አንድነት የሌላቸው አንድነትን የማይወዱ ብዙ እምነቶች አሉና ከነሱ በንፅፅር አንድ ተዋህዶ ሃይማኖት አለን ይኸውም አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ በስም በአካል ሶስት በመለኮት ፣ በባህሪ ፣ በጌትነት አንድ አምላክ ከሶስቱ ሰምና አካል ወልድ ከእኛ ጋር አንድ እንደሆነና ለእኛም መንፈስ ቅዱስ እንደሰጠን የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ልጆች እንድንሆን በሳደረገንና በዚህ ቃል የሚያምን ብፁዕና ቅዱስ ነው ሙሉ ሕይወትና አካል ያለው ቤተሰቡን በእንክብካቤ የያዘና ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ አዋቂ ይመስላል በዚህ ቃላቶችን ላቀምና ወደ ታሪኩ እን መለስ

አባ እምደ ስላሴም ቀን በፀሎት ሌሊት በሰኢታት ከብዙ መነኮሳት ጋር ሱባኤ ገብተው ሲጨርሱ ሱሰንዮስን አጥምቀው ሥጋ ወደሙ በመጨረሻ ቀን ቢአቀምቧቸው የተዘጋ እንደበታቸው ተከፈተ ጆሮአቸው ሰማ እጅ እግራቸው ተንቀሳቀሰ በዚህን ጊዜ ልጆቸውን ፋሲለደስን ወንድሞቻቸውን አፃገ መልክ ክርስቶስ ብላቴን አፈክርስቶስ ብላቴን ጌታ ሳህለ ክርስቶስ ራስ የማንክርስቶስን ዋናው አፃገ ጢኖ ፈይሳን ጠርተው የእስክንድሪያ ሃይማኖት ይመለስ የሮም ሀይማኖት ይርከስ ፋሲል በተዋህዶ ሃይማኖት ይነገስ ብላቹሁ አዋጅ ንገሩ ብለው ተናገሩ እንዚህም ባለሥልጣኖች ወደተዋህዶ ሃይማኖት ተመለሱ አፃገ ጢኖም በእሷሁ መንኩሴ እጅ ተጠምቶ ስመንም ተክለ ሥላሴ ተብሎ ከዚህ በኋላ አጼ ሱሰንዮስ ወደትንድ ተክለ ሃይማኖት ወርደው ገብተው ቀኖና ይዘው ማህለ እግዚአብሔርን በበደልኩህ ይቅር በለኝ ብለው በሶስተኛው ሱባኤ በንጉሡ በሃያ ሰምንት አመታቸው የታህሳስ ተከለሃይማኖት ዕለት አረፉ ።

1626

በዚሁ በታህሳስ ወር በአንድ ሺህ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት አመተ ምሀረት በእሷሁ በአባ እምደስላሴ እጅ ቅባአ መንግሥት ማርን ተቀብቶ ስመ መንግሥቱ ዓለም ሰገድ ንጉሡ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብሎ ልጃቸው ፋሲለደስ ነገሡ አባቱ አጼ ሱሰንዮስ የተናዘዙትንም ነገዜ በአዋጅ ተናገሩ የካቶሊክ ትምህርት ቤት በታው የነበረው ተዘጋ የተዋህዶ ሃይማኖት ትምህርት ቤት ከዛሬ እስከዛሬ ተከፈተ ይህም አዋጅ እንደተነገረ በየዋሻው በየበረሃው የተሰደዱት ሊቃውንት ከመጽሐፍቶቻቸው ጋር ወደየቤቶቻቸው ተመለሱ ለአባ እምደ ሥላሴም አለም ሰገድ የተባሉት አጼሱ ንጉሥ

ነገሥት አጼ ፋሲለደስ ሲቆረቆሩት ገዳም ቆዳ(አርባ አራት ጉልት መቀ ጸዩሪያ ስማቸው እሳቸውም ወደአባታቸው ተመልሰው ማህበረ ሥላሴ ብለው ሰይመው ገዳማቸውን አቀኑ ።

አጼ ፋሲለደስ ስመ መንግሥታቸው አለም ሰገድ የተባሉት ከአለስክንድርያ አዲስ ጳጳስ እንዲመጣላቸው ለካይሮን ሱልጣን ደብዳቤና ስሊቀ ጳጳሱ የሚላከውን ገፀ በረከት ጨምረው ላኩ ወዲያውኑ የካቶሊኩን ፓትሪያርክ ሜንዴዝ አልፎንሱን ሚሲዮናቶቻቸውን ጨምሮ ያለውን የጦር መሳሪያ አስረክበው በቶሎ ከዚህ በደንብያና በበየምድር ያሉት ሁሉ ይዘው ወደትግሬ ፍሬምና እንድንትይዱ በእናንተ የተነሳ የኢትዮጵያ ምእመናን ሕዝብ ደም በከንቱ ፈሰሰ እናንተ ሕዝቡን በማጋደልና በማፋጀት ሳይወድ በግድ ሊታላምኑት መጣችሁ እንጅ ኢየሱስ በወንጌል እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዷችሁም ፀልዩ እርሱ በክፉዎችና በበጎች ላይ ፀሃዩን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢያተኞች ላይ ዝናቡን ይዘንባልና የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን ! ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ ብትነሱ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ አህዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተም ፍፁማን ሁኑ የሚለውን ልትፈጽሙ ቀርቶ ላመናችሁ እንኳን የማትታመኑ ጠላቶች ናችሁ ። ስለዚህ ሕዝቡን ሊታዘቱ መጣችሁ እንጅ ሊታስሙ አልመጣችሁም እውነት የወንጌሉን ቃል የምትፈጽሙ ቢሆን ኖሮ ክርስቲያን ያልሆነውን አህዛብ ሄዳችሁ በአስተማራችሁና ባጠመቃችሁ ነበር ነገር ግን እናንተ የዚህ ዓለም ሰይጣን ልጆች ናችሁ እንጅ የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም ስለዚህ ውጡልኝ ብለው ላኩባቸው ።

እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ የሚባሉት የቤተክህነቱ ባለሥልጣን ጃንሆይ እባክዎ ይሆን የካቶሊክ ጳጳስ በከንቱ አስር ጀህ የሚሆን የኢትዮጵያ ምእመናን ደም አፍስሶዋልና ሳይገድሉት ይፍቀዱልኝ ብለው ነበር አጼ ፋሲለደስ ግን ሐዋቱን እምንው የመጡ ስለሆን ሁሉቱንም እግዚአብሄር እንደሥራቸው ይክፈላቸው እንጅ አንድ የካቶሊክ ቄስ እንዳይነካ በቶሎ ወደሃገራቸው እንዲሄዱ የሞቱትም ሰማዕትነትን አግኝተዋል ቢሉ መለሱለት ካቶሊኮችም ጳጳሳቸውን ይዘው ከደብረታቦርና ከጎንደር የነበሩት ወደትግሬ ፍሬምና ሄዱ ።

ከዚያም በባሕር ነጋሺ ወልደ አክሱም ልጅ እንደሚማሩት ወን ድሙ እንደ ሌሎች የአፁቱ ዘቢብ ልጅ ባሕር ነጋሺ የሞንስ አካይ ከቱርኮች ጋር ሆኖ የምጣዉንና የምዕዋን አካባቢ ይገዛ ነበርና ውስጥ ውስጡን ተላልከው ከእሱ ጋር ተገናኙ ባሕር ነጋሺ የሞንስ አካይም አጼ ፋሲል ከሰን ፈራና ወደ ሱአኪን ላካቸው ከሱአኪን ወደሀገራቸው ፖርቱጋል የሆኑት ሄዱ ሦማርቹ ግን ወደኢትዮጵያ ተመልሰው ግማ ሾቹ ከአሌክሳንድርያ የመጡ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አስተማሪ መስለው ለኢትዮጵያ ህዝብ ሥጋና ቅባት የሚባልን ሃይማኖት ፈጥረው እያስ ተማሩና እየዞሩ አደሱ መቀሰቀሳንም ለብዙ ኢትዮጵያውያን ሰጥተው ኑሮ በዚሁ በቅባትና በፀጋ ሃይማኖት ክርክር ብዙ ህዝብ በከንቱ ደመ ፈሰስ እንዳንዶች ግን ካቶሊኮች መሆናቸው ስለታወቀ ተይዘው ተገደ ሏል ።

ከዚህ ላይ ልታውቁትና ልትረዱት የምዕፍላችሁ በካቶሊክና በተዋህዶ ሃይማኖት ያለውን ባለፈው እንደጻፍኩላችሁ ሁሉ አሁንም ፀጋና ቅባት ተዋህዶ እየተባሉ የሚከፋፈሉበትንና የሚጋደሉበትን እገልጻለሁ ።

1ኛ/ ተዋህዶ ማለት የእግዚአብሔር ቃል ከአብ ሳይለይ ሳይከ ፈል የእኛን ሥጋ ተዋህዶ በተዋሃደው ሥጋው እንደ አብ መንፈስ ቅዱስ ያለ ፍፁም አምላክ ነው ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የማይለይ የማይከፈል የባህሪይ አምላክ ነው አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብለን ሦስት ስም ብንጠራ በአገዛዝ በጌትነት በሥራ በምስጋና አንድ አም ላክ ነው የሚሉት ተዋህዶ ናቸው ።

2ኛ/ የእግዚአብሔር ቃል የተቀባውን ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ ክብር ከባህሪይ አምላክነትን አገኘ የቃልና የሥጋ መዋሃድን ግን ሁለትነትን አጠፋ እንጅ የባህርይ አምላክነትን ክብር ያከበረ መንፈስ ቅዱስ ነው የሚሉ ቅባቶች ናቸው ።

3ኛ/ የእግዚአብሔር ቃል እንደኛ በለበሰው ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ክብር አግኝቶ ክርስቶስ ተባለ የሚሉት ደግሞ የፀጋ ሰዎች ናቸው ።

እንዚህ የሶስቱን እምነት ልዩነት በዝርዝር ለማስረዳት ብዙ ገፅ ስለሚወስድብን አሁን ወደዋናው ታሪክ እንመለስ ፣

እንደዚህም ሆኖ የዛሬ ፃዘ የሆነ የምግ ሽግም ቃል ክርስቶስ በዚሁ በፀጋ ሃይማኖት የሚያስተምሩትን ካህናት ለብሰባብሰማንኛውም ም ፎና ዕሎት የፈለቻችሁኝ እንደሆን ሃይማኖታችሁን እስ ከብርላቸኋለሁ

አጼ ፋሲለደስ በንግሥ በሠለጠኑበት ዓመት እንፍራንዝ ነበሩና አድብቶ ለመግደል መጣ ነገር ግን የንጉሡ ነገሥቱ ሰው የሚሆን መም ጣቱን ተናገር ኑር ሲዖ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ጦርነት ገጥመው በሁለቱ በኩል ብዙ ሰው አለቀ መጨረሻ አቤቶ ቶወር ቃለ ክርስቶስን በተደጋጋሚ ተኩሶ ገደለው ከዚያም መልክአ ማርያም የሚባለው የቃለ ክርስቶስ ልጅ ከጦር አምልጦ ከትግሬ ጭፍራዎች ጋር ወደላስታ ተመልሶ ገባና የአባቱን ደም ለመበቀል የሃይማኖት ሰዎችን በየበታው እየሳበ በፋሲለደስ ላይ የሚነሳ ጠላት ያፈልግ ጀመር ከሸዋ አቤቶ ሥግዎ ቃልን የገራም ፋሲል የልጅ ልጅን አቤቶ ሥግዎ ቃልን ከተንቤን አቤቶ ዘማርያምን ወሰደ ለመሾም ሞከረ። አጼ ፋሲለደስ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ በተባለ በአምስተኛው አመት ላይ ሰጦርነት እንገጥም ብለው ተነሱባቸው ግን በዚሁ ዘመን እረፍብና በሽታ ነበርና በድርቅ ምክንያት ሁሉም ከየአሉበት የአጼው ጦር ሄዶ የገደለውን ገድሎ ምርኮኞቹን ወደ ደንቀዝ አመጣቸው ከሸዋ ተማርኮ መጥቶ የነበረው አቤቶ ሰግዎ ቃል ነበረና ይቅርታ ተደርጎለት ወደ ሸዋ ተመልሶ መልካ ማርያም ደግሞ ልጃቸውን ትውከልያን ለማስትነት ጻፉለት ። ይህ ካላበቃ ደብረ መድሃኒት ከተንቤን እንዲ ሰላም ከሸዋ እንደመጣ የሚገ ት ከሀገሮችና ሊቃውንቶች የዘጋ ሃይማኖትን የሚከተሉ በዚሁ ዘመን የተመደቡ ሆነው ቀርተው ነበር ።

ከዚህ በኋላ አስር አመት ፍቅርና ሰላም በኢትዮጵያ ምድር ቃኖ በሙም ከአንድ ሃገር ወደ አንዱ ሃገር እንደልቡ ይዛወር ጀመረ ።

አጼ ፋሲለደስ ስመ መንግሥታቸው አለም ሰገድ የተባሉት ንጉሠ ነገሥት በሆኑ በአስራ አምስት አመታቸው በአንድ ሺህ ስድስት መቶ አርባ አንድ ዓ.ም 1641 ዓ.ም. በአጼ አምደጽዮን ዘመን መንግሥት ከሸዋ ወደ ደንቢያና ወደወገራ ወደእንፍራዝ ቤት ታዛው በዚሁ ተደልደለው የተቀመጠው የጼዋ ጦር ነበር ። እነዚህም ሳሞት ጉንደር እደደር ስቀልት ይባላሉ ሞት በእንፋ ቤት ጋይንት ጉንደር በወገራ እደደር በተባሉ ስቀልች በደንቢያ በባለገሩ ላይ ተደልድለው ሲኖሩ የተደለደሉበትና የሠፈሩበት ሃገር በስማቸው እስከ ዛሬ ይጠራል ። የሐዚህ አጼ ፋሲለደስ አጼ ሠርፀ ድንግል ለእይሁዶች ፈላሾች እርስት ብለው የሰጧቸውን መሬት ነቀቀው ጉንደር ከተባለው የጼዋ ሠፈር ላይ ዋና ከተማቸውን ለመስራት አስራ አንድ ሺህ አይሁዶች በአጼ ሦስጦዮስ ጊዜ ለእርዳታ የመጡት ጣማጆች የፖርቱጋልና የህንድ ሰዎች በእርቆያለስ ሃይማኖት ተጠምቀው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ነበሩና እስከ ልጅ ልጆቻቸው አንድ ሺህ ሰባት መቶ ነበሩና እነሱንም ሰብስበው

ከሆነፊው ህዝብ ጋር አርባ አንድ ሺህ አናሲያና ግንበኛ ሰብስበው ቤተ
መንግሥታቸውንና አርባ አንድ ቤተክርስቲያን ማስገንባት ጀመሩ ቤተ
መንግሥቱና አርባ አንድ ቤተ ክርስቲያኖች ከተሠሩና ዙሪያቸው
በፈ ግንብ አጥር አስገንብተው በእምር አሙቱ ሥራው ከተፈጸመ
በኋላ ቤተ መንግሥቱና በስማቸው ፋሲል የፋሲል ግንብ አሉት ከተ
ማውን ጉንደር ብለው ሰየሙት አጼ ፋሲለደስ ያስገነቡት የሠፃ በ
የተምቀት መዋይ ብዙ ቤተክርስቲያኖች በመርነት ደርቡሾች አቃ
ለውታል ዘርፈውታል አፈራርሰውታል ይሄ ከመሆኑ በፊት ጉንደ
በጣም የደመቀና ያማረ ከተማ ነበረ ዛሬም ግን እስከ ዛሬም ከ
ጉደል የሆንጸው ፍርስራሽና የፋሲል ግንብ አለ ጉንደር ዋና መና
ከመሆኑ በፊት አባታቸው አጼ ሱስንዮስ በፖርቱጋሎች እርዳታ ቀ
ቤተ መንግሥታቸውን እንዱን ደብረታቦር አዲት ደብረመዊእ መድ
ጓለም ዳሞት አድርገው ነበር አጼ ገላውዲዎስ ግራኝ አህመድን ድ
ባደረጉበት የገር መናገሻውን ከተማ ደንቀዝ አድርገው ነበር ነገር ግ
ፋሲለደስ ያስገነቡት ግንብና የቆረቆሩት ጉንደር ከተማ በዳግማዊ
ምኒልክ ወደ ሸዋ አዲስ አበባ ነበረ ።

አጼ ፋሲለደስ ቤተ መንግሥታቸውንና ቤተክርስቲያኖችን
አስገንብተው ከጨረሱ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአንድ ሃገር ወደ
ሌላው ሃገር በክረምት ወራት ለመሻገር እንዳይቸገር ብለው በአን
ቤት በአፈርሞናት በወንበርማ በሱኪ የአባይን ድልድይ ከአራት መል
ላይ በጉንደር የእንገረብን በርገራ የርብን ተከዜን ሌሎችንም ወን
ከአርባ አራት ከሚበልጠው ገንቢ አናጺ ልከው ድልድዮችን አሠርተዋል
አጼ ፋሲለደስ መልካቸው እንደአባታቸው ሱስንዮስ አይናቸው ትላል
ጠጉረ ለዛ ጥርሳቸው ክፍት አፍንጫ እረጅም ሰውነታቸው ግዙፍ
የሰውነታቸው ጠጉር ከብዛቱ የተነሳ በየወሩ ይላጩት ነበር ይሄም
በአባታቸው እናት በሃመልማላዊት የፖርቱጋል ዘር ስለሆኑ የፖርቱ
ጋሉ ወታደር የነበረው የሰውነቱ ጠጉር እንደራስ ጠጉር ነበር ይባላል
ስለዚህ ከዘር የመጣ ነው እየተባለ ስለሚወራ የጉንደር ያም ሆነ ይ
የዛጉዌ ዘር የሆንችውን የሞጣ ሹምን ልጅ ልእልት አደይን አግብተው
ሁለት ሴቶች አራት ወንዶች ወልደዋል የሴቶች ስም ለሳቢታው
ማርያም ያጋቡዋቸት ትወክልያ ለጉጃም ገዢ ደጃች ወሌ ያገቡዋቸ
እንቆቁልዕየን ናቸው ወንዶች የሞገስ አበቶ ጉንዳ—ጉንደር አበ
ሥጋስ እምሳከ ናቸው ።

ወ/ሮ እንቆቁልዕየን ደጃች ወሌን አግብተው ሲኖሩ ባለቤታቸው
በደ/በአጼ እያሱ ላይ ስለአመፁ ተገደሉ በዚህን ጊዜ ደጃዝማች

ለሚስቷን እንብተው ደጃዝማች አፍሬን ወልደማል ሰማቸውም ከእንቁ የቆየውን ሰብለ ወንጌል ተብለው ብዙ ርስት ከአጼ ዮሃንስና ከአጼ ሊያሱ ተሰተዋል ።

እጼ ፋሲል ከመንፈሳዊ ትምህርትና ከእጅ ሥራ ጋር ወታ ዋና ዋና ጨዋታ ይወዱ ነበር ከሁሉ ይበልጥ አደን በጣም ይወዱ ነበር ።

ከእለታት አንድ ቀን ወደቋራ በረሃ ከወታደሮቻቸው ጋር ዝሆን ለማደን ሄዱ ከበርሃው እንደደረሱ ድንኳናቸውን አስተከሉው ሰፈር ከአደረጉ በኋላ ከትንሽ አሽከሮች ጋር ሆነው ዝሆን ለመግደል ሄዱና ትልቅ ጥርስ ያለው ዝሆን አገኙና በትልቅ ጨብሬ ወግተው በጥይት ተኩሰው መቱት ዝሆኑ ግን ደሙን እያንጠበጠበ ሲሮጥ በፈረስ ሆነው ሲከተሉት ብቻቸውን መንገድ ያውቁ መውጫውም በማያውቁበት በረሃ ገቡ ከዚያም ዝሆኑን አግኝተው ደግመው ከመቱትና ከጣሉት በኋላ ወታደር ሥላሴሉ ብቻቸውን ጥርሱን አውልቀው ወደሠፈር ሊመለሱ ቢሞክሩ መንገዱ ጠፍቶባቸው ከዚያው ከበርሃው አደሩ። በጠዋት ሲነሱ እንደ አጋጣሚ አንድ ቀለኛ ባለሃገር አገኙ ከዚያም የከተማ ንጉሡ ንጉሥት ወደሠፈሩበት ሠፈር የሚወስድ መንገድ ምራኝ አሉት ቀለኛውም እኔ ወንድሜ አንደኛ ከፈረሰኛ ጋር እኩል መሄድ አይችልም ሁለተኛ ደግሞ የበረሃ ጌጅ ቀርጨ ለመምጣት ስለምሄድ ሆዳ ገብቶት ያርጅ ለመመለስ ፈልጌአለሁ አላቸው የድካምህን ዋጋ እከፍልሃለሁና ከእኔ ጋር ተፈናጠጥና በቶሎ እንሂድ አሉትና ተፈናጠ ለዋንኑው ንጉሥ ደግነት ቀለኛው እያወራ ሲሄድ በመሃከሉ በማህ ወንድሜ እኔ ከአንተ ዋጋ አልፈልግም ነገር ግን እግዚአብሔር የአንተ ወሎን ንጉሥ የደግ አባቱን መልኩን እንዳየው አፈሲጋለሁና ይሆን የዝሆን ጥርስ እንደሰጡልህ አሸከመኝ ካለበት ድረስ እንድወስዳኝ እጅ እንድነሳው አላቸው እሺ ወንድሜ አሉት ወደሠፈሩ እንደደረሱ እጼ ፋሲለደስም በጣም ወንድሜ የንጉሥ ሠራዊት ከፈረሱ እየወረደ የሚሰግድላት እጼው ነውና የሃገሩን እንተም ወርደህ ስግድ ስገድላት አሉት ። እሺ ወንድሜ መስገድ ብቻ ሳይሆን መሬት ስሞት ጊዜ እስምላሳለሁ እያለ ሲሄዱ ሠራዊቱም የንጉሡ ንጉሥቱን መምጣት እያዩ እየተደሰቱ ከፈረስ እየወረዱ ሲሰግዱለት ሁለቱ ብቻቸውን ከፈረስ ያለው እንደተደፋገጠ ቀሩ እጼ ፋሲለደስም ንጉሡን እየሄው አሉት እየሰሙትም ነገር ግን ሠራዊቱ ከፈረሱ እየወረደ የሚሰግድ ለእኛ ነው ከፈረስ ያልወረድንም እኔና አንተ ብቻ ነን እንጂ ከፈረሱ ወርዶ ያልሰገደ የለም እንግዲያው ንጉሡ አንተ ወይም እኔ መሆኔ ነው ሲል መለሱቸው ከዚያም በንግግሩ ሰቀው ፈረስና በቅሎ ከሙሉ መጣሪያ ጋር ሸልመው የአርማጭሆን ግዛት ሰጥተው ወደሃገሩ ሰደዱት ።

አጼ ፋሲለደስ በስዋኪን በአዶሊስ በባፅዓን በታጁራ በመቃድሾ በበርበራ በዛንዚባሩ የሚገኙት ሱልጣኖችና አሚሮች ይማሞችና ነጋዶች የፍቅርና የሰላም ደብዳቤ በምፅዋ በሚገኘው ቱርክ ባሻ ላኩላቸው ይሄውም ከጥንት ጀምሮ በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጠላት እያስነሳ ሲያስወጋቸው ከነበረው ከአባቶቻቸው ጠላት ከቱርክ መንግሥት ጋር የጠበቀ ወዳጅነትን ስላደረጉ ነው የቱርክ መንግሥትም ከአጼ ፋሲለደስ ፍቃድ ማግኘው ሰውና የንግድ እቃ ወደኢትዮጵያ እንዳይገባ ብሎ በግዛቱ ለሚገኙት ሱልጣኖች ትእዛዝ አስተላልፎ እንደ ነበር በውላቸው ላይ ተፅፎ ተገኝቷል ።

ይሄውም አጼ ፋሲለደስ የካቶሊክን ቄስና አስተማሪ ከኢትዮጵያ ምድር ፈጽመው ስለአወጡና ስለአጠፉ በዚሁ የተነሳ የእስፓኝና የፖርቱጋል መንግሥት የሮማ ሊቀ ጳጳሳት በጣም ተናደውና የኢትዮጵያ መንግሥት ለማስጠፋት ይጥሩ ነበር በዚህን ጊዜ አቡቶ ዘማርያም የተገባቡን ነገር ብዙ ካቶሊኮች በቤቱ ደብቆ እረዳት ወታደር ከአውሮፓ እንዲመጣለት ተጻጽፎ ነበርና ብዙ ሚሲዮኖች በምፅዋ በኩል ለመግባት ሲሞክሩ የምፅዋው ቱርክ ፓሻ ሙስጠፋ እስር ከገደላቸው በኋላ እራሳቸውን ቆርጦ ለአጼ ፋሲለደስ ላከላቸው እሳቸውም ስለአደረገላቸው ውለታ ከወርቅ የተሠራ ዘንግ ላኩለት ሌሎች ካቶሊኮች በመቃድሾ በኩል ለመግባት ሲሞክሩ የመቃድሾ አሚር ይዞ ገደላቸው ።

አጼ ፋሲለደስ በግብፅ ለሚገኙት ሱልጣኖች ከአስክንድርያ ጳጳስ እንዲልኩላቸው ስለጻፉ ወዲያውኑ ሁለተኛ አባ ሚካኤል የሚባሉ ጳጳስ ተላኩላቸው ። ግብጾችም እስከ ካርቱም ድረስ እየመጡ ነገር እየወረሩ አስቸግረው ነበርና በዚሁ ከቱርክ መንግሥት ጋር በአደረጉት ወዳጅነትና ውል ከሱዳን በረሃ በመለስ ጉብተው ሃገር ሳይወሩ ካሉበታቸው የባዕድ ሰው ሳያስገቡ የተጻፈ ውል ስላለ ከዳር እስከዳር ያለው ህዝብ ለአጼ ፋሲለደስ ተገዝላቸው በዚሁ በጉዚያ በሱዳን መንግሥት ላይ የሚቀመጠው የጉርብትን ልጅ ዘጊዮርጊስን እንግሙ መቀመጫውን ከሱኪ ወደሰናር አድርገው እስከ ዛሬም ግብፅ ድረስ ገዝተዋል ።

በዚህ ጊዜ ገጣሚ እንዲህ ሲል ግጥሙን ገጥሟል ።

ጉንደር ቢያጉረመርም ፋሲል ፈረስህ
ኑቢያን አመሳ ወርቋን ሜንሊህ
ሱሩን ተጠየፈ የፋሲል ፈረሱ
ከምር የሱዳን ወርቅ ገፈፈው ነው ለሱ

አጼ ፋሲለደስ ቃለ ክርስቶስን አቤቶ ዘማርያምን ጠላቶቻቸውን በአቤቶ ቀዘር በጦር ሃይሎቻቸው በእነ ራስ ብእለ ክርስቶስ በነደ ጃች ማህደረ ክርስቶስ በንብላቴን ጌታ ላቀበ በንመልካአ ባህር በን ፈታውራሪ ማሞ እየጓኩ ከእስወጉአቸውና ታርቆ የገባውን ይቅር ብለው ወደስልጣኑ ሲመልሱ ሌላውን ደግሞ አልገዛም አልታረቅም ያለውን ካስገደሉ በኋላ ሃገርም ሰላምና ደስታ ከሆነ በኋላ ንጉሡ ነገ ሥት በኢትዮጵያ ስመ መንግሥታቸው አለም ሰገድ በተባሉ በሰላሳ አራት አመታቸው በ1660 ዓ/ም በተወለዱ በስልሳ ሁለት አመታቸው አረፉ ። በዚህን ጊዜ በሃገር ውስጥ ሁከት እንዳይነሳ ሞታቸው ለህዝብ እንዲደበቅ ተደርጎ የንጋሲን ዘሮች ከየአሉበት እየተያዙ ታስረው ብላቴን ጌታ መልካ ክርስቶስ ወደ ወህኒ አምባ እንዲወሰዱ አደረገ ከዚህ በኋላ ታላቁ ልጃቸው አቤቶ ዮሃንስ በዙፋና ቸው እንዲ ቀመጡ ተናግረው ኖር አቤቶ ዮሃንስን ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ ስመ መንግሥት አእላፍ ሰገድ ብለው በእቡነ ሚካኤል እጅ ቅባአ መንግሥት ቀብተው ዘውድ ማስሬው ዘውዱን በራሳቸው ላይ ደፉላ ቸው ። ከዚህ በኋላ ወደውጭ ወጥተው እንደቀንቱ ልማድ ንጉሡ ነገ ሥታችን አጼ ፋሲለደስ አርፈዋል ። ልጃቸውን አቤቶ ዮሃንስን ንጉሡ ነገሥት በኢትዮጵያ አዕላፍ ሰገድ ብለን አንግሰናል ። ሁንም የሞት ነው እኛ ያለንም እኛ ጠላታችን ይዘን ወዳጃችን ደስ ይበለው ብለው በንጋሪት አዋጅ አናገሩ ከዚህ ከአዋጁ ቀጥሎ በሰሞኑ በግልጽ ሃዘን ተደረገ በታላቅ ሰልፍና ስርአት የአጼ ፋሲል ደብን ሬሳ ከቤተ መንግ ሥቱ እስከ አዘዞ ድረስ ተጉዞ ከአባታቸው መቃብር አጠገብ አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበረ ።

# ምዕራፍ ሃያ አራት

## የአጼ ዮሐንስና የአጼ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት

አቤቶ ዮሣንስ ከአባታቸው ከአጼ ቴዎፍሎስ መንፈሳዊ ለመማር አ... ፈቅደው ከጐንደር ውስጥ በደረቢ ዮሐቅላ ቂርቆስ በባስ ማባ ነዳዊ በሊ... ከሚካኤል በማቻከል ደብረ ኤሊያስ በጭካሉ እየተዘዋወሩ እንዳለኝ ... በእያታቸው በአጼ ሱስንዮስ እያሉት መድኃኔአለም ባለው ቤተ መንግሥ... እየተቀመጡ የመንፈሳዊን ትምህርት ሽ! መሰየኖት ያንበቡና ... ዜማ እስከአጋባቡ የተማሩ ሊቅ ናቸው ። ጊዜያቸውንም መሰየኖት በ... ዕዮኖት በመጾንስ አብረዋቸው የሚውሉትን ሁሉ ሃይማኖትን በማስ... ማር ያሳሉቁ ነበር እንጅ እንደአባታቸው ወሃ ጭና እያ... ነበር ስለዚህ ሁዝበን ጳድቁ ዮሣንስ ባዜታቸው ዮሣንስ ያሳናው ያ... ስለዚህ ነው አባታቸው አጼ ቴዎፍሎስ በታመሙ ጊዜ የሚወዱ እሾ... ልጃቸውን አቤቶ ዮሣንስን ከዲማ ጊዮርጊስ ነበሩና አስመጥተው ... ጆቻቸውን በዙፋኔ ለንድታስቀምጡልኝ ብለው ስለተናዘዙ... የዙፋናቸው ወራሽ ሆኑ ።

ስለዚህ አጼ ዮሣንስ የአባታቸውን መንግሥት ወርሰው ... ማካደድ በጀመሩ ጊዜ የአባቶቻቸውን ወዳጆች ሥልጣን እያ... ሁሉንም ከፍ ስለአደረጉ ከዳር እስከ ዳር በደስታ አከበሩዋቸው ... ያውካሉ በማለት ወንድሞቻቸውንና አጐቶቻቸውን የኒቃሲን ዘር... በወህኒ አምባ ተቀምጠው እንዲጠብቁ አደረጉ የቀረውን እ... ሙሉ ምህረት አድርገው ወደየሃገሩ ሰደዱት ከዚህ በኋላ በመንፈ... ትምህርት ወደአደጉበት የገር ጉጃም ሲጄዱ ለጉጃም ከሆነ የሊ... መሬት ለቸቻለሉ ብለው ብዙ ቤተ ክርስቲያን አሰተከሉ ... ይወዱት ስለነበር የኢሳቸው ግዛት እስከሚያልቅ ከንጉሥ ... ነቶ ሆነ ይሄውም የበጌምድር ሀዝብ በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመን ... ግሥት ግብር እንዳይከፍል ተደርጓል ። ይሄውም እግሩን ለመጠር ... ቱን ለሥር ስለሚያደርግ በስማይ በምድር በበጌምድር የለም ... ተብሉ ታውጆ ነበር ። ከጐጃምና ከላሞት እንደተመለሱ የክርስቲያ... የእስላም የአይሁድም መንደር ለየብቻ ይሁን ሲሉና ወንጌም ...

የታቸውን እንዳያረክሱ ሲሉ እንዳይጋቡ ከለከሉ፡ ፈረንጆች ግን ከዚህ ቢቆዩ ሀገሩን ያፋጁታልና ወደሃገራቸው እንዲሄዱ ሲሉ በእሪንጉ ይሚኖሩት የንጉሡ ነገሥቱን ትእዛዝ ሳከብሩቸው እርቆያከስን የሚያ ቃወም ግን ይቀመጥ አሉ የኢትዮጵያን ካህናት ግን ሰብስበው በቅባ ቅና በፀጋ በተዋህዶ ያሉትን ያከራክሩ ነበር እንጂ እንተ ግድ ይሄን የይማኖት በውድ እንጅ በግድ ማሳመን አይፈቀድም ብለው ስለአወጁ የቅባት ሃይማኖት የበዛ በአጼ ዮሃንስ ዘመን መንግሥት ነው ይባላል።

አጼ ዮሐንስ ከትእግስታቸው ብዛት የሚነገርላቸውን እንሰማ ከአለታት አንድ ቀን ቄስ አጼ ንጉሥ አባታቸው ከባለቤታቸው ከአቴን ስብሰወንጌል ጋር ተኝተው ቢያገኙአቸው ዝም ብለው ሳይቀሰቅሱ ከማ ዕረጉም ሳይሸሹ ምህረት አድርገውለት ሁለቱኛ እንዳይደግም መክ ረው አሰቀመጡት ይባላል። አጼ ዮሐንስ አባታቸው ከሙሩላቸው ጠላ በሆር ማንብ ሚካኤል ቤተመንግሥታቸው አጠገብ ባህር አስበጅተው በባህሩ ውስጥ አሳ እያሰረቡ ከዚያ አሳ እያስወጡ አስርተው ለግብር ይቀርብ ነበር ከአለታት አንድ ቀን ግብር ገብቶ ከባለቤታቸውና ከን ስሃ አባታቸው ጋር ተቀምጠው የተጠበሰው አሳ ከማዕዱ ቀርቦ ሳለ የሁለቱ የባለቤታቸውና የንስሃ አባታቸው አሳ የሚያንሱ መስለው ለመንከስት ፍላጎት እኔ ዳሳቸው አውቀው እኛ ሰስታችን እውነት ብንናገር ይህ የተጠበሰ አሳ በህይወት ተነስቶ ከባህሩ ውስጥ በገባ ብለው አጼ ዮሐንስ ተናገሩ ከዚህ በኋላ እቴጌይቱ ቄስ አጼን አግብቼ ብኖር እወዳለሁ አሉ ቄስ አጼውም እቴጌን አግብቼ ብቀመጥ እወዳ ለሁ አሉ ንጉሡ ነገሥቱ ግን ይችን ከንቱ አለም ንቄ ብመንን እወዳ ለሁ ብለው ሲናገሩ የተጠበሰው አሳ ተነስቶ ዘሎ ከባህሩ ገባ ስለቱም እውነታቸውን በመናገራቸው እግዚአብሔር ተአምርን ሠራ።

ስለዚህ በዛንጊዜ የነበረው ባለቅኔ ሥዓሊ ቅኔ ሲቀኝ እንዲህ አለ።

ከአዳም እስ ዴዋርስ ለምንልእ እሳት ወአምሃምሃቲ አስፈፈጸተ ዋትሕ የሥራ ወክልኤ እምድህረ ተርፉ ኢማሃላ ኢዮሱስ እመአሳ በው ለዘምኔት ሃሣሳ ወለመንግ እለመ ልበዮሃንስ ሃሠሥ (አመዮሃንስ) እስኖሂሁ ቅድመ ይግሥግ በፈቃዱ ዘተግዘም አሳ

ትርጉም፦ ኢዮሱስ ለአምስት ሺህ ሰው ባበዛበው ጊዜ የዱቀ ርስ እጆች ከሁለት እሳና ከአምስት እንጀራ የተረፈውን አስራሁለት አንቅብ እነሱ የዮሃንስ ሊብ እለምን በመናቅ በፈለገ ጊዜ ግን እጆቹ ሳይዳስሱት የተነሳ አሳ ብዙርን ሞላት።

አማርኛ ግጣሚ

የድጉ ዮሃንስ የእውነት ቃል ቢነሳ
ከባህር ዘሎ ገባ የተጠበሰ አሳ
የዚህን አለም ደስታን ንጉሥ ቢንቁት
ያኔ የሞተ አሳ ተነሳ ከሞት
ጻድቁ ዮሃንስ ዘውድ ይዞ ብቃት
ልበ አምላክም ሆነ ደግሞ እንደዳዊት

ቀ/እጬ ዮሃንስ ሊበን በነበሩበት ጊዜ በመንፈሳዊነታቸውና በፀሎታቸው የታወቁትን የመደባዩን ባላባት የገብረመስቀል ጃንታማን ልጅ ሰብለ ወንጌልን አግብተው አቤቶ ዮስጦስን አቤቶ ኢያሱን፣ ልዕልት እሌኒን፣ አቤቶሁን ቴዎፍሎስንና አቤቶ ቀላዣን ወልደዋል ።

ቀ/እጬ ዮሃንስ አእላፍ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በአስራ አምስት አመታቸው የዚህን አለም ደስታ ንቀው ልጃቸውን አቤቶ ኢያሱን በሌላ ጉንድ ተክለሃይማኖት ገዳም አባፀጋ አበው የሚባሉ የመፅሐፍት መምህር ተሰጧቸው መፅሐፍተ ቅዱሳንን ያጠኑ ነበርና አስመጥተው ልጃቸውን መርቀው ብላቴን ጌታ ገብረ ልኡል ብላቴን ጌታ አካለ ክርስቶስ ፀኃፊ ትእዛዝ ወልደ ሃይማኖት ፀኃፊ ትእዛዝ ወልደ ክርስቶስ ራቅ ማሰሬ ጴጥሮስ እና አባ ሲኖዳ እጨጌ ሀርያቆስ በአሉበት የዮሃንስ ንጉሳችን ሞቱ እንጅ ይህን አለም ንቀው ገዳም ገቡ እንዳትሉ ብለው አእላፍ ሰገድ በተባሉ በአስራ አምስተኛ አመት መንግሥታቸውን ለልጃቸው አድያም ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው መነኑ ። ከዚህ በኋላ የጻድቁ ዮሃንስ መመነን ለማንም እንዳይነገር እራሳቸው ስለከለከሉና ስለአወገዟቸው በሺህ ስድስት መቶ ስልሳ አምስት አቤቶ ቴዎፍሎስንና አቤቶ ቅላዣን ወደ ወህኒ አምባ አስወሰደው ሥርዓተ ንግሱን ከፈጸሙ በኋላ ደጃዝማች አስጠንጣስዮስ ንጉሳችን አጼ ዮሃንስ አርፈዋልና ልጃቸውን አድያም ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለን እንግሰናል ብሎ አሳወጀ ባለቤታቸውም እቴጌ ሰብለ ወንጌል የዚህን አለም ደስታ ንቀው ጫና ደብር ምዕራፍ ማርያም ከምትባለው ቤተ ክርስቲያን በፀሎትና በጾም ተጠምደው ሲኖሩ ልጃቸው ኢያሱ በነገሡ በሶስት አመት ላይ አርፈው በክብር ልጃቸው አስቀብሯቸው ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሲባሉ የሃያ አድሜ ሰው ነበሩ ። አጼ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት ሲሆን በአባታቸው

ዙፋኑን በተቀመጡ በሶስተኛው ወር በመስከረም ሹም ሽር አደረጉ ባለ ቶት ነጋሥታት የተጠራበሩ ሙግታ እንዲያደርሱ ፈ እየተባለ የንጋሲ ዘሮች በወህኒ አምባ ታስረው ነበርና ከሥራ ቤቱ ድረስ ሄደው ግብዣ ካደረጉላቸው በኋላ ስጦታ ሽልማት እየሰጡ አስደስቷቸው ሁሉንም አንድ አንድ ሥልጣን እየሰጡ በሥራ ላይ አስቀመጧቸው እነሱም የንጋሲ ዘሮች እንዲህ አሉ እኛን በወህኒ አምባ ታስረን የተረሳነውን ለምን ፈትህ ለዚህ ደስታና ማዕረግ እንዳበቃሃን እግዚአብሔር መንግሥትህን ከልጅ ልጅህ አያውጣው እያሉ መረቋቸው በህይወታቸው ሙሉ በቅን እንደሚያገለግሏቸው ነገሯቸው ።

እንደዚሁም ሆኑ አባታቸው አድቄ የሚገስ ሲማሩበትና ሲዘዋወሩ የነበሩበትን ሃገር ለመጎብኘት ወደጐጃም ሄዱ ከዚያም ፎአምባ ጉንዳ አደረገው ጀፍጀፍን ደርሰው ይባባ ገቡ ይባባ እጌ ሲሰንቅበ የተወለዱበት መንደር ስለነበረ የዳሞት ከተማ አዴት ሲሆን የጐጃም ዋናው ከተማ ይባባ ነበርና ከዚያ አርፈው ለባሻ ሩሩ የብላቴን ጌታን ለሌጥ ሮብ ፊት ማሰራያን ማዕረግ ሰጣቸው ከዚያ የአባቶቻቸውን ተክል የሆነችን አብያተ ክርስቲያናት እየዞሩ አይ ከዚያም ደስ ባላቸው ቦታ ቤተ ክርስቲያን እያስተከሉ ለካህን መተዳደሪያ መሬት እየሰጡ በሰባተኛው ወራቸው በሰላም ወደጐንደር ተመለሱ ።

ከዚያም ሚስት አጣቡም ነበርና በሃማሴን ውስጥ ምድረ በቀላ ከሚባለው አገር ከደቅአስገዴ ነጋድ የሆነውን የሃብተ ኢየሱስን ልጅ ወለተ ሰዮንን አጭተው በጳጳሱ በአባ ሲኖዳና በእጨጌ አባሀሮዶ ቆይ መሰየፈ ተክለ ሊል ተነቦ ሥርዓተ ጋብቻው በሥነ ሥርዓት ተፈጸሞ በክብርነት አገቧት ።

እጌ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጐጃም በነበሩበት ጊዜ ለካህን ብቻ መተዳደሪያ መሬት ሰጥተው በአባታቸው ጊዜ ግብር እንዳይገብር የጐጃም ሀገብ ተብሎ የነበረውን አሁን ልጃቸው እጌ ኢያሱ ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲገብር ብለው ደጃች ጠሚን የጸሐፊላሁምን ሥልጣን ሰጥተው ወደጐንደር ሲመለሱ ደጃች ወሉ የእጌ ሱስንዮስን የልጅ ልጅ የነወይዘሮ ልጅ ይስሃቅን እንግስ የጐጃምን አውራጃ ከተማ ዎች በቁጥጥሩ አደረገ ።

በዚህን ጊዜ እጌ ኢያሱ ይህን ነገር ሲሰሙ ሠራዊትን ከተቀ ጣው አውጀው ወደጐጃም ገቡ አደረጉ ጻህፊላሁም ማሜ ቀፊንዮ ላይ ሆኖ የእጌውን መምጣት ሲሰሙበት ቆይቶ ከጌታው ጋር ተገና ኘና የሆነውን ሁሉ ነገሯቸው ።

ከዚያም ወደጉዳዩም ተጉዘው ሰንቀሬ ሜዳ ደረሱና በየአለቃው በየአገሮቻቸው አሰልፈው አዲስ ከሚባለው ሃገር ላይ ጦርነት ገጥመው ብዙ የቱሉማ የጋፋት ነገዶች ሞቱ ሁለት ሺህ ሰዓት ሙሉ ተጋረሱ ደጃች ወልዴ ተማርኮ በፍርድ ጎንደር ተወሰደ ተሰቀለ ይስሐቅ ገላውዲዮስ ግን ከትንሽ ጦር ጋር ሸሽቶ በሸዋ ይኖር ነበር ከቀን ብዛት የነጋሲ ዘር መሆኑን ለሸዋ መሣፍንት ከነገረ በኋላ በዚጋሙሉ ላይ ሆኖ ለመንገስ ሲዘጋጅ አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ እረኘኑ ነበሩና ሰሙ ይሄውም በነገሱ በአስር አመታቸው የበኳሩን እናት ያወቁት በዚህ ዘመን በዚህን ጊዜ ለደጃዝማች ድሜጥሮስ እንዲህ ሲሉ መልእክት ላኩለት ወሬኛ ይስሐቅ ያለበትን ሥፍራ የሚያዝበትን ዘዴ አዘጋጅተህ በቶሎ መልሱን ላክልኝ እኔ እስከምረፍቂቱ በፊት በራስህ መሳ በቀን ብዙ ይዘህ ያመጣህልኝ እንደሆነ እስከ ዘር ዘርህ የሸዋን ግዛት እንደ ምሰጣቸው ቃል እገባለሁ ብለው ለላኩለት መልስ ደጃች ድሜጥሮስ ብዙ ልብሰን ከአጼ ኢያሱ የተላከ አስመስሎ አሲዞ ወደ ዋሀሬላህም እጋር ልማኛ ቤት ተገዝ ከዚያም ለዋሀሬላህም ለጋሎች ልብስ ሰጠ ሰጡት ከንጉሡ ነጋሥቱ ታዝዤ ወደእንተ መጣሁ አለው ዋሕሬላህም እኢጋርም በየወረዳው ላሉት ለሰላሌ ጋሎችና ለቱሉማ ዘሮች በነገሬ ጊዜ ሰምተው ተሰብስበው መጡ ደጃዝማች ድሜጥሮስ ወታደሮቹን በየመንደሩ በየዱሩ የጥይት ድምፅ ስትሰሙ እንድትመጡ ብሎ ደብቋቸው ኖር ጋሎች ሁሉ ተሰብስበው እንደመጡ የጥይት ድምፅ ሰማ ታደርቸ እሰጣ ወዲያውኑ ወታደሮቹ ጋሎቹን ከበቧቸውና ያዟቸው ደጃች ድሜጥሮስ እንዲህ ሲል ተናገረ እናንተ ከዚህ ያላችሁ ጋሎች የምትገዙትሁን ሰሙኝ ከእናንተ ጋር ጠብ የለንም ነገር ግን በመካከላችን ገብቶ የሚበጠብጠንን ወሬኛ ይስሐቅን ያስቀመጣችሁትን ሰጡን እንጂ ካላችሁ እንደታሠራችሁ ወደ አጼው እወስዳችኋለሁና ትፈቱ ይላላችሁ ለዚህ ጉዳይ ተማክሩና በቶሎ መልሱን ንገሩኝ አላቸው ።

በዚህን ጊዜ የቱሉማ ዘሮች የሆኑ ሁሉ እንዲህ አሉ እኛ ታሰርን ሄደን ከምንሞት የራሳቸውን የንጉሥ ዘር ሰጥተን በወዳጅነት ከነሱ ጋር ተስማምተን መኖር ይሻላል ብለው የጓምብቹ ያብቹን አለቃ አባ ጋዳ ጢቆን ከሰማኒያ ሁለት ሰዎች ጋር መርጠው ላኩት ። አባጋዳ ጢቆና አባ በላ ሜቶ አቢቶ ይሥሐቅ ገላዉዲዮስን ከደበቁበት ሃገር ሄደው አታለው ይዘው አምጥተው ለደጃዝማች ድሜጥሮስ ወስደው አስረከቡት እሱም ወዲያውኑ አጼ ኢያሱ ከአረንጉ ወደ ቡሺ ቀልጦ ደማስቆ (ጉጃም) ነበሩና ወስዶ አስረከባቸው ።

አጼ ኢያሱም ወደወሀኒ አምባ ጄዶ በግዞት እንዲኖር ብለው ነበር ነገር ግን እዛጥችና ፈራጆች በእርስዎ ላይ እንደገና ጦር እስኪሰበሰብ ያስፈጀል ሃገር ያወካልና ይገደል ተብሎ ተገደለ ከዚህ በኋላ በሸዋና በጉጃም ሰላም ሆነ ከዚያም በጾሬ በአማራ ሳይንት የአቡቶቻቸውን አብያተ ክርስቲያናት እየተሳለሙ የተዘረፈውን ነገር እየሞሉ የአመፀውን አገር እያስገበሩ በአንዳ ቤት አድርገው በአባ ጉንዳ ቤተርዳ ደርሰው በሰላም ወደዋና ከተማቸው ጉንደር ገቡ ።

በዚሁ በአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመነ መንግሥት ዘሩ አርመናዊ የሆነ አቤቶ በአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት መጥቶ ኢትዮጵያዊት ሴት አግብቶ ሙራድ የሚባለውን ወልዶ ሙራድም ከኢትዮጵያ ጋር የና ከሮቤ ወደግብጽና ወደህንድ እየወሰደ የሚሸጥ ከዚያም ልዩ ልዩ የጦር ጨርቃ ጨርቅ እያመጣ ለኢትዮጵያ መኳንንት ሲያስደስት ይኖር ነበር ነገር ግን የምፅዋ ብርክ ባሻ ናይብ ሙሳ ቀረጥ እያበዛና ለንጉሠ ነገሥቱ የሚላከውን ሁሉ አይገባም እያለ ስለከለከለበት ሙራድ ምጽዋ ላይ ሆኖ ለአጼ ኢያሱ ላከላቸው አጼ ኢያሱም የምግቤን ገቢዎች ለትግሬ መኮንን ለንዲህ ሲሉ ትእዛዝ አስተላለፉ ማንኛውም ነጋዴ ቅቤ ማር ወርቅ እህል ይዞ ከምግቤን ወደምፅዋ የሚወስድ ብዙ ቅጣትና ሞት ያገኘዋል ብለው ለማቤኑ ገዢ ለከንቲባ ወልደአብ ዘለ ስለ ለትግሬው ገዢ ትግሬ መኮንን ዘር አብሩክ ኢልላ ላኩ በዚሁ ምጽዋና የአርኪቶ ህዝብ ተቸገረ በዚህ ላይ እንዳሉ አጼ ኢያሱ ወደ አለቃም ተገዝው ሳለ ብርክ ባሻ ናይብ ሙሳ በቀረጥ ምክንያት የቀ ማውንና ሌላም ጌጣጌጥ አምጥቶ ለንጉሠ ነገሥቱ ሰጥቶ ታረቀ የሚ ሉትንም ሊያደርግ ቃል ገባላቸው ።

አጼ ኢያሱም በአጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተደረገውን ውል ደገፈው የምግቤን ሕዝብ ወደምፅዋ የምፅዋም ሕዝብ ወደ የማቤን እየ መጣ እንዲነግድ እንዳያከለክሉ ሲሉ ተዋዋሉ ከዚያም ሁሉቱ ወደ የና መቀመጫቸው በፍቅርና በሰላም ተመለሱ ።

አጼ አድያም ሰገድ የሥላሴን ቤተ ክ/ጉንደር ውስጥ አሰርተው ጨርሰው አዲሱ ጳጳስ አቡነ ማርቆስ እጨጌ ፀጋ ክርስቶስ ከቀሳውስት ጋር ታቦቱን ይዘው ሲሄዱ ጉቤን ከሚባለው ፈረሳቸው ላይ ሆነው ታቦቱን ይከተሉ ነበር ። ከዚያ ታቦቱ ከደጃፉ እንደደረሰ ከቁሱ የተባለው አጼ ኢያሱ ከመንበሩ ላይ አስቀመጡት ከዚያ በጸሎት መንገዱ ተባረከ ቅዳሴ ተደገፈና ትልቅ በአል ተከበረ ።

ከዚያ በኋላ ለካህናትና ለመኳንንት ትልቅ ግብር በደብረብርሃን (ጐንደር) አደረጉ ። በዚሁ ቀን ለንጉሡ ነገሥቱ ሊቃውንቱ እየተነሡ ቅኔ ተቀኙላቸው ከቅኔዎቹ አንድ ሰላሴ ቅኔ አምላክ ዘኢፈቀድከ ደቂቀ ቆሪ ወአዝያን

ሰባ ማእጠንተ ወርቅ ነስአ ከመያኩት ካህናተ
ነስአ ተቀስፎ መለብሱ እሳተ
እለ ይፈርሁከ ሰብአ ባህቱ እምሃ በብረክከ አንተ
ወዘወሃብኮሙ ትምህርተ
እመርህበ በል አ ዳዊት መሥዋእተ
ወኢያሱ አንሥአ ፅላተ

ትርጉም -የአዝያንና የቆሬ ልጆች ካህናት ለመሆን አሰበው እምላክ ያልፈቀደውን የወርቅ ጥና - በወሰዱ ጊዜ ተቀሥፈው እሳት በላቸው አንተን ከሚፈሩህ ሰዎች ግን በሰጠሃቸው ምልክት ተመርተው ዳዊት ቢራብ መሥዋዕትን በላ ኢያሱም ፅላትን አነሳ በመኳንንቱ በኩል

ወዴት ሄዶ ኖሯል ሰሞነኛ ቄሱ
ታቦት ተሸክመው ዘወዱን ትቶ ኢያሱ
የተሸሸገውን ያባቱን ቅስና
ገለጠው ኢያሱ ታቦት አነሳና
አየነው ኢያሱን ደብረ ብርሃን ቆሞ
ከኩሩቤል ጋር ሥላሴን ተሸክሞ
ሰውነቱን ትቶ መልአክ ሆነ ደግሞ ።

ሰላሴን ቢሸከም እያሱ ገነን ለአራቱ ኪሩቤል አምስተኛ ሆነ

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በሸዋ መሳፍንትና በወላስማው ዙፋን የተቀመጠው የባሌው ገራድ በየጊዜው ጠብና ሁከት እየተነሳ ስለአስቸገረ እራሳቸው ዙፋን ጠባቂ አፋሪሰን ጐንደር ትተው ንጉሠ ነገሥት በሆኑአስራ አራተኛው ዓመት አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሰምንት (1688) ዓ.ም ላይ ወደሸዋ ጉዞ አደረጉ ከዚያም እንደደረሱ የሰላሌ የተሉማ የጂሌ የአማራ ነገዶች በክብር በሰልፍና በሆታ ተቀበሏቸው ከየጕጡ የተላከው አዛውንትም ግብራንና ገፀበረከቱን ይዞ መጥቶ ተዋወቀ ከአማራ ጐሣዎች መርድ አዝማች ዘሚካኤል እንዲህ የሚል ቅኔ ለአጼው ተቀኙላቸው ።

በአስተአ ማህሌት ወይባቤ ኢያሱ አጼን ተቀበልና ከእስመ ይደሎ እግዚአ እምሃብናከ ሰጊዶ ።

ወአምረሰይናከ አምላከ ዋህደ ባህቱ አምላከ ዘአምቤትከ ታወልደ ውስተ ደብረሲና አመወረደ በቅድመ ሙሴ ወአሮን ይቤ ገሃዳ ኢንበሌየ ኢታምልኬ ባእዳ

ትርጉም ከወገንህ የተወለደው አምላክ በደብረሲና በወረደ ጊዜ በሙሴና በአሮን ፊት ከእሱ በቀር ሌላ አምላክ አታምልኩ ብሎ በግብፅ ባይናገር ኑሮ አንተን ኢያሱን አጼአችንን አምላክ አድርገን በሰገድንልህ በርና ሆኖ ግን በማህሌትና በዘፈን ተቀብልንህ ለዚሁ ለመርድ አዝማች ዘሚካኤል የአንጾኪያን ግዛት ሰጣቸው ንጉሡ ነገሥቱን በተቀበሉበት ቦታ የሰነበቱበትን ሠፈር ደብረ ሲና ተባለ በቅኔው መሰረት ውስተ ደብረሲና አመወረደ መሠረት ነው ይባላል ። እርስ በእርሳቸው ሲጣሉ የነበሩትን መሣፍንት አስታርቀው የአቤቶ ሰማዎ ቃልን ልጅ አቤቶ ነጋሲን የበላይ አድርገው ሾመው ወደጐንደር ተመለሱ ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በግብርና በቀረጥ የተነሳ ሕዝባቸው እንዳይቸገር ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የቀረጥ ህግ አፅፈው አሳወጁ ።

1ኛ/ በአንድ አውራጃ አንድ ኬላ

2ደ/ በአምስት በቅሎና አህያ አንድ አሞሌ ጨው

3ኛ/ በአምስት ግመል ጭነት ሁለት አሞሌ ጨው

4ኛ/ በትከሻ የሚነግድ ቀረጥ እንዳይከፍል

5ኛ/ በጐንደር መካከል ባለው ገበያ የሚውለው ከብት ነጋዴ ከቀረጥ ነጻ እንዲሆን አደረጉ

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጠፍቶ የነበረውን መከሊይት ዲናር ድሪ እሪያ የሕዝብ መገበያን ገንዘብ ከወርቅና ከብር ከነሃስ በስማቸው አስቀርፀዋል ስሙንም የአንጥረኞችና የቀራጦች * አዛዢ ነጋድራስ ብር ገውና ይባል ነበርና የገንዘቡ ስም ብር እንዲባል አድርገዋል ። እንዲሰራ አዘው የነበሩት አንድ ሺህ ሚሊዮን ወቄት ነበር ይባላል ሆኖ ግን ልጃቸው አቤቶ ተክለሃይማኖት የወርቅ ማንጠሪያውን ግንብ ስለአፈረሰው አራት መቶ ሽህ ከወርቅ ከብር እንደተሠራ አቁሟል በዚህን ጊዜ አንጠረኞች ተገለዋል ልጃቸው አቤቶ ፋሲል አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዙፋን ጠባቂ አድርገው ወደ እናሪያ ከፋና ወሊጋ ሄደው ነበርና በዚሁ እለት የአባቱን ግምጃ ቤትና የወርቅ ቤት አላስነካም ብለው ሲዋጉ ሞተዋል ። የፋሲል እናት

ወይዘሮ ቅድስቱ በዚሁ እለት ባልታወቀ ሕመም ሞተው ተገኙተ
ዋል አጼ ኢያሱ አናሪያ ሆነው ልጃቸው ተክለሃይማኖት ሹማምን
ቱን ገለው የአባታቸውን ዙፋን በሃይል መያዛቸውን ሲሰሙ ገስግ
ሰው ጐንደር ገቡ ከዚያም ልጃቸው ተክለሃይማኖት ወደሃማሴንወደ
እናቱ ወሰተ ፅዮን ሀገር ሄደ ከዚያም ሄጂ አሊ አቡበከር ዶክተር
ሽርልጃ ፖንሴት እንደዚሁም ነጋድራስ ሙራድ ናቡቱ ተላልከው ከአ
ባቱ ከአጼ ኢያሱ ጋር አስታረቋቸው እሳቸውም ቀን ጥሎት ነውና
ብለው ይወዱት ስለነበር የራስነት ማዕረግ ሰጥተው የድንቢያን
ግዛት ፈቀዱለት ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው
በነገሡ በአሰራሰባተኛው ዓመት ከዳር እስከዳር ሀገር ሰላም ሆነ
በነገሡ በአሰራሰባተኛው ዓመት ከዳር እስከዳር ሀገር ሰላም ሆነ
ገበሬውም በግብርናው ነጋዴው በንግዱ ኢትዮጵያን ሃብታም አደረ
ጓት ነገር ግን በዚሁ ዘመን አንጥረኛና ቅርፅ ቀራጭ ተስማምቶ
የገንዘብን ጥቅም ከወርቅና ከብር ሰርተው በሚያቀርቡበት ጊዜ ከቱ
ርክና ከፈረንሳይ መንግሥት ተልከው የሚመጡት እንግዶችአልተደ
ሰቱም ነበርና ልጃቸውን አቤቶ ተክለሃይማኖትን እያታለሉ የአባቱን
ሕግና ሥራት እንዲያፈርስ ያደረጉ የፈረንሳዩ ዶክተር ሻርል ጃክ ፖን
ሴና ሃጂ አሊ አቡበከር ነበሩ እነዚህም መጀመሪያ ለንጉሠ ነገሥቱ
የሚያገለግሉ መስለው ሲታዩ ቆይተው በተክለሃይማኖት ዘመኑ መን
ግሥት ዋና ባለመዋል ሆነው ብዙ ሕዝብ አስገድለዋል ።

ይሄው ዶክተር ሻርልስ ጃፖንሴት ለትንሽ ጊዜ ለአጼ
ኢያሱ ዶክተር ሆኖ እንደልቡ የፈለገውን ሁሉ ወደውጭ ይሰድ
ስበነር ከ14ኛው ሉዊ ከፈንረንሳዊ ንጉሥ ጋር ከእስፓኝ ከሆላንድ
መንግሥት ጋር ተዋውሎ በአጼ ኢያሱ ፈቃድ ብዙ ሺህ የሚሆን
ወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ባሮች የዝሆን ጥርስ ወርቅ በየጊዜው
ያሻግር ነበር ለዚሁ ሁሉ በጣም የረዳው የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ አቤቶ
ተክለሃይማኖት ነበር ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር
ቀጥ ብሎም ቢገዛላቸው ልጆቻቸውና የነገሥታት ዘሮች ነን የሚሉት
ሁሉ ከፈረንሳይ ከቱርክ ከሆላንድ ከእንግሊዝ የሚያደርጉትን የወዳጅ
ነትና የንግድ ልውውጥ የእጅ ሥራ በውስጥ በውጭ ያለውን ያፈርሱ
ባቸው ነበር ዳሩ ምን ይሆናል የወጡት ሁላ በየቦታው ፈረሰባቸው
በዚህ ዓይነት እንዳሉ ሰውነታቸውም ወደ መድከም ደረሰ የሆድ
በሽታም ፀናባቸው ፀበሉንም ዶክተሩንም ሞከሩን ሊሻላቸው አል

ቻለም ከዚያ ሃይላቸው ስለ ደከመ ሹማምንቱ እጌውን ችላ እያሉ ወይትልቁ ልጃቸው ተክለሃይማኖት በግልፅም በስውርም መማከርና ማገ ልገል ጀመሩ ።

እጌ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከደቅ እሰገዱ ነገድ የምትወለደውን ወለተ ፅዮን ሃብተ ኢየሱስን በክህነት አግብተው ሳሉ እኚሁ እቴጌ ወለተፅዮን ተክለሃይማኖትን እንደወለዱ ሞቱ ከዚያም የአክሱም ንቡረ እድ ገብረስላሴን እህተ መለኮታዊትን በሕግ አግብተው ሲኖሩ መካን ስለሆኑቅድስቱ የምትባለውን እቁባት አድርገው ፋሲልን ወለዱ እቴጌ መለኮታዊት ተክለሃይማኖት ከልጅነቱ ጀምረው ስለአሳደጉት ይወ ዱት ስለነበር መሣፍንቱ እንዲያግዙት ይሞክሩ ነበር ።

አጌ ኢያሱ ጉጃም ይባባ ሄደው ከዚያም ምድረ ዲማ ሄደው ሳለ የራስ ወልደ ጊዮርጊስ ልጅ የአቤቶ ሚካኤልን ልጅ ማርያም መዋኢት ማርየማዊት የምትባለውን መልክና ደም ግባት አይተውደስ አላቸውና ይዘዋት አደሩ ከዚያም በካፋ ተፀንሰው ተወለዱ በካፋ እን ደተወለዱ ማርያማዊት ዲማ ጊዮርጊስ በሚባል ዶብር ቤተ መንግሥት ተሠርቶላት ነበርና ወደጐንደር እንዲመጡ ተላከባቸው ከዚያም እንደ ደረሱ ከአፄ ኢያሱ ጋር አድረው ሁለተኛ ልጅ ዳዊት ወለዱ በዚያም ከአራት አመት በኋላ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ አጌ ኢያሱ በለሳ ሄደው ጥጥ አዘርተው እራሳቸው ቆመው ጥጥ ሲያስለቅሙ ከረሙ ይሄውም የልብስ ፋብሪካ ሊያስከፍቱ ከውጭ ሀገር ነገሥ ታት ጋር ሲላላኩ በነበረበት ዘመን ነው ከቁንጅናዋና ከደም ግባቷ ሌላ ፀሎተኛ የሆነች የነገላ ገገር ራስ አንሰጣስዬስ ልጅ ማሚት የምትባለውን እቁባት አድርገው ወልደጊዮርጊስን ወለዱ ።

የአጌ ኢያሱ አድያም ልጆች ስም

| ተክለሃይማኖት- | ወ/ ፅዬን | የሴቶች ስም |
|---|---|---|
| ፋሲልና ል/ማርታ | ቅድስት | ልእልት ሰበኔ ከማ ርያማዊት |
| ወልደጊዮርጊስ | ከማሚት | ልዕልት ብስለን ንትያ |
| በካፋ | ከማርያማዊት | ወለተ ሩፋኤል |
| ዳዊት ዮሐንስ | ከማርያማዊት | ወለተ እስራኤል ከማሚት |

አጌ ኢያሱ አድያም ሰገድ ከአስተዋይነታቸው ሌላ ይቅር ባይ ነታቸውን ከሚያስረዳው ታሪክ እቀርብላችኋለሁ ።

ከእለታት አንድ ቀን ከቅንጃ የእልፍኝ አሽከሮቻቸው ጋር በ
ባሲት በር ወጥተው ፈረሳቸውን በወርቅ መጣብር አጊጦ የወ
ኮርቻ ጌጡን ተጭኖ እፊታቸው እየተሳቡ ሲሄድ አንድ መጠጥ የ
ሰካራም ሰው ከመንገድ አገኛቸውና ወንድም ይህ የምታስበው ፈ
ይሸጣል ወይ ብሎ ጠየቃቸውና እየተወላገደ አለፈ እጼውም የሚ
በትን ቤት እቶ ብለው አሽከሮቻቸውን አዘዙና በነጋታው
መንግሥታቸውን ለብሰው ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን ግራና ቀኝ አቁመ
ችሎት ተቀመጡ ከዚያ በኋላ ያንኑን ፈረስ የወርቅ ኮርቻው
እንደተጫነ ከመካከል አስቀምጠው ይሸጣል ወይ ያሉቸውን
አስመጥተው ትናንት ልትገዛው የነበረውን ፈረስ ያውልህ አ
ግዛው አሉት ሰውየውም ጃንሆይ ትላንት ከእኔ ጋር ከነበሩት ባለ
ሮቹ ጋር መካፈ ነው የምገዛው ሲል መለሰላቸው እጼውም ት
ብቻህን ነው የነበርከና ምን ባልንጀራ አለህ ቢሉት ንጉሥ
ከኔ ጋር የነበሩት ባልጀሮቼ ከጠላ ከጠጅ የሚገቡት ጌሾ ግ
ብቅል ናቸው ብሎ ስለመለሰላቸው ቁጣቸውን ወደምህረት መለስ
በሰላም ወደ ቤቱ እንዲሄድ መለሱት ።

2ኛ ደግሞ እጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ሁገር ሰላም ሆኖ ሲበና
ጠፍቶ ባለ መንግሥታቸው የረጋ መሆኑን ለመግለፅ ከቁስቋም
መጪቸው ሁለት ትላልቅ የናሃስ ሙከቶች ነበሩ ለነዚህ ሙክ
የወርቅ ጉትቻ" ባንገታቸው ተንጠልጥሎ በጉንደር ከተማ እየ
የመንደሩን እህል የተሰጣ ብቅል ሰውም ምጣውን ሲበላ ዘለው
ተው ይበሉ ነበር እንጅ የሚመታቸውና የሚያስወጣቸው ሰው አ
በረም ከእለታት አንድ ቀን አለቃ ዮሐንስ የሚባሉ ደብተራ
ፍቀው መጽሐፍት እየጻፉ የሚተዳደሩ ሊቀ ነበሩ ከሳቸው ቤት
ተው የተዘጋጀላቸውን ሲበሉ ደረሱባቸውና ሁሉቱንም ይዘው
ደው ቆዳቸውን ሲብሩና ሥጋቸውን ለምግብ የወርቅ "ጉትቻውን
አስቀመጡ በዚህን ጊዜ የእጼው ሙከቶች ጠፉ ተብሎ ቆዳ
በየመንደሩ ወታደር ተልኮ ሲፈለግ ከእሁ ከአለቃ ዮሐንስ
ደረሱ ወታደሮቹም አለቃ እኛ እርስዎን ጠርተረን ሳይሆን እ
ገቡ እንዲፈተሽ ቤትዎ አሏቸው አለቃውም ከቤታቸው ውስጥ
ከንድ ጉድጓድ አስቆፍረው በበሳዩ እንደሳንቃ የመሰለ መዝገ
ጋጅተው በበሳዩ ላውጀ ምንጣፍ እንጥፈው ሁረያውን ወንበር
ጉበት ነበርና ወታደሮችን እሺ የንጉሥ ወታደሮች ግቡና ሙ
ተቀምጣችሁ ጠጅ ጠጡ አሏቸው እነሱም ሳይጠረጥሩ እንደተ
ሄደው ከወንበሩ ሲቀመጡ የጉድጓዱን ሰረገላ ቆልፍ ከፈቱባቸው

ቃሉም ከጉድጓዱ ውስጥ ወደቀና ሞቱ በዚህ የተነሳ ንጉሡ ተናደዱና ምክር ተደርጎ የበግ ሙክት በእንግዱ የድቀስ ቀንድና ቢላዋ ከሚሀደሩ እንጠልጥለው ላኩት ይሄውም በበጉና በድቀሉ የእረብ አሰማት ተደማምበት ነው የተላከና እንደልማዱ ሲያርድ ተያዘ ይገደላል ተብሎ ነበር ግን ያ ተንኮለኛ ካህን

ዕድሜ እሰምናለሁ ለአጼ ኢያሱ
ያንን የበግ ሙክት ቢሰደው ንጉሡ
በጉባ ቢላዋ በጉባ ድቀሉ
አመሰግኘ በላሁ ከነራሱ ምላሱ

ብሎ ቶሎ መንደር ለመንደር የምትዞር የንጉሥ ሎሚ ነበረችና በእንግትም ዕሁቱን አሰር ላከው ከዚያም አጼ ኢያሱ ቶሁቱን አይተው በጣም ተናደዱና ከፈረንሳይ ሀገር ለማንኛውም ምክርና ሙላ እንዲነገሩቸው ዶክተር ሻልርልስ ጂያን ሴን አስመጡ ዶክተሩም ነገሩን ሁሉ ከሰማና ከተረዳ በኋላ አንገረብ ወንዝ አጠገብ ካለው ሜዳ ላይ ድንኳን አስተከለው በውስጡ በወርቅ ጉቸላ ያስቀምጡ በደጃፉ ላይ የብረት ወጥመድ እንዲጠመድና የለመደው ሌባ እንደልማዱ ሊሰርቅ ሲመጣ ይያዛል ሲል መከራቸው እሳቸውም እንደተባሉት ከደረጉ በኋላ ሌባና ወንበዴ ጠፉ ሀገር ሰላም ሆኖ የንጉሥ ወርቅ ያስጠባቂ በሜዳ አደረ እያለ አፈቀላጤ በገበያው በመንደሩ እየዞረ ተናገረ በዚህን ጊዜ አለቃ የልጉስ አንድ ወደል ባሪያ ነበራቸውና እሱን ይዘው ወርቁ ወደአለበት አንገርብ ሜዳ ሄዱ ከዚያም ከባሪያቸው ጋር እንደደረሱ ከዚህ ድንኳን ውስጥ ግባና ወርቁን ተሸክመህ አምጣ አሉት ባሪያውም እንደተባለው ወርቁን ሊያወጣ ሲገባ የብረት ወጥመድ እግሩን ሲይዘው እግሬን ወጥመድ ያዘኝ አላቸው ከዚያው እንደሆንክ ወርቁን አቀብለኝ ብለው ወርቁን ሰጥቶ ሲጨርስ እንገትክን ብቅ አድርግ አሉና በሰይፍ አንገቱን ቆርጠው ከወርቁ ጋር ይዘውት ወደቤታቸው ተመለሱ ከዚያ የንጉሥ ወታደሮች በበነጋው ቢሄዱ በወርቁ ፈንታ እራሱ የተቆረጠ የሰው እሬሳ አገኙ ከዚያም ለአጼ ኢያሱ ሲነግሯቸው ከወርቁ ጥፋት እራሱ የተቆረጠ ሰው በመገኘቱ በጣም አዝነው ካህናቱንና መኳንንቱን ግብር አድርገው የሆነውን ሁሉ ከተናገሩ በኋላ ይህን የሚያደርገውን ሰው ፈልጉን አይቼው የሚፈልገውን ባደረኩለት ግንም ጀግና ድል ያላደረገኝን ከከተማዩ ሆኖ አንድ ያላወኩት ሰው

ድል እኔን በማድረጉ እንድንቀበለው እንጂ አልንቀውም እንደ...
ቱም አላየውም ሲሉ ተናገሩ ።

ከዚህ መልሲ አለቃ ዮሐንስ የሚባለው ደብተራ ተነሳና ... ሆይ ሕዝብም ቀጥ ብሎ ቢገዛልዎ አምላካችንን እንደማመሰግን ... ብዎትን እንደማስደሰት ይልቅ ወደል መኳንንቶች እየላኩ ለምስ... ሰራዊቱ ያዘጋጀውን ምግብ ያስበሉ ጀመር በእስዎ* መኳንንቶች ያ... ድሃና ሀብታም አልነበረም ስለዚህ ከትምህርትዎ የተነሳ እኔ ... አርጂ የበላኋቸው ወታደሮችንም የገደልኩ ደብዳቤም የጻፍኩ የ... ደውን ባሪያዎችንም አንገቱን የቆረጥኩ ብለው በድፍረት ተናገሩ ...

አጼ ኢያሱም አድያም ሰገድ በሁቀኝነቱና በድፍረቱ አመ... ነውና ሸልመው በኋላም አሰናበቱት ሆኖም ግን አለቃ ዮሐንስ ... ዋልድባ ገዳም ሄደው ወዲያውኑ መንነው ተቀመጡ ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በሽታ ስለአደከማቸው ያሰ... ሁሉ አልሟላ ስላለ ሁሉንም ትተው በ፲፱ ሰድስት ... ዘመና ሰምንት ዓ/ም ላይ ልጃቸውን ተክለሃይማኖትን የመንግሥ... እንዲረከቡት ሰጥተው ጣና አጠገብ ደቅ ማርያም ወደምትባለው ... ክርስቲያን ሄደው እንደመናኝ ሰባኤ ገብተው ተቀመጡ ።

እንደዚህም ሆኑ ራስ ተክለሃይማኖት በእናታቸው ወንድም ... ጎራው ሃገር ራስ ፋሪስ በዶክተር ኸርሊስ እየተመከሩ በኢሉ... ላይ ሽፈቱና ሳይሞቱ በበላያቸው ላይ ነገሡ በዚህን ጊዜ መኳንንቱ... መማከርንቱ እርስዎ እንደ አጼ ካሌብ እንደሊባትም አጼ ዮሐንስ መንግ... የሚባል ወሬ ሰንሰማ ታላቅ ልጅዎን እንግሥና ሲሉ የመኳ... መልእክተኛ ላኩላቸው ራስ ተክለሃይማኖት በእሳቸውም ... መስኮታዊት በፍስ ፋሪስ በደጃች ፍሰል ክርስቶስ በእነዚህ በዳውሮ... በጀርመን በዶክተር ቸርሊስ ሃንሬን በንጉጂ እሊ እየተረዱ ከ... ጉንደር ዋናው ከተማ ገብተው ልሉል ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ... ቋያ ተብለው ነገሡ ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በመንኩሰብት ቤተ ክ/ ሆነው ሲ... ልጃ ተክለሃይማኖት ሰዎች መክረው ካላስከደዱት በቀር እኔ ... ቅድሰት አልጋዬን በፈቃዴ ቀምቶ በግድ ለመንገስ አያስብም ... መልእክተኛ እንዲህ ሲሉ ላኩ ልጄ እንደሆንክ ቤቴን ልቀቅ ... የም ወረድ ከነበርከበት በታ ተመልሰህ ቆይ የሌሎች ሰዎች ... ከመጉዳት በቀር አይጠቅምህም ከእኔ ፍቃድና ከሃይማኖቱ ከሌ...

መንግሥቱ ከአንተ አያልፍም ከእኔ ፍቃድና ከእኔ ሃይማኖት ከመጣህ ግን እንኳን የመጣሉትን ርዕስ የሰማይ አርበኛ የለህም ብለው ሳሉለት ነገር ግን ንጉሡ ተከለሃይማኖት ከሳቸው የመጡትን መልእክተኞች አስረው እንዲህ ሲሉ ጻፉላቸው በትምንም አለቅ ከዘፋኑም አልወርድ የመንን ሰው መንግሥት ምት ነው የመንን ከዱር የምተ ከመቃብር ይመልሳልን ዛሬ በእርስዎ የተገዘመረ እንደሆነ ወይም ለምን መንገሥ ብለው ተፀፅተው እንደሆነ ከመንኑበት ደሴት ይውጡና ከቸጊ ፈረስዎም ፈረሴ ሠራዊትም ሠራዊቴ ነው አብረው ያሉት ደቀቀ የሚረና ፈታመራፈ ያዕቆብ ሲያድንም አይችሉም ሲሉ ላኩላቸው አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ የእግዚአብሔር ቀጸባዝ ነው ብለው ከዘፋኑን መኳንንቱን እየመረቁ ወደሀገራቸው አሰናበቷቸው ለልጃቸው እንዲህ ሲሉ ላኩላቸው ባባትህ ከተ እንደመከርከ ከተ መንበር ያውርድብህ ሹመትህም ለባዕድ ይስጥ ሰውም አይገባልህ ብከንዘ ይጠላት እጅ መት ብለው የርግማን ደብዳቤ ጽፈው ላኩላቸው ።

በዚህን ጊዜ ተክለሃይማኖት ዳርመንና ጳውሎስ የሚባሉትን እንደራሲያቸውቸውን አጼ ኢያሱ ከደቀ ሄዳችሁ ወደ ጨቅላ መንዘ ወስዷቸው አልሄድም ካሉ ግደሏቸው ብለው አዘዙ እነሱም እንደ ተባሉት አራት መቶ ሠራዊት ይዘው ሄደው በሌተ ከርስቲያኑ ያለ ውሃ ገለው አጼ ኢያሱን አድያም ሰገድ ወደጨቅላ መንዘ ቢታንኳ አድርገው ይዘዋቸው ሄዱ ።

ከዚያም የደረሱን ወገን የሆነ በጕጃም ደረባ ከሚባል ሀገር መጥቶ ለተክለሃይማኖት የሚያገለግለውን ቀናውን ጦር አገምን ሰማኒን ባሉት ሱማሜም ወደ አጼ ኢያሱ ጉጅ መስተ ገባ ኢያሱም ባየት ጊዜ እኔሃላፊውን መንግሥትን በማያልፈው ሰው ጨዋለው ነገር ግን በእኔ ሞት ተክለሃይማኖት የሚጠቀመው ምንድ ነው ! ባገንቱ በት አይሰራበት በደሜ እዳል እያበቅልበት ሥጋዬም ቶቶል ነው የግፍ ብዛት ምን ይጠቅመዋል አሉት ። ሱማሜም የአጼ ኢያሱን ንግግር ሰምቶ በልቡ አዘነ ከዚያም መግደሉን ትቶ ወደ ሰቀ ወጣና እአ አጼ ኢያሱን ደትን ንጉሡ ነገሥት ገደሞ በአ ሥራል ልጆች አገልግሎንና በወገኖቹ በደረበና በጋፋት በሚሜም ልጅች ቂም በቀል አልተከለም ግፍም አላደርግም ሲል አብረውት ለመጡት ወገኖቹ ተናገረ ።

ነገር ግን ጳውሎስና ዳርመን ተክለሃይማኖትን ለማስደሰት እያ ሉ እንደነና ልናንግስም ነው እያሉ ጕተቷቸው ርግጥ በሰማይ ሊታኑ

ግሱኝ ከፈጣሪዩ ጋር ሊታገናኙኝ እንደመጣችሁ አውቃለሁ ብለው ቀና ገድቸው ከዚያም ከተኙበት አልጋ በጥይት መቷቸው አልሞት ሲሉ እንደገና በጦር ደጋግመው መትተው መሞታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ገዳዮች ጸሎቱስና ዳርመን ለእህታቸው ለእቴጌ መስኮታዊት ለ[illegible] እቴጌይቱም ለእንጀራ ልጃቸው ለተክለሃይማኖት ደብ ደብዳቤ በሰ[illegible] ላኩ ከዚህ በኋላ ካህናቱና መነኮሳቱ አፈሳቸውን ወስደው እናታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌል ከተቀበሩበት አጠገብ መቃብር አስርተው [illegible] በምዕራዊ ማርያም ቤተክርስቲያን በክብር በሐዘን በልቅሶ በ[illegible] ስድስት መቶ ዘጠና ስምንት ሐምሌ ሃያ በዐኝ ቀን ተቀበሩ የ[illegible] በት ዘመን ሃያ አራት ዓመት ነው የታላቁ ንጉሥ ንጉሥት የኢ[illegible] ኢያሱ አድያም ሰገድ ታሪክ ከብዙ በጥቂቱ መሪሪስ በግዜር [illegible] ፈው መሪሪስ ኢም በዓይ ጽሔ አቅርበላቸኋለሁ ።

የአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ በግፍ መሞት በየሀገሩ ሲሰማ ቂምና በቀልን በሃአለበት በተክለሃይማኖት ላይ አደረጋ ተክለ ሃይማኖትም ለራስ ፋሪስ የእንደራሴነትን ሹመት ለዳርሊመን ጉጃምን ለ[illegible] መቁስ በጓምድርን ለሌሎችም ወዳጆቻቸው ሹመትሌጣውን እየሸ[illegible] ሾሟቸው ነገር ግን በየቦታው ጦርነት ሁከት ተነሳባቸው ረሀብና በሽታ በሀገሩ ላይ መጣ ስለዚህ ንጉሡን ተክለሃይማኖትን ለመ[illegible] ደል ጉጃሞች አምጻደፅዮን የሚባለውን የአንበሳ ዳዊትን አገግወ[illegible] ለመርነት ተሰለፉ በዚሀን ጊዜ ዳርሙንና ፋሪስ ጉጃሙን እንዲወ[illegible] ታዘው ብዙ ሕዝብ ከንደሉና መንደር ከሊቃወሉ በኋላ ይባባ ከተ[illegible] በመጨረሻ ትልቅ ጦርነት ሆንና ንጉሡ አምጻፅዮን በጀግንነት ሲዋ[illegible] ውሎ ድል ሆንና ተማርኮ በጥይት ተደብድቦ ሞተ ጸሎቱስም የበጋ[illegible] ድሩን በአጼ ኢያሱ ጊዜ ግፍ የነበረውን ደጃዝማች ድሀን [illegible] ድል አደረገውና ገድሎ አራሱን ቆርጦ ለተክለሃይማኖት ላከላቸው እሳቸውም በዚህ ደስታ ሲሉ በግዞት የነበሩትን የአጼ ኢያሱን ል[illegible] ጆች አስወጥተው በጥይት አስደበደቧቸው ከዚህ በኋላ በዳሞት የሸፈተበ[illegible] ውን የንጉሥ ወሰን ሰገድ የልጅ ልጅን ደጃች ወልደ አባብን ለመ[illegible] ጋት ወደ አዲት ሄዱ ከዚያም የአገው ባላባቶች እየመ[illegible] እጅ እየነሱ ገፀ በረከት አቀረቡላቸው በዚሁ በአዲት [illegible] የአገው ባላባቶች የሚገደሉበትን ዘዴ ከተማከሩ በኋላ ንጉሡ አ[illegible] ይወዱ እንደሆን በአገው ምድር ዝሆንና ጉሺ አንበሳም ስላለ [illegible] ቢያድኑ ጥሩ ነው ብለው ለዋና አማካሪያቸው ስለነገሩት እሱም [illegible] ውን ምስጢር ሳያውቅ ነገራቸው ተክለሃይማኖትም አደን ወዳድ ነ[illegible] ሩና ቅንጅ ወታደሮች ይዘው ወደ አገው ምድር አደና ሄዱ ከዚያም

የአፄ ጃኖን ወንድም ባላንበራስ ዮሐንስ ጥሩ ጀግና ሰው የሚሆኗቸው አዘጋጅተው ነበር።

ንጉሡ ተክለሃይማኖት በአዘን ምድር እንደደረሱ ጎሽ ገደሉ ከዚያም አንበሳና ዝሆን ሰሎ ግደሉ ዱር ለዱር በፈረሳቸው ሆነው ሲገቡ ገዳዮችም አውሬ የሚያድኑ መስለው በጥይት መቷቸው ወራፍ የሚባለው የወበርማ ተወላጅ ፊክር ሄዶ በጦር ወጋቸው ከዚያም ከፈረሱ ላይ ሲወድቁ የሞቱ መሰላቸው ገዳዮች ሸሹ ነገር ግን እንዳልሞቱ በባላንበራስ ዮሐንስ በለሰማ ብዙ ወታደሮች ይዞ ሄዶ ያሉበትን ቤት አቃጠሉት ከዚያም ከቃጠሎው ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን ይዘው ሲወጡ ጋሻ ጃግሬዎችን በጥይትና በጦር ገለው ንጉሡን አሰከንፍላቸው በእንጨት ላይ ሰክተው ከመንገድ ላይ ሰቀሏቸው

ከዚያም በተሰቀሉ በበነጋታው አቃጠሏቸው የእኚህ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ግዛት ሁለት ዓመት ሲሆን በዚሁ ዘመን የተገባላቸው ነገር አልነበረም የአባታቸው ሀዘንና እርግማን በቶሎ ደረሰባቸው።

እንደዚሁም ሆኖ የንጉሥ ተክለሃይማኖት መሞት በጉንደር ሲሰማ የአጼ ኢያሱን አድያምሰገድን ወንድም ቴዎፍሎስን ከወህኒ አምባ አውጥተው በሺህ ሰባት መቶ ዓ/ም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥታቸውን አጽራር ሰገድ ብለው አነገሡዋቸው።

ከዚህ በኋላ አጼ ቴዎፍሎስ ሹም ሽር ካደረጉና ለመንግሥትንት ያደረሷቸው የረዳቸውን ከሾሙ በኋላ የወንድማቸውን የአጼ ኢያሱን ገዳዮች የአጼ ኢያሱን ባለቤት እቴጌ መለኮታዊትንና ደውሎስን በአደባባይ ሰቀሏቸው ደጃች ዳርመሮንም ሸፍቶ እንደገና ደብረመዊእ ቤተ ክ/ ደውሎ ገብቶ ነበር ነገር ግን አጼ ቴዎፍሎስ ሊያዝሉት ቀርቶ አስይዘው አጼ ኢያሱን በገደሉበት ጦር በአደባባይ ተጨቅጭቆ ተገደለ ለዚሁ ኢያሱን አድያምሰገድን ለመግደል የተባበሩትን ሁሉ እያስፈለጉ በገመድ አንቀቸው።

ለዚሁ መንግሥት ያበቋቸው ራስ ዮስጦስን የእንደራሴነት ማዕረግ ሰጥዋቸው ባለ ንጉሡ ነገሥት በተባሉ በሶስት አመታቸው የአርባ አምስት እድሜ ሰው ታመው በሺህ ሰባት መቶ ሶስት ዓ/ም ላይ አረፉ በዚህን ጊዜ ራስ ዮስጦስ የጻድቁ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ከሌሉላት እሉኔ የሚወለዱ ስለሆነ መንግሥቱን ለመያዝ የሚያስፈራቸው ነገር ስላለ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥታቸውን ፀሐይ ሰገድ አሰኝተው ነገሡ የጉንደር ሕዝብ በጣም ይወዳ

ቸው ነበር እሳቸውም የልደታን ቤተ ክርስቲያን አሥርተው
ሆኖ ግን አምስት ዓመት ነግሠው የሆድ በሽታ ስለታመሙ
ከዲማ ጊዮርጊስ ባላባት ከሆኑትው ከማርዳማዊት እጼ ኢያሱ
አድያም ሰገድ የወለዱትን የሃያ አንድ ዓመት ወጣት ዳዊትን በአቡነ
ማርቆስ እጅ ቅባአ መንግሥት ተቀብተው ስመ መንግሥቱን አድባር
ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ብለው በዚህ ሰበት መቶ ዓመት
1708 ዓ.ም እንግሡአቸው ወዲያውኑ አጼ ዮስጦስ በጣም ታመው
ነበርና በሰባተኛው ቀን አርፈው በአሰሩት ቤተ ክርስቲያን በልደታ
ተቀበሩ።

አጼ ዳዊት በአባታቸው አልጋ ከተቀመጡና ዙፋኑን በ
ረሱ ጊዜ ለእናታቸው ለማርያማዊት ወንድም ፊታውራሪ
እኘ ሚካኤል የቢትወደድነትን ማዕረግ ሰጥተው የቤተ መንግሥት
ተቆጣጣሪና አዛዥ እንዲሆኑ አደረጓቸው። በዚሁ በአጼ ዳዊት
አድባር ሰገድ ዘመነ መንግሥት የቅባት ሃይማኖት ተከታዮች እንደ
ልባቸው ስለተፈቀደላቸው ይሰብኩና ያስተምሩ ጀመር።

አጼ ዳዊት የእናት የአባታቸው ልጅ በካፋን ታላቅ ወንድማ
ቸው ሸለሆነ መንግሥቱን ይቀማኛል በሀገር ላይ ሁከት ያነሳብኛል
ብለው ከሀገር ወደሀገር የንጉሥ ልጅ ሳይመስል ቅኔና መጽሐፍ
ይማር ነበርና እስፈልገው እሱን ለሚያዝ ልጄን እድርለታለሁ
ብለው በአዋጅ ተናግረው ኖር የመንፈሳዊ ተማሪን በ
የበግ ለምድ ለብሶ ከሚኖርበት ዳሞት ጉንጂ ቤተክርስቲያን
ዘማች ዘጊዮርጊስ እንበሚበዑስ ዳሞትን ይገዛ ነበርና በጠቋሚ
ፋን ካለበት ይዞ ለአጼ ዳዊት አስረከበ አጼ ዳዊትም ልጃቸውን
ሰጡት ደጃዝማች ዘጊዮርጊስ ትልቅ ሰው ስለሆኑባቸው የቢትወደድነ
ትን ማዕረግ ሰጥተው እንዲሆሩ አድርገው አጠገባቸው አስቀመጡ
ታላቅ ወንድማቸውን በካፋን ግን ከነገሥታት ልጆች ጋር ወህኒ
አምባ እንዲቀመጥና እንዲጠበቅ አደረጉ ይሄንንም ያደረጉበት የአ
የቋያ ሕዝብ የሚያውቃቸው ሆነ ስለደግነታቸው የሰማ ሁሉ ይወዳ
ቸውና በካፋ መጀ ነግሶ አይቀሩነው የሚሉ ባህታዊዎች ስለነበሩ
ተውና በበላዩ ይነግሡብኛል ብለው ተጠራጠረው ነው ይባላል።

አጼ ዳዊት ምንም ለቅባት ሃይማኖት ቢያደሉ በጣም በሥተኛ
ምቀኛ ሰው ለደሃ አዛኝ ነበሩ እጅ መንሻና ግብር ሆኖ የሚመጣ
ውን ገንዘብ ለቤተመንግሥት እንጅ እራሳቸው ወስደው አይበሉትም
ነበር ነገር ግን እጅ ሥራ አዋቂ ጽፈት መጻፍ ድርስት በእል መል

ይጠዱ ስለነበር በዚህ ሙያቸው በሚያገኙት ገንዘብ ብቻ ይኖሩ
ነበር ።

አጼ ዳዊት መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ማንው የሰው ገንዘብ
ሳይደባልቅ ደክሞ ባፈራው ገንዘብ የሚኖር እሷቸው ገበሬ ነው
ብለው ሲመልሱላቸው ከገበሬዎች ውስጥ ሽማግሌዎችን አምጡልኝ
ብለው ከነሱ ጋር የሰንበቴ ማህበር ገብተው ይ ጠጡ ጀመር ሆኖ
ግን ከእለታት አንድ ቀን አንዱ ማህበርተኛ የኮረፈውን ጥሩ ጠላ
ደጋግሞ ጠጥቶ ሰክሮና አጼ ዳዊትን ተነስቶ በጥፊ መታቸው ከዚህ
መልስ በሰውም ተነስቶ እንዲገድሉበው ሲል ተውት ሰክሮ ነውና ወስዳ
ችሁ ከቤቱ አስቀምጡት አሉ ።

በማግስቱ ችሎት ተዘርግቶ በዚሁ ሰው ! ላይ ፍርድ ተጀመረ
ሊቃውንቱ የሞት ፍርድ ፈረዱበት ።

እንደዚሁ አራቱ ሊቃ መኳንንት ባለፍትሃ ነገሥቶች ዘያወርድ
እዴሁ ላዕለ መሲሁ እግዚአብሔር ይትመተር እንዲሁ የሚለውን ጠቅ
ሰው እግዚአብሔር በንጉሡ ላይ እጁን የሚዘረጋ እጅ ይቆረጥ
ብለው ፈረዱ ።

አጼ ዳዊትም ወንጀለኛውንና ዳኞችን ወደቤት ወስደው አንድ
ጀንፎርና የአንበሳ ለማዳ አምጥተው ሲያቆሙ ጀንፎሩ አንበሳ
ውን አይቶ ይንቀጠቀጥ ጀመር በኋላ ግን ጠላ አቀረቡለትና ጠላውን
ጀንፎሩ ጠጥቶ ሰክሮና ከአንበሳው ራስ ላይ ወጥቶ ይቀናጣ ጀመር
እውነስ በማን ትፈርዳላችሁ ቀድሞም ከገበሬ ጋር ማህበር በመጠጣቴ
ያጠፋሁ እኔ ነኝ በማህበር ባንገናኝ ኖሮ ይህ ሰው መቼ ይደፍረኛል
ብለው ወደችሎት ተመልሰው ምሕረት አደረጉለት ወደቤቱ በሰ
ላም ሰደዱት አጼ ዳዊት አምስት ዓመት ከገዙ በኋላ በተወለዱ
በሃያ ስድስት ዓመታቸው በሺህ ሰባት መቶ አስራ ሶስት ዓ/ም እሬ
ቶና ታዳት ወንድማቸው በካፋ ከወህኒ ወጥተው በአባታቸው አልጋ
ተቀመጡ ።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት

የአጼ በካፋና የልጃቸው ዳግማዊ ኢያሱ የልጅ ልጃቸው የኢዮአስ ዘመነ መንግሥት

ከመጀመሪያ የበካፋን አስተዳደርና ከመንገሣቸው በፊት ያሳለፉት በድትግና ችግር እጽፍላችኋለሁ ።

አጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ትንሹ ንጉሥ በኢትዮጵያ በተ በአሰረኛው ዓመት በሸህ ሰድስት መቶ ሰማንያ አምስት (1685 ዓ.ም ወ ጉጃም ሄደው የአባቶቻቸውን ትክል የሆኑትን አብያተ ክርስቲ ሲጎበኙ የአመፀውንም ሀገር ወግተው ሲያስገብሩ ባለ ምድረ ዲ ከሚባለው ሀገር ሄደው ሳለ በእናቸው በኩል በምንጉሣዊ ቤተሰብ የሆ አቤቶ ሚካኤል በሰልፍና በክብር ተቀበሏቸው ከዚያም የአቤቶ ሚካ ኤል ታላቅ ልጅ ማርያም መቅኢት ። (ማርያማዊትን) የምትባለው ለን ጉሡ ንጉሥቱ ባሉበት አዳራሽ ግብር ሊታገባ በሰረያምዝ ታጅባ ግብ ሩን በመሰብ ወርቅ አሸከማ ገባች አጼ ኢያሱም ገና ሲያዩዋት መል ክና ውበት ተሰማምተው ያኤጡዋት ከተንጀናዋ ሌላ በምትናገር ጊዜ የድምጿ ማማር ይሄነው ብለው ለመናገር እስከሚሳናቸው ድረስ በፍቅር ተያዙ ከዚያም አብረው በአንድ ላይ ሰንበቱ ማርያማዊትም ጥብቅ ነበረችና በካፋን ወንሳ 1686 ዓ.ም ሐምሌ አንድ ቀን ወለደ ስሙንም በካፋ አሉትው ።

አቤቶ በካፋ ዲማ ተክለአልፋ መምህር ተቀጥርላቸው ለፍ ደግመው ዜማና ቅኔ እየተቀበሉ ሳሉ አባታቸው አጼ ኢያሱ ከሰዐት ይብር ድረስ መጥተው ከአኖሩአቸው በኋላ በጣም ከመልካቸው በሀ ቸው ስለአስደነቃአቸው ወደ እናሪያ ሲሄዱ ይዘዋቸው ጉን በጉን እያወሩ ይሄዱ ነበር በካፋ የግስላ ለምድ ለብሰው ጦር የሚያዩ ሁሉ ካሆናቱ ባህታዊ ወደፊት እንደሚነግሡ" ይነገሯቸው ጀመር አባ ታቸው ከእናሪያ ሲመለሱ ወደጉንደር ይዘዋቸው ሄደው የቤተ መን ግሥት ሥርዓት ሲያስተምሯቸው ሳለ የአባታቸው ልጅ ራስ ተክለ ይማኖት በመርዝ ሊያስገድላቸው እንደተማከሩ ሰምተው ከአባታቸው ሳይሰናበቱ ተራ ሰው መስለው ወደ ማህበረ ስላሴ ገዳም ተሰደዱ

ከዚያም አባታቸው አጼ ኢያሱ እድሜያቸው ሰባት እንደሚያከብሩላቸው
ሰምተው በሱዳን አድርገው ወደ ግብፅ ሲሄዱ ሲሉ ከመንገድ ታመው
ሞተው የቋራ ቀኛዝማች እሸቴ ጌታ አግኝቶ ወደቤቱ ወስዶ
ለአጼ ኢያሱ ልጅ መሆናቸውን ሳያውቅ ያስተምሯቸው ጀመር
ከመልካቸው ማማር የተነሳ ልጁን አጋብቶ ሊያስቀምጥ ወዶ ታላቂ
ቱን ልጅ ልዕልት ምንትዋብን እንድታስተምሯቸውና እንድታገለ
ግላቸው አደረገ ።

ከዚያም አቤቶ በኋላ እንደተሻሻላቸው ከምንትዋብ ጋር በግብረ
ሥጋ እንደተዋወቁ ዘመዶቼን እያቼ እመጣለሁ ብለው ወደ ዳሞት
ሄዱ ከዚያም የበግ ለምዳቸውን ለብሰው የንጉሥ ነገሥት ልጅ መሆ
ናቸውን ሳይገልፁ በድብቅ ከአንድ ጎብር ወደ አንዱ እየተዘዋወሩ
ሲኖሩ የአጼ ኢያሱ ልጅ በኋላ መጥፋታቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ
ስለሚያውቅ አንዳንድ ሰወች ይሆናሉ ተብለው ይጠረጠሩ ነበርና
ንጉሥ ዳሞት ውስጥ ሳሉ ወንድማቸው አጼ ዳዊት ያስፈልጓቸው ስለ
ነበር የዳሞቱ ገዢ ደጃዝማች ዘጊዮርጊስ በጠቋሚ አገኛቸውና ይዞ
ወስዶ ለአጼ ዳዊት አስረከበ አጼ ዳዊትም ይፈሯቸውና በበላያቸው
ይነግሡብኛል ብለው ወሀኒ አምባ በዘብ እንዲጠብቁ አደረጓቸው ።

ከዚህ በኋላ አጼ ዳዊት አምስት ዓመት ገዝተው በሺህ ሰባት መቶ
አስራ ሶስት ዓ.ም በሞቱ ጊዜ ደጃዝማች ዘጊዮርጊስ በኋላን ይዞ በመጣ
ጊዜ የቢትወደድን ማዕረግ አግኝቶ እንደራሴ ነበረና በኋላ የንጉሥ
እንደዚህን ያስፈኛል ብሎ ከበሊጣ አጼ ኢያሱ ከወይብር ማሚት የወ
ለዱትን አቤቶ ወልደ ጊዮርጊስን እናንግስ ብሎ መማፍገቱን ጠየቀ
እነሱም ይፈሩት ስለነበር እሺ አሉት ከዚያም የእሁቱን ልጅ ራስ
ቢትወደድ ዘጊዮርጊስ አንግሶ አጼ ዳዊት አርፈዋል ወንድማቸውን
አቤቶ ወልደ ጊዮርጊስ አንግሠናል ብለው በአዋጅ አናገሩ ።

በዚህን ጊዜ የቤጌምድሩ ገዢ ደጃዝማች አምሃየስ በቀና በኋላን
ይወዳቸው ነበርና ከታሰሩበት አውጥቶ ለማንገሥ ብሎ ሠራዊት ይዞ
ዘምቶ ፈረሰው ቀጋ መድረሱ ሲሰማ በወሀኒ አምባ የነበሩት የንጉሥ
ሥታት ልጆች አደራ በንግሥ ጊዜ ከዚህ አስረህ እንዳታኖረን ሲሉ
ቃል ግባልን አሏቸው ። እሳቸውም እሺ ብለው ከወሀኒ አምባ
ወጥተው ከደጃዝማች አምሃየስ ጋር ተገናኙ ወዲያውኑ የንጉሥ ንጉሥ
ነቱን ሰባስ አልብሰው በንጫ ፈረስ ላይ አስቀምጠው መስከረም እያስነቀ
ነጋሪት እያስመቱ ወደ ጎንደር ከተማ ይዘዋቸው ገቡ በዚህን ጊዜ
ቤቱ ከርስተደሉና እጨጌ ተክለሃይማኖት ከሊቃውንቱ ጋር ወታደሩም
ሕዝቡም በአንድነት በሰልፍ ሆኖ ተቀበላቸው ።

ከዚህ በኋላ ጳጳሱ አቡነ ክሊስቶቶስ ደብረብርሃን ሥላሴ ቅባ መንግሥት ተቀብለው ስራማ ማሰሬው ዘውዱን በራሳቸው ላይ ደፉ ላቸው ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ መሲህ ሰገድ ተብለው ሥርዓ ንግሳቸው በደንብ ተከበረ ከዚህ በኋላ አዋጅ ነጋሪው ወደ አደባባ ወጥቶ የእቤቶ ወልደ ጊዮርጊስ ግዛት ስድስት ሰዓት ብቻ ሆኖ ሲቢ በአጼ ዳዊት ዙፋን ላይ ወንድማቸው በከፋን አስቀምጠን እንግ ናል ጠላቶቻቸውን ይፈሩ ወዳጆቻቸው ይደሰቱ ብሎ አወጀ ።

አጼ በከፋ መሲህ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ ተብለው በአባቶቻቸው ዙፋን እንደተቀመጡ የመንግሥቱን ሥራ ሲጀምሩ እ ሪዎችን ሁሉ በነጻ ለቀቁ ሹም ሽር አደረጉ ። ነገር ግን ግማሽ ቀን ገሠውን ወንድማቸውን ወልደ ጊዮርጊስን ብቻ ወዘኒ አምባ እን ቀመጥ አደረጉት ጠላታቸው የነበረውን ራስ ቢትወደድ ዘጊዮርጊስ ግን ከሥልጣን አውርደው በእደጋቸው ቀላ ተራሰው ሆኖ እንዲቀመ አደረጉ ።

እንደዚህም ሆነ አጼ በከፋ ንጉሠ ነገሥት በሆኑ ጊዜ ተዋናይ የሚባል የትንሽም ተማሪ ለንጉሡ ቅኔ አበርክቶ ሽልማት አገኘ ሁለተኛም አብረን በቅኔ ትምህርት ቤት የተማርን ጓደኛዬ በሊ የድብር እሌቅና ። (እለቃ) ያደርጉኛል ብሎ ከአደረበት ሀገር ከም ዲማ ወደጉንደር ይመጣል ከዚህ መሐል ንጉሠ ነገሥቱን የሚ በት ሰዓት አጥቶ ሳለ ከእለታት አንድ ቀን ለካህናት አጼው ግብ አርገው ነር ከካህናቱ ጋር ደብሎውን ለብሶ ደከዚያም እን ዎች ቀዳና ቀዳሽ ልብስ የለበሰ ስለማያስገባ ከለከሉት ራውም በንዴት የነደኛን በካፋን ግብር እንዳልበላና ቅኔ እንዳል ትከለከሉኝ ብሎ ሲናገር አጼውን ጓደኛ አደረጉቸው ይዞ ንጉሡን ቀና የሰደበ ተብሎ ተይዞ እስር ቤት አስገቡት አንድ ቀን ንጉሡ እስር ሲጉበኙ ገብተው ሳላ ነው ንጉሡ ንጉሥ ብሎ የተናገረው እንደ ብሎ ቅኔ ገባሉ ቃና ተቀኘላቸው ።

በካፋ ኢትርስአ ዘተዋነይኑ ከሉን

እንዘ አብ አብርሃም አንተ ወብእሲተ አብርሃም አነ ትርንጉም ፤

በከፋ የአብርሃም አባት አንተ በታራና የአብርሃም

ሚስት እኔ ሣራ ሁለታችን የተጠሞወጉንውን እ

ይዳም ማለት ምሳሌው የአብርሃም አባት ስሙ ታራ ሲ

እንዘ ሲጠመር ስራይሆናል ። የአብርሃም ሚስት ስም ሣራ

ዶች በስዕሉ የታሪኩ ተዋናዮና በካፋ ምድረ ዲማ በጉንጂ በደብረው ሪቱ አብረው ሲማሩና በአንድ ላይ ያደጉ ጓደኞች ናቸው ከእለታት አንድ ቀን ሁለቱ ሜዳ ተቀምጠው በካፋን ሲታድግ ምን ሊመሆን እፈልጋለሁ [አላቸው እኔ በእባቱ በኢያሱ ዙፋን ተቀምጬ ኢትዮጵያ ለመግዛት እመኛለሁ አሉት እሱ ደግሞ የቅኔ መምህር ሆኜ ለመኖር እፈልጋለሁ አላቸው በካፋም እግዚአብሔር አባባችን ይመላው አሉት እሱም እግዚአብሔር የፈጸመልን እንደሆነ ያችን ተቀምጠን የትናን ናትን ምኞች እንዳትረሳ ተባባሉ በዚህ ጊዜ እጼ በካፋ ቅኔ አዋቂ ነበሩና ወዲያውኑ አስጠርተው አንተ ማነህ አሉት እኔ ተዋንኝ ለምን ታመጊስ ! ለአንተ ትኔ ላበረከት ብመጣ አታነፉምችሁ አስረው ከዚህ አምጥተው ከተቱኝ ሲላቸው በጣም ደወዱት ነበርና አል ቸሰው ተታቅፈው ተሳሳሙ ከዚያም ለጓደኛቸው ፍቅር ሲሉ እስ ረኛውን ሁሉ በነጻ ለቀቁት ግብርም አደረጉለት ደስታ ሆኖ በቤተ መንግሥቱ በነበተ ከዚያም ከእኔ ጋር ተቀመጥ የፈለከውን ስልጣን ልስጥህ ቢሉት እንቢ ብሎ ካባና የወርቅ መቋሚያ ተሸልሞ የደ ብር አለቃ ሆኖ ወደ ጉንጂ ተመለሰ ለዚሁ ለተዋንይ ሲሉ ታናሽ ወንድሙን ሲኖዳን ከዲማ አስመጥተው የበጋፊ ትእዛዝን ሥልጣን ሰጥተው ካህናቶቻቸው አስቀመጡት እሱም አባ ሲኖዳ እየተባለ ሲያም ነበር ሌላም ተደፊብሊ ማዕረግ ነበረው አግናጉ ሲኖዳ በተባለ ቦታ ሀገር ሄዶ ሲኖዳ ደብር ተከሏል ።

እጼ በካፋ በስደት ጊዜ ታመው ከመንገዱ ላይ ወድቀው ሳለ ተኛሁባቸው እሸቱ ጌታ ከቤቱ ወስዶ እንደሴት ሲያስታምማቸው ወና ልጇን ተዋበችን እንደ ታሲታምማቸው በማዘዙ ከዚያም መጣሁ በኋላ ሳይመለሱ በመቅረታቸው ውለታው ሁሉ ትዝ ብሏቸው ወደዱሬ ሄደው ለእሴት ምትዋብን ለማግባትና ወደ ጉን ደሬ ለማምጣት ወሰኑ መጀመሪያ እንደነገሩ ያገቡት ወይዘሮ አወለደ ንግሥት ባልታወቀ ሕመም የሙርጉሰት በለሞቱ እጼ በካፋ እግዚአ ብሔር አልፈቀደልኝም ብለው ያለሚስት መኖር ወሰነው ነበሩና አሁን ግን ደችው ምንትዋብ ድንግልናዋን በቀድታ ቤተሰቦዋ ሁሉ እከብረ ቸው ሳለ ወጥተው በመቅረታቸው ተፀፅተው እግዚአብሔር ምንት ዋብን ብቻ እንዲፈቀድላቸው ተረድተው ወዲያውኑ ወደዱሬ ሄዱ ከዚ ያም የንጉሡ ነጋሪት መሬድ በተሰማ ጊዜ የዱሬ ሕዝብ በደስታና በክብር ተቀብሏቸው የሀገሩ ገበርም ሕዝቡን አዝዞ ንጉሡ ነጋሪት ግብር የሚያበላበት ትልቅ ዳስ አሠርቶ ነበር ።

እንደዚህም ሆነ ከፀኃፊ ትእዛዝ ሲኖዳ ጋር ተማክረው እሳቸውን የሚመስል ሰው አስቀምጠው ከሁለት ጋሻ ጃግሬዎች ጋር በርኖስ ለብሰው በድብቅ ወደ ምንትዋብ አባት ቤት ሄዱ አባትዋም ቀኛዝማች እሸቴ አፅመ ጊዮርጊስ (የአጼ በካፋ ስም) ደህና መጣህ ብለው በክብር ተቀብለው ሚስትህ ይቻትና ከሚስትህ ጋር ተቀመጥ እኔ ግን ደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ሀገሬን መጥተው በመርገጣቸው በጣም ደስ ብሎኛል በሰላም ተመልሰው እስከሚሄዱ ከፊታቸው አልቀርም አሉ አፅመ ጊዮርጊስም እኛስ አብረን ሄደን ከዚያው ብናገለግል አሉት ቀኛዝማችም ከመንገድ ስለመጣችሁ ብዬ ነው እንጅ እን ሂድ አብረን ልላችሁ ነበር ከሆነላችሁ ቅኔ ብትቀኙላቸው ክብር ታገኛላችሁ እያሉ ምንትዋብም በንጉሠ ነገሥቱ ፊት የሚቀርብ መሶበ ወርቅ ተሸክማ ከቀኛዝማች እሸቴ ጓታ ጋር የንጉሠ ነገሥቱ ድንኳን ወደ ተተከለበት ሰፈር ደረሱ ከዚያም በየአለቃው ወታደሩ ተሰልፎ ግብር ሲደረግ ደረሱ ፀኃፊ ትእዛዙ አዛዥ ሲኖዳም ሲያቸው ምንትዋብንና አፅመጊዮርጊስን የተባሉትን በካፋን ወደንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ድንኳን የወርቅ አልጋ (መቀመጫ) በክብር ወደተዘረጋበት ለይቶ ወስዳቸው ከዚያም ለልዕልት ምንትዋብ ተዘጋጅቶ የመጣውን የሠርግ ልብስና በራሳቸው ላይ የወርቅ አክሊል አደረጉላቸውና ከአጼ በካፋ ጋር ሕዝቡና ሠራዊቱ ወደተሠለፈበት ትልቅ ዳስ ወጡ ከዚያም መጽሐፈ ተክሊል ተነቦ ደንበኛ የጋብቻ ሥርዓት በደስታና በእልልታ ተፈጸመ ።

ግራዝማች እሸቴ ጌታ ግን ከደስታው ብዛት በጣም ታሞ ከሁለት ቀን በኋላ ስለተሻለው ወደንጉሠ ነገሥቱ አጼ በካፋ ዘንድ ቀርቦ ደጃዝማች እሸቴ ጌታ ቀብሎ የደንቢያን የአለዳ ጣቁሳን ግዛት ተሰጠው ከዚህ በኋላ አጼ በኩፋና ባለቤታቸው ልዕልት ምንትዋብ ወደ ጐንደር ሄደው በትልቅ ሰልፍና ክብር ጥሩንባና መለከት እየተነፋ ወደ ተዘጋጀላቸው አዳራሽ ሄዱ በበነጋታው ብዙ ሊቃውንት መሣፍንት ባሉበት የእቴጌነት ማዕረግ ሰጥተው በራሳቸው ላይ አጼ በካፋ ዘውድ ደፋላቸው ።

እቴጌ ምንትዋብ አጼ በካፋን እንደአገቡ በአመታቸው አቤቶ ኢያሱን ወለዱ እቴጌ ምንትዋብ ከመልካቸውና ከደም ግባታቸው ሌላ አስተዋይና ብልህ ነበሩ ወንድማቻቸውን ወልደልዑል እሸቴን የነጮ እሸቴ ተስፋ ኢየሱስ እሸቴን ማሙዬ እሸቴን ከቋራ አስመጥተው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ እንዲኖሩና የመንግሥትን ሥርዓት እንዲያጠኑ አደረጉ ከዚያም ሁሉም ሁሉም ሥልጣን አግኝተው በው

ጭና በቤተመንግሥቱ ውስጥ ያዙበት ነበር እቴጌ ምንትዋብ ከን ጉሥ አንበሳ ዳዊት ከአጼ ልጅ ከፊቅጦርዘር የሚወለዱ ባላ ባት ናቸው እናታቸው ግን ከፖርቱጋል የተወሰዱ ናቸው ። አጼ አጼ በከፋ መሲህ ሰገደ ምንም በአንዳንድ ሀገር የጋሲ ዘር ነኝ እያለ ሀገር በያወክና ቢያምፅ በጦር መሪዎቻቸው እየጠፋ የኢትዮጵያ ሀገሮችን ዘጠኝ ዓመት ገዙ በዘጠነኛው ዓመት ላይ ጠላትና ወዳጅን ለመለየት ሳይታመሙ ታምሜአለሁ ብለው ተኙ እጅ ሊነሳ የሚመጣውን መሣ ፍንትም አጼ ታመዋልና ማንኛውም ሰው ሊያቸው አይችልም እያሉ መለሰሷቸው ።

በዚህን ጊዜ ብላቴን ጌታ ኰቶ ወታደሩን ሰበሰበና አሁን ንጉሠ ነገሥቱ በጣም ታመዋልና ከወህኒ አምባ ያለውን ወልዲ ጊዮርጉስን እናንግሥ ብሎ ከጉንደር ወደወህኒ አምባ ሲሄድ አጼው ሰምተው ከቤተ መንግሥቱ በፈረስ ሆነው ወደአደባባይ በታዩ ጊዜ መኳንን ቱና ሕዝቡ ተገልብጦ ወደ እሳቸው መጣና እጅ እየነሳ ይሰግድላ ቸው ጀመር ።

ከዚያም መኳንንቱን ነገ እማነጋግራችሁ ስላለ ወደየቤታችሁ ሂዱ ብለው ከካህናቱ ጋር በፍቅርና በሰላም ሲነጋገሩ ዋሉ በበነጋ ታው ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው በአደባባይ ተቀመጡ መኳን ንቱም እጅ እየነሳ ግራና ቀኝ እንደየማረጉ ተቀመጠ ።

አጼ በከፋም እንዲህ ሲሉ ተናገሩ ለጥቂት ቀን ታምሜ ብተኛ በከተማ ሽብር ያስነሳችሁ ለምንድነው ብለው መኳንንቱን ቢጠይቁ መኳንንቱ እየተነሱ እኛ ለእርስዎ ሕይወት ከማሰብ በስተቀር ምንም የበደልነው ነገር የለም ነገር ግን በከተማው ሕዝቡ እንዲረበሽ እንዲ ታወክ ያደረጉ የወንድምዎ የወልደ ጊዮርጊስ እህቶችና ዋናው የጦር አላቃ ብላቴን ጌታ ኰቶ ናቸው ብለው እየተነሱ ተናገሩ ስለዚህ በአ ድማው መገኘታቸውን ሕዝብ ማወካቸው ስለተረጋገጠ ብላቴን ጌታ ከቶና የአጼ ኢያሱ ልጆች የንጉሠ ነገሥቱ እህቶች ወለተ ሩፋኤ ኤልና ወለተ እስራኤል ተይዘው በአደባባይ ተገደሉ ።

አጼ በካፋ መሲህ ሰገድ የሚወዳቸው እናታቸው ከጐጃም መጥ ተው ጐንደር ይኖሩ ነበርና ታመው ።በመጨረሻ አረፉና በታላቅ ሃዘ ንና ፍታት ደብረ ብርሃን ሥላሴ በክብር ተቀብሩ ። እናታቸው ወይ ዘሮ ማርያማዊት እንደሞቱ እስከ አርባ ቀን ሲያዝኑ ሲያለቅሱ ሰነ በቱ ከዚያም ከጣና ሃይቅ ደሴት ወጥተው ተዝጋካራቸውን አደረጉላቸው በዚህን ጊዜ ፀኃፊ ትእዛዝ ሲኖዳ ለዚሁ ሀዘን ማስረሻ የሚ

ሆን ድርሰት መርስኤ ሃዘን የሚባል መጽሐፍ ፅፎ ስለአበረከቱላቸው የ
ርቅ እንባር ሸለሙት ከ ጐጃም ከብዙ ሊቃውንት ጋር ሊቁ ፈሰን ቅ
ያት የተባለው ተሞናይ መጥቶ ከእጼ ባካፋ በፊት የነገሥታት ያሉ
ረሰላቸው ድርሰትና ቅኔ አቀረባላቸው የተጻፉት መጽሐፍቶች አስ
ለየራሳቸው ሰባ ሰባ የሚሆኑ የቅኔ ግጥሞች እሷቸው ለዚሁ ሊቱ
ንይ ፊት ከሰጡት ሌላ የወርቅ መቋሚያ ዘረያው በብሩና በሰማያ
ሐር የተጠለፈ ሻሽ አብረውት ለመጡት ካባና ፀናፅል እንደየደረ
ቻው ሸልመው አስደስተው ላኳቸው እናታቸው በሞቱ በአምስ
ኛው ወር ፀኃፊ ትእዛዝ ሲኖዳ ሞተና በጣም ደንግጡ አዘኑ ከዚያም
ከሕዝብ ተለይተው ሱባኤ ገቡ ።

እጼ በካፋ መሲህ ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በ
ስረኛው ዓመት በተወለዱ በሰላሳ ስድስት ዓመታቸው 1723 ዓ.ም.
ቀኖና እንደገቡ ታመሙና አረፉ በዚህን ጊዜ እቴጌ ምንትዋ
ከቋራ ያሉትንና በግዞት ወደ ዳሞት የሄደውን ወንድማቸውን ደጃ
ማች ራስ የሆኑትን ወልደ ልኡል እሸቴን ደጃች አውሳ
ፉስ ነሙንና አባቴን ግራዝማች ነሙ እሸቴ እስከሚመጡላቸው
ድረስ የንጉሠ ነገሥቱን ሞት ደብቁ ከዚያም ወንድሞቻቸውን
ከመጡ በኋላ ልጃቸውን አቤቶ ኢያሱን ዳግማዊ እጼ ኢያሱ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስመ መንግሥት ብርሃን ሰገድ ብለው
ከአነገሱ በኋላ ንጉሠ ነገሥታችን እጼ በካፋ አርፈዋል ። ልጃቸውን
ዳግማዊ እጼ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መንግሥታቸውን
ብርሃን ሰገድ ብለን አንግሰናል ጠላታችን ይፈር ወዳጃችን ይከ
በር ብለው በአዋጅ ተነገረ የእጼ በካፋ ቀብር በአስሩት መኪ
ሆኖ ከብርጊዳ ገዳም መጥቶ ጉንደር ደብረብርሃን በክብር ተቀበረ።

ዳግማዊ እጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ተብለው በአባታቸው ዙፋን ሲቀመጡና አልጋውን ሲወርሱ በአንድ
ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ሰስት አመት ምህረት የስምንት አመት
ልጅ ነበሩ ስለዚህ እናታቸው እቴጌ ምንትዋብ እሸቴ እንደንግ
ሥት ንገሥታት ሆነው ዘውድ ደፍተው በመንግሥቱ ያዙበት ይሸመ
በት ነበር ።

እቴጌ ምንትዋብ አጼ በካፋ ከመሞታቸው በፊት ወንድሞቻ
ውን የወንድሞቻቸውን ልጆች ከቋራ አስመጥተው ሥልጣኑን ሁሉ
አሲዘዋቸው ስለነበር ማንም ሊደፍራቸው አልቻለም ነገር ግን ግ
ባይሰካለት ራስ ቢትወደድ ዘጊዮርጊስ በወልደታይት በእጼ በካፋ

ትእዛዝ እንደሚገዛት ሆና ይኖር ነበርና ብዙ ሰው አስነስቶ የኢሁቴን
ልጅ አቤቶ ወልደጊዮርጊስን ከወህኒ አምባ አውጥቶ ሊያነግሥ ወደወ
ሎ አምባ ተጓዘ ። ከዚያም ከአቴጌ ምንትዋብ ወንድም ከደጃች ወልደ
ልዑል እሸቴ ጋር ገጥሞ ሁለት ቀን ከተዋጋ በኋላ ድል ሆነና አብረ
ውት የነበሩትን ጭፍራ ሁሉ ተማርከው በእቴጌይቱ ትእዛዝ ተገ
ደሉ ።

እንደዚሁም በዓመቱ በኸርሮንድ ማሞ ቆቅ አዳኝ የሚባለው
ሥልጣኑ ተሽሮ ተራ ሰው ሆኖ በንደራት ይኖር ነበርና አቤቶ ህዝቅ
ያስን ከወህኒ አምባ አውርዶ ጉንደር በጦር ከበበው ። ሕዝቡም የእ
ቴጌ ምንትዋብ ወንድሞች ሥልጣኑን ከሁሉ ተምተው እንደያዙ
ስለሚያውቅና እነሱን በመጥላት እንደሆን እውቀው ወደ አቤቶ ህዝ
ቅያስ እየሄዱ ተጠመሩ ። ህዝቅያስንም እንግሰናል ብለው አወጁ ።
ነገር ግን ቀዳማዊ አጼ ኢያሱ ወታደሮች ቤተ መንግሥቱን እናስን
ኑም ከጊታችን ጋር እንሞታለን ብለው ጠንክረው ይዋጉ ጀመር ።
ጦርነቱ አራት ቀን ከሆነው በኋላ የዳሞቱ ገዢ ደጃዝማች ተስፋ ኢየ
ሱስ እሸቴ ከአዛዥ ጊዮርጊስ ጋር የአቸፈርንና የበሊያን የዳሞትን
ፈረሰኛ ጦር ይዞ በግስጋሴ ደረሰና ይዋጋ ጀመር ። ብዙ ሕዝብ
በሁለቱ በኩል አለቀ የሰው ደም እንደውሃ ፈሰሰ በመጨረሻ ሕዝቅ
ያስ የተባለው የነጋሲዎች ዘር ተማረከና ጦርነቱ ተፈጸመ ።

ለዚህ ጦርነት ቀስቃሽ የነበረው በኸርሮንድ ማሞ ቆቅ አዳኝና
ልጁ ተንሳይ ማሞ በአደባባይ ከሁለት መቶ አምስት ሰዎች ጋር
ተሰቀሉ አቤቶ ሕዝቅያስ ግን የነጋሲ ዘር በመሆኑና በግድ ተይዞ
ከወህኒ አምባ እንደወጣ ስለሚታወቅ ወደነበረበት ወህኒ አምባ ተመ
ልሶ ታሠረ ። እንጅ አልተገደለም ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ከእናታቸው ጋር እየተማከሩ ብዙ አብያተ
ክርስቲያናት ተክለዋል ። በጣና ደሴት በአቸፈር በዘጌ በበሊያ በቋራ
ትልልቅ አድባራት የተከሉ እሳቸው ናቸው ። ከነዚህ ሁሉ በጣም
አምሮ የተሠራው የክብራን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ነው
እንደዚሁም ዳግማዊ አጼ ኢያሱ አባታቸው አጼ በካፋ ከህናት ወዳ
ጅና እራሳቸውም በቤተ ክህነት ትምህርት ቤት እንዳደጉ ስለሚያው
ቁና ትምህርትም እንዲስፋፋ ስለሚፈልጉ አስተማሪውና ተማሪው
እንዲበረታ ያደርጉ ነበር ይሄውም ከቤተ መንግሥቱ ተዘጋጅቶ በየት
ምህርት ቤቱ ።

፮ኛ/ ለፊደል ቆጣሪ እንጀራና ወጥ

፯ኛ/ ለዜማ ተማሪ እንጀራና ወጥ ከጠላ ጋር

፰ኛ/ ለቅኔ ተማሪ እንጀራና ወጥ ከጠጅ ጋር

፱ኛ/ ለመጽሐፍትና ለድግዋ ተማሪእንጀራና ወጥ ጠጅና ጠላ እንደዚሁም ሲወርስ ካባ በርኖስ ይሸለሙና ይላክላቸው ነበር ። ስለ ዚህ በዳግማዊ አጼ ኢያሱ ዘመን ብዙ ሊቃውንቶች ተነሱ መጽሐፍት ንም ከአረብኛ ወደግእዝ እያስተረጐሙ በየገዳማቱ በየአድባራቱ ልክ ዋል አባታቸው በተወለዱበት ሀገር በአንዳንድ ደብሮች እሳቸው ያደሩ ቸው እኔ እራሴ መሪራስ ኤም በላይ አይቻለሁ አንብቤለሁ ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ለክብራን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ገዳም የሰጡት የመጽሐፍት አይነት ብዛት ሰባት መቶ አርባ ነበሩ ይህም ገዳም በመጽሐፍት ሐብታም ስለነበረ ከትግሬ ከሸዋ ከጐጃም ከጐንደር ያሉ ሊቃውንት በታንኳ እየገቡ አመት ሁለት ዓመት መጽሐፍቱን በማንበብና በመገልበጥ ጊዜያቸውን ያሳ ልፉ እንደነበር ዘግዱር ዘእንዳ ቤት በሰፊው ጽፎላቸዋል ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ለአባታቸው ክብር ሲሉ ለብዙ ካህናት የወርቅ ጫማ ሸለሟቸው እንዳያደረጉም ፈቀዱላቸው ከእሳቸው በፊት የቤት ክህነት ተማሪ ያደፈ ልብስ ይለብስ የነበረውን ከልክ ለው በከተማው ዙሪያ እንዶድ ተተክሎ ካህናቱም ተማሪውም በዚያ እያጠበ እንዲለብስ አደረጉ ። በሳቸው ዘመን መንግሥት ያደፈ ልብስ የሚለብስ እንደ ነውረኛ ይታይ ስለነበር የጐንደር ሕዝብ ነጫጭ ልብስ ለብሶ ከተማውን አሸብርቆ ይታይ ነበር ።

እንደዚሁም በሚካኤል ደብር በታች የሚገኘውን ሀገር ቃሮዳ በትእዛዝ ሀገሬውን ወይን አስተክለው በወይኑ ፍሬ ጠጅ እያስደረጉ በቤተ መንግሥቱ እሁድ እሁድ ለካህናት ያጠጡ ነበር ። ሊቃውን ቱም ያለፉትን ታላላቅ ነገሥታት ስምና የዳግማዊ ኢያሱን የእቴጌ ምንትዋብን ስም በቅኔና በወረብ እያነሱ ያመስግኑዋቸው ነበር በዳግ ግማዊ አጼ ኢያሱ ዘመን በኢትዮጵያ ሀገሮች ተድላና ደስታ ፍቅ ርና ሰላም ነበረ ሕዝቡም እንዲህ እያለ ይዘፍንላቸው ነበር ።

ወደአሰብኩት ሀገር ተነስቼ ልሂድ
ስንቅም አልሸከም ብወድም ባልወድ
ደስታ ከተድላ ጋር አለና ከመንገድ
በኢያሱ ዘመን በብርሃን ሰገድ

በአጼ ኢያሱ ዕድሜ እለምናለሁ
ከአሰብኩት ሀገር በደህና እደርሳለሁ
ዕድሜ እለምናለሁ ለአጼ ኢያሱ
ከቤቴ ስወጣ ስንቄ ነውና እሱ

ቁርስና ምሳውን መክሰሱን እራቱን እየተመገበ
ኧረ ለመሆኑ በኢያሱ ዘመን ማነው የተራበ

እቴጌ ምንትዋብ የቅድስት ቁስቋምን ቤተ ክርስቲያን ሽህ ወቄት አውጥተው ከገንቢዎቹ ጋር ጢጥትና ማታ አብረው እየዋሉ ሲያበራቱና ሲያግዙ ለጥሩ ሠራተኛም የተለየ የገንዘብ ጉርሻ እየሰጡ በሚያስደንቅ ሁኔታ አሠሯት ። ሥራው እንዳበቃ የህዳር ቁስቋም ዕለት ከአድባራትና ከገዳማት በመጡ በብዙ ሽህ ሊቃውንት ከፍ ባለ ሁኔታ ተከብራ ታቦትዋ ተባርካ ገባች በዚሁ ቀን ትልቅ ግብዣ ተደርጐ ዋለ በዚህ ግብዣ ላይ እቴጌ ምንትዋብ እንዲህ አሉ ሁልጊዜ በንግግርም በመጠጥም ካህን ያሸንፋል ዛሬ ግን እኔ ሳላሸንፍ አልለቀውም ምና ዋናውን የስርቆሹን በር ደህና አድርጋችሁ ዝጉ ለካህኑም የወይን ጠጅ እየደጋገማችሁ ስጡ ብለው እቴጌ አሳላፊዎቻቸውን አዘዙ ካህናቱም ከበሉ በኋላ ያማረውን የወይን ጠጅ እየጠጡ ሽንታቸው መጣባቸው ካሉበት ሥጋጃ ምንጣፍ እንዳይሸኑ ነውር ነው እንዳይወጡም በሩ ሁሉ በጥብቅ ተዘግቶ ማንም ሰው ግብሩ ግብዣው እስኪያልቅ እንዳይወጣ ለሁሉ ተነግሯቸዋል በዚህ ጊዜ ካህናቱ በሽንት ተወጥረው የሚያደርጉት አጡ በዚህ መካከል አንድ ካህን ተነሳና አንድ ነገር እንድጠይቅ ይፈቀድልኝ ብሎ እቴጌይቱ ወደአሉበት ጠየቀ እቴጌይቱም ተፈቅዶልሃል ጠይቅ አሉት ካህኑም አምስት መቶና አምስት መቶ ሲጋጠም ስንት ነው አላቸው እቴጌይቱም ሺነዋ አሉት ካህኑም ወደጓደኞቹ ዞሮ ሸነዋ ብለዋል እቴጌይቱ ብሎ ተናገረ በዚህን ጊዜ በሽንት የተቸገረው ሁሉ በየተቀመጡበት ምንጣፍ ሥጋጃ ላይ ሸና እቴጌይቱም በካህኑ ጥያቄ ተገርመው ሽልመው ሰደዱት ይሄውም ካህናቱ የእቴጌይቱን ቃል ለማክበር ስንል ሸናነዋ ብለው ተናገሩ ይባላል ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ወደእናታቸው ሀገር ወርደው ከከረሙ በኋላ በማህበረ ሥላሴ ገዳም ጐብኝተው ከዚያም የቅድመ አያታቸውን የፃድቁ ዮሐንስን መቃብር ጐብኝተው መተማ የሚባለውን ከተማ ቆረቆሩ የዮሐንስ ቤተ ክ/ ተክለው ካህናት ደልድለውበት ወደስናርና ወደሱኪ ከተማ ተጓዙ በዚህን ጊዜ የሥርና ገገር ባዲ ኢብን ሻሎክ

ይባል የነበረው በስልፍና በክብር ተቀብሎ አስተናገዳቸው ገፀ በረ ትና ግብሩንም አቀረበላቸው እሳቸውም የወርቅ ከታብ አደረጉለ ከዚያም ወደጀዚራ ተጉዘው የዳርፋሬ ባባት ጉሳዎችን ይዞ ሃማር ገርቢ የሚባለው መጥቶ በንጉሡ ወታደር ላይ አደጋ ጥሎ ብዙ ወ ደር ፈጁ ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ከጎቻቸው ተከፍሎ የሚሄደው ወታደ የኢትባርን ወንዝ እንደተሻገሩ ሰሙ በዚህን ጊዜ ተመልሰው ሲዋ ነበር ሠራዊታቸው ስለደከመ ወደሴቲት ተጉዘው ከዚያም ጉንደ ከተማቸው ተመልሰው ገቡ ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ከኑቢያ እንደተመለሱ የአጼ ልብነ ድንግ ዘር በማለት መርዕድ አዝማች አብዬ በሸዋ ለዳግማዊ እያሱ አል ዛም ብለው ሸፈቱ ነገር ግን በብዙ ካህናትና መነኮሳት እርቅ ተ ርጉ ጦርነቱ ቀረ ።

እንደዚሁም የተነቤኑ ራስ ሚካኤል የንጋሲነት ዘር አለኝ ብ በዳግማዊ አጼ ኢያሱ ላይ ሸፈተ ወደእራሳቸው የሚላከውን ሁ ከለከለ በዚህን ጊዜ ከሰባ ሽህ በላይ የሚሆን ጦር ይዘው ሄደው እ ካለሁበት ድረስ ና ብለው ቢልኩበት ከአርኪቆ ገገር ከናይቡ ጋ ተሰማምተው ኑሮ እንቢ አሉ ከዚያም ራስ ሚካኤል የራያንና በ ቦን ጋላ አስታጥቀው እራሳቸው ሰማያት ወደሚባለው ተራራ ተደዘ በድል አድራጊነት ንጉሡ ነገሥቱ ይዘዋቸው መጡ ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ከወቀሷቸው በኋላ ሞቱ ቀርቶ ራስ ሚካ ኤልን ወህኒ እንባ እንዲቀመጡ ተደረገ ከትንሽ ወር በኋላ አ ኢያሱ ራስ ሚካኤልን ያከብሯቸው ነበሩና ፈቷቸውና የዘፋን ችሎ እማካሪ አደረጓቸው እህታቸውን አስቴር ዳሩላቸው ።

እንደዚህም ሆኖ እቴጌ ምንትዋብ አጼ በካፋን አግብተው ዳ ማዊ አጼ ኢያሱ ብርሀን ሰገድን እንደወለዱ በወጣትነታቸው ን አጼ በካፋ ስለ ሞቱ ደንበኛ ባል ሳያገቡ በኙሁ በዳግማዊ አጼ ኢያ እንደ ንግሥት ሆነው ከልጃቸው ጋር በፍቅርና በደስታ ይኖሩ ነበ ሆኖ ግን ምንም ደንበኛ ባል ባይኖራቸው ከአጼ ኢያሱ አድያም ሰ ድና ከዘለሳይቱ ከወይዘሮ ማሚት እንሰጣስዮስ ልጅ ከልዕልት ወለተ እስራኤል የሚወለደውን ኢያሱን መልምለው ይዘውት ይኖ ነበር ። ምንም በድብቅ እንዲባል አድርገው ቢይዙት ወይዘሮ አ ጣሽ ወይዘሮ አስቴር ወይዘሮ ወለተ እስራኤልን የሚባሉ ሴቶች ልጆች ስለወለዱ ሕዝቡ ምልምል ኢያሱ እያለ ሲ ሚጥጥ ስለሰሙ ሁለተኛ ምልምል እንዳትሉት ብለው እቴጌይቱ የ

ቆቱን ጌታ ማዕረግ ሰጡት ዳሩ ግን የእትጌ ምንትዋብ ባለቤት የነበሩት አጼ በከፋ ላብላቴን ጌታ ኢያሱ አጐት ስለነበሩ የአጐቴን ሚስት ያዘ እያለ የጐንደር ሕዝብ ያሽሟጥጥና ያማ ነበር በዚህ የተነሳ ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ከእናታቸው ጋር ተቀያይመው ከብላቴን ጌታ ኢያሱ ጋር ቂም ይዘው ሲኖሩ ከእለታት አንድ ቀን ብላቴን ጌታ ኢያሱን አስገድለው በድብቅ ባህር ውስጥ ጣሉት እሬሳውም ከባህር ውስጥ ወጥቶ በክብር ቅድስት ቁስቋም ቤት ክርስቲያን ተቀበረ ።

የሆነ ሆኖ ዳግማዊ ኢያሱ ከብላቴን ጌታ ኢያሱ የሚወለዱትን እህቶቻቸውን ለታላላቆች ባላባቶች ዝምድና ለመመሥረት መጣሪያ አደረጓቸው ከነዚህም ለታዬ እስራኤልን ለጐጃሙ ለደጃች ዮሲዲቅ ለተንቤን ባላባት ለራስሚካኤል አስቴርን ለትግሬ ባላባት ለራስ!ባሪያው ዘመርያም አልጣሽን ዳሩላቸው ኋላ ግን ራስ ገብሬ አገቧቸው እራሳቸውም ዳግማዊ ኢያሱ ከራያ ዘቦ ገገር የምትወለድውን ከየጁ ባላባት የወረሴህ ዘር የእማዞ ልጅ ውቢት የሚባሉትን እስላም ክርስትና አስነስተው ስማቸውን በርሳቤህ አሰኝተው አግብተዋቸው ነበርና የእቴጌ በርሳቤህ ወንድሞች እህታችን እንጠይቃለን እያሉ ከየጁ መጥተው በጐንደር ከተማ ይኖሩ ነበር እንዲያውም ለወንድሞቼ ሀገር ይሰጣቸው ከዚሁ ከእኔ እንዳይርቁ ብለው ባለቤታቸውን ስለጠየቁ ዳግማዊ ኢያሱም ቅማንቶች የሚኖሩበትን ሀገር እስከ አርማጭሆ ያለውን ሀገር ሰጣቸው ያንም ሀገር ከራያና ከየጁ ጋላ እየመጣ ስለተቀመጠበት እስከዛሬ ጋላ ሀገር ይባላል ቤርሳቤህ የተባሉት የውቢት አባታቸው አሚዞ ጉንጉል ናቸው እኚሁ እቴጌ በርሳቤህ ከዳግማዊ ኢያሱ ኢዮአስን ወለዱ ።

ዳግማዊ አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ በንጉሥ ነገሥትነት የኢትዮጵያን ሀገሮች በደስታና በፍቅር ሀገር ሳይራብ በሽታ ሳያጠፋው እልቂት ሳይኖር ሃያ አምስት ዓመት ከገዙ በኋላ የብላቴን ጌታ ኢያሱ እህት የምትሆን ወይዘሮ ሰንኪ በወንድምዋ ሞት ቂም ነበራትና ከመብል ጋር መርዝ ጨምራ ዳግማዊ አጼ ኢያሱን አብልታ በተወለዱ በሠላሳ ሶስት ዓመታቸው በሺህ 747 ዓ.ም ገደለቻቸው ።

እሬሳቸው በእሠሩትና በቆረቆሩት ገዳም ከብራን ቅዱስ ገብርኤል ጣና ደሴት ሄዶ በሳጥን በክብር ተቀበረ ከሳቸው ቀጥሎ ከእቴጌ በርሳቤህ የተወለዱት ኢዮአስ ንጉሥ ኢዮአስ ልኡል ሰገድ ተብለው በአባታቸው ዙፋን ላይ ሲቀመጡ የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት ለጋ ሰው ነበሩ እንደዚህም ሆነ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብ

ሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚመሩበትና በሚስተዳደሩበት ጊዜ እ
ታቸው እቴጌ በርሣቤህ እቴጌ ምንትዋብ ከልጃቸው ከዳግማ
ኢያሱ ጋር ሆነው ሲያደርጉት እንደነበር እኔም ከልጄ ከኢያሱ ጋ
ሆኘ የመንግሥቱን ሥራ ልሰራ የሚሻረውን ልሻር የሚሾመው
ልሹም አሉ ።

በዚህን ጊዜ ከእቴጌ ምንትዋብ ጋር ከፍ ያለ ጠብና ክርክ
እነሱ ልጃቸውም አጼ ኢዮአስ በሁለቱ ጠብ የተነሳ ተቸገሩ ሆኖ
እቴጌ ምንትዋብ ወንድሞቻቸው ሥልጣኑን ይዘውት ስለነበር የሚ
ፍራቸው ከሥልጣናቸው ሥልጣኑን ይዘውት ስለነበር የሚደፍራቸ
ከሥልጣናቸው የሚያወርዳቸው ጠፋ በዚህ አይነት እንዳሉ እ
ቤርሣቤህ ወንድሞቻቸውን ባልጋዳ ልበና ብርሌ የሚባሉትን
የጁ ባላቸውና ሺህ ዘጠኝ መቶ የጋላ ፈረሰኛ ጦር ይዘው መጥተ
በጉንደር ዙሪያ ዳግማዊ ኢያሱ በሰጧቸው ሀገር ላይ ድንገት ጦር
የተነሳ እንደሆን እህታቸውን ለመርዳት ተዘጋጁ ያንም የሰፈሩበ
ሀገር ጋላ ሀገር ይባላል እንደ ዚሁም ከቀን ወደቀን የፈረሰኛም የ
ረኛም ወታደር በየእለቱ እየሆነ ከየጁና ከራያ እየመጣ ጉንደ
ከተማ ገብቶ ተቀመጠ ለባልጋዳ ልበና የፊታውራሪነትን ለብር
የቀኛዝማችነትን ለአንደርታ ባልጋዳ ለአባታቸው አሚዞ የአዛገነ
ሥልጣን እኒሁ እቴጌ ቤርሣቤህ አስጥተው ከጉናንቸው አስቀመ
ቸው የእቴጌ ምንትዋብን ወንድም ራስ ወልደ ልኡልን የእንደራሴ
ቱን ሥልጣን ሽረው ንጉሥ ኢዮአስ ለእናታቸው ወንድም ለፊታውራሪ
ኞቻቸው በዚህን ጊዜ የጉንደር ሕዝብን እና መኳንንት ንጉሥ ኢዮአስ
ከመንግሥታቸው አውርደው አንዱን የነጋሲ ልጅ ከወህኒ አምባ አም
ተው እንደሚያነግሡ ስለሰሙና ሕዝቡም ስላልተቀበላቸው የእንደራ
ነቱ ሥልጣን በራስ ወልደ ልኡል እሸቴ እንዲቆይ ተደረገ ከዚያም
ወልደ ልኡል እሸቴ እንደሞቱ ልጃቸው ደጃች እሸቴ ተብለው
ትን ይገዛ ነበር ከዳሞት መጥቶ በአባቱ ራስ እሸቴ ወልደ ልኡ
ተብሎ የእንደራሴነት ሥልጣን ያዘ ይኸው ራስ እሸቴ በዳሞት ል
ደጃዝማች ዘውዴ ብሎ ሾሞ አስቀመጠው ይሄው ዘውዴ የ
ጉሹ አባት ነው ። ራስ እሸቴ ወልደ ልኡል የእንደራሴነቱን ሥል
ይዞ ቤያስተዳድርበት ጊዜ የአቤቶ ይስሃቅ ግላውዴዎስን ልጅ አ
ፋሲል ከበረና የሳዎች ጉጣ የተወለደ ነበርና የነጋሲነት ዘር አ
ብሎ ጃዊ የሚባሉትን ወገኖቹን በንጉሡ ኢዮአስ ላይ ጦር ነት አ
ያነሱ አደረገ ። በዚህን ጊዜ ራስ እሸቴ ጃዊዎችን ሊዋጋ ሄዶ ሳለ
ቤቶ ፋሲልና ከቀኛዝማች ብርሌ የተሰበ ወታደር በጦርነት ላይ

ግቶ ገደለው የገደለውም ወታደር ተይዞ በእቤቶ ፋሲልና በቀኛዝማች
ወርሴ ታዝዞ እንደገደለ ተናገረ በዚህን ጊዜ እቤቶ ፋሲል ይስሃቅ
እኔ በዚህ ነገር የለሁም እንደኛ ከዚህ ሰውዬ ጋር መናገር ቀርቶ
መልኩንም አሁን ነው ያየሁት ስላለ በሌሊ በኩል የጂዎች ለዚሁ
ለእቤቶ ፋሲሲ እንዋታለን እሱንም አላደረገ ስለእሱ ከጐንደር ውጥቶ
ወደዳሞት በቶሎ ሄደ ከዚያም የዳሞት ገገር ዳጃዝማች ዘውዴ ፊር
ተው በክብር ተቀበሉት ይሄውም ይነግሳሉ የሚባል ንግርት ስለነበ
ረው ነው ። ንጉሡ ኢዮአስ በነገሡ ጊዜ በዳግማዊ ኢያሱ ብርሃን
ሰገድ መጥተው ጐንደር የሚቀመጡበትን ራስ ሳህለ ሚካኤልን የት
ግሬን ግዛት ሰጥተው በትግሬ ሀገር ይኖሩ ነበር ነገር ግን በእና
ታቸው ወገኖች በየጂዎችና በእያታቸው ዘመዶች ቋራዎች መካከል
ስፍ ያለ ጠብና ቂም እየበረታ ስለሄደ ራስ ሳህለ ሚካኤልን ከትግሬ
አስመጥተው የእንደራሴነቱን ስልጣን ሰጣቸው ።

ንጉሥ ኢዮአስና እንደራሴያቸው ራስ ሳህለ ሚካኤል በየጊዜው
የሚረባና የማይረባው ነገር ሁሉ ያጣላቸው ጀመር የጐንደር ህዝብና
አካባቢው ግን በራስ ሳህለ ሚካኤል አስተዳደርና ፍርድ በጣም ደስ
ብሎት ይኖር ነበር በዚህ ጊዜ የእንደራሴነቱ ሥልጣን ለምን የእኔ
አይሰጠኝም የሚለው የዳሞት ገገር ደጃች ፋሲል የጃ ዊና የአገውን
ጦር ይዞ ጐንደርን ሊወርና ሊወጋ መጣ በዚህን ጊዜ ራስ ሳህለ ሚካ
ኤል ሃያ ሁለት ሽህ የትግሬ ጦር ነበራቸውና ሌላም ይጨምሩኝና
አብረን ሄደን እናውጋው ብለው ኢዮአስን ጠየቁ ንጉሡ ኢዮአስም
ደጃዝማች ፋሲልን ውስጡን መጥተህ ራስ ሳህለ ሚካኤልን ውጋና
ሥልጣኑን እንድትይዝ ብለውት ነበርና ፡ አልሄድም እራስህ ከጦርህ
ጋር ተዋጋ አሉት ራስ ሳህለ ሚካኤልም ጦራቸውን አሰልፈው ከአ
ዞ ወደ ላይ ሲጠባበቁት እቴጌ ምንትዋብ ለራስ ሣህለ ሚካኤል እን
ዲህ ብለው ምስጢር ላኩላቸው ንጉሡ ኢዮአስ ለጋላዎች አብሮ አን
ተን በድብቅ ሊያስገድሉህ የእሱን ወታደሮች ልኮአልና ተጠንቀቅ ።

ራስ ሣህለ ሚካኤልም የኢዮአስን ወታደሮች ግን ከእኔ ጦር
ተደባልቁ ያላችሁ ብለው አስገደሏቸው ደጃዝማች ፋሲልንም ድል
አድርገው አስራ ሁለት ሺህ ሠራዊት ሲገሉበት አንድ ሺህ ቁስለኛ
ግሪኩ የጃዝማች ፋሲል ከጥቂት ወታደር ጋር ሸሽቶ ወደ ዳሞት ሄዶ
ከደጃዝማች ዘውዴ ጋር እየተማከረ ተቀመጠ ራስ ሳህለ ሚካኤል በድል
አድራጊነት ጋር እየተማከረ ተቀመጠ ራስ ሳህለ ሚካኤል በድል
አድራጊነት ወደ ጐንደር ከተማ ሲገቡ ሕዝቡ በሰልፍና በክብር ተቀበላ
ቸው ። ከዚህ በኋላ መኳንንቱንና ካህናቱን አጼ ኢዮአስን የሚጠላ ሰብ

ሰበው እኔ በንጉሡ ነገሥታችን ትእዛዝ የሸፈተውን ልወጋ ብሄድ እንደ መርዳት ሸፍታውን ለመርዳት ሲሉ እኔን የሚገል የሳቸውን ወታደር ላኩ ግማሾችን ሳስገድል ለምስክር የሚሆኑ ይዠ ቀር ሲሉ አሉና የታሰሩትን አቀረቡ እንዚያን እንደላኳቸው ተናገሩ እናንተ ፍረዱኝ አሉ ሁሉም ይገደሉ ብሉ ፈረዳባቸውና ፊታቸ በሻሽ ተሸፍነው ተገደሉ ግማሹ በሻሽ ታንቀው ሞቱ አሬሳቸው እንደተራ ሰው በቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ አራት ዓመት በደከመ ሥልጣን ገዝተው አለፉ ሲሞቱ የስላሳ ዓመት ሰው ነበሩ እቴጌ ምንትዋብ ምንም የሳቸውን ወንድሞች ተው የእናታንቸውን ወገኖች ጋላዎችን ቢወዱ የልጇ ልጅ ለንጉሥ ኢዮአስ በጣም አዘኑ ከቀን በኋላ ተስካራቸውን በሚገባ ጡላቸው ።

ራስ ሳሁለ ሚካኤል ኢዮአስን በሻሽ ሸፍነው እንዳስገደሉ ቸው የሚስማማቸውን በወህኒ አምባ ከሚኖሩት የነጋሲ ዘር ኢያሱ አድያም ሰገድን ልጅ ዮሐንስን አውርደው ንጉሠ ነገሥት ቅዮጵያ ስመ መንግሥታቸውን አድማስ ሰገድ አሰኝተው 762 ዓ.ም አነገሷቸው ።

ዳግማዊ አጼ ዮሐንስ በአባቶቻቸው ዙፋን ሲቀመጡ ቸው ስላሳ ዘጠኝ ነበር በዚሁ ወህኒ አምባ በነበሩበት ሰዓት መጽሐፍትን እያስተማሩ ይኖሩ ነበር እንጅ ስለቤተ መንግ አስተዳደር አያውቁም ይሄውም እንግሳለሁ ብለው ተስፋም አል ቸው ይሄውም በልጅነታቸው አጼ ዳዊት ወንድማቸው ይነግ ብለው ሀልም አልመው እጃቸው አስቆረጣቸው ቆራጣ ሰውንት ቤተመቅደስ አይገባም ዘውድ ደፍቶ አይነግስም ስለሚባል ነበር ደዚሁ ዳግማዊ አጼ ዮሐንስ በነገሡ ጊዜ ብዙ ሰው አይነግሱም ይጣሏቸውና ይጨቃጨቋቸው ነበር ወደመጨረሻው ያለውን ቃል ልጻፍላችሁ እሳቸው የተቀኙት

ጊዚያቶሂ አእላፈ አመ መክሩ አእላፍ
አንተ ዘሃለይኮ ወዘወሰንኮ እይትርፍ

ትርጉም በሺህ ጊዜያቶች ብዙ ሺህ ሰው ቢመክር አንተ ከአሰ ውና ከወሰንከው አያልፍም ብለው በደብረ ብርሃን ሥላሴ ተቀኙ

ሌላው ደግሞ ራስ ሳሁለ ሚካኤል እህታቸውን ወይዘሮ ሥላሴን ለአጼ ዮሃንስ ዳሩላቸው በዚህን ጊዜ ሙሉ ባለሥል

ባው እቴጌ ምንትዋብ ያዙበት የነበረውን ሁሉ ንጥቀው እራሳቸው ይሾሙበትና ይሺሩበት ጀመር ። እቴጌ ምንትዋብ እሸቴ በንግሥትነትና በእንደራሴነት አርባ ዓመት ተወደውና ተከብረው ገዙ በኋላ ብዙ ውድቀትና ብዙ ንቀት ሲመጣባቸው አይተው ወደሠሩዋት ቤተ ክርስቲያን ቁስቋም ሄደው በፀሎትና በጾም እንደቆዩ በዚሁ ቤት ክርስቲያናቸው በተወለዱ በሰባ ስምንት ዕድሜያቸው አረፉና በታላቅ ክብር ተቀበሩ ።

ራስ ሳህለ ሚካኤል ዳግማዊ አጼ ዮሐንስ አድማስ ሰገድን እንደ ነሱ ደጃዝማች ፋሲል አልገዛም እያለ ጐጃምና ዳሞትን ወሲጋንና ቁን እያስታጠቁ እስከቦረና እየሄደ በጐንደር ንጉሥ እንዳትገብሩ እያለ ጠላት ያስነሳባቸው ጀመር ጐንደር አካባቢ ሄደው የተተመጡት የእቴጌ በርሚቤህ ወገኖች በኢዮአስ መሞትና በጋላዎች የሚከሄዶውን ሴራ ከዚያው ጐንደር ሆነው ይሰሙ ጀመር ። እንዲያውም ራስ ሚካኤል ይሄን ጐንደርን ለቃችሁ እንድትሄዱ ብለዋቸው ነበር ነገር ግን አንሄድም የመጣው ጦር ይመጣል እህታችን በርሚቤህን አናስነካም አናስደፍርም አሉ ።

በዚህን ጊዜ ራስ ሳህለ ሚካኤል ሰላሳ ሁለት ሺህ ጦር አዘጋጅና ደጃች ፋሲልን እንውጋው ብሎ ዳግማዊ ዮሐንስን ጠየቋቸው እሳቸውም አልችልም በዚህም ላይ ሽምግያለሁ ብትፈልግ ከነበርኩበት ወህኒ አምባ መልሰህ አስረኝ እኔ የፀሎት ሰው እንጅ የጦር ሰው አይደለሁም አሉት በዚህንጊዜ ራስ ሚካኤል እኔ አልፍ ስል ሌላ ሰው እንደራሴ አድርገው ይሾማሉ ብሎ በእንገሳቸው በእመታቸው መርዝ አስበልቶ አስገደሏቸው የሰባ ዕድሜ ሰው ነበሩ ወዲያውኑ በኋላ የዳግማዊ አጼ ዮሐንስን ልጅ ተክለሃይማኖትን ስመ መንግሥታቸውን ጥበብ ሰገድ አሰኝቶ አነገሳቸው ።

ከዚህ በኋላ ደጃች ፋሲልን ለመውጋት ወደጐጃም ከብዙ ጦር ጋር ሄዱ ፋሲልም ሳይዘጋጅ በአካባቢው ያለውን ያገውንና የዳሞትን ጦር ይዞ ፋግታ ላይ ገጠሟቸው ነገር ግን ብዙ ወታደር በሁለቱ በኩል ካለቀ በኋላ ደጃዝማች ፋሲል ድል ሆንና ሸሽቶ ወደቦረና ወሎ ሄዶ ተቀመጠ ከፋሲል ጋር የነበሩትን የወታደሮች ምርኮኛ የሞተውን ሰው እሬሳ ቆዳውን አስገፍፈው እንደስልቻ አድርገው ገለባ አስሞልተው ነዶአቸው ይባላል በዚህን ጊዜ የላስታው ደጃች ወንድወሰን ያማራ ሳይንቱ ራስ ጉሹ የሸዋው መሪድ አዝማች አስፋወሰን ለጐንደር መንግሥት አንገዛም እያሉ ተላልከው ሸፈቱባቸው ።

ራስ ሳህለ ሚካኤል ሥዑል ይሄን ነገር ሲሰሙ ከጐንደር ወ
ወደአክሱም ከንጉሡ ከተክለሃይማኖት ጋር ሄደው ተቀመጡ በ
ህን ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ሰላዮችን እየላከ ሀገር ያሰልፍ
ነበር በቤተ መንግሥቱ በኩል የተላከው ጀሚስ ብሩስ ነበረና ከራ
ሚካኤል ጋር ሆኖ ብዙ ምክርና ዘዴ ይረዳቸው ነበር የሚፈልገው
የኢትዮጵያን መጽሐፍትና በየጊዜው የተደረሱትን የፀሎት መጽሐ
ቶች እሳቸውም ሰተውታል ።

ራስ ሳህለ ሚካኤል አክሱም ለሰባት ወር ከቆየ በኋላ በጐንደ
ላይ ሌላ ንጉሥ ለማንገስ ሕዝቡ ይማከራል የሚባል ወሬ ሰምተው
አርባ ሰባት ሽህ ጦር ይዘው በግሥጋሴ ጐንደር ገቡ ። ከዚህ በኋ
ንጉሡን ተክለሃይማኖትን አምተዋል እንደራሴው ራስ ሳህለ ሚካኤ
ላይ ክፉ መክረዋል እየተባለ ብዙ ሰው ተገደለ ።

በዚህን ጊዜ የላስታው ወንድ በወሰን የቤጌምድርን የጐጃም
የየጁን ወታደር ይዞ ደንቢያ ላይ ሰፍሮ ነበርና የጐንደር ሕዝብ እ
ራውና ጋላው እየሄደ ተጨመረ ።

የቦረናው ገገር ራስ ጐሹ የደጃች ፋሲል እህት ልጅ ነበሩና የቦ
ረናን ጋላና የጂሌን ጦር ይዞ ደረሰ ከዚያም ከደጃች ወንድ ወሰን ጋ
ተገናኝቶ የሁለቱን ጦር በየአለቃ አሰልፈው ጐንደርን ከበቡት ከዚያ
ብዙ ሰው ካለቀ በኋላ ራስ ሚካኤል ተማረኩና በወህኒ አምባ በደጃ
ማች ወንድወሰን አላፊነት ተይዘው ላስታ ሄዱና ታሠሩ እኒህ ራ
ሳህለ ሚካኤል ልዑል በእንደራሴነት ከኢዮአስ ጀምረው ከገዙ በኋላ በ
ህኒ እንዳሉ ሞቱና እሬሳቸው ከዚያው በወህኒ አምባ ወርዶ ተቀበረ ።
ንጉሥ ተክለሃይማኖት ግን ከዙፋናቸው ሳይወርዱ ተዋቸው ከዚያ
በንጉሥ ኢዮአስ ላይ የሞት ፍርድ የፈረዱትን ካህናትና የቅጣ
መኳንንቶች እየተያዙ በአደባባይ በጥይት ተደብድበው ሞቱ ።

ራስ ጐሹ ለስሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን በዙፋን አስቀምጠ
ማንኛውንም ሥራ ይዘው በመንግሥቱ ላይ ይሾሙበት ይሻሩበት
ነበር ለጓደኛቸው ለደጃዝማች ወንድ ወሰን አማራሳይንትን ወሎ
ላስታን ጐጃምን እንዲገዙ ፈቀዱላቸው ተክለሃይማኖትን ከዙፋናቸው
አውርደው በግዞት ዋልድባ ገዳም ላኳቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖትም
ወዲያው እንደሄዱ በሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው አረፉና በዚያው
ከገዳሙ ውስጥ ተቀበሩ ለስሙ በዙፋን የነበሩ ሰባት ዓመት ነበ
ከሳቸው ቀጥሎ ልጃቸውን ሰለሞንን ከብሬን ሰገድ ብለው የአ
ስት ዓመቱን ልጅ ለስሙ አነገሡት እሱም ልጅ በለነበር ከዙፋን አ

ራትን ሴላ አንገሱ ለስሙ የገዛው ሁለት ዓመት ነበረ ከስለዋን ቀዋ ለው አቤቶ ተክለ ጊዮርጊስ የሚባሉት የዳግማዊ ዮሐንስን ልጅ ከወህኒ አምባ አምጥተው ስመ መንግሥታቸውን ፍቅር ሰገድ ብለው ለስሙ አነገሷቸው ።

ራስ ጉግሳ እንደራስ ሳህለ ሚካኤል ሥዑል ለስሙ አንድን የን ጉሥ ልጅ እያነገሡ ሲቀመጡ ሥልጣኑም እራሳቸው ቢይዙት ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ሕዝብ አልተገዛላቸውም እርስ በርሱ ይጣላና ይጋደል ነበር ሰላምና ፀጥታ አልተገኘም መጨረሻ ከፈረስ ላይ ወድቀው ስለሞቱ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ኢትዮጵያን ጠቅልየ እገዛለሁ እንደ አባቶቼም የንጉሠ ነገሥቱን ማዕረግ እደርጋለሁ ብለው ነበር ነገር ግን መሣፍንቱ በየሀገሩ ስለገነኑ ሊገዙላቸውና ሊገብሩላቸው አልፈቀዱም ሁሉም ለየራሱ ለመንገሥ በየቦታው ጳጳስ ከእስክን ድርያ ከሮም ለማስመጣት ይላላክ ጀመር ።

እንደዚህም ሆነ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ በራስ ጉግሳ ትእዛዝ እንደነገሡና ራስ ጉሻም እንደራሴነቱን ይዞ ሲኖር ስለሞቱ የሱን ሥራ የእቴጌ ቤርሣቤህ እጉት እሊ ቤሩ ጓንጉል የቤተመን ግሥቱን ሥራትንና ሕግ ስለሚያውቁ ራስ እሊ ብለው የእንደራሴ ነቱን ሥራ ሰጣቸው ራስ እሊ ቤሩ ጓንጉልም ለንጉሡ በቀን እየገለ ለገሉ ተስማምተው ሳለ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ በቀድሞ ነገሥታት ያል ነበረውን የማርና የገንዘብ ግብር ክፈል ብለው የጐንደርን ሕዝብ አስገደዱት የጐንደር መኳንንትና ባለመሬት ተሰብስቦ አባቶቻችን ለአያቶቻችን በሄዱበት ሄደው ባደሩበት አድረው የንጉሣቸውን ቃል አክብረው ትእዛዛቸውን ፈጽመው ስለሚኖሩ ደጉ ንጉሥ ነገሥታችን የበሩት እጼ ሠርፀ ድንግል በሰማይ የለም ዱር በበጌምድር የለም ግብር ብለው ቢናገሩ አንዳንዶች ለምን ? ቢሏቸው የበገምድር ሕዝብ አገሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር አድርጎ ስለሚኖር ግብር እንዳይጠ የቅ ያሉትን እርስዎ ሽረው ገብሩ እሉን አሁንም እንደአባቶቻችን ሕግ ይምሩን ያስተዳድሩን ብለው በመናገራቸው ንጉሥ ተክለጊዮርጊ ስም እኔ በእኔ ሕግ አስተዳድራችኋለሁ እንጅ እናንተ እንደምትናገ ሩት ከሆነ ምን ንጉሥ ነኝ አሁንም የምላችሁን አድርጉ የተጣለባች ሁን ግብርም ክፈሉ አሏቸው ።

ሕዝቡም ከዳር እስከዳር ተላላከና ተዋጐጡ አንድ ሰው ልኮ ደብረታቦር ላይ ተገናኝ በዚህን ጊዜ ነገሩ እንዲባባስ በጐንደር አካባቢ ሚኖሩትን የእቴጌ በርሣቤህ ወገኖች ግማሹ ጉልበቱን ግማሹ

ፈረስን እየሰጠ ለዚህ አድማ አገልግለዋል ራስ አሊ ቤሩ ንንጉልም ደብረታቦር ድረስ ሄደው እናንተ የወደዳችሁትን እወዳለሁ የሻራችሁትን ሽሬ የፈለጋችሁትን እሾማለሁ እኔ ከእናንተ ቃል አልወጣም ሲሉ ተናገሩ ሕዝቡም በንግግራቸው ተደስተና ይበሉ ከዛሬ ጀምሮ ንጉሥ ተ/ጊዮርጊስ የሰጠዎትን እንደራሴነት ይተውትና በእኛ በኩል እንደራሴ አድርገምንታል ከዛሬ ጀምሮ እኛ በመረጥነው በመስፍን አገዛዝ እንጅ በንጉሥ ሥልጣን አንገዛም ነገር ግን የንጉሥ መቀመጫ ወይናደጋውን ሀገር ሰጥተን ለስሙ እያነገሥን እናስቀምጣለን ብሎ ደጃዝማች እሸቴ ኃይሌ በሕዝቡ በኩል ሆኖ ተናገረ ።

ራስ አሊም ከወገኖቻቸው ጋር ሆነው ከተቀመጡበት ተነስተው ሕዝቡን ሶስት ጊዜ እጅ ነሱት ከዚያም ወደጐንደር ተመልሰው ለንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ እናቴ ወይዘሮ ገልቤ በጠና ታማላችና ሳትሞት እንድደረስ ይፍቀዱልኝ ልሂድ አሏቸው ንጉሡም ይከዳኛል ብለው ጥርጥር ስላልነበራቸው ፈቀዱላቸው ። ራስ አሊም የንጉሡ ነገሥት የጉዞ ማረፊያ በነበረው ሁሉ ምሪት ያስቀመጡት ፈረስ ነበራቸውና ከግራዝማች የኔነው ብርሌ ጋር ሆነው ከጐንደር ፍርቃ በር ከፍርቃ በር ደብረታቦር ከደብረታቦር ክምር ድንጋይ ከክምር ድንጋይ ገረገራ ከገረገራ አገራቸው የጁ ፈረስ እየቀያየሩ በሁለት ቀን ገብተው አደሩ ።

ወዲያውኑ ሰባት ቤት ወሎ መልእክተኛ ልከው የወሎን የየጁን የራያን ጦር አስከትለው በአምስተኛው ቀን ተመልሰው ደብረ ታቦር ገቡ ከዚያም ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ የበጌምድር ባላባትና መኳንንት ተማምሎ የሀገሩን ግዛት ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶ የሕዝብ እንደራሴ አድርጎኛል እስዎ የነገሥታት ፍጻሜ ስለሆኑ ዝም ብለው ከግንብዎ ይቀመጡ ሲሉ ለንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ላኩባቸው ።

ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስም የበጌምድር ሕዝብ መክዳቱን ስለአወቁት በጌምድር ከእኔ ከወንድምህ የየጁ ጋላ የራያ ባላባት ከጠቀመህና ከተሻለህ ደግ ነዋ ብለው አክሱም ሄደው ተቀመጡ ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ የነገሡበት ዘመን አምስት አመት ነው እኚህ ተክለ ጊዮርጊስ ፍጻሜ ነገስት ወይም ተፍጻሜተ ነገሥት ሲባሉ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ዓመት ምህረት ነው ከዚህ ቀጥየ ዘመነ መሣፍንት እጽፍላችኋለሁ ። ፀሐፊው መራሪስ ኤ.ኤም በማላይ

አጼ ማለት ታላቅ የንጉሦች ንጉሥ ማለት ነው ኃይሉ እየደከመ ሲሄድ ንጉሠ ነገሥት መባሉ ቀርቶ ንጉሠ እባል ጀመር የነጋሲ ዘር

ነኝ እያለ በየቦታው ስለተነሳ የነጋሲን ሥልጣን ለራስ ተሰጠና ንጉሥ የሚባለው አንድ ብቻ ሆነ የግዛቱም እገር ትንሽ ነው ።

በኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ ውስጥ አጼው ወይም ንጉሡ ነገሥቱ በመኳንንቱና በሊቃውንት በወታደሩና በሕዝቡ ላይ የነበረው መፈራትና መከበር የማዘዝ ሥልጣኑን ችሎታው ወሰን የለውም ይሄውም ከንጉሠ ነገሥቱ አፍ አንድ ጊዜ ከወጣ ምህረትም ሆነ መገደል ግዴታ መፈጸም አለበት ቢሾም ቢሻር ቢያስር ቢፈታ በገደል ቢያድን ጠያቂ ፈጽሞ የለውም እግዚአብሔርን ካልፈራ የፈለገውን ለማድረግ ሙሉ ስልጣን አለው ሕዝቡም ከእግዚአብሔር በታች ንጉሠ ነገሥቱ ብቻ እንደሆነ በማመን ቀጥ ብለው ይገዛሉ በምድር የእግዚአብሔር እንደራሴነት እንደተሰጠ ካህናቱ ስዩመ እግዚአብሔር መሲህ እግዚአብሔር እያሉ ይሰብኩለታል በእርሱ ላይ እንደብቱን ያነሳው ምላሱ ይቆረጣል እንጂ ያነሳው እጁ ይቆረጣል ብሎ ፍትሃ ነገሥት ያዘዘውን በደንብ ይጠቀምበታል መኳንንቱም መሳፍንቱም ይበልጥ ጊዜውን ለንጉሠ ነገሥቱ ማገልገል ማሸርገድ እገልጋይ ታዛገር እንጅ ተከራካሪ አይደሉም ስለዚህ የሚደፍር አልነበረም ነገር ግን ራስ ሚካኤል ስሁል እንደራሴ አድርገው የሾሟቸውን ንጉሠ ኢዮአስን አሳንቀው ሲገሉ በንጉሡ ሥልጣን እንደልባቸው ሲያዙ የተመለከቱ መሳፍንት ለራሳቸው እንዲህ ካለ ዘውድ አገዛዝ ነጻ ሆነው እራሳቸው እየሾሙ ለመኖር ከዳር እስከ ዳር ተቀስቅሶ በንጉሡ ላይ ትንሳ ከዚህ በፊት የነገሥታት ዘሮች እራስ በራቸው ከመጋደል በስተቀር ከመኳንንቱና ከሕዝቡ አንድ ሰው ተነስቶ የሚደፍር አልነበረም አሁን ግን ራስ ሚካኤል የጀመሩትን ድፍረት ራስ አሊ ቤሩ ንንጉል ከየጁ መጥተው ሁሉን በዚዶ ገልብጠው አዲስ የመስፍን አስተዳደር ጀመሩ ።

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

### ዘመነ መሣፍንት ከትልቁ ራስ አሊ እስከ ትንሹ ራስ አሊ

ትልቁ ራስ አሊ ትውልዳቸው በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ከየመን ሃረር ግራኝን ለመርዳት መጥተው ግራኝ አህመድ በአጼ ገላውዴውስ ጦር ድል ሆኖ ሲሞት ከአረብ ሃገር መጥተው የነበሩት ግማሹ ወደሃገራቸው ሲሄዱ ግማሹ ግን በየሃገሩ በየጁ በራያ በወሎ በይፋት የሚበልጡት ግን አደሬ ተብለው በሃረር ከተማ የተቀመጡ ናቸው ከነዚህ ውስጥ በየጁ ከነበሩት አንዱ ጦር አዝማች የነበረ ሺህ ኡመር ይባላል ሸህ ኡመር የየጁን ባላባት የሺይትን አግብቶ ብዙ ልጆች ወለደ የልጁ ልጅ አይቶ ብዙ ስለነበሩ ወረሺህ አላቸው ።

የሼህ ኡመር አንደኛው ልጁ ወሴ ይባላል ወሴ አብዩን ወለደ አብዩ በአባቱ ስም ወሴን ወለደ ወሴ አባ ጉትየን ወለደ አባ ጉትየ አባ ሴሩ ጉንዋንጉልን ወለደ ሴሩ ጉዋንጉል ሁለት ሚስቶች ነበሩትና ከመጀመሪያይቱ ከእንኮየ አሚሮን ወለዱ ባልጋዲ አሚዝ ውቢትን ውቢት ቤርሣቤህ ተብላ አጼ ኢያሱ ብርሃን ሰገድን አግብታ ንጉሥ ኢዮአስን ወለደች በእስዋ እቴጌነት ዘመነ ነው የየጁ መሣፍንት ወደ ጐንደር ሄደው የተቀመጡ ሴሩ ጓንጉል የራስ ፋሪስን እህት ገለቤን አግብቶ ከወይዘሮ ገለቡ ራስ አሊን ወደዘሮ ከፊይን ራስ አሊጋዝን ወለደ ።

ራስ አሊ የወንድማቸውን የአሚሮን ልጅ ለመጠየቅ ብለው ሄደው ጎንደር በዚያው ይኖሩ ነበርና በንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግሥት የእንደራሴነትን ሥልጣን ሲይዙ የነገሥታቱ ሥልጣን በሙሉ ለእንደራሴዎች ተላለፈ ይሄውም ራስ አሊ ሼዋሚ ሻሪ እሜሪ ፊቺ ሆኑ የነገሥታቱ ልጆች በመሣፍንቱ ትእዛዝ እየነገሡ ለስሙ ዘውድ ደፍተው ስሙን ብቻ አግኝተው በፋሲል ግንብ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገ ።

ነገር ግን ራስ አሊ እንደራሴ ሆነው የንጉሡን ሙሉ ስልጣን ቢይዙ በትንቤን ራስ ገብረ መስቀል በእንደርታ ራስ ወልደ ሥላሴ በሰሜን ራስ ገብሬ በላስታ ደጃች ወሰን ሰገድ በዳሞት የዳዊት ዘር ደጃች

ወቆ በጉጃም ከብፄቱን ጌታ ኢያሱን ከእቴጌ ምንትዋብ ከወለተ እስራኤልና ከደጃች ዮሴዴቅ የሚወለዱትን ታላቁ ራስ ሃይሉ በሸዋ መርእድ አዝማች አስፋ ወሰን ለጉንደሩ ንጉሥና ለእንደራሴው እንገ ም እንታዘዝም እንገብርም አሉ እንዲያው ለየብቻ ሌላ የንጉሥ ዘር እንግሠው በእንደራሴነትና በንጉሥነት ለመግዛት አሰበው ተነሱ ።

ራስ አሊ የኢትዮጵያ ህዝብ ያለ ንጉሥ እንደማይገዛቸው አው ቀው ጕንደርን ለቀው ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ወደአከሱም ሄደው ተቀምጠው ሳለ የንጉሥ ኢዮአስን ልጅ ሣልሣዊ ኢያሱ ወይም ንጉሥ ጎንደር ኢያሱ ብለው ለጊዜው አነገሡት አሁንም ህዝቡ ሶስተኛው ኢያሱ ተብሎ የነገሠው ስለአልተቀበለላቸው በሶስተኛው ወር የዳግ ማዊ አጼ ኢያሱን ልጅ የኢዮአስን ወንድም ህዝቅያስን አንግሠው ዙፋን ላይ አስቀምጠው እራሳቸው ይሾሙና ይሽሩ ጀመር በዚህን ጊዜ ራስ አሊ ዘዴኛና መላ አዋቂ ነበሩ የእንደርታውን ገዢ ራስ ወልደሥላሴን ከእንደርታ ላይ የተንቤንን ግዛት ጨምሩላቸው ።

ከዚህ በኋላ ራስ ወልደሥላሴ ተዋጊኞቻቸውን ራስ ገብረ መስቀልን ተንቤን ድረስ ሄደው በጦርነት ወግተው ድል ካደረጉት በኋላ የትግ ራይ ግዛት የበላይነታቸውን አረጋገጡ በዚህን ጊዜ ራስ ወልደሥላሴን የተንቤን ገዢ ከራስ ገብረመስቀል ጋር ማጣላታቸውን የሰሙ ራስ እስራትና ራስ ወልደገብርኤል ራስ አሊ ቤሩ ጓንጉልን ከጉንደር አስ ወጥተው እራሳቸው እንደራሴነቱን የመያዝና የፈለጉትን ለማንገሥ ተሰባቸው ነገር ግን ራስ አሊና ወንድማቸው ራስ አሊጋዝ ቤሩ ጓንጉል እየተዋጉ ከበጌምድር አስወጧቸው የበጌምድርም ህዝብ እራሱ ጦርነ ስለሾማቸው ወዶ ይገዛላቸው ጀመር ሌላው ሃገር ግን በራሱ መኮንን እየተመራ ተቀመጠ በዚህን ጊዜ የጕጃሙ ገዢ ታላቁ ራስ ሃይሉ ጉጃምን የበላይ ሳይኖርባቸው ያስተዳድሩት ጀመር ራስ ሃይሉ ከህዝብ ከሚያገኙት ግብር እራሳቸው አሳርሰው ብዙ እህል ያስመርቱ ነበር አንድ ጅ ከባላገር ግብር አስገብረው እያወቁም የሚያርሱት መሬት ለምበት መቶ ጥንድ በሬ ይውልበት ነበር በዚህ ምክንያት መኳንንቱ ነበር በዘመናቸውም ህዝቡን ካሁኑቱን ግብር እያገኑ መብ ማጠጣት ይወዱ ነበርና መኳንንቱ እየኩሩ ከግብራቸው ይቀሩ ነበር ለምንድነው የቀራችሁት ሲላቸው የምን ሥጋ እንደሆን ስለማና ነው አሏቸው ከዚህ ቀን በኋላ ከመኳንንቱ ፊት ታርዶ እንዲቀ ርባቸው ቢያዝዙ እነርሱ ደግሞ የቱም ሺም ወይም ጓዋኝ አይደለንም ብሎ ያስቸግራቸው ጀመር ታላቁ ራስ ሃይሉ የሴዴቅ ጉጃምን ብዙ

ዘመን ገዝተው ሲሞቱ ልጃቸው ልጅ መርእድ የራስነትን ማዕረግ ይዘው በአባታቸው ወንበር ላይ ተቀመጡ እንደዚሁም ሆነ ።

ራስ መርእድ ሃይሉ ግብር አሠርተው ሲጨርሱ ወታደሩንና መኳንንቱን እንደማዕረጉ እንዲገባ ያዛሉ ወደግብር ሳይገባ ወይም ዘግይቶ የመጣውን መኳንንት ካጋፋሪዎቻቸው እየጠየቁ በእግረ ሙቅ እያሰሩ እየጊረፉም ይቀጡት ጀመር በዚህን ጊዜ መኳንንቱ ታላቅ ድንጋጤ አደረበት ስለዚህ ግብር ባለ ቀን እንኳን ተጠርቶ ያልተጠራው ሁሉ ቀደም ብሎ እየመጣ በአዳራሹ በራፍ እየተሰበሰበ ደጅ እየጠና ይበላ ጀመር ።

በራስ መርእድ ኃይሉ ዘመን የእህታቸው ባል የዳሞቱ ገዢ ደጃች ዘውዱ ጐጃምን ከራስ መርዕድ ነጥቀው ከዳሞት ጋር ለመግዛት ሃሳብ አድርገው ናፍቃኛለችና ይዘሀት መጥተህ እንዳያት መልስ ጠርቻለሁ ብለው ላኩባቸው ደጃች ዘውዱም ነገሩ ሳይገባቸው ሚስ ታቸውን ይዘው ወደ ይባባ ከተማ ሄዱ ከዚያም እህታቸውን አስቀር ተው ራስ መርዕድ የደጃዝማች ዘውዱን ልጃቸውን አስያዙና አስፋው ቀራንዮ ዋሻ ወስደው አስቀመጧቸው ደጃች ዘውዱም ትንሽ ጊዜ እንደታሠሩ ሚስቴ ድንቅነሽን ይላኩልኝ ናፍቃኛለችና ብለው ወደራስ መርእድ ላኩ ራስ መርእድም አስጠንቅቀው ዘበኞችን እህታቸውን ላኩላቸው ከዚያም ባልና ሚስቱ አብረው አድረው ደጃች ጐሹ ተፀንሰው ተወለዱ ደጃቹ ጐሹ ደጃዝማች ተሰማን ወለዱ ደጅአዝ ማች ተሰማ ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ወለዱ እነዚህ በዳሞት የአን በሳ ዳዊት በጐንደር ነገሥትና በሸዋ የአቤቶ ያቆብ ልጅ ከወይዘሮ ወለተማርያም የሚወርድ የዘር ሃረግ አላቸው ።

አሁን ወደበጌምድር ታሪክ እንለመስና ንጉሥ ህዝቅያስ ፋሲል በአሰራው ግንብ ውስጥ ሆነው ራስ አሊ በበጌምድሩ እንደራሴ ሆነው አራት አመት እንደገዙ በአድሚያም ሸምግለው ነበርና የእንደራሴነቱን ሥራ ለወንድማቸው ለራስ አሊጋዝ ቤሩ ጓንጉል በ1781 ዓ/ም ለቀቁ ለት ።

ራስ አሊጋዝም በዙፋን እንደተቀመጡ በእደማርያም የሚባለውን የነጋሲ ዘር ከዳግማዊ አጼ ኢያሱ የሚወለደውን አንግሠው ነበር ከዚ ያም እሱውን አውርደው ከአሁን በፊት ነግሶ የነበረውን የተክለሃይ ማኖትን ልጅ ሰሎሞንን እንደገና ከዙፋን አውጥተው አስቀመጡት ።

ራስ አሊጋዝ አምስት አመት በጐንደር ከተማ ሆነው በጌምድ ርን እንደገዙ ራስ ወልደገብርኤልና ወንድማቸው ራስ አስራት የበጌ

ከ1786 - 1792.

ምድር ሕዝብ እንዴት ለየጁ ጋላ ትገዛለህ ብለው መኳንንቱን ቀስ ቅሰው ጦር አስነሱና ከላስታ ወደጐንደር ከተማ ሄደው ራስ አሊጋዝን ተዋግተው ድል ካደረጉ በኋላ የእንደራሴነቱን ሥራ ከሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ዓ/ም እስከ ሺህ 792 ዓ/ም ገዙ ።

እንደዚህም ሆነ ሁለቱ በአንድነት ሲያስተዳድሩ መጀመሪያ እርስ በራሳቸው ካጣሏቸው በኋላ ራስ ገብሬ ከላስታ ደጃዝማች እሸቴ ከእ ስቴ ራስ መርእድ ከጐጃም ተላልከው ራስ ወልደገብርኤል ተጣልተው ወንድሙን ራስ አስራትን ተላልከው ተገናኙትና ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር በዚህን ጊዜ ራስ ወልደገብርኤል የወንድሙን መከዳት ሲሰማ ከራስ አሊና ከራስ አሊጋዝ እህት ከወይዘሮ ከፋይ የሚወለዱትን አዛዥ ጉግሣን እህታቸውን ሴሚንት አጋብተው የራስነት ማዕረግ ሰጡተው ከሄዱበት ሃገር ከትግሬ ሲመለሱ ወንድማቸው ራስ አስራት ከነራስ መርእድ ጋር ሆኖ ወገራ ላይ ለጦርነት ተዘጋጅቶ ቆያቸው ከዚህ በኋላ የሁለቱ ጦር ገጥሞ ራስ ወልደገብርኤል ድል እንዳደረጉ በጥይት ተመትተው ከፈረሣቸው ላይ ወድቀው ወዲያውኑ ሞቱ በዚሁ ቀን ራስ መእድ በመጀመሪያ ስለሞቱ ጦርነቱ አበቃና ድሉ ለራስ ወልደ ገብርኤል ስለሆነ እህታቸውን ላገባ ለራስ ጉግሣ እንደራሴነቱ ተሰጠ እራስ አስራትም ሸሽቶ ወደላስታ ሄደ ራስ ገብሬም ወደሰሜን ሃገራ ቸው ሄደው እያረሱ ለማንም ሳይገብሩ በበጌላ በቀላ ወገራ ተከብረው ሲኖሩ ሞቱና ደረስጌ ተቀበሩ ። ያም ሆነ ይህ የእንደራሴነቱ ስልጣን ወደላስቶች ራስ ወልደገብርኤልና ራስ አስራት ተዛውሮ የነበረው በስድስት አመቱ ለየጁዎች ለቤሩ ጉዋንጉል ዘሮች ተመልሶ ገባ ማለት ነው ።

ራስ ጉግሳ አባታቸው የኤልማና ዴንሣ ዳሞት ባላባት መርሶ በሬንቶ ወይም አባ መርዞ ቡሬንቶ ይባላሉ ራስ ጉግሣ በእንደራሴነት ሆነው ጐንደርን ሲገዙ ለስሙ ዮናስ የሚባለውን የኢያአስ ልጅን አንግሠው ነበር ንጉሥ ተብሎ ዮናስ በዙፋን እንዳለ በራስ ጉግሣ ላይ ከፉ መክሯል ተብሎ ታሠራና ድሜጥሮስ የሚባል እንደዚሁ የነጋሲ ዘር አንግሰው ነበር ራስ ጉግሣ የራስ አሥራትንና የራስ ወልደ ገብር ኤልን እህት ሴሚትን አግብተው ራስ ማርየን ራስ ዶሪን ራስ ይማምን ወይዘሮ ሂሩትን ወለዱ ወይዘሮ ሂሩት የሰሜን ባላባት የራስ ገብሬን ልጅ ደጃች ሃይለማርያምን አግብተው ደጃዝማች ብጡልን ደጃች መር ሶን ወይዘሮ የጡብዳርን ወለዱ ደጃ/ውቤ ከጃና ሞራ ደጃዝማች ብጡል እቴጌ ጣይቱን የዳግማዊ ሚኒሊክን ባለቤት ወለዱ እቴጌ ጣይቱ ልጅ አልወለዱም ከራስ ወልደገብርኤል ታላቅ እህት ከወይዘሮ ሴሚት

1792

ሌላ ራስ ጉግሣ በሽህ ሰባት መቶ ዘጠና ሁለት ዓ/ም ላ
የንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ልጅ ወለተፍቅርትን አግብተው ከንጉ
ስልጣን በላይ ከንጉሥ ስም በታች በእንደራሴነት ሆነው በ
ምድርን ትግሬን ሲገዙ ሁለት ንጉሶች አንግሰው እነሱም ስለአ
ስማሙአቸው ዮናስና ድሜጥሮስን አስረው አሁን ደግሞ እጉ
ፅዮን የሚባለውን የሀዝቅያስን ልጅ አንግሰው ለስሙ አስቀመጡ
በራስ መርድ ወንበር ልጃቸው ደጃዝማች ጓሉ ተተክተው ነበርና የራ
ጉግሳን እንደራሴነት ተቀብለው ተገዙ በፋንታው የትግሬን ህዝ
እንግዛም ሲል ራስ ወልደስላሴን ሾሞ አስቀመጠ ፡፡

በዚህን ጊዜ ራስ ጉግሣ የአጋሜውን ባላባት ወልዱን የአጋሜ
ግዛት ከአንተና ከልጅ ልጅህ አይወጣም ስላሉት ደስ አለውና ለራ
ወልደስላሴ የሚገዛ ከባድ ቅጣት ያገኘዋል ብሎ አወጀ በዚህ ጊ
ልጁ ሲባጋዲስ ሃይለኛ ጀግና ስለነበር የትግሬ ህዝብ እንደገና ለራ
ጉግሣ ይገዛ ጀመር ፡፡ በዚህን ጊዜ ሰበጋዲስ ሃይል እየተሰማው የት
ሬን ግዛት ጠቅልሎ ለመግዛት ተነሳ ፡፡

የጐጃም ነገር ደጃዝማች ጓሉ ከራስ ጉግሣ ጋር ቢስማሙ የአ
ስታቸውን የወይብር ደንቅነሽን ባል ደጃች ዘውዱ ራስ መርድ በ
ገራ መርነት ላይ ሲሞቱ ራስ መርእድን የጠላ ባለሃገር ፈትቶ ከታሰ
በት ቆሻ አስወጥተው ወደዳሞት ሃገራቸው ሄደው ይኖሩ ነበር
ደጃች ኢልያስ አገውን በራስ ጉግሣ ስር ሆኖ ይገዛ ነበርና አጎቸው
ደጃዝማች ዘውዱን ለመውጋት ሰባት ቤት አገውን የሚሜንና የአ
ፈርን ጦር ይዞ ፋግታ ድረስ ሄዶ ለሳቸው የሚገብረውን ሃገር ወረረ

ደጃዝማች ዘውዱም ወታደራቸውን ይዘው በመግጠም ፈን
አርባ ቆርበት በአርባ ግልገል በቅሎ አንገት ላይ አስረው የደጃዝማ
ኢልያስ ጦር በሰፈረበት ሌሊት ወስደው ለቀቁበት በዚህን ጊዜ ግ
ገል በቅሎዎች ቆዳቸውን እያንኳኩ ደንብረው ሲሯሯጡ የደጃዝማ
ኢልያስ ሠራዊት ምን መጣ እያለ ደንግጦ ገደል እየገባ ወደቀ ግማ
እየሮከረ እርስ በራሱ ተጋደለ የቀረውም ደንግጦ በቁጥቋጦው ተ
ብቆ የተገኘውን ወደንጋቱ እየያዙማረኩት እራሱ ደጃዝማች ኢልያስ
ተማረከ ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ዘውዱ ደጃች ጓሉን ለመውጋት ከ
ሞት ወደጐጃም ጦራቸውች ይዘው ጉዞ አደረጉ በመንገድ ላይ የሚ
ገኙትን ጊደርና ወይፈን ሰብስበው በፈረሰኛ አስከብበው የደጃዝማ
ጓሉ ወታደሮች ወዳሉበት ወደሳንተራ ሜዳ ሄዱ ፡፡ የደጃዝማች ጓ
ወታደሮች ብዛቱን አይተው ከብት መሆኑን ሳያውቁ ሸሹ በሰዚ

የደጃዝማች ዘውዱ ብልሃት አገዎችን በቁርበት ጉጃሞችን በከብት አሸንፋቸው እየተባለ ብዙ ጊዜ ይተረክ ነበር ።

ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ዘውዱ የዳሞትን ጦር ሰብስበው ራስ ጉግሣን ለመውጋት ወደበጌምድር ሄዱ ራሴ ጉግሣም ወታደራቸውን ይዘው ደብረታቦር ላይ ተገናኙና ሲዋጉ እንደዋሉ በኋላ የጐጃም ጦር በደጃዝማች ኃሉ የሚመራው ለእርዳታ መጥቶ የደጃዝማች ዘውዱን ጦር ሲወጋ ዳሞቶች ድል ሆኑና ሸሹ ደጃዝማች ዘውዱም ተማርከው ጠቅላ መንዞ ከሚባለው ከጣና ሃይቅ ውስጥ ታስረው ሞቱ ።

ለደጃዝማች ዘውዱ የተገጠመላቸው ግጥም ደጃዝማች ዘውዱ ያለው ብልሃት አገውን በቆርበት ጐጃምን በከብት ሁሉን ድል ሲያደርግ ያለአንድ ሰው ሞት ። ደብረታቦር ሄዶ ተጠቃ በሴት ። በሌላ በኩል ደግሞ በእሳቸው ጊዜ በኩል ደግሞ በእሳቸው ጊዜ ዳሞትና ጐጃም አንድ ሆነ ብለው እንደዚህ ነው የተባለ ይላሉ አገውን በቁርበት ዳሞትን በከብት ጐጃም አየድ ሆነ ያለአንድ ሰው ሞት ይሄም የተባለበት ባለቤታቸው ወይዘሮ ድንቅንሽ ለራስ ጉግሣ ሆና እያገለገለት እውቃሴ መጥተህ ከታሰርከበት እስፈትትህ ውሰደኝ ብላ ልካላቸው ኖሮ እሱዋን ለማስለቀቅ ሄደው ነው ድል ሆነው የተማረኩ የሚባል ባለቤታቸው ተቆርቁረው እሱ ከሞተ ባል አላገባም ብለው ንሥሃ ገብተው አያሩባሉም ሄደው ሳለ በዚያው ሞተው ተቀበሩ ።

ከደጃዝማች ዘውዱ ቀጥለው በዳሞት ልጃቸው ደጃች ጉሹ ተተኩ እራሳቸውም ለራስ ጉግሣ አልገዛም ብለው የበላይ ሳይኖርባቸው አገውንና አቸፈርን አራት መከራከር ድረስ ሲገዙ ቆይተው የጐጃም ገዥ ደጃዝማች ኃሉ ሲሞቱ ከልጃቸው ከይመር ጉዋሉ ቀምተው ይገዙ ጀመር ።

ራስ ጉግሳ በሰላምም በጦርነትም ዘውዱን ለሰሙ ሃያ ስድስት አመት ሙሉ ከእንደራሴነት እንደገዙና ከአንጥሉ ፅዮን ቀጥለው ጊጋርን የእንሰዕዮን ልጅ በዙፋን እንዳስቀመጡ በሺህ 818 ዓ/ም ሞተው በደብረታቦር ተቀበሩ እንደዚሁም ራስ ጉግሣ ሲሞቱ ልጃቸው ራስ ይማም የእንደራሴነቱን ሥልጣን ይዞ በአባቱ ወንበር ተቀምጦ ይገዛ ጀመር ። ነገር ግን እንደ አባቱ እንደራስ ጉግሣ በጣም ህገቡ አልተገዛለትም ነበርና በዘመኑ በጦር በረሃብ ብዙ ኢትዮጵያውያን አለቁ

ራስ ይማም ሁለት ዓመት እንደገዛ 1820 ዓ/ም ሲሞት ኢወን ድሙ ራስ ማርዬ በፈንታው የወንድሙን ወንበር ይዞ በመስፍን ይገዛ

ጀመር ለእሱም ከዳሞት ደጃዝማች ጐሹ ከሰሜን ደጃዝማች ውቤ ሃይለ ማርያም ከአጋሜ ሰባ ጋዲስ እንገዛም እያሉ በየጊዜው ተዋግተዋቸ ዋል ከሁሉም የሚበልጡት በአስተዳደርም ሆነ በጀግንነት ሰባአ ጋዲ ስን የሚወዳደራቸው ስላልነበረ የመላው ትግሬ ገገር ነበሩ እንጅ የበ ላይ አልነበራቸውም በከፋና በወለጋ ያለመሪ ያለገዢ ይኖር ነበር በሸዋ በአ በሃረር ቱርኮች ከቱርክ ቀጥሎ ግብፃውያን ይገዙት ነበር በሸዋ በአ ሩሲ በሲዳሞ የመርዕድ አዝማች ኋላ ራስ ጉግሣ ጋር እኩል ለመሆን ራስ ወሰን ሰገድ የተባሉት የእሳቸው ልጅ ሜኒሊክ ይባሉ የነበሩት ንጉሥ አቢሲንያ ሣህለ ሥላሴ ተብለው በንጉሥነት ያስገብሩና ይገዙ ነበር ።

ራስ ማርዬ ደጃች ሰባአጋዲስ አልገዛም ሥላላቸው ለሰሜኑ ገገር ለደጃች ውቤ ሃይለማርያም ሰባአጋዲስን ድል ያደረክ እንደሆነ የትግ ሬን ግዛት ለአንተ እሰጥሃለሁ ብለው ቃል ገብተው ሽማግሌ ላኩባ ቸው ደጃች ውቤም ልጃቸውን ያገባውን ሲባጋዚዮን አታለው ለመያዝ ሞክረው አልሣካላቸው ቢል ጦራቸውን ይዘው ለመውጋት ሄዱ ራስ ማርዬም ደጃዝማች ውቤ መሄዳቸውን ሲሰሙ ሰባአ ጋዲስ ሃይለኛ እንደሆነ ስለሚያውቁ ራሳቸው የበጌምድርን ጦር ይዘው ሄደው ከሰባ አጋዲስ ጦር ጋር ማይ አስላማይ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ገጥመው ደጃች ሰባጋዲስ ተሸንፈዎ ተማረኩ ከዚህ መሃል ደጃዝማች ሃጎስ አባቱ መማ ረካቸውን ሲሰማ የደጃዝማች ውቤ ወታደር መስሎ ራስ ማርዬን ገደላቸው እሱም በጥይት ቆስሎ አምልጦ ነበር ነገር ግን በጠጰሚ ተይዞ ተገደለ አባቱም ደጃዝማች ሰባጋዲስ የልጃቸውን ሞት ሲሰሙ በሃዘን ላይ እንዳሉ የራስ ማርዬ አሽከሮች ገደሏቸው ያም ሆነ ይህ ድሉ የራስ ማርዬና ለደጃዝማች ውቤ ሆነ ደጃዝማች ውቤም ትግሬን በሞላ ገዙት ራስ ማርዬ በእንደራሴነት ሶስት አመት ገዝተው ሲሞቱ ወንድማቸው ራስ ዶሪ በሺህ 824 ዓ/ም በወንድማቸው ወንበር ተቀ ምጠው በጌምድርና ጐጃምን ለሶስት ወር ገዝተው ባልታወቀ ምክን ያት ታመው ስለሞቱ ከርሳቸው ቀጥለው የወንድማቸው የራስ አሉላ ልጅ ትንሹ ራስ አሊ በሺህ 824 ዓ/ም በሚያዝያ ወር እንደራሴነቱን ሥልጣን ይዘው ያስተዳድሩ ጀመር ። ደጃዝማች የአሉላ መርሶ አባ መርሶ በሬንቶ ከመሃመዶች ይማሞች (አባጋሮ) የሚወለዱትን መነን ይማምን አግብተው አሊን ወለዱ መነንም እቴጌ ተብለው ጐንደር እስከመጡ ድረስ ደብረ ታቦር ከተማ ይኖሩ ነበር ።

ትንሹ ራስ አሊ ለአጐታቸው ራስ ጉግሣ ያነገቧቸውን ጓጋርን ከዙፋን አውርደው የዳግማዊ አጼ ኢያሱን ልጅ አባታቸው በአሰሩት

በከበሩራን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የሚኖሩትን መምህር ገብረ ክርስቶ ስን አምጥተውና አንግሰው በዙፋን ላይ አስቀመጣቸው ንጉሡም ትንሽ ቀን እንደቆዩ አልፈልግም ስላሉት ሳህለ ድንግል ብለው ሳል ሳዊ ዮሃንስን አንግሰው አስቀመጣቸው ።

ሣህለ ድንግል ሣልሳዊ ንጉሥ ዮሃንስ ብለው እናታቸውን የደጃች አሉላ ሚስት የነበሩትን ወይዘሮ መነን አጋብተው እቴጌ አሰኝተው በጐንደር አልጋ ላይ አስቀመጣቸው ።

እቴጌ መነን ሣልሣዊ ዮሐንስን ከማግባታቸው በፊት ደጃዝማች አሉላን አግብተው ደብረ ታቦር ጉና ስማራ ላይ ይኖሩ ነበርና በዚህ ሥፍራ ትንሹ ራስ አሊ ተወልደው ያደጉበት ስለነበር ራስ አሊ ከእና ታቸው ጋር ብዙ ጊዜ ደብረ ታቦር እየሄዱ ይቀመጡ ነበር የሴሩ ጓን ጉል ዘር የሆኑት እነዚህ እነራስ አሊ ጐንደርን በሚገዙበት ሰዓት በየጊዜው ከሰሜን ከምዕራብ ከደቡብ አንገዛም የሚሏቸውና ጦር የሚያ ነሳባቸው ብዙ ነበር ነገር ግን ወሎና የጁ ኤራያ ቤተሰብ ስለሆኑ ጦርነት አንስቶባቸው አያውቅም ።

ከነዚህም ስከታወቁት ዋና ዋናዎቹ በዳሞትና በጐጃም ደጃዝማ ብሩና ደጃዝማች ጐሹ በደንቢያና በቋራ ደጃዝማች ክንፉ በሰሜ በትግሬ ደጃዝማች ውቤ በሸዋ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ እነዚህ ሁሉ የየግል ሃገራቸውን ያስተዳድራሉ እንጂ ለጐንደሩ ንጉሥና ለእንደራሴው አልገበሩም ሆኖም ግን ለራስ በራሳቸው እንደራሴው ተጠቅሞባቸዋል ከሁሉም የሚበልጡት ዋና አስፈሪ የነበሩት ደጃዝማች ውቤ ነበሩ ለእሳቸውም ከራሣቸው ከሰሜን ግዛት ያዘጋጁት ጦር አርባ አም ስት ሺህ አዲስ ከሚገዙት ከትግሬና ከሃማሴን አምሳ ሽህ ጦር ነበር ቸው እንደዚህም በናይብ ግዛትና በምፅዋ በኩል በአሽከራቸው በብ ላቴ ኮከቤ አማካኝነት ከቱርክ ናይብ ግንኙነት እያደረጉ ብዙ የጠ መሣሪያ ነበራቸው ይሄንም ሁሉ ሊያዘጋጁ የቻሉበት ምክንያት እራሳ ቸው ለመያዝ አስበው ነበር እንዲያውም ዋናው ሃሳባቸው በእንደራ ሴነት ብቻ ሳይወሰን ዘውድ ጭነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመ ሆን ምኞት ስለነበራቸው አሊቃ ሃብተሥላሴን ወደካይሮ ልከው ሲነ ግቡ ቀባአ መንግሥት የሚቀቢቸው ጳጳስ አቡነ ሰላማን አስመጡ የሚነግሱበትንም የደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ባማረ ሁኔታ አሠሩ

ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ውቤ ጳጳሱን አስከትለው ከትግሬ ወደበ ጌምድር መምጣታቸውኔ ሲሰሙ ትንሹ ራስ አሊ ከትልቁ ራስ አሊ ጀምሮ የተደራጀውን የወሎ የየጁ የራያ ይልቁንም የበጌምድር ወታደር

ከሰባ ሺህ በላይ ነበራቸውና በሺህ 834 ዓ/ም በጥር ወር በደብረ ታቦር አካባቢ አመድ በር (እንደማማሹ ደ/ታቦር) በሚባለው ሥፍራ ላይ ገጥመው ሳለ ጳጳሱ አቡነሠላማ ደጃዝማች ውቤን የሚወጋ እው ግለሁ ስላሉ ዋና ዋናዎች ወደደጃች ዌቤ ገቡ ነገር ግን ግዞትና ስ ኩት የማይፈታው የራያና የወሎ ጦር በጀግንነት ይዋጋ ጀመር ። የደ ጃዝማች ውቤም የሰሜንና የትግሬ ጦሬ በርትቶ ይዋጋ ጀመር በዚህ ጊዜ የደጃዝማች ውቤ ጦረኛ የራስ አሊን የፈረሰኛ ወታደር በነፍ እየመታ ሲጥለው ራስ አሊ አሉላ ይመለከቱ ነበርና ከእንግዲህ ወ ያ ምን ተስፋ አለ ብለው ከጦርነቱ ቦታ ሸሽተው ወደዋድላ ገ ሄደው ተቀመጡ ።

ደጃዝማች ውቤም የራስ አሊ ፈረሰኛ ወታደር የትግሬንና የሰ ሜንን ጦር በነፍጥም በጐራዴም እየመታ ሲጥለው አዩና እንደራ አሊ ከእንግዲህ ወዲያ ምን ተስፋ አለኝ ብለው ድል የሆኑ መስሏቸው ሸሹ ነገሬ ግን ደጃዝማች ውቤ የልጃቸውን የሂሩት ባል ራስ አሊ መሸሻቸውን ከእውነተኛ ሰው ስለሰሙ ከሸሹበት ተመልሰው ሲያዩ ድል አደረጉና በድል አድራጊነት ደብረ ታቦር ከተማ ገብተው በራ አሊ አዳራሽ ውስጥ ገብተው ተቀመጡ ልጃቸውንም ሂሩትን ከራ አሊ ነጥቀው ለጉጃም ገዢ ለደጃዝማች ጉሹ ሊድሩለት ቃል ገቡለት ደጃዝማች ጉሹ ይዘዋት ለ15 ቀን ቆዩ ።

እንደዚህም ሆኖ ደጃዝማች ውቤ በደብረታቦር ትልቅ ግብርና ግብዣ አድርገው ሳለ የራስ አሊ የጦር አለቃ አዛዥ አሊጋዝ ዋና ምርጥ ጀግና ወታደሮች ይዞ መሣሪያውን ለማስረከብ የመጣ አስመ ርሎና አስጠርቶ የደጃዝማች ውቤም ሠራዊት በየቦታው ተብትኖ ሳለ አዘንጋና ደጃዝማች ውቤን አሠራቸው አብረዋቸው የነበሩትን አጋፋሪዎች ፍታደኛ የሆነውን ሲያስር እንቢ ያለውን በጥይት አስ ብድቦ ገደላቸው በዚህን ጊዜ የተማረኩትን ደጃዝማች ውቤን ለ ታው ለራስ አሊ ለማስረከብ ቢፈልግ ቢፈልግ አጣቸው ከዚያም ግን ወደሃገሩ ሲመለስ የዚህን የጦርነት ወሬ ያልሰማ ተመላሹን ወታደር ከመንገድ አግኝቶ እንዲህ ብሎ ጠየቀው እባክህ እራስ አሊና የደጃዝ ማች ውቤ ጦርነት በምን አለቀ ።

ደጃዝማቹ ውቤ ሸሽተው እንደገና ተመልሰው ድል አድርገው ደብረታቦርን ከያዙ በኋላ ተማርከው ቃስፋ ራስ አሊ ደግሞ ሸሽ ተው የሄዱበት ሃገር ጠፋ — እረ እባክሀን በወግ አድርገህ አውራኝ ብሎ እንደገና ቢጠይቀው ።

እነሱ እራሳቸው በውጊ ያልሆኑትን እኔ እንዴት አደርጌ በውጊ -አደርጌ ሳውራህ አለውና ተሳስቀው መንገዳቸውን ቀጠሉ ይባላል ።

ምንም የሁለቱ ደካማነት ቢታይ አዛገር አሊ.ጋዝ ራስ አሊ ያሉበትን አሰልሉ ድሉ የርስዎ ነውና ጠላትዎን ደጃዝማች ውቤን ማርኬ ልጅናቸው ብሎ ላከባቸው ራስ አሊም ከተደበቁበት ከዋድላ በአስራ ሰባት ቀን ተመልሰው ደብረታብር ገቡና ከሚስታቸው ከሰይዘሮ ሂሩት ጋር ተገናኙ በሁለቱ በኩል ያለውን ተመልካች ምንም ቢያሳዝነውና ቢያስገርመው ብዙ ሰው ቢያጋድሉና እራስ በራሳቸው ቅጡ የጠፋ ድርጊት ቢፈጽሙ መጨረሻ ሁለቱ ታርቀው ራስ አሊ የበላይነት ደጃዝማች ውቤ የበታች ሆነው ትግሬን እንዲገዙ ተፈቀደላቸው የተደመደውን ግብር ሊልኩ ጳጳሱንም ለራስ አሊ ትተው ሲሄዱ ተስማሙ ። ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ውቤና ራስ አሊ አንድ ጊዜ ሲስማሙ አንድ ጊዜ ሲጣሉ እስከ ሺህ 843 ዓ/ም ደረሱ ከ1843 እስከ 1845 ዓ/ም ለሁለት አመት ያክል ተኮራርፈው ሲኖሩ ራስ አሊ ደጃዝማች ካሣን እንግዲህ ጦርነት እንድትገጥመው ብለው ለደጃዝማች ውቤ ቢልኩባቸው እኔ አልመጣም እራስህ ሄደህ ግጠመው ብለው አለመታዘዛቸውን ገለጡ ራስ አሊም በ1845 ዓ/ም በመጋቢት ወር ጦርነት ከደጃዝማች ካሣ ጋር ገጥመው ድል ሆኑና ወደየጁ ሃገራቸው ሄደው ተቀመጡ የእንደራሴነት ግዛታቸው ሃያ ሁለት ነው የወሬ ሴሰኞች ዘመንም የመሣፍንት ግዛት 68 ዘመን ነው እንደዚህ ሆነ አጼ ቴዎድሮስ ምንም ጠላታቸው ቢሆኑ የየጁን የራያ ዘቦን ሃገር እንዲገዙ ፈቀዱላቸው ይሄውም የባለቤታቸው አባት ስለሆኑ ነው በዚህን ጊዜ እምሳት ቤት ክርስቲያን ሲተከሉ የጥንቶችን ትባርጃ ማርያምን ጉባ ለፍቶ ሐለሃይማኖትን አሳድሰው አሰርተዋቸዋል ። ከዚያም እንግሊዝ አጼ ቴዎድሮስን ለመግደል ሲመጣ ሃገሬውን አዘው ከአራት ሺህ በላይ የሚሆን ጭፍራ ልከው በእንግሊዝ ጦር ሠራዊት ጉን እንዲሰለፍና እንዲዋጋ አድርገዋል ከዚያም ብዙ ዘመን ከተቀመጡ በኋላ በአጼ ሚኒሊክ ዘመን መንግሥት አርፈው በተከሉት ቤት ክርስቲያን ገዶ ምድኃኔዓለም በክብር ተቀበሩ ።

## ምዕራፍ ሠላሳ

### የታላቁ ጀግና የአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት

ልጅ ካሣ በአባታቸው ከአንበሳ ዳዊት የልጅ ልጅ ከወሰን ሰገ ልጅ ከወይዘር ኢፍራታና ከአጼ ልብነድንግል ልጅ ከአቤቶ ፈቅ ዘር የተወለዱ ናቸው ።

የትውልዱ ሃረግ እንደዚህ ነው አንበሳ ዳዊት ወሰን ሰገድና ወናግዝጉን ወለደ (ዳሞት ነጋሺ ወሰን ሰገድ ዘርአ ዮሃንስን እምደ ብ ሃንን ሃርቦን ሴቶች ደግሞ ኢፍራታ ንግስት አዜብን ወለደ ወይዘር ኢፍራታ አቤቶ ፈቅጦርን አግብታ ባህፈላህም መዝሙርን እንደወ ደች ፈቅጦር በግራኝ አህመድ ጦርነት ሲሞት ወደአባትዋ ሃገር ልጅ ዋን ይዛ ወደዳሞት ሄዳ ተቀመጠች ፃህፈላ ህም መዝሙሬ ሰረገ አዝማች ሰረገላን ፣ ዘሥላሴን ፣ ራስ ዘሥላሴ ፣ ጣሚንደጃዝማች ጣ እናፌኖ ደጃዝማች አዳኖሬ ወልደ አቢብን ፣ ደጃዝማች ወልደ አቢብ ወልደ ጊዮርጊስን ፣ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ጌታን ፣ ፊታውራሪ ጌታ እ ቴን ወለዱ ደጃዝማች እሸቴ የአጼ በካፋ ባለቤትን እቴጌ ምንትዋብ ወልደ ልዑልን ለሙን ተሰዳ ኢየሱስን ማሙየን ወለዱ ራስ ወል ልዑል እንደአበታቸው ስም እሸቴን ራስ እሸቴ ዘውዱን ደጃዝማች ዘውዱ ድንቅነሽ ሃይሉን አግብተው ደጃዝማች ጉሹን ደጃዝማች ጉ ደወይን ውሃና ከባላምባራስ እንቁ ፀሃይ ልጅ ከወይዘሮ ውብእ ደጃዝማች ተሰማን ደጃዝማች ብሩን ደጃዝማች አለሜቱን ደጃዝማች ጃቶቤን ደጃዝማች ማሩን ልጅ ሃይሉን ልጅ ይማምን ልጅ ይልማ ሩጉች ደግሞ ድንቅነሽን ሁሉ አገርነሺን ወለተ ጊዮርጊስን መነብር ስምንት ወንዶች አራት ሴቶች ወልደዋል ልጅሃይሉ የደጃዝማች ክ አን እህት የአቶ አብተውን ልጅ ወይዘር አትጠገብን አግብተው ልጅ ካሣን በ1810 ዓ/ም ወለዱ ልጅ ካሣ በተወለዱ በአራተኛው አመ ከባታቸው ልጅ ሃይሉ ከእያታቸው ከደጃዝማች ዘውዱ ጋር አለ ንግሥን ለመውጋት በሄዱ ጊዜ አብረው ሄደው በጦርነቱ ስለሞቱ እና ታቸው ወይዘር አትጠገብ አብተው ወደ አባታቸው ሃገር ቋራ ይዘዋቸው ሄዱ በዚህን ጊዜ የእናታቸው ወንድም ቀኛዝማች ክን አብተው እለቱ ጨቁጫን እቋዋራንም ጨምር ይገዛ ነበርና እናታቸው



አፄ ቴዎድሮስ

ለሞቶች ማህበረ ሥላሴ ከጎጃም ለትምህርት ይዘው ወሰደዊ ለመነ ኩሳቱ አደራ ብለው ሰጥተዋቸው ሄዱ ።

በዚህን ጊዜ ምንም ራስ ጉግሣ ልጃቸውን ወይዘሮ ወለተተክሌን ለደጃዝማች ማሩ ቢያጋቡት የአባቱን አባት ደጃዝማች ዘውዱን በጣና ውስጥ ዕንደታሠሩ ስለሞቱ እያቱን ይወዳቸው ነበርና ራስ ማርዬ በእንደራሴነት በሚገዙበት ዘመን የመሣፍንቱን ልጆች በየአሉበት ነገር እየፈለገ ይገድል ነበረና ወደ ማህበረ ሥላሴ ገዳም ሄዶ ብዙ ህፃናት የማን ልጆች እንደሆን እየጠየቀ ሊገድል ሲል የወንድሙን

ልጅ ካሣን አግኝቶ ወደብልያ ንጉሡ ይዟቸው ሄደ ከዚያም ደንገ
ለሁለት አመት መምህር መላኩ የሚባል ቀኛርላቸው ዳዊት ደገመ
እስከሚጨርሱ ከዚያ ቆዩ በዚህን ጊዜ የአስራ ሁለት አመት አደ
ልጅ ነበሩ ከዚያም የአባታቸው አባት ወደሆኑትወደ ደጃዝማች ጉ
ቤት ሰከላ ሄደው ስምንት አመት አብረው እየተላኩ ተቀመጡ ካ
ሣን ልጅ ካሣ በደጃዝማች ጉሹ ቤት በነበሩበት ጊዜ እንደልጃቸ
ልጅ ቀርቶ እንደአጋፋሪዎቻቸው ልጆች እያዩአቸውም ነበር እንዲ
ውም አንተ የድሃ ልጅ እናትህ ኮሶ ሻጣ አላላደገችህም ብለው ሲና
ሩት ከደጃዝማች ጉሹ አፍ የሰሙት ሁሉ አንተ የኮሶ ሻጭ ልጅ እያ
ሲሰድቡዋቸው ተናደው ከቋዋሬት ተነስተው መተከል ከዚያ ትግ
ርት ሲማሩበት የነበረውን ሃገር ደርሰው ወደ ኩንፈል ሄዱ ከዚያ
የሃያ አንድ አመት ወጣት በነበሩበት ጊዜ በአደንም ሆነ በሚያደ
ጉት ሁሉ የሚወዳደራቸው ሰው ስላልነበረ የሁሉ አለቃ ነኝ ሲ
ሠራዊታቸውን ሰብስበው መይሣው በሉኝ አሉ ከዚያም ከሠራዊታ
ቸው ጋር ወደ ሱዳን ሄደው ሰናርና ካሰቲ ከዚሬ የሚገቡትን የቱርክ
ወታደሮች በ1831 ዓ/ም ድል አድርገው የድንጊላ ጉሣ የሆነ ሼ
መሃመድ አሊን የበርሃው ንጉሥ መሃዲ ብለው ከቱርኮች የተማረከውን
ልብስና ድንኳን ሰጥተው ቱርኮችን ተባብረው ከአፍሪካ ምድር እንዲ
ያወጡ ከተማከሩ በኋላ ወደሰፈራቸው በሰላም ተመለሱ እሳቸውም
ግ ብጾችን ተዋግተው ብዙ የጦር መሣሪያ ስላገኙ ልጅ ካሣ በአካባቢያ
ቸው ያለውን ሃገር ከሌላ ገገር ነፃ አውጥተው ይመሩት ጀመር ስማ
ቸውም ከሱዳን እንደተመለሱ ልጅ ካሣ መባላቸው ቀርቶ መይሣው
ካሣ ይባሉ ነበር ።

መይሣው ካሣ በደጃዝማች ጉሹ ቤት በነበሩበት ጊዜ ተምህር
ማታ የሚወራው ከየጁ የሴሩ ንጉሥ ልጆችና የልጅ ልጆች ጉንደርን
ትግሬን ጊዜም ሲሰጣቸው ሲያስገብሩ እነሱን ለማውረድ ከትግሬ
ከሸዋ እንደዚሁም ከዳሞት ጀግና በመጥፋቱ ሀሉም እያዘነና የሚያጠ
ቃበትን ዘዴ እየፈለገ እንደተቀመጠ ደህና አድርገው ተረድተዋል
እንደዚህም ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ከምሥራቅ ይመጣና ኢትዮ
ጵያን አንድ አድርጎ ይገዛል እያሉ ሽማግሌዎችና አዛውንቶች ሲያወሩ
ይሰሙ ነበርና ይሄን ስም ለራሳቸው ለማድረግ ጠዋትና ማታ ዳዊት
ደግመው ሲጨርሱ አምላካቸውን ይለምኑት ነበር ።

መይሣው ካሣ አለፋ ጣቁሣንና አርማጭሆውን ቋራንና በለያ
ሱኪንና ኑብያን የበላይ ሳይኖርባቸው ሸርኔ ግርያም ተቆጣጠሩ
በሚያስተዳድሩበት ጊዜ የጉንደሩ መስፍን ትንሹ ራስ አሊ ቀኛዝማች

ይባል የነበረውን ደጃዝማች ክንፉ ብለው ያንን ሽፍታ ካሣ አስረህ ይዘህ የመጣኸው እንደሆን እስከ ሱዳን ያለውን ሃገር እሰጥሃለሁ ብለው ላኩበት ደጃዝማች ክንፉ ምንም የእሁቱ ልጅ ቢሆን ለሹመት ሲሉ ከደንቢያ ከአርብያ መድሃኔዓለም ተነስተው የሚጠይቁ መስለው ወደ ቋሯራ ሄዱ ከዚያም እንደደረሱ ደህንነቱን ሲጠይቁት ከቆዩ በኋላ አታለውና አድብተው በአሽከሮቻቸው ይዘው አስሩት በበነጋታው ራስ አሊ ወደሚገኙበት ደብረታቦር ይዘው ሲሄዱ ደንቢያ ጨዋሂት የሚባለው ሥፍራ ላይ ሲደርሱ አሽከሮቻቸው ተኝተው ነበርና መይሣው ካሣ እጃቸው በሰንሰለት እንደታሠሩ ሌሊት አምልጠው በስንት መከራና ችግር እንደገና ቋሯራ ገቡ ከዚያም የሳቸው ወዳጆች ከእሱ ቤት ተጠርተው ሰንሰለቱን በመጋዝ ቆረጡላቸው ደጃዝማች ክንፉም ተናዶ መጀመሪያም ከሴሩ ጉዋንጉል ዘሮች ጋር አይዋደድም ነበረና ለመጥፋቱ መልስ ሳይልክ እንደገና ሄዶ ከመይሳው ካሣ ጋር ጦርነት ለመግጠም ይዘጋጅ ጀምር ራስ አሊም ከደጃዝማች ውቤ ጋር ጦርነት አድርገው ነበርና የካሣን ነገር ችላ አሉት ።

ራስ አሊና ሚስታቸው የሂሩት አባት ደጃዝማች ውቤ በጥር ወራት ተጋጥመው ሁለቱም በጦርነቱ ሸሽተው ህዝብ በሚሰቅባቸው ጊዜ ደጃዝማች ክንፉ በእሳቸውም ህዝብ የሳቀባቸው መስሏቸው በ፲ሀ 1834 ዓ/ም ተናደው መይሣው ካሣን ለመውጋት ሄዱ ከዚያም የሁለቱን ጭፍራ ለአራት ሰዓት እንደተዋጋ ደጃዝማች ክንፉ በተይት ተመቱና ከፈረሳቸው ላይ ወደቁ ከዚያም አንድ ጉቢዝ ወታደር ሄዶ ገደላቸው ግማሹ ጦር ቢሸሽ ግማሹ ለመይሣው ካሣ እጁን ሰጠና በታማኝነት ያገለግላቸው ጀመር መይሣው ካሣም አጐቱን ደጃዝማች ክንፉን አሬሳቸውን በክብር ወደ ደንቢያ ልከው አስቀበሯቸው በዚህን ጊዜ መይሣው ካሣ የሃያ አራት አመት እድሜ ወጣት ነበሩ ።

እንደዚሁ በሃያ አራት እድሜያቸው አንድ ሺህ ሁለት መቶፈረሰኛ ጦር ይዘው ሥርናን ቁርኮች ይገዙት ነበርና ሌሊት ከተማውን ከበው ዋናውን የከተማውን አስተዳዳሪውን አብደል አዚዝ ሙስጠፋን አስረው ብዙ የጦር መሳሪያ የሚበቃቸውን ያክል ይዘው አንድ ሰው ሳይሞትባቸው መሃመድ አሊን ሸመው ተመልሰው ቋሯራ ሄደው ተቀመጡ በዚህን ጊዜ በእንዱርማንና በካይሮን ስማቸው ታወቀ መይሣው ካሣ ለአሽከሮቻቸው በጣም ምቹ ከመሆናቸው ሌላ ከማዘዝ መታዘዝን ይወዱ ነበር ይሄን ሥራ ከማለት እራሳቸው ተነስተው መስራት ይወዱ ነበር ከሚያደርጉት ነገር በሰፊው የሚነገርላቸው አሽከሮቻቸው ግብር ቀርበው ከበሉ በኋላ ነበር የሚበሉ ይሄውም

መንገድም ውለው ሆነ ወይም ከሥራ ሲመለሱ አብረዋቸው የዋሉት ወታደሮች መጀመሪያ በሥነሥርዓት አስቀምጠው ሰንጋ በሬ አርደ እራሳቸው አሳላፊ ሆነው ያበላሉ ያጠጣሉ ሠራዊታቸው ከበላና ከጠ በኋላ በፈንታቸው ሲያሳልፉና ሲያስተናግዱ ከነበሩት ከዋና መሪዎቻቸው ጋር ሆነው ለግብር ይቀመጣሉ በዚህን ጊዜ የበላ ሠራዊት ግማሹ በተራው ሲያሳልፍ ግማሹ በበር በር ሆኖ ዘበ ሆኖ ይጠብቃል ፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ጦርነት ውለው ድል አድርገው በድል አ ራጊነት እንደተለመደው ለሠራዊታቸው ቆመው ካበሉ በኋላ በፋንታ ቸው ሲበሉ ተቀመጡ በዚህን ጊዜ በጣም እርቧቸው ነበርና ሥጋ ቁርጥ የሚያቀርበው አሳላፊ የሥጋውን ጉን ትቶ አጥንት ያለበት ክፍል እያዞረ አቀረበላቸው አሁንም እንደገና ሥጋውን ክፍል ትቶ አጥንቱን እያዞረ እንቢ ስላላቸው በያዙት ካራ (ቢላዋ) ሆዱን ቀደዱት ከእግራቸው በታች ተረግጠው ሌላውን ሥጋ ቁርጥ አሳላፊ አም ብለው ያንም እየተንቀጠቀጠ ይዞ ቀረበ ፍራቱን አይተው ከእናንተ እንጨት ይሻለኛል ብለው ከፊታቸው አጠገብ የሥጋ ቁርጥ መስቀ አስተከሉ ከዚያም ከሙጣው ትንሽ እየቆረጡ ከበሉ በኋላ ከአራ መቶ በላይ ከሚሆኑት አለቆችና አዛገች አንድ እንኳ የሚያወሩ የሚናገር ጠፋ ከዚህ በኋላ አጫዋቻቸው የሆነውን አዝማሪ ተነስቶ እንደዚህ በል አሉት

ያሁሉ ድንፋታ ያ ሁሉ ፉከራ
ለምነው የቀረ ለምነው የጠፋ

ለማኮኮስ እንኳ ምነው ልብ የፈራ በል አሉት

ከዚህ ከመኳንንቱ መሃል አለቃ ሳህሌ የሚባል ሊቅ እንዲህ በልብሱ አዝማሪው ተናገረ ይባላል ፡፡

እንዲህ ያለ ቁርጥ ከፊታችን መጥቶ
ማነው የሚናገር እረ አፉን ሞልቶ

ምሳሌው ቁርጥ ሥጋ ከፊታችን መጥቶና አፋችንን ስለሞላነው መናገር አንችልም ሲሆን ሌላው ታሪክ ምሳሌው ደግሞ ከፊታችን ጨክነው በካራ ወግተው ሲገሉት አፉን ሞልቶ እንደልቡ ማነው የሚያወራ ማለታቸው ነው ከዚህ ቀን ጀምሮ በመይሣው ካሣ ፊት ቀልድና እኛ ሙር ዛቻና ቸልታ ንቀትና ኩራት ፈፅሞ አይደረግም በጦር ሜዳ ላይ ጨዋታና ሣቅ ፈጽሞ ተሞክሮ አያውቅም ፡፡

እሳቸውም እንዲህ ያለ ቁርጥ ላለው እለታ ግሀሉ ለአዝማሪቸው እንደዚህ በል አሉት

ደብቆ ጮማውን ቢያሳየኝ አጥንት

የደበቀውን ቁርጥ ዘርግፌ ጣልኩት

ብለው መለሱለት ከዚያም የወደቀውን ሬሳ አንሱትና ወስዳችሁ ቅበሩት ብለው አዘዙ ።

መይሣው ካሣ በገዛ ሃይላቸው የያዙትን ሥልጣን የአስተዳደር ወሰን ከሌሎች መሣፍንት ተሽሎ ስለታየ ህዝቡም ወደሣቸው እየሄደ ስለሚያመለከት ጉዳዩ በቶሎ ይፈጸምለት ነበር ሌላው ደግሞ በመሣፍንቱ አስተዳደር እየተናደደ ቤቱን እያቃጠለና እያፈረሰ ለኗሁ ለመይሣው ካሣ ወታደርነት እየሄደ ገባ በዚህን ጊዜ ጦራቸው ከቀን ወደቀን እየበረታ በሄደ ቁጥር ለጉንደር ንጉሥ እንደራሴ ለሆኑት ይጥርና ለጉጃሙና ለትግሬው ገዢ ጥዋትና ማታ በግብርም ጊዜ ሆነ በሌላ ሰዓት ስለመይሣው ካሣ ነበር የሚወራው ።

በዚህን ጊዜ የመይሣው ካሣ ጦር ከቀን ወደቀን እየበረታና እየበዛ በመሄዱ ትንሹ ራስ አሊና እናታቸው የሶስተኛው የማንስ ባለቤት እቴጌ መነን እንዲህ ያለውን ጀግና ዝም ብሎ ከመስማትና ከመፍራት ይልቅ በጋብቻ መዛመድ ያስፈልጋል ብለው ተማክረው ልጃቸውን ወ/ሮ ተዋበችን በ1840 ዓ/ም በሚያዝያ ወር ዳሩላቸውና የደጃዝማችነትን ማዕረግ ሰጥተው ከደንቢያ እስከ ኑብያ ያለውን ግዛት ፈቀዱላቸው ከዚያም ደጃዝማች ካሣ ወደከሰላ ዘምተው ቱርኮችንና ግብጾችን ድል አድርገው ወደ እንዱርማን አባረው ሰደዷቸው በዚህን ጊዜ በጦርነቱ ቆስለው ወደ ዋና መቀመጫቸው መተማ ተመልሰው ገብተው ሳለ አያታቸው የጉጃም ገዢ ደጃች ጉሹ ከራስ አሊ ጋር ደብረታቦር ተገናኝተው ከተነጋገሩ በኋላ ለደጃዝማች ጉሹ ሰጡባቸው ።

ደጃዝማች ጉሹ ዘውዱ ለመንገሥ ምኞት ነበራቸውና ከዚህም ላይ የውጭ ሃገር ሰዎችን ከፈረንሳይ ሃገር አርናና ዳቢድቤና አንቷን ዳቢድ ወንድማማቾችን እንደዚሁም ከእንግሊዝ ስማቸው ያልታወቀ ብዙ ሚሲዮኖች ሃገር መርማሪዎችን በቤታቸው ማስቀመጥና መርዳት ይወዱ ነበር ። እንዚህም ሚሲዮኖች ከሃገራቸው መንግሥት ጋር አስተዋውቀው ብዙ የጦር አዳዲስ መሣሪያ እንደሚያስመጡላቸው ቃል ገብተውላቸው ነበር ይባላል ። ለዚህ ይሄን የወጠኑትን

የጦር ሃይል ከግብ ለማድረስ በሚመኙበት ጊዜ የልጃቸው ልጅ ደጃ ዝማች ካሣ ተብሎ ከእርሳቸው የበለጠ ስምና ጀግንነት ይዞ ስላዩት ቀኑበት ሊያጠፉት ተነሱ ።

ሆኖም ግን ደጃዝማች ካሣ ለአያቱ ለደጃዝማች ጐሹ እንዲህ ብሎ መልእክት ላከላቸው ይሄ የሰማሁት ነገር እውነት ሆኖ ከሆን ከእኔ ነጥቀው ለእርስዎ ከሰጡዎ ራስ አሊ የእኔን ብቻ ሳይሆን የእርስዎ ጠላት ናቸው አባትና ልጅን ለማጣላት ያደረጉት ዘዴ ነውና ይቅር ብዎ ብሎ ላኩባቸው ነገር ግን ደጃዝማች ጐሹ ከጐጃም ላይ የጐን ደር አካባቢ ከተማ ስለተጨመረላቸው ደስ ብለው ራስ አሊንም አው ርደው እራሳቸው ለመንገስና ለመግዛት ነበር የፈለጉትና ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት ጦራቸውን ይዘው ወደ ደንቢያ ሄደው ተቀመጡ ። ደጃዝማች ጐሹና እቴጌ መነን ይማም ለሰሙ የነገሱት ሣልሣዊ ዮሃ ንስ ሶስቱ ጐንደር ከተማ ውስጥ ትልቅ ግብዣ ሲያደርጉ ሰነበቱ ።

በዚህን ጊዜ ደጃች ወንድ ይራድ በደጃዝማች ጐሹ ቤት የሰማ ውን ንግግር ያንን የኮሶ ሻጭ ልጅ ይዠ ከነህይወቱ አመጣዋለሁ ብሎ በእቴጌይቱና በደጃች ጐሹ ፊት ተናግሮ ሄደ ።

ደጃዝማች ካሣ ጦር ሄደው ሳለ ግዛታቸው ለሌላ መሰጠቱን ለማረጋገጥ ሁለት ልዩ ልዩ ምርጥ ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ደን ቢያ ሲመጡ ጫሞት ከሚባለው ሥፍራ ላይ ድንገት ከደጃች ወንድ ይራድ ጋር ተገናኝቶ ውጊያ እንዲጀምሩ ወንድ ይራድ ተማረከና ለምን እንደመጣ ምን ብሎስ እንደመጣ ሲመረምሩት የተናገረውን ሁሉ ነገራቹው ።

በዚህን ጊዜ ደጃዝማች ካሣ ትልቅ ግብዣ አደረጉና ለሠራዊታ ቸው ጠጅና ጠላ ሲያጠጡ ለደጃዝማች ወንድ ይራድ መጠን የሌለው ኮሶ አጠጡ ። ከዚህ ቀጥሎ ያለው ግጥም

> የእንቆቆ ልጅ እንቆቆ የኮሶ ልጅ ኮሶ
> በሽታው ያሽራል እንኳንስ ተቀምሶ
> ኮሶ ሻጭ ናት ብሎ ማነው የነገረህ
> በል እንካ ቅመሰው አትጐፍንን አይከፋህ
> የጀግናወን እናት የእኔን የመይሣው
> ኮሶ ሻጭ ናት ብሎ የነገረህ ማነው
> ደቁሰህ ለውስህ በል እንካ ተጋተው

በህዝቡ ዘንድ ሲዘፈን የነበረው ግጥም ደግሞ
እንቆቆና ኮሶ ሲጠጣ ለውሶ
እየነጡ ወንድ ይራድን ሲፈጭ ትጉንብሶ
ወዳጄ ወንድ ይራድ ምነው የማይኮራ
ነውር አይደለም ወይ መግባት በቤት ሥራ
ደጃች ወንድ ይራድን የሚመከረው ጠፍቶ
ሲፈጭ አደረ አሉ በቤት ሥራ ገብቶ

ደጃዝማች ወንድ ይራድን ኮሶ እያስደቆሱና እያስበጠበጡ ሲያጠጡት ሰነበቱ ። ደጃዝማች ካሳ በእንዲህ ያለ ጭካኔና ውርደት ከሰነበቱት በኋላ በመጨረሻ ቀን ልክ የሌለው ኮሶ ግተው ወንድይራድን ገደሉት አብሮ የመጣውን ወታደር ፈቃደኛ የሆነ ከሣቸው ጋር ሊቀመጥ ፍቃደኛ ያልሆነ ወደሃገሩ እንዲመለስ ትእዛዝ ሰጡ ነገር ግን ሁሉም ከደጃዝማች ካሣ ጦሩ ጋር ተደባልቆ በየአለቃው ተቀመጠ ከዚያም ጉርጉራ የሚባል ሃገር ላይ ከጣና ሃይቅ አጠገብ ሄደው ተቀመጡ ።

የደጃዝማች ወንድ ይራድ አሟሟት በየሃገሩ ይወራና ይዘፈን ነበርና እቴጌ መነንም ተናደው 1900 ወታደሮቻቸውን ይዘው ደጃዝ ማች ካሣን ሊወጉ ጉዞ አደረጉ ከዚያም ደጃዝማች ካሣ የእቴጌመነንን መምጣት ሲሰሙ ባኩዎን ከእኔ ጋር ጦርነት ባይጀምሩ ጥሩ ነው ብለው ደጃዝማች ካሣ ሚስታቸውን ተዋበችንና ሁለት ቄሶች አማ ላጅ ላኩባቸው ነገር ግን ይሄ ቆለኛ ከእኔ ጋር ጦርነት ቢያደርጉ ብሎ የሚልክብኝ እንዴት ቢንቀኝ ነው ብለው ለሽምግልና የተላኩ ትን የልጃቸውን ልጅ ወይዘሮ ተዋበችን አሳሰሩዋት ይሄን ወሬ ደጃ ዝማች ካሣ ሲሰሙ ባለቤታቸው እኔ ከአንተ ተለይቼ አልሄድም ምንም የአባቴ እናት ብትሆን ከእሱዋ አንተ ነህ የምትቀርበኝ ብለው የነበሩት ትዝ አላቸውና ብዙ ሰው በጦርነት ከ ማለቁ በፊት በዘዴ ማጥቃት ይሻላል ብለው ጦራቸውን ከአራት ከፍለው አንደኛው እን ዲሸሽ ሁለተኛውና ሶስተኛው ግራና ቀኝ ተከፍሎ ሄዶ በኋላቸው ደርሶ ሌላ የነሱ ጦር መስሎ እንዲከተል አራተኛው ክፍል በሸለቆ ውስጥ እንዲደበቅ አድርገው ነበር ከዚህ መሃል እቴጌይቱም የሚሸሽ ወታደር እንጅ ወደእኛ የሚመጣ የለም ሲሏቸው በስተቀርማ ከእኔ ፊት እንዴት ብሎ ሊቆም አሉ ይባላል ከዚያ ትንሽ እንደተጓዙ ከኋ ላቸው የነበረው የደጃዝማች ካሣ ጦር ደርሶ ሲወጋቸው የሚሸሽ የመሰለውም ተመልሶ ሲመጣ ጦርነት ለጊዜው ገጠሙ ነገር ግን እንደተከበቡ ስለአወቁ ሁሉም ጦር ፈራና እጁን ሰጠ እቴጌይቱም

በእንካሴ ተውግተው ስለነበር አስተኝተው በአሊጋ ወ/ሮ ምንትዋብ እስረኛ የነበሩትንም ፈትተው ለደጃች ካሣ አቀረቧቸው ደጃዝማች ካሣም እኔ እስምን መግደል ይትርና በእርስዎ እንኳን እራሴን በራሴ አንቀዋለሁ ስለዚህ እንደሴት ወይዘር ከግንብ ውስጥ ተደብቆ ወይ ሚኖሩት ባልዎ ይመለሱ ብለው ያመጡትን ወታደር እስከመጣሪያቸው ተረክበው መላሷቸው በዚህን ጊዜ የእቴጌ መነን መማረክና በነጻ መለ ቀቅ ከዳር እስከ ዳር ተሰማ ። እቴጌ መነን በሚማረኩበት ጊዜ ደጃዝ ማች ጉሹና ራስ አሊ አሉላ ደብረታቦር ሆነው ሰሙ ።

በዚህን ጊዜ ራስ አሊ ለደጃዝማች ካሣ ለእርሶዎ የሰጠሁትን ግዛት ልመልስለት ላእስዎና ለልጅዎ ለደጃዝማች ብሩ ጉሹ ጉዳ ምና ዳሞት ይብታዎታል ቢሏቸው ደጃዝማች ጉሹ ዘውዱ እንዲህ ያለ ፍሬት እያሳያችሁት ነው የኮሬ እንደልጅነቱ እሱውን ይገዛ ያለ ገረፍኩት እንደሆን እኔ የዘውዱ ልጅ የሃመር ጌታ አይደለሁም ብለው ደጃዝማች ጉሹ የራሳቸውንና የራስ አሊን ጦር ሃያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ የጉጃምንና (ምዕራብ ጉጃምን) የዳሞትን የወሎንና የራያን ጦር ይዘው ከሰባት ደጃዝማች ከአምሳ ሰባት ፊታውራሪና እንደዚሁም ብዙ የጦር አዝማቾች በየአሊታው አሰልፈው ወደ ደንቢያ ሄዱ ።

ደጃዝማች ካሣ በሺህ ስምንት መቶ አርባ አራት 1844 ዓ.ም ላይ በግንቦት ወር ከእቴጌ መነን ጋር መጥተው ፍቃደኛ ሆነው እ ቸውን የሰጡትንና ምርኮኛውን ግማሹን ግማሹ ወደመተማ እንዲሄ ትእዛዝ ከአስተላለፉ በኋላ ሶስት ሺህ ምርጥ የሆኑ ወታደሮችን እ ቀርተው ጉር አምባ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ሆነው ይጠባበቋቸው ጀመሩ ።

በዚህን ጊዜ አዝማሪ በጦሩ መሃል እየገባ ያቅራራና ይዘፍ ነበረና እንዲህ ሲል ዘፈነ ፣

ጉሹ አረጀና ልቡ ቢዘነጋ
ጉር አምባ ወረደ አንበሳን ሊወጋ
ጉሹ እስከልጅ ልጆቹ ጉር አምባ ላይ ወርዶ
የአንበሳን ፊት ቢያየው ወደቀ ተዋርዶ

ይሄውም ደጃዝማች ጉሹ በሄዱበት ቦታ ቢያንስ ሁለት በስተቀ አምስት ጭን ገረድ ሳይዙ ሄደው አያውቁም ይባላል አዝማሪ እንዲ አለ ፣

እዩት ተመልከቱት የራስ አሊን እብድ
በጉን አሰልፎ አምስት የጭን ገረድ
ለማን ሊሰጥ ነው ጉር አምባ የሚወረድ
ያዘው ያዘው አትላቀቀው
እንትነትህን ይወቅህ ንገረው
የትም አድሮ የትም ሄዶ
ያችንም ይችንም አፍቅሮና ወዶ
ሳይመለስ ቀረ ጉር አምባ ላይ ወረዶ
ወዶ ወዶ በሴቶች ተወዶ
በወይዛዝርት በንቆንጆት ለምዶ

ጉር አምባ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት እስከ ስምንት ሰዓት የተፋፋመ ጦርነት ተደረጎ በደጃዝማች ጉሹ ጦር ሃይል ከበባት ሊያጠቁና ቦታውን በቁጥጥር ስር አድርገው ሊይዙት ትንሽ ሲቀራቸው ደጃዝማች ጉሹ ዘውዱ የእናታቸውን ሃገር ጉጃም የአባታቸውን ሃገር ዳሞትን እንተጥቅጠው ገዝተው በሺህ ስምንት መቶ አርባ አራት ዓ/ም ጉር አምባ ላይ በጥይት ተመተው በተወለዱ በሰባ አንድ አመታቸው ሞቱ ።

ደጃዝማች ጉሹ እንደሞቱ ሠራዊታቸ ለደጃዝማች ካሣ ገባ ትላልቅ የጦር መኮንኖች ግን ራስ አሊ ወደሚኖሩበት ወደ ደብረ ታቦር ሸሽተው ሄዱ ደጃዝማች ጉሹን ዘውዱን አሬላ ደጃዝማች ካሳ ጠብር እስነስተው የወርቅ ካባ አጐናጽፈው በሻሽ ሸፍነው በክብር ሥርአተ ቀብራቸውን ደብረሲና ማርያም አስፈጸሙላቸው ደጃዝማች ጉሹን ደጃዝማች ካሣ ከጦርነቱ በፊት እባክዎን እኔና እርስዎ አባትና ልጅ ነን መዋጋት አይገባንም ብለው እማላጅ ልከውባቸው ነበር ነገር ግን ገፍተው ለጦርነት መጡ ምንም ድል ሆነው ቢሞቱም ደጃች ጉሹ ለደጃዝማች ካሣ አያት ከመሆናቸው ሌላ በቤታቸው ያደጉ በነበሩ በጣም አዝነውላቸው ሰንበቱ ።

በዚህ በለቅሶው ዕለት የተለቀሰላቸው ግጥም
ጉሹ እንደአርዬ አሊ እንደ ዳዊት፣
ከጥንት አይደለም ወይ ተልኮ መሞት
እግዜር የሾመውን እሻራለሁ ብሎ
ጉሹ መሬት ገባ ተመቶና ቆስሎ

አፍሮና ተዋርዶ እንዲያው ቀሎ መቅረት
ሰማይን በጥቅሻ ይቀላል መንካት ።

ደጃዝማች ካሣ ከደጃዝማች ጐሹ ጋር ጉርአምባ ላይ ጦርነት ሲያደርጉ የሠላሳ ሰስት እድሜ ሰው ነበሩ ።

በዚህን ጊዜ ራስ አሊ የደጃዝማች ጎሹን ድል ሆኖ መሞት በሰሙ ጊዜ ከደጃች ውቤ ጋር ተላልከው በአንድ ላይ ሆነው ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት ተማከሩ ደጃዝማች ውቤ ሃይለማርያም ጎን እራሳቸው ለመንገሥ ምኞት ስለነበራቸውና ራስ አሊንም ቢገልላቸው ደስ ስለሚላቸው አንተ ካጠገቤ ተቀምጠህ እኔን ከሩቅ ያለሁትን እንድረዳህ የምትጠይቅ አታፍርም አሁንም ደስ ስለሚላቸው እራስህ ሄደህ ግጠመው እኔ ግን በዚህ ያለው ጠላት ልወጋ ልሄድ ነው ብለው እንቢ አሏቸው ።

ከዚህ በኋላ ራስ አሊ ሰባ ስምንት ሽህ ጦራቸውን ወደ ጐርጐፍ ድንገት ይዘው ሄደው በነደጃዝማች ያዘው በነደጃዝማች አቤ ጦር መሪነት በሺህ 845 ዓ/ም አይሻል ተራራ ስር በመጋቢት ወር ጦርነት ገጠሙት ነገር ግን የደጃዝማች ካሣ ጦር ስልትና ዘዴ የተመለከተ የራስ አሊ ሠራዊት ሽሽቱን ጀመረ ግማሹም ለደጃዝማች ካሣ ገባ

በዚህ ጦርነት ራስ አሊ ድል ሆነና ወደ ደጃዝማች ብሩ ጐሹም አባቴን ያስገደሉት እስዎ ነው ብሎ እንዲያውም ሊገላቸው ነበር ይባላል። ከዚያ ከዳሞት ሸሽተው ወደደራ ሄዱ ከዚያም የደራ ገገር ግራዝማች ዋቄ ዲቦ ይዞ አሠራቸው በዚህን ጊዜ ደጃዝማች ካሣ መታሠራቸውን ሰምተው እንዲፈታቸውና ወደፈለጉት ሃገር እንዲሄዱ ብሎ ላከበት ግራዝማች ዋቄም በዝና ስማቸውን ስለሰማና ስለፈራ ለቀቃቸው ግማሹ ሰው ደግሞ የሸዋው ንጉሥ ሃይለመለኮት ሰምተው ግራዝማች ዋቄን ተዋግተው ድል ካደረጉት በኋላ ራስ አሊን አስፈትተው ወደ የጁ ከሰው ጋር አድርገው ላኳቸው ይባላል ።

ደጃዝማች ካሣ ለአጎታቸው ለደጃዝማች ብሩ ጐሹ የአባትክን ግዛት አልከለክልህም ስለዚህ ጎጃምና ዳሞትን ግዛ ከአባትህ ጋር ያጣላን ቀን ነው እኔም ደ/ጐሹን እባክዎን ከልጅዎ ጋር ጦርነት አያድርጉ ብየ ሽማግሌ እንደላኩ ታውቃለህ ስለዚህ እኔ ካለሁበት ድረስ ብለው ላኩበት ነገር ግን ደጃዝማች ብሩ ጐሹ ጊዜውን ጠብቆ ለመውጋት ብዙ ጦር ያዘጋጅ ነበር ደጃዝማች ካሣ ሃይሌ እንደዚሁ ራስ አሊን ድል ካደረጉ በኋላ የጐንደርን ቤተ መንግሥት ከንጉሡ

ማልማዊ የሃንስና ከኢቴጌ መነን ይማፃም የደብረታቦርን ግምጃ ቤት የራስ አሊን የጦር እቃ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ሂሩት ውቤ ተረክበው በቤተ መንግሥቱ ሹም ሽር አድርገው ይመሩት ጀመር ። ከዚያም ለደጃዝማች ውቤ ከግብፅ ያስመጣቸውን ጳጳስ አባ ሰላማንና የደንቡን ግብር ይላኩልኝ ብለው መልዕክተኛ ላኩባቸው ደጃዝማች ውቤም የምትለውን ሁሉ አልቀበልም ሲሉ ለተላኩት መልእክተኛ ተናግረው መለሷቸው ።

ደጃዝማች ካሣም ለአጎታቸው ለደጃዝማች ብሩ ለላኩት መልእክት ጥያቄና መልስ ማግኘት ይቅርና ለጦርነት እንደተዘጋጀ ባለ ሃገሩን እየሰበሰበ የጦር ዘዴ እንደሚያስተምርና ለጦርነት እንደተዘጋጀ ሰሙና በግሥጋሴ ሞጣ ቀራንዮ አድርገው ይባባ ገቡ ከዚያም ሹም ሽር ሲያደርጉ ሰነበቱና የጎጃምን ግዛት ከደጃዝማች ብሩ ጎሹ ነጥቀው ቀኛዝማች ተድላ ጉሉ ይባሉ የነበሩት ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ብለው የጐጃምን ግዛት ሰጣቸው በዚህን ጊዜ ፈለገ ብርሃን ከሚባለው ላይ ከደጃዝማች ብሩ ጎሹ ጋር ጦርነት ገጥመው ስለደጃች ካሣ በንግርት መነሳታቸውን ህዝቡና ሠራዊቱ ስለሚያውቅ የብሩ ወታደሮች እየከዱ ለደጃዝማች ገቡለት ሚስቱም በዚሁ ቀን ተማርካ በደጃዝማች ካሣ ፊት ቀረበች እሳቸውም የአባትዋ እርስትና ጥንት ይደረግላት የነበረው ሁሉ ክብር እንዳይጎድልበት ብለው አዘዙላት ደጃዝማች ብሩ ግን ሸሽቶ ሲያመልጥ ትንሽ ወታደሮች ተከታትለው ጦርነት አድርገው ድል ካደረጉት በኋላ ተማረከ የተማረከበትም በር ወንዝ ላይ ነው ። በዚህን ጊዜ

አትዋጋ ብየ ለዚያ ለወንድሜ
ነግሬው ነበረ እኔማ አስቀድሜ

አቅራሪ ዘፋኝ ደግሞ እንደዚህ አለ

ተገዛ ዳሞት ተገዛ ጐጃም
እግዜር የላከውን አንተ አትመልሰውም

እንኳን መጥቶ ሄደጣበት ጠላቱን ሁሉ ያገባል መሬት
አትንኩት አትነካኩት ለወዳጅ መራር ነው ለጠላቱ እሬት
ሃይልንም አቅምንም ማወቅነው መገመት

ይበልጣል ይጠቅማል ገምቶ መነሳት
ማየት ነው ደጁን አስቀድሞ ማወቅ
ከጦር መሃል ገብቶ በነፍጡ ከማለቅ

የእኛም የዚያም ሠራዊት ሄዶለት ኀረፈለት ለዚያ ለካሣ ለጀግኖች አባት ታሪቀው ተስማሙ ለዚያ ለጀግናው እግዜር ለላከው ካሣ ለወ ዳጁ ደግነው በጣም አርፋችሁ ተገዙ ዳሞት እና ጎጃም ደጃዝማች ካሣ ዳሞትንና ጐጃምን በጌምድርንና ወሎን በቤታቸው ሆኖ የሚገዛ ገር ከሾሙበትና ከላኩበት በኋላ ፊታቸውን ወደትግሬ አዞሩ ከይ ባባ ወደላስታ የላስታ ህዝብም በክብር ተቀበላቸው ከዚያም ከላስታ ተነስተው በገላ እንደደረሱ ደጃዝማች ውቤ ደጃዝማች ካሣ ወየ እሳቸው ለጦርነት ተዘጋጅቶ እንደመጣ ሰምተው ደህና አድርገው ለጦርነት እስከሚዘጋጁ ድረስ እንቢ ብለው የነበሩትን ግብርና ጳጳ ሱን አባ ሰላማን በልጃቸው ለፊታውራሪ ኀንጉልና ለብላታ ኮከቤ አሲይዘው ላኳቸው ደጃዝማች ካሣ ግን መምጣቴን ሲሰሙ አሁን የላከልኝ ብለው ለመውጋት መንገዳቸውን ቀጥለው ነበር ነገር ግን ጳጳሱ ስለለመኗቸው ጦርነቱ ቀርቶ ፊት ለፊት እንዲገናኙና ሰላም እንዲያደርጉ እኔ ካለሁበት ድረስ ይምጡና ፊት ለፊት ተያይተን ቃል ኪዳን ካደረግን በኋላ ወደሃገርዎ በሰላም ይመለሳሉ ብለው ለል ጃቸው ለፊታውራሪ ኀንጉል ውቤና ለብላታ ኮከቤ ላኩባቸው ደጃዝ ማች ውቤ ግን ከውጭ ሃገር ከፈረንሳይ ከእንግሊዝ እንደዚሁም ምፅዋ ከሚገኘው ከቱርክ ባሻ የጦር መሣሪያ እርዳታ ጠይቀው ሲኖሩ እሱ እስኪመጣ ይጠባበቁ ነበርና ወዲያውኑ መጣላቸው አሁንም ለጊዜው ለመጣም ስለፈሩ እንደገና በምፅዋ በሚገኙ ቆንሲሎችና በእንግሊዝ ቆንሲል ጥሎ ውዲን አማካኝነት የጦር አስልጣኝ እንዲመጣ ጣላቸው ገፀ በረከትና ደብዳቤ አሲዘው ወደ እንግሊዝ መንግሥት ላኩ ።

ደጃዝማች ካሣ ግን ደጃች ውቤ ሃይለማርያም አለመምጣታቸውን ሲያውቁ ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋር ስለጦርነቱና ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ይማከሩና ይወያዩ ጀመር በዚህን ጊዜ አቡነ ሰላማ የኢት ትዮጵያን ሀገሮች አንድ ኦድርጎ ለመግዛት አስቀድሞ የሕዝቡ ሃይማኖት አንድ መሆን አለበት ብለው ስለመከሯቸው ደጃዝማች ካሣም አቡነ ሰላማ የሚያስተምሩትን ሃይማኖት የማይቀበል ከላይ አንገቱ ከታች ባቱ ይቆረጣል ሲሉ በ1846 ዓ. ም. አዋጅ አናገሩ በዛን ጊዜ የነበሩት የቅባትና የፀጋ የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች እንቢ እያሉ ሁከት ሲያነሱ ብዙ የተገደሉና የተገረፉ ሲኖሩ ተራው ሕዝብ ግን የቆየውን የተዋህዶ ሃይማኖት የሚያምንና የሚያከብር ከሃይማኖትዎ አንወጣም ቃልዎ ይድረሰን እያለ በደስታና በእልልታ አክብሮ አዋጁን ተቀበለ ።

ከዚህ በኋላ ለደጃች ውቤ ደጋግመው እሳቸው ካሉበት ጐንደር ድረስ የላኩባቸውን መልእክት አክብረው ባለመምጣታቸው ለጦርነት ተዘጋጅተው ወደሰሜን ሄዱ ከዚያም ከደጃች ውቤ ሀገር ደረስጌ ላይ ጦርነት ገጥመው የሁለቱ ሠራዊት በጀግንነት ሲዋጋ ከዋለ በኋላ ደጃች እሸቴ ውቤ በጥይት ተመቶ ወደቀ በዚህን ጊዜ የቆላ ወገናንና የበገላን አዝማች የነበረው ብላታ ኮከቤ እስከ ሠራዊቱ ለደጃች ካሣ ገባ ሌላውም እሱውን እያየ ወደ ደጃዝማች ካሣ ጦር እየመነ ገባ ከዚህ በኋላ ትንሽ ቆይተው ደጃዝማች ውቤ እጃቸውን ሰጥተው ገቡ ።

ደጃዝማች ካሣም በድል አድራጊነት በትልቅ ሰልፍና ክብር ወደ ደረስጌ ማርያም ሄደው በጀግንነት ሲዋጉ ለዋሉት ሽልማትና ሹመት እየሰጡ አስደሰቱአቸው በዚህን ጊዜ ብላታ ኮከቤ ለእርስዎ ስል ደጃች ውቤን ጌታየን ከድቼ ብዙ ሥራ ስለሠራሁ ሹመትና '' ሽልማት ይገባኛል ብሎ ለደጃዝማች ካሣ አመለከተ ደጃዝማች ካሣም እኔ ጌታውን ከሚከዳ አሽከር ጋር አንድነት የለኝም ብለው በጠየቀው ጥያቄ ምክንያት ወስደው ከጌታው ከደጃች ውቤ ጋር አሰሩት ።

ከዚያም ፊታውራሪ ጓንጉል ውቤ የአባቱን መታሠር ሲሰማ የትግሬ ጦር ይዞ ራስ አምባ ዳሺ ወደሚባለው ትራራ ሄዶ ተቀመጠ በዚያም ተራራ ዋሻ ውስጥ ደጃች ውቤ እነግሳለሁ ብለው ከወርቅ የተሠራ ዘውድና ብዙ የወርቅ መስቀል ብዙ አልባሳት እንደዚሁም የጦር እቃና ልብስ ነበረበት ።

ደጃዝማች ካሣም ከመጋዋጋታቸው በፊት መልእክተኛ መላክ ይወዱ ነበርና ደጃች ውቤን በሰንሰለት አስረው ከፍት አስቀድመው የአባትክን ሕይወትና የአንተም ሕይወት የፈለክ እንደሆነ እስከ መሣሪያህና እስከ ሠራዊትህ እጅህን ስጥ በየተራራው ያለውንም የአባትክን ሀብት አስረክብ ይሄን ባታደርግ ለአባትህ መጀመሪያ ሽማግሌ እንደላኩባቸው ታውቃለህና አሁንም የአባትህ ውርደት እንዳይደርስህ ሲሉ ከእስረኛው ጋር ወታደሮች ላኩ ።

ፊታውራሪ ጓንጉልም የተባለውን ሁሉ እሺ ብሎ አባቱ አሠርተውት የነበረውን የወርቅ ዘውድና እንደዚሁም አምሳ የወርቅ አክሊሎች ትላልቅ የቤተክርስቲያን መስቀሎች እስከ መጎናፀፊያቸው ለደጃዝማች ካሣ ወስዶ አስረከበ ።

ደጃዝማች ካሣም ድል ባደረጉ በሰባተኛው ቀን በ1947 ዓ.ም የካቲት 5 እሁድ ቀን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ቅባአ መንግሥት ተቀብተው ስመ መንግሥት ዳግማዊ ቴዎድሮስ እግዋለአንበሳ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ደጃች ውቤ ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን ለራሳቸው ብለው ደ/ ውቤ ያሠሩትን ዘውድ ደፍተው ነገሡ ።

ቴዎድሮስ ሊባሉ የፈለጉበት በልጅነታቸው አዛውንት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ሲያወሩ ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሥና ሃይለኛ ፍርድ አስተካካይ ይሆናል የጥንቱን የኢትዮጵያን ግዛትከባህር ጠረፍ እስከ ባህር ጠረፍ ድረስ አንድ ያደርገዋል እየተባለ ሲነገር የነበረው ሁሉጊዜ ትዝ ስለሚላቸው ነው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ ትልቁን ደጃዝማች እርያን የትግሬን ግዛት ሰጥተው ባለህበት እርጋ ገገርህም ንጉሠ ነገሥትህም እኔ ነኝ ብለው ደጃች ውቤን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይዘው ወደጐንደር አምጥተው ወህኒ አምባ አውጥተው አውራቸው እሳቸውም አጼ ቴዎድሮስ ልጃቸውን ጥሩወርቅን እስከ ሚያገቡ ድረስ ወህኒ አምባ ታስረው ቆዩ ።

አጼ ቴዎድሮስ በለሳ አምባጣራ ክረምቱን ከከረሙ በኋላ ደጃች ውቤ እንደሞቱ ወሎንና ሸዋን ለማስገበር ጉዞ አደረጉ በዚያም በሰቆጣ አድርገው ሹም ሽር እያደረጉ ወሎ ደረሱ የወሎ ገዢ የእቴጌ መነን እህት የመሐመዶች ዘር የምትሆነው ወርቂት ነበረችና እሷም ሕዝቡን ግብር ከገበረላቸው በኋላ አታለው አጼ ቴዎድሮስን አዘንግተው እንዲወጉዋቸውና እንዲያዙ አዝዞ ስለነበረ የወሎ ሕዝብ ግብር እየያዘ መጥቶ ተቀበላቸው ከዚያም ጊምቢያ ከሚባለው ሜዳ ወረይሉ ሰፍረው ሳለ ከወርቂት የተላኩት አሽከሮች አድብተው ሊገኟቸው መጥተው ከአጼ ቴዎድሮስ አጠገብ የነበረውን ደጃች ወርቄ ተሰማን ተኩሰው ገደሉት ከዚያም ግብር ይዞ የመጣው ባላሀገር እንደ ጊዜ ተነስቶ በወታደራቸው ላይ ጦርነት አንስቶ ብዙ የጦር ሠራዊት ገደለባቸው ከዚያም ባላባቱና የንጉሡ ነገሥቱ ሠራዊት ገጥሞ ሲዋጋ እንደገና ባላባቱ ሸሽቱን ቀጠለ በዚህን ጊዜ የወርቂን ልጅ ጃንጥራር አግደው አሊ ብቻ ተይዞ እስር ቤት መቅደላ እንዲቀመጥ ሲያደርጉ ሌላውን ባላባቱ የተማረከውን አታሎ በግብር እስመስሎ ከወጋኝ ምህረት አይገባውም ብለው ላመጹ ሕዝብ መቀጣጫ እንዲሆን እጁን እየቆረጡ በየአንገቱ እያሠሩ ወደቤቱ ላኩት ከዚያም ቀን በኋላ የወሎ ህዝብ በሰላም ተገዛላቸው ከዚያም የደራው ገዢ ግራዝማች

ዋቂ ዲቦ ገና መምጣቸውን ሲሰማ ግብሩንና ገፀ በረከት ብዙ ሰንጋ አምጥቶ አቀረበላቸው ለእሱም የደጃዝማችነትን ማዕረግ ሰጥተው ቦረናን ጨመሩለት ከወረይሉ ተነስተው ወደመንዝ ግሼ ሄዱ ከዚያም በንጉሥ ሃይለመለኮት ሥር የሚገዛው ጻሀፊላሀም ሐብተማርያም ነበረና ያለውን ጦር ይዞ ገጠማቸው እሱም ትንሽ ወታደሮች ተዋግተው ያዙትና ማርከው አቀረቡት ለምንድነው የወጋኸኝ ብለው ቢጠቢ መጣ ልዋጋ ቃል እንደገባሁ ቃሌን ልፈጽም ነው አላቸው እሳቸውም ጠላት አሁን የታዘዝከውን ፈጽመህ ትማርከሐልና ሞትነው ወይስ ሹመት አሉት እርስዎ በእኔ ላይ ይፍረዱ እንጅ እኔ አልፈርድም ስላለ ግዛቱን ፈቀዱለትና በነጻ ለቀቁት ከዚያም በመንዝ ያለው ሀገር የይፍራታና የግድም የላሉ ምድር ሕዝብ እየመጣ ገበረላቸው ከመንዝ ወደተጉለት ጉዞ አድርገው ገርብዋሻ ሲደርሱ የጠራው ገገር ብላታ ሀብተማርያም የንጉሥ ሃይለመለኮትን ጦር ይዞ ገጠማቸው እሱም ወዲያው ድል ሆነና በጦርነቱ ሞተ ።

አጼ ቴዎድሮስ የደብረሊባኖስን መምህር ገብረህይወትን ሰው ከማለቁ በፊት እጅዎን ይሰጡና ከእኔ ቃል ኪዳን አድርገን ግዛትዎን እንዲፈቅድልዎ ብለው ላኩባቸው ንጉሥ ሃይለመለኮት ግን እንቢ አልመጣም ብለው አታክልት ከሚባለው ሥፍራ ላይ ጦራቸውን ይዘው ለጦርነት ይጠብቁ ጀመር ከዚያም የአጼ ቴዎድሮስ ወታደሮች ምሽቱን ጥሰው እየተዋጉ ቢገቡ ንጉሥ ሃይለመለኮት በ1848 ዓ/ም ጥቅምት 30 ቀን ሙተው ተገኙ ። አጼ ቴዎድሮስም በደብረ በግእ ሕፃን ሞአ ደብር ሥርዓተ ቀብራቸው ህዳር አንድ ቀን አስፈጽመው በክብር አስቀበሯቸው በዚህን ጊዜ የአንኮበር ከተማ ተቃጠለ የሚባ ላ ወሬ ሰለሰሙ ወደአንኮበር ሄደው የአቃጠሉትን ሄደው ይዘው ገደሏቸው ።

ከዚህም የሃይለመለኮት ልጅ ሚኒልክን ይዘው ለአጼ ቴዎድሮስ ስለአቀረቡላቸው ሚኒሊክን ይዘው በሸዋ የሃይለመኮትን ወንድም ሞርእድ አዝማች ሃይለሚካኤልን ሾመው በሰላም ወደጐንደር ተመ ሱ ከዚያም ለአቤቶ ሚኒልክ ልጃቸውን ወ/ሮ አልጣሽን አጋብተው ክብር አስቀመጣቸው ። በዚህን ጊዜ እንዲህ ያለ ዘፈን በጐንደር በጊምድር ተዘፈነ

ኢትዮጵያ ሀገሬ ላሜ ቦራ ቦራ
ገደል ገብታ ሳለ ወድቃ ተሰባብራ

ከትግራይ ጅብ መጣ ጭሆ እያጉራ
ከጉጃም ጅብ መጣ ጭሆ እየጉደራ
ከወሎ ጅብ መጣ ጭሆ እየጉደራ
ከሸዋ ላይ ሆኖ ጅብ ሎሽ ጉደራ
ከፋፍለው ሊበሉዋት አራዊት በተራ
ነገር ግን እንበሳው የአራዊቶች አውራ
አንድ ብቻ ያዛት ብቅ ብሎ ከቋራ

በየቤቱ በላኩት ጊዜ ደግሞ እንዲህ ሲል ተዘፈነ

እባ ታጠቅ ካሣን እወጋለሁ ብሎ
ተማርኮ ድል ሆኖ እጁን ሰጠ ወሎ
አጼ ቴዎድሮስ እንዴት ጀግና ናቸው
ወሎን አስገበሩት የጁን ነጥለው
ጊምቢያ ከሜዳው ላይ ሰፍረው ወረታሉ
ሰብስበው በተራ የወሎን ሕዝብ ሁሉ
ሰው የእጁን አያጣም የእጁን ይሰጥህ አሉ
ለካስ ቴዎድሮስ መመረቅ ያውቃሉ

ለወሎ ባላባት ወሎን ግዛ ብለው
የተቆረጠውን የጁንም ጨምረው
አጼ ቴዎድሮስ ሰጡት መርቀው
አጼ ቴዎድሮስ ሰው ማክበር ሲወዱ
የወሎን ባላባት እጅ ነስተው ሄዱ

አጼ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉ በሁለተኛው ዓመታቸው ኢትዮጵያን የንጉሠ ነገሥት ሀገር አንድ መንግሥት ካደረጉ በኋላ ከዚህ በታች የሚገኙትን ህጎች አወጁ መጀመሪያ አገርና አባት ያለህ በየአገርህ በየአባትህ ግባ አባትና አገር የሌለህ ግን እኔ አባት እሆንሃለሁ ሀገርም እሰጥሃለሁ አሉ ።

1ኛ( ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያንም በክርስቲያንነቱ እስላምም በእስልምናው ፀንቶ እንዲቀመጥ ነገር ግን ክርስቲያንም ከአንድ ሃይማኖት ከኦርቶዶክስ ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ቢከተል እስላሙም ከእስልምናው ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ይዞ ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪውም እንገቱ በሰይፍ ይቆረጣል ደረቱ በጦር ይወጋል ።

2ኛ/ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ እንዲያገባ አግብቶ ቢገኝ ሃብቱን እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና እርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው

3ኛ/ ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበረው ሆኖ ይቆያል ።

4ኛ/ የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች በእለት ተግባራቸውና በደሞዝ እንዲሰሩ እንጅ ባሪያ መግዛት መሸጥ እንዳያደርጉ ሲሸጡ ወይም ሲገዙ ቢገኙ እንደነፍስ ገዳይ በአደባባይ እንዲሰቀሉ ወይም በግዞት እንዲኖሩ ።

5ኛ/ የቤት ሠራተኞች ገረድና አሽከሮች ወደው በነጻም ሆነ በደሞዝ ቢያገለግሉና ከአሠሪያቸው ጋር ተጣልተው ቢወጡ በውላቸው መሠረት ነገሩ ይፀድቃል ።

6ኛ/ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በየሙያው እንዲሰለፍ ገበሬም በግብርናው ነጋዴው በንግዱ እንዲተዳደር

7ኛ/ ገበሬ ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስና ነጋዴ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ግብር እንዲከፍል ነገር ግን በትከሻው ተሸክሞ የሚነግድና ቆፍሮ የሚዘራ ገበሬ ግብር ከፈል መዋጮ አውጣ ተብሎ እንዳይገደድና እንዳይከፍል ሲሉ በአዋጅ አናገሩ ነገር ግን ባሪያ ሲሸጥ ከበሬና ሸፍቶ በየመንገዱ በየዱሩ ሆኖ ሲቀማና ሲሰርቅ የነበረ በየቦታው እየተነሳ አስቸገረ

ከነዚሁም ከእስቱ ግራዝማች ብጡል የሚባሉ ብዙ ባሪያዎች ነበራቸው ከቤታቸው የሚወለዱትን ይሸጡ ነበርና ለአጼ ቴዎድሮስ ቀርበው ጌታየ ሁሉን ነገር የሚሉትን ሁሉ እቀበልሃለሁ ነገር ግን እኔም አባቴም የአባቴም አባት ከጥንት ጀምረን ባሪያ እየሸጥን ነበር የምንተዳደር አሁን ይሄ ከቀረ እኔ ምን እባላለሁ ለሚስቴስ ሆነ ለእኔ ማን ምግብ ሰርቶ ያቀርባል ።

በደሞዝ እንዳንቀጠር የምንሸጠው ከሌለ በምን ገንዘብ አሽከር እንቀጥራለን ብለው አመለከቱ አጼ ቴዎድሮስም ለመሆኑ ከእያትዎ ጀምሮ ሲያገለግልዎ የነበረው ባሪያ የትኛው ነው አኳቸው አንዱን ጠቅሰው አባዩ በል አንተ የጌታህን ግራዝማችነት ማዕረግ ወስደህ ቤተሰቡንና ንብረቱን ወርሰህ አስተዳድርበት ይሄን ብጡልን ግን ስቀሉት ብለው የሞት ፍርድ ፈረዱበት ።

በሌላ በኩል ደግሞ የቁልማ ሰዎች ሁሉም ሌባና ሸፍታ ነበሩ
አጼ ሆይ እኛ ሁሉንም ወደ የሙያው እንዲገባ ብለው ከአላወ
እኛም ከሽፍትነት ሌላ ሙያ ስላለን ይፍቀዱልን አሏቸው አጼ ቴ
ሮስም እኔስ የምፈልገው እንደናንተ ያለውን አደለ ነገር ግን ያ
ሁት ጥቂት ናችሁና ሌላ ባእድ ሳትጨምሩ የዚህን ልማድ ያላቸው
ብቻ ይዛችሁ ቅረቡ ብለው አሰናበቷቸው እነዚህ ሰዎች በተቀጠ
በት ቀን ዘመዶቻቸውን የሆኑትን ሽፍቶች ይዘው ቀረቡ አጼ ቴዎድ
ሮስም ርነሱ ብቻ መሆናቸውን ጠይቀው አወን ካሏቸው በኋላ
ዶሮቻቸወን በጥይት እንዲገሏቸው አዘው ወዲያውኑ በጥይት ሁሉ
ተደብድበው ሞቱ በዚህን ጊዜ ሁሉም ፈፉ ዶንገጠ ለትንሽ አመ
ሃገር ሰላም ሆነ ነጋዴም እንደልቡ ከአንድ ወደ አንዱሃገር እየ
ይነግድ ጀመር ። ነገር ግን ጊዜ እየፈለገና የአጼ ቴዎድሮስ መሬ
ምክንያት እየፈለገ ባሪያ መሸጥና ከፋፍሎ ለያይቶ ህዝብን የሀ
ለመግዛት የሚመኘው የመሣፍንት ልጅ ተነሳባቸው ከነዚሁም 1
መለኮት ወንድም አቤቶ ሰይፉ በሽዋ 2ኛ/ የመሃመዶች ዘር ወ
ወርቂት ይመም በወሎ 3ኛ/ የአጼ ቴዎድሮስ አጉት ደጃዝማች ን
ጉሹ የደጃዝማች ውቤን ልጅ አግቡቶ ትግሬን ይገዛ ነበር 4
ደጃዝማች ተድላ ጓሉ አጼ ቴድሮስ አምነው የጐጃምን ግዛ
ከአጐታቸው ነጥቀው ሰጥተዋቸው የነበሩት እኒሁ ሰው ከድተ
በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ሸፈኑ ።

በዚህን ጊዜ አቤቶ ሰይፉ የሚባል የንጋሲ ዘር ነኝ ብሎ በሸ
ላይ መሸፈቱንና አጼ ቴዎድሮስ የሾሙትን መርእድ አዝማች ሃይ
ሚካኤልን ተዋግተው ድል አድርገው በአንኮበር ከተማ ተቀመ
የሚባልን ሲሰሙ አጼ ቴዎድሮስ በግሥጋሴ ሸዋ ደርሰው አቤቶ ሰ
ፉን ተዋግተው ድል አድርገው ከገደሉት በኋላ ህዝቡን ሰብስበ
የትኛው ነው ሃገር የከዳ እያሉ ሲመረምሩት እራሳቸው የሾሟቸ
መርእድ አዝማች ሃይለሚካኤል ከአቤቶ ሰይፉ ጋር ተማክረው እን
ሸፈቱባቸው መሰከሩባቸው ። ስለዚህ በእሳቸው ምትክ አቶ በዛብ
የሚባሉትን የፈታውራሪነትን ማዕረግ ሰጥተው የሸዋ ገዢ አደረ
ቸው መርእድ አዝማች ሃይለሚካኤልን በኬላሽ አምባ እንዲታሠሩና
እንዲጠበቁ አደረጉ ።

ከዚያም የጐጃሙ ገዢ ደጃዝማች ተድላ ጓሉ ከሸዋ ባላባቶ
ጋር ውስጥ ውስጡን ተማክረው ኖሮ የሸዋ ሰው ስለአጋለጠባቸ
ሊይዛቸው ወደ ጐጃም ሄዱ ደጃዝማችተድላ ጓሉም ሊይዛቸው እን
መጡ ስለአወቁ ጦርነት ገጠሟቸውና ወዲያውኑ ድል ሆነው ተይዘ

ተገደሉ ከዚያም የውቤ ቤት ከ ተወሰደው እንደተራ ሰው ተቀበሩ ። በዚያን ጊዜ የጐጃም ሰው በጣም ይወዳቸው ስለነበር እሁድ እሁድ እየደገሱ ያበሉት ስለነበር እንዲህ ያለ ዘፈን ተዘፈነላቸው ።

እልሞተም ይላሉ ደጃዝማች ተድላን
እሁን እሁድ ሲተር የምናወቀውን
የውቤ ወሰደው ጣሉት ደጃዝማች ተድላን
ይነሳ ነበረ አብማ ቢሆን
ውሃ ዋና እንኳ አላውቅ ዋ ምን ሊበጀኝ
ጌታ የውቤ ገቡ ሜዳ ጥለውኝ
በሸዋም ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው ።
በትግሬም ተላከ ጥናው ሊመጣ ነው
ተድላ ጓሉ ሞቶ ጐጃም ሊፈታ ነው

እጂ ቴዎድሮስ የደጃዝማች ተድላን ልጅ ንጉሴ ከሥልጣን አር ቀው በእርሻ ብቻ እያሳረሱ ይኖሩ ነበርና ደጃዝማች ንጉሴ ብለው የጐጃምን ግዛት በሙሉ ሰጥተው ወደ ጐንደር ተመለሱ ከዚያም የሚ ወደት የጠኋትን ጠሏት የምትኖረው ባለቤታቸው እቴገ ተዋበች አሊ ታመው ደረሱ ፤

እጂ ቴዎድሮስ ባለቤታቸው እቴገ ተዋበች በወረይሂመኑ በንበሩ በት ጊዜ የሃገሩን የአየር ጠባይ ስለወደዱት ወደ ወሎ ይዘዋቸው ሄዱ ከዚያም አህመድ ሸሪፍ የሚባል ሸፍታ እስላሞችን ይዞ ተነስቶ ነበ ርና እሱውን አጥፍተው በዚያው በወረሄምኑ ሳሉ ባለቤታቸው እቴገ ተዋበች አረፉ እጂ ቴዎድሮስም የባለቤታቸውን አሬሳ ወርቅ በተለ በጠ ሳጥን አስደርገው መቅደላ መድሃኔዓለም በክብር ከቤተ መቅ ደሱ ደጃፍ በሲቱ በኩል አስቀበሯቸው ይሄንም ያደረጉት እኔም በሞ ትኩ ጊዜ ከዚህ መቅደላ እምጥታችሁ የእኔን እሬሳና የሚስቴንእፅም እንድትቀብሩት ብለው ለሚወደቀቸው መሣፍንት ተናገሩ ከዚያም ቀን ጀምሮ መቅደላ በክብር ዘብ እየተጠበቀ የመሳፍንት ልጆች የሚ ቀመጡበተን የግዛት እንባ ሆነ ሌሎች ፀኃፊዎች ግኘን ግሪያም እን ዳንዶች ግን ጣና ሃይቅ ነው የተቀበሩት ይላሉ እና ሃሰት ነው በመ ቅደላ እንደተቀበሩና የወርቅ ሳጥኑ በእንግሊዝ ጦር ተቆፍሮ እንደተ ወሰደ ሥርዓተ ቀብሩ በሚፈጸምበት ጊዜ የተለቀሰ የልቅሶ ግጥም ከእጂ ቴዎድሮስ ፤

ቸኩላ ተዋበች የሃገሬ መሬት
አብባ እረገፈች ሳይወጣ ክረምት
እስቲ ጠይቁልኝ ርቃ ሳትሄድ
እቴጌ ተዋበች ሚስትናት ገረድ
እጅግ ሥራ አዋቂ ትናንትና ሞተች
ማን ይሰራው ይሆን እስዋማ ከሌለች

አልቃሾች ፤

እቴገ ምንትዋብ አንቺ የእኛ እመቤት
ሁሉ ሞልቶባለ ከቴዎድሮስ ቤት
ምኑ ውሎብሽ ነው የገባሽ መሬት ፤

ልጅ ጋረድ የአጼ ቴዎድሮስ አጐት የእናታቸው ወንድም የደጃች ክንፉ ልጅ ነው እሱም የአባቱን ገዳይ ገድሎ እንደ ቴዎድሮስ እሆናለሁ ብሎ የአማራን ህዝብ እየሰበከ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ ዋና ጠላት ሆኖ ተነሳባቸው ከዚያም አጼ ቴዎድሮስ ወደ ወገራ ሄደው ደባርቅ ከሚባለው ሃገር ላይ ተዋግተው ድል አድርገው ገደሉት ። ልጅ ጋረድ ክንፉን ድል ከአደረገና ተከታዩን ሁሉ ካጠፋ በኋላ ኪክል ፕሌውዴን የሚባለው የእንግሊዝ ቆንሲል ለንጉሠ ነገሥቱ ወዳጅና አማካሪ ሆኖ ሲኖር ወደ እንግሊዝ ሃገር ለመመለስ ከአጼ ቴዎድሮስ ተሰናብቶ ጉዞ እንደጀመረ የእጌታቸው የደጃዝማች ንጉሴ አሽከሮች ገደሉት ። በዚህን ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ የካፒቴን ኪክል ፕሌውዴን መሞት ሲሰሙ በጣም ወዳጃቸው ነበረና አዝነው ከሰነበቱ በኋላ ከደባርቅ ወደ ወልቃይት ሄደው ከደጃች ንጉሴ ጋር ተዋግተው ወዲያውኑ ድል አደረጉት የእሱን ተከታይና አጃቢ ያለርህራሄ በጥይት አስገደሉት ግማሹን እጁን ጆሮውን አስቆረጡት ፈረንሳዮችም አብረው ስለ ተገኙ ተገደሉ ።

ደጃች ንጉሴ በቀይ ባህር በኩል ከፈረንሳይ መንግሥትና ከናፖሌዎን ሶስተኛ ንጉሥ ጋር ተላልከው አጼ ቴድሮስን የምወጋበት መሣሪያና የጦር አስልጣኞችን ላኩልኝ ብለው ኖሮ ተልኮ በዚሁ ቀን ብዙ የጦር መሣሪያ ተገኝቶ ተማረከ ።

አጼ ቴዎድሮስ በትግሬ ያለውን አገር ካስገበሩና ሹም ሽር ካደረጉ በኋላ ለህዝቡ ግብር አድርገው ሳለ አባትዋ የታሠሩባት የደጃዝማች ውቤ ልጅ ወ/ሮ ጥሩወርቅ አባትዋን እንዲፈቱላት ደጅ

ልትጠና መጥታ እዩአትና በቁንጅናዋ ተማርከው ይዘዋት ወደ ጐንደር መጥተው በክርብ ሥርአት ጋብቻው ተፈፅሞ አገቡዋት በዚሁ በጋብቻው ቀን አባትዋ ደጃዝማች ውቤና ሰባት መቶ እስረኞች ተለቀቁ ።

አጼ ቴዎድሮስ መጀመሪያ ታላላቅ መሣፍንትን አጥፍተው የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት ከመሠረቱ በኋላ አሁን ዋናው አሳባቸው ቱርኮችን ከአፍሪካ ምድር እንዲወጡ ሲሉ በየአሉበት የባህር ወደብና ደሴቶች መልእክት በ 1852 ዓ/ም በመስከረም ወር አስተላለፉ በዚህን ጊዜ የእስክንድርያዊ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ ወደ ኢትዮጵያ መጡ ይሄውም አጼ ቴድሮስ ቱርኮችን ከሃገሬ ውጡ ብለው የማስፈራሪያ አዋጅ ስለተናገሩና መልእክት ስለላኩ ለማስታረቅ ነበር የመጡ ነገር ግን አቡነ ቁርሌስ አጼ ቴዎድሮስ በክብርና በፍቅር ተቀብለው ሲያስተናግዱዋቸው ሳለ ከመንፈሳዊ ንግግር ይልቅ ወደ ሥጋዊ ንግግርና ከቱርኮች ጋር የሚያደርጉት ጠብ ጥሩ አይደለም ስላሏቸው አጼ ቴዎድሮስ ተናደው እስዎ ለእኔ ለክርስቲያኑ መንግስት እንደመርዳት ለእስላሙ መንግሥት ባህር ተሻግሮ አገሬን ለሚገዛው እንዴት ይረዱታል አሁንም እርስዎ የተላኩት ለሥጋዊ ሥራ እንጅ ለመንፈሳዊ ቃል አልመጡም አሉና ሊቀ ጳጳሱን አቡነ ቄርሎስንና አቡነ ሰላማን አሠሯቸው ።

ጥቂት ቀን እንዳሠሯቸው ሊቀ ጳጳሱም ስህተታቸውን ስለአመኑ ፈታቸውና ወደ ሃገራቸው ወደ ካይሮ መለሷቸው ከዚህ ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አላፊዎችና መነኮሳት ሊቀ ጳጳሱን ሃገራችን ሊባርኩ ቢመጡ ይህ አላዊ ንጉሥ አሠራቸው ለእሱ የሚገዛ ውጉዝ እያሉ ስለ ሰበኩ ብዙ ካህናቶች ተይዘው በእሳት ታቃጠሉ ።

አጼ ቴዎድሮስ ቱርክን ከአፍሪካ ምድር አባረው ለመሰደድ በተነሱ ጊዜ ከውጭ ከክርስቲያን መንግሥት ጋር ወዳጅነትን አድርገው የበሃር የጦር ሃይል ስላላቸው አሰልጣኝ ለማግኘት ሲሉ ለፈረንሳይ ንጉሥ ለናፖሊዮን ሶስተኛ በባርዴል በኩል ለእንግሊዝ ንግሥት ቢክቶርያ በካፒቴን ካሜሮን በኩል ደብዳቤዎች አሲዘው ላኩ ደብዳቢዎችም የሚሉት እናንተ ክርስቲያን ህዝብ እንደምትወዱ በቆንሲሎቻችሁ በኩል ስለሰማሁ በጣም ደስ አለኝ ከእናንተ ጋር በየጊዜው በደብዳቤም ሆነ አይን በአይን እንድንገናኝ የክርስቲያን ጠላቶች የሆኑት ቱርኮች በበሃር ላይ የሚላከውን መልእክተኛ የን እያ

ስሩ የተላከውን ዕቃ ስለሚዘርፉ ከእናንተ ጋር መገናኘ አጥቼ እኖ
ራለሁ ስለዚሁ እናንተም ክርስቲያኑ መንግሥት እኔደመሆናችሁ
መጠን ለእኔ ለክርስቲያኑ ንጉሥ የበሃር መርከቦችን መስራትና የበ
ሃር ልምድ ያላቸውን አዋቂዎችን ላኩልኝ በሃገሬም የመድፍ ጥይት
በማሠራት ላይ ስለሆንኩ ለዚሁ ልምድ ያላቸውን ላኩልን እኔ በሃገ
ሬም ሆነ በባህር በኩል የምትሉኝን አደርጋለሁ የሚል ነበር ነገር
ግን በዚሁ ዘመን የእንግሊዝም የፈረንሳይም የኢጣሊያም እንደዚሁ
ሌሎች አውሮፓ ሃገሮች አፍሪካን ከፋፍለው ቅኝ ግዛት ለማድረግ
በሚሯሯጡበት ጊዜ ነበረ ግን ይሄንየጠየቁትን እርዳታ መስጠት ቀርቶ
መልስ ሳይልኩ አጼ ቴዎድሮስን የአንድ ትልቅ መንግሥት ሃገር ለማ
ድረግ የተነሳው ጀግና ለማስገደል ይላላኩ ጀመር ።

አጼ ቴዎድሮስ ለላኩት ደብዳቤዎች ከፈረንሳይናምከእንግሊዝ
መንግሥታት መልስ ሳያገኙ ሁለት አመት አለፈ ከዚህ በኋላ ወደ
እንግሊዝ ሃገር ከአጼ ቴዎድሮስ ለንግሥት ቢክቶርያ ደብዳቤ ይዞ
ዶ የነበረው የእንግሊዝ ቆንሲል ካሜሮን ከሌሎቹ ጓደዋች ሚሲ
ዮናውያን ጋር በሁለተኛ አመቱ ተመለሰ በዚህን ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ
ቢጋፋት ላስጀመሩት ለመድፍና ለጠመንጃ ኢንዱስትሪ የሚሰሩ የመጡ
መስሏቸው በክብር ተቀብለው ቢያነጋግሯቸው የእንግሊዝ መንግሥት
እርዳታ እንደማያደርግ ገለፁላቸው ግን እነዚህ አብረው የመጡት
ሃይማኖት ለማስተማር ብቻ ስለሆነ እንደሚፈቅዱላቸው እስዎን ተማ
ምኜ ይዣቸው መጣሁ ብሎ ካሜሮን ተናገረ ።

አጼ ቴዎድሮስ የእንግሊዝና የፈረንሳይ መንግሥት ከጠላታቸው
ከቱርክ ጋር የተስማሙባቸው መሰላቸውና የመጡትን እንግዶችን
ወደ ሃገራችሁ በቶሎ እንድትመለሱ እናንተ የሃይማኖት አስተማሪ
ዎች ብትሆኑ እስላሙንና አረመኔውን ሃገር ሊብያንና ናይጀሪያን እን
ደዚሁ በእስላም የተያዙትን ሃገሮች አስተማራችሁ ክርስቲያን ባደረ
ጋችሁ ነበር ነገር ግን እናንተ የመጣችሁ የእኔን ህዝብ ክርሀቲያን
የሆነውን ልታፋጁ እንጂ ሌላ አልመጣችሁም አሁንም በመጣችሁ
በት እንድትመለሱ አሏቸው ።

በዚህን ጊዜ ጳጳሱ አቡነ ሰላማ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ እያደ
ሙና ጠላት እያስነሱ ካህናቱንም እየሰበሰቡ የኢትዮጵያን ህዝብ እን
ዳትገዙለት እያላችሁ አውግዙ ብለው ሲልኩ ተገኝተው በግዞት እንዲ
ቀመጡ አደረጓቸው በዚህን ጊዜ አጼ ቴዎድሮስ ቱርክን ከአፍሪካ
ምድር አስወጥተው ለመሰደድ በሚዘጋጁበት ጊዜ የቱርክ መንግሥት
ግብጾችን በወኪልነት እያስቀመጠ የራሱን ህዝብ ያወጣ ጀመር ።

በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ በጣጥም እንዲህ ያለ ያመስግ ናቸውና ይዘፍንላቸው ነበር ።

አባትና እናቱ ካለአንድ አልወለዱ
ካሣ ያው አንዱ ያው አንዱ
አጼ ቴዎድሮስ ሞትን የማይፈራው
እሱ እንደ ክርስቶስ ለእናቱ አንድ ነው
አእላፍ ሰራዊት ሲራመድ በፊቱ
ሞቱ ሳያዩለት እናትና አባቱ ።

እናንተ ጭራሮች የተበተናችሁ
አንድ ቤት ለመሆን አልበቃ ብላችሁ
አባ ታጠቅ ካሣ እየለቀመ አቃጥሎ ይፍጃችሁ
ተበትኖ ነበር ፍልጥና ጭራሮው
ካሣ ለቀመና ሰብስቦ አነደደው

ለቅሞ ያነደደው ካሣ ለብልሃት
ለኢትዮጵያ ብሎ ነው ሁሉ እንዲታያት
ሃገሬን እግዜር ሲኖር በድኗት
ሊታረቅ ፈልጉ ካሣን ላከላት

ስሙ ቴዎድሮስ አባ ታጠቅ ካሣ
ያደረገው ሁሉ ምንም አይረሳ
ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም
እርብ እርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም
እንቅልፍም አልተኛ የኢየሩሳሌም ሰው
ካሣበፈረሱ በህልሙ እየታየው

ሲጮህ ሲታኘ ያድራል አረብ /በሥራው/ ከመኘታው
ከተኛበት ደርሶ ካሣ እያበነነው
አባ ታጠቅ ካሣ ነገር ሲያስላስል
ባህሩን ያስባል መረብ ጣይ ይመስል

የታጠቅ ፈረሶች እንዴት ያሽካካሉ
ባህር ማዶ ጨፌ መልቀም ያስባሉ
አበሻ በመላው ምን ያጉመተምታል
በመርከብ ተሻግሮ ገና እስያ ይዘምታል
የታጠቅ ጉራዴ ብረት የነበረ

እየቀላ ሄዶ መልኩም ተቀየረ
የቱርኮችን ደም ስለተነከረ

ፈረሱ አባታጠቅ ስሙ ቴዎድሮስ
ጠላትን የሚያበን እንደ አውሎ ነፋስ

ስሙ ቴዎድሮስ ፈረሱ አባ ታጠቅ
በእራስ ላይ ሆኖ ልብን የሚያስጨንቅ

ታጠቅን በል ብሎ ማን አምኖ ይቀርባል
ሲሰኛውን ጉበዝ የእራቱን ማእዘን ባል
የሸዋ የጉጃም የወሎ የትግሬ ተበተነ ሃብቱ
ግዛው አባ ታጠቅ ሰብስቦ በሃብቱ

አጼ ቴዎድሮስ ከካሜሮን ጋር የመጡት ሚሲዮኖች ወደ ሃገራቸሁ በቶሎ እንድትመለሱ ብለው አሰናብተዋቸው ነበር ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ የውጭ ሰው ስለሚያከብሩ ምንም እያደርጉን ብለው በየመኳንንት ቤት ተቀምጠው ስለተገኙ እንዲታሠሩ አዘዙ በዚህን ጊዜ ካሜሮን አማላጅ ሆኖ ሄዶ እኔን ብለው አብረው የመጡ ስለሆነ አይታሠሩም እንዲወጡ ከፈለጉ ክረምቱ ሲያልፍ ወደ ሃገራቸው ይመለሳሉ አላቸው ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ እራሱ ካሜሮንን ስለተጠራጠሩት እንዲያውም አምኘ ልኬህ ለላኩት መልስ ሳታመጣ የቀረህ ከቱርክ ጋር ተሰማምተህ ከዚህ እኔ የማዘጋጀውን ሁሉ ለመናገር ነው የመጣህ ብለው በሰላይነት ከሌሎች ነጮች ጋር ጨምረው አሰሩት ።

በዚህን ጊዜ የካፒተን ካሜሮን መታሠር የእንግሊዝ መንግሥት በሰማ ጊዜ መጀመሪያም ተጠልቶ ሃገሩን ከፋፍሎ የማያስቀምጥበት ዘዴ ይፈልግ ነበረና የአፍሪካን ምስራቅ ሃገሮች የሚያውቀውን ሆርሙዝድ ራሳም ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ የታሠሩትን እንዲያስፈታ የእንግሊዝ መንግሥት የተለያዩ ጨርቃ ጨርቅ ሰጦታ አሲዞ ላከው ሆርሙዝድ ራሳም በካይሮን አድርጎት አንዱር ማንገባ ከአንድርማን ላይ ሆኖ የእንግሊዝ መንግሥት ወደእርስዎ ልኮኛልና እንድመጣ ይፍቀዱልኝ ብሎ ላከባቸው ።

አጼ ቴዎድሮስም ስናር ድረስ ሰው ልከው ይባባ ከተማ እሳቸው ካሉበት ድረስ እስመጡትና የመጣበትን ጉዳይ ጠየቁት ራሳም ከእንግሊዝ መንግሥት የተላከላቸውን ልብስ አቀረበላቸውና እነዚህን

ያሰሩዋቸውን የውጭ ሃገር ሰዎች እንዲፈቱለት ጠየቃቸው አጼ ቴዎ
ድሮስም ያሰሩበትን ምክንያት ገልፀው ፈትተው ካሰረከቡት በኋላ
መጀመሪያ የእንግሊዝ መንግሥት ለጻፉት ደብዳቤ መልስ ባለመስ
ጠቱ የተላከላቸው ልብስ መልሰው ሰጡት ከጠላታቸው ከቱርክ ጋር
ተስማምቶ ጦርነት እንደሚያካሂዱባቸው አውቀው እንደገና ተመል
ሰው እንዲታሠሩ አደረጉ በዚህን ጊዜ ራሳም እነዚህን የውጭ ሃገር
ሰዎች ቢያስሯቸው የእንግሊዝ መንግሥት በጦር ሃይል መጥቶ እንደ
ሚፈታቸው ግልፅ ነው ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ይፍቷቸው ብሎ እን
ደገና ቀርቦ ጠየቃቸው አጼ ቴዎድሮስም ራሳምን እንዲታሠር አዘዙ
በትና ወሰደው የአጼ ቴዎድሮስ ሠራዊት አሠሩት በዚህን ጊዜ የእን
ግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣኖች ውስጥ ውስጡን ከኢትዮጵያ መሣ
ፍንት ጋር እየተላላኩ ሌላ የጀርመን ተወላጅ የሆነውን ፍላድን ይፈቱ
እንደሆን ይፍቱ አለዚያ ወገኖቻችንን መጥተን በጦር ሃይል እንፈታቸ
ዋለን የሚል ደብዳቤ አሲዘው ላኩ አጼ ቴዎድሮስ የጦርነት ድል በእ
ግዚአብሄር እጅ እንጅ በእናንተ ጦር ኃይል አይደለም ብለው መልስ
ሰጥተው ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር ነገር ግን በውስጥና በውጭ በአጼ
ቴዎድሮስ ላይ ህዝባቸው ሳይቀር ተነሳባቸው ካህናቱም በየጉጡ
ለእሱ የሚገባ ወጉዝ እያሉ አወገዙባቸው በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያን
ህዝብ አንድ ለማድረግ በሚታገሉበት ጊዜ እነዚህ ሲወዱዋቸው የነ
በሩት ካህናት በጳጳሱ መታሠር የተነሳ አትገዙለት ብለው በማውገዛ
ቸው የውስጥ ጠላት የውጭ ወዳጅ የሆኑትን ካህናት ያለርህራሄ በወ
ታደር አስገደሏቸው እንደዚሁም ከታሰሩ እስረኞች መቶ ሰው እው
ቃችሁ በበቀላ

ቤት ሞልታችሁ አቃጥሏቸው ብለው አዘዙ በዚህን ጊዜ እስረኞች
ዘና ዘጠኝ ብቻ ስለነበሩ አንድ ወታደር ሄዶ ጃንሆይ መቶ አልሞ
ሉም አንድ ጐደለ ብሎ ተናገራቸው እሳቸው አንተ ሙላው ብለው
አብሮ ሄዶ ተቃጥሎ ሞተ ይባላል ።

አጼ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተባበራቸው ሲል ከጐ
ጃም ከቱማ ከያባባ ተነስተው በቀራኒዮ ሞጣ አድርገው ወደበጌም
ደር ተሻገሩ ከዚያም የጐንደር ሕዝብ እንደከዳቸው ስለአወቁ እስረ
ኞቻቸውን አርባ አምስት የውጭ ሀገር ሰዎች ሁለት መቶ የመሳፍ
ንት ልጆች ይዘው ወደ ሰሌ ሄዱ ከዚያም በመንገድ ሳሉ የባለቤታ
ቸው የቱጌ ጥሩወርቅ አባት ደጃዝማች ውቤሞቱና ለቴጌቱ በበነጋ
ታው ከተነገረ በኋላ ይለቀስ ጀመር ።

በዚሁ ለጦርነት በሚዘጋጅበት ጊዜ ዘመዱ ሞተ ብሎ ሰው እን ዳያለቅስ ተከልክሎ ነበርና በደጃዝማች ውቤ ምክንያት ዘመድ የሞ በት ሁሉ ሲያለቅስ ዋለ በዚህን ጊዜ የጋይንት አልቃሽ እንዲህ አለች የኢታ ደጃዜማች ሁልጊዜ ደግነት ። ዛሬ እንኳን ለድሃው እንባ አትረፉለት አለች ።

ከደባባ ተነስተው ወደበጌምድር ሲገቡ ብዙ ሰው ሲገደል ሲሰ ቀል ያየው አልቃሽ ደግሞ በዚሁ እለት እንደዚሁ ብሎ አለቀሰ

ሞጣ ቀራንዬ ምነው አይታረስ
በሬሳ ላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ
አንጠረኛው ብዙ ከንጉሡ ቤት
ባል አልቦ አደረጉት ይህን ሁሉ ሴት

አጼ ቴዎድሮስ ከደብረታቦር ተጉዘው ወደ ወረይመኑ ገቡ ከዚ ያም ወደ መቅደላ ሂደው በግዞት የሚኖሩትን እስረኞች ከፊታቸው እየቀረቡ ቀላል ወንጀል ያለበትን በነጻ ሲለቁ ከባድ ወንጀል ያለበትን የከዳቸው ሁሉ ገደል አስጥለው ገደሉት ።

የእንግሊዝ መንግሥትም ወደኢትዮጵያ ሄዶ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት አጼ ቴዎድሮን ገድሎ እስረኞችን አስፈትቶ ይዞ የሚ መጣ የጦር ሃይል አዘጋጅቶ የበላይ አዛዡ ጄኔራል ሮቤርት ናፒየር የሚባለውን ሹም አራት ሽህ የእንግሊዝ ስምንት ሺህ የህንድ ወታ ደሮች አሲዞ ላከው ።

ጄኔራል ናፒየርም በሺህ 860 ዓ.ም ምፅዋ አጠገብ በምትገኘው ዙላ ወደብ ደረሰ ከዚያም በቱርክ ወታደሮችና በሀገሬው እየተረዳ በሶነፌ ሄደው ሰፈሩ ከሰነፌፌም አንዳሉ የትግሬ የላስታ መሳፍን ቶች በተስፋ ሲጠባበቁት ለነበረው ለእንግሊዝ ወታደር ስንቃና ለጭ ነት የሚሆን አጋሰስ ፈረስ አስረክበው ከጄኔራሉ ናፒየር ጋር ተዋ ወቁ ።

ጄኔራል ናፒየርም ሰናአፌ ላይ ሆኖ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ሆኖ ስምምነቱን ከፈፀመ በኋላ የኢትዮጵያን ባለሀገር ሕዝብ ወደፊት አስቀድሞ አጋሜን አድርደገው በሚያውቁት ሰዎች እየተ መራ ዋድላ ደረሰ ከዚያም የአጼ ቴዎድሮስን ሞት የሚመኘው የመሳ ፍንት ልጅና ዘመድ የሞተበት እንደዚሁም በካህናቱ የሚላከው ጦር መጥቶ ከእንግሊዚ ጦር ጋር ቀሰለፈ ።

እጼ ቴዎድሮስ ግን ምንም የኢትዮጵያ ምድር ባትከዳቸው የሚያምኑት ሁሉ ስለከዳቸው ሕዝቡ እንደጠላቸው አውቀው ትንሽ ወታደሮች አስቀርተው ወደየሀገራቸችሁ ሂዱ እያሉ እየመረቁ ሠራዊታቸውን አሰናበቱ ነገር ግን ሃያ አንድ ሽህ የሚሆን ሲሄድ ሰባት ሽህ የሚሆን አብረን ከእርስዎ ጋር እንሞታለን ሲል አንሄድም ሲል አንሄድም ብለው ተናገሩ ።

በዚህን ጊዜ የእንግሊዝ ጦር መንገዱ ክፍት መሆኑን ስለአወቀ ከዋድላ ድላንታ ወገልጤና ከሚባለው ላይ ሰፍሮ ጀኔራሉ የታሰሩትን እስረኞች ፈተው ይላኩልን ሲል ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

እንግሊዞች መጡ ባህርን ተሻግረው

እጼ ቴዎድሮስ ይበልጠናል ብለው

መድፍና መትረየስ ማሰራቱን አውቀው ።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከትውልድ የሚተላለፍ ቃል አምባላጌ ላይ ሆነው የተናገሩት ንግግር ይህ ነው ። በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ በስመ ሦስትነት በባህሪያ አንድነት ከሦስትነት ሦስትነት ከአንድነት የማይለየው እግዚአብሔር መርጦ ያነገሠውን ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ በዛሬው ዕለት በአሁኑ ሰዓት በጐኔ የተሰለፋችሁ ጀግኖች አንድነትን የምትወዱና የምትከተሉ ተከታይ ትውልዶች ልነግራችሁና ለአስተምራችሁ የምፈቅደው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል ነው ።

አባቶቻችን ነገሥታቱ ፈጣሪያችን ቢበድሉት ሀገራቸውን ለቱርክ እስላም አሳልፎ ሰጠባቸው መንግሥታቸውንም ለእንደራሴዎቻቸው አሳልፎ ቢሰጥ እንደራሴዎቻቸው እርስ በእርሳቸው በተቀያየሙ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በእርሱ አጋደሉት ለያዩት ሁሉም በየቤቱ ተነስቶ ለራሱ ንጉሥ ሆኖ ወገኖቹን ፈጀ ገደለ በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር እኔን ከታናሽነቴ ጀምሮ መርጦ ለሕዝብ ተቆርቋሪና መኪታ ሆኜ እንድነሳ አደረገኝ ለዚሁም የራሴን ወገኖች ቀጣሁ ገደልኩ ለተከታዩ ትውልድ መልካም ሥራና ሃይል ያለው አንድነት እንዲኖረው ስል ሌትና ቀን ሳላርፍ ፈጽሞ ደከመኝ ሳልል እሮጥኩ ታገልኩ የውስጤን እረሠኔ ሳጠፋ ከባህር ማዶ መጥቶ ሀገራችንን ለሚወርና ሕዝቡን ባሪያ አድርጎ ለሚወስደው ለቱርክ መንግሥት ሳጠፋ ካህናቱ ጳጳሳቱ ጠላት ሆነው ተነሱብኝ እነሱም አሠርኩ ገደልኩ ነገር ግን አሁን ያመንኩት ሕዝቤ ጠላት ሆኖ ስለተነሳ

ብኝ የማያሳድሙብኝን የውጭ ሀገር ሰዎች አብሬ አሠርኩ ይሄውም ክርስቲያኑን መንግሥት ወንድማቸውን እኔን ትተው የእስላሙን መንግሥት ቱርክን ወደው ሶእሱ ሲለሚላላኩና ስለሚያግዙት አይቼ ነው ከሀገሬም እንዲወጡ ብል እንወጣም አሉ ። ስለዚህ አሰርኳቸው እንጂ አልገደልኳቸውም አሁን በነሱ አመካኝቶ የእንግሊዝ መንግሥት ጠ ሠራዊት አንድነታችን ለማፍረስ ሀይላችን ለማድከም በቱርክ መንግሥት እየተረዳ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ባህር ተሻግሮ ገባ ገኪዚያ በፊት ሲላላኩ ኑ ድረሱልን ሲሉ የነበሩት መሣፍንት ከሞተ የተረፋትን ቀሪዎች ጋር ተገናኝተው ትጅና ብትር ሆነው መጡብን አሁን በአጠገቤ ያላችሁ ሕዝቦቼ የኢትዮጵያ ሠራዊት ለአንድነት የቆማችሁ ሆይ ያለፈውን የመሣፍንት አመራርን በማጥፋትና የቀና አስተዳደር በቦታው በመተካት የተለያዩት ወገኖቻችን በማገናኘት የትኛው ጠፍቶ የትኛው መልካም ሥራና ዘመናዊ ጥበብ እንዲስፋፋ ለማድረግ ለአደረኩት ድካሚ የኢትዮጵያ ምድር በስሜ ላይ ትመሰክር መቼም እድሚየችውን ሙሉ በወገኖቼ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሲመኙ ክፉ ሲየደርጉ የሚኖሩ ሡሣፍንትና የነገሥታት ቅምጥል ዘሮች ደግ ሥራ ሡስራት ስለማይችሉና መልካም ትምህርትና ጥበብ ማስተማር ቀርቶ በቀን ልቡና የሚሰሩትንና የሚጠበቡትን ተከታይ ትውልድ እንዳይወዳቸው ለማድረግ ስለሚያጠፉቸው እናንተ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለቆማችሁለትና ለደከማችሁለት አንድነት ታማኝ ሆናችሁ እነሱን የለማዳን መገኘት የአንድነቱ ጥሪ ነው ነገር ግን አንድነታችሁንና ሃይላችሁን ሊያጠፋ ከተሰለፉባቸው ጠላቶች ፊት መሸሽ ወይም የምን ግዴለሽ ማለፍ ወገንኑ አታሎ ሀሊናን ገድሎ ሳይሞቱ ሞቶ በውርደት መቃብር ታፍኖ መኖር ነው በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ሀገሩ ላይ የመልካም ሥራና ደግ ሥራው አንድነቱ ነጻነቱና አላማውን ተግባሩ እንዲፈጸም መንገድ ሡረ መሆን ነው ።

የድል ባለቤት ሃይላችንና አመራራችን የሚለው የሕዝብ ጠላት የሆነው ያለፈውን ክፉ ሥራ ከስሁተቱ ተገንዝቦ ለመልካም ተግባርና አንድነት ቢመለስ መቀበል አልመለስም ካለ ምንጊዜም ከእጥፊ መሸሸ አጥፊ እንዲያጠፋ መፍቀድ ስለሆነ አጥፊን ሕዝብን ሳያጠፋ አስቀድሞ ማጥፋቱ ፈለግ ነው ። ስለዚህ ከተቻለ አጥፊን ጠላት አጥፍቶ ለመጭው ትውልድ መልካም መሪ መተካት ካልተቻለ በአለው የአንድነት ሃይል በያዘው መሣሪያ ጠላትን አጥፍቶ የማምለጥ እድል ካልተገኘ አብሮ

መጥፋት የጀግኖች ሥራ ነው ማንኛውም ትውልድ በወረደ ልማድና በተበታተነ ሥርዓት ታፍኖ በከፋ ሰሪት ተዋርዶ ሺህ ዘመን ተንቆ ከመኖር ለከፍተኛ አንድነቱ ለመልካም ሥራው በታማኝነቱ ለሀገሩ ክብር ሲል የሞተ ጀግናው ወታደር በክብር ይበልጠዋል ለተከታዩ ትውልድ የመልካም ሥራው መስዋዕትነት መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል ይህ ትውልድ ቢያፍነው ሌላው ትውልድ ይገልጠዋል ለዚህ ታዛቢና መስካሪ ሀገርህ የኢትዮጵያ ምድር ነው እነዚህ አሁን የከበቡህ የመሣፍንት ጭፍራዎችና አጃባዎች የውጭውን ሀገር የእንግሊዝ ጦር ሃይልን ይዘው ቢመጡብህ አትፍራቸው ለክብርህ ብትሞት በሕይወት አለህ ባትሞት ግን የሞትክና የተዋረድህ ነህ ስለዚህ አሁን ለቀረበልህ ክብር ትንስ ታጠቅ ተቀበለው ጠላቶችህ መሣፍንት ደስ ይበላቸው የዛሬ ደስታ የነገ ሃዘናቸውና ልቅሶቸው ነው ፡፡

በየጊዜው ትውልድ ሁሉ የራሱ መብትና ምርጫ መኖሩን ያለፉት ነገሥታት ቢያውቁ ኖሮ ሕዝባቸውን በከንቱ ባልገደሉት ባላጠፉት ነበር ፡፡ ለጊዜው ግዛታቸውና ታሪካቸው የሚኖር መስሏቸው ይከመውበት በከንቱ ጊዜያቸው ጋር አለፉ ለሌቹም ገና አሁን ጠላት ሆነውህ አሉ ነገር ግን የትናትና ሰውዎች ስለሆኑ ያልፉሉ አሉ ያልኳቸው ከዛሬው ትውልድ ጋር ከእኛ ጋር ሆነው ሳለ የትናትትውልድ ተከታዮች ናቸው እኛ ግን ከነሱ ስንለይ የዛሬው ትውልድ ባለቤቶች ነን የነገው የነገሁም ወዲያ ባለቤቶች ነን ይሄውም መልካም ሰሪንና መልካም ስራውን ስለምንመኝና ለአንድነትና ለትባበረ ሃይል ለማቆም ስንደክም ስንታገል ነው እንጅ የነገው ትውልድ ባለቤት ለመሆን መልካም ሥራንና አንድነትን ለይቶ የመምረጥ መብት የነገው ትውልድ ነው አሁን እናንተ ለሕዝባችሁ አንድነት ምድነው የምትሰሩለት ? የሕዝባችሁ አንድነትስ ለእናንተ ምን ያክል ክብር ነው የሚያስቀምጥላችሁ አንድነት ከሌለ ሕዝብ የለም ሕዝብ ከሌለ ደግሞ ሀገር የለም ሀገር ለባዕድ ይሆናል ሕዝብ በአንድነት ከቆመ ግን ሀገር ነው ፡፡

ሀገርን የሚያሳምራት የሕዝብ አንድነት እንጅ ሀገር የህዝብ አንድነትን አይሰራውም አያቆመውም ነገር ግን ሀገር ታኖረዋለች ታስመሰግንዋለች መኖሪያና ስፈሩ ሆኖ እውነተኛ ትውልድ ትተላለፍለች እናንተም ሆናችሁ እኔ ለምን ደከመን? ለምን እንደምንሞት ማወቅ የራሳችን መብት ነው ነገር ግን መብታችን የራሳችን ሲሆን ሞታችን ደግሞ በታሪክ የሚኖር ለትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ሕይወት ነው ስለዚህ በሕይወታችን እንደምንኖር ቁጠሩት እንጅ ሳይ

ሞቱ ከሞቱት ጋር ያለን እንዳይመስላችሁ የእኛ ሞት ለተከታዩ ትው ልድ ክብር ነው ስለዚህ ሞታችን ጣፋጭ ማር እንጅ መራራ አይመስላችሁ ብለው ለወታደሮቻቸው የሚያፅናና ንግግር አድርገው የሚወዱቸውን መኳንንቶች እየሳሙ ከእኔ ጋር ለመሞት ፍላጐት ያላ ችሁ ከዚሁ ቆዩ ፍላጐት የሌላችሁ ግን በደጆ፥ በደጅን ሆናችሁ ወደየፈለጋችሁበት ሀገር ሂዱ ብለው አሰናበቱቸው በዚህ ጊዜ ሊቀ ሊቃውንት ፍፁም ፍሰሃና መልአከ ብርሃን እንግዳ ቀርበው ለምን ወታደሩን ያሰናብቱታል ብለው ቢጠይቋቸው እኔ ሕዝቤን የቀጣሁትና የገደልኩት ከሞት የቀረው አንድ ሆኖ ይተባበርና ትልቅ ሀገር ለመሆን ይደርሳል ብዩ እንጅ አሁን እራሱ መለያየትን ፈልጌ የውጭ ሰው ከተከተለ ለምን ? እነዚህስ ይሞታሉ አሏቸው ። ከዚያ ደግሞ ነጋድራስ አፈወርቅ የሚባል የአጼው ባለሟል ጃንሆይ እንግሊዞች እኛ መሞታችን ካልቀረ የዚህ ጦር ምክንያት የሆኑትን ነጮች እስረኞች እንግደላቸውና ሂደን እንሙት አላቸው አጼ ቴዎድሮስ ግን ያገሬን ሕዝብ አንድ ለማድረግ እኔ ያስታየሁት አልበቃ ብሎ ደግሞ እነዚህን እንግሊዞች የውጭ ሀገር ሰዎች ገድዩ ደግሞ ሕዝቤን እንደገና በውጭ እንዲጠቃ አላደርግም ማሰሬ እንኳ ሌላው እንዲፈራ ብዩ ነው ያሠርኳቸው ይሂዉ እስራት በቃቸው ብለው ተናገሩ ።

ንግግራቸውን ጨርሰው ወደተዘጋጀላቸው የጦር ግንባር ሄዱ የእንግሊዝም ጦር ሠራዊት በኢትዮጵያን መሣፍንት እየተመራ ከመገ ጤና ተነስቶ የበሸሎን ወንዝ ተሻግሮ ወደ አሮጌ ሲደርስ ፋሀላ ስላ መሸጉ የነበረው የአጼ ቴዎድሮስ የጦር ሠራዊት በፊታውራሪ ገብ ርዩ መኮንን እየታዘዘ ሄዶ ጦርነት ገጠማቸው ትንሽ እንደቆየና እንደ ተዋጋ ድል ሆንና ድሉ ለፊታውራሪ ገበርዩ ሆነ ። ከሞት የተረፈው እጁን ሰጠ ከአሮጌ ተነስቶ ወደሸበሌ ወንዝ ወደሚያወርደው መን ገድ እየሮከረና እያቅራራ ሲሄድ ወደኋላ አፈግፍጉ ጥሩ ሥፍራ መሽጉ የሚጠባበቃቸው የነበረው የእንግሊዝ ጦር ሠራዊት በመትረየስ ደግሞ ከኋላና ከፊት ሆኖ በፊታውራሪ ገብርዩ የሚመራውን ጦር ሠራዊት ገደሏቸው ከዚያም ገና በጉዞ ላይ የነበረው ተመልሶ ለአጼ ቴዎድሮስ ወደአሉበት ምሽግ ሄዶ የሆነውን ሁሉ ነገራቸው በዚህን ጊዜ በጣም አዘኑ ይሄውም ኢትዮጵያን ትልቅ ሀገር አደርጋታለሁ ሕዝብዋንም ከዳር እስከዳር ያለውን አዛምጄ በጥበብ አሠለጥንዋለሁ ትልቅ ሕዝ ብም አደርገዋለሁ ያሉት ተስፋ ተቆርጦ የህይወታቸው ፍጻሜ የኢት ፍጻሜ የጥፋት ቀን ሆኖ ታያቸው ።

ከዚያም ጄኔራል ናፒየር ያሠሯቸውን እንግሊዞችን ለቀው እራሳቸው አጼ ቴዎድሮስ እጃቸውን እንዲሰጡ የሃያ አራት ሰዓት ጥያቄ አቀረበላው ነገር ግን አጼ ቴዎድሮስ ወደአምላካቸው ፀልየው ሲጨርሱ ይህ የእንግሊዝ ሰው ስለመይሣው ካሣ ቆራጥ ጀግና መሆኑን አልሰማም እንዴት ሃይለኞችንና ጀግኖችን እንደቆሉ በእፍኝ ይገዞ የኖርኩ እንደእኔ ያለ ጀግና ዛሬ ምንም የመጨረሻ ቀኔ ቢሆን በሰው እጅ መያዝ ቀርቶ መጠየቁ እንኳን ንቀት ነው ለሕዝቤ ሰል ብናት አይገደኝም ሕዝቤን አላስፈጀም ብየ እንጅ ጎና ሲመጣ በአለኝ ሃይል ከጠረፍ ላይ እንጥመው ነበር ጀግንነቱ ቆራጥነቱ ከሁለታችን ማን እንደሆነ ይለይልን ነበር ነገር ግን በሁለት ቆራጦች መካከል የሚያልቀውን ሕዝብን አይቼ ከዚህ ብመጣ እንዲህ ያለ መልእክት ይላክብኝ አሁንም ሕዝቤን አላስጨርስም ብለው እንደገና ሂዱ ብሎ አሰናበተቸው ወደ መቅደላ ሄዱ የአፄ ቴዎድሮስ የጦር ሃይል እንሸሽም ጌታችንም አናስነካም እያለ በጀግንነት እየተዋጋ ሞተ የሥላሴ ጦርነት በ1860 ዓ.ም ሚያዝያ ፬ ቀን ሐሙስ ቀን ተፈጸመ ነገር ግን ጥቂት ወታደሮች መቅደላ በር ላይ ሆነው ጥቂት ጥቂት ቀን ተዋጉ በአራተኛው ቀን ዋናው ጦር መጥቶ በመድፍ የምሽጉን መግቢያ ሰብሮ ገባለው ከዚያም ያሉት ወታደሮች መሞታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በተወለዱ በሃምሳ ዓመታቸው ንጉሠ ነገሥት ኢትዮጵያ ዳግማዊ ቴዎድሮስ በተባሉ በአስራ ሶስት ዘመናቸው በ1860 ዓ.ም ሚያዝያ 6 ቀን ሰኞ በገዛ ሽጉጣቸው ራሳቸውን ገድለው አለማቸውን ተንተርሰው ተገኙ በዚህን ጊዜ እንግሊዞችም ጀግንነታቸውን አመስግነው ከባለቤታቸው ከእቴጌ ተዋበች ጋር እንደተሞቱት መቅደላ መድኃኒዓለም ቤተ ክ/ በክብር ተቀበሩ ። ባለቤታቸው ተቀብረው የነበሩበት የወርቅ ሣጥን ግን በድብቅ ወደ እንግሊዝ ሀገር ተወስዶ በኢትዮጵያ ሊቋቋም የነበረው የጥይት እንዱስትሪ ፋብሪካ ጎንደር አካባቢ ወዝባ -ውዛባ በሸዋ አካባቢ ሊቋቋም ነበር ።

እምላክን መስሎ ቴዎድሮስ
ንዑግ ሑሩ ሲል ወለ ሐሙስ
ሰኞ መቅደላ ተጨንቀ
ሰው መሆኑ ዛሬ ገና ታወቀ

በመቅደላ በኩል ጭኸት በረከተ
የሴቷን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ
ጠጅና ጠላ ሰው ሲጠጣ አይቶ

የእንበሳ ልጅ ሽጉጡን ጠጥቶ
እርፎ ተጋደመ መቅደላ ወጥቶ

በሰው እጅ መሞት ነውር አድርጎት
እዩት ተመልከቱት ያንበሳውን ሞት
ዳር እስከዳር ዘምቶ የገዛው ንጉሥ
እንዲህ ቆራጥ ነው ሽጉጥ የሚጎርስ

ጠላቶቹን ሁሉ አጭዶ እንደገብስ
መቅደላ ተጣለው ራሱን በራስ
መላው የጐጃም ሰው መላው የትግሬ ሰው ተይዞ በምጥ
እንግሊዝ ሐኪሞች መጥተው ቢይዙት
ተገላገለ አሉ ይህ ሁሉ ፍጥረት

ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኛቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ ሀገራቸው
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኛ ናቸው
ነገር ግን በመንገድ ተማክረው የያዙት ወርቅ ግማሹን ደብቀው ለሕ
ዝቡ አሳዩት በጋዜጣ አውጥተው
በምስራቅ ያሉ ሕዝብ ቀን ሌት ተላልከው
በሰሜንም ያሉት ነጭን አስመጥተው
በምዕራብ ያሉት ለጠላት ሰው ሆነው
በደብብ ያሉት ጉትጉተው ነዝንዘው ።
ጀግናውን ለማጥፋት ከመጡ ሁላቸው
ይብሉት ከጣማቸው ያው ወደቀላቸው
አንድ ሆኖ ተስማምቶ መኖር ያለመዱ
ጀግና ለሀገሩ ቢነሳም አይወዱ
አንድነት ለነሱ ጥቅም መሆኑን ሲያውቁት
በታችነው ነጣጥለው ነጥለው ለመግዛት
ጀግናን ቴዎድሮስ የጀግኖችን አባት አሳልፈው ሰጡት ለውጭ ሀገር
ጠላት የአጼ ቴዎድሮስን መውደቅ ሲመኙ የነበረ መሳፍንት ቢሞቱ
ደስ ያላቸው እነዚህም በሸዋ ንጉሥ ሚኒልክ በጐጃም ራስ ደስታ አባ

ቀኛው በወሎ ወርቂት ይማም በየጁ አማታቸው የነበሩት ራስ አሊ በላስታ ዋግ ሥዩም ጎበዜ ገብረመድህን በትግሬ ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ በወልቃይት ጣሰው ጐበዜ ናቸው ።

እነዚህ ሁሉ በነደጃች መሸሻ አማካኝነት ማንኛውንም እርዳታ ለእንግሊዝ ጦር ሠራዊት እየረዱ እየመሩ አፄ ቴዎድሮስ ካሉበት ድረስ ሄደው የተዋጉና የረዱ ናቸው ።

እንግሊዞችም በእነዚህ እየተረዱ እየተመሩ አፄ ቴዎ ድሮስን ድል ካደረጉ በኋላ ከመቅደላ ያገኙትን የአፄ ቴዎድሮስን የባለ ቤታቸውን የወርቅ አክሊልና ተቀብረው የነበሩትን የወርቅ ሳጥኔ የራሳቸውን የወርቅ ዘውድ ወርቅ እየተለበጡ የተሰሩትን ጋሻዎ ቻችና ጦሮች መስቀሎችና ፀናፅሎች የጥንት የሆኑ መሣሪያ አቃዎችና ብዙ መጽሐፍቶች የአፄ ቴዎድሮስን ባለቤት እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ንና ልጅዋን አቤቶ አለማየሁን አስረው ይዘው ወደ ሀገራችው ሄዱ ።

ለዚሁ አፄ ቴዎድሮስን ለመግደል ለረዳቸው መሣፍንት እንዲ ሁም አብረው ለነበሩት ለትግሬው ገገር ለደጃች በዝብዝ ካሳ ብዙ የጦር መሣሪያ ሰጥተዋቸው ስለሄዱ ለአንድ ዓመት ያክል ሁሉም ለየራሱ ለመንገስ ያስብ ነበርና ሲዋጋ ሲጋደል ከረመ ከዚያም ቆጊ ዜው ብዙ ጦር ሠራዊት ስለነበራቸው መሣፍንቱን ድል አድርገው ዋግ ሰዩም ጐበዜ አፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ነገሱ የአፄ ተክለ ጊዮርጊስን ታሪክ በመቀጠል አቀርብላችኋለሁ ። አዘጋጁ መሪራስ ኤ ኤም በላይ

# ምዕራፍ ሀያ ስምንት

## የአጼ ተክለ ጊዮርጊስና የአጼ ዮሐንስን ዘመነ መንግሥታቸውን የመሣፍንት ወረራ

ዋግ ሥዩም ጕበዜ ገብረ መድህን ዘራቸው ከቀዳማዊ ሚኒልክ ወንድም ከቀዳማዊ ዛጉዌ እስከ ዳግማዊ ዛጉዌ መራ ተክለሃይማኖት አዜብን - አዘቦ በንጉሥነት ከዳግማዊ ዛጉዌ መራ ተ/ሃ እስከ ነአኩቶ ለአብ እሊመክኑን ድረስ በንጉሠ ነገሥትነት ከላሊበላ ልጅ ከይትባረክ ጀምሮ ግን አንድ ጊዜ ተራ ንጉሥ አንድ ጊዜ ዋግ ሥዩም እየተባሉ ክብርና ማዕረግ ሳይጎድልባቸው ከሚኖሩት ከዛጉዌ ዘሮች የሚወለዱ ሥርዎ መንግሥት ያላቸው ናቸው።

ዋግ ሥዩም ጕበዜ ለአጼ ቴዎድሮስ ታዛዢ ሆነው የአባቶቻቸውን ግዛት ፈቅደውላቸው ሲኖሩ ውስጥ ውስጡን ከነደጃች ንጉሤ ጋር ሆነው ውጭ ሀገር ለሚገኙት ለፈረንሳይ ለጀርመን መንግሥት ሲላላኩ ኩቶዩ በኋላ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ መሣፍንት እንደገና ተማክሮ ጠላት ሆኖ ሲነሳባቸው እሳቸውም የመንገስ ፍላጐት ነበራቸውና አምሳ ዘጠኝ ሺህ በላይ የጦር ወታደር አስታጥቀው ይዘው የእንግሊዝን የጦር ሠራዊት ረድተዋቸዋል እነሱም ስለ ውለታቸው በቂ የሆነ መሣሪያ ጥለውላቸው ሄዱ በዚህን ጊዜ የአጼ ቴዎድሮስ ሞት የሰማ ጣሰው ጕበዜ የሚባል የደንቢያንና የወልቃይትን ሕዝብ ሰብስቦ ከዋግ ሥዩም ጕበዜ ጋር እዋጋለሁ ብሎ በለማ ዲማ ሚካኤል ልዩ ሀገሩ ጭዋርታን ከሚባለው ላይ ጦርነት ገጥመው ድል ሆኖ ጣሰው ጕበዜ በጦርነቱ ላይ ሞቱ ።

ከዚህ በኋላ እንደ አጼ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመንገስ አሰቡና ከበላሣ በጌምድር ወደጐጃም ሄዱ በዚህን ጊዜ ደጃች ደስታ አባ ቀማው ጐጃምን ይገዛ ነበር አባ ቀማው የተባሉበትም ታላቅ ወንድማቸውን ንጉሤ ተድላን ቤት ክርስቲያን ሊሳለም በሄደበት የአባታቸው የተድላ ጓሉን አሽከሮች አሳድሞ ቤቱን ወርሶ ስላገኘው እሱም ጥሎለት በርሃ ስለሄደ አባ ቀማው ተባለና ጐጃምን ይገዛ ጀመር ።

ጥግ ሥዩም ጉበዜም ለደጃዝማች ደስታ ተድላ አባ ቀማው ኅብረለኝ ብለው ቢልኩባቸው አልገብርም በማለት ተዋግተው ድል ሆኑ በኋላ በርሃ ገቡ ።



አጼ ዮሐንስ

ነገረ ግን ልጃቸው ከአባታቸው ከደጃዝማች ተሰማ ጋር ተጣልተው የሚኖሩት ባለአምባራስ አዳል ተሰማ ስለገቡላቸው እህታቸውን ወይዘሮ ላቀች ገብረመድህን ድረው የራስነት ማዕረግ ሰጥተው የጉጃ

ምን ግዛት ከአባታቸው ነጥቀው ሰጧቸው ከዚህ በኋላ የበጌምድሩም የትግሬውም እንገብርልዎት አለን ስላለና ተገርነቱን ሕዝብ ስለአፀደቀላቸው በ1861 ዓ.ም በጥቅምት ወር አጼ ተክለጊዮርጊስ ንጉሠ ነገሥትዘኢትዮጵያ ተብለው ላስታ ሀገራቸው ላሊበላ ካሠራው ቤተ ጊዮርጊስ ላይ ነገሡ ። በዚህን ጊዜ አሊ ፋሪስ በየጁ ሐገር አልገዛም ብሎ ሸፍቶባቸው ነበረ ነገር ግን በንገሡ በአራተኛው ወር ሄደው ድል አድርገው ተመለሱ ።

አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲነግሡ በሸዋ የሣይለ መለኮት ልጅ ንጉሥ ሚኒልክ በትግሬ የባለቤታቸው ወንድም ርዕሰ መኳንንት ካሣ ግብሩን እየላኩ ውስጥ ለውስጥ በቂ የጦር መሣሪያ ለማግኘትና ለመዘመድ በየአሉብት ደብዳቤ ደጻፉ ጀመር ።

አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ለፈረንሳዩ ንጉሥ ናፖሊዎን ለብር ታንያ - ንግሥት ቪክቶርያ በመላፍንቶቻቸው ዘንድ የሚላከውን ደብዳቤ ስለሰሙ በዚህ የተነሳ ተጣልተው ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር መጀመሪያ ርእሰ መኳንንት ካሣን ትግሬ ሀገር ሄደው ለመውጋት ተነሱ ።

አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ርእሰ መኳንንት ካሣን የሚስታቸውን ወንድም ለማስፈራራት እንደ ስልቻ ጤፍ በአህያ አስጭነው የእኔ የጦር ወታደር በዚህ ልክ ነው ብለው ላኩላቸው ርእሰ መኳንንት ካሣም ለአጼ ተክለ ጊዮርጊስ የላኩትንጤፍ በእሳት አክስለው በእንክላ አህያ አስጭነው ላኩላቸው ወታደርህ እንደዚህ ቢበዛ በጥይት አከስልልሃለሁ አህያይቱም እንክላዋን የላኩዋቸው አጼ ተክለ ጊዮርጊስ እንካ ስለነበሩ ነው ። ይባላል በዚህን ጊዜ በ1863 ዓ.ም ሐምሌ አምስት ቀንአድዋ ላይ ላይ ጦርነት ገጥመው አሰም ከሚባለው ወንዝ ላይ አጼ ተክለ ጊዮርጊስ በጥይት ተመተው ተማረኩ ከዚያም አባ ሰላማ ከሚባል ዋሻ ውስጥ እንዲታሰሩ በገዙ በ፫ ዓመታቸው ሞተው ተገኙ በዚህ ጦርነት በሁለቱ በኩል ያለቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስራ ስምንት ሺህ በላይ ነበረ ። በዚህን ጊዜ ለሁለቱ የተገጠመላቸው ግጥም ፣

ጥሬውን ጤፍ ቢልክ ተክለጊዮርጊስ
ስልቻው ተፈቶ ትግሬ ላይ ቢፈስ
አባ በዝብዝ ካሣ ቆላው እንደገለስ
ከወንዱ አባ ታጠቅ ተቀባይ ሆነህ (ከአጼ ቴዎድሮስን ቀጥለው
ስለነገሡ ምነው በሶስት ዓመት ደከመ ሃይሌህ

ለአባ በዝብዝ ካሣ ቃጥሮ ግንባርህ
ተሸክመህ ወርደህ አልጋህን ስጠህ
በሙሉ ሶስት ዓመት የተሠራው አልጋ
ከሰቆጣ ወርዶ ትግሬ ተዘረጋ
ለምን ትለኛለህ ሰቆጣ ሰቆጣ
የንቱን አይደለም ወይ ለአክሱም የመጣ



## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

### የአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት

ርእሰ መኳንንት በዝብዝ ካሣ ከተንቤን ባላባት የራስ ሳሀለ ሚካ ኤል
ስሑል የልጅ ልጅ የመረጩ ልጅ ናቸው በእንግሊዞች መጽሐፍ በሁለ
ይሏቸዋል ራስ ሣህለ ሚካኤል የዳግማዊ አጼ ኢያሱን እህት አስቴርን አግ
ብተው እቤቴ ሥዩምን ወለዱ ራስ ሣህለ ሚካኤል ትግሬን ጐጃምን ጐንደ
ርን በእንደራሴነት ከንጉሠ ነገሥቱ ስም በታች ከሥልጣን ላይ ሆነው
ከዳግማዊ አጼ ኢያሱ እስከ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ድረስ የገዙ ትልቅ
ባለ ሥልጣን ነበሩ በዘመነ ሽምግልናቸው የአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ቅድም
ቅድመ አያት የሚሆኑት ደጃች ወንድ በወሰን ድል አድርገው ማርከው
ሳስታ እመኪና አምባ ወስደው እንዳሰረቻቸው ሞቱ እቤቴ ሥዩም
መረጩን ወለዱ መረጩ የእንደርታውን ገገር የራስ አርአያን እህት
ወይዘሮ ወለተ ሥላሴን አግብተው በ፲፰፻፳፭ (1825) ዓ/ም (በዝብዝ የተባሉ
ትን ካሣን ወለዱ በዝብዝየተባሉበትም እሳቸው የተወለዱ ቀን ደጃች ውቤ
ከሰሜን ወገራ ወደ ተንቤን ሄደው ወረው ቤቱንም ንብረቱንም አበ
ፉትሸው ሲሄዱ ሀገሬውን ስለበዘበዙት አባ በዝብዝ ተባሉ ሲሉ
ማግኘ ሰው ደግሞ የፈረሳቸው ስም ነው ይባላል ።

ርእሰ መኳንንት በዝብዝ ከመባላቸው በፊት በመንፈሳዊ ትምህ
ርት ቤት ካደጉ በኋላ ለአጼ ቴዎድሮስ እንጫጋይ ሆነው ገብተው
ሳለ አጼ ቴዎድሮስ ብዙ ካህናትና መነኮሳት ሲያስገድሉና ሲያስ
ርሩ አይተው ወደ ሀገራቸው ተንቤን ሄደው አጼ ቴዎድሮስን የሚ
ገድል ትልቅ ጠላት እየፈለጉ ተቀመጡ ከዚያም ደጃዝማች በሎ
ብለው በዝብዝ ርእሰ መኳንንት እየተባሉ ከእንግሊዝ ጋር መወ
ጀት ጀመሩ ።

ስለዚህ ነው የእንግሊዝ የጦር ሠራዊት በማንኛውም አይነት
ከሌሎች ለየት ብለው ስለረዱት ይበልጡን የጦር መሣሪያ ሰጥተ
ቸው የሄዱ ለርእሰ መኳንንት በዝብዝ ካሣ ከእንግሊዝ ጦር ሠራ
ዊት ያገኙት መሣሪያ አስሪ ሀላት መድፍ ዘጠኝ መቶ ስማንያ ጠመ
ንጃ ይሄነው ያልተባለ በመጋዘን የነበረ ጥይት የተረከቡት

ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ሐምሌ ፮ ቀን ፲፰፻፷፫ (1863) ዓ/ም አጼ ተክለ ጊዮርጊስን ወግተው ድል ካደረጉ በኋላ ሐምሌ ፺ ቀን የአድዋ ሥላሴን ቤተ ክ/ አክበሩ ከዚያም ከአድዋ ተነስተው ወደ ሞጣ ሄዱ ከዚያም እህታቸውን የአጼ ተክለ ጊዮርጊስን ባለቤት ድንቅነሽ አይተው እየተዋጋ የሬያ ዘቦ እስላም ከየጁ ክርስቲያን ጋር ጠዋትና ማታ ሥት አድርጐ ነበርና ሄደው አጥፈውን ገለው ሀገሩን አረጋግተው ወደ አክሱም ተመለሱ ከዚያም በ፲፰፻፷፬ 1864 ዓ/ም ሥርዓተ ንግሥን አክሱም ላይ አድርገው ፩ኛው አጼ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ነገሡ ።

አጼ ዮሐንስ በነገሡ በአንደኛው ዓመት ወደ ጐጃም ሄደው የአጼ ተክለ ጊዮርጊስ እህት የወ/ሮ ላቀችን ባል ራስ አዳል ተሰማን ተዋግተው ድል ካደረጉ በኋላ በጐጃም ራስ ደስታን ሾመው ወደጐንደር ተመለሱ ራስ አዳልም ራስ ደስታን የአጼ ዮሐንስን መሬት ሰጠው ራስ ደስታን ጦርነት ገጥመው ድል አደርገው ጐጃምን ገዢህ ነኝ ብለው አሳወጁ ።

አጼ ዮሐንስም ከጐንደር ወደ አክሱም እንደገቡ የሾሙትን ራስ ደስታን አዳል ተዋግተው መግደላቸውን ሲሰሙ መጣሁብህ ተዘጋጅተህ ቆየኝ ብለው ለራስ አዳል ላኩባቸው ራስ አዳልም የአባቴን ግዛት ከፈቀዱልኝ እገብርልዎታለሁ ይሄን ግዛቴን ከነሰከሉኝ ለጦርነቱ ተዘጋጅቼ እጠብቅዎታለሁ ብለው ላኩና በሁለቱም መካከል ቄስና መነኩሴዎች ገብተው አስታረቋቸው የጐጃም ግዛትም ለራስ አዳል ተሰጠ ።

አጼ ዮሐንስ በነገሡ በሁለተኛው ዓመታቸው የግብፅ ንጉሥ የቱርክ እንደራሴ ኢስሚኤል በቱርክ መንግሥት እየተረዱ የጀግናው አጼ ቴዎድሮስን መሞት ሲሰማ በምስራቅ በርበራን ዘይላን መቋድሾን ሐረርን ታጁራን የዛሬው ጅቡቲ በሰሜን ከምፅዋ ተነስቶ ከሰነኸረንን ሰዋኪን በምዕራብ ቡኪን ጁባን ያዘ ።

ከዚህ በኋላ በሰሜን ያለው የግብፅ ጦር ሠራዊት ከሁለት ሺህ በላይ መድፍና መትረየስ ይዞ በኰሎኔል አሬን ድጥ እየተመራ አሥመራን አልፎ አዲ ቀይህንና ጐንዳንጐንዲን ያዘ ።

በዚህን ጊዜ አጼ ዮሐንስ የጦር ሃላፊውን ሰብስበው ወደመረብ ሄደው ከግብፅ ጦር ሠራዊት ጋር ገጠሙ ግብጾችም ድል ሆኑና ግማሹ ሲማረክ ጥቂቶች ሸሽተው ምፅዋ ገቡ ።

እንደዚሁ ሁለተኛ አጼ ዮሐንስ በንግሥ በአራተኛው ዘመነ መን
ግሥታቸው በታህሣሥ ወር የግብፅ ንጉሥ እስማኤል ልጁን ሙሴ
ሐሰን ፓሻን ጠቅላይ ጦር አዛዥ አድርጎ አርባ አምስት ሺህ ጦር
ከራሱም ከሀገሬው ተወላጅ አዘጋጅቶ ከምፅዋ በጉንደት ልዩ በታ
ጉራእ ከሚባለው ስፍራ መጥቶ ሰፈረ አጼ ዮሐንስም በራስ አሉላ ጠቅ
ላይ ጦር አዝማች ሰለሣ ሺህ ጦር ሠራዊት ይዘው የግብፅን ጦር ለመ
ውጋት ወደ ጉራእ ሄዱ ከዚያም በሁለቱ በኩል የተፋፋመ ጦርነት
አድርገው መጨረሻ ግብፆች ድል ሆኑና ዋናው ጠቅላይ ጦር አዛዥ
ቸው ሙሴይ ሐሰን ፓሻ ተማርኮ ከአጼ ዮሐንስ ፊት ቀርቦ እሳ
ውም ከክንዱ ላይ የመስቀል ምልክት አስነቀሱት ።

ከዚያም ከጉራእ ወደ አክሱም ሲመለሱ ካህናቱና ሕዝቡ በእል
ልታና በመረብ በታላቅ ደስታ አክብሮ ተቀበላቸው አጼ ዮሐንስም
በዚህ ጦርነት ምንም ድል ቢያገኙ የመጡትን ከጉራእ ወደ ምፅዋ
መለሷቸው እንጂ ፈልመው ከሐማሴን ግዛት ከምፅዋ አላስወጧቸውም
እንዲያውም በእንግሊዝ አማካኝነት የተማረከውን ሙሴይ ሐሰ
የተማረከውን ሙሴይ ሐሰን ፓሻን ታርቆ ወደ ሀገሩ በሰላም ለመለሱ ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የግብፅን ጦር ሠራዊት ድል አድ
ርገው በመለሱት ጊዜ ከልብ ወደዳቸው በጣም አከበሯቸው ከዚያም
የአበሲኒያው ንጉሥ ምኒልክ የጐጃሙ ራስ አዳል መጥተው ለአጼ
ዮሐንስ የሚገባቸውን የክብር ገፀበረከትና ግብሩን በሥነ ሥርዓት
አቀረቡላቸው ይሄውም በጐጃም በኩል የቀረበው ገፀ በረከት የወ
ርቅ ሁችላ ልጥልጥ ወርቅ አምስት ሽህአለሉ ነበረ ይባላል ። በዚያ
አጼ ዮሐንስ ከጥንት የነበረውን የጐጃም ንጋሽነትን የአንበሳ ዳዊት
ዙፋን እንዲዘረጋ አድርገው ራስ አዳልን ንጉሥ ተክለሃይማኖት ብለው
ወሊጋን ከፋን ጐጃምን ዳሞትን እንዲገዙ ፈቀዱላቸው በሌላ ታሪክ
ከፋንና ወሊጋን ያቀኑ ምኒሊክ ናቸው ። ተብሎ በንጉሥ ሚኒሊክ
ታሪክ ላይ ይገኛል ይሄውም የንጉሥ ሚኒሊክ አሽከር ራስ ጐበና ከን
ጉሥ ተክለሃይማኖት ጦር አዛዥ ከራስ ደርሶ ጋር ተጋጥመው ራስ
ደርሶ ድል ሆኑና ንጉሥ ተክለሃይማኖት ተማርከው ወደሚኒሊክ ተወ
ሰዱ ከዚያም አጼ ዮሐንስ የሁለቱን መጣላት ሰምተው ሁለቱም እን
ደመጡ ብለው ቦሩ ሜዳ አምባሳል ላይ ተገናኙ ሁለቱንም ከወቀሱ
በኋላ አስታርቀው የወሎን ግዛት ከሚኒልክ ነጥቀው ለክርስትና ልጃ
ቸው ለራስ ሚካኤል አሊ አገው ምድርን ከተክለሃይማኖት ነጥቀው
ለራስ አሉላ ከራሳቸው ደግሞ በጌምድርን ላስታና የጁን ለልጃቸው
ለራስ አርአያ ሰጡዋቸው በዚሁ ቀን ለልጃቸው ለራስ አርአያ ሥላሴ የሚ

ሊክን ልጅ ዘውዲቱን ይድሩላቸው ዘንድ ጠየቋቸው እሳቸውም እጂ ብለው ፈቀዱላቸው ራስ አርአያ ሥላሴና ወይዘሮ ዘውዲቱ (1875) ዓ/ም በጥቅምት ወራት ተጋቡ ።

እንደዚሁም ሆኖ የኢጣሊያ መንግሥት ወታደር ከመላኩ በፊት አባ ማስያስ ጁሴፔ ሣፔቶንና የካቶሊኮች ቄሶች በሃይማኖት ስብከት አመካኝቶ ሀገሩን የሚሰልሉና የሚያርፍበት ቦታ ለማወቅ ሚሲዮኖችን ወደ ኢትዮጵያ ላከ እነዚሁም የተላኩት የካቶሊክ ሚሲዮኖች ጠዋትና ማታ ከክርስቲያኑ መንግሥት ጋር ከሚጣሉት ከአሰብና ከራሂታ ሱልጣኖች ከኢብራሂምና ከሃሰን መሐመድ ጋር ተነጋግረው አሰብን ገዚት በአካባቢው ያለውን ደሴት ሁሉ ሸጡላቸው ከዚህ በኋላ የኢጣሊያን መንግሥት አሰብን ከገዛ በኋላ ከኢጣሊያ ሀገር ብዙ የጦር ሠራዊት አምጥቶ አስፍሮበት ይኖር ነበርና ግብጾች ምፅዋን ለቀው ለመሄድ በቀረቡበት ጊዜ ኰሎኔል ማሊታን ስምንት መቶ ጣሊያኖች ይዞ ፲፰፻፸፰ (1878) ዓ/ም የጉራራን ደሴቶች ያዘ ግብጾችም በክብር ተቀብለው አስተናገዱቸው ።

በዚህን ጊዜ የኢጣሊያ መንግሥት ወደ አጼ ዮሐንስ ካቡሊዮር ብራንኪ ወደብ አቢሲንያ ንጉሥ ሚኒሊክ ማርኪዝ አንቲኖ የወዳጅነት ደብዳቤ ይዘው ሄደው ከአስረከቡ በኋላ እንደቆንሲል ሆነው በሌቹ ከተማ ተቀምጠው ነበር አጼ ዮሐንስም ለኢጣሊያው ንጉሥ አምቢርቶ ሴትና ወንድ አንበሳዎች ከሌላ ከገፀ በረከት ጋር ላኩለት ።

በዚህን ጊዜ የምግቤን ነገር ራስ አሉላ ቁቢ የኢጣሊያ መንግሥት ወደምፅዋ ብዙ ጦር መላኩን ስለሰሙና ከዚያም ሰሃጤና ዋአ ድረስ ጦሩ እየመጣ አገር ይይዝና ያስፋፋ ስለነበር ለጀኔራል ካርሎ ገኔ እላ ግባብ የያዘውን አገር ለቆ እንዲመለስ ላኩበት ነገር ግን አለቅም የሚል መልስ ስለላኩባቸው ዶጋሊ - አዳሊ ከሚባለው ሥፍራ ላይ ፲፰፻፸፱ (1879) ዓ.ም ጦርነት ገጥመው ድል አደረጉት በዚህን ጊዜ በዶጋሊ ላይ የኢጣሊያን ጦር ድል መሆኑ ሲሰማ ሌላ ሃያ ሺህ በላይ አዲስ ጦር መጥቶ የኢጣሊያን ወታደር ምፅዋ ላይ ሰፈረ ።

እንደዚሁም ሆኖ ሼህ አሊ ከሚባል ጀልባ ሰሪ ጥርስ ከፍት ከግራ ጉንጩ ላይ ምልክት ያለው ተወልዶ ስሙንም መሐመድ አሉት እሱም እንደነቢያቸው ያዩትና ይወዱት ጀመር ብዙ ሸሆችም የነብያን መንግሥት ከቱርክ ነጻ አውጥቶ ትልቅ የመንግሥት ሀገር ያደርጋል እያሉ ትንቢት ተናገሩለት ።

መሐመድ አሊም የእስላሞች መሪ ሆኖ ብድንጉላ በኤልፋሽር በጂዚራ ያሉትን እስላሞች እየሰበሰበ ከውጭ ሀገር ነገር ነጻ እንዲ ሆኑ (1810) እስከ (1831) ዓ/ም ለሃያ ዓመት ከቱርኮች ባለሥል ጣኖችና ከግብፅ ወታደሮች ጋር እየተዋጉ አንድ ጊዜ ድል ሲሆን አንድ ጊዜ ድል ሲያደርግ ኖረ በዚህን ጊዜ የቱርክና የግብፅ ዋና ጠላት የሆነው መይሣው ካሣ ከምሥራቅ ሀገር ተነስቶ ድል እያደረገ ኩሰቲ ደረሰ ከዚያም መሐመድ አሊ የመይሣው ካሣን መምጣት ሰምቶ አስራ ሰባት ሽህ ሠራዊቱን ይዞ መጥቶ ተገናኘኑቱን አመነ መይሣው ካሣ በኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ፈቃድ የመጣ አለመሆኑን ወደፊት ኢት ዮጵያን አንድ አድርጐ ለመግዛትና ቱርክን ከአፍሪካ ምድርእንዲያ ያስወጣ ከገለፀለትና ሽህ መሐመድ አሊም በንገሩ ደስ ከተሰኘበት በኋላ መይሣው ካሣ የበርሃው ንጉሥ የሚል ስም መሃዲ ብሎ የወርቅ ሻሽና ካባ ከቱርኮች የተማረከ ብዙ አበባ ምንጣፎች ሰጠው መሃዲም ከግዛቱ የሰበሰበውን ወረቅ ገፀበረከት ፲፰፻፴፩ (1831)ዓ/ም ታህሳስ አምስት ቀን አበረከተ ከዚያም ሁለቱ በሰላም ወደሀገራቸው ተመልሰው ሳለ ግብፅን ይገዛ የነበረው የቱርክ እንደራሴ ከዲብ መሐ መድ ቴውሪቅ ሃያ ሁለት ሽህ የግብፅን ተወላጆች የሆኑ ወታደሮች ከብዙ መሳሪያ ጋር ወደገደሪፍና ወደሰናር ላከ በዚህን ጊዜ መይሣው ካሣ ሥናር የሚገኙትን ቱርኮችና ግብጾች ጦር ገጥመው አብደል አዚ ዝን የሀገሩን አስተዳደር ማርከው በተለያዩ በሶስተኛ ዓመታቸው በ1834 ዓ/ም ለመሐመድ አሊ ኑባንና ጅዚራን እስከ ከሰላ እንዲገዙ ቱርኮችንና ግብጾችን ከኑቢያ ምድር ፈጽሞ እንዲያጠፋ ለስላሳ ሰባት ሺህ ወታደር የሚሆን ከቱርክ ወታደር የተማረከ መሳሪያ አስረከ በውት በሰላም ወደቋራ ተመለሱ ። መሐመድ አሊም ከዚህ ቀን ጀምሮ ጦሩ እየበዛ እያየለ ሄደ በየጊዜው ከቱርኮች ላይ ጦርነት እያነሳ ድል ያደርግ ጀመር የቱርክ መንግሥትም ለግብፅ እያስረከበ እንግሊዞ ችም እንዲገቡ አደረገ ።

ኢልመሐዲ መሐመድ አሊ ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር በሃሳብ እየተ ረዳ የእስላሞች ሊቅና መሪ ሆኖ ሲገዛና ሲመራ በውጭ ሀገር ሰዎ ችና በኢትዮጵያ መኳንንቶች አጼ ቴዎድሮስ መሞታቸውን ሲሰማ ወዳጅ ነበሩና በጣም ለብዙ ቀናት አዘነ ይባላል ።

በዚህን ጊዜ አጼ ዮሐንስ ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ቀጥለው ነግ ሠው ሳለ ቴዎድሮስ እስላም ከእስልምናው ክርስቲያን ከክርስትናው ሃይማኖት እንዳይወጣ ሌላው አዲስ ሃይማኖት እንዳይገ ያሉትን ህግ

ቀሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሁሉ አንድ ሃይማኖት እንዲይዝ እስላሙ ክርስቲያን እንዲሆን ብለው ተነሱ ።

በዚህን ጊዜ ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር ጠላት ከነበረው ከቱርክ መንግሥት ተላልከው አራት ጳጳሳት ከካይሮን አስተመጥተው አንደኛውን ለጐጃም ሁለተኛውን አባ ማቴዎስን ለሸዋ ሰጥተው ሁለቱን ግን ለትግሬ ሕዝብ አንዱን አድዋ አንዱን አቡነ ጴጥሮስን አክሱም እንዲቀመጡና ክህነት እየሰጡ እንዲሰብኩ አደረጉ ።

በጐንደር የሚኖሩትን እስራኤሎች ግድ ክርስቲያን ሁኑ እየተባሉ ተገደሉ ተሰቀሉ ።

በወሎም የሚኖሩትን እስላሞች በግድ ክርስቲያን ሁኑ እያሉ በማቸውን እየቀያየሩ አጠመቋቸው በእስላም ስም የሚጠራ እንዲገደል ሲሉ አሳወጁ በዚህንጊዜ አንድ ቄስ በንጉሡ አዋጅ ምክንያት የወሎን ሕዝብ ሰብስቦ ሲያጠምቅና ስም ሲያወጣ አጼ ዮሐንስ የአወጁት አዋጅ ቢዝሙና በስላሙ ሕዝብ ላይ ይህ ነው እግዚአብሔር በቸርነቱ ሁላችን በፍቅር አንድ ካደረገን በሃይማኖትም አንድ እንሆናለን እንጅ ሁለት ሃይማኖቶች በኢትዮጵያ አይኖሩም ። ቀድሞ በጥንቀት በስቃይ ግራኝ የክርስቲያንን ሃይማኖት አጠፋብንና አደከመብን እንጅ ሀገሩ የክርስቲያን ሀገር ነው ሁላችሁ ታውቁታላችሁ አሁንም በሰላም ጋላ ክርስቲያን ሁን በክርስቶስ እመን ብለው በሩ ግዳ ላይ አወጁ ወልደ ኢየሱስ ገብረሚካኤል ወልደ ሚካኤል ገብረ ማርያም እያለ የተለያየ ስም ሲሰጥ ቆይቶ ለአንዱ እስላም ወልደ ገላውዲያስ ብሎ ሰየመው ሰውየውም ስምቶት የማያውቅ ስለሆነ አባ ቄሱ ስለአላህ ብለው የምችለውን ስም ይስጡኝ አላቸው ይባላል ሌላው ደግሞ በንጉሡ አዋጅ ግድ ክርስቲያን ሁን ተብሎ የተገደደ እስላም ለስሙ ክርስቲያን የሆነ ክርስቲያንና ከእስላም ማንኛው ነው የሚበድቅ ቢሉት ክርስቲያን እንዳይል አላመነበትም እስላም እንዳይል በንጉሡ ትእዛዝ እንደሚገደል ስለሚያውቅ መቼም ከሁለቱ አንዱ አላህ ገነት ያገባዋል አንዱን ግን ገሃነም ያወርደዋል አለ ይባላል ።

ያም ሆነ ይህ ግድ ክርስቲያን ሁኑ የሚባሉት የኢትዮጵያ እስላሞች ለጊዜው ክርስቲያን እየሆኑ ማታ በድብቅ ማታ በግልጽ ወደሱዳን እየሄዱ ከሃይማኖት ወንድሞቻቸው ጋር እየተገናኙ በአጼ ዮሐንስ ላይ ጦርነት ለማንሳትና ለመውጋት ይዘጋጁ ጀመር ።

ስለዚህ አጼ ዮሐንስም በሃይማኖት በባህል ከማይመስላቸው ከቱርክ ጋር ተስማምተው በሱዳን ያሉትን እስላሞችና የመሐዲን ተከታይ ለመውጋት በእንግሊዝ መንግሥት አማካኝነት ተዋዋሉ ።

ከቱርክ ቀጥሎ የግብፅና የሱዳን ገዢ ለመሆን ፍላጐት የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ለጥቅሙ ሲል ግብጾችን ለመርዳት ተነሳ ። በኢትዮጵያ በግብፅ የነበረውን ጠብ አስወግዶ በ1876 ዓ/ም የእንግሊዝ መንግሥት የሄዊት ውል የተባለውን ሰር ዊሊያም ሄዊትን ልኮ ሀሉቱን የግብፅን ከዲብ መሐመድ ተወፊክ - ቲውፊክቅንና የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት አጼ ዮሐንስን አስታቆ ሰባት አንቀጾች ያሉበት ውል አዋውሎ በመካከላቸው ሰላም እንዲሆን አደረገ ። ነገር ግን በአምስተኛው ቁጥር ላይ ከቅጣት ለመዳን ከአንዱ ሀገር ወደሌላው ሀገር የተሰደዱትን ስደተኞች ይዞ አሳልፎ ለመስጠት አጼ ዮሐንስና ከዲብ የተዋዋሉበትን በመመልከት አልመሃዲ የቻድንና የናይጀሪያን የሊቢዕያንም የእስላም ሊቆች ጥሪ አድርጐ ውላቸውን ለማፍረስና ለመውጋት ተነሳ በህዛን ጊዜ ንዳሪፍ ከሰላን አምድብና ሰንሂት የሚገኙትን ግብጾች ወረረ ግማሹንም ገደለ የሚባል ወሬ አጼ ዮሐንስ ሲሰሙ ሹም ደህና ፈንታ መተማ የሚገኙትን ቱርኮችን ግብጾችን ከመሃዲ ጦር ተዋግቶ ወደሀገራቸው እንዲሸኙ በደዳቸው እሳቸውም እንደተባሉት አደረጉ ከዚያ ቀን በኋላ የመሃዲ ጦር ከወሎ በተሰደዱት እስላሞች እየተመራ ጐንደርን በአጼ ፋሲል አምሮ ተሰርቶ የነበረውን ከተማ ወረሩት ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች አቃጠሉ አፈራረሱ ቀሳውስቱና መነኮሳቱ በ1880 ዓ/ም ጥር 11 ቀን አረዷቸው ግማሹንም እያሰለሙ ወደቻድ ወደሊብያ ወሰዳቸው ።

በዚህን ጊዜ አጼ ዮሐንስ አድዋ ላይ ሆነው የጐንደር ከተማ መወረርና ቤተክርስቲያኖች መቃጠል ሕዝቡም መጨፍጨፉንና መሄዱን ሲሰሙ ለጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ወደመተማ ሄደህ ከደርቡሾች ጋር ተዋግተህ የተቃጠለውን የቤተ ክርስቲያንና የፈሰሰውን የቀሳውስትና የመነኮሳቱን ደም ተበቀል ብለው ለኳቸው ንጉሥ ተክለሃይማኖትም ሰማኒያ ሺ የጦር ሠራዊት ይዘው ሄደው ሣር ውሃ ከሚባለው ሥፍራ ላይ አቡአንጋ - ከሊፋ አብዱላሂ ጦር አዛዦች ጋር ከአንድ መቶ ስምንት ሺህ ጦር ጋራ መዋጋተው ጦርነት ገጠሟቸው እነዚህም በመሃዲ ስም የሚታዘዙት ደርቡሾች ነጭ ጠምጣሚዎች ከብዛታቸው ድል አድርገው የንጉሥ ተክለሃይማኖትን ብዙ መሣሪያና እቃ መኳንንትና ወታደሮች እንደዚሁም ልጃቸው ወይዘሮ ምንትዋብ ተማርከው ተወሰዱ ።

ንጉሥ ተክለሃይማኖትና ልጃቸው ራስ በዛብህ ከትንሽ ወታደር ጋር በፈረሳቸው ሸሽተው አመለጡ ከዚያም የደርቡሹ ነጭ ጠም ጣሚ ጦር ከመተማ እስከ ወገራ እየሄዱ ብዙ ካህናቶች ገደለ ቤተክ ክርስቲያኖች አቃጠለ ሕዝቡም የአጼ ቴዎድሮስ ግፍ ነው እያለ በየአዛውንቱና በሽማግሌዎች አፍ ይነገር ነበር ይሄውም መሃዲ መሐ መድ አሊ ምንም ክርስቲያን ቢሆን ወዳጅ ነበርና የቴዎድሮስን ጠላቶች ግደሉ እንድ እንዳትተው ይልና ይሰብክ ነበር ።

በዚህን ጊዜ የተገጠመ ፣

ማር ውሃ ከሚዳው የተዘራ አዝመራ
አሜጃ ደርቡሺ ነው ሰብሳቢው አሞራ
አትክለክልም ወይ ይዘህ መሣሪያህን
አሞራ ሲበላው የገዛ ገላህ ን

ምርኮኞች የገጠሙት ፣

ተከተልከኝ ብየ ዙሬ ዙሬ ሳይ
ወይ ጥጋብ ወይ ኩራት ጉንደር ቀረህ ወይ
ወገራ አሳላፊ ደንቢያ እንጀራ ጣይ
ተበለህ ጉንደሬ አትነሳም ወይ

የንጉስ ተ ሃይማኖት ልጅ ደግሞ

የምትሄዱ ሰዎች የምትሻገሩ
ድመት በሊታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ

ተብሎ ተገጠመ ይባላል ።

ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከደረሰባቸው ውርደትና እዶጋ የተነሳ ተበሳ ጭተው ሳለ ንጉሥ ሚኒሊክ ከሸዋ ወደጐጃም መጥተው ከአፅናኑዋ ቸው በኋላ አጼ ዮሃንስ ከትርኮችና ከግብጾች ጋር የሚያደርጉትን ውል ተቃውመው እንገዛም እንታዘዝላቸውም ሲሉ ቃል ኪዳን አድርገው በመሃላ ፈጸሙ ንጉሥ ሚኒሊክም ለንጉሥ ተክለ ሃይማ ኖት የጦር መሣሪያ በቂ ስላልነበራቸው ብዙ የጦር እቃ ሰጥተዋቸው በሰላም ወደ ሸዋ ሄዱ ከዚህ በኋላ አጼ ዮሃንስ እድዋ ላይ ሆነው የንጉሥ ተክለሃይማኖት ድል መሆንና የመሃዲ ንጉሥ ተክለሃይማኖት በርሳቸው ላይ ማደማቸውን ሲሰሙ የትግሬን ጦር ከተት ብለው የጐ ጃምንና የሸዋን ህዝብ እወጋለሁ ብለው ወደጐጃም ሄደው ብዙ ህዝብ ከቀጡና ከገደሉ በኋላ ንጉሥ ተክለሃይማኖትም ጂበላ ከሚባለው

ሥፍራ ላይ መሽገው እየተዋጉ ሰንበቱ ነገር ግን በመካከላቸው ቀሳውስትና መነኩሳት ታቦትና መስቀል ይዘው ስለለመኗቸው ታርቀው አብረው ሊዘምቱ ቃል ገቡ ከዚያም አጼ ዮሃንስ የሸዋን ህዝብ ሊቀጡ ሚኒሊክን ለመያዝ ጉዞ እንደጀመሩ በወገቡ በንሰለት የታጠቀ ዳባ እጽና የለበሰ መነኩሴ ከመንገድ አገኙ አጼ ዮሃንስ ሀሌሞዲና ዶጋሚ ባህታዊ ወዳጅ ስለነበሩና ስለሚያከብሩ እሳቸው ወደአሉበት እስተርበው ስለጦርነቱ ቢጠይቁት ወደሸዋ ሄደህ ክርስቲያኑን ህዝብ ጦርነት ብትገጥም ድል ታደርጋለህ ነገር ግን ገሃነም እሳት ትገባለህ።

ወደመተማ ወርደህ አረመኔን ህዝብ ጦርነት ብትገጥም ድል ሆነህ ትሞታለህ ነገር ግን በሰማእትነት መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ አሏቸው እሳቸውም መንግሥተ ሰማያት ብገባ ይበልጠኛል ብለው ወደደጋቢያ ተመለሱ ይሄን ባህታዊ የላኩት ንጉሥ ሚኒሊክ ናቸው ይባላል ።

አጼ ዮሃንስም የጐጃምንና የትግሬን ጦር ሠራዊት ይዘው ወደ መተማ ሲሄዱ መቶ አርባስምንት ሺህ ጦር ሠራዊት ነበረ ከአጼ ዮሃንስ ጋር የነበሩት ጦር አዝማቾች ንጉሥ ተክለሃይማኖት አጉታቸው ትልቁ ራስ አርአያ የወሎው ራስ ሚካኤል ራስ ሃይለማርያምና ራስ አሉላ ራስ መንገሻ ራስ ሃጐስ እንዲዚሁም ለጃዝማችና ፊታውራሪው ሃያ ስምንት ነበሩ ።

የአጼ ዮሃንስን መምጣት የደርቡሾች መሪ ከአቡ አንጋ ተጥቶ የተሾመው ዚኪ ቱማል ከኢትዮጵያና ከኑቢያ ከሌሎችም ከእስላ ሊቶች የተላከለትን ጦር ይዞ በ1881 ዓ/ም መጋቢት አንድ ቀን ጦርነት ገጠሙ በሁለቱ በኩል የተፋፋመ ጦርነት ከአደረጉ በኋላ አጼ ዮሃንስ የወርቅ ጥላቸውን አዘርግተው በወታደሮቻቸው መካከል ሸገው ሲያበራቱና ሲያዋጉ በጠላት ጥይት ተመተው ሲወድቁ ወታደሮቻቸው አንስተው ወደተከዜ ወንዝ ይዘዋቸው ሸሹ አጼ ዮሃንስም የወንድማቸውን የደጃች ጉግሣን ልጅ ራስ መንገሻን አስጠርተው ወራሼ ልጄ ራስ መንገሻ ነውና ለእኔ እንዳደረጋችሁልኝ አገልግሉት ለእሱም አድርጉለት ብለው ለጦር አዛዦች ለነራስ አሉላ ለነራስ ሃጐስ አደራ ሰጥተው በንጋቱ በአስራ ሰባት በተወለዱ በአምሳ ስድስት እድሜያቸው በ1881 መጋቢት ሁለት ቀን አረፉ ።

እሬሳቸውን ከሞት የተረፉት መኳንንቶች በማጥን አድርገው ሲሸሹ የጦር አዛዡ ዜኪ የጦር ሠራዊቱን ይዞ በግመልና በፈረስ ተከታትሎ ጦርነት ገጥሞ ብዙ ካህናትና መኳንንት ከገደለ በኋላ

የያዙትን የንጉሡ ነገሥቱን እቴ በመርች የተሰበሰበ ወንጌል መስማት፡
ብዙ የጦር እቃ ማረከ ከዚያም የአጼ ዮሃንስን እራስ በሳጥን ውስጥ ያለውን አስከሬኑ እራሳቸውን ቆርጦ ለአሊቃው ለከሊፋ አብዱ ላሂ ወደ እንዱርማን ላከለት ከሊፋም ታላቅ ደስታ አድርጎ የአጼ ዮሃንስን ራስ በግመል ላይ በጦር ሰክቶ ገበያ ለገበያ እያዞረ ለህዝቡ ሲያሳይ ለአጼ ዮሃንስ የተንጠመላቸው ግጥም

አጼ ዮሃንስ ምን ናቸው
እኛም ሁላችን ናቅናቸው

ንጉሥ ቢሏቸው በመሃሉ
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ
አጼ ዮሃንስ ይዋሻሉ
መጠጥ አልጠጣም እያሉ

ሲጠጡ አይተናል በርግጥ
እራስ የሚያዞር መጠጥ
እንዳያሥረው ብሎ ደሃ ወዳጁን
መተማ አፈሰሰው ዮሃንስ ጠጁን

የጎንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ
አንገቱን ሰጠላት ዳግማዊ ዮሃንስ

አጼ ዮሃንስ እንደሞቱ ደርቡሽ ነጭጠም ጣሚ ጐንደር መጥቶ ህዝቡን እንደበግ አረደው ግድ እስላም ሁኑ እያለ አጼ ዮሃንስ በወሎ ላይ እንዳደረጉት የእስላም ስም እየሰጡ አሰለመ እንቢ ያለውን አንገቱን በሰይፍ ቆረጠው ቤቱን ህፃናቱን እየያዘ ወደሃገሩ ሄደ በዚህን ጊዜ የጎንደር ደብተራ አለምር የሚባል እግዚአብሄር የእስላምን ሃይማኖት ቢወድ ነው እስላሞች ድል አድርገው ይሄን ሁሉ ሕዝብ የጨረሱትና እስላም ያደረጉት ብሎ ሰለመ በዚሁ ምክንያት ሚስቱ ተማርካ ተወስዳበት ነበር ተመለሰችለት እሱም ሰልሞ ቀረ ይባላል፡፡ሆኖም ግን ሁሉም የሰራውን እግዚአብሔር እንደሚከፍለው አላወቁም ይሄው አጼ ዮሃንስ እግዚአብሄር ያስደሰቱ እየመሰላቸው በግድ ሰለሙ ከማለትና ከመግደል የተነሳ ይህ ሥራቸው ለእሳቸውና ለብዙ መነኮሳትና ቀሳውስት ሞት ለብዙ ቤተ ክርስቲያን ቃጠሎ ሆነ ።

ከዚህ ቀጥሎ የአቢሲንያ ንጉሠ ነገሥት ሚኒሊክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው ከአጼ ዮሃንስ ቀጥለው እደነገሡ እስፍላችኋለሁ እዘጋጄ መረራስ ኢ.አም በላይ ።

## ምዕራፍ ሰላሳ

የራስ ወሰን ሰገድ የሚኒሊክ ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ ሸዋ ወይም አቢሲኒያ ተብለው እንደነገሡ የልጃቸው ልጅ የዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት

ዳግማዊ አጼ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ከአቤቶ ያዕቆብ ዘር ከሸዋው ንጉሥ ከሣህለ ሥላሴ ከልጅ ልጅ ከሸዋው ንጉሥ ከሃይለመለኮት የተወለዱ ናቸው ። የዘሩም ሃረግ እንደዚህ ነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መቀመጫው ሰባ ከኑባ ወደ ሳባ እስከሚዛወር ድረስ የነገሥታት ዘር በሰትም ሆነ በወንድ ይቆጠር ነበር ነገር ግን ኢትያ በኢትዮጵያ ሃገሮች ውስጥ በሚገኙት ነገሥታት ላይ የበላይና የአዜብ ንግሥት በነበረች ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ወርዳ ከእስራኤል ንጉሥ ከሰለሞን ቀዳማዊ ሚኒሊክን ወልዳ ከመጣችና ልጅዋን በኢትዮጵያ ነገሥታት ላይ የበላይ ንጉሠ ነገሥት አድርጋ ከአነገሰች በኋላ የዘር ትውልድ ከሴት ይልቅ እንደ እብራውያን በወንድ ይቆጠር ጀመር ከዚያ ወዲህ የሚነግሡት ሁሉ የሰለሞን ዘሮች መባል ተለመደና እስከ ዳግማዊ ሚኒሊክ ድረስ እየተቆጠረ መጣ

በዚሁ በነገሥታት ታሪክ እንደ ገለጽኩላችሁ አጼ ልብነ ድንግል በግራኝ አህመድ ጦር ተሸንፈው በሺህ አምስት ፲፻ ሃያ ስምንት (1523 ዓ.ም) ከሸዋ ወደ አማራሳይንት ከዚያ ወደትግሬ ቤተ ሰባቸውን ይዘው ሲሰደዱ አቤቶ ያዕቆብ የሚባሉ ልጃቸውን ልብሰ መንግሥታቸውን ሰጥተው መንዝ ውስጥ ገሆር ከሚባለው ሃገር ላይ ለባላገሮቹ አደራ ብለው ትተው ሄዱ አቤቶ ያዕቆብ የግራኝ አህመድ ጦርነት በወንድሙ በአጼ ገላውዲዎስ ተደምስ እስከሚጠፋ ድረስ የአጼ ልብነድንግል ልጅ መሆኑ ሳይገለፅ በድብቅ ይኖር ጀመር በዚህን ጊዜ ወንድሙ ገላውዲዎስ በህይወት መኖሩን ሰምተው ወደደንቀዝ እንዲመጡ ላኩባቸው አቤቶ ያዕቆብ የድል ባለቤት ለሆኑት ለአጼ ገላውዲዎስ ከሸዋ ወደደንቀዝ ሄደው በሰላም ከወንድማቸውና ከእናታቸው ከእቴጌ ሰብለወንጌል ጋር ተገናኝተው ወደ ተወለዱበት ሃገር ወደሸዋ ተመለሱ ወንድማቸው

አጼ ገላውዲዎስ አብረው እንዲቀመጡ የመንግሥትን ሥራ እንዲ ያግዙቸው ጠይቀዋቸው ነበር ። ነገር ግን ስላልፈቀዱ ከደንቢያ ሰቀ ልት ባላባት እንደታሪክ ነገሥት ንግሥት አዜብ እንደ ታሪክ ፀሃ ፊው ዘግዱር ዘአንደቤት የቋዋራ ንግሥት የሆነችውን የአንበሳ ዳዊት የበሊያው ንጉሥ የልጅ ልጅ አዜብ የወሰን ሰገድን ልጅ አጋብተው ሃገር እንዲያቀኑና የተቃጠለውን ቤተክርስቲያን እንዲ ያሰሩ ከብዙ ካህናትና አዳዲስ ጠበንጃ ከያዙ ወታደሮች ጋር ወደ ነበሩበት ሃገር ላኳቸው ። አቤቶ ያዕቆብ ከኢህ ከንግሥት አዜብ ጋርም ፋሲልን አቤቶ ሥግዎ ቃልን አቤቶ ተገዝካረ ቃልን ወ ሮ ወለተ ማርያምን ወለዱ ።

ገራም ፋሲል ከአንበሳ ዳዊት የልጅ ልጅ ከራስ ወሰን ሰገድ ከእ ምዬ ብርሃን ልጅ ከወ/ሮ ሃመልማል ሱስንዮስን ወልደው ከሱስንዮስ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊት ንገሥት ተክለ ጊዮርጊስ ድረስ በጎንደር ላይ የነው በንጉሡ ነገሥትነት መግዛታቸው የታወቀ ታሪክ ነው ። የገራም ፋሲል እህት ወ ሮ ወለተማርያም ለጉጃም ባላባት ግንድ ሆነው ደቀ ጠራሉ ። የገራም ፋሲል ትንሽ ወንድም ሥግዎቃል ለሸዋ ባላባት የዘ ሩን ግንድ ናቸው አቤቶ ሥግወቃል ወረደ ቃልን አቤቶ ወረደ ቃል ልብስቃልን አቤቶ ልብስቃል የደጃች ፋሪስን ወ ሮ ሰንበልትን አግ ብተው ነጋሢን ይወልዳሉ መስፍን ጌታቸው በደብ ፡ መስፍን ወልዱ ዘሩሁን በኮሬ በመርሃቤቴ መስፍን ጥዱ አድማስ በሞረት አዛዥ መሐዲ በምሁይ ፡ መስፍን ይገባዋል ዘውዱ በተጉለት መኮንን ሃርያቆስ በወግዳ ባላምበራስ ላሌ በላሌምድር መስፍን ላሉየ ባህር ማማ በመንዝ ስታቢ ግድም መስፍን አውሳብዩስ በግሼ መስፍን ወልደገብርኤል በኤፍራታ መርድ አዝማች ዘሚካኤል በአንጾኪያ እነዚህ ሁሉ አምደፂዮን እስከ ልብነድንግል ድረስ የጭዋ መሬት ላይ የሰፈሩ በግራኝ ወረራ ምክን ያት በእጼ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት የተደለደለ የመስፍንና የጭቃ ሹም መቀመጫ ስለነበር ለነዚህ የበላያቸው አቤቶ ነጋሲ ነበሩ ። አቤቶ ነጋሲም አጼ ኢያሱ አድያምሰገድ በሺህ 688 ዓ.ም ላይ ከጐንደር ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ባላባቱ ሁሉ በየተራ እጅ በንሳና ሲተዋወቃቸው እሳቸውም የአጼ ልብነ ድንግል ዘር መሆና ቸውን ስለተናገሩ ለሸዋ የበላይ ርእስ መኳንንት ብለው ሾሟቸው በዚሁ እለት የአርጐባው የወላስማው ዘር በበረከት በይፋት ያሉው ገራድ አሊ ከንጉሡ ነገሥቱ ከአጼ ኢያሱ ጋር መጥቶ እጅ መንሻና ግብር ሰጥቶ ነበርና ከርሱ ጋር የነው አገር እንዲያቀኑ አዘዟቸው የመ ጀባያ የቱሉማ የጀሉ ዘሮች ከአጼ ልብነድንግል ጀምረው እየተዋጉ ሃገር

እያጠፉ ይኖሩ ነበርና ክርስቲያኑን እስላ ሙን በአንድ ላይ ሆነው እን
ዲያስለግሏቸው አበዙ እጼ ኢያሱ ከሸዋ ወደ ጐንደር እንደተመለ
ርእስ መኳንንት ተጋሲ ከጋሎች ጋር እየተዋጉ ብዙ ሃገር አቀኑ አያ
የምትባል ከተማ ቆረቆሩ በዚያውም የማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠ
በዚህን ጊዜ ስማቸውን በማህተም ለማስቀረፅና ግብር ለመስጠት ጐ
ደር ሄደው ሳሉ በድንገት ሞቱና ከዚያም ጐንደር ፊት አቦ ተቀበ
ርእስ መኳንንት ነጋሲ ሰባት ልጆች ነበሯቸው ሰባቱም እርስ በርሳቸ
ሲጣሉ ከኖሩ በኋላ የሸዋ ህዝብ ሰብስቴን ይወድ ነበርና በአባታቸ
አሉ ን አስተመጣቸው በዚህን ጊዜ በቡልጋ አጠገብ ሾላ ሜዳ ድረ
መጥታችሁ ለአባቴ ለነጋሲ ወሴ ውል አደርጋለሁና ተሰብሰባቹ
አላቀሰን ብለው ለዘመድ ሁሉ መልክት ላኩ ።

በዚህን ጊዜ በመኳንንትና መማፍንት በተሰበሰበበት ቦታ ለቅ
ተሰተስ ካለቀ በኋላ ከዛሬ ጀምሮ የማዕረግ ስሜ መርእድ አዝማ
ነው ወደፊት መርእድ ሰብስቴ ብሎ ያልጠራኝ እቀጣለሁ ብለ
አዋጅ አስነገሩ መርድ አዝማች ሰብስቴ ከደብ ባላባት ወገን ከሚለወ
ሴት ከአንኮ አብዩን ወለዱ አብዩም ተወልደው እንዳደጉ ከመንዝ የ
ማን ልጅ ታጒንስቲያን አግብተው ሲኖሩ ወታደር ሞፍራ አዘጋጅተ
በዶቃቲት ከአባታቸው እርቀው መኖር ጀመሩ በዚህን ጊዜ መር
በሲፃቸው መረቅ ተናደው ከአለበት ደቃቂት ድረስ ሂደው ሲመ
ሲጋለባሉ የአብዩ አሽከር በጦር ወርውሮ ገደላቸው ልጅየውም ት
ማሌ ነበር እንጅ አባቴን ለምን ገደልክ ብሎ ገደለው ።

አባቱ መርድ አዝማች ሰብስቴ እንደሞቱ ልጅየው የአባቱን አለ
ጋና ስም ወረስ መርድ አዝማች አብዩ ተባለ በዚሁ ጊዜ ደቃቂት ማ
ሚካኤልን ከአሠሩ በኋላ ከዚያ አልፈው የሃር አምባር ከተማ ቆርቆረው
የቅ ሚካኤልን ቤተ ክ አሠሩ መርድ አዝማች አብዩ ለጐንደር ንገ
ንገሥት ለዳግማዊ ኢያሱ ብርሃን ሰገድ ግብር ከልክለው ለብ
በር በራስ ወልደ ልዑል በራስ ወዳጆ በእየሌ ወሰኑ የሚመራ ጦ
ተፈነዘባቸው የተላኩትንም አሸንፈው ብዙ መማረያም መማረካቸው ይነ
ራሱ መርእድ አዝማች አብዩ ከሃር አምባ ሄደው የአንኮበርን ከተማ ቆረቆ
የደብረ ብርሃን ባላባት እናታቸው አንኮ በዚሁ ዘመን ስለሞቱ ከተማው
አንኮበር አሉት መርድ አዝማች አብዩ ከአባታቸው በኋላ ሃያአምስት
አመት ከገዙ በኋላ 1733 አመተ ምህረት አረፋና በሃር አምባ ቅዱስ
ሚካኤል በአሠሩት ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

በተራቸው ልጃቸው እምኃየስ መርድ አዝማች እምኃየስ ተብለው በአባታቸው እልጋ ተቀመጡ መርድ አዝማች እምኃየስ የአባታቸውን ከተማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክ/ ተክለው እንዲደምቅ አደረጉ ።

በዘመናቸው ቢዛን ወልደ የሚባሉ የቅኔና የመጻሕፍት ሊቅ ከአዘዞ ጐንደር መጥተው በመንዝ የሚቀመጡ ነበሩ መርእድ አዝማች እምኃየስ ልጃቸውን አስፋ ወሰንን ቅኔ እንዲማሩ ከእሸከሮች ጋር ወደ ቢዛን ወልዴ ላኩዋቸው አስፋወሰንም በአመታቸው ቅኔ ተቀኝተው ከተመረቁ በኋላ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ስለመሸባቸው በአንድ ቅሬት አዳርሽ ቤት የእግዚአብሔር እንግዳ ብለው አደሩ ። የቤቱ ባለ ቤት የሆኑት ወይዘሮ እትመች ሁኖ የመርድ አዝማች እምኃየስ ልጅ መሆናቸውን አስፋወሰንን አውቀው ከንዚህ ከኮጋሲ ልጆች ለመወለድ ይፈልጉ ነበርና የእምኃየስ እቁባት መሆናቸውን ሳይገልጡ አብረው አደሩ ሴትዮቱም መልክ መልካም ነበሩና ለአንድ ሳምንት አብረው ቆዩ በዚህ ግንኙነት ሴትዮዋ ፀንሰው በኋላ ወሰን ሰገዱን ወለዱ ።

አስፋ ወሰንም ወደአንኮበር ከተማ ገብተው ከአባታቸው ጋር በጥቂት ሲኖሩ ወይዘሮ እትሞች ሁኖ ከአስፋ ወሰን ወሰን ሰገድን መውለዳቸው ተሰማ አስፋ ወሰንም የአባታቸው እቁባት መሆናቸውን ሲሰሙ ፈርተው ከአንኮበር ወደፍርኩታ ገዳም ሂደው እንደመነኩሴ ቆብ ደፍተው ተቀመጡ ነገር ግን አባታቸው በየገዳማቱና በየአድባራቱ ጣና እግን አየላኩ በልጃቸው መጥፋት ተዘልተው አትርሱኝ ብለው ነበር አስፋ ወሰን የአባታቸው መጨነቅ አይተው ለገዳሙ አበምኔት በዝርዝር አስ አስረዱና ተፈላጊው እርሳቸው መሆናቸውን ገለፁ አበምኔቱም ለአባታቸው ልከው እራሳቸው አንኮበር ድረስ ሂደው በዝርዝር ነገሩ ፍን አስረድተው አስታረቋቸው አባትየው ይስ ብሏቸው የተወለደውን ልጅ ስሙን ወሰን ሰገድ ብለው ሰየሙት መርእድ አዝማች እምኃየስ 34 አመት ከገዙ በኋላ በሺህ 767 ዓ.ም በጥር ወር ሞተው ሬሳቸው በሥሩት በአንኮበር በቅ/ ጊዮርጊስ ቤተ ክ/ ተቀበሩ ።
ተተኪው ልጃቸው አስፋ ወሰን በአልጋው ተቀመጡ በእርሳቸው ዘመን በጐንደር ዙፋን ላይ የተቀመጡት አጼ ተክለሃይማኖት ቀዋሚው አጼ ተክለጊዮርጊስ ተፍጻሜት ነገሥት በመጨረሻ የነበሩት ታላቁ ራስ አሊ የነበሩት ዘመን ነው ።

መርእድ አዝማች አስፋ ወሰን ከአባታቸው አልጋ ከተቀመጡ መኖሪያ በዚሁ በአንኮበር ከተማ አባታቸው ቅዱስጊዮርጊስን እንደሰሩ እሳቸውም ቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሰሩ ። አስፋ ወሰን 33 አመት ከገዙ በኋላ ባልታወቀ ህመም ታመው ሞቱ የተቀ

በሩትም ባሠሩት ቤተ ክ/ በቅድስት ማርያም ቤተ ክ/ ነው ከነዚሁ ቀጥለው ከወይዘሮ እትመኝ ሆኖ የተወለዱት ወሰን ሰገድ መርድ አዝማች ተብለው በአባታቸው እልጋ ተቀመጡ ። መርድ አዝማች ወሰን ሰገድ የቁንዳን ከተማ ቆርቆረው የጊዮርጊስን ቤተ ክ/ የሠሩ በደብረ ብርሃንም የሥላሴን ቤተ ክ/ እሰሩ ከዚጋመል ወደ ደብረ ሊባ ኖስ ሄደው በግራኝ ጦር ምክንያት ተቃጥሎና ፈራርሶ የነበረውን ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራና እንዲታደስ ያደረጉ እርሳቸው ናቸው ።

እንደዚህም ሆኖ ከአጼ ልብነድንግል ልጅ ከያዕቆብ እስከ ንጋሤ አቤቶ ከአቤቶ ነጋሲ ልጅ ከሰብስቴ እስከ ወሰን ሰገድ ''መርድ አዝማች'' እየተባሉ ይጠሩ ነበር አሁን ግን በወሰን ሰገድ ዘመን የነገሥታት ዘር ነኝ በማለት እንጉላላ ከሚባለው ሥፍራ አማራና ጋላውን ሰብስበው ከዛሬ ጀምሮ የማዕረግ ስሜ ራስ ወሰን ነው ሰገድ በዚህ ጥሩኝ ብለው አዋጅ እናገሩ በዚህን ጊዜ የሸዋ መኳንንት አይመው የራስ ሳ ቸውን እሽከር በገንዘብ ገዝተው በ1805 ዓ.ም ላይ በገዙ በእሬት እ ቸው እስገደሏቸው ።

ከራስ ወሰን ሰገድ ቀጥለው ልጃቸው ራስ ሚካኤል ተብለው በአባታቸው እልጋ ተቀመጡ በዚህን ጊዜ ኢትዮጵያ በመሣፍንት ተቆራርጣ መሣፍንቱም በፈንታው ለመንገሥ የሚዘጋጁበትና የአመፀኞን እርዳታ በየግሉ ለማግኘት የሚሯሯጡበት ጊዜ ነበር ስለዚህ ራስ ሚካኤል መንገሥ የተዘጋጀበት ጉዞ በምኒልክ ስም የንጉሥ እንዲቀጥ እንደሆን መንግሥትህ አይፀናም ብሉ የቤቀ ወይም የዘይ ባዛ ታዊ ስለነገሩቸው ሳህለ ሥላሴ ንጉሥ አቢሲንያ ብለው በአሥራ ስምንት አመታቸው ነገሡ ። በዘመናቸውም ያንኮበር ሚካኤልን የገዳመ መድኃኔአለምን የአፈር ባይኔ ተሃይማኖትን የየፍ ሚካኤልን አብያተ ክርስቲያን እሠሩ ።

በግእዙ ሳህለ ሥላሴ ንጉሥ ጋላ እዳል የሚሉና ንጉሥ ሸዋ የሚል ማኅተም አስርተው በሚልኩት ደብዳቤና በሚቀጥሉት መል ላይ ያትሙበት ነበር ሣህለ ሥላሴ ንጉሥ ሸዋ ወይም አቢሲንያ ተብለው በሚገዙበት ጊዜ የፈረንሳይ የእንግሊዞች ሰላዮች መንፈሳዊ በወንጌል ሃዋርያ መስለው ቀጥለው የንጉሥ መልእክተኛ ሆነው ከሳህለ ሥላሴ ጋር መተዋወቅ ጀመሩ ።

ከነዚህም የታወቁት ብዙም ቢሆን ጥቂቶች ምንሽነር ዮ ጆቤስ ጆን ባቲስታ ኩልቦ ሮሺ ዳሪኩር እንደዚሁ በኢትዮጵያ መሣፍንት ቤት እየዞሩ እናንግሳችኋለን ጠንካሩ ተዋጉ ከዘራችን መንግሥት መስርያ እስፈቅደን እናመጣላችኋለን እያሉ ተሰሩ ሲሰጡ እሬብ

በራሱ ሲያጋድሉት የነበሩት ወንድማማቾች እንቲዋንና አርኖ ዳባዲ
ነበሩ ።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የፈረንሳይዊ ንጉሥ ሉዊ ፊልጶስ ሙሴ
ሮሼ ዴሪኩርን የእንግሊዝ (ንግሥት ቪክቶሪያ ካፒቴን ውሊያም ሃሪ
ስን ልከው ከንጉሡ አቢሲኒያ ሣህለ ሥላሴ መተዋወቅ ጀመሩ ። እነዚ
ህም መምእክተኞች መጥተው ከተነጋገሩና ከተስማሙ በኋላ የሸዋ
ው ንጉሥ ሳህለ ሥላሴ ባንድ ወገን የንግሥት ቪክቶሪያ ወኪል
ካፒቴን ሃሪስ በሌላው ወገን ሆነው ባንኮባ ከተማ ህዳር 10 ቀን
1834 ዓ. የወዳጅነትና የንግድ ውል ተዋዋሉ ። ውሉም ከአንድ እስከ
አስራ አምስት አንቀፅ ቁጥር ነበር ሃሳባቸው ነገሥታቱም ሆኑ የነገሥታቱ
መልእክተኞ የሚፈልጉትን ነገር ለመውሰድና ለመቀባበል የሚገልፅ
የሁለቱ ሀገሮች ነጋዴዎች እንዲነግዱ የሁለቱም አገር ነገሥታት
በማናቸውም እንዲደግፉትና የነጋዴዎችን ችግር ለማቃለል የሚቻ
ለውን እንዲያደርጉ ሌላው ደግሞ የሁለቱ ሃገር ሰዎች ለንግድ
ሲሆን ለግላቸው ላመጡት እቃ ቀረጥ እንዳይጠየቁ ከአውራጃ ወደ
አውራጃ ለመዘዋወር እንዳይከለከሉ ሁለቱም ሃገሮች እየተደጋገፉ እን
ዲኖሩ የሚያስጠነቅቅና የሚያስገድድ ነበር የሚል የእንግሊዝ
ተቃዋሚ የነበረውም ፈረሳይ በበኩሉ በሁለተኛው አመት ላይ ሙሴ
ሮሼ ዴሪኩርን ልኮ እንደ ተፎካካሪ ተመሳሳይ የንግድና የወዳጅነት
ውል በ1836 ዓ.ም ተዋዋሉ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ 33 ዓመት የአማራ
የጋላን አገር ሸዋን ከገዙ በኋላ በሺህ 840 ዓ.ም ጥቅምት 12 ቀን
በደብረ ብርሃን ከተማ አርፈው አሬሳቸው በሰሩት ቅዱስ ሚካኤል
ቤተ ክ እንኮበር ሄዶ በክብር ተቀበሩ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ቀጥለው
ልጃቸው ሃይለ መለኮት ንጉሡ ሸዋ ወይም አቢሲኒያ ተብለው ነገሡ
ናታቸውም ወይዘሮ በዛብሽ ከኮድ ወለዱና አምራት ጥሩ የሚወለዱ
ያሉት ዘር ልጅ ናቸው እኔንም ወይዘሮ በዘብሽ ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ
ንጉሡ ሃይለመለ ኮትን አቤቶ ሰይፉን ወይዘሮ በለጥሻቸው ወልደዋል ።

ንጉሥ ሃይለመለኮት አባታቸው ሳህለ ሥላሴ ከመሞታቸው በፊት
ባሰቡት ባላባት ከሆኑት ከደጃች እድያም ልጅ ከለማ የተወለዱትን
ወይዘሮ እጅጋየሁን አግብተው በአባታቸው ስም ሚኒሊክ የሚባል ልጅ
ወለዱ ከአጼ ልብነድንግል እስከሚኒሊክ አስራ አራት ትውልድ ሆኗል
የተወለዱበት ዘመን 1836 አመተ ምህረት ነሃሴ 12 ቀን ነው ።

ሃይለ መለኮት ንጉሠ ሸዋ በተባሉ በስምንተኛው አመት ሃገር
ለማቅናት ወደአሩሲ ሄደው ቢመለሱ የአማራንና የትግሬን ሃገር መሣ
ፍንት መኳንንት ድል አድርጐ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አጼ ቴወ

ድሮስ ተብሎ ነገሠ አሁንም ወደዚህ ወደሸዋ መምጣቱ አይቀርም
ብለው ነገሯቸው ሃይለ መለኮትም መኳንንቱን ሰብስበው ብሞት
አልጋ ወራሼ ሚኒሊክ ነውና እያራ ልጄን ለእኔ እንደምታደርጉ ልጄ
ለእሱም አድርጉለት ብለው አጼ ቴወድሮስን ለመግጠም መኳንንቶቻ
ቸውን ሰብስበው ደብረ ብርሃን አጠገብ አታክልት ከሚባል ሥፍራ መኘ
ነው ይጠብቁ ጀመር አጼ ቴወድሮስም ወሎን ድል አድርገው ወደ ሸዋ
ሲመጡ ብዙ ጦር ገጥሟቸው ነበር ግን ከፊታቸው የበገረ አልነበረም
ሃይለ መለኮት ግን ሰው ከመሞቱ በፊት እጃቸውን እንዲሰጡና መን
ግሥታቸውን በእጼው በንጉሠ ነገሥቱ ሥር ሆነው እንዲያስተዳድሩ
ደጋግመው ልከውባቸው ነበር ነገር ግን የሸዋ መኳንንት አይሆንም
እያሉ ሊይገዋት ነው ስላሏቸው ሃይለ መለኮት ለጦርነት እንደተዘ
ጋጁ የደብረ ሊባኖስ መምህር ገብረሀይወት የሚባሉትን ላኩባቸው ለአጼ
ቴወድሮስም የሸዋ ግማሹ ህዝብ ቤተ መንግሥትና ቤተክህነት መሰ
ማማቱ በዚህን ጊዜ ከትንሽ ከትንሽ ጦር ጋር ሃለመለኮት እንደተዋጉ
ባልታወቀ ምክንያት በ1848 ዓ.ም ህዳር አንድ ቀን አረፉ አጼ ቴወድ
ሮስም በክብር በደብረ በግዞ ህጻን ሞ ደብር አስቀበሯቸው በዚህን ጊዜ
ጊዜ የሃይለ መላኮትን ሞት ሲሰሙ የአንኮበር መኳንንት በጌታችን
ቤት ጠላት አይገባበትም ብለው ቤተ መንግሥቱንና ከተማውን አቃ
ጠሉ ይህን ወሬ አጼ ቴወድሮስ ሲሰሙ ወደ አንኮበር ሄደው ያቃጠ
ሉትን በጠቋሚና በምርመራ ይዘው እንደ ወንጀሉ ግማሹን ገደ
ሉት ግማሹን አሰሩት ይባላል ።

የሃይለ መለኮት ልጅ ሚኒሊክ ከየረር ቤተ መንግሥት ተነስተው
በምንጃር ቆላ ከአባታቸው አሽከሮች ጋር እለፉ አጼ ቴወድሮስ ራስ
እንግዳን ጠቅላይ አዛዥ አድርገው ከብዙ ጦር ጋር ላኩዋቸው
ከዚያም የሁለቱ ወገን ትንሽ እንደተዋጋ ሁሉም እጃቸውን ሰጡ ያንም
ሃገር በረኸት ይባላል ራስ እንግዳም የአስራሁለቱን አመት ልጅ ሚኒ
ሊክን ለአጼ ቴወድሮስ ወስደው አስረከቡ አጼ ቴወድሮስም የሃይለመ
ለኮትን ልጅ ሚኒሊክን በፍቅርና በደስታ ተቀብለው ለሸዋ አል
የሣህል ሥላሴን ልጅ የሃይለመለኮትን ወንድም መርእድ አዝማች ሃይ
ለሚካኤልን ሾሙው አበጋዝ አቶ እንዳርጋቸውን አድርገው ሚኒሊክ
የቤተ መንግሥትንና የአስተዳደር ስርዓት ተመረው እስከሚመ
ድረስ እስቀመጣቸው ።

አጼ ቴወድሮስ ሣህለ ሥላሴና ልጃቸው ሃይለመለኮት ከእንግሊዝ
ከፈረንሳይ መላላኪቸውን ያውቁ ነበርና የተላከላቸውን መገሪያና መል
ቸውን ለማወቅ ይፈልጉ ነበርና የአስራ ሁለቱን ዓመት ልጅ ሚኒሊ

ክን አባትህ ምን አወረሰህ ብለው ቢጠይቋቸው በአንገታቸው ያለው
በወርቅ ተለብጦ የተሰፋውን ክታብ አሳየ በዚህን ጊዜ ከውስጡ ያለ
ውን ክታብ ፈትተው ቢያነቡት ወደፊት ከእንግሊዝ ጋር ብዙ ውል
እንደሚያደርጉ የሚያስረዳ የውል ሰነድ ወረቀትና ሲጊዜው በማጀር
ሃሪስ በኩል የእንግሊዝ መንግሥት የላካቸውን በድፍና ጠበንጃ ሌላም
ብዙ ወርቅ አብሮ ተቀብሮ ተገኘ በዚህን ጊዜ ተደብቆ የተገኘውን
ሲወስዱ ከታጠሉው የተረፈውን ለመርእድ አዝማች ሃይለ ሚካኤል
ሰጥተው ሚኒሊክን ይዘው በደህና ጐንደር ገቡ ።

በዚህ በጐንደር አጼ ቴወድሮስ የሚኒሊክን አስተዋይነት ተመ
ልክተው አብረው በማእረግ ይዘዋቸው ሲኖሩ በመጨረሻ ቤት ልጃቸ
ውን ወይዘሮ አልጣሽ ቴወድሮስን ዳሩላቸው ።

ነገር ግን አጼ ቴወድሮስ የዛሬውን አፍሪካ የጥንቱን ኢትዮጵያ
እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ አንድ አደርጋለሁ በማለት ያቀዱትን እቅድ
ሲያስቡት በእንግሊዝ በፈረንሳይ እየተረዱ መኳንንቱና ካህናቱ ስለአበ
ሸባቸው ከዚያም የሰለሞን ዘርነት የለውም እያሉ ካህናቱ ቀሳውስቱ
ቅዳሴ በኋላ ለህዝብ ስለሚያሰሙ ይህ ወሬ አጼ ቴዎድሮስ ዘንድ
ከደረሰ በሏላ በኩል ቤተ መንግሥትታቸው በክብር ልጃቸውን
አጋብተው ያስቀመጡዋቸ ው አቤቶ ሚኒሊክ ከእናታቸው ከ ወይዘሮ
እጅጋየሁ ለማ ጋር በአሽከሮቻቸው ውስጥ ውስጡን መላላካቸው ከዚ
ያም እንግሊዝ እንደሚረዳቸው በመተማመን ለብዙ ሰው ተናግረው
ስለነበር ወሬውን ለአጼ ቴወድሮስ ስለደረስ ቴዎድሮስም ተናደው
አቤቶ ሚኒሊክን አስረው ወደ መቅደላ ላኳቸው አቤት ሚሊክ ከእና
ታቸው ወገን ከላስታዎችና ከወሎዎች ጋር እንዲሁም ከወርቂት ጋር
ቃልኪዳን አድርገው ከመቅደላ አምልጠው ወረይሉ ገቡ በዚህን ጊዜ
ርእስ መኳንንት በዛብህ ሸዋን ሲገዙ ሳለ የሚኒሊክን ማምለጥ ስለሰ
ሙ ከአንቺ ጋር ነውና ያለ አቤቶ ሚኒሊክ አስረሽ ላኪልኝ ብለ ው ለወሎ
ንግ ሥ ቷ ወርቂት ገፀበረከት ጨምረው ላኩ ወይዘሮ ወርቂትም ቃል
ኪዳን አፍርሰ መቅደላ ሲታሰረው ልጅዋ ለውጥ ለማድረግና አጼ ቴዎድ
ሮስ ለመመለስ በአሽከሮቿ ሚኒሊክን ታስጠብቀው ነበር ነገር ግን አጼ
ቴወድሮስ የሚኒሊክን ማምለጥ ስለሰሙ ዘበኞችንና በነገሩ አሉ የተባ
ሉትን የመኳንንት ልጆችና የወርቂትን ልጅ አግደው አሊን ገደሉ መጣ
ላቸውን ወይዘሮ ወርቂት ስለሰማች ሚኒሊክን ስለአጉላላችና ስለእቆ
የችው ይቅርታ ጠይቃ ከመሣሪያና ከአጃቢ ጋር ወደሸዋ ላከቻቸው ።

ርእስ መኳንንት በዛብህም የሚኒሊክን መምጣት ሰምተው ጋዴሎ
ላይ ጦርነት ገጠሟቸው ነገር ግን በበዛብህ ላይ ህዝብ ስለአደመባቸው
ወደሚኒሊክ ስለ ዞረ ድል ሆነና ሸሽተው አፍቀራ ገቡ ።

ከዚህ በኋላ አቤቶ ሚኒሊክ በወጡ በአስር አመት ቢተወለዱ በ24 ዓመታቸው በ1860 ዓ.ም ንጉሥ ሸዋ (ንጉሠ አቢሲኒያ) ተብለው በአ ባታቸው እልጋ ላይ ነገሡ ።

ንጉሥ ሚኒሊክም የሸዋ ንጉሥ እየተባሉ ለ10 አመት የበላይ ሳይ ላይኖራቸው ሸዋን ሲገዙ ኖሩ በ1870 ዓ.ም ላይ አጼ ዮሃንስ በነገሡ በ7ኛው አመት ሸዋን ለማስገበር ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ወደሰላሌ ደብረ ሊባኖስ ሄዱ ንጉሥ ሚኒሊክም መምጣታቸውን ስለሰሙ ለመዋጋት አቅማቸው እንደማይፈቅድላቸው ተረድተው ገፀ በረከትና ደብዳቤ አሲዘው እንደ ደንቡ እገብራለሁ ብለው መልክ ተኛ ላኩ አጼ ዮሐንስም እኔ ከአለሁበት ድረስ ናና ቃል ከዳኛችንና እርቃችን ፊት ለፊት ተነጋግረን እንፈጽም ብለው ላኩባቸው ንጉሠ ሚኒሊክም ወዲያውኑ ከጀሬና ከሳማሰንበት ዋና ከተማቸው ተነስተው በሽኩራና በዚጋለም አድርገው ደብረ ሊባኖስ ገቡና አጼ ዮሐንስ ጋር ተገ ናኙ ንጉሠ ነገሥቱም አጼ ዮሐንስ በክብር ተቀብለው የንጉሥ የወርቅ ዘውድ ሸልመው የሸዋን ንጉሥነት አፀደቁላቸው ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ዮሐንስና ንጉሥ ምኒሊክ በፍቅርና በሰላም ተሰነባበቱተው ወደ የከተ ማቸው ተመለሱ ንጉሥ ሚኒሊክ ንጉሠ አቢሲንያ ተብለው በፈረንሳይ በእንግሊዝ በኢጣልያን የታወቁ ከዚህ በኋላ ነው የሚኒሊክን ንጉሥነት በ1870 ዓ.ም እንደ አፀደቁላቸው ራስ አዳልን ከጐጃም ወደ ጐንደር አስጠርተው ንጉሥ ሚኒሊክን በአሉበት ቀን የንጉሥነት ማእረግ የአ ባታቸውን የእንበሳ ዳዊትን አልጋ ተክለሃይማኖት ብለው አወረሷቸው የሸዋው ንጉሥ ሚኒሊክ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ሃገር እንዲ ያቀኑና እንዲያስፋፉ ላኳቸው ነገር ግን የሚኒሊክና የተክለሃይማኖት ጭፍራ ጉድሩ ላይ ተገናኝተው ተዋጉ በዚህ ጦርነት ንጉሥ ተክለሃይ ማኖት ቆስለው ነበርና ንጉሥ ሚኒሊክ ጦር አለቃ በራስ ጐበና እጅ ተማረኩ ራስ ጐበናም ለሚኒሊክ ወስዶ አስረከባቸው ሚኒሊክም ንጉሥ ተክለሃይማኖት በክብር ይዘው አብረው እንደቆዩ አጼ ዮሐንስ ጠባቸውን ስለሰሙና መማረካቸውን ስላወቁ ሚኒሊክን ምርኮኛውን ተ/ሃ ይዘኸው ቦሩ ሜዳ ድረስ እንድትመጣ ብለው ስለላኩባቸው የንጉ ሡ ነገሥቱን ቃል አክብረው ንጉሥ ተክለሃይማኖትን ይዘው ወሎ ቦሩ ሜዳ ድረስ ሄደውበነሃሴ ወር 1874 ዓ.ም ከአጼ ዮሐንስ ጋር ተገናኙ ።

አጼ ዮሐንስም እርስ በራስ ከመረዳዳት ይልቅ በመዋጋታቸው ሁለቱንም ወቅሰው የወሎን ግዛት ከሁለት ከፍለው አንደኛውን ለልጃ ቸው ለራስ አርአያ ሁለተኛውን መሃመድ አሊ ለሚባሉት ክርስትና አስነስተው ስማቸውን ሚካኤል አስኝተው ለክርስትና ልጃቸው ለራስ

ሚካኤል ሰጧቸው እንደዚሁ ከንጉሥ ተክለሃይማኖት አገው ምድርን ወስደው ለራስ አሉላ ቁቢ ሰጣቸው አጼ ዮሐንስም በሚኒሊክ በር ሳቻቸው ዝምድና እንዲመሰረት ለልጃቸው ለራስ አርአያ ሥላሴ ወይዘሮ ዘውዲቱ ሚኒሊክን እንዲድሩላቸው ለምነው በ1875 ዓ.ም በጥቅምት አስራ ሶስት ቀን ተጋቡ ። በዚሁ እለት አጽ ዮሐንስ ኢማም መሃመድ አሊን ሚካኤል ብለው ክርስትያን ካደረግዋቸው በኋላ የወሎን ሕዝብ ግድ ግድ ክርስቲያን ሁኑ እያሉ ይገድሏቸው ጀመር ንጉሥ ሚኒሊክ ወደ አጼ ዮሐንስ ቀርበው ግድ ክርስቲያን ሆን ብሎ ማስቆረቡ እግዚአ ብሔር አይወደውም ቢሏቸው ጥንት ክርስቲያን ነው የነበረ ግራኝ ነው በእሳትና በሰይፍ ያሰለመው ዛሬ ደግሞ እኛ ያልመለስነው ማን ሊመል ሰው ነው አሏቸው ። በዚህን ጊዜ በንጉሠ ነገሥቱ በአጼ ዮሐንስና በን ጉሥ ሚኒሊክ ዝምድና ከተመሰረተ በኋላ ለምኒሊክ በሸዋ በደቡብና ምዕራብ ሃገር ግዛታቸውን ያስፋ ዘንድ ፈቀዱላቸው ።

ንጉሥ ሚኒልክም ከወሎ ከቦሩ ሜዳ እንደተመለሱ ከአባ ጂፋር ጋር ተላልከው አባጂፋርም ለንጉሡ ሊገብር ንጉሥነታቸውን አመነ ራስ ጐበና የወሊጋን አገር ጠፍቶ የነበረውን ሃገር ሲያቀኑ ደጃች በሻህ አቦዬ በጂማ አልፈው የጉማን የጊራን አገር አቀኑ ቀውጥለውም ከፋን አገር ሲገዙ በጊቤና በአዋሽ መካከል ያለውን አቅኑ ራስ ወልደ ጊዮ ርጊስ ከንጉሥ ሚኒሊክ ጋር ሄደው የወላሞን አገር ሊሙን ጃጀርን አስ ገበሩ በዚህ ጊዜ የጂማው አባ ጂፋር የከፋው ባላባት ጐጀብ የከፋን አገር በማቅናት ረድተዋል ።

ራስ አርአያ ሥላሴ ዘውዲቱን ባገቡ በአምስት አመታቸው ስለሞቱ የአጼ ዮሐንስና የንጉሥ ሚኒሊክ ወዳጅነት ተቋረጠ በዚህ ምክንያ ት ንጉሥ ሚኒሊክ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር በሳህለ ሥላሴ ዘመ ዘመን መንግሥት ተጀምሮ የነበረውን የወዳጅነትናየንግድ ውል ለማ ድረግ ይጸጸፉ ጀመር ።

በኢጣሊያን በኩል አባ ማስያስ የሚባሉ ሚሲዮናዊ አማካኝነት ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር ደብዳቤ ተላልከው የወዳጅነት ግንኙነት አደረጉ በዚህ ምክንያት ማርኪዝ አንትኖሪከጓዋደኞቹጋር ወደሸዋ ገብቶ በአባ ማስያስና በአዛዥ ወልደ ጻድቅ አስተዋዋቂነት በ1870 ዓ.ም. ላይ ልቼ ከሚባለው ከተማቸው ላይ ከንጉሥ ሚኒሊክ ጋር አገናኘአቸው ልቼ ቀበና ወንዝ አካባቢ ፍንፍኔ ከፍልውሃ እስከ ገፈርሳ ያለው ሃገር ነው።

በዚሁ አይነት በአባ ማስያስ አስተርጓሚነት ተነጋግረው ከጨ ረሱ በኋላ ልጥ ማረፍያ ከተባለው ልዩ ስፈር ከቆዩ በኋላ ከንት ፔየ

ትሮ አንቶኔሊ የኢጣሊያን መንግሥት ልዩ መልእክተኛ ሆኖ ከዋና አዲስ ከተማቸው ልቼ (አዲስ አበባ)መጥቶ ተቀመጠ የኢጣሊያ መንግሥትና ከአቢሲኒያ ንጉሥ ሚኒሊክ ጋር ስለወዳጅነት በኮንት ፔየትሮ አንቶኒሊ ከተነጋገሩ በኋላ መሳሪያ ላክልኝ ብለው የኢጣልያንን መንግሥት ስለጠቀቁት ለጊዜው የተጠየቀውን መሣሪያ ላከላቸው ።

በዚህ ጊዜ የኢጣሊያን መንግሥት ወደኢትዮጵያ ለመግቤት አስቀድሞ እግሩን የሚያስቀምጥ በት ጡሩን የሚያሠፍርበት ሠፈር ይፈልግ ነበርና ጁስፔ ሣፔቶ ቀዶም ብለው በወንጌል ስብከት አስመስለው በገቡት በማስያስና በንዶኞቹ የሐገሩን አኳኋን የህዝቡን ሁኔታ የሚመረምሩ በየጊዜው ይልክ ጀመር ።

ስለዚህ ጁስፔ ሣፔቶ የሚባለው ሚስዮናዊ ከጥንት ከነአጼ ልብነድንግል ጀምሮ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ላይ ሲያምፁና ሲሸፍቱ የኖሩ ከደንከል ጐሣዎች ኢብራሂምን ሃሰን መሃመድ ከሚባሉት ከራሂታ ሱልጣኖች ጋር የወደብ በር ለመግዛት ተነጋገረ ።

ሡልጣኖችም ሰባት ኪሎ ሜትር የሚሆን መሬት በስምንት ሺህ አንድ መቶ ብር ሊሸጡለት ቃል ገቡለት በዚህን ጊዜ ሚሲዮናዊ ጁሴፔ ከአሰብ ተነስቶ ወደፍሬንስ የኢጣልያን ዋና ከተማ ሂዶ ለኢጣሊያን መንግሥትና በመርከብ ሸቀጥ ከሚያመላልሰው ሩባቲኖ ከሚባለው ማህበር መሪ ጋር ተነጋግሮ ዶስ ስለአሰኛቸው ገንዘቡን ሰጥተው ወዲያውኑ ላኩት እሱም እንደደረሰ ለሡልጣኖች ገንዘቡን አስረክቦ በሩባቲኖ ማህበር ስም ተፈራረመ ።

ከዚህ በኋላ ለ13 ዓመት በሩባቲኖ የንግድ ማህበር ስም እንደቆየ የኢጣሊያ መንግሥት ለማህበሩ 416 ሺህ ሊሬ ከፍሎ ወስዶ በአሰብ ያለውን ቀይ ባህር ውስጥ ያሉትን ደሴቶች ጭምር በማታለል እያስፋፉ ያዘ በዚህን ጊዜ በንግድ በወዳጅነት ምክንያት ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባሉት ወደ አጼ ዮሐንስ ከቫሊዩር ብራንኪ ንጉሠ አቢሲኒያ ወደሚባሉት ወደ ምኒልክ ማርኬዝ ኡንቴኖር የሚባል እንደ ቆንሲል ሆነው ተልከው ነበር ።

የኢጣሊያን መንግሥት በሌላ በኩል ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ግብጾች የሚለቁትን ምፅዋን ለመያዝ ምክር ያደርግ ነበር የእንግሊዝ መንግሥት ግን ከዚህ ቀደም በሂዊት አማካኝነት የምፅዋ በር ለኢትዮጵያ ሊሰጥ የኢትዮጵያና የግብፅን መንግሥት ካዋዋለ በኋላ ከድቶ አሁን አስቀድሞ የኢጣሊያ መንግሥት ምፅዋን እንዲይዝ መከረው

የግብፅንም ባለሥልጣኖች ለኢጣሊያኖች ለቀው እንዲሄዱ በሱዋኪን ላይ ስብሰቦበው ነገሯቸው ።

ስለዚህ የኢጣሊያ መንግሥት ኮሌኔል ሳሊታን 80 ወታደሮ ከና ፖሲ. አሲዞ ምፅዋን እንዲይዝ ላከው ወታደሩም በፅ በ1878 ዓ.ም ጥር 25 ቀን ምፅዋን ላይ ተራግፈና የቶሉዱን የአቴምሉን የምንኩሉን የራስ ማዱር መንደሮችና የጌራሪራ ደሴቶችን ጭምር ያለ ጦር ነት ያዘ የግብፅም ወታደር በሚገባ አክብሮ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች እንደነገሯቸው እያስረከቡ ስነበቱ የሁሉቱም በአንዲራ ተሰቅሎ ሰነበት ።

በዚህን ጊዜ ንጉሥ ሚኒሊክ ለጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት የሚያሳዝንና የሚያናድድ ደብዳቤ የምፅዋን ወደብ ጣሊያኖችን አስለቅቀው አጼ ዮሐንስ ካልያዙ እንታዘዛቸውም ሲሉ ላኩላቸው ።

ለንጉሠ ነገሥቱም ለአጼ ዮሐንስ ይሄ የምሰማው ነገር እውነት ነውስ እውሸት ግብጾችስ ቢሆኑ ውሉን አፍርሰው ለኢጣልያኖች የሚለቁበት በአክብርዎት ነውስ? ወይስ ቢንቅዎ የሚል ደብዳቤ አሲዘው መልዕክተኛ ላኩላቸው ይባላል አጼው ግን ተናደው መልስ አልሰጡም ።

በዚህ ጊዜ ንጉሥ ሚኒሊክ ወታደር ይመለምሉና ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር ኢጣሊያንም አሰብን በግዢ ምፅዋን መጀመሪያ በእንግሊዝ እርዳታ ኋላ በጦርነት ከአገኘ በኋላ ሃረርን ከግብፅ ተገዢነት ሲወጣ የእንግሊዝን መንግሥት አስፈቅዶ ሃረርን ለመያዝ ሲዘጋጅና ሰላዮችን ሲልክ ንጉሥ ሚኒሊክ ሰምተው ከእንጠጦ ከተማቸው ሃረርን ለመያዝ 1879 ዓ.ም ተነሱ ። ከዚያም አሩሲን አድርገው በጩርጩር አልፈው ጨለንቆ እንደደረሱ ሃረርን ይገዛ የነበረው አ ሚር አብዱላሂ መምጣታቸውን ሰምቶ ንጉሡ ወደሰፈሩበት ሄዶ ጦርነት ገጠማቸው ነገር ግን ብዙ የጦር ጭፍራ ስላለቀ በት በፈረስ አምልጦ ሃረር ገባ ከዚያም ቤተሰቡን ይዞ ከተማውን ጥሎ ጠፋ ። ንጉሥ ሚኒሊክም በሠራዊታቸው ታጅበው በታላቅና በሚያስፈራ ግርማ ሃረር ገብተው ባለሀ እርጋ ብለው የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ አቆሙ ። ለሀረርጌም ያን ግዜ ባላምባራስ የነበሩትን ደጃዝማች መኮንን ብለው ሾሟቸው ንጉሥ ሚኒሊክ የካቲት ሃያ ስምንት ቀን 1879 ዓ.ም እንጦጦ ከተማቸው ተመልሰው በደህና ገቡ ።

የኢጣሊያንም መንግሥት በዚህን ሰዓት ከአጼ ዮሃንስ ጋር ተጣልቶ ነበርና ከሁለቱ ጋር መጣላት ተፈላጊ አለመሆኑን ተረ

ድቶ እንኳን ደስ አልዎት የሙል ደብዳቤ ለንጉሥ ሚኒሊክ ከቆ ንሲሉ በኩል ላከላቸው ።

በ1880 ዓ/ም ላይ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከመሃዲ ጋር ተጋ ጥመው ድል ከሆኑ በኋላ ወደ ሃገራቸው ተበሳጭተው ተመልሰው ሳለ ንጉሥ ሚኒሊክ ከሸዋ ወደጐጃም መጥተው ከእፄናንአቸው በኋላ የአጼ ዮሃንስ የአስተዳደር አያያዝና ስልት የሚያደርጉትን ስሀተት ከተወያዩበት በኋላ ለአጼ ዮሃንስ እንገዛም ሲሉ ቃል ከዳን አድርገው በመሃላ ፈጸሙ በዚህን ጊዛ ንጉሥ ተክለሃይማ ኖት ንጉሥ ሚኒሊክን ያከብሯቸውና ይወዷቸው ጀመር ህዝቡም ንጉሥ ሚኒሊክን ለንጉሠ ነገሥትነት ደረሰ እያለ በዘፈን በጨ ዋታ ያነሳሳ ጀመር (ይሄውም የሰለሞን ዘር በመሆናቸው ነው)

አጼ ዮሃንስም ከደርቡሽ ጋር ሲዋጉ በ1881 ዓ/ም ስለ አረፉ ንጉሥ ሚኒሊክ ከየአውራጃው የጦር ሠራዊታቸውን ሰብስበው በሠራዊታቸው ታጅበው ወደወሎ ሄዱ ከዚያም እንደደረሱ የአጼ ዮሃንስ መተማ ላይ መሞት ተሰምቶ ነበርና ለንጉሥ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት አድርጐ በደስታና በፍቅር ተገዛላቸው እርማቸውም ገገርሀ እኔ ነኝ ባለህ እርጋ ብለው አዋጅ አስነገሩ ።

በሚያዚያ 10 ቀን 1881 ዓ/ም ወደ የጁ ተጉዘው ለደጃዝ ማች ወሴ የራስነት ማዕረግ ጨምረው ከጨጭሆ በመለስ ባለው አገር ላይ ሾሟቸው በዚሁ በየጁ ሳሉ የጐጃሙ ንጉሥ ተክለሃይ ማኖት የላኩትው ዋግ ስዩም ብሩ የሰሜኑ ወልደሥላሴ የአጼ ቴዎ ድሮስ ልጅ ራስ መሸሻ እየመጡ እጅ እየነሱ ገቡላቸው ንጉሥ ሚኒሊክም ግዛት ላነሳቸው እየጨመሩ የቀሩትንም በየአባት ሃገ ራቸው ላይ ሾሟቸው ድንበር እስከ ድንበር ተጫከለቸው ።

በዚህን ጊዜ የኢጣሊያን መንግሥት የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚ ኒሊክ እንደሚገዛ ስለአወቀና ስለሰማ ውጫሌ ከሚባለው ሥፍራ ላይ እንባበል ሰፍረው ሳለ ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ/ም በኩንት አንቶኔሊን አማካኝነት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ውል ተዋዋሉ ።

ውሉ 20 አንቀፅ ሲሆን ያልተስማሙበትን 17ኛውን አን ቀፅ አቀርባለሁ ከመጀመሪያ እንደዚህ ይላል የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ በስም መጀመሪያ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ሚኒሊክ ለኢትዮጵያ መንግሥትና ለኢጣሊያ መንግሥት ሰላምና ፍቅር ለማድረግ የንግድ ውል ተዋዋሉ ከኢጣሊያ መንግሥት ኮንት አን

ኔሊን ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ምኒሊክ ሙሉ ሥልጣን ተቀ ብሎ የተላከ የሚልና ሶስተኛው አንቀፅ ላይ ስለድንበር የደጋው አፈር ከኢትዮጵያና ከኢጣሊያ መሃል ወሰን ይሆናል ከራፋሊ ጀምሮ ሐላይ ሰገነይቲ አሥመራ የኢጣሊያን መንግሥት ይሆናል ። በበጉስ በኩል አዲ ዋገስ በኢጣሊያን ድንበር ውስጥ ይሆናል አራ ተኛው ደግሞ የደብረ ቢዘን ገዳሙ ከነጉልቱ ለኢትዮጵያ መንግ ሥት እንደሆነ ይቀራል የጦር ሰፈር መሆን ግን አይቻለውም አስራ ሰባተኛው አንቀፅ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤውሮፓ ነገሥታት ጋር ለሚያደርጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግሥት አጋገርነት መላላክ ይቻላቸዋል ብለው ተዋውለው ጨርሰዋል የሚል ነበር ነገር ግን ለንጉሡ ነገሥት ሲመለከቱት ሲያጤኑት የኢትዮጵያ መን ግሥት ከውጭ ሃገር መንግሥታት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ሊያደርግ ይችላል የሚለው ቃል ለንጉሡ ነገሥት ምኒሊክ በጣም ስላናደዳቸውና ንጉሠ ነገሥት እንደመሆናቸው መጠን ለ5 ዓመት ተፈራርመው የነበሩትን ውል አፍርሰው ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር በዚህን ጊዜ ወደአድዋ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ/ም በጳጳሱ በአቡን ማቴዎስ እጅ ተቀብተው ዳግማዊ አጼ ምኒሊክ ንጉሠ ነገሥት በኢትዮጵያ ተብለው በኢትዮጵያ ሃገሮች ላይ እንጦጦ ማርያም ቤተ ክ/ንገሡ ። ከዚህ በፊት የአቢሲኒያ—ሸዋ እንጅ የኢትዮጵያ ንጉሥ አልነበሩም ዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ምኒሊክ ወደትግሬ በሄዱ ጊዜ ራስ መንገሻን የትግሬን ግዛት ሸሟቸው ነበር ነገር ግን ራስ መንገሻ የአጼ ዮሃንስ ወራሽ እንደመሆናቸው መጠንና አጼ ምኒ ልክ ከኢጣሊያን መንግሥት ጋር በመጣላታቸው አልገዛም ብለው ወደ ኢጣሊያን መንግሥት ገብተው ነበር ግን ራስ አሉላና ራስ ሃጐስ ስለመከሯቸው እሺ ብለው ከሁለቱ ጋር አዲስ አበባ መጥተው ለምኒሊክ ገቡላቸው እሳቸውም ከመከፋና የኢጣሊያን መንግሥት በዶ ሊያጣላቸው በሁለቱ በኩል ስላደረገው ከነገሯቸው በኋላ የት ግሬይን ግዛት እንደገና ሰጥተው በሰላም አሰናበቷቸው ።

የኢጣሊያ መንግሥት በነደጃች ባህታ ሃጐስና በነደቡብ እየ ተመራ ብዙ መንደር ያዘ ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደጃች ባህታ ሃጐስ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚያደርገው ግፍና ውርደት ተመ ልክተው የሰገነቲን ምስለኔ ቴኔንቴ ሳንጉይኔቴን አሰሩ ብዙ ኢጣ ልያኖችንም ገደሉ በዚህን ጊዜ ሸሽተው ሸፈቱና ከማጆር ቶዜሊ ወታደሮች ጋር በሃላይ ሲዋጉ ሞቱ ።

ከዚህ በኋላ በጥር 8 ቀን 1887 ዓ/ም ራስ አሉላና ራስ መንገሻ ኩአቲት ላይ ከኢጣሊያ ወታደር ጋር ገጥመው ብዙ የኢጣሊያን ወታደር ከገደሉ በኋላ ጄኔራል አሪሞንዲ ሃሰተኛ ሰላይ ሰውልኮ ለኢጣሊያኖች አዲስ ጦር መጣ ብሎ ለነራስ መሸሻ ነገራቸው እነሱም እውነት መስሏቸው ወደ ሰናአፌ መጥተው መሽጉ በዚህን ጊዜ የኢጣሊያን ጦር በግሥጋሴ ደረሰ አደጋ ጣለባቸው ስለዚህ ራስ መንገሻ ከሰፈራቸው ያለውን ድንኳንና ብዙ መሳሪያ ጥለው ሸሹ ። በዚሁ ጦርነት የሞቱት ደጃዝማች ተድላ ደጃዝማች በየነ ደጃች ካሣ ቀኛዝማች አንዳርጋቸውና ብዙ መኳንንቶች አብረው ሞቱ የሞቱት 900 ሲሆኑ የቆሰሉት ከሞቱት ይበልጣሉ በዚሁ ድል የኢጣሊያን መንግሥት ደስ ስለተሰኘና የትግሬን ሃገር ለመግዛት ቀላል በመሆኑ ወደፊት እንዲገፉ ለጄኔራል ባራቲዮሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክርስፒ ቴሌግራም አስተላለፈለት በዚህን ጊዜ ከአስመራ ሰብሰቦና አጠራቅሞ የቀራቸውን የሃገር ተወላጆችን ከፊት የኢጣሊያን ተወላጆች ከኋላ አድርጐ አድዋ ድረስ መጣ እንደገና የሚገጥመው ሰላጣና ክፍት ሆኖ ስለአገኘው ከአድዋ እስከመቀሌ እስከ አምባላጌ ደረሰ ።

በዚህን ጊዜ አጼ ምኒልክ ኢጣሊያኖች ወደፊት መግፋታቸውን ሰምተው ላጐታቸው ለራስ ዳርጌ እልጋቸውን እንዲጠብቁ ሰጥተው ደጃዝማች ሃይለ ማርያምና አዛዢ ወልደጻድቅን ረዳት ጨምረው በጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ/ም አዋጅ አድርገው ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ሄደው ለጦርነቱ ሰራዊታቸውንና ታማኝ መኮንኖችን የጦር መሪዎች ያሰልፉ ጀመር ። የጦር መሪዎች ከዚህ ቀጥለው የሚገኙት ናቸው

1ኛ/ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ግንባር ቀደም ሆነው ኢዲማህሊያ ከሚባለው ሥፍራ ከሰላሳ ሽህ የጦር ወታደር ጋር

2ኛ/ እቴጌ ጣይቱ አልለይም ብለው ጦራቸውን ይዘው አብረው ስለዘመቱ ከሶስት ሺህ የጦር ወታደር ጋር

3ኛ/ ፊታውራሪ ገበየሁ ከንጉሠ ነገሥቱ በስተቀኝ የአሰምን ወንዝ ተሻግረው በማይ ጉዋጉዋ ከስድሽት ሺህ የጦር ወታደር ጋር

4ኛ/ ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከ3 ሺህ የጦር ወታደር ጋር

5ኛ/ ራስ ወሌ ከንጉሠ ነገሥቱ በስተግራ በማይገላአታ ከ3 ሽህ የጦር ወታደር ጋር

6ኛ/ ራስ ሚካኤል በእንግዳ ሚካኤል ከ8 ሺህ የጦር ወታደር ጋር

7ኛ/ ልዑል ራስ መንገሻ ዮሃንስ ከራስ አሉላና ከራስ ሃጎስ ጋራ ከአራት ሺህ የጦር ወታደር ጋር

8ኛ/ ልዑል ራስ መኮንን በአዲ አቡን ከ8 ሺህ የጦር ወታደር ጋር

9/ ዋግ ስዩም ጓንጉል ከ6ሺ የጦር ወታደር ጋር

10ኛ/ ራስ መንገሻ አቲካም ከ3ሺህ የጦር ወታደር ጋር በድምሩ ሰባ አራት 74 ሺህ የጦር ወታደር ሌሎች ደግሞ ዘግይተው የመጡ ከኢጣሊያ ጋር የነበሩና ከድተው ወደንጉሠ ነገሥቱ የገቡ ራስ ሰብ ሃትና ደጃች ሃጎስ ተፈሪ እስከ ባንዳቸው ጋር መጥተው ከኢትዮጵያ እናት ሃገራቸው ህዝብ ተቀላቅለው ጣሊያንን ሊወጉ ተሰለፉ

ከሰባ አራቱ ሺህ የጦር ወታደር ሌላ በነደጃች ወልዴ በነደጃች በሻህ አቦየ በነደጃች ውቤ በነደጃች ገሠሠ በነደጃች ተሰማ በነሊቀ መኳስ አባተ በነቢትወደድ አጥናፌ አፈ ንጉሥ ነሲቡ በነሊቀ መኳስ አድነው በነበጂሮንድ ከተማ በነፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ በነደጃች ቢትወደድ ወልደ ገብርኤልና በነቱርክ ባሻ ታምሬና ከዚህ ባልጠራ ናቸው የተሰለፈው ጦርና ጋሻ የያዘው አርባ ሺህ በላይ ይሆናል በአ ጠቃላይ ለአድዋ ጦርነት የተሰለፈው መቶ አስራ አራት ሺህ በላይ እንደነበረ የታወቀ ነው ።

በ1888 ዓ/ም የካቲት 23 እሁድ ቀን የመጀመሪያው ግንባር ቀደም ጠቅላይ ጦር አዛዥ ፊታውራሪ ገበየሁና ቀኛዝማች ታደሰ ጦርነቱን ወደፊት ተጋፍተው ጀመሩት ።

የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ያገር ተወላጁን ባንዳ ከፊት አስቀድሞ ሲዋጋ ለስድስት ሰዓት ያክል እንደቆየ ግማሹ እጁን ሲሰጥ ግማሹ ወደጄኔ ራል አርሞንዲ ሠራዊት ሄዶ ተቀላቀለ ጉሰሶ የሚባለው ቦታ እራሳ በራሳ ላይ ተከምሮ ይታይ ነበር በዚህን ጊዜ ፊታውራሪ ገበየሁ ከሠራዊታቸው ተለይተው ከጠላት መካከል ገብተው በጀግንነት ወኔ በቆራጥነት መንፈስ እየፎከሩ ብዙ ጠላት በጐራዴ አንገት አንገቱን ከቆረጡ ቡኋላ በጠላት ጥይት ተመተው ወደቁና በዚያው አረፉ ጣሊያንም ጀግንነታችውን በማድነቅ በታሪኩ ላይ ስማቸውን ጽፎ እስከዛሬ ድረስ ያወሳቸዋል ። በሌላው ምሽግ በኩል የራስ መንገሻና የራስ ሚካኤል የዋግ ስዩም ጉንጉልና የራስ አሉላ ቀቢ እንደዚሁ የነበጅሮንድ ባልቻ የነደጃች

በሻሁ አቦዬ የንሊቀ መኳስ አባተ የጦር ወታደሮች ከበው በመድፍና በጠመንጃ ጠላት ከተደበቀበት ምሽግ ድረስ እየሄዱ ብዙ የጣሊያን ወታደር ገደሉ ግማሹን ከጄኔራል አልበርቶኒ ጋር ተማረከ ።

የጄኔራል አልበርቶኒ ሠራዊት ከተደመሰሰና ግማሹ እጁን ከሰጠና ከተማረከ በኋላ በራእድ የመሸገው የጄኔራል አሪሞንዲ ሠራዊት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከተዋጋ በኋላ አዛዡ ጄኔራል አርሞንዲ ከጦሩ ላይ ስለሞተ ግማሹ ሲማረክ ከሞት የተረፈው ማርያም ሸዊቶ ወደ ሚባለው ሥፍራ ከመሸገው የጠላት ሠራዊት ጋር ሄዶ ተቀላቀለ ።

የኢትዮጵያ ጀግኖችም ተከታትለው ከአለበት ምሽግ ድረስ ሄደው ከጠላት ሠራዊት ጋር ተቀላቅለው በጨበጣ ይዋጉ ጀመር በዚህ ጊዜ በሁለቱ ወገን ብዙ ሰው አለቀ ከጠላት ወገን ዋናው አዝማች ጄኔራል ዳቦርሚዳ በጥይት ተመቶ ከተማረከ በኋላ ሞተ በዚህ ጦርነት ላይ ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ምኒልክ የጦር ወታደራቸው እየዞሩ ሲያበረታቱና ሲያደፋፍሩ እንዲሁም ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ የቆሰለውን ሲያሳኑሱ ለተጠማው መጠጥ ለተራበው እንጀራ ሲሰጡ ዋሉ ።

በተን እለት የቅዱስ ጊዮርጊስ ፅላቱን አሲዘው በጦር በኋላ ውስጥ ነበረ ድል ለአምላካቸውና ለቅዱስ ጊዮርጊስ ምስጋና አቅርበው አስራ ሁለት ጊዜ መድፍ ተተኩሶ ድሉ በማያወላውል ለኢትዮጵያ ሆኖ በአስራ ሁለት ሰዓት ፀሐይ ሲገባ ተፈጸመ ።

በዚህ ዕለት በጦርነቱ የሞቱት 5000 የኢጣሊያን ወታደሮች ከተለያዩ ከሃማሴንና ከከረን የተጠራቀሙ ሰባት ሺህ 7000 ባንዳዎች ሞቱ ከሃገር ተወላጁ ሌላ 2400 ኢጣሊያኖች መድፍና ጠብመንጃ እንደያዙ ተማረኩ ቁስለኛው ደግሞ 2000 ነበር ።

በኢትዮጵያ በኩል የሞተው አስርሺህ በላይ ሲሆን ቁስለኛው አራት ሺህ በላይ ነበር ። የኢትዮጵያ ጀግኖች ድል አድራጊነት በከፍቱ ተመኩቶ የመጣው የጣሊያን ወታደር ተጠቂነትና በኢትዮጵያ ወታደር መመታት በአለም ሃገሮች ስለተሰማ የኢጣሊያን ወዳጆች ሁሉ አፈሩ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሃገሮች ኮሩ ተደሰቱ ከነዚህም የፈረንሳይ መንግሥት የኢትዮጵያን ድል አድራጊነት በሰማ ጊዜ ታላቅ ደስታና ግብዣ አድርገዋል የእንግሊዝ መንግሥት ግን በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት በጣሊያን ተሸናፊነት መገረምና ሃዘን ተሰምቶት እንደነበር ተፎካካሪው የነበረው የፈረንሳይ መንግሥት በፈረንሳዮች በዚሁ በአ

ድዋ ጦርነት የኢትዮጵያን ተከላካይነት የኢጣሊያንን አጥቂነትና ትምክህትንት ተረድተው ለኢትዮጵያ ያረዱ ነበር ።

በዚህን ጊዜ የኢጣሊያን መንግሥት አዲስ ጦር መሪዴ ሩዲኒ የሚባል ሾሞ በምክር ቤቱ ስብሰባ አደረገ የተሰበሰቡበትም በአድዋ ላይ ድል በመሆናቸውና ወደፊት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ምን አይነት ውል እንደሚያደርጉ የሚሻለውን ሃሳብ ለመማከር ነበር በዚሁ ስብሰባ ላይ የሚበልጠው አማካሪ እንደዚህ የሚል የምክር ቃል ስላ ቀረበ ሁሉም ተስማማበት ቃሉም ይህ ነው መጀመሪያ ከንጉሠ ነገ ሥቱ ጋር እርቅ አድርገን እሥመራን ከተማውን ይዞ መጠባበቅ ነገር ግን ይሄን ሳናደርግ ሌላ ወታደር ብንልክ ወታደራችን አልቆ ቀኝ አገር አጥተን እንቀራለን የሚልና ወደፊት የሃይማኖት ሠባኪዎች እየ ሄዱ ብዙ ሰው እንዲተዋወቁ የሚል ነበር ።

በዚህም ምክር ሁሉ ስለተስማማበት ጀኔራል ባልዲስራ አሥመ ራና ምፅዋን ብቻ እንዲቆጣጠር 15 ሺህ ወታደር በፍጥነት ይዞ ምፅዋ ገባ እሱም እንደደረሰ ማጆር ሳልባ የሚባለውን ልኮ እርቅ እንዲያደርግና ወሰኑንም በሰላም እንዲከልሉ ወደ አጼ ምኒልክ ላከ አጼ ምኒሊክም የጦር መሪዎች መሣፍንትና መኳንንት ሰብስበው ለመማከር ድል ከአደረጉ ከአስር ቀን በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመ ለሱ ።

አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማጥፋትና ታሪኳን ለመደ ምሰስ ወዳጅ መስሉ የመጣውን ጠላት ጣልያንን መጀመሪያ አምባላጌ ቀጥሉ መቀሌ መጨረሻ አድዋ ላይ በታላቅ ጦርነት ድል አድርገው ምፅዋን አሥመራን ሳያስለቅቁ መረብን አሻግረው የተመለሱበት ምክ ንያት ጥር 25 ቀን 1878 ጀምሮ እስከ 1888 ዓ/ም ድረስ አስር ዓመት ሙሉ የጣሊያን መንግሥት የሃማሴንና የከረንን የአውሳን የሌሎችንም ባላባት ሰብስቦ ለእስላሙ ልዩ ልዩ ጩርቃ ጩርቅና በእንግሊዝ መን ግሥት አማካሪ እየተረዳ ስኩዋር መቁጠሪያ የተለያዩ የእስላም ሃይ ማኖትን የሚያጥግሱ መፅሃፍቶች ለክርስቲያኖችም እንደዚሁ እያቀ ረበ በነጻ አድኗቸውና ጊሬራና ሃማሴን ይባል የነበረውን ምድር ኤርትራ ብሉ አዲስ ስም አውጥቶ ስለነበርና እነሱም እርዳታ በዚሁ በአድዋ ጦርነት ፊት ግንባር ቀደም ሆነው ከወገኖቻቸው ጋር ሲዋጉ የነበር አጼ ምኒልክ ከጠላት ኢጣሊያን ወታደር ይልቅ የሃገር ተወ ላጅ ባላባት በጠላት ወገን ሆኖ ያለአግባብ ስለሞቱና ስለቆሰሉ እንደ ገና በጥቂት ባላባቶች የቀረውን እያስገደደ ለጦርነት በአስመራ ላይ

ሆኖ ማዘጋጀቱን ስለአወቁ ነው ስለዚህ እሳቸውም በእግዚአብሄር እርዳታ በጦሩ ተመክቶ የመጣውን ጠላታቸውን ጣሊያንን በአድዋ ላይ ድል አድርገው ወደፊት ላለው ነገር ሁሉ ከጦር መሪዎቻቸው ጋር ለመማከር ወደአዲስ አበባ የተመለሱበት ጉዳይ ወደ ዋና ከተማቸው አዲስ አበባ እንደገቡ የሮማ ጳጳስ 13ኛው ልኩ የታሰሩትን ለማስ ፈታትና ከኢጣሊያን መንግሥት ጋር በወዳጅነታቸው እንደሚቀ ጥሉ የኢጣሊያንም መንግሥት ንጉሥ ነገስታቸውን እምኖ ለልጅ ልጅ የሚቀይ የወዳጅነት እርቅ እንደሚያደርግ ሞንሲኛር ማካሪዮንን የሚ ባል መልእክተኛ ደብዳቤ አሲዞ ወደ አጼ ምኒሊክ ላከ አጼ ምኒሊክም መልእክተኛውን በጥላቻ ሳይመለከቱ ተቀብለው ከአነጋገሩ በኋላ ተስፋ ያለው ደብዳቤ አሲዘው ሞን ሲኞር ሚካሪዮንን መልሰው ወደሮማ ላኩት የኢጣሊያንም መንግሥት ለጊዜው የተላከለትን ደብዳቤ ተቀ ብሎ በደስታ ወዲያውኑ ዶክቶር ኔራዚኒ የሚባል ባለስልጣን ከአጼ ምኒልክ ጋር ውል እንዲያደርግ መስከረም 25 ቀን እስከ ህዳር 10 ቀን ሲማከርና ሲያጠና ቆይቶ በ1889 ዓ/ም ላይ ቀጥሎ ያለውን እር ቅና ወሰን አደረጉ ።

1ኛ/ በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣሊያን መንግሥት መካከል ከዚህ ቀደም እንደተየረገው ያለ ጦርነት ቀርቶ ለልጅ ልጅ የሚቆይ የወዳጅነት የእርቅ ውል ተደርጓል ።

2ኛ/ ከዚህ ቀደም ውጫሌ ተደርጎ የነበረው ውል ፈርሶአል።

3ኛ/ የኢጣሊያ መንግሥት የኢትዮጵያን መንግሥት ሙሉ መብት እንዳለው ህዝቡም አንድነትና ነጻነት እንዳልተሰየው ያውቃል።

4ኛ/ ለጊዜው የመረብ ወሰን ሆኖ እንዲቆይ ተደርጓል ።

5ኛ/ የኢጣሊያ መንግሥት የኤርትራን ሃገር ከፍሎ ለመስጠት የፈለገ እንደሆን ለኢትዮጵያ መንግሥት ይለቃል እንጅ ለሌላ መንግ ሥት አሳልፎ መስጠት አይችልም ።

ብለው ሁለቱ ሃገሮች ተዋውለው የውሉ ቃል ለኢጣሊያ መንግሥት ተልኮለት በጣም ደስ ተሰኘበት አጼ ምኒልክም የኢጣሊያንን ምር ኮኞች በነጻ ለቀው በዛይላ በኩል አልፈው ወደሃገራቸው ገቡ ። የኢ ጣሊያ መንግሥት በኤርትራ በስተምዕራብ በኩል ከሰላን ይዞ ይገዛ ነበር ነገር ግን ለእንግሊዝ መንግሥት ከሱብዳሬት ወዲያ ያለውን ሃገር ሁሉ ለቀቀለት ይሄውም የኤርትራን ምድር ያገኘ በእንግሊዝ እርዳታና ምክር ስለነበር ነው በሌላ በኩልም የሡሃዲ ወታደሮች

አቆርዳት ድረስ እየሄዱ ብዙ ጣሊያን ወታደሮችና ለጣሊያን መንግሥት የሚያገለግሉትን ሁሉ ይገድሉበት ስለነበር ያለ እንዳች ነገር በፍትር ለቀቀለት ።

አጼ ምኒልክ የውጭ አገር መሣሪያ እየሰበሰቡ በየጊዜው ወታደራቸውን ያደራጁና ያሰለጥኑ ነበር መጀመሪያ ከመጣላታቸው በፊት ከኢጣሊያ አስር ሺህ ጠብመንጃ ብዙ ምልዮን ጥይት ካገኙና በሙሴ ሺፍኔ አማካኝነት ከፈረንሳዊ መንግሥት ብዙ መሣሪያ እንዳገኙ ኢጣሊያኖችን አባረው ከአድዋ ጦርነት በኋላ ለጊዜው ግዛታቸው በሰሜን በኩል እስከመረብ ድረስ ሆኖ እንዲቆይ ከተዋዋሉ በኋላ በምስራቅ በኩል ራስ መኮንን ውጋዴን አልፈው እስከሱማሌ ድረስ አስገበሩ እንደዚሁም 25 ሺህ የሆነ የጦር ሠራዊታቸውን አስከትለው ከፋሌና ሺሆጂሌን ለኢትዮጵያ መንግሥት አስገበሩ ።

ደጃች ተሰማ ናደው የባሮን መሬት አልፈው ሰባትን እስከነጭ አባይ ያለውን ሁሉ አስገበሩ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ከፋን ኩሎያ ኮንታን ሊሙን እስከነጭ አባይ ድረስ ያለውን ጉሚ ለኢትዮጵያን መንግሥት አስገበሩ ።

ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ 15 ሺህ የጦር ወታደር ይዘው በቦረና እስከ ኬንያ ድረስ ያለውን አቀኑ ራስ መንገሻ ዮሃንስ አንድ ጊዜ ከኢጣሊያን መንግሥት ጋር ውስጥ ውስጡን ሲላላኩ አንድ ጊዜም ከምኒልክ ጐን ሆነው በአድዋ ዘመቻ ኢጣሊያኖችን በመውጋት ታላቅ ሙያ ሰርተው የትግሬን ግዛት ተሰተው ነበር ነገር ግን የአጼ ዮሃንስ አልጋ ወራሽ እንደመሆናቸው መጠን ከራስ ስብሃትና ከደጃዝማች ሃጎስ ተፈሪ ጋር ተስማምተው በኢጣሊያን እርዳታ ተመክተው ሸፈቱ በዚህን ጊዜ አጼ ምኒልክ ራስ መ ኮንንም የጦር ሠራዊታቸውን ይዘው በ1891 ዓ.ም. በቆቦና በአሸንጌ አልፈው አላጌ ደረሱ ራስ መንገሻም ለጊዜው ያላቸው ሃይል ከራስ መ ኮንን ጦር ጋር ለመግጠም አለመቻሉን ተረድተው ከአጼ ው ጋር እንዲያስታርቋቸው እጃቸውን ሰጡ ።

ራስ መኮንንም ለአጼ ምኒልክ ምህረት እንዲያደርጉላቸው የልመና ደብዳቤ ጨምረው ወደ ንጉሠ ነገሥታቸው ላኳቸው አጼ ምኒልክም ግን ሁለት ጊዜ ሸፍተህ የኢትዮጵያን ህዝብ ልታስፈጅ ሞከርክ አልሳካልህ ሲል አሁን ወደእኔ መጣህ አሁን ለራስ መኮን ስል ምህረት ባደርግልህ የረጋውን መንግሥቱን ታነቃንቃለህ ለውጭ ጠላት መግቢያ ትሆናለህ ስለዚህ አንተን በግዞት መኖር እንጅ መልቀቅ አይገባም ብለው በግዞት ወደአንኮበር ላኳቸው የትግሬንም ግዛት

ለራስ መኮንን ሰጥተዋቸው አንድ አመት ተኩል እንደቆዩ መክሬ ይቅር አስደርግልሀለሁ ብለው ቃል ኪዳን ያደረጉለትን ራስ መንገሻን ስለአሰሯቸው ግዛቱን አልፈልግም ብለው አገሩን ለራስ ወሌ አስረክበው በ1982 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው መጡ በ1899 ዓ/ም ላይ ታህሳስ 5 ቀን የፈረንሳይና የእንግሊዝ የኢጣሊያንም መንግሥታት የሶስቱ መንግሥታት ስምምነት ተብሎ የተጠራውን ውል ተዋዋሉ ውሉም እንደዚህ ነበር ።

1ኛ/ የእንግሊዝ መንግሥት በግብፅና በሱዳን ምድር በሚወርደው የአባይ ወሃና በሃገሩ ላይ በጥቅም ልዩ ሥልጣን እንዲኖረው

2ኛ/ የፈረንሳይ መንግሥት በጅቡቲ ባለው በቅኝ አገሩ ይዞታ ከዚህ ቀደም በጀመረው የሃዲድ መንገድ ለማሰራት ለማመላለሻ የሚሆን የመንገድ ሥፍራ እንዲያገኝ

3ኛ/ የኢጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ሰሜን በደቡብም በሱማሊያ በኩል ብዙ ሥፍራ እንዲያገኝ

4ኛ/ የፈረንሳይ መንግሥት የሚዘረጋው የሃዲድ መንገድ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ድረስ እንዲሆን ከዚያ እንዳያልፍ

የእንግሊዝ መንግሥት በበኩሉ በኢትዮጵያ ምዕራብ ከሱዳን ወደኤርትራ ከበናዲርና ከኤርትራ ጋር የሚገናኝ የሃዲድ መንገድ ለመዘርጋት የተስማሙበት ውል ነበር ስለኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት መብት የንጉሠ ነገሥቱን ሥልጣን እንንካም ሲሉ ሶስቱ ሃገሮች ወኪሎች ተስማምተው ከጨረሱ በኋላ ለአጼ ምኒልክ ነገሩን እንዲያውቁትና በሃሳባቸው እንዲተባበሩ የስምምነቱ ግልባጭ ወረቀት ተላከላቸው ፡ አጼ ምኒልክም ሃሳባቸውና ውላቸውን እስተውለው ስለሃዲዱ መንገድ መዘርጋት ተደስተው ነገር ግን የኢትዮጵያ መልእክተኛ በሌለበት ብቻችሁን ስለተዋዋላችሁና ስለተስማማችሁ በስምምነታችሁ ውስጥ እኔን የሚያስገድደኝ የለም ብለው ለሶስቱ መንግሥታት በ1899 ዓ/ም መልሱን በደብዳቤ አስታወቁ ። አጼ ምኒሊክ በአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ (1900) ዓ/ም ከነሃሴ ወር አንስቶ የእንጀት በሽታ ታመው ወደየፀበሉ ይወስዳቸው ጀመር ከደብረ ሊባኖስ ብዙ ቀን ከተቀመጡ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከተማቸው ተመልሰው ወርቅነህ እሸቴና ሙሴ ሃርሚ ኒዩር የሚባሉት ሃኪሞቹ እያከሟቸው ሳለ ጥቅምት 17 ቀን 1902 ዓ/ም እንደበታቸው ተዘጋ በዚህን ጊዜ ህዝቡ አዝኖ በየቤተክርስቲያኑ ፀሎት እየተደረገላቸው በሶስተኛው ቀን እንደበታቸው ተከፈተና ስለ አልጋ ወራሻቸው ኑዛዜ አደረጉ ።

አጼ ምኒልክ በዙፋናቸው የሚተካ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው ከሴት ልጃቸው ከወይዘሮ ሸዋረጋ ለተወለዱት ለኢያሱ ሚካኤል ለማውረስ አስበው ከመታመማቸው በፊት በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ያኖሯቸው ነበርና ጥቅምት 20 ቀን 1902 ዓ/ም ልጅ ኢያሱ ሚካኤል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተሰማ ሞግዚት ሆነው እንዲያገለግሏቸው ተደረገ ። ከዚህ ቀን ጀምሮ ህመማቸው እየበረታ ሄዶ አጼ ምኒልክ ንጉሠ አቢሲንያ ተብለው ከፋና ጂማን አሩሲንና ሲዳሞን ሸዋንና ሐረርጌን ሃያ ሁለት አመት አጼ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሃያ አራት አመት በክብርና በደስታ ገዝተው በተወለዱ በሰባ አመታቸው ታህሳስ ሶስት ቀን 1906 ዓ/ም አረፉ ።

## ምዕራፍ ሰላሳ አንድ

### የአጼ ኢያሱ ሚካኤልና የንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት

### ኢትዮጵያ በዓለም ማህበር ውስጥ መግባት፤

### አቤቶ ኢያሱ ከራስ ሚካኤል

### ከወይዘሮ ሸዋረጋ ምኒልክ

ይኸውም የአፄ ምኒልክ የልጅ ልጅ ስለሆኑ አጼ ምኒልክ በዙፋናቸው የሚተካ ወንድ ልጅ ስላልነበራቸው በ1901 ዓ.ም የአቤቶ ኢያሱ አልጋ ወራሽነት በአዋጅ ተነገረ ።

አጼ ምኒልክ ታመው በነበረበት ጊዜ ራስ ተሰማ የአልጋ ወራሽ ኢያሱ እረዳትና አማካሪ እንዲሆኑ ተሾሙ ።

አልጋ ወራሽ ኢያሱ አጼ ምኒልክ በአረፉ ጊዜ ሞታቸው የተሰማ እንደሆነ ሃገር ይሸበራል እየተባለ ይፈራ ነበርና በድብቅ አጼ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥቱ ዘኢትዮጵያ ተብለው በአባታቸው ዙፋን ላይ ተቀመጡ አጼ ሚኒሊክ በኑዛዜያቸው ላይ ከልጅ ኢያሱ ጋር ሆናችሁ አገራችሁን ጠብቁ የሚል ቃል ኑዛዜ ስለነበረ ህዝቡ በደስታና በክብር ተቀበላቸው በኢትዮጵያ ሃገሮች በረከት ሞላ በኢያሱ ጻባ ነው ትሩሱ የሚባል ዘፈን በዘመናችው ይዘፈን ነበር ነገር ግን አጼ ኢያሱ በውስጥ ሃገር ከእስላሞች ጋር በውጭ ሃገር ከጀርመኖች ጋር የሚያደርጉትን ወዳጅነት የሸዋ መሳፍንት አልወደዱላቸውም ። ነበር በዚህኔ ጊዝ አድመዋል የተባሉትን ሁሉ ራስ አባ ራስ ወሌ በግዞት እንዲቀመጡ አደረጉ ። ከዚያም እህታቸውን ወ.ሮ ዘውዲቱን ከአዲስ አበባ ወደ ፉሌ ሄደው በዘብ እንዲጠበቁ አደረጉ ።

አጼ ኢያሱ ንጉሠ ነገሥት በሆኑ በአመታቸው ዝቋላ ገዳም ሄደው በመጋቢት የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስን በዓል በስነ ሥርዓት አከበሩ ከዚያም ወደአዳል አገር ሄደው ጨናዩ የምትባል ከተማ ቆረቆሩ ህዝቡም በሰልፍና በደስታ ተቀበላቸው ከአዳል ሀገር ወደ ደሴ ሄደው ቆብ.ካን ከአባታቸው ከራስ ሚካኤል ጋር ዋሉ።

ስለዚህ በግንቦት ወር 1907 ዓ/ም "ዘሥልጣኑ ዕሁፍ ዲመ መቅከፍቱ ሚካኤል ንጉሠ ፅዮን ዘአክሱም" ብለው በወሎና በትግሬ በጉጃም ላይ እንዲገዙ ሲሉ የንጉሥነት ዘውድ ደፋላቸው የአባታቸውን የንግሥና በዓል በሥነ ሥርዓትና በክብር ካበከበሩ በኋላ ወደ ሸዋ በሰላም ተመለሱ ።

አጼ ኢያሱ እስላሙንና ክርስቲያኑን ህዝብ እኩልነትና አንድነት እንዲኖረው ሲሉ ለኢትዮጵያ ክርስቲያን ከእስላም እስላምም ከክርስቲያን አያንስም አይበልጥም ሀሉም የሃይማኖት እምነት ቢከፍላቸው በሃገር አንድ ናቸው ስለዚህ እስላሙ እንደሌሎች ሃገሮች ከፍ ማድረግ አለበት ሲሉ በአዋጅ ተናገሩ ።

በዚህን ጊዜ የኢትዮጵያ እስላሞች አጼ ኢያሱን ከልብ ወደዳቸው በሄዱበት ሃገር ከክርስቲያኑ ይልቅ እስላሙ ህዝብ አክብሮ በሰልፍና በእልልታ ይቀበሉላቸውና ያስተናግዳቸው ነበር እንደዚህም የአውሳን ባላባት የደጃዝማች አቡበክርን ልጅ ለማግባት አጭተውለት እንደነበርና አፍቅረዋት እንደነበር በሰፊው ይነገር ነበር ።

ስለዚህ ኢያሱ ወደ እስላም ሃይማኖት ተመልሰዋል እየተባለ የሸዋ መሣፍንትና መኳንንት ያወሩ ጀመር ይሄ ሰው ንጉሠ ነገሥትነት መሆኑ ስህተት ነው ብለው አጼ ኢያሱ ሐረር በሄዱበት ጊዜ መኳንንቱ ስብሰባ አድርገው የአጼ ምኒሊክን በልጅ አክስታቸውን ወይዘሮ ዘውዲቱን በዙፋን ለማስቀመጥ የግሀለ ሥላሴን የልጅ ልጅ ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ራስ ተብለው የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ እንደራሴ እንዲሆኑ የምክር ቃሉን ከታተመና ተፈራርመው በምክር ከጨረሱ በኋላ በ1909 ዓ/ም መስከረም 17 ቀን አጼ ኢያሱ በሌሉበት ቀን የዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታትና የራስ ተፈሪ አልጋ ወራሽነት በቤተ መንግሥቱ አደባባይ በአዋጅ ተነገረ በዚህን ጊዜ ንጉሥ ሚካኤል በደሴ ኀተማቸው አጼ ኢያሱ ሐረርጌ ሆነው የንግሥተ ዘውዲቱን መንገስ ሰሙ ንጉሥ ሚካኤል ለጦርነት ሲዘጋጁ ወዲያውኑ አቤቶ ኢያሱን ለመያዝ ደጃዝማች አያሌው ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር በባቡር ተላኩ በዚያም ምኤሶ ላይ ደጃዝማች ጉግሳን ወግተው ድል አደረጉት ሌሎች ወታደሮች ከኢያሱ ደጃች አያሌውን ተዋግተው ለመመለስ ተላኩ ነገር ግን የሐረር ባላባትና ወታደር ተፈሪን ይወድ ነበርና ኢያሱን ክደው ከሸዋ ተልከው ከመጣው ጦር ጋር ተደረቡ በዚህን ጊዜ ኢያሱ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ሆነው ወደ አውሳ ሄዱ ኢማም መሃመድ አሊ ይባሉት የነበሩት ንጉሥ ሚካኤል

ስልሳ ሽህ ወታደር ይዘው ልጃቸውን ለመርዳት ወደሸዋ መጡ ከዚያም ቆሬ ሜዳ ላይ ከራስ ሉልሰገድና ከደጃዝማች ተሰማ ጋር ገጥመው ድል አደረጉ ከዚያም ወደፊት ሲጓዙ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ የጦር ሠራዊታቸውን ይዘው ሰገሌ ላይ ይጠባበቋቸው ጀመር ሌላውም ጦር በራስ ደምሰው እየተመራ መጥቶ ተጨመረ፤

ጥቅምት 17 1909 ዓ/ም እርብ ቀን ሰገሌ ሜዳ ላይ ጦርነት ገጥመው ሲዋጉ ውለው በመጨረሻ ንጉሥ ሚካኤል ድል ሆነው እጃቸውን ሰጥተው ተማረኩ በዚሁ እለት ልዑል እሌጌ ወራሽ ራስ ተፈሪ ከተማውን ደጃች ባልቻ እንዲጠብቁ ትተው በዚሁ በሰገሌ ጦርነት ነበሩና ጀግንነታቸውን ያየና የሰማ ከዳር እስከዳር እመሰገናቸው። ድል ያደረጉም ራስ ተፈሪ ከጦሩ ሜዳ በገቡ ጊዜ ነው ይባላል ከጦሩ ከተፈፀመ በኋላ ራስ ተፈሪ በድል አድራጊው ሠራዊታቸው ታጅበው ምርኮኞቻቸውን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ ወይዘሮ ዘውዲቱ ከአጼ ሚኒሊክና ከወይዘሮ አብቺው ጅሩ እንዋሪ ከተማ ተወለዱ ወይዘሮ ዘውዲቱ መጀመሪያ የአጼ ዮሃንስ ልጅ ራስ አርያን አገቡ ራስ አርያ ሲሞቱ ደጃዝማች ውቤን ከደጃዝማች ውቤ በኋላ ራስ ጉግሳ ወሌን አግብተው ሲኖሩ አባታቸው እንደታመሙ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከእንጀራ እናታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ሆነው አጼ ምኒልክን እያስታመሙ ተቀምጠው ነበር አባታቸው እንደሞቱ በአጼ ኢያሱ ትእዛዝ ወደፋሌ ይኖሩ ነበር። ነገር ግን የሸዋ መኳንንትና መሣፍንት ይወድዋቸው ስለነበር በኢያሱ ላይ የተደረገው ምክር ካለቀ በኋላ ከፋሌ አስመጥተው መስከረም ሃያ አንድ ቀን 1909 ዓ/ም "እቴጌ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ተብለው በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቀባኢ መንግሥት ተቀብተው እንዲነግሡ ተደንገገ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስና እጨጌ ወልደ ጊዮርጊስ ኢያሱን የተከተሉክ የአነገሥናትን ዘውዲቱንና ራስ ተፈሪን የከዳሁ ውግዝ ከመአርዮስ ኢያሉ በአዋጅ ተናገሩ የመከሩንም ቃል አፀኑ።

የሸዋ ካህናትና መሣፍንት በምክሩ ተደሰቱ ከዚህ በኋላ በጥቅምት የሰገሌ ጦርነት ከተደረገ በኋላ የንግሥት ዘውዲቱን የዘውድ በዓል በመላ ኢትዮጵያ በ1909 ዓ/ም የካቲት አራት ቀን እንዲከበርና ታላቅ ሰልፍ እንዲደረግ ትእዛዝ ተላለፈ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተ መንግሥቱ በስተተር የኤሌክትሪክ መብራት በየመንገዱ አልነበረምና በዚህ

ቀን ከቤተ መንግሥቱ እስከ አራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ድረስ በየመንገዱ መብራት ስለበራ ሁሉም ደስ አለው ።

በዚህ ዕለት አባታቸው በሠሩት በአራዳ ጊዮርጊስ ታላቅ በዓል ተደርጎ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ቅባአ መንግሥት ተቀብተው እቴጌ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ተብለው በመላ ኢትዮጵያ ሃገሮች ነገሡ ታላቅ የወርቅ ዘውድ ተደፋላቸው ራስ ተፈሪም በዚህ እለት ለአልጋወራሽ የሚገባው ሥርዓት አድርገው ክብ ራስ ወርቅ አደረጉላቸው ከዚህ በኋላ ካራዳ ጊዮርጊስ ወደ እንቁላል ቤተ መንግሥት ሄደው በአባታቸው ዙፋን ሲቀመጡ መቶ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

የንግሥተ ነገሥታትን ሥልጣን ለማሳወቅ ሲባል ራስ ወልደ ጊዮርጊስ የካቲት 11 ቀን ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ንጉሠ ጐንደር ብለው አንግሠው ዘውድ ደፉላቸው ።

እንደዚሁ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪን መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ/ም ብዙ መኳንንትና መሣፍንት ሊቃውንትና ጳጳሳት በዓሉበት በአዲስ አበባ መካነ ሥላሴ የንጉሥነት ዘውድ ደፉላቸው ።

ልጅ ኢያሱ ከሰገሌ ጦርነት የተረፉትንና የራስ ይመርን ጦር ይዘው ወሎ ገብተው ለጦርነት ይዘጋጃሉ የሚባል ወሬ በሸዋ ስለ ተሰማ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ራስ አባተ ብዙ መሣፍንትና ጦር ሠራዊታቸውን ይዘው ኢያሱን ለመያዝ ወደወሎ ሄዱ ከዚያም ደሴ ላይ ጦርነት አድርገው ኢያሱ ድል ሆኑና ወደመቅደላ ሸሽተው ሄዱ ከዚያም ከመቅደላ ጦር ለማዘጋጀት ወደ አውሣ ሄዱ ነገር ግን የአውሳ ህዝብ ሊያብርላቸውና ሊደግፋቸው እንደተነሳ አውቀው ወደ ትግሬ ሸሹ ከዚያም ያሉበት ጠፍቶ ሲፈለጉ በ1913 ዓ/ም በትግራይ ውስጥ ግብፅያ በሚባል ገዳም ተደብቀው ሳለ በተቋሚ የራያ ጉግሣ አርአያ ሰዎች አግኝተው ያዟቸው ራስ ጉግሣም የኢያሱን መያዝ ለተፈሪ አስታወቁ አልጋ ወራሽ ተፈሪም ደሴ ድረስ ሄደው ከራስ ጉግሣ እስረኛውን ልጅ ኢያሱን ተረክበው ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ሰላሌ ፍቼ ከተማ በልዑል ራስ ካሣ እጅ እስረኛ ሆነው መኖሪያ ቤት ተሠራላቸው ነገር ግን በ11 ዓመታቸው ልጅ ኢያሱ ከፍቼ አምልጠው ወደ ጐጃም ሄዱ በዚህን ጊዜ ራስ ካሣ ወደ አዲስ አበባ ሄደው ሳለ ቢመለሱ ኢያሱ መጥፋታቸውን ሲያዩ ወዲያውኑ አስታወቁ ።

በዚህን ጊዜ የአገኘ ይሽለማል የሚባል ወሬ በመሰፍንቱ በድብቅ ተነግሮ ኑሮ ለጎጃም ህዝብም በከንቲባ ማተቢ እጅ ተላከ በዚህን ጊዜ የጐጃም መሣፍንት የአዋጁን ቃል በሰማ ጊዜ ኢያሱን ይዞ ለመስጠት ይሽቀዳደ ምና ይፈልግ ጀመር

በዚህን ጊዜ አጼ ኢያሱ በግንደበረት አድርገው ኩሜ ሚካኤል ገቡ በዚህን ጊዜ የራስ ሃይሉ የወንድም ልጅ ፊታውራሪ ገሰሰ በለው የሊበንን አገር ይገዛ ነበርና ተእርሱ ቤት አርፈው ባለ ወደ ራስ ሃይሉ ላኩት እርሱም በከንቲባው የመጣውን ቃል ሲሰማ ከራስ ደስታ ጋር ተገናኝቶ ከእርሱ ቤት እንዳሉ ገልጾ ከራስ ሃይሉ ተል ከው ለመቀበል የመጡ አስመስሎ አታሎ የራስ ደስታ ይዞ አስረከበ ላቸው ከዚህ በኋላ ወደአዲስ አበባ አምጥተው ወደገራ ሙለታ ወሰ ደው በእስረኛነት እንዲቀመጡ ተደረገ በዚያው ሳሉ በ1927 ዓ/ም በህዳር ወር ሞቱ ።

ራስ ሃይሉም ለአጼ ኢያሱ እረዳት ናቸው ተብለው አድማውን ያልሰሙ አስመስለው እንዲመጡና እስዎ ባሉበት ስለ ኢያሱ ፍርድ እንዲሰሙና እንዲፈረድባቸው የሚባል ሌላም ወሬ ተላከዕቸው ራስ ሃይሉም የሸዋን ምክርና አድማ ሳያውቁ ወደሸዋ መጡና በዚያው በግዞት እንዲኖሩ በራሳቸው ላይፈረዱባቸው አሁን የነሱን እንተ ውና ወደ ንግሥት ዘውዲቱ ታሪክ እንመለስ ። ኢትዮጵያ በዚሁ ዘመን በአፍሪካ ምስራቅ የምትገኝ ተቆራርጣና ተቀንሳ የምትገኝ ሃገር ሆና ሰች ሴሎች ሃገሮች እርስ በራሳቸውም አንዳንድ ጊዜ ቢዋጉ እና ቢጋደሉ ብዙ ጊዜ ሌላውን በመውረር ቅኝ ሀገር በመያዝና ሃገራቸውን ታላቅ ሃገር በማድረግ በየሃገሩ ባህር ተሻግረው ቅኝ ሃገር በመያዝ ይሽቀዳደማሉ ኢትዮጵያ ግን ህዝብዎቻ መሣፍንትዋ ሲጋደሉበት ሲፋጁበት እርስ በርሳቸው ሲተራረዱበት የምትታይ ሃገር ሆናለች ። ይሄን ያየ ወይም የሰማ ከጣልያን በቀር ኢትዮጵያን ወርሬ ቅኝ ሃገር አደርጋለሁ ያለ ቀርቶ የተመኘ አልነበረም ሆኖ ግን በተያዙት ሃገሮች በሚገዙት አገሮች ስብሰባና ምክር ቤት የኢትዮጵያ ህዝቦች ያልሰለጠኑ እርስ በራሳቸው የሚዋጉ ጨካኞች ሰውን መሸጥና መለወጥ ያልተው እየተባለ ይወራና ይነገር በጋዜጣም ይወጣ ጀመር ።

ስለዚህ የእሊዝ መንግሥት አለመሰልጠን የሚለውን ቃልተ ደግፎ የናይጀሪያ አገሬ ገዢ ሰር ፍሬድሪክ ሉጋርድ የሚባለው በ1911 ዓ.ም ከዚህ የሚቀጥለው አሳብ አቀረበ ።

"በኢትዮጵያ ስፐ ባሪያን የሚገዛትና የባሪያን ንግድ ለስማ ቀረት የመግሪያውም አይነት ለመመርመር በውስጣዊ አስተዳደርዋም አብሮ ለመስራት የእንግሊዝና የፈረንሳዊ የኢጣሊያን መንግሥት ወኪሎቹን ያሻል ወይም ስዚሁ ነገር የአለም ማህበር ለኢትዮጵያ አስተዳደር ልዩ አማካሪዎች ሊሾም ያስፈልጋል" ሲል አቀረበ ይህን አሳብ የእንግሊዝ ምክር ቤት ከመረመረና ከአጠና በኋላ የአለም ማህበር ከሚያደርጋቸው አማካሪዎች ጋር አብሮ ለመስራት ፍቃድ መሆኑንና አለመሆኑን ለመጠየቅ ሲባል አዲስ አበባ ያለውን የእንግሊዝ ሚኒስትር ትእዛዝ ተላልፎለት ይህንን ጥያቄ ለኢትዮጵያ መንግሥት አቀረበ።

በዚህን ጊዜ በጥያቄው መሰረት ተደስቶ የኢትዮጵያ መንግሥት የአለም ማህበር ህግን ለመፈጸም የተዘጋጀ በመሆኑ ሃገሩንም ለማሰልጠን በሃገሩ ው ስጥ ያለውን ነውር ባሪያ መሸጥ በተቻለው መጠን ለማስወገድ ፈቃዱ መሆኑን ገልጾ የአለም ማህበር ገብቶ ማህበረተኛ እንዲሆን በ1915 ዓ/ም ነሐሴ ስድስት ቀን በደጃዝማች ናደውና በአቶ ፋሲካ እጅ ወደ አለም ማህበር ላከ።

በዚህን ጊዜ አትገባም ትገባለች የሚል ክርክር ተነስቶ ነበር ነገር ግን የፈረንሳዊ መንግሥት ከአሁን በፊት የነበሩትን ስህተቶች ልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ ለማስቀረትና ሃገራቸውንም ለማሰልጠን እንደተነሱ በኢትዮጵያ የባሪያ አገዛዝ በሀጋቸው እንደተሻረ በጉባኤው መካከል ከአስረዱ በኋላ ኢትዮጵያ ከአለም ማህበር መግባት ይገባታል ሲሉ የፈረንሳዊ መልእክተኛ ዳኞች ፈረዱ።

የኢጣሊያ መንግሥትም ይገባታል ሲል ተናገረ ኢትዮጵያ በነፃነት የነበረችና የምትኖር መሆንዋን በአለም ማህበር ውስጥ አረጋግጣ በ1916 ዓ ም በሚያዝያ ወር ከማህበሩ ገብታ ከማህበሩ እንደ አንድ ንባል ሆነች።

## ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት

### የአጼ ኃይለሥላሴ ማህጸ ነገሥት (ተፈጸሚተ ነገሥት ዘመን መንግሥት)

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ድረስ ከሴም ነገድ ከእስራኤል ዘር የወረዱት የእግአዝያን ዘር እየተባሉ ሲጠሩ የኖሩ የነገሥታት ዘር ናቸው የዘሩም ሐረግ እንደዚህ ነው ሣህለ ሥላሴ ንጉሠ አቢሲንያ ወይዘሮ በዛብሽን አግብተው ንጉሥ ሃይለመለኮት አ ቤቶ ሰይፉን ወይዘሮ በለጥሻቸውን ወለዱ ።

እራስ መኮንን አባታቸው የዶባ ባላባትደጃዝማች ወልደሚካኤል ይባላሉ ከአቤቶ ያዕቆብ ከአጼ ልብነድንግል ዘር አላቸው ይሄም አባቶቻቸው የደባን መሳፍንት ይዘው የኖሩ ናቸው ። ራስ መኮንን ከህጻንነታቸው ጀምረው በትምህርት ያደጉ ብልህ አስተዋይ ነበሩ በዚሁ ምክንያት አጼ ምኒልክ አክብረው ይዘዋቸው ይኖሩ ነበር እርሳቸውም ምንም ዘመድ ቢሆን በትን አገልግለዋቸው ለሃገራቸው በታማኝነት በአስተዳዳሪነት በጥሩ ሁኔታ ይመሩት ነበር ።

ራስ መኮንን ከጉራጌ ባላባት ወይዘሮ የሺመቤትን አግብተው ሐረርጌን ሲገዙ ሳለ ሃረር አውራጃ ኤጀርሣ ጎሮ ከሚባለው ሃገር ላይ በ1884 ዓ.ም ሃምሌ 16 ቀን አጼ ኃይለ ሥላሴ የተባሉትን ተፈሪን ወለዱ ።

ልጅ ተፈሪ የአማርኛና የፈረንሳዊ ትምህርት እየተማሩ ልዩ አስተማሪ ተቀጥሮላቸው ሳለ በ14 ዓመታቸው ህዳር አስር ቀን አባታቸው ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የደጃዝማችነትን ማዕረግ ሰጥተው ጋራ ሙለታን እንዲገዙ ፈቀዱላቸው መኳንንቱንም ለእኔ እንደምታደርጉልኝ ለልጄ ለደጃዝማች ተፈሪ እንድታደርጉለት ብለው ራስ መኮንን በ1898 ዓ.ም መጋቢት 13 ቀን ተናገሩ ሞቱ እንደማማሹ ህዝብ መኑን ይባላል ።

በዚህን ጊዜ ዳግማዊ ሚኒሊክ ደጃዝማች ተፈሪን ከጋራ ሙለታ እስመጥተው ባጠገባቸው እንዲቀመጡ የሰላሴን ግዛት ሰጣቸው ደጃ

ዝማች ተፈሪም የፈረንሳዊን ትምህርት በዳግማዊ ምኒሊክ ት/ቤት ይቀጥሉ ጀመር ።

በአመታቸው የባሶን ግዛት ከዚያም ሲዳሞን ተሾመው በ1902 ዓ/ም ሲዳሞን ትተው ሃረር ጌን የአባታቸው ግዛት የነበረውን ተሰጣቸው በ1903 ዓ/ም የንጉሥ ሚካኤልን የልጅ ልጅ ወይዘሮ መነንን አገቡ ከዚያም በአጼ ኢያሱ ትእዛዝ የሃረርን ግዛት ተቀምተው ወደ አዲስ አበባ መጥተው እንዲቀመጡ ታዘዘ ።



በዚሁ ምክንያት አዲስ አበባ ሳሉ እጼ ኢያሱ ሃረር በሄዱበት ሰዓት ንግሥት ዘውዲቱን እንግሰው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የአ ልጋ ወራሽነት የራስ ወርቅ አሰሩ ። ራስ ተፈሪ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ በ1916 ዓ/ም የአውሮፓ ከተሞችን እየተዘዋወሩ ጉብኝተዋል የአውሮፓን መሪዎችን ትላልቅ ባለሥልጣናትና አነጋግረዋል ።

ራስ ተፈሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ በንግሥተ ነገ ሥታት ግርማዊት ዘውዲቱ ፍቃድ መስከረም 27 ቀን 1921 ዓ/ም በመካነ ሥላሴ የንጉሥነት ዘውድ ደፉ በዚሁ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ በነሃሴ 12 አውሮፕላን ወደኢትዮጵያ አስገቡ በ1923 ዓ/ም የዳግማዊ ምኒልክን ሃውልት አቆሙ የወንጀለኛ መቅጫ ደንብ አቋቋሙ ።

ግርማዊት ቀዳማዊት ንግሥት ዘውዲቱ በነገሡ በ13 አንደኢኔ በ14 ዓመታቸው አረፋና የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ንጉሥ ተፈሪ እጼ ሃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ስዩመ እግዚአብሔር ተብለው በ1923 ዓ/ም የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ደፉ ።

እጼ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እንደሆኑ ህገ መንግሥታቸውን ሲያቆሙ የንጉሥነት ስምና ስልጣን እንዲጠፋ አደረጉ ራስና ደጃዝ ማች የሚለው የማዕረግ ስምና ስልጣን ብቻ እንዲኖር አሉ ስለዚህ ማህጸ ነገሥት ተባሉ በ1924 ዓ/ም የነፋስ ስልክ እንዲቆም አደረጉ ቀዋ ሰው ጥቅምት 1 ቀን የኢትዮጵያን ባንክና የምክር ቤት ከፈቱ ።

እጼ ኃይለሥላሴ በዚሁ በመጀመሪያ ዘመነ መንግሥታቸው ተማሪ ቤት ሆስፒታል የልዩ ልዩ መስሪያ ቤት አስከፍተው የመገኛኛ መንገድ ስልክ ራዲዮ አዘርግተው ወታደርም በአዲስ ሥልጣኔ እንዲ ራመድ ማንኛውም ጥበብ በየመልኩ እንዲስፋፋ በሚጥሩበት ጊዜ ይሄን አላማቸውንና ውጥናቸውን ለማሰናከል የኢጣሊያ መንግሥት በወ ልወል 1927 ዓ/ም በፊታውራሪ አለማየሁና በፊታውራሪ ሽፈራው ላይ በአይሮፕላንና በእግረኛ ወታደር ድንገት ደርሶ ብዙ የኢትዮጵያን በር ጠባቂ ገደለ በዚሁ ምክንያት እጼ ኃይለሥላሴ ከሐረር ወደ ጀኔቭ ለተባበሩት መንግሥታት ማህበር አማካሪዎችና ለፕሬዚዳንቱ መልእክት አስተላለፉ መልእክቱም ፥

እኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያን ጥያቄ በሚመረመር በት በአሁኑ ጉባኤ ይህን ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን መልእክት ከቡር ነትዎ መልካም ፈቃድዎ ሆኖ እንዲነበብ እንዲያደርጉ እንጠይቃለን ።

1ኛ/ በእኛ በኩል እስከዛሬ ድረስ መጣሪያም ወታደርም ሳንሰከ
ት ነገርም ሳናናሳ የኢጣሊያ መንግሥት በወሰናችን አቅራቢያ የወ
ዶር ኃይልና የጦር አቢዮን ታንክ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማብዛቱ ማንኛ
ንም ህዝብ ያውቀዋል ።

2ኛ/ የኢጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት አል
ፈው ወታደሮቹ መያዛቸውና የኢትዮጵያን ህዝብ እንደአረመኔ ህዝብ
ቆጥረው በአረመኔ ህዝብ ላይ ማንኛውንም ነገር ማድረግ የሚገባ
ው ብለው ለአቆሙት ፕሮፓጋንዳ ወሬ የኢትዮጵያ መንግሥት በሚ
ያስፈልገው ጊዜና ሥፍራ ላይ ለጥያቄው የሚገባውን መልስ ለመስ
ጠት የተዘጋጀን ነን ።

3ኛ/ የኢትዮጵያ መንግሥት የተባበሩት መንግሥታት ዳኝነት
አልቀበል አለ ብሎ የኢጣሊያ መንግሥት የሚቀርበው ፕሮፓጋንዳ
ወሬ ሃሰት ነው ለዚህም የኢትዮጵያ ተወላጅ ያልሆኑ ሽማግሌዎችን
መርጠን በሁለታችን ያለውን የወልወል ግጭት እንዲመረምሩና ኢት
ዮጵያ ሰላም ፈላጊና የኢንተርናሽናል ህግ የምታከብር መሆንዋን
እንዲገልፁ አቅርበናል ።

4ኛ/ የኢጣሊያ መንግሥት ምንም በወሰናችን ላይ ጦር ማከ
ማቸቱ ባይቀር እኛም በወሰን ላይ ግጭት ዳግመኛ እንዳይሆን የተባ
በሩት መንግሥታት ማህበር ሙል ቃል እንዲፈጹምና በእውነት ላመ
ከላከያ ያልሆነውን የኢጣሊያ የጦር ብዛትና ማከማቸት እንዲያቆም
እንዲያደርጉ አማካሪዎችን አጥብቀን እንጠይቃለን ስለአለፈው የወ
ልወል ግጭት ሽማግሌዎች መርምረው እንዲፈርዱ የኢጣሊያ መንግ
ሥት አልቀበልም ካለ ግን አማካሪዎቹ. መርማሪ እንዲያደርጉበትና
15ኛውን ክፍል መሰረት አድርገው ከመረመሩ በኋላ በአጥፊው ላይ
ሙሉ ውሳኔ እንዲወስኑ እንጠይቃለን ፡

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ሃይለ ሥላሴ ግንቦት 8
ቀን 1927 ዓ/ም ሐረር ከተማ ስለዚህ የተባበሩት መንግሥታት ማህበር
ዋና ፀሐፊው ከሁለት ወገን የቀረበለትን ሪፖርት መርምሮ ሲጠይቅ
የእንግሊዝና የፈረንሳይ የእስፓኝና የቱሬክ ሽማግሌዎች በሁለቱ መን
ግሥታት ጠብ የተነሳ ሁለተኛው የአለም ጦርነት እንዳይነሳ ብለው
“ኢትዮጵያ በውጋዴን በኩል አገር ቆርጣ ለኢጣሊያን እንድትሰጥ
የእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ የባህር ወደብ እንድታገኝ የዘይላንን
ወደብ እንዲሰጥ የሚል ቢያቀርቡ ለሁለቱ መንግሥታት ሙሴ ሙሶ
ሎኒ የኢጣሊያ መንግሥት ከበርሃ ጉዳይ የለውምና ይሄን የመሰለ

እርሷ አልቀበልም ሲል ለእስላም ሕዝብ በእስላም ጋዜጣ አስታወቀ ከዚህም ቀጥሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደ አረመኔ እየተጠራ ገብቼ ማሰልጠን ይገባኛል ። ሲል የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር እንዲያፀድቀለት ጠየቀ ሽማግሌዎችም የፈረንሳይና የእንግሊዝ የአሜሪካና የቱርክ መልእክተኞች ኢጣሊያን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያሰልጥን ማለታቸውን ትተው እንደ ታዘዙት የጣሊያ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር አብሮ እየሰራ ሊያሰለጥን የሚገባው የዓለም ማኅበር ነው ሲሉ የመጨረሻው ውሳኔያቸው ይህ ሆነ ።

የኢጣሊያ መንግሥትና (ቫቲካን) የካቶሊክ ቄሶች ከኢትዮጵያ መንግሥትና ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናን ጋር የነበረቸው ጠብ የኖረ ባለታሪክ ረጅም ዘመን ያለው ነው ከዚያም በቅርቡ ጊዜ በአፄ ገላዴዎስና በወንድማቸው በአፄ ሚናስ ዘመን መንግስት የነበሩት የካቶሊክ ቄሶች በአፄ ሱስንዮስ ዘመን መንግሥት በርትተው እራሱንም የኢትዮጵያን መንግሥት ከኦርቶዶክስ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት አዛውረውት ሳለ በዚሁ ጠብ ተነስቶ በካቶሊኮች ቄሶች ትእዛዝ የብዙ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ ፈሰሰ በአደባባይ ተገረፈ ተሰቀለ ስንቱ ሊቃውንት ምላሱ ተቆረጠ በረሃ ሲሰደድ ብዙው ወገኖችን በሰማዕትነት ተሰውተው ሞቱ ከትንሽ ዘመን በኋላ አቡኖ ፋሲለደስ እንደነገሱ ለሕዝባቸው ተቆርቋሪ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ ስለነበሩ ከኢትዮጵያ ምድር የካቶሊክ ቄሶች ፈጽመው እንዲወጡ ሕዝቡም ወደጥንት ኦርቶዶክስ ሃይማኖቱ እንዲመለስ ብለው ስለአወጁ የተሰደዱት ሊቃውንት በሰላም ከዱር ከበርሃ የነበሩት ሁሉ ወደቤታቸው በሰላም ተመለሱ ሀገርም ፀጥታና ደስታ ሆነ ዳሩ ግን ሕዝቡ በሰላም እንዳይኖር ከኢትዮጵያ ምድር ተባረው የወጡት የካቶሊክ ቄሶችና ሮማ የሚገኘው ሊቀ ጳጳስ በየጊዜው ለኢትዮጵያ መሳፍንትና መኳንንት እጅ መንሻ እየላኩ እየተወዳጁ ግማሹ በተለያዩ ሃይማኖቶች አሳብ እንዲነሳ ግማሹ ስልጣን እነስኝ ብሎ እንዲነሳ አድርገው እርስ በርሱ አጋደሉት አለያዩት ነገር ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይሄን የመሰለ እሻጥር ሲያካሄዱ እነርሱም 1800 ዓ/ም ላይ ተከፋፍለው አንድ መስፍን በጎጃም አንድ መስፍን በጎንደር አንድ መስፍን በሲሲል በሌሎችም አውራጃዎች ተከፋፍለው አንዱ አንዱን እየወጋ ይገዛ ነበር በኋላ ግን በናፖሊዮን ሶስተኛው እርዳታ በብዙ ድካም ጦርነት በሳርዲው መስፍን በካርሎ አልቤርቶና በልጁ በቢክቶር አማኑኤል እንዲሁም በጋሪባልዲ በብስለት አንድ የጋ ትሥ ሀገር አደረጓት ከዚያም ወዲህ የኢጣሊያ መንግሥትና የባቲ

ካን ቄሶች ኢትዮጵያን ቅኝ ሀገር ለማድረግ ይማከሩ ጀመር በዚሁ ዘመን የእንግሊዝና የፈረንሳይ እስፓኝና ቱርክ የጀርመን መንግሥታት የአፍሪካ ምድር እየተከፋፈሉ ቅኝ አገር ያደረጉ ነበርና የኢጣሊያንም መንግሥት ሌሎች የአውሮፓ መንግሥታት የያዙትን አገር በመፍራት ከመጀመሪያ ጀምሬ በነጻነትዋ ኮርታ የምትኖረውን አገር ኢትዮጵያን ለመያዝ እንዲመቸው አሰበን በግዢ አስመስሎ ያዘ ከዚያም በኤርትራ ምድር ያሉት ግብጾችና ቱርኮች ከምፅዋ ለቀው የሚሄዱበት ጊዜ ስለነበር በእንግሊዝ መንግሥት እርዳታ ምክር ከአሰብ የነበረውን ወታደር ሌላም አዲስ ጦር እያስመጣ ምፅዋ ላይ አሰፈረ ።

በዚሁ ዘመን በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ይገዙት የነበር አጼ ዮሐንስ የኢጣሊያን ወታደር ከኢትዮጵያ ምድር ወጥቶ እንዲሄድ ብለው በእንሱት ከእርከር በዶጋሊ ላይ ጦርነት ተነስቶ በሁለቱ በኩል ብዙ ሕዝብ አለቀ በዚህን ጊዜ ለቀው ከአቢሲንያው ንጉሥ ምኒልክ ጋር ወዳጅነታቸውን እየቀጠሉ ሁለቱን ለማዋጋት አሰበው ሳለ በአጼ ዮሐንስ ላይ የመሃዲ ተከታዮች ተነስተው ጐንደር ከተማን ወረሩት ብዙ አብያተ ክርስቲያኖችን አቃጠሉ የመሣፍንት ቤተሰቦችና ካህናት ሊቃውንት ተገደሉ የሚባል ተሰማ በዚህን ጊዜ አጼ ዮሐንስ ጦር ክተት ብለው አክሱም ነበሩና ከአክሱም ወደመተማ ሄዱ በዚህን ጊዜ ከምፅዋ የነበረው የኢጣሊያን ወታደር የአጽ ዮሐንስን መሄድና መራቅ ሰምቶ አምባላጌ ድረስ መጥቶ ሰፈረ ።

በመተማ ጦርነት የአጼ ዮሐንስ እረፍት ስለተሰማና ንጉሥ ሚኒሊክ እኔ ነኝ ንጉሥህ ብለው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መልእክት ስለአስተላለፉ ከኢጣሊያን መንግሥት ጋር የነበራቸው ወዳጅነት ተቋረጠና በአምባላጌና በመቀሌ በመጨረሻ በአድዋ ላይ ጦርነት ሆኖ የኢጣሊያኖች ወታደር ድል ሆነው ግማሹ ሲሞትና ሲማረክ ከሞት የተረፈው ሸሽቶ መረብን ተሻግሮ ተቀመጠ የኢጣሊያ ወታደር በአድዋ ድል ከሆነ በኋላ በኤርትራ ምድር ኤርትራን ገዢነቱን እስታውቆ መረብን ሊያላፍ ውል ገብቶ እንዲቀመጥ ተደረገ ።

የኤርትራን ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ቅኝ አገር ስለአገኘ የበኩር አገሬ ኤርትራ ቢል በአለም ጋዜጣ አሳወቀ በዚሁ በኤርትራ ምድር ሆኖ ብድሩን የአድዋን ጦርነት ለመመለስ ብዙ ሺህ ጦርና ብዙ የካቶሊክ ቄሶች እየላከ ግማሾች ሰላም ሆነው ግማሹ የኦርቶዶክስ ሰው መስለው በየመሳፍንቱ በየባላባቱ ቤት እየተቀመጡ ይሰብኩ ጀመር እንደዚሁም ሊቢያን ከቱርክ መንግሥት ቀምቶ ሰፊሉ

ለማድረግ ጦርነት ጀመረ የሊቢያም ሕዝብ ከቱርክ ወታደር ጋር ተባብሮ በአሊ ሙኽታር መሪነት ስለተዋጋው ሊቢያን ጠቅልሎ ለመግዛት አቃተው ነገር ግን ቱርክ በጀርመን ጎን ስለተሰለፈ ጀርመንን የሚጠሉ ሀገሮች ፈረንሳይና እንግሊዝ ጣሊያንን ስለረዱት የሊቢያን ዋና ዋና ሰዎችን ገድሎ ሊቢያን ቅኝ አገር አደረገ የእንግሊዝም መንግሥት ቀደም ብሎ ከያዘው ከሱማሌ ሀገር ግዛቱ የኪሲማዮን ግዛት ለኢጣሊያን ለቀቀለት ።

ከዚህ በኋላ ሙሴ ሙሶሊኒ የኢጣሊያ 1ኛ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ሙሉ ስልጣን እንዳገኘ ሌሎቹን ቅኝ ሀገሮች ከመፈለግ ይልቅ ኢትዮጵያን በሆነ መንገድ ገብቶ ቅኝ ሀገር ማድረግ ይሻላል ብሎ በሮማ የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳሱንና ሌሎች የካቶሊክ ቄሶች ስለመካሩት ወዲያውኑ ባርን ራይሞንዶ ፍራንኬቴ የሚባለውን በጥብቅ አዘዘው ።

አጼ ኃይለ/ ሥላሴም የኢጣሊያ መንግሥት በዓለም ማህበር ውል 12ኛውን 13ኛውን 15ኛውን አንቀጽ ተላልፎ የሚያደርገውን ለአለም ማህበረተኞች እንደገና ልከው በዋና ከተማቸው በአዲስ አበባ ሐምሌ 11 ቀን 1927 ዓ.ም የኢትዮጵያን መሳፍንትና መኳንንት ሚኒስትሮቹን የቤተክህነቱንም ባለሥልጣን ሰብስበው ለጦርነት እንዲዘጋጁ ጥሪ አደረጉ ።

የኢጣሊያንም ወታደር በብዙ አይሮፕላኖች መጥተው በደአር ተከሉ ምሽግ ያሉትን ወታደሮች በቦምብ መትተው ከአጠፉ በኋላ የኢጣሊያ ወታደር የአደዋን ከተማ ያዘ ከዚያም በሱማሌ በኩል ያለው ጅጅጋን በአሰብ ያለው ደሴን ይይዝ ጀመር ።

የኢትዮጵያም ወታደር በአድዋ በተንቤን በሽሬ በእንደርታ በመንዱን ደግሞ ባኮራት በደጋሚይ በጃን ቀቦ በቢርኩት በደጋሃቡር ብዙ ቀን እየተመላለሱ ሲዋጉ ከሁለቱም ብዙ ወታደር አለቀ የኢጣሊያን አውሮፕላኖች ከቦምብና ከመትረየስ ሌላ በኢትዮጵያ ወታደር ላይ የረጩት ያርከፈከፉት የጋዝ መርዝ ያለው ጢስ ነበርና በዚሁ በሚያርከፈክፉት የጋዝ መርዝና በቦምብ ነበልባል እያጠፋ ማይጨው ድረስ መጡ ።

በማይጨው ጦርነት ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ/ሥላሴ የክብር ዘበኛን ጦር እንዲያዙ ከተንቤን ጦርነት የተመለሱትን ልዑላን ራስ ካሣንና ራስ ስዩምን አቡነ ጴጥሮስን እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን በኋላ

ሊቀጳጳሳት የሆኑትን አቡነ ባስልዮስን ፊታውራሪ ብሩ ወልደገብር ኤል ራስ ከበደ መንገሻ ራስ ጌታቸው አባተ ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ሌሎችም የጦር መሪዎችና አዝማቾችን በምክር የሚረዱትን ይዘው ተሰልፈው ነበር ።

መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ/ም ማክሰኞ ሌሊት ጦርነት እንዲጀመር አዘዙ ።

## ማ ይ ጨ ው

የኢትዮጵያ ጦር ከሠፈረበት ከማይጨው ሶስት ኪ/ሜትር ርቆ መካን ከተባለው ቦታ የኢጣሊያ ጦር ጉድጓድ ምሶ ምሽጓል ይህም የምሽግ ቦታ ማይጨውንና አካባቢውን ሁሉ ወለል አድርጐ ስለሚያሳይ ለቁጥጥር አመቺ ነው በስተቀኝ አምባ በሆር በተባለው ቦታ አልፒን የሚባለው የተራራ ወጪ ክፍል ጦር ሠፍሯል ። በመሐል የማይጨውን ጦር የሚከለክል 2ኛው ክፍል ጦር ሲኖር በስተግራ 1ኛው ክፍለ ጦር መሽጓል በጠቅላላውም አርባ ሽህ የኢጣሊያ ወታደሮች ተሰልፈዋል ለዚሁ ለቀዳሚው ጦር ደጀን እንዲሆን ሳባውዳ ሴሬና እና ቁርዞ 3ኛ ጃንዋሪ የተባሉት ሶስት ዲቪዥኖች ከበላጉ እስከ አባላጌ ድረስ ሰፍረዋል ።

ስለኢጣሊያ ምሽግ መጠናከር ተማቤሊ ሲፅፉ የመጀመሪያው የማይጨው ምሽጋችን እንደሌላው ጊዜ በሽቦ አልታጠረም ፈንጅም ለመከላከያ አልቀበርንም ጥሩ አድርገን የተማመነው በጥሩ ሁኔታ ቆፍረንና ገንብተን በግንድ ከምር ያበጀነው ምሽጋችንን ነው ይህን ሁሉ በማዘጋጀት የረዳንና ጊዜም ያገኘነው ኢትዮጵያውያኖች ጦርነቱን ለመጀመር ከጊዜ ጊዜ እየለዋወጡ በምክር ብቻ ጊዜውን ስላራዘሙ ልን ነው ” ብሏል ።

ኩሎኔል ከኖባሎች የኢጣሊያን ጦር አሰልሉ ካወቀ በኋላ መጋቢት 12 ቀን 1928 ዓ/ም ከንጉሡ ዘንድ ቀርቤ ባሁኑ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ገና በመዘጋጀት ላይ ስለሆነ አመቺ ጊዜ ነውና እንግጠም አልኳቸው ንጉሡም ማርች 24 ቀን በኛ መጋቢት 15 እንገጥመዋለን አሉኝ በማርች 24 ቀንም ከሰዓት በኋላ ንጉሡ ግብር አደረጉ ግብሩ የተደረገበት ቀኝ አርባ ሜትር ያዐል ርዝማኔ አለው ። ቀኛው በሙሉ ምንጣፍ ተነጥፎበታል በበራፉ ላይ ነሚዊ የሀገር የለበሱ የሥራ ሚኒስቴር ሠራተኞች ቆመዋል ንጉሡ ለጊዜው በተዘጋጀላ

ቸው ዙፋን ላይ ተቀምጠዋል ራስ ካሣና ራስ ስዩም ከንጉሡ ጐን አሉ ከእነሱም ዝቅ ብሎ ሌሎች ሹማምንት ተቀምጠዋል እኔ ስገባ ግብሩ መብላት ተጀምሮ ነበር የተወደደውን ጥሬ ሥጋ የአልፍኝ አሽከሮች በየገበታው ያደላድላሉ ሌሎችም በየትናንሽ ኩባያ ጠጅ ይሠጣሉ ብሏል መብልና መጠጡ (ግብሩ ካለቀ በኋላ ንጉሡ ለተሰበሰበው ሠራዊት ንግግር አደረጉ በንግግራቸውም ለጦር መዘጋጀታቸውን ገልፀው ዛሬ ለሊት ይጀምራል አሉ የተሳከረው መኳንንትም ጊዜው አጠረብን እያለ ይናገር ጀመር አብዛኛው ሠራዊት በሬት ከነበረበት አያ ኩላ ባለው ቦታ አልተነሳም ነበርና ነው ። በዚህ ምክንያት አቅም ያንሠናል ብለው ተቃወሙ ስለዚህ ነገሩም ባርከር ሲተች . . .መሣሪያ የያዘው ወታደር አልደረሰም ከማይጨው ያለው ወታደር ቢሆን ቀደም ብሎ ስላልተነገረው ለውጊያ አልተዘጋጀም ስለዚህ ነው ውጊያው ለሌላ ቀን ይተላለፍ ብለው ያመለከቱት . . ይላል ።

የጦርነቱ መጀመሪያ ለመጋቢት 15 ቀን መሆኑ ቀርቶ ለመጋቢት 19 ቀን እንዲሆን ተወሰነ መጋቢት 19 ቀን ያረሰ ከኖባሎች እንደ ጻፈው በዚያን ቀን ንጉሡ አዛገሮችን ሰብስበው ውጊያውን ትገጥማላችሁ እኔም ከዚህ ሆኜ በመድፍና በሞርተር ድጋፍና ሽፋን እሰጣችኋለሁ አሉን ይላል ጦሩም በሶስት ክፍል ተከፍሎ ራስ ካሣ ራስ ስዩምና ራስ ጌታቸው እንዲመሩ ተደረገ ። ስለዚህም የጦር አክፋፊል አንቀሎ ዴል ቦካ ቱች ” ራስ ካሣና ስዩም ይዋጋሉ ብሎ ማሰቡ ምኝነት ነበረ ሁለቱም ኢጣሊያን ጦር ቀምሰው ሸሽተው የተመለሱ ናቸው ከተከበሩ ሰዎች ተወለዱ ሰዎች በመሆናቸው ብቻ የጦር አዛዥነት ቦታ ተሰጣቸው ሌሎቹም የጦር አዛገሮች ቢሆኑ ያው ናቸው ። ደጃች መንገሻ ይልማ ሲጋባ ጣሰው ራስ ከበደ መንገሻ ደጃች በጥ ይበሉ ደጃች ወንድይራድ ሁሉ የጦር አዝገሮች ተብለዋል ግን ጦርነቱ ሲጀመ ከጦርነቱ ቦታ 24 ሰዓት አልቆየም . . ” ይላል ።

ለመጋቢት 19 ቀን የተወሰነው ውጊያ የጦር ዝግጅት አልተሟላም ተብሎ ለ21 ተቀጠረ ለመጋቢት 21 መቀጠሩን የኢትዮጵያ ወታደር ሳይሰማ ባዶሊዩ ሠማ ባዶሊዩ ይህን ቀጠሮ ሊያውቅ የቻለው ጉንሁ ንጉሡ ለእቴጌይቱ በሬዲዮ “ ቅዳሜ ወይም ሰኞ እንገጥማለን ” ብለው ካሳለፉት መልዕክት ነው ባዶሊዮ ይህን ካወቀ በኋላ ጦሩን ለቅዳሜ ውጊያ አዘጋጀው ቅዳሜ ጧት መኳንንቱ ተሰብስቦ አልተዘጋጀንምና የውጊያው ቀን ይተላለፍልን ብለው አመለከቱ ኮኖ ባሎፍ ስለዚዮች ቅዳሜ እለት ሲገልፅ እንደጦር አማካሪነቱ ተጠርቼ ከንጉሡ ዘድን ገባሁ በዚያም ቦታ ሊመናገርም ሆነ ለማድመጥ ፈጽሞ

የማይቻል ነው ከውጭ ወታደሩ ለብዙ ጊዜ እየጠበቀ የተጉላላ በመሆኑ ተሰላችቶ ጥይቱን ወደሰማይ ይተኩሳል ከነዚህም ጥቂቶቹ እየተያዙ ታሰረዋል አንዳንድዶቹም ለመቀጣጫ በአደባባይ ተገርፈዋል ይህ ሁሉ ቅጣት ወታደርን ፀጥ ሊያደረገው አልቻለም ። ይላል በዚያ ቀን በተደረገው ምክር ውጊያው ለመጋቢት 23 ቀን እንዲሆን ተቀጠረ ።

" ኢጣሊያ ምሽጉን በሚገባ አጠናክሮ ከሩቅም በሽቦ ማጠሩን ንጉሡ በመነፅር ያዩት ሰኞ ዕለት ነው ጫማ የሌለው የኢትዮጵያ ወታደር ያን ሽቦ እንዴት ያልፈዋል ሰኞ ከሰዓት በኋላ ውጊያው የሚመራው በራስ ካሣ በራስ ስዩምና በራስ ጌታቸው መሆኑ ባዋጅ ተነገረ ። እነዚህ ሰዎች ጦሩን ሊመሩ ብቻ ተሾሙ ሌሎች ወጣቶች የጦርነት ሙያ ትምህርት ያላቸው ምርጥ መኰንኖች ነበሩ ። በንጉሡ አስአስተያየት እኒያን መኰንኖች መሾም መሳፍንትን መንካት ሆነባቸው የጦርነቱ ፕላን የተዘጋጀው በንጉሡ ብቻ ነው ፕላኑም እንደጥንቱ ወደራ የተዘጋጀ በመሆኑ ይሄው ፕላን ለመኳንንቱ ቀረበ መኳንንቱም በትክክል እንደ አድዋ ድል እናደርጋለን ብለው በፕላኑ ተማመኑ በማለት ባርከር ይተቻል ።

መጋቢት 23 ቀን ደረሰ እንደተለመደው መኳንንቱ መጋቢት 21 ቀን ማታ ተሰበሰበ የጊዮርጊስ ዕለት መጋጠሙ ጥሩ ስላይደለ ጊዜው ይተላለፍ ብለው ጠየቁ ይላል አንጀሎ ዴስ በካ አንድ ስሙን ላገኝ ያልቻልኩት የሃማሴን ተወላጅ በክብር ዘበኛ ጦር ውስጥ ነበር ይህ ቀድሞ በኢጣሊያ ወታደር ወስጥ ተቀጥሮ ሲያገለግል ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ስትከፍት ወንድሞቼን አልወጋም ብሎ ከኢጣሊያ ጦር ገከድቶ ወደ ኢትዮጵያ ጦር የገባ ነው ይህ አገሩን የሚወድ የሃማሴን ተወላጅ በቀጠሮው መብዛት ምክንያት ተናዶል የመጨረሻ የተባለው ቀጠሮ በመፍረሱ የባሰ ተበሳጨ ።

ይህ ጀግና የሃማሴን ተወላጅ ሌሊት ከኢትዮጵያውያን ጠፍቶ ወደ ኢጣሊያኖች ሠፈር ሄደ በዚያም ከጀኔራል ነግሪ ዘንድ አቅርቡኝ ብሎ ከቀረበ በኋላ ባለፈው የሙከዳት ስሁተቱ ተፀፅቶና ኢትዮጵያ ወታደር ጋር መኖር እንደማይችል ነግሮ አሁን የመጣሁ ዛሬ ሌሊት የኢትዮጵያውያን በድንገት ሊወሯችሁ ተዘጋጅተዋል ያሳደገኝ የኢጣሊያ መንግሥት በድንገት ተወርሮ እንዲዋረድ ስለማልፈልግ ይህን ልገልፅላችሁ ነውና ተዘጋጁ አላቸው ቶማሴሊና ማቴውስ በየመጽሐፍቶቻቸው ስለዚህ ሐማሴን ታሪክ በሠፊው ፅፈዋል ብዙም

እትጨኑቁ እለ ይላሉ ታሪክ ፀሐፊዎቹ እኔ እንደነበርኩ መስዬ ወደ ኢትዮጵያ ጦር ሄጄ እደበቃለሁ የኢትዮጵያ ጦር ሌሊት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ለየት ብዬ ከመሐል ቦታ ሆኜ ሁለት የሽጉጥ ጥይት ተኩሼ ምልክት እሠጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁን ምልክት መስማታችሁንና መዘጋጀታችሁን እንዳውቅ ቀይ ሮችት ተኩሱልኝ ብሎ ሌሊቱን ከኢጣሊያኖች ሠፈር ወጥቶ ወደ ኢትዮጵያኖች ሠፈር ሄደ ።

"በኢትዮጵያን ጦር ሠፈርም ሌሊቱን ገብቶ የኢጣሊያን ጦር ሠፈር በልዩ መጣሁ ዛሬ ሌሊት ሳይታሰብ በድንገት ሊገጥሙን ዝግጅታቸውን ጨርሰዋል ተሰልፈዋልና ታጠቁ ብሎ የተኛውን ሁሉ ቀሰቀሶ ከጦር መሪዎቹ ዘንድ ቀርቦ ሲጠየቅ ያንኑ ቃል ተናግሮ እኔ ከናንተ ለየት ብዬ ወደ ኢጣሊያ ምሽግ ተጠግቼ ከረባዳው እሆናለሁ የኢጣሊያ ጦር መንቀሳቀሱንም እንዳየሁ ሁለት የሽጒጥ ጥይት ተኩሼ ምልክት እሰጣችኋለሁ የኢጣሊያ ጦርም ወታደሩን ከዳር እስከ ዳር ለመቀስቀስ ቀይ ሮችት ይተኩሳልና በዚህ ምልክት ተጠቀሙ ብሎ ነገረና የሁለቱንም ወገን ጦር ሌሊቱን በሚገባ ተዘጋጀ..ይላል ሁለቱ ታሪክ ፀኃፊዎች

ማቴዎስ እንደሚገልፁት.. የሃማሴን ተወላጅ ከሌሊቱ 05.45 ሰዓት ሲሆን ከመሃል ቦታ ሆኖ ሁለት ጥይት ተኩሶ ኢጣሊያኖቹም የምልክት ተኩስህን ሰምተናል ለሚለው መልስ ቀይ ሮችት ተኩሰው ገለፁለት ኢትዮጵያኖችም ሐማሴን በነገራቸው መሠረት የኢጣሊያ ጦር በሙሉ ለመንቀሳቀሱ የሮችቱን ተኩስ አዩ እንዲህም አድርጐም በቀጠሮው ብዛት የተናደደው ሃማሴን የማይጨውን ጦር ማጋጠም ቻለ ።

ተኩሱ ለመጋቢት 22 አጥቢያ ከሌሊቱ ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን የተከፈተው በ2ኛው ክፍለ ጦር በቻስቴሪያ አቅጣጫ ነበር ውጊያው እንደተጀመረ ኢትዮጵያውያን አጠቁ የኢጣሊያ ሠራዊትም ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ ኢትዮጵያውያን እያባረሩ የኢጣሊን ሠራዊት ከምሽጉ ሲገባ ኢትዮጵያውን ከወጥመድ ገቡ " የዚያን ዕለት ውጊያ በጣም ከበደን የ24ኛው ብርጌድ አዛዥ ኰሎኔል ሮማለተመትቶ ሲወድቅ የመድፍ እርዳታ መጠየቃቸውን ሮችት አስተኩሶ ሞተ ከኰሎኔል ሮማ ሞት ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሎ የ7ኛው ብርጌድ አዛዥ በጥይት ክፉኛ ተመትቶ ወድቋል መትረየስ ተኳሾችን ምእሳ አሊቃም ተመትቶ ሲወድቅ አጠገቡ የነበረ የአልፒን ወታደር በቦታው ተተክቶ መትረየሱን ገና ከመያዙ በሰከንድ ጊዜ ውስጥ ተገደለ

እዚያው መትረየሱ አጠገብ የነበረ ሌላ የአልፒን ወታደር እየተኩሠ ወደ ምሽግ ሲሸሽ ራስና ትከሻው ላይ ክፉኛ ተመትቶ ወደቀ . . ." እያለ ቶማሲሊ የጦርነቱን ዝርዝር ሁኔታ ጽፏል ።

አን ቢቶሪ ዴላ ሲቢላዛሽን የተባለው መጽሐፍም ከሐረርጌ የመጡ የጦር ትምህርት የተማሩ ወጣት መድፈኞች የኢጣሊያ 2ኛ መድፈኛ ባታሊዮንን ወታደሩን ብቻ ሳይሆን መኩንኖችን ጭምር ፈጀትው ኢትዮጵያውያን ግብር በማግባትና ፀሎት ይዘው ለቀጠሮ ብዛት ባቆዩ ኖሮ ከዚያ ቦታ ለኢጣሊያ ሠራዊት ተርፎ አይመለስም ነበር ። የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች ግብር እየበሉ ፀሎት ፀሎት እያሉ በሚሉበት ጊዜ ኢጣሊያኖች ጥሩ ምሽግና ሰውን በቁመቱ ሙሉ የሚከልል ጉድባ አዘጋጅተው ጦርነቱ ተጀምሮ አበሾቹ ባጠቁ ጊዜ ኢጣሊያኖችን ከእልቂት ያዳቸው ከውጊያቸው ይልቅ ምሽጋቸው ነው በማለት ይተቻል ።

የኢትዮጵያ ጦር አማካሪ የነበረው ኮሞባሎፍ ደግሞ የኛ መድፈኞች ስለፕላኑም ሆነ ስለ ሌላው የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ብዙ ጊዜ የሚተኩሱት የመድፍ ጥይት ጠላት ላይ ሳይሆን ጠላት ወደሌለበት አቅጣጫ ነበር እንዳንዴም በራሳቸው ወገን ላይ ተተኩሶበት ነበር ለምን እንዲህ እንደ ሚሆንም ንጉሡን ብጠይቅ የኛ ሰው የመድፍ ድምፅ ሲሰማ ጀግንነት ይሰማዋል ሞራሉም ይበረታል አሉኝ በማለት ጽፏል ።

በተገኘው የዕለት ድል የተደሰተው የኢትዮጵያ ሠራዊት ግዳይ ለመጣል ወደ ኋላ እየተመለሰ ተቀምጦ ከሚጠብቀው የጦር አለቃው ፊት ይፎክር ጀመር በዚህ ጊዜ የኢጣሊያ ጦር ፋታ አግኝቶ መሰባሰብ ጀመረ የደጃች ጦርም ደረሰለት ይህንኑ የግዳይ መቀበሉን ጉዳይ የየአን ቢቶቶሪ ዴላ ሲቢላዜሽን ደራሲ ለምን እንዲህ እንደሚሆን ንጉሡን ጠይቆ ነበር እየህ አሉኝ ንጉሡ ይላል እንደ አገራችን ባህል መሠረት በጦርነት ጊዜ ወታደሩ ግዳይ መጣል ስላለበት እኔ ወዳለሁበት ወደ ዋናው ጦር ሰፈር ወታደሩ ይመጣል ። ሲመጣም የማረከውን መሣሪያ በትከሻው እየተሸከመና እየሸለለ ነው ። ከኔም ዘንድ ደርሰው ሲፎክሩ ወኔያቸውን ለማነቃቃት የግል መትረየስ ተኳሾቼን መትረየስ እንዲትኩሱላቸው አዝግዛለሁ አሉን ይላል

የደጃች የኢጣሊያ ጦር እስኪደርስ ድረስ የጥቁር ወታደሮች ብርጌድ አዛዥ የሆነው ፔሬዚዮ ቢሮሊ ምሽግ የገባ ወታደሩን ሰብስቦ አበሾች አጥሩን አልፈው ከምሽግ ገብተው ይፈጁናል ብላችሁ አታ

ስቡ አሁን እናንተ ማድረግ ያለባችሁ አንዳንድ ጥይት እየተኮሳችሁ ጥይታችወኅ አስጨርሷቸው ብሎ አዘዘ እንዳለውም ኢትዮጵያውያን ለአንዳንድ ተኩስ መልስ ለመስጠት በማለት በብዛት ይተኩሱ ጀመር ። ምትክ የሌለው የወገባቸው ጥይት እዳለቀም ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ ኮሞባሎናም ጠንከር የሆኑ 900 ሰዎች ያህል በጀግንነት ተዋጉ የወገባቸው ጥይት ሲያልቅ ምንም ማድረግ አይቻልምና እነሱም እንደ ሌሎች ወደ ኋላ ተመለሱ ብሏል ። ይህ ሁሉ የሆነው ግና በማለዳ ነበር ።

እረፋዱ ገደማ ላይ ይጀኑ የኢጣሊያ ጦር ደረሰ የኢጣሊያ አውሮፕላኖችም ከጧቱ ሁለት ሰዓት የተጀመረ የቦምብ ድብደባቸውን አጠናከሩ የጦር ትምህርት የተማሩት የሆለታ ምሩቃን ከቡር ዘበኞች ወደፊት ገፉ ባዶሊዮ እንደሚገልፀው የአየር ሐይሉ ማጥቃት እንደ እንደጀመረ ጠቅላላው የክብር ዘበኛ ወታደር ሶስት ሰዓት ሲሆን በደጀን ተኳኾች ተከልለው ሊያጠቃ መጣ በጥሩ የጦርነት ትምህርት የሠለጠኑ መሆናቸውን የሚያስመሰክር ውጊያ ተዋጉን 10ኛውን ባታሊዮንም በመግደልና በማቁሰል ወረሱት እየፎከሩ አሻፈረኝ የሚል ዘፈን እየዘፈኑ ገፉ ያሉበትንም ምድር በጥሩ የጦርነት ታክቲክ ተጠቀሙበት ከአደጋ ተጠንቅቀው አደጋ መጣል የሚያስችል ትምህርት የተማሩ መሆናቸውንም አወቅሁ ሲል መስክሮላቸውል ።

ከጠዋቱ በአምስት ሰዓት ላይ 10ኛው ባታሊዮን ባዶ በመሆን የባታሊዮን አዛዥ ሌተና ኮሎኔል ዙሬት ለጠቅላይ ጦር ሠፈር ከባድ የጠላት ኃይል ገጥሞናል ይህን እኛ ያለንበትን ቦታ ማርቢቶች ካሉበት አካባቢ ደህናአደርጋችሁ በመድፍ ደብድቡልን . . ሲል አመለከተ ይህን ባመለከተ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የ10ኛው ባታሊዮን አዛዥ ራሱ ኮሎኔል ዙሬት እና ኮሎኔል ሩጀሮ ተገደሉ በዚያ ቦታ ካዳኑት ጥቂት መኮንኖች ውስጥ የኒእፖሊታኑ መኮንን ታሪንቲኒ በነሱ ቦታ ተተክቶ ማዘዝ ጀመረ በቦታው ተተክቶ ማዘዝ እንደጀመረም ለ፩ኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ለጀኔራል ዳልማዞ ባስተላለፈው

መልዕክት አሁን ከዚህ ቦታ የሚታኰሰው የቆሰለ ሠራዊት ብቻ ነው በቅርብ ጊዜ ሁላችንም እንሞታለን እስከንሞት ድረስ ግን መታኮሳችንን እንቀጥላለን ሲል ማመልከቱን ቶማሲሲ ጽፎታል የክፍለ ጦሩ አዛዥ ጄኔራል ዳልማዞ ሠራዊቱ ጠመንጃውን ይዞ ወደፊት እንዲገፋ አዝዞ ያዋጋ ጀመር ።

የክብር ዘበኛ ወታደሮችም የኢጣሊያን ምሽግ ሰብረው ሲገቡ ሲሉ ከምሽጉ ውስጥ ያሉ ኢጣሊያኖች ቦምብ በብዛት እየጣሉ መለ ዪቻቸው ብዙውም ከዚያች ቦታ ተሰዋ በዚያች ዕለት ያዳነን የእጅ ቦምባችንና የቅርብ መትረየሳችን ነው በማለትም ባዶሊዮ መስክ ሯል ። ጦርነቱን ጀምበርም አልቆትም ኀላገለው የኢትዮጵያ ሠራዊት እስከምሸቱ ሁለት ሰዓት ተዋግቶ በትዕዛዝ ተመለሰ ።

የአፍሪካም የኢጣሊያም ጦር ጠቅላይ አዛዥ ማርሻል ባዶሊዮ ቀኑ ሲጨልም ጦርነቱ ስለቆመ ኢትዮጵያውን ተዘጋጅተው በንጋታው እንደሚገጥሙ አስቦ ፕላን በማውጣት ላይ ሳለ ንጉሠ ነገሥቱ ለንጉሥ ይቱ ማታውኑ ያስተላለፉት የሬዲዮ መልዕክት ተጠልፎ ደረሰው መልእክቱም ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምረን እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ ሠራዊታችን ከባዱን የኢጣሊያን ጦር ሲያጠቃ ቆየ በጀግንነትም ተዋጋ በውጊያውም ውስጥ እኛ ራሳችን ተካፋይ ነበርን ከመኳንንቶቻ ችንና ከታማኝ ወታደሮቻችን መሃል የሞቱም የቆሰሉም አሉ በኛ ሠራ ዊት ላይ የደረሰው ጉዳት ከባድ ነው ጠላትም ቢሆን ተጐድቷል የክ ብር ዘበኞች በአስደናቂ ጀግንነት ተዋግተዋል ሠራዊታችን እንደ አው ሮፓ ያን የጦር ትምህርት ባለመማሩ ሊፈታ ቻለ የሚል ነበር ባዶሊዮ ይህን መልዕክት ከሠማ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ድል መሆኑን አረ ጋገጠ በማግሥቱ መጋቢት 23 ቀን ከሞት የተረፈው የኢትዮጵያ ጦር ተጠራቅሞ ሊዋጋ ነበር በዚያ ዕለት ከባድ ዝናብ በመጣሉና ቦታ ውን ሀሉ ደመና ስለሸፈነው ንጉሠ ነገሥቱ ተስፋ የሌለው መሆኑን አውቀው ጦሩ እንዲመለስ አዘው የደሴ ጉዞ ተጀመረ ።

"ከልካዮች" ይላል ኮናባሎች የመጋቢት 23 ቀኑን ሁኔታ ሲገ ልፅ ከልካዮች ሰው ወደ ንጉሡ ዋሻ እንዳይጠጋ ይከለክላሉ በግራም በቀኝም በእርጨውሚ ይደበደባሉ ንጉሡም ምን ዓይነት የተዋረደ የሥነ ሥርዓት አጦት ነው ? ከዋሻው ወጥተንስ እንዴት ማዘዝ ይቻላል ! አሉኝና ግራና ቀኙ እያዩ ፊታውራሪ ተፈሪ የት ነው ? የለም እንዴ ! ቶሎ ፈልጋችሁ አምጡልኝ አሉ ይህም አለቃ ጉራጊውን መሀ እንደያዘ መጣ ንጉሡም በእጃቸው እያመለከቱ ትመለከታለህ ያን ደጋ የለበሰ ቦታ ? በፍጥነት ሰዎችን ይዘህ ሂደህ ያን ቦታ ፈረንጆች እንዳ ይዙት ተጠባበቅ አሉት ፊታውራሪው እጅ ነስቶ ወጣ ከሁለት ሰዓት በኋላ እዚያው አምሺጋቸው ውስጥ ፊታውራሪው ከሰዎቹ ጋር ሲሆ ጫኸ አግኝሁት እንደምንም ብሎ አምሳ ወታደሮች ላከ እሱ ግን እዚያው ከንጉሡ አጠገብ ቀረ ። በማለት የዕለቱን ሥነ ሥርዓት መበ ላሸት ያብራራል ።

ሲም በመጽሐፍ ስለ አንድ ኢትዮጵያዊ ምርኮኛ ጽፋል አንድ የአበሻ ወታደር ተማርኮና በአስተርጓሚ እንጠይቀው ጀመር ይህ ሰው ከፉኛ ቆስሎ ስለነበር እንደማይቆይ ታውቆታል ምን ነበርክ አልነው "የ፲ አዛዥ (ሻለቃ) ነኝ"

"ለምን ከዚያ ከቀሻችን ውስጥ ገብተህ አትተኛም? ኢጣሊያኖች አኬ እስረኛ እንገልም

"ተኝቼ ሳይሆን በእግሬ ቆሜ መሞትን እመርጣለሁ"

"እንዲህ ማለትህ የጀግንነት መሰለህ"

"ከሁለት ቀን በፊት እኛ አበሾች ተማምለናል የተማመልነውም ድል እናደርጋለን ካልሆነም እንሞታለን ብለን ነው አሁን አሳሽንን ፍንም ስለዚህ መሞት አለብኝ ተመልከት እዚያ ማዶ የወደቀውን ሬሳ ብሎ አሳየኝና እሱም እንደኔ ቆሬጥን ነው የምጠብቀው አለ ።..."

በማይጨው ያለቀውን የኢትዮጵያን ሠራዊት ታሪክ ፀሐፊዎች በትክክል አይጽፉትም ኮሞባሎና አንድ ሺ ሰው ነው ሲል ቶማሲሲ ደግሞ 5000 ነው ይለዋል ማርሻል ባዶሊዮ ደግሞ ስምንት ሺ ያደርሰዋል በኢጣሊያኖች በኩል ኢጣሊያኖች እንደገለፁት 68 መኰንኖች 332 ነጭ ወታደሮችና 873 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሞተዋል ።

በማይጨው ጦርነት ሰባ አውሮፕላኖች ተካፋይ ሆነው ከነዚህ ውስጥ 36 አይሮፕላኖች ተመትተው መውደቃቸውን ኢጣሊያኖቹ አምነዋል ተመትው ከወደቁትም መሃል አንዱ የሙሶሊኒ ልጅ ቢቶሪዮ ሙሶሎኒ የሚባለው ነበር እነኝህም ሰባ አይሮፕላኖች በመመላለስ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ 34 ቶን የሚመዝን በምብና የመርዝ ጋዝ ጥለዋል በሌላው የኢጣሊያ መሣሪያ በኩል 61,200 የመትረየስ ጥይት መተኰሱን ኢጣሊያውያን ጽፈዋል ።

ባዶሊዮም ለሙሶሊኒ ባሳለፈው ቴሌግራም...በኢትዮጵያ ያለው ጦርነት አለቀ በማይጨው የተዋጋን የኢትዮጵያ ጦር ከተቂት ወታደሮች በቀር የተረፈ የለም" አለ

አጼ ኃይለ ሥላሴ ከስደት ሀገር ከአውሮፓ ተመልሰው በኢትዮጵያ ነገሥታት ዙፋን ላይ እንደገና ተቀመጡ ።

በዚህን ጊዜ ከፋሽስት ጣሊያን ጋር ደከመን ሳይሉ ሌትና ቀን ሲዋጉ ለሀገራቸው ክብር ሲሉ ሲቆስሉላት ሲደክሙላት የነበሩት አር በኞች ተሰብስበው " ጃንሆይ ለምንድነው አርበኞችን እየተው የሀገራ ቸውን ሕዝብ በወጉና ጠላታችንን ጣሊያን ሲረዱ ለነበረ ባንዳ የሚ ሾሙና የሚሸልሙ አላቸው ።

እጼ ኃይለሥላሴም እኛ ከስደት ሀገር ወደምድራችን ኢትዮጵያ ስንገባ በላይ ዘለቀ ቀድሞ በአርበኞቹ ባይመራንና ከዚህ ባያደርሰን እና ንተ ልትወጉን እንደነበራችሁና እናስገባም ለማለት እንደተዘጋጃችሁ ታውቃላችሁ ስለዚህ ለእኛ ሁላችሁ አንድ ናችሁ ሲሉ መለሱላቸው በዚህ የተነሳ ከዚህ ያደረሳቸው በላይ ዘለቀ ነውና ከሳቸው ጋር ለማጣላት የሸዋ መኳንንትና መሳፍንት በላይ ዘለቀን እንዲሸፍትና በእጼ ኃ/ሥላሴ ላይ ጠላት ሆኖ እንዲነሳ ገፋፉት እንረዳሃለን ብለ ውም ቃል ገቡለት እርሱም ወደጐጃም ሀገሩ ሄዶ ሸፈተ ነገር ግን መጀመሪያ የገፋፉት ከድተው አሲያዙትና አስገደሉት

እጼ ኃ/ሥላሴ በላይ ዘለቀን ከአስገደሉት በኋላ እርሳቸውን በመ ቀበሉና በመርዳቱ አርበኞች ተማክረውእንዳሸፈቱት ሰሙ በዚህን ጊዜ በጣም አዝነው ሰነበቱ (ይባላል)።

በዚህ ጊዜ እንዲህ ያለ ዘፈን ተዘፈነ
አርበኞች ተንቀው መብታቸው ሲወድቅ
የባንዳዎች መብት ተከብሮ ሲጠበቅ
እንዲህ ያለ ጊዜም አይቼም አላውቅ

ለካስ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ
የሞተልሽ ሳለ የገደለሽ በላ
ነጭ ጣሊያን ቢወጣ ጥቁር ጠላት ገባ

የሀገሬ አርበኛ አንተ ባለካባ
ምንም ደስታ የለህ ጉድጓድ እስክትገባ

ሀገሬ ኢትዮጵያ ይግረምሽ በጣም
አርበኛሽ ተሸሮ ጠላትሽ ሲሾም

እጼ ኃይለሥላሴ ለመሣፍንቶቻቸውና ለመኳንንቶቻቸው በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ሹመውና ሸልመው ሲያበቁ ንግግር በሚያ ደርጉ ጊዜ እንዲህ የሚል ቃል ተናግረው ነበር " በእግዚአብሔር

ፈቃድና እርሱ እራሱ መርጦ በትረ መንግሥቱን ሲያስጨብጠንና በዙፋናችን ላይ ሲያስቀምጠን ሕዝባችን ልናገለግልና በሕዝባችን ላይ የሚደረገውን ግፍና ጭቆና ልናጠፋ ህጋችን ልናከብርና ልናስከብር ነው ። ስለዚህ እናንተም በእግዚአብሔር ስም ሆኜ የምሰጣችሁን ስል ስልጣን ሕዝባችሁን ያከመን ሳትሉ ልታገለግሉ ህግን ልታከብሩና ልታስከብሩ እንጅ በሰጠናችሁ ስልጣን ተመክታችሁ ሕዝባችንን ብትበድሉና ያለአግባብ ብታንገላቱ ያላግባብም ብታሰቃዩ የሰጠና ችሁ ሹመት ሥልጣን አይሆንም ሺ ሞት እንጅ ።

በዚህን ጊዜ ይህ ትንቢት በዘመኑ መስተጻልእ ተፈጸመና እንደ ዚህ የሚባል ዘፈን ተዘፈነ

ግርማዊ ጃንሆይ ሰብስበው አጠራቅመው
ለመሣፍንት ሁሉ ሹመት ቢሰጣቸው
ከራሳቸው አልፎ እስከልጆቻቸው
ስልጣኑ ቀረና ሺህ ሞት ሆነላቸው

እጼ ኃይለሥላሴ ሥልጣንን በጊዜያቸው ካልመለሱት የተነሳ ሀገ ሩን ከጠላት ይጠብቃል ወገኑን ከችግር ያድናል ብለው እምነው ያስ ቀመጡት ወታደር (ወቶ አደር) ሀገሩን ከጠላት ሊጠብቅ ቃል የገባ ውን ክዶ በሕግ ሳይሆን በሃይል በጥያቄ ሳይሆን በርሳስ የዘውድን አገዛዝ ልቦ እራሱ ተለጠፈበት ።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩ ከዘውድ አገዛዝ ይልት የኮሚኒ ስትን አገዛዝ መርጦ ከዳር እስከዳር በደስታና በእልልታ ተቀብለው እውነት ሀገሩን ጠብቆ ለጭቁን ሕዝብ የቆመ መስሎት በየቀበሌው በየጉጡ ተደሰተ ነገር ግን የሶሻሊስትን አገዛዝ እራሱ ጊዜያዊ ወታ ደራዊ መንግሥት ነኝ ብሎ የተቀመጠውን ወታደእርን በመጥላት በ66ና በ67 ዓ.ም ለኮሚኒስቶች ወታደር ሀገራችን ያረከሳታል ሃይማ ኖታችን ይጠፋብናል በማለት ለሕዝቡ አርያ ለመሆን በቀዳሚነት ቀዋ ማተው የሞቱና የቆሰሉ እንደዚሁም ሕዝቡ ስላልተቀበላቸው የተሰደ ደዱ በሰው ሀገር ያሉ ያርግ ብሎ ስሙን የሰየመው እስከሚለት ድረስ ሲታገሉና ሲያታግሉ የነበሩ ብዙ ናቸው ነገር ግን ቀዳሚነት ያላቸ ውን የስም ዝርዝር አቀርብላችኋለሁ ።

1ኛ/ በሸዋ በጅሩ በደነባ ዜጋመል በሚባል ሀገር ላይ የጡት ልጆቻቸው ከድተው ወታደር አምጥተው ሲያስገድሏቸው ሲሉ እም

ልጠው ከትንሽ ሰዎች ጋር ሆነው በደፈጣ ውጊያ ከሁለት መቶ ወታደር በላይ ገድለው እራሳቸውን የገደሉ ደጃዝማች ዐሐይ እንቲሶማሊ ።

2ኛ/ በሸዋ በመንዝ በሰላሌ ምድር በአፍቀራ ሕዝቡን ለወታደር መንግሥት እንዳይገዛ ሲሰብኩና ለጦርነት ሲያዘጋጁ የነበር በየጊዜው የመጣውን ጦር ተዋግተው ድል በማድረግ ዕድል የነበራቸው በመጨረሻ በከባድ መሳሪያና በአየር በቦምብ ያሉበት ቦታ ተደብድበው የሞቱ ወንድማማቾች መስፍን ብሩና መርእድ ብሩ ።

3ኛ/ በሃውሳ ብዙ ጊዜ ሲታገሉና ሲያታግሉ የነበር ወደውጭ ሀገር የወጡ ቢትወደድ አሊሚራ ።

4ኛ/ በጐጃም በዳሞት በስካላ በአቸፈር በቁዋሪት በደንግላ በአገው ምድር እየተዘዋወሩ ብዙ ጊዜ እየተዋጉ ድል በማድረግ የታወቀላቸው በመጨረሻ በጦርነት ላይ የሞቱ ቀኛዝማች ስሜነው ደስታ

5ኛ/ በላስታ በሌሎችም አውራጃዎችና ወረዳዎች ብዙ ጊዜ የተዋጉና ድል በማድረግ ዝና የነበራቸው ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ የወታደርን አስተዳደር በመደገፍ በለተረዱ ትግሉን ትተው ወደውጭ ሀገር የተሰደዱ ደጃዝማች ብርሃኑ መስቀል ደስታ

6ኛ/ በሰቆጣና በሌሎችም አውራጃዎች የወታደርን ሠራዊት በማበረር ብዙ ጊዜ በጦር ኃይል ተከበው የማምለጥ እድል የነበራቸው ደጃዝማች ጉግሣ እንባው በመጨረሻ ተዋግተው ለደርግ ተወካይ ለገብረሀይወት እጃቸውን ሰጥተው ሳለ እጅና እግራቸውን በማሰር እየጎረቱ በሊማሊሞ ገደል የጣሏቸው ።

7ኛ/ በዋድላ ድላንታ ሕዝቡን በመቀስቀስ አንድ አድርገው ደሴ ከተማን ለመቆጣጠር ቀርበው የነበር ወገል ጤና በምትባል ከተማ ላይ ተዋግተው የሞቱ በ68 ዓ.ም መስከረም 28 ቀን ቀኛዝማች አሰፋ ታረቀኝ ።

8ኛ/ በተንታና በወረሀይመኑ ሲታገሉ የነበር በደሴ አካባቢ በጦርነት የሞቱ በላይ ዘለለው ከአሰፋ ታረቀኝ ከበላይ ዘለለው ጋር ሕዝቡን በመቀስቀስና በማታገል አብረው የነበሩና ወደ ውጭ የተሰደዱ የሸ. አለቃ ወሴ ታደሰ

9ኛ/ በጋይንት ደጃዝማች ታደሰ ለማና ግራዝማች አድማሱ በላይ

10ኛ/ በሰሜን ጀኔራል ነጋ ተገኝ ቢትወደድ መኮንን የሸ. አለቃ አማኖው ዋቤ

11ኛ/ በወሲጋ ደጃዝማች ደረጃ መኰንን

12ኛ/ በትግራይ ልዑል ራስ መንገሻ እንዲሁም አሊቃ ተስፋዬና ፊውታራሪ አበራ ማስው

ከዚህ በላይ ስማቸውን የዘረዘርኩትና ብዙዎች ስማቸው ያልተ ጠራ የወታደርን አገዛዝ በመጥላት የተነሱ ናቸው እነዚህ መሣፍንትና መኳንንት ቡትንሱበት ጊዜ ስሙ የታወቀ ቡድን አልነበረም ኋላ ግን በሀገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ሀገሬ ብዙ ቡድኖች ተነስተው ደርግን ለማጥፋት ያላደረጉት ጥረት አልነበረም ስለዚህ ከቡድኖች በኋላ የተ ነሱትን የጀግኖች ስም ዝርዝር ወይም ታሪካቸው በሌላው ክፍል ምዕ ራፍ እስከምፅፍላቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ሊቀ መንበር ሆነው የተሾሙትን የአማን ሚካኤል አምዶን አጭር ታሪክ አቀርባለሁ ።

አማን ሚካኤል አንዶም —አንዶም ማለት ምስዕአቸው ማለት ነው በግለዙ አዎድ ሲል በትግሬ እንደ ይላል በኤርትራ ሀገር በሃማ ሴን አውራጃ ፀአዘጋ በትባለች ቀበሌ ተወለዱ ከዚያ ከአባታቸው ከሚካኤል አምዶም ጋር በሱዳን ሀገር ሲኖሩ አጼ ኃይለሥላሴ ከአውሮፓ ወደኢትዮጵያ ሲገቡ ይዘዋቸው ገቡ ከዚያም እስተፃ ይና ጀግና በመሆናቸው ተመልክተው ሌተና ጀኔራል ማዕረግ ሰጥተው በሐረር ፫ኛ ክፍለ ጦሬ አዛዥ ሆነው በውጋዴ ጦሬነት ብዙ ጀብዱ ሰርተዋል ነገር ግን ከአሳደጓቸውና ከዚህ ደረጃ ያዳረሷቸውን ኃይለ ሥላሴን በመጥላት ለመገልበጥም በማሰብ ወደውጭ ሀገር ይኖሩ ነበር ፡፡ በዚህን ጊዜ የምድር ጦር ሠራዊት ከአሉበት እንዲመጡ ከአ ደረገ በኋላ በጃንሆይና በአማን መካከል ያለውን ጥላቻ ያውቅ ስለነ በር በስልሳ ሰባት ዓ/ም መስከረም ሁለት ቀን ኃይለሥላሴን አው ርዶ አማን ሚካኤል አንዶምን የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሊቀ መንበር አድርጐ ሾመው ።

ሊቀ መንበር ማለት ከግዕዝ ወደአማርኛ ሲተረጐም የወንበር አሊቃ ማለት ነው እራሱንም የሕዝበ እንባ ጠባቂ የለውጥ ሃዋርያ ወዘተ እያለ በብዙ ዓይነት መስመሮች ገብቶ ከኮሚኒስት አመራር ሶሻሊስት ኢትዮጵያ ማለት ጀመረ ።

ሌ/ ጀኔራል አማን ሚካኤል በተሾሙ በሁለተኛ ወራቸው በየጊ ዜው ከክፍለ ጦሩ ይሄን ይስሩ ይሄን እንዳያደርጉ ማንኛውም የው ጭም ሰው ሆነ የውስጥ ካለጊዜያዊ ወታደራዊ መግሥት ፈቃድ

እንዳያነጋግሩ እንዳያስናብቱ የሚል ትእዛዝ ስለተሰጣቸው እኔነኝ ወይስ እናንተ የሀገሪቱ መሪና አዛገር ብለው ስለተጣሉ በዚሁ ጠብ የተነሳ እንዳይቀሳቀሱና እጃቸውን እንዲሰጡ ቢጠየቁ እንቢ ብለው ስለተቀመጡ በአሉበት ቤት በታንክና በከባድ መሣሪያ ህዳር አስር ቀን 1967 ዓ/ም ተመተው ተገደሉ ህዳር 12 ቀን ሞታቸው በሬዲዮ ተሰማ ።

| ተራ ቁጥር | የትውልድ ቁ. የአባት ስም | ስሙ በሱባ | ትርጉም | የክህነት ስም | ትርጉም | ሀገሩ የኖረበት | የኖረበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የእግዚአብሔር ፍጡር | አዳም | የሰላም ቀን | ኢዶም | የሰላም ወር | ኤዶምያስ | 930 |
| 2 | የአዳም ልጅ | ሴት | ምትክ | አሴኤል | የእግዚአብሔር ምሳሌ | ሰዶም | 912 |
| 3 | የሴት | ሄኖስ | የሰላም ተስፋ | ኤልሄና | የእግዚአብሔር ስም | | 905 |
| 4 | የሄኖስ | ቃይናን | የክሳ ሰው | ቁዋይን | የክሳ | | 910 |
| 5 | የቃይናን | መላልኤል | የእግዚአብሔር አውቀት | ላልኤል | የእግዚአብሔር ሃይል | | 895 |
| 6 | የመላልኤል | ያሬድ | ድምፅ | ያሬኤል | የፈጣሪ ድምፅ | | 962 |
| 7 | የያሬድ | ሄኖክ | ማስረጃ | ሄኖኤል | የእግዚአብሔር ቃልኪዳን | | 365 |
| 8 | የሄኖክ | ማቱሳላ | የተራራ ሰው | ኤሉሬ | የእግዚአብሔር ድምፅ | | 969 |
| 9 | የማቱሳላ | ላሜህ | ጠንካራ | | | | 747 |
| 10 | የላሜህ | ኖህ | እረጅም እረፍት | | | | 950 |
| 11 | የኖህ | ካም | ልዩ ሰላም | ኩማኤል | | | |
| 12 | የካም | ኩሽ—(ኩሳ) | የጌለም የለ | ኤልዘበ | | | |
| 13 | የኩሽ | ማባ ማቢውስ | በረኸኛ ጣፋጭ | ሃርቀዲ | | | |
| 14 | የሳባ | ኑባ | የንብ ሰፈፍ | ቁቅ (ኩሚ) | | አዜብ | |
| 15 | የኑባ | ጋኖን | አስፈሪ ቁጥር | ካሳዮኒ | | | |
| 16 | የጋኖን | ኢታና | ስጦታ | ናሁመለክ | የአሁን ንጉሥ | | |
| 17 | የኢታና | ናምሩድ— | ሃይለኛ አዋቂ | አበመለክ | የንጉሶች አባት | ኤሬሴን ሬሴን | |
| 1 | የናምሩድ | አዳማ | የአማራሰላም ቀን | | | | |
| 19 | የአዳማ | ራፈልብ— | ጌታ | | | | |
| 20 | የራፈብል | ቁና ·ኪና | ብልሂት | አበሜሊክ | | ጉራራ | |
| 21 | ቀቂና | ጌራ · (ጌራራ) | የሶስት ቀለሞች | መልክሄዲቅ | የፅድቅ ንጉሥ | ጣሌም | |

| ተራ ቁጥር | የትውልድ ቁ. የአባት ስም | ስሙ በሉባ | ትርጉም አቻናፍ | የነሀንት ስም | ሀገሩ ትርጉም የኖረበት | | የኖረበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | የጊራራ ልጅ | ኢትዮጵ | የወርቅ ስጦታ | ኢትኢል | የአምላክ ስጦታ | | 98 |
| 23 | የኢትዮጵ | እቲባ (አቶአባ) | ውድ አበባ | መልከዘበ | የወርቅ ንጉሥ | | 49 |
| 24 | የኢትዮጵ | አቤብ | የወርቅ ሀገር | ወርከዘበ | የተፍለቀለቀወርቅ | | 32 |
| 25 | የአቤብ | ዋሬ - (ሰቢ) | ውስጣዊ ጥበብ | ዋሬያ - ዋረሽ | የዋረቱ ንጉሥ | | 77 |
| 26 | የዋሬ | ልብና | እማን | ሬሊብኖስቢ | ሊባኖስ | | 44 |
| 27 | የልብና | መሊክ - (መለክ) | ንጉሥ | አበሚሌክ | የንጉስ አባት | ጌራራ | 24 |
| 28 | የመለክ | ጋዝያ | ነጻ | አበሲኒ ሲና | የእውነት አባት | አቢሲኒያ(ሲና) | 48 |
| 29 | የጋዝያ | አዲያም | የእሁት ሰላም | የለክዱን | | | 83 |
| 30 | የአድያም | ታንዛን | ክብደት | ኖርእስ | | | 88 |
| 31 | የታንዛን | የቶርእብ | የከበረ አባት | ራትኤል | | ምድያም | 22 |
| 32 | የዩተር | አባብሂር | አዋናል | ኢትዮጵ | ጋዳ -የወርቅ ስጦታ | ሱበያ | 10 |
| 33 | የአባብ ሄር | ኢትዮጵስ | ገዐ በረከት | ሰንደቅ ዓግን | የፀሃይልጅ ንጉስ | ሱብያ | 10 |
| 34 | የኢትዮጵስ | ኤልካኖ | የአምላክተሰፋ | ኢትዮጵያስ | ጋዳ -ገፀበረከቶች | ሶባ | 25 |
| 35 | የኢልካኖ | አኽ - (ኢሲ) | ታላቅ | ሰንደቅ ዓለልማ | | አቡሲኒ ሱባ | 10 |
| 36 | የአኽ | ታምሪያ | | መልክናው | | ሱባ ሱባያ | 10 |
| 37 | የአጺ | ሸሚያ | | ኢዩጱራ | | ሳባ | 10 |
| 38 | የአጺ | አክናውስ | | ሰንደቅ ዓለማ | | ሱኪ | 10 |
| 39 | የአጺ | አክናሱስ | | ሰንደቅ ዓለማ | | ሱቢ | 10 |
| 40 | የአክናውስ | ኩሣ ዮጉ | | አለምሰገድ | | ሣቤት | 10 |
| 41 | የአክናውስ | ቦኑ - ሰንካ | | ቀቡቀበ | | ሣባ | 10 |
| 42 | የቦኑ | እሚን | | ካኖለ | | | 10 |

| | | | | ሀገር | |
|---|---|---|---|---|---|
| 43 | የአሚን | አረፋፈ | ዲውስ | አዜብ | 10 |
| 44 | የአሚን | ዮጵዮሪ | የአሚን አሚን | ሳባ | 10 |
| 45 | የአረፋፈ | አሞር | መረብማባ | ሳባ | 10 |
| 46 | የአረፋፈ ልጅ | ብሊና | ኢትያ ቀዳማዊት | » | 10 |
| 47 | የአሞር | ዘነዱር | ቀለመ ዮጵ | » | 10 |
| 48 | የአሞር ልጅ | ሂር ሂተር | ማዱር ማባ | » | 10 |
| 49 | የአሞር | አንጋቦ | ዘአንሳባ | » | 10 |
| 50 | የኢልካና | ኢጋቦስ | እሲ -እጺ ሰንደቅ | » | 130 |
| 51 | የአሞር | ኩርፋን | ሰቢሳባ | » | 55 |
| 52 | የኩርፋን | ሰርፈ | ግንዘቦ | » | 82 |
| 53 | የሰርፈ | አኪላ | ግንቃቦ - ቆቦ | » | 80 |
| 54 | የሰርፈ | ጹርሰቅላ | እንዘቦ አዜብ | » | 40 |
| 55 | የሰርፈ | አቅጃቦ | ሰባትሶ - ሰብደ | » | 50 |
| 56 | የሰርፈ | ኢጋቦና | ዘዋሰያ - ሳቢ | » | 16 |
| 57 | የኢጋቦና ሲ/ል | ኢትያ | ጉሎማከዳ (የሴም ዘሮች) | አዜብያ | 51 |

ከአዳም ስከ ሰለሞን

ተራ

| ቁጥር | የአባት ስም | ስሙ በሰባ | ስመመንግሥት | ዕድሜ | ዓመተ ምሀረት | ሀገሩ | የነገሡበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሰሎሞን ልጅ | እብነል ሐኪም | ቀ ሚኒሊክ | 39 | ዓመተ ምሀረት | ሳባ | 21 |
| 2 | የእብነልሐኪም | ቶማይ | ሃንድያን | 33 | » | — | 13 |
| 3 | የቶማይ | ዘግዱር | አሚንሆ | 53 | » | — | 41 |
| 4 | የዘግዱር | አክሱማይ | አፈለስ | 107 | » | አክሱም | 83 |
| 5 | የአክሱማይ | አውሳብ ዮስ | ሲራህ | | » | » | 10 |
| 6 | የአውሳብ ዮስ | አብራሌ ዮስ | በሰበሐይ | | » | » | 17 |
| 7 | የአብራሌዮስ | ወረደፀሐይ | ደንገሺ | | » | » | 30 |
| 8 | የወረደ ፀሐይ | ሀንደር | ዓሰምስገድ | | » | » | 41 |
| 9 | የሀንደር | ቋርጃቅ | ወረደንጋሽ | | » | » | 48 |
| 10 | የቋርጃቅ | አውስያ | አርድአሚን | | » | » | 30 |
| 11 | የአውስያ | ኤልሜልዮን | ታኽታውሙን | | » | » | 39 |
| 12 | የኤልሜልዮን | ቶማስዮን | ቶማደዮኒያ | | » | » | 29 |
| 13 | የቶማስዮን | ባሲልዮስ | ገደረት | | » | » | 70 |
| 14 | የባሲልዮስ | አውጥጥ | አብርሃሲራታ | | » | » | 42 |
| 15 | የአውጥጥ | ዚያንጊር | ዘዋሬንብረት | | » | » | 41 |
| 16 | የዚያንጊር | ሰይፋ | ዛግንሸዋ | | » | » | 38 |
| 17 | የሰይፋ | ራመሃይ | ደንቀዝ | | » | » | 60 |
| 1 | የራመሃይ | ሃንዴ | ዋዜብ | | » | » | 22 |
| 19 | የሃንዴ | ሶርልያ | ፈንታሌ | | » | » | 51 |

| ተ. ቁ. | የአባት ስም | ስሙ (በሱባ) | ስመመንግሥት | ዕድሜ | ዓ. ም. | ሀገሩ | የነገሠበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | የሰርሕያ | አግልቡሱ | ቾላሉ | | | | 49 |
| 21 | የአግልቡል | በጥውል | ናግሽሬ | | | | 70 |
| 22 | የበጥውል | በወረስ | ደግሃሬ | | | | 83 |
| 23 | የበወረስ | መሃሲ | ኢንዛይ ቀሬ | | | | 27 |
| 24 | የመሃሲ | ናልክ | ራማናልኪ | | | | 47 |
| 25 | የናልክ | ባዜን | ሰዛ ቢዛ ሰገል | | ከ8—9 | የክርስቶስ መወለድ | 17 |
| 26 | የባዜን | ራስዳሺ | ፀንፈ አርአድ | | 9 ላይ | | 22 |
| 27 | የራስዳሺ | ሶረን | ኡዛና | 39 | | | 20 |
| 28 | የባዜን ሲ/ልጅ | ገርማሞት | እት ያሀንዴኬ | | 31 | | 8 |
| 29 | የሶረን ሲ/ልጅ | ብልብላ | ሀንዴኬገርን | 59 | | | 22 |
| 30 | ሶረን ልጅ | ኩኩብ | ባሀረሰገድ | 81 | | | 24 |
| 31 | የኩቱብልጅ | ግርማሰፈር | ግርማ አስፈሬ | | 105 | | 60 |
| 32 | የግርማሰፈር | ሰርግዋይ | ዣንቢዛን | | 165 | | 40 |
| 33 | የሰርግ ዋይ | ዘርአይ | ደቅመሃሪ | | 205 | | 19 |
| 34 | የዘርአይ | ሰብአሰገድ | ቢጋማይ | | 234 | | 22 |
| 35 | የሰብአሰገድ | ፅዮን ግዛ | ሀዝብሰገድ | | 253 | | 29 |
| 36 | የፅዮን ግዛ | አጓዴር | ዣን ሰገድ | | 275 | | 19 |
| 37 | የአጓዴር | አልአሜዳ | ሰይፈ አርአድ | | 294 | | 16 |
| 38 | የአልአሜዳ | ኢዛና | አብርሃ | | 310 | | 40 |
| 39 | የኢካልሜድ | ኢካፍሀ | አፅብሃ | | 350 | | 59 |
| 40 | የኢዛና | አስፍሀ | ዋዜብ | | 409 | | 31 |
| 41 | የአስፍሃ | አርፍድ | አልሚራስዮስ | | 440 | | 11 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 42 | የአርፍድ | አምሲ | ማላዶባኢዛ | 451 | 10 |
| 43 | የአምሲ | አል ማሪስ | አልአሜዳ | 461 | 12 |
| 44 | የአልሚሪስ | ታዚና—ቲዛና | እያዛና ሃሊጋ | 473 | 10 |
| 45 | የታዚና | ካሌብ | እለአስብሃ | 483 | 40 |
| 46 | የካሌብ | ገብረመስቀል | እለሃታዛ | 523 | 14 |
| 47 | የገ/መስቀል | ቆስጠጢኖስ | እለገበዝ | 537 | 2 |
| 48 | የቆስጠጢኖስ | ባዝጋር | ወሰንሰገድ | 565 | 15 |
| 49 | የባዝጋር | ፍሬሁ | ፍሬገበዝ | 5 0 | 23 |
| 50 | የፍሬሁ | አድርአዝ | አልኣጋሽ | 503 | 20 |
| 51 | የአድርአዝ | አክለውድም | አርማህ | 623 | 0 |
| 52 | የአክለውድም | ግርማአስፈሬ | አልባሀርኑጋሲ | 630 | 15 |
| 53 | የግርማአስፈሬ | ዝርጋዝ | ጃንአስፋሁ | 646 | 10 |
| 54 | የዝርጋዝ | ድግና | ግድናሚካኤል | 656 | 26 |
| 55 | የድግና | ባሀረ ኢክላ | • አዛኤል | 62 | 19 |
| 56 | የባሀረኢክላ | ጉም | ዝርሰም | 701 | 24 |
| 57 | የጉም | አስጉምጉም | በካሣ | 725 | 05 |
| 58 | የአስጉምጉም | ለትም | ኢዩኤል | 730 | 16 |
| 59 | የለትም | ተላትም | እንድቢስ | 746 | 21 |
| 60 | የተላትም | አድጉሺ | ማህዩዊ | 767 | 13 |
| 61 | የአድጉሺ | አይዘር | | | 5 ሰዓት |
| 62 | የአይዘር | ድድም | አልፍሬም | 780 | 05 ዓመት |
| 63 | የድድም | ውድድም | ዳንኤል | 785 | 10 |
| 64 | የውድድም | ውድም አስፈሬ | | 795 | 30 |

የቀ ሚኒሊክ ዘር ወደ ዛጉዌ ዘር ያዘወሩት ነገሥታት

| ተራ ቁጥር | የአባት ስም | መጠሪያ ስም | ስመ መንግሥት | ዓመተ ምህረት | የገዙበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|
| 65 | የቢያዶም አስፋ | አርማህ | እለቶስመንጢኖስ | 825 | 05 |
| 66 | አርማህ | ዳንግዝን | ደግናዝን | 830 | 19 |
| 67 | የዳንግዝን | ግደዝን | የገበናን | 849 | 09 |
| 68 | የግደዝን | ሙደም | አንበስሰገድ | 858 | 20 |
| 69 | የውድም | ድልነአድ | የቀስደደ | 879 | ያልነገሡ ናቸው |
| 70 | የድልነአድ | አግባእፅዮን | | | |
| 71 | የአግባእፅዮን | ፅንፈአርድ | | | |
| 72 | የፅንፈአርእድ | ነጋሽ ዛሬ | | | |
| 73 | የነጋሽዛሬ | አስፍሐ | | | |
| 74 | የአስፍሐ | ያዕቆብ | | | |
| 75 | የያዕቆብ | ባሀርአስግድ | | | |
| 76 | የባሀርአስግድ | አድምአስግድ | | | |
| 77 | የአድም አስግድ | ተስፋ ኢየሱስ | | | |

## ከሰሎሞን ዘር የመጡ የዛጉዬ ልጆች

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጊዶዎን | አስቴር | ዮዲት | 7 | 41 |
| 2 | የባህርሰፍ | መራ ተ ሃ ማራራ | ዛጉዌ | 919 | 13 |
| 3 | የመራር ተ ሃ | ጠጠውድም | ፀርሰገደ | 932 | 40 |
| 4 | የጠጠውድም | አኩቴት | ጃን ስዩም | 972 | 20 |
| 5 | የጠጠውድም | በእምኑቱ | ግርማስዩም | 992 | 20 |
| 6 | የበእምነት | ምይራሪ | ድልአድ | 1012 | 40 |
| 7 | የአኩቴት | ሃርቤይ | ሃርየንመህቀል | 1052 | 40 |
| | የሃርቤይ | አስዳ | ይምርሃነ ክርስቶስ | 1092 | 40 |
| 9 | የእስዳ | ሀርቤ | ገ/ማርያም | 1132 | 40 |
| 10 | የእስዳ | ላሊበላ | ገ/መስቀል | 1172 | 40 |
| 11 | የሃርቤ | ነአኩቶ ለአብ | እልመለክኑን | 1212 | 40 |
| 12 | የላሊበላ | ይትባረክ | | 1252 | 10 |

# በነገሥታቱ ስም ሆነው የገዙት የመሳፍንት
## የስም ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | የአባት ስም | መጠሪያ ስም | ስመ መንግሥት | ዕድሜ | ዘመን | የነገሰበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቤሩ ጓንጉል | ራስ አሊ ታላቁ | | | 1777 | 4 |
| 2 | ቤሩ ጓንጉል | ራስ አሊጋዝ | | | 1781 | 5 |
| 3 | » » | ራስ ወ/ሚካኤል | | | | |
| 4 | አባ መርዝ | ራስ ወ/ገብርኤል | | | 1792 | 26 |
| 5 | በሬንቶ | ራስ ጉግሣ | | | 1818 | 02 |
| 6 | የራስ ጉግሣ | ራስ መሚም | | | 1820 | 03 |
| 7 | የራስ ጉግሣ | ራስ ማርዬ | | | | 3 ወር |
| 8 | የራስ ጉግሣ | ራስ ዶሪ | | | 1823 | 22 |
| 9 | የደጃች አሉላ | ራስ አሊ ትንሹ | | | 1845 | 02 |
| 10 | ሃይሉ | ደጃዝማች ካሣ የበላይ እንደራሴ | | | 1847 | 13 |
| 11 | ካሣ | ቴዎድሮስ | | | 1556 | 34 |
| 12 | የማናስ | አጼ ሰርፀ ድንግል | መላክ ሰገድ | 46 | 1590 | 47 |
| 13 | የሰርፀ ድንግል | ,, ያዕቆብ | መለክ ጋዲ | 16 | 1597 | 02 |
| 14 | የሚናስ ልጅ | ,, ዘድንግል | አጥናፍ ሰገድ | | 159 | 2 |
| 15 | የማሪያም ፋሲል | ,, ሲስንዮስ | ስልጣን ሰገድ | | 1626 | 34 |
| 16 | የሱስንዮስ | ,, ፋሲለደስ | ዓለም ሰገድ | 62 | 1660 | 15 |
| 17 | የፋሲል | ,, ዮሃንስ | አይላፍ ሰገድ | | 1675 | 24 |
| 1 | የዮሐንስ | ,, ኢያሱ | አድያም ሰገድ | 44 | 169 | 02 |
| 19 | የኢያሱ | ተክለሃይማኖት | አብሪክ ሰገድ | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | የዮሐንስ | ቴዎፍሎስ | አድራር ሰገድ | 45 | 1700 | 03 |
| 21 | የዮሐንስ የልጅ ልጅ | ዮስጦስ | ፀሐይ ሰገድ | | 1703 | 06 |
| 22 | የታላቁ ኢያሱ | ዳዊት | አድባር ሰገድ | 26 | 17183 | 50 |
| 23 | ” ” | በካፋ | መሲህ ሰገድ | 37 | 1713 | 10 |
| 24 | የበካፋ | ኢያሱ | ብርሃን ሰገድ | 33 | 1723 | 25 |
| 25 | የኢያሱ ሁለተኛ | ኢዮአስ | ል ል ሰገድ | 31 | 1748 | 14 |
| 26 | የታ ኢያሱ | ዮሐንስ | አድማስ ሰገድ | 70 | 1762 | 01 |
| 27 | ዮሐንስ ሁለተኛ | ተክለሃይማኖት | ጥበብ ሰገድ | 22 | 1763 | 07 |
| 28 | የተክለሃይማኖት | ሰለሞን | ክብራን ሰገድ | | 1770 | 02 |
| 29 | ዳ/ዮሐንስ ሁለተኛ | ተ/ጊዮርጊስ | ፍቅር ሰገድ | | 1772 | 05 |
| 30 | በመማፍንት | ተይዘው | ለስሙ የነገሡ | | 1777 | |
| 31 | ኢዮአሱ | ኢያሱ | | | | |
| 32 | የኢያሱ | ሀዝቅያስ | | | | |
| 33 | የጾግ/ኢያሱ | በዕደማርያም | | | | |
| 34 | የተ/ሃይማኖት | ሰለሞን | | | | |
| 35 | የኢዮአስ ልጅ | ዮናስ | | | | |
| 36 | | ዲሚጥሮስ | | | | |
| 37 | የሕዝቅያስ | እንለዕዮን | | | | |
| 38 | የእንለጸዮን | | | | | |
| 39 | | ዮሐንስ | ማህለ ድንግል | | | |
| 40 | የገይሉ | ካሣ | አጼ ቴዎድሮስ | 50 | 1847 | 13 |
| 41 | የዋግ ሹም | ጉበዜ | ተ/ጊዮርጊስ | | 1861 | 03 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 42 | የጉብረመድኅን | | | 56 | 1864 | 17 |
| 43 | የመርጫ | በዝብዝ ካሣ | ዮሐንስ | 70 | 1882 | 24 |
| 44 | የሃይለመለኮት | ሚኒሊክ | ሚኒሊክ | | 1906 | 03 |
| 45 | የሚካኤል | ኢያሱ | ኢያሱ | | 1909 | 19 |
| 46 | የሚኒሊክ | ዘውዲቱ | ዘውዲቱ | | 1923 | 44 |
| 47 | የመኰንን | ተፈሪ | ኃይለሥላሴ | | 1967 | 2 ወር |
| 4 | የእምዶም | አማን | ሊቀመንበር | | 1967 | 02 |
| 49 | የባንቲ | ተፈሪ | ሊቀመንበር | | 1969 | 14 |
| 50 | የኃ/ማርያም | መንግሥቱ | ሊቀመንበር | | | |

# ማ ው ጫ


ገጽ

መቅደም ........................................ 3

1. ምዕራፍ አንድ ነገደ አደም .............................. 12

2. ምሕራፍ ሀለት
ሥላሶች ለሔዋን ዕንቁ አርያ እንደሰጧት ........ 29

3. ምዕራፍ ሶስት
የኢትዮጵያ ዘመን መንግሥትና የነገደ አመጣጥ .... 26

4. ምዕራፍ አራት
የአዜ ዘመን መንግሥት ........................ 38

5. ምዕራፍ አምስት
የኢትዮጵያ ዜጎች የሚገኙባቸው ሃገሮችና ወንዞቻቸው ... 51

6. ምዕራፍ ስድስት
የማክዳና የልጅዋ የምኒልክ ዘመን መንግሥት ....... 60

7. ምዕራፍ ሰባት
የቀዳማዊ ሚኒልክ ጉዞና እርፍት ............... 78

8. ምዕራፍ ስምንት
የአክሱም አመሰራረት ......................... 81

9. ምዕራፍ ዘጠኝ
የፒያንኪ (አጼዘዋሪ ንብረት) ዘመን መንግሥት... 108

10. ምዕራፍ አስር
የአጼሊዛ ቤዛ ዘመን መንግሥት ............... 118

11. ምዕራፍ አስራ አንድ
የአጼ አብርሃና አጽብሃ ዘመን መንግሥት ......... 135

12. ምዕራፍ አስራ ሁለት
የአጼ አልሜድ ዘመን መንግሥት ............... 145

13. ምዕራፍ አስራ ሶስት
የአጼ አርሜህ ዘመን መንግሥት ............... 154

14. ምዕራፍ አስራ አራት
የቅዱስ ላሊበላ ዘመን መንግሥት ............... 162

15. ምዕራፍ አስራ አምስት
የጉዲት (ዮዲት) ታሪክ.................... 197

16. ምዕራፍ አስራ ስድስት
ቀዳማዊ አጼ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት..... 210

17. ምዕራፍ አስራ ሰባት
የአጼ ዳዊትና የልጃቸው የአጼ ዘራያዕቆብ
ዘመን መንግሥት.................... 240

18. ምዕራፍ አስራ ስምንት
የአጼ በዕደማርያም ዘመነ መንግሥት.......... 249

19. ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ
የአጼ እስክንድር ዘመን መንግሥት............ 258

20. ምዕራፍ ሃያ
የአጼ ልብነድንግል ዘመነ መንግሥት.......... 260

21. ምዕራፍ ሃያ አንድ
የአጼ ገላዲዎስ ዘመነ መንግሥት............. 308

22. ምዕራፍ ሃያ ሁለት
ገየአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት.............. 313

23. ምዕራፍ ሃያ ሶስት
የአጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት............. 334

24. ምዕራፍ ሃያ አራት
የአጼ ዮሐንስና ኢያሱ ዘመነ መንግሥት........ 348

25. ምዕራፍ ሃያ አምስት
የአጼ በካፋና የልጃቸው ዳግማዊ ኢያሱ ዘመነ መን 306

26. ምዕራፍ ሃያ ስድስት
ዘመነ መሣፍንት ከትልቁ ራስ አሊ እስከ ትንሹ
ራስ አሊ......................... 386

27. ምዕራፍ ሃያ ሰባት
የታላቁ ጀግና የአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት.... 396

28. ምዕራፍ ሃያ ስምን
የአጼ ተክለጊዮርጊስና የአጼ ዮሐንስ ዘ. መንግሥት. 430

29. ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ
የአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት. . . . . . . . . . . . . . 434

30. ምዕራፍ ሰላሳ
የሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት. . . . . . . . . . . . . . . 444

31. ምዕራፍ ሰላሳ አንድ
የአጼ ኢያሱ ሚካኤልና የንግስት ዘውዲቱ ዘመነ
መንግ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 466

32. ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት
የአጼ ኃይለ ሥላሴ ማህፀወ ነገሥት (ተፍፃሜተ
ነገሥት) ዘመነ መንግሥት . . . . . . . . . . . . . . . 472

33. የማይጨው ጦርነት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 478

34. በ66ና በ67 ዓ.ም. የደርግን አገዛዝ እንቀበልም
በማለት የተዋጉ መኳንንት. . . . . . . . . . . . . . . 489

35. የጀኔራል አማን ታሪክ. . . . . . . . . . . . . . . . . 490

36. በመጨረሻ ከአዳም እስከ ኃይለሥላሴ የነገሥታት
የትውልድ ሐረግ መቁጠሪያ እጀንዳ. . . . . . . . . . . 492




አፄ ዘሞሴ ንብረት የተባለው ፒያኒር ከሰባ ፊደል ለይቶ የጻፈው



የአዘጋጁ አባት ቄስ በላይ ድሉ





ረዳት አዘጋጆች

ዓይነኩሉ ከሣዬ
ወልዴ አድማሱ



በኖርያ ከፋ የሚቀመጠው ንጉሥ ይሄን ይመስል ነበር ስሙ ዘማርያም
ሲቢኒኒ በኖርያ ታሪክ ላይ ይመለከቱ